መጽሐፍ ቅዱስን ሊገነዘቡት ይችላሉ!

# የሐዋርያት ሥራ፡ በሉቃስ ታሪከኛው

ቦብ አትሊ
የትርጓሜ ሊቅ (ፕሮፌሰር)
(የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ)

የጥናት መመሪያ ሐተታዊ ጽሑፍ
አዲስ ኪዳን፣ ቅጽ 3

ዓለም አቀፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት፣ ማርሻል፣ ቴክሳስ
1998፣ በ2008 የተከለሰ

# ማውጫ


የጸሐፊው መልእክት፡ ይህ ሐተታ እንዴት ይረዳዎታል? . . . . . i

ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ፡የተፈተነ እውነትን በግል ለመፈለግ. . . . . iii

የሐዋርያት ሥራ መግቢያ. . . . . 1

የሐዋርያት ሥራ 1 . . . . . 7

የሐዋርያት ሥራ 2 . . . . . 24

የሐዋርያት ሥራ 3 . . . . . 54

የሐዋርያት ሥራ 4 . . . . . 69

የሐዋርያት ሥራ 5 . . . . . 84

የሐዋርያት ሥራ 6 . . . . . 99

የሐዋርያት ሥራ 7 . . . . . 106

የሐዋርያት ሥራ 8 . . . . . 120

የሐዋርያት ሥራ 9 . . . . . 129

የሐዋርያት ሥራ 10 . . . . . 141

የሐዋርያት ሥራ 11 . . . . . 151

የሐዋርያት ሥራ 12 . . . . . 158

የሐዋርያት ሥራ 13 . . . . . 166

የሐዋርያት ሥራ 14 . . . . . 179

የሐዋርያት ሥራ 15 . . . . . 188

የሐዋርያት ሥራ 16 . . . . . 197

የሐዋርያት ሥራ 17 . . . . . 207

የሐዋርያት ሥራ 18 . . . . . 218

የሐዋርያት ሥራ 19 . . . . . 226

የሐዋርያት ሥራ 20 . . . . . 234

የሐዋርያት ሥራ 21 . . . . . 243

የሐዋርያት ሥራ 22 . . . . . 251

የሐዋርያት ሥራ 23 . . . . . 258

የሐዋርያት ሥራ 24 . . . . . 264

የሐዋርያት ሥራ 25 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 269
የሐዋርያት ሥራ 26 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 274
የሐዋርያት ሥራ 27 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 283
የሐዋርያት ሥራ 28 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 290
ተጨማሪ መግለጫ አንድ: የግሪክ ሰዋሰዋዊ ቃት አጭር መግለጫዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . 296
ተጨማሪ መግለጫ ሁለት: ጽሑፋዊ ትንተና . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 303
ተጨማሪ መግለጫ ሶስት: የቃላት ፍቺ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 306
ተጨማሪ መግለጫ አራት: የእምነት መግለጫ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 314

# የልዩ ርዕስ ማውጫ


የጥንታዊቷ ቤተክርስቲያን ኬሪግማ (ስብከተ ወንጌል) የሐዋ 2፡14 . . . . . . . . . . . . . . . . 4

ዕርገት የሐዋ 1፡2 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 8

እሱም በመንፈስ ቅዱስ አድርጓልና የሐዋ 1፡2 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 9

የእግዚአብሔር መንግሥት የሐዋ 1፡3 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 11

በዳመና መምጣቱየሐዋ 1፡7 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 15

የሐዋሪያት ስም ዝርዝር የሐዋ 1፡9 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 16

ከኢየሱስና ከደቀመዛሙርቱ ጋር የተጓዙት ሴቶች የሐዋ 1፡314. . . . . . . . . . . . . . 17

ቁጥር አስራ ሁለት የሐዋ 1፡22 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 21

ልብ የሐዋ 1፡24 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 22

እሳት 2፡3 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 26

መጽሐፍ ቅዱሳዊ አግማሚያ በአልኮል (ሆምጣጤነት)

እና በአልኮለኝነት (ሱሰኝነት) 2፡13 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 28

የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ስብከተ ወንጌል 2፡14. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 31

ይህ ዘመንና የሚመጣው ዘመን 2፡17. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 32

ሴቶች በመጽሐፍ ቅዱስ 2፡17 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 32

የፍጻሜ ትንቢታዊ ሥነ—ጽሑፍ 2፡19 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 35

ዳግም ምጽአቱ 2፡20. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 35

የጌታ ስም 2፡21. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 36

ኢየሱስ የናዝሬቱ 2፡22 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 37

ተስፋ 2፡25. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 39

ሙታን የት ናቸው?2፡27 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 40

ሥላሴ2፡32 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .42

አመሳስዮሽ አገላለፅ 2፡32. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 43

ንስሐ 2፡38 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 46

ጥምቀት 2፡38. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .46

የግሪክ የግሥ ጊዜያቶች ለደህንነት ጥቅም ላይ የዋሉ 2፡40 . . . . . . . . . . . . . . . . . 48

ኮይኖኒያ 2፡42. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 50

መመረጥ/ቅድመ ውሳኔ (መታደል) እና የሥነ መለኮት ሚዛን አስፈላጊነት 2:47. . . . . . . . . . . . . . . . . . . 51
ኪዳን 2:47 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .51
መመጽወት 3:2 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 56
ክብር 3:13 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .59
ጴንጤናዊው ጲላጦስ 3:13 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 59
የተቀደሰው 3:14. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 60
ጽድቅ 3:14 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .61
መሪ/ ደራሲ/ጀማሪ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 63
እምነት (ፒስትስ pists [ስም]፣ ፒስቱ pisteuq [ግሥ]፣ ፒስቶስ [pistos [ቅጽል])3:16. . . . . . . . . 64
ሰዱቃውያን 4:1 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 71
የፍርድ ችሎት 4:5. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 73
የማዕዘን ድንጋይ 4:11. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 76
መቀባት በመጽሐፍ ቅዱስ 4:27. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 79
ግልጽነት (ፓሬሲያ).4:29. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 80
በርናባስ 4:36 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .82
ክፋት 5:3. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 85
የቀብር ልማዶች 5:6 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 87
የግሪክ ቃላት ስለ መፈታተን ያላቸው ትርጓሜ 5:9. . . . . . . . . . . . . . . . . . . 88
ቤተክርስቲያን/ ኤክሌሽያ/ 5:11 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 89
ክፉ መናፍስት 5:16. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 91
መናፍስትን ማስወጣት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 92
ፈሪሳዊያን 5:34. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 96
ገማልያል 5:34 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 96
እጆችን መጫን በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ 6:6. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 103
በእስራኤላዊያን ከግብፅ በመጡበት ቀን 7:18 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 111
የሲና ተራራ አቀማመጥ 7:30. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 113
ቅርጽ (*Tupos*) 7:43 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 115
"ጥንቆላ" 8:9 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 123
“ቅዱሳን” 9:13 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .133
“የእግዚአብሔር ልጅ” 9:20 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 135

መንፃት 9፡32. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 138

የአዲስ ኪዳን ትንቢት 11፡27. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 155

የምልጃ ፀሎት 12፡5. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 160

የኢየሱስ ወንድም ያዕቆብ 12፡17 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 164

ፆም 13፡2. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 168

የዕብራውያን ህግ 13፡15. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 171

ኢየሱስ ከትንሳኤው በፊት13፡39. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 174

መላክ (አፖስቴሎ)14፡4 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 181

መፅናት 14፡22 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .185

"ሲላስ" 15፡22 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 193

የክርስቲያን ነፃነት እና ሃላፊነት 15፡29. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 195

ኢየሱስና መንፈስ 16፥6 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 200

የቆሮንቶስ ከተማ የሐዋ 17 መግቢያን ተመልከት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 219

የቆሮንቶስ ከተማ የሐዋ 18፡1 ሀሳብን ተመልከት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 221

የኤፌሶን ከተማ የሐዋ 18፡19 ሀሳብን ተመልከት. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 223

መናዘዝ የሐዋ 18፡1 ሀሳብን ተመልከት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .230

"የናዝዊነት መሃላ" 21፡24.. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 248

መርገም (Anathema) 14፡23 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 261

የፕራይቶሪየም ጠባቂ/የአገረ ገዢው ወታደሮች 23፡35. . . . . . . . . . . . . . . . . . 263

ሄሮድስ አግሪጳ ሁለተኛው የሐዋ 25፡13 መግቢያን ተመልከት. . . . . . . . . . . . . . . 271

ቤሪንሲ የሐዋ 25፡13 መግቢያን ተመልከት. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 271

"እውነት" በጳውሎስ ደብዳቤዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 280

# የጸሐፊው መልእክት:
# ይህ ሐተታ እንዴት ይረዳዎታል?

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጓሜ አስተውሎት እና መንፈሳዊ ሂደት ያለበት የጥንቱን ተመስጧዊ ጸሐፍት በዚህ መልኩ ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን መልእክት በዘመናችን ለመረዳትና ለመተግበር የተዘጋጀ ነው፡፡

መንፈሳዊ ሂደቱ ወሳኝ እና ለመግለጽ አስቸጋሪ ነው፡፡ ለእግዚአብሔር መሰጠትንና ግልጽነትን ይጠይቃል፡፡ (1) ለእሱ፣ (2) እሱን ለማወቅ እና (3) እሱን ለማገልገል ጉጉትን ይፈልጋል፡፡ ይህ ሂደት ደግሞ ጸሎት፣ ንስሐ እና የሕይወትን አኗኗር ለመለወጥ ፍቃደኝነትን ይጠይቃል፡፡ በትርጓሜ ሂደት መንፈስ ወሳኝ ነው፣ ዳሩግን ትሑታንና፣ የእግዚአብሔር ሰዎች የሆኑ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን በተለየ መልኩ እንደሚረዱት ምስጢር ነው፡፡

የማስተዋሉን ሂደት ለመግለጽ ቀላል ነው፡፡ እኛ ለጽሑፉ የማናወላውልና ተገቢ ልንሆን፣ በራሳችን ወይም በእምነት ክፍላችን አስተሳሰብ ሳንወሰድ ይገባል፡፡ ሁላችንም በታሪካዊ ሁኔታዎች ውስጥ ነን፡፡ ማናችንም ብንሆን ጉዳዩ የማይነካንና ገለልተኛ ተርጓሚዎች አይደለንም፡፡ ይህ ሐተታ በጥንቃቄ ማስተዋል ሂደት የተቀመረ ሦስት የትርጓሜ መርሖዎችን አዋቅሮ የያዘና አድልዎአዊ የሆኑ አስተሳሰቦቻችንን ለመቅረፍ የሚረዳ ነው፡፡

### የመጀመሪያው መርሕ

የመጀመሪያው መርሕ የቅዱሱ መጽሐፍ ክፍል የተጻፈበትን ታሪካዊ መቼት ማጤን ነው፤ እንዲሁም የጸሐፊውም የወቅቱ ታሪካዊ ሁኔታ ይታያል፡፡ ዋነኛው ጸሐፊ ለማስተላለፍ የፈለገው ተግባርም ሆነ መልእክት አለው፡፡ ጽሑፉ ለእኛ አንዳች የሚሆን ዋነኛው፣ ጥንታዊው፣ ተመስጧዊው ጸሐፊ የጻፈው አይደለም ማለት ፈጽሞ አይደለም፡፡ የእሱ ፍላጎት– የእኛ ታሪካዊ፣ ስሜታዊ፣ ባህላዊ፣ ግላዊም ሆነ ክፍለ ሃይማኖታዊ ፍላጎት አይደለም– ቁልፉ ነው፡፡ ተግባር ዋነኛው ጓደኛ ነው፣ በትርጓሜ ሰዓት፣ ዳሩግን ሁልጊዜ ትክክለኛ ትርጓሜ ተግባርን መቅደም ይኖርበታል፡፡ እሱም ደግሞ የሚያጠናክረው እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፍ አንድ እና አንድ ብቻ ፍቺ እንዲኖረው ነው፡፡ ይህም ፍቺ የሚሆነው ዋነኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊ በመንፈስ ተመርቶ በዘመኑ ሊለው የፈለገውና ሊገናኝበት ያለውን ነው፡፡ ይሄው አንዱ ፍቺ ምናልባት በርካታ አማራጭ አግባቦች ለተለያዩ ባህሎችና ሁኔታዎች ሊኖረው ይችላል፡፡ እነዚህ አገባቦች ግን ከዋነኛው ጸሐፊ ማዕከላዊ እውነት ጋር የተገናኙ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህን ምክንያት፣ ይህ የጥናት መመሪያ ሐተታ የተነደፈው ለእያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ መግቢያ እንዲሆን ነው፡፡

### ሁለተኛው መርሕ

ሁለተኛው መርሕ ሥነ ጽሑፋዊ አሀዶችን መለየት ነው፡፡ እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ሙሉ ዶሴ ነው፡፡ ተርጓሚዎች አንደኛውን የእውነት ገጽታ ከሌሎች የመነጠል መብት የላቸውም፡፡ ስለሆነም እያንዳንዱን የመጽ/ፍ ቅዱስ ክፍል ከመተርጎማችን በፊት የሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ ዓላማ መረዳት ይኖርብናል፡፡ ተናጠላዊ የሆኑት ክፍሎች ማለትም– ምዕራፎች፣ አንቀጾች፣ ወይም ቁጥሮች ሙሉው ክፍል ያላለውን የማይሉ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ ትርጓሜ ከሙሉ አጠቃላይ አቀራረብ ወደ ዝርዝር ክፍላዊ አቀራረብ መሆን ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም የዚህ የጥናት መመሪያ ሐተታ የተነደፈው ተማሪዎች የእያንዳንዱን ጽሑፋዊ ክፍል በአንቀጽ በመተንተን እንዲገነዘቡት ለመርዳት ነው፡፡ የአንቀጽን ሆነ የምዕራፍ ክፍሎች ተመስጧዊ አይደሉም፤ ነገር ግን የዋና ሐሳብ ክፍሎችን ለመገንዘብ ያስችሉናል፡፡

ዓረፍተ ነገርን፣ ንዑስ አንቀጽን፣ ሐረግን ወይም በቃል ደረጃ ሳይሆን በሙሉ አንቀጽ ደረጃ መተርጎም፣ የመጽሐፍ ቅዱሱን ጸሐፊ ዋነኛ ሐሳብ ለመረዳት ቁልፉ ነገር ነው፡፡ አንቀጾች ብዙውን ጊዜ የተመሠረቱት አንድነት ባለው ርዕስ፣ ማለትም ጭብጥ ወይም መሪ ዓረፍተ ነገር በሚባለው ነው፡፡ እያንዳንዱ ቃል፣ ሐረግ፣ ንዑስ አንቀጽ፣ እና ዓረፍተ ነገር በአንቀጹ ውስጥ ያለው፣ ይብዛም ይነስም ከዋነኛው ጭብጥ ጋር ይገናኛል፡፡ ይወስኑታል፣ ያስፋፉታል፣ ያብራሩታል፣ ብሎም/ወይም ይጠይቁታል፡፡ ለትክክለኛ ትርጓሜ ቁልፉ ነገር የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ መከተል ሆኖ አንቀጽ በአንቀጽ ላይ በተመሠረተ አካሄድ የመጽሐፍ ቅዱሱን መጽሐፍ ባስገኙት በተናጠላዊ የጽሑፍ ክፍል በሚደረግ አግባብ ነው፡፡ ይህ የጥናት መመሪያ የሆነ ሐተታ የተዘጋጀው ተማሪዎች አዲሶቹን የእንግሊዝኛ ትርጉሞች እያነጻጸሩ እንዲያዩ ለመርዳት ጭምር ነው፡፡ እነዚህ ትርጓሜዎች ተመራጭ የሆኑበት ምክንያት የተለያዩ የትርጓሜ ንድፈ-ሐሳቦችን በመጠቀማቸው ነው፡

1. የተባበሩት መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበረሰብ የግሪክ ቅጂ የተለከሰው አራተኛ እትም (የተመጽማ[4])፡፡ ይህ ጽሑፍ በዘመናዊ የጽሑፍ ሊቃውንት አንቀጹ ተሰናድቶለታል፡፡

2. አዲሱ የኪንግ ጀምስ ቅጂ (አኪጀቅ) ቃል በቃል የተደረገ ጥሬ ትርጉም ሲሆን የተመሠረተውም የግሪክ የእጅ ጽሑፍ ባህል በሆነው ቴክስተስ ሪሴፕትስ በሚባለው ነው። የአንቀጽ አደራደሩ ከሌሎቹ ትርጉሞች ረዘም ይላል። እነዚህ ረጃጅም ክፍሎች ተማሪዎች የተዋሐዱትን ርዕሶች እንዲረዱ ያስችላቸዋል።
3. አዲሱ የተከለሰው መደበኛ ትርጉም (አየተመት) ስልታዊ የሆነ የቃል በቃል ትርጉም ነው። እሱም የሚከተሉት ሁለት ዘመናዊ ቅጅዎች ማዕከላዊ የሆነ ነጥብ ይዟል። የአንቀጽ አደራደሩ ርዕሰ ጉዳዮችን ለመገንዘብ በእጅጉን ይረዳል።
4. የጊዜው እንግሊዝኛ ትርጉም (የጊእት) ዋነኛ አቻ ትርጉም ሲሆን በተባበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ሶሳይቲ (ማኅበረሰብ) የታተመ ነው። የመጽሐፍ ቅዱሱ ትርጉም የሚሞክረውም ዘመናዊ እንግሊዝኛ አንባቢ ወይም ተናጋሪ የግሪኩን ትርጉም እንዲረዳው ማድረግ ነው። በተለይ ደግሞ የወንጌላትን አንቀጾች የሚደረድረው በርዕሰ-ጉዳዩ ሳይሆን በተናጋሪው ቃል ነው የሚደረድረው፣ በአኢት እንደተደረገው። ለተርጓሚዎች ተግባር ይሄኛው የሚረዳ አይሆንም። እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ሁለቱም (የተየመቅሶ[4]) እና (የጊእት) የታተሙት በአንድ ዓይነት አህድ ሆኖ አንቀጻቸው ይለያያል።
5. የኢየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ (ኢመቅ) ዋነኛው አቻ ትርጉም ሲሆን በፈረንሳይ ካቶሊክ ትርጉም ላይ ነው። የአውሮጳውያንን የአንቀጽ አደራደር ስልት ለማነጻጸር በእጅጉን ይረዳል።
6. በ1995 የታተመው የተሻሻለው አዲሱ የአሜሪካን መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ (አአመመቅ)፣ የቃል በቃል ትርጉም ነው። ይህንን የአንቀጽ አደራደር ተከትሎም የየቁጥሩ አስተያየቶች ሰፍረዋል።

*ሦስተኛው መርሕ*

ሦስተኛው መርሕ ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስን የተለያዩ ትርጉሞችን በማንበብ ሰፋ ያለ የትርጉም አገባቦችን ማወቅ ይቻላል (በትርጉም መስክ) የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ወይም ሐረጎች የያዙትን። ብዙ ጊዜ የግሪክ ሐረግ ወይም ቃል በተለያየ መንገድ ነው መረዳት የሚቻለው። እነዚህ የተለያዩ ትርጉሞች እነዚህን አማራጮች በማቅረብ የተለያዩ የግሪክ አማራጭ ጽሑፎችን ለመለየት ያስችላሉ። ይህም መሠረተ እምነትን አይጻረርም፣ ዳሩግን ተመልሶ ወደ ዋናው ጽሑፍ በመውሰድ በተመስጦ የጻፈው የጥንቱ ጸሐፊ ጋ እንድንጓዝ ይረዱናል።

ይህ ሐተታ፣ ፈጠን ባለ ሁኔታ፣ ተማሪ የራሱን ትርጉሞች ይመረምር ዘንድ እንዲረዳው የታሰበ ነው። ይህም ማለት ግብ ሙሉ ለሙሉ ፍጹም ነው ማለት ሳይሆን መረጃ ሰጪ እና በጥልቀት እንድናስብ የሚያነቃቃ ነው። እርግጥ ሌሎች አማራጭ ትርጉሞችም ይረዱናል፣ አስተጋቢ፣ ቀኖናዊ፣ ወይም በመሠረተ እምነት የታጠርን እንዳንሆን። ተርጓሚዎች ሰፋ ያለ የትርጉም ዳርቻዎች እና አማራጮች ያሿቸዋል፣ የጥንቶቹ ጽሑፎች የቱን ያህል አሻሚ እንደነበሩ ለመረዳት። በጣም የሚረብሸው ነገር መጽሐፍ ቅዱስ የእውነት ምንጯችን ነው የሚሉት ክርስቲያኖችም ያላቸው ስምምነት ጥቂት መሆኑ ነው።

እነዚህ መርሖዎች ብዙዎቹን ታሪካዊ ችግሮቼን እንዳሸንፍ ረድተውኛል፣ ከጥንቱ ጽሑፍ ጋር እንድተጋ በማስገደድ። እርሶንም ደግሞ እንደሚባርክዎት ተስፋ አደርጋለው።

ቦብ አትሊ
ኢስት ተክሳስ ባፕቲስት ዩኒቨርሲቲ
ሰኔ 27፣1996

# ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ፡
# የተፈተነ እውነትን በግል ለመፈለግ

እውነትን ለማወቅ እንችላለን? የት ይገኛል? ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ለማረጋገጥ እንችላለን? የመጨረሻ ወሳኝ ይኖር ይሆን? ሕይወታችንንም ሆነ ዓለማችንን ሊመሩ የሚችሉ የተሟሉ (ፍጹማን) ይኖራሉ? ለሕይወት ትርጉም አለው? እዚህ መሆናችን ለምድነው? የትስ እንሄዳለን? እነዚህ ጥያቄዎች፣ አስተዋይ ሰዎች የሚሰላስሏቸውና ከዘመናት መጀመሪያ አንሥቶ የሰዎችን እውቀት የሚፈትሹ ናቸው (መክ. 1፡13-18፤ 3፡9-11)። የኔን ግላዊ ጥናት የማስታውሰው የሕይወቴ ዋነኛ ማዕከል አድርጌ ነው። በኢየሱስ አማኝ የሆንኩት በወጣትነት ጊዜዬ ነው፤ በቅድሚያም በዋነኛነት በሌሎች የቤተሰቤ አባላት ምስክርነት። እየጎለመስኩ ስመጣ ስለራሴም ሆነ ስለ ዓለሜ ያሉኝ ጥያቄዎች እያደጉ መጡ። ተራ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ድግግሞሾች ስለ አነበብኳቸውና ስለተረዳኋቸው የሕይወት ልምዶች፣ ትርጉም ሊሰጡ አልቻሉም። የውዥንብር ፤ የምርምር፣ የመናፈቅ እና ብዙውን ጊዜም ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ነበር፣ በምኖርበት በድን በሆነው ደንዳና ዓለም ውስጥ።

ለእነዚህ ዋነኛ ጥያቄዎች ብዙዎች ምላሽ እንዳላቸው ይናገራሉ፣ ነገር ግን ከፍተሻ እና ከማገናዘብ በኋላ የእነሱ መልሶች የተመሠረቱት (1) በግል የሕይወት ፍልስፍናዎች፣ (2) በጥንታዊ አፈ-ታሪኮች፣ (3) በግል የሕይወት ልምዶች፣ ወይም (4) በሥነልቦናዊ ቅድመ እይታዎች ላይ ነው። በማስተዋል የሆነና ስለ ዓለም ያለኝ አመለካከት መሠረት፣ የሕይወቴ ዋነኛ ማዕከል፣ የመኖሬ ዋነኛ ምክንያት ላይ ማረጋገጫ አስፈልጎኝ ነበር፣ ማስረጃ።

እነዚህን መጽሐፍ ቅዱስን ሳጠና አገኘኋቸው። ታማኝ እንዲሆንም ማስረጃ መፈለጌን ጀምሬ ያገኘሁትም፣ (1) በጥንታዊ ቅርስ ምርምር ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የተገኘው ታሪካዊ ማረጋገጫ፣ (2) የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ትክክለኛለት፣ (3) በአስራ ስድስት መቶ የመጻፍ ጊዜው ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ የመልእክት ኅብርና መኖር እና (4) ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ከተገናኙ በኋላ ፍጹም የሕይወት ለውጥ ያገኙት ሰዎች የግል ምስክርነት ናቸው። ክርስትና ኅብር እንዳለው የእምነትና የሃይማኖት ሥርዓት የሰው ልጆችን ውስብስብ ጥያቄዎች የመመለስ ችሎታ አላቸው። ይህን በማድረግም የማስተዋል ውቅር ብቻ አይሰጥም፣ ነገር ግን በፍትነታዊ ገጽታው የመጽሐፍ ቅዱስ እምነት የስሜት ደስታ እና መረጋጋትን ይሰጣል።

እንደማስበው፣ የሕይወቴን ዋነኛ ማዕከል– ክርስቶስን በቃሉ ውስጥ አግኝቼዋለሁ። በሕይወት ልምዴ ንቁ እና ስሜተ-ስሱ ነበርኩ። ቢሆንም እስካሁን ድረስ የማስታውሰው ወገግ ሊልልኝ ሲል የነበረብኝን ነውጥ እና ሥቃይ ሲሆን፣ የቱን ያህል የመጽሐፉ ትርጓሜዎች እንደሚከራከሩና፣ አልፎ አልፎም በአንድ አብያተ ክርስቲያን እና አስተምህሮዎች እንዳሉ ሳይ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን የተመስጠ መሆንና ጠቃሚነቱን ማረጋገጥ የመጨረሻው ሳይሆን የመጀመሪያው ብቻ ነው። የተለያዩ እና ተቃርኖ ያላቸውን የመጽሐፉን ከባባድ አንቀጾች ትርጓሜዎች፣ ሁሉም ትክክለኛ እና በሥልጣን ነን እያሉ እንዴት አድርጌ እንደምቀበል ወይም እንደምተው ሳውቅ እችላለሁ?

ይህም ተግባር የሕይወቴ ግብ እና የእምነቴ ምናኔ ሆነ። የተረዳሁት ነገር በክርስቶስ ያለኝ እምነት፣ (1) ታላቅ ሰላምና ደስታ እንዳመጣልኝ፣ (2) የተቀናቃኝ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች (የዓለም ሃይማኖቶች) ቀኖናዊነት፤ እና (3) የአንድ ክፍለ ሃይማኖት ዕብሪተኝነት እንዳለበት ተረድቻለሁ። የጥንታዊውን ሥነ ጽሑፍ ትርጓሜ ተገቢ ዋጋ ያለው ፍለጋዬን ሳካሂድ ያስደነቀኝ ነገር ቢኖር የራሴን የግሌን ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ክፍለ ሃይማኖታዊ እና በሕይወት ልምድ አድልኦዎች መለየት ነው። የራሴን አመለካከት ለማጠናከር መጽሐፍ ቅዱስን እንደዋዛ አዘውትሬ አነባለሁ። የራሴን ያልተሟላ ዋስትናና የብቃት ማነስ ሲያመላክተኝ ሌሎችን የማጠቃበት ቀኖናዊ ምንጭ አድርጌ እወስደዋለሁ። ይህንን ሀቅ መረዳት ለእኔ የቱን ያህል አስቸጋሪ ነበር!

ምንም እንኳ የተሟላ ተጨባጭነት ባይኖረኝም የመጽሐፍ ቅዱስ ደኅና አንባቢ ለመሆን እችላለሁ። ያሉብኝን አድሏዊነቶች ለመለየትና እንዳሉም እውቅና በመስጠት የተወሰኑ ሳደርጋቸው እችላለሁ። ከእነሱ ገና አሁንም ነጻ አይደለሁም፣ ነገር ግን ከራሴ ድክመት ተሟግቻለሁ። ተርጓሚ ዘወትር የመልካም መጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ጠላት እንደሆነ ነው!

እስቲ ጥቂት ቅድመ ግምቶችን፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቴ ያገኘኋቸውን እርሶ አንባቢው ከእኔ ጋር ሆነው ይመረምሯቸው ዘንድ ልዘርዝራቸው፡

I. ቅድመ ግምቶች

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ተመስጧዊ የሆነ የእውነተኛው አምላክ የራሱ መገለጥ መሆኑን አምናለሁ። ስለሆነም፣ መተርጎም ያለበት በዋነኛው መነሻ ብርሃን መለኮታዊ ጸሐፊ (መንፈስ) ሆኖ በተወሰነ ታሪካዊ ወቅት በነበረ ሰው ጸሐፊነት ነው።

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ለተራ ሰዎች፣ ለሁሉም ሰዎች እንደተጻፈ አምናለሁ! እግዚአብሔር ለእኛ በግልጽ ለመናገር በታሪካዊና በባህላዊ አግባብ ራሱን አዘጋጅቶልናል። እግዚአብሔር እውነትን

አይሸሽግም– እንድንረዳው ይፈልጋል! ስለሆነም በእኛ ሳይሆን በራሱ ጊዜ ብርሃን የግድ መተርጎም አለበት:: መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ ከሰሙት ወይም ካነበቡት በተለየ መንገድ የምንረዳው ማለት አይደለም:: በተራ ሰው ልቦና ሊረዱት የሚችል እና ተገቢ የሆነ የሰው ልጆች መግባቢያ አግባቦችና ስልቶችን የሚጠቀም ነው::

ሐ. መጽሐፍ ቅዱስ ኅብር ያለው መልእክትና ተግባር እንዳለው አምናለሁ:: ምንም እንኳ አያአዎአዊ የሆኑ አንቀጾች ቢኖሩትም ራሱን በራሱ አይቃረንም:: ስለሆነም፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ዋነኛው ተርጓሚ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ነው::

መ. እያንዳንዱ አንቀጽ (ትንቢታትን ጨምሮ) አንድ እና አንድ ብቻ ትርጉም እንዳላቸውና ይህም በዓይነተኛው ተመስጧዊ ጸሐፊ መነሻ ሐሳብ መሆኑን አምናለሁ:: ምንም እንኳ ፍጹም ርግጠኞች ባንሆንም የዓይነተኛውን ጸሐፊ ሐሳብ እንረዳዋለን፣ ብዙ ጠቋሚዎች አቅጣጫውን ስለሚያመላክቱን፡

1. የዘውግ (የሥነ ጽሑፋዊ) ዓይነቱ፣ መልእክቱን ለማስተላለፍ የተፈለገበት
2. ጽሑፉ ሊያወጣ የፈለገው እውነት ታሪካዊ ዳራ እና /ወይም የተለየ ዐውድ
3. የአጠቃላይ የመጽሐፉ ሥነ ጽሐፋዊ ሁኔታ እና እንዲሁም የእያንዳንዱ የጽሑፍ አሀድ
4. ጽሑፋዊ ንድፉ (ዋና ዋና ይዘቱ) ማለትም የእያንዳንዱ ጽሑፍ አሀድ ከአጠቃላይ መልእክቱ ጋር ያለው ዝምድና
5. መልእክቱን ለማስተላለፍ የተጠቀመበት የተለየ ሰዋሰዋዊ ባሕርይ
6. መልእክቱን ለማቅረብ የተመረጡት ቃላት
7. ትይዩ አንቀጾች

በእነዚህ በእያንዳንዳቸው አካባቢ የሚደረገው ጥናት በአንቀጽ ላይ የምናደርገው ጥናት ዓላማ ሆኗል:: ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚሆነውን የእኔን ዘዴ ከመግለጤ በፊት ጥቂት ተገቢ ያልሆኑ በአሁን ጊዜ ጥቅም ላይ በመዋል ላይ ያሉትንና በርካታ የተለያዩ ትርጉሞች እንዲፈጠሩ ያደረጉትና የግድ መወገድ ያለባቸውን ላመላክት፡

## II. ተገቢ ያልሆኑ ዘዴዎች

ሀ. የመጽሐፍ ቅዱስን መጻሕፍት ሥነጽሑፋዊ ዐውድ ችላ በማለት እያንዳንዱን ዓረፍተ ነገር፣ ሐረግ እንዲያውም ግለሰባዊ ቃላትን እንደ እውነታዊ መግለጫ፣ ከጸሐፊው ዓላማ ባልተገናኘ መልኩ ወይም ከሰፊው የጽሑፉ ክፍል ጋር ባልተያያዘ ሁኔታ መውሰድ:: ይህም ዘወትር "የጽሑፍ ማጣራት" ይባላል::


ለ. የመጻሕፍቱን ታሪካዊ ዐውድ ችላ በማለት እና በግምታዊ ታሪካዊ ዳራ በመቀየር ከጽሑፉ ጋር መጠነኛ ግንኙነት ወይም ምንም ዓይነት ድጋፍ በሌላቸው ጋር ማያያዝ

ሐ. የመጻሕፍቱን ታሪካዊ ዐውድ ችላ በማለት እንደ አካባቢያዊ የጧት ጋዜጣ ዓይነት ቀድኖውኑ ለዘመናዊ ክርስቲያን እንደተጻፈ ዓይነት ማንበብ


መ. የመጻሕፍቱን ታሪካዊ ዐውድ ችላ በማለት ለጽሑፉ ተምሳሌታዊ ፍቺ በመስጠት ፍልስፍናዊ/ሥነ-መለኮታዊ በማድረግ በመጀመሪያ ቃሉን ከሰሙት እና ዋናው ጸሐፊ ሊል ከፈለገው ሐሳብ በማይገናኝ መልኩ መያዝ

ሠ. ዋነኛውን መልእክት ችላ በማለትና የራስን የሥነ-መለኮት ሥርዓት፣ አባባይ መሠረተ- እምነት፣ ወይም የወቅቱን ጉዳይ በመቀየር፣ እና ከማይገናኝ ጋር በማያያዝና፣ ዋናው ጸሐፊ ሊል ከፈለገው ቁምነገርና ከተቀመጠው መልእክት መውጣት:: ይህ የአካሄድ ክስተትም ዘወትር የሚደረገው የተናጋዊውን ሐሳብ ለማጠናከር በቅድሚያ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማንበብን ነው:: ይህን ዘወትር፣ "የአንባቢ ምላሽ" ("ጽሑፉ ለእኔ የሚሰጠኝ" ትርጉም ተብሎ ይታወቃል::

በሰዎች የጽሑፍ መግባቢያ ላይ ቢያንስ ሦስት አካላት ያስፈልጋሉ፡



ቀደም ሲል የተለያዩ የምንባብ ስልቶች ከሦስቱ በአንደኛው ክፍሎች አተኩረው ነበር። ነገር ግን በእውነት ለማጽናት ልዩ የሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ ተመስጦ የተሻሻለው ንድፍ ይበልጥ ተገቢነት አለው።




እንደ እውነቱ ሦስቱም አካሎች በትርጓሜ ሂደት የግድ መካተት ይኖርባቸዋል። ለማረጋገጥ ያህልም የእኔ ትርጓሜ ያተኮረው በቀዳሚዎቹ በሁለቱ አካላት ላይ ነው፡ ዋነኛው ጸሐፊ እና ጽሑፉ። ምናልባት የእኔ ተቃርኖ ባስተዋልኩት ተገቢ ያልሆነ ሁኔታ ላይ ይሆናል። (1) ተምሳሌታዊ ወይም መንፈሳዊ በተደረጉ ጽሑፎች እና (2) "የአንባቢ ምላሽ" (ለእኔ የሚረዳኝ) ትርጓሜዎች። በዛባት በሁሉም ደረጃ ላይ ሊከሰት ይችላል። ዘወትር የእኛን መሻት፣ አድሏዊነት፣ አግባብ፣ እና አፈጻጸማችንን መመርመር ይኖርብናል። ምንም ዓይነት ወሰኖች ለትርጉሞች በሌሉበትኝ፣ ገደብና መስፈርት በሌለበት እንዴት አድርገን መፈተሽ እንችላለን? ለዚህ ነው የጸሐፊው መነሻ ሐሳብና የጽሑፉ አወቃቀር የተወሰኑ መስፈርቶችን ሰጥቶኝ ዳራውን ለመወሰንና ተገቢ የሆነ ይሁንታ ያለው ትርጓሜ እንዳደርግ ያስቻለኝ።

በእነዚህም ተገቢ ባልሆኑ ስልቶች ጭላንጭል ምን ዓይነት ታሳቢ አግባቦች ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ እና ትርጓሜ በተረጋገጠ ደረጃ የሚያመጡ እና ቋሚነት ያላቸው ሊኖሩ ይችላሉ?

## III. ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ተገቢ አገባቦች

በዚህ ነጥብ የተወሰኑ የትርጓሜ ዘውጎችን የተለዩ ስልቶችን አላብራራም፤ ነገር ግን ለሁሉም ዓይነት የቅዱሳን መጻሕፍት አጠቃላይ የጽሑፍ ትርጓሜ ተገቢ መርሖዎች ላይ ነው። ለተወሰነ ዘውጋዊ አግባብ መልካም የሆነው መጽሐፍ፣ መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ ጠቀሜታው እንዴት እንደሚነበብ፣ በጎርደን ፊ እና ዳግላስ ስቱአርት፣ በዞንደርቫን የታተመው ነው።

የኔ ዘዴ በመነሻው ያተኮረው አንባቢ ለመንፈስ ቅዱስ መጽሐፍ ቅዱስን ያበራላቸው ዘንድ ሲፈቅዱ የሚያልፉባቸውን አራት የግል የንባብ ዑደቶችን ነው። ይህም መንፈስን፣ ጽሑፉን እና አንባቢውን ቀዳሚ ያደርጋቸዋል፣ ተከታይ ሳይሆን። ይህም ደግሞ አንባቢው በተንታኞች ሐሳብ አለቅጥ እንዳይወሰድ ያደርገዋል። ሲባል የሰማሁትም፣ "መጽሐፍ ቅዱስ እጅግ ብርሃን በሐተታዎች ላይ ያበራል" የሚል ነው። ይህም ማለት ግን የጥናት መርጃዎችን ለማንኳሰስ አይደለም፣ ነገር ግን ለአጠቃቀማቸው ተገቢ ጊዜ ማስፈለጉን ለማመላከት ነው እንጂ።

ትርጓሜዎቻችንን ከቃሉ ከራሱ ለማስደገፍ መቻል ይኖርብናል። አምስቱ አካባቢዎች ምናልባት የተወሰኑ የእውነት ማረጋገጫ ይሰጡናል፡

1. የዋናው ጸሐፊ
   ሀ. ታሪካዊ መቼት
   ለ. ሥነ-ጽሑፋዊ ዐውድ
2. የዋናው ጸሐፊ ምርጫ
   ሀ. ሰዋሰዋዊ መዋቅር (አገባብ)
   ለ. የተመሳሳይ ሥራዎች አጠቃቀም
   ሐ. የጽሑፍ ዓይነት (ዘውግ)
3. የእኛ ተገቢ የሆነውን የመረዳት ችሎታ
   ሀ. ጠቃሚ ትይዩ አንቀጾች

ከትርጓሜአችን ጀርባ ምክንያቶችንና አመክኖዎችን (ሎጂክ) ማሳየት መቻል አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ ብቸኛው የእምነትና የድርጊት ምንጫችን ነው። ቢያሳዝን መልኩ፣ ክርስቲያኖች በሚያስተምረው ወይም በሚያጸናው ላይ ዘወትር አይስማሙም። ይህም መጽሐፍ ቅዱስ ተመስጧዊ መሆኑን ተቀብሎ ከዚያም አማኞች ለሚያስተምረውም ሆነ ለሚጠይቀው ላለመስማማት መቻል በራስ እንደመሸነፍ ነው!

አራቱ የንባብ ዑደቶች የተነደፉት የሚከተለውን ጠለቅ ያለ ትርጓሜ ለመስጠት ነው።

ሀ. የመጀመሪያው የንባብ ዑደት

1. መጽሐፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ ያንብቡት። ከተለያዩ የትርጉም ንድፈ ሐሳቦች አገኛለሁ ብለው ተስፋ በማድረግ በድጋሚ በተለያዩ ትርጉሞች ያንብቡት
   ሀ. ቃል በቃል (አኪጀት፣ አአሰመቅ፣ አየተመት)
   ለ. ንቁ ቀጥተኛ (የአእቅ፣ ኢመቅ)
   ሐ. ማብራሪያ (ሕያው ቃል፣ የተብራራ መጽሐፍ ቅዱስ)
2. የሙሉ ንባቡን ማዕከላዊ ሐሳብ ይፈልጉ። ጭብጡን ይግለጡት።
3. የጽሑፋዊ አሀዱን (ከተቻለ) ይለዩት፤ ምዕራፍ፣ አንቀጽ ወይም ዓረፍተ ነገር በትክክል ሊያብራራ የሚችለውን፣ የጭብጡን ማዕከላዊ ሐሳብ ለማግኘት።
4. ዋነኛውን ገዢ የሥነ-ጽሑፋዊ ጭብጥ ዘውግ (ዓይነት) ይግለጡት
   ሀ. ብሉይ ኪዳን
      (1) ይዕብራይስጥ ትረካ
      (2) የዕብራይስጥ ቅኔ (መጽሐፈ- ጥበብ፣ መዝሙራት)
      (3) የዕብራይስጥ ትንቢት (ስድ ንባብ፣ ቅኔ)
      (4) ሕግጋት
   ለ. አዲስ ኪዳን
      (1) ተራኪ (ወንጌላት፣ ግብረ-ሐዋርያት)
      (2) ምሳሌዎች (ወንጌላት)
      (3) ደብዳቤዎች/መልዕክቶች
      (4) ትንቢታዊ ሥነ-ጽሑፍ

ለ. ሁለተኛው የንባብ ዑደት
1. ሙሉ መጽሐፉን እንዳለ በድጋሚ ያንብቡት፣ ዋናውን ርልሰ-ጉዳይ፣ ቁም-ነገሮች ለመለየት ፈልጉ
2. ዋናዎቹን ርዕሶች በዋና ሐሳብ ለይተው አጠር ባለ እና በቀላል መግለጫ ይዘቱን ያስቀምጡ
3. የድርጊት መግለጫውን ይፈትሹና ሰፋ ያለ የርዕሰ ጉዳይ ዝርዝር በጥናት መርጃ ይጠቀሙ

ሐ. ሦስተኛው የንባብ ዑደት
1. ሙሉ መጽሐፉን በድጋሚ ያንብቡት፣ ለጽሑፉ ታሪካዊ መቼትና የተለየ ዐውድ ለማግኘትና ለመለየት ከራሱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይሞክሩ.
2. በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱትን ታሪካዊ ዓይነቶች ይዘርዝሩ
   ሀ. ጸሐፊው
   ለ. ዘመኑ
   ሐ. ተቀባዮች
   መ. ለመጻፍ የተለየ ምክንያት
   ሠ. ከመጽሐፉ ዓላማ ጋር የተያያዙ ባህላዊ መቼቶች ገጽታ
   ረ. ከታሪካዊ ሰዎችና ሁነቶች የሚጠቀሱ
3. የምትተረጉመውን ያንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የዋና ፍሬ ሐሳቡን ዝርዝር ወደ አንቀጽ ደረጃ አስፋፉት። ዘወትር የሥነ ጽሑፉን አሀድ ለዩት፣ እንዲሁም የፍሬ ሐሳቡን ዝርዝር አውጡ። ይህም ምናልባት በርካታ ምዕራፎች ወይም አንቀጾች ይሆናል። ይህም የዋናውን ጸሐፊ የሐሳብ ተገቢነት (ሎጂክ) ጽሑፋዊ ንድፍ ለመከተል ያስችልዎታል።
4. የጥናት መረጃዎችን በመጠቀም የርሶን ታሪካዊ መቼት ይፈትሹ።

መ. አራተኛው የንባብ ዑደት
1. የተለየውን የጽሑፍ ክፍል በልዩ ልዩ ትርጉሞች ያንብቡት
   ሀ. ቃል በቃል (አኪጀት፣ አአሰመቅ፣ አየተመት)
   ለ. ንቁ አቻ (የአእቅ፣ ኢመቅ)
   ሐ. ማብራሪያ (ሕያው ቃል፣ የተብራራ መጽሐፍ ቅዱስ)
2. ሥነ-ጽሑፋዊ ወይም ሰዋሰዋዊ መዋቅሮችን ይፈልጉ
   ሀ. ተደጋጋሚ ሐረጎች፣ ኤፌ. 1፡6፣12፣13
   ለ. ተደጋጋሚ ሰዋሰዋዊ መዋቅሮች፣ ሮሜ. 8፡31
   ሐ. ተጻጻሪሪ ጽንሰ-ሐሳቦች
3. የሚከተሉትን ዓይነቶች ይመዝግቡ
   ሀ. ወሳኝ ቃላት
   ለ. ያልተለመዱ ቃላት
   ሐ. ዋነኞቹ ሰዋሰዋዊ መዋቅሮች
   መ. የተለዩ አስቸጋሪ ቃላት፣ ሐረጎች፣ እና ዓረፍተ ነገሮች
4. ዋነኞቹን ትይዩ አንቀጾች ይለዩ

ሀ. ከርዕስ ጉዳዩ ጋር በጣም ግልጽ የሆነውን የማስተማሪያ አንቀጽ ይፈልጉ
(1) "ስልታዊ ሥነ-መለኮት" መጻሕፍት
(2) የማጣቀሻ መጽሐፍ ቅዱስ
(3) የቃላት ዝርዝር
ለ. በርዕሰ ሐሳብህ ዙሪያ ተስማሚ አያዎአዊ ጥንዶችን ከጽሑፉ ይፈልጉ:: አብዛኞቹ የቅዱሳት መጻሕፍት እውነታዎች የሚቀርቡት በአከራካሪ ጥንዶች ነው፤ በርካታ የመሠረተ እምነት ግጭቶች የሚመነጩት ከጽሑፍ አቃቂር ማውጣት ማለትም ከፊል ከሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ክርክሮች ነው:: መላው መጽሐፍ ቅዱስ ተመስጧዊ ነው፣ እኛም የተሟላውን መልዕክት በመፈለግ፣ የመጽሐፍ ቅዱስን ሚዛን በትርጓሜአችን መጠበቅ ይኖርብናል::
ሐ. በዛው በመጽሐፉ ውስጥ ፣ በዛው ጸሐፊ ወይም በዛው የሥነ ጽሐሁፍ ዓይነት፣ አቻዊ ትይዩ ይፈልጉ፤ መጽሐፍ ቅዱስ የራሱ ምርጥ ተርጓሚ ነው፤ ምክንያቱም፣ አንድ ብቸኛ ጸሐፊ ስላለው– መንፈስ ቅዱስ::

5. ታሪካዊ መቼቱንና የተለየ ዐውዱን ለመፈተሽና ለማስተዋል የጥናት መረጃዎችን ይጠቀሙ::
ሀ. የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ
ለ. የመጽሐፍ ቅዱስ ዐውደ-ጥበባት፣ መምሪያ መጻሕፍ እና መዝገበ ቃላት
ሐ. የመጽሐፍ ቅዱስ መግቢያዎች
መ. የመጽሐፍ ቅዱስ ሐተታዎች (በዚህ ነጥብ ላይ በጥናትዎ፣ አማኝ የኅብረተሰብ ክፍሎችን፣ ማለትም የቀደምቱም ሆኑ ያሁኖቹ የራስዎን ጥናት ለማገዝና ለማረም ይጠቀሙባቸው::)

## IV. የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ አተገባበር

በዚህ ነጥብ ወደ አተገባበር እንቃኛለን:: ጽሑፉን ከዋናው መቼት አንጻር ለመረዳት ጊዜ ወስደዋል፤ አሁን ደግሞ ይሄንኑ በሕይወትዎ፣ በባህልዎ ሊተገበሩት ይገባል:: የመጽሐፍ ቅዱስ የመረዳት ሥልጣን ማለት በእኔ አገላለጽ፣ "ዋናው የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊ በእሱ ጊዜ ሊለው የፈለገውን መረዳትና ያንን በራሳችን ጊዜ መተርበር" ማለት ነው::

ድርጊት መከተል ያለበት የዋናውን ጸሐፊ የትርጓሜ ሐሳብ በጊዜም ሆነ በሎጂክ አኳያ ነው:: የመጽሐፍ ቅዱስን አንቀጽ በጊዜው ምን ለማለት እንደፈለገ እስካላወቅን ድረስ በዘመናችን ልንተገብረው አንችልም! የመጽሐፍ ቅዱስ አንቀጽ ሊለው ያልፈለገውን ፈጽሞ ሊሆን አይችልም!

የእርስዎ የተዘረዘረ የዋና ሐሳቦች ዝርዝር በአንቀጽ ደረጃ (የንባብ ዑደት ቁጥር 3)፣ የእርስዎ መመሪያ ይሆናል:: ትግበራ መደረግ ያለበት በአንቀጽ ደረጃ እንጂ በቃላት ደረጃ መሆን የለበትም:: ቃላት ትርጉም የሚኖራቸው በከፊል- ጽሑፍ ደረጃ ነው፤ ሐረጎች ትርጉም የሚኖራቸው በከፊል- ጽሑፍ ደረጃ ነው፤ ዓረፍተ ነገሮች ትርጉም የሚኖራቸው በከፊል- ጽሑፍ ደረጃ ነው:: ብቸኛው ተመስጧዊ ሰው በትርጓሜው ሂደት ውስጥ ዋነኛ ጸሐፊው ነው:: በመንፈስ ቅዱስ አብራሪነት (ማብራሪያ) የእሱን ምሪት ብቻ መከተል ይኖርብናል:: ማብራሪያ ግን ተመስጦ ማለት አይደለም:: "እግዚአብሔር እንደዚህ ይላል፣" ለማለት ከዋናው ጸሐፊ ሐሳብ ጋር የግድ መኖር አለበት:: ትግበራ በተለይ መያያዝ ያለበት በሙሉ መጽሐፉ ሐሳብ ላይ ሲሆን፣ የተለየው የጽሑፍ አሀድ እና በአንቀጽ ደረጃ እያደገ በሚሄድ መልኩ::

የዘመናችን ጉዳዮች መጽሐፍ ቅዱስን እንዲተረጉሙ አትፍቀዱ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገር! ይህ ምናልባት የተወሰኑ ከጽሑፉ እንድናወጣ ይጠይቀን ይሆናል:: ይህም ተገቢ የሚሆነው ጽሑፉ ለመርሖቹ ድጋፍ ሲሆን ነው:: በሚያሳዝን መልኩ ግን፣ ብዙውን ጊዜ የእኛ መርሖዎች፣ "የእኛ" መርሖዎች ናቸው– የጽሑፉ መርሕ በመሆን ፈንታ::

መጽሐፍ ቅዱስን ለመተግበር፣ (ከትንቢት ብቻ በቀር) ማስታወስ የሚገባን ጠቃሚ ነገር ለእያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አንድና አንድ ብቻ ትርጉም እንዳለው ነው:: ያም ትርጉም ግንኙነቱ ከዋናው ጸሐፊ ሐሳብ ጋር፣ እሱም የዘመኑን ውድቀትም ሆነ ፍላጎት እንዴት እንዳቀረበው ነው:: በርካታ ተስማሚ ድርጊቶች ከዚህ ከአንዱ ትርጉም ሊመነጩ ይችላሉ:: አተገባበሩም የሚመሠረተው በተቀባዮቹ መሻት ላይ ሆኖ፣ መገናኘት ያለበት ግን ከዋናው ጸሐፊ ሐሳብ ላይ ነው::

## V. የትርጓሜ መንፈሳዊ ገጽታዎች

እስካሁን አመክኖአዊ የሆነ እና የሥነ ጽሑፋዊ ሂደት በምን መልኩ በትርጉምና በአተገባበር ላይ መሆን እንዳለበት ለማብራራት ሞክሬአለሁ:: አሁን ደግሞ ስለ ትርጉም መንፈሳዊ ገጽታ በአጭሩ ላብራራ:: የሚከተሉት የመቆጣጠሪያ ዝርዝሮች ረድተውኛል:

ሀ. ለመንፈስ ርዳታ ይጸልዩ (1ኛ ቆሮ. 1:26-2:16)::
ለ. ከሚታወቅ ኃጢአት በግልዎ ምሕረትንና መንጻትን እንዲያገኙ ይጸልዩ (1ኛ ዮሐንስ 1:9)::

ሐ. ስለ እግዚአብሔር ለማወቅ ከፍተኛ ፍላጎት እንዲያድርብዎ ይጸልዩ (መዝ. 19፡7-14፤ 42፡1፤ 119፡1)።

መ. አዲስ ማስተዋልን በሕይወትዎ ወዲያውኑ ይተግብሩ።

ሠ. ትሑትና ለመማር የተዘጋጁ ይሁኑ።

በሎጂካዊ ሂደት እና በመንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ መሪነት መካከል ያለውን ሚዛን ለመጠበቅ በጣም አዳጋች ነው። የሁለቱን ሚዛን ለመጠበቅ የሚከተሉት ጥቅሶች ረድተውኛል፡

ሀ. ከ ጀምስ ደብሊዩ. ሲር፣ *ቃሉን መጠምዘዝ (ማጣመም)* ገጽ 17-18

*"ማብራሪያ የሚመጣው ወደ እግዚአብሔር ሕዝቦች ሐሳብ ነው– ወደ መንፈሳዊ ምሑር ሳይሆን። በመጽሐፍ ቅዱስ ክርስትና የተለየ የመማሪያ ክፍል የለም፣ ምንም የተለየ የሚያብራራ፣ ተገቢው ትርጓሜ የሚመጣላቸው የተለዩ ሰዎች የሉም። እና ስለዚህ፣ መንፈስ ቅዱስ ልዩ የጥበብ፣ የእውቀት፣ እና መንፈስን የመለየት ጸጋ ሲሰጥ፣ እነዚህ ባለጸጋ ክርስቲያኖች ብቻ የቃሉ ሥልጣናዊ ተርጓሚዎች እንዲሆኑ መመደቡ አይደለም። ሁሉም የራሱ ሕዝቦች ሊማሩ፣ ሊዳኙ እና ሊለዩ፣ በእነሱ፣ እግዚአብሔር የተለየ ችሎታ ለሰጣቸው እንኳ ሥልጣን ያለውን መጽሐፍ ቅዱስ መጥቀስ እንደሚችሉ ነው። ለማጠቃለል፣ በሙሉው መጽሐፍ ያቀረብኩት ሐሳቤ መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛው የእግዚአብሔር መገለጥ ለሰው ልጆች ሁሉ ነው፣ በሚናገረው ሁሉ የመጨረሻው ባለሥልጣን ነው፤ በጥቅሉ ምሥጢራዊ ሳይሆን በማንኛው ባህል ባሉ ተራ ሰዎች በበቂ መልኩ ለመረዳት የሚቻል ነው።"*

ለ. በኬርክጋርድ፣ በቤርናንድ ራም በሚገኘው፣ የፕሮቴስታንት የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ፣ ገጽ 75፡

እንደ ኬርክጋርድ ከሆነ ሰዋሰዋዊ፣ ቃላዊ፣ እና ታሪካዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች አስፈላጊ ናቸው፤ መቅደም ያለበት ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ልባዊ ንባብ ነው። "መጽሐፍ ቅዱስን እንደ እግዚአብሔር ቃል ለማንበብ፣ ማንም አፍ ከልብ ሆኖ፣ በተጠንቀቅ ሆኖ፣ በጉጉትና ተስፋ በማድረግ፣ ከእግዚአብሔር ጋር እየተነጋገረ ማንበብ አለበት። መጽሐፍ ቅዱስን በሐሳበ ቢስነት ወይም በግዴለሽነት ወይም እንደ ትምህርት ወይም እንደ ልዩ ሞያ ማንበብ መጽሐፍ ቅዱስን እንደ እግዚአብሔር ቃል ማንበብ አይደለም። አንዱ የፍቅር ደብዳቤ እንደሚነበብ የሚያነበው ከሆነ እሱ እንደ እግዚአብሔር ቃል እያነበበው ነው።"

ሐ. ኤች. ኤች. ሮውሊ *በየመጽሐፍ ቅዱስ ጠቀሜታ*፣ ገጽ 19፡

"የተሻለ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሑራዊ መረዳት፣ ምንም ያህል ፍጹም ቢሆን ሁሉንም ሀብቶች ሊያስገኝ አይችልም። ይህን መሰሉን መረዳት ዝቅ ለማድረግ አይደለም፣ ለፍጹም መረዳት አስፈላጊ ነው። ነገር ግን ፍጹም ይሆን ዘንድ ወደ መጽሐፉ መንፈሳዊ ሀብቶች የሚያመራ መንፈሳዊ መረዳት ማስፈለጉን ለማሳየት ነው። እናም ለዛ መንፈሳዊ መረዳት ከምሑራዊ ንቁነት የተሻለ ነገር ያስፈልጋል። መንፈሳዊ ነገሮች በመንፈሳዊነት የሚለዩ ናቸው፤ እናም የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ የመንፈሳዊ ተቀባይነት አዝማሚያ ሊኖረው ይገባል፣ ራሱን ይሰጥ ዘንድ እግዚአብሔርን ለመፈለግ ጉጉት ያለው፣ ከሳይንሳዊ ጥናቱ ባሻገር ወደ ተትረፈረፈ ሀብት ወራሽነት ወደሚያስገኝ ወደዚህ ከመጻሕፍት ሁሉ ታላቅ ወደ ሆነ።"

## VI. የሐተታው ዘዴ

*የጥናት መመሪያ ሐተታው የተሰናዳው የእርስዎን የትርጉም አግባብ በሚከተሉት መንገዶች ለማገዝ ነው፡*

ሀ. እያንዳንዱን መጽሐፍ የሚያስተዋውቅ አጭር ታሪካዊ የዋና ሐሳብ መግለጫ። "የንባብ ዑደት ቁጥር 3" ካነበበቡ በኋላ ይህን መረጃ ያረጋግጡት።

ለ. ጽሑፋዊ ማብራሪያዎች በየአንዳንዱ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ ይገኛል። ይህም ሥነ ጽሑፋዊ አሀዱ እንዴት እንደተዋቀረ ለመመልከት ይረዳል።

ሐ. በእያንዳንዱ ምዕራፍ ወይም ሥነ ጽሑፋዊ አሀድ፣ የአንቀጽ ክፍሎች እና መግለጫ ጽሑፎች ከተለያዩ በርካታ ዘመናዊ ትርጉሞች ተሰጥተዋል፡

1. የመጽሐፍ ቅዱስ ኅብረት ሶሳይቲ የግሪክ ጽሑፍ፣ አራተኛ እትም (የተመቅሶ)
2. አዲሱ የአሜሪካ መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ፣ 1995 የተሻሻለ (አአመመቅ)
3. አዲሱ ኪንግ ጀምስ ዕትም (አኪጀዕ)
4. አዲሱ የተከለሰው መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ (አየመመቅ)
5. አዲሱ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ (አእመቅ)
6. ኢየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ (ኢመቅ)

*የአንቀጽ ክፍሎች ተመስጧዊ አይደሉም። ከጽሑፉ መረጋገጥ ይኖርባቸዋል። ከተለያዩ የትርጉም ንድፈ ሐሳቦች እና ሥነመለኮታዊ አስተሳሰቦች የተለያዩ ዘመናዊ ትርጉሞችን በማወዳደር የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን ለመተንተን እንችላለን። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድ ዋነኛ እውነት ይዟል። ይህም "መሪ ዓረፍተ ነገር" ወይም "የጽሑፉ ማዕከላዊ ሐሳብ" ተብሎ ይጠራል። ይህም ኅብር ያለው*

ሐሳብ አግባብነት ላለው ታሪካዊ፣ ሰዋሰዋዊ ትርጉም ቁልፉ ነው። ማንም ከአንድ አንቀጽ ባነሰ መተርጎም፣ መስበክ ወይም ማስተማር አይኖርበትም! በተጨማሪም እያንዳንዱ አንቀጽ ከአካባቢው አንቀጾች ጋር እንደሚዛመድ አስታውሱ። ለዚህ ነው በአንቀጽ ደረጃ ያለ የዋና ሐሳቦች ዝርዝር ለሙሉ መጽሐፉ በጣም አስፈላጊ የሆነው። በዋናው ተመስጧዊ ጸሐፊ የተገለጠውን ርዕሰ ጉዳይ አመክኖአዊ ፍሰት መከተል መቻል ይኖርብናል።

መ. የቦብ ማስታወሻዎች በትርጓሜ የሚከተሉት ቁጥር በቁጥር የሆነውን አግባብ ነው። ይህም የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ እንድንከተል ያስገድደናል። ማስታወሻዎቹ ከብዙ አካባቢዎች መረጃዎችን ይሰጡናል።

1. ሥነ ጽሑፋዊ ተጓዳኝ ጽሑፍ
2. ታሪካዊ፣ ባህላዊ መረዳቶች
3. ሰዋሰዋዊ መረጃ
4. የቃላት ጥናቶች
5. ጠቃሚ ትይዩ አንቀጾች

ሠ. በተወሰኑ ነጥቦች በሐተታው ውስጥ፣ አዲሱ የአሜሪካን መደበኛ ትርጉም (በ1995 የተሻሻለ) የኅትመት ጽሑፍ፣ ከሌሎች በርካታ ዘመናዊ ትርጉሞች በደጋፊነት ይኖራሉ፡

1. አዲሱ የኪንግ ጀምስ ቅጂ (አኪጀቅ)፣ የጽሑፋዊ እጅ ጽሑፎችን ማለት "ቴክስተስ ሪሴፕተስ" የሚከተል ነው።
2. አዲሱ የተከለሰው መደበኛ ቅጂ (አየተመቅ)፣ ማለትም ቃል በቃል የሆነ ትርጉም ሲሆን፣ እሱም የተከለሰው መደበኛ ትርጉም ከቤተክርስቲያን ብሔራዊ ምክር ቤት ነው።
3. የጊዜው እንግሊዝኛ ትርጉም (የጊእት)፣ ከአሜሪካን የመጽሐፍ ቅዱስ ሶሳይቲ የተሻሻለ አቻ ትርጉም ነው።
4. የኢየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ (ኢመቅ)፣ ከፈረንሳይ ካቶሊክ የተሻሻለ አቻ ትርጉም ላይ የተመሠረተ የእንግሊዝኛ ትርጉም ነው።

ረ. ግሪክኛን ለማያነቡ፣ ተነጻጻሪ እንግሊዝኛ ትርጉሞች በጽሑፉ ውስጥ ያሉትን አስቸጋሪ ክፍሎች ለመረዳት ይጠቅማሉ፡

1. የእጅ ጽሑፍ ልዩነቶች
2. አማራጭ የቃላት ፍቺዎች
3. ሰዋሰዋዊ አስቸጋሪ ጽሑፎችና አወቃቀሮች
4. አሻሚ ጽሑፎች

የእንግሊዝኛ ትርጉም እነዚህን ችግሮች ባያቃልልም እንኳ፣ ጠለቅ እና ውስጣዊ የሆነ ጥናት ይደረግ ዘንድ ዒላማና ስፍራውን ያሳያሉ።

ሰ. በእያንዳንዱ ምዕራፍ መዝጊያ ላይ ጠቃሚ የውይይት ጥያቄዎች ተሰጥተዋል፣ እነዚህም የምዕራፉን ዋነኞቹን የትርጓሜ ጉዳዮች ዒላማ ለማድረግ የሚሞክሩ።

## *የሐዋርያት ሥራ መግቢያ*

### *የመክፈቻ ጽሑፎች*

*ሀ. የሐዋርያት ሥራ በኢየሱስ ሕይወት (ወንጌላት) መካከል የማይቋረጥ ትስስር ፈጥሯል፤ በሐዋርያት ሥራ የነበረውን ስብከት፣ ትርጓሜአቸው፣ የሐዋርያዊ መልዕክቶች አተገባበር በአዲስ ኪዳን ያሳያል።*

*ለ. ጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ሁለት የአዲስ ኪዳን ጽሑፎችን እያራባች ታሰራጭ ነበር፡ (1) ወንጌላት (አራቱ ወንጌላት) እና (2) የሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክቶች)። ቢሆንም፣ በጥንታዊው፣ በሁለተኛው ክፍለ ዘመን በነበረው  የጥርጣሬ ክርስትና የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ዋጋው ከፍ ያለ መሆኑ ግልጽ ነው። ግብረ ሐዋርያት የሐዋርያዊ ስብከት (ኬሪግማ) ይዘትና ተግባራትን ይገልጻል፤ እንዲሁም የወንጌልን አስደናቂ ውጤት።*

*ሐ. የግብረ ሐዋርያት ታሪካዊ እውነተኛነት በዘመናዊ የጥንታዊ ቅርስ ምርመራ ግኝቶች (አርኪዮሎጂ) የመርምሮ ተረጋግጧል፤ በተለይም ከሮሜ የመንግሥት ሹማምንት ማዕርግ ጋር የተያያዘው (ለምሳሌ፡ ስትራቲጆይ፣ 16፡20፣ 22፣35፣36 [በተጨማሪም ለቤተ መቅደስ ኃላፊዎች ጥቅም ላይ ይውላል፣ ሉቃስ 22፡4፣ 52፤ ሐዋ. 4፡1፤ 5፡24-26]፤ ፖሊታርካስ፣ 17፡6፣8፤ እና ፕሮቶ፣ ሐዋ. 28፡7፣ ዝ.ከ ኤ. ኤን. ሸርዊን-ኋይት፣ የሮሜ ኅብረተሰብ እና የሮሜ ሕግ በአዲስ ኪዳን)። ሉቃስ ክርክሮቹን የመዘገበው በጥንታዊቷ ቤተ-ክርስቲያን ሲሆን፣ ይህም በጳውሎስና በበርናባስ መካከል ያለውን ነው፣ (ሐዋ. 15፡39)። ይህ የሚያንጸባርቀው ተገቢ የሆነ፣ ሚዛናዊ፣ በጥናት የተገኘ ታሪካዊ) ሥነ-መለኮታዊ ጽሑፍ ነው።*

*መ. የመጽሐፉ ርዕስ የተገኘው ከጥንታዊው የግሪክ ጽሑፎች በተለየ መልኩ ሲሆን፡*
1. *የእጅ ጽሑፍ (ሲናይቲከስ)፣ ቴረቱሊያን፣ ዲዲሞስ፣ እና ኢዩሲበስ "ሐዋ. ሥራ" አላቸው (አመት፣ አዓአት)*
2. *የእጅ ጽሑፍ ለ (ቫቲካነስ)፣ መ (ቤዜ) በተጓዳኝ ጽሑፍ፣ ኢሪኒዩስ፣ ቴረቱሊያን፣ ሲሪያን፣ እና አትናሲየስ "ግብረ-ሐዋርያት" አሏቸው (ኪጀት፣ የተመት፣ አእመቅ)*
3. *የእጅ ጽሑፍ ሀ$^{2}$ (የአሌክሳደርዮስ የመጀመሪያው እርማት)፣ ኢ፣ ጂ፣ እና ክሪሶስተም "የቅዱሳን ሐዋርያት ሥራ" አሏቸው። ማለት የሚቻለውም የግሪክ ቃላት ፓራክሲይስ፣ ፓራክሲስ (ድርጊቶች፣ መንገዶች፣ ባሕርያት፣ ተግባሮች፣ ልምምዶች) የሚያንጸባርቁት የጥንታዊ ሜዲትራኒያን ሥነ-ጽሑፋዊ ዘውጎችን ሲሆን የሚያመላክቱትም የዝነኛ ወይም ታዋቂ ሰዎችን ሕይወትና ድርጊት ነው፤ (ለምሳሌ ዮሐንስ፣ ጴጥሮስ፣ እስጢፋኖስ፣ ፊሊጶስ፣ ጳውሎስ)። መጽሐፉ ምናልባትም ከመነሻው ርዕስ ላይኖረው ይችላል (እንደ ሉቃስ ወንጌል)።*

*ሠ. ሁለት ዓይነት የተለያዩ ጽሑፋዊ ባህል ያላቸው ግብረ-ሐዋርያት አሉ። አጭሩ ዓይነት የአሌክሳንደሪያው ሲሆን (ኤም ኤስ ኤስ ፒ$^{45}$፣ ፒ$^{74}$፣ □፣ ኤ፣ቢ፣ሲ)። የምዕራባዊ ቤተሰብ የሆኑት የእጅ ጽሑፎች (ፒ$^{29}$፣ፒ$^{38}$፣ፒ$^{48}$ እና ዲ)ሌሎች ተጨማሪ በርካታ ዝርዝሮችን ይዘዋል። እነሱም ቀድሞውኑ በደራሲው ይጻፉ ወይም ኋላ ላይ በጸሐፊዎች ይጨመሩ ለማወቅ በርግጠኝነት መናገር አይቻልም፣ በጥንታዊቷ ቤተ-ክርስቲያን ባህል ላይ በመንተራስ። አብዛኞቹ የጽሑፍ ሊቃውንት እንደሚያምኑት የምዕራባውያን የእጅ ጽሑፎች ኋላ ላይ የተጨመሩበት ይኖራሉ፣ ምክንያቱም እነሱ (1) ያልተለመዱ አስቸጋሪ ጽሑፎችን ለማለዘብ፤ (2) ተጨማሪ ዝርዝሮችን በማከል፤ (3) ኢየሱስ፣ ክርስቶስ መሆኑን የሚያስረግጡ የተወሰኑ ሐረጎችን ማከል፤ እና (4) በማንም የቀድሞ ክርስቲያን ጸሐፍት በመጀመሪያዎቹ ሦስት ክፍለ ዘመናት በየትኛውም ጊዜ አለመጠቀሳቸው (ኤፍ. ኤፍ. ብሩስ፣ ግብረ ሐዋ፡ የግሪክ ጽሑፍ፣ ገጽ 69-80)። ለተጨማሪ የተብራራ ገለጻ ጽሑፋዊ ሐተታ በግሪክ አዲስ ኪዳን በብሩስ ኤም. ሜዝገር፣ በተባበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ሶሳይቲ የታተመው፣ ገጽ 259-272 ተመልከት።*

*በርካታ ቁጥር ያላቸው ኋላ ላይ የተደረጉ ተጨማሪዎች በመኖራቸው ሳቢያ፣ ይህ ሐተታ ሁሉንም ዓይነት ጽሑፋዊ አማራጮች አይመለከትም። ለትርጓሜ የሚሆኑ የተለያዩ ጽሑፎች የግድ አስፈላጊ ሲሆኑ፣ እናም ያኔ ብቻ በዚህ ሐተታ ላይ ይካተታሉ።*

### *ደራሲው*

*ሀ. መጽሐፉ ስም የሌለው ቢሆንም፣ ግን የሉቃስ ጸሐፊነት በእጅጉን ያመዝናል።*
1. *የተለየውና የሚያስገርመው "እኛ" ክፍሎች (16፡10-17 [ሁለተኛው የሚሲዮናዊ ጉዞ በፊሊጵስዩስ]፤ 20፡5-15፤ 21፡1-18 [የሦስተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞ] እና 27፡1-28፡16 [ጳውሎስ እንደ እስረኛ ወደ ሮም የተላከበት]) በእጅጉን የሚያመላክተው ሉቃስ ደራሲ እንደሆነ ነው።*
2. *የሦስተኛው ወንጌልና የሐዋርያት ሥራ ግንኙነት ግልጽ የሚሆነው ሉቃስ 1፡1-4ትን ከሐዋ. 1፡1-2 ጋር በማስተያየት ነው።*
3. *ሉቃስ፣ ከአሕዛብ የሆነ ሐኪም፣ የጳውሎስ ጓደኛ መሆኑ በቆላ. 4፡10-14፣ ፊሊሞና 24፣ እና 2ኛ ጢሞ. 4፡11 ላይ ተጠቅሷል። ሉቃስ ብቸኛው የአዲስ ኪዳን የአሕዛብ ጸሐፊ ነው።*
4. *የጥንታዊቷ ቤተ-ክርስቲያን የጋራ መግባባት የተደረሰበት ሉቃስ ጸሐፊ እንደሆነ ነው።*
   *ሀ. የሙራቶሪያን ፍራግሜንት (ስባሪ) (ዓ.ም 180-200 ከሮም፣ "በመድኃኒት አዋቂው በሉቃስ የተቀናበረ" ይላል።)*
   *ለ. የኢሪናዩስ ጽሑፎች (ዓ.ም 130-200)*

ሐ. የአሌክሳንደሪያው የክሌሜንት ጽሑፎች (ዓ.ም 156-215)
መ. የጠርጠሉያን ጽሑፎች (ዓ.ም 160-200)
ሠ. የኦሪጅን ጽሑፎች (ዓ.ም 185-254)

5. ውስጣዊ የሆነው ማስረጃ የአጻጻፍ ስልቱ እና ቃላቱ (በተለይም የሕክምና ቃላት) የሚያረጋግጠው ሉቃስ ደራሲው እንደሆነ ነው (ሰር ዊሊየም ራምሴ እና ኤ. ሃርናክ።

ለ. ስለ ሉቃስ ሦስት የመረጃ ምንጮች አሉን።

1. በአኪ. ያሉት ሦስቱ አንቀጾች (ቆላ. 4፡10-4፤ ፊሊሞን 24፤ 2ኛ ጢሞ. 4፡11) እና የሐዋርያት ሥራ ራሱ።
2. የሁለተኛው ክፍለ ዘመን ጸረ-ማርሲኦን መቅድም ለሉቃስ ወንጌል (ዓ.ም 160-180)
3. የጥታዊቷ ቤተ ክርስቲያን፣ የአራተኛው ክፍለ ዘመን የታሪክ ሰዎች፣ ኢዩሲቢዩስ፣ በእሱ የቤተ *ክርስቲያን ታሪክ*፣ 3፡4፣ እንዲህ ይላል፣ "ሉቃስ በዘሩ፣ የአንቲሆች ተወላጅ ነው፣ እንዲሁም በሙያው፣ ሐኪም ነው። በአብዛኛው ከጳውሎስ ጋር የተወዳጀ ሲሆን ከሌሎቹ ሐዋርያት ጋር ግን ብዙም ባልንጀርነት የለውም፣ ለእኛ የተወልንም ምሳሌ ነፍስ እንዴት እንደሚፈወስ ሲሆን ይህንንም በጻፋቸው ሁለት የተመስጠ መጻሕፍት በኩል ነው። ወንጌልና የሐዋርያት ሥራ።"
4. ይህ የተጠናቀረ የሉቃስ የሕይወት ታሪክ ነው።
   ሀ. አሕዛብ (ቆላ. 4፡12-14 የተመዘገበ ከኢጳፍራስ እና ከዴማስ ጋር፣ ከአይሁድ ረዺዎች ጋር ሳይሆን)
   ለ. አንድም ከሲሪያው አንቲሆች (ጸረ-ማርሲኦን መቅድም ለሉቃስ ወንጌል) ወይም የመቄዶንያው ፊሊጲ ((ሰር ዊሊየም ራምሴ በሐዋርያት ሥራ ላይ 16፡19)
   ሐ. መድኃኒት አዋቂ (ቆላ. 4፡14)፣ ወይም ባመዛኙ በጣም የተማረ ሰው
   መ. በመካከለኛ ዕድሜው ላይ የተለወጠ ይህም በአንቲሆች ቤተ ክርስቲያን ከተቋቋመ ወዲህ (ጸረ-ማርሲኦን መቅድም)
   ሠ. የጳውሎስ የጉዞ ባልንጀራ ("እኛ" የሚለው የሐዋ. ክፍል)
   ረ. ያላገባ
   ሰ. ሦስተኛውን ወንጌል እና የሐዋርያትን ሥራ የጻፈ (ተመሳሳይ መግቢያ እና ተመሳሳይ የአጻጻፍ ስልት እና ቃላት ያላቸው)
   ሸ. በቦቲያ በ84 ዓመቱ ያረፈ

ሐ. በሉቃስ ጸሐፊነት ላይ የሚነሡ ተቃርኖዎች

1. ጳውሎስ በማርስ ሂል በአቴንስ ያደረገው ስብከት ላይ የግሪክን ፍልስፍናዊ ፊርጆች ተጠቅሟል እንዲሁም ተራ ለሆኑ አገላለጾች የሚሆኑም (ሐዋ. 17)፣ ነገር ግን ጳውሎስ፣ በሮሜ 1-2፣ ምንም ዓይነት "ተራ አገላለጾች" እንደተጠቀመ (ተፈጥሮ፣ ውስጣዊ የግብረገብ ምስክር) ጥቅም ላይ አላዋለም።
2. የጳውሎስ ስብከቱም ሆነ አስተያየቱ በሐዋ. የሚያሳየውቅ እንደ አይሁድ ክርስቲያን ሆኖ ሙሴን በምር እንደያዘ ሲሆን፣ ነገር ግን የጳውሎስ መልዕክቶች ግን ሕግን ችግር እንዳለበትና ሊወገድ እንደሚገባው ማሳየታቸው።
3. የጳውሎስ መልዕክት በሐዋ. ላይ የመጨረሻ ግብ (መለኮታዊ) ላይ አለማተኮራቸው፣ እንደ ቀደምት መጻሕፍቱ (ይህም 1ኛ እና 2ኛ ተሰሎንቄ)።
4. ይህ የቃላት፣ የስልት ተቃርኖ፣ እንዲሁም አጽንኦት የሚሰጥባቸው ርዕሰ-ጉዳዮች ግን አለመጠቃለላቸው። ተመሳሳይ መስፈርት በወንጌላት ላይ ተፈጻሚ ሲደረግ የሲኖፕቲኩ ኢየሱስ ከዮሐንሱ ኢሱስ ፈጽሞ በተለየ መልኩ በተናገረ ነበር። ግን፣ ጥቂት ሊቃውንት ብቻ ሁለቱም የኢየሱስን ሕይወት ማንጸባረቃቸውን በካዱ ነበር።

መ. የሐዋ. ደራሲን በተመለከተ ክርክሮች ሲደረጉ የሉቃስን ምንጭ ማወቁ የግድ ይላል፤ ምክንያቱም ብዙ ሊቃውንት (ምሳ. ሲ. ሲ. ቶሪ፣) የሚያምነው ሉቃስ የተጠቀመው የአራሚክ ሰነዶችን (ወይም ሥነ-ቃሎችን) ሲሆን ይህም በመጀመሪያዎቹ አስራ አምስት ምዕራፎች ላይ ነው። ይህ እውነት ከሆነ፣ ሉቃስ የዚህ ሥራ አርታኢ ነው ማለት እንጂ ደራሲ አይሆንም። በኋለኞቹ የጳውሎስ ስብከቶች እንኳ፣ ሉቃስ የሚያሳየን የጳውሎስን የማጠቃለያ ቃል ነው እንጂ ዝርዝር ቃሉን አይደለም። የሉቃስ የምንጭ አጠቃቀም ዋነኛው ጥያቄ ሆኖ እንደ ደራሲነቱ ሁሉ ጥያቄ ያስነሣል።

**ጊዜው**

ሀ. ሐዋ. ስለ ተጻፈበት ዘመን በርካታ ገለጻዎችና አለመግባባቶች ያሉ ሲሆን፣ ዳሩግን ሁነቶቹ ራሳቸው የሚሸፍኑት በግምት ዓ.ም 30-63 ያለውን ነው (ጳውሎስ ከሮም እስር ቤት የተፈታው በ60ዎቹ አጋማሽ ላይ ሆኖ ዳግመኛ የታሰረው እና የተሠዋው በኔሮ፣ በግምትም በ65ዓ. ም በተደረገው ፍጅት ነው)።

ለ. አንዱ የመጽሐፉን የዘመን አፈጣጠር ባሕርይ ከሮሜ መንግሥት ጋር ቢያያይዘው፣ ቀኑ ሊሆን የሚችለው (1) ከ64 ዓ. ም በፊት ነው፣ (የኔሮ ፍጅት መጀመሪያ በሮም ክርስቲያኖች ላይ የፈጸመው) ወይም (2) ከአይሁድ ዐመጽ ጋር በ66-73 ተደርጎ ከነበረው ጋር ይያያዛል።

ሐ. አንዱ ሐዋ.ን ከሉቃስ ወንጌል ጋር በቅደም ተከተል ቢያያይዘው፣ ከዚያም የወንጌሉ መጻፊያ ጊዜ ተጽዕኖውን በሐዋ. ጽሑፍ ላይ ያሳያል። የኢየሩሳሌም መውደቅ በቲቶ በ70 ዓ.ዓ ከተተነበየ በኋላ (ይህም በሉቃስ 21 ላይ ያለው፣ ግን ያልተገለጸው፣ ጊዜውን ከ70ዓ.ዓ በፊት ያደርገዋል። እንዲህ ከሆነ፣ ሐዋ. ሊጻፍ የሚችለው በቅደም ተከተል መሠረት ከወንጌሉ ወዲህ ነው።

መ. አንዱ ከድንገተኛ ሁኔታ ጋር በተያያዘ ቢችገር (ጳውሎስ በሮም ባለበት ሰዓት፣ ኤፍ. ኤፍ ብሩስ)፣ እናም ቀኑ ሊገናኝ የሚችለው በጳውሎስ የመጀመሪያው የእስር ሰዓት ማገባደጃ ላይ ነው ተመራጭ የሚሆነው፣ ከ58-63 ዓ.ም።

ሠ. አንዳንድ ታሪካዊ ቀናት ከታሪካዊ ሁነቶች ጋር የተገናኙት ሐዋ.ን ይመዘግባሉ፡፡
1. በክላውዲዎስ ጊዜ የነበረው አገር አቀፍ ረሀብ (ሐዋ. 11፡28፣ ዓ.ም 44፡48)
2. የአግሪጳው ሄሮድስ 1ኛ ሞት (ሐዋ. 12፡20-23፣ ዓ.ም 44 [መፀው])
3. የሰርጊዩስ ጳውሎስ ሹመት (ሐዋ. 13፡7፣ የተሾመበት በ53 ዓ.ም)
4. የአይሁድ ከሮም እንዲወጡ መደረግ በክላውዲዮስ (ሐዋ. 18፡2፣ በ49 [?] ዓ.ም)
5. የጋልዮስ ሹመት፣ ሐዋ. 18፡12 (በ51 ወይም 52 [?] ዓ.ም )
6. የፊሊክስ ሹመት (ሐዋ. 23፡26፤24፡27፣ በ52-56 [?] ዓ.ም)
7. የፊለክስ በፊስቶስ መተካት (ሐዋ. 24፡27፣ 57-60[?] ዓ.ም)
8. የይሁዳ የሮሜ ሹሞች
   ሀ. እንደራሴዎች
      (1) ጴንጤናዊው ጲላጦስ፣ ከ26-36 ዓ.ም
      (2) ማርሲለስ፣ ከ36-37 ዓ.ም
      (3) ማሩለስ፣ ከ37-41 ዓ.ም
   ለ. በ41ዓ.ም የሮሜ አስተዳደር የሥልጣን ሥርዓት ወደ ንጉሣዊ ሥርዓት ተቀይሯል፡፡ የሮሜ ንጉሠ ነገሥት፣ ክላውዲዮስ፣ ሄሮድ አግሪጳ 1ኛን በ41 ዓ.ም ሾመው፡፡
   ሐ. ከሄሮድስ አግሪጳ 1ኛ ሞት በኋላ፣ በ44 ዓ.ም፣ የአገዛዝ ሥርዓቱ እንደገና እስከ 66 ዓ.ም ድረስ ተቋቋመ፡፡
      (1) አንቶኒዮስ ፍሊክስ
      (2) ፖርከስ ፌስቶስ

**ዓላማና አወቃቀሩ**

ሀ. አንደኛው የሐዋ. መጽሐፍ ዓላማ የኢየሱስን ተከታቶች በፍጥነት መጨመር በሰነድ ለማስፈር ሆኖ ይህም ከአይሁድ ሥር ያለውን ወደ ዓለም አቀፍ አገልግሎት ለማምጣት፣ እንዲሁም ከተዘጋው የደርቡ ክፍል ወደ ቁሳር ቤተመንግሥት ለማምጣት ነበር፡
1. መልክዓ ምድራዊ ሁኔታው የሐዋ. 1፡8 የሚከተለው ይህም የሐዋ.ታላቁ ተልዕኮ (ማቲ. 28፡19-20) ያለው ነው፡፡
2. መልክዓ ምድራዊ መስፋፋቱ በተለያዩ መንገዶች ተገልጿል፡፡
   ሀ. ዋነኞቹን ከተሞችና ብሔራዊ ወሰኖችን መጠቀሙ፡፡ በሐዋ. 32 አገሮች፣ 54 ከተሞች እና 9 የሜዲትራኒያን ደሴቶች ተጠቅሰዋል፡፡ ሦስቱ ታላላቅ ከተሞች ኢየሩሳሌም፣ አንቲሆች እና ሮም ናቸው (ሐዋ. 9፡15፡፡)
   ለ. ዋነኛ ሰዎችን መጠቀም፡፡ ሐዋ. ከሞላ ጎደል በሁለት እኩል ሊከፈል ይችላል፡ የጴጥሮስና የጳውሎስ አገልግሎቶች፡፡ ከ95 በላይ ሰዎች በሐዋ. የተጠቀሱ ሲሆን፣ ነገር ግን ዋነኞቹ፡ <u>ጴጥሮስ</u>፣ እስጢፋኖስ፣ ፊሊጶስ፣ በርናባስ፣ ያዕቆብ እና <u>ጳውሎስ</u> ናቸው፡፡
   ሐ. ሁለት ወይም ሦስት ጽሑፋዊ ቅርጾች ሲኖሩት እነርሱም በሐዋ. በተደጋጋሚ የተገለጹ ሆነው የጸሐፊውን በመዋቅሩ ውስጥ የተጠቀሰውን ሐሳቡን ለመግለጽ የሚሞክሩ ናቸው፡

| (1) የማጠቃለያ መግለጫዎች | (2) የዕድገት መግለጫዎች | (3) የቁጥሮች አጠቃቀም |
|---|---|---|
| 1፡1-6፡7 (በኢየሩሳሌም) | 2፡47 | 3፡41 |
| 6፡8-9፡31 (በፍልስጥኤም) | 5፡14 | 4፡4 |
| 9፡32-12፡24 (ወደ አንቲሆች | 6፡7 | 5፡14 |
| 12፡25-15፡5 (ወደ ታናሹ እስያ) | 9፡31 | 6፡7 |
| 16፡6-19፡20 (ወደ ግሪክ) | 12፡24 | 9፡31 |
| 19፡21-28፡31 (ወደ ሮም) | 16፡5 | 11፡21፣24 |
| | | 12፡24 |
| | | 14፡1 |
| | | 19፡20 |

ለ. ሐዋ. በግልጽ የሚያያዘው ኢየሱስ ከሞተበት ምክንያት ጋር በተፈጠረው ያለመረዳት ነው፡፡ ባጠቃላይ፣ ሉቃስ የጻፈው ለአሕዛብ ነው (ቴዎፍሎስ፣ ምናልባትም የሮሜ ባለሥልጣን)፡፡ የተጠቀመበትም (1) የጴጥሮስን፣ የስጢፋኖስን፣ እና የጳውሎስን ንግግሮች ሆኖ ይህም ለአይሁድ ጠቀሜታ እንዲሆንም ነው፤ እንዲሁም (2) የሮሜ የመንግሥት ባለሥልጣናት ቀናነት ለክርስትና ያላቸውን ለማሳየት ነው፡፡ ሮማውያን ከኢየሱስ ተከታዮች የሚፈሩት ምንም ነገር የለም፡፡
1. የክርስቲያን መሪዎች ንግግሮች
   ሀ. ጴጥሮስ፣ 2፡14-40፤ 3፡12-26፤ 4፡8-12፤ 10፡34-43
   ለ. እስጢፋኖስ፣ 7፡1-53
   ሐ. ጳውሎስ፣ 13፡10-42፤ 17፡22-31፤ 20፡17-25፤ 21፡40-22፡21፤ 23፡1-6፤ 24፡10-21፤ 26፡1-29
2. ከመንግሥት ባለሥልጣናት ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶች
   ሀ. ጴንጤናዊው ጲላጦስ፣ ሉቃስ 23፡13-25
   ለ. ሰርግዮስ ጳውሎስ፣ ሐዋ. 13፡7፣12
   ሐ. የፊሊጶስ ዋነኛ ሹሞች፣ ሐዋ. 16፡35-40

መ. ጋሊዮ፣ ሐዋ. 18፡12-17
ሠ. የኤፌሶኑ አስኪለስ፣ ሐዋ. 19፡23-41 (በተለይም ቁ. 31)
ረ. ክላውዲዮስ ሊስያስ፣ ሐዋ. 23፡29
ሰ. ፊሊክስ፣ ሐዋ. 24
ሸ. ፖርሲየስ ፊስተስ፣ ሐዋ. 24
ቀ. አግሪጳ 2ኛ፣ ሐዋ. 26 (በተለይም ቁ. 32)
በ. ፓብሊዩስ፣ ሐዋ. 28፡7-10

3. አንዱ የጴጥሮስን ስብከት ከጳውሎስ ጋር ቢያነጻጽር በግልጽ የሚታየው ጳውሎስ አዳዲስ ሐሳቦችን እንዳላመነጨ ነው፤ ነገር ግን ታማኝ ሐዋርያዊና የወንጌል እውነት አዋጅ ነጋሪ። የእምነት አስተምህሮቱ ኅብር አለው!

ሐ. ሉቃስ ክርስትናን በሮሜ ባለሥልጣኖች ዘንድ በመከላከል ብቻ አያበቃም፣ ነገር ግን ጳውሎስንም በአሕዛብ ቤተ ክርስቲያኖች ዘንድ ተከላክሎለታል። ጳውሎስ በተደጋጋሚ በአይሁድ ቡድኖች ጥቃት ደርሶበታል (በገላትያ ይሁዲዎች፣ "ልዕለ ሐዋርያት" በ2ኛ ቆሮ. 10፡13፤ እንዲሁም በሔለናዊ ቡድኖች (በቆላስይስና በኤፌሶን ግኖስቲካውያን)። ሉቃስ የጳውሎስን ተገቢነት በግልጽ በማስታወቅ የልቡን ሐሳብና ሥነመለኮቱን በጉዞውም ሆነ በስብከቱ ያለውን አሳይቷል።

መ. ምንም እንኳ ሐዋ. የእምነት መግለጫ ዓይነት እንዲሆን ባይታሰብም፣ የሐዋርያትን ቀደምት ስብከቶችን ፍሬ ሐሳብ ይዞልናል፣ ይህም ሲ. ኤች ዶድ "የጥንት ስብከተ ወንጌል" (ስለ ኢየሱስ ጠቃሚ እውነቶች) ብሎ እንደሚጠራው። ይህም የሚረዳን በወንጌል ጠቀሜታ ምን ይሰማቸው እንደነበር ያሳየናል፣ በተለይም ከኢየሱስ ጋር የሚገናኘውን ሞቱንና ትንሣኤውን።

**ልዩ ርዕስ፡ የጥንታዊቷ ቤተክርስቲያን ኬሪግማ (ስብከተ ወንጌል)**

ሀ. በአዲስ ኪዳን የተሰጠው የእግዚአብሔር ተስፋ በኢየሱስ መሲሑ መምጣት ሳቢያ ተፈጽሟል። (ሐዋ. 2፡30፤ 3፡19፣24፤ 10፡43፤ 26፡6-7፣22፤ ሮሜ. 1፡2-4፤ 1ኛ ጢሞ. 3፡16፤ ዕብ. 1፡1-2፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡10-12፤ 2ኛ ጴጥ. 1፡18-19)።
ለ. ኢየሱስ እንደ መሲሕ በእግዚአብሔር የተቀባው በጥምቀቱ ነው (ሐዋ. 10፡38)
ሐ. ኢየሱስ አገልግሎቱን የጀመረው በገሊላ ከጥምቀቱ በኋላ ነው (ሐዋ. 10፡37)።
መ. የአገልግሎቱም ባሕርይ መልካምን በማድረግና ታላላቅ ሥራዎችን (ተአምራትን) በመከወን ሲሆን ይህም በእግዚአብሔር ኃይል ነው (ማርቆስ 10፡45፤ ሐዋ. 2፡22፤ 10፡38)።
ሠ. መሲሑ የተሰቀለው በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዓላማ መሠረት ነው (ማርቆስ 10፡45፤ ዮሐንስ 3፡16፤ ሐዋ. 2፡23፤ 3፡13-15፣18፤ 4፡11፤ 10፡39፤ 26፡23፤ ሮሜ. 8፡34፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡17-18፤ 15፡3፤ ገላ. 1፡4፤ ዕብ. 1፡3፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡2፣19፤ 3፡18፤ 1ኛ ዮሐ. 4፡10)።
ሸ. እሱም ከሞት ተነሥቶ ለሐዋርያት የተከሰተላቸው (ሐዋ. 2፡24፣31-32፤ 3፡15፣26፤ 10፡40-41፤ 17፡31፤ 26፡23፤ ሮሜ. 8፡34፤ 10፡9፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡4-7፣12፤ 1ኛ ተሰ. 1፡10፤ 1ኛ ጢሞ. 3፡16፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡2፤ 3፡18፣21)።
ቀ. ኢየሱስ በእግዚአብሔር ከፍ ብሎ "ጌታ" የሚል ስያሜ ተሰጠው (ሐዋ. 2፡25-29፣33-36፤ 3፡13፤ 10፡36፤ ሮሜ. 8፡34፤ 10፡9፤ 1ኛ ጢሞ. 3፡16፤ ዕብ. 1፡3፤ 1ኛ ጴጥ. 3፡22)።
በ. አዲሱን የእግዚአብሔርን ማኅበረሰብ ለመፍጠር መንፈስ ቅዱስን ሰጠ (ሐዋ. 1፡8፤ 2፡14-18፣38-39፤ 10፡44-47፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡12)።
ተ. እሱም ዳግመኛ ተመልሶ ይመጣል፣ ለፍርድና ሁሉንም ነገር ለመመለስ (ሐዋ. 3፡20-21፤ 10፡42፤ 17፡31፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡20-28፤ 1ኛ ተሰ. 1፡10)።
ቸ. መልዕክቱን የሚሰሙት ሁሉ ንስሐ ሊገቡና ሊጠመቁ ይገባል (ሐዋ. 2፡21፣38፤ 3፡19፤ 10፡43፣47-48፤ 17፡30፤ 26፡20፤ ሮሜ. 1፡17፤ 10፡9፤ 1ኛ ጴጥ. 3፡21)።

ዘዴው የሚያገለግለው የጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ዋነኛ አዋጆች በተለያዩ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች የተዉልንን ድርሻ ወይም አጽንዖት የሚሰጠውን በተለየ መልኩ በስብከታቸው ላይ ያለውን ነው። ሙሉው የማርቆስ ወንጌል በቅርበት የሚከተለው ስብከተ ወንጌል ጴጥሮሳዊ ገጽታ ነው። ማርቆስ ከባህል አኳያ የሚታየው የጴጥሮስን ስብከቶች በማዋቀር ነው፣ በሮም የተሰበከውን፣ ወደ ተጻፈ ወንጌል በመቀየር። ሁለቱም ማቲዎስና ሉቃስ የማርቆስን መሠረታዊ መዋቅር ተከትለዋል።

ሠ. ፍራንክ ስታግ በሐተታው፣ *የሐዋርያት ሥራ፣ ወደ ኋላ ለማይታጠፈው ወንጌል ቀደምት ትግል፣* የሚለው ዓላማው በቅድሚያ ስለ ኢየሱስ ያለውን መልእክት ንቅናቄ ነው (ወንጌሉ) ፍጹም ጥብቅ ከሆነው ብሔራዊ ይሁዲነት ወደ ሁለንተናዊ ለሰው ልጆች ሁሉ ወደሆነው መልእክት ነው። የስታግ ሐተታ ያተኮረው በሉቃስ ዓላማ ላይ ነው፣ ሐዋ.ን ሲጽፍ። መልካም የሆነው ማጠቃለያና የተለያዩ ንድፈ ሐሳቦች ትንታኔ ገጽ 1-18 ላይ ይገኛል። ስታግ የመረጠው በ28፡31 ላይ ባለው "የማይታጠፍ" በሚለው ቃል ላይ ማተኮር ነው፣ ይህም መጽሐፍን ለመደምደም ያልተለመደና የሉቃስን አጽንኦት ለመረዳት ክርስትና ሁሉንም መሰናክሎች ጥሶ መሄድ እንዳለበት ያሳየውን።

ረ. በሐዋርያት *ሥራ* ላይ *መንፈስ* ቅዱስ ከሃምሳ ጊዜ በላይ ቢጠቀስም፣ እሱ ግን "*መንፈስ ቅዱሳዊ የሐዋርያት ሥራ*" አይደለም። አስራ አንድ *ምዕራፎች መንፈስ* ቅዱስ *ያልተጠቀሰባቸው* ይገኛሉ። ብዙውን የጠቀሰው በሐዋ. በመጀመሪያው *አጋማሽ* ላይ ሲሆን፣ ሉቃስ ሌሎች *ምንጮችን* የጠቀሰበት (*ምናልባትም* በመጀመሪያ በአራሚክ የተጻፈውን)። ሐዋ. የመንፈስ አይደለም ወንጌላት ለኢየሱስ እንደሆኑት ያለ! ይህ ማለት ግን የመንፈስን ስፍራ ወደ ኋላ ለማለት ሳይሆን፣ ነገር ግን ይህ *መንፈስ* ከሐዋ. በቀዳሚነት ወይም በተናጠል የሚል *ሥነመለኮት* እንዳይመሠረት ለመከላከል ነው።

ሰ. ሐዋ. የእምነት *መግለጫን* ለማስተማር ተብሎ የተዘጋጀ አይደለም (ፊ እና ስቱዋርት፣ *መጽሐፍ ቅዱስን ከሙሉ ጠቀሜታው አኳያ እንዴት ማንበብ ይቻላል*፣ ገጽ 94-112)። ለዚህ አንድ ምሳሌ የሚሆነው፣ የመለወጥ *ሥነ* መለኮት ከሐዋ. የመመሥረት ሙከራ፣ ይህም ሳይሳካ ያበቃለት ነው። የመለወጡ ቅደም ተከተልና ይዘቶቹ በሐዋ. ይለያሉ፤ ስለሆነም የትኛው አግባብ ነው ተገቢ የሚሆነው? ለመሠረተ እምነት እርዳታ መልእክቶችን የግድ ማየት ይኖርብናል።

ሆኖም፣ አስገራሚ የሚሆነው አንዳንድ ሊቃውንት (ሃንስ ኮዚልማን) ሉቃስን የተመለከቱት ሆን ብለው የመጨረሻውን መለኮታዊ ግብ ዳግም ለመቃኘት በአንደኛው ክፍለ ዘመን ትዕግሥት በተሞላው አገልግሎት ወደ ዘገየው ፓሮሲያ በመቃረብ ነው። መንግሥቱ አሁንም እዚህ በሥልጣን ላይ ሆኖ ሕይወትን ይቀይራል። ቤተ ክርስቲያን አሁን የምትሠራው አትኩሮቱ ስለሆነ ነው እንጂ በመጨረሻው ግብ ተስፋ አይደለም።

ሸ. ሌለኛው የሐዋ. ዓላማ ከሮሜ. 9-11 ጋር ተመሳሳይ ነው፡ አይሁድ ለምን አይሁዳዊ የሆነ መሲሕን ሳይቀበሉ ቀርተው ቤተ ክርስቲያንም ባብዛኛው የአሕዛብ ሆነች? በሐዋ. በብዙ ስፍራዎች የወንጌል ዓለም አቀፍ ባሕርዩ በግልጽ ተስተጋብቷል። ኢየሱስ በሁሉም ዓለም ልኳቸዋል (ዝ.ከ 1፡8)። አይሁድ አልተቀበሉትም፣ ነገር ግን አሕዛብ ምላሽ ሰጡት። መልእክቱ ሮም ደረሰ።

የሉቃስ መክእክት የሚመስለው፣ የሚያሳየው የአይሁድ ክርስትና (ጴጥሮስ) እና የአሕዛብ ክርስትና (ጳውሎስ) አንድ ላይ ሊኖሩ እና ሊያድጉ እንደሚችሉ ነው! በፉክክር ላይ አይደሉም፣ ነገር ግን ዓለምን በወንጌል ለማዳረስ ተገናኝተዋል።

በ. ዋነኛው ነገር ዓላማ ስለሆነ ከኤፍ. ኤፍ. ብሩስ (*አዲሱ ዓለም አቀፍ ሐተታ፣ ገጽ* 18) እስማማለሁ፣ ማለትም ሉቃስ እና ሐዋ. በመጀመሪያ አንድ ቅጽ ነበሩ፣ ይህም በሉቃስ መቅድም ላይ (1፡1-4)፣ ለሐዋ. ም እንደ መቅድም አገልግሏል። ሉቃስ፣ ምንም እንኳ ለሁሉም ሁነቶች የዓይን ምስክር ባይሆንም፣ በጥንቃቄ መርምሮ እና መዝግቦ አስረግጧል፣ የራሱን ታሪካዊ፣ ጽሑፋዊ፣ *ሥነመለኮታዊ* መነሻ በመጠቀም።

ከዚያም ሉቃስ፣ በሁለቱም በወንጌሉና በትረካው፣ ለማሳየት የሞከረው ታሪካዊ እውነታውን እና *ሥነመለኮታዊ* ተአማኒ ጠቀሜታውን ነው፣ (ሉቃስ 1፡4) የኢሱስንና የቤተ ክርስቲያንን። ይህም ሊሆን የሚችለው የሐዋ. ትኩረት ጭብጥ የፍጻሜው (የማይታጠፈው፣ ዝ.ከ 28፡31፣ ይህም የመጨረሻው የመጽሐፉ ቃል)። ይህ ጭብጥ በበርካታ ቃላትና ሐረጎች ወደፊት እንዲራመድ ተደርጓል (ዋልተር ኤል. ላይ ፊልድ፣ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍን መተርጎም ገጽ 23-24)። ወንጌል ተጨማሪ ፈጠራ አይደለም፣ ሁለተኛ ዕቅድ፣ ወይም አዲስ ነገር። እሱ የእግዚአብሔር ቀድሞ የተወሰነበት እቅድ ነው (ሐዋ. 2፡23፤ 3፡18፤ 4፡28፤ 13፡29)።

**ዘውጉ (ዘርፉ)**

ሀ. ሐዋ. ለአዲስ ኪዳን ነው፣ ልክ ኢያሱ በ2ኛ ነገሥት ለብሉይ ኪዳን እንደሆነ፡ ታሪካዊ ትረካ። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትረካ እውነታዊ ሲሆን፣ ነገር ግን አትኩሮቱ በታሪክ ቅደም ተከተል ወይም ሁነቶችን አጠናቆ በመመዝገብ ላይ አያተኩርም። አንዳንድ ሁነቶችን ይመርጣል፣ እግዚአብሔር ማን እንደሆነ የሚገልጹትን፣ እኛ ማን መሆናችንን፣ ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት ትክክል እንደምንሆን፣ እግዚአብሔር እንዴት መኖር እንዳለብን እንደሚሻ።

ለ. የመጽሐፍ ቅዱስን ትረካ በመተርጎም ላይ ያለው ችግር የጸሐፊዎቹ በጽሑፉ ላይ አለመስፈር ሆኖ (1) ምን ዓላማ እንዳላቸው፣ (2) ዋነኛው እውነት ምን እንደሆነ፣ ወይም (3) እኛ እንዴት የተመዘገቡልንን ነገሮች በተሻለ እንደምንረዳ። አንባቢ በሚከተሉትን ጥያቄዎች በኩል ሊያጤን ይገባል፡

1. ሁነቶቹ ለምን ተመዘገቡ?
2. እሱም ከቀደምቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፍ ጋር እንዴት ይገናኛል?
3. ማዕከላዊው ሥነ መለኮታዊ እውነት ምንድነው?
4. ሥነ ጽሑፋዊ ይዘቱ ጠቀሜታ ይኖረው ይሆን? (ምን ሁነት ይቀጥላል ወይም ይመጣል? ፍሬ ሐሳቡ በሌላም ስፍራ ተገልጾ ይሆን?)
5. ጽሑፋዊ ይዘቱ ምን ያህል ትልቅ ነው? (አንዳንድ ጊዜ ሰፋ ያሉ ትረካዎች አንድ ሥነመለኮታዊ ጭብጥ ወይም ዓላማ ብቻ ይይዛሉ።)

ሐ. ታሪካዊ ትረካዎች ብቻ የእምነት መግለጫ ምንጭ መሆን የለባቸውም። ዘወትር ነገሮች ድንገታዊ የሆኑት ከደራሲው ዓላማ አኳያ ሊመዘገቡ ይችላሉ። ታሪካዊ ትረካዎች እውነትን ሊያብራሩ ይችላሉ፣ በሌላ የመጽሐፍ ክፍል የሰፈሩትን። አንድ ነገር በመሆኑ ብቻ ለሁሉም አማኞችና በሁሉም ዕድሜ ለሚገኙት የእግዚአብሔር ፍቃድ ነው ማለት አይደለም (ምሳ. ራስን ማጥፋት፣ ከአንድ በላይ ማግባት፣ ቅዱስ ጦርነት፣ እባቦችን መያዝ፣ ወዘተ...)።

መ. በጣም የተሻለው ማብራሪያ፣ ታሪካዊ ትረካዎችን ለመተርጎም በጎርደን ፊ እና ዳግላስ ስቱዋርት *መጽሐፍ ቅዱስን ከሙሉ ጠቀሜታው እንዴት እናነበዋለን፣* ገጽ 78-93 እና 94-112።

**የታሪካዊ መቼት ዋቢ ጽሑፎች**

አዳዲስ መጻሕፍት ሐዋ.ን በአንደኛው ክፍለ ዘመን መቼቱ ላይ የሚያስቀምጡት በጥንታውያኖቹ ታትመዋል። ይህ መስተጋብራዊ (ብዙ ዘርፎችን የሚያገናኘው) አገባብ አ.ኪን ለመረዳት በእጅጉን ይረዳል። ተከታታዩ እትም በብሩስ ኤም. ሚንተር ተዘጋጅቷል።

*ሀ. የሐዋርያት ሥራ በጥንታዊ ጽሑፋዊ መቼቱ*

*ለ. የሐዋርያት ሥራ በግሪክ ሮሜ መቼቱ*

*ሐ. የሐዋርያት ሥራ እና ጳውሎስ በሮሜ ማረፊያ ቤት*

*መ. የሐዋርያት ሥራ በፍልስጥኤም መቼት*

*ሠ. የሐዋርያት ሥራ በተበተኑት (ስደተኞች) መቼት*

*ረ. የሐዋርያት ሥራ በሥነ መለኮታዊ መቼቱ*

እንዲሁም በጣም ሊረዱ የሚችሉት

1. ኤ. ኤን. ሼርዊን-ኋይት፣ *የሮሜ ኅብረተሰብና የሮሜ ሕግ በአዲስ ኪዳን*
2. ፖል ባርኔት፣ *ኢየሱስ እና የጥንት ክርስትና አነሣሥ*
3. ጀምስ ኤስ. ጄፈርስ፣ *የግሪክ ሮሜ ዓለም*

**የንባብ ዑደት አንድ (ገጽ vi ተመልከት)**

ይህ የጥናት መመሪያ ሐተታ ነው፣ ያም ማለት መጽሐፍ ቅዱስን በግል ከመተርጎም አኳያ ራሱ ተርጓሚው ኃላፊነት እንዳለበት ይገልጻል። እያንዳንዳችን ባለን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ እና መንፈስ ቅዱስ በትርጓሜው ቅድሚያ ናችሁ። ይህን በሐተታ አቅራቢው ልዩ ትርጉም መያዝ አይኖርብዎትም።

የመጽሐፍ ቅዱሱን ክፍል በአንድ ጊዜ አንብብ። የመጽሐፉን ሙሉውን ክፍል ማዕከላዊ ጭብጥ በራስህ ቃል ጻፈው።

1. የሙሉ መጽሐፉ ጭብጥ
2. የሥነ- ጽሑፉ ዓይነት (ዘውግ)

**የንባብ ዑደት ሁለት (ከ "ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ" ገጽ Vi- Vii ተመልከት)**

ይህ የጥናት መመሪያ ሐተታ ነው፣ ያም ማለት መጽሐፍ ቅዱስን በግል ከመተርጎም አኳያ ራሱ ተርጓሚው ኃላፊነት እንዳለበት ይገልጻል። እያንዳንዳችን ባለን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ እና መንፈስ ቅዱስ በትርጓሜው ቅድሚያ ናችሁ። ይህን በሐተታ አቅራቢው ልዩ ትርጉም መያዝ አይኖርብዎትም።

የመጽሐፍ ቅዱሱን ክፍል በድጋሚ በአንድ ጊዜ አንብብ። ዋናዎቹን ርዕሰ-ጉዳዮች ዘርዝሩና አንዱን ርዕሰ-ጉዳይ በአንድ ዓረፍተ ነገር አቅርብ።

1. የመጀመሪያው ጽሑፋዊ ምድብ ርዕሰ-ጉዳይ
2. የሁለተኛው ጽሑፋዊ ምድብ ርዕሰ-ጉዳይ
3. ሦስተኛው ጽሑፋዊ ምድብ ርዕሰ-ጉዳይ
4. አራተኛው ጽሑፋዊ ምድብ ርዕሰ-ጉዳይ
5. ወዘተርፈ

# የሐዋርያት ሥራ 1

## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| የተየመቅሶ[4] | አኪጀት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የመንፈስ ቅዱስ ተስፋ | መቅድም | መግቢያ፤ የተነሣው ክርስቶስ | መግቢያ | መቅድም |
| 1:1-5 | 1:1-3 | 1:1-5 | 1:1-5 | 1:1-5 |
| | የመንፈስ ቅዱስ ተስፋው | | | |
| | 1:4-8 | | | |
| የኢየሱስ እርገት | ኢየሱስ ወደ ሰማይ አረገ | እርገት | አየሱስ ወደ መንግሥተ ሰማያት አረገ | እርገት |
| 1:6-11 | 1:9-11 | 1:6-11 | 1:6 | 1:6-8 |
| | | | 1:7-9 | 1:9-11 |
| በአስቆሮቱ ይሁዳ ምትክ መምረጥ | የደርቡ ክፍል የጸሎት ስብሰባ | የአስራ ሁለቱ መሰባሰብ | የይሁዳ ምትክ | የሐዋርያት ቡድን |
| 1:12-14 | 1:12-14 | 1:12-14 | 1:12-14 | 1:12-14 |
| | ማትያስ ተመረጠ | | | ይሁዳ ተተካበት |
| 1:15-26 | 1:15-26 | 1:15-26 | 1:15-17 | 1:15-20 |
| | | | 1:18-19 | |
| | | | 1:20 | |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (ከ **"መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ" ገጽ** vii)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

---

*ተመስጧዊ ባይሆኑም፣ የአንቀጽ ምድቦች የሚከተለውን የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ ለመረዳት ቁልፍ ናቸው፡፡ እያንዳንዱ ዘመናዊ ትርጉም አንቀጾቹን መድቦ ማጠቃለያውን እንዲያቀርብ ተደርጓል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድ ማዕከላዊ ርዕሰ-ጉዳይ፣ እውነት፣ ወይም እሳቦት አለው፡፡ እያንዳንዱ ቅጂ ያንን ርዕስ በራሱ የተለየ መንገድ አጽዕሮቱን አስፍሯል፡፡ ጽሑፉን ስታነበው፣ የትኛው ትርጉም በርዕሰ ጉዳይም ሆነ በቁጥር ምድቦች ከአንተ መረዳት ጋር እንደሚስማማ ራስህን ጠይቅ፡፡

በእያንዳንዱ ምዕራፍ በቅድሚያ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ይኖርብናል፣ እንዲሁም ርዕሰ ጉዳዮቹን መለየት (አንቀጾቹን)፣ አኪያም የእኛን መረዳት ከአዲሶቹ ትርጉሞች ጋር ማወዳደር አለብን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ልንረዳ የምንችለው የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ ምን እንደሆነ የሱን አምክኖአዊ (ሎጂክ) እና አቀራረቡን ስንረዳ ነው፡፡ ዋነኛው ጸሐፊ ብቻ ነው ተመስጧዊው— አንባብያን መልዕክቱን ለመቀየርም ሆነ ለማሻሻል መብት የላቸውም፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢዎች ተመስጧዊውን እውነት በየዕለቱና በሕይወታቸው ሁሉ ተግባራዊ ለማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

*ማስታወሻ፡ ሁሉም ሙያዊ ቃላትና አጽሕሮተ ቃላት በሙሉ በቅጥያ አንድ፣ ሁለት፣ እና ሦስት ላይ ተብራርተዋል።*

1. *ምንባብ አንድ*
2. *ምንባብ ሁለት*
3. *ምንባብ ሦስት*
4. *ወዘተርፈ*

***የቃልና የሐረግ ጥናት***

> **አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ ሐዋርያት ሥራ 1፡1-5**
> [1-2]**ቴዎፍሎስ ሆይ፥ ኢየሱስ የመረጣቸውን ሐዋርያትን በመንፈስ ቅዱስ ካዘዛቸው በኋላ እስከ ዐረገበት ቀን ድረስ፥ ያደርገውና ያስተምረው ዘንድ ስለ ጀመረው ሁሉ መጀመሪያውን ነገር ጻፍሁ፤ [3]ደግሞ አርባ ቀን እየታያቸው ስለ እግዚአብሔርም መንግሥት ነገር እየነገራቸው፥ በብዙ ማስረጃ ከሕማማቱ በኋላ ሕያው ሆኖ ለእነርሱ ራሱን አሳያቸው። [4]ከእነርሱም ጋር አብሮ ሳለ ከኢየሩሳሌም እንዳይወጡ አዘዛቸው፥ ነገር ግን። ከእኔ የሰማችሁትን አብ የሰጠውን የተስፋ ቃል ጠብቁ፤ [5]ዮሐንስ በውኃ አጥምቆ ነበርና፥ እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ አለ።**

1፡1 "***በመጀመሪያ ልጽፍልህ ያሰብኩት***" ይህ ያልተጠናቀቀ መካከለኛ አመላካች፣ በጥሬው፣ "አበጀሁ" ማለት ነው። ሉቃስ የማያሻማው የሁለቱም ማለትም የሉቃስ ወንጌልና የሐዋርያት ሥራ ደራሲ ነው፣ (ሉቃስ 1፡1-4 እና ሐዋ. 1፡1-2 አነጻጽር)። "ቅጽ" የሚለው ቃል በግሪክ ጥቅም ላይ የሚውለው ለታሪካዊ ትረካ ነው። ከስልት አኳያ (ማለትም፣ በጥንታዊ ግሪክ) ከሦስት ሥራዎች መካከል ቢያንስ አንደኛው ይሆናል። በርግጥ ሊሆን የሚችለው ያልተለመደው የሐዋርያት ሥራ አጨራረስ ሊብራራ የሚችለው ሉቃስ ተጨማሪ ቅጽ ለመጻፍ ማቀዱን ነው። አንዳንዶች ሲያስተነትኑም መጋቢያዊ መልእክቶች (1ኛ ጢሞቲዎስ፣ 2ኛ ጢሞቲዎስ፣ እና ቲቶ) በሉቃስ ሳይጻፉ አልቀሩም ይላሉ።

▣ "***ቴዎፍሎስ***" ይሄ ስም የተመሠረተው ከ (1) እግዚአብሔር (ቲዎስ) እና (2) ወንድማዊ ፍቅር (ፊሎስ) ከሚለው ነው። "እግዚአብሔር አፍቃሪ፣" "የእግዚአብሔር ወዳጅ፣" ወይም "በእግዚአብሔር የተወደደ" በሚል ሊተረጎም ይችላል።
*ማዕርጉም* "በጣም ለተከበርከው" በሉቃስ 1፡3 ለሮሜ የመንግሥት ባለሥልጣን የክብር ማዕርግ ሊሆን ይችላል፣ ሐዋ. 23፡26፤ 24፡3፤ 26፡25)፣ ጥቅም ላይ የሚውለው የፈረሰኛ ሠራዊት ማዕረግ ነው፣ በሮሜ ኅብረተሰብ። እሱ ምናልባትም የጽሑፋዊ ክፍል ጋር አግባብ ያለውና በጽሑፍ፣ በቅጅና በማከፋፈል ረገድ የሉቃስን ሁለቱን መጻሕፍት ያከናወነ ሊሆን ይችላል። የቤተክርስቲያን ባህል እሱን ሲጠራው ቲ. ፍላቪዩስ ክሌሚነስ፣ የዶሚታን የወንድም (እኅት) ልጅ በሚል ነው።

▣ "***ኢየሱስ ሊሠራ የጀመረውን በሙሉ***" ይህ የሚያመለክተው የሉቃስን ወንጌል ነው። ሉቃስ "ሁሉም" ሲል የሚያስደንቅበት ምክንያት ኢየሱስ ያደረገው፣ የሚልበት ምክንያት፣ የሉቃስ ወንጌል (እንደ ሌሎቹ የተጨመቁ ወንጌላት) በጣም የተመረጡ የኢየሱስን ሕይወትና ትምህርቶችን ስለሚመዘግብ ነው።

1.2 "***ወደ ሰማይ እስካረገበት ቀን ድረስ***" በርካታ ቁጥር ያላቸው የግሪክ ቃላት የኢየሱስን ወደ ሰማይ ማረግ ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውለዋል።

> ***ልዩ ርዕስ፡ ወደ መንግስተ ሰማያት ተመልሶ ማረግ***
> የኢየሱስን ወደ መንግስተ ሰማያት ተመልሶ ማረግ የሚያሳዩ በርካታ ሀረጎች በግሪኩ ቋንቋ ውስጥ ይገኛሉ።
> 1. analambanō፣ ወደ ላይ መውሰድ (ሐዋ. 1፡2፣11፣22፣ 1ኛ ጢሞ. 3፡16)፣ በድጋሚም ጥቅም ላይ በሴፕቱዋጊንት፣ 2ኛ ነገሥት 2፡9፣11 ለኤልያስ ትርጉም ወደ ሰማይ ለመነጠቁ እና 1ኛ መቃብያን 2፡58 ጥቅም ላይ ውሏል
> 2. epair, ወደ ላይ መነሣት፣ ወደ ላይ ማረግ፣ ማሻቀብ (ሐዋ. 1፡9)
> 3. analepsis, (ሉቃስ 9፡51፣ የቁጥር 1 ቅርጽ)
> 4. distani, መለየት
> 5. anabainō, ማረግ (ዮሐንስ 6፡62)
>
> ይህ ሁነት በማቲዎስም ሆነ በማርቆስ ወንጌል አልተጠቀሰም። የማርቆስ ወንጌል የሚያበቃው 16፡8 ላይ ሲሆን፣ ዳሩግን ከሦስቱ ኋለኛ ተረፈ ጽሑፎች መካከል አንደኛው ሁነቱን ይገልጻል፣ በ16፡19 ላይ (analambanō)።

▣ እርሱ በመንፈስ ቅዱስ አለው ሚለውን ከሚቀጥለው ሠንጠረዥ ይመልከቱ።

**ልዩ ርእስ፡ እሱም በመንፈስ ቅዱስ አድርጓልና**

*ይህ በሐዋርያት ሥራ ዋነኛ የሆነው "መንፈስ ቅዱስ" ለመጀመሪያ ጊዜ የተገለጠበት ነው። በብ.ኪ. "የእግዚአብሔር መንፈስ" (ruach ሩሕ) የያህዌህን ተግባር ለመፈጸም የሚሆን ኃይል ነበር፣ ነገር ግን አካላዊ ለመሆኑ ምንም ዓይነት ፍንጭ የለም፣ (ብ.ኪ. አንድነታዊነት)። ቢሆንም፣ በአ.ኪ. የመንፈስ ቅዱስ ሙሉ አካላዊነት እና አካላዊ ኀብረት ተጽፏል።*

1. *የማይገባ ቃል ሊባል ይችላል (ማቴ. 12፡31፤ ማርቆስ 3፡29)*
2. *ያስተምራል (ሉቃስ 12፡12፤ ዮሐንስ 15፡26)*
3. *ምስክርነት ይሰጣል (ዮሐንስ 15፡26)*
4. *ይወቅሳል (ይከሳል)፣ ይመራል (ዮሐንስ 16፡7-15)*
5. *"ማን" ተብሎ ይጠራል (hos፣ ኤፌ. 1፡14)*
6. *ሊያዝን ይችላል (ኤፌ. 4፡30)*
7. *ሊጠፋ (ጸጥ ሊል) ይችላል (1ኛ ተሰ. 5፡19)*

*ሥላሴያዊ ጽሑፎች ደግሞ ስለ ሦስቱ አካላት ይናገራሉ (ልዩ ርዕስ፡ሥላሴ 2፡32-33) ተመልከት*

1. *ማቴ. 28፡19*
2. *2ኛ ቆሮ. 13፡14*
3. *1ኛ ጴጥ. 1፡2*

*መንፈስ ከሰዎች ተግባር ጋር ይያያዛል።*

1. *ሐዋ. 15፡28*
2. *ሮሜ. 8፡26*
3. *1ኛ ቆሮ. 12፡11*
4. *ኤፌ. 4፡30*
5. *1ኛ ተሰ. 5፡15*

*በሐዋ. በመጀመሪያው ላይ የመንፈስ ሚና ገነን ተደርጓል። ጰንጠቆስጤ የመንፈስ ሥራ መጀመሪያ አልነበረም፣ ነገር ግን አዲስ ምዕራፍ እንጂ። ኢየሱስ ሁሌም መንፈስ አለው። የሱ መጠመቅ የመንፈስ ሥራ መጀመሪያ አልነበረም፣ ነገር ግን አዲስ ምዕራፍ እንጂ። ሉቃስ ቤተክርስቲያንን ያዘጋጃት ለአዲሱ ውጤታማ አገልግሎት ነው። አትኩሮቱ አሁንም ኢየሱስ ነው፣ መንፈስ አሁንም ውጤታማ አድራጊና የአባት ፍቅር፣ ይቅር ባይነት እና ሁሉንም የሰው ልጆች በአምሳሉ የተፈጠሩትን መመለስ ነው!*

▣ **"የተሰጡ ትዕዛዞች"** *ይህ የሚያመለክተው በሉቃስ ወንጌል ላይ ያልተመዘገበ መረጃን ሲሆን፣ ነገር ግን በማቴ.* 28፡18-20 *እና ሐዋ.* 1፡8 *ላይ አለ።*

▣ **"ትዕዛዞች"** *ይህ ያለፈ የድርጊት መካከለኛ (አረጋጋጭ) ቦዝ አንቀጽ ነው። አንዳንድ ሊቃውንት ይሄንን የሚመለከቱት እንደ* 1፡8 *(ማቴ.* 28፡19-20፤ *ሉቃስ* 24፡45-47 *ወይም ሉቃስ* 24፡49) *ነው። ቤተ ክርስቲያን ሁለት ቀጣይነት ያላቸው ተግባራት አሏት፡* (1) *ወንጌላዊነት እና ክርስቶስን የመምሰል ብስለት። እያንዳንዱ አማኝ እነዚህን ለመቀዳጀት የእግዚአብሔርን ኃይል መጠበቅና መታጠቅ ይኖርበታል።* (2) *ሌሎች ደግሞ የሚያጣቅሱት "የመንፈስን መምጣት እና ኃይል መላበስን፣ በኢየሩሳሌም ሆኖ መጠበቅን" ነው፣ ዝከ ቁ.* 4፤ *ሉቃስ* 24፡49)።

▣ **"ሐዋርያት"** *የሐዋርያትን ስሞች ዝርዝር የሚለውን በ*1፡13 *ላይ ተመልከት።*

▣ **"እሱ ተመርጧል"** *"የተመረጠ"* (eklegō፣ *የድርጊት መካከለኛ አመላካች) ሲሆን በሁለት ዓይነት ሐሳብ ነው የገባው። ዘወትር በብ.ኪ. የሚጠቀሰው ለአገልግሎት እንጂ ለደኅንነት አይደለም፤ ነገር ግን በአ.ኪ. የሚጠቀሰው ለመንፈሳዊ ደኅንነት ነው። እዚህ የተጠቀሰ የሚመስለው ለሁለቱም ሐሳቦች ነው (ሉቃስ* 6፡13)።

**1፡3 "ራሱን ሕያው አድርጎ አቅርቧልና"** *ይህ ምናልባት የሚያመለክተው የኢየሱስን ሦስት ገጽታዎች፣ በደርቡ ከፍል ላይ ለሞላው ኀብረት በቀጣዩ እሑድ ምሽት የታየበትን ሲሆን፣ ነገር ግን ደግሞ ሊያመለክት የሚችለው ሌሎች መከሰቶችን ይሆናል (1ኛ ቆሮ.* 15፡5-8)። *የኢየሱስ ትንሣኤ ወሳኝ የሚሆነው ለወንጌል እውነተኛነት ነው፣* (2፡24፣32፤ 3፡15፣26፤ 4፡10፤ 5፡35፤ 10፡40፤ 13፡30፣33፣34፣37፤ 17፡31፤ *እና በተለይ 1ኛ ቆሮ.* 15፡12-19፣20)። *የሚከተለው ሰንጠረዥ ድህረ-ትንሣኤ ክስተቶችን ከጳውሎስ ባርኔት፣ ኢየሱስ እና የጥንት ክርስትና አነሣሥ፣ ገጽ* 185 *ላይ ያለ ነው።*

| ዮሐንስ | ማቲዎስ | ሉቃስ | 1ኛ ቆሮንቶስ |
|---|---|---|---|
| | | ***የኢየሩሳሌም ገጽታዎች*** | |
| ማርያም (ዮሐ. 20፡15) | | | |
| | ሴቶች (ማቲ. 28፡9) | | |
| | | ስምዖን (ሉቃ. 24፡34) | ኬፋ (1ኛ ቆሮ. 15፡5) |
| | | ሁለቱ በኢማኦስ መንገድ ላይ (ሉቃ. 24፡15) | |
| | | ደቀ መዛሙርት (ሉቃ. 24፡36) | አስራ ሁለቱ(1ኛ ቆሮ. 15፡5) |
| አስሩ ደቀ መዛሙርት (ዮሐ. 20፡17) | | | |
| አስራ አንዱ ደቀ መዛሙርት (ዮሐ. 20፡26) | | | |
| | ***የገሊላ ገጽታዎች*** | | |
| | | | 500+አማኞች (1ኛ ቆሮ. 15፡6፤ ከማቲዎስ ጋር ሊገናኝ የሚችል፡፡ 28፡16-20) |
| | | | ያዕቆብ (1ኛ ቆሮ. 15፡7) |
| ሰባቱ ደቀ መዛሙርት (ዮሐ. 21፡1) | | | |
| | ደቀ መዛሙርት (ማቲ. 28፡16-20) | | |
| | | ***የኢየሩሳሌም ገጽታዎች*** | |
| | | ዕርገቱ (ሉቃ. 24፡50-51) | ሁሉምሐዋርያት(1ኛ ቆሮ. 15፡7) |

▣
**አአመመቅ፣ አየተመት፣**

| | |
|---|---|
| **አኢት** | **"በብዙ አሳማኝ ማረጋገጫዎች"** |
| **አኪጀት** | **"በብዙ ጽኑ ማረጋገጫዎች"** |
| **አእት** | **"ብዙ ጊዜ በብዙ መንገዶች ያለ ጥርጥር የተረጋገጠ"** |
| **አኢመቅ** | **"በብዙ ማስረጃዎች"** |

ቴክሜሪዮን (tekmērion) የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው እዚህ ብቻ በአ.ኪ. ነው፡፡ ደጎና የቃላት ማብራሪያ፣ በግሪክ ሥነ-ጽሑፍ ጥቅም ላይ የዋሉ፣ በሙልቶንና ሚሊጋን፣ *የግሪክ አዲስ ኪዳን መዝገበ ቃላት፣* ገጽ 628፣ ፍችውም "የድርጊት ማረጋገጫ" የሚል ነው፡፡ ይህ ቃል ሌላም ጥቅም ላይ የዋለው በጥበበ-ሰለሞን ላይ ነው፣ 5፡11፤ 19፡3 እና 3ኛ መቃብያስ 3፡24፡፡

▣ **"ከመከራው በኋላ"** የአይሁድ አማኞች ይህንን የወንጌል ገጽታ ሊቀበሉ የቻሉት በብዙ ችግር ነው (1ኛ ቆሮ. 1፡23)፡፡ የመሲሑ መከራ በብ.ኪ. የተጠቀሰው (ዘፍ. 3፡15፤ መዝ. 22፤ ኢሳ. 53፤ እና በሉቃስ 24፡45-47 ተመልከት)፡፡ ይህ ዋነኛው የሐዋርያዊ ስብከት ሥነ-መለኮታዊ ማጽኛ ነው (ጥንታዊ ስብከተ-ወንጌል፤ 2፡13 ልዩ ርዕስ ተመልከት፡፡)

ሉቃስ አዘውትሮ የተጠናቀቀ የአሁን ንዑስ አንቀጽ ይጠቀማል፣ ለፓስቾ (መከራ) ይህም የኢየሱስን ስቅለት ለማመላከት (ሉቃስ 9፡22፤ 17፡25፤ 22፡15፤ 24፡26፣46፤ ሐዋ. 1፡3፤ 3፡18፤ 9፡16፤ 17፡3)፡፡ ሉቃስ ይሄንን ያገኘው ለማርቆስ ወንጌል ሊሆን ይችላል (ዝ.ከ 8፡31)፡፡

▣ **"ለእነሱ እየተገለጠላቸው"** በአ.ኪ. ተመዝግበው የተተዉልን የኢየሱስ የትንሣኤ ገጽታዎች አስር ወይም አስራ አንድ ናቸው፡፡ ሆኖም፣ እነዚህ ወካይ ሊሆኑ የሚችሉ ናሙናዎች ናቸው እንጂ አጠቃላይ ዝርዝሩ አይደለም፡፡ ባጠቃላይ ኢየሱስ በጊዜው መጥቶ ሄዷል፣ ነበር ግን ከማንም ቡድን ጋር አልቆየም፡፡

▣ **"አርባ ቀናት"** ይህ የብ.ኪ. ዘይቤ ሲሆን ለረጅም ላልተወሰነ ጊዜ ነው፣ ከጨረቃ ዑደት የሚበልጥ፡፡ እዚህ የሚያያዘው ከዓመታዊው የአይሁድ የፋሲካ በዓል እና ጰንጠቆስጤ መካከል ያለውን ሲሆን (እሱም ሃምሳ ቀናት ነው)፡፡ የዚህ መረጃ ብቸኛው ምንጭ ሉቃስ ነው፡፡ የዕርገቱ ቀን ዋና ጉዳይ አይደለም (እንዲያውም እስከ አራተኛው ክፍለ ዘመን፣ ዓ.ም ድረስ በክርስቲያን ጸሐፊዎች አልተመዘገበም)፣ ለቁጥሩ ሌላ ዓላማ ሊኖረው ይችላል፡፡ ከሙሴ በሲና ተራራ ላይ፣ እስራኤል በምድረ በዳ፣ የኢየሱስ የፈተና ጊዜ፣ ወይም በማናውቀው ምክንያት፣ ነገር ግን ግልጽ የሆነው ራሱ ጊዜው ዋነኛ ጉዳይ አይደለም፡፡

▣ *“ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የሆኑትን ጉዳዮች እየተናገሩ”* ግኖስቲኮች፣ ኢየሱስ ምሥጢራዊ የሆነ መረጃን ለእነሱ ቡድን በፋሲካ እና በጰንጠቆስጤ ባሉት ቀናት እንደገለጠላቸው ይከራከራሉ:: ይህ በርግጥ ስህተት ነው:: ሆኖም፣ የሁለቱ የኢማኦስ መንገደኞች  ጉዳይ ስለ ኢየሱስ የትንሣኤ ኂላ ትምህርት ጥሩ ምሳሌ ነው:: እኔ እንደማስበው፣ ኢየሱስ ራሱ፣ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከብሉይ ኪዳን የሚያመላክታቸው፣ ትንበያዎቹ እና ጽሑፎች ከእሱ ሕይወት፣ ሞት፣ ትንሣኤና ዳግም ምጽዓት ጋር እንደሚያያዙ ነው:: ልዩ ርዕስ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት የሚለውን ቀጣዩን ተመልከት::

**ልዩ ርዕስ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት**

በብ.ኪ ያህዌ የሚታሰበው እንደ እስራኤል ንጉሥ ነው (1ኛ ሳሙ. 8፡7፤ መዝ. 10፡16፤ 24፡7-9፤ 29፡10፤ 44፡4፤ 89፡18፤ 95፡3፤ ኢሳ. 43፡15፤ 44፡4፣6) እና መሲሑን እንደ መጻዒ ንጉሥ ይቆጥሩታል፣ መዝ. 2፡6። ኢየሱስ በቤተልሔም በመወለዱ (6-4 ዓ.ም) የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ ሰዎች ታሪክ በአዲስ ኃይል እና መቤዠት ገባ (አዲስ ኪዳን፣ ኤር. 31፡31-34፤ ሕዝ. 36፡17-36)። መጥምቁ ዮሐንስ የመንግሥቱን መቃረብ አውጇል (ማቴ. 3፡2፤ ማቴ. 1፡15)። ኢየሱስ በግልጽ መንግሥቱ በራሱ እና በትምህርቱ እንደሆነ አስተምሯል (ማቴ. 4፡17፣23፤ 9፡35፤ 10፡7፤ 11፡11-12፤ 12፡28፤ 16፡19፤ ማርቆስ 12፡34፤ ሉቃስ 10፡9፣11፤ 11፡20፤ 12፡31-32፤ 16፡16፤ 17፡21)። ቢሆንም መንግሥቱ ወደፊት ነው፣ ማቴ. 16፡28፤ 24፡14፤ 26፡29፤ ማርቆስ 9፡1፤ ሉቃስ 21፡31፤ 22፡16፣18)።

በማርቆስና በሉቃስ ትይዩነት የሚከተለው አቻ ሐረግ ይገኛል፣ “የእግዚአብሔር መንግሥት።” ይህ የኢየሱስ ትምህርቶች የታወቁ ርዕሶች በአሁኑ የእግዚአብሔር አገዛዝ በሰዎች ልብ ውስጥ መግባት፣ አንድ ቀን በመላው ዓለም ጥቅም ላይ ይውላል። ይህ በኢየሱስ ጸሎት በማቴ. 6፡10 ላይ ተንጸባርቋል። ማቲዎስ፣ ለአይሁድ ሲጽፍ የእግዚአብሔርን ስም የማይጠቅስ ሐረግን መርጧል (የእግዚአብሔር መንግሥት)፣ በሌላ በኩል ማርቆስና ሉቃስ፣ ለአሕዛብ ሲጽፉ፣ በሁሉም ዘንድ የሚታወቀውን የመለኮትን ስም መጠቀም መርጠዋል።

ይህ ክርክር የተፈጠረው በሁለቱ የክርስቶስ ምጽዓቶች ነው። ብ.ኪ ያተኮረው በእግዚአብሔር መሲሕ፣ ወታደራዊ፣ ፈራጅ፣ ባለግርማ ሆኖ መምጣት ላይ ሲሆን፣ ነገር ግን አ.ኪ የሚያመለክተው የመጀመሪያ ምጽዓቱ መከራን እንደሚቀበል ባርያ በኢሳ. 53 እንዳለው እንዲሁም ትሑቱ ንጉሥ ዘካ. 9፡9። ሁለቱ የአይሁድ ዘመናት፣ የኩነኔ ዘመናት እና አዲሱ የጽድቅ ዘመን ይደራረባሉ። ኢየሱስ አሁን በአማኞች ልብ ውስጥ ይገዛል፣ ነገር ግን አንድ ቀን በሁሉም ፍጥረታት ላይ ይገዛል። በብ.ኪ እንደተተነበየው ይመጣል። አማኞች የሚኖሩት “በገና ድሮው” ወይም “ገና በሚመጣው” የእግዚአብሔር መንግሥት ነው። (ጎርዶን ዲ. ፊ እና ዳግላስ ስቱዋርት *መጽሐፍ ቅዱስ ከነሙሉ ጠቀሜታው እንዴት ይነበባል*፣ ገጽ 131-134)።

1፡4

| | |
|---|---|
| አአመመቅ | “ሁሉንም አንድ ላይ ሰበስበው” |
| አኪጀት | “ከእነሱ ጋር አንድ ላይ ተሰብስበው” |
| አየተመቅ | “ከእነሱ ጋር በቆዩ ጊዜ” |
| አእት | “አንድ ላይ በመጡ ጊዜ” |
| አእት[ሀ] | “ከእነሱ ጋር በቆዩ ጊዜ” |
| አእት[ለ]፣ አኢት | “ከእነሱ ጋር በማዕድ በነበሩበት ጊዜ” |
| አኢመቅ፣ KNOX | “በማዕድ ከእነሱ ጋር በተቀመጡ ጊዜ” |

ቁጥር 4-5 የሚጠቀመው አንዱን የኢየሱስን ገጽታ ምሳሌ ነው፣ ከብዙዎቹ የእሱ ገጽታዎች እና ማስረጃዎች መካከል:: ሱናሊዞሜኖስ (sunalizomenos) የሚለው ቃል አነባበቡ ልዩ ነው:: አነባበቡ ትርጉሙን ይቀይራል::

1. ረጅሙ - መሰብሰብ)አንድላይ
2. አጭር - መመገብ አንድላይ (በጥሬ ትርጉሙ “ከጨው ጋር”)
3. መካከለኛ - አንድ ላይ መቆየት

የትኛው ተገቢ እንደሆነ ርግጥ አይደለም፣ ነገር ግን ሉቃስ 24፡41-43 (ዮሐንስ 21) የሚያመለክተው ኢየሱስ ከሐዋርያዊ ወገን ጋር አብሮ መመገቡን ነው፣ ይህም ሊሆን የሚችለው ለትንሣኤ አካሉ ማስረጃ ነው (ቁ.3)::

▣ **“ከአየሩሳሌም እንዳይወጡ”** ይህ የተመዘገበው በሉቃስ 24፡49 ነው:: የመጀመሪያው የሐዋርያት ሥራ ክፍል የሉቃስ ወንጌል ማጠቃለያን መቃኘት ሲሆን፣ ይህም በጽሑፋዊ ዘዴ ሁለቱን መጻሕፍት ለማገናኘት ነው::

▣ **“አብ የሰጠውን ተስፋ ለመጠባበቅ”** በ2፡16-21 ጴጥሮስ ይሄንን ከመጨረሻው ጊዜ ትንቢት ከኢዩኤል 2፡28-32 ጋር ያዛምደዋል:: እስከ ጰንጠቆስጤ ድረስ አስር ቀናት ጠብቀዋል:: ሉቃስ በተለየ መልኩ “የአብ ተስፋ” የሚለውን የሚሰይመው እንደ መንፈስ ቅዱስ ነው (ሉቃስ 4፡49፤ ሐዋ. 2፡33):: ኢየሱስ ቀደም ሲል ለእነሱ ስለ መንፈስ ቅዱስ መምጣት በዮሐንስ 14-16 ላይ ነግሯቸዋል:: ሆኖም፣ ሉቃስ የአብን ተስፋ የተረዳው እንደ አንድ ነገር ብቻ አይደለም ብሎ መውሰድ ይቻላል (ያም ማለት፣ መንፈስ ቅዱስ) ነገር ግን ደግሞ በብ.ኪ ቃል የተገባው ተስፋ ወደ እስራኤል የሚመጣው በመሲሑ አካል በኩል ነው (ሐዋ. 2፡39፤ 13፡23፣ 32፤ 26፡6)::

▣ “አብ” ብ. ኪ. የሚያስተዋውቀው ወዳጃዊ ቤተሰባዊ የሆነውን ዘይቤ ለእግዚአብሔር፣ አብ በማለት ነው፡ (1) የእስራኤል ሕዝቦች ዘወትር የሚገልጹት የያህዌ “ወንድ ልጅ” እንደሆኑ ነው (ሆሴ. 11፡1፤ ሚልክ. 3፡17)፤ (2) እንዲያውም ቀደም ሲል በዘዳግም የእግዚአብሔር ምስያ እንደ አብ  ጥቅም ላይ ውሏል (1፡31)፤ (3) በዘዳ. 32፡6 እስራኤል የሚጠራው “የእሱ ልጆች” በሚል ነው፣ እንዲሁም እግዚአብሔር የሚጠራው “የእናንተ አባት” በሚል ነው፤ (4) ይህ ምስያ በመዝ. 103፡13 እና ተሻሽሎ በመዝ. 68፡5 (የደሀ አደጎች አባት (የሙት ልጆች አባት) በሚል ተጠርቷል፤ እንዲሁም (5) በነቢያትም የተለመደ ነበር (ኢሳ. 1፡2፤ 63፡8፤ እስራኤል እንደ ወንድ ልጁ፣ አግዚአብሔር እንደ አባት፣ 63፡16፤ 64፡8፤ ኤር. 3፡4፣19፤ 31፡9)።

ኢየሱስ ይናገር የነበረው አራምኛ ሲሆን፣ ይህም ማለት አብዛኛዎቹ ቦታዎች “አባት” የሚገኙት እንደ ግሪኩ ፓተር የሚያንጸባረቀው የአራምኛውን አባ ነው (ዝ. ከ 14፡36)። ይህ ቤተሰባዊ ቃል “አባ” ወይም “አባዬ” የሚያንጸባርቀው የኢየሱስን ለአብ ቅርበት ነው። ይህን ለተከታዮቹ መግለጡ ደግሞ የእኛን ከአብ ጋር ያለ ወዳጅነት ያበረታታል። “አብ” የሚለው ቃል በብ.ኪ. ጥቅም ላይ የሚውለው አልፎ አልፎ ነው (እናም ፈጽሞ በራቢያዊ ሥነ-ጽሑፍ) ለያህዌ፣ ነገር ግን ኢየሱስ አዘውትሮና በስፋት ይጠቀመበታል። እሱም ዋነኛው የአማኞች መገለጥ አዲስ ኅብረት በክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ነው። ማቴ. 6፡9)

1፡5 “ዮሐንስ” ሞላው አራቱም ወንጌላት (ማቴ. 3፡1-12፤ ማርቆስ1፡2-8፤ ሉቃስ 3፡15-17፤ ዮሐንስ 1፡6-8፣ 19-28) የመጥምቁ ዮሐንስን አገልግሎት ይናገራሉ። “ዮሐንስ” ጆሐናን የሚለው የዕብራይስጥ ስም አጽሕሮታዊ ቅርጽ ሲሆን ትርጉሙም “ያህዌ ባለ ግርማ ነው” ወይም “የያህዌ ስጦታ” ማለት ነው። የእሱ ስም እጅግ ትርጉም ያለው ነው፣ ምክንያቱም እንደሌሎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ስሞች እግዚአብሔር በሕይወቱ ያደረገለትን አመላካች ነው። ዮሐንስ የብሉይ ኪዳን ነቢያት የመጨረሻ ነው። ከሚልክያስ ወዲህ፣ 430 ዓ.ም አካባቢ በእስራኤል ምንም ነቢይ አልነበረም። የእሱ መኖር ታላቅ መንፈሳዊ ደስታ በእስራኤል ላይ ፈጥሯል።

▣ “በውኃ ተጠምቀው” ጥምቀት በአንደኛውና ሁለተኛው ክፍለ ዘመን በአይሁድ የተዘወተረ ሥርዓት ነበር፣ ነገር ግን በተለይ ወደ ይሁዲነት ከሚቀየሩ ጋር ነው። አንዱ ከአሕዛብ ወገን ሆኖ የእስራኤል ሙሉ ልጅ ለመሆን ቢፈልግ ሦስት ነገሮችን መፈጸም ይጠበቅበታል፡ (1) ግዝረት፣ ወንድ ከሆነ፤ (2) በሦስት ምስክሮች ፊት በውኃ ውስጥ በመጥለም መጠመቅ፤ እና (3) በቤተ መቅደስ መሥዋዕት ማቅረብ፣ ከተቻለ። በአንደኛው ክፍለ ዘመን ፍልስጥኤም ልዩ ወገን፣ እንደ ኤሰንስ ያሉት፣ ጥምቀት ባጠቃላይ የተለመደ፣ የሚደጋገም ልምድ ነው። ሆኖም፣ ወደ ይሁዲነት ለመግባት፣ አምልኳዊ ሥርዓቶች ለዚህ ክብረ በዓላዊ መታጠብ የሚያስፈልገው፡ (1) እንደ መንፈሳዊ መንጻት (ኢሳ. 1፡16፤ እና (2) በቄሶች እንደሚደረግ  መደበኛ አምልኳዊ ክዋኔ ነው (ዘጸ. 19፡10፤ ሌዋ. 15)።

▣ “እናንተም በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ” ይህ የትንቢት ተገብሮ አመላካች ነው። የተገብሮ ጊዜው ኢየሱስን አመላካች ሊሆን ይችላል፣ በማቴ. 3፡11፤ ሉቃስ 3፡16 ምክንያት። ኢቪ. የሚለው መስተጻምር ሊሆን የሚችለው “በ...ውስጥ፣” “ከ...ጋር፣” ወይም “በ” ሲሆን (ይህም ማለት መሣርያ፣ ማቴ. 3፡11)። ሐረጉ ሁለት ሁነቶችን ሊያመላክት ይችላል፡ (1) ክርስቲያን መሆንን (1ኛ ቆሮ. 12፡13) ወይም (2) በዚህ ጽሑፍ፣ ተስፋ የተደረገው ለውጤታማ አገልግሎት መንፈሳዊ ኃይል። መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ አገልግሎት ዘወትር በዚህ ሐረግ ይገልጻል፣ (ማቴ. 3፡11፤ ማርቆስ 1፡8፤ ሉቃስ 3፡16-17፤ ዮሐንስ 1፡33)።

ይህ የዮሐንስ ጥምቀት ተቃርኖ ነው። መሲሑ አዲሱን የመንፈስ ዘመን ይመርቃል። የእሱ ጥምቀት የሚሆነው ከ (ወይም “በ” ወይም “በ”) መንፈስ ነው። ይህ ምን እንደሚያመለክት በርካታ ክርክሮች በየ መሠረተ እምነቱ የነበሩ ሲሆን፣ ይህም በምን ዓይነቱ ክርስቲያናዊ ልምድ እንደሆነ ነው። አንዳንዶች የሚወስዱት ከመዳን በኋላ ያለውን ኃይል መሞላት ነው፣ እንደ ሁለተኛ መባረክ ዓይነት። እኔ በበኩሌ የምወስደው ክርስቲያን ከመሆን ጋር ነው (1ኛ ቆሮ. 12፡13)። ኋላ ላይ የሚሆኑትን መሞላቶችና መታጠቆች ልክድ አይደለም፣ ነገር ግን አንድ መነሻ የሚሆን መንፈሳዊ ጥምቀት አማኞች በኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ የሚገለጡበት አለ ብዬ ስለማምን ነው፣ (ሮሜ. 6፡3-4፤ ኤፌ. 4፡5፤ ቆላ. 2፡12)። ይህ የመንፈስ የማነሣሣት ሥራ በዮሐንስ 16፡8-11 ላይ ታይቷል። እንደ እኔ መረዳት የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች፡

1. ኃጢአትን ማስታወቅ (መውቀስ)
2. ስለ ኢየሱስ እውነትን መግለጥ
3. ወንጌልን ወደ መቀበል መምራት
4. ወደ ኢየሱስ ማጥመቅ
5. ቀጣይ ኃጢአትን ለአማኝ ማስታወቅ (መውቀስ)
6. በአማኝ ውስጥ ክርስቶስን መምሰል ማካሄድ

▣ “ከአሁን በኋላ ብዙ ባልሆኑ ቀናት” ይህ የሚያመለክተው የአይሁድን በዓል ጰንጠቆስጤን ሲሆን እሱም የሚውለው ከፋሲካ በኋላ በሰባተኛው ቀን ነው። የሚያሳስበውም የእህሉ አዝመራ ባለቤት እግዚአብሔር መሆኑን ነው። እሱም ከፋሲካ በኋላ በሃምሳኛ ቀኑ ይውላል (ዘሌዋ. 23፡15-31፤ ዘጸ. 34፡22፤ ዘዳ. 16፡10)።

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፥ 1፡6-11**

[6]እነርሱም በተሰበሰቡ ጊዜ። ጌታ ሆይ፥ በዚህ ወራት ለእስራኤል መንግሥትን ትመልሳለህን? ብለው ጠየቁት። [7]እርሱም፦ አብ በገዛ ሥልጣኑ ያደረገውን ወራትንና ዘመናትን ታውቁ ዘንድ ለእናንተ አልተሰጣችሁም፤ [8]ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ። [9]ይህንም ከተናገረ በኋላ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ፤ ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው። [10]እርሱም ሲሄድ ወደ ሰማይ ትኵር ብለው ሲመለከቱ ሳሉ፥ እነሆ፥ ነጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በአጠገባቸው ቆሙ፤ [11]ደግሞም፦ የገሊላ ሰዎች ሆይ፥ ወደሰማይ እየተመለከታችሁ ስለ ምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት፥ እንዲሁ ይመጣል አሉአቸው።

1፡6 **"ይጠይቁት ነበር"** ያልተጠናቀቀ ጊዜ ሲሆን አንድም የተደገመ የኃላፊ ጊዜ ድርጊት ወይም የአንድ ድርጊት መነሻ ነው:: ባጠቃላይ እነዚህ ሐዋርያት ይሄንን ብዙ ጊዜ ጠይቀዋል::

▣ **"ጌታ"** የግሪኩ ቃል ጌታ (ኩሪዮስ) ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው በአጠቃላይ ሁኔታ ወይም በተሻሻለ ሥነ መለኮታዊ አግባብ ነው:: እሱም ሊሆን የሚችለው "አቶ፣" "ጌታው፣" "ጌታ፣" "ባለቤት፣" "ባል፣" ወይም "ፍጹም የእግዚአብሔር ሰው" (ዮሐንስ 9፡36፣38):: ብ.ኪ. (የዕብራይስጥ፣ አዶን) የዚህ ቃል አጠቃቀም የመጣው ከአይሁድ ሙሉ ፍቃደኛ ካለመሆን የኪዳን ስሙን ለመጥራት በእግዚአብሔር፣ ያህዌ፣ ይህም ምክንያት የሆነ የዕብራይስጥ ግሥ "መሆን" ነው (ዘጸ. 3፡14):: "የጌታ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ አትጥራ" የሚለውን ትዕዛዙን እንዳይሰብሩ ፈርተዋል (ዘጸ. 20፡7፤ ዘዳ. 5፡11):: ስለሆነም፣ እነሱ ካልጠሩት፣ በከንቱ እንዳላነሡት አስበዋል:: ስለሆነም፣ የዕብራይስጡን ቃል አዶንን ቀይረዋል፣ ይህም ከግሪኩ ቃል ኩሪዮስ (ጌታ) ጋር ተመሳሳይ ፍች አለው:: የአ.ኪ. ጸሐፍት ይህን ቃል የሚጠቀሙት የኢየሱስን ፍጹም መለኮትነት ለመግለጽ ነው:: "ኢየሱስ ጌታ ነው" የሚለው ሐረግ የአደባባይ የእምነት መግለጫ እና የጥንት ቤተ-ክርስቲያን የጥምቀት ቀመር (መግለጫ) ነው፣ (ሮሜ. 10፡9-13፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡3፤ ፊሊጵ. 2፡11)::

▣ **"' በዚህ ጊዜ የእስራኤልን መንግሥት የምትመልስበት ነው'"** እነሱ አሁንም ቢሆን አይሁዳዊ ብሔረተኝነት አስተሳሰብ አላቸው (መዝ. 14፡7፤ ኤር. 33፡7፤ ሆሴ. 6፡11፤ ሉቃ. 19፡11፤ 24፡21):: እነሱ ምናልባትም ስለ ኃላፊነት ሥልጣናቸው ሳይጠይቁ አይቀሩም::

ይህ ሥነ መለኮታዊ ጥያቄ አሁንም ብዙ ውዝግብ እንደፈጠረ ነው:: እዚህ ላይ ለመጨመር የምፈልገው በራዕይ ላይ የጻፍኩትን ሐተታ ከፊሉን ሲሆን እሱም ርዕሰ- ጉዳዩን ደኅና አድርጎ የሚገልጽ ይመስለኛል::

> "የብ.ኪ. ነቢያት የአይሁድን መንግሥት መመለስ በፍልስጥኤም በኢየሩሳሌም ማዕከል እንደሚሆንና ይህም ሁሉም የምድር ሕዝቦች ተሰብስበው የዳዊትን ገዥ ያመሰግናሉ፥ ዳሩ ግን የአ.ኪ. ሐዋርያት በዚህ (ርዕሰ-ጉዳይ) አጀንዳ ላይ ፈጽመው አላተኮሩም:: ብ.ኪ. ተመስጦአዊ አይደለምን (ማቴ. 5፡17-19)? የአ.ኪ. ጸሐፍት ዋነኛውን የፍጻሜ ሰዓት ሁነት ይገድፉታልን?
>
> ስለ ዓለም ፍጻሜ በርካታ የመረጃ ምንጮች አሉ፡
>
> 1. የብ.ኪ. ነቢያት
> 2. የብ.ኪ. የምጽዓት ጸሐፊዎች (ሕዝ. 37-39፤ ዳን. 7-12)
> 3. አዋልዳዊ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ የማይቆጠሩ የአይሁድ የትንቢት ጸሐፍት (እንደ 1ኛ ሄኖክ)
> 4. ኢየሱስ ራሱ (ማቴ. 24፤ ማርቆስ 13፤ ሉቃስ 21)
> 5. የጳውሎስ ጽሑፎች (1ኛ ቆሮ. 15፤ 2ኛ ቆሮ. 5፤ 1ኛ ተሰ. 4፤ 2ኛ ተሰ. 2)
> 6. የዮሐንስ ጽሑፎች (የራዕይ መጽሐፍ)::

እነዚህ ሁሉ በግልጽ የመጨረሻውን ዘመን አጀንዳ (ሁነቶች፣ ቅደም ተከተል፣ ሰዎች)? ካልሆነ፣ ለምን? ሁሉም ተመስጧዊ አይደሉምን (ከአይሁድ አዋልዳዊ ጽሑፎች በቀር)?

መንፈስ እውነትን ለብ.ኪ. ጸሐፍት የሚገልጸው በቃላትና ሊረዱት በሚችሉት ምድቦች ነው:: ሆኖም፣ ቀጣይነት ባለው መገለጥ መንፈስ እነዚህን የብ.ኪ. ከፍጻሜ ጋር የተያያዙ ጽንሰ-ሐሳቦች በሁለንተናዊ ደረጃ ቀርበዋል (ኤፌ. 2፡11-3፡13):: እዚህ ጠቃሚ ምሳሌዎች ተሰጥተዋል፡

1. የኢየሩሳሌም ከተማ ለእግዚአብሔር ሕዝብ (ጽዮን) እንደ ዘይቤ ነው ጥቅም ላይ የዋለው፣ የሚያመለክተውም ለአ.ኪ. ደግሞ ቃሉ የሚገልጸው እግዚአብሔር ሁሉንም በንስሐ የተመለሱትን፣ አማኝ ሰዎችን (በራዕይ 20-22 እንደተመለከተው አዲሲቱን ኢየሩሳሌምን) ማሳየቱ ነው:: ሥነ-መለኮታዊ ዳርቻው በጥሬው የተገለጠው፣ ሥጋዊው ከተማ ለእግዚአብሔር ሕዝብ የሚሆነው እንደ ንግር፣ ለእግዚአብሔር ተስፋ የወደቀውን የሰው ልጅ ለመቤዠት በዘፍ. 3፡15፣ ይህም አንድም አይሁድ ወይም የአይሁድ ዋና ከተማ ሳይኖር ነው:: የአብርሃምም ጥሪ (ዘፍ. 12፡3) አሕዛብንም አካቷል::
2. በብ.ኪ. ጠላቶች የነበሩት በዙሪያው ያሉት የጥንታዊው ቅርብ ምስራቅ ሕዝቦች ነበሩ፤ ነገር ግን በአ.ኪ. የተስፋፉት ወደ ሁሉም የማያምኑት፣ ጸረ-እግዚአብሔር (ዐመጸኞች) በሰይጣን መንፈስ ሥር ወደ አሉ ሕዝቦች ነው:: ጦርነቱ የቀጠለው ከመልክዓ ምድራዊ፣ ክልላዊ ግጭት ወደ ዓለም አቀፍ ግጭት ነው::

3. የምድሩ ተስፋ እሱም ከብ.ኪ. ጋር ጽኑ ቅርኝት አለው (ለአባቶች የተሰጠው ተስፋ) አሁን ደግሞ ለመላው ዓለም ሆነ፡፡ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ዳግም ወደተፈጠረችው መሬት መጣች፣ ቅርብ ምስራቅ ብቻ ያልሆነ ወይም ያልተወ (ራዕ. 20-22)፡፡
4. ሌሎች ተጨማሪ ምሳሌዎች ከብ.ኪ. ነቢያታዊ ጽንሰ-ሐሳቦች ተስፋፊ የሚሆኑት (1) የአብርሃም ዘር የሆኑት አሁን በመንፈስ የተገረዙት ናቸው (ሮሜ 2፡28-29)፤ (2) የቃል ኪዳኑ ሕዝቦች አሁን አሕዛብንም ያካትታል (ሆሴ. 1፡9፤ 2፡23፤ ሮሜ. 9፡24-26፤ እንዲሁም ሌዋ. 26፡12፤ ዘጸ. 29፡45፤ 2ኛ ቆሮ. 6፡16-18 እና ዘጸ. 19፡5፤ ዘዳ. 14፡2፤ ቲቶ 2፡14)፤ (3) ቤተ-መቅደሱ አሁን የአጥቢያ ቤተ-ክርስቲያን ነች (1ኛ ቆሮ. 3፡16) ወይም አማኙ ምዕመን (1ኛ ቆሮ. 6፡19)፤ እና (4) እስራኤል እና ባሕርዩ የገለጻ ሐረጉ አሁን የሚያመለክተው ሁሉንም የእግዚአብሔር ሕዝቦች ነው (ገላ. 6፡16፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡5፣ 9-10፤ ራዕ. 1፡6)

ትንቢታዊ ማሳያው ተፈጽሟል፣ ተንሰራፍቷልም፣ አሁንም ብዙ ጨምሯል፡፡ ኢየሱስና ሐዋርያዊ ጸሐፊዎች እንደ ብ.ኪ. ነቢያት የመጨረሻው ዘመንን በተመሳሳይ መንገድ አላቀረቡትም፡፡ (ማርቲን ወይንጋርደን፣ *ቀጣዩ መንግሥት በትንቢትና ፍጻሜው)*፡፡ ዘመናዊ ተርጓሚዎች የብ.ኪን አምሳያ በጥሬ ትርጉምም ሆነ በአግባቡ ራዕይን በመጠምዘዝ የአይሁድ መጽሐፍ አድርገው፣ እንዲሁም ትርጉሙን በማድቀቅ፣ የኢየሱስንና የጳውሎስን ሐረጎች ይጠቀማሉ! የአ.ኪ. ጸሐፊዎች የብ.ኪን ነቢያት አይቃረኑም፣ ነገር ግን የመጨረሻ ሁለንተናዊ ውጤታቸውን ያሳያሉ እንጂ፡፡"

1፡7

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"አብ በገዛ ሥልጣኑ ያደረገውን ወራትንና ዘመናትን ታውቁ ዘንድ ለእናንተ አልተሰጣችሁም"** |
| **አኪጀት** | **"ጊዜያትንና ወቅቶችን ማወቅ ለእናንተ አልተሰጠም"** |
| **አየተመት** | **"ጊዜያትንና ወቅቶችን ማወቅ ለእናንተ አልተሰጠም"** |
| **አእት** | **"ጊዜያትንና ወቅቶችን"** |
| **አኢመቅ** | **"ጊዜያትንና ቀናትን ማወቅ ለእናንተ አልተሰጠም"** |

"ጊዜያት" (ክሮኖስ) ማለት፣ "ዘመናት" ወይም "ጊዜያት" (ይህም፣ የጊዜ ሂደት) ማለት ሲሆን "ክፍለ ዘመን" (ካይሮስ) ማለት "የተወሰነ ሁነት ወይም ወቅቶች ጊዜ" ማለት ነው፣ (ቲቶ 1፡2-3)፡፡ ሎው እና ኒዳ፡ *የግሪክ እንግሊዝኛ ሥርው-ቃል፣* የሚለው እነሱ ተመሳሳይ እንደሆኑና ጊዜያትን እንደሚገልጹ ነው (1ኛ ተሰ. 5፡1)፡፡ በግልጽ እንደሚታወቀው አማኞች የተለየውን ቀን ለማውጣት መሞከር አይኖርባቸውም፤ ኢየሱስም የመመለሻውን ጊዜ አያውቀውም (ማቴ. 24፡36፤ ማርቆስ 13፡32)፡፡ አማኞች አጠቃላይ ወቅቶችን ሊያውቁ ይችላሉ፣ ነገር ግን ዝግጁና ንቁ ሆነው መጠበቅ ይኖርባቸዋል፣ ለሁነኛው ሰዓት፣ መቼም ቢሆን (ማቴ. 24፡32-33)፡፡ የአ.ኪ. መንታ አጽንዖቶች ለዳግም ምጽዓቱ፣ <u>ንቁ</u> እና <u>ዝግጁ</u> <u>ሆኖ</u> መጠበቅ ነው፡፡ ቀሪው ነገር የእግዚአብሔር ነው!

**1፡8 "ነገር ግን ኃይልን ትቀበላላችሁ"** የመንፈስ ቅዱስ መምጣት ከኃይልና ከምስክርነት ጋር መያያዙን ልብ በል፡፡ ሐዋ. ስለ "ምስክርነት" (ማለት ማርተስ) ነው፡፡ ይህ ጭብጥ መጽሐፉን ሸፍኖታል (ዝ.ከ 1፡8፣22፤ 2፡32፤ 3፡15፤ 5፡32፤ 10፡39፣41፤ 13፡31፤ 22፡15፣20፤ 26፡16)፡፡ ቤተ-ክርስቲያን የተሰጣት ተግባር ለክርስቶስ ወንጌል ምስክር እንድትሆን ነው! ሐዋርያት የኢየሱስ ሕይወትና ትምህርቶች ምስክሮች ነበሩ፣ አሁንም ለእሱ ሕይወትና ትምህርቶች መስክሮች ናቸው፡፡ ውጤታማ ምስክርነት የሚፈጠረው በመንፈስ ኃይል ብቻ ነው፡፡

▣ **"ኢየሩሳሌም… ይሁዳ… ሰማርያ… እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ"** ይህ የሐዋ. መልክዓ ምድራዊ መገለጫ ነው፡ ኢየሩሳሌም፣ ምዕራፍ 1-7፤ ይሁዳ እና ሰማርያ፣ ምዕራፍ 8-12፤ እስከ ዓለም ዳርቻ (ያም ማለት ሮም)፣ ምዕራፍ 13-28፡፡ ይህ መግለጫ የሚያሳየው የጸሐፊውን ጽሑፋዊ መዋቅርና ተግባር ነው፡፡ ክርስትና የይሁዲነት ተቀጥያ አይደለም፣ ነገር ግን ዓለም አቀፍ ንቅናቄ የአንዱ እውነተኛው አምላክ፣ የብ.ኪ. ተስፋዎችን መፈጸም እናም ዓመጸኞቹን የሰው ልጆች ወደ እሱ ኅብረት የመመለስ ሥራ ነው፣ (ዘፍ. 12፡3፤ ዘጸ. 19፡5፤ ኢሳ. 2፡2-4፤ 56፡7፤ ሉቃስ 19፡46)፡፡

የመጀመሪያዎቹ የአይሁድ መሪዎች፣ ሴፕቱዋጂንትንም ሆነ ሌሎቹን በርካታ ትንቢታዊ ተስፋ ቃሎች፣ ያህዌ ኢየሩሳሌምን እንደሚመልስ፣ ኢየሩሳሌምን እንደሚያነሣ፣ ዓለምን ሁሉ ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚያመጣ፣ እነዚህ ሁሉ በጥሬው ይፈጸሙ ዘንድ ተስፋ ያደርጋሉ፡፡ ኢየሩሳሌም ቆይተዋል (ዝ.ከ 8፡1)፡፡ ነገር ግን ወንጌል የአ.ኪን ጽንሰ-ሐሳቦች ለወጠው እንዲሁም አስፋፋው፡፡ ዓለም አቀፉ ውክልና (ማቴ. 28፡18-20፤ ሐዋ. 1፡8) አማኞችን ወደ ዓለም ሁሉ እንዲሄዱ እንጂ ዓለም ወደ እነሱ እስኪመጣ ድረስ እንዲጠብቁ አላዘዘም፡፡ የአ.ኪ. ኢየሩሳሌም የመንግሥተ-ሰማያት ተምሳሌት (ዘይቤ) (ራዕ. 21፡2) ነች እንጂ በፍልስጥኤም ያለች ከተማ አይደለችም፡፡

**1፡9 "እሱም ከፍ አለ"** ይህ ሁነት ዕርገት ይባላል፡፡ ከሙታን የተነሣው ኢየሱስ ከፍጥረት በፊት ወደነበረው የክብር ቦታው ተመልሷል (ሉቃስ 24፡50-51፤ ዮሐንስ 6፡22፤ 20፡17፤ ኤፌ. 4፡10፤ 1ኛ ጢሞ. 3፡16፤ ዕብ. 4፡14፤ እና 1ኛ ጴጥ. 3፡22)፡፡ ያልተጠበቀው ወኪል በተገብሮ ድምጸት አብ ነው፡፡

▣ **"ደመናው"** ደመናት ለመለኮት ትንቢት ምልክት የመሆን ጠቀሜታ አላቸው፡፡ ደመናት በብ.ኪ. በሦስት የተለያዩ መንገዶች ጥቅም ላይ ይውላሉ፡

1. የእግዚአብሔርን አካላዊ መገኘት፣ የሼኪናህ የክብር ደመና (ዘጸ. 13፡21፤ 16፡10፤ ዘኍ. 11፡25)፤
2. የእሱን ቅድስና ለመሸፈን፣ ይህም ሰው እግዚአብሔርን አይቶ እንዳይሞት (ዘጸ. 33፡20፤ መዝ. 18፡9፤ ኢሳ. 6፡5)፤ እና
3. መለኮትን ለማጓጓዝ (መዝ. 104፡3፤ ኢሳ. 19፡1)፡፡ በዳንኤል 7፡13 ደመናት መለኮታዊውን መሲሕ ለማጓጓዝ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

የዳንኤል ትንቢት በ30 ጊዜ በላይ በብ.ኪ. ተጠቅሷል። ተመሳሳይ የመሲሑ ከሰማይ ደመናት ጋር የተያያዘው የሚገኘው፣ በማቲ. 26፡64፤ ማርቆስ 13፡26፤ 14፡62፤ ሐዋ. 1፡9፣11 እና 1ኛ ተሰ. 4፡17።

**ልዩ ርዕስ: በዳመና መምጣቱ**
ይህ በደመና የመምጣቱ ነገር ለዳግም ምፅአት በጣም ጠቃሚና ወሳኝ ነገር ነው። በብሉይ ኪዳን ውስጥ በተለያዩ በሦስት መንገዶች ጥቅም ላይ ውሏል።

I. የእግዚአብሔርን በአካል መገኘት ለማሳየት የእግዚአብሔር የክብሩ ደመና (ዘፀ 13፡12፣ 16፡10፣ ዘኀ 11፡25)
II. የሰው ልጅ እርሱን አይቶ እንዳይሞት ቅድስናውን የሸፈነበት (ዘፀ 33፡20፣ ኢሳ 6፡5)
III. መለኮትን ለማሸጋገር (ኢሳ 19፡1)

በዳንኤል 7፡13 ደመና መሲሁን ለማጓጓዝ ጥቅም ላይ ውሏል። ይህ በዳንኤል ላይ የተጠቀሰው ነገር በአዲስ ኪዳን ውስጥ ለ30 ጊዜ ያህል ሀሳቡን ተጠቅሞበታል። ከመሲሁ ጋር የተያያዘው ይህ ነገር በማቴ 24፡30፣ ማር 13፡26፣ ሉቃ 21፡27፣ ሐዋ 1፡9,11 እና በ1ተሰ 4፡17 ላይ ተጠቅሶአል።

1፡10 "አተኩረው እየተመለከቱ ሳለ" ይህ ያልተጠናቀቀ ቅድመ-ሐረግ ነው። እነሱ በተቻላቸው መጠን ኢየሱስን አተኩረው መመልከታቸውን ቀጥለዋል። ከእይታቸው ከወጣ በኂላ መመልከታቸውን ቀጥለዋል።

ቃሉ በሉቃስ ጽሑፎች ባሕርይ ነው (ሉቃስ 4፡20፤ 22፡56፤ ሐዋ. 1፡10፤ 3፡4፣12፤ 6፡15፤ 7፡55፤ 10፡4፤ 11፡6፤ 13፡9፤ 14፡9፤ 23፡1፣ ከሉቃስና ከሐዋ. ውጭ የሚገኘው ሁለት ጊዜ በ2ኛ ቆሮ. 3 ላይ ብቻ ነው)። "አተኩሮ መመልከት" የሚያሳየው "ወደ ላይ ማተኮርን" ወይም "አንዱ ዓይኑን ወደ ላይ ማተኮርን ነው።"

▣ "ወደ ሰማይ" የጥንቶቹ፣ ሰማይ ወደ ላይ እንደሆነ ያምኑ ነበር፣ በእኛ ጊዜ ግን ወደ ላይ አንጻራዊ ነው። በሉቃስ 24፡31፣ ኢየሱስ ተሰወረ። ለእኛ ባህል ይህ ጥሩ ማሳያ ይሆናል። መንግሥተ-ሰማያት ወደላይ እንዲሁን ውጭ አይደለም፣ ሊሆን የሚችለው በሌላ ገጽታ ጊዜና ቦታ ነው። መንግሥተ-ሰማያት አቅጣጫ አይደለም፣ አካል እንጂ!

▣ "ሁለት ሰዎች ነጫጭ ለብሰው" አ.ኪ. ዘወትር መላእክትን የሚገልጸው በብሩኅ ነጭ ልብስ ነው፣ (ሉቃስ 24፡4፤ ዮሐንስ 20፡12)። መላእክት በልደቱ ተገኝተዋል፣ በፈተናው ሰዓት፣ በጌቴሴማኒ፣ በመቃብሩ፣ እንዲሁም እዚህ በዕርገቱ ላይ።

1፡11 "የገሊላ ሰዎች" በሐዋ. በርካታ ጊዜ ሉቃስ የሐዋርያትን ገሊላዊ መነሻ አስፍሯል (ዝ.ከ 2፡7፤ 13፡31)። አስራ ሁለቱ ሁሉ፣ ከአስቆሮቱ ይሁዳ በቀር ሁሉም ከገሊላ ናቸው። ይህ አካባቢ ደግሞ በይሁዳ ነዋሪዎች ዝቅ ተደርጎ ነው የሚታየው፣ ምክንያቱም በርካታ የአሕዛብ ቁጥር ስላለውና "ሕጋዊ" (ማለት ቀጥተኛ) ስላልሆነ፣ በባህላዊው (ሥነ-ቃላዊው) (ታልሙድ) አፈጻጸም።

▣ "ኢየሱስ... ይመጣል" አንዳንድ የሥነ-መለኮት ሊቃውንት በኢየሱስና በክርስቶስ መካከል ልዩነት ለማድረግ ይሞክራሉ። እነዚህ መላእክት የሚያረጋግጡት ይህ የሚያውቁት ኢየሱስ ተመልሶ እንደሚመጣ ነው። የከበረው፣ ያረገው ክርስቶስ እሱ ራሱ የናዝሬቱ ኢየሱስ ነው። እሱ እግዚአብሔር)ሰው እንደሆነ ይቀራል።

ኢየሱስ እንደሄደ ተመልሶ ይመጣል፣ በሰማይ ደመናት (ማቲ. 10፡23፤ 16፡27፤ 24፡3፣27፣37፣39፤ 26፡64፤ ማርቆስ 8፡38-39፤ 13፡26፤ ሉቃስ 21፡27፤ ዮሐንስ 21፡22፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡23፤ 1ኛ ተሰ. 1፡10፣ 4፡16፤ 2ኛ ተሰ. 1፡7፣ 10፤ 2፡1፣8፤ ያዕቆብ 5፡7-8፤ 2ኛ ጴጥ. 1፡16፤ 3፡4፣12፤ 1ኛ ዮሐንስ 2፡28፤ ራዕ. 1፡7)። የኢየሱስ ዳግም ምጽዓት ወቅታዊና ዋነኛው የአኪ. ጭብጥ ነው። ወንጌል በጽሑፍ መልክ ለመዘጋጀት ረዘም ያለ ጊዜ የወሰደበት ምክንያት የጥንት ቤተ-ክርስቲያን የኢየሱስን ያኔውኑ መመለስ ስለምትጠባበቅ ነው። የእሱ አስገራሚ መዘግየት፣ የሐዋርያት ሞት፣ እና የመናፍቃን መነሣት ሁሉም ተጠቃሎ ቤተ-ክርስቲያን የኢየሱስን ሕይወትና ትምህርቶቹን በጽሑፍ መልክ እንድትመዘግብ አስገደዳት።

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 1፡12-14**
*12በዚያን ጊዜ ደብረ ዘይት ከሚባለው ተራራ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፥ እርሱም ከኢየሩሳሌም የሰንበት መንገድ ያህል የራቀ ነው። 13በገቡም ጊዜ ወደሚኖሩበት ሰገነት ወጡ፥ ጴጥሮስና ዮሐንስም፥ ያዕቆብም፥ እንድርያስም፥ ፊልጶስም፥ ቶማስም፥ በርተሎሜዎስም፥ ማቴዎስም፥ የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብም፥ ቀናተኛ የሚባለው ስምዖንም፥ የያዕቆብ ልጅ ይሁዳም። 14እነዚህ ሁሉ ከሴቶችና ከኢየሱስ እናት ከማርያም ከወንድሞቹም ጋር በአንድ ልብ ሆነው ለጸሎት ይተጉ ነበር።*

1፡12 "ተመለሱ" ሉቃስ 24፡52 "በታላቅ ደስታ"ን ይጨምራል።

▣ "ደብረ-ዘይት በተባለው ተራራ" ይህ ሉቃስ 24፡50 (ማለት ቢታንያ) ጋር የሚቃረን ይመስላል፤ ሆኖም፣ ሉቃስ 19፡29 እና 21፡37 ከማርቆስ 11፡11-12 እና 14፡3 ጋር አነጻጽር። የደብረ ዘይት ተራራ በመባል የሚታወቀው ኮረብታ

2.5 ማይል ያለው ኮረብታ ሲሆን 300-400 ጫማ ከኢየሩሳሌም በላይ፣ ይህም ከቢታንያ አፍዛፕ (በተቃራኒው) ከቄድሮን ሸለቆ፣ ከቤተ-መቅደሱ አግድም ነው። እሱም በብ.ኪ. ከፍጻሜው ትንቢት ተጠቅሷል (ዘካ. 14፡4)። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ብዙ ጊዜ ለጸሎትና ገለል ብሎ ለመስፈር ተሰብስበውበታል።

▣ **"የአንድ ሰንበት ጉዞ ርቀት"** አይሁዳዊ በሰንበት መጓዝ ያለበትን ርቀት ራቢዎች ወስነውለታል (ዘጸ. 16፡29፤ ዘኍ. 35፡5)። ይህም ርቀት 2000 ኩቢት (ደረጃዎች)፣ ይህም ራቢዎች ከፍ ሲል አንዱ መጓዝ ያለበትን ነው፣ የሙሴን ሕግ እንዳትሰብር።

1፡13 **"የደርቡ ክፍል"** ይህ ምናልባት የመጨረሻው ራት (ቅዱስ ቁርባን) የተካሄደበት ስፍራ ይችላል (ሉቃስ 22፡12፤ ማርቆስ 14፡14-15)። ከባህል አኳያ ላይኛው ወለል (2ኛ ወይም 3ኛ ወለል) ይህም የዮሐንስ ማርቆስ ቤት (ሐዋ. 12፡12)፣ እሱም የጴጥሮስን ማስታወሻ ወደ ማርቆስ ወንጌል የጻፈው። ይህም 120 ሰዎችን ለመሰብሰብ ትልቅ ክፍል መሆን አለበት።

▣ **"እነሱ"** ይህ ከአራቱ የሐዋርያት ዝርዝሮች አንደኛው ነው (ማቴ. 10፡2-4፤ ማርቆስ 3፡16-19፤ እና ሉቃስ 6፡14-16)። ዝርዝሮቹ መንታዊ አይደሉም። ስሞቹና ቅደም ተከተላቸው ተለውጧል። ሆኖም፣ ከአራቱ ምድቦች በሦስቱ ዘወትር ተመሳሳይ ስሞች ናቸው የተጠቀሱት። ጴጥሮስ ሁልጊዜ ቀዳሚ ሲሆን ይሁዳ ደግሞ ዘወትር መጨረሻ ነው። እነዚህ ሦስት ምድቦች ከአራቱ ምናልባት ሰዎቹን ለመፍቀድ፣ በየቤታቸውም በየጊዜው ለመመለስ፣ ለመቆጣጠር እና ለቤተሰባቸውም ለመስጠት ጠቀሜታ ታስቦ ነው።

### የሐዋርያት ስም ዝርዝር

| | ማቴዎስ 10፡2-4 | ማርቆስ 3፡16-19 | ሉቃስ 6፡14-16 | ሐዋ. 1፡12-18 |
|---|---|---|---|---|
| **የመጀመሪያው ምድብ** | ስምዖን (ጴጥሮስ)<br>እንድርያስ (የጴጥሮስ ወንድም)<br>ያዕቆብ (የዘብዴዎስ ልጅ)<br>ዮሐንስ (የያዕቆብ ወንድም) | ስምዖን (ጴጥሮስ)<br>ያዕቆብ (የዘብዴዎስ ልጅ)<br>ዮሐንስ (የያዕቆብ ወንድም)<br>እንድርያስ | ስምዖን (ጴጥሮስ)<br>እንድርያስ (የጴጥሮስ ወንድም)<br>ያዕቆብ<br>ዮሐንስ | ጴጥሮስ<br>ዮሐንስ<br>ያዕቆብ<br>እንድርያስ |
| **ሁለተኛው ምድብ** | ፊሊጶስ<br>በርተሎሜዎስ<br>ቶማስ<br>ማቴዎስ (ቀራጭ) | ፊሊጶስ<br>በርተሎሜዎስ<br>ማቴዎስ<br>ቶማስ | ፊሊጶስ<br>በርተሎሜዎስ<br>ማቴዎስ<br>ቶማስ | ፊሊጶስ<br>ቶማስ<br>በርተሎሜዎስ<br>ማቴዎስ |
| **ምድብ ሦስት** | ያዕቆብ (የእልፍዮስ ልጅ)<br>ታዲዮስ<br>ስምዖን (ቀነናዊው)<br>ይሁዳ (አስቆሮቱ) | ያዕቆብ (የእልፍዮስ ልጅ)<br>ታዲዮስ<br>ስምዖን (ቀነናዊው)<br>ይሁዳ (አስቆሮቱ) | ያዕቆብ (የእልፍዮስ ልጅ)<br>ስምዖን (ቀናተኛው)<br>ይሁዳ (የያዕቆብ ልጅ)<br>ይሁዳ (አስቆሮቱ) | ያዕቆብ (የእልፍዮስ ልጅ)<br>ስምዖን (ቀናተኛው)<br>ይሁዳ (የያዕቆብ ልጅ) |

▣ **"ጴጥሮስ"** አብዛኞቹ የገሊላ አይሁዶች አይሁዳዊ ስም አላቸው (ምሳ. ሲሞን ወይም ስምዖን፣ ፍችውም "ማዳመጥ") እናም የግሪክ ስም ፈጽሞ የማይሰየም)። ኢየሱስ "ዓለቱ" የሚል ቅጽል ስም አውጥቶለታል። በግሪክ *ጴጥሮስ* ነው፣ እንዲሁም በአራምኛ *ኬፋ* (ዮሐንስ 1፡42፤ ማቴ. 16፡16)።

▣ **"እንድርያስ"** የግሪክ ቃል ትርጉሙም "ወንዳዊ" ነው። ከዮሐንስ 1፡29-42 የምንረዳው እንድርያስ የዮሐንስ መጥምቁ ደቀ መዝሙር ነበር፣ ወንድሙን ጴጥሮስን ከኢየሱስ ጋር አስተዋውቋል።

▣ **"ፊሊጶስ"** የግሪክ ቃል የሚለው "ፈረስ ወዳድ" ማለት ነው። ስሙ በዮሐንስ 1፡43-51 ተሻሽሏል።

▣ **"ቶማስ"** የዕብራይስጥ ቃል ትርጉሙም "መንትዮች" ወይም ዲዲሞስ ነው (ዮሐንስ 11፡16፤ 20፡24፤ 21፡2)።

▣ **"በርተሎሜዎስ"** የቃሉ ትርጉም "የፓቶሎሚ ልጅ" ነው። እሱ ምናልባት የዮሐንስ ወንጌሉ ናትናኤል ሊሆን ይችላል (ዮሐንስ 1፡45-49፤ 21፡20)።

▣ *"ማቲዎስ"* የዕብራይስጥ ቃል ትርጉሙም "የያህዌ ስጦታ" ነው። ይህ የሚያመለክተው ሌዊን ነው (ዝ.ከ 2:13-17)።

▣ *"ጀምስ"* ይህ የዕብራይስጥ ስም "ያዕቆብ" ነው። ከአስራ ሁለቱ ዝርዝር ውስጥ ሁለት ሰዎች ያዕቆብ ተብለው ተሰይመዋል። አንደኛው የዮሐንስ ወንድም ነው (ማርቆስ 3:17) ከዋነኞቹ ዙሪያ ምድብ ነው (ማለት ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ፣ እና ዮሐንስ)። ይሄኛው የሚታወቀው ያዕቆብ ትንሹ ነው።

▣ *"ስምዖን ቀናተኛው"* የግሪኩ የማርቆስ ጽሑፍ "ቀነናዊ" የሚል አለው (ማቴ. 10:4ም)። ማርቆስ፣ ወንጌሉ ለሮማውያን የተጻፈው፣ ምናልባት ፖለቲካዊ "እሳት ጫሪ" የሆነውን "ቀናተኛ" የሚለውን ቃል ላለመጠቀም ፈልጎ ይሆናል፣ ይህም የሚጠቅሰው የአይሁድ ጸረ-ሮማ የደፈጣ ንቅናቄ ነው። ሉቃስ በዚህ ቃል ጠርቶታል (ሉቃስ 6:15 እና ሐዋ. 1:13)። ቀነናዊ የሚለው ቃል በርካታ መገለጫዎች ይኖሩታል።

1. የገሊላ ክፍል ቃና የሚባል
2. ከብ.ኪ. ከነአናውያንን እንደ ነጋዴ
3. ከአጠቃላይ መታወቂያ እንደ ከነአን ተወላጅ

የሉቃስ ገለጻ ትክክል ከሆነ፣ እናም "ቀናተኛ" ከአራምኛ ቃል "የጋለ ፍላጎት" ነው (ሉቃስ 6:15፤ ሐዋ. 1:17)። ኢየሱስ ጠራሾቹ አስራ ሁለት ደቀ መዛሙርት ከተለያዩ በርካታ ተቀናቃኝ ወገኖች ነው። ስምዖን ከብሔረተኛ ቡድን፣ እሱም የሮሜን ባለሥልጣናት በዐመጽ ለማስወገድ የሚሻ ነው። ይህ ስምዖንና ሌዊ (ማለት ማቲዎስ ቀራጩ) ከሌሎቹ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ምድብ አልነበረውም።

▣ *"ታዲዮስ"* እሱም "ሌቢዮስ" ተብሎ ይጠራል (ማቴ. 10:3) ወይም "ይሁዳ" (ሉቃስ 6:16፤ ዮሐንስ 14:22፤ ሐዋ. 1:13)። ሁለቱም፣ ታዲዮስም ሆነ ሌቢዮስ ፍችው "ተወዳጅ ልጅ" ማለት ነው።

▣ *"የአስቆሮቱ ይሁዳ"* ሁለት ስምዖኖች፣ ሁለት ያዕቆቦች፣ እና ሁለት ይሁዳዎች አሉ። "አስቆሮቱ" ሁለት መለያዎች ሊኖሩት ይችላሉ፡ (1) በይሁዳ የኬሮይዝ ሰው ነው (ኢያሱ 15:23) ወይም (2) "ባለ ሰይፍ ሰው" ወይም ገዳይ፣ ይህም ማለት ደግሞ ቀናተኛ ነበር ማለት ነው፣ እንደ ስምዖን።

**1:14 "እነዚህ ሁሉ በአንድ ልብ"** ቃሉ "የዚህ ዓይነት" ድብልቅ ነው፣ (ሆሞ) እና "የሐሳብ ስሜት" (ቱሞስ)። ቅድመ መስፈርት ሳይሆን በተስፋ የመጠባበቅ ድባብ ነው። ይህ አቋም በሐዋ. በተደጋጋሚ ተጠቅሷል (ለአማኞች፣ ዝ.ከ 1:14፤ 2:46፤ 4:24፤ 5:12፤ እንዲሁም ሌሎችም በ7:57፤ 8:6፤ 12:20፤ 18:12፤ 19:29)።

▣

| | |
|---|---|
| አአመመቅ | "በቀጣይነት በመትጋት" |
| አኪጀት | "በቀጣይነት" |
| አየተመት | "በጽናት በመትጋት" |
| አእት | "በተከታታይ በመሰብሰብ" |
| አኢመቅ | "በቋሚነት በመገናኘት" |

ይህ ቃል *(ፕሮስ እና ካፕቴሮ)* ማለት ሆን ብሎ፣ በጽናት ወይም ሆን ብሎ በመጠመድ (በመስጠት) ማለት ነው። ሉቃስ እሱን ዘወትር ይጠቀምበታል (ዝ.ከ 1:14፤ 2:42፣46፤ 6:4፤ 8:13፤ 10:7)። እሱም ጥርት ያላለና ያልተጠናቀቀ ነው።

▣ *"ከሴቶች ጋር"* አብረው የሄዱ የሴቶች ቡድን ነበሩ፣ ለኢየሱስ እና ለሐዋርያት ጋር የሆኑ (ማቴ. 27:55-56፤ ማርቆስ 15:40-41፤ ሉቃስ 8:2፤ 23:49፤ እና ዮሐንስ 19:25)።

**ልዩ ርዕስ፡ ከኢየሱስና ከደቀመዛሙርቱ ጋር የተጓዙት ሴቶች**

| ማቴ. 27:55-56 | ማርቆስ 15:40-41 | ሉቃስ 8:2፤ 23:49 | ዮሐንስ 19:75 |
|---|---|---|---|
| *መግደላዊት ማርያም* | *መግደላዊት ማርያም* | *መግደላዊት ማርያም* | *ማርያም፣ የኢየሱስ እናት* |
| *ማርያም፣ የያዕቆብና የዮሴፍ እናት* | *ማርያም፣ የያዕቆብ ትንሹ፣ ጆሴ እናት* | *ዮና፣ የኩዛ ሚስት (የሄሮድስ ባለሟል)* | *የእናቱ እኅት ማርያም፣ የቀሊኦጳ ሚስት* |
| *የዘብዴዎስ ልጆች (የያዕቆብና ዮሐንስ) እናት* | *ሰሎሜ* | *ሱሳና እና ሌሎች* | *መግደላዊት ማርያም* |

**የሚከተለው ከእኔ ሐተታ ማርቆስ 15:40-41 ስለእነዚህ ሴቶች ከተጻፈው የተወሰደ ነው**

***"እንደዚሁም ሌሎች ሴቶች በርቀት የሚከተሉ ነበሩ"*** *ሐዋርያዊው ወገን በገንዘብም ሆነ በጉልበት በበርካታ ሴቶች ይገለገል ነበር (ማለትም ምግብ በማዘጋጀት፣ በማጠብ፣ ወዘተ... ዝከ ቁ.* 41፤ *ማቴ.* 27፡55፤ *ሉቃስ* 8፡3)።

***"መግደላዊት ማርያም"*** *መግዳላ በገሊላ ባሕር ዳር የምትገኝ ትንሽ ከተማ ነች፣ ከጥብርያዶስ በስተሰሜን ሦስት ማይል ርቀት ላይ። ማርያም ከገሊላ አንሥታ፣ ብዙ አጋንንት ያወጣላትን ኢየሱስን ተከትላለች* (*ሉቃስ* 8፡2)። *እሷም ያላግባብ በዝሙት አዳሪነት ብትኮነነም በብኪ ምንም ዓይነት ማስረጃ አልተገኘም፣ ለዚህ።*

***"ማርያም የትንሹ ያዕቆብ እና የጆሰስ እናት"*** *በማቴ.* 27፡56 *"የያዕቆብና የዮሴፍ እናት" ተብላ ተጠርታለች። በማቴ.* 28፡1 *"ሌላዋ ማርያም" ተብላ ተጠርታለች። ተገቢው ጥያቄ፣ ማንን ነው ያገባችው? የሚል ነው። በዮሐንስ* 19፡25 *ቅሊኦጳን እንዳገባችና፣ ልጇም ያዕቆብ "የእልፍዮስ ልጅ" ተብሏል* (*ማቴ.* 10፡3፤ *ማርቆስ* 3፡18፤ *ሉቃስ* 6፡15)።

***"ሰሎሜ"*** *ይህቺ የያዕቆብና የዮሐንስ እናት ስትሆን፣ ከኢየሱስ ደቀ-መዛሙርት ይበልጥ የሚቀርቡት (የውስጠኛው ክበብ አባላት)፣ የዘብዴዎስ ሚስት ነች* (*ማቴ.* 27፡56፤ *ማርቆስ* 15፡40፤ 16፡1-2)።

***የሚከተሉት ደግሞ ከእኔ የዮሐንስ* 19፡25 *ሐተታ ስለነዚህ ሴቶች ከተደረገው ላይ ማስታወሻ ነው፡***

***"ከኢየሱስ መስቀል አጠገብ እናቱ ማርያም፣ እንዲሁም የእናቱ እኅት ማርያም፣ የክሌኦጳ ሚስት፣ እና መግደላዊት ማርያም ነበሩ።"*** *እዚህጋ አራት ወይም ሦስት ስሞች ለመጠቀሳቸው ብዙ ክርክር አለ። አራት ስሞች ናቸው ብሎ መውሰድ ይቻላል፣ ምክንያቱም ሁለት ማርያም ተብለው የሚጠሩ እኅትማማቾች ስለማይኖሩ ነው። የማርያም እኅት፣ ሰሎሜ፣ በማርቆስ* 15፡40 *እንዲሁም በማቴ.* 27፡56 *ላይ ተጠቅሷል። ይህ እውነት ከሆነ፣ ሊሆን የሚችለው ያዕቆብ፣ ዮሐንስ እና ኢየሱስ የኅትማማች ልጆች ናቸው ማለት ነው። በሁለተኛው ክፍለ ዘመን ባህል (ሄጂሲፐስ) ክሎኦጳ የዮሴፍ ወንድም ነው ይላል። መግደላዊት ማርያም ኢየሱስ ሰባት አጋንንት ያወጣላት ስትሆን፣ ከትንሣኤው በኋላ በመጀመሪያ እንድትገኝ የመረጣት ነች* (*ዝከ* 20፡1-2፤ 11-18፤ *ማርቆስ* 16፡1፤ *ሉቃስ* 24፡1-10)።

▣ ***"ወንድሞቹም"*** *የኢየሱስ ያንድ ወገን ወንድሞች የሆኑ ብዙዎችን እናውቃለን፡ ይሁዲ፣ ያዕቆብ (ልዩ ርዕስ* 12፡17 *ተመልከት)፣ እና ስምዖን (ማቴ.* 13፡55፤ *ማርቆስ* 6፡3 *እና ሉቃስ* 2፡7)። *ቀደም ሲል የማያምኑ ነበሩ (ዮሐንስ* 7፡5)፣ *ነገር ግን አሁን የሐዋርያት የውስጠኛው ክበብ አካል ሆነዋል። ስለ ማርያም "ዘላለማዊ ድንግልና" ታሪክ፣ አጠር ያለውን ማብራሪያ፣ ኤፍ. ኤፍ. ብሩስ፣ አዲሱ ዓለም አቀፍ ሐተታ፣ ሐዋ፣ ገጽ* 44፣ *የግርጌ ማስታወሻ* 47 *ተመልከት።*

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 1፡15-26**
**[15]በዚህም ወራት ጴጥሮስ መቶ ሀያ በሚያህል በሰዎች ማኅበር አብረው በነበሩ በወንድሞቹ መካከል**
**ተነሥቶ አለ። [16]ወንድሞች ሆይ፥ ኢየሱስን ለያዙት መሪ ስለሆናቸው ስለ ይሁዳ መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ**
**በዳዊት አፍ የተናገረው የመጽሐፍ ቃል ይፈጸም ዘንድ ይገባ ነበር፤ [17]ከእኛ ጋር ተቈጥሮ ነበርና፥ ለዚህም**
**አገልግሎት ታድሎ ነበርና። [18]ይህም ሰው በዓመፅ ዋጋ መሬት ገዛ በግንባሩም ተደፍቶ ከመካከሉ ተሰነጠቀ**
**አንጀቱም ሁሉ ተዘረገፈ፤ [19]በኢየሩሳሌምም ለሚኖሩ ሁሉ ታወቀ፤ ስለዚህም ያ መሬት በቋንቋቸው**
**አኬልዳማ ተብሎ ተጠራ፥ እርሱም የደም መሬት ማለት ነው። [20]በመዝሙር መጽሐፍ። መኖሪያው ምድረ**
**በዳ ትሁን የሚኖርባትም አይኑር፤ ደግሞም፦ ሹመቱን ሌላ ይውሰዳት ተብሎ ተጽፎአልና። [21-22]ስለዚህ**
**ከዮሐንስ ጥምቀት ጀምሮ ከእኛ ዘንድ እስካረገበት ቀን ድረስ፥ ጌታ ኢየሱስ በእኛ መካከል በገባበትና**
**በወጣበት ዘመን ሁሉ ከእኛ ጋር አብረው ከነበሩት ሰዎች፥ ከእነዚህ አንዱ ከእኛ ጋር የትንሣኤው ምስክር**
**ይሆን ዘንድ ይገባል። [23]ኢዮስጦስም የሚሉትን በርስያን የተባለውን ዮሴፍንና ማትያስን ሁለቱን አቆሙ። [24-**
**25]ሲጸልዩም። የሁሉን ልብ የምታውቅ አንተ ጌታ ሆይ፥ ይሁዳ ወደ ገዛ ራሱ ስፍራ ይሄድ ዘንድ በተዋት**
**በዚህች አገልግሎትና ሐዋርያነት ስፍራን እንዲቀበል የመረጥኸውን ከእነዚህ ከሁለቱ አንዱን ሹመው አሉ።**
**[26]ዕጣም ተጣጣሉላቸው፥ ዕጣውም ለማትያስ ወደቀና ከአሥራ አንዱ ሐዋርያት ጋር ተቈጠረ።**

**1፡15 "በዚህ ጊዜ"** *ይህ በጥሬው፣ "በእነዚህ ጊዜያት"* (en tais hēmerais) *ማለት ነው። ይህ ሐረግ ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው ለምዕራፎች መክፈቻ ነው (ማለትም፣* 1-15) *የሐዋ. (ዝከ* 1፡15፤ 2፡18፤ 5፡37፤ 11፡27፤ 13፡41)። *ሉቃስ በተጨማሪም ሌላ የዓይን ምስክሮች ምንጮችም ተጠቅሟል። እሱም በተጨማሪ "ከቀን ወደ ቀን"* (kath hēmeran) *እንደ ተለመደው፣ አሻሚ ጊዜ አመላካች ቀደም ባሉት የሐዋ. ምዕራፎች ተጠቅሟል (ዝከ* 2፡46፣47፤ 3፡2፤ 16፡5፤ 17፡11፣31፤ 19፡9)። *ከምዕራፍ* 15 *በኋላ ሉቃስ ስለሚጽፋቸው በርካታ ሁነቶች በቂ ግንዛቤ ይዟል። አሁንም "ቀን" የሚለውን አዘውትሮ ይጠቀማል፣ ነገር ግን እንደነዚህ አሻሚና፣ ዘይቤአዊ ሐረጋት ያይደለ።*

▣ ***“ጴጥሮስም ተነሥቶ ቆመ”*** ጴጥሮስ ለሐዋርያት ቃል አቀባይ መሆኑ ግልጽ ነው (ማቴ. 16)። እሱም የመጀመሪያውን የቤተ ክርስቲያን ስብከት፣ ከመንፈስ መውረድ በኋላ አቅርቧል (ሐዋ. 2) እንዲሁም ሁለተኛውን ስብከት በሐዋ. 3። ከዳግም ትንሣኤ መገለጥ በኋላ ኢየሱስ በቅድሚያ የተገለጠው ለእሱ ነው (ዮሐንስ 21 እና 1ኛ ቆሮ. 15:5)። ስሙም በዕብራይስጥ “ስምዖን” ነው፣ (ሐዋ. 15:14፤ 2ኛ ጴጥ. 1:1)። ይህ ስም በግሪክኛ ሲነገር “ሲሞን” ይባላል። “ጴጥሮስ” የሚለው ቃል የግሪክ ቃል ሲሆን (ጴጥሮስ) “ብቸኛ ዐለት” ማለት ነው። በአራምኛ “ኬፋ” ወይም “ድንጋይ” ነው (ማቴ. 16:18)።

▣ ***“አንድ መቶ ሃያ የሚሆኑ ሰዎች እንደተሰበሰቡ”*** ይህ ሐረግ በተመቅሶ[4] የግሪኩ ጽሑፍ በቅንፍ የተቀመጠ ነው (ነገር ግን በቁ. 18-19 አይደለም)። ይህ ቡድን አስራ አንዱን ሐዋርያት፣ ኢየሱስን የተጎዳኙት ሴቶች፣ እና በኢየሱስ የስብከት እና ፈውስ አገልግሎት ያካተተ መሆን አለበት። ይህ ቁጥር ምናልባት ተምሳሌታዊ ሊሆን ይችላል፣ ከራቢያዊ ትንተና የመሪዎችና ተከታዮች የቁጥር አንጻር (ማለትም ከ1-10፣ ሳንሄድሪን 1:6)።

1:16 ***“ቅዱስ ጽሑፍ”*** ሁሉም ማጣቀሻዎች “ለቅዱስ ቃል” በአኪ. (ከ2ኛ ጴጥ. 3:15-16 በቀር) የሚያመለክቱት ብኪ ነው (ከማቴ. 5:17-20፤ 2ኛ ጢሞ. 3:15-17 በቀር)። ይህ ምንባብ በተጨማሪም የመንፈስ ቅዱስ ተመስጧዊነትን ያስረዳል (2ኛ 1:21) በዳዊት በኩል። እሱም ደግሞ ‘ጽሑፎቹን” ቅዱስነት ያመለክታል፣ የዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ክፍል።

▣ ***“መሆን የሚገባው”*** ይህ dei ሲሆን መሻትን ያሳያል። እሱም ያልተጠናቀቀ የአሁን ድርጊት አመላካች ነው፣ የሚያመለክተውም በቁ. 20 ያለውን ጥቅስ ነው።

*ቃሉ የኢየሱስን ሕይወትና የጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን የብኪ ጽሑፎች ተቀጥላ መሆንዋን የሉቃስ መረዳት ባሕርይ ነው (ሉቃስ 18:31-34፤ 22:37፤ 24:44)። ሉቃስ ቃሉን አዘውትሮ ይጠቀማል (ሉቃስ 2:49፤ 4:43፤ 9:22፤ 11:42፤ 12:12፤ 13:14፣16፣33፤ 15:32፤ 17:25፤ 18:1፤ 19:5፤ 21:9፤ 22:7፣37፤ 24:7፣26፣44፤ ሐዋ. 1:16፣21፤ 3:21፤ 4:12፤ 5:29፤ 9:6፣16፤ 14:27፤ 15:5፤ 16:30፤ 17:3፤ 19:21፣36፤ 20:35፤ 23:11፤ 24:19፤ 25:10፣24፤ 26:9፤ 27:21፣24፣26)። ቃሉ የሚለው “አሳሪ ነው” “አስፈላጊ ነው” “ተገቢ ነው” ማለት ነው። ወንጌልና ዕድገቱ በዕድል የፈጠረ አይደለም፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ቀደም ሲል የታቀደበት እና፣ በብኪ ቅዱሳን መጻሕፍትን ፍጻሜ ያገኙበት ነው። (የሰባው አጠቃቀም)።*

▣ ***“ተፈጽሟል”*** አንዱ እነዚህን የብኪ ጥቅሶች ሲያነብ (ቁ. 20)፣ የይሁዳ ክህደት የመዝሙራት ጸሐፊ የልብ ሐሳብ አይደለም። ሐዋርያት ብኪን የሚተረጉሙት በዚህ ዓይነቱ ልምዳቸው ነው፣ ከኢየሱስ ጋር በማያያዝ። ይህም ጥቅልዮሽ ትርጓሜ ይባላል። ኢየሱስ ራሱ ይሄንን ዓይነቱን አግባብ ተጠቅሟል፣ ከሁለቱ የኢማኦስ መንገደኞች ጋር ሲራመድና ሲነጋገር (ሉቃስ 24:13-35፣ በተለይም ቁ. 25-27)። የቀድሞ ክርስቲያን ተርጓሚዎች የብኪን ሁነቶች እና የኢየሱስን ሕይወትና ትምህርት በንጽጽሮሽ ያቀርባሉ። ኢየሱስንም የሁሉም የብኪ ትንቢቶች ፍጻሜ አድርገው ነው የሚመለከቱት። አማኞች ዛሬ ይህንን አግባብ ሊጠነቀቁ ይገባል! እነዚህ ተመስጧዊ የአኪ ጸሐፍት በተመስጦ ሥር እና በኢየሱስ ሕይወትና ትምህርት ላይ በግለሰብ ደረጃም ቅርርቦሽ ነበራቸው። የእነሱን እውነትና፣ የምስክርነታቸውን ሥልጣን እናጸናለን፣ ነገር ግን ስልታቸውን ልናፈልቅ አንችልም።

▣ ***“ይሁዳ”*** የይሁዳ መካድ እንጂ ሞቱ አይደለም ተቀያሪ ሐዋርያ እንዲኖር ያስደረገው። በቁ. 20ለ፣ የይሁዳ ድርጊቶች የትንቢቱ ፍጻሜ ተደርገው ነው የሚወሰዱት። አኪ ሌላ የሐዋርያት ምርጫ ከያዕቆብ ሞት በኋላ መካሄዱን አይጠቅስም (ሐዋ. 12:2)። እዚህጋ በርካታ ምሥጢራትና አሳዛኝ ሁኔታ በይሁዳ ሕይወት ይታያል። ከገሊላ ያልሆነው ብቸኛ ደቀ መዝሙር ነው። የሐዋርያዊው ቡድን ገንዘብ ያዥ ተደርጓል (ዮሐንስ 12:6)። ኢየሱስ ከእሱ ጋር በነበረበት ጊዜ ሁሉ ገንዘብ በመስረቅ ይከሰስ ነበር። እሱም በትንቢት የተነገረው የሰይጣን ጥቃት ፍጻሜ ነው። የውስጥ ሐሳቡ ፈጽሞ አልተገለጸም፣ ነገር ግን የጉቦ ገንዘቡን ከመለሰ በኋላ የራሱን ሕይወት ማጥፋቱ በፈጸመው ድርጊት መጸጸቱን ያመላክታል።

በይሁዳ እና በውስጣዊ ፍላጎቱ በርካታ ክርክር አለ። በዮሐንስ ወንጌል ዘወትር ተጠቅሷል፣ ተብራርቷልም (6:71፤ 12:4፤ 13:2፣26፣39፤ 18:2፣3፣5)። ዘመናዊው ቲያትር “ኢየሱስ ክርስቶስ ልዕለ ኮከቡ”፣ እንደ ታማኝ፣ ነገር ግን ጥርት ያለ፣ ተከታይ ኢየሱስን አስገድዶ የአይሁድን መሲሕ ተግባር እንዲፈጸም የሚሻ ነው– ይህም ሮማውያንን ለመገልበጥ፣ በደለኞችን ለመቅጣት፣ እንዲሁም ኢየሩሳሌምን የዓለም ከተማ ለማድረግ ነው። ሆኖም፣ ዮሐንስ የሚያመለክተው የልቡ ሐሳብ ስስትና ክፋትን የተሞላ መሆኑን ነው።

*ዋነኛው ችግር የሥነ-መለኮታዊው፣ የእግዚአብሔር ሊዓላዊነትና የሰዎች ነጻ ፍቃድ ነው። እግዚአብሔር ወይም ኢየሱስ ይሁዳን ተጭነውት ይሆን? ይሁዳ በሰይጣን ቁጥጥር ሥር እንዲሆን ላደረገው ድርጊት ራሱ ተጠያቂ ይሆን ወይስ እግዚአብሔር ቀደም ብሎ በተነበየው ምክንያት ኢየሱስን እንዲክድ አደረገው? መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህን ጥያቄዎች በቀጥታ አይመልስም። እግዚአብሔር ታሪክን ይቆጣጠራል፤ ቀጣይ ሁነቶችን ያውቃል፤ ነገር ግን የሰው ልጅ ለሚያደርገው ምርጫ እና ድርጊት ተጠያቂ ነው። እግዚአብሔር ፍትሐዊ ነው እንጂ ተጽዕኖኛ አይደለም።*

*ይሁዳን ለመከላከል የሚሞክር አዲስ መጽሐፍ አለ– ይሁዳ ከሐዲ ወይስ የኢየሱስ ወዳጅ? በዊሊያም ክላሰን፣ ፎርትረስ አሳታሚ፣ 1996። እኔ በዚህ መጽሐፍ አልስማማም፣ ግን በጣም ማራኪና ሐሳብ ጫሪ ነው።*

▣ ***“ኢየሱስን ላሰሩት መሪ የሆነው”*** ቀጥሎ ከእኔ ሐተታ ከማቲዎስ 26:47-50 የተጠቀሰ ነው።

> *“ስለ ይሁዳ የልብ ሐሳብ በርካታ ውይይቶች አሉ። ሊባል የሚችለው ይህ ርግጠኛ ሳይሆን እንደሚቀር ነው። የእሱ ኢየሱስን መሳም ቁ. 49 ላይ አንድም (1) ለወታደሮቹ ምልክት ነው፣ የሚታሰረውን ሰው*

ለማሳየት (ዝከ. ቁ. 48)፤ ወይም (2) በዘመናዊው ንድፈ ሐሳብ የኢየሱስን እጅ ለማንቀሳቀስ ለማስገደድ ነው፣ (ዝከ. 27:4)። ሌሎች የወንጌል ምንባቦች እንደሚያመላክቱት እሱ ቀማኛና ከመነሻውም የማያምን ነበር (ዮሐንስ 12:6)።

ከሉቃስ 22:52 የተሰበሰቡትን ሰዎች ማንነት እንረዳለን። የሮሜ ወታደሮች ነበሩ፣ ምክንያቱም በሕጋዊ መንገድ ሰይፍ መታጠቅ የሚችሉ እነሱ ብቻ ናቸው። እንዲሁም የመቅደስ ጠባቂዎች ነበሩ፣ ምክንያቱም አዘውትረው ዱላ የሚይዙት እነሱ በመሆናቸው። ከአይሁድ የፍርድ ችሎት ተወካዮችም ደግሞ ነበሩ፣ በእስሩ ላይ (ዝከ ቁ. 47:51)።"

1:17 ይሁዳ የተመረጠው በኢየሱስ ነው፣ የኢየሱስን ንግግር አድምጧል፣ የኢየሱስን ተአምራት ተመልክቷል፣ ለተልዕኮ ተሰማርቷል በኢየሱስ ለኢየሱስ፣ በደርቡ ክፍል ተገኝቶ በእነዚህ ሁነቶች ተካፍሏል፣ እናም ኢየሱስን ክዷል!

1:18

**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**

**አየተመት፣ አኢመቅ፣**

**አኢት** "በፊት ለፊቱ ተደፍቶ ሆዱ ተዘረገፈ"

**አእት** "ወድቆ ሞተ፣ ሆዱም ተዘረገፈ"

"በፊት ለፊቱ መውደቅ" የሕክምናዊ ቃል ነው "ማበጥ" (ሞልቶንና ሚሊጋን፣ የግሪክ ኪዳን መዝገበ ቃላት፣ ገጽ 535-536)፣ በአንዳንድ የእንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት ላይ የሚገኝ (ምሳ. ፊሊፕስ፣ ሞፋት እና ጉድ ስፒድ)። ለመልካም ማብራሪያ የተለያዩ ትርጉሞች፣ በይሁዳ ሞት ላይ፣ (ማቴ. 27:5 ወይም ሐዋ. 1:18) *የመጽሐፍ ቅዱስን ጠንካራ አባባሎች፣ ገጽ* 511-512 ተመልከት።

▣ **"ይህም ሰው መሬትን ወስዶ"** ቁጥር 18-19 በቅንፍ የተቀመጡ ናቸው (አአመመቅ፣ አኪጀት፣ አየተመት፣ አኢመቅ፣ አኢት)። ጸሐፊው ይህን መረጃ የሚሰጠው ለአንባቢው መረዳት ነው። ከማቴ. 27:6-8 የምንማረው ካህናቱ ይህንን መሬት ገዝተዋል፣ የብኪ. ትንቢት ቃል ይፈጸም ዘንድ፣ (ማቴ. 27:9)። እሱም የይሁዳ ገንዘብ ነበር፣ ካህናቱ ርኩስ እንደሆነ የቆጠሩትና ላልታወቁ ሰዎች የቀብር ስፍራ የተገዛበት። ቁጥር 18-19 የሚነግረን ይሄው ቦታ ራሱ ይሁዳ የሞተበት ነው። ይህ መረጃ ስለ ይሁዳ ሞት ሌላ ስፍራ አልተደገመም።

1:19

**አአመመቅ፣ አየተመት** "አኬልዳማ፣ ያም የደም መሬት"

**አኪጀት** "አኬል ዳማ፣ ያም፣ የደም መሬት"

**አእት** "አኬልዳማ፣ ይህም ማለት የደም መሬት"

**አኢመቅ** "የደም ቀርጥ… አኬል-ዳማ"

ይህ የግሪክ ትርጉም የሆነ አራምኛ ቃል ነው። እሱም ዘወትር በወጥነት ለመግለጽ ያስቸግራል፣ ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላው። ከግሪኩ የሆሄያት ልዩነት በላይ በአራምኛ "የደም መሬት" ማለት ነው። ይህም ሊሆን የሚችለው (1) በደም ገንዘብ የተገዛ መሬት (ማቴ. 27:7ሀ፤ (2) ደም የፈሰሰበት መሬት (ሐዋ. 1:18)፤ ወይም (3) ነፍሰ ገዳዮች ወይም ባዕዳን የተቀበሩበት መሬት (ማቴ. 27:7ለ)።

1:20 እነዚህ ከመዝሙራት ሁለት ጥቅሶች ናቸው። አንደኛው መዝ. 69:25። በዋናው ላይ ድርብ (የብዙ ቁጥር) የሆነ። እሱም ከይሁዳ ጋር የተያያዘ የርግማን ቃል ነው። ሁለተኛው ጥቅስ ከመዝ. 109:8 (LXX)። እሱም የሚሆነው ያለፈ ትንቢትን ሆኖ የይሁዳን መተካት በቁ. 21-26 የተብራራውን ነው።

▣

**አአመመቅ፣ አኪጀት**

**አኢመቅ** "ሹመት"

**አየተመት** "የእረኝነት ሥልጣን"

**አእት** "ያገልግሎት ቦታ"

በሴፕቱዋጂንት ኤጲስቆጶስ የሚለው ቃል በአንድ ሹመት ያለ ኃላፊነትን ወይም አገልግሎትን የሚያመላክት ነው፣ ዘኍ. 4:16፤ መዝ. 109:8)። በሮሜ ካቶሊክ የጽሕፈት ሥርዓት መለያን ያመለክታል፣ ነገር ግን፣ በግሪክ የግሪክ የከተማ አስተዳደር ለመሪ የሚሰጥ ነው፣ (ዝከ አኢት)፣ እንደ ሽማግሌ (ፕሬስቤተሮስ) በአይሁድ ቃል ለመሪ ነበር (ዘፍ. 50:7፤ ዘጸ. 3:16፣18፤ ዘኍ. 11:16፣24፣25፣39፤ ዘዳ. 21:2፣3፣4፣6፣19፣20 እና ሌሎችም)። ስለሆነም ከያዕቆብ የተለየ መሆን በስተቀር፣ "እረኛ" እና "ሽማግሌ" ከሐዋርያት ሞት በኋላ መጋቢን የሚጠቅስ (ሐዋ. 20:17፣28፤ ቲቶ 1:5፣7፤ ፊሊጵ. 1:1)።

1:21 **"አስፈላጊ ነው"** ይህ ቃል ዳይ ነው (ዝከ ቁ. 16)። ባጠቃላይ ጴጥሮስ የሚሰማው አስራ ሁለቱ ሐዋርያት የሚወክሉት አስራ ሁለቱን ነገዶች ወይም ሌላ ተምሳሌት፣ ያም መጥፋት የሌለበት ነው።

1:21-22 ለሐዋርያነት የሚያበቁ መስፈርቶች አሉ። ሌሎች አማኞች ከአስራ ሁለቱ ውጭ ኢየሱስን በዚህ ዓለም አገልግሎቱ ሁሉ የተከተሉት እንዳሉ አስተውል። እነዚህ መስፈርቶች ኋላ ላይ አንዳንዶች የጳውሎስን ሐዋርያነት እንዳይቀበሉ አድርጓቸዋል።

ሉቃስ እነዚህን ሁለት ቁጥሮች በአጠቃላይ በማካተት የሐዋርያዊ ምስክሮች ቅደም ተከተልን ለማሳየት ተጠቅሞባቸዋል፣ ለማትያስ መመረጥ ሳይሆን፣ ከዛም በኋላ ብዙም ስለ እሱ ስላልሰማነው፡፡ ቤተክርስቲያንና የአኪ ቅዱስ ጽሑፎች መገንባት ያለባቸው በኢየሱስ ሕይወት፣ እና ትምህርቶች ላይ ሆኖ፣ የሚተያየውም በዓይን ምስክሮች፣ ሥልጣን ባላቸው ምስክሮች፣ በተመረጡ ሥነመለኮታዊ ምስክሮች ነው፣ የአኪ፡፡ ይህ የሥነ መለኮት ጉዳይ ነው እንጂ "የአስራ ሁለቱ" ተምሳሌት አይደለም!

**ልዩ ርዕስ፡ ቁጥር አስራ ሁለት**

አስራ ሁለት ዘወትር የድርጅት ተምሳሌታዊ ቁጥር ነው
1.ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ
ሀ. የዞዲክ አስራ ሁለቱ ምልክቶች
ለ. የዓመቱ አስራ ሁለት ወራት
2.በብኪ
ሀ. የያዕቆብ ልጆች (የአይሁድ ነገዶች)
ለ. የሚመላከቱትም
(1) አስራ ሁለቱ የመቅደሱ ዐምዶች፣ በዘጸ. 24፡4
(2) አስራ ሁለት ጌጦች በሊቀ ካህኑ ልብስ ላይ ያሉት (ነገዶቹን የሚወክሉ) በዘጸ. 28፡21
(3) አስራ ሁለት ሙልሙል ዳቦዎች በመቅደሱ ቅዱስ ስፍራ በሌዋ. 24፡5
(4) አስራ ሁለት ሰላዮች ወደ ከነአን የተላኩት በዘኁ. 13 (ከየነገዱ አንድ)
(5) አስራ ሁለት በትሮች (የነገድ መስፈርቶች) በቆሬ ዐመጽ በዘኁ. 17፡2
(6) አስራ ሁለት ድንጋዮች የኢያሱ፣ በኢያ. 4፡3፣9፣20
(7) አስራ ሁለት ያስተዳደር አውራጃዎች በሰሎሞን አስተዳደር በ1ኛ ነገሥ. 4፡7
(8) አስራ ሁለት ድንጋዮች የኤልያስ መሠዊያ ለያህዌ በ1ኛ ነገሥ. 18፡31
3.በአኪ
ሀ. አስራ ሁለት ሐዋርያት ተመረጡ
ለ. አስራ ሁለት ቅርጫት ዳቦ (አንድ ለእያንዳንዱ ሐዋርያ) በማቴ. 14፡20
ሐ. አስራ ሁለት ዙፋኖች፣ በእነሱም የአኪ ደቀ መዛሙርት የሚቀመጡባቸው (አስራ ሁለቱን የእስራኤል ነገዶች የሚያመላክቱ) በማቴ 19፡28
መ. አስራ ሁለት የመላእክት ጥፍራ ኢየሱስን የሚታደጉ በማቴ. 26፡53
ሠ. የራዕይ ተምሳሌታዊነት
(1) 24 ሽማግሌዎች በ24 ዙፋኖች ላይ በ4፡4
(2) 144000 (12X12) በ7፡4፤ 14፡1፣3
(3) አስራ ሁለት ከዋክብት በሴቲቱ አክሊል ላይ በ12፡1
(4) አስራ ሁለት ደጆች፣ አስራ ሁለት መላእክት አስራ ሁለቱን ነገዶች ያመላክታሉ በ21፡14
(5) አስራ ሁለት የመሠረት ድንጋዮች፣ ለአዲሲቷ ኢየሩሳሌም እና በእነሱም ላይ የአስራ ሁለቱ ሐዋርያት ስሞች በ21፡14
(6) አስራ ሁለት ሺህ አደባባይ በ21፡16 (የአዲሲቷ ከተማ መጠን፣ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም)
(7) ግድግዳው 144 ኩብ ነው በ21፡7
(8) አስራ ሁለት የዕንቁ (ሉል) በሮች በ21፡21
(9) ዛፎች በኢየሩሳሌም ከአስራ ሁለት ዓይነት ፍሬዎች ጋር (በየወሩ አንድ) በ22፡2

**1፡23 "ሁለቱን መደቡ"** በዚህ ሐረግ ላይ ካለው የሥነ መለኮት ጉዳይ የተለየ የያዘ የግሪክ የእጅ ጽሑፍ አለ፡

1. estēsan ("እነሱ መደቡ") በኤም ኤስ ኤስ N፣ ኤ፣ ቢ፣ ሲ፣ ዲ[1]፣ ኢ
2. estesen ("እሱ መደበ") በ ኤም ዲ[2] እና አውግስጢኖስ

ቁጥር አንድ ከሆነ፣ የዚህ ምሳነቱ የሁሉም ምድብ ደቀ መዛሙርት የይሁዳን መተካት ያሳዩበት ድምጽ ነው (የማኅበረ ምዕመናን ውሳኔ ዓይነት (ዝክ 15፡22)፣ ነገር ግን ቁጥር 2 ከሆነ፣ ለጴጥሮስ ልዕለ ሥልጣን ማስረጃ ነው (ዝክ 15፡7-11፣14)፡፡ እንደ ግሪክ የእጅ ጽሑፍ ማስረጃ የቁጥር አንድ ቃል ርግጠኛ ነው (ዩመቅሶ[4] የሚመርጠው "ኤ"ን ነው)፡፡

▣ "ዮሴፍ... ማትያስ" ስለ እነዚህ ሰዎች በአኪ የሚታወቅ ነገር የለም፡፡ ማስታወስ የሚገባን ወንጌላትና ሐዋ. የምዕራባውያን ታሪክ አለመሆናቸውን ነው፣ ነገር ግን የተመረጡ ሥነ-መለኮታዊ ጽሑፎች፣ ኢየሱስን የሚያስተዋውቁ፣ እንዲሁም መልእክቶቹ በዓለም ተጽዕኖ እንደሚያደርጉ እንጂ፡፡

1፡24
**አአመመቅ** **"የሁሉንም ሰው ልብ የሚያውቀው"**
**አኪጀት** **"የሁሉንም ልብ የሚያውቀው"**
**አየተመት** **"አንተ የእያንዳንዱን ልብ ታውቃለህ"**

አእት          *“አንተ የእያንዳንዱን ሐሳብ ታውቃለህ”*
አኢመቅ        *“የእያንዳንዱን ልብ መረዳት ትችላለህ”*

*ይህ ድብልቅ ቃል ነው፣ “ልቦች እና መታወቅ”* (ዝከ 15፡8)፡፡ ይህ የሚያንጸባርቀው የብኪ. እውነትን ነው (1ኛ ሳሙ. 2፡7፤ 16፡7፤ 1ኛ ነገሥ. 8፡39፤ 1ኛ ዜና. 28፡9፤ 2ኛ ዜና. 6፡30፤ መዝ. 7፡9፤ 44፡21፤ ምሳ. 15፡11፤ 21፡2፤ ኤር. 11፡20፤ 17፡9-10፤ 20፡12፤ ሉቃስ 16፡15፤ ሐዋ. 1፡24፤ 15፡8፤ ሮሜ 8፡27)፡፡ እግዚአብሔር እኛን ሙሉ ለሙሉ ያውቀናል እንዲሁም ይወደናል (ሮሜ. 8፡27)፡፡

ደቀ መዛሙርት የሚያጸኑት፣ ያህዌ የእነሱን የልብ ሐሳብ እንደሚያውቅ ነው፣ እንዲሁም የሁለቱን እጩዎች የልብ ሐሳብና ሕይወት፡፡ በምርጫው ላይ የእግዚአብሔርን ፍቃድ ፈልገዋል *(የድርጊት መካከለኛ)*፡፡ ኢየሱስ አስራ ሁለቱን መርጧል፣ አሁን ግን ከአብ ጋር ነው፡፡

---

**ልዩ ርዕስ፡ ልብ**

የግሪኩ ቃል ካርዲያ በሴፕቱዋጂንት እና በአኪ. ጥቅም ላይ የዋለው ሌብ የሚለውን የዕብራይስጥ ቃል ለማንጸባረቅ ነው፡፡ በተለያየ መንገድ ጥቅም ላይ ይውላል (ባዩር፣ አርንድት፣ ጊንግሪች እና ዳንከር፣ መልካም የእንግሊዝኛ ሥርወ ቃል፣ ገጽ 403-404)፡፡

1. የሥጋዊ ሕይወት ማዕከል፣ ለሰው በዘይቤአዊ (ሐዋ. 14፡17፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 3፡2-3፤ ያዕቆብ 5፡5)
2. የመንፈሳዊ (የግብረገብነት) ሕይወት ማዕከል
   ሀ. እግዚአብሔር ልብን ያውቃል (ሉቃስ 16፡15፤ ሮሜ 8፡27፤ 1ኛ ቆሮ. 14፡25፤ 1ኛ ተሰ. 2፡4፤ ራዕ. 2፡23)
   ለ. ለሰው ልጅ መንፈሳዊ ሕይወት ጥቅም ላይ ይውላል (ማቴ. 15፡18-19፤ 18፡35፤ ሮሜ 6፡17፤ 1ኛ ጢሞ. 1፡5፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡22፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡22)
3. የአስተሳሰብ ሕይወት ማዕከል (ማለትም፣ እውቀት፣ ማቴ. 13፡15፤ 24፡48፤ ሐዋ. 7፡23፤ 16፡14፤ 28፡27፤ ሮሜ 1፡21፤ 10፡6፤ 16፡18፤ 2ኛ ቆሮ. 4፡6፤ ኤፌ. 1፡18፤ 4፡18፤ ያዕቆብ 1፡26፤ 2ኛ ጴጥ. 1፡19፤ ራዕ. 18፡7፤ ልብ ከአእምሮ ጋር የመሳሳይ ነው፣ 2ኛ ቆሮ. 3፡14-15 እና ፊሊጵ. 4፡7)፡፡
4. የምርጫ ሐሳብ ማዕከል (ማለትም፣ ፍቃድ፣ ሐዋ. 5፡4፤ 11፡23፤ 1ኛ ቆሮ. 4፡5፤ 7፡37፤ 2ኛ ቆሮ. 9፡7
5. የስሜት ማዕከል (ማቴ. 5፡28፤ ሐዋ. 2፡26፣37፤ 7፡54፤ 21፡13፤ ሮሜ 1፡24፤ 2ኛ ቆሮ. 2፡4፤ 7፡3፤ ኤፌ. 6፡22፤ ፊሊጵ. 1፡7)
6. ለመንፈስ እንቅስቃሴ የተለየ ስፍራ (ሮሜ. 5፡5፤ 2ኛ ቆሮ. 1፡22፤ ገላ. 4፡6 (ማለትም፣ ክርስቶስ በልባችን፣ ኤፌ. 3፡17))
7. ልብ ለሞላው ስብዕና በዘይቤአዊነት ይጠቀሳል (ማቴ. 22፡37፣ ከዘዳ. 6፡5 በመጥቀስ)፡፡ ሐሳቦች፣ የውስጥ ፍላጎቶች፣ እና ድርጊቶች ከልብ ሲፈልቁ የሰውየውን ማንነት በምላት ይገልጻሉ፡፡ ብኪ. ጥቂት አስገራሚ አጠቃቀም አለው፣ ስለ ቃሉ
   ሀ. ዘፍ. 6፡6፤ 8፡21፣ (እግዚአብሔር በልቡ ተከፋ” (እንዲሁም ሆሴዕ 11፡8-9 ተመልከት)
   ለ. ዘዳ. 4፡29፤ 6፡5፣ “በፍጹም ልብህና በፍጹም ነፍስህ”
   ሐ. ዘዳ. 10፡16፣ “ያልተገረዘ ልብ” እና ሮሜ 2፡29
   መ. ሕዝ. 18፡31-32፣ “አዲስ ልብ”
ሠ. ሕዝ. 36፡26፣ “አዲስ ልብ” ወይም “የድንጋይ ልብ”

---

**1፡25 “ወደ ራሱ ስፍራ”** ይህ “ለርጉም” ሥራ የተሰጠ ስያሜ ነው፡፡ ሰይጣን እሱን ለራሱ ዓላማ ተጠቅሞበታል (ሉቃስ 22፡3፤ ዮሐንስ 13፡2፤ 27)፣ ነገር ግን ይሁዳ ለራሱ ምርጫና ድርጊት ተጠያቂ ነው (ገላ. 6፡7)፡፡

**1፡26 “ለእነሱም ዕጣ ጣሉላቸው”** ይህ የብኪ. የኂላ ታሪክ አለው፣ ከሊቀ ካህኑ የኡሪምና ቱሚም አጠቃቀም ጋር በተያያዘ፣ በሌዋ. 16፡8፣ ወይም ተመሳሳይ በሆነ ዘዴ ለሚጠቀሙ ግለሰቦች (ምሳ. 16፡33፤ 18፡18)፡፡ የሮሜ ወታደሮች ለኢየሱስ ልብሶች ዕጣ ተጣጥለዋል፣ ሉቃስ 23፡34)፡፡ ሆኖም፣ ይህ በአኪ. የመጨረሻ ጊዜ ነው፣ የእግዚአብሔርን ፍቃድ ለማወቅ የተጠቀሰው፡፡ ማንም ጽሑፉን ለመፈተሽ ቢፈልግ ዘዴው መንፈሳዊ ውሳኔ ለመወሰን ይሆናል በሚል፣ ምናልባትም ጥሩ ላይሆን ይችላል፣ (ምሳ. መጽሐፍ ቅዱስን በመክፈት ጣትን ቁጥሮቹ ጋ በማኖር የእግዚአብሔርን ፍቃድ መወሰን)፡፡ አማኞች በእምነት መኖር ይገባቸዋል እንጂ ስልታዊ በሆነ አግባብ የእግዚአብሔርን ፍቃድ ለማወቅ በመሞከር አይደለም (ምሳ. ማሚረት (ማታለል)፣ መሳ. 6፡17፣ 36፡40)፡፡

▣ “ማትያስ” ኢዩሲቢዩስ እንደሚለው፣ እሱ በሰባው ተልዕኮ ውስጥ ነበረበት (ሉቃስ 10)፡፡ ኂላ ላይ በመጣ ባህል እሱ ኢትዮጵያ ውስጥ ተሰውቷል፡፡

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት _መመሪያ_ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ለመርዳት ነው የተሰናዱት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋነኞቹን ጉዳዮች ለማጤን እንዲረዳ ነው። ሐሳብ ለማጫር እንጂ መደምደሚያ አይደሉም።

1. ኢየሱስ ከሐዋርያት ጋር ለምን 40 ቀናት ቆየ?
2. "የመንፈስ ጥምቀት" ምን ማለት ነው?
3. ቁጥር 7 በጣም ጠቃሚ የሆነው ለምንድን ነው?
4. እርገት ለምን ይጠቅማል?
5. ጴጥሮስ የይሁዳን ቦታ ለመሙላት አስፈላጊነት ለምን ፈለገ?
6. ጳውሎስ እንዴት ሐዋርያ ሊሆን ይችላል፣ መስፈርቱን ሳያሟላ? (1:21-22)

# የሐዋርያት ሥራ 2

## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንቀጽ ምድቦች

| የተየመቅሶ[4] | አኪጀት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የመንፈስ ቅዱስ መምጣት<br>2:1-4 | የመንፈስ ቅዱስ መምጣት<br>2:1-4 | የጰንጠቆስጤ ቀን<br>2:1-4 | የመንፈስ ቅዱስ መምጣት<br>2:1-4 | ጰንጠቆስጤ<br>2:1-4 |
| | የሕዝቡ ምላሽ | | | |
| 2:5-13 | 2:5-13 | 2:5-13 | 2:5-13 | 2:5-13 |
| የጴጥሮስ ንግግር በጰንጠቆስጤ | የጴጥሮስ ስብከት | የጴጥሮስ ስብከት | የጴጥሮስ ስብከት | የጴጥሮስ ንግግር ለሕዝቡ |
| 2:14-21 | 2:14-39 | 2:14-21 | 2:14-21 | 2:14-21 |
| 2:22-28 | | 2:22-28 | 2:22-28 | 2:22-28 |
| 2:29-36 | | 2:29-36 | 2:29-35 | 2:29-35 |
| | | | 2:36 | 2:36 |
| | | የንስሐ ጥሪ | | የመጀመሪያው ንግግር |
| 2:37-42 | | 2:37-42 | 2:37 | 2:37-41 |
| | | | 2:38-39 | |
| | የሁነኛው ቤተ ክርስቲያን እድገቱ | | | የቀደምት ክርስቲያን ንግግሮች |
| | 2:40-47 | | 2:40-42 | |
| | | | | 2:42 |
| ሕይወት በአማኞች መካከል | | | በሕይወት በሚያምኑት መካከል | |
| 2:43-47 | | 2:43-47 | 2:43-47 | 2:43 |
| | | | | 2:44-45 |
| | | | | 2:46-47 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (ከ "**መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ**" **ገጽ** vii)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. ምንባብ አንድ

2. ምንባብ ሁለት

3. ሦስተኛው አንቀጽ

5. ወዘተርፈ

**የቃልና የሐረግ ጥናት**

> **አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 2፡1-4**
> **1በዓለ ኀምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ፥ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ፥ 2ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ**
> **ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ፥ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው። 3እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች**
> **ታዩአቸው፤ በያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው። 4በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ**
> **እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር።**

2፡1 **"ጰንጠቆስጤ"** ይህ ዓመታዊ የአይሁድ በዓል "የሳምንቱ በዓል" በመባልም ይታወቃል፣ (ዘጸ. 34፡22፤ ዘዳ. 16፡10)። "ጰንጠቆስጤ" የሚለው ቃል "ሃምሳኛ" ማለት ነው። በዓሉ የሚከበረው ከፋሲካ በሃምሳኛው ቀን (በሰባት ሳምንት) ሲሆን፣ (ይህም ማለት አቆጣጠሩ ከቂጣ በዓል ከሁለተኛው ቀን ጀምሮ ነው።) ከኢየሱስ ቀን ጋር ሦስት ተግባራት አሉት፡ (!) የሕግ ለሙሴ መሰጠትን ለመታሰቢያ (ኩፋሌ) 1፡1)፤ (2) ስለ መኸሩ ለእግዚአብሔር ምስጋና ለመስጠት፤ እና (3) የበኵራትን ስጦታ ለማበርከት (ይህም ማለት ያዝመራው ሁሉ፣ የእህሉ ባለቤት ያህዌ መሆኑን ምልክት ለማድረግ ነው።) የብ. ኪ. ቅድመ ታሪክ ያለው ዘጸ. 23፡16-17፤ 34፡22፤ ሌዋ. 23፡15-21፤ ዘኍ. 28፡26-31 እና ዘዳ. 16፡9-12 ነው።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አየተመት** | **"መጥቷል"** |
| **አኪጀት** | **"በምላት መጥቷል"** |
| **አእት** | **"መጥቷል"** |
| **አኢመቅ** | **"በመጣ ጊዜ"** |

ይህ በጥሬው "ተፈጽሟል" ማለት ነው። እሱም የአሁን ተገብሮ ንዑስ አንቀጽ ነው።ይህ የመለኮታዊ ቀጠሮና ፍጻሜ ነው፣ ለመለኮታዊ ዓላማ። ይህ ጥቅም ላይ የዋለው በሉቃስ ጽሑፎች ላይ ነው (ሉቃስ 8፡ 23፤ 9፡51፤ እዚህ፤ እንዲሁም ተመሳሳይ ዘይቤ በሉቃስ 2፡6)። የሰዎች ታሪክ ቀኑ የሚቆጠረው በያህዌህ ነው።

ኤም. አር. ቬንሲንት፣ *የቃል ጥናት፣* ቅጽ 1፣ ገጽ224፣ የሚያሳስበን አይሁድ ቀንን የሚመለከቱት እንደሚሞላ የብረት ጋን (ኮንቴነር) ነው። የጴንጠቆስጤ ቀን በምላት መጥቷል! እሱም ደግሞ የእግዚአብሔር ልዩ የሆነው ምርቃት የመንፈስ ቅዱስን ዘመን፣ የቤተ ክርስቲያን መጀመር ነው።

▣ **"ሁሉም በአንድ ላይ በአንድ ስፍራ ነበሩ"** ሐረጉ የሚያሳየው የሁለቱንም የቦታንና የሐሳብን ኅብረት ነው (1፡14)። ይህ የት እንደሆነ ርግጠኛ አይደለም። ምናልባትም "በደርቡ ክፍል" ላይ ይሆናል (ሐዋ. 1፡13፤ 2፡22)፣ ነገር ግን በተመሳሳይ ነጥብ መቅደሱም በዚህ መሰሉ ልምድ ላይ ገብቶበታል (ሉቃስ 24፡53)።

2፡2 **"ከሰማይም እንደ ኃይለኛ ንፋስ ያለ ድምጽ መጣ"** በዚህ ሙሉ ክፍል አጽንዖቱ ለድምጹ እንጂ ለነፋሱና ለእሳቱ አይደለም። ይህም ተመሳሳይነቱ ከዘፍ. 3፡8 ጋር ነው። በብ.ኪ. *ሩሀ* (ruah) የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የሚውለው እስትንፋስ፣ ንፋስ፣ እና መንፈስ ነው (ሕዝ. 37፡9-14)፤ በአ.ኪ. *ኒውማ* (pneuma) ጥቅም ላይ የሚውለው ለነፋስ እና ለመንፈስ ቅዱስ ነው (ዮሐንስ 3፡5-8)። ንፋስ የሚለው ቃል በዚህ አገባቡ ኖ (pnoē) ነው። ጥቅም ላይ የዋለው እዚህና 17፡25 ብቻ ላይ ነው። ኒውማ pneuma የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው ለመንፈስ ቁ. 4 ላይ ነው።

2፡3 **"እንደ እሳት የሆኑ ልሳኖች ተከፋፈሉአቸው"** ጽሑፉ የተከሰተው የድምጽና የብርሃንን ትዕይንት ለመግለጽ ነው። ብርሃን መሰል እሳት በመጀመሪያ በኅብር ሆነ፣ ነግር ግን ወደ ተለያዩ መገለጫዎች ተከፋፍሎ እናም በእያንዳንዱ አማኝ ላይ ዐረፈ። በላይኛው ክፍል ያለ ማንም ሰው– ሐዋርያት፣ የኢየሱስ የቤተሰብ አባላት፣ እና ደቀ-መዛሙርት የማኅበርተኝነታቸውን ማረጋገጫ በግልጽ አገኙ። ቤተ ክርስቲያን አንድ ነበረች!

በብ.ኪ. እሳት ምሳሌ የሚሆነው (1) የመለኮትን መኖር ፤ (2) ፍርድን (ኢሳ. 66፡15-18)፤ ወይም (3) መንጻትን (ዘጸ. 3፡2፤ ዘዳ. 5፡4 እና ማቴ. 3፡11)። ሉቃስ ይህንን ልዩ የሆነ አካላዊ የመንፈስ ቅዱስ መገለጥ ለማሳየት አንድ ምሳሌ ተጠቅሟል።

የጰንጠቆስጤ በዓል በይሁዲነት እየተለመደ የመጣው በሲና ተራራ ላይ ሕግ ለሙሴ መሰጠቱን ለማክበር ሲሆን፣ (መቼነቱ ርግጠኛ ባይኮንም በርግጥ በሁለተኛው ዓ.ም፣ ወይም ከዚያ በጣም ቀደም ብሎ ይሆናል)። ስለሆነም ጩኸታሙ ንፋስ እና እሳት ምናልባት የያህዌን በኮሬብ ተራራ ላይ መውረድ አስታዋሽ ይሆናል፣ (ዘጸ. 19፡16)።

**ልዩ ርዕስ፡ እሳት**

እሳት የሚለው በመጽሐፍ ቅዱስ በአዎንታዊ እና አሉታዊ መልኩ ተገልፆአል።

ሀ. አዎንታዊ

1. ያሞቃል (ኢሳ 44፡15፤ ዮሐ 18፡18)
2. ብርሃን (ኢሳ 50፡11፤ ማቴ 25፡1-13)
3. ለማብሰል ይረዳል (ዘፀ 12፡8፤ ኢሳ 44፡15-16፣ ዮሐ 21፡9)
4. ያነፃል (ዘኀለቁ 31፡22-23፤ ምሳ 17፡3፤ ኢሳ 1፡25፣6፡6-8)
5. ይቀድሳል (ዘፍ 15፡17፤ ዘፀ 3፡2፣19፡18፤ ሕዝ 1፡27፤ ዕብ 12፡29)
6. የእግዚአብሕርን መሪነት ያሳያል (ዘፀ 12፡21፤ ዘኀልቁ 14፡14፤ 1ነገ 18፡24)
7. የእግዚአብሕርን ሃይል ያሳያል (የሐዋ 2፡30

ለ. አሉታዊ ጎኑ

1. ያቃጥላል (ኢያሱ 6፡24፤ 8፡8፤ 11፡11፤ ማቴ 22፡7)
2. ያስወግዳል (ዘፍ 19፡24፤ ሌዋ 10፡1-2)
3. ይቆጣል (ዘኀልቁ 21፡28፤ ኢሳ 10፡16፣ ዘካ 12፡6)
4. ቅጣትን ያመለክታል (ዘፍ 38፡24፣ ሌዋ 20፡14፤ 21፡9፤ ኢያሱ 7፡15)
5. የሃሰተኛውን ክርስቶስ ምፀዓት ምልክት (ራዕ 13፡13)

ሐ. እግዚአብሔር በሃጢአት ላይ ያለውን ቁጣ በእሳት ምሳሌነት ገልፆአል።

1. ቁጣው ተቃጠለ (ሆሴኤ 8፡5፤ ሶፎ 3፡8)
2. እሳቱን አዝንቧል (ነህምያ 1፡6፡
3. የዘላለም እሳት (ኤር 15፡14፤ 17፡4)
4. የዕውነተኛው የክርስቶስ ምፅዓት ነው (ማር 3፡10፣13፤40 ዮሐ 15፡6፤ 2ተሰ 1፡7፣ 2ጴጥ 3፡7-10፤ ራዕይ 8፡7፣ 13፡13፣ 16፡8)

መ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳሉ እንደሌሎቹ ምሳሌዎች (እርሾ፣ አንበሳ) መሳሰሉት እሳትም በረከት ወይም መርገም ሊሆን ይችላስ። በዓውዱ ውስጥ እንዳለው አገባብ

▣ *"እያንዳንዱም"* ምንም ዓይነት ልዩነት በሐዋርያትም ሆነ በደቀመዛሙርት መካከል አልተደረገም፤ በወንድም ሆነ በሴት (ኢዩ. 2፡28-32፤ ሐዋ. 2፡16-21)።

**2፡4 "በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው"** *"መሞላት"* የተደጋገመ ነው፣ (ዝ.ከ 2፡4፤ 4፡8፣31፤6፡3፣5፤7፡55፤ 9፡17፤ 11፡24፤ 13፡9)። እሱም የሚያሳየው የየዕለቱን ክርስቶስን መምሰል ነው (ኤፌ. 5፡18ን ከቆላ. 3፡16 ጋር በማነጻጸር)። ይህ በመንፈስ ከመጠመቅ ጋር ይለያያል፣ የመነሻው ክርስቲያን ልምድ ወይም ወደ ክርስቶስ መጠቃለል ከሆነው (1ኛ ቆሮ. 12፡13፤ ኤፌ. 4፡4-5)። መሞላት መንፈሳዊ ኃይል መላበስና ለውጤታማ አገልግሎት፣ የውርስ ወንጌላዊነት ነው! በ3፡10 ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት** | **"በሌሎች ልሳናት መናገር ጀመሩ"** |
| **አየተመት** | **"በሌሎች ቋንቋዎች መናገር ጀመሩ"** |
| **አእት** | **"በሌሎች ቋንቋ ተናገሩ"** |
| **አኢመቅ** | **"በተለያዩ ቋንቋዎች መናገር ጀመሩ"** |

በጥሬ ትርጉሙ "ሌሎች ልሳናት" ነው (ሄቲራይስ ግላሳይስ heterais glassais)። የ "ተለያዩ ቋንቋዎች ትርጓሜ የሚያንጸባርቀው የዚህን ቃል መረዳት በቁ. 6 እና 11 ባለው ጽሑፍ መሠረት ነው። ሌላው ሊሆን የሚችለው ትርጉም "የደስታ ድምጽ" የሚል ነው በ1ኛ ቆሮ. 12-14 እና እንዲሁም ሐዋ. 2፡13 መሠረት። ምን ያህል የተለያዩ ቋንቋዎች እንደተነገሩ ርግጠኛ ባይኮንም ቅሉ፣ ብዙ ናቸው። በቁ. 9-11 ያሉትን አገሮችና ግዛቶች ብትደምራቸው ከሃያ ብልጫ ይኖራቸዋል። አብዛኞቹ 120 አማኞች ተመሳሳይ ቋንቋ መናገር ይኖርባቸዋል።

እግዚአብሔር እነዚህን በፍራቻ የተዋጡ አናሳ ስብስብ ወንዶችና ሴቶች፣ በላይኛው ክፍል ሆነው የወንጌል አዋጅ ነጋሪ ለመሆን በመጠባበቅ ላይ የሆኑትን (ወንዶችም ሴቶችም) በተለየና ኃያል በሆነ መሳጭ ሁኔታ ሊሠራ ተነሥቷል። ምንም ያህል የዚህ የመነሻ ምልክት ተስፋ ለተሰጠው ለመንፈስ ቅዱስ መምጣት ቢሆንም፣ እግዚአብሔር ሌሎች ሕዝቦችን መቀበሉን ያረጋገጠበት ነው (ሳምራውያን፣ የሮሜ ጦር ሠራዊት አለቆች፣ እና አሕዛብ)። "ልሳናት" በሐዋርያት ሥራ ዘወትር ምልክትነቱ ወንጌል ለደረሳቸው ሌሎች ዘሮች፣ መልክዓ ምድራዊ ድንበሮችን መድረሱን ለማጽናት ነው። በሐዋርያት ሥራ ልሳናትና፣ ጳውሎስ በኋለኛ አገልግሎቱ በቆሮንቶስ (1ኛ ቆሮ. 12-14) የገለጸው ሰፊ ልዩነት አለው።

ከሥነ መለኮታዊ አኳያ ጰንጠቆስጤ ከባብኤል ግንብ በቀጥተኛ ተቃርኖ ያለ ነው ማለት ይቻላል (ዘፍ. 10-11)። በኩራት የተሞሉት ዐመፀኛ የሰው ልጆች የራሳቸውን ነጻነት ሲገልጹ (ማለትም፣ ዓለምን ተሰራጭተው እንዲሞሉ የተባሉትን እምቢ ሲሉ)፣ እግዚአብሔር የራሱን ፍቃድ በርካታ ቋንቋዎችን በመደባለቅ ገልጿል። አሁን አዲሱ የመንፈስ ዘመን፣ ብሔረተኝነት የሰው ልጆችን አንድ ከመሆን ያገዳቸው (ያም ማለት የአንድ ዓለም መለኮታዊ መንግሥት) ለአማኞች እንዲዞር ተገርጓል። ክርስቲያናዊ ኅብረት ሁሉንም የሰዎች ወሰን ያልፋል (ያም ማለት፡ ዕድሜ፣ ጾታ፣ መደብ፣ መልክዓ ምድር፣ ቋንቋ) የዘፍ. 3 የተገላቢጦሽ የሆነ ውጤት ነው።

▣ *"መንፈስ እንዲናገሩ በተሰጣቸው"* ግሡ ያልተጠናቀቀ የአሁን አመላካች ነው፣ ትርጓሜውም መንፈስ ይሰጣቸው ጀመር:: "በተሰጣቸው" የሚለው ቃል (apophtheggomai) የአሁን ተገብሮ (አረጋገጭ) ንዑስ አንቀጽ ነው:: ቃሉ ጥቅም ላይ የዋለው በሉቃስ በሐዋርያት ሥራ ላይ ብቻ ነው (ዝ. ከ 2:4፣14፤ 26:25):: በሴፕቱዋጂንት ላይ ለነቢያት ንግግር ጥቅም ላይ ውሏል (ያም ማለት የመንፈስ ተመስጦ ንግግር፣ ዘዳ. 32:2፤ 1ኛ ዜና. 25:1፤ ሕዝ. 13:9፣19፤ ሚክ. 5:11፤ ዘካ. 10:2)::

እኔ ይህንን ትርጓሜ ለጥንታዊ ግሪክ ሥርወ ቃላዊ ፍቺ "የተነሣው መጠን፣" "የስሜት ንግግር፣" ወይም "ደረጃ ያለው አንደበተ ርቱዓዊ ንግግር" በሚል መውሰድን እመርጣለሁ:: ሉቃስ ሴፕቱዋጂንትን አውቆ በሱም ቃላት ተጽዕኖ አድሮበታል::

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 2:5-13**

**[5]ከሰማይም በታች ካሉ ሕዝብ ሁሉ በጸሎት የተጉ አይሁድ በኢየሩሳሌም ይኖሩ ነበር፤ [6]ይህም ድምፅ በሆነ ጊዜ ሕዝብ ሁሉ ተሰበሰቡ፥ እያንዳንዱም በገዛ ቋንቋው ሲናገሩ ይሰማ ስለ ነበር የሚሉትን አጡ። [7]ተገርመውም ተደንቀውም እንዲህ አሉ። እነሆ፥ እነዚህ የሚናገሩት ሁሉ የገሊላ ሰዎች አይደሉምን? [8]እኛም እያንዳንዳችን የተወለድንበትን የገዛ ቋንቋችንን እንዴት እንሰማለን? [9]የጳርቴና የሜድ የኢላሜጤም ሰዎች፥ በሁለት ወንዝም መካከል በይሁዳም በቀጰዶቅያም በጳንጦስም በእስያም፥ [10]በፍርግያም በጵንፍልያም በግብፅም በቀሬናም በኩል ባሉት በሊቢያ ወረዳዎች የምንኖር፥ በሮሜም የምንቀመጥ፥ አይሁድም ወደ ይሁዲነትም የገባን፥ [11]የቀርጤስና የዓረብ ሰዎች፥ የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ በልሳኖቻችን ሲናገሩ እንሰማቸዋለን። [12]ሁሉም ተገረሙና አመንትተው እርስ በርሳቸው። እንጃ ይህ ምን ይሆን? አሉ። [13]ሌሎች ግን እያፌዙባቸው። ጉሽ የወይን ጠጅ ጠግበዋል አሉ።**

2:5 **"ትጉሀን"** ቃሉ የሚለው "አንድን ነገር በጥብቅ መያዝ" ነው (LXX ሌዋ. 15:31፤ ሚክ. 7:2):: በአንደኛው ክፍለ ዘመን ይሁዲ መሠረት የሚያመለክተው ወደ እግዚአብሔር መሆን እና የሽማግሌዎች ባህል ነው (ያም ማለት ሥነ ቃል (ባህላዊ ልምዶች)፣ ታልሙድ የሆኑት):: እነዚህም፣ ጻድቃን ሃይማኖታዊ ሰዎች (ዝ.ከ 8:2፤ 22:12፤ ሉቃስ 2:25)::

▣ **"ከሰማይም በታች ካሉ ሕዝቦች ሁሉ"** ሁሉም አይሁድ ወንዶች ሦስቱን ዋና ዋና የበዓላት ቀናት እንዲያከብሩ በጥብቅ ይታዘዛሉ፣ (ሌዋ. 23) በቤተ መቅደስ (ዘዳ. 16:16):: እዚያም (1) ምናልባትም ከሜዲትራኒያን አካባቢ ሁሉ ወደ ኢየሩሳሌም ለፋሲካ በዓል የመጡና እስከ ጴንጤቆስጤ ድረስ የሚቆዩ መናኞች ይኖሩ ይሆናል፣ ወይም (2) ቋሚ ነዋሪዎች ማለትም ከኢየሩሳሌም ውጭ ይዘዋወሩ የነበሩ (ዝ.ከ የቃሉ አጠቃቀም በ4:16፤ 7:24፤ 9:22፣32)::

2:6 **"ይህም ድምጽ በተሰማ ጊዜ"** ይህ የሚያመለክተው (1) የከባድ ዐውሎ ነፋሱን ድምጽ (ዝ.ከ ቁ. 2) ወይም (2) በሌላ ቋንቋ የሚናገሩ አማኞች (ዝ. ከ ቁ.4)::

▣

**አአመመቅ፣ አየተመት**

| | |
|---|---|
| **አኢመቅ** | **"መደነጋገር"** |
| **አኪጀት** | **"መምታታት"** |
| **አእት** | **"በስሜት መያዝ"** |

ቃሉ በጥሬው የሚለው "አንድ*ጋ* መያያዝ" ሲሆን ይህም "መመሸግ ወይም መዝጋት" ማለት ነው፣ (ሉቃስ 8:45፤ 19:43፤ 22:63):: አንዳንድ ጊዜ በዘይቤአዊ ለአስተሳሰብ ወይም ለስሜቶች ይውላል (ሉቃስ 8:37፤ 12:50 እና በሌላው የቃሉ ቅርጽ በሉቃስ 21:25 ላይ ይውላል)::

ይሄው ተመሳሳይ ቃል በሴፕቱዋጂንት በዘፍ. 11:7፣9፣ በባብኤል ግንብ *ጋ* በቋንቋ መደባለቅ በተያያዘ ጥቅም ላይ ውሏል:: እንደሚመስለኝ ጰንጠቆስጤ በባብኤል ግንብ ለተነሣው ብሔረተኝነት ተገላቢጦሻዊ ተምሳሌት ሆኖ፣ የመጀመሪያው ቅጣት፣ የሰው ልጆች በኃጢአተኝነት የእግዚአብሔርን ፍቃድ ሳልተቀበሉበት የተበታተኑበት እና ዳግመኛም ባለ አንድ ዓለም መንግሥት የሰው ልጆች የተከለከሉበት ነው:: የየሮም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐተታ፣ ቅጽ2፣ ገጽ172፣ በሐዋ. 2:3 የተቀመጠውን ዲያሜዚዞ (diamezizo) በተጨማሪ በማጠናከር፣ ማለትም አልፎ አልፎ በሚነገር ቃል፣ ግን ደግሞ በሴፕቱዋጂንት በዘጸ. 32:8 ለባብኤል ግንብ በመታተን ጥቅም ላይ ውሏል:: አማኞች ከእንግዲህ በብሔረተኝነት አይከፋፈሉም!

▣ **"ሕዝቡም አንድ ላይ መጥተው"** ይህ የሚያመለክተው ይህ የተከሰተው በቤተመቅደስ አካባቢ ነው፣ ምክንያቱም ለበርካታ ሕዝብ አነስተኛው የደርቡ ክፍል በኢየሩሳሌም ባለ አናሳ መንደር ስለማይበቃው ነው::

▣ **"በየራሳቸው ቋንቋ ሲናገሩ ይሰሙ ነበር"** ይህ ምናልባት የመስማት ተአምር እንጂ የመናገር አይሆንም (ዝ.ከ ቁ. 8 እና 11):: እነዚህ ብዙ ሰዎች፣ ሁሉም የተለያየ ቋንቋ ቢናገሩ፣ ንግግራቸውም አንድ ላይ ቢሆን መደማመጥ አይቻልም:: ይህ ሥነ-መለኮታዊ የተገላቢጦሽ ለባብኤል ግንብ ነው (ዘፍ. 11)::

ይህ የግሪክ ቃል ዲያሌክቶስ (dialektos) (ዝ.ከ ቁ.8)፣ "ዘዬ" የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል የምናገኝበት ነው:: ሉቃስ ይሄንን ቃል የተጠቀመው ዘወትር በሐዋ. ነው (1:19፤ 2:6፣8፤ 21:40፤ 22:2፤ 26:14):: ጥቅም ላይ የዋለው

"በቋንቋ" አግባብ ነው። ሆኖም፣ በዚህ ጽሑፍ፣ ዘዬ ምናልባት የታሰበው ፍቺ ይሆናል። እነዚህ አይሁዳውያን ስለ ኢየሱስ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሰምተዋል። ይህም ለማረጋገጥ የሚፈልገው ስለ እግዚአብሔር ወደ እነሱ የመጣው አዲሱ መልእክት ትክክለኛ መሆኑን ለማጽናት ነው።

2:7 በጽሑፉ ውስጥ የሚገኙትን ከፍ ያለ ስሜትን የሚገልጹትን የተለያዩ ቃላት ተመልከት።

1. *sunechō*, "*መደነጋገር*"
2. *existēmi*፣ "*መደነቅ*"
3. *thaumazō*, "*መገረም*"
4. *diaporeō*, "*መገረም*"

▣ "*እነዚህ የሚናገሩት ሁሉ የገሊላ ሰዎች አይደሉምን*" ሁነኛ ጥያቄው የተጠየቀበት ምክንያት በሰሜንኛ ዘዬአቸው ነው (ያም ማለት ዘዬ፣ ማቴ. 26:73)። "ለምን" የሚለው ቃል የሚያንጸባርቀው idou (እነሆ) የሚለውን ሲሆን፣ ሃያ ሦስት ጊዜ በሐዋ. እና በሉቃስ ላይ ጥቅም ላይ ውሏል።

2:9 "*የጳርጤስ፣ የሜደስ፣ የኢላሜዴስ እና የሜሶፖታሚያ ነዋሪዎች አይደሉምን*" እነዚህ ሁሉ ወገኖች ከለሙ መሬት (ሜሶፖታሚያ) ነው፣ አብርሃም ከተጠራበት ስፍራ፣ (ዑር ከከለዳውያን፣ ዘፍ. 11:28) እንዲሁም እስራኤልና ይሁዳ የተጋዙበት ነው (ሶርያ፣ ባቢሎን)።

▣ "*ይሁዳ*" ይሁዳ ለምን ከሁለት ከማይዛመዱ አገሮች መካከል ለምን ተጠቀሰ? ለምንስ ተገቢውን አንቀጽ ሳይዝ፣ ሰዋሰዋዊ አግባቡ ተዛንፎ ለምን ተጻፈ? የይሁዳ ሰዎችስ ገሊላውያን አራምኛ መናገራቸው ለምን አስገረማቸው? ከእነዚህ ጥያቄዎች የተነሣ አንዳንዶች የአጻጻፍ ስህተት ተፈጥሯል፣ ስለሆነም ይሄ ቃል የሚያመለክተው ሌላ ሕዝብን ነው ይላሉ።

1. ቱርቱሊያን፣ አውግስጢኖስ- አርመናዊ
2. ጄሮም - ሶርያ
3. ክሪሶስተም፣ ኢራስመስ- ህንድ
4. ለተጨማሪ ዘመናዊ አስተያየቶች ብሩስ ኤም. ሜዚገር፣ በግሪክ አዲስ ኪዳን ጽሑፋዊ ትንታኔ፣ ገጽ 293።

2:9-10 "*ቀጰዶቅያ፣ ጳንጦስ፣ እና እስያ፣ ጵርግያ እና ጳንፍልያ*" እነዚህ ከዘመናዊ ቱርክ ወገኖች ናቸው።

2:10 "*ግብፅ እና የሊብያ ወረዳዎች የቀሬና አካባቢ*" እነዚህ የሰሜን አፍሪካ ወገኖች ናቸው።

▣ "*ከሮሜ*" የአይሁድ ምዕመናን በዚህ ሁኔታ የተለወጡ የሮሜ ቤተ ክርስቲያን መሥራቾች ሳይሆኑ አይቀሩም።

▣ "*ፕሮሲሊተስ (ወደ ይሁዲነት የገባን)*" ይህ ከአሕዛብ ወደ ይሁዲነት የተለወጡትን፣ ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርት ያሳየል (1) የሙሴን ሕግ መጠበቅ፤ (2) ወንዶች እንዲገረዙ፤ (3) በምስክር ፊት እንዲጠመቁ፤ እና (4) ከተቻለ በመቅደስ መሥዋዕት ማቅረብ። እነርሱም በኢየሩሳሌም ነበሩ፣ ምክንያቱም ሁሉም የአይሁድ ወንዶች በየዓመቱ በሦስቱ ዋነኛ በዓላት ላይ መገኘት ስለሚኖርባቸው ነው፣ (ዘጸ. 23 እና ሌዋ. 23)።

2:11 "*ቀርጤስ*" ይህ ትልቅ ደሴት በሜዲትራኒያን ባሕር በቱርክ አጠገብ የሚገኝ ነው። እሱም በኤጅያን የሚገኙት በርካታ ደሴቶች ስብስብ ስያሜ ሊሆን ይችላል።

▣ "*ዓረቦች*" ይህ የሚያመለክተው የኤሳውን ዝርዮች ነው። በርካታ የዓረብ ነገዶች በደቡባዊው ቅርብ ምስራቅ ተሰራጭተው ይገኛሉ። ይህ ዝርዝር የሚወክለው በአንደኛው ክፍለ ዘመን ከሚታወቀው ከመላው ዓለም የአይሁድን ሕዝቦች ነው። ይህም ዘይቤነቱ ተመሳሳይ የሚሆነው ለሰባዎቹ የዓለም ቋንቋዎች እንደ አይሁድ ተምሳሌት ለመላው ሰዎች ነው (ሉቃስ 10)። ይሄው ተመሳሳይ ሐሳብ ዘዳ. 32:8 በሰባ LXX ተገልጿል።

2:12 እነዚህ ምዕመናን ልዩ ሁኔታውን ጠቀሜታ እንዳለው ምልክት ተገንዝበውታል። ጴጥሮስ ወቅቱን ጥያቄአቸውን ለመመለስ ተጠቅሞበታል።

2:13 "*ተሞልተዋል*" ይህ ሐረጋዊ የተጠናቀቀ ተገብሮ አመላካች ሲሆን፣ የሚለውም እነዚህ ደቀ መዛሙርት በጣም ጠጥተው በመስከር፣ በስካር ላይ መሆናቸውን ነው።

▣ "*ጉሽ የወይን ጠጅ*" የሁኔታው አንደኛው መገለጫ እነዚህ የኢየሱስ ተከታዮች መስከራቸውን ነው (ኤፌ. 5:18ሀ)። ሰካራሞች እንዴት አድርገው የቋንቋ ችሎታቸውን ያሳያሉ? የመደነቅና የደስታ ስሜት ያለ ይመስለኛል።

**ልዩ ርዕስ፡ *መጽሐፍ ቅዱሳዊ አግማሚያ በአልኮል (ሆምጣጤነት) እና በአልኮለኝነት (ሱሰኝነት)***

I. *መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት*

ሀ. ብሉይ ኪዳን

1. *ያይን* - ይህ የወይን አጠቃላይ ቃል ነው፣ እሱም 141 ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለ። *ሥርወ ቃሉ* ርግጠኛ አይደለም፣ ምክንያቱም ከዕብራይስጥ *ሥርወ ቃል* ስላልሆነ። እሱም የሚሆነው የኮመጠጠ የፍራፍሬ ጭማቂ፣ ባብዛኛውም ወይን ነው። ጥቂት ሁነኛ ምንባቦች፣ ዘፍ. 9:21፤ ዘጸ. 29:40፤ ዘኍ. 15:5፣10።
2. *ቲሮሽ* - ይህ ጉሽ "የወይን ጠጅ" ነው። በቅርብ ምስራቅ የዓየር ሁኔታ ምክንያት፣ ኩምጠጣ የሚጀምረው ጭማቂው ከተሰናዳ ከስድስት ሰዓት በኋላ ነው። ይህ ቃል የሚያመለክተው በመኮምጠጥ ሂደት ላይ ላለ ወይን ነው። ለሁነኛ ምንባቦች፣ ዘዳ. 12:17፤ 18:4፤ ኢሳ. 62:8-9፤ ሆሴ. 4:11 ተመልከት።
3. *አሲስ* - ይህ የአልኮል መጠጥ ነው፣ (ኢዩኤል 1:5፤ ኢሳ. 49:26)።
4. *ሴካር* - ይህ "ጠንካራ መጠጥ" ነው። የዕብራይስጡ *ሥር* ጥቅም ላይ የሚውለው "ሰካራም" ወይም "ሰካር" በሚል ነው። እሱም አንዳች የተጨመረበት ይኖራል የበለጠ አስካሪ እንዲሆን። እሱም ከያይን ጋር ትይዩ ነው (ምሳ. 20:1፤ 31:6፤ ኢሳ. 28:7)።

ለ. አዲስ ኪዳን

1. *ኢኖዮስ* - ከግሪኩ ያይን ጋር አቻ ነው
2. *ኒኦስ ኦይኖስ* (ጉሽ ወይን) የግሪኩ አቻ *ቲሮሽ* (ማርቆስ 2:22)
3. *ግሊዩኮስ ቪኖስ* (ጣፋጭ ወይን፣ ኤሲስ) - በአዲስነት መፍላት ላይ ያለ ወይን (ሐዋ. 2:13)

II. መጽሐፍ ቅዱሳዊ አጠቃቀሙ

ሀ. ብሉይ ኪዳን

1. ወይን የእግዚአብሔር ስጦታ ነው (ዘፍ. 27:28፤ መዝ. 104:14-15፤ መክ. 9:7፤ ሆሴ. 2:8-9፤ ኢዩ. 2:19፣24፤ አሞጽ 9:13፤ ዘካ. 10:7)።
2. ወይን የመሥዋዕታዊ ስጦታው አንደኛው አካል ነው (ዘጸ. 29:40፤ ሌዋ. 23:13፡ ዘኍ. 15:7፣10፤ 28:14፤ ዘዳ. 14:26፤ መሳ. 9:13)።
3. ወይን እንደ መድኃኒት ያገለግላል (2ኛ ሳሙ. 16:2፤ ምሳ. 31:6-7)።
4. ወይን ተጨባጭ ችግር ሊሆን ይችላል (ኖህ - ዘፍ. 9:21፤ ሎጥ- ዘፍ. 19:33፣35፤ ሳምሶን- መሳ. 16:19፤ ናባል- 1ኛ ሳሙ. 25:36፤ ኦርዮ- 2ኛ ሳሙ. 11:13፤ አምኖን- 2ኛ ሳሙ. 13:28፤ ኢላሁ- 1ኛ ነገሥ. 16:9፤ ቤንሃዳድ- 1ኛ ነገሥ. 20:12፤ ገዥዎች- አሞጽ 6:6፤ እና ሴቶች- አሞጽ 4)።
5. ወይን ሊያዛባ ይችላል (ምሳ. 20:1፤ 23:29-35፤ 31:4-5፤ ኢሳ. 5:11፣22፤ 19:14፤ 28:7-8፤ ሆሴዕ 4:11)።
6. ወይን ለተወሰኑ ወገኖች ክልክል ነው (ካህናት በሥራ ላይ፣ ሌዋ. 10:9፤ ሕዝ. 44:21፤ ናዝራውያን፣ ዘኍ. 6፤ እና ገዥዎች፣ ምሳ. 31:4-5፤ ኢሳ.56:11-12፤ ሆሴዕ 7:5)።
7. ወይም እንደ የፍጻሜ መዳረሻነት መቼት ተደርጎ ተወስዷል፣ (አሞጽ 9:13፤ አዩኤል 3:18፤ ዘካ. 9:17)።

ለ. ተረፈ መጽሐፍ ቅዱስ

1. ወይን በልኩ በጣም ይረዳል (መክብብ 31:27-30)።
2. ራቢ እንዲህ ይላል፣ "ወይን ከመድኃኒት ሁሉ ታላቁ ነው፣ ወይን ሲያልቅ ነው ሌላ መድኃኒት የሚያስፈልገው።" (ቢ.ቢ.58ለ)

ሐ. አዲስ ኪዳን

1. ኢየሱስ በርካታ ውኃ ወደ ወይን ቀይሯል (ዮሐንስ 2:1-11)።
2. ኢየሱስ ወይን ጠጥቷል (ማቴ. 11:18-19፤ ሉቃስ 7:33-34፤ 22:17)።
3. ጴጥሮስ በስካር ተከሷል፣ በጰንጠቆስጤ "ጉሽ ወይን" በመጠጣቱ፣ (ሐዋ. 2:13)።
4. ወይን እንደ መድኃኒት ያገለግላል (ማርቆስ15:23፤ ሉቃስ 10:34፤ 1ኛ ጢሞ. 5:23)።
5. መሪዎች ጠጪ መሆን አይኖርባቸውም። ይህም ባጠቃላይ መጠጥን አለመቅመስ ማለት አይደለም (1ኛ ጢሞ. 3:3፣8፤ ቲቶ 1:7፤ 2:3፤ 1ኛ ጴጥ. 4:3)።
6. ወይን መንፈሳዊ ለሆነ መቼት ያገለግላል (ማቴ. 22:1፤ ራዕ. 19:9)።
7. ጠጪነት የተወገዘ ነው (ማቴ. 24:49፤ ሉቃስ 11:45፤ 21:34፤ 1ኛ ቆሮ. 5:11-13፤ 6:10፤ ገላ. 5:21፤ 1ኛ ጴጥ. 4:3፤ ሮሜ 13:13-14)።

III. ሥነ መለኮታዊ ይዘት

ሀ. ተቃርኗዊ ክርክር

1. ወይን የእግዚአብሔር ስጦታ ነው።
2. ሰካራምነት ዋነኛው ችግር ነው።
3. አማኞች በአንዳንድ ባህሎች ነጻነታቸውን መገደብ ይኖርባቸዋል፣ ለወንጌል ብለው (ማቴ. 15:1-20፤ ማርቆስ 7:1-23፤ 1ኛ ቆሮ. 8-10፤ ሮሜ 14:1-15:13)።

ለ. ከተወሰነው ገደብ በላይ የመውጣት ዝንባሌ

1. እግዚአብሔር የመልካም ነገር ሁሉ ምንጭ ነው (ተፈጥሮ "በጣም ጥሩ" ነው፣ ዘፍ. 1:31)።
2. የወደቀው የሰው ልጅ ሁሉንም የእግዚአብሔር ስጦታዎች እግዚአብሔር ካስቀመጠለት ገደብ

በላይ በመውሰድ አበላሽቷቸዋል።

ሐ. ያላግባብ መጠቀሙ ከእኛ እንጂ ከነገሮች አይደለም። በሥጋዊ ተፈጥሮ ምንም ክፉ የለም (ማርቆስ 7፡18-23፤ ሮሜ 14፡14፣20፤ 1ኛ ቆሮ. 10፡25-26፤ 1ኛ ጢሞ. 4፡4፤ ቲቶ 1፡15)።

IV. የአንደኛው ክፍለ ዘመን የአይሁድ ባህልና አልኮል (ሆምጣጤ)

ሀ. መኮምጠጥ የሚጀምረው ወዲያው ነው፣ በግምት ከ6 ሰዓት በኋላ፣ ወይኑ ተረግጦ ሲያበቃ፣ በተለይም በሞቃት የዓየር ሁኔታ እና ንጽሕናው ባልተጠበቀበት ሁኔታ።

ለ. የአይሁድ ባህል እንደሚለው ከበስተላዩ ልከኛ አረፋ መታየት ሲጀምር (የመፍላት ምልክት)፣ የወይን መባ ለመስጠት ይደርሳል (ማ አሴሮዝ 1፡7)። እሱም "አዲስ ወይን" ወይም "ጣፋጭ ወይን" ይባላል።

ሐ. የመጀመሪያው አስካሪ ፍላት የሚያበቃው ከአንድ ሳምንት በኋላ ነው።

መ. ሁለተኛው ፍላት 40 ቀን ይወስዳል። በዚህ ጊዜ "ያረጀ ወይን"እንደ ሆነ ይቆጠራል፣ በመሠዊያው ላይም ለመሥዋዕትነት ይቀርባል (ኢድሁዮዝ 6፡1)።

ሠ. ሰፈፉ ላይ የረጋ ወይን (ያረጀ ወይን) መልካን እንደሆነ ይቆጠራል፣ ነገር ግን ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት መከለስ አለበት።

ረ. ወይን በተገቢው አረጀ የሚባለው ከፍላት ከአንድ ዓመት በኋላ ነው። ሦስት ዓመት ትልቁ ጊዜ ነው፣ ወይንን በተገቢው ለማስቀመጥ። እሱም "ያረጀ ወይን" ይባላል፣ ስለሆነም በውሀ መበረዝ ይኖርበታል።

ሰ. ባለፉት 100 ዓመታት በንጹሕ ቦታ እና ቅመም በመጨመር ኮምጣጥነቱን ማሻሻል ተችሏል። የጥንቱ ዓለም የኩምጠጣን ተፈጥሯዊ ሂደት ሊያስቀረው አልቻለም።

V. የመዝጊያ መግለጫ

ሀ. ያንተ ልምድ፣ ሥነ መለኮት፣ እና የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ የኢየሱስንና የአንደኛውን ክፍለ ዘመን አይሁድ)ወይም ክርስቲያናዊ ባህል እንዳያንኳስስ ተጠንቀቅ! እነሱ ጨርሰው አልኮል የማይቀምሱ አልነበሩም።

ለ. እኔ የአልኮል ማህበራዊ ጠቀሜታ ተከራካሪ አይደለሁም። ሆኖም፣ ብዙዎች በዚህ ጉዳይ ላይ የመጽሐፍ ቅዱስን አቋም ስለሚያጋንኑ እናም አሁን ልዕለ ጽድቅ የተመሠረተው በባህል)በመሠረተ እምነት ላይ ባለ አድሏዊነት በመሆኑ።

ሐ. ለእኔ፣ ሮሜ 14፡1-15፡13 እና 1ኛ ቆሮ. 8-10 በፍቅርና በአክብሮት ላይ የተመሠረተ ይዘትና መመሪያ ይሰጡኛል፣ ይህም ለአማኞችና ለወንጌል ስርጭት በሁሉም ባህል፣ ግለሰባዊ ነጻነት ወይም ፍርዳዊ ሂስ ሳይሆን። መጽሐፍ ቅዱስ ብቻውን የእምነትና የተግባር ምንጭ ከሆነ፣ እናም ሁላችንም ይሄንን ጉዳይ ዳግም ልናጤነው ይገባል።

ሠ. ጨርሶ መታቀብን እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ ብንወስደው፣ ስለ ኢየሱስ ምን እንላለን፣ እንዲሁም ስለ ዘመናዊዎቹ ባህሎች፣ በመደበኛነት ወይንን የሚጠቀሙ፣ (ለምሳሌ አውሮጳ፣ እስራኤል፣ አርጀንቲና)።

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 2፡14-21**

**[14]ነገር ግን ጴጥሮስ ከአሥራ አንዱ ጋር ቆመ፥ ድምፁንም ከፍ አድርጎ እንዲህ ሲል ተናገራቸው። አይሁድ በኢየሩሳሌምም የምትኖሩ ሁላችሁ፥ ይህ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን፥ ቃሎቼንም አድምጡ። [15]ለእናንተ እንደ መሰላችሁ እነዚህ የሰከሩ አይደሉም፥ ከቀኑ ሦስተኛ ሰዓት ነውና፤ [16]ነገር ግን ይህ በነቢዩ በኢዩኤል የተባለው ነው። [17]እግዚአብሔር ይላል። በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል፤ ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፥ ጎበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ፥ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልም ያልማሉ፤ [18]ደግሞም በዚያች ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎቼ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ ትንቢትም ይናገራሉ። [19]ድንቆችን በላይ በሰማይ፥ ምልክቶችንም በታች በምድር እሰጣለሁ፤ ደምም እሳትም የጢስ ጭጋግም ይሆናል፤ [20]ታላቅ የሆነ የተሰማም የጌታ ቀን ሳይመጣ ፀሐይ ወደ ጨለማ ጨረቃም ወደ ደም ይለወጣሉ። [21]የጌታን ስም የሚጠራም ሁሉ ይድናል።**

2፡14 "ጴጥሮስ" እስቲ አስቡት፣ ከሁሉም ደቀ-መዛሙርት መካከል፣ የመጀመሪያውን የክርስቲያን ስብከት እንዲያቀርብ የተደረገው ጴጥሮስ ነው! ሦስት ጊዜ ኢየሱስን እንደማያውቀው የካደው (ሉቃስ 23)! የጴጥሮስ ከፈሪነትና ከክሕደት ወደ ግልጽነትና መንፈሳዊ ውስጠት መቀየር፣ ሌለኛው ማስረጃ የሚሆነው የመንፈስ ዘመን ጎሕ መቅደዱንና ወደ ሕይወት ቀያሪ ኃይል መምጣቱን ነው። ይህም የመጀመሪያው በሐዋ. የተመዘገበ ስብከቱ ነው። እሱም የሚያሳየን የሐዋርያትን ስብከት ይዘትና አጽንዖት ነው። ይህ ሐዋርያዊ ስብከት በሐዋ. ወሳኝ ክፍል ሆኗል።

**ልዩ ርዕስ፡ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ስብከተ ወንጌል**

1. በእግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን የተደረገው ተስፋ አሁን በኢየሱስ በመሲሑ መምጣት ተፈጽሟል (ሐዋ. 2፡30፤ 3፡19፣24፤ 10፡43፤ 26፡6-7፣22፤ ሮሜ. 1፡2-4፤ 1ኛ ጢሞ. 3፡16፤ ዕብ. 1፡1-2፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡10-12፤ 2ኛ ጴጥ. 1፡18-19)፡፡
2. ኢየሱስ እንደ መሲሕ በእግዚአብሔር የተቀባው በጥምቀቱ ነው (ሐዋ. 10፡38)፡፡
3. ኢየሱስ አገልግሎቱን የጀመረው በገሊላ ከጥምቀቱ በኂላ ነው (ሐዋ. 10፡37)፡፡
4. የእሱም አገልግሎት ባሕርዩ፣ መልካምን በማድረግና ታላላቅ ሥራዎችን በእግዚአብሔር ኃይል በማድረግ ነው (ማርቆስ 10፡45፤ ሐዋ. 2፡22፤ 10፡38)፡፡
5. መሲሑ የተሰቀለው በእግዚአብሔር ዓላማ ነው (ማርቆስ 10፡45፤ ዮሐንስ 3፡16፤ ሐዋ. 2፡23፤ 3፡13-15፣18፤ 4፡11፤ 10፡39፤ 26፡23፤ ሮሜ 8፡34፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡17-18፤ 15፡3፤ ገላ. 1፡4፤ ዕብ. 1፡3፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡2፣19፤ 3፡18፤ 1ኛ ዮሐንስ4፡10)፡፡
6. እሱ ከሙታን ተነሥቶ ለደቀመዛሙርቱም ታይቷል (ሐዋ. 2፡24፣31-32፤ 3፡15፣26፤ 10፡40-41፤ 17፡31፤ 26፡23፤ ሮሜ 8፡34፤ 10፡9፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡4-7፣12፤ 1ኛ ተሰ. 1፡10፤ 1ኛ ጢሞ. 3፡16፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡2፤ 3፡18፣21)፡፡
7. ኢየሱስ በእግዚአብሔር ከፍ ተደርጎ "ጌታ" የሚል ስም ተሰጠው (ሐዋ. 2፡25-29፣33-36፤ 3፡13፤ 10፡36፤ ሮሜ 8፡34፤ 10፡9፤ 1ኛ ጢሞ. 3፡16፤ ዕብ. 1፡3፤ 1ኛ ጴጥ. 3፡22)፡፡
8. አዲሱን የእግዚአብሔር ማህበረሰብ ለመመሥረት መንፈስ ቅዱስን ሰጠ (ሐዋ. 1፡8፤ 2፡14-18፣38-39፤ 10፡44-47፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡12)፡፡
9. እሱም ዳግመኛ ተመልሶ ይመጣል፣ ለፍርድና ሁሉንም ነገር ለመመለስ (ሐዋ. 3፡20-21፤ 10፡42፤ 17፡31፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡20-28፤ 1ኛ ተሰ. 1፡10)፡፡
10. መልእክቱን የሚሰሙት ሁሉ ንስሐ መግባትና መጠመቅ ይኖርባቸዋል (ሐዋ. 2፡21፣38፤ 3፡19፤ 10፡43፣47-48፤ 17፡30፤ 26፡26፤ ሮሜ 1፡17፤ 10፡9፤ 1ኛ ጴጥ. 3፡21)፡፡

ይህ ቅንብር የጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ዋነኛ ደንብ ሆኖ አገልግሏል፣ ምንም እንኳ የአዲስ ኪዳን የተለያዩ ጸሐፊዎች ድርሻ ወይም አጽንዖት በስብከታቸው በተለይ ቢያስቀምጡም፡፡ አጠቃላዩ የማርቆስ ወንጌል በቅርበት የሚከተለው ጴጥሮሳዊ ገጽታ ነው፣ የስብከተ ወንጌሉን፡፡ ማርቆስ ከባህል አኳያ የሚታየው የጴጥሮስን ስብከት በማዋቀር ነው፣ በሮም የተሰበከውን፣ ወደ ጽሑፍ ወንጌል በመቀየር! ማቲዎስና ሉቃስ ሁለቱም የማርቆስን ዋነኛ አወቃቀር ተከትለዋል፡፡

▣ **"ከአስራ አንዱ ጋር"** ይህ ሁለት ነገሮችን ያሳያል፡ (1) ጴጥሮስ ቃል አቀባይ ነው፣ ነገር ግን ከሐዋርያዊ ወገን፡፡ እሱ ብቻውን በራሱ ሥልጣን አይናገርም፡፡ መንፈስ ልዩ በሆነ መልኩ በዚህ ሁሉ ቡድን፣ የዓይን ምስክሮች በሚባሉት ውስጥ ይናገራል፣ እንዲሁም፣ (2) ማቲያስ፣ ምንም እንኳ ስለ እሱ አገልግሎት ባናውቅም፣ ከሐዋርያዊው ወገን አካል በይፋ ሆኗል፡፡

▣ **"የይሁዳ ሰዎችና በኢየሩሳሌም የምትኖሩት ሁሉ"** እዚህ ንግግር የሚደረግላቸው ሰዎች ከምዕመናን በዘር ከተዘረዘሩት የተለዩ ይመስላሉ፣ ቁ. 7-11፡፡

▣ **"በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን፣ አስተውሉም"** እነዚህ ሁለቱም አስገዳጅ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው የአሁን የድርጊት ሲሆን፣ ሁለተኛው የድርጊት መካከለኛ (አረጋጋጭ) ነው፡፡ ጴጥሮስ የእያንዳንዳቸውን አትኩሮት ፈልጓል፡፡

ሐረጉ ባጠቃላይ ሴማዊ ዘይቤ ነው፡፡ የጴጥሮስን ስብከት ለማስተዋወቅ ሁለት ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል (2፡14፤4፡10) እንዲሁም ለጳውሎስ ሁለት ጊዜ፣ (ዝከ 13፡38፤ 28፡28)፡፡ ሉቃስ በጉልምስናው ከአሕዛብ የተለወጠ ነው፡፡ ይህ ያለፈ ሴማዊ ዘይቤ የሚያሳየው ሉቃስ የሐዋ. ስብከቶችን ከራሱ ሥነመለኮታዊ ዓላማ እንዳልፈጠራቸውና፣ ምንጮቹን በታማኝነት እንዳጠቃለለ ነው፡፡

2፡15 **"እነዚህ ሰዎች አልሰከሩም"** ጴጥሮስ፣ በቁ. 13 ላይ ላለው ክስ ምላሹን ሰጠ፣ ለቀጥተኛ አይሁድ ወይን ለመጠጣት ገና ጠዋት መሆኑን፡፡ ይህም ራቢያዊ የሆነውን የዘጸ. 16፡8 ትርጉም ይከተላል (ኢ. ኤም. ብላይክሎክ፣ ቲንዳሌ አኪ የሐተታ ዝርዝር፣ ሐዋ. ገጽ 58)፡፡

▣ **"ሦስተኛው ሰዓት"** ይህ ጠዋት 3፡00 ቢሆን ነው፡፡ ይህም በቤተ መቅደስ የማለዳ መሥዋዕት የሚቀርብበት፡፡ እሱም ለአይሁድ ልዩ የጸሎት ጊዜ ነው፡፡ "ሦስተኛው ሰዓት" የአይሁድ ሰዓት አመላካች ነው፡፡ የአዲስ ኪዳን ጸሐፍት (በተለይም ዮሐንስ) ሁለቱንም የአይሁድንም ሆነ የሮሜን የሰዓት አመላካቾች ይጠቀማል፡፡

2፡16 **"ይህም በነቢዩ ኢዩኤል በኩል የተነገረው ነው"** ይህ የተጠቀሰው ከኢዩኤል 2፡28-32 ከሴፕቱዋጂንት ነው፡፡ ኢየሱስ ራሱ ይህንን የትንቢት ምንባብ መፈጸሙን በምንጭነት ጠቅሶታል (ሉቃስ 24፡27)፡፡

2፡17 **""በመጨረሻው ቀን"**ይህ ምናልባት ሉቃስ ከሴፕቱዋጂንት ጽሑፍ የጠቀሰው ሊሆን ይችላል፡፡ በብኪ ይህ ሐረግ የሚያመለክተው የዘመኑን መጨረሻና የመሲሑም መምጣት ነው፡፡ በአኪ "የመጨረሻዎቹ ቀናት" የሚያመለክቱት ሁለት የተነባበሩ የአይሁድን ዘመናት ነው፡፡ አዲሱ ዘመን የጀመረው የኢየሱስ ሥጋ መልበስ በቤተልሔም ሲሆን

የሚያበቃውም በዳግም ምጽዓቱ ነው:: እኛ የምንኖረው “በገና ድሮው” እና “በገና ወደፊቱ” መካከል ባለው ተቃርኖ በእግዚአብሔር መንግሥት ነው::

**ልዩ ርዕስ፡ ይህ ዘመንና የሚመጣው ዘመን**

የብኪ ነቢያት የወደፊቱን የሚመለከቱት የአሁኑ ተቀጥላ አድርገው ነው:: ለእነሱ የወደፊቱ የሚሆነው የመልክዓ ምድራዊው እስራኤል መመለስ ነው:: ሆኖም፣ አዲሱን ቀን እንኳ ተመልክተውታል (ኢሳ. 65፡17፤ 66፡22):: ያህዌን በገዛ ፍቃዳቸው ባለመቀበል ቀጥለው፣ በአብርሃም ዘሮች (ከስደት በኋላ) አዲስ ዓይነት የአይሁድ ኪዳናዊ የሆነ የትንቢታዊ ሥነ ጽሑፍ (ማለትም፣ 1ኛ ሄኖክ፣ 4ኛ እዝራ፣ 2ኛ ባሩክ):: እነዚህ ጽሑፎች በሁለቱ ዘመናት መካከል ያለውን ይገልጻሉ፡ የአሁኑ ክፉ ዘመን በሰይጣን ሥር የሆነው እና መጪው የጽድቅ ዘመን በመንፈስ ሥር የሚሆነውና በመሲሁ የተመረቀው (ሁሌም ኃይለኛ ተዋጊ)::

በዚህ በኩል ያለው ሥነመለኮት (መለኮታዊ) ግልጽ የሆነ እድገት አለ:: የሥነ መለኮት ሰዎች ይሄንን “እየሻሻለ የሚሄድ ራዕይ” በማለት ይጠሩታል:: አኪ ይሄንን ዓለማዊ እውነታ በሁለት ዘመናት ያጸኑታል (ማለትም፣ ጊዜያዊ ምንታዌ)፡

| <u>ኢየሱስ</u> | <u>ጳውሎስ</u> | <u>ዕብራውያን</u> |
|---|---|---|
| ማቴዎስ 12፡32 | ሮሜ 12፡2 | 1፡2 |
| ማቴዎስ 13፡22 እና 29 | 1ኛ ቆሮ. 1፡20፤ 2፡6፣8፤3፡18 | 6፡5 |
| ማርቆስ 10፡30 | 2ኛ ቆሮ. 4፡4 | 11፡3 |
| ሉቃስ 16፡8 | ገላትያ 1፡4 | |
| ሉቃስ 18፡30 | ኤፌ. 1፡21፤ 2፡1፣7፤ 6፡12 | |
| ሉቃስ 20፡34-35 | 1ኛ ጢሞቲዎስ 6፡17 | |
| | 2ኛ ጢሞቲዎስ 4፡10 | |
| | ቲቶ 2፡12 | |

በአኪ ሥነ መለኮት እነዚህ ሁለት የአይሁድ ዘመናት ይነባበራሉ፣ ምክንያቱም ያልታሰቡትና በጣም የሚጠበቁት ሁለቱ የመሲሁ ምጽዓቶች:: የኢየሱስ ሥጋ መሆን የብኪን ትንቢትን ከፍጻሜ አደረሰው፣ በአዲሱ ዘመን መመረቅ:: ሆኖም፣ ብኪ ደግሞ የተመለከተው የሱን ምጽዓት እንደ ፈራጅና እንደ ድል አድራጊ ሲሆን፣ እሱ ግን በመጀመሪያ የመጣው መከራ እንደሚቀበል አገልጋይ ነው (ኢሳ. 53)፣ ትሑትና የተዋረደ ሆኖ ነው (ዘካ. 9፡9):: እሱም በኃይል ተመልሶ ይመጣል፣ ልክ ብኪ እንደተነበየው (ራዕ. 19):: የእነዚህ ሁለት ደረጃዎች መፈጸም የመንግሥቱን መምጣት ምክንያት ይሆናሉ (ይመረቃል)፣ ነገር ግን የወደፊቱ (ሙሉ ለሙሉ አይቀዳጅም)::

▣ **“እግዚአብሔር ይላል”** ኮዴክስ ባዜ ኤም ኤስ ዲ ኩሪዮስ (ጌታ) አለው:: ኩሪስ የብኪን ያህዌ ነው የሚያመለክተው ወይስ ኢየሱስን? እሱም በርግጥ ሊሆን የሚችለው ቴዎስ (እግዚአብሔርን) ተናጋሪውን በጽሑፉ ለማመልከት እየሞከረ ነው::

▣ ***“መንፈሴን በሰው ልጆች ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ”*** (ዝከ ቁ. 39) ሁለንተናዊ ይዘት እንዳለው አስተውል:: ሁሉም አሮጌ ባህላዊ መሰናክሎች በክርስቶስ ተወግደዋል (1ኛ ቆሮ. 12፡13፤ ገላ. 3፡28፤ ኤፌ. 3፡6፤ ቆላ. 3፡11):: ምንም እንኳ በአይሁድ-አሕዛብ መካከል ልዩነት መደረጉ፣ በኢዩኤል 2 ላይ ባይገለጥም፣ ቁ. 38 ተመልከት፣ ልዩነት አለመደረጉን ያመለክታል:: ያህዌ መንፈሱን ያካፈለው በአምሳሉ ለተፈጠሩት ለሁሉም ሰዎች ነው (በጥሬ ቃሉ፣ “ለሁሉም ሥጋ”) ይህም በዘፍ. 1፡26-27 የተመለከተው::

▣ ***“‘ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ... ወንዶችም ሆኑ ሴቶች፣ መንፈሴን አፈስሳለሁ’”*** የጾታ ልዩነት አለመኖሩን ተመልከት::

**ልዩ ርዕስ፡ ሴቶች በመጽሐፍ ቅዱስ**

I. ብሉይ ኪዳን

ሀ. ከባህል አኳያ ሴቶች የሚታዩት እንደ ንብረት ነው
1. ከንብረት ዝርዝር ውስጥ ሰፍረዋል (ዘጸአት 20፡17)
2. የሴት ባሮች አያያዝ (ዘጸአት 21፡7-11)
3. የሴቶች መሀላ በኅብረተሰቡ ዘንድ በተከበሩ ወንዶች ሊሻር ይችላል (ዘኍልቁ 30)
4. ሴቶች እንደ ጦር ምርኮኛ (ዘዳግም 20፡10-14፤ 21፡10-14)

ለ. በተግባር ግን የሚያግባባ ነገር ነበር
1. ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በእግዚአብሔር አምሳል ነው የተፈጠሩት (ዘፍጥረት 1፡26-27)
2. አባትህንና እናትህን አክብር (ዘጸዓት 20፡12 [ዘዳ. 5፡16])

3. እናትንና አባትን ፍራ (ሌዋውያን 19፡3፤ 20፡9)
4. ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ናዝራዊ ለሆኑ ይችላሉ (ዘኍልቁ 6፡1-2)
5. ሴቶች ልጆች የመውረስ መብት አላቸው (ዘሁልቁ 27፡1-11)
6. የኪዳኑ ሕዝቦች አካል ናቸው (ዘዳግም 29፡10-12)
7. የአባትንና እናትን ትምህርት አስተውል (ምሳሌ 1፡8፤ 6፡20)
8. ወንዶችና ሴቶች የሄማን ልጆች (የሌዋውየን ቤተሰብ) በመቅደስ ዝማሬ ይመሩ ነበር (1ኛ ዜና 25፡5-6)
9. በአዲሱ ዘመን ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ትንቢት ይናገራሉ (ኢዩኤል 2፡28-29)

ሐ. ሴቶች መሪነት ድርሻ ነበራቸው፡፡
1. የሙሴ እህት፣ ማርያም ነቢይት በመባል ተጠርታለች (ዘፀ 15፡20-21)
2. ለማደሪያው ድንኳን የሚሆነውን ዕቃ ለማዘጋጀት ተሰጥተዋል (ዘፀ 35፡25-26)
3. ዲቦራ የተባለች ሴትም ነቢይት ነበረች መሳ 4፡4፣ ሁሉንም ነገዶች ትመራም ነበር መሳ 4፡4-5፣ 5፡7)
4. ሁልዳ የተባለች ሴትም ነቢይት ነበረች፡፡ አዲስ የተገኘውኘ የህጉን መጽሐፍ እንድታነብና እንድትተረጉም በንጉስ ኢዮስያስ ታዝዛም ነበረች (2ነገስት 22፡14፣ 2ዜና 34፡22-27)
5. ንግስት አስቴርም መልካም ሴትና በፋርስ አይሁድን ያዳነች ነበረች፡፡

II. አዲስ ኪዳን

ሀ. ከባህል አኳያ ሴቶች በሁለቱም፣ በይሁዲነትም ሆነ በግሪክ-ሮማ ዓለም፣ እንደ ሁለተኛ ዜጋ ይቆጠሩ ነበር፣ ጥቂት መብት ወይም ዕድል እንዳላቸው (የተለየ የሆነው መቄዶንያ ነበር)

ለ. ሴቶች በመሪነት ሚና
1. ኤልሳቤጥና ማሪያም፣ መልካም ሴቶች ለእግዚአብሔር ሆነው ተገኝተዋል (ሉቃስ 1-2)
2. ሐና፣ መልካም ሴት በቤተ መቅደስ ታገለግል ነበር (ሉቃስ 2፡36)
3. ሊድያ፣ አማኝና የቤተ ክርስቲያን ቤት መሪ ነበረች (ሐዋ. 16፡14፣40)
4. የፊሊጶስ አራቱ ደናግል ልጆች ነቢይቶች ነበሩ (ሐዋ. 21፡8-9)
5. ፎቢያ፣ የሴንክሪያ ቤተ ክርስቲያን ዲያቆን ነበረች (ሮሜ. 16፡1)
6. ጵርሲላ (ጵርስቅላ)፣ የጳውሎስ የሥራ ባልደረባ እና የአጵሎስ መምህርት (ሐዋ. 18፡26፤ ሮሜ 16፡3)
7. ማርያም፣ ትሪፋንያ፣ ትሪፎሳ፣ ፔርሲስ፣ ጁሊያ፣ የኔርዩስ እኅት፣ በርካታ ሴቶች የጳውሎስ የሥራ ባልደረባ ነበሩ (ሮሜ. 16፡6-16)
8. ጁኒያ (ኪጀት)፣ ሴት ሐዋርያ ሳትሆን አትቀርም (ሮሜ 16፡7)
9. ኢዩዲያ እና ሲንቲቄ፣ የጳውሎስ የሥራ ባልደረቦች ነበሩ (ፊሊጵ. 4፡2-3)

III. ዘመናዊው አማኝ የተለያዩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌዎች እንዴት ሚዛናዊ ያደርጋል?

ሀ. አንዱ ታሪካዊና ባህላዊ እውነቶችን እንዴት ሊወስን ይችላል፣ እነሱም በዋናው ጽሑፍ ጋር ብቻ ሊታይ የሚችልትን፣ ከዘላለማዊ እውነት አኳያ በሁሉም ቤተክርስቲያናት፣ በሁሉም አማኞች፣ በሁሉም ዕድሜ ተቀባይነት ሊያገኙ የሚችሉት?
1. የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ ፈጽሞ መውሰድ ይኖርብናል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው፣ እሱም የእምነትና የድርጊት ብቸኛ ምንጭ
2. ማየት የሚገባን ተመስጧዊ ጽሑፎች ታሪካዊ ሁኔታዎች ላይ መሆን አለበት
   ሀ. ያምልኮ ሥርዓት (ያምልኮ እና የደንብ) የእስራኤል (ሐዋ. 15፤ ገላ. 3)
   ለ. የአንደኛው ክፍለ ዘመን ይሁዲነት
   ሐ. የጳውሎስ ታሪካዊ ነክ የሆነ መልእክት በ1ኛ ቆሮንቶስ
      (1) የሮሜ ጣዖታዊ የሕግ ሥርዓት (1ኛ ቆሮ. 6)
      (2) ባርያ ሆነው የቀሩት (1ኛ ቆሮ. 7፡20-24)
      (3) ምንኩስና (ንጽሕና) (1ኛ ቆሮ. 7፡1—35)
      (4) ደናግል (1ኛ ቆሮ. 7፡36-38)
      (5) ለጣኦት የተሠዋ መብል (1ኛ ቆሮ. 10፡23-33)
      (6) በጌታ ራት ጊዜ አላስፈላጊ ድርጊቶች (1ኛ ቆሮ. 11)
3. እግዚአብሔር ራሱን በሙላት እና በግልጽ ለተወሰነ ባህል፣ በተወሰነ ቀን ገልጿል፡፡ እኛም መገለጡን በሚገባ መውሰድ ይኖርብናል፣ ነገር ግን የታሪካዊ ሁኔታዎቹን ዝርዝር አይደለም፡፡ የእግዚአብሔር ቃል የተጻፈው በሰው ቃል ነው፣ መልእክቱም ለተወሰነ ባህል በተወሰነ ጊዜ፡፡

ለ. የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ መፈለግ አለበት፡፡ ለዚህ ዘመን ምን አለ? ይህም ለትክክለኛ ትርጓሜ መሠረታዊና ዋነኛ ነው፡፡ ነገር ግን ይሄንን ከዘመናችን ተግባራዊ ልናደርገው ይገባል፡፡ አሁን፣ በሴቶች መሪነት ላይ ያለው ችግር (ሁነኛው የትርጓሜ ችግር ቃሉን ለገልጸው ይችላል፡፡ በርካታ አገልጋዮች ነበሩን፣ ከእረኞች ይልቅ፣ እነሱም እንደ መሪ የሚታዩ? ዲያቆናት ወይም

ነቢይቶች እንደ *መሪ ይታዩ* ነበርን? ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ. 14፡34-35 እና 1ኛ ጢሞ. 2፡9-15 ያለው ሴቶች በአደባባይ አምልኮ *መሪ* እንዳይሆኑ ያለው ግልጽ ነው! ነገር ግን ያንን ዛሬ እንዴት እተገብረዋለሁ? የጳውሎስንም ባህል ወይም የእኔን ባህል የእግዚአብሔርን ቃልና ፍቃድ ለማስተው አልፈልግም፡፡ የጳውሎስ ጊዜ ሊሆን የሚችለው በጣም የተወሰነ ነው፣ ነገር ግን የእኔ ቀን ደግሞ በጣም ግልጽ፡፡ ምቾት አይሰማኝም፣ የጳውሎስ ቃልማ ትምህርቱ ሁኔታዊ፣ የአንደኛው ክፍለ ዘመን አጥቢያዊ ሁኔታዎች ያሉት እውነታ ናቸው ስል፣ ተመስጧዊውን ጸሐፊ እቃወም ዘንድ፣ አስተሳሰቤም ሆነ ባህሌ እኔ ማን ነኝ?!

ሆኖም እኔ ምን ላደርግ እችላለሁ የሴት መሪዎች በመጽሐፍ ቅዱስ በምሳሌነት ከተጠቀሱ (በራሱ በጳውሎስ ጽሑፎች፣ ሮሜ 16)? ደህና ምሳሌ የሚሆነው የሕዝብ አምልኮን በተመለከተ ጳውሎስ ያብራራው ነው፣ በ1ኛ ቆሮ. 11-14፡፡ በ11፡5 የሴቶችን ስብከትና ጸሎት የፈቀደ ይመስላል፣ በአደባባይ አምልኮ ራሳቸውን ተሸፍነው፣ እንዲሁም 14፡34-35 ጸጥ እንዲሉ ይጠይቃል! ዲያቆናት ነበሩ፣ (ሮሜ 16፡1) እንዲሁም ነቢይቶች (ሐዋ. 21፡9)፡፡ ይህ የተለያየ ሐሳብ ነው የጳውሎስን ሐሳብ እንዳይ ነጻነት ሰጥቶ የፈቀደልኝ (የሴቶችን ክልከላ በተመለከተ) በአንደኛው ክፍለ ዘመን ቆሮንቶስና ኤፌሶን እንደተወሰነ፡፡ በሁለቱም ቤተ ክርስቲያናት ከሴቶች ጋር በተያያዘ ችግሮች ነበሩ፣ አዲስ ያገኙትን ነጻነት በመጠቀም ላይ (ብሩስ ዊንተር፣ ቆሮንቶስ ጳውሎስ ከሄደ በኂላ) ይህም በቤተ ክርስቲያናቸው ችግር ፈጥሯል የእነሱን ህብረተሰብ በክርስቶስ ለመድረስ፡፡ ነጻነታቸው ተገድቧል፣ ወንጌል በተሻለ ሁኔታ ውጤታማ ይሆን ዘንድ፡፡

የእኔ ዘመን ከጳውሎስ ተቃራኒው ነው፡፡ በእኔ ዘመን ወንጌል ሊገደብ ይችላል፣ የሠለጠኑ፣ አንደበተ ርቱዕ ሴቶች ወንጌልን እንዲያካፍሉ ካልተፈቀደላቸው፣ የመሪነት ቦታ መያዝ ሳይሆን! የአደባባይ አምልኮ ዋነኛ ግብ ምንድነው? ወንጌልን ማዳረስና ደቀ መዛሙርትን ማፍራት አይደለምን? እግዚአብሔር በሰት መሪዎች ይከብራል ወይስ ይደሰታልን? መጽሐፍ ቅዱስ ባጠቃላይ "አዎን" የሚል ይመስላል!

ለጳውሎስ የምለው አለኝ፤ የእኔ ሥነመለኮት በመሠረቱ ጳውሎሳዊ ነው፡፡ ከመጠን ያለፈ በዘመናዊ ሴታዊነት ተጽዕኖ እንዲኖርብኝ አልሻም! ሆኖም፣ ቤተ ክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታን ምላሽ ከመስጠት ወደ ኂላ ቀርታለች፣ ልክ እንደ ባርነት ተገቢ አለመሆን፣ ዘረኝነት፣ ፍርደ-ገምድልነት እና ወሲበኛነት፡፡ ሴቶች በዘመናዊው ዓለም የሚደርስባቸውን ያልተገባ ነገር፣ ተገቢ ምላሽ ከመስጠት ዝግተኛ ሆናለች፡፡ እግዚአብሔር በክርስቶስ ባሮችንና ሴቶችን ነጻ አውጥቷቸዋል፡፡ ባህላዊ እስራት ያለው ጽሑፍ እንደገና እንዲያስራቸው አልደፍርም፡፡

አንድ ተጨማሪ ነጥብ፡ እንደ ተርጓሚ፣ ቆሮንቶስ በጣም የተበጠበጠች ቤተ ክርስቲያን መሆንዋን አውቃለሁ፡፡ የክርስቶሳዊ ስጦታዎች ዋጋ እየተከፈለባቸው ያላግባብ ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ ሴቶች ምናልባት በዚህ ተይዘው ይሆናል፡፡ እኔ እንደማምነው ኤፌሶኖች በሐሰተኛ መምህራን ተጎድተዋል፣ እነሱም ሴቶችን ይዘው በቤት ባለ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ተቀያሪ እንዲሆኑ፡፡

ሐ. ለተጨማሪ ንባብ አስተያየቶች

*መጽሐፍ ቅዱስን ከነሙሉ ጠቀሜታው እንዴት እንደሚነበብ* በጎርደን ፊ እና ዶንግ ስቱዋርት (ገጽ 61-77)

ወንጌልና *መንፈሱ የአዲስ ኪዳን ትርጓሜ ፍሬ ሐሳቦች* በጎርደን ፊ

*የመጽሐፍ ቅዱስ ዋነኛ አባባሎች* በዋልተር ሲ. ኬይሰር፣ ፒተር ኤች. ዴቪስ፣ ኤፍ. ኤፍ. ብሩስ እና ማንፍሪድ ቲ. ብራንች (ገጽ 613-616፤ 665-667)፡፡

▣ "ትንቢት" ይህን ዓይነት ለመረዳት ቢያንስ ሁለት መንገዶች አሉ፡ (1) በቆሮንቶስ መልእክት ይህ ቃል የሚያመለክተው ወንጌልን ለማካፈል ወይም ለማወጅ ነው፣ (ዝከ 14፡1፤ ሐዋ. 2፡17)፤ (2) የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ነቢያትን ይገልጻል (ዝከ 12፡27፤ 13፡1፤ 15፡32፤ 22፡10፣ ነቢይቶችንም ጭምር፣ 21፡9)፤ መጻዒውን የተነበዩ፡፡

የዚህ ቃል ችግር የሚሆነው የአኪ. የትንቢት ስጦታ ከብኪ. ትንቢት ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ነው፡፡ በብኪ. ነቢያት የጽሑፉ አስፋሪዎች ናቸው፡፡ በአኪ. ይህ ተግባር የተሰጠው ለዋነኞቹ አስራ ሁለት ሐዋርያት እና ለረዳቶቻቸው ነው፡፡ "ሐዋርያ" የሚለው ቃል የሚያያዘው ቀጣይነት ባለው ስጦታ ነው (ኤፌ. 4፡11)፣ ነገር ግን አስራ ሁለቱ ከሞቱ በኂላ በተለየ ተግባር ነው፣ የነቢያት ሃላፊነት እንደሆነ ሁሉ፡፡ ተመስጦ አቁሟል፣ ሌላ ተጨማሪ ተመስጧዊ ቅዱስ ቃል የለም (ይሁዳ 3፣20)፡፡ የአዲስ ኪዳን ትንቢቶች ቀዳሚ ተግባር ወንጌልን ማወጅ ነው፣ ነገር ግን ደግሞ የተለየ ተግባር፣ እሱም የአኪን እውነት ለአሁኑ ሁኔታና ፍላጎት፡፡

▣ "'ወጣት ወንዶች…ሽማግሌ ወንዶች'" የዕድሜ ልዩነት እንደሌለ አስተውል፡፡

2፡18 "'በባሪያዎቼ ላይ'" ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ልዩነት እንደሌለ ተመልከት ጴጥሮስ "ትንቢት" የሚለውን ቃል ጨምሮበታል፣ በኢዩኤል ትንቢት ላይ፡፡ እሱም መሲሐዊ ዕብራይስጥ ጽሑፍ ወይም የግርክ ሴፕቱዋጂንት ላይ አይደለም፣ ከቁ. 17 ላይ የተመለከተ ነው፡፡

2፡19-20 ይህ ትንቢታዊ ቋንቋ ነው፣ እሱም ጴጥሮስ መፈጸሙን፣ ግን እነዚህ የተገለጹት የተፈጥሮ ክስተቶች ገና አልተከሰቱም፣ ኢየሱስ በመስቀል ላይ በነበረበት ጊዜ ከተፈጠረው ጨለማ በቀር፡፡ የሚናገረውም በዘይቤአዊ ቋንቋ ነው፣ ስለሚመጣው ፈጣሪና ፈራጅ፡፡ በብኪ. የሱ መምጣት ለበረከትና ለፍርድ ነው፡፡ ፍጥረት ሁሉ በሱ መምጣት

ይንቀጠቀጣል (ኢሳ. 13፡6 እና አሞጽ 5፡18-20)። በብኪ. ትንቢት ግልጽ የሆነ ልዩነት በሥጋ መልበሱ (የመጀመሪያ ምጽአቱ) እና በፓሮሲያ (በዳግም ምጽአቱ) መካከል የለም። አይሁድ ይጠባበቁ የነበሩት አንደኛውን ምጽአቱን ብቻ ነው እንደ ኃያል ፈራጅ)አዳኝ።

**ልዩ ርዕስ፡ የፍጻሜ ትንቢታዊ ሥነ—ጽሑፍ**

ይህ ልዩ ርዕስ ከእኔ የራዕይ ሐተታ ላይ የተወሰደ ነው።

ራዕይ ልዩ የሆነ የአይሁድ የሥነ ጽሑፍ ዘርፍ ነው፣ የፍጻሜ ትንቢት። እሱም ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው በከርክር በተሞሉ ጊዜያት ማረጋገጫውን ለማስቀመጥ ይህም እግዚአብሔር ታሪክን የሚቆጣጠርና ለሕዝቡም መታደግን እንደሚያመጣ ነው። ይህ ዓይነቱ ሥነ ጽሑፍ በባሕርዩ

1. የእግዚአብሔር ሁለንተናዊ ሉዓላዊነት ጠንካራ አግባብ (አሀድነት እና ቁርጠኝነት)
2. በመልካምና በክፉ መካከል የሚደረግ ትግል፣ የዚህ ዘመንና የሚመጣው ዘመን (ምንታዌነት)
3. ልዩ ፍች ያላቸውን ቃላት መጠቀም (ዘወትር ከብኪ. ወይም መልእክት አዘል ከሆኑ የአይሁድ ትንቢታዊ ሥነ-ጽሑፎች)
4. ቀለማትን፣ ቁጥሮችን፣ እንስሳትን አንዳንድ ጊዜ እንስሳትን)ሰዎችን መጠቀም
5. የመላእክትን ምልጃ በራዕይና በሕልሞች መጠቀም፣ ነገር ግን ዘወትር በመልአካዊ ምልጃ በኩል
6. ቀዳሚው ትኩረት በፍጻሜው ሰዓት ላይ ነው (በአዲሱ ዘመን)
7. የተወሰኑ የምልክቶች ስብስብ መጠቀም፣ እውነታውን ሳይሆን፣ የመጨረሻውን ዘመን መልእክት ለማስተላለፍ
8. የዚህ ዓይነቱ ዘውግ ጥቂት ምሳሌዎች

   ሀ. ብሉይ ኪዳን
   - (1) ኢሳይያስ 24-27፣ 56-66
   - (2) ሕዝቅኤል 37-48
   - (3) ዳንኤል 7-12
   - (4) ኢዩኤል 2፡28-3፡21
   - (5) ዘካርያስ 1-6፣ 12-14

   ለ. አዲስ ኪዳን
   - (1) ማቲዎስ 24፣ ማርቆስ 13፣ ሉቃስ 21፣ እና 1ኛ ቆሮንቶስ 15 (በአንዳንድ መልኩ)
   - (2) 2ኛ ተሰሎንቄ 2 (በብዙ መልኩ)
   - (3) ራዕይ (ምዕራፍ 4-22)

   ሐ. ከመጽሐፍ ቅዱስ ያልተካተቱ (ከዲ. ኤስ. ሩሴል፣ የአይሁድ የፍጻሜ ትንቢቶች አግባብና መልእክት፣ ገጽ 37-38)
   - (1) 1ኛ ሄኖክ፣ 2ኛ ሄኖክ (የሄኖክ ምሥጢራት)
   - (2) መጽሐፈ ኩፋሌ
   - (3) የሲቢሊን ታሪክ 3፣ 4፣ 5
   - (4) የአስራ ሁለቱ አባቶች ምስክርነት
   - (5) የሰሎሞን መዝሙራት
   - (6) የሙሴ ግምቶች
   - (7) የኢሳይያስ መሥዋዕታዊነት
   - (8) የሙሴ ትንቢት (የአዳምና የሔዋን ሕይወት)
   - (9) የአብርሃም ትንቢት
   - (10) የአብርሃም ምስክርነት
   - (11) 2ኛ እስድራስ (4ኛ እስድራስ)
   - (12) ባሩክ 2፣ 3

2፡20 **"ታላቁና የሚያስፈራው የጌታ ቀን"** "የሚያስፈራው" የሚለው ቃል ከተመሳሳይ ሥር እንደ ኢጲፋንያ ሲሆን፣ ዘወትርም ጥቅም ላይ የሚውለው ለኢየሱስ ዳግም ምጽዓት ነው (1ኛ ጢሞ. 6፡14፤ 2ኛ ጢሞ. 4፡1፤ ቲቶ 2፡13)።

**ልዩ ርዕስ፡ ዳግም ምጽአቱ**

ይህ በጥሬው "ፓሩሲያ" ሲሆን፣ ፍችውም "መገኘት" ነው፣ ጥቅም ላይ የሚውለውም መንግሥታዊ ጉብኝትን ነው። ሌሎቹ የአኪ. ቃላት ለዳግም ምጽአቱ ጥቅም ላይ የሚውሉት (1) አጲፋንያ፣ "ፊት ለፊት መከሰት"፤ (2) አፖካሉፒስ፣ "መገለጥ"፤ እና (3) "የጌታ ቀን" እንዲሁም የዚህ ሐረግ የተለያዩ መልኮች ናቸው።

አኪ. ባጠቃላይ የተጻፈው በብኪ. ዓለም እይታ ነው፣ የሚገልጸውም

1. ያሁኑን ክፉ፣ ዓመጸኛ ዓለም
2. መጪውን አዲሱን የጽድቅ ዘመን
3. እሱም የሚመጣው በመንፈስ አማካኝነት በመሲሑ (በተቀባው) ሥራ በኩል ነው

የሥነመለኮታዊው ቀጣይነት ያለው ራዕይ አተያይ ያስፈልጋል፣ ምክንያቱም የአኪ. ጸሐፍት የእስራኤልን ተስፋ በመጠኑ አሻሽለውታል። ከወታደራዊና ከብሔረተኝነት አትኩሮት (እስራኤል) የመሲሕ አመጣጥ፣ ሁለት ምጽአቶች አሉ ወደሚል። የመጀመሪያው ምጽአት የነበረው የመለኮት ሥጋ መልበስ በናዝሬቱ ኢየሱስ መጸነስና መወለድ። የመጣውም ጠረኛ ሳይሆን፣ ፈራጅ ሳይሆን፣ "መከራ እንደሚቀበል አገልጋይ" ነው ኢሳ. 53፤ ደግሞም የአህያ ውርንጫ እየጋለበ (የጦር ፈረስ ወይም የንጉሥ በቅሎ ሳይሆን)፣ በዘካ. 9፡9። የመጀመሪያው ምጽአት የተመረቀው አዲሱ መሲሐዊ ዘመን ነው፣ የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ላይ። በአንድ በኩል መንግሥቱ እዚህ ነው፣ ነገር ግን በሌላው አንጻር ገና ሩቅ ነው። ይህ በሁለቱ ምጽአቶች መካከል ያለ ተቃርኖ፣ በሁለቱ የአይሁድ ዘመናት ይነባበራል፣ ያም በብኪ. የማይታየው ቢያንስ ግልጽ ባልሆነው። በእውነታው ይህ መንታ ምጽአት አጽንዖት የሚሰጠው የያህዌን ቁርጠኝነት ነው ሰዎችን ሁሉ ለማዳን (ዘፍ. 3፡15፤ 12፡3፤ ዘጸ. 19፡5 እና የነቢያት ስብከት፣ በተለይም ኢሳይያስ እና ዮናስ)።

ቤተ ክርስቲያን የብኪ. ትንቢት መፈጸምን አትጠባበቅም፣ ምክንያቱም አብዛኞቹ ትንቢቶች የሚያመለክቱት የመጀመሪያውን ምጽአት ነው (መጽሐፍ ቅዱስን ከነ ሙሉ ጠቀሜታው እንዴት እንደሚነበብ፣ ገጽ 165-166)። አማኞች መጠበቅ ያለባቸው ግርማ ሞገስ ያለውን የተነሣውን የነገሥታት ንጉሥ፣ እና የጌቶች ጌታ በተስፋ የተጠበቀው ታሪካዊው አዲሱ የጽድቅ ዘመን በምድር ላይ፣ በሰማይ እንደሆነ ሁሉ ነው (ማቴ. 6፡10)። የብኪ. አቀራረቦች ርግጠኛ አልነበሩም፣ ነገር ግን ያልተጠናቀቁ ነበሩ። እሱም ነቢያት እንደተነበዩት በያህዌ ኃይልና ሥልጣን ዳግመኛ ይመጣል።

ዳግም ምጽአቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል አይደለም፣ ነገር ግን ጽንሰ-ሐሳቡ የቃሉን ቅርጽ ያሳየዋል፣ እንዲሁም የሙሉ አኪ. አወቃቀርን። እግዚአብሔር ሁሉንም በትክክል አስቀምጦታል። በእግዚአብሔርና በአምሳሉ በተሠራው ሰው መካከል ያለ ኅብረት ይመለሳል። ክፉው ይፈረድበታል ይወገዳልም። የእግዚአብሔር ዓላማ ፈጽሞ በምንም ዓይነት አይወድቅም!

2፡21 "'እያንዳንዱ'" እዚህ ሁለንተናዊ ይዘት ነው ያለው፣ በድጋሚ (ዝከ ቁ. 17 እና 39)። ኢየሱስ የሞተው ለዓለም ሁሉ ኃጢአት)ኃጢአቶች ነው (ዮሐንስ 3፡16፤ 1ኛ ጢሞ 2፡4፤ 2ኛ ጴጥ. 3፡9)። መንፈስ በሁሉም የሰው ልጅ ላይ መፍሰሱን አስተውል (ዝከ ቁ. 17)።

▣ "'የጠራን'" ይህ ያለፈ ድርጊት መካከለኛ ሁኔታ ገላጭ ነው። የሰዎች ምላሽ የእግዚአብሔር የማዳኑ እቅድ አካል ነው (ኢዩኤል 2፡32፤ ዮሐንስ 1፡12፣ 3፡16፤ እና ሮሜ 10፡9-13)። ግለሰብ የሰው ልጆች የተጠሩት ንስሐ ሊገቡና በወንጌል እንዲያምኑ ነው፣ እናም በክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ወደ አለ ግላዊ ህብረት (ዝከ 3፡16፣19፤ 20፡21፤ ማርቆስ 1፡15)። ኢየሱስ የሞተው ለመላው ዓለም ነው፤ ምሥጢር የሚሆነው አንዳንዶች ለመንፈስ መቃተት ምላሽ ሲሰጡ (ዮሐንስ 6፡44፣65) አንዳንዶች እምቢ ማለታቸው ነው፣ (2ኛ ቆሮ. 4፡4)።

▣ "'በጌታ ስም'" ይህ የሚያመለክተው የኢየሱስን ባሕርይ ወይም ስለ እሱ ያለውን ትምህርት ነው። እሱም ግለሰባዊና መሠረተ እምነታዊ ይዘት አለው።

**ልዩ ርዕስ፡ የጌታ ስም**

ይህ የተለመደ የአኪ. ሐረግ ሲሆን በቤተ ክርስቲያን የሦስቱ አካል (ሥላሴ) በሙሉ ኃይል መገኘት ነው። ምትሀታዊ ቀመር ሳይሆን የእግዚአብሔርን ባሕርይ ማሳየት ነው።

ሐረጉ ዘወትር የሚያመለክተው ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ ነው (ፊሊጵ. 2፡11)

1. አንዱ በኢየሱስ ያለውም እምነት በጥምቀት ሲገልጽ (ሮሜ 10፡9-13፤ ሐዋ. 2፡38፤ 8፡12፣16፤ 10፡48፤ 19፡5፤ 22፡16፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡13፣15፤ ያዕቆብ 2፡7)
2. ርኩስ መንፈስን በማውጣት (ማቴ. 7፡22፤ ማርቆስ 9፡38፤ ሉቃስ 9፡49፤ 10፡17፤ ሐዋ. 19፡13)
3. በፈውስ ጊዜ (ሐዋ. 3፡6፣16፤ 4፡10፤ 9፡34፤ ያዕቆብ 5፡14)
4. በአገልግሎት ላይ (ማቴ. 10፡42፤ 18፡5፤ ሉቃስ 9፡48)
5. በቤተ ክርስቲያ ሥነ ሥርዓት አወሳሰድ ጊዜ (ማቴ. 18፡15-20)
6. ለአሕዛብ በሚሰበክበት ጊዜ (ሉቃስ 24፡47፤ ሐዋ. 9፡15፤ 15፡17፤ ሮሜ 1፡5)
7. በጸሎት ጊዜ (ዮሐንስ 14፡13-14፤ 15፡2፣16፤ 16፡23፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡2)
8. ክርስትናን የመግለጫ መንገድ (ሐዋ. 26፡9፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡10፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡19፤ ያዕቆብ 2፡7፤1ኛ ጴጥ 4፡14)

እንደ አዋጅ ነጋሪ፣ አገልጋይ፣ ረዳት አድራጊ፣ ፈዋሽ፣ ገሣጭ፣ ወዘተ ስንሠራ በሱ ባሕርይ፣ በሱ ሃይል፣ በእሱ ስጦታ– በእሱ ስም እንሠራለን!

▣ -"'ይድናል'" በዚህ ጽሑፍይህ የሚያመለክተው መንፈሳዊ መዳንን ሲሆን፣ በኢዩኤል ደግሞ ማለት የሚሆነው ከእግዚአብሔር ቀጣ የአካላዊ መጠበቅ ነው (ዝከ ቁ. 40):: "ድኗል" የሚለው ቃል በብኪ. ጥቅም ላይ የሚውለው ለአካላዊ መታደግ ነው (ማቴ. 9:22፤ ማርቆስ 6:56፤ ያዕቆብ 5:14፣ 20):: ሆኖም፣ በአኪ. ጥቅም ላይ የሚውለው በዘይቤአዊነት በመንፈሳዊ ደህንነት ወይም ከእግዚአብሔር ቁጣ ስለ መጠበቅ ነው (ያዕቆብ 1:21፤ 2:14፤ 4:12):: የእግዚአብሔር የልቡ ሐሳብ በአምሳሉ ለተፈጠሩት ለሁሉም ወንዶችና ሴቶች መዳን ነው፤ ለህብረት ለተፈጠሩት!

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ: 2:22-28**
**[22]የእስራኤል ሰዎች ሆይ፥ ይህን ቃል ስሙ፤ ራሳችሁ እንደምታውቁ፥ የናዝሬቱ ኢየሱስ እግዚአብሔር በመካከላችሁ በእርሱ በኩል ባደረገው ተአምራትና በድንቆች በምልክቶችም ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠ ሰው ነበረ፤ [23]እርሱንም በእግዚአብሔር በተወሰነው አሳቡና በቀደመው እውቀቱ ተሰጥቶ በዓመፀኞች እጅ ሰቅላችሁ ገደላችሁት:: [24]እግዚአብሔር ግን የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነሣው፥ ሞት ይይዘው ዘንድ አልቻለምና:: [25]ዳዊት ስለ እርሱ እንዲህ ይላልና:: ጌታን ሁልጊዜ በፊቴ አየሁት፥ እንዳልታወክ በቀኜ ነውና:: [26]ስለዚህ ልቤን ደስ አለው፥ ልሳኔም ሐሤት አደረገ፥ ደግሞም ሥጋዬ በተስፋ ያድራል፤ [27]ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና፥ ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትሰጠውም:: [28]የሕይወትን መንገድ አስታወቅኸኝ፤ ከፊትህ ጋር ደስታን ትሞላብኛለህ::**

2:22 "የእስራኤል ሰዎች ሆይ" እነዚህ አድማጮች የኢየሱስ ምድራዊ ሕይወት የመጨረሻው ሳምንት ሁነቶች የዓይን ምስክሮች ናቸው:: ጴጥሮስ ስለሚናገረው የመጀመሪያ ደረጃ እውቀቱ አላቸው:: መንፈሳዊ ውስጠት ያላቸው ወደ ሦስት ሺህ የሚጠጉ በመጀመሪያው ስብከት ለወንጌል ምላሻቸውን ሰጥተዋል (ዝከ ቁ. 41)::

▣ "ያደመጡ" ይህ የድርጊት የአሁን ተተኪ ነው:: የመንፈስ አካላዊ መገኘት ትኩረታቸውን ሳበው፤ አሁን እንግዲህ የወንጌል መልእክት ይመጣል::

▣ "የናዝሬቱ ኢየሱስ" ይህ ዘወትር የሚወሰደው ከ "ኢየሱስ የናዝሬቱ" ከሚለው ጋር በትይዩ ነው:: ነገር ግን፣ ይሄንን ለመግለጽ ያልተለመደው መንገድ ነው:: ይህ ሐረግ መሲሐዊውን ማዕርግ የሚያንጸባርቅ ይመስላል "ብራንች" (ዝከ ኢሳ. 4:2፤ 6:13፤ 11:1፣10፤ 14:19፤ 53:2፤ ኤር. 23:5፤ 33:15-16፤ ዘካ. 3:8፤ 6:12-13):: የዕብራይስጡ ቃል ለ "ብራንች" ኒዘር ነው::

**ልዩ ርዕስ: ኢየሱስ የናዝሬቱ**

በርካታ የተለያዩ የግሪክ ቃላት አሉ፣ ማለትም አኪ. በተብራራ መልኩ ኢየሱስን የሚገልጽበት

ሀ. የአኪ. ቃላት

1. ናዝሬት - በገሊላ ያለች ከተማ (ሉቃስ 1:26፤ 2:4፣39፣51፤ 4:16፤ ሐዋ. 10:38):: ይህች ከተማ በተንዳኝ ምንጮች አልተጠቀሰችም ነገር ግን በቅርብ ጊዜ ጽሑፎች ላይ ተገኝታለች::
   ኢየሱስ ከናዝሬት መሆኑ አሻሚ አይደለም (ዮሐንስ 1:46):: በኢየሱስ መስቀል ላይ የተደረገው የዚህ ስፍራ ምልክት ስም ለአይሁድ የንቀት ማሳያ ነው::
2. ናዛሮስ - የሚያመለክተው ደግሞ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥን ነው (ሉቃስ 4:34፤ 24:19)::
3. ናዛሮስ - የሚያሳየው ከተማን ሲሆን ነገር ግን በተጨማሪ ደግሞ በዕብራይስጡ መሲሐዊ ቃል "ብራንች" ጨዋታን (ትርዒትን) ያሳያል (ኒዘር፣ ኢሳ. 4:2፤ 11:1፤ 53:2፤ ኤር. 23:5፤ 33:15፤ ዘካ. 3:8፤ 6:12):: ሉቃስ ይሄንን ለኢየሱስ ይጠቀምበታል በ18:37 እና ሐዋ. 2:22፤ 3:6፤ 4:10፤ 6:14፤ 22:8፤ 24:5፤ 26:9::

ለ. በአኪ. ውጪ ታሪካዊ አጠቃቀሙ:: ይህ ሹመት ሌላም ታሪካዊ አጠቃቀም አለው::

1. እሱም የሚያሳየው የአይሁድን (ቅድመ ክርስትና) የመናፍቃን ወገንን ነው::
2. እሱም ጥቅም ላይ የዋለው በአይሁድ ማህበረሰብ በኢየሱስ የሚያምኑትን ለመግለጥ ነው (ሐዋ. 24:5፣14፤ 28:22)::
3. እሱም በሶርያ (የአራምኛ) ቤተ ክርስቲያናት አማኞችን ለማመልከት ነው:: "ክርስቲያን" በግሪክ አብያተ ክርስቲያናት የሚያመለክተው አማኞችን ነው::
4. አንዳንዴ ከኢየሩሳሌም መውደቅ በኋላ፣ ፈሪሳውያን በጃሚና ዳግም ተደራጅተው በቤተ ክርስቲያንና በምኩራብ መካከል ይፋ የሆነ ልዩነት አስቀምጠዋል:: ለዚህ ምሳሌ የሚሆንም የውግዘት ቀመር ክርስቲያኖችን በመቃወም "በአስራ ስምንተኛው ቃለ ቡራኬ" ከባርኮት 28ለ-29ሀ አማኞችን "ናዝራውያን" የሚል ተገኝቷል::
   "ናዝራውያን እና መናፍቃን ወዲያውኑ ይጥፉ፤ ከሕይወት መጽሐፍ ይደምሰሱ እንዲሁም ከታመኑት ጋር አይጻፉ::"

ሐ. የጸሐፊው አስተያየት

በቃሉ በርካታ ሆሄያት መኖር እገረማለሁ፣ ይህም በብኪ. ያልተሰማ ቢሆንም እንደ "ኢያሱ" በርካታ ሁሄያት በዕብራይስጥ አሉት:: ይህም፣ የሆነበት ምክንያት (1) ከመሲሐዊው ቃል ከ "ብራንች" ጋር ባለው የቀረበ ትስስሮሽ፤ (2) ከአሉታዊ ትርጉም ጋር በመደበላለቁ፤ (3) ጥቂት

*ወይም ምንም ተጓዳኝ ማረጋገጫ ከገሊላዋ የናዝሬት ከተማ ጋር መኖሩ እርግጠኛ እንዳልሆን አድርጎኛል፣ ትክክለኛውን ፍች ለማግኘት፤ እንዲሁም* (4) *በመለኮታዊ መልኩ ከአጋንንት አፍ ወጥቷል (ማለትም፣ "ልታጠፋን መጣህን?")።*

*ለዚህ ቃል ምድብ ለሙሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥናት፣ የነጻ ትምህርት የኮሊን ብራውን (አዘጋጅ)፣ አዲሱ ዓለም አቀፍ መዝገበ ቃላት የአዲስ ኪዳን ሥነ መለኮት፣ ቅጽ* 2፣ *ገጽ* 346 *ተመልከት።*

▣ **"ለእናንተ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተገለጠ ሰው"** ይህ *የተፈጸመ ተገብሮ ቦዝ አንቀጽ* ነው። *ቃሉ የሚለው "በተግባር የታየ" ነው።* እግዚአብሔር በግልጽና በተደጋጋሚ በኢየሱስ ቃልና ሕይወት ራሱን ገልጧል። እነዚህ የኢየሩሳሌም አድማጮች አይተዋል ሰምተዋልም!

▣ **"በተአምራትና ድንቆች በምልክቶችም"** እነዚህ አድማጮች፣ ኢየሱስ በሕይወቱ መጨረሻ ሳምንት ላይ በኢሩሳሌም *ያደረገውን የዓይን ምስክር ናቸው።*

*"ድንቆች" (ቴራስ) የሚለው ቃል ያልተለመደ ምልክት አመላካች ሲሆን፣ ዘወትር በሰማይ ነው የሚከሰተው፣ እንደ ቁ.* 19-20። *"ምልክት" (ሴሚዮን) የሚለው ቃል የሚያሳየው ልዩ ሁነትን ሲሆን ትርጉም ወይም ጠቀሜታ ያለው ነው። በዮሐንስ ወንጌል ይህ ቁልፍ ቃል ነው (ሰባት የተለዩ ምልክቶች፣ ዝከ* 2:1-11፤ 4:46-54፤ 5:1-18፤ 6:1-15፣16-21፤ 9:1-41፤ 11:1-57)። *ምልክቶች ብዙ ጊዜ በግልጽ ብርሃን አይታዩም (ዮሐንስ* 2:18፤ 4:48፤ 6:2)። *እዚህ ጥቅም ላይ የዋለው ጽኑ ለሆነ የኃይል መግለጫ ሲሆን የአዲሱ የመንፈስ ዘመን መገለጫ መጀመሩን የሚያሳይ ነው!*

*ማራኪ የሚሆነው ጴጥሮስ በመጀመሪያው ስብከት ላይ ብዙ ጊዜ አለማጥፋቱ ነው (ቢያንስ ጥቅል ሐሳቡ በሐዋ.* 2 *ላይ) ስለ ኢየሱስ ፊተኛ ሕይወት እና ትምህርት። የብኪ ትንቢት ፍጻሜ፣ የእሱ ቀድሞ የተወሰነ የመሥዋዕታዊ ሞት፣ እና ባለግርማ ትንሣኤው ዋነኛ ነጥቦች ናቸው።*

2:23 **"ይህ ሰው"** ይህ ምናልባት የንቀት ዘይቤ ነው (ዝከ 5:28፤ 6:13፤ ሉቃስ 23:14፤ ዮሐንስ 9:16፤ 18:29)፣ ነገር ግን በሐዋ. 23:9 እና 20:31-32 አሉታዊ ዘይቤ አይደለም።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ቀድሞ የተወሰነ እቅድ"** |
| **አኪጀት** | **"የተወሰነ ምክር"** |
| **አየተመት** | **"የተወሰነው እቅድ"** |
| **አእት** | **"የእግዚአብሔር የራሱ እቅድ"** |
| **አኢመቅ** | **"ሆን ተብሎ የተደረገ ሐሳብ"** |

ይህ ቃል ሆሪዞ የተጠናቀቀ ተገብሮ ቦዝ አንቀጽ ቅርጽ ያለው ነው። *መሠረታዊ ፍችው፣ መወሰን፣ መሾም፣ ወይም ማጽናት ነው።* በብኪ ጥቅም ላይ የሚውለው የመሬት ድንበሮችንና ፍላጎቶችን ለመወሰን ነው። ሉቃስ ዘወትር ይጠቀምበታል (ሉቃስ 22:22፤ ሐዋ. 2:23፤ 10:42፤ 11:29፤ 17:26፣31)። መስቀል እግዚአብሔርን የሚያስገርመው አይደለም፣ ነገር ግን ዘወትር የእሱ ምርጫ መሣርያ ነው (ማለትም፣ *የመሥዋዕታዊው ሥርዓት የሌዋ.* 1-7) *ለዐመጸኞቹ ሰዎች መቤዠትን ለማምጣት* (ዘፍ. 3:15፤ ኢሳ. 53:10፤ ማርቆስ 10:45፤ 2ኛ ቆሮ. 5:21)።

የኢየሱስ ሞት ድንገተኛ አልነበረም። የእግዚአብሔር እቅድ ነበር (ሉቃስ 22:22፤ ሐዋ. 3:18፤ 4:28፤ 13:29፤ 26:22-23)። ኢየሱስ የመጣው ሊሞት ነው (ማርቆስ 10:45)!

▣ **"እግዚአብሔር ቀድሞ የሚያውቀው"** ይህ ቃል ፕሮግኖሲስ (ቀድሞ ማወቅ)፣ ጥቅም ላይ የዋለው እዚህና 1ኛ ጴጥ. 1:2 ላይ ነው። ይህ የእግዚአብሔር አስቀድሞ ማወቅ ጽንሰ-ሐሳብ የሰው ልጆችን ታሪክ፣ ለእኛ ለሰዎች ነጻ ፍቃድ ጋር ለማመሳከር ይቸግረናል እግዚአብሔር ዘላለማዊ ነው፣ *መንፈሳዊ ሕላዌ፣ በሥጋዊ አግባብ ሊወሰን የማይቻል።* ምንም እንኳ እሱ ታሪክን ቢቆጣጠርና ቅርጹን ቢያበጅም፣ የሰው ልጆች የልብ ሐሳባቸውና ድርጊታቸው ሀላፊነቱን ይወስዳሉ። ቅድመ እውቀና የእግዚአብሔርን ፍቅርና ምርጫ ተጽዕኖ አያሳድርበትም። እንዲህ ከሆነ፣ በሰው ልጆች ቀጣይ ጥረትና ውጤት የሚወሰን ይሆናል። እግዚአብሔር ሉዓላዊ ነው፣ እናም እሱ የኪዳኑን ተከታዮች መርጧል፣ ለእሱም ምላሽ ለመስጠት የምርጫ ነጻነት አላቸው (ሮሜ 8:29፤ 1ኛ ጴጥ. 1:20)።

በዚህ ዓይነቱ የሥነ መለኮታዊ ዙሪያ ሁለት ጽንፎች አሉ፡ (1) በጣም የተገፋ ነጻነት፡ አንዳንዶች እንደሚሉት እግዚአብሔር የሰው ልጆችን መጻዒ ምርጫንና ድርጊት አያውቅም (ኦፕን ሲስም፣ ይህም ፍልስፍናዊ የሆነ የሂደት አስተሳሰብ ነው) እንዲሁም (2) ሉዓላዊነት በጣም ሲገፋ፣ እግዚአብሔር አንዳንዶችን ለሰማይ አንዳንዶችን ደግሞ ለሲኦል መርጧል (ሱፐራላፕሳሪያኒዝም ባለ መንታ ጠርዝ ካልቪናዊነት)። እኔ የምመርጠው መዝ. 139ን ነው!

▣ **"እናንተ"** ጴጥሮስ ለኢየሱስ ሞት እነዚህን የኢየሩሳሌም አድማጮች ተጠያቂና በደለኛ እንደሆኑ ይነግራቸዋል (ዝከ 3:13-15፤ 4:10፤ 5:30፤ 10:39፤ 13:27፣28)። እነሱ እንዲሰቀል ካደሙት ጋር አይደሉም፤ ከአይሁድ የፍርድ ችሎት፣ እሱንም ወደ ጲላጦስ ካመጡት ጋር አልነበሩም፤ እነርሱም እሱን የሰቀሉት የሮሜ ባለሥልጣናት ወይም ወታደሮች አልነበሩም፣ ነገር ግን ተጠያቂ ነበሩ፣ እኛ ተጠያቂ እንደሆንን። የሰዎች ኃጢአትና ዐመጸኝነት እንዲሞት አስገደደው!

▣ **"በመስቀል ላይ ቸንክረው"** በጥሬ ቃሉ "መጠርነቅ" (አፖስፒግኑሚ) ማለት ነው:: በአኪ. ጥቅም ላይ የዋለው እዚህ ብቻ ነው:: እሱም የሚያጣቅሰው በመስቀል ላይ መቸንከርንና ማሰርን ነው:: በ5:30 ላይ ተመሳሳይ የሆነ ሂደት "በመስቀል ላይ ሰቅለው" በሚል ተገልጿል:: የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስ በድንጋይ እንዲወገር አልፈለጉም፣ በመሳደብ እስጢፋኖስ እንደተደረገው፣ (ሐዋ. 7)፣ ነገር ግን እንዲሰቀል ፈለጉ (ሎው እና ኒዳ ይሄንን ሃፓስሎጎሜኖን ያሉት፣ ስታውሮ፣ መስቀል ከሚለው ጋር አቻ ይሆናል [ገጽ 237 የግርጌ ማስታወሻ 9]):: ይህም ምናልባት የሚያያዘው ከዘዳ. 21:23 ርግማን ጋር ነው:: ከመነሻው ይሄ ርግማን የሚያያዘው በሕዝብ መወገርና ተገቢ ቀብር ያለማግኘትን ነው፣ ነገር ግን በኢየሱስ ጊዜ ራቢዎች ከስቅለት ጋር አያያዙት:: ኢየሱስ የብኪን ሕግ ርግማን ተሸከመ፣ ለሁሉም አማኞች (ገላ. 3:13፤ ቆላ. 2:14)::

▣ **"ክፉ ሰዎች"** በጥሬው የሚያመለክተው "ሕገወጥ ሰዎችን" ነው፣ ሮማውያንን የሚያመለክት::

2:24 **"እግዚአብሔር አስነሣው"** አኪ. የሚያጸናው ሦስቱም የሥላሴ አካላት በኢየሱስ ትንሣኤ እንደተሳተፉ ነው፡ (1) መንፈስ (ሮሜ 8:11)፤ (2) ወልድ (ዮሐንስ 21:19-22፤ 10:17-18)፤ በጣም በተደጋጋሚ (3) አብ (ሐዋ. 2:24፣32፤ 3:15፣26፤ 4:10፤ 5:30፤ 10:40፤ 13:30፣33፣34፣37፤ 17:31፤ ሮሜ 6:4፣9):: የአብ ድርጊት የነበረው የኢየሱስን ሕይወት፣ ሞት፣ እና ትምህርት ማረጋገጥ ነው:: ይህም የሐዋርያት የቀድሞ ስብከት ዋነኛ ገጽታ ነበር:: ልዩ ርዕስ፡ ስብከተ ወንጌል 2:14 ተመልከት::

▣ **"የሞትን ጣር ወደ ፍጻሜ ለማምጣት"** ይህ ቃል የሚለው (1) በጥሬው፣ የወሊድ ምጥ (ጥንታዊ ግሪክ፣ ሮሜ 8:22)፤ (2) በዘይቤነቱ ከዳግም ምጽአቱ በፊት ያለውን መከራ (ማቴ. 24:8፤ ማርቆስ 13:8፤ 1ኛ ተሰ. 5:3):: የዕብራውያንን ቃላት "ወጥመድ" ወይም "ሽምቀቆ" ያንጸባርቃል በመዝ. 18:4-5 እና 116:3፣ እነሱም የብኪ. የፍርድ ዘይቤ የነበሩ (ኢሳ. 13:6-8፤ ኤር. 4:31)::

▣ **"እሱም በኃይሉ ይይዘው ዘንድ አይቻለውምና"** ዮሐንስ 20:9 የኢየሱስን ትንሣኤ ከብኪ. ትንቢት ጋር ያያይዘዋል (ዝከ ቁ. 25-28)::

▣ 2:25 **"ዳዊትም ስለ እሱ ብሏልና"** ይህ ከመዝሙር 16:8-11 የተጠቀሰ ነው:: ጴጥሮስ የሚለው መዝ. 16 መሲሐዊ ነው (ጳውሎስ በቁ. 13:36 ) እና እሱም የሚያመለክተው በቀጥታ ኢየሱስን ነው:: የኢየሱስ ትንሣኤ የመዝሙረኛው ተስፋ ነው፣ እንዲሁም የአኪ. አማኝ ተስፋ::

2:26 **"ተስፋ"** ይህ ቃል በወንጌላት ጥቅም ላይ አልዋለም፣ ነገር ግን በሐዋርያት ሥራ ጥቅም ላይ ውሏል፣ አማኞች ወደፊት እምነት ስለሚቀዳጁት ስለ ወንጌል የተስፋ ቃል (ዝከ 23:6፤ 24:15፤ 26:6፣7፤ 28:20):: እሱም ዘወትር በጳውሎስ ጽሑፎች ጥቅም ላይ ውሏል፣ ነገር ግን በብዙ መልኩ ከእግዚአብሔር ዘላለማዊ የመቤዠት እቅድ ጋር የተያያዘ ነው::

**ልዩ ርዕስ፡ ተስፋ**

ጳውሎስ ይሄንን ቃል አዘውትሮ ይጠቀማል፣ በበርካታ የተለያዩ ነገር ግን ተጓዳኝ አግባቦች:: እሱም ዘወትር የሚያያዘው የአማኞች እምነት ስለሚቀዳጀው ነው (1ኛ ጢሞ. 1:1):: ይህም ሊገለጥ የሚችለው እንደ ክብር፣ የዘላለም ሕይወት፣ የመጨረሻ መዳን፣ ዳግም ምጽዓት፣ ወዘተ ነው:: ይህ መቀዳጀት ርግጠኛ ነው፣ ነገር ግን የጊዜ ሁኔታው የወደፊትና የማይታወቅ ነው::

1. ዳግም ምጽአቱ (ገላ. 5:5፤ ኤፌ. 1:18፤ 4:4፤ ቲቶ 2:13)
2. ኢየሱስ ተስፋችን ነው (1ኛ ጢሞ. 1:1)
3. የአማኞች ለእግዚአብሔር መሰጠት (ቆላ. 1:22-23፤ 1ኛ ተሰ. 2:19)
4. ተስፋም ያረፈው በሰማይ ነው (ቆላ. 1:5)
5. አጠቃላይ ደህንነት (1ኛ ተሰ. 4:13)
6. የእግዚአብሔር ክብር (ሮሜ 5:2፤ 2ኛ ቆሮ. 3:7-12፤ ቆላ. 1:27)
7. በክርስቶስ የአሕዛብ መዳን (ቆላ. 1:27)
8. የመዳን ዋስትና (1ኛ ተሰ. 5:8-9)
9. የዘላለም ሕይወት (ቲቶ 1:2፤ 3:7)
10. የፍጥረት ሁሉ መቤዠት (ሮሜ 8:20-22)
11. የልጅነት መቀዳጀት (ሮሜ 8:23-25)
12. የእግዚአብሔር ማዕርግ (ስም) (ሮሜ 15:13)
13. ብኪ. ለአኪ. አማኞች መመሪያ (ሮሜ 15:4)
14. ለእግዚአብሔር የተሰጠ አርዕስት (ሮሜ 15:13)
15. ጳውሎስ ለአማኞች ሚመኘው (2ቆሮ 1:7)
16. ብሉይ ኪዳን ለአዲስ ኪዳን አማኞች እንደመመሪ የሚሰጠው (ሮሜ 15:4)

2:27 "ሲኦል" ይህ የግሪክ ቃል የሙታን ማቆያ ስፍራ ነው፡፡ ከዕብራይስጡ ቃል ከሲኦል ጋር አቻ ነው፣ በብኪ፡፡ በብኪ ከሕይወት በኋላ የሚገለጠው ንቁ በሆነ ሕላዌ ከወገኑ ጋር ሲሆን፣ ነገር ግን ደስታም ሆነ ኅብረት አይኖርም፡፡ የአኪ የተሻሻለው ትንቢት ብቻ ነው በጣም በግልጽ የሚያስረዳው፣ ከሕይወት በኋላን (ማለትም ሰማይና ገሃነም)፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ ሙታን የት ናቸው?**

I. ብሉይ ኪዳን

*ሀ.* ሁሉም ሰዎች ወደ ሲኦል ይወርዳሉ (ከሥርወ ቃል አኳያ ርግጠኛ ያልሆነ)፣ እሱም ሞትን የሚያመለክት ወይም መቃብርን፣ ባብዛኛው በጥበብ ሥነ ጽሑፍ እና በኢሳይያስ፡፡ በብኪ፣ ጥላማ፣ ንቁ፣ ነገር ግን ደስታ የሌለበት ሕላዌ ነበር (ኢዮብ 10፡21-22፤ 38፡17፤ *መዝ.* 107፡10፣14)፡፡

ለ. ሲኦል በባሕርዩ

1. ከእግዚአብሔር ፍርድ ጋር ይያያዛል (እሳት)፣ ዘዳ. 32፡22
2. ከፍርድ ቀን በፊት ካለው ቅጣት ጋር ይያያዛል፣ *መዝ.* 18፡4-5
3. ከአባዶን (ጥፋት) ጋር ይያያዛል፣ ነገር ግን ለእግዚአብሔር የታወቀ፣ ኢዮብ 26፡6፤ *መዝ.* 139፡8፤ አሞጽ 9፡2
4. ከ "ጉድጓድ" (ከመቃብር) ጋር ይያያዛል፣ *መዝ.* 16፡10፤ ኢሳ. 14፡15፤ ሕዝ. 31፡15-17
5. ክፉዎች ከነሕይወታቸው ወደ ሲኦል ይወርዳሉ፣ ዘሁ. 16፡30፣33፤ *መዝ.* 55፡15
6. ዘወትር ሰውኛ የሚሆነው አፈ ሰፊ በሆነ እንስሳ ነው፣ ዘሁ. 16፡30፤ ኢሳ. 5፡14፤ 14፡9፤ *ዕብ.* 2፡5
7. ሰዎች እዚያ ሼደስ ተብለው ይጠራሉ፣ (ኢሳ. 14፡9-11)

II. አዲስ ኪዳን

*ሀ.* የዕብራይስጡ ሲኦል በግሪኩ ሀዳስ ነው የሚተረጎመው (ያልታየው ዓለም)

ለ. ሃዳስ (ሲኦል) በባሕርዩ

1. ሞትን ያመላክታል፣ *ማቴ.* 16፡18
2. ከሞት ጋር ይያያዛል፣ *ራዕ.* 1፡18፤ 6፡8፤ 20፡13-14
3. ዘወትር የሚመሰለው የቋሚ ቅጣት ስፍራ ነው (ገሃነም)፣ *ማቴ.* 11፡23 (የብኪ ጥቅስ)፤ ሉቃስ 10፡15፤ 16፡23-24
4. ዘወትር የሚመሰለው ከመቃብር ጋር ነው፣ ሉቃስ 16፡23

ሐ. ይከፋፈላል (ራቢዎች)

1. የጻድቃኖች ክፍል ገነት ይባላል (በርግጥ የሰማይ ሌለኛው ስም፣ 2ኛ ቆሮ. 12፡4፤ *ራዕ.* 2፡7)፣16፡23-43
2. የክፉዎች ክፍል እንጦርጦስ ይባላል፣ 2ኛ ጴጥ. 2፡4፣ እሱም ለክፉዎች መላእክት ማቆያ ስፍራ (ዘፍ. 6፤ 1ኛ ሄኖክ)

*መ.* ገሃነም

1. የብኪን ሐረግ ያንጸባርቃል፣ "የሄኖም ልጆች ሸለቆ፣" (ከኢየሩሳሌም በስተደቡብ)፡፡ እሱም የፍንቄአውያን የእሳት ጣዖት፣ የሞሎክ አምልኮ የሚፈጸምበት የሕጻናት መሥዋዕት የሚቀርብበት ነበር፣ (2ኛ *ነገሥ.* 16፡3፤ 21፡6፤ 2ኛ ዜና. 28፡3፤ 33፡6)፣ እሱም በሌዋ. 18፡21፤ 20፡2-5 የተከለከለው
2. ኤርምያስ እሱን ከጣዖት ማምለኪያነት ወደ ያህዌ የፍርድ ስፍራ ቀይሮታል (ኤር. 7፡32፤ 19፡6-7)፡፡ እሱም የእሳት፣ የዘላለም ፍርድ ቦታ ሆኗል፣ 1ኛ ሄኖክ 90፡26-27 እና ሲብ. 1፡103፡፡
3. በኢየሱስ ጊዜ የነበሩት አይሁድ በአባቶቻቸው የሕጻናት መሥዋዕት ጣዖት አምልኮ በጣም ያፍሩ ስለነበር፣ ስፍራውን ለኢየሩሳሌም የቆሻሻ መጣያ ስፍራ አድርገውታል፡፡ አብዛኞቹ የኢየሱስ ዘይቤዎች፣ ስለ ዘላለማዊ ፍርድ የተገኙት ከዚህ ስፍራ (እሳት፣ ጭስ፣ ትሎች፣ ግማት፣ ነው፣ ማርቆስ 9፡44፣46)፡፡ ገሃነም የሚለው ቃል በኢየሱስ ብቻ ነው ጥቅም ላይ የዋለው (ከያዕቆብ 3፡6 በቀር)፡፡
4. የኢየሱስ የገሃነም አጠቃቀም
   *ሀ.* እሳት፣ *ማቴ.* 5፡22፤ 18፡9፤ *ማርቆስ* 9፡43
   ለ. ቋሚ፣ *ማርቆስ* 9፡48 (*ማቴ.* 25፡46)
   ሐ. የጥፋት ስፍራ (የነፍስም የሥጋም)፣ *ማቴ.* 10፡28
   *መ.* ከሲያል ጋር ትይዩ ነው፣ *ማቴ.* 5፡29-30፤ 18፡9
   *ሠ.* ክፉዎችን "የሲኦል ልጆች" በሚያስብል ባሕርይ፣ *ማቴ.* 23፡15
   *ረ.* የፍርድ ውሳኔ ውጤት፣ *ማቴ.* 23፡33፤ ሉቃስ 12፡5
   ሰ. የገሃነም ጽንሰ ሐሳብ የሁለተኛ ሞት ትይዩ ነው (*ራዕ.* 2፡11፤ 20፡6፣14) ወይም የእሳት ባሕር (*ማቴ.* 13፡42፣50፤ *ራዕ.* 19፡20፤ 20፡10፣14-15፤ 21፡8)፡፡ እሱም ማለት የሚቻለው የእሳት ባሕር የሰዎች ቋሚ መኖርያ ስፍራ ተደርጎ ነው (ከሲያል) እንዲሁም ክፉ መላእክት (ከእንጦርጦስ፣ 2ኛ ጴጥ. 2፡4፤ ይሁዳ 6 ወይም ጥልቁ፣ ሉቃስ 8፡31)፤ *ራዕ.* 9፡1-10፤ 20፡1፣3)፡፡
   ሸ. ለሰዎች አልተሠራም ነበር፣ ነገር ግን ለሰይጣንና ለመላእክቱ፣ *ማቴ.* 25፡41

*ሠ.* በሲያል፣ በሀዳስ፣ እና በገሃነም መካከል መነባበር ስላለ ማለት የሚቻለው፣

1. በዋነኛነት ሁሉም ሰዎች ወደ ሲዖል)ሀዳስ ይወርዳሉ
2. እዚያም ያደረጉት ሥራ (መልካም ቢሆን ክፉ) ከፍርድ ቀን በኋላ ይብስባቸዋል፣ ነገር ግን የክፉዎች ስፍራ እንደዛው ይቀራል (በዚህን ምክንያት ነው ኪጀት ሃዳስን ሲተረጉም (መቃብር) ገሃነምን (ሲዖል) ያለው።
3. የአኪ ጽሑፍ ብቻ ነው ከፍርድ ቀን በፊት ያለው እሳት ምሳሌ መሆኑን የገለጠው፣ የሉቃስ 16:19-31 (አልአዛርና ሃብታሙ ሰው)። ሲኦል ደግሞ እንደ አሁኑ ቅጣት ስፍራ ተገልጧል፣ (ዘዳ. 32:22፤ መዝ. 18:1-5)። ሆኖም፣ ማንም በምሳሌ ላይ መሠረተ እምነቱን አይጥልም።

III. በሞትና በትንሣኤ መካከል ያለ ማዕከላዊ ስፍራ

ሀ. አኪ "የነፍስን መዋቲነት" አያስተምርም፣ እሱም ከበርካታ ጥንታዊ የከሕይወት በኋላ አመለካከቶች አንዱ የሆነው።
1. የሰዎች ነፍሳት ከሥጋዊ አካል በፊት ነበር
2. የሰዎች ነፍሳት ከሥጋዊ ሞት በፊትም ሆነ በኋላ ዘላለማዊ ናቸው
3. ሥጋዊ አካል የሚታየው እንደ እስር ቤት ሲሆን፣ ሞት ደግሞ ወደ ቅድመ ተፈጥሮ ተፈትቶ መመለስ ነው

ለ. አኪ ከአካሉ ስለ ተለየ ሕይወት፣ በሞትና በትንሣኤ መካከል ስላለው ፍንጭ ይሰጣል
1. ኢየሱስ በሥጋና በነፍስ መካከል ስላለው ክፍል ተናግሯል፣ ማቴ. 10:28
2. አብርሃም አሁን ምናልባት አካል ሊኖረው ይችላል፣ ማርቆስ 12:26-27፤ ሉቃስ 16:23
3. ሙሴና ኤልያስ በመለወጥ ጊዜ ሥጋዊ አካል ነበራቸው፣ ማቴ. 17
4. ጳውሎስ የሚለው በዳግም ምጽአት በኢየሱስ ያሉት ነፍሳት በመጀመሪያ አዲሱን አካላቸውን ይይዛሉ፣ 2ኛ ተሰ. 4:13-18
5. ጳውሎስ የሚለው አማኞች አዲሱን መንፈሳዊ አካል በትንሣኤ ቀን ያገኛሉ፣ 1ኛ ቆሮ. 15:23፣52
6. ጳውሎስ የሚለው አማኞች ወደ ሲዖል አይወርዱም ነው፣ ነገር ግን በሞት ከኢየሱስ ጋር ይሆናሉ፣ 2ኛ ቆሮ. 5:6፣8፤ ፊሊጵ. 1:23። ኢየሱስ ሞትን ድል ነሥቷል፣ እናም ጻድቁን ከእሱ ጋር ወደ ሰማይ ይወስደዋል፣ 1ኛ ጴጥ. 3:18-22።

IV. ሰማይ

ሀ. ይህ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ በሦስት መልኩ ጥቅም ላይ የሚውል ነው።
1. ከመሬት በላይ ያለው ከባቢ ዓየር፣ ዘፍ. 1:1፣8፤ ኢሳ. 42:5፤ 45:18
2. ከዋክብታማ ሰማይ፣ ዘፍ. 1:14፤ ዘዳ. 10:14፤ መዝ. 148:4፤ ዕብ. 4:14፤ 7:26
3. የእግዚአብሔር ዙፋን ስፍራ፣ ዘዳ. 10:14፤ 1ኛ ነገሥ. 8:27፤ መዝ. 148:4፤ ኤፌ. 4:10፤ ዕብ. 9:24 (ሦስተኛው ሰማይ፣ 2ኛ ቆሮ. 12:2)

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ከሕይወት በኋላ ብዙም አይገልጽ። ምናልባትም የወደቀው ሰው ነገሩን የመረዳት መንገዱም ሆነ አቅሙ ስለሌለው ይሆናል፣ (1ኛ ቆሮ. 2:9)።

ሐ. ሰማይ ስፍራም (ዮሐንስ 14:2-3) እንዲሁም አካል ነው፣ (2ኛ ቆሮ. 5:6፣8)። ሰማይ ምናልባት የኤደን ገነት መመለስ ይሆናል፣ (ዘፍ. 1-2፤ ራዕይ 21-22)። ምድር ትጸዳለች ትታደሳለችም (ሐዋ. 3:21፤ ሮሜ 8:21፤ 2ኛ ጴጥ. 3:10)። የእግዚአብሔር አምሳል (ዘፍ. 1:26-27) በክርስቶስ ተመልሷል። አሁን የኤድን ገነት ወዳጃዊ ኅብረት ዳግም ተችሏል።

ሆኖም፣ ይህ ዘይቤአዊ ነው፣ (ሰማይ፣ እንደ ግዙፍ፣ ኩብ ከተማ የራዕይ 21:9-27) በጥሬ ቃሉ አይደለም። 1ኛ ቆሮንቶስ 15 የሚገልጸው የሥጋዊ አካልንና የመንፈሳዊ አካልን ልዩነት፣ እንደ ትልቅ ተክል ዘር አድርጎ ነው። ደግሞም 1ኛ ቆሮ. 2:9 (ከኢሳ. 64:4 እና 65:17 የተጠቀሰ) ታላቅ ቃል ኪዳንና ተስፋ ነው! እሱን ስናየው እሱን እንደምንመስል አውቃለሁ፣ (1ኛ ዮሐንስ 3:2)።

V. የመርጃ ምንጮች

ሀ. ዊሊየም ሄንድሪክሰን፣ *መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ከዚህ ሕይወት በኋላ*

ለ. ማውሪክ ራውሊንግስ፣ *ከሞት ደጅ ባሻገር*

▣ "**ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትሰጠውም**" ይህ መሲሐዊ አመላካች ሲሆን የሚዛመደውም ከሞት ጋር ሆኖ፣ መበስበስ ከሌለበት ተስፋ ከተሰጠው፣ ከተቀባው፣ እንዲሁም ከቅዱሱ ጋር ነው (መዝ. 49:15 እና 86:13)።

2:28 "**ከመገኘትህ ጋር ደስታን ትሞላብኛለህ**" ይህ ሐረግ የሚያሳየው፣ ግላዊ ደስታን የተሞላ ልምምድን ነው፣ ከአብ ጋር፣ (ቁ. 22-28) በሰማይ በመሲሑ ሞት የተነሣ (ኢሳ. 53:10:12)። ይሄው ተመሳሳይ የሆነ አዎንታዊ አተያይ ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረግ ግላዊ ህብረት፣ ከሕይወት በኋላ በኢዮብ 14:14-15፤ 19:25-27 ተመዝግቧል።

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 2:29-36**

**[29]ወንድሞች ሆይ፥ ስለ አባቶች አለቃ ስለ ዳዊት እንደ ሞተም እንደ ተቀበረም ለእናንተ በግልጥ እናገር ዘንድ ፍቀዱልኝ፤ መቃብሩም እስከ ዛሬ በእኛ ዘንድ ነው። [30]ነቢይ ስለ ሆነ፥ ከወገቡም ፍሬ በዙፋኑ ያስቀምጥ ዘንድ**

እግዚአብሔር መሐላ እንደ ማለለት ስለ አወቀ፥ 31ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ አስቀድሞ አይቶ፥ ነፍሱ በሲኦል እንዳልቀረች ሥጋውም መበስበስን እንዳላየ ተናገረ። [32]ይህን ኢየሱስን እግዚአብሔር አስነሣው ለዚህም ነገር እኛ ሁላችን ምስክሮች ነን፤ 33ስለዚህ በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ ብሎና የመንፈስ ቅዱስን የተስፋ ቃል ከአብ ተቀብሎ ይህን እናንተ አሁን የምታዩትንና የምትሰሙትን አፈሰሰው። [34-35]ዳዊት ወደ ሰማያት አልወጣምና፥ ነገር ግን እርሱ። ጌታ ጌታዬን። ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው [36]አለ። እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ በእርግጥ ይወቅ።

2:29-31 ለዘመናዊ ምዕራባውያን አንባቢዎች የጴጥሮስን የዚህ መዝሙር ትንታኔ ለመከተል ቀላል አይሆንም፣ ምክንያቱም እሱ የተጠቀመው ራቢያዊ የትርጓሜ አግባብን ነው የተከተለው (ይህም በዕብራውያን መጽሐሐፍም ትክክል ነው)። ጴጥሮስ ይህንን ክርክር በምኩራብ አድምጦት ይሆናል፣ ስለሚመጣው መሲሕ እንዲሁም አሁን ኢየሱስ የናዝሬቱ ተብሎ ስለሚጠቀሰው።

2:29 ጴጥሮስ የሚያሳየው መዝ. 16፣ ምንም እንኳ በአንድ በኩል ስለ ዳዊት ቢጠቅስም (በተለይም 16:10ለ)፣ ሙሉ ለሙሉ ስለ ዳዊት የሚጠቅስ ሊሆን አይችልም።

2:30 "ነቢይ ስለነበረ" አይሁድ፣ እግዚአብሔር በነቢያት በኩል እንደሚናገር ያምናሉ። ሙሴ ነቢይ ተብሎ ተጠርቷል (ዘዳ. 18:18)። የብኪ መጻሕፍት፣ ኢያሱ፣ መሳፍንት፣ 1ኛ ና 2ኛ ሳሙኤል እና 1ኛ ና 2ኛ ነገሥት በአይሁድ ሕግ "ቀደምቱ ነቢያት" በሚል ይታወቃሉ። ከመጨረሻውው ነቢይ ከሚልክያስ ሞት በኋላ ራቢዎች ራዕይ መቆሙን ይቀበላሉ። ይህ፣ አይሁድ ለቃሉ ያላቸው መረዳት ነው (ማለትም፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን የሚጽፉ) ዳዊት ነቢይ መሆኑን የሚገልጹት። ቀደም ሲል በብኪ፣ እግዚአብሔር ለሙሴ ተገልጧል (ዘፍ. 49) ያም ነቢይ ከይሁዳ ነገድ እንደሚሆን። በ2ኛ ሳሙ. 7 እግዚአብሔር የገለጠው፣ እሱ ከዳዊት የንጉሣዊ የዘር ግንድ እንደሚሆን ነው። በመዝ. 110 እግዚአብሔር ጨምሮ የገለጠው እሱ እንዲሁም ከመልከጼዴቅ ዘር እንደሚሆን ነው (ገዘ ቁ. 34-35)።

▣ "'እግዚአብሔር ለእሱ ምሎለታልና ከዘርያዎቹ መካከል በዙፋኑ እንደሚያስቀምጥ'" ይህ የአጠቃላይ ማጣቀሻዎቹ ማጠቃለያ ነው፣ የ2ኛ ሳሙ. 7:11-16፤ መዝሙር 89:3-4፤ ወይም 132:11። ይህ የሚያሳየው የእግዚአብሔር የጥንቱ የልቡ ሐሳብ በኢየሱስ የናዝሬቱ መፈጸሙን ነው። የእሱ ሞትና ትንሣኤው ሁለተኛ እቅዶች አይደሉም፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ቀድመ የተወሰነ፣ ከፍጥረት በፊት የነበረ የመዋጀት እቅድ ነው (ኤፌ. 2:11-3:13)።

2:31 "ክርስቶስ" ይህ የግሪኩ ትርጉም "መሲሕ" ማለት ነው፣ ወይም በጥሬው "የተቀባው።" ኢየሱስ የእስራኤል ንጉሥ የዳዊት ልጅ ብቻ አልነበረም፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጅ እናም በሰማያዊ ዙፋን የተቀመጠ (መዝ. 110)።

▣ "እሱም በሲዖል አልተተወም፣ ወይም ሥጋው መበስበስን አላየም" ይህ የብኪ ጥቅስ ሆኖ በ1995 አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ ላይ ተወስዷል። እሱም በግልጽ የሚያሳየው መዝ. 16ን ነው።

2:32-33 "ኢየሱስ... እግዚአብሔር... መንፈስ" ምንም እንኳ "ሥላሴ" የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ባይጠቀስም፣ የሦስቱ (አምላክ) አጽንዖት የተሰጠው (1) የኢየሱስ መለኮትነት እና (2) የመንፈስ አካልነት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ይሄንን ጽንሰ ሐሳብ የሚያስተላልፈው ሦስቱን የሥላሴ አካላት በአንድ ጽሑፍ በመጥቀስ ነው (ሐዋ. 2:32-33፤ ማቴ. 28:19፤ 1ኛ ቆሮ. 12:4-6፤ 2ኛ ቆሮ. 1:21-22፤ 13:14፤ ኤፌ. 4:4-6 እና 1ኛ ጴጥ. 1:2)።

**ልዩ ርዕስ፡ ሥላሴ**

የሦስቱን የሥላሴ አካላት ተግባር አስተውል። "ሥላሴ" የሚለው ቃል በመጀመሪያ የተቀመረው በቱርቱሊያን ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል አይደለም፣ ነገር ግን ጽንሰ-ሐሳቡ ተሰራጭቷል።

1. ወንጌላት
   - ሀ. ማቴዎስ 3:16-17፤ 28:19 (እና ትይዩዎች)
   - ለ. ዮሐንስ 14:26
2. ሐዋ. -ሐዋ. 2:32-33፣ 38-39
3. ጳውሎስ
   - ሀ. ሮሜ. 1:4-5፤ 5:1፣5፤ 8:1-4፣ 8-10
   - ለ. 1ኛ ቆሮንቶስ 2:8-10፤ 12:4-6
   - ሐ. 2ኛ ቆሮንቶስ 1:21፤ 13:14
   - መ. ገላትያ 4:4-6
   - ሠ. ኤፌሶን 1:3-14፣17፤ 2:18፤ 3:14-17፤ 4:4-6
   - ረ. 1ኛ ተሰሎንቄ 1:2-5
   - ሰ. 2ኛ ተሰሎንቄ 2:13

ሸ. ቲቶ 3፡4-6
4. ጴጥሮስ - 1ኛ ጴጥሮስ 1፡2
5. ይሁዳ - ቁ. 20-21

በብኪ. ተጠቁሟል

1. ለእግዚአብሔር የብዙ ቁጥር መጠቀም
   ሀ. ኤሎሄም የሚለው ስም የብዙ ነው፣ ነገር ግን ለእግዚአብሔር ጥቅም ላይ ሲውል የነጠላ ግሥ ይኖረዋል
   ለ. "እኛ" በዘፍጥረት 1፡26-27፤ 3፡22፤ 11፡7
   ሐ. "አንድ" በሼማ የዘዳግም6፡4 የብዙ ነው (እንደ ዘፍ. 2፡24፤ ሕዝ. 37፡17)
2. የእግዚአብሔር መልአክ እንደሚታይ የመለኮት ወኪል
   ሀ. ዘፍጥረት 16፡7-13፤ 22፡11-15፤ 31፡11፣13፤ 48፡15-16
   ለ. ዘጸአት 3፡2፣4፤ 13፡21፤ 14፡19
   ሐ. መሳፍንት 2፡1፤ 6፡22-23፤ 13፡3-22
   መ. ዘካርያስ 3፡1-2
3. እግዚአብሔርና መንፈስ ይለያያሉ፣ ዘፍጥረት 1፡1-2፤ መዝሙር 104፡30፤ ኢሳ. 63፡9-11፤ ሕዝ. 37፡13-14
4. እግዚአብሔር (ያህዌ) እና መሲሕ (አዶናይ) ይለያያሉ፣ መዝሙር 45፡6-7፤ 110፡1፤ ዘካርያስ 2፡8-11፤ 10፡9-12
5. መሲሕ እና መንፈስ ይለያያሉ፣ ዘካርያስ 12፡10
6. ሦስቱም ተጠቅሰዋል በኢሳ. 48፡16፤ 61፡1

የኢየሱስ መለኮትነት እና የመንፈስ አካላዊነት ለቀድሞዎቹ ጥብቅ፣ አሀዳዊ (አንድ አምላክ) አማኞች ችግር ፈጥሮባቸዋል፡

1. ቴርቱሊያን - ወልድን ወደ አብ ያስጠጋዋል
2. ኦሪጅን - የወልድንና የመንፈስን መለኮትነት ያስጠጋዋል
3. አሪዮስ - የወልድንና የመንፈስን መለኮትነት ክዷል
4. ሞናርኪያዊነት - በእግዚአብሔር ተተኪአዊ መገለጥ ያምናሉ

ሥላሴ ከታሪክ አንጻር እየተስፋ የመጣ ቀመር ነው፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይዘት መነሻ

1. የኢየሱስ ፍጹም መለኮትነት፣ ከአብ ጋር እኩልነቱ በኒቅያ ጉባኤ በ325 ዓ.ም ጸንቷል
2. የመንፈስ ፍጹም አካላዊነት ከአብ እና ከወልድ ጋር እኩል መሆኑ በቁስጥንጥንያ ጉባኤ (በ381 ዓ.ም) ጸንቷል
3. የሥላሴ ሙሉ የሃይማኖት መግለጫ በአውግስጢኖስ ጽሑፍ ስለ ሥላሴ ላይ ተገልጧል።

እዚህ ጋ በርግጥ ምሥጢር አለ። ነገር ግን አኪ. የሚመስለው አንድ መለኮት ሕላዌ በሦስት ዘላለማዊ በሆኑ አካላት መገለጡን የሚያጸና ይመስላል።

2፡32 **"ይሄንን ኢየሱስን እግዚአብሔር ዳግም አስነሣው"** በ2፡24 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

▣ **"ለዚህም እኛ ሁላችን ምስክሮች ነን"** ይህ የሚያመለክተው የተነሣውን ክርስቶስን ለተመለከቱት ነው። ከፖል ባርኔት ጋ የሚገኘውን ከትንሣኤ በኋላ ያለው መልክ የሚለውን መግለጫ ተመልከት፣ ኢየሱስና የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አነሳሥ፣ ገጽ 185፣ 1፡3 ላይ (ገጽ 9)።

2፡33 **"በእግዚአብሔር ቀኝ ዘንድ"** ይህ የሰው አካላዊ የሆነ ዘይቤ ሲሆን የኃይልን ስፍራ፣ ሥልጣንን፣ እና ምልጃን የሚያሳይ ሆኖ፣ (1ኛ ዮሐንስ 2፡1)፣ እሱም ከመዝ. 110፡1 የተወሰደ ነው፣ (በአኪ. ከሌሎቹ መዝሙራት ሁሉ በእጅጉን የተጠቀሰ ነው) ወይም መዝ. 118፡16። እግዚአብሔር ዘላለማዊ መንፈስ ነው፣ በሁሉም ሥጋዊና መንፈሳዊ ፍጥረት ላይ የሚገኝ። ሰዎች የግድ በምድር የተወሰነውን ቋንቋ መጠቀም ይኖርባቸዋል፣ እንዲሁም ጽንሰ ሐሳቦችን፣ ስለ እሱ ለመናገር፣ ነገር ግን እነሱ ሁሉ (1) ተቃርኖዎች (2) ተምሳሌቶች (3) ዘይቤዎች ናቸው። "አብ" የሚለው ስም እንኳ፣ እግዚአብሔርን ለመግለጽ ወይም "ወልድ" ኢየሱስን ለመግለጥ ዘይቤአዊ ናቸው። ሁሉም ዘይቤዎች በአንድ ነጥብ ላይ ይከፋፈላሉ። እነሱም የሚያሳዩት ማዕከላዊውን እውነት ወይም ስለ መለኮት ያለውን ጽንሰ-ሐሳብ ነው። ቃላታዊ ከመሆን ተጠንቀቅ! በርግጥ ወደ ሰማይ ስትደርስ ሽማግሌ ሰው፣ ወጣት ሰው፣ ነጭ ወፍ አገኛለሁ ብለህ መጠበቅ አይኖርብህም።

**ልዩ ርዕስ፡ አመሳስዮሽ አገላለፅ**

I. እንዲህ አይነቱ የማመሳሰል ቋንቋ በብሉይ ኪዳን በጣም የታወቀ ነበር፡፡ (የተወሰኑ ምሳሌዎች)
   ሀ. የሰውነት ክፍሎች
      1. አይኖች፡ ዘፍ 1፡4,31፣ 6፡8 ዘፀ 33፡17፣ ዘኅ 14፡14፣ ዘዳ 11፡12 ዘካ 4፡10
      2. እጆች ፡ ዘፀ 15፡17፣ ዘኅ 11፡23፣ ዘዳ 2፡5

3. ክንድ፡ ዘፀ 6፡6፣ 15፡16 ዘኀ 11፡23፣ ዘዳ 4፡34፣ 5፡15
4. ጆሮዎች፡ ዘኀ11፡18፣ 1ሳሙ 8፡21፤ 2ነገ 19፡16፣ መዝ 5፡1፣ 10፡17፣ 18፡6
5. ፊት፡ ዘፀ 32፡30፣ 33፡11 ዘኀ 6፡25፣ ዘዳ 34፡10፣ መዝ 114፡7
6. ጣቶች፡ ዘፀ 8፡19፣ 31፡18፣ ዘዳ 9፡10፣ መዝ 8፡3
7. ድምፅ፡ ዘፍ 3፡8,10፣ ዘፀ 15፡26፣ ዘዳ 26፡17፣ 27፡10
8. እግር፡ ዘፀ 24፡10፣ ሕዝ 43፡7
9. የሰው ዓይነት፡ ዘፀ 24፡9፣ -11፣ መዝ 47፣ ኢሳ 6፡1፣ ሕዝ 1፡26
10. የጌታ መልዓክ፡ ዘፍ 16፡7-13፣ 22፡11-15፣ 31፡11፣ 48፡15-16፣ ዘፀ 3፡4,13-21፣ 14፡19፣ መሳ 2፡1፣ 6፡22-23፣ 13፡3-22

ለ. አካላዊ እንቅስቃሴ
1. ፍጥረትን ለመፍጠር በቋንቋ መናገሩ ዘፍ 1፡3,6,9,11,14,20,24,26
2. መራመዱ በኤደን ገነት ውስጥ ዘፍ 3፡8,18፣ 18፡33፣ ዕንባቆም 3፡15
3. የኖህን መርከብ መዝጋቱ ዘፍ 7፡16
4. መስዋዕትን መቀበሉ (ማሽተቱ) ዘፍ 8፡21፣ ሌዋ 26፡31፣ አሞፅ 5፡21
5. መውረዱ ዘፍ 11፡5፣ 18፡51፣ ዘፀ 3፡8፣ 19፡11,18,20
6. ሙሴን መቅበሩ ዘዳ 34፡6

ሐ. ሰዋዊ ስሜቶች
1. ማዘኑ/መፀፀቱ ዘፍ 6፡6,7፣ ዘፀ 32፡14 መሳ 2፡18፣ 1ሳሙ 15፡29,35፣ አሞፅ 7፡3-6
2. ቁጣ ዘፀ 4፡14፣ 15፡7፣ ዘኀ 11፡10፣ 12፡9፣ 22፡22፣ 25፡3,4፣ 32፡10,13,14፣ ዘዳ 6፡5፣ 7፡4፣ 29፡20
3. መቅናቱ ዘፀ 20፡5፣ 34፡14 ዘዳ 4፡24፣ 5፡9፣ 6፡15 32፡16፣21፣ ኢያሱ 24፡19
4. መፀየፍ ሌዋ 20፡24፣ 26፡30፣ ዘዳ 32፡19

መ. የቤተሰብ ቃላቶችን
1. አባት
   ሀ. የእስራኤል ዘፀ 4፡22፣ ዘዳ 14፡1፣ 39፡5
   ለ. ለንጉሡ 2ሳሙ 7፡11-16፣ መዝ 2፡7
   ሐ. የአባትን ተግባር በማከናወን ዘዳ 1፡31፣ 8፡5፣ 32፡1፣ መዝ 27፡10፣ ምሳ 3፡12፣ ኤር 3፡4,22፣ 31፡20፣ ሆሴዕ 11፡1-4፣ ሚል 3፡17
2. ቤተሰብ/ወላጅ ሆሴ 11፡1-4
3. እናት መዝ 7፡10 (እንደተንከባካቢ እናት)
4. እንደታማኝ አፍቃሪ ወጣት ሆስ 1-3

II. እንደ እነዚህ አይነት ቋንቋዎችን የተጠቀመበት ምክንያት፡
ሀ. ለሰው ልጅ ራሱን መግለጥ በጣም አስፈላጊ በመሆኑ፡፡ እግዚአብሔር እንደ ወንድ የተጠቀሰበት ምክንያትም ምሳሌያዊ ነው፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር መንፈስ ነው፡፡
ለ. እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ትርጉም ያለውን ቋንቋ ተጠቅሞ ነው ለወደቀው የሰው ዘር ራሱን ያስተዋወቀው፡፡
ሐ. በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ እግዚአብሔር በየትኛውም ዓይነት ቅርፅና መልክ አይወሰንም (ዘፀ 20 ዘዳ 5)
መ. ከሁሉ በላይ በትክክል የእርሱ ማሳያ ሰው የሆነው ኢየሱስ ነው፡፡ እግዚአብሔር በእርሱ በኩል የሚጨበጥና የሚዳሰስ ሆነ፡፡ (1ዮሐ 1፡1-3
የእግዚአብሔር መልዕክት የእግዚአብሔር ቃል ሆነ (ዮሐ 1፡1-18)

▣ "**የመንፈስ ቅዱስን ተስፋ**" ብኪ ስለ አዲሱ መንፈስ መር ጽድቅ ያለበት ዘመን ተስፋ የሰጠው አለ፣ እሱም በመሲሑ ሥራ በኩል የሚሆን።
1. ዮሐንስ 7፡39፣ አዲሱ ዘመን ደርሷል
2. ገላ. 3፡14፣ የአብርሃም በረከት (ዘፍ. 12፡3) አሁን ለመላው ዓለም ይገኛል
3. ኤፌ. 1፡13፣ አማኞች በዚህ ዘመን በመንፈስ ታትመዋል።

▣ "**እናንተ ያያችሁት የሰማችሁትን**" ይህ ቀጣይነት ያለው አጽንዖት በዚህ ስብከት ላይ የዓይን ምስክር በሆኑት በእነዚህ አድማጮች ላይ ነው (ቁ. 14፣22፣32፣33፣36)። ጴጥሮስ የሚናገረው እውነት መሆኑን ያውቃሉ፣ ምክንያቱም እዚያ ነበሩና። ሕግ አዋቂዎች ይሄንን አንደኛ ደረጃ ማስረጃ ይሉታል።

2፡34 "'**ጌታ ጌታዬን አለው**'" ይህ ከመዝሙር 110፡1 የተጠቀሰ ነው። ኢየሱስ በማቴ. 22፡41-46 ተጠቅሞበታል። በአኪ የሚያሳየው የመንግሥቱን ሁለትዮሽ ገጽታ ነው፤ ኢየሱስ ቀድሞውኑ በእግዚአብሔር ቀኝ ነው፣ ነገር ግን ጠላቶቹ ገና የእግሩ መረገጫ አልሆኑም። ልዩ ርዕስ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት 1፡3 ላይ ተመልከት።

2:36 "የእስራኤል ቤት ሁሉ" ይህ የሚያመለክተው የአይሁድን አመራርና ሕዝቡን ሲሆን፣ እነሱም ጴጥሮስ የሚናገራቸው ናቸው። እሱ የሚለው የብኪ ትንቢት በናዝሬቱ ኢየሱስ መፈጸሙንና መደምደሙን ነው። ልዩ ርዕስ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት 1:3 ላይ ተመልከት።

▣

**አአመመቅ** **"በርግጥ ይታወቅ"**
**አኪጀት** **"አስረግጦ ይታወቅ"**
**አየተመት** **"ከርግጠኝነት የታወቀ"**
**አእት** **"በትክክል ይታወቅ"**
**አኢመቅ** **"ርግጠኛ በመሆን"**

ይህ የሚያመላክተው ሁለት የግሪክ ቃላትን ሲሆን፣ ተውሳከ ግሡ አፋሉስ፣ ፍችውም "በአስተማማኝ መጣበቅ" ነው፣ (በዘይቤአዊነት በርግጠኝነት፣ ዝከ 16:23) እና የአሁን የድርጊት ተተኪሪ ግኖስኮ፣ "ማወቅ" ነው። እነዚህ የኢየሱስ የመጨረሻው ሳምንት የሞቱ፣ እና የትንሣኤው የዓይን ምስክሮች፣ በጴጥሮስ ቃል ላይ ምንም ዓይነት ጥርጣሬ አይኖራቸውም።

▣ **"ጌታና ክርስቶስ"** "ጌታ" የሚለው ቃል (ኩሪዮስ) በአጠቃላይ መልኩ ወይም በተናጠላዊ የሥነመለኮት መልኩ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል። እሱም ሊሆን የሚችለው፣ "ጌታው፣" "ጌታዬ፣" "ጌታ፣" "ባለቤት፣" "ባል፣" ወይም "ፍጹም አምላክ-ሰው" ነው። በብኪ የዚህ ቃል አጠቃቀም (አዶናይ) የመጣው፣ ከአይሁድ ይሄንን የኪዳን ቃል ለመጥራት ፍቃደኛ ካለመሆን ነው፣ እሱን ለእግዚአብሔር፣ ያህዌ፣ ምክንያታዊ ቅርጽ፣ የዕብራይስጥ ግሥ "የመሆን ግሥ" (ዘጸ. 3:14)። እነርሱም ትእዛዙን ላለመስበር ፈርተው ነው፣ "የጌታ የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ" የሚለውን፣ (ዘጸ. 20:7፣ ዘዳ. 5:11)። እነሱ ያሰቡት፣ ካልጠሩት፣ በከንቱ እንዳላሉት አድርገው ነው። ስለዚህ፣ የዕብራይስጡን ቃል አዶናይ ቀየሩት፣ እሱም ተመሳሳይ ፍች ያለውን የግሪክ ቃል ኩሪዮስ (ጌታ)። የአኪ ጸሐፍት ይሄንን ቃል የሚጠቀሙት የክርስቶስን ፍጹም ጌትነት ለመግለጽ ነው። "ኢየሱስ ጌታ ነው" የሚለው ሐረግ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የአደባባይ የእምነት መግለጫና የጥምቀት ማስታወቂያ ነው (ሮሜ 10:9-13፤ 1ኛ ቆሮ. 12:3፤ ፊሊጵ. 2:11)።

"ክርስቶስ" የግሪክ አቻ የዕብራይስጥ ቃል መሲሕ ሲሆን፣ ፍችውም "የተቀባው" ማለት ነው (ዝከ 2:31፣36፤ 3:18፣20፤ 4:26፤ 5:42፤ 8:5፤ 9:22፤ 17:3፤ 18:5፣28፤ 26:23)። እሱም የሚያመላክተው "በእግዚአብሔር የተጠራውና ለልዩ ተግባር የተዘጋጀው ነው።" በብኪ ሦስት ዓይነት የመሪነት ክፍሎች፡ ካህናት፣ ነገሥታት፣ እና ነቢያት፣ ይቀቡ ነበር። ኢየሱስ እነዚህን ሦስት ሹመቶች ፈጽሟቸዋል (ዕብ. 1:2-3)።

እነዚህን ሁለቱን የብኪ ማዕርጎች ለናዝሬቱ ኢየሱስ በመጠቀም፣ ሉቃስ ሁለቱንም መለኮትነቱንም ይገልጻል (ፊሊጵ. 2:6-11) እና የእሱ መሲሕነት (ሉቃስ 2:11)። ይሄ በርግጥ የሚያሳየው የአዋጁን ደረጃ (የስብከተ ወንጌሉን)፣ በሐዋ. ያለውን ሌለኛውን ስብከት ነው!

▣ **"ይህም ኢየሱስ እናንተ የሰቀላችሁት"** ጴጥሮስ እነዚህን የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች የሚከሰው በአየሱስ ሞት ተጠያቂነት ነው። ሁሉም የወደቀ ሰው በዚህ ኃጢአት ላይ እኩል ተጠያቂነት አለበት። በ2:23 ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

▣ **"ይህ ኢየሱስ"** "ይህ ኢየሱስ" የሚለው ስያሜ(ዝከ 2:23፣32፣36) የጴጥሮስን አዋጅ፣ የታሪካዊው ኢየሱስ፣ ወደ የተነሣውና ከፍ ወዳለው ክርስቶስ ነው። ሁለቱም ጽንሰ ሐሳቦች ርግጠኛና እውነት ናቸው። ምንም ዓይነት መጽቃፍ ቅዱሳዊ ልዩነት በጥንቱ ኢየሱስና በእምነቱ ኢየሱስ መካከል የለም!

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 2:37፡42**

**37ይህንም በሰሙ ጊዜ ልባቸው ተነካ፥ ጴጥሮስንና ሌሎችንም ሐዋርያት። ወንድሞች ሆይ፥ ምን እናድርግ? አሉአቸው። 38ጴጥሮስም፦ ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ። 39የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና አላቸው። 40በብዙ ሌላ ቃልም መሰከረና። ከዚህ ጠማማ ትውልድ ዳኑ ብሎ መከራቸው። 41ቃሉንም የተቀበሉ ተጠመቁ፥ በዚያም ቀን ሦስት ሺህ የሚያህል ነፍስ ተጨመሩ፤ 42በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቍረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር።**

2:37 "እነሱም ልባቸው ተነካ" ይህ የግሪክ ቃል ካታ እና ኑሶ ነው። ሥርወ ቃሉ በዮሐንስ 19:34 ጥቅም ላይ ውሏል፣ ስለ ኢየሱስ በመስቀል ላይ መቸንከር። የጴጥሮስ ስብከት እነዚህን አድማጮች ከወንጌል እውነት ጋር ቸንክሯቸዋል። ይህ በግልጽ የሚያመላክተው የመንፈስ ቅዱስን ክስ (ወቀሳ) እሱም ደህንነትን የሚከተለውን ነው፣ (ዮሐንስ 16:8-11)።

2:38 "ንስሐ" ይህ የድርጊት የአሁን ተተኪሪ ሲሆን፣ የሚለውም ዋነኛ ውሳኔ መወሰን ነው። የዕብራይስጡ ቃል ለንስሐ የሚሆነው የድርጊት ለውጥ ነው። የግሪክ ቃል ደግሞ የአስተሳሰብ ለውጥ ነው። ንስሐ ለመለወጥ ፍቃደኝነት ነው። እሱም የአጠቃላይ የኃጢአት መቋረጥ ማለት አይደለም፣ ነገር ግን እግዚአብሔርን የማስደሰት ፍላጎት ነው፣ ራስን ሳይሆን። እንደ ወደቀ ስብዕና፣ የምንኖረው ለራሳችን ነው፣ ነገር ግን እንደ አማኝ፣ የምንኖረው ለእግዚአብሔር ነው! ንስሐና እምነት ለመዳን የእግዚአብሔር ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው (ማርቆስ 1:15፤ ሐዋ. 3:16፣ 19፤ 20:21)። ኢየሱስ ብሏል፣ "ንስሐ ካልገባችሁ ሁላችሁም ትጠፋላችሁ" (ሉቃስ 13:3፣5)። ንስሐ የእግዚአብሔር ፍቃድ ነው፣ ለወደቀው ሰው (2ኛ ጴጥ. 3:9፣ ሕዝ. 18:23፣ 30፣32)። የእግዚአብሔር ሉዓላዊነትና የሰው ነጻ ፍቃድ ምሥጢር

በግልጽ የሚታየው በንስሐ አስፈላጊነት ነው፣ ለደህንነት። ሆኖም፣ አያዎ (ፓራዶክስ) ወይም ተቃራኒ ጥንድ የሚሆነው እሱ ደግሞ የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑ ነው (5:31፤ 11:18 እና 2ኛ ጢሞ. 2:25)። በመጽሐፍ ቅዱስ አቀራረብ፣ ዘወትር ክርክር አለ፣ በእግዚአብሔር የመነሻ ጸጋ እና በሰዎች ኪዳናዊ ምላሽ አስፈላጊነት ላይ። አዲስ ኪዳን እንደ ብሉይ ኪዳን የ "ከ-ሆነ ወዲያ" አወቃቀር አለው። በርካታ ቃላት በአኪ ጥቅም ላይ ውለዋል፣ ከንስሐ ጽንሰ ሐሳብ ጋር የሚያያዙ።

ገላጭ የሆነው ጽሑፍ 2ኛ ቆሮ. 7:8-11 ነው። ቃላቶቹ (1) "ሀዘን" (ሉፒ፣ ቁ. 8፣9፣10፣11)፣ እሱም ከግብረገብ አንጻር ገለልተኛ ነው፤ (2) "መጸጸት" (ሚታሜሎማይ፣ ቁ. 8፣10)፣ "ባለፈው ድርጊት ማዘን" ማለት ነው። እሱም ስለ ይሁዳ ጥቅም ላይ ውሏል (ማቴ. 27:3) እና ኢሳው (ዕብ. 12:16-17)፤ እና (3) "ንስሐ መግባት" (ሜታኖኒኦ፣ ቁ. 9፣10፣11)፣ እሱም የአስተሳሰብ ለውጥ ነው፣ አዲስ ባሕርይ፣ አዲስ የሕይወት አቅጣጫ። ንስሐን ባሕርይ የሚያደርገው ሀዘን አይደለም፣ ነገር ግን ለመለወጥ ፍቃደኝነት ነው፣ የእግዚአብሔርን ፍቃድ ማጽናት። እዚህ ልዩ ርዕስ ይገኛል፣ ስለ "ንስሐ" በ2ኛ ቆሮንቶስ 7 ላይ ከጻፍኩት ሐተታ።

---

**ልዩ ርዕስ፡ ንስሐ**

ንስሐ (ከእምነት ጋር) ኪዳናዊ መስፈርት ነው ለሁለቱም፣ ለብሉይ ኪዳን (ናካም፣ 1ኛ ነገሥ. 8:47፤ ሹብ፣ 1ኛ ነገሥ. 8:48፤ ሕዝ. 14:6፤ 18:30፤ ኢዩኤል 2:12-13፤ ዘካ. 1:3-4) እና አዲስ ኪዳን።

1. ዮሐንስ መጥምቁ (ማቴ. 3:2፤ ማርቆስ 1:4፤ ሉቃስ 3:3፣8)
2. ኢየሱስ (ማቴ. 4:17፤ ማርቆስ 1:15፤ 2:17፤ ሉቃስ 5:32፤ 13:3፣5፤ 15:7፤ 17፣3)
3. ጴጥሮስ (ሐዋ. 2:38፤ 3:19፤ 8:22፤ 11:18፤ 2ኛ ጴጥ. 3:9)
4. ጳውሎስ (ሐዋ. 13:24፤ 17:30፤ 20:21፤ 26:20፤ ሮሜ 2:4፤ 2ኛ ቆሮ. 2:9-10)

ነገር ግን ንስሐ ምንድነው? ሀዘን ነውን? ከሀጢአት መቋረጥ ነውን? በአኪ የተሻለ ምዕራፍ የሚሆነው፣ የዚህን ጽንሰ ሐሳብ የተለያዩ ፍችዎች ለመረዳት 2ኛ ቆሮንቶስ 7:8-11፣ ሦስት ተያያዥ የሆኑ፣ ነገር ግን የተለያዩ የሆኑ ቃላት ጥቅም ላይ ውለዋል።

1. "ሀዘን" (ሉፒ፣ ዝከ ቁ. 8 [ሁለት ጊዜ]፣ 9 [ሦስት ጊዜ]፣ 10 [ሁለት ጊዜ] 11)። እሱ የሚለው ሀዘን ወይም መሠቃየት ከሥነ መለኮት አኳያ ገለልተኛ ፍች ይኖራቸዋል።
2. "ንስሐ" (ሜታኖኢኦ፣ ዝከ ቁ. 9፣10)። እሱም የ "በኋላ" እና "ሐሳብ" ድብልቅ ነው፣ እሱም የሚያመለክተው አዲስ አስተሳሰብ ነው፣ አዲስ የአስተሳሰብ መንገድ፣ ስለ ሕይወትና እግዚአብሔር አዲስ አቋም መያዝ ነው። ይህ ትክክለኛው ንስሐ ነው።
3. "መጸጸት" (ሜታሚሎማይ፣ ዝከ ቁ. 8 [ሁለት ጊዜ]፣ 10)። እሱም የ "በኋላ" እና "ጥንቃቄ" ድብልቅ ነው። እሱም ስለ ይሁዳ በማቴ. 27:3 እና ኤሳው በዕብ. 12:16-17። እሱም የሚያመላክተው በተፈጠረው ውጤት ማዘን እንጂ በድርጊቱ አይደለም።

ንስሐና እምነት አስፈላጊ የሆኑ የኪዳን ድርጊቶች ናቸው (ማርቆስ 1:15፤ ሐዋ. 2:38፣41፤ 3:16፣19፤ 20:21)። እግዚአብሔር ንስሐን እንዲሰጥ የሚያመላክቱ ጽሑፎች አሉ (ሐዋ. 5:31፤ 11:18፤ 2ኛ ጢሞ. 2:25)። ነገር ግን አብዛኞቹ ጽሑፎች ይሄንን የሚመለከቱት እንደ አስፈላጊ የሰው ኪዳናዊ ምላሽ አድርገው ነው፣ ለእግዚአብሔር ነጻ የመዳን ስጦታ (የተመለሰ ቤተሰባዊ ህብረት፣ ሉቃስ 15:20-24)።

የሁለቱም የዕብራይስጥም ሆነ የግሪክ ቃላት ፍችዎች ሙሉውን የንስሐ ፍች ማካተትን ይሻሉ። ዕብራይስጡ "የድርጊት ለውጥን" ይሻል፣ የግሪኩ ደግሞ "የአስተሳሰብ ለውጥን" ሲፈልግ። የዳነ ሰው አዲስ አስተሳሰብና ልብ ይቀበላል። እሱም የሚያስበው በተለይ ነው፣ እንዲሁም የሚኖረው በተለይ ነው። "ለእኔ ምን በሱ ውስጥ ምን አለው?" ከማለት ፈንታ ጥያቄው አሁን፣ "የእግዚአብሔር ፍቃድ ምንድነው?" የሚል ይሆናል። ንስሐ የስሜት ጉዳይ አይደለም፣ ቆይቶ የሚደበዝዝ፣ ወይም ፈጽሞ ኃጢአት የለሽ መሆን አይደለም፣ ነገር ግን አዲስ ዓይነት ግንኙነት ነው፣ ከቅዱሱ ጋር፣ እሱም አማኙም ወደ ተሻለ ቅዱስነት የሚለውጠው።

---

▣ **"ተጠመቁ"** ይህ የተጠናቀቀ ተገብሮ አመላካች ነው (አአመመቅ፣ አኪጀት)።

---

**ልዩ ርዕስ፡ ጥምቀት**

ኩርቲስ ቫዩጋን፣ አስደናቂ የሆነ የግርጌ ማስታወሻ አለው፣ ገጽ 28 ላይ።

"የግሪኩ ቃል ለ 'ተጠመቁ' ሦስተኛ መደብ አስገዳጅ ነው፤ ለ 'ንስሐ' ደግሞ ሁለተኛ መደብ አስገዳጅ ነው። ይህም ለውጥ፣ ማለትም ከተሻለው ቀጥተኛ ከሁለተኛ መደብ ትዕዛዝ አንቀጽ ወደ አነስተኛ ቀጥተኛ ወደ ሆነው ሦስተኛ መደብ 'ተጠመቁ' መደረጉ የሚያመለክተው የጴጥሮስን ቀዳሚ መሠረታዊ ጥያቄ ንስሐ መሆኑን ነው።"

ይህን የዮሐንስ መጥምቁን የስብከት አጽንኦት (ማቴ. 3:2) እና ኢየሱስ (ማቴ. 4:17) ይከተላል። ንስሐ መንፈሳዊ ቁልፍ ነገር እንዲሁም ጥምቀት የመንፈሳዊ መለወጥ ውጫዊ መግለጫ ይመስላል። አዲስ ኪዳን ስለ አልተጠመቁ አማኞች ምንም የሚያውቀው የለም! ለቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን ጥምቀት የነበረው እምነትን በይፋ መግለጫ ነበር። እሱም በሕዝብ ፊት በክርስቶስ ያለን እምነት መግለጫ መድረክ ነበር፣ የደህንነት መሣርያ

ሳይሆን! ማስታወስ የሚያስፈልገው በጴጥሮስ ሁለተኛው ስብከት ጥምቀት አለመታዘዙን ነው፣ ንስሐ እንጂ (ዝክ 3፡19፤ ሉቃስ 24፡17)። ጥምቀት ኢየሱስ የተቀመጠ ምሳሌ ነው (ማቴ. 3፡13-18)። ጥምቀት በኢየሱስ የታዘዘ ነው (ማቴ. 28፡19)። ዘመናዊው ጥያቄ በጥምቀት ለደህንነት አስፈላጊነት ላይ በአዲስ ኪዳን አልተመለከተም፤ አማኞች ሁሉ እንዲጠመቁ ይጠበቃሉ። ሆኖም፣ መጠበቅ የሚገባን ድርጊታዊ ከሆነ መንፈሳዊነት (ቅዱሳን ምሥጢራት) ነው! መዳን የእምነት ጉዳይ ነው እንጂ የትክክለኛ ቦታ፣ የትክክለኛ ቃላት፣ የትክክለኛ ያምልኮ ሥርዓት ጉዳይ አይደለም!

▣ **"በኢየሱስ ስም"** ይህ የዕብራይስጥ ዘይቤ ሲሆን፣ (በኢዩኤል 2፡32 የተንጸባረቀ) የሚያመላክተውም የኢየሱስን አካል ወይም ባሕርይ ነው። እሱም ምናልባት የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የጥምቀት መግለጫ ሊሆን ይችላል፣ በተጠማቂው የሚገለፀው፣ "እኔ፣ ኢየሱስ ጌታ መሆኑን አምናለሁ" (ሮሜ 10፡9-13)። ይህ ሁለቱም፣ ሥነመለኮታዊ ማጽኛና በግል የማመን ማጽኛ ነው። በታላቁ ተልእኮ፣ በማቴ. 28፡19-20 የሦስቱ ስም የጥምቀት መግለጫ ሆኗል። አሁምን መጠበቅ የሚኖርብን ድርጊታዊ ከሆነ ቅዱሳነ ምሥጢራዊነት ነው! ርዕሱ ወይም መግለጫው ቁልፉ ነገር አይደለም፣ ነገር ግን የሚጠመቀው ሰው ልብ እንጂ።

▣

**አአመመቅ፣ አኢመቅ**

| | |
|---|---|
| **አኢት** | **"ለኃጢአታችሁ ሥርየት"** |
| **አኪጀት** | **"ለኃጢአታችሁ ምሕረት"** |
| **አየተመት** | **"ስለሆነም ኃጢአታችሁ ይቅር ይባል ዘንድ"** |
| **አእት** | **"ስለሆነም ኃጢአታችሁ ይቅር እንዲባል"** |

ሥነ መለኮታዊው ጥያቄ "ለ" (ኢስ) ይከናወናል? ነው። ምሕረት "ከንስሐ" ወይም "ከመጠመቅ" ጋር ይያያዛልን? ምሕረት የሚወሰነው ከንስሐ እና)ወይም ከጥምቀት ጋር ነውን?

የኢስ አጠቃቀም በርካታ ነው። የተለመደው አጠቃቀም "ለማመላከት" ወይም "ለዚህ ዓላማ ሲባል" ነው። አብዛኞቹ መጥምቃውያን (ባብቲስት) ሊቃውንት የሚመርጡት "በዚህ ምክንያት" የሚለውን ለሥነመለኮታዊ ምክንያቶች ነው፣ ነገር ግን እሱ አናሳ አማራጭ ነው። ዘወትር የእኛ ግምቶች በዚህ መሰሉ ሰዋሰዋዊ ደረጃ ላይ ይካሄዳሉ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲናገር መፍቀድ ይኖርብናል፣ በጽሑፉ፤ ከዚያም ትይዩዎቹን ማስተያየት፤ ከዚያም የእኛን ስልታዊ ሥነ መለኮት መቅረጽ። ሁሉም ተርጓሚዎች ከታሪክ አንጻር፣ ከክፍለ መሠረተ እምነቶች፣ እና ከልምድ አኳያ ነው ሁኔታቸው ያለው።

በኢየሱስ በማመን ያለ ምሕረት ደግሞ የታየ ጭብጥ ነው፣ በእነዚህ የሐዋ. ስብከቶች ላይ (ማለትም፣ ጴጥሮስ 2፡38፤ 3፡19፤ 5፡31፤ 10፡43፤ እና ጳውሎስ 13፡38)።

▣ **"የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ተቀበሉ"** ይህ የትንቢት መካከለኛ (አረጋጋጭ) አመላካች ነው። የመንፈስ ስጦታ የነበረው (1) የተረጋገጠ ደህንነት፤ (2) የሚያድርብን መገኘት፤ (3) ለአገልግሎት ማዘጋጀት፤ እና (4) እያደገ የሚሄድ ክርስቶስን መምሰል ናቸው። የደህንነትን ይዘቶች ወይም የሁነቱን ቅደም ተከተል ልንገፋው አይገባም፣ ምክንያቱም እነሱ በሐዋ. ዘወትር የተለዩ በመሆናቸው። ሐዋ. ማለት ቋሚ የሆነ ቀመር (መግለጫ) ወይም ሥነመለኮታዊ ቅደም ተከተል ማስተማር ማለት አይደለም (መጽሐፍ ቅዱስን ከነሙሉ ጠቀሜታው እንዴት እንደምናነብ፣ ገጽ 94-112)፣ ነገር ግን ምን እንደሆነ ተጽፏል።

ተርጓሚ ይህንን ጽሑፍ የደህንነትን ቅደም ተከተላዊ ድርጊቶችን ለማሳያነት ሊጠቀምበት ይችላልን፡ ንስሐ ግቡ፣ ተጠመቁ፣ ይህም ለይቅርታ እናም የመንፈስ ስጦታ? የእኔ ሥነ መለኮት የሚጠይቀው መንፈስ ንቁ እንደሆነ ነው በመጀመሪያውንም (ዮሐንስ 6፡44፣ 65) እና፣ በእምነት ማጽኛ ሁደት ላይ ዋነኛ ነው፣ (ዮሐንስ 16፡8-12)፣ ንስሐ (ዝክ 5፡31፤ 11፡18፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡25)፣ እና እምነት። መንፈስ ቀዳሚና አስፈላጊ ነው (ሮሜ 8፡9) ከመነሻው እስከ ፍጻሜ። በቅደም ተከተል መጨረሻ ፈጽሞ ሊሆን አይችልም!

2፡39 **"ተስፋውም ለእናንተና ለልጆቻችሁ ነው"** ይህ ከብኪ የተጠናቀረ፣ ባለ ብዙ ትውልዶች፣ ቤተሰባዊ ጽንሰ ሐሳብ ነው (ዘጸ. 20፡5-6 እና ዘዳ. 5፡9-10፤ 7፡9)። የልጆች እምነት በወላጆች ተጽዕኖ አለበት እናም የወላጆች ሀላፊነት ነው (ዘዳ. 4፡9፤ 6፡6፤ 20-25፤ 11፡15፤ 32፡46)። ይህ የተጠናቀረ ተጽእኖ ደግሞ አስፈሪ ገጽታ አለው በማቴ. 27፡25 አንጻር ሲታይ፣ ("ደሙም በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁን")።

ባለ ብዙ ትውልዶች የተስፋ እምነት እኔን ረድቶኛል፣ እግዚአብሔር በእኔ እምነት፣ ተጽዕኖ ለማሳደር፣ ለመባረክ፣ እና ዝርዮቼን ለመጠበቅ። ይህ ግን የግል ሃላፊነትን የሚክድ አይደለም፣ ነገር ግን ለተጠናቀረ ተጽዕኖ ተጨማሪ ይዘት ያክላል። የእና እምነትና ታማኝ የሆነው አገልግሎት በክርስቶስ ለቤተሰቤና ለእነሱም ቤተሰብ እንዲሁም ለሌሎቹ ተጽዕኖ ይኖረዋል (ዘዳ. 7፡9)። እንዴት ዓይነት የሚመች ተስፋና አበረታች ቃል ኪዳን ነው። እምነት ወደ ቤተሰብም ይወርዳል!

▣ **"በሩቅ ላሉትም ሁሉ"** ጴጥሮስ የሚናገረው ለአይሁድ ሕዝቦች ነው። ይህ ሐረግ በዋናነት የሚያመለክተው በግዞት ላይ ለነበሩት አይሁድ ነው፣ ወደ ተስፋይቱ ምድር ለሚመለሱት (ኢሳ. 57፡19)። ሆኖም፣ እሱ ደግሞ፣ በአንዳንድ ምንባቦች አሕዛብን የሚመለከት ይመስላል፣ እነሱም ከያህዌ እውቅና ከራቁት (ኢሳ. 49፡1፤ ዘካ. 6፡15)። የወንጌል መልካም የምስራች፣ አንዱ እውነተኛ አምላክ (ማለትም አህዳዊው) ሰዎችን ሁሉ በአምሳሉ የፈጠረው (ዘፍ. 1፡26-27)፣ ከሁሉም ጋር ህብረት እንዲኖረው ይፈልጋል (1ኛ ጢሞ. 2፡4፤ 2ኛ ጴጥ. 3፡9)። ይህ በክርስቶስ ላሉት ሰዎች

ሁሉ ተስፋ ያለው ህብረት ነው። በእሱም ከአንግዲህ አይሁድ-አሕዛብ፣ ባሪያ-ነጻ፣ ወንዶች-ሴቶች ማለት አይቻልም፣ ነገር ግን ሁሉም አንድ ናቸው (ኤፌ.2፡11-3፡13)። አዲሱ የመንፈስ ዘመን ያልተጠበቀ ህብረት አምጥቷል!

▣ **"ጌታ አምላካችን ወደ ራሱ የጠራቸው ብዙዎች"** ይህ የተጠናቀቀ መካከለኛ (አረጋጋጭ) ሁኔታን ገላጭ ነው። እሱም በመነሻው የሚያመለክተው ለተበታተነው ይሁዲነት ነው። እግዚአብሔር ዘወትር ተነሣሽነቱን ይወስዳል (መካከለኛ ድምጸት፣ ዮሐንስ 6፡44፣65)። ከሕዝ. 18፡32፤ ዮሐንስ 3፡16፤ 1ኛ ጢሞ. 2፡4፤ 2ኛ ጴጥ. 3፡9 እሱ ሰዎችን ሁሉ በየደረጃው ወደ ራሱ ይጠራቸዋል። ነገር ግን፣ እነሱ ምላሽ መስጠት ይጠበቅባቸዋል (ማለትም ሁኔታን የሚገልጽ ድባብ)።

"ብዙ" እና "ሁሉም" የሚሉት ቃላት በመጽሐፍ ቅዱስ ትይዩ ናቸው (ኢሳ. 53፡6፣ "ሁሉም"ን ለኢሳ. 53፡11፣12 "ብዙ" ወይም ሮሜ 5፡18፣ "ሁሉም"ን ከ ሮሜ 5፡19 "ብዙ" ጋር አስተያይ)። የእግዚአብሔር ልብ ለጠፋው ዓለም ነው፣ በአምሳሉ ለተፈጠረው፣ ከእሱ ጋር ህብረት እንዲኖረው ለተፈጠረው!

2፡40 **"በሌላም በብዙ ቃል"** ይህ ጽሑፋዊ ማስረጃ ነው፣ በሐዋ. የተደረጉት ስብከቶች ማጠቃለያቸው ብቻ እንደተመዘገቡ። ይህም ደግሞ ለኢየሱስ ትምህርትና የወንጌል ስብከት ተመሳሳይ ነው። እኛ በቅድመ ግምት ደረጃ የእነዚህን ማጠቃለያዎች ተመስጧዊነትና ርግጠኝነት እናጸናለን። የአንደኛው ክፍለ ዘመን ዓለም ልማድ ያደረገው ቃላዊ አቅርቦትና እነሱንም በማስታወስ ነው።

▣ **"በምር ቃል መስክሮ"** የግሪኩ ቃል (ዲያ ሲደመር ማርቱሮማይ) በሉቃስ የታወቀ ነው (2፡40፤ 8፡25፤ 10፡42፤ 18፡5፤ 20፡21፣23፣24፤ 23፡11፤ 28፡23፤ ሉቃስ 16፡28)። ወንጌል አጣዳፊነትና የመጨረሻነት አለው፣ ወንጌልን መስበኩም ሆነ ማዳመጡ ችላ ሊባል የማይቻል።

▣ **"ቀጥሎም እየመከራቸው"** ሰው በክርስቶስ ለሆነው ለእግዚአብሔር ስጦታ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል (ዮሐንስ 1፡12፤ 3፡16፤ ሮሜ 10፡9-13)። ይህ የእግዚአብሔር ሉዓላዊነትና የሰውን ነጻ ፍቃድ አያዎ (ፓራዶክስ) ነው፣ ፊሊጵ. 1፡12-13)።

▣

**አአመመቅ፣ አኪጀት** **"ይድናሉ"**

**አየተመት፣ አእት፣**

**አኢመቅ** **"ራሳችሁን አድኑ"**

የዚህ ቃል አረባብ *የድርጊት ተገብሮ ተተኳሪ* ነው፣ ነገር ግን ልትገልጹ እንደምትችሉት፣ አየተነት፣ አእት እና አኢመቅ የሚተረጉሙት እንደ *መካከለኛ ድምጸት* ነው። ይህ ደህንነትን በተመለከተ ሥነ መለኮታዊ ክርክር አለው። ሁሉም በእግዚአብሔር ነውን፣ ወይም አድማጩ እግዚአብሔር በሕይወቱ)ቷ እንዲሠራበት)ባት መፍቀድ ይኖርበታል)ባታልን?

የግሪኩ ቃል "መዳን" (ሶሶ) የሚያንጸባርቀው የዕብራይስጡን ጽንሰ-ሐሳብ (ያሻ) እሱም የአካላዊ ትድግናን ነው (ያዕቆብ 5፡15፣20)፣ በአኪ. አጠቃቀሙ ግን የሚኖረው ትርጉም መንፈሳዊ ትድግና ወይም ደህንነት ነው (ያዕቆብ 1፡21፤ 2፡14፤ 4፡12)።

**ልዩ ርዕስ፡ የግሪክ የግሥ ጊዜያቶች ለደህንነት ጥቅም ላይ የዋሉ**

ደህንነት ውጤት አይደለም፣ ነገር ግን ግንኙነት ነው። አንዱ በክርስቶስ ሲያምን አይጠናቀቅም፤ መጀመሩ ነው! የእሳት አደጋ ዋስትና አይደለም፣ ወይም የመንግሥተ ሰማያት ትኬት አይደለም፣ ነገር ግን ክርስትስን በመምሰል የማደግ ሕይወት ነው። በአሜሪካ ምሳሌያዊ አነጋገር አለ፣ እንዲህ የሚል፣ ጥንዶች ረጅም ጊዜ አብረው በኖሩ ቁጥር፣ መመሳሰላቸው እየጨመረ ይሄዳል። የመዳን ግብ ይህ ነው!

ደህንነት እንደ ተጠናቀቀ ድርጊት (የተጠናቀቀ)

- ሐዋ. 15፡11
- ሮሜ 8፡24
- 2ኛ ጢሞቲዎስ 1፡9
- ቲቶ 3፡5
- ሮሜ 13፡11 (የተጠናቀቀውን ከወደፊቱ ጋር አደባልቆ የሚያስረዳ)

ደህንነት ፍጹም የመሆን አቋም

- ኤፌሶን 2፡5፣8

ደህንነት ቀጣይነት እንዳለው ሂደት (የአሁን)

- 1ኛ ቆሮንቶስ 1፡18፤ 15፡2
- 2ኛ ቆሮንቶስ 2፡15
- 1ኛ ጴጥሮስ 3፡21

ደህንነት ወደፊት እንደሚቀዳጁት (የትንቢት በግሥ ጊዜያቱ ወይም በጽሑፉ)

- (በማቴ. 10፡22፣24፡13፤ ማርቆስ 13፡13 በተመለከተው አንድምታ)
- ሮሜ 5፡9፣10፤ 10፡9፣13

- 1ኛ ቆሮንቶስ 3፡15፤5፡5
- ፊሊጵስዩስ 1፡28
- 1ኛ ተሰሎንቄ 5፡8-9
- ዕብራውያን 1፡14፤9፡28
- 1ኛ ጢሞቲዮስ 4፡16
- 1ኛ ጴጥሮስ 1፡5፣9

ስለሆነም፣ ደህንነት የሚጀምረው በመነሻ የእምነት ውሳኔ ነው (ዮሐንስ 1፡12፤ 3፡16፤ ሮሜ 10፡9-13)፣ ነገር ግን ይህ በሕይወት ስልት እምነት ቀጣይነት ያለው ሂደት የግድ መሆን አለበት (ሮሜ 8፡29፤ ገላ. 3፡19፤ ኤፌ. 1፡4፤ 2፡10)፣ እሱም አንድ ቀን በመመልከት የምንቀዳጀው (1ኛ ዮሐንስ 3፡2)። ይህ የመጨረሻ የሆን አቋም መክበር ይባላል። ይህም ሊገለጽ የሚችለው እንደ

1. የመነሻ ደህንነት – መጽደቅ (ከኃጢአት ቅጣት መዳን)
2. ቀጣይነት ያለው ደህንነት – መቀደስ (ከኃጢአት ሀይል መዳን)

የመጨረሻ ደህንነት – መክበር (ከኃጢአተኝነት መዳን)

▣ **"ይህ ጠማማ ትውልድ"** ይህ ምናልባት የዘዳ. 32፡5 እና መዝ. 78፡8 ጠቃሽ ይሆናል። የብኪ ሥር ለዚህ ቃል፣ "ትክክለኛ፣" "ጻድቅ፣" "ልክ፣" "ፍትሐዊ፣" "የወንዝ ሸንበቆ" ነው። እሱም የግንባታ ዘይቤ ሆኗል፣ የመለኪያ ዘንግ፣ ወይም ቀጥተኛ መስፈርያ። እግዚአብሔር ይሄንን ዘይቤ መርጧል፣ የራሱን ባሕርይ ለመግለጽ። እግዚአብሔር መለኪያ ነው። አብዛኞቹ የኃጢአት ቃላት በዕብራይስጥና በግሪክ የሚያመለክቱት ከዚን መለኪያ ማፈንገጥን ነው (የተወላገደ፣ ጠማማ)። ሁሉም ሰዎች መዳንና መታደስ ይገባቸዋል።

2፡41

**አአመመቅ** **"ተቀበሉ"**
**አኪጀት** **"በደስታ ተቀበሉ"**
**አየተመት** **"የቀበሉ"**
**አእት** **"አመኑ"**
**አኢመቅ** **"ተቀበሉ"**

ይህ የተጠናቀቀ መካከለኛ ቦዝ አንቀጽ ነው፣ ላፖዴቾማይ። ሎውና ኒዳ፣ የግርክ እንግሊዝኛ ሥርወ ቃል፣ የዚህን ቃል ሦስት አጠቃቀሞች ዘርዝረዋል (ቅጽ. 2፣ ገጽ28)።

1. ሰውን መቀበል
2. አንድን ነገር ወይም ሰው በእውነተኛ ወይም በተገቢው መልኩ ምላሽ መስጠት
3. የአንድን ነገር ወይም ሰው እውነተኝነት ወይም ዋጋ እውቅና መስጠት

ሉቃስ ይህንን ቃስ አዘውትሮ ይጠቀማል (ሉቃስ 8፡40፤ 9፡11፤ ሐዋ. 2፡41፤ 18፡27፤ 24፡3፤ 28፡30)። ወንጌል ሊቀበሉት የሚገባ እውነት፣ ሊታምን የሚገባ እንዲሁም ያንን አካል በመሰለ ሊኖሩት የሚገባ ነው። ሦስቱም ወሳኞች ናቸው።

▣ **"እናም ተጠመቁ"** ጥምቀት ለአይሁድ ሃይማኖታዊ ተስፋ አልነበረም። ፕሮሲሊተስ በራሳቸው የሚጠመቁ ነበሩ፣ ነገር ግን አይሁድ አልነበሩም። ይህ አዲስ ሃይማኖታዊ ሁነት ነው፣ ለእነዚህ አድማጮች። ኢየሱስ ተጠምቋል፤ ኢየሱስ እንድንጠመቅ አዞናል– ያ ነው ያንን የደረገው! አኪ ስላልተጠመቁ አማኞች ምንም የሚለው የለም። ይህም ለእኔ እንደሚመስለኝ ከይሁዲነት መቆራረጫና ለአዲሱ የእግዚአብሔር ሕዝብ መጀመሪያ ነው።

▣ **"ሦስት ሺ ነፍሳት"** ይህ ግምታዊ ቁጥር ነው፣ ነገር ግን ብዙ ቁጥር። የጴጥሮስ መልእክት እነዚህን የዓይን ምስክሮች ነክቷቸዋል። እነሱም ለማመን የተጠየቀውን የእምነት እመርታ ለማድረግ ዝግጁ ናቸው።

1. ኢየሱስ መሲሕ ነው
2. መሲሕ ማለት ደግሞ ይሠቃያል
3. በሱ ማመን ለይቅርታ ብቸኛው መንገድ ነው
4. ጥምቀት ተገቢ ነው

ይህ የታዘዘው ወሳኝ፣ የወዲያውኑ፣ ሕይወትን ቀያሪ ውሳኔ (ዛሬ እንደሆነው ነው)! ልዩ ርዕስ፡ ስብከተ ወንጌል 2፡14 ተመልከት።

2፡42 **"እነርሱም ቀጣይነት ባለው መልኩ ራሳቸውም በመስጠት"** ሉቃስ ይሄንን ጽንሰ ሐሳብ ዘወትር ይጠቀማል (1፡14፡2፡42፣46፤ 6፡4፤ 8፣13፤ 10፡7)። አንድ ላይ ሲሆኑ ያደረጓቸውን ነገሮች አስተውል፡ (1) መማር (ዝከ 2፡42፤ 4፡2፣18፤ 5፡21፣25፣28፣42)፤ (2) ህብረት፤ (3) እንጀራን መቁረስ (ማለትም፣ ይህ ሊገልጽ የሚችለው የጌታ ራትን ነው)፤ እንዲሁም (4) ጸሎት (ዝከ ቁ. 43-47)። እነዚህ ነገሮች አዲስን አማኝ የምናስተምራቸው ሊሆኑ ይገባል! እነደዚህ አዲስ አማኞች እውነትንና አብሮነትን ተርበዋል።

**ልዩ ርዕስ: ኮይኖኒያ**

"fellowship" (ኮይኖኒያ) ማለት

1. ከአንድ ሰው ጋር ያለን የቀረበ ግንኙነት የሚያሳይ ሲሆን ይህም
   ሀ. ከልጅ ጋር (1ዮ 1፡6፤ 1ቆሮ 1፡9)
   ለ. ከመንፈስ ጋር (2ቆሮ 13፡13፤ ፊሶ 2፡1)
   ሐ. ከአብና ከወልድ ጋር (ዮሐ 1፡3)
   መ. ከቃል ኪዳን ወንድሞች (እህቶች (1ዮሐ 1፡3፡7፤ ሐዋ 2፡42፤ ገላ 2፡9፤ ፊሊሞና 17)
2. ከነገሮች ወይም ከቡድኖች ጋር ያለውን የቀረበ ግንኙነት የሚያሳይ ሲሆን ይህም
   ሀ. ከወንጌል ጋር (ፊሊጵ 1፡5፤ ፊልሞና 6)
   ለ. ከክርስቶስ ደም ጋር (1ቆሮ 10፡16)
   ሐ. ጨለማ ካልሆነ ጋር (2ቆሮ 6፡24)
   መ. ከመከራ ጋር (ፊልጵ 3፡10፤ 4፡14፤ 1ጴጥ 13)
3. በልግስና መንገድ የሚደረግ ሥጦታ ወይም መዋጮ የሚያሳይ ነው (ሮሜ 12፡13፤ 15፡26፤ 2ቆሮ 8፡4፤ 9፤13፤ ፊልጵ 4፡15፤ ዕብ 13፡16)
4. የሰው ዘር ከአምላኩ ጋር ያለውን ሕብረት የሚያድስ በክርስቶስ ተገለጠን የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ የሚያመለክት ነው።

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ: 2፡43-47**

**[43]ነገር ግን በሰው ሁሉ ፍርሀት ሆነ፤ በሐዋርያትም እጅ ብዙ ድንቅና ምልክት ተደረገ። [44]ያመኑትም ሁሉ አብረው ነበሩ፤ [45]ያላቸውንም ሁሉ አንድነት አደረጉ። መሬታቸውንና ጥሪታቸውንም እየሸጡ፥ ማንኛውም እንደሚፈልግ ለሁሉ ያካፍሉት ነበር። [46]በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ፥ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር፤ [47]እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው። ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር።**

2፡43 **"በእያንዳንዱ ላይ የፍርሃት ስሜት አደረባቸው"** ይህ ያልተጠናቀቀ ተገብሮ (አረጋጋጭ) አመላካች ነው። እኛም የእንግሊዝኛውን "ፍርሃት" ከ "ፍራቻ" ወይም "ፍርሃት" እናገኘዋለን። የእግዚአብሔር መገኘት እና ሃይል ቅዱስ የሆነ ሁኔታን ይፈጥራል፣ ያልዳኑ ኃጢአተኞች እንኳ የቅድስናውን ጊዜና ቦታ ይገነዘቡታል!

2፡44 **"የተቀበሉት ሁሉ"** 3፡16 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

▣ **"ሁሉንም ነገር በጋራ ያደርጉት ነበር"** ይህ የጥንት ሙከራ "በማህበር" አልሰመረም (ዝከ 4፡32-5፡11)። ይሄም ማለት ግን ሁሉን አቀፍ መመሪያ እንዲሆን አይደለም፣ ነገር ግን የፍቅር፣ የጋራ መግባባትና መረዳዳት ያለበት የእምነት ማህበረሰብ ሙከራ ነው። ይህም ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው ሁሉም በመጽሐፍ ቅዱስ የሰፈረው ነገር በዓለም አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ ይደረጋል ማለት አይደለም! እነዚህ የጥንት አማኞች እርስ በርሳቸው ታላቅ ፍቅር ነበራቸው። ምናለ ይሄንን ፍቅር እና የእግዚአብሔር ሃይል በመካከላችን መገኘትን ዳግመኛ ብናገኘው (ዮሐንስ 17፡11፣ 21፣22፣23)!!

2፡46 **"በአንድ ልብ"** የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ህብረትና ዓላማ ባሕርይ ነበረች (ዝከ 1፡14፤ 2፡46፤ 4፡24፤ 5፡12)። ይህ ግን በሁሉም ነገር ይስማማሉ ማለት አይደለም፣ ነገር ግን በልባቸው እና በሐሳባቸው አንድላይ ነበሩ፣ ለመንግሥቱ ቅድሚያ በመስጠት፣ ከግል ፍላጎትና ዓላማ (አጀንዳ) ይልቅ።

▣ **"በመቅደስ"** እነሱ ምናልባት "በሰሎሞን ደጅ" ተገናኝተው ይሆናል (ዝከ 3፡11፤ 5፡12)። ኢየሱስ እዚያ አስተምሯል (ዮሐንስ 10፡23)። የሰሎሞን ደጅ ወይም መመላለሻ የተከለለ ባለ ዐምድ ስፍራ ሆኖ ከአሕዛብ መመላለሻ በስተምስራቅ፣ በሄሮድስ መቅደስ ነው (ጆሴፈስ አንቲክ 15፡11፡3)። ራቢዎች እዚያ አስተምረዋል። ሰዎች ትምህርት ለመስማት እዚህ ስፍራ ዘወትር ይሰበሰባሉ።

የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ቤተ መቅደስ ትገኝ ነበር፣ እንዲሁም ምናልባት በየአጥቢያ ምኩራቦች፣ አይሁድ የርግማን መግለጫ እስካወጡበት ጊዜ (70 ዓ.ም አካባቢ)፣ ይህም የምኩራብ አባላት ኢየሱስን ያወግዙ ዘንድ እስካስገደዱበት ድረስ። ይህም በቤተ ክርስቲያንና በይሁዲነት መካከል መቆራረጥን ፈጠረ። የጥንት አማኞች የሳምንት አምልኳቸውን ያጸኑ ነበር፣ ይሰበሰቡ የነበረው ግን እሑድ ነበር፣ የኢየሱስን ትንሣኤ ለማሰብ።

▣ **"በየቤቱም እንጀራን በመቁረስ"** "እንጀራን መቁረስ"፣ ለጌታ ራት ስልታዊ ስያሜ ከሆነ (ሉቃስ 22፡19 እና በተለይም፣ በአጋፔ ምግብ ጽሑፍ [1ኛ ቆሮ. 11፡17-22፤ 2ኛ ጴጥ. 2፡13-14፤ ይሁዳ ቁ. 12] በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን፣ ሐዋ. 20፡7)፣ ከዚያም ይህ የሚያመለክተው ለየቀኑ በየቤቱ የሚደረገውን መሰባሰብ ነው (ነገር ግን

መወሰድ ያለበት እሱ ለመደበኛ ምግብም ነው በሉቃስ 24:30፣35):: ቀኖናዊ ከሆነው አጥቢያዊ ባህል ተጠንቀቁ፣ ስለ ጌታ ራት፣ መቼ፣ የት፣ ድግግሞሽ እና ቅርጽ ሁኔታ::

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ደስተኝነትና የልብ ትሕትና"** |
| **አኪጀት** | **"ደስተኝነትና የልብ ቅንነት"** |
| **አየተመት** | **"ደስታና ለጋስ የሆነ ልብ"** |
| **አእት** | **"ደስታና ትሑት ልብ"** |
| **አኢመቅ** | **"ደስታና ለጋስነት"** |

የትርጉሞቹ የተለያየ መሆን የሁለተኛው ቃል የሚያሳየው አፌሎትስን ለመተርጎም ያለውን ችግር ነው:: በጥሬው፣ የሚለው ለስላሳና ዝርግ ሲሆን፣ ነገር ግን በዘይቤ ጥቅም ላይ ሲውል "ግልጽ" "አክባሪ" ወይም "ትሑት" ነው (ሎው እና ኒዳ):: ልዩ ርዕስ፡ ልብ 1:24 ላይ ተመልከት::

2:47

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት** | **"በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው"** |
| **አየተመት** | **"በሕዝብ ሁሉ ፊት መልካም ፍቃድ ነበራቸው"** |
| **አእት** | **"ከሕዝቡ ሁሉ መልካም ፍቃድን እያገኙ"** |
| **አኢመቅ** | **"በሁሉም ዘንድ መልካም አስተያየት ነበራቸው"** |

ይህ ሐረግ የሚያመለክተው የጥንት ክርስቲያኖች በኢየሩሳሌም ሰዎች ተቀባይነት ማግኘታቸውን ነው:: ሁሉም የተለያዩ የህብረተሰብ ዓይነቶች እና ደረጃዎች ስለ እነዚህ ቀደምት አማኞች የነበራቸው አስተሳሰብ ቀና ነበር:: ክርስቲያኖች ለሮሜ ባለሥልጣናትም ሆነ ለሰላም ተቸታታኝ አልነበሩም (አንደኛው የሐዋ. ዓላማ):: በቤተ ክርስቲያን መጀመሪያ ላይ ከራቢያዊ ይሁዲነት ጋር መቆራራጥ አልነበረም::

▣ **"ጌታም ይጨምር ነበር"** ይህ *ያልተጠናቀቀ የድርጊት አመላካች* ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ለእግዚአብሔር ሉዓላዊነት አጽንዖት ይሰጣል:: ምንም ነገር ከእግዚአብሔር ፍቃድ ውጭ አይሆንም ምንም ነገር እግዚአብሔርን አያስገርመውም:: ሆኖም፣ ይህ የብኪ መንገድ የሆነው አሀዳዊነትን የመግለጽ ነገር (ማለትም፣ ባለ አሀድነት) በትትክል አልተረዳም:: ሁለት ልዩ ርዕሶችን ለማስገባት ፈልጌአለሁ፣ አንደኛው ስለ ሚዛን አስፈላጊነት እና ሌለኛው ስለ ኪዳን:: ይህም ብርሃንን እንደሚያመጣ ተስፋ አደርጋለሁ፣ ሙቀትን ሳይሆን!

---

**ልዩ ርዕስ፡ መመረጥ/ቅድመ ውሳኔ (መታደል) እና የሥነ መለኮት ሚዛን አስፈላጊነት**

መመረጥ አስደናቂ መሠረተ እምነት ነው:: ሆኖም፣ እሱ የውዴታ ጥሪ አይደለም፣ መተላለፊያ መስመር የመሆን ጥሪ እንጂ፣ ለሌሎች መዋጀት መሣርያ ወይም ምክንያት! በብሉይ ኪዳን ቃሉ በቀዳሚነት ጥቅም ላይ ይውል የነበረው ለአገልግሎት ነበር፤ በአዲስ ኪዳን ጥቅም ላይ የዋለው ለደህንነት ነው፣ እሱም ከአገልግሎት በተያያዘ:: መጽሐፍ ቅዱስ ተቃርኖ ያለው የሚመስለውን የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነትና የሰውን ነጻ ፍቃድ አያስታርቅም፣ ሁለቱንም ያጸናል እንጂ! ለመጽሐፍ ቅዱስ የተሻለ ክርክር ሊሆን የሚችለው ሮሜ 9ነው፣ በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ምርጫ እና ሮሜ 10 በሰው ልጅ ምላሽ አስፈላጊነት (ዝከ 10:11፣13)::

ለዚህ ሥነመለኮታዊ ክርክር ቁልፉ ሊገኝ የሚችለው በኤፌሶን 1:4 ነው:: ኢየሱስ በእግዚአብሔር የተመረጠ ሰው ነው እንዲሁም ሁሉም በእሱ ሃይል የተመረጡ ናቸው (ካርል ባርዝ):: ኢየሱስ የእግዚአብሔር "አዎን" ነውለወደቀው የሰው ልጅ ፍላጎት (ካርል ባርዝ):: ኤፌሶን 1:4 ደግሞ ጉዳዩን ለማብራራት እገዛ የሚያደርገው የቅድመ መታደል ግብ ሰማይ አለመሆኑን ነው፣ ቅድስና እንጂ (ክርስቶስን መምሰል):: ዘወትር በወንጌል ጠቀሜታ እየተሳብን፣ ሃላፊነታችንን ችላ እንላለን! የእግዚአብሔር ጥሪ (ምርጫ) ለጊዜው እንዲሁም ለዘላለም ነው!

መሠረተ እምነቶች ከሌሎች እውነቶች ጋር ለመያያዝ ነው የሚመጡት እንጂ፣ ለተናጠላዊ፣ ለማይያያዙ እውነቶች አይደለም:: የተሻለ ምስያ የሚሆነው ህብረ ክዋክበትና አንድ ነጠላ ኮከብ ነው:: እግዚአብሔር እውነትን ያቀረበው በምስራቅ ዘውግ እንጂ በምዕራብ አይደለም:: እኛ ክርክሮቹን ልናስወግዳቸው አይገባም፣ በተቃርኗዊ (አያዎ (ፓራዶክስ)) ጥንዶች የቀረቡትን መሠረተ እምነታዊ እውነቶች (እግዚአብሔርን ከተፈጥሮ በላይ እንደሆነ ወይም አብሮ እንዳለ፣ መጠበቅ ወይም መጽናት፤ ኢየሱስ ከአብ ጋር እኩል መሆኑ እና ኢየሱስ ለአብ የሚሠራ፤ ክርስቲያናዊ ነጻነት ወይም ክርስቲያናዊ ሀላፊነት ለኪዳን ባልደረባው፤ ወዘተ)::
"የኪዳን" ሥነ መለኮታዊ ጽንሰ ሐሳብ የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት (ዘወትር መነሻውን የሚወስደውና አጀንዳውን የሚያዘጋጀው) ከ አስገዳጅ መነሻ እና ቀጣይነት ካለው ንስሐ፣ ከሰዎች ከሚፈለግ የእምነት ምላሽ (ማርቆስ 1:15፤ ሐዋ. 3:16፣19፤ 20:21):: ጽሑፍን ከማጥራት ተጠበቁ፣ አንደኛውን የፓራዶክስ ጎን ብቻ ከመመልከት እና ሌለኛውን ከማንኳሰስ! የራሳችሁን ተወዳጅ መሠረተ እምነት ብቻ ወይም የሥነ መለኮት ሥርዓት ከማስረዳት ተጠንቀቁ!

---

**ልዩ ርዕስ፡ ኪዳን**

የብኪ ቃል የሆነው ቤሪዝ፣ ኪዳን፣ ለመግለጽ ቀላል አይደለም:: በዕብራይስጥ የሚገጥም ግሥ የለውም:: ሥርወ ቃላዊ ፍች ለማምጣት የተደረጉት ሙከራዎች ሁሉ የማያሳምኑ ሆነዋል:: ሆኖም፣ የጽንሰ ሐሳቡ

ማዕከላዊነት የቃሉን አጠቃቀም ይመረምሩ ዘንድ ሊቃውንትን አስገድዷቸዋል፣ ተግባራዊ ፍችውን ለመወሰን።

ኪዳን አንዱ እውነተኛው አምላክ ከእሱ ፍጡር ከሆነው ሰው ጋር የሚደረግ ውል ነው። የኪዳን ጽንሰ ሐሳብ፣ ውል፣ ወይም ስምምነት የመጽሐፍ ቅዱስን መገለጥ ለመረዳት ወሳኝነት አለው። በእግዚአብሔር ሉዓላዊነት እና በሰው ልጆች ነጻ ፍቃድ መካከል ያለው ክርክር በኪዳን ጽንሰ ሐሳብ በግልጽ ይታያል። አንዳንድ ኪዳናት የተመሠረቱት በእግዚአብሔር ባሕርይ፣ ድርጊት፣ እና ዓላማ ላይ ነው።

1. ተፈጥሮ ራሱ (ዘፍ. 1-2)
2. የአብርሃም መጠራት (ዘፍ. 12)
3. ከአብርሃም ጋር ኪዳን (ዘፍ. 15)
4. የኖህ መጠበቅና ተስፋ (ዘፍ. 6-9)

ሆኖም፣ የኪዳን ዋነኛ ባሕርዩ ምላሽን መፈለጉ ነው

1. በእምነት አዳም እግዚአብሔርን መታዘዝና በኤደን ገነት መሐል ከሚገኘው ዛፍ መብላት የለበትም (ዘፍ. 2)
2. በእምነት አብርሃም ወገኖቹን ትቶ፣ እግዚአብሔርን መከተል፣ እንዲሁም ስለ መጪው ዝርዮቹ ማመን ነበረበት (ዘፍ. 12፡15)
3. በእምነት ኖህ ትልቅ መርከብ ገንብቶ፣ ከውሃ ራቅ ያለ፣ እንስሳትን ማሰባሰብ ነበረበት (ዘፍ. 6-9)
4. በእምነት ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብፅ አውጥቶ የተወሰኑ መመሪያዎችን፣ ለሃይማኖታዊና ለማህበራዊ ሕይወት የሚሆኑ፣ የበረከትና የርግማን ተስፋዎችን መቀበል ነበረበት (ዘዳ. 27-28)።

ተመሳሳይ የሆነ ክርክር እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ስላለው ግንኙነት "በአዲስ ኪዳን" ተመልክቷል። ክርክሩ በግልጽ የሚታየው ሕዝ. 18 ን ከሕዝ. 36፡27-37 ጋር በማወዳደር ነው። ኪዳኑ የተመሠረተው በእግዚአብሔር የጸጋ ድርጊት ነውን ወይስ ለሰው በተሰጠ የውክልና ሃላፊነት? ይህ አንገብጋቢ ጉዳይ ነው፣ በብሉይ ኪዳን፣ በአዲሱም ጭምር። የሁለቱም ግቦች ተመሳሳይ ናቸው፡ (1) የጠፋው ህብረት መመለስ፣ ዘፍ. 3 እና (2) የእግዚአብሔርን ባሕርይ የሚያንጸባርቅ ጻድቅ ሕዝብ መመሥረት።

የኤር. 31፡31-34 አዲስ ኪዳን ክርክሩን ያቃልላል፣ የሰዎችን ድርጊት ተቀባይነት ለማግኘት የሚደረገውን በማስቀረት። የእግዚአብሔር ሕግ ውስጣዊ መሻት ሆነ፣ ውጫዊ ድርጊት መሆኑ ቀርቶ። መልካም፣ ጻድቅ ሕዝብ የመሆን ግብ በተመሳሳይ መልኩ ነው የሚቀረው፣ ነገር ግን ዘዴው (አገባቡ) ነው የተቀየረው። የወደቀው የሰው ልጅ የእግዚአብሔር አምሳል ነጸብራቅ ከመሆን ብቃት እንደሌለው ተረጋግጧል (ሮሜ 3፡9-18)። ችግሩ ኪዳኑ አልነበረም፣ ነገር ግን የሰው ሃጢአተኝነትና ድካም ነው (ሮሜ 7፤ ገላ. 3)።

ተመሳሳይ ክርክር በብኪ ሁኔታዊ ያልሆነና በሁኔታዊ ኪዳናት መካከል እንዳለ ይኖራል፣ በአኪ። ደህንነት በፍጹም ነጻ ነው በኢየሱስ ክርስቶስ የተፈጸመ ሥራ፣ ነገር ግን ንስሐና እምነትን ይጠይቃል (ሁለቱንም በመነሻነትም ሆነ በቀጣይነት)። እሱም ሁለቱም፣ ሕጋዊ ሥልጣናዊ አዋጅና ክርስቶስን ወደ መምሰል መጠራት፣ አመላካች መግለጫ ለተቀባይነትና አስፈላጊ ቅድስና! አማኞች በራሳቸው ድርጊት የዳኑ አይደሉም፣ ነገር ግን በመታዘዝ (ኤፌ. 2፡8-10)። እግዚአብሔርን በመምሰል መኖር የመዳን ማስረጃ ነው እንጂ የመዳን ምክንያት አይደለም።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አየተመት** | **"በቁጥራቸው ላይ"** |
| **አኪጀት** | **"በቤተ ክርስቲያን ላይ"** |
| **አእት** | **"በእነሱ ወገን ላይ"** |
| **አኢመቅ** | **"በእነሱ ህብረት ላይ"** |

ኢፒ ለአውቶ (epi ለ auto) የሚለው ሐረግ ጥቅም ላይ የዋለው በጥንታዊ ግሪክ እና በኮኒ ግሪክ ነው፣ (ሴፕትዋጂንት እና ሐዋ. 1፡15፤ 2፡1፣47፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡20፤ 14፡23)፣ ፍችውም "አንድ ላይ መሰባሰብ" ነው። እዚህ በአኪ የሚያመለክተው የቤተ ክርስቲያንን ስብሰባ ነው። ስለዚህ፣ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ጨመረ (ማለትም፣ ተሰብሳቢውን) በየዕለቱ።

▣ **"የሚድኑትን"** "ጌታ (እግዚአብሔር ወይም ክርስቶስ) ይጨምር ነበር" የሚለው ሐረግ ያልየጠናቀቀ የድርጊት አመላካች ሲሆን፣ ነገር ግን ይህ ሐረግ ግን የአሁን ተገብሮ ቦዝ አንቀጽ ነው። የገላጩ አካል የተገብሮ ድምጹ፣ ጌታ ነው። "የዳኑት" በሂደቱ ነው። ደህንነት በእምነት)በመታመን)በማመን ይጀምራል፣ በየዕለቱ። ደህንነት በእግዚአብሔር)መንፈስ መነሻ የተደረገ ነው፣ (ዮሐንስ 6፡44፣65)፣ ነገር ግን ቀጣይነት ያለው ልምድ መሆን አለበት። ለመንግሥተ ሰማያት ትኬት ወይም የሕይወት ኢንሹራስ ፖሊሲ አይደለም፤ እሱ የየቀኑ፣ የሚያድግ፣ የእምነት ግንኙነት ነው። ልዩ ርዕስ፡ የግሪክ ግሥ ጊዜያቶች ለደህንነት ጥቅም ላይ የዋሉትን 2፡40 ተመልከት።

### የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት ለማገዝ ነው፣ ዋናዋናዎቹን የዚህን መጽሐፍ ክፍል ፍሬ ሐሳቦች በጥልቀት እንድታጤን። እነሱም ሐሳብ ለማጫር እንጂ መደምደሚያ አይደሉም።

1. የጴጥሮስን ስብከት ዋናዋናውን አሳይ
2. የጴንጠቆስጤ ዓላማ ምንድን ነበር።
3. የኢዩኤል ትንቢት ከዚህ ጽሑፍ ጋር እንዴት ይዛመዳል?
4. የጴጥሮስን የብሉይ ኪዳን ምንባብ አጠቃቀም አሳይ።

# ሐዋርያት ሥራ 3

## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንቀጽ ምድቦች

| የተየመቅሰ[4] | አኪጀት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ሽባው ሰው በመቅደስ ደጅ ላይ ተፈወሰ | ሽባው ሰው ተፈወሰ | በመልካም ደጅ ላይ ፈውስ | ሽባው ለማኝ ተፈወሰ | የሽባው ሰው ፈውስ |
| 3:1-10 | 3:1-10 | 3:1-10 | 3:1-10 | 3:1-10 |
| የጴጥሮስ ንግግር በሰሎሞን መመላለሻ | ስብከት በሰሎሞን መመላለሻ | የጴጥሮስ ስብከት | የጴጥሮስ መልእክት በመቅደስ | ጴጥሮስ ለሕዝቡ ተናገረ |
| 3:11-26 | 3:11-26 | 3:11-16 | 3:11-16 | 3:11-16 |
| | | 3:17-26 | 3:17-26 | 3:17-24 |
| | | | | 3:25-26 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (ከ **"መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ" ገጽ** vii)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. ምንባብ አንድ
2. ምንባብ ሁለት
3. ምንባብ ሦስት
4. ወዘተርፈ

**ጽሑፋዊ ይዘት**

በምዕራፍ 3-4 በኢየሱስ ትምህርትና በሐዋርያት ተአምራት ላይ በኢየሩሳሌም ክርክር ነበር። የመጀመሪያዎቹ አምስት ምዕራፎች የጊዜ ርዝማኔ አንድ ዓመት ያህል ነው።

ሀ. ጴጥሮስና ዮሐንስ ሽባውን ፈወሱ፣ 3:1-4:31 (የሐዋ. 2:43 ምሳሌ)
1. ፈውሱ ራሱ
2. የጴጥሮስ ሁለተኛው ስብከት ፈውሱን ማብራሪቱ
3. ተቃውሞና ምርመራ (የጴጥሮስ ሦስተኛው ስብከት፣ ለጥንታዊ የፍርድ ችሎት የተሰጠ)
4. ስደት ተጀመረ

ለ. የጋራ ሕይወት የመኖር ሙከራ፣ ሐዋ.4:32-5:11
1. የጥንቱ የአማኞች ኅብረት
2. የአናንያና የሰጲራ ችግር

ሐ. የጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያ ከራቢያዊ ይሁዲነት ጋር የነበራት ግንኙነት፣ 5:12-42
1. የቤተ ክርስቲያን ሕይወት

2. የአይሁድ ፈራጆች ቅናት
3. የመላእክት ጣልቃ ገብነት
4. የጴጥሮስ አራተኛው ስብከት
5. ተቃውሞና ቅጣት

**የኢየሱስ ማዕርጎች በምዕራፍ 3-4**

ሀ. የናዝሬቱ ኢየሱስ፣ 3:6፤ 4:10
ለ. የእሱ አገልጋይ ኢየሱስ፣ 3:13፣26፤ 4:27
ሐ. ቅዱሱና ጻድቁ ሰው፣ 3:14
መ. የሕይወት ራስ፣ 3:15
ሠ. ክርስቶስ፣ 3:18፣20፤ 4:10
ረ. ነቢይ፣ 3:22
ሰ. በጠቃሽነት "የአብርሃም ዘር" የሚል ማዕርግ 3:25-26
ሸ. የማዕዘን ድንጋይ፣ 4:11

**የቃልና የሐረግ ጥናት**

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 3:1-10**
**[1] ጴጥሮስና ዮሐንስም በጸሎት ጊዜ በዘጠኝ ሰዓት ወደ መቅደስ ይወጡ ነበር። [2] ወደ መቅደስም ከሚገቡት ምጽዋት ይለምን ዘንድ፥ ሰዎች ተሸክመው መልካም በሚሉአት በመቅደስ ደጅ በየቀኑ ያስቀምጡት የነበሩ ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ አንካሳ የሆነ አንድ ሰው ነበረ። [3] እርሱም ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ መቅደስ ሊገቡ እንዳላቸው ባየ ጊዜ፥ ምጽዋትን ለመናቸው። [4] ጴጥሮስም ከዮሐንስ ጋር ትኵር ብሎ ወደ እርሱ ተመልክቶ። ወደ እኛ ተመልከት አለው። [5] እርሱም አንድ ነገር ከእነርሱ እንዲቀበል ሲጠብቅ ወደ እነርሱ ተመለከተ። [6] ጴጥሮስ ግን። ብርና ወርቅ የለኝም፤ ይህን ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ፤ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ አለው። [7] በቀኝ እጁም ይዞ አስነሣው፤ በዚያን ጊዜም እግሩና ቍርጭምጭምቱ ጸና፥ [8] ወደ ላይ ዘሎም ቆመ፥ ይመላለስም ጀመር፤ እየተመላለሰም እየዘለለም እግዚአብሔርንም እያመሰገነ ከእነርሱ ጋር ወደ መቅደስ ገባ። [9] ሕዝቡም ሁሉ እግዚአብሔርን እያመሰገነ ሲመላለስ አዩት፤ [10] መልካምም በሚሉአት በመቅደስ ደጅ ስለ ምጽዋት ተቀምጦ የነበረው እርሱ እንደ ሆነ አወቁት፤ በእርሱም ከሆነው የተነሣ መደነቅና መገረም ሞላባቸው።**

**3:1 "ጴጥሮስና ዮሐንስም ወደ መቅደስ ይወጡ ነበር"** ይህ ያልተጠናቀቀ የድርጊት አመላካች ነው። ይህም የቀደምት ደቀ መዛሙርት ወደ መቅደስ በየቀኑ የመሄድ ልማድ ነበር (ሉቃስ 24:53፤ ሐዋ. 2:46)። ዋነኞቹ የኢየሱስ ተከታዮች በፍልስጥኤም የሚሰግዱት (1) በመቅደስ (ቢያንስ በልዩ ቀናት በየቀኑ ካልተቻለ)፤ (2) በአጥቢያ ምኩራቦች (በየሰንበቱ)፤ እንዲሁም (3) ከአማኞች ጋር በየእሑዱ ነው። ይህ ልማድ ለረጅም ጊዜ ቆይቷል። እነዚህ አማኞች በኢየሱስ የቃል ኪዳን መሲሕነት ባላቸው እምነትም ሆነ በይሁዲነት መካከል ልዩነት አልነበራቸውም። ራሳቸውን የሚመለከቱት እንደ "እስራኤል ማኅበረ ምዕመናን ሕዝብ" ነው። በዚህን ምክንያት ነው ለቡድናቸው ኢክሊሳ (ekklesia) የሚል ስያሜ የወሰዱት። በሴፕቱዋጂንት የዕብራይስጥ ኪዳናዊ ሐረግ፣ "ማኅበረ ምዕመናን (ቃሀል quhal) የእስራኤል" በሚል ነው የተተረጎመው።

አይሁድ ከኢየሩሳሌም መውደቅ በኋላ ይፋ የሆነ የርግማን ቃል በተግባር ላይ አውለዋል፣ (ኢየሱስን እንደ መሲሕ ያለመቀበል) በአጥቢያ ምኩራቦች አባልነትን መከልከል። ይህም የሆነው ቤተ-ክርስቲያን የአምልኮ ቀኗን ዕሑድ ስታደርግ ነው፣ (የኢየሱስን ትንሣኤ የማክበሪያ ቀን፤ ኢየሱስ በላይኛው ክፍል ሦስት ጊዜ ለሐዋርያት የታየበት ቀን)።

ዮሐንስ ሁልጊዜ ከጴጥሮስ ጋር ነው የሚታየው በሐዋ. (ዝከ. 1:13፤ 3:1፣3፣4፣11፤ 4:13፣19፤ 8:14)። ይህም በርግጥ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም የነበረችው፣ የመሪ ቡድኖች ነበሯት፣ እነሱም የተለያየ የወንጌል አተያይና አጽንዖት የሚሰጡበትን የሚወክሉ። ጴጥሮስና ዮሐንስም ለአሕዛብ ወንጌል ላይ ነበሩ (ዝከ ቁ. 8፣10)፣ ያዕቆብ (የኢየሱስ ያንድ ወገን ወንድም) ደግሞ የሚታወቀው በወግ አጥባቂ የአይሁድ ይዘቱ ነው። ይህ ሁሉ ከኢየሩሳሌም የሐዋርያት ጉባዔ ሐዋ. 15 በኋላ በመጠኑ ተቀይሯል።

▣ **"በዘጠኝ ሰዓት፣ በጸሎት ሰዓት"** ይህ የሚያሳየው ከንጋት በኋለ ያለውን ሦስት ሰዓት ነው። አይሁድ (ማለትም፣ ፈሪሳውያን) በልምድ ሁል ጊዜ በ3፣ 6 ቀትር ላይ፣ እና 9 ሰዓት ይጸልዩ ነበር (በመዝ. 55:17 ላይ በመመሥረት)። ይህ ጽሑፍ የሚያመለክተው የማለዳውን መሥዋዕት፣ ማለትም በ3 ሰዓት የሚሆነውን (የማለዳው መሥዋዕት በ3 ሰዓት ነው)። ብዙ ሰዎች በዚህን ጊዜ በመቅደስ ይገኛሉ (ዝከ 10:30)።

**3:2 "ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ሽባ የነበረው ሰው"** ሁሉም የመቅደሱ አዘውታሪዎች የዚህን ሰውዬ ሁኔታ ያውቃሉ ("በተደጋጋሚ ይሸከሙት ነበር" ይህም ያልተጠናቀቀ ተገብሮ ነው)፤ ስለሆነም፣ በፈውሱ ላይ ሊገባ የሚችል ተንኮል የማድረግ ዕድል አይኖርም (ዝከ. 3:10፤ 4:22)። ይህም የብኪ መሲሐዊ ትንቢት ፍጻሜ ነው (ኢሳ. 35:6)። አይሁድ ምልክትን ይሻሉ፤ ኢየሱስ በርካታ ሰጥቷቸዋል፣ የሚያዩበት ዓይን ካላቸው።

ይህ በእግዚአብሔር ቤት ደጅ ላይ በየቀኑ የሚቀመጠው ሕመምተኛ አስደንጋጭ አያዎ (ፓራዶክስ) ነው። እንደ እውነቱ፣ እዚህ ጋ ለእንደዚህ ዓይነት ሰዎች በአምልኮ ላይ እንዳይገኙ ክልከላ አለ (ማለትም፣ እንደ ካህን ለማገልገል፣

ሌዋ. 21፡16-24)። ወንጌል አዲስ ዕለት ሰጥቷል። ኢትዮጵያውያዊው እንኳ (የዘር ልዩነት ሳይደረግ) ጃንደረባ (አካላዊ ልዩነት ሳይደረግ) በአዲሱ መንግሥት መልካም አቀባበል ተደርጎላቸዋል (ዝክ 8፡26-40)።

▣ ***"መልካም በሚሏት መቅደስ"*** የዚህ ደጅ ትክክለኛ ስፍራ አልታወቀም። የኒካኖር ደጅ ሊሆን ይችላል፣ እሱም ከቆሮንቶስ ነሐስ የተሠራ (ፍላቪየስ ጆሴፈስ አንቲክ. 15.11.3፤ ጦርነቶች 5.5.3)። እሱም ከአሕዛብ ስፍራ አንሥቶ እስከ ሴቶች ስፍራ ድረስ ይዘልቃል። እሱም ከመቅደሱ በስተምስራቅ ሲሆን፣ ከሰሎሞን ደጅ በደብረ ዘይት ተራራ ትክክል ነው።

▣ ***"ወደ መቅደስ ከሚገቡት ምጽዋት ለመለመን"*** *መመጽወት፣* ወይም ለድሃ መስጠት የአይሁድ እምነት <u>የሚያዘው</u> ክፍል ነው (ማቴ. 6፡1-4፤ ሉቃስ 11፡41፤ 12፡33፤ ሐዋ10፡2፣4፣31፤ 24፡17)። ዘወትር ገንዘብ በየሳምንቱ በየአጥቢያ ምኩራቦች ተሰብስቦ፣ ከዚያም ምግብ ይከፋፈላል፣ ነገር ግን ባጠቃላይ አንዳንዶች በቤተ መቅደስ ስፍራ በየቀኑ ይለምናሉ።

**ልዩ ርዕስ፡ መመጽወት**

I. ቃሉ ራሱ
   ሀ. ቃሉ የተገኘው ከይሁዲነት ውስጥ ነው (ማለትም በሴፕተዋጂንት ጊዜ)።
   ለ. እሱም የሚያመለክተው ለድሃ እና)ወይም ለችግረኛ መስጠትን ነው።
   ሐ. የእንግሊዝኛው ቃል "መመጽወት" የተገኘው የግሪኩን ቃል ኢሌሞሱኒ (ele[illegible]mosun[illegible]) ነው።
II. የብሉይ ኪዳን ጽንሰ ሐሳብ
   ሀ. ድሃን የመርዳት ጽንሰ-ሐሳብ ጥንት በቶራ ተገልጿል (የሙሴ ጽሑፎች፣ ዘፍጥረት-ዘዳግም)።
      1. ዓይነተኛው ጽሑፍ፣ ዘዳ. 15፡7-11
      2. "ማስቃረም" ቃርሚያን ለድሃ ማሳው ውስጥ መተው፣ ሌዋ. 19፡9፤ 23፡22፤ ዘዳ. 24፡20
      3. "የሰንበት ዓመት" የሰባተኛውን ዓመት ምርት (እክር) ድሆች እንዲበሉ መፍቀድ፣ ዘጸ. 23፡10-11፤ ሌዋ. 25፡2-7።
   ለ. ጽንሰ-ሐሳቡ የተሻሻለው በጥበብ ሥነ ጽሑፍ ነው (የተመረጡ ምሳሌዎች)
      1. ኢዮብ 5፡8-16፤ 29፡12-17 (በደለኛው በ24፡1-12 ላይ ተጠቅሷል)
      2. መዝሙራት 11፡7
      3. ምሳሌ 11፡4፤ 14፡21፣31፤ 16፡6፤ 21፡3፣13
III. በይሁዲነት እድገቱ
   ሀ. የሚሽናህ የመጀመሪያው ክፍል የሚያተኩረው ድሆችን፣ ችግረኞችን፣ እና የአጥቢያ ሌዋውያንን ስለመርዳት ነው።
   ለ. የተመረጡ ጥቅሶች
      1. "ውኃ የእሳት ነበልባልን እንደሚያጠፋ፣ እንደዚያው ምጽዋት ኃጢአትን ያስወግዳል" (መክብብ (እንዲሁም መጽሐፈ ሲራክ 3፡30፣ አየተመት)
      2. "ከሀብትህ ሁሉ ምጽዋትን አኑር፣ እሱም ከጥፋት ሁሉ ይጠብቅሃል" (መክብብ 29፡12፣ አየተመት)
      3. "ከእውነት ጋር የሚሠሩ በሚያደርጉት ሁሉ ይከናወንላቸዋል። ጽድቅን የሚለማመዱ^ [7]ከሀብትህ ሁሉ ምጽዋት ስጥ፣ ምጽዋት ስታደርግም ዓይንህ አትሰስት። ድሃ ከሆነ ሁሉ ዓይንህን አትመልስ፣ የእግዚአብሔር ፊትም አይመለስብህም። [8]ብዙ ሀብት ቢኖርህ ከሁሉም በተዋረድ ስጦታ ስጥ፤ ጥቂት እንኳ ቢኖርህ ከሱ ለመስጠት አትፍራ። [9]ለክፉ ቀን የሚሆንህን መልካም መዝገብ ታከማቻለህ። [10]ምጽዋት ከሞት ያድናልና አንተም ወደ ጨለማ እንዳትገባ ይከለልሃል። [11]በእርግጥ ምጽዋት ለሚለማመዱት ሁሉ መልካም የሆነ መሥዋዕት ነው በልዑሉ ፊት" (ጦቢት 4፡6-11፣ አየተመት)
      4. "[8]ጸሎትና ጾም^ መልካም ነው፣ ከሁለቱ ግን ምጽዋት በጽድቅ ይበልጣል። በጽድቅ የሆነ ጥቂት በበደል ካለ ሀብት ይበልጣል። ወርቅን ከማከማቸት ምጽዋት መስጠት ይበልጣል። ምጽዋት ከሞት ያድናል፣ ከኃጢአትም ይታደጋል። ምጽዋትን የሚሰጡ ሙሉ ሕይወታቸውን ይደሰታሉ" (ጦቢት 12፡8-9፣ አየተመት)
   ሐ. ከጦቢት መጨረሻ የተጠቀሰው 12፡8-9 የሚያሳየው የችግሩን ማደግ ነው። የሰዎች ድርጊት)የሰዎች ቅርስ ለይቅርታና ለብልጽግና ምክንያት ተደርጎ ተወስዷል።
      ይህ ጽንሰ-ሐሳብ በሴፕቱዋጂንት እያደገ መጥቷል፣ የግሪኩ ቃል የምጽዋት ኤልሙሱኒ (eleēmosunē) ከጽድቅ (dikaiosunē) ጋር ተመሳሳይ ሆኗል። እነሱም በትርጉም እርስ በርስ ሊቀያየሩ ይችላሉ፣ ከዕብራይስጡ ቃል ሄስድ ጋር (የእግዚአብሔር ኪዳናዊ ፍቅርና ታማኝነት፣ ዘዳ. 6፡25፤ 24፡13፤ ኢሳ. 1፡27፤ 28፡17፤ 59፡16፤ ዳን. 4፡27)።
   መ. የሰዎች ተግባርና ኀዘኔታ በራሳቸው ግብ የሆኑት ብልጽግና እዚህ፣ እንዲሁም ከሞት በኋላ ደህንነት ተደርጎ ነው። ድርጊቱ ራሱ፣ ከድርጊቱ ጀርባ ያለው ነገር ሳይታይ ከሥነመለኮት አኳያ ተቀባይነት አግኝቷል። እግዚአብሔር ልብን ነው የሚያየው፣ ከዚያም የእጅን ሥራ ይፈርዳል። ይህ የራቢዎች ትምህርት ነበር፣ ነገር ግን በሰዎች የራስ ጽድቅ ምክንያት ሊበላሽ ችሏል (ሚክ. 6፡8)።

IV. የአዲስ ኪዳን ምላሽ
*ሀ. ቃሉ የሚገኘው*
1. *ማቴ*. 6፡1-4
2. *ሉቃስ* 11.41፤12፡33
3. *ሐዋ*. 3፡2-3፣10፤ 10፡2፣4፣31፤ 24፡17
*ለ. ኢየሱስ ባህላዊ የአይሁድ የጽድቅ መረዳትን ገልጿል* (2ኛ *ክሌመንት*16፡4) *በተራራው ስብከት ላይ* (*ማቴ*. 5-7) *እንዲህ በማጣቀስ*
1. *ምጽዋት መስጠት*
2. *ጾም*
3. *ጸሎት*

*አንዳንድ አይሁድ በድርጊታቸው ያምኑ ነበር። ይህም ድርጊት የሚመነጨው ለእግዚአብሔር ካለ ፍቅር፣ ከቃሉ፣ ከኪዳን ወንድሞች እና እኅቶች እንጂ ከራስ ፍላጎት አይደለም! ትሕትናና ምሥጢራዊነት ለተገቢ ድርጊት መመሪያ ናቸው። ልብ ወሳኝ ነው። ልብ ፈጽሞ ክፉ ነው። እግዚአብሔር ልብን መለወጥ አለበት። አዲስ ልብ እግዚአብሔር ይቀበለዋል!*

3፡3 የሰው የልቡ ሐሳብ ከመነሻው ለግሉ ነው (ዝከ ቁ. 5)።

3፡4 **"አተኩሮ እየተመለከተ"** በ1፡10 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

▣ **"ተመልከተን"** የሱን አትኩሮት ፈልገዋል። (ብሌፖ blepō የአሁን የድርጊት ተተኪ ቅርጽ ነው)።

3፡5 ሐዋርያት በግላቸው ሀብታም ሰዎች አይደሉም፣ ነገር ግን ከእግዚአብሔር መንፈሳዊ ሀብት ቀረቤታ አላቸው (ዝከ ቁ. 6) ።

3፡6 **"በኢየሱስ ክርስቶስ ስም"** "ስም" የዕብራይስጥ ዘይቤ ሲሆን የአንድን ሰው ባሕርይ የሚገልጽ ነው (ሉቃስ 9፡48፣49፤ 10፡17፤ 21፡12፣17፤ 24፡47)። ይህ ለዚህ ሰው አስደንጋጭ ነበር። ኢየሱስ በቅርብ የተፈረደበትና የተሰቀለ ወንጀኛ ነው፣ ይሄ ጸጉረ ልውጥ (ጴጥሮስ) "መሲሑ" ብሎ የሚጠራው (ማለትም "መሲሑ" የግሪክ ትርጉም ነው)።

▣ **"የናዝሬቱ"** 2፡22 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

▣ **"ተራመድ"** ይህ የአሁን የድርጊት አስገዳጅ ነው። ጴጥሮስና ዮሐንስ፣ እንደ ኢየሱስ፣ የሚያገኙትን ዕድል ለእግዚአብሔር ፍቅርና ኃይል መግለጫና የወንጌልን መልእክት ለማጽኛ ይጠቀሙበታል (ዝከ ቁ. 9) ይህ ፈውስ የአይሁድ አምላኪዎችን ትኩረት ስቧል (ዝከ ቁ. 12)።

3፡7 ይህ የዓይን ምስክር የሰጠው የብዙ ተጓዳኝ ነገሮች ትዝብት ነው። አንድ እዛ የነበረ ሰው የዚህን አስገራሚ ሁኔታ ዝርዝር ነግሮት ይሆናል።

▣ **"ወዲያውኑ"** ይህ የግሪክ ቃል ፓራክሬማ (parachrēma) ነው። ሉቃስ ይሄንን በእሱ ወንጌል ላይ አስር ጊዜ እንዲሁም በሐዋ. ላይ ስድስት ጊዜ ተጠቅሞበታል (ዝከ 3፡7፤ 5፡10፤ 12፡23፤ 13፡11፤ 16፡26፣33)። እሱም ጥቅም ላይ የዋለው በማቴዎስ ሁለት ጊዜ ብቻ ሲሆን ሌላ ስፍራ በአኪ. አይገኝም። በሴፕቱዋጂንት በርካታ ጊዜያት ጥቅም ላይ ውሏል። ሉቃስ ዘይቤዎችንና ቃላትን ዘወትር ይጠቀማል፣ ከዚህ የግሪክ ትርጉም ከሆነው የዕብራይስጥ ብኪ። እሱም ብኪን በሚገባ የሚያውቅ መሆን አለበት፣ ይህም ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር ካለው ግንኙነት ወይም ከአዲስ አማኞች ክርስትና እምነት መግለጫ።

3፡8 **"ዘሎም ቀጥ ብሎ ቆመ"** ይህ የአሁን መካከለኛ ቦዝ አንቀጽ ነው (ዝከ ቁ.9). ይህ ሰው ይሄንን የመቅደስ ክፍል ዙሪያውን መራመድ ጀመረ። ወንጌልን ለመካፈል ምንኛ ዕድል ነው!

3፡10 እነሱ ይሄን ሰው ያውቁታል (ያልተጠናቀቀ የድርጊት አመላካች፣ ሰውየውን ያስተውሉት ጀመር)። ባዕድ ወይም እንግዳ አይደለም። በደጁ ላይ ከቀን ወደ ቀን የሚመለከቱት ነው፣ አልፈውት የሚሄዱት! ሆኖም፣ የኢየሱስ ተወካዮች አልፈውት አልሄዱም፣ በጸንጠቀስጤ ኃይል መሥራት ጀመሩ!

▣ **"እነሱም ተሞልተው"** ሉቃስ ይሄንን ቃል አዘውትሮ ይጠቀማል። ሰዎች በብዙ ነገሮች "ሊሞሉ" ይችላሉ (ማለትም ባሕርያቸው ሊሆን)።
1. ቁጣ፣ ሉቃስ 4፡28፤ 6፡11
2. ፍርሃት፣ ሉቃስ 5፡26
3. ቅናት፣ ሐዋ. 5፡17፤ 13፡45
4. ውዥንብር፣ ሐዋ 19፡29
5. መደነቅና መገረም፣ ሐዋ. 3፡10

6. *መንፈስ ቅዱስ፣* ሉቃስ 1፡15፣41፣67፤ ሐዋ. 2፡4፤ 4፡8፣31፤ 9፡17፤ 13፡9

ጴጥሮስና ዮሐንስ እነዚህን የተደነቁትን ፈልገዋቸዋል (እሱ አትኩሮታቸውን ስቧል) በወንጌል ለመሞላት!

▣ "*መደነቅና መገረም*" እነዚህ ነገሮች ደግሞ በሉቃስ ጽሑፎች የተለመዱ ናቸው፡፡

1. *መደነቅ፣ ታምቦስ* (thambos) ሉቃስ 3፡6፤ 5፡9፤ ሐዋ. 3፡10 እና *ኢክታምቦስ* (ekthambos) በ3፡11
2. *መገረም*
   *ሀ. ኢክስታሲስ፣* (*ekstasis*) ሉቃስ 5፡26፤ ሐዋ. 3፡10፤ 10፡10፤ 11፡5፤ 22፡17
   *ለ. ኢግዚስተሚ፣* (*existemi*) ሉቃስ 2፡47፤ 8፡56፤ 24፡22፤ ሐዋ. 2፡7፣12፤ 8፡9፣11፤ 9፡21፤ 10፡45፤ 12፡16

የእግዚአብሔር ፍቅር ዘወትር ያስደንቃል (እነዚህ የግሪክ ቃላት በሴፕቱዋጂንት ጥቅም ላይ የዋሉት በእግዚአብሔር ፍርሃትና መሸበር ላይ ነው፣ ዘፍ. 15፡12፤ ዘጸ. 23፡27፤ ዘዳ. 28፡28)፡፡

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 3፡11-16**
**[11]እርሱም ጴጥሮስንና ዮሐንስን ይዞ ሳለ፥ ሕዝቡ ሁሉ እየተደነቁ የሰሎሞን ደጅ መመላለሻ በሚባለው አብረው ወደ እነርሱ ሮጡ፡፡ [12]ጴጥሮስም አይቶ ለሕዝቡ እንዲህ ሲል መለሰ፡፡ የእስራኤል ሰዎች ሆይ፥ በዚህ ስለ ምን ትደነቃላችሁ? ወይስ በገዛ ኃይላችን ወይስ እግዚአብሔርን በመፍራታችን ይህ ይመላለስ ዘንድ እንዳደረግነው ስለ ምን ትኵር ብላችሁ ታዩናላችሁ? [13]የአብርሀምና የይስሐቅ የያዕቆብም አምላክ፥ የአባቶቻችን አምላክ፥ እናንተ አሳልፋችሁ የሰጣችሁትንና ሊፈታው ቈርጦ ሳለ በጲላጦስ ፊት የካዳችሁትን ብላቴናውን ኢየሱስን አከበረው፡፡ [14]እናንተ ግን ቅዱሱን ጻድቁንም ክዳችሁ ነፍሰ ገዳዩን ሰው ይሰጣችሁ ዘንድ ለመናችሁ፥ [15]የሕይወትንም ራስ ገደላችሁት፤ እርሱን ግን እግዚአብሔር ከሙታን አስነሣው፥ ለዚህም ነገር እኛ ምስክሮች ነን [16]በስሙም በማመን ይህን የምታዩትንና የምታውቁትን የእርሱ ስም አጸናው፥ በእርሱም በኩል የሆነው እምነት በሁላችሁ ፊት ይህን ፍጹም ጤና ሰጠው፡፡**

3፡11 "**እሱም ጴጥሮስን በያዘው ጊዜ**" ይህ የአሁን የድርጊት ቦዝ አንቀጽ ነው፡፡ እኔ እንደማስበው ጴጥሮስን የያዘው ልክ ማርያም ኢየሱስን በአትክልት ስፍራ እንደያዘችው ይመስለኛል (ዮሐንስ 20፡16-17)፡፡

▣ "**በሰሎሞን መመላለሻ ደጅ**" ይህ ረዥም ስፍራ በአሕዛብ ስፍራ በስተምስራቅ ያለ ነው (ጆሴፈስ አንቲክ 20.9.7)፡፡ ጣሪያው በብዙ ዐምዶች ተደግፏል፡፡ ስሙን ያገኘውም ከጥንታዊው የሰሎሞን ቤተ መቅደስ መሠረት ሲሆን፣ ያለውም በተመሳሳይ አጠቃላይ ቦታ ላይ ነው፡፡ ኢየሱስ እዚህ ዘወትር አስተምሯል (ዮሐንስ 10፡23)፡፡

3፡12 "**ጴጥሮስም ይሄንን ባየ ጊዜ**" እነሱ የሕዝቡን መደነቅና ንቁ መሆን ተመልክተው አጋጣሚውን ወንጌልን ለማካፈል ተጠቀሙበት (የአዲሷ ቤተክርስቲያን ሁለተኛ ስብከት)፡፡

▣ "'**የእስራኤል ሰዎች ሆይ**'" ጴጥሮስ እንዲህ ጠራቸው በ2፡22፡፡ ጴጥሮስ አሁንም ለአይሁድ ይናገራል፡፡

▣ "**ለምን...ለምን**" ጴጥሮስ ለምን በፈውሱ ተአምር በጣም እንደተደነቁ ጠየቀ፡፡ ኢየሱስ እንዲህ ዓይነቱን ተአምራት በሕይወቱ የመጨረሻ ሳምንት አላደረገምን?

ደግሞም፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ ራሳቸው እንዳደረጉት በአድናቆት ለምን ይመለከቷቸዋል? ይህ በወንጌል ኃይል እና በተነሣው መሲሕ የማመን ምልክት ነው፡፡

*መንፈስ ይሄንን ተአምር በብዙ ምክንያቶች አድርጓል፡፡*

1. የጴጥሮስንና የዮሐንስን መሪነት ለማረጋገጥ
2. ችግረኛውን ሰው ለመርዳት
3. በመቅደስ ለአይሁድ ለመመስከር

3፡13 "**የአብርሃም፣ የይስሐቅ እና የያዕቆብ አምላክ**" ይህ የሚያመለክተው የኢየሱስ አገልግሎት እና ወንጌል በእጅጉን የተያያዙት በእግዚአብሔር ኪዳንና የብሉይ ኪዳን ከሆኑት የቃል ኪዳኑ ሕዝቦች ጋር ነው፣ (ዘጸ. 3፡6፣15፤ ሉቃስ 20፡37)፡፡

ክርስትና የግድ ባሕርይ ማድረግ ያለበት በተመሳሳይ ተያያዥነት ወይም እድገት ከይሁዲነት ጋር ነው፡፡ ዘመናዊዎቹ አይሁድ ይሄንን የሚመለከቱት እንደ መዛባት ሲሆን፣ ነገር ግን የአኪ. ጸሐፊዎች የሚመለከቱት እንደ ፍጻሜ ነው፡፡ የኢየሱስ ተከታዮች "የአዲሱ ኪዳን" ተስፋ ፍሬዎች ናቸው፣ የኤር. 31፡31-34፡፡ እስራኤል ተልእኮዋን ስላልተወጣች፣ ለዓለም የካህናት መንግሥት መሆን የነበረባትን (ዘጸ. 19፡5-6)፡፡ ቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት ተሰጥቷታል (ማቴ. 28፡18-20)፡፡ የእግዚአብሔር ዓላማ በሰው ልጅ ያለውን የራሱን አምሳል መመለስ ሲሆን፣ ይህም የእሱ መነሻ ኅብረት ይፈጸማል፡፡ አንድ እግዚአብሔር ካለ (ማለትም  አሀድነት)፣ የተለየ ሕዝብ የለም ማለት ነው፣ የእግዚአብሔርን ሁለንተናዊ ዓላማ ለሁሉም የሰው ልጆች ያለውን የሚፈጽሙት አገልጋዮቹ ብቻ ናቸው፡፡

▣ "**አከበረው**" ይህን ቃል በብዙ መንገዶች መረዳት ይቻላል፡፡

1. የሽባው ሰው በኢየሱስ መፈወስ በኂላ የመጀመሪያው ቃል
2. ኢየሱስ መነሣቱና ከዚያም መክበሩን የሚያመላክት የጴጥሮስ ስብከት ረጅሙ ቃል
3. ስለ ኢየሱስ የሚመጣው መሲሕ መሆን የብኪ. ቃል

4. በዮሐንስ ወንጌል ይህ ቃል በራሱ በኢየሱስ ለትንሣኤው ዘወትር ጥቅም ላይ ውሏል (ዝከ 7፡39፤ 12፡10፣23፤ 13፡31-32፤ 16፡14፤ 17፡1)።

**ልዩ ርዕስ፡ ክብር**

የመጽሐፍ ቅዱሳዊው የ "ክብር" ጽንሰ ሐሳብ ለመግለጽ ያስቸግራል። የአማኞች ክብር፣ ከእግዚአብሔር የሆነውን የክብር ወንጌል ማወቅ ነው እንጂ በራሳቸው አይደለም (ዝከ. 1፡29-31፤ ኤር. 9፡23-24)።

በብኪ. በጣም የተለመደው ለዕብራይስጥ ቃል ለ "ክብር" (ከብድ kbd) በዋነኛነት ከጥንድ ሚዛኖች ጋር የተያያዘ የንግድ ቃል ነው ("ከባድ መሆን")። ከበድ የሚል ዋጋ ያለውና የሚጠቅም ነው። የብሩኅነት ጽንሰ ሐሳብ በቃሉ ላይ ይታከልበታል የእግዚአብሔርን ግርማ ለማሳየት (ዘጸ. 19፡16-18፤ 24፡17፤ ኢሳ. 60፡1-2)። እሱ ብቻውን ጠቃሚና የሚከበር ነው። እሱ ለወደቀው የሰው ልጅ ለመድረስ ግሩም ነው (ዘጸ. 19፡16-18፤ 24፡17፤ ኢሳ. 6፡5)። ያህዌ በእውነት ሊታወቅ የሚችለው በክርስቶስ በኩል ብቻ ነው (ኤር. 1፡14፤ ማቴ. 17፡2፤ ዕብ. 1፡3፤ ያዕ. 2፡1)።

"ክብር" የሚለው ቃል አሻሚነትም አለው፡ (1) ከ"የእግዚአብሔር ጽድቅ" ጋር ተነጻጻሪ ነው፤ (2) እሱም ምናልባትም የሚያጣቅሰው ከእግዚአብሔር ቅድስና ወይም "ፍጹምነት" ጋር ነው፤ ወይም (3) የሰው ልጅ ከተፈጠረበት ከእግዚአብሔር አምሳል ጋር ያመላክታል (ዘፍ. 1፡26-27፤ 5፡1፤ 9፡6)፣ ነገር ግን ቆይቶ በዐመጽ ምክንያት ወደቀ (ዘፍ. 3፡1-22)። በመጀመሪያ ጥቅም ላይ የዋለው በያህዌ መገኘት ከሕዝቡ ጋር በምድረ በዳ በሚዞሩበት ጊዜ፣ በዘጸ. 16፡7፣10፤ ሌዋ. 9፡23፤ እና ዘኁ. 14፡10።

▣ **"የእሱ አገልጋይ"** "አገልጋይ" የሚለው ቃል (ፔየስ በሰባ LXX) በብኪ ለክብር ማዕርግ ነው የዋለው፣ ለያዕቆብ፣ ሙሴ፣ ኢያሱ፣ እና ዳዊት (መዝ. 105፤ ሉቃስ 1፡69)። ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው በኢሳይያስ የአገልጋዮች መዝሙር ነው። (42፡1-5፤ 49፡1-7፤ 50፡4-11፤ 52፡13-53፡12) ለ (1) ለእስራኤል ሕዝብ (ዝከ 41፡8-9፤ 42፡19፤ 43፡10፤ 44፡1፣21፤ እንዲሁም LXX ሉቃስ 1፡54) እና (2) የእግዚአብሔር መሲሕ (ዝከ 42፡1፤ 52፡13፤ 53፡11)። እዚህ ጋ ግልጽ የሆነ ልዩነት አለ፣ በተጠናቀረውና በግለሰባዊው ገጽታ መካከል፣ በተለይም በመጨረሻው መዝሙር ላይ (ኢሳ. 52፡13-53፡12)። በጽሑፉ እስራኤልን አያመለክትም።

1. ሕዝቡ መቤዥትን ለማምጣት ታማኝ ሊሆን አልቻለም፣ ምክንያቱም ሕዝቡ መፍርድ ላይ ስለወደቀ (ኢሳ. 53፡8መ)
2. ሴፕቱዋጂንት "አንተ" የሚለውን በኢሳ. 52፡14 ወደ "እሱ" ለውጦታል፣ (እንዲሁም በቁ. 15)። የአይሁድ ትርጉም ከክርስቶስ ልደት በፊት (ይህም 250-150 ዓ.ዓ) ጽሑፉን የሚመለከተው እንደ መሲሐዊና እንደ ግለሰብ ነው።
   *ፔየስ ጥቅም ላይ የዋለው ለኢየሱስ እንደ አገልጋይ)መሲሕ ነው፣* በሐዋ. 3፡13፣26፤ 4፡27፣30!

▣ **"ኢየሱስ"** ኢየሱስ በራሱ ጥቅም ላይ ሲውል፣ ዘወትር አጽንዖት የሚሰጠው ሰውነቱን ነው (ዝከ ቁ. 6)።

▣ **"እናንተም አሳልፋችሁ የሰጣችሁትና የካዳችሁት"** "እናንተ" የሚለው ግነት ነው! የአይሁድ መሪዎች ብቻ አልነበሩም ለኢየሱስ ሞት ተጠያቂዎች (ዝከ ቁ. 17፡2፡23)። ጴጥሮስ የተለየ ማጣቀሻ ለሕዝቡ በጲላጦስ ስላደረጉት ያደርግ ነበር (ሉቃስ 23፡18-25)። ከእነዚህ አንዳንዶቹ እዚያ እንደነበሩ መገመት ይቻላል፣ ነገር ግን ጴጥሮስ ሕዝቡን በጥቅሉ ተጠያቂነት እንዳለባቸው ያመለክታል (ዝከ ቁ. 15)። የእግዚአብሔር የተመረጡ ሕዝቦች (አይሁድ) የእግዚአብሔርን መሲሕ "አሳልፈው ሰጡት" "ካዱትም"።

▣ **"ጲላጦስ"** ከታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

**ልዩ ርዕስ፡ ጴንጤናዊው ጲላጦስ**

I. ሰውየው
   ሀ. የትውልድ ቦታውና ዘመኑ አልታወቀም
   ለ. ከኢኮስትሪያን ተራ ነበር (ከከፍተኛው መካከለኛ መደብ ከሮሜ ኅብረተሰብ)
   ሐ. ያገባ ግን ልጆች እንዳሉት ግን ያልታወቀ
   ሠ. ቀደም ሲል የነበረው ሹመት ( በርካታ እንደሚሆን ይገመታል) አልታወቀም
II. ስብዕናው።
   ሀ. ሁለት የተለያዩ አመለካከቶች
      1. ፊሎ (ሌጋሾ እና ጌዩም፣ 299-305) እና ጆሴፈስ (አንቲክ. 18.3.1 እና የአይሁድ ጦርነቶች 2.9.2-4) የሚፈርጁት እንደ ጨካኝ እንደማይራራ ዐምባ ገነን ነው።
      2. አኪ. (ወንጌላት፣ ሐዋ.) ደካማ፣ በቀላሉ የሚሸነፍ የሮሜ ገዥ
   ለ. *ፖል ባርኔት፣ ኢየሱስና የጥንት ክርስትና አነሣስ፣* ገጽ 143-148 ስለ እነዚህ ሁለት ዓይነት አተያዮች ግሩም ማብራሪያ አለው።

1. ጲላጦስ በገዥነት ተሹሞ የነበረው በ26 ዓ.ም በጥብርዮስ ሥር ነበር፣ እሱም የአትሁድ ደጋፊ የነበረው (ፊሎ፣ ሴጋሾ እና ጌዩም፣ 160-161)፣ ነገር ግን በሴጃነስ፣ ጽብርዮስ ጸረ-አይሁድ አማካሪ።
2. ጥብርዮስ ለ ኤል. ኤሊየስ ሴጃነስ የፖለቲካ ሥጣኑን አጥቶ ነበር፣ ፕራቶሪያን የአስተዳደር ሹም እሱም ከዘውዱ ጀርባ እርግጠኛው ባለ ሥልጣን የሆነ፣ እናም አይሁድን የሚጠላ (ፊሎ ሴጋሾ እና ጌዩም፣ 159-160)።
3. ጲላጦስ በሲጃኖስ የተተካና እሱን ለመማረክ የሚጣጣር ነው፡
   ሀ. የሮሜን ደንቦች ወደ ኢየሩሳሌም አምጥቷል (26 ዓ.ም)፣ ሌሎቹ ገዥዎች ያላደረጉትን። እነዚህ የሮሜ ጣዖታት ምልክቶች አይሁድን አበሳጫቸው (ጆሴፈስ፣ አንቲክ. 18:31፤ የአይሁድ ጦርነቶች 2.9.2-3)።
   ለ. ሳንቲቦችን ማተም (29-31 ዓ.ም)በራሳቸውም ላይ የሮሜ አምልኮ ያለባቸው። ጆሴፈስ እንደሚለው፣ እሱ ሆን ብሎ የአይሁድን ሕግጋትና ልማድ ለማጥፋት ሞክሯል (ጆሴፈስ፣ አንቲክ. 18.4.1-2)።
   ሐ. በኢየሩሳሌም የመጠጥ ውኃ ቦይ ለማሠራት ከመቅደስ ገንዘብ ወስዷል (ጆሴፈስ፣ አንቲክ. 18.3.2፤ የአይሁድ ጦርነቶች 2.9.3)።
   መ. በርካታ ገሊላውያን በኢየሩሳሌም በፋሲካ መሥዋዕት ሲያቀርቡ ተገድለዋል (ሉቃስ 13:12)።
   ሠ. የሮሜን መከላከያዎች በ31 ዓ. ም ወደ ኢየሩሳሌም አምጥቷል። የታላቁ ሄሮድስ ልጅ እንዲያስወግዳቸው አመለከተ፣ ነገር ግን እሱ እምቢ አለ፣ ስለሆነም ለጥብርዮስ ደብዳቤ ጻፉ፣ በባሕር አድርገው ወደ ቂሳርያ እንዲመለሱ (ፊሎ ሴጋሾ እና ጌዩም፣ 299-305)።
   ረ. በርካታ ሳምራውያን በጌሬዛን ተራራ ላይ ታርደዋል፣ (36)37 ዓ.ም) ለሃይማኖታቸው የሚሆን የጠፉ ንዋያተ ቅዱሳን ሲፈልጉ። ይህም ጲላጦስ በአገሬው ላይ የበላይ እንዲሆን አበቃው (ቪቴሊየስ፣ የሶርያ የአስተዳደር ሹም) ከሥልጣኑ ሽሮ ወደ ሮሜ አሰናበተው (ጆሴፈስ፣ አንቲክ. 18. 4.1-2)።
   ሰ. ሴጂነስ በ31 ዓ.ም ተገደለ፣ እናም ጥብርዮስ ቦታውን ለመያዝ ተመለሰ፤ ስለሆነም፣ ቁ. 1፣2፣3 እና 4 ሊደረጉ የሚችሉት በጲላጦስ ነው፣ የሳጃነስን አመኔታ ለማግኘት። ቁጥር 5 እና 6 የጥብርዮስን አመኔታ ለማግኘት ታስበው ሲሆን ዳሩ ግን ወደ ራሱ ሳይመለሱ አቀሩም።
   ሸ. አፍቃሪ አይሁድ ገዥ መመለሱ እውነት ነው፣ ደግሞም ከጥብርዮስ ለአገረ ገዥዎቹ፣ ለአይሁድ ገራም ይሆኑላቸው ዘንድ ግልጽ ደብዳቤ ተልኳል (ፊሎ ሴጋሾ እና ጌዩም፣ 160-161)፣ ያም የአይሁድ መሪዎች በኢየሩሳሌም ያሉት፣ ጲላጦስ ከጥብርዮስ ጋር ያለውን የፖለቲካ ባላንጣነት በመጠቀም ኢየሱስ እንዲሰቀል ተጭነውታል። የባረንት ንድፈ-ሐሳብ በጲላጦስ ላይ ያሉትን ሁለት አተያዮች በግሩም አኳኋን አንድ ላይ ያሳያል።

III. የእሱ ዕጣ-ፈንታ
   ሀ. ከጥብርዮስ ሞት በኋላ ወዲያውኑ ወደ ሮም ተመለሰ (37 ዓ.ም)
   ለ. ድጋሚ አልተሾመም
ሐ. ከዚህ በኋላ ሕይወቱ አይታወቅም። ኋላ ላይ የመጡ በርካታ ሐሳቦች ቢኖሩም እውነትነታቸው አልተረጋገጠም።

▣ **"እሱ ሊፈታው ፈልጎ ሳለ"** ይህ የሚያመለክተው ሉቃስ 23:4፣14፣22፣ ጲላጦስ ሦስት ጊዜ፣ "በዚህ ሰው ምንም በደል አላገኘሁበትም" ካለ በኋላ፣ እንዲሁም ሦስት ጊዜ ሊፈታው ከፈለገ በኋላ ነው (ሉቃስ 23:16:20፣22)። በርካታ ሊቃውንት እንደሚያምኑት ሐዋርያት ሥራ ለማሳየት የተጻፈው የሮሜ ሹሞች ኢየሱስን ሕግን ተላላፊ ሆኖ እንዳላገኙት ነው። ጲላጦስ በአይሁድ አመራሮች ተገዶ ራሱ ሊያደርግ ያልፈለገውን አድርጓል።

**3:14 "ቅዱሱንና ጻድቁን ሰው"** ይህ የኢየሱስን ፍጹምነትና በደል የለሽነት ያሳያል። ምርመራው የቁጣ ነበር። ይህም ሌለኛው የብኪ መሲሐዊ ማዕርግ ነው (ኢሳ. 53:11፤ ሐዋ. 7:52፤ 22:14፤ ዮሐንስ 6:69)። አጋንንት ኢየሱስን አንተ የእስራኤል ቅዱሱ በማለት ማርቆስ 1:24፤ ሉቃስ 4:34 ላይ ጠርተውታል።

**ልዩ ርዕስ፡ የተቀደሰው**
'ቅዱስ' የሚለው የሚያመለክተው
1. እግዚአብሔር አብን ሊሆን ይችላል (አብዛኛው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት 'የእስራኤል ቅዱስ' ብለው ይጠሩታል።
2. እግዚአብሔር ወልድን ሲያመለክት ይችላል (ማር 1:24፤ ሉቃ 4:34፤ ዮሐ 6:69፤ የሐዋ 3:14)።
3. እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ሊያመለክት ይችላል (ዮሐ 1:33፤ 14:26፤ 20፤22)።

በሐዋ 10:38 ላይ ሦስቱም ስላሴዎች በመቀባት ሥራ ውስጥ ተሳትፈዋል። ኢየሱስ ቀብቶ ነበር ሉቃ 4:18፤ የሐዋ 4:17፤ 10:38)። በ1ዮሐ 2:27 ላይ ደግሞ ሁሉንም አማኞች የሚያጠቃልል ነው። የተቀባው የተቀባ ይሆናል። ይህ ከክርስቶስ ተቃዋሚ ጋር በተነፃፃሪነት የተገለፀ ነው። (1ዮሐ 2:18) በበሉይ ኪዳን በአካል ላይ

ዘይትን በመቀባት የሚደረግ ተምሳሌታዊ ነገር አለው፡፡ (ዘፀ 29፡7፤ 30፡25፤ 37፡29) የሚያመለክተው ለተለየ ዓላማ ተጠርተው በእግዚአብሔር ብቁ እንዲሆኑ የተጠሩትን ነው፡፡ (ነቢያት፣ ካህናት እና ነገስታት) ክርስቶስ የሚለስ ቃል የተተረጎመው 'የተቀባ' ወይም 'መሲህ' ማለት ነው፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ ጽድቅ**

"ጽድቅ" የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ የግድ ተከታታይ የሆነ የግል ጥናት በጽንሰ ሐሳቡ ላይ ማድረግ ያለበት ወሳኝ ርዕስ ነው፡፡

በብኪ የእግዚአብሔር ባሕርይ የሚገለጸው "ትክክለኛ" ወይም "ጻድቅ" በሚል ነው፡፡ ሜሶፖታሚያዊው ቃል ራሱ የመጣው ከወንዝ ዳር ሸንበቆ ሲሆን፣ የግድግዳና የአጥርን አግድሞሽ ቀጥተኛነት መለኪያ የሚሆን የግንባታ መሣርያ ነው፡፡ እግዚአብሔር ቃሉን በዘይቤነት ለራሱ ባሕርይ መጠሪያ እንዲሆን መርጦታል፡፡ እሱ ቀጥተኛ የሆነ (የማስመሪያ) ጫፍ ነው፣ በእሱም ሁሉም ነገር የሚመዘንበት፡፡ ይህ ጽንሰ ሐሳብ የእግዚአብሔርን ጽድቅ ይገልጻል፣ እንዲሁም ለመፍረድም ሥልጣን እንዳለው፡፡

ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር አምሳል ነው (ዘፍ. 1፡26-27፤ 5፡1፣3፤ 9፡6)፡፡ የሰው ልጅ የተፈጠረው ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲኖረው ነው፡፡ ሁሉም ፍጥረታት የተዘጋጀውና ያለው ለእግዚአብሔር እና ለሰው ልጆች መስተጋብር ተብሎ ነው፡፡ እግዚአብሔር ልዕለ ፍጡሩን ይፈልገዋል፣ የሰው ልጅ፣ እንዲያውቀው፣ እንዲወደው፣ እንዲያገለግለው፣ እንዲሁም እሱን እንዲመስል! የሰው ልጅ ታማኝነት ተፈትኗል (ዘፍ. 3)፣ እናም ሁለቱ ዋነኛ ጥንዶች ፈተናውን ወድቀዋል፡፡ ይህም በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል ያለውን ግንኙነት አበላሽቶታል (ዘፍ. 3፤ ሮሜ 5፡12-21)፡፡

እግዚአብሔር ኅብረቱን ለማደስና ለመመለስ ቃል ገብቷል (ዘፍ. 3፡15)፡፡ ይህንንም ያደረገው በራሱ ፍቃድና በራሱ ልጅ ነው፡፡ ሰዎች የተጣሰውን ሊመልሱት አልቻሉም (ሮሜ 1፡18-3፡20)፡፡

ከውድቀት በኋላ፣ የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ርምጃ፣ ለተሐድሶው የኪዳናዊ ጽንሰ-ሐሳብ የተመሠረተው በእሱ ግብዣና በሰው ልጅ የንስሐ፣ የእምነት፣ የመታዘዝ ምላሽ ነው፡፡ በውድቀት ምክንያት፣ ሰዎች ተገቢ ድርጊት ለመፈጸም አልቻሉም (ሮሜ 3፡21-31፤ ገላ. 3)፡፡ እግዚአብሔር ራሱ መነሻውን ወስዷል፣ ኪዳን አፍራሽ የሆኑትን የሰው ልጆች ለመመለስ፡፡ ይሄንንም ያደረገው

1. ኃጢአተኛውን ሰው በክርስቶስ ሥራ በኩል ጻድቅ አድርጎ <u>ማወጅ</u> (የፍርድ ጽድቅና)
2. <u>በነጻ የተሰጠ</u> የሰው ልጅ ጽድቅ በክርስቶስ ሥራ በኩል (የተሰጠ ጽድቅ)
3. <u>የተሰጠ</u> የሚያድረው መንፈስ ጽድቅን ይፈጥራል (ሥነ ምግባራዊ ጽድቅ) በሰው ልጆች፡፡
4. <u>መመለስ</u> የኤደን ገነት ኅብረት በክርስቶስ የእግዚአብሔርን አምሳል መለሰ (ዘፍ. 1፡26-27) በአማኞች (ግንኙነታዊ ጽድቅ)፡፡

ሆኖም፣ እግዚአብሔር ኪዳናዊ ምላሽ ይፈልጋል፡፡ እግዚአብሔር አውጇል (በነጻ ሰጥቷል) እናም ይሰጣል፣ የሰው ልጆች ግን <u>የግድ</u> ምላሽ መስጠት አለባቸው እንዲሁም በምላሻቸው መቀጠል በ

1. ንስሐ
2. እምነት
3. በሕይወት ኑሮ መታዘዝ
4. መጽናት

ጽድቅ፣ ስለዚህ ኪዳናዊ ነው፣ በእግዚአብሔርና በልዕለ ፍጡሩ መካከል ያለ ሁለትዮሽ ድርጊት፡፡ እሱም የተመሠረተው በእግዚአብሔር ባሕርይ፣ በክርስቶስ ሥራ፣ በመንፈስ አስቻይነት፣ ይህም እያንዳንዱ ሰው በግሉ እና በቀጣይነት በተገቢው ምላሽ መስጠት ያለበት ነው፡፡ ጽንሰ ሐሳቡም "በእምነት መጽደቅ" ይባላል፡፡ ጽሥሰ ሐሳቡ በወንጌላት ተገልጿል፣ ነገር ግን በእነዚህ ቃልት አይደለም፡፡ እሱም በመጀመሪያ የተገለጠው በጳውሎስ ሲሆን እሱም የግሪኩን ቃል "ጽድቅ" ን በተለያየ መልኩ ከ100 ጊዜ በላይ ተጠቅሟል፡፡

ጳውሎስ የሠለጠነ ራቢ እንደ መሆኑ መጠን፣ ዲካዮሱኔ (dikaiosun) የሚለውን ቃል በዕብራይስጥ አገባቡ SDQ በሴፕቱዋጂንት ጥቅም ላይ የዋለውን፣ ከግሪክ ሥነ ጽሑፍ ሳይሆን፡፡ በግሪክ ጽሑፎች ቃሉ የሚያያዘው፣ ለአንዱ የመለኮት ተስፋ በኅብረተሰቡ ዘንድ ለማረጋገጥ ነው፡፡ በዕብራይስጥ አግባቡ ዘወትር የኒያያዘው ከኪዳናዊ ቃላት ጋር ነው፡፡ ያህዌ ፍትሐዊ፣ ሥነምግባራዊ፣ ግብረገባዊ አምላክ ነው፡፡ እሱም ሕዝቦቹ የሱን ባሕርይ እንዲያንጸባርቁ ይሻል፡፡ የተቤዠ የሰው ልጅ አዲስ ፍጥረት ሆኗል፡፡ ይህ አዲስነት ውጤቱ አዲስ የመልካምነት የሕይወት ስልት ያሳያል (የሮማን ካቶሊክ የጸድቅ ትኩረት)፡፡ እስራኤል ቲዎክራሲያዊ (የአምላክ መንግሥት) እንደመሆኑ መጠን በሥጋዊ (የኅብረተሰቡ ደንቦች) እና በተቀደሰው (የእግዚአብሔር ፍቃድ) መካከል እንዲሁም "በጽድቅ" (ከሃይማኖት ጋር በተያያዘ) ግልጽ የሆነ መለያ የለውም፡፡ ይህ ልዩነት የሚገለጠው በዕብራይስጥና በግሪክ ቃላት ነው፣ እነርሱም ወደ እንግሊዝኛ ሲተረጎሙ "ፍትሕ" (ከኅብረተሰቡ ጋር በተያያዘ) እንዲሁም "ጽድቅ" (ከሃይማኖት ጋር በተያያዘ)፡፡

ወንጌል (መልካም የምስራች) የኢየሱስ፣ የወደቀው የሰው ልጅ ወደ እግዚአብሔር ኅብረት መመለሱን ነው፡፡ የጳውሎስ አያም (ፓራዶክስ) የሚሆነው፣ እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል በደልን ማስወገዱ ነው፡፡ ይህም ሊገኝ የሚችለው በእግዚአብሔር ፍቅር፣ ምሕረት፣ እና ጸጋ ሲሆን፣ የልጁ ሕይወት፣ ሞት፣ እና ትንሣኤ፤ እንዲሁም የመንፈስ መቃተትና ወደ ወንጌል መሳብ ነው፡፡ ጽድቅ የእግዚአብሔር ነጻ ድርጊት ነው፣ ነገር ግን መልካምነትን ሊያመነጭ ይገባል (የአውግስጢኖስ አቋም፣ እሱም የሚያሳየው ሁለቱንም፣ የተሐድሶ አጽንኦት በነጻ ወንጌል ላይ

እና የሮማን ካቶሊክ አጽንኦት በተለወጠ ሕይወት በፍቅርና በታማኝነት ላይ ነው)፡፡ ለባለ ተሐድሶዎች ቃሉ "የእግዚአብሔር ጽድቅ" ተጨባጭ ባለ መብትነትን ሲያሳይ (ማለትም፣ ኃጢአተኛውን የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ተቀባይነት እንዲያገኝ የማድረግ ሥራ [አቋማዊ ቅድስና])፣ ለካቶሊክ ደግሞ የተሳቢ ባለመብትነት ነው፣ ይህም እግዚአብሔርን የመምሰል ሂደት ነው፣ (ተሞክሯዊ ተራማጅ ቅድስና ነው)፡፡ በተጨባጭ ግን ሁለቱም ነው!!

በእኔ አስተያየት መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ ከዘፍ. 4-ራዕይ 20 የተመዘገበው እግዚአብሔር የኤደንን ኅብረት እንደሚመልስ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔርና በሰው ልጅ ኅብረት በምድራዊ መቼት ይጀምራል፣ (ዘፍ. 1-2) እናም መጽሐፍ ቅዱስ በተመሳሳይ መቼት ነው የሚያበቃው (ራዕ. 21-22)፡፡ የእግዚአብሔር አምሳልና ዓላማ ይመለሳል!

የላይኛውን ማብራሪያ ለማጠቃለል የሚከተሉትን የተመረጡ የአኪ. ምንባቦችን የግሪኩ ቃለት ምድብ የሚያመላክቱትን እይ፡፡

1. እግዚአብሔር ጻድቅ ነው (ዘወትር የሚያያዘው እግዚአብሔር እንደ ፈራጅ ነው)
   ሀ. ሮሜ 3፡26
   ለ. 2ኛ ተሰሎንቄ 1፡5-6
   ሐ. 2ኛ ጢሞቲዎስ 4፡8
   መ. ራዕይ 16፡5
2. ኢየሱስ ጻድቅ ነው
   ሀ. ሐዋርያት ሥራ 3፡14፤ 7፡52፤ 22፡14 (የመሲሕ ማዕርግ)
   ለ. ማቲዎስ 27፡19
   ሐ. 1ኛ ዮሐንስ 2፡1፣29፤ 3፡7
3. የእግዚአብሔር ሐሳብ ለፍጥረቱ ጽድቅ ነው
   ሀ. ሌዋውያን 19፡2
   ለ. ማቲዎስ 5፡48 (ዝክ 5፡17-20)
4. የእግዚአብሔር ጽድቅን የመስጠትና የመፍጠር አግባብ
   ሀ. ሮሜ 3፡21-31
   ለ. ሮሜ 4
   ሐ. ሮሜ 5፡6-11
   ሠ. ገላትያ 3፡6-14
   ረ. በእግዚአብሔር የተሰጠ
      1) ሮሜ 3፡24፤6፡23
      2) 1ኛ ቆሮንቶስ 1፡30
      3) ኤፌሶን 2፡8-9
   ሰ. በእምነት የሚቀበሉት
      1) ሮሜ 1፡17፤3፡22፣26፤ 4፡3፣5፣13፤ 9፡30፤ 10፡4፣6፣10
      2) 1ኛ ቆሮንቶስ 5፡21
   ሸ. በልጁ ሥራ በኩል
      1) ሮሜ 5፡21-31
      2) 2ኛ ቆሮንቶስ 6፡14
      3) ፊሊፕስዩስ 2፡6-11
5. የእግዚአብሔር ፍቃድ ተከታዮቹ ጻድቅ እንዲሆኑ ነው
   ሀ. ማቲዎስ 5፡3-48፤ 7፡24-27
   ለ. ሮሜ 2፡13፤ 5፡1-5፤ 6፡1-23
   ሐ. 2ኛ ቆሮንቶስ 6፡14
   ሠ. 1ኛ ጢሞቲዎስ 6፡11
   ረ. 2ኛ ጢሞቲዎስ 2፡22፤ 3፡16
   ሰ. 1ኛ ዮሐንስ 3፡7
   ሸ. 1ኛ ጴጥሮስ 2፡24
6. እግዚአብሔር ዓለምን በጽድቅ ይፈርዳል
   ሀ. ሐዋ. 17፡31
   ለ. 2ኛ ጢሚቲዎስ 4፡8

ጽድቅ የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው፣ በክርስቶስ በኩል ለኃጢአተኛው የሰው ልጅ በነጻ የተሰጠ፡፡ እሱም

1. የእግዚአብሔር ደንብ
2. የእግዚአብሔር ስጦታ
3. የክርስቶስ ድርጊት ነው፡፡

ነገር ግን እሱ ደግሞ ጻድቅ የመሆን ሂደት፣ ያም በጽናት እና በብርታት መያዝ ያለበት ነው፤ አንድ ቀን በክርስቶስ ዳግም ምጽዓት የምንቀዳጀው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ኅብረት በደኅንነት ይመለሳል፣ ነገር ግን ሂደቱ በሕይወት ዘመን ሁሉ ፊት ለፊት ይገኛል በሞት ወይም በፓሮሲያ!

እዚህ መልካም ጥቅስ አለ፣ ከጳውሎስና ጽሑፎቹ መዝገበ ቃላት የተጠቀሰ አይ ቪ ፒ

"ካልቪን፣ ከሉተር ከፍ ባለ መልኩ አጽንዖት የሚሰጠው ግንኙነታዊ በሆነው የእግዚአብሔር ጽድቅ

ገጽታ ላይ ነው፡፡ የሉተር አተያይ በእግዚአብሔር ጽድቅ ላይ፣ ከጥፋተኝነት ነጻ መሆንን ገጽታ የያዘ ይመስላል፡፡ ካልቪን አጽንዖት የሚሰጠው የእግዚአብሔርን ጽድቅ ለእኛ ያለውን አስደናቂ አፈጣጠር ከግንኙነት ወይም ከተካፋይነት አኳያ ነው" (ገጽ 834)፡፡

እንደ እኔ የአማኝ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት ሦስት ገጽታዎች አሉት፡

1. ወንጌል አካል ነው (የምስራቅ ቤተ ክርስቲያንና የካልቪን አጽንዖት)
2. ወንጌል እውነት ነው (የአውግስጢኖስና የሉተር አጽንዖት)
3. ወንጌል የተለወጠ ሕይወት ነው (የሮማን ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አጽንዖት)

ሁሉም እውነት ናቸው እናም አንድ ላይ መያዝ ይኖርባቸዋል፣ ለጤናማ፣ ትርጉም ላለው፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና፡፡ ማንም በጣም አጽንዖት ከሰጠ ወይም ካንኳሰሰ ችግሮች ይፈጠራሉ፡፡

ኢየሱስን መቀበል ይኖርብናል!

ወንጌልን ማመን ይኖርብናል!

ኢየሱስን መምሰል ይኖርብናል!

▣ **"ነፍሰ ገዳዩን ለመናችሁ"** በርናባስ፣ ኢየሱስን በከሰሱበት በብጥብጥ ወንጀል ትክክለኛው ወንጀለኛ መሆኑ ውስጠ ወይራ ነው (ሉቃስ 23፡18-19፣23-25)፡፡

3፡15

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት** | **"የሕይወት ራስ"** |
| **አየተመት፣ አኢት** | **"የሕይወትን ፈጣሪ"** |
| **አእት** | **"ወደ ሕይወት የሚመራው"** |
| **አኢመቅ** | **"የሕይወት ራስ"** |
| **ሞፋት** | **"የሕይወት ፈላሚ"** |

ርዕሱ የሚያሳየው የአርኪጎስን (arch□gos) ከሦስቱ አንደኛውን ፍች ነው፡ (1) ፈጣሪ ወይም መገኛ (አየተመት፣ ዕብ. 2፡10፤ 12፡2)፤ (2) የፍጥረታት መገኛ (ዮሐንስ 1፡3፤ 1ኛ ቆሮ. 8፡6፤ ቆላ. 1፡16፤ ዕብ. 1፡2)፤ ወይም (3) ቀድሞ የሚሄድ የመፈተኛ እሳት (አእት፣ አእመቅ፣ ሞፋት፣ ሐዋ 5፡31፡፡ ቃሉ "ከነፍሰ ገዳይ" ጋር ፈጽሞ የሚቃረን ነው (ቁ. 14)፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ *መሪ/ደራሲ/ጀማሪ (Archegos)***

'ደራሲ' ወይም 'መሪ' የሚለው ቃል የመጣው *Archegos* (አርኬጎስ) ከሚባል የግሪክ ቃል ነው፡፡ 'በመጀመሪያ' (አርኬ) ከሚል ከግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን 'መሄድ' ወይም 'መምራት' (ኤጎ) የሚል ትርጉም አለው፡፡ ይህም ዓረፍታ ነገር እንደ ገዥ ወይም አለቃ ወይም መሪ (ሰዎችን ወይም መላዕክቶችን) ለመግለጽ ይጠቅም ነበር፡፡ ቃሉም በአዲስ ኪዳን ውስጥ ብቻ ጥቅም ላየ ውሏል፡፡

1. አለቃ ወይም ጀማሪ ሐዋ 3፡15
2. አለቃ ወይም መሪ ሐዋ 5፡21
3. የእምነታችን ፈጻሚ ዕብ 2፡10
4. ደራሲ (ቀዳሚ) እና የእምነታችን ፈጻሚ ዕብ 12፡2

ኢየሱስ የደህንነታችን ጀማሪ፣ አቅራቢ እና ፈጻሚ ነው፡፡

▣ **"እግዚአብሔር ከሞት ያስነሣው"** በአኪ. ዘወትር አብ ወልድን ከሙታን ያስነሣው የኢየሱስን ሕይወት፣ ትምህርት፣ እና ምትካዊ ሞት መቀጽደቁን ምልክት ነው፡፡ አኪ. ደግሞም የሚያረጋግጠው ሦስቱም የሥላሴ አካላት በኢየሱስ ትንሣኤ ላይ ተሳታፊ መሆናቸውን ነው፡፡ (1) መንፈስ (ሮሜ 8፡11)፤ (2) ወልድ (ዮሐንስ 2፡19-22፤ 10፡17-18)፤ እና (3) አብ (ሐዋ 2፡24፣32፤3፡15፣26፤ 4፡10፤ 5፡30፤ 10፡40፤ 13፡30፣33፣34፣37፤ 17፡31፤ ሮሜ 6፡4፣9)፡፡ ይህ የጥንቱ ስብከተ ወንጌል ዋነኛው ሥነመለኮታዊ ገጽታ ነው፡፡ ይህ እውነት ካልሆነ፣ ሌላው ሁሉ እውነት አይደለም (1ኛ ቆሮ. 15፡12-19)፡፡

▣ **"እኛም ምስክር የሆንንለት እውነት"** ይህ አንድም (1) ዋነኛ ምንጭን አጽንዖት የሰጠ ነው፤ እነዚህ አድማጮች የዓይን ምስክሮች ናቸው (ዝከ 2፡22) ወይም (2) በላይኛው ክፍል የነበሩትን ሐዋርያትና ደቀ መዛሙርት የሚያመለክት ነው፣ (ዝከ 1፡22፤ 2፡32)፡፡ በቁጥር 2 ላይ ያለው ጽሑፍ የተሻለ ይመስላል፡፡

3፡16 **"በእምነት መሠረት ላይ"** የግሪኩ ቃል "እምነት" (ፒስቲስ pistis) ወደ እንግሊዝኛ ሲተረጎም "እምነት" "መታመን" ወይም "ማመን" ነው፡፡ እሱም የሰዎች ሁኔታዊ ምላሽ፣ ለእግዚአብሔር ሁኔታ ያልሆነ ጸጋ የሚሰጥ ነው (ኤፌ. 2፡8-9)፡፡ እሱም በመሠረቱ የአማኙ መታመን በሚገባው በእግዚአብሔር ማመን ነው (ማለትም፣ የሱን ባሕርይ፣ ቃል ኪዳኑን፣ መሲሑን) ወይም የእግዚአብሔርን ታማኝነት መታመን ነው! በፈውስ ላይ በወንጌልና በሐዋ. በተቀመጡት መንፈሳዊነትን ማኖር አስቸጋሪ ነው፣ (ማለትም፣ ኪዳናዊ) የሁኔታውን ገጽታ፡፡ እነዚህ የተፈወሱት ሁሉ ሁሌም "ላይድኑ" ይችላሉ (ዮሐንስ 5)፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ እምነት (ፒስትስ pists [ስም]፣ ፒስቱ pisteuq [ግሥ]፣ ፒስቶስ [pistos [ቅጽል])**

ሀ. ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ አስፈላጊ የሆነ ቃል ነው (ዕብ. 11፡1፣6)። የኢየሱስ ስብከት ፊተኛ ርዕሰ ጉዳይ ነው (ማርቆስ 1፡15)። እዚህጋ ሁለት አዲስ ኪዳናዊ መስፈርቶች አሉ፡ ንስሐ እና እምነት (ዝክ 1፡15፤ ሐዋ. 3፡16፣19፤ 20፡21)።

ለ. ሥርወ ቃሉ

1. "እምነት" የሚለው ቃልበብኪ ታማኝነት፣ እውነተኝነት፣ ወይም መታመን እና የእግዚአብሔር ባሕርይ መግለጫ ማለት ነው፣ የእኛ ሳይሆን።
2. የተገኘውም ከዕብራይስ ቃል (ኢሙን፣ ኢሙናህ) ከሚለው ሲሆን፣ ፍችውም "ርግጠኛ መሆን ወይም መጽናት" ማለት ነው። የሚያድን እምነት የአእምሮ ጉዳይ ነው (የእውነት መገኘት)፣ የግብረ ገብ ኑሮ፣ (የአኗኗር ስልት)፣ እና በቅድሚያ ግንኙነታዊ የሆነ (ሰውን መቀበል) እና በፍላጎት ላይ የሆነ ቁርጠኝነት (ውሳኔ) ለዚያ ሰው ነው።

ሐ. የብኪ አጠቃቀሙ

አጽንዖት መስጠት ያለበት የአብርሃም እምነት በሚመጣው መሲሕ ላይ አለመሆኑ ነው፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ተስፋ እሱም ልጅና ዝርያ እንደሚኖረው (ዘፍ. 12፡2፤ 15፡2-5፤ 17፡4-8፤ 18፡14)። አብርሃም ለእግዚአብሔር ተስፋ ምላሽ በመስጠት አመነ። ስለ ተስፋው ጥርጣሬና ችግር ቢኖርበትም፣ ለመፈጸም አስራ ሦስት ዓመት ፈጅቷል። የእሱ ፍጹም ያልሆነ እምነት፣ ሆኖም፣ በእግዚአብሔር ተቀባይነት አግኝቷል። እግዚአብሔር በወደቁ የሰው ልጆች ጋር ሲሠራ ፍቃደኛ ነው ለእሱና ለተስፋው በእምነት ምላሽ ለሚሰጡ፣ ከሰናፍጭ ቅንጣት ያነሰ ቢሆንም (ማቴ. 17፡20)።

መ. የአኪ አጠቃቀሙ

"አመነ" የሚለው ቃል ከግሪክ ቃል (ፒስቴዩ pisteu) የመጣ ሲሆን እንዲሁም ሊተረጎም የሚችለው "እምነት" "መታመን" ወይም "ማመን" ይሆናል። ለምሳሌ፣ ስሙ በዮሐንስ ወንጌል አልተከሰተም፣ ነገር ግን ግሡ ዘወትር ጥቅም ላይ ይውላል። በዮሐንስ 2፡23-25 የተሰበሰቡት ሰዎች የናዝሬቱ ኢየሱስን እንደ መሲሕ መቀበል ላይ ርግጠኛ ያለመሆን ይታያል፣ ከቅንነት አኳያ ። ሌላ የቃሉ ግልብ አጠቃቀም "ማመን" ደግሞ በዮሐንስ 8፡31-59 እና ሐዋ. 8፡13፣ 18፡24 ላይ አለ። እውነተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ እምነት ከመነሻው ምላሽ ከፍ ይላል። በደቀ መዝሙራዊ ሂደት መከተል ይኖርበታል (ማቴ. 13፡20-22፣ 31-32)።

ሠ. መስተጻምሩ

1. ኢስ (eis) ማለት "ወደ ውስጥ" ማለት ነው። ይህ የተለየ አወቃቀር አጽንዖት የሚሰጠው አማኞች እምነታቸውን)በታመናቸውን በኢየሱስ ላይ ማድረግ እንዳለባቸው ነው።
   ሀ. በስሙ (ዮሐንስ 1፡12፤ 2፡23፤ 3፡18፤ 1ኛ ዮሐንስ 5፡13)
   ለ. በእሱ (ዮሐንስ 2፡11፤ 3፡15፣18፤ 4፡39፤ 6፡40፤ 7፡5፣31፣39፣48፤ 8፡30፤ 9፡36፤ 10፡42፤ 11፡45፣48፤ 17፡37፣42፤ ማቴ. 18፡6፤ ሐዋ. 10፡43፤ ፊሊጵ. 1፡29፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡8)
   ሐ. በእኔ (ዮሐንስ 6፡35፤ 7፡38፤ 11፡25፣26፤ 12፡44፣46፤ 14፡1፣12፤ 16፡9፤ 17፡20)
   መ. በልጁ ላይ (ዮሐንስ 3፡36፤ 9፡35፤ 1ኛ ዮሐንስ 5፡10)
   ሠ. በኢየሱስ (ዮሐንስ 12፡11፤ ሐዋ. 19፡4፤ ገላ. 2፡16)
   ረ. በብርሃን (ዮሐንስ 12፡36)
   ሰ. በእግዚአብሔር (ዮሐንስ 14፡1)
2. ኢን (en) ማለት "ውስጥ" ማለት ነው እንደ ዮሐንስ 3፡15፤ ማርቆስ 1፡15፤ ሐዋ. 5፡14
3. ኢፒ (epi) ማለት "ውስጥ" ወይም በላይ ማለት ነው፣ እንደ ማቴ. 27፡42፤ ሐዋ. 9፡42፤ 11፡17፤ 16፡31፤ 22፡19፤ ሮሜ 4፡5፣24፤ 9፡33፤ 10፡11፤ 1ኛ ጢሞ. 1፡16፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡6
4. ቀጥተኛ ያልሆነው ተሳቢ ግሥ ጉዳይ ያለ ምንም መስተጻምር እንደ ገላ. 3፡6፤ ሐዋ. 18፡8፤ 27፡25፤ 1ኛ ዮሐንስ 3፡23፤ 5፡10
5. ሆቲ (hoti) ማለት "ማመን ብሎም" ለሚያምኑበት ይዘት መስጠት
   ሀ. ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቅዱሱ (ዮሐንስ 6፡69)
   ለ. ኢየሱስ እኔ ነኝ ነው (ዮሐንስ 8፡24)
   ሐ. ኢየሱስ በአብ ይኖራል እንዲሁም አብ በእሱ ይኖራል (ዮሐንስ 10፡38)
   መ. ኢየሱስ መሲሕ ነው (ዮሐንስ 11፡27፤ 20፡31)
   ሠ. ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው (ዮሐንስ 11፡27፤ 20፡31)
   ረ. ኢየሱስ በአብ የተላከ ነው (ዮሐንስ 11፡42፤ 17፡8፣21)
   ሰ. ኢየሱስ ከአብ ጋር ያለ ነው (ዮሐንስ 14፡10-11)
   ሸ. ኢየሱስ ከአብ ዘንድ የመጣ ነው (ዮሐንስ 16፡27፣30)
   ቀ. ኢየሱስ ራሱን ሲገልጥ በአብ ኪዳናዊ ስም ነው፣ "እኔ ነኝ" ብሎ ነው (ዮሐንስ 8፡24፤ 13፡19)
   በ. ከእሱ ጋር እንኖራለን (ሮሜ 6፡8)

ተ. ኢየሱስ ሞቶ ዳግም ተነሥቷል (1ኛ ተሰ. 4፡14 )

▣ የቁ. 16 ሁለተኛው ክፍል የተመለከተው በተመሳሳይ ንጽጽሮሽ ነው፣ ከዕብራይስጥ የጥበብ ሥነ ጽሑፍ በሚመሳሰል መልኩ።

1. ሀ. "የኢየሱስ ስም"
   ለ. "ይሄንን ሰው አጸናው"
   ሐ. "እናንተ ያያችሁትንና የምታውቁትን"
2. ሀ. "በእሱ በኩል የሆነ እምነት"
   ለ. "ይህንን ፍጹም ጤና ሰጠው"
   ሐ. "በእናንተ በሁላችሁ ፊት"

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 3:17-27**

**[17]አሁንም፥ ወንድሞቼ ሆይ፥ እናንተ እንደ አለቆቻችሁ ደግሞ ባለማወቅ እንዳደረጋችሁት አውቄአለሁ፤ [18]እግዚአብሔር ግን ክርስቶስ መከራ እንዲቀበል አስቀድሞ በነቢያት ሁሉ አፍ የተናገረውን እንዲሁ ፈጸመው። [19-20]እንግዲህ ከጌታ ፊት የመጽናናት ዘመን እንድትመጣላችሁ አስቀድሞም ለእናንተ የመረጠውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲልክላችሁ፥ ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሐ ግቡ ተመለሱም። [21]እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በቅዱሳን ነቢያቱ አፍ የተናገረው፥ ነገር ሁሉ እስከሚታደስበት ዘመን ድረስ ሰማይ ይቀበለው ዘንድ ይገባልና። [22]ሙሴም ለአባቶች። ጌታ አምላክ እኔን እንዳስነሣኝ ነቢይን ከወንድሞቻችሁ ያስነሣላችኋል፤ በሚነግራችሁ ሁሉ እርሱን ስሙት። [23]ያንም ነቢይ የማትሰማው ነፍስ ሁሉ ከሕዝብ ተለይታ ትጠፋለች አለ። [24]ሁለተኛም ከሳሙኤል ጀምሮ ከእርሱም በኋላ የተናገሩት ነቢያት ሁሉ ደግሞ ስለዚህ ወራት ተናገሩ። [25]እናንተ የነቢያት ልጆችና እግዚአብሔር ለአብርሃም። በዘርህ የምድር ወገኖች ሁሉ ይባረካሉ ብሎ፥ ከአባቶቻችን ጋር ያደረገው የኪዳን ልጆች ናችሁ። [26]ለእናንተ አስቀድሞ እግዚአብሔር ብላቴናውን አስነሥቶ፥ እያንዳንዳችሁን ከክፋታችሁ እየመለሰ ይባርካችሁ ዘንድ፥ ሰደደው።**

**3:17** "*እናንተም ባለማወቅ እንዳደረጋችሁት አውቄአለሁና*" ይህ የሚያንጸባርቀው ኢየሱስ በመስቀል ላይ የተናገረውን ቃል ነው (ሉቃስ 23:34)። ሆኖም፣ በእነሱ ያለማወቅ፣ ሕዝቡ አሁንም በመንፈስ ተጠያቂዎች ናቸው! በአንድ በኩል ይህ ይቅርታ፣ ሰዎች ኃላፊነታቸውን እንዲቀበሉ የሚረዳ መንገድ ነው (ዝከ 13:27፤ 17:30፤ 26:9፤ 1ኛ ቆሮ. 2:8)። ለጽንሰ ሐሳቡ የተሻለ ማብራሪያ ሚላርድ ኢሪክሰን፣ የክርስቲያን ሥነ መለኮት፣ 2ኛ እትም ገጽ 583-585 ተመልከት።

▣ "*የእናንተ መሪዎች እንዳደረጉት ሁሉ*" ሉቃስ ዘወትር ልዩነትን በሕዝቡና በመሪዎቻቸው መካከል ያደርጋል (ሉቃስ 7:29-30፤ 23:35፤ ሐዋ. 13:27፤ 14:5)። ይህንን ለማድረግ ተገቢ የሆነው ጉዳይ ምናልባት መግባባታዊ የሆነ የሁለቱም ወገኖች ኃላፊነት ነው። ሁሌም እንደሚባለው ኢየሱስ አይሁድን በሙሉ እለኮነነም፣ ነገር ግን የእነሱን ሕገወጥ መሪዎች ነው፣ (ማለትም፣ ከአሮን ወገን ያልሆኑትን)። የበለስ ዛፏ ርግማን መሆኑን ለማወቅ አስቸጋሪ ነው (ማርቆስ 11:12-14፣ 20-24) እና የበደነኞቹ የወይን ቦታ አራሾች ምሳሌ (ሉቃስ 20:9-18) የአንደኛው ክፍለ ዘመን የይሁዲነት ርግማን እንደሆነ ወይም የመሪዎቹ ብቻ። ሉቃስ ለማሳየት የሚፈልገው ሁለቱንም ይመስላል!

**3:18** "*ቀደም ሲል እንደተነገረው*" ወንጌል የእግዚአብሔር ኋላ የመጣ ሐሳብ አይደለም፣ ነገር ግን ዘላለማዊ፣ ዓላማዊ እቅድ ነው (ዘፍ. 3:15፤ ማርቆስ 10:45፤ ሮሜ 1:2፤ ተሰ. 2:22፤ ሐዋ. 2:23፤ 3:18፤ 4:28)። የሐዋ. ቀደምት ስብከቶች (ስብከተ ወንጌል) ኢየሱስን የሚያቀርቡት የብሉ. ትንቢታት ፍጻሜ አድርገው ነው።

የጥንታዊ ስብከተ ወንጌል በርካታ ገጽታዎች አሉ (ማለትም፣ ዋናው የሥነ መለኮት ገጽታ ስብከቶች በሐዋርያት ሥራ) የተገለጡት በእነዚህ ቁጥሮች ነው።

1. በኢየሱስ ማመን አስፈላጊ ነው
2. የኢየሱስ አካልና ሥራ በብሉ. ነቢያት ተተንብዮአል
3. መሲሑ የግድ መከራ መቀበል አለበት
4. ንስሐ መግባት አለባቸው
5. ኢየሱስ ዳግም ይመጣል

▣ "*እግዚአብሔር ቀደም ብሎ በሁሉም ነቢያት አንደበት ተናግሯል*" ኢየሱስ የብሉን ትንቢት ፈጸመው (ዝከ ቁ. 34፣ ማቴ. 5:17-48)። እንደ እኔ ኢየሱስ ራሱ ለሁለቱ በኢማኦስ መንገድ ላይ አሳይቷቸዋል (ሉቃስ 24:13-35) የብሉ ትንቢቶች ስለ እሱ መከራ፣ ሞት፣ እና ትንሣኤ የተናገሩት ስለ መፈጸማቸው። ይሄንን ከሐዋርያት ጋር ተካፍለዋል፣ የስብከታቸው ክፍል ካደረጉት። ልዩ ርዕስ፡ የአኪ. ትንቢት 11:27 ተመልከት።

▣ "*ክርስቶስ*" ይህ የግሪክ ትርጉም፣ የዕብራይስጡ ቃል "መሲሕ" ሲሆን፣ የተቀባው ማለት ነው። ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ልዩ ወኪል፣ ሕይወትና ሞቱ አዲሱን የጽድቅ ዘመን የሚመርቀውን ነው፣ አዲሱ የመንፈስ ዘመን።

▣ "*መከራ መቀበል*" ይህ በብዙ የብሉ. ጽሑፎች ይገኛል (ዘፍ. 3:15፤ መዝ. 22፤ ኢሳ. 53)። የመሲሑ የመሠቃየት ገጽታ አይሁድን አስገርሚቸዋል (1ኛ ቆሮ. 1:23)። እነሱ ይጠብቁ የነበሩት ድል አድራጊ የጦር መሪ ነበር (ራዕ. 20:11-16)። ይህ ጳውሎሳዊ አጽንዖት ነው፣ (ሐዋ. 17:3፤ 26:23) እንዲሁም ጴጥሮሳዊ (1ኛ ጴጥ. 1:10ጥ12፤ 2:21፤ 3:18)።

**3:19** "*ንስሐ ግቡ ተመለሱ*" የግሪኩ ቃል "ንስሐ" ማለት የአስተሳሰብ ለውጥ ነው። ይህም ያልተጠናቀቀ የድርጊት ተተኳሪ ነው፣ (የሚታኖ metanoeō)። የዕብራይስጡ ቃል ለንስሐ ማለት "የድርጊት ለውጥ" ነው፣ ("ተመለሱ"

[emistrephō] ሊያንጸባርቅ የሚችለው የዕብራይስጡን “መመለስ” ሹብ ነው፣ ዘኁ. 30፡36፤ ዘዳ. 30፡2፣10) በሴፕቱዋጂንት። ንስሐ በእምነት መዳንን በተመለከተ አስፈላጊ ኪዳን ነው (ማርቆስ 1፡15 እና ሐዋ. 3፡16፣19፤ 20፡21)። ንስሐ በጣም አስፈላጊ ነው (ሉቃስ 13፡3 እና 2ኛ ጴጥ. 3፡9)። እሱም በመሠረቱ ለመለወጥ ፍቃደኝነት ነው። እሱም የሰው የፍቃደኝነት ድርጊትና የእግዚአብሔር ጸጋ ነው (ሐዋ. 5፡31፤ 11፡18፤ 2ኛ ጢሞ.2፡25)። 2፡38 ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

▣ **“ኃጢአት ሁሉ ይወገዳል”** ይህ ቃል “መደምሰስ” ማለት ነው፤ “ማጥፋት” (ቆላ. 2፡14፤ ራዕ. 3፡5፤ 7፡17፤ 21፡4)። ምን ያለው ቃል ኪዳን ነው! በቀደመው ዓለም ቀለም አሲድነት ስለነበረው ለማጥፋት ያስቸግር ነበር። ይህ የእግዚአብሔር ጸጋ እውነተኛ ተአምር ነው (መዝ. 51፡1፤ 103፡11-13፤ ኢሳ. 1፡18፤ 38፡17፤ 43፡25፤ 44፡22፤ ኤር. 31፡34፤ ሚክ. 7፡19)። እግዚአብሔር ይቅር ካለ፣ ይረሳዋል (ያጠፋዋል)!

3፡20 **“የመታደስ ዘመን”** የግሪኩ ቃል (anapsuch, anapsuxis) በመሠረቱ “የመናፈሻ ስፍራ፣ መዝናኛ፣ ማረፊያ” ማለት ነው (ቤከር፣ አርንድት፣ ጂንጀሪች፣ እና ዳንከር፣ የግሪክ እንግሊዝኛ ሥርወ ቃል፣ ገጽ 63)፣ “ዓየር መቀበል” ወይም “ቁስልን ማናፈስ፣ ኪትል፣ የአዲስ ኪዳን ሥነመለኮታዊ መዝገበ ቃላት፣ ቅጽ 9፣ ገጽ 663)። ዘይቤአዊ ስፋቱ ሥጋዊ ወይም መንፈሳዊ መታደስ ወይም መመለስ ነው።

በሴፕቱዋጂንት ጥቅም ላይ የዋለው ከውጊያ በኋላ አካላዊ ኃይልን መልሶ ለማግኘት ነው (ዘጸ. 23፡12፤ መሳ. 15፡19፤ 2ኛ ሳሙ. 16፡14) ወይም የስሜት መታደስ ነው፣ እንደ 1ኛ ሳሙ. 16፡23።

የጴጥሮስ ማመሳከሪያ የብኪ ተስፋዎችን ይመስላል፣ ነገር ግን ሐረጉ በብኪ ጥቅም ላይ አልዋለም። ለበረሀ ሰዎች ወጪ የሚገለጸው በነጻነትና በደስታ ነው፣ ባንጻሩ በቦታ መከለል ያለመመቸትና የችግር ምልክት ነው። እግዚአብሔር ሰፋ ያለ የሚያድስ የመንፈሳዊ ድርጊት ሊያመጣ ነው። መሲሐዊ ድርጊት በወንጌል መጥቷል። “የመታደስ ዘመን” በናዝሬቱ ኢየሱስ መጥቷል። ሆኖም መጨው መቀዳጀት አዲሱን የመንፈስ ዘመን ያመጣል። በተለየው ጽሑፍ ጴጥሮስ ዳግም ምጽዓቱን ጠቅሷል። ይህ ሐረግ “የመታደስ ዘመን” ከሚለው ጋር አቻዊ ነው፣ ቁ. 21)። ልዩ ርዕስ፤ ስብከተ ወንጌል 2፡14 ተመልከት።

▣ **“እሱም ኢየሱስን ልኮታል”** ይህ የድርጊት የአሁን የሁኔታ ግሥ ነው፣ የመጠባበቂያ ክፍልን የሚገልጽ። የጴጥሮስ አድማጮች ድርጊት፣ በአንድ መልኩ መንፈሳዊ መቀዳጀትን ይወስነዋል (ኤፍ. ኤፍ. ብሩስ፣ ጥያቄና መልሶች፣ እሱም ሐዋ. 3፡19-21 ከሮሜ 11፡25-27 ጋር በማያያዝ፣ ገጽ 201)።

ከጎኑ የመሆን አቋም (“የኢየሱስ” ማዕርግ) ከ “ክርስቶስ)መሲሑ” ቀጥሎ የሚመስለው፣ የጴጥሮስ ትርጉም በተለይ የሚለው የናዝሬቱ ኢየሱስን መሲሕነት ይመስላል። በኋላም በአኪ፣ “ጌታ” እና “ክርስቶስ ይሆናል፣ ባብዛኛው የተደባለቀ ማጣቀሻ፣ ለኢየሱስ (ማለትም፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ) ከዚያም ይልቅ ለመሲሑ ማዕርግ አጽንዖት በመስጠት። ይህም በተለይ ባመዛኙ በአሕዛብ አብያተ ክርስቲያናት ነው።

▣ **“ክርስቶስ ለእናንተ የተመረጠው”** ይህ የተጠናቀቀ ተገብሮ ቦዝ አንቀጽ ነው። ይሄው ተመሳሳይ ቃል ለእግዚአብሔር ቅድም ምርጫ በ10፡41፤ 22፡14፤ 26፡16፤ ጥቅም ላይ ውሏል፤ የኢየሱስ መምጻትና መሞት የእግዚአብሔር ዘላለማዊ የመቤዠት ዕቅድ ነው (ዝከ 2፡23፤ 3፡18፤ 4፡28፤ 13፡29)።

በሴፕቱዋጂንት ይህ ቃል የሚያመለክተው ምርጫን ነው፣ ነገር ግን ቀደም ብሎ ሳይታወቅ (ማለትም፣ ሉቃስ “ቀደም” ሲል በፊት ማለቱ ነው፣ ዘጸ. 4፡13 እና ኢያ. 3፡12)፣ ይህም በሐዋ. ላይ ያለው የዚህ ቃል አጠቃቀም ነው። እሱም ሊሆን የሚችለው ኢየሱስን መላኩ የእግዚአብሔር የመባረክና የመዋጀት ምርጫ ነው!

3፡21

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት** | **“ሰማይ ሊቀበለው ይገባልና”** |
| **አየተመት** | **“በሰማይ ሊሆን ይገባዋልና”** |
| **አእት፣ አኢት** | **“እሱም በሰማይ ሊሆን ይገባዋልና”** |
| **አኢመቅ** | **“ሰማይ ሊቀበለው ይገባልና”** |

የዚህ ሐረግ ባለቤት “ሰማይ” ነው፤ ተሳቢው “ማን” (እሱም ኢየሱስ)። ሁለት የግሥ ዓይነቶች በዚህ ሐረግ ውስጥ ይገኛሉ። የመጀመሪያው ዲይ፣ ከዲኦ፣ እሱም “አስፈላጊ” ወይም “ተገቢ” ማለት ነው።

ሁለተኛው የድርጊት መካከለኛ (አረጋጋጭ) ንዑስ አንቀጽ ነው፣ የዲኮማይ። ሃሮልድ ኬ ሙልቶን፣ የተከለሰው የግሪክ ሥርወ ቃል ትንታኔ፣ ስለዚህ ጽሑፍ ሲገልጽ “ወደ ውስጥ መቀበል እና ማጽናናት” ማለት ነው፣ (ገጽ 88)። የእንግሊዝኛቹ ትርጉሞች የጽሑፉን ገጽታ እንዴት እንደነቀሱት ማየት ይቻላል። ሉቃስ ከማንኛውም የአኪ ጸሐፊ ይሄንን ቃል በብዛት ተጠቅሟል (13 ጊዜ በሉቃስና 8 ጊዜ በሐዋ.)። ቃላት መገለጽ ያለባቸው በሞላ ጽሑፉ የአጠቃቀም አግባብና አንድምታ እንጂ በሥርወ ቃል አይደለም። ሥርወ ቃላት (መዝገበ ቃላት) አጠቃቀምን ብቻ ነው የሚያሳዩት። ትርጉምን አያሳዩም!

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **“እስከ”** |
| **አኪጀት፣ አየተመት፣ አእት** | **“እስከ”** |
| **አኢመቅ** | **“እስከ”** |

ይህ ቃል በግሪክ የተመቅሶ[4] ጽሑፍ ውስጥ ነው። አአመመቅ በኢታሊክ ሆሄ ለምን እንዳስቀመጠው አይገባኝም፣ ይህም በግሪክ ጽሑፍ ውስጥ እንደማይገኝ የሚያሳየው፣ ነገር ግን ለእንግሊዝኛ ተናጋሪዎች ለመረዳት የተጨመረ።

በ1970 የአአመመቅ ትርጉም፣ "ው… ይቱ" (the) በኢታሊክስ ሆሄ ነው፣ "እስከ" ሳይሆን፣ እሱም ትክክለኛ።

▣ ***"የሁሉም ነገር የመታደስ ዘመን"*** *ይህ የሚያሳየው መታደስን ነው* (ማቴ. 17፡11፤ እና በተለይም ሮሜ 8፡13-23)። በዘፍ. 3 ያለው የሰዎች የዐመጸኝነት ክፋት ተሰርዞ ተፈጥሮ ተመለሰ፤ ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ኅብረት ዳግም ተመሠረተ። የተፈጥሮ መነሻ ዓላማ በመጨረሻ ተፈጸመ።

▣ ***"እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በቅዱሳን ነቢያቱ አንደበት እንደተናገረው"*** የማርቆስ ወንጌል የሚጀምረው ከሚል. 3፡1 በመጥቀስ ነው። ማቴዎስ 1፡22-23 የሚያሳየውም የኢሳ. ትንቢት 7፡14 ነው። ሉቃስ ይሄንኑ ሐረግ በሉቃስ 1፡70 ላይ ተጠቅሟል። የስብከተ ወንጌል አንደኛው ገጽታ (ማለትም፣ በሐዋ. ስብከት ላይ በድጋሚ የታየ ሥነመለኮታዊ እውነት ነው፣ ልዩ ርዕስ 2፡14 ተመልከት) የኢየሱስ ልደት፣ ሕይወት፣ ሞት፣ እና ትንሣኤ የብሊ.ኪ ትንቢት ተፈጻሚ አድርጎታል። የኢየሱስ አገልግሎት ኋላ የመጣ ሐሳብ ወይም ሁለተኛ እቅድ አይደለም። የእግዚአብሔር የቀድሞ ውሳኔ እቅድ እንጂ (ዝከ 2፡23፤ 3፡18፤ 4፡28፤ 13፡29)። ሁሉም ነገር እየሠራ ያለው እግዚአብሔር ለፍጥረት ያለውን ፍቃድ ለመመለስ ነው።

3፡22 ***"ሙሴ እንዳለው"*** "ነቢይ" የሚለው ማዕርግ ጥቅም ላይ የዋለው ለሚመጣው መሲሕ ነው (ዘዳ. 18፡14-22፤ በተለይም 15፣18፤ ዮሐንስ 1፡21፣25)። ይህ ከሙሴ ሕግ ሰነድ በኢየሱስ የተጠቀሰ (ማለትም፣ ለአይሁድ በእጅጉን ታላቅ የሆነ የብሉ. ጽሑፍ ነው፣ ለአይሁድ፣ ለሰዱቃውያንም ሆነ ለፈሪሳውያን) ለእነዚህ አይሁድ አድማጮችም በጣም ጠቃሚ ነው። ኢየሱስ ዘወትር የእግዚአብሔር የመቤዡቱ እቅድ ነው። የመጣው ሊሞት ነው (ማርቆስ 10፡45፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡21)።

3፡23 ይህ የማስጠንቀቂያ ጽኑ ቃል ነው። ከዘዳ. 18፡19 የተጠቀሰ ነው። ኢየሱስን አለመቀበል ፊትም አሁንም ጽኑ ዘላለማዊ ጉዳይ ነው።

ይህ ከዘዳ. 18፡14-22 የተጠቀሰው በተጨማሪም ጠቃሚ የሥነመለኮት ይዘት አለው።

1. የተናጠልም ሆነ ጥቅሉን ገጽታ ተመልከት። እያንዳንዱ ነፍስ ለመሲሑ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል። የእስራኤል አጠቃላይ አካል ክፍል መሆን ብቻውን በቂ አይደለም።
2. "ጨርሶ መደምሰስ" የሚለው ሐረግ ለ "ቅዱስ ጦርነት" መጥቀሻ ነው። እግዚአብሔር የራሱን ወይን ያጠራል (እስራኤል፣ ሮሜ 9-11)። "ነቢዩን" የሚንቁ በእግዚአብሔር ይናቃሉ። የደኅንነት ጉዳይ አንዱ ለእግዚአብሔር መሲሕ ምላሽ ሲሰጥ ነው። ቤተሰብ፣ ዘር፣ ግብረ ገብ እና የሕግጋት ማራኪ አፈጻጸም፣ የአዲሱ ኪዳን መስፈርቶች አይደሉም፣ በኢየሱስ ያለ እምነት እንጂ።

3፡24 ***"ሳሙኤል"*** በአይሁድ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደ *"ፊተኞቹ ነቢያት"* ነው የሚታየው፣ የሁለተኛው ምድብ የዕብራየስጥ ቅዱሳን መጻሕፍት ክፍል። ሳሙኤል ነቢይ ተብሎ ይጠራል፣ በ1ኛ ሳሙ. 3፡20 እና ደግሞ ባለ ራዕይ (ለነቢይ ሌለኛው ቃል) 1ኛ ሳሙ. 9፡9፤ 1ኛ ዜና 29፡29።

▣ ***"እነዚህ ቀናት"*** "የመታደስ ዘመን" (ቁ. 20) እና "የሁሉን ነገር የመመለሻ ዘመን" (ቁ. 21) የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን መንግሥት መቀዳጀት ነው፣ በክርስቶስ ዳግም ምጽዓት፣ ነገር ግን ይህ ሐረግ የሚያመላክተው የመሲሑን መንግሥት መመረቅ ነው፣ ይህም የኢየሱስን ሥጋ መልበስ በቤተ ልሔም ወይም የሁለት ጊዜያት አጠቃላይ ዘመን፣ ይህም የክርስቶስ በበዚህ ምድር ላይ ሁለት ምጽዓቶች መካከል ነው። ብኪ. በዋነኛነት የሚረዳው አንደኛውን የመሲሕ ምጽዓት ብቻ ነው። የመጀመሪያ ምጽዓቱ "መከራ እንደሚቀበል አገልጋይ" (ቁ. 18) አስገራሚ ነው፤ የእሱ ግርማ የተሞላው እንደ ጦር መሪ እና ፈራጅ ሆኖ የሚመጣው ተጠብቆ ነበር።

3፡25 ጴጥሮስ አይሁድን የተናገራቸው እንደ አብርሃም ልጆች ነው፣ የኪዳኑ ሕዝቦች። ሆኖም፣ እነዚህ የኪዳኑ ሕዝቦች ምላሻቸውን በእምነትና በንስሐ ለኢየሱስና ለወንጌል መስጠት ይኖርባቸዋል፣ አለበለዚያ ይናቃሉ (ቁ. 23)!

አኪ. (አዲስ ኪዳን) የሚያተኩረው በግለሰብ እንጂ በዘር ወገን ላይ አይደለም። በአብርሃም መጠራት እንኳ አጠቃላይ ይዘት ነበር (ዘፍ. 12፡3)። ሁለንተናዊው ስጦታ በክርስቶስ መጥቶ ለሁሉም ይገኛል (ማለትም፣ ሉቃስ በመጀመሪያ የጻፈው ለአሕዛብ ነበር። የእሱ ወንጌልና ሐዋ. ይሄንን ግብዣ በተደጋጋሚና በተለየ መልኩ አድርጓል)።

▣ ***"ኪዳን"*** ልዩ ርዕስ፡ ኪዳንን በ2፡47 ተመልከት።

▣ ***"ሁሉም የዓለም ወገኖች ይባረካሉ"*** ይህ የሚያመላክተው የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ለአብርሃም፣ በዘፍ. 12፡1-3 ያለውን ነው። በዘፍ. 22፡18 የሚገኘውን አጠቃላይ ይዘት ተመልከት። እግዚአብሔር አብርሃምን የመረጠው ሕዝቡን ለመምረጥ ነው፣ ዓለምን ለመምረጥ (ዘጸ. 19፡5-6፤ ኤፌ. 2፡11-3፡13)።

3፡26 ***"ለእናንተ በቅድሚያ"*** አይሁድ፣ በኪዳናዊ ውርሳቸው ምክንያት፣ የወንጌልን መልእክት ለመስማት እና ለመረዳት ቀዳሚ እድል ተሰጥቷቸዋል (ሮሜ. 1፡16፤ 9፡5)። ሆኖም፣ ምላሽ መስጠት ያለባቸው መንገድ እንደሌላው ነው፡ ንስሐ፣ እምነት፣ የጥምቀት ታዛዥነት፣ እና ጽናት።

▣ ***"አገልጋዩን አስነሥቶ ላከው"*** 2፡24 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

▣ ***"እናንተን ለመባረክ"*** ይህ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሁሉ የሚፈልገው ነው (ዘፍ. 12፡3)። ሆኖም፣ ኢየሱስን በቅድሚያ ለጠፉት የእስራኤል በጎች ላከው!

▣ ***"እያንዳንዳችሁን ከክፉ መንገዳችሁ ለመመለስ"*** ደኅንነት የሚያካትተው የአስተሳሰብ ለውጥ፣ በኃጢአት ላይ ሆኖ በውጤቱም የድርጊትና የቅደም ተከተል ለውጥ ነው። ይህ ለውጥ የትክክለኛ መቀየር እውነተኛ ማስረጃ ነው! ዘላለማዊ ሕይወት የሚታይ ባሕርይ አለው።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወስን አይደለም።

1. "ቀጣይነት" ምን ማለት ነው?
2. ፊውሱ ኃይለኛ የሆነው ለምንድነው?
3. መከራ የሚቀበለው መሲሕ ለአይሁድ አስደንጋጭ ለምን ሆነ?
4. ሉቃስ ዘፍ. 12፡3 ለምን ጠቀሰ?
5. አይሁድ ከአሕዛብ በተለየ መልኩ ይድናሉን?

# የሐዋርያት ሥራ 4

## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንቀጽ ምድቦች

| የተየመቅሰ[4] | አኪጀት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጴጥሮስና ዮሐንስ በሸንጎ ፊት | ጴጥሮስና ዮሐንስ ታሰሩ | የጴጥሮስና የዮሐንስ መታሰርና መፈታት | ጴጥሮስና ዮሐንስ በሸንጎ ፊት | ጴጥሮስና ዮሐንስ በፍርድ ችሎት |
| 4:1-4 | 4:1-4 | 4:1-4 | 4:1-4 | 4:1-4 |
| | በችሎት ላይ መናገር | | | |
| 4:5-22 | 4:5-12 | 4:5-12 | 4:5-7 | 4:5-12 |
| | የኢየሱስ ስም ተከለከለ | | 4:8-12 | |
| | 4:13-22 | 4:13-22 | 4:13-17 | 4:13-17 |
| | | | 4:18-22 | 4:18-22 |
| አማኞች ለግልጽነት ጸለዩ | ለግልጽነት ጸሎት | | አማኞች ለግልጽነት ጸለዩ | በስደት ላይ የሐዋርያት ጸሎት |
| 4:23-31 | 4:23-31 | 4:23-31 | 4:23-30 | 4:23-26 |
| | | | | 4:27-31 |
| | | | 4:31 | |
| ሁሉም ነገር በጋራ | ሁሉንም ነገር መካፈል | ቁሳቁሶችን መጋራት | አማኞች ያላቸውን ተከፋፈሉ | የጥንታዊ ክርስቲያኖች ማኅበረሰብ |
| 4:32-37 | 4:32-37 | (4:32-5:6) | 4:32-35 | 4:32 |
| | | 4:32-5:11 | | |
| | | | | 4:33 |
| | | | | 4:34-35 |
| | | | | የበርናባስ ለጋስነት |
| | | | 4:36-37 | 4:36-37 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ከ "መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ" ገጽ vii)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. ምንባብ አንድ
2. ምንባብ ሁለት
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

**ጽሑፋዊ ይዘት**

ሀ. በሐዋ. የምዕራፍ አከፋፈሉ ተገቢ እንዳይደለ ግልጽ ነው።
ለ. ቁጥር 1-31 የሚያስረዳው በምዕራፍ 3 ያለውን የሽባውን መፈወስና ያስከተለውን ውጤት ነው።
ሐ. ቁጥር 32-37 የሚሄዱት ከምዕራፍ 5:1-11 ጋር ነው።
መ. ችግሮቹ ቀጥለዋል፣ በዝተዋልም፣ ነገር ግን የመንፈስ ጸጋና ኃይልም እንዲሁ። ቤተ-ክርስቲያን አድጋለች!
ሠ. የሉቃስ አጽንዖት በኢየሩሳሌም በነበረችው ጥንታዊት ቤተ-ክርስቲያን የፍቅርና የለጋስነት ተፈጥሮ ላይ፣ ዘመናዊዎቹ የምዕራባውያን ተርጓሚዎች ከካፒታሊስት አድሏዊ አመለካከት መጠበቅ አለባቸው። ሉቃስ ለማጽናት የሚሻው ፍቃደኛ መግባባትን ነው። ሐዋ. ኮሚኒዝምንም ሆነ ካፒታሊዝምን አይደግፍም፣ ምክንያቱም ሁለቱም በዚያን ሰዓት ስለማይታወቁ ነው። ጽሑፉ መተርጎም ያለበት በጊዜው ብርሃን፣ በጸሐፊው የልብ ሐሳብ፣ እንዲሁም በአድማጮቹ ዘመን ነው።

**የቃልና የሐረግ ጥናት**

> **አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 4:1-4**
> **[1]ለሕዝቡም ሲናገሩ የካህናት አለቆችና የመቅደስ አዛዥ ሰዱቃውያንም፥ [2]ሕዝቡን ስለ አስተማሩና በኢየሱስ የሙታንን ትንሣኤ ስለ ሰበኩ ተቸግረው፥ ወደ እነርሱ ቀረቡ፥ [3]እጃቸውንም ጭነውባቸው አሁን መሽቶ ነበርና እስከ ማግሥቱ ድረስ በወኅኒ አኖሩአቸው። [4]ነገር ግን ቃሉን ከሰሙት ብዙዎች አመኑ፥ የወንዶችም ቍጥር አምስት ሺህ ያህል ሆነ።**

4:1 "ካህናቱ" ይህ ቃል በጥንታዊት ግሪክ የብራና ጽሑፎች ጥቅም ላይ የዋለ ነው Ñ፣ ሀ፣ መ፣ እና ሐ ሊቀ ካህናት አላቸው (አርከሪስ)። የተመቅሶ4 "ለካህናት" የሚሰጣቸው ደረጃ ለ ነው፣ (በከፊል እውነተኛ)። የምዕራፍ 4 ጽሑፍ የሚያሳየው፣ ተቃውሞ ከሊቀ ካህነቱ እንዳልመጣ ነው (ዝከ ቁ. 6)።

በብኪ የየሌዊ ነገድ (ማለትም የሙሴና የአሮን ነገድ) ያህዌን ለማገልገል ተመርጠዋል፣ "ከበኵር" ይልቅ (ዘጸ. 13)። ከዚህ ነገድ የተለዩ ወገኖች ያገለግሉ ነበር (1) የአካባቢ የሕግ መምህራን፤ (2) የቤተ መቅደስ አገልጋዮች፤ እና (3) በመቅደስ የሚያገለግሉ ካህናት፣ በተለይም በመሥዋዕት ማቅረብ አገባቦች (ሌዋ. 1-7)። ሊቀ ካህናቱ ከሚመጣበት ልዩ ቤተሰብ ከሙሴና ከአሮን ቤተሰብ መምጣት ይኖርበታል። ይህ አጠቃላይ ነገድ እንደ ሌሎቹ የእስራኤል)ያዕቆብ ነገዶች የመሬት ይዞታ ክፍፍል አይደረግለትም። የተወሰኑ ከተሞች በተለይ ተሰጥተዋቸዋል (ማለትም፣ 48 የሌዋውያን ከተሞች፣ ኢያሱ 20)። እነዚህ የሌዋውያን ከተሞች ጥገኛ የሚሆኑት በሌሎቹ ነገዶች ድጋፍ፣ ማለትም ለቤተ መቅደስ በሚሰጥ መባዕ እና በየሦስት ዓመቱ በሚደረግ የአካባቢ መባዕ ነው።

ሮም ፍልስጥኤምን ስትቆጣጠር ይሄ ሁሉ እንዲቀር ተደረገ። የሊቀ ካህናቱ ጽሕፈት ቤት ከሮም ተሸጠ። ከዚያም በኋላ የብኪ ጽሕፈት ቤት ሆኖ ሊቀጥል አልቻለም፣ ዳሩግን የንግድና የፖለቲካ ሥልጣን ጽሕፈት ቤት እንጂ።

የአሁኑ ሊቀ ካህናት ቀያፋ ነበር፣ (ማቴ. 26:3፤ ሉቃስ 3:2፤ ዮሐንስ 18)፣ ነገር ግን ዋነኛው ኃይል ከጽሕፈት ቤቱ ጀርባ የነበረው የቀድሞው ሊቀ ካህናት ሐና እጅ ነበር (ሉቃስ 3:2፤ ዮሐንስ 18:13፣24፤ ሐዋ. 4:6)። ይህ ቤተሰብ የይሁዲነት የሰዱቃውያን ክፍል ነበር።

▣ *"የቤተ መቅደሱ ጠባቂዎች አዛዥ"* ይህ የተለየ የሌዋውያን ጽሕፈት ቤት ሲሆን ከሊቀ ካህናቱ ቀጥሎ ሥልጣን ያለው ነው (ጆሴፈስ፣ ጦርነቶች 6:5:3)። እሱም የቤተ መቅደሱን ጠባቂዎች ይቆጣጠራል፣ (1ኛ ዜና. 9:11፤ ነህ. 11:11፤ ሉቃስ 22:4፣52፤ ሐዋ. 5:24፣26)። በዕብራይስጥ "የቤቱ ተራራ ሰው (ጉበኛ)" ተብሎ ይጠራል።

▣ *"ሰዱቃውያን"* እነዚህ ሀብታም የፍርድ ችሎት የፖለቲካ መሪዎች ናቸው።

ልዩ ርዕስ፡ ሰዱቃውያን

I. የቡድኑ መነሻ

ሀ. ብዙዎቹ ሊቃውንት የሚስማሙት ስሙ ከሳዶቅ መምጣቱን፣ ከአንደኛው የዳዊት ሊቀ ካህናት (2ኛ ሳሙ. 8፡17፤ 15፡24)። ኋላም ሰለሞን አብያታርን አጋዘው፣ የአዶኒያስን ዐመጽ ደግፌሃል በሚል (1ኛ ነገሥ. 2፡26-27) እናም ሳዶቅን እንደ ብቸኛ ሊቀ ካህን እውቅና ሰጠው (1ኛ ነገሥ. 2፡35)። ከባቢሎን ግዞት በኋላ ይህ የካህናት ሐረግ በኢያሱ ወይም እዬሱ ዳግም ተመሥርቷል (ሃጌ. 1፡1)። ይህ የሌዋዊ ቤተሰብ ቤተ-መቅደሱን ለማስተዳደር ነው የተመረጠው። ኋላም በዚህ የክህነት ባህል የነበሩ እና ደጋፊዎቻቸው ሰዱቃውያን ተብለው ተጠሩ።

ለ. በዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም ራቢያዊ ባህል (ራቢ. ናታን) ሳዶቅ የሶኮሆ አንቶጎነስ ደቀመዝሙር ነበር ይላል (ሁለተኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ዓ)። ሳዶቅ የሱን መምሕር የታወቀ አባባል "ከሙታን ዋጋ በኋላ" በስሕተት ተረድቶት ከሕይወት በኋላን የሚክድ ሥነ መለኮት አውጥቷል፣ የሥጋ ትንሣኤንም የሚክድ።

ሐ. በኋላም በይሁዲነት፣ ሰዱቃውያን ከቦኤቱሲያውያን ጋር ተለይተዋል። ቦኤቱስ ደግሞ የአንቲጎነስ የሶኮ ደቀ መዝሙር ነበር። ከሳዶቅ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሥነመለኮት አዘጋጅቷል፣ እሱም ደግሞ ከሕይወት በኋላን በመካድ።

መ. ሰዱቃውያን የሚለው ስም እስከ ዮሐንስ ሃይርካነስ ጊዜ ድረስ አልተከሰተም (135-104 ዓ.ዓ)፣ በጆሴፈስ እንደተጠቀሰው (በጥንት ቅሪቶች 13፡10፡5-6)። በጥነት ቅሪቶች 13፡5፡9 ጆሴፈስ "ሦስት አስተምህሮዎች" ነበሩ ብሏል፡ ፈሪሳውያን፣ ሰዱቃውያን፣ እና ኢሴናውያን ናቸው።

ሠ. የባላንጣነት ንድፈ ሐሳብ ከሴሌዩሲድ ገዥዎች ጀምሮ የነበረ ሲሆን በአንቲሆች 4ኛ ኢጲፋንያ ሥር ሔለናዊ የክህነት ሥርዓት ለመዘርጋት ሙከራ ተደርጓል፣ (175-163 ዓ.ዓ)። በመቃብያን ዐመጽ ጊዜ አዲስ የክህነት ሥርዓት ተጀመረ በስምዖን መቃብያስ (142-135 ዓ.ዓ) እና የእሱ ዝርዮች (1ኛ መቃ. 14፡41)። እነዚህ አዲሶቹ ሀስሞናዊ ሊቃነ ካህናት የባላባታዊዎቹ ሰዱቃውያን መነሻ ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው። ፈሪሳውያንም በዚህ ተመሳሳይ ጊዜ ከሀሲደም (ማለትም "የተለዩት") ተነሥተዋል 1ኛ መቃ. 2፡42፤ 7፡5-23)።

ረ. ዘመናዊ ንድፈ ሐሳብ አለ፣ (ማለትም ቲ. ደብሊዩ. ማንሶን)፣ ሰዱቃውያን ከግሪኩ ቃል ሳንዲኮይ በተወራራሽነት የመጣ ነው የሚል። ይህ ቃል የሚያመለክተው የአካባቢ ባለሥልጣናትን እነሱም ከሮሜ ባለሥልጣናት ጋር የሚገናኙትን ነው። ይህም ሊያሳይ የሚችለው አንዳንድ ሰዱቃውያን ባላባታዊ ካህናት እንዳልነበሩ ሲሆን ነገር ግን የፍርድ ችሎቱ አባላት ነበሩ።

II. የተለየ እምነታቸው

ሀ. እነሱ ከአይሁድ አኗኗር ከወግ አጥባቂ ካህናት ወገን ነበሩ፣ በሀስሞኒያንና በሮማውያን ጊዜያቶች።

ለ. እነሱ በተለይ የሚያተኩሩት በቤተ መቅደስ ደንቦች፣ አገባቦች፣ የአምልኮ ሥርዓቶች፣ እና አምልኮ ላይ ነበር።

ሐ. የተጻፈውን ሕግ (ቶራ) (ማለትም፣ ዘፍ. - ዘዳ.) እንደ ሕጋዊ (ሥልጣን እንዳለው) አድርገው የያዙ ሲሆን የቃል ባህሎችን ትተዋል (ማለትም፣ ታልሙድ)።

መ. ስለሆነም እነሱ፣ በርካታዎቹን የፈሪሳውያንን የተሻሻሉ መሠረተ እምነቶች አይቀበሉም

1. የሥጋን ትንሣኤ (ማቲ. 22፡23፤ ማርቆስ 12፡18፤ ሉቃስ 20፡27፤ ሐዋ. 4፡1-2፤ 23፡8)
2. የነፍስን መዋቲ አለመሆን (የጥንት ቅሪቶች 18፡1፡3-4፤ ጦርነቶች 2፡8፡14)
3. የመላእክት ማዕርግ ሕልውና (ሐዋ. 23፡8)
4. እነሱ "ዓይን ስለ ዓይንን" ይቀበላሉ (ሌክስ ታሊዮኒስ) በጥሬው እና በአካላዊ ቅጣት በታገዘ እንዲሁም የሞት ቅጣት (ከፍርድ ውሳኔ ይልቅ)

ሠ. የሥነ መለኮት ሁከት ሌለኛው ዘመን የነበረው ቀድሞ የተወሰነ ወይም ነጻ ፍቃድ በሚለው መካከል ነበር። ከሦስቱ ወገኖች በጆሴፈስ ከተጠቀሱት

1. ኢሴናውያን ውሳኔአዊ ዓይነት እንደሚኖር አረጋግጠዋል
2. ሰዱቃውያን ለሰዎች ነጻ ፍቃድ አጽንኦት ይሰጣሉ (የጥንት ቅርሶች 13፡5፡9፤ ጦርነቶች 2፡8፡14)
3. ፈሪሳውያን ከሁለቱ መካከል የሆነውን ሚዛናዊ አቋም ነው የያዙት

ረ. በአንድ በኩል በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለው አለመግባባት (ማለትም፣ ሰዱቃውያን -ፈሪሳውያን) በካህናትና በነቢያት መካከል ያለውን ክርክር ያሳያሉ፣ በብኪ።

ሌላው ክርክር የሚነሣው ሰዱቃውያን ማኅበራዊና መሬት ነክ ጉዳዮችን ይወክላሉ በሚል ሐቅ ነው። ባላባቶች ነበሩ (የጆሴፈስ የጥንት ቅርሶች 13፡10፡6፤ 18፡1፡4-5፤ 20፡9፡1)፣ ፈሪሳውያንና ጻፎች ግን ከአገሩ ሰው ይልቅ ሊቃውንትና ሃይማኖተኛ ነበሩ። ይህ ክርክር ባሕርይ የሚያደርገው በኢየሩሳሌም ያለችው ቤተ መቅደስ ወይም በምድሩ ላይ የነበረውን የአጥቢያ ምኲራቦች ነው።

ሌላው ክርክር ሊወክል የሚችለው በፈሪሳውያን ሥነ መለኮት ላይ የዞሮአስትሪአውያን ተጽዕኖ መኖሩን ሰዱቃውያን መቃወማቸው ነው። ምሳሌ፡ በጣም የተራቀቀ ሥነ መላእክት፣ በያህዌ እና በሰይጣን መካከል ያለ ምንታዌ እና ሰይጣንና የለዘበ የከሕይወት በኋላ አመለካከት በአካላዊ ቃላት መግለጽ ነው። እነዚህ ተጨማሪዎች በኢሴአውያንና በፈሪሳውያን ዘንድ በሰዱቃውያን ላይ የተቃውሞ ምክንያት ሆኑ። ወደ ሙሴ ወግ አጥባቂ አቋም ተመለሱ- በሥነመለኮት ብቻ ሌሎቹን

የአይሁድ ቡድኖች በክርክራቸው ለማሰናከል።

III. የመረጃ ምንጮች

ሀ. ጆሴፈስ ዋነኛው የመረጃ ምንጭ ነው ስለ ሰዱቃውያን። በፈሪሳውያን ቁርጠኝነት ላይ አድሏዊ አስተሳሰብ ይዟል፣ እንዲሁም በሮሜ የአይሁድ ሕይወት መልካምነትን የሚያሳይ ምስል በመያዙ።

ለ. ሌለኛው የመረጃ ምንጭ ራቢያዊ ሥነ ጽሑፍ ነው። ሆኖም፣ እዚህ፣ በእጅጉን ጠንከር ያለ አድሏዊ አስተሳሰብ አለ። ሰዱቃውያን የአባቶችን ባህላዊ እሴቶችን ጥቅምና ሥልጣን ክደዋል (ማለትም ታልሙድ)። እነዚህ ፈሪሳዊ ጽሑፎች ተቃዋሚዎቻቸውን በአሉታ እንደሚመለከቱ ግልጽ ነው፣ ቢያንስ የተጋነኑ ስልቶች ነው የሚሆኑት።

ሐ. የሰዱቃውያን የራሳቸው ጽሑፍ ምንም አልተገኘም። ከኢሩሳሌም እና ከቤተ መቅደሱ ጥፋት ጋር በ70 ዓ.ዓ ሁሉም ሰነድና የክህነታዊ ምሁራን ቅሪቶች ወድመዋል።እነሱ ክልላዊ ሰላም እንዲኖር ይሹ ነበር፣ ያንንም የማድረጊያ መንገዱ በአንደኛው ክፍለ ዘመን ወደ ሮም መጠቃለል ነበር (ዮሐንስ 11፡48-50)።

4.2

| | |
|---|---|
| አአመመቅ፣ አኪጀት | "በጣምም ተደናግጠው" |
| አየተመት | "በጣም ተረብሸው" |
| አእት | "ተረብሸው" |
| አኢመቅ | "በእጅጉን ተረብሸው" |

ይህ አልፎ አልፎ የሚሆን የግሪክ ቃል (እዚህ የአሁን መካከለኛ (ተተኳሪ) ቦዝ አንቀጽ) "በአንድ ነገር ላይ በብርታት መሥራት" ማለት ነው። በሌላ ስፍራ አንዴ ይገኛል በሐዋ. (16፡18)። በሴፕቱዋጄንት አይገኝም፣ ወይም በኮኔ ወረቀት፣ ግብፅ።

የሰዱቃውያን አመራር ቅር ተሰኝቷል፣ ምክንያቱም የክርስቲያን መሪዎች ሕዝቡን በቤተመቅደስ በኢየሱስ ስም በማስተማራቸውና ትንሣኤውን በማወጃቸው ሲሆን (ይህም ሰዱቃውያን የካዱት፣ ብሎም፣ የትንሣኤን ሥነ-መለኮታዊ ጽንሰ ሐሳብ ባጠቃላይ)። እንዲሁም ከቁ. 2 ቃላት አኳያ፣ ሐዋርያት ስለ ኢየሱስ ትንሣኤ ብቻ አልነበረም የተናገሩት፣ ነገር ግን የሞላውን የአማኞች ትንሣኤ አመላካች ነበር (1ኛ ቆሮ. 15)። ሞት አንዱን አማኝ ብቻ አይደለም ያጣው፣ <u>ሁሉንም አማኞች</u> አጥቷል!

4፡3 "እነሱ" በቁ. 2 ሁነቶቹ ጴጥሮስ፣ ዮሐንስ፣ እና የተፈወሰው ሽባ ሰው ጭምር ናቸው። በቁ. 3 ሁነቶቹ ካህናቱ እና የመቅደሱ ፖሊስ ናቸው።

▣ **"እጃቸውን ጭነውባቸው"** ይህ የግሪክ ቃል ሰፋ ያለ የፍቺ አግባብ ያለው ሲሆን፣ ነገር ግን ሉቃስ አዘውትሮ የሚጠቀመው በዚህ መሰሉ የእስር አጠቃቀም ነው፣ (ሉቃስ 20፡19፤ 21፡12፤ ሐዋ. 5፡18፤ 12፡1፤ 21፡27)።

▣ **"እስከሚቀጥለው ቀን ድረስ"** የአይሁድ ሕግ ከመሸ በኋላ ፍርድ እንዳይፈጸም ያግዳል። እነዚህ መሪዎች፣ ይህ ትምህርት)ስብከት እንዲቆም እናም ወዲያውኑ እንዲቆም ፈልገዋል። ስለሆነም ሌሊቱን በእስር አንዱጋ የመቅደሱ ታችኛ ክፍል እንዲቆዩ አደረጉ፣ ከሕዝብ ማሰሪያው በተቃራኒ (ዝከ 5፡18)።

4፡4 **"ያደመጡትም… አመኑ"** ሁለቱም እነዚህ ግሦች ያለፈ ጊዜ ናቸው። እምነት የሚጀምረው ከመስማት ነው (ሮሜ 10፡17)። ወንጌልን የማድመጥ ውጤቱ (በመንፈስ ርዳታ፣ ዮሐንስ 6፡44፣65፤ 16፡8-11) በወንጌል ማመንን ያመጣል። ልዩ ርዕስ፡ የግሪክ የግሥ ጊዜያቶች ለደህንነት ጥቅም ላይ የዋሉ 2፡40 ላይ ተመልከት።

▣ **"የወንዶቹም ቁጥር አምስት ሺህ ያህል ነበር"** ይህ ቁጥር ሴቶችና ሕፃናትን እንደማያካትት አስተውል። ዘወትር በአኪ የአባትየው ማመን ተስፋፍቶ ሁሉንም ቤተሰብ ያጠቃልላል (ዝከ 11፡14፤ 16፡15፣31፣33)። በደርቡ ክፍል ላይ የነበሩት ቡድኖች ቁጥራቸው 120 ያህል ነበር። በጰንጠቆስጤ 3000 ተጨመሩ (ዝከ 2፡41)፤ አሁን የአማኞቹ ቁጥር 5000 ደርሷል! የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን በፍጥነት አደገች!

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 4፡5-12**

**5-6 በነገውም አለቆቻቸውና ሽማግሌዎች ጻፎችም ሊቀ ካህናቱ ሐናም ቀያፋም ዮሐንስም እስክንድሮስም የሊቀ ካህናቱም ዘመዶች የነበሩት ሁሉ በኢየሩሳሌም ተሰበሰቡ፤ 7 እነርሱንም በመካከል አቁመው። በምን ኃይል ወይስ በማን ስም እናንተ ይህን አደረጋችሁ? ብለው ጠየቁአቸው። 8 በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ መንፈስ ቅዱስንም ተሞልቶ እንዲህ አላቸው፦ እናንተ የሕዝብ አለቆችና ሽማግሌዎች፥ 9 እኛ ዛሬ ለድውዩ ሰው ስለ ተደረገው መልካም ሥራ ይህ በምን እንደዳነ ብንመረመር፥ 10 እናንተ በሰቀላችሁት እግዚአብሔርም ከሙታን ባስነሣው በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይህ ደኅና ሆኖ በፊታችሁ እንደ ቆመ፥ ለእናንተ ለሁላችሁ ለእስራኤልም ሕዝብ ሁሉ የታወቀ ይሁን። 11 እናንተ ግንበኞች የናቃችሁት፥ የማዕዘን ራስ የሆነው ይህ ድንጋይ ነው። 12 መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።**

4:5 “ገዥዎቻቸው እና ሽማግሌዎች እንዲሁም ጸሐፍት” የፍርድ ችሎት (ማለትም፣ ሸንጎው፣ 5:21፣ ከኢየሩሳሌም ስፍራ፤ የሽማግሌዎች ሸንጎ፣ 22:5) ከሰባ የአይሁድ ሽማግሌዎች ነው የተቋቋመው:: እሱም ከፍተኛው የፖለቲካ)ሃይማኖታዊ አካል ነው (ሮሜ የፈቀደለት)፣ በይሁዲነት፣ ኢየሱስ በነበረበት ሰዓት:: ጽንስ ሐሳቡ የጀመረው (ማለትም፣ የአይሁድ ባህል) በዕዝራ እና “በታላቁ ምኵራብ ሰዎች” ነው:: ዘወትር  በአኪ የሚገለጠው፣ “ጻፎች፣ ሽማግሌዎችና ሊቀ ካህናት” በሚል ሐረግ ነው፣ (ሉቃስ 23:13፤ ሐዋ. 3:17፤ 4:5፣8፤ 13:27)::

**ልዩ ርዕስ፡ የፍርድ ችሎት**

I.የመረጃ ምንጮች
  ሀ. አዲስ ኪዳን ራሱ
  ለ. ፍላቪዩስ ጆሴፈስ የአይሁድ ቅርሶች
  ሐ. ሚሽናህ የታልሙድ ክፍል (ማለትም፣ ትራክቴት “ችሎት”)
    ያለመታደል ሆኖ አኪ እና ጆሴፈስ በራቢያዊ ጽሑፎች ላይ ስምምነት የላቸውም፣ ስለ ሁለት ችሎቶች በኢየሩሳሌም ስላሉትና አንደኛው የካህናት (ሃይማኖታዊ ችሎት)፣ በሊቀ ካህናቱ ምሪት ያለውና፣ የፍትሐብሔርና የወንጀለኛ ጉዳዮችን የሚያየው፣ እንዲሁም ሁለተኛው በፈሪሳውያንና በጸሐፍት ቁጥጥር ሥር ያለውና ሃይማኖታዊና ባህላዊ ጉዳዮችን የሚያየው ነው። ሆኖም፣ ራቢያዊ ጽሑፎች ከ200 ዓ.ዓ ጀምሮ ነው ጊዜያቸው የተመዘገበው፣ የሚያንጸባርቁትም በ70 ዓ.ዓ ኢየሩሳሌም በሮሜ የጦር መሪ በቲቶ እጅ ከወደቀች በኋላ ያለውን ነው። አይሁድ ሃይማኖታዊ ሕይወታቸውን ጃሚና በተባለች ከተማ (በ118 ዓ.ዓ) ዳግም ከጀመሩ በኋላ፣ ቆየት ብለውም ወደ ገሊላ ተዛውረዋል።
II. ሥርወ ቃሉ
  ይሄንን የፍትሕ አካል የመግለጽ ችግር በተለያዩ ስሞች መሰየሙ ነው። በርካታ ቃላት የፍትሕ አካላትን ለመግለጽ በአይሁድ ማኅበረሰብ በኢየሩሳሌም ጥቅም ላይ ውለዋል።
  ሀ. ጌሮሲያ - “ሸንጎ” ወይም “ምክር ቤት”። ይህ ጥንታዊው ቃል ሲሆን በፋርስ ዘመን መጨረሻ ላይ ጥቅም ላይ የዋለ ነው፣ (ጆሴፈስ ጥንታዊ ቅርሶች 12.3.3 እና 2ኛ መቃብያስ 11:27)። እሱም በሉቃስ ሐዋ. 5:21 “ከፍርድ ችሎት” ጋር ጥቅም ላይ ውሏል። ይህም ምናልባት ቃሉን ለግሪክኛ ተናጋሪ መሪዎች ለመግለጽ ታስቦ ይሆናል (1ኛ መቃብ. 12:35)።
  ለ. ሲኔድሪኦን - “ችሎት።” ይህ ድብልቅ ቅርጽ (አንድ ጋ) የሚል ተመሳሳይ ያለውና ሄድራ (መቀመጫ) ማለት ነው። ይህ ቃል ባስገራሚ ሁኔታ በአራምኛ ጥቅም ላይ ውሏል፣ ነገር ግን የሚያንጸባርቀው የግሪክ ቃል ነው። በመቃብያን ዘመን ማብቂያ ላይ ይህ ተቀባይነት ያገኘ ቃል ሆነ፣ በኢየሩሳሌም ያለውን የአይሁድ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለመግለጽ፣ (ማቴ. 26:59፤ ማርቆስ15:1፤ ሉቃስ 22:66፤ ዮሐንስ 11:47፤ ሐዋ. 5:27)። ችግር የሚፈጠረው ተመሳሳይ ቃል ለአጥቢያ ፍርድ ቤቶች ጥቅም ላይ ሲውል ነው (የአካባቢ ምኵራብ ችሎቶች) ከኢየሩሳሌም ውጭ (ማቴ. 5:22፤ 10:17)።
  ሐ. ፕሬስቢቴሪያን - “የሽማግሌዎች ሸንጎ” (ሉቃስ 22:66)። ይህ በብኪ የሚያሳየው የነገድ አለቆችን ነው። ሆኖም፣ የኢየሩሳሌምን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለማመልከት ነው፣ እዚህ የገባው (ሐዋ. 22:5)።
  መ. ቦሌ - ይህ ቃል “ሸንጎ” በጆሲፈስ ጥቅም ላይ ውሏል (ጦርነቶች 2.16.2፤ 5.4.2)፣ ነገር ግብ በአኪ በርካታ የፍርድ አካላትን ለመግለጽ አይደለም፡ (1) በሮም ያለው ሸንጎ፤ (2) የሮሜ የአካባቢ ሸንጎዎች፤ (3) በኢየሩሳሌም ያለው የአይሁድ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፤ እና (4) የአካባቢ የአይሁድ ፍርድ ቤቶች። የአርማትያው ዮሴፍ የሸንጎ አባል መሆኑ በዚህ ቃል አግባብ ተገልጿል (ማለትም፣ ቦሊዩተስ፣ ፍችውም “አማካሪ፣” ማርቆስ 15:43፤ ሉቃስ 23:50)።
III. ታሪካዊ እድገቱ
  በመነሻው እዝራ ታላቁን ምኵራብ እንዳደራጀ ይታወቃል (ታርጉም ማኅልየ ማኅልይ 6:1) ከስደት ዘመን በኋላ፣ ይህም የኢየሱስ ጊዜ የነበረው ችሎት ይመስላል።
  ሀ. ሚሽናህ (ታልሙድ) በኢየሩሳሌም ሁለት ዋነኛ ፍርድ ቤቶች እንደነበሩ ዘግቧል (ሳንህ. 7:1)።
    1. አንደኛው በ70 (ወይም 71) አባላት ያሉት (ሳንድ. 1:6 እንዲያውም ሙሴ የመጀመሪያውን ችሎት ማቋቋሙን ዘኁ. 11፣ ዘኁ. 11:16-25)።
    2. አንደኛው 23 አባላት የነበሩት ሲሆን (ይህ የሚያመለክተው ግን የአካባቢ ምኵራብ ፍርድ ቤቶችን ነው)።
    3. አንዳንድ የአይሁድ ሊቃውንት በኢየሩሳሌም 23 አባላት ያሉት ችሎት እንደነበረ ያምናሉ። ሦስቱ አንድ ላይ ሲሆኑ፣ እነሱም ከሁለቱ መሪዎች ጋር፣ “ታላቁን ችሎት” 71 አባላት ያሉትን ያቋቁማሉ (ናሲ እና ኤቪ ቤተ ዲን)።
      ሀ. ባለ አንድ ካህን (ሰዱቃዊ)
      ለ. ባለ አንድ ሕግ አዋቂ (ፈሪሳዊ)
      ሐ. ባለ አንድ ባባላት (ሽማግሌዎች)
  ለ. ከሰደት ጊዜ በኋላ፣ የተመለሰው የዳዊት ዘር ዘሩባቤል ነበር እንዲሁም የተመለሰው አሮናዊ ዘር ኢያሱ (ኢየሱ) ነበር። ከዘሩባቤል ሞት በኋላ ሌላ ዋዊታዊ አር አልቀጠለም፣ ስለሆነም የፍርድ አልባሳቱ ለካህናት ተላለፈ (1ኛ መቃ. 12:6) እንዲሁም የአጥቢያ ሽማግሌዎች (ነህ. 2:16፤ 5:7)።
  ሐ. ይህ ካህናዊ ሚና በፍርድ ውሳኔ ላይ በዲኦዶረስ ሰነድ ተደግፏል 40:3:4-5 በሔለናውያን ዘመን።
  መ. ይህ ካህናዊ ሚና በመንግሥት ቀጥሏል፣ በሴሉሲድ ዘመን። ጆሴፈስ አንቲሆችን ጠቅሷል “ታላቁ” 3ኛ

(223-187 ዓ.ዓ) የጥነት ቅርሶች 12፡138-142።

ሠ. ይህ ካህናዊ ሥልጣን በመቃብያን ጊዜ ቀጥሏል፣ በጆሴፈስ የጥንት ቅርሶች እንደተጠቀሰው 13፡10፡5-6፤ 13፡15፡5።

ረ. በሮሜ ጊዜ የሶርያ ገዥ (ጋቢኒዩስ፣ ከ57-55 ዓ.ዓ) አምስት ክልላዊ "ችሎቶችን" አቋቁሟል (የጆሴፈስ ጥንታዊ ቅርስ 14፡5፡4፤ እና ጦርነቶች 1፡8፡5)፣ ነገር ግን ይሄ በሮሜ ታግዷል (47 ዓ.ዓ)።

ሰ. የፍርድ ችሎቱ ፖለቲካዊ መደራደሮችን ከሄሮድስ ጋር ያደርጋል (የጥንት ቅርሶች 14.9.3-5) እሱም በ37 ዓ.ዓ ታግዶ አብዛኞቹ የከፍተኛ ፍርድ ቤት አባላት ተገድለዋል (ጆሴፈስ ጥንታዊ ቅርሶች 14.9.4፤ 15.1.2)።

ሸ. በሮሜ ገዥዎች (6-66 ዓ. ዓ) ጆሴፈስ የሚነግረን (የጥንት ቅርሶች 20.200.251) የፍርድ ችሎቱ በድጋሚ ሥልጣንና ተሰሚነት ሊያገኝ ችሏል (ማርቆስ 14፡55)። በአኪ ሦስት የተመዘገቡ የፍርድ ቤቶች አሉ፣ እነሱም የፍርድ ችሎቱ፣ በሊቀ ካህናቱ ወገን ብይን የሚሰጥበት።

1. የኢየሱስ ፍርድ (ማርቆስ 14፡53-15፡1፤ ዮሐንስ 18፡12-23፣28-32)
2. ጴጥሮስና ዮሐንስ (ሐዋ. 4፡3-6)
3. ጳውሎስ (ሐዋ. 22፡25-30)

ቀ. አይሁድ ሲያምጹ በ66 ዓ.ም ሮማውያን አያይዘው የአይሁድን ማኅበረሰብ አጠፉ እንዲሁም ኢየሩሳሌምን በ70 ዓ.ዓ። የፍርድ ችሎቱ ፈጽሞ ተበተነ፣ ምንም እንኳ ፈሪሳውያን በጃምኒያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለማቋቋም ቢሞክሩም (ቤዝ ዲን) ወደ አይሁድ ሃይማኖታዊ ሕይወት መመለስ (ነገር ግን ሲቪል ወይም ፖለቲካዊ አልነበረም።)

IV. አባልነት

ሀ. የመጀመሪያው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኢየሩሳሌም የተጠቀሰው 2ኛ ዜና. 19፡8-11 ላይ ነው። የተቋቋመውም (1) ሌዋውያን (2) ካህናት፤ እና (3) የቤተሰብ መሪዎች ነው (ሽማግሌዎች፣ 1ኛ መቃ. 14፡20፤ 2ኛ መቃ. 4፡44)።

ለ. በመቃብያን ጊዜ በብዛት ተይዞ የነበረው (1) በሰዱቃውያን የካህናት ቤተሰቦች እና (2) በአጥቢያ ባላባቶች ነው (1ኛ መቃ. 7፡33፤ 11፡23፤ 14፡28)። በኋላም "በጸሐፍት" ጊዜ (የሙሴ ሕግ አዋቂዎች፣ ዘወትር ፈሪሳውያን) ተጨምረው ባጠቃላይ በአሌክሳንደር ጃኒዩስ ሚስት በሰሎሜ (76-67 ዓ.ዓ)። እሷ እንዲያውም ፈሪሳውያንን ዋነኞቹ ቡድኖች አድርጋለች ይባላል (ጆሴፈስ የአይሁድ ጦርነቶች 1፡5፡2)።

ሐ. በኢየሱስ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ተቋቁሞ የነበረው

1. በሊቀ ካህናቱ ወገኖች
2. በአጥቢያ ሀብታም ወገኖች
3. ጸሐፍት (ዝክ 11፡27፤ ሉቃስ 19፡47)

V. ዋቢ ምንጮች

ሀ. የኢሱስና የወንጌላት መዝገበ ቃላት፣ አይቪፒ፣ ገጽ728-732
ለ. የዞንደርቫን የመጽሐፍ ቅዱስ ስዕላዊ ኢንሳይክሎፒድያ፣ ቅጽ 5 ገጽ 268-273
ሐ. አዲሱ ስካፍ- ሄርዞግ የሃይማኖታዊ እውቀት ኢንሳይክሎፒድያ፣ ቅጽ 10፣ ገጽ 203-204
መ. የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች መዝገበ ቃላት፣ ቅጽ 4፣ ገጽ 214-218
ሠ. ኢንሳይክሎፒድያ ጁዳሲያ (የይሁዳ)፣ ቅጽ 14 ገጽ 836-839

4፡6 "ሐና" ስሙ በግሪክ ሀናስ ነው፤ ዮሴፈስ፣ ሃናኖስ ብሎ ይጠራዋል:: ስሙ ከዕብራይስጡ "መሐሪ" የተገኘ ይመስላል ወይም "ባለ ጸጋ" (hãnãn)

በብኪ ሊቀ ካህነነት እስከ ሕይወት ፍጻሜ ነበር የሚቆየው፣ ከአሮን ዘር:: ሆኖም፣ ሮማውያን ይሄንን ሹመት ወደ ፖለቲካዊ ተቋም ቀይረው ለሌዋዊ ቤተሰብ ሸጡት:: ሊቀ ካህኑ የሴቶችን ክፍል ንግድ ይቆጣጠራል፣ ይመራል፣ ያስተዳድራል:: ኢየሱስ ቤት መቅደሱን ሲያጸዳ የነቀፈው ይሄንን ቤተሰብ ነው::

እንደ ፍላቪዩስ ጆሴፈስ፣ ሐና በ6-14 ዓ.ም ሊቀ ካህን ነበር:: የተሾመውም በቆርናሊዮስ በሶርያ ገዥ ሲሆን፣ የተሻረውም በቫሊሪየስ ግራተስ ነበር:: ብተሰቦቹ (5 ወንዶችና 1 የልጅ ልጅ) ተክተውታል:: ቀያፋ (18-36 ዓ.ም)፣ አማቹ (ዮሐንስ 18፡13)፣ የቅርብ ተኪው ነበር:: በጽሕፈት ቤቱ ዋነኛው ኃይል ሐና ነበር:: ዮሐንስ እሱን፣ ኢየሱስ ሲያዝና ሲወስድ ዋነኛ ሰው አድርጎታል (ዝከ 18፡13፣19-22)::

▣ "ቀያፋ" እሱ ሊቀ ካህን ሆኖ የተሾመው በቫሌሪየስ ግሬተስ ሲሆን፣ የይሁዳ አቃቤ ሕግ ነው (ኤም ኤስ ዲ፣ 'ኢዮናታስ፣ አእመቅ፣ አኢመቅ) ከ18-36 ዓ.ም::

▣ "ዮሐንስ" ይህ ምናልባት የሚያመለክተው "ዮናታን"፣ እሱም ጆሴፈስ እንደሚነግረን አንደኛው የሐና ልጅ የነበረና ከቀያፋ በኋላ በ36 ዓ.ም ሊቀ ካህን የነበረ:: ሆኖም፣ የተመቅሶ[4] አዮነስ (ዮሐንስ) የሚል አለው፣ በርግጠኝነት፤ አርኢቢ (REB) እንኳ ተመልሶ ወደ "ዮሐንስ" ነው የሚሄደው::

▣ **“አሌክሳንደር”** ስለዚህ ሰው ምንም አይታወቅም፣ ነገር ግን እንደ ዮሐንስ፣ ምናልባት የሐና ወገን ሊሆን ይችላል፣ ወይም የሰዱቃውያን ፓርቲ አባል።

4፡7 **“በስተመካከል ባቆሟቸው ጊዜ”** የችሎት አባላት በግማሽ ክብ መድረክ ላይ ነው የሚቀመጡት።

▣ **“ይጠይቋቸው ጀመር”** ይህ ያልተጠናቀቀ ጊዜ ሲሆን፣ የሚለውም (1) ካለፈው የቀጠለ ድርጊት ወይም (2) የአንድ ድርጊት መጀመሪያ ነው።

▣ **“በምን ኃይል ወይም በማን ስም”** እነሱ ያሰቡት ፈውሱ በጥንቆላ ኃይል እንደተደረገ ነው (ዝከ 19፡13)። ይህንን ተመሳሳይ ብልሃት በኢየሱስ ላይ ተጠቅመዋል (ሉቃስ 11፡14-26፤ ማርቆስ 3፡20-30)። ተአምራቶቹን ሊክዱ አይችሉም፣ ስለሆነም ዘዴውን ወይም የኃይሉን ምንጭ ለማወቅ ሙከራ አደረጉ።

4፡8 **“መንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ”** መንፈስ የሐዋርያት የጥበብና የግልጽነታቸው ምንጭ ነበር፣ ሉቃስ 12፡11-12፤ 21፡12-15)። ይሄው ሰውዬ ከጥቂት ቀናት በፊት ከፍርሃት የተነሣ ጌታን የካደ እንደነበር አስተውል፣ (ዝከ 4፡13)። ጴጥሮስ “መሞላቱን” ተገንዘብ (ዝከ 2፡4፤ 4፡8፣31)። ይህ የሚያመለክተው ንስሐ ሲገቡበት የሚቻል ልምምድ መሆኑን ነው፣ ኤፌ. 5፡18)። በ2፡4 እና 3፡10 ያለውን ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት።

4፡9 **“እንደ... ከ”** ይህ አንደኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ሲሆን፣ በጸሐፊው ዓላማ ተገቢ ነው ተብሎ ይታመናል።

▣ **“ዛሬ በምርመራ ላይ ብንሆንም”** የግሪኩ ቃል በጥሬው የሚለው “በፍርድ ቤት ተመረመሩ” ነው (ዝከ 12፡19፤ 24፡8፤ 28፡18፤ ሉቃስ 23፡14)። የቤርያ አይሁድ ቅዱስ ቃሉን ይመረምሩ እንደነበረው፣ ማለትም ጳውሎስ በትክክል እየተረጎመላቸው መሆኑን ለማወቅ ያደርጉት እንደነበረ (ዝከ 17፡11)።

▣ **“ለሕመምተኛው ሰው ስለተደረገው ፈውስ”** ጴጥሮስ የእነዚህ ኃላፊዎች ምርመራ ተገቢ እንዳይደለ ያስረዳው፣ በዚህ ባላንጣዊ ሁኔታ የተደረገውን አስደናቂ ፈውስና ምሕረት በተመለከተ ነው። እግዚአብሔርን ሊያመሰግኑ በተገባ ነበር!

▣ **“ደኅና አደረገው”** ይህ የተፈጸመ ተገብሮ አመላካች ሲሆን፣ ፍችውም ሙሉ ጤናና የእግሩ መፈወስ ነው።

4፡10 **“ይሄም በእናንተ ሁሉ ዘንድ የታወቀ ይሁን እንዲሁም በእስራኤል ሕዝብም”** ይህ የተፈጸመ የአሁን ትዕዛዝ አንቀጽ ነው። መንፈስ ጴጥሮስን ግልጽ አድርጎታል። እሱ በፍርድ ቤት አካባቢ ቀረቤታ የለውም። እነዚህ መሪዎች ክርስቶስን በመቃብር ሊያስቀሩት አልቻሉም፣ እንዲሁም ተፈውሶ ፊታቸው የቆመውን ሰው መካድ አልቻሉም!

▣ **“በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም”** ጴጥሮስ ጥያቄአቸውን አንሥቶ በተለይ ተአምራቱ እንዴት እንደተከሰተ መለሰላቸው። የናዝሬቱ ኢየሱስ የሚለውን ልዩ ርዕስ 2፡22 ተመልከት።

▣ **“እናንተ የሰቀላችሁት”** ይህ ግልጽ እውነት ነው። እንዲሞት መነሣሣቱን ያደረጉት እነሱ ናቸው። “በእናንተ” የሚለውን ተመልከት፣ ቁ. 11፣ የእነሱን ኃጢአት ደግሞ የሚያስረዳውን።

▣ **“እግዚአብሔር ግን አስነሣው”** አኪ. ሦስቱም የሥላሴ አካላት በኢየሱስ ትንሣኤ ላይ እንደነበሩ ያስረግጣል፡ (1) መንፈስ፣ ሮሜ 8፡11፤ (2) ኢየሱስ፣ ዮሐንስ 2፡19-22፤ 10፡17-18፤ እና (3) አብ፣ ሐዋ. 2፡24፣32፤ 3፡15፣26፤ 4፡10፤ 5፡30፤ 10፡40፤ 13፡30፤ 33፣34፣37፤ 17፡31፤ ሮሜ 6፡4፣9። ይህም ማረጋገጫነቱ የኢየሱስ ሕይወት፣ እና ትምህርት ስለ እግዚአብሔር እና ደግሞ የኢየሱስን የተቀያሪነት ሞት አብ ሙሉ ለሙሉ እንደተቀበለው ነው። ይህ የጥንቱ ስብከተ ወንጌል ዋነኛ ገጽታ ነበር (የሐዋ. ስብከቶች)።

▣ **“ይህ እዚህ የቆመው ሰው”** ይህ ቃል የሚያሳየው “የቆመውን” ነው። ሽባው ሰው ቀጥ ብሎ ቆሟል፣ እናም በፊት ለፊታቸው ቆሟል።

4፡11 ይህ የተጠቀሰው ከመዝ. 118፡22 ነው፣ ነገር ግን ከማሶረቲክ ጽሑፍ ወይም ሴፕቱዋጂንት አይደለም (ኤፌ. 2፡20፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡4)። ኢየሱስ ይሄንን ስለ ራሱ በማርቆስ 12፡10 እና ሉቃስ 20፡17 ተጠቅሟል፣ ከሴፕቱዋጂንት የተወሰደ። እሱም የሚያሳየው የብኪ. ትንቢት፣ ስለ ተናቀው መሲሕ መፈጸሙን ነው፣ እሱም የእግዚአብሔር ዘላለማዊ እቅድ የእስራኤል እና የዓለም መቤዠት ዋነኛ ጉዳይ ነው። ይህ ለእነዚህ የአይሁድ መሪዎች አስደንጋጭ መግለጫ ነው (1ኛ ጢሞ. 2፡5)።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **“ዋናው የማዕዘን ድንጋይ”** |
| **አኪጀት** | **“ዋናው የማዕዘን ድንጋይ”** |
| **አየተመት፣ አኢመቅ** | **“የማዕዘን ድንጋይ”** |
| **አእት** | **“ድንጋይ... ከሁሉም የሚበልጥ”** |

**ልዩ ርዕስ፡ የማዕዘን ድንጋይ**

I. የብሉይ አጠቃቀም

ሀ. የድንጋይ ጽንሰ-ሐሳብ እንደ ጠጣር ጽኑ ዓይነት ለመልካም መሠረት ጥቅም ላይ የሚውለው ለያህዌህ ተገልጿል (መዝ. 18፡1)።

ለ. እሱ ከዚያም መሲሐዊ ማዕርግ ከፍ ብሏል (ዘፍ. 49፡24፤ መዝ. 118፡22፤ ኢሳ. 28፡16)።

ሐ. እሱም የሚወክለው ከያህዌ በመሲሕ በኩል የሆነ ፍርድ ነው (ኢሳ. 8፡14፤ ዳን. 2፡34-35፤44-45)።

መ. ይህም ወደ ግንባታ ዘይቤ አደገ።

1. የመሠረት ድንጋይ፣ በቅድሚያ የሚነጠፈው፣ ለቀሪው ሕንፃና ማዕዘኖቹን አስተማማኝ ለማድረግ የሚሆን፣ ስሙም "የማዕዘን ድንጋይ" ይባላል።
2. እሱም በስፍራው የሚቀመጥ የመደምደሚያው ድንጋይ ተብሎም ይጠቀሳል፣ ግድግዳዎቹን እርስ በርስ ያያይዛቸዋል (ዘካ. 4፡7፤ ኤፌ. 2፡20፤21)፣ "የመደምደሚያ ድንጋይ" ይባላል፣ ከዕብራይስጥ ሩሽ (ራስ) ከሚለው
3. እሱም "ዋነኛው ድንጋይ" በሚል የጠቀሳል፣ በበሩ መንገድ በጉበኑ በኩል ሆኖ የግድግዳውን ክብደት በሙሉ የሚሸከም ነው።

II. አኪ አጠቃቀም

ሀ. ኢየሱስ መዝ. 118ን ስል ራሱ ማጣቀሻ በርካታ ጊዜ ጠቅሶታል (ማቴ. 21፡41-46፤ ማርቆስ 12፡10-11፤ ሉቃስ 20፡17)

ለ. ጳውሎስ መዝ. 118ን ተጠቅሞበታል ያህዌ የማያምኑትን ዐመጸኞች እስራኤላውያንን እንደናቃቸው ከማመልከት ጋር በተያያዘ (ሮሜ 9፡33)

ሐ. ጳውሎስ "የመደምደሚያ ድንጋይን" ጽንሰ-ሐሳብ ተጠቅሟል፣ በኤፌ. 2፡20-22 ክርስቶስን ለመጥቀስ

መ. ጴጥሮስ ይሄንን የኢየሱስ ጽንሰ-ሐሳብ በ1ኛ ጴጥ. 2፡1-10 ላይ ተጠቅሟል። ኢየሱስ የማዕዘን ድንጋይ አማኞች ደግሞ ሕያው ድንጋዮች ናቸው (ማለትም፣ አማኞች እንደ ቤተ-መቅደስ፣ 1ኛ ቆሮ. 6፡19)፣ በእሱ ላይ ተገንብተዋል (ኢየሱስ አዲሱ ቤተ መቅደስ ነው፣ ማርቆስ 14፡58፤ ማቴ. 12፡6፤ ዮሐንስ 2፡19-20)።

አይሁድ ዋነኛውን የተስፋቸውን መሠረት ነው የናቁት፣ ኢየሱስን እንደ መሲሕ ባልተቀበሉት ጊዜ

III. ሥነመለኮታዊ መግለጫዎች

ሀ. ያህዌ ዳዊት/ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን እንዲገነቡ ፈቀደ። ቃል ኪዳኑን ከጠበቁ እንደሚባርካቸውና ከእነሱ ጋር እንደሚሆን ገለጸላቸው፣ ነገር ግን እንዲያ ካላደረጉ ቤተ መቅደሱ ይፈርሳል (1ኛ ነገሥ. 9፡1-9)!

ለ. ራቢያዊ ይሁዲነት የሚያተኩረው ቅርጽና የአምልኮ ሥርዓት ላይ ሲሆን፣ የግለሰባዊ የእምነት ግጽታን ችላ ይላል (ይህ የተመቻቸ መግለጫ አይደለም፤ በርካታ ደጎና ራቢዎች ነበሩ)። እግዚአብሔር የየቀኑ፣ ግላዊ፣ መልካም ግንኙነትን በአምሳሉ ከፈጠራቸው ጋር ለማድረግ ይሻል፣ (ዘፍ. 1፡26-27)። ሉቃስ 20፡17-18 የፍርድን አስፈሪ ቃላት ይዟል።

ሐ. ኢየሱስ የቤተመቅደስን ጽንሰ ሐሳብ የሱን ሥጋዊ አካል እንዲወክል አድርጎ ተጠቅሞበታል። ይህም የግልንጽንሰ ሐሳብ እየቀጠለና እያሰፋፋ አስኪዶታል። ኢየሱስን እንደ መሲሕ ማመን ከያህዌ ጋር ላለ ግንኙነት ቁልፍ ነው።

መ. ደኅንነት ማለት የእግዚአብሔርን አምሳል በሰው ልጆች ያለውን መመለስ፣ ይህም ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት እንዲሰምር ነው። የክርስትን ግብ አሁን ክርስቶስን መምሰል ነው። አማኞች ሕያው ድንጋይ ሆነው በክርስቶስ ላይ ይገነባሉ (አዲሱ መቅደስ)።

ሠ. ኢየሱስ የእምነታችን መሠረት እንዲሁም የእምነታችን መደምደሚያ ነው (አልፋና ኦሜጋ)። እንዲሁም የማሰናከያ ድንጋይና ዐለት ነው። እሱን ማጣት ሁሉንም ነገር ማጣት ነው። እዚህ ጋ አማካኝ ስፍራ አይኖርም!

4፡12 **"መዳን በሌላ በማንም የለምና"** ይህ ጠንካራ ድርብ አሉታ ነው:: በአብርሃምም ሆነ በሙሴ መዳን የለም፣ (ዮሐንስ 14፡6፤ 1ኛ ጢሞ. 2፡5):: እንዴት የሚያስደነግጥ ክርክር ነው! እሱም በጣም ጥብቅ ነው፣ ግን በጣም ግልጽ ነው፣ ማለትም ኢየሱስ የሚለው ከእሱ ጋር በሚደረግ የግል ግንኙነት ብቻ ነው ማንም እግዚአብሔርን የሚያውቀው:: ጴጥሮስ ይሄንን በግልጽ ለተማሩት የአይሁድ መሪዎች አውጇል:: ይህ ዘወትር የሚጠራው ከክርስትና የማይደበልቅ ክፉ ድርጊት ይባላል:: እዚህጋ መካከለኛ ስፍራ የለም:: ይህ መግለጫ እውነት ነው አልያም ክርስትና ሐሰት ነው!

▣ **"ከሰማይ በታች ለሰዎች የተሰጠ ሌላ ስም የለምና"** "የተሰጠ ስም" የሚለው ቦዝ አንቀጽ የተጠናቀቀ ተገብሮ ነው:: እግዚአብሔር ይሄንን አጽንቷል! ኢየሱስ ለሰዎች መንፈሳዊ መሻት ምላሽ ነው:: ሌለኛ እቅድ የለም! በክርስትና ያለመካተት ጥያቄ ለመልካም መጽሐፍ ኤች. ኤ. ኔትላንድ፣ ያልተጣጣሙ ድምጾች: *ሃይማኖታዊ ምንታዌነትና የእውነት ጥያቄን* ተመልከት::

▣ **"በሰዎች መካከል"** ሁለንተናዊ ይዘትን አስተውል (ዮሐንስ 3፡16፤ 1ኛ ጢሞ. 2፡5፤ 2ኛ ጴጥ. 3፡9)::

▣ **"በእሱም የምንድንበት"** ይህ ሐረግ ሁለት ግፆች አሉት::

1. *dei*፣ የአሁን የድርጊት አመላካች፣ "እኛ የግድ"
2. *sōthēnai*፣ የድርጊት ተገብሮ ንዑስ አንቀጽ የ*sōzō*

"መዳን" የሚለው ቃል በአኪ. ሁለት አጠቃቀም አለው::

1. አካላዊ መዋጀት (ብኪ. አግባብ፣ ማቲ. 9:22፤ ማርቆስ 6:56፤ ሉቃስ 1:71፤ 6:9፤ 7:50፤ ሐዋ. 27:20፣31፤ ያዕቆብ 1:21፤ 2:14፤ 4:12፤ 5:20)
2. መንፈሳዊ ደኅንነት (አኪ. አግባብ፣ ሉቃስ 19:10፤ ሐዋ. 2:21፣40፣47፤ 11:14፤ 15:11፤ 16:30-31)

ሸባው ሰው ሁለቱም ደርሶበታል:: ሃይማኖታዊዎቹ መሪዎች ኢየሱስን ሊያምኑ የሚገባቸው እንደ ብቸኛ ተስፋቸው መቀበያና ይቅር መባላቸው ነው! ሰዎች ሊድኑ ይገባል፣ ይሄንንም ለመቀዳጀት ኢየሱስ ብቸኛው መንገድ ነው:: የብኪ. ጥቅስ በቁ. 12 የሚያሳየው እሱ ዘወትር የእግዚአብሔር እቅድ እንደሆነ ነው (ኢሳ. 8:14-15፤ 28:14-19፤ 52:13-53:12)::

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 4:13-22**

**[13]ጴጥሮስና ዮሐንስም በግልጥ እንደ ተናገሩ ባዩ ጊዜ፥ መጽሐፍን የማያውቁና ያልተማሩ ሰዎች እንደ ሆኑ አስተውለው አደነቁ፥ ከኢየሱስም ጋር እንደ ነበሩ አወቁአቸው፤ [14]የተፈወሰውንም ሰው ከእነርሱ ጋር ቆሞ ሲያዩ የሚመልሱትን አጡ። [15]ከሸንጎም ወደ ውጭ ይወጡ ዘንድ አዘዘው። በእነዚህ ሰዎች ምን እንሥራ? [16]የታወቀ ምልክት በእነርሱ እጅ እንደ ተደረገ በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ ሁሉ ተገልጦአልና፥ እንሸሽገው ዘንድ አንችልም፤ [17]ነገር ግን በሕዝቡ ዘንድ አብዝቶ እንዳይስፋፋ፥ ከእንግዲህ ወዲህ ለማንም ሰው በዚህ ስም እንዳይናገሩ እየዛትን እንዘዛቸው ብለው እርስ በርሳቸው ተማከሩ። [18]ጠርተውም በኢየሱስ ስም ፈጽመው እንዳይናገሩና እንዳያስተምሩ አዘዙአቸው። [19]ጴጥሮስና ዮሐንስ ግን መልሰው። እግዚአብሔርን ከመስማት ይልቅ እናንተን እንሰማ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት የሚገባ እንደ ሆነ ቍረጡ፤ [20]እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ዝም ማለት አንችልም አሉአቸው። [21]እነርሱም እንደ ምን እንደሚቀጡ ምክንያት ስላላገኙባቸው፥ እንደ ገና ዝተው ከሕዝቡ የተነሣ ፈቱአቸው፤ ሰዎች ሁሉ ስለ ሆነው ነገር እግዚአብሔርን ያከብሩ ነበርና። [22]ይህ የመፈወስ ምልክት የተደረገለት ሰው ከአርባ ዓመት ይበልጠው ነበርና።**

4:13 "ያልተማሩ" ቃሉ ቃግራማቶስ ሲሆን፣ "መጻፍ" የሚል ቃል ሆኖ በአልፋ ፕራይቬቲቭ መጻፍ ነው:: ይሄም ምናልባት እነሱ (1) ማይም ወይም ያልተማሩ ሊሆኑ ይችላሉ (ሙልቶን፣ ሚሊጋን፣ መዝገበ ቃላት ገጽ 6) ወይም (2) በራቢያዊ ትምህርት ቤቶች ያለሠለጠኑ ሊሆኑ ይችላሉ (ኤ. ቲ. ሮበርትሰን፣ በግሪክ አዲስ ኪዳን የቃላት ስዕሎች፣ ቅጽ 3፣ ገጽ 52 እና ሎው እና ኒዳ፣ ሥርወቃል፣ ቅጽ 1፣ ገጽ 328)::

▣ "ያልሠለጠኑ" ይህ ቃል idiōtēs፣ ዘወትር የሚተረጎመው "ተራ ሰው" ወይም "በአንድ ሙያ ያልሠለጠነ" ማለት ነው:: በመነሻው የሚያመለክተው ለተራው ሰው መሪን ወይም ቃል አቀባይን እንደሚቃወም ተደርጎ ነው:: ጥቅም ላይ የዋለውም በውጭ ያለ እና የቡድኑ አባልን በተቃርኖ ነው፣ (1ኛ ቆሮ. 14:16፣23-24፤ 2ኛ ቆሮ. 11:6)::

ይህንን ሐረግ የተለያዩ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች እንዴት እንደተረጎሙት ተመልከት::

| | |
|---|---|
| አአመመቅ፣ አኪጀት | "ያልተማሩና ያልሠለጠኑ ሰዎች" |
| አየተመት | "ያልተማሩና ተራ ሰዎች" |
| አእት | "ተራ ሰዎች ትምህርት የሌላቸው" |
| አኢመቅ | "ያልተማሩ ተራ ሰዎች" |

▣ "እነሱም ተደንቀው" ይህ ያልተጠናቀቀ የአሁን አመላካች ነው፣ (እንደ ተከታዮቹ ሁለት ግሦች):: እነሱም የሚያሳዩት የአንድን ድርጊት መጀመር ወይም ካለፈው ጊዜ ድርጊት የተደገመውን ነው (ባመላካች ድባብ):: ሉቃስ ይሄንን ቃል አዘውትሮ ይጠቀማል (18 ጊዜ በሉቃስ እና በሐዋ.)፤ አዘውትሮ ነው፣ ሁልጊዜም ባይሆን፣ ይህም አሉታዊ ፍች አለው (ሉቃስ 11:38፤ 20:26፤ ሐዋ. 4:13፤ 13:41)::

▣ "ከኢየሱስ ጋር እንደነበሩ አወቋቸው" ይህ በርግጥ ማሚያ ነው:: ኢየሱስ በራቢያዊ ትምህርት ቤቶች አልተማረም፣ ሆኖም ብሉይ ኪዳንን በሚገባ ያውቃል:: በምኵራብ ትምህርት ቤቶች ይገኝ ነበር እንደ ማንኛውን የአይሁድ ልጅ (እንዲሁም ጴጥሮስና ዮሐንስ) እንዲሁ እንዲያደርጉ::

እነዚህ መሪዎች የጴጥሮስንና የዮሐንስን ግጽልነትና ኃይል ተገንዝበዋል:: ይህንንም በኢየሱስ ተመልክተዋል::

4:14 ሁሉም የህንን ሽባ ሰውዬ ያውቀዋል፣ ምክንያቱም በመደበኛነት በቤተ መቅደስ ደጅ በየዕለቱ ስለሚቀመጥ ነው:: ነገር ግን ካሁን በኋላ አይቀመጥም! በመቅደስ ያሉት ሕዝቦች ይሄንን ሊክዱ አይችሉም (ዝከ ቁ. 16፣22)::

4:15 ሦስቱንም እንዲሄዱ ጠየቋቸው፣ እነሱ በአማራጮቻቸው ላይ ሲወያዩና የክህደትና ያለመቀበል እቅዳቸውን ነድፈው (ዝከ ቁ. 17-18)::

4:17-18 ዕቅዳቸው ይህ ነበር! ስለ ኢየሱስ መናገርን ማስቆም፣ እንዲሁም በእሱ ስም ሰዎችን መርዳትን ማስቆም! ስለ ፈውሱ እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑት ሰዎች እንዴት ነው (ዝከ 3:8-9፤ 4:16)?

4:19 "የ… እንደሆነ" ይህ አንደኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ነው፣ እርግጠኛ ላልሆነ ጉዳይ ግልጋሎት ላይ የሚውል፣ ነገር ግን ለክርክር ሲባል:: ጴጥሮስና ዮሐንስ ትዕዛዛቸው ዋጋ ያለው መሆኑን አልተረዱላቸውም (ዝከ 5:28)::

▣ "ትክክል" ልዩ ርዕስ፡ ጽድቅ 3:14 ተመልከት::

▣ "እናንተው ፍረዱ" ይህ ያለፈ ድርጊት ተተኳሪ ነው:: በራሳቸው ቃል፣ የልብ ሐሳብ፣ እና ድርጊት ኮነኗቸው::

4:20 ጴጥሮስና ዮሐንስ የተለማመዱትን ፈጽሞ እንደማይክዱና ማካፈልንም እንደማያቆሙ ገለጹ!

4:21 "እንደገናም በዛቱባቸው ጊዜ" ለምን እንደሚዝቱባቸው ይገርኛል:: ኢየሱስ ከሙታን ተነሥቷል::ሰውየውም ከአልጋው ላይ ተነሥቷል፤ እነዚህ መሪዎች ጴጥሮስንና ዮሐንስን ምን አድርጉ እያሏቸው ነበር?

▣ "(እነሱን የሚቀጡበት ምንም መነሻ አላገኙም)" ይህ የሉቃስ ጽሐፍ አንደኛው ተግባር አመላካች ሊሆን ይችላል:: ክርስትና ሮምን መገዳደር ወይም የኢየሩሳሌም ሰላም አይደለም:: የፍርድ ችሎቶች እንኳ መሪዎቹን ከመወንጀል ምንም መሠረት አይኖራቸውም::

▣ "ስለ ሕዝቡ ብለው" በኢየሩሳሌም የተደረጉት ሁነቶች የዓይን ምስክሮች የጥንቷን ቤተ ክርስቲያን በከፍተኛ ስሜት ቀረቧት (2:47):: የአይሁድ መሪዎች በዚህ ታዋቂ ጉዳይ ተቸገሩ (ዝከ 5:13፣26)::

| |
|---|
| **አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 4:23-31**<br>**[23]ተፈትተውም ወደ ወገኖቻቸው መጡና የካህናት አለቆችና ሽማግሌዎች ያሉአቸውን ሁሉ ነገሩአቸው:: [24]እነርሱም በሰሙ ጊዜ በአንድ ልብ ሆነው ወደ እግዚአብሔር ድምፃቸውን ከፍ አደረጉ እንዲህም አሉ:: ጌታ ሆይ፥ አንተ ሰማዩንና ምድሩን ባሕሩንም በእነርሱም የሚኖረውን ሁሉ የፈጠርህ፥ [25]በመንፈስ ቅዱስም በብላቴናህ በአባታችን በዳዊት አፍ:: አሕዛብ ለምን አጕረመረሙ? ሕዝቡስ ከንቱን ነገር ለምን አሰቡ? [26]የምድር ነገሥታት ተነሡ አለቆችም በጌታና በተቀባው ላይ አብረው ተከማቹ ብለህ የተናገርህ አምላክ ነህ:: [27-28]በቀባኸው በቅዱሱ ብላቴናህ በኢየሱስ ላይ ሄሮድስና ጴንጤናዊው ጲላጦስ ከአሕዛብና ከእስራኤል ሕዝብ ጋር፥ እጅህና አሳብህ እንዲሆን አስቀድመው የወሰኑትን ሁሉ ሊፈጽሙ፥ በዚች ከተማ በእውነት ተሰበሰቡ:: [29-30]አሁንም፥ ጌታ ሆይ፥ ወደ ዛቻቸው ተመልከት፤ ለመፈወስም እጅህን ስትዘረጋ በቅዱስ ብላቴናህም በኢየሱስ ስም ምልክትና ድንቅ ሲደረግ፥ ባሪያዎችህ በፍጹም ግልጥነት ቃልህን እንዲናገሩ ስጣቸው:: [31]ከጸለዩም በኋላ ተሰብስበው የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ፥ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ ተናገሩ::** |

4:23 እነሱም ተመልሰው ወደ ደርቡ ክፍል ሄዱ፣ ደቀ መዛሙርትን ለመገናኘት::

4:24 "በአንድ ልብ" ይህ የልብ እና የሐሳብ ኅብረት የጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን መለያ ነበር (ዝከ 1:14፤ 2:46፤ 4:24፤ 5:12፤ 15:25):: መንፈሳዊ ኃይልና ተተኳሪ ድርጊት በዓላማ አንድነት ሁኔታ ውስጥ ይኖራል::

▣ "ጌታ" ይህ የግሪክ ቃል ዲስፖታ ሲሆን፣ ከዚህም የእንግሊዝኛውን ቃል ፍጹም ገዥ እናገኛለን:: እሱም ሲተረጎም ፍጹም ሥልጣን ያለውን ነው! እዚህ ላይ የተጠቀሰው እግዚአብሔር አብን ነው (ሉቃስ 2:29 እና ራዕ. 6:10):: ለኢየሱስም ጥቅም ላይ ውሏል )2ኛ ጴጥ. 2:1 እና ይሁዳ 4)::

▣ "እሱም ሰማይና ምድርን እንዲደሁም የብሱንና ባሕሩን፣ በውስጣቸው ያለውን ሁሉ የፈጠረውን" ይህ ምናልባት ዘጸ. 20:11ን የሚያጣቅስ ነው:: በ14:15 ላይ ደግሞ ተጠቅሷል፣ እንዲሁም እውነታው 17:24 ላይ ተጠቅሷል::

4:25 የዚህ ቁጥር የመጀመሪያ ክፍል በርካታ የተለያዩ ምንባቦች አሉት:: ጥንታውያን የእጅ ጽሑፎች ፒ74፣ N፣ ሀ፣ እና ለ ቀደም ብለው አሻሚዎቹን ልዩነቶች ይዘዋል:: ትክክለኛው የቃላት ሁኔታ ርግጠኛ ባይኮንም የቃሉ መታመን ግልጽ ነው:: ሙሉ ችግሩን ለረዳትና ንድፈ ሐሳቡ ምን እንደሆነ ለመረዳት፣ ብሩስ ኤም. ሜዝገር፣ የግሪክ አዲስ ኪዳን ጽሑፋዊ ሐተታ፣ ገጽ 321-323 ተመልከት)::

▣ "በመንፈስ ቅዱስ በኩል በአባታችን በዳዊት አንደበት" ይህ የሚያመላክተው የብሉይ ኪዳንን ተመስጧዊነት ነው:: ይህ የተጠቀሰው ከሴፕቱዋጂንት ላይ ከመዝሙር 2:1-2፣ የንጉሣዊው መሲሐዊ መዝሙር:: የዓለም ተቃውሞ የሚጠበቅ ነው፣ ሆኖም ግን የያህዌም ድል አድራጊነት::

በሐዋ. ሉቃስ በርካታ የብኪ. ጥቅሶችን መዝግቧል፣ ከወንጌል ጋር የተያያዙትን::

1. ኢዩኤል 2:1-5 በሐዋ. 2:16
2. መዝሙር 16:8-11 በሐዋ. 2:25
3. ኢሳይያስ 52:12-53:13 በሐዋ. 3:18
4. ዘዳ. 18:15-20 በሐዋ. 3:22
5. ዘፍ. 12:3፤ 22:18 በሐዋ. 3:25
6. መዝሙር 118:22 በሐዋ. 4:11

7. *መዝሙር* 2፡1-2 በሐዋ. 4፡25-26
ክርስትና አዲስ ነገር አይደለም፣ ነገር ግን የብሉይ ኪዳን ፍጻሜ እንጂ (ማቴ. 5፡17-48)።

4፡25-26 **"አሕዛብ... ሕዝቦች... ነገሥታት... ገዥዎች"** ደቀ መዛሙርት ራቢያዊ ቃል "ከገዥዎች" ጋር የሚያያዘውን የተጠቀሙ ይመስላል። የጥንታዊውን ችሎት የሚጠሩ ይመስላል (ማለትም አሕዛብ)!

▣ "ቁጣ" ይሄ በጥሬው "በአፍንጫ ማንኮራፋት ነው።" ይህም አጉል ግትርነትን ያሳያል።

4፡26 **"ጌታ... የሱም ክርስቶስ"** ያህዌና መሲህ አንድ ላይ እንደሚባሉ ተመልከት። ለምን መዝ. 110፡1 እንዳልጠቀሱት ይደንቀኛል!

አሀድኛ ሆኖ የክርስቶስን ፍጹም መለኮትነት እና የመንፈስን አካልነት መናገር በጣም ይከብዳል (ዝከ ቁ. 25)። እናም እነዚህ ሦስት መለኮት፣ ዘላለማዊ አካላት በጽሑፉ የሚገለጡት በአኪ ጽሑፍ በኋላ ነው። ሁሉም ጸሐፊዎች ከሉቃስ በስተቀር አሀዳዊ፣ አይሁድ ክርስቲያኖች እንደሆኑ አስተውል። ሥላሴን ለማስገባት አንዳች ጽኑ ነገር ምክንያት ሆኖባቸዋል (እሱም ወንጌል)። ሥላሴ የሚለውን ሙሉ ማስታወሻ 2፡32 ተመልከት።

4፡27 **"በቀባኸው በቅዱሱ ብላቴናህ፣ በኢየሱስ"** እነዚህን መሲሐዊ ማዕረጎች አስተውል።

1.ቅዱስ (ዝከ 3፡14፤ 4፡30)
2.አገልጋይ (ፔይስ፣ ዝከ. 3፡13፣26፤ 4፡25፣27፣30)
3.የተቀባው (ክሪኦ፣ ከሱም ክርስቶስ የመጣ፣ ሉቃስ 4፡18፤ ሐዋ. 4፡27፤ 10፡38)

ይህ ቁጥር ኢየሱስ በያህዌ እንደ ተላከና ሥልጣን እንደ ተሰጠው በተለያየ መንገድ ያሳያል። ኢየሱስ የእግዚአብሔር የመቤዣ እና የተሐድሶ ዘላለማዊ እቅድ እና ዘዴ ነው (ዝከ ቁ. 28)።

**ልዩ ርዕስ፡ መቀባት በመጽሐፍ ቅዱስ**

*ሀ. ለመዋቢያነት ያገለግላል* (ዘዳ. 28፡40፤ ሩት 3፡3፤ 2ኛ ሳሙ. 12፡20፤ 14፡2፤ 2ኛ ዜና. 28፡1-5፤ ዳን. 10፡3፤ ዐሞጽ 6፡6፤ ሚክ. 6፡15)
*ለ. ለእንግዶች ይሆናል* (መዝ. 23፡5፤ ሉቃስ 7፡38፡46፤ ዮሐንስ 11፡2)
*ሐ. ለፈውስ ይሆናል* (ኢሳ. 6፡1፤ ኤር. 51፡8፤ ማርቆስ 6፡13፤ ሉቃስ 10፡34፤ ያዕቆብ 5፡14) (በንጽሕና አጠባበቅ አግባብ ሕዝ. 16፡9 ላይ ውሏል)
*መ. ለቀብር ዝግጅት* (ዘፍ. 50፡2፤ 2ኛ ዜና. 16፡14፤ ማርቆስ 16፡1፤ ዮሐንስ 12፡3፡7፤ 19፡39-40)
*ሠ. ለሃይማኖታዊ ጉዳይ ይውላል* (እንደ አንድ ቁስ፡ ዘፍ. 28፡18፡20፤ 31፡13 (ምሰሶ)፤ ዘጸ. 29፡36 (መሠዊያ)፤ ዘጸ. 30፡36፤ 40፡9-16፤ ሌዋ. 8፡10-13፤ ዘኁ. 7፡1 (ማስተሠርያ))
*ረ. መሪዎችን ለመሰየም*
   1. ካህናት
      ሀ. አሮን (ዘጸ. 28፡41፤ 29፡7፤ 30፡30)
      ለ. የአሮን ልጆች (ዘጸ. 40፡15፤ ሌዋ. 7፡36)
      ሐ. ቋሚ ሐረግ ወይም ማዕርግ (ዘኁ. 3፡3፤ ሌዋ. 16፡32)
   2. ነገሥታት
      ሀ. በእግዚአብሔር (1ኛ ሳሙ. 2፡10፤ 2ኛ ሳሙ. 12፡7፤ 2ኛ ነገሥ. 9፡3፡6፡12፤ መዝ. 45፡7፤ 89፡20)
      ለ. በነቢያት (1ኛ ሳሙ. 9፡16፤ 10፡1፤ 15፡1፡17፤ 16፡3፡12- 13፤ 1ኛ ነገ". 1፡45፤ 19፡15-16)
      ሐ. በካህናት (1ኛ ነገሥ. 1፡34፡39፤ 2ኛ ነገሥ. 11፡12)
      መ. በሽማግሌዎች (መሳ. 9፡8፡15፤ 2ኛ ሳሙ. 2፡7፤ 5፡3፤ 2ኛ ነገሥ. 23፡30)
      ሠ. ለኢየሱስ እንደ መሲሐዊ ንጉሥ (መዝ. 2፡2፤ ሉቃስ 4፡18 (ኢሳ. 61፡1)፤ ሐዋ. 4፡27፤ 10፡38፤ ዕብ. 1፡9 (መዝ. 45፡7))
      ረ. ለኢየሱስ ተከታዮች (2ኛ ቆሮ. 1፡21፤ 1ኛ ዮሐንስ 2፡20፡27 (ክሪስማ))
   3. ለነቢያት (ኢሳ. 61፡1)
   4. የማያምኑ የመለኮት አዳኞች
      ሀ. ሳይረስ (ኢሳ. 45፡1)
      ለ. የጢሮስ ንጉሥ (ሕዝ. 28፡14)
   5. ቃል ወይም ማዕርግ "መሲሕ" "የተቀባው" ማለት ነው።

▣ **"እነሱም በቅዱሳን ባሪያዎችህ ላይ ተሰብስበው ተነሡ"** ቀጥሎ ያለው በኢየሩሳሌም የኢየሱስ ተቃዋሚዎች ዝርዝር ነው።

1. ሄሮድስ፣ ሮማውያን የሾሙት ኤዶማዊ የፍልስጥኤም ገዥ
2. ጴንጤናዊው ጲላጦስ፣ የሮሜ አስተዳደር መሪ በፍልስጥኤም
3. አሕዛብ፣ ይህም ምናልባት የሚያመለክተው የሮሜን ጦር ሠራዊት ወይም አዲስ ወደ ይሁዲነት የተቀየሩትን ነው
4. "የእስራኤል ሕዝቦች" ይህም የሚያመለክተው የአይሁድ ባለሥልጣናትን እና የአይሁድ አድመኞች እነሱም በርናባስ እንዲፈታ ኢየሱስ እንዲሰቀል የጠየቁ

4:28 **"እጅህና ሐሳብህ ቀደም ሲል የተወሰነው እንዲሆን"** ከፍጥረት በፊት እንኳ እግዚአብሔር የራሱ የመዋጀት እቅድ ነበረው (ማቴ. 25:34፤ ዮሐንስ 17:24፤ ኤፌ. 1:4፤ 1ኛ ጴጥ. 1:20፤ ራዕ. 13:8፤ ሐዋ. 2:13፤ 3:18፤ 13:29)። እነዚህ የኢየሱስ ጠላቶች ያከናወኑት እግዚአብሔር እንዲያደርጉ የፈቀደውን ነው። ኢየሱስ የመጣው ሊሞት ነው (ማርቆስ 10:45)። ቃሉ እዚህ የተተረጎመው "ቅድመ ውሳኔ"፣ የመስተጻምር "በፊት" እና "ውል ማሰናዳት" ከሚለው ነው፣ (ሮሜ 8:29፣30፤ 1ኛ ቆሮ. 2:7፤ ኤፌ. 1:5፣11)።

ገጻጭ የሆኑት ምንባቦች በቅድመ ውሳኔ፣ በአኪ ላይ ሮሜ 8:28-30፤ ሮሜ 9፤ እና ኤፌ. 1:3፣14 ናቸው። እነዚህ ጽሑፎች በግልጽ ለእግዚአብሔር ሉዓላዊነት አጽንዖት ይሰጣሉ። እሱ ሁሉንም ነገር አጠቃሎ ይቆጣጠራል፣ የሰዎችንም ታሪክ ጭምር። መለኮታዊ የሆነ የመዋጀት እቅድ አሁን አለ፣ በጊዜው የሚሠራ። ሆኖም፣ ይህ ዕቅድ አሻሚ ወይም አማራጭ ያለው አይደለም። እሱም የተመሠረተው በእግዚአብሔር ሉዓላዊነትና ቀድሞ አዋቂነት ላይ ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን ደግሞ በእሱ የማይለወጥ ባሕርይ፣ በፍቅር፣ በምሕረት፣ እና በማይለካ ጸጋ ነው።

እኛም ከምዕራብ (ከአሜሪካ) ግለሰበኝነት መጠንቀቅ አለብን ወይም የእኛ የወንጌላዊነት ፍላጎት ይህንን አስደናቂ እውነት እንዳይሸፍነው። ደግሞም መጠበቅ ያለብን አንድ አቅጣጫዊ ከሆን የታሪክ፣ ሥነመለኮታዊ ግጭት በአውግስጢኖስ እና በፐሌጊዩስ ወይም ካልቪን እና አርመናዊነት መካከል ካለው ነው።

ቅድመ ውሳኔ መሠረተ እምነት አይደለም ማለት የእግዚአብሔርን ፍቅር፣ ጸጋ፣ እና ምሕረት መወሰን ነው። ማለትም አማኞችን ለማጠናከር፣ ስለ ዓለም ያላቸውን አተያይ መልክ ለማስያዝ ነው። የእግዚአብሔር ፍቅር ለሁሉም የሰው ልጆች ነው (1ኛ ጢሞ. 2:4፤ 2ኛ ጴጥ. 3:9)። እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ይቆጣጠራል። ከእሱ ማን ወይም ምን ይለየናል? (ሮሜ. 8:31-39)። ቅድመ ውሳኔ በሕይወት እንዲታይ ከሁለት አንድ መንገድ አለው። እግዚአብሔር ሁሉንም ታሪክ የሚመለከተው በአሁን ነው። ሰዎች በጊዜ የተወሰኑ ናቸው። የእኛ አስተሳሰብም ሆነ የአእምሮ ችሎታ የተወሰነ ነው። በእግዚአብሔር ሉዓዊነትና በሰው ልጆች ነጻ ፍቃድ መካከል ተቃርኖ የለም። እሱ ኪዳናዊ መዋቅር ነው። ይህ ሌለኛው ምሳሌ ዓይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት፣ በአያዋዊ (ፓራዶክስ)፣ ክርክራዊ፣ በክርክር የተሞሉ ጥንዶች ናቸው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረተ እምነቶች የሚቀርቡት በተለያየ አተያይ ነው። እነሱም ዘወትር የሚከሰቱት አያኦአዊ ሆነው ነው። እውነቱ ሚዛናዊ ሆኖ ቀርቧል፣ ተቃራኒ በሚመስሉት ጥንዶች። ክርክሩን ልናስወግደው አይገባም፣ አንዱን እውነት ብቻ በማንሣት። አንዱን ብቻ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ነጥለን በመያዝ በራሱ ብቻ ወደ አጠቃላይ ልናመጣው አይገባም።

እዚህ ጋ መጨመር ደህና የሚሆነው የመመረጥ ግብ ስንሞት መንግሥተ ሰማያት ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን አሁንም ክርስቶስን መምሰል ነው፣ (ኤፌ. 1:4፤ 2:10)! የተመረጥነው "ቅዱስና ያለ ነውር" እንድንሆን ነው። እግዚአብሔር የመረጠን ሊለውጠን ነው፣ ስለሆነም ሌሎች ለውጡን አይተው በእምነት በኢየሱስ በኩል ለእግዚአብሔር ምላሽ እንዲሰጡ። ቅድመ ውሳኔ በግል የሚደረግ አድልኦ አይደለም፣ ነገር ግን ኪዳናዊ ኃላፊነት ነው! የዳንነው ለማገልገል ነው!

4:29 **"ቃልህን እንዲናገሩ"** ይህ የአሁን የድርጊት ንዑስ አንቀጽ ነው። ይህ ለቀጣይ ግልጽነት የተደረገ ጸሎት ነው (ኤፌ. 6:19 እና ቆላ. 4:3) እና የተመስጦው ማጽኛ ነው (2ኛ ጢሞ. 3:15-17)።

▣

| | |
|---|---|
| አአመመቅ | "በሙሉ ድፍረት" |
| አኪጀት፣ አየተመት | |
| አእት | "በሙሉ ግልጽነት" |
| አኢመቅ | "ያለ ምንም ፍርሃት" |

የሚከተለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት

**ልዩ ርዕስ፡ ግልጽነት (ፓሬሲያ)**

የግሪኩ ቃል የ "ሁሉም" (ፓን) እና "ንግግር" (ሬሲስ) ድብልቅ ነው። ይህ ነጻነት ወይም ግልጽነት በንግግር፣ ዘወትር የግልጽነት ፍች የሚኖረው በተቃውሞ ወይም ተቀባይነትን በማጣት መካከል ነው (ዮሐንስ 7:13፤ 1ኛ ተሰ. 2:22)።

በዮሐንስ ጽሑፎች (13 ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለው) ዘወትር የሚጠቀሰው በሕዝብ ፊት ማወጅን ነው (ዮሐንስ 7:4፤ እንዲሁም በጳውሎስ ጽሑፎች፣ ቆላ. 2:15)። ሆኖም፣ አንዳንዴ "በግልጽ" ይሆናል (ዮሐንስ 10:24፤ 11:14፤ 16:25፣29)።

በሐዋ. ሐዋርያት ስለ ኢየሱስ መልዕክታቸውን ሲያቀርቡ በተመሳሳይ መልኩ ነው፣ ልክ ኢየሱስ ስለ አብና እቅዱ እንዲሁም ስለ ተስፋው (ሐዋ. 2:29፤ 4:13፣29፣31፤ 9:27-28፤ 13:46፤ 14:3፤ 18:26፤ 19:8፤ 26:26፤ 28:31)። ጳውሎስ ደግሞ ወንጌልን በግልጽ እንዲሰብክ እንዲጸለይለት ጠይቋል (ኤፌ. 6:19፤ 1ኛ ተሰ. 2:2) እና ወንጌልን ለመኖር (ፊሊጵ. 1:20)።

የጳውሎስ የመጨረሻው ተስፋ በኢየሱስ፣ ግልጽነትንና መተማመንን ሰጥቶታል በዚህ ጊዜያዊ ክፉ ዘመን ላይ ወንጌልን ለመስበክ (2ኛ ቆሮ. 3:11-12)። እሱም ደግሞ ጽኑ እምነት አለው፣ የኢየሱስ ተከታዮች በተገቢው እንደሚራመዱ (2ኛ ቆሮ. 7:4)።

አንድ ሌላ ደግሞ የዚህ ቃል ተጨማሪ ገጽታ አለ። ዕብራውያን የሚጠቀሙበት በተለየ የግልጽነት አግባብ ነው፣ እግዚአብሔርን በክርስቶስ ስለመቅረብና እሱን ስለማናገር (ዕብ. 3:6፤ 4:16፤ 10:19፣35)። አማኞች ሙሉ ተቀባይነትና መልካም አቀባበል፣ ከአብ ጋር ቤተሰባዊነት በልጁ በኩል አላቸው!

4:30 “*እጅህን ለመፈወስ ስትዘረጋ*” ይህ አካላዊ የሆነ ሐረግ ሲሆን፣ ጥቅም ላይ የዋለውም እግዚአብሔር ረድኤቱንና ሃይሉን እንደሚያደርግ ነው። ምልክቶቹ የወንጌልን መልዕክት ለማጽናት መንገዶች ናቸው። እሱም ፈጽሞ የተለየ መልዕክት ነው፣ ሕይወታቸውን ሙሉ በምኩራብ ይሰሙ ከነበረው።

4:31 “*እነሱ ተሰብስበውበት የነበረው ስፍራ የነቃነቀ*” እግዚአብሔር እነዚህን ምስክሮች በሌላ አካላዊ ድርጊት፣ በሃይሉ እና በመገኘቱ፣ በጰንጠቆስጤ እንዳደረገው ሁሉ አበረታታቸው። ቃሉ ጥቅም ላይ የዋለው በሚንሳፈፍ ዕቃ ላይ እንደሚነፍስ ነፋስ ነው።

▣ “*ሁሉም መንፈስ ቅዱስን ተሞሉ*” እዚህ ሁሉም በድጋሚ እንደተሞሉ አስተውል (ዝከ 2:4፤ 4:8፣31፤ 9:17፤ 13:9፣52)። ይህ ሙላት ወንጌልን በግልጽ ለመስበክ ነው። እንዲሁም ልሳናት <u>አለ</u>መጠቀሳቸውን አስተውል። በሐዋ. ልሳናት ሲጠቀሱ፣ ዘወትር በወንጌላዊነት ደረጃ ነው፣ ማለትም ወንጌል ባህል-ዘርን እንደሚያሸንፍ እንዲሁም)ወይም መልክዓ ምድራዊ ወሰኖችን።

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 4:32-35**

*[32]ያመኑትም ሕዝብ አንድ ልብ አንዲትም ነፍስ ነበሩአቸው፥ ገንዘባቸውም ሁሉ በአንድነት ነበረ እንጂ ካለው አንድ ነገር ስንኳ የራሱ እንደ ሆነ ማንም አልተናገረም። [33]ሐዋርያትም የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በታላቅ ኃይል ይመሰክሩ ነበር፤ በሁሉም ላይ ታላቅ ጸጋ ነበረባቸው። [34]በመካከላቸው አንድ ስንኳ ችግረኛ አልነበረምና፤ መሬት ወይም ቤት ያላቸው ሁሉ እየሸጡ የተሸጠውን ዋጋ ያመጡ ነበርና፥ [35]በሐዋርያትም እግር አጠገብ ያኖሩ ነበር፤ ማናቸውም እንደሚፈልግ መጠን ለእያንዳንዱ ያካፍሉት ነበር።*

4:32 “*የሚያምኑትም አንድ ልብና ነፍስ ነበራቸው*” በአማኞች መካከል የነበረው የህብረት መንፈስ (ዝከ 1:14) የሥላሴን (እግዚአብሔርን) ህብረት ያንጸባርቃል (ኤፌ. 4:4-6)። እነዚሁ ሁነኛ ቃላት በማርቆስ 12:30 ጥቅም ላይ ውለዋል የመጀመሪያውን ትእዛዝ ዘዳ. 6:4-5 ያለውን ለማንጸባረቅ።

▣ “*ሁሉም ነገር በጋራ በአግባቡ ይከፋፈል ነበር*” የሚሰማቸውም የሚንቀሳቀሱትም እንደ ቤተሰብ ነበር። ይህ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎትን ለመደገፍ ያደረገችው የመጀመሪያ ሙከራ ነበር። እሱም በፍቃደኝነትና በመግባባት እንጂ አስገዳጅ አልነበረም። ፍቅርና ውዴታ እንጂ መንግሥታዊ ወይም ማህበራዊ ደረጃ አልነበረም መነሻ ሐሳቡ!

4:33 “*የትንሣኤውን ምስክርነት እየሰጡ*” ይህ የመልእክታቸው ማዕከላዊ እውነት ነበር (1ኛ ቆሮ. 15)። ኢየሱስ በሕይወት አለ!

▣ “*በሁሉም ላይ ጸጋው በምላት ነበረባቸው*” ከጳውሎስ መልእክቶች የምንማረው በቀድሞ ጊዜ ይህች ቤተ-ክርስቲያን በጣም ደሀ እንደነበረች ነው፣ (ሮሜ. 15:3፤ ገላ. 2:10)። የተትረፈረፈ ጸጋ፣ እንደ ተትረፈረፈ ኑሮ (ዮሐንስ 10:10) ቁሳዊ ነገር የሚረባው ጥቂት ነው። ይህ መትረፍረፍ ለሁሉም እንደሆነ አስተውል፣ ለመሪዎች ብቻ ሳይሆን፣ የተወሰኑ ስጦታዎችን የያዙት፣ ወይም በተወሰነ ማህበረ-ኮኖሚያዊ ደረጃ ላይ የሚገኙት።

4:34 ቤተ ክርስቲያን አንደኛው ለሌላው ኃላፊነት ይሰማው ነበር። ያላቸው፣ ለሌላቸው በነጻ ያካፍላሉ (ዝከ ቁ. 35)። ይህ ኮሚኒዝም አይደለም፣ ነገር ግን በተግባር መውደድ እንጂ።

4:35 “*በሐዋርያት እግር ሥር ያኖሩ ነበር*” ይህ ባህላዊ ዘይቤ ነው፣ አንዱ ለሌላው አንድ ነገር የሚሰጥበት። ዕቃቸውንና ገንዘባቸውን በሐዋርያት እግር ሥር ያኖሩ ነበር፣ ምክንያቱም ሕይወታቸውን በኢየሱስ እግር ሥር በማኖራቸው።

▣ “*ያከፋፍሉ ነበር*” ይህ ያልተጠናቀቀ ተገብሮ አመላካች ሲሆን፣ ባለፈው ጊዜ የሆነ ቀጣይ ድርጊትን ያሳያል።

▣ “*እያንዳንዱ እንደሚያስፈልገው*” አስደናቂ አስተያየት አለ፣ በክሊን፣ ብሎምበርግ፣ እና ሁባርድ ለመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ መግቢያ፣ ገጽ 451-453፣ ማለትም የማርክስ መግለጫ ከሐዋ. ሁለት ጥቅሶች መያዙን፡

1. “ከእያንዳንዱ እንደ ችሎታው” — 11:29
2. “ለእያንዳንዱ እንደ ፍላጎቱ”

የትርጓሜ ችግር የሚሆነው ዘመናዊው ሰው መጽሐፍ ቅዱስን ለደጋፊነት ለመጠቀም ፈጽሞ ያላለውን ወይም የማይገልጸውን መውሰዳቸው ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በዋነኛው ጸሐፊ ወይም አድማጭ ያልተባለውን ለእኛ ሊሆን ፈጽሞ አይችልም። ቃሉን በተለያየ መንገድ በባህላዊም ሆነ በነባራዊው ሁኔታ መጠቀም እንችላለን፣ ነገር ግን ከዋናው ጸሐፊ ሐሳብና ትርጉም ተለይቶ መሆን አለበት። እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሐሁፍ አንድ ትርጉም ብቻ ነው የሚኖረው፣ ነገር ግን በርካታ አገባብና ጠቀሜታዎች።

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፥ 4፡36-37**
[36]**ትውልዱም የቆጵሮስ ሰው የነበረ አንድ ሌዋዊ ዮሴፍ የሚሉት ነበረ፥ እርሱም በሐዋርያት በርናባስ ተባለ ትርጓሜውም የመጽናናት ልጅ ነው፤ [37]እርሻም ነበረውና ሸጦ ገንዘቡን አምጥቶ ከሐዋርያት እግር አጠገብ አኖረው።**

4፡36 **"ሌዋዊው ዮሴፍ"** በብሉይ ኪዳን ሕግ ካህናት ርስት እንዲኖራቸው አይፈቀድም፡፡ ግን የሮማውያን ባለስልጣናት በፍልስጤም ብዙ ነገሮችን ለውጠዋል፡፡

▣ **"በሐዋርያትም በርናባስ ተብሎ የተጠራ (ትርጉሙም የመጽናናት ልጅ ማለት ነው)"** ይህ የ "በርናባስ" የታወቀ ትርጉም ነው፡፡ በአራምኛ "የትንቢት ልጅ" ማለት ነው፡፡ እሱም የጳውሎስ ጓደኛና የአገልግሎት ባልደረባው ነበር፡፡ ኢዩሲበስ፣ የቀድሞ ቤተ ክርስቲያን፣ እሱ ከሰባዎቹ አንዱ ነበር ይላል ሉቃስ 10፡፡

**ልዩ ርዕስ፥ በርናባስ**

I. ሰውየው
   - ሀ. በቆጵሮስ ተወለደ (ሐዋ. 4፡36)
   - ለ. ከሌዊ ነገድ ነው (ሐዋ. 4፡36)
   - ሐ. የቅጽል ስሙ "የመጽናናት ልጅ" (ሐዋ. 4፡36፤ 11፡23)
   - መ. የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን አባል (ሐዋ. 11፡22)
   - ሠ. የትንቢትና የማስተማር መንፈሳዊ ስጦታ አለው (ሐዋ. 13፡1)
   - ረ. ሐዋርያ ተብሎ ተጠርቷል (ሐዋ. 14፡14)

II. አገልግሎቱ
   - ሀ. በኢየሩሳሌም
     1. ንብረቱን ሸጦ ያለውን ገንዘብ ሁሉ ለሐዋርያት ሰጠ፣ ድሆችን ለመርዳት (ሐዋ. 4፡34)
     2. የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪ ነበር (ሐዋ. 11፡22)
   - ለ. ከጳውሎስ ጋር
     1. የጳውሎስን መለወጥ እውነተኝነት ካመኑት መካከል የመጀመሪያው ነበር (ሐዋ. 11፡24)።
     2. ጳውሎስን ለመፈለግና ለመግኘት የአንቲሆችን አዲስ ቤተ ክርስቲያን ለመደገፍ ወደ ጠርሴስ ተጉዟል (ሐዋ. 11፡24-26)።
     3. የአንቲሆች ቤተ ክርስቲያን በርናባስንና ጳውሎስን ለድሆች ዕርዳታ በማስያዝ ወደ ኢየሩሳሌም ልካለች (ሐዋ. 11፡29-30)።
     4. በርናባስና ጳውሎስ የመጀመሪያውን ሚሲዮናዊ ተልዕኮ ተጉዘዋል (ሐዋ. 13፡1-3)
     5. በርናባስ በቆጵሮስ የቡድን መሪ ነበር (የትውልድ ደሴቱ)፣ ነገር ግን የጳውሎስ መሪነት እውቅና እንዳገኘ (ሐዋ. 13፡13)
     6. እነሱም ለኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን በአሕዛብ መካከል የፈጸሙትን ተግባር ሪፖርቱን አስረድተዋል፣ በሰነድም አስመዝግበዋል፣ (ሐዋ. 15፣ የኢየሩሌም ምክር ቤት ለሚባለው)።
     7. በርናባስና ጳውሎስ የመጀመሪያውን አለመግባባት፣ ስለ አይሁድ የምግብ ሕግጋት እና የአሕዛብ ኅብረት ተመዝግቧል፣ ገላ. 2፡11-14።
     8. በርናባስና ጳውሎስ ሁለተኛውን ሚሲዮናዊ ጉዞ አቀዱ፣ በገር ግን በበርናባስ የወንድም ልጅ፣ ዮሐንስ ማርቆስ አማካኝነት አለመግባባት ተፈጠረ (ቆላ. 4፡10)። የመጀመሪያውን ሚሲዮናዊ ተልዕኮ ሥራውን የተወ (ሐዋ. 13፡13)። ጳውሎስ ሊወስደው እምቢ አለ፣ በሁለተኛው ጉዞው ላይ፣ ስለሆነም ቡድኑ ተለያየ (ሐዋ. 15፡36-41)። ይህም ሁለት ቡድኖችን ፈጠረ (ማለትም፣ በርናባስ)ዮሐንስ ማርቆስ እና ጳውሎስ)ሲላስ)።

III. የቤተ ክርስቲያን ባህል (ኢዩሲቢዩስ)
   - ሀ. በርናባስ፣ ኢየሱስ ከላካቸው ከሰባዎቹ አንዱ ነበር (ሉቃስ 10፡1-20)።
   - ለ. የሞተውም እንደ ክርስቲያን ሠማዕት በትውልድ ደሴቱ፣ በቆጵሮስ ነው።
   - ሐ. ተርቱሊያን እንደሚለው እሱ የዕብራውያንን መልእክት ጽፏል።
   - መ. የአሌክሳንደሪያው ክሌመንት እንደሚለው የበርናባስ መልእክት የሚል አዋልድ መጽሐፍ አለው።

4፡37 **"የእርሻ መሬት የነበረው"** ይህ ለአነስተኛ መሬት የሚሆን ቃል አይደለም፡፡ ምናልባት ለቀብር የሚሆን ቦታ ሊሆን ይችላል፡፡ ምዕራፍ 5 የሚያሳየው ይህንን መሰሉን ዘዴ ያላግባብ ለመጠቀም ያለውን ዕድል ነው፣ በገንዘብ አገልግሎት ረገድ (ምሳሌ. ቅናት፣ ውሸት፣ እና ሞት)፡፡

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ለመርዳት ነው የተሰናዱት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋነኞቹን ጉዳዮች ለማጤን እንዲረዳ ነው። ሐሳብ ለማጫር እንጂ መደምደሚያ አይደሉም።

1. ሰዱቃውያን እነማን ናቸው? ለምን እንደዚህ ሆኑ?
2. ሳሄንድሪን (የአይሁድ የፍርድ ችሎት) ምንድነው?
3. የመዝ 118 ጠቀሜታ ምንድነው?
4. ቁ. 12 ጠቀሜታው ምንድነው?
5. ቁ. 28 ላይ ያለው ቅድመ እውቅና የሚያመለክተው የሰዎችን ወይስ የእግዚአብሔርን የመቤዠት እቅድ? ለምን?
6. ሉቃስ የሚሞክረው ለቤተ ክርስቲያን ቅድመ ሁኔታ ነውን? 4:32-5:11?

# የሐዋርያት ስራ 5

## የተሻሻሉ ትርጓሜዎች የአንቀፅ አከፋፈል

| የተየመቅሶ[4] | አኪጀት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ሐናንያ እና ሰጲራ | መንፈስ ቅዱስና መዋሸት | ንብረት ክፍፍል | ሐናንያ እና ሰጲራ | የሐናንያ እና የሰጲራ ማታለል |
| | | (4:32-5:11) | | |
| | | 4:32-5:6 | | |
| 5:1-11 | 5:1-11 | | 5:1-6 | 5:1-6 |
| | | 5:7-11 | 5:7-8 | 5:7-11 |
| ብዙ ምልክቶችና ድንቆች ተደረጉ | በቤተክርስትያን የእግዚአብሔር ኃይል መጨመር | የሐዋርያት ለሁለተኛ ጊዜ መያዝ | ተአምራት እና ድንቆች | አጠቃላይ ሁኔታው |
| 5:17-26 | 5:12-21 | 5:12-21a | 5:12-16 | 5:12-16 |
| የሐዋርያት መሰደድ | የታሰሩት ሐዋርያት መፈታት | | ሐዋርያት ተሰደዱ | የሐዋርያት መያዝና መፈታት |
| 5:17-26 | 5:17-21 | | 5:17-21a | 5:17-18 |
| | | | | 5:19-21a |
| | | | | በሸንጎ ፊት እንዲቀርቡ የተሰጠ መጠሪያ |
| | ሐዋርያት እንደገና | 5:21b-26 | 5:21b-26 | 5:21b-26 |
| | 5:22-32 | | | |
| 5:27-32 | | 5:27-32 | 5:27-32 | 5:27-33 |
| | የገማልያል ምክር | ገማልያል | | |
| | 5:33-42 | 5:33-39a | 5:33-39a | የገማልያል ጣልቃ መግባት |
| | | 5:39b-42 | 5:39b-42 | 5:34-39a |
| | | | | 5:39b-41 |
| | | | | 5:42 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ከ “መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ” ገጽ vii)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ሐተታ ነው፡፡ በመሆኑም መፅሐፍ ቅዱስን በሚመለከት ላሞች ሰጠሙ የራስህ አተረጓጐም ኃላፊነት አለብህ፤ እያንዳንዳችን መሄድ ያለብን ባለን ብርሐን መሠረት መሆን አለብን፤ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጐም ውስጥ ቅድሚያ የሚሰጣችሁ ናችሁ፤ ይህንን ጉዳይ ሐተታውን ወይም ማብራሪያውን ለሚያቀርበው ብቻ መተው የለብህም፡፡

በአንድ ጊዜ ተቀምጠህ ምዕራፊን አንብበው የአንተን የርዕስ አከፋፈል በአሁኑ ጊዜ ከምንጠቀመው አምስቱ ትርጓሜዎች ጋር አንፃፅር፡፡ አንድን ምዕራፍ በአንቀፅ መከፋፈል በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የተደረገ አይደለም፣ ነገር ግን የመጀመሪያውን ፀሐፊ ዋና ሐሳብ መከተል ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ እያንዳንዱ አንቀፃ ሁል ጊዜ አንድ ዋና ሐሳብ የያዘ ነው፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀፅ

2. ሁለተኛው አንቀፅ

3. ሶስተኛው አንቀፅ

4. ወ.ዘ.ተ

**የቃልና የሐረግ ጥናት**

**NASB (የተሻሻለው) መፅሐፍ ቅዱስ ምዕ 5:1-6**
**ሐናንያም የተባለ አንድ ሰው ስጺራ ከተባለች ከሚስቱ ጋር መሬት ሸጠ ፤ ሚስቱም ደግሞ ስታውቅ ከሽያጩ አስቀረና እኩሌታውን አምጥቶ በሐዋርያት እግር አጠገብ አኖረው፡፡ ጴጥሮስም፡- ሐናንያ ወይ፣ መንፈስ ቅዱስን ታታልልና ከመሬቱ ሽያጭ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለምን ሞላ ሳትሸጠው የአንተ አልነበረምን ይህን ነገር ስለምን በልብህ አሰብህ እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አልዋሸህም አለው፡፡ ሐናንያም ይህን ቃል ሰምተ ወደቀ፣ ሞተም በሰሙትም ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሃት ሆነ፡፡ ጐበዞችም ተነስተው ከፌኑት፣ አውጥተውም ቀበሩት፡፡**

5:1 “ሐናንያ” ሙሉው የእብራይስይ ስም ሐናንያ ይሆን ነበር ፤ ይህም ማለት “ያሕዊ በቸርነቱ ሰጠ” ወይም “ያሕዊ ቸር ነው”

▣ “ሰጺራ” ይህቺ የአናንያ ሚስት ነበረች፡፡ በአራማይክ የስሙ ትርጓሜ “ቆንጆ” ማለት ነው፡፡ ሁለቱም አማኞች ነበሩ፡፡

5:2 “አስቀረና” ይህ አነደ አይነት ቃል በሰበትዋኘርደንት (LXX) ኢያሱ 7:1 ላይ የአካንን ኃጢአት ለመግለፅ በጥቅም ላይ ውሏል፡፡
ኤፍ.ኤፍ ብሩስ አናንያ ለቀድሞዋ ቤተክርስትያን ሲሆን አካን ደግሞ ለ በማለት ማብራሪያ ሰጥቶበታል፡፡ ይህ ኃጢአት መላውን ቤተክርስትያን የመጉዳት አቅም ነበረው፡፡ ይህ ቃል በቲቶ 2:10 ላይ ከጌቶታቸው የሚሰርቁ ባራያዎችን ለመግለፅ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

▣ **“እኩሌታውን አምጥቶ በሐዋርያት እግር አጠገብ አኖረው”** ፤ ይህ በርናባስ በሐዋ 4:37 ያደረገውን ይመስላል፡፡ እነዚህ ጥንዶች አስቀድሞም ቢሆን የራሳቸውን ንብረት የመሸጥም ሆነ ያለመሸጥ መብት)ነፃነት ነበራቸው፡፡ (ቁ. 4) የተወሰነውን ወይም ሙሉውን ንብረታቸውን ለጌታ ሥራ መስጠት ይችሉ ነበር፡፡ (ቁ. 4ሐ፣ ሉቃ 21:14) እግዚአብሔር ልብን ያያል ( 1ሳሙኤል 16:7፣ 1ኛ ነገ 8:39፣ 1ዜና 28:9፣ ምሳ 21:2፣ ኤር 17:10፣ ሉቃ 16:15፣ ሐዋ 1:24 ሮማ 8:27)፡፡

5:3 “ሰይጣን … **መንፈስ ቅዱስ**” ይህ በዓለማተንና ሕይወት ውስጥ አሁንም በስራ ላይ ያሉ ሁለን መንፈሳዊ ኃይላትን መኖር የሚያመለክት ነው፡፡ በኤፌ 2:2-3 ላይ (1) የወደቀው የአለም ስርዓት (2) የእኛ ጠላታችን እና (3) የቀደመው ማንነታችን፡፡

**ልዩ ርዕስ: ክፋት**
በተለያዩ ምክንያቶች ይህ ርዕስ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡
1.ብሉይ ኪዳን ለደግነት ታላቅ ጠላት ብሎ አያስቀምጥም ነገር ግን የያህዊ አገልጋይና ለሰው ልጆች አማራጭ በመስጠት በፅድቅ ባለመሆኑ የሚከስ መሆኑን ነው፡፡

2. የክፋት ዋና ሃሳብ እየተስፋፋ የመጣው ኪዳን ባስነበረበት ዘመን ሥን ፅሁፍ ነበር፤ ይህም ሊስፋፋ የቻለው በፊሪሳዊያን ኃይማኖት (ዘራሽ ትራኒያንዝም) አማካኝነት ነበር። ይህም በተራው የረቢዎችን ኃይማኖት በከፍተኛ ሁኔታ ተፅዕኖ አሳድሮበታል።
3. አዲስ ዲን የብሉይ ኪዳን ዋና ሐሳባችን የሚያስፋፋው በሙሉ በሙሉ ባይሆንም የተወሰኑትን መርጦ ነው።

አንድ ሰው ከመፅሐፈ ቅዱስ አንፃር ክፋትን ለማጥናት ቢፈልግ፣ ስለክፋት የተለያዩ አመለካከቶኛ ወይም እሳቤዎተን ያገኛል።

ይሁን እንጂ አንድ ሰው ከመፅሐፍ ቅዱስ ውጪ ወይም ተጨማሪ ከሚመለከቱት ከዓለም ወይም ከምስራቅ ኃይማኖቶች አንፃር ክፋትን የሚመረምር ከሆነ አብዛኛው የአዲስ ዲን ትምህርት በፋሪሳዊያን እና በግሪኩ ሮማን የመናፍስት አምልኮ ይሸፈናል ማለት ነው።

አንድ ሰው በቅድሚያ ለመፅሐፍ ቅዱስ መለኮታዊ ስልጣን የሚገዛ ከሆነ የአዲስ ኪዳን መስፋፋት ሊታይ የሚገባው እንደ ቀጣይ መገለጥ ነው። ክርስትያኖች መፅሐፍ ቅዱሳዊውን ሐሳብ ለመለፅ ከአይሁድ ተረትና ምሳሌ መጠበቅ አለባቸው (ዳንቲ፣ ሚስተን)። በዚህ መረዳት ላይ ግራ መጋባትና ሚስጢራዊነት እንዳለ የማታመን ነው። እግዚአብሔር የመረጠው ሁሉንም የክፋት አቅጣጫዎች ለመግለጥ ብቻ አይደለም ነገር ግን የክፋትንም መሸነፍ ጥምር እንጂ፦

በብሉይ ኪዳን አጠራር ሰይጣን ወይም ከሳሽ ከሶስት የተለያዩ ቡድኖች ጋር ይዛመዳል

1. የሰው ከሳሾች (1ሳሙ 29፡4፣ 2ሳሙ 19፡22፣ 1ነገ 11፡14-23-25፣ መዝ 109፡6)
2. የመላዕክት ከሳሾች (ዘሑል 22፡23፣ ዘካ 3፡1)
3. የክፉ መናፍስት ከሳሾች (ዜና 21፡1 22፡21 ዘካ 13፡2)

በዘፍ 3 ላይ የተጠቀሰው እባብ ሰይጣን መሆኑ የታወቀው በኃይለኛው የዝምታ ግዜ ነበር (የጥበብ መፅሐፍ 2፡23-24፣ 2ሔኖክ 31፡3) ከኂላም ቢሆን ይህ ሁኔታ በረቢዎች እንደአማራጭም አልታየም ነበር። የእግዚአብሔር ልጆች (ዘፍ 6) በሔኖክ 54፡6 ላይ መላህክት ተብለው ተጠቅሰዋል። ይህን የምገልፅው ሥን መለኮታዊ ትክክለኛነቱን ለመንገር ሳይሆን ዕድገቱን ለማሳየት ነው።

በአዲስ ኪዳን እነዚህ የብሉይ ኪዳን እንቅስቃሴዎች ስብዕና ካለው መልዕክት ጋር ይዛመዳል (ሰይጣን) ፦ 2ቆሮ 11፡3፣ ራዕይ 12፡9

ስብዕና ያለውን ክፋት በብሉይ ኪዳን ለመወሰን አስቸጋሪ ወይም የማይቻል ጉዳይ ነው (በአንተ እይታ በመመርኮዝ) ለዚህም አንድ ምክንያት የእስራኤል የአንድ አምላክ አምልኮ ነው። (1ነገ 22፡20-22፣ መክ 7፡14 ኢሳ 45፡7 አሞ 3፡6) ሁሉም መልካም ያልሆነ ነገር ከያህዌህ ጋር የተገናኘ ነበር፤ ልዩ እና ቀዳሚ መሆኑን ለማመልከት (ኡሳ 43፡11፣ 44፡6፣ 8፡24፣ 45፡56፣ 14፡18፣21፡22) የመረጃ ምንጨች እንደሚያመለክቱት (1) ኢዮብ 1-2 ሰይጣን ከእግዚአብሔር ልጆች አንዱ እንደሆነ (2) ኢሳ 24፣ ሕዝ 28 ትዕቢት የተሞሉትን የቅርብ ምስራቅ ነገስታት (ባቢሎን ጢሮስን) የሰይጣንን ትዕቢት ለማሳየት መጠቀሙ (1ጢሞ 3፡6)። ሕዝቅኤል የኤደን ገነትን የጢሮስን ንጉስ በሰይጣን ተምሳሌትነት ብቻ አልተጠቀመም (ሕዝ 28፡12-16) ነገር ግን የግብፅንም ንጉስ መልካሙንና ክፋውን እንደምታስታውቀው የእውቀት ዛፍ መስሏታል (ሕዝ 31) ይሁን እንጂ ኢሳ 14 በተለይም ቁ. 12-24 በተዕቢት ምክንያት የተነሳ የመላህክት አመፅን ለመግለፅ ይመስላል። እግዚአብሔር እያንዳንዱን የሳይጣን ባህሪ መግለፅ ቢፈልግ ኖሮ ይህ እንግዲህ በስራ ላይ ለማዋል በጣም ገዳዳ የሆነ አመለካከት ነው።

አልፍሬድ ኢድርሻይም (The Life and Times of Jesus the Messiah, Vo. 2፤ ማውጫ 13 (ገፅ 748-763) እና ማውጫ 16 (ገፅ 770-776) እንደሚናገሩት የረቢዎች የአይሁድ ኃይማኖት በፋሪሳውያን የጣምራ ፍልስፍና እና አጋንታዊ ግምቶች በብዙ ተፅዕኖ እንደደረሰበት ነው። ረቢዎች በዚህ ጉዳይ ላይ ጥሩ የመረጃ ምንጮች ሊሆኑ አይችሉም። ኢየሱስ በምኩራብ ከሚሰጠው ትምህርት ለየት ይላል።

ሁለቱ የኢራናዊያን አማልዕክት (ዱዋሊዝም) Aukiman እና Ormaza መልካም እና ክፉ በተጨማሪም የረቢዎች ሐሳብ ተደምሮ ያቀዊና ሰይጣን የሚሉትን አመጣ የክፋትን ዕድገት በሚመለከት በአዲስ ኪዳን ቀጣይነት ያለው መገለጥ አለ ነገር ግን ረቢዎች እንደሚያብራሩት አይደለም። ጥሩ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው "በሰማያት ላይ ያለው ጦርነት" የሚለው ነው የሰይጣን ውድቀት አስፈላጊ ነው ነገር ግን ዝርዝሮች አልተሰጡም። የተጠቀሰው እንኳን በታዩ ራዕየች ምክንያት የተሸፈነ ይመስላል። (ራዕ 12፡4፡7፣ 12-13) ምነም እንኳን ሰይጣን የተሸነፈና የተጣለ ቢሆንም አሁንም የእግዚአብሔር ባሪያ ሆኖ ይሰራል (ማቴ 4፡1፣ ሉቃ 22፡31-32፣ 1ቆሮ 5፡5 1ጢሞ 1፡20)።

በዚህ አቅጣጫ ላይ ያለንን መደነቅ ልንገታው ይገባል። በግላችን የሚገጥመን ክፋትና ፈተና አለ ነገር ግን ያለን አንድ አምላክ በቻ ስለሆነ የሰው ልጅ ለሚወስደው ማናቸውም ምርጫ ኃላፊነት አለበት። ከደህንነት በፊትም ሆነ በኂላ መንፈሳዊ ውግያ አለ። ድል ሊመጣና ሊጠበቅ የሚችለው በእግዚአብሔር ብቻ ነው። ክፋት ተሸንፏል ደግሞም ወደፊትም ይወገዳሉ።

▣ "ሞላ" ይህ መንፈስ ቅዱስን ለመግለፅ በስራ ላይ የሞላ ተመሳሳይ ቃል ነው። (ኤፌ 5፡18)። መሞላት መተግበርን ይጠይቃል፤ በአንድ ነገር እንሞላለን ሰይጣን ሊሳተፍ ይችላል ነገር ግን እኛ ኃላፊነት አለብን (ሉቃ 22፡3-6) Three Crucial Questions Abut Spiritual Warfare ተብሎ በክሊንተን ኢ.አርኖልድ የተፃፈውን መፅሐፍ እንዲያነቡ

እጠቁማለሁ፡፡ ይህም ደግሞ በአማኞች ሕይወት ውስጥ የሰይጣን ተፅዕኖ መኖሩን የሚያመለክት ማስረጃ ነው (1ዩሐ 5፡18-19) ሙሉውን ማስተወሻ በ2፡4 እና በ3፡10 ላይ ይመልከቱ፡፡

▣ **"መንፈስ ቅዱስን ታታልልና"** የዋሹት ጴጥሮስንና ቤተክርስቲያንን ነበር ፤ ነገር ግን በዋናነት የዋሹት መንፈስ ቅዱስን ነበር ከነገረ መለኮት አንፃር ይህ ኢየሱስ ጳውሎስን በደማስቆ መንገድ ላይ "ስለምን ታሳድደኛለህ?" ብሎ ከጠየቀው ጋር ተመሳሳይ ነው (ሐዋ 9፡4)፡፡ ጳውሎስ ያሳደደው አማኞችን ነበር ነገር ግን ኢየሱስ የተመለከተው በግል ነበር ልክ በዚህ ስፍራ መንፈስ ቅዱስ እንዳደረገው ማለት፡- ይህ በአሁኑ ጊዜ ላሉት አማኞች የማስጠንቀቂያ ቃል ሊሆን ይገባል፡፡

5፡4 **"እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አልዋሸህም"** ከሸጡት ገንዘብ የተወሰነውን ክፍል ማስቀረታቸው አልነበረ ነገር ግን ራሳቸውን መንፈሳዊ ለማድረግ መዋሸታቸው እንጂ ከፋፍ መሻት በመነሳት የሚደረግ መልካምና ቸርነት የተሞላበት ድርጊት ኃጢያት መሆኑን ማስተዋል ይገባል፡፡ በቁ . 3 ላይ የተጠቀሰው መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር መሆኑን አስተውል፡፡

5፡5 **"ወደቀ ሞተም"** በቀድሞ ዘመን አንድ ሰው ሲሞት መንፈሱ ለቆት ለመሔዱ ማስረጃ ነበር (መሳ 4፡2፣ ሕዝ 21፡7 በሰብትዋጅነት ውስጥ)፡፡ ይህ ብዙ ጊዜ የማይገኝ ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኘው በሐዋርያት ስራ ውስጥ ነው ( 5፡4፡10፣ 12፡23) ይህ ለጊዜው የሚሰጥ ፍርድ ምሳሌ ነው፡፡ ይህ በዘሌዋውያን 10 ላይ እግዚአብሔር በአሮን ልጆች ላይ ካሳለፈው ፍርድ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ እግዚአብሔር ኃጢአትን እንዲሁ በችልታ አይመለከተውም፡፡ ሕይወትን የሚጠይቅ ነው (2 ነገ 14፡6፣ ሕዝ 18፡4-20)፡፡

▣ **"በሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሐት ሆነ"** ይህ በጊዜያዊነት የተሰጠው ፍርድ ዋና ዓላማ ይመስላል፡፡ ይህ በብሉይ ኪዳን በዘሌዋዊያን 10 ላይ ለሞቱት ናዳብና አብዮዳ እንዲሁም በ2ኛ ሳሙኤል 6 ላይ ለሞተው ሎዛ ተምሳሌት ነው፡፡ 1ኛ ቆሮ 11፡30፣ ያዕቆብ 5፡20 እና 1ዮሐንስ 5፡16-27 ን መሠረት በማድረግ አማኞች የሚፈፅሟቸው አንዳንድ ኃጢአቶች ያለጊዜያቸው ለመሞታቸው ምክንያት ሊሆኑ እንደሚችሉ መገመት ይቻላል፡፡ በእግዚአብሔር ቅድስና እና በእግዚአብሔር አባትነት መካከል ያለውን ሚዛን ለመጠበቅ የሚያስቸግር ነው፡፡

5፡6 **"አውጥተውም ቀበሩት"** ምናልባት በዘፍ 3፡19 ምክንያት በ1ኛው ክ)ዘ የነበሩ አይሁዶች አስከሬን የማድረቅ ዘዴን አይጠቀሙም ነበር (እስከአሁንም አይጠቀሙም) መዝ 103፡14፣ 104፡29፡፡ አንድ ሰው እንደሞተ በዚያኑ ቀን በፍጥነት መቀበት አለበት፡፡ ተቃውሞም ስለነበረ ምንም አይነት የመታሰቢያ አገልግሎት ወይም ሌላ ክርስትያናዊ የቀብር ልማድ አልነበረም፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ የቀብር ልማዶች**

I. ሜስፐተሚያ
   ሀ. ከሕይወት በኋላ ላለው ሕይወት ትክክለኛ አቀባበር በጣም አስፈላጊ ነው፡፡
   ለ. የተለመደው የማስፓተሚያ እርግማን ለምሳሌ "መሬት አስከሬንህን አትቀበለው" የሚል ነው፡፡

II. ብሉይ ኪዳን
   ሀ. ትክክለኛ ቀብር በጣም አስፈላጊ ነበር (መክ 6፡3)
   ለ. በፍጥነት ይካሄድ ነበር (ሳራ በዘፍ 23 ላይ፣ ራሔል በዘፍ 35፡19 ላይ እና ዘዳ 21፡23)
   ሐ. ትክክለኛ ያልሆነ ቀብር ተቀባይነት የማጣት እና የኃጢአት ምልክት ነበር
      1. ዘዳግም 28፡26
      2. ኢሳያስ 14፡2
      3. ኤርምያስ 8፡2፣ 22፡19
   መ. የሚቻል ከሆነ ቀብር የሚካሔደው በቤተሰብ ዋሻ ውስጥ ይካሔዳል
   ሠ. በግብፅ እንደሚደረገው አስከሬን ማሸት)መቀባት አልነበረም የሰው ልጅ)ዘር) ከአፈር ነው የመጣው ወደ አፈርም መመለስ አለበት (ዘፍ 3፡19፣ መዝ 103፡14፣ 104፡12)
   ረ. በረቢዎች እምነት የሞተ አካልን በሚመለከት ከእርኩሰት ጋር በተያያዘ ምክንያት ተገቢውን ክብር ለመስጠትና ለመንከባከብ አስቸጋሪ ነው፡፡

III. አዲስ ኪዳን
   ሀ. አንድ ሰው እንደሞተ ወዲያውኑ ይቀበራል፣ ብዙ ጊዜ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ አይሁዶች አንድ ሰው ከሞተ በኋላ እስከ ሶስት ቀን ድረስ የሚችል ነፍስ ተመልሳ ትመጣለች በሚል እምነት መቃብሩን ሁል ጊዜ ይመለከቱታል፡፡ (ዮሐ 11፡39)
   ለ. ቀብር አስከሬኑን ማጠብ እና በሽቶ መከፈንን ያካትታል ዮሐ 11፡44፣ 19፡39-40)
   ሐ. በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የፍልስጥኤም ምድር የአይሁድ ወይም የክርስትናን ለየት ያሉ የቀብር ሒደቶች ወይም በመቃብር ውስጥ የሚቀመጡ ነገሮች አልነበሩም፡፡

**NASB (የተሻሻለው) መፅሐፍ ቅዱስ ምዕ 5:7-11**

**[7]ከሶስት ሰዓት ያህል በኋላም ሚስቱ የሆነውን ሳታውቅ ገባች። ጴጥሮስም መልሶ፡- እስቲ ንገሪኝ መሬታችሁን ይህን ለሚያህል ሸጣችሁትን አላት እርስዎም፡- አዎን ይህን ለሚያህል ነው አለች። ጴጥሮስም፡- የጌታን መንፈስ ትፈታተኑ ዘንድ ስለምን ተሰማማችሁ? እነሆ ባልሽን የቀበሩት ሰዎች እግር በደጅ ነው አንቺንም ያወጡሻል አላት ያን ጊዜም በእግሩ አጠገብ ወደቀች ሞተችም ጐበዞችም ሲገቡ ሞታ አገኙአት አውጥተውም በባልዎ አጠገብ ቀበሩዋት። በቤተክርስትያንም ሁሉ ይህንንም በሰሙ ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሃት ሆነ።**

5:7 **"ከሶስት ሰዓት ያህል በኋላም"** ይህ የሚያሳየው የተፈፀመው ክስተት በዓይን ምስክሮች ፊት መሆኑን ነው። የሉቃስ አፃፃፍ የሚታወቀው ለዝርዝር ጉዳዮች ትኩረት በመስጠት ነው። ይህም የሚያንፀባርቀው የአፃፃፍ ዘይቤውንና የምርምር መንገዶቹን ነው።

5:8 ውሸቱና ማስመሰል እንዲቀጥል ነው

5:9 **"ትፈታተኑት ዘንድ"** መፈታተንን ለማመልከት ሁለት የግሪክ ቃላት አሉ። የሔኛው የሚያመለክተው "ለማጥፋት መፈታተን" ነው። ይህም ምናልባት የሚያመለክተውዘፀ 17:2ን እና ዘፀ 6:16ን ነው። እነዚህ ጥቅሶች መፈተን)መፈታተን በሚመለከት የተሰጡ ማስጠንቀቂያዎች ፍቺው (መዝ 78:18፣ 41፣ 56)

**ልዩ ርዕስ፡ የግሪክ ቃላት ስለ መፈታተን ያላቸው ትርጓሜ**

የግሪክ ቃላት ስለ መፈታተን ያላቸው ትርጓሜና ማሳሰቢያዎቻቸው አንድን ሰው ለአንድ ዓላማ ስለመፈተን የሚያሳይ ሐሳብ ያላቸው ሁለት የግሪክ ቃላት አሉ።

ሀ. ዶኪሚዮን

ይህ ቃል አንድ ብረት የሚሰራ ሰው የአንድን ነገር እውነተኝነት ለማረጋገጥ የሚጠቀምበት ቃል ነው (ማለትም አንድ የብረት ሠራተኛ ፤ ይህም በእሳት የፈተን ነው። እሳቱም እውነተኛውን ብረት ያሳያል ከዚያም ይጠፋል። ይህም አካላዊ)ውጫዊ ሂደት ለእግዚአብሔር እና)ወይም ለሰዎች እና ወይም ለሰይጣን ሌሎችን ስለመፈተን ኃይለኛ ፈሊጣዊ አገላለፅ ሆነ። ይህ ቃል ስለመፈተን አዎንታዊ አካሄድን ያዘለ ነው።

ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን ስለመፈተን ሥራ ላይ ውሏል።

1. በሬዎች ሉቃ 14:19
2. ራሳችንን 1ቆሮ 11:28
3. እምነታችን ያቆ 1:3
4. እግዚአብሔርንም ዕብ 3:9

የእነዚህ ሁሉ ፈተናዎች እምነታዊ ይዘት እንዳላቸው ይታወቃል (ሮሜ 1:28፣ 14:22፣ 16:10፣ 2ቆሮ 10:18፣13-3፣ ፊሊ 2:27፣ 1ጴጥ 1:7)። ስለዚህም ቃሉ የሚያሳየው ሃሳብ አንድ ሰው ተፈትኖና ተረጋግጦ፤

1. የሚረባ
2. መልካም
3. ግልፅ
4. ዋጋ ያለው
5. የከበረ

ለ. ቃሉ ስህተትን ለማግኘት ወይም ተቀባይነት እንዳይኖር ዓላማ የሚደረግን ምርመራ የሚያመለክት ነው። ኢየሱስ በምድረበዳ ከመፈተኑ ጋር በተያያዘ በስራ ላይ ውሏል።

1. ኢየሱስን ለማጥመድ የተደረገውን መከራ ያሳያል (ማቴ 4:1፣16:1፣19:3፣ 22:18፣ 35፣ ማር 1:13፣ ሉቃ 4:38፣ ዕብ 2:18)
2. ይህ ቃል ለሰይጣን እንደመጠሪያ)ማድረግ ተጠቅሷል። በማቴ 4:3፣ 1ተሰ 3:5
3. ኢየሱስ እግዚአብሔርን እንዳንፈታተን ለመግለፅ ተጠቅሞታል (ማቴ 14:7፣ ሉቃ 4:12)። አንድን ነገር ለማድረግ ተሞክሮ ነገር ግን ስላልተነካ ሁኔታ ለማመልከት (ሐዋ 9:20፣ 20:21፣ ዕብ 11:29፣ ከአማኞች መፈተንና መከራ ጋር በተያያዘ ጥቅም ላይ ውሏል (1ቆሮ 7:5፣10:9፣13 ፤ ገላ 6:1 ፤ 1ተሰ 3:5:ዕብ 2:18፣ ያቆ 1:2፣13:14፣ 1ጴጥ 4:12፣ 2ጴጥ 2:9)።
4. ከአማኞች መፈተንና መከራ ጋር በተያያዘ ጥቅም ላይ ውሏል (1ቆሮ 7:5፣10:9፣13 ፤ ገላ 6:1 ፤ 1ተሰ 3:5:ዕብ 2:18፣ ያቆ 1:2፣13:14፣ 1ጴጥ 4:12፣ 2ጴጥ 2:9)።

5:10 **"ጐበዞች"** የሚለውን ለመግለፅ የተጠቀመው ቃል በቁ. 6 ላይ ያለው በቁ. 10 ላይ ካለው የተለየ ነው። የስልጣን ልዩነት እንዳለ ለማመልከት እንደሆነ ወይም የተለያዩ የጐበዞች ቡድኖች በቤተክርስቲያን እንዳሉ ለማሳየት እንደሆነም አይታወቅም። ሁለቱም የግሪክ ቃላት የመጡት ከአንድ ቃል ነው።

5፡11 “*ይህንም በሰሙ ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሃት ሆነ*” ሉቃስ የተለመደውን ቃል በአጠቃላይ ስሜት ደጋግሞ ይጠቀመዋል (ሉቃ 1፡69፣ 3፡37፣ ሐዋ 19፡17)። ለአማኞች አክብሮታዊ ፍርሃትን ማክበርን፣ አክብሮችን የሚያመለክት ስሜትን ሲሰጥ ለማያምኑት ግን የመከልከልን ፍርሃትን እና የሽብርን ስሜት ያሳያል (ሉቃ 12፡4-5፣ ዕብ 10፡31)።

▣ “*ቤተክርስትያን*”*ይህ ቃል በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ቢጠቀስም* Textus Receptus *ምዕ* 2፡47። በሚቀጥለው ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።

**ልዩ ርዕስ፡ ቤተክርስትያን**

ላይ ይህ የግሪኩ ቃል ኤክሌስያ ይባላል ቃሉ የሁለት ቃላት ጥምረት ነው፤ የመጡ እና የተጠሩ ከሚባሉት ስለዚህ ቃሉ የሚያመለክተው በመለኮት ተጠርተው የወጡትን የሚያሳይ ነው። የቀደመችው ቤተክርስትያን ይህን ቃል የወሰደችው ከዓለማዊው አጠቃቀም ነው (ሐዋ 19፡32፣ 39፣41) እንዲሁም ደግሞ የሰብትዋጅንት ትርጉም ይህን ቃል የእስራኤልን “ማህበር” ለማመልከት በመጠቀሙም ጭምር ነው (ዘኑልቁ 16፡3፣20፡4)። የብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝቦች ቀጣይነታቸውን ለማመልከት ለራሳቸው ተጠቀሙት እነርሱም አዲሷ እስራኤል ነበሩ (ሮሜ 2፡28-29፣ ገላ 6፡16፣ 1ጴጥ 2፡5፡9፣ ራዕ 1፡6) የእግዚአብሔርን አለም አቀፋዊ ተልዕኮ መሪውም ለማመልከት (ዘፍ 3፡15፣ 12፡3 ዘፀ 19፡5-6፤ ማቴ 28፡18-20፤ ሉቃ 24፣47፤ ሐዋ 1፡8)።

ይህ ቃል በወንጌላትና በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የተለያዩ ትርጓሜዎችን ይዟል።

ሀ. በከተማ ውስጥ ያለን መገናኘት ሐዋ 19፡32፤ 39፡41

ለ. በክርስቶስ ያለን አጠቃላይ የእግዚአብሔር ሕዝብ ማቴ 16፡18 እና ኤፌሶን

ሐ. በአንዲት አጥቢያ በክርስቶስ የሚገኙ አማኞችን ማቴ 18፡17፤ ሐዋ 5፡11 (በእነዚህ ጥቅሶች በኢየሩሳሌም ያለችውን ቤተክርስትያን ያመለክታል።

መ. የእስራኤል ሕዝብ በጥቅሉ ሐዋ 7፡38፤ በእስጢፋኖስ ስብከት

ሠ. በአንድ አካባቢ ያለን የእግዚአብሔር ሕዝብ ሐዋ 8፡3 (በይሁዳ ወይም በፍልስጤም ምድር)

NASB (የተሻሻለው) *መፅሐፍ ቅዱስ ምዕ* 5፡12-16

**በሐዋርያትም እጅ ብዙ ምልክትና ድንቅ በሕዝብ መካከል ይደረግ ነበር። ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው በሰለሞን መመላለሻ ደጅ ነበሩ። ከሌሎችም አንድ ስንኳ ሊተባበራቸው የሚደፍር አልነበረም ሕዝቡ ግን ያከብሩአቸው ነበር፤ የሚያምኑትም ከፊት ይልቅ ለጌታ ይጨመሩለት ነበር፤ ወንዶችና ሴቶችም ብዙ ነበሩ። ስለዚህም ጴጥሮስ ሲያልፍ ጥላውም ቢሆን ከእነርሱ አንድን ይወርድ ዘንድ ድውያንን ወደ አደባባይ አውጥተው በአልጋና በወሰካ ያኖሩአቸው ነበር። ደግሞም በኢየሩሳሌም ዙሪያ ካላቸው ከተማ ድውያንና በርኩሳን መናፍስት የተሰቃዩትን እያመጡ ብዙ ሰዎች ይሰበሰቡ ነበር። ሁሉም ይፈወሱ ነበር።**

5፡12-16 *ይህ የሐዋርያት ስራ መፅሐፍ መለያ የሆነ አጭሩ ማጠቃለያ ነው።* (*ሐዋ* 2፡43-47፣ *እና* 4፡32-35)

5፡12 “*ብዙ ምልክትና ድንቅ*” እነዚህ ሁለት ቃላት ጴጥሮስ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ከኢዮኤል መፅሐፍ ጠቅሶ በፃፈው ውስጥ ይታያሉ (ኢዮ 2 በሐዋ 2፡19)። ተአምራት በተደጋጋሚ ሲፈፀሙ ነበር (2፡43፣ 4፡30፣ 5፡12፣ 6፡8፣ 7፡36፣ 14፡3፣ 15፡20)። ተአምር የመለኮት ምልክት ላይሆን ይችላል (ማቴ 24፡24 እና 2ተሰ 2፡9) ነገር ግን ክርስትያናዊ መልዕክትን ለማረጋገጥ መንገድ ነበር።

▣ “*ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው*” በምዕ 1፡14 ላይ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ

▣ “*በሰለሞን መመላለሻ ደጅ*” ይህ በቤተመቅደሱ በስተምስራቅ አቅጣጫ ለአሕዛብ የተዘጋጀው አደባባይ ያለ ክፍት መመላለሻ ነበር። ኢየሱስም እንዲሁ በዚህ ስፍራ አገልግሏል (አስተምbል) ( ዮሐ 10፡23)። ይህ ዮሐንስና ጴጥሮስ ለመጀመሪያ ጊዜ ለመታሰር የተያዙበት ስፍራ ነበር።

5፡13

| | |
|---|---|
| NASB | ከሌሎችም አንድ ስንኳ ሊተባበራቸው የሚደፍር አልነበረም።” |
| NKJV ፡ NRSV | “ከሌሎችም አንድ እንኳ ቢገናኛቸው የሚደፍር አልነበረም።” |
| TEV | “ማንም ከቡድኑ ውጪ ሊገናኛቸው የሚደፍር አልነበረም” |
| NJB | “ማንም ሊገናኛቸው የሚደፍር አልነበረም።” |

ይህ ያልተለመደ ሐረግ ነው። የ”ፍርሃትን” አሉታዊ ጐኑን ለመግለፅ የሚፈልግ ይመስላል። በዚህ ዓውድ ውስጥ የተለያዩ ድድኖች ተሰይመዋል (ቁ. 12-16)። ለብዙዎች ክስተቶቹ በክርስቶስ ወደሚገኘው እምነት መሳቢያ ነበሩ ወይም በክርስቶስ ላለው እምነት ማረጋገጫ ነበሩ (#5 እና #6 እና #7) ወይም በክርስቶስ ላለው እምነት ማረጋገጫ ነበሩ (#3)።

1. ሐዋርያት ቁ. 12

2. ሕዝቡ ቁ. 12፣ 13
3. አማኞች (በአንድ ልብ ሆነው በሰለሞን ልጅ መመላለሻ) ቁ. 12
4. ሌሎች (የአይሁድ መሪዎች) ቁ. 13
5. አዲስ አማኞችነት ቁ. 14
6. በኢየሩሳሌም ያሉ ድውያን ቁ. 15
7. በኢየሩሳሌም ዙሪያ ካሉት መንደሮች የመጡ ድውያንና በርኩሳን መናፍስት የተሰቃዩት ቁ. 16

"የአሁን ድርጊትን አመልካች ግስ መተባበር" በጥሬ ትርጉሙ "መጠበቅ" ማለት ነው፡፡ ሉቃስ ይህንን ቃል ብዙውን ጊዜ ይጠቀማል ነገር ግን በተለያዩ ትርጉሞች ነው፡፡ እዚህ ላይ የሚያመለክተው ከአዲሶቹ ክፍሎች ጋር አለመሆናቸውን ለማሳየት ነው (ኢየሱስ ሲጠበቅ የነበረው መሲህ መሆኑን ያመኑ አማኞች)፡፡

5፡14 **"የሚያምኑትም"** ሲሆን የሚያመለክተውም በሂደት ላይ ያለ ድርጊት መሆኑን ነው፡፡ በምዕ 2፡40 ላይ የተሰጠውን ልዩ ርዕስ ተመልከት፡፡

▣

NASB, TEV
NJB, NIV "በጌታ"
NKJB,NRSV "ለጌታ"

ይህ ሰዋሰዋዊ አፃፃፍ (ስምንተኛው ዘዴ) አንድ አመልካች ተደርጐ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ይህ አማኞች የጌታ መሆናቸውን ለማመልከት የተጠቀመበት ነው፡፡ እኛ የእርሱ ነን እርሱም የእኛ ነው፡፡

▣ **"ይጨመርለት ነበር"** ሉቃስ ስለቤተክርስትያን ዕድገት የማጠቃለያ አረፍተ ነገር ነበር የተጠቀመው (2፡47፣ 5፡14፣ 6፡7፣9፡31፣ 12፡24፣ 16፡5፣ 19፡20)

5፡15 **"ጴጥሮስ ሲያልፍ ጥላውም"** በዚህ ደረጃ ያሉ ተአምራት የወንጌልን እውነተኝነት ለማረጋገጥ የተለመደ ነበሩ፡፡ ጴጥሮስም ለሐዋርያት እንደ ቃል አቀባይ ነበር፡፡ ተመሳሳይ አይነት ማረጋገጫ ፈውስ በጳውሎስ አማካኝነት ተደርጐ ነበር፡፡ (19፡12)

እንደ አስተርጓሚዎች ማስታወስ ያለብን እነዚህ የተአምራት ምልክቶች የተሰጡት

1. የእግዚአብሔርን ምህረት ለማሳየት
2. የወንጌልን እውነት ለማሳየት
3. በእግዚአብሔር የተጠሩ መሪዎች እነማን እንደሆ ለማሳየት

እነዚህ ምልክቶች የተሰጡት በተወሰነ ባሕል ለተለየ ዓላማ ነበር፡፡ እግዚአብሔር በዚያ ስፍራ ስላደረገ በማንኛውም ጊዜ በማንኛውም ባሕል ውስጥ ያንን ይፈፅማል ማለት አይደለም፡፡ በማናቸውም ዘመን ወይም የማይሰራ ወይም ምሕረት የማያደርግ ስለሆነ ሳይሆን የእግዚአብሔር ሕዝብ ግን በማየት ሳይሆን በእምነት መራመድ አለባቸው፡፡ ተአምሪት ይቀጥላሉ ፤ ነገር ግን ደህንነት ዋናው ግብ መሆን አለበት፤ ወደፊት ለሚሞቱት አካላዊ ፈውስ መስጠት አይደለም ዋናው ጉዳይ እንደሚመስለኝ እግዚአብሔር አልተለወጠም፡፡

ባሕሪው፣ ኃይሉ፣ ምህረቱ እና መሻቱ ሁሉም እንዲድኑ አልተለወጠም፡፡ ነገር ግን ታሪክን ከስነ-መለኮት አንፃር ስንመለከት ከእግዚአብሔርና ከሰይጣን ኃይልንና ከተፈጥሮ በላይ የሆኑ ምልክቶችን በሚመለከት ሁለት ዋና ጊዜያቶች አሉ፤

1. በተሰጦዎ ጊዜ አከባቢና በቀደመችው ቤተክርስትያን ዕድገት ዙሪያ
2. አማኞች በታላቅ መከራ ወይም ለየት ከሚያስፈበት የመጨረሻ ዘመን ክስተቶች ቀደም ብሎ ኤ.ቲ.ሮበርትስን ከፃፈው Word Pictures in the New Testament Vol. III, ገጽ 62 ከተሰኘው መጽሐፍ መጥቀስ እወዳለሁ፤

"በእርግጥ በጴጥሮስ ጥላ ውስጥ የተለየ ጥቅም ወይም ሐይል አልነበረም፡፡ ልክ በወንጌላት ውስጥ እንደሚታየው ከአጉል እምነት የተነሳ የሚታየ እምነት ነበር (ማቴ 9፡20፣ ማር 6፡56፣ ዮሐ 9፡5) እንዲሁም ደግሞ የጳውሎስን መሐረም መጠቀም (ሐዋ 19፡12) ምንም እንኳን ከእምነት በመነሳት የተገለፀ አጉል እምነት ቢሆንም እግዚአብሔር ግን ያከብረዋል፡፡

ጥቂት ሰዎች ግን ከአጉል እምነት ሙሉ በሙሉ ነፃ ናቸው

5፡16 **"ሁሉም ይፈወሱ ነበር"** ይህ ያላለቀ ድርጊትን የሚያመለክት ሱሆን እያንዳንድ ሰው መፈወሱን የሚያረጋግጥ ነው (ድርጊቱን ያነሳሳው ባይታወቅም ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ሊሆን ይችላል) ይህም እያንዳንዱ አንድ ባንድ በተደጋጋሚ ምንም ሳይቀር ሁሉ እንደተፈወሱ ያመለክታል፡፡

ይህ አጠቃላይ (ማጠቃለያ የሚመስስ አረፍተ ነገር ነው፡፡ በጥሬ ትርጉሙ መወሰድ አለብን (ማለትም እያንዳንዱ ሰው) ኢየሱስ የፈለገው እምነትን ነበር ወይም ፈውስን የተጠቀመው (1) ደቀመዛሙርትን ለማሰልጠን ነበር (2) ሕዝቡ እንዲሰማው ለማድረግ ነበር፡፡

በአዲስ ኪዳን የተፈወሱ ሰዎች ወዲያውኑ "አለመዳናቸው" ለእኔ የሚያስደነግጠኝ ሁኔታ ነው (በክርስቶስ ማመንና የዘላለም ሕይወትን ማግኘት)፡፡ አካላዊ ፈውስ ለመንፈሳዊ ድነት በጣም የተንደለ ምትክ ነው፡፡ ተአምራት ለእኛ የሚረዱን እኛን ወደ እግዚአብሔር የሚያመጡጠን ብቻ ከሆኑ ነው፡፡ ሁሉም የሰው ልጆች በወደቀው ዓለም ውስጥ ይኖራሉ መጥፎ ሁኔታዎችም ይከሰታሉ፡፡ እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ ጣልቃ ለመግባት ባይመርጥም ይህ ግን ስለ እግዚአብሔር ፍቅር እና ለው ልጆች ግድ እንደሚለው ምንም የሚለው ነገር የለም፡፡

በዚህ ክፉ ዘበን እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ተአምራታዊ በሆነ ሁኔታ እንዲገለጥ ከመጠየቅ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። እግዚአብሔር ሉዓላዊ ከመሆኑም ባሻገር የማንኛውንም ሁኔታ የተሟላ ግንዛቤ ላይኖረን ይችላልና። በዚህ ነጥብ ላይ ስለጳውሎስና አካላዊ ፈውስ በ2ኛ ጢሞ 4:20 ላይ ከሰጠሁት ማብራሪያ መጨመር እፈልጋለሁ።

"የአዲስ ኪዳን ፀሐፊዎችን ስንጠይቅ የምንፈልጋቸው ብዙ ጥያቄዎች አሉን። አንድና ዋነኛው አማኞች ሁሉም ሊጠይቁት የሚፈልጉት ጉዳይ ቢኖር ስለ አካላዊ ፈውስ ነው። በሐዋርያት ሥራ (19:12፣ 28:7-9) ጳውሎስለመፈወስ ችሎ ነበር ነገር ግን እዚህ እና በ2ኛ ቆሮ 12:7-10 እና ፊሊጱ 2:25-30 ላይ መፈወስ ያልቻለ ይመስላል። ለምንድነው ሁሉም ሳይሆኑ ጥቂቶች ብቻ የሚፈወሱት፣ ወይስ ከፈውስ ጋር በተገናኘ የጊዜ ጉዳይ ግምት ውስጥ ሊገባ ይችላል ወይ?

አካላዊ ሆነ መንፈሳዊ ፈውስን በሚሰጥና ሊሰጥ በሚችል ሉዓላዊ ምህረትን በተሞላ አምላክ)አባት) አምናለሁ ፤ ነገር ግን ለምንድ ነው ይህ የፈውስ አቅጣጫ ያለ እየመሰለ በእርግጥ ደግሞ የማይኖረው ይህ ሁኔታ ከሰው እምነት ጋር የተያያዘ ነው ብዬ አላስብም፤ ምክንያቱም ጳውሎስ በእርግጠኝነት ለመናገር እምነት ነበረውና (2ቆሮ 12) ወንጌል ለመጀመሪያ ጊዜ በታወጀበት ስፍራ ሁሉ ፈውስና ተአምራት የወጌልን እውነተኝነትና አስፈላጊነት ያረጋገጠ መስሎ ይሰማኛል። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በማየት ሳይሆን በእምነት እንድንመላለስ የሚፈልግ ይመስለኛል። አካላዊ ፈውስ በአማኞች ሕይወት ውስጥ የተፈቀደው (1) ለተሰራ ኃጢአት ጊዜያዊ ቅጣት (2) በወደቀው ዓለም ውስጥ እንዳለ የሕይወት ውጤት (3) አማኞች በመንፈሳዊ ብስለት እንዲኖራቸው ለመረዳት። የእኔ ችግር ግን የትኛው እንዳለ)እንደተካተተ በፍፁም አለማወቄ ነው። በእያንዳንዱ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲሆን መፀለዩ እምነት የማጣት ጉዳይ አይደለም ነገር ግን እግዚአብሔር በእያንዳንዱ ሕይወት ውስጥ ፈቃዱንና እንደ ቸርነቱና ምህረቱ እንዲገለጥ ነው።

▣ "ርኩሳን መናፍስት" ቀጥሎ ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት

**ልዩ ርዕስ: ክፉ መናፍስት**

ሀ. የጥንት ሰዎች አረማዊያን ነበሩ። ስብዕናን ለተፈጥሮ ኃይላት፣ ተፈጥሮአዊ ለሆኑ ነገሮች እንዲሁም ለሰው የስብዕና ባህሪይ በማገናኘት ያምኑ። ሕይወት ለተረጐም የሚችለው የሰው ልጅ ከእነዚህ መንፈሳዊ አካላት በሚኖረው ተፅዕኖ እንዓር ነው።

ለ. ይህ የመምሰል ሒደት በብዙ አማልዕክት ማመንን አመጣ (ብዙ አማልዕክት) ክፉም ሆነ ደግ) በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ተፅዕኖ የሚያመጡ

1. ሜስፓተሚያ
2. ግብፅ
3. ከነዓን

ሐ. ብሉይ ኪዳን ጥብቅ የሆነ በአንድ አምላክ ብቻ የማመን አቁም ስላለው ስለመላዕክት አነሰ ስላሉ አማልዕክት ወይም ስለ እርኩሳን መናፍስት ምንም የሚለው የለም (ዘፀ 8:10፣ 9:14፣ 15:11፣ ዘዳ 4:35፣ 39፣ 6:4፣ 33:26፣ መዝ 35:10፣ 71:19፣ 86:6፣ ኢሳ 46:9 ኤር 10:6-7፣ ሚክ 7:18) ሐሰት ስለሆኑት የአርማዊያን ሕዝቦች አማልዕክት ይገልፃል (Shedim ዘዳ 32:17 መዝ 106:37) አንዳንዶችንም ስማቸውን ይዘረዝራል።

1. Se'im (satyrs ወይም የፀጉር መናፍስት ዘሌ 17:7 2ዜና 11:15)
2. Lilith (female, አሳሳች መናፍስት ኢሳ 34:14

3. Mavet (የዕብራዊያን ቃል ሲሆን Mot የሚባለው የከነዓናዊያን አምላክ ኢሳ 28:18 ኤር 9:21 እና ዘዳ 28:22)
4. Reshep (Plague ዘዳ 33:29፣ መዝ 78:48፣ ዕንባ 3:5)
5. Dever (ቸነፈር ዘዳ 33:29 መዝ
6. Dever (ቸነፈር መዝ 91:5-6፣ ዕንባ 3:5)
7. Az'azel (ስሙ አይታወቅም ነገር ግን የበረሐ መንፈስ ወይም የቦታ ስም ይመስላል)

)እነዚህ ምሳሌዎች የተሰጡት ከ (Encyclopedia Judaica, ቁ. 5፣ ገፅ 1523) ነገር ግን የሁለትዮሽ እምነት ወይም በብሉይ ኪዳን ከያህዌህ ነፃ የሆነ የመላዕክት ዓለም የለም። ሰይጣን የያህዌህ አገልጋይ ነው (ኢዮ 1:3፣ ዘካ 3) እንጂ ጠላት አይደለም (ኤ.ቢ.ዳቪድስን፣ A Theilogy of the Old Testament ፤ ገፅ 300-306)

መ. የአይሁድ እምነት የተስፋፋው በባቢሎን የምርኮ ጊዜ ነበር (586-538 ከክ.ል.በ) ይህም እምነት በፈሪሳዊያን ዘራስትራኒያኒዝም ከፍተኛ ተፅዕኖ ይዳስስበት ነበር። በዚህም እምነት "Mazda` ወይም "Ormazd" የመልካም መገለጫ ሲሆን የክፍ ተምሳሌት "Ahrimam" ይባል ነበር። ይህም ሁኔታ ከምርኮ በኋላ እግዚአብሔርና መላዕክት እንዲሁም ሰይጣን እና እርኩሳን መናፍስቱ የሚል ፅንሰ ሐሳብን አመጣ።

ስብዕና ስላለው ክፋት (ሰይጣን) የአይሁድ ኃይማኖት ሥነ መለኮት በአልፍሬድ ኢደርሼይም መጽሐፍ ውስጥ ተጠቅሷል (The life and Jimes of Jesus the Messcal ቁ. 2)።

የአይሁድ ኃይማኖት የክፋትን ስብዕና የሚገልፀው በሶስት መንገዶች ነው

1. ሰይጣን ወይም ሳሙኤል
2. በሰው ያለ ክፉ ሃሳብ (yether Ham)
3. የሞት መልአክ

ኤደርሼይም እነዚህን የሚለየው (1) እንደ ከሳሽ (2) እንደ ፈታኝ (3) እንደ ቋሚ (vol. 2 (ቁ. 2) ገፅ 756)፡፡ ከምርኮ መልስ የአይሁድ ኃይማኖትና አዲስ ኪዳን መካከል በግልፅ የሚታይ ስነ መለኮታዊ ልዩነት አለ ክፋትን በሚመለከት ባለው አቀራረብና ገለፃ፡፡

ሠ. አዲስ ኪዳን በተለይም ወንጌላት የክፋ መንፈሳዊ ኃይላትን መኖር እና ተቋውሞ ከሰው እና ከእግዚአብሔር አንፃር ይመለከተዋል፡፡ በአይሁድ እምነት ሰይጣን የሰው ጠላት እንጂ የእግዚአብሔር ጠላት ተደርጐ አይታሰብም)፡፡ እነዚህ ክፊ ኃይላት የእግዚአብሔርን ፈቃድ፣ አገዛዝንና መንግስቱን ይቃወማሉ፡፡ ኢየሱስ እንዝህን ክፊ ኃይላት ተጋፍጦ ከሰዎች አስወጥቷል፡፡ እነዚህም ክፊ ኃይላት (በርኩሳን መናፍስት ይባላሉ ሉቃ 4፡36፣ 6፡18) ክፊ መናፍስት ሉቃ 7፡21፣ 8፡2 ከሰዎች አስወጥቷል፡፡ ኢየሱስ በሕመምና (አላዊም ሆነ አዕምሮአዊ) በአጋንንት መካከል ግልፅ የሆነ ልዩነት አድርጓል፡፡ እርኩሳን መናፍስትን በመለየትና በማስወጣት ኃይሉንና መንፈሳዊ መረዳቱን አሳይቷል፡፡ ብዙሉን ጊዜ መናፍስቱ ይለዩታል እንዲላካቸውም ይጠይቁታል፡፡ ኢየሱስ ግን የእነሱን ምስክርነት ባለመቀበል ፀጥ እንዲሉና እንዲወጡ ያዛቸዋል፡፡

በጣም የሚያስደንቅ የመረጃ እጥረት በዚህ ጉዳይ ላይ በአዲስ ኪዳን መልዕክቶች ውስጥ ይታያል፡፡ አማኝነትን ማውጣት እንደመንፈሳዊ ስጦታ አልተጠቀሰም ወይም በሚመጣው ትውልድ ላሉ አገልጋዬች ወይም አማኞች ወይም ሒደት)ዘሌ ተደርጐ አይታይም፡፡

ረ. ክፋት እውነት ነው፣ስብዕና አለው፣ አሁንም አሉ፣ ምንጩም ሆነ ዓላማውም አልተገለፀም መጽሐፍ ቅዱስ ሕልውናውን እየረጋገጠ ተፅዕኖውን ደግሞ በፅኑ ይቃወማል፡፡ ምንም አይነት ዘላቂ የሆነ ሁለትዮሽ የለም ፤ እግዚአብሔር ሁሉን ይቆጣጠራል፡፡ ክፋት ተሸንፏል ተፈርዶበታል እንዲሁም ከፍጥረት ይወገዳል፡፡

ሰ. የእግዚአብሔር ሕዝቦች ክፋትን መቃወም አለበት (ያዕ 4፡7) ክፋት ሊቆጣጠራቸው አይችልም ነገር ግን ሌሊት እንዲሁም ምስክርነታቸውም ሊበላሽ ይችላል፡፡ (ኤፌ 6፡10-18) ክፋት የክርስትያኒ የአለም አመለካከት በመፅሐፍ ቅዱስ የተገለጠው ክፍል ነው፡፡ የዘመኑ ክርስትያናች ክፋትን ደግመው የመግለፅ፣ አሳንሶ ማየት (የፖል ቲሎች ማህበራዊ መዋቅሮች) ወይም በሳይክሎች ቃላት ሙሉ በሙሉ የመግለፅ (እንዲሲግመንድ ፎሮይድ) መብት የላቸውም ነገር ግን የክፋት ተፅዕኖ መጠነ ሰፊ ነው፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ መናፍስትን ማስወጣት**

ኢየሱስ በነበረበት ዘመን መናፍስትን ማስወጣት ተለመደ ቢሆንም የኢየሱስ መንገዶች በፍፁም የተለዩ ነበር፡፡ እርሱ መናፍስትን የሚያስወጣበት መንገድ የአዲሱ ዘመን ምልክት ነበር፡፡ ርቢዎች የጥንቆላ መንገድን ሲከተሉ ኢየሱስ የተጠቀመው የራሱስ ስልጣን ነበር፡፡ በዛሬው ዘመን መናፍስትን በማስወጣትና በመናፍስት ላይ ብዙ ግራ መጋባትና የተሳሳተ መረጃ እንዳለ ይታወቃል፡፡ የዚህም ችግር አንዱ ገጽታ አዲስ ኪዳን እነዚህን ጉዳዮች ትኩረት ሰጥቶ ሰለማይወያይበት ነው፡፡ እንደ አንድ መጋቢ ከዚህ የበለጠ መረጃ ቢኖረኝ ደስ ይለኝ ነበር፡፡ የሚከተሉት መፃህፍት እምነት የምጥልባቸው ናቸው፡፡

1. *Christian Counseling and the Occult*, Kurt E. Koch
2. *Demous in the World Today*, Merrill F. Unger
3. *Biblical Demmology*, Merrill F. Unger
4. *Principalities and Powers*, John Warwiek Montogomery
5. *Christ and the Powers*, Hendik Berkhof
6. *Three General Questions About Spiritual Warfare* by Clinton Anton.

በጣም የሚስደንቀኝ ነገር መናፍስትን ማስወጣት ከመንፈሳዊ ስጦታዎች እንደ አንዱ ያለመጠቀሱና በሐዋርያትም ደብዳቤዎች (መልዕክቶች) ውስጥ ትኩረት ያለመሰጠቱ ነው፡፡ መንፈሳዊውን ዓለም (መልካምና ክፉውን ባካተተው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምልከታ አምናለሁ፡፡

**NASB (የተሻሻለው) መፅሐፍ ቅዱስ ምዕ 5፡17-26**

**ሊቀካህናቱ ግን የሱድቃዊያን ወገን ሆነውም ከእነርሱ ጋር የነበሩት ሁሉ ተነሱ ቅንአትም ሞላባቸው፤ በሐዋርያትም ላይ እዳቸውን ጭነው በሕዝቡ ወሕኒ ውስጥ አኖሩአቸው፡፡ የጌታ መልአክ ግን በሌሊት የወህኒውነን ደጅ ከፍቶ አወጣቸውና ሂድና ቆማችሁ የዚህን የሕይወት ቃል ሁሉ ለህዝብ በመቅደስ ንገሩ አላቸው፡፡ በሰውም ጊዜ ማልደው ወደ መቅደስ ገብተው አሰተማሩ፡፡**

**ግን ሊቀካህነቱና ከእርሱ ጋር የነበሩት መጥተው ሸንጐውንና የእስራኤልን ልጆች ሽማግሌዎች ሁሉ በአንድነት ጠሩ ያመጡአቸውም ዘንድ ወደ ወህኒ ላኩ፡፡ ሌሎዎችም መጥተው በወህኒው አላጉኙአቸውም፡፡ ተመልሰውም ወህኒው በጣም በጥንቃቄ ተዘግቶ ጠባቂዎችም በደጅ ፊት ቆመው አገኙን በከፈትን ጊዜ ግን በውስጡ አንድ እንኳ አላገኘንም አሉአቸው የመቅደስ አዛዥና የካህናት አለቆችም ይህን ነገር በሰሙ ጊዜ እንጃ ይህ ምን ይሆን እያሉ ስለእነርሱ አመለከቱ አንድ ሰውም መጥቶ እነሆ በወህኒ ያኖራቸዎቸው ሰዎች እየቆሙ ሕዝቡንም እያስተማሩ በመቅደስ ናቸው ብሎ አወራላቸው፡፡ በዚያን ጊዜ አዛዡ ከሌሎች ጋር ሔዶ አመጣቸው በኃይል ግን አይደለም ሕዝቡ እንዳይወግሩአቸው ይፈሩ ነበርና፡፡**

**5፡17 "ቅንአትም ሞላባቸው"** የግሪኩ ቃል "በንዴት መጦር" ይለዋል፡፡ ስለዚህም አውድ)አገባቡ መልካም መሻት ወይም ቅንአት መሆኑን ሊነግረን ይገባል፡፡ ይህ የሚያመለክተው የሐይማኖት መሪዎችን እውነተኛ መንፈስ ያሳያል፡፡ ቅንአት ባሳደሩት ውስጥ የኢየሱስ ዋነኛ ጠላቶች ፈሪሳዊያን ነበሩ ፤ ነገር ግን በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የተከታዮቹ ዋነኛ ጠላቶች ሰዱቃዊያን ነበሩ፡፡

**5፡18** በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የሚገኙ እነዚህ የመጀመሪያዎች ምዕራፎች የቀድሞዋ ቤተክርስትያን የተጋለጠችውን (የገጠሟትን ችግሮች ያሳያል፡፡ ችግሮች ከዘመን ዘመን፣ ከባህል ባህል ይለያሉ ነገር ግን እግዚብሔር ለእኛ ነው፣ ከእኛ ጋር ነው፣ ማሸነፍ እንድንችልም ሐይልን ይሰጠናል፡፡ ምንም አይነት ነገር እስራት፣ ውይይት፣ዛቻ ወዘተ አማኞች በክርስቶስ ካላቸው ሰላምና የእርሱ መገኘት ሊለያቸው አይችልም (ሮሜ 8፡31-39)

**5፡19 "የጌታ መልአክ"** ይህ ሐረግ በብሉይ ኪዳን በሁለት መንገድ በስራ ላይ ውሏል፡፡

1. መልአክ (ዘፍ 24፡7፣ 40፣ ዘንፀ 23 ፡20-23፣ 32፡34፣ ዘሕል 22፡22 መሳ 5፡23፣ 1ሳሙ 24፡16፣ 1ዜና 21፡15፣ ዘካ 1፡28)
2. ያሕዊን ለማመልከት (ዘፍ 16፡7-13፣ 22፡11-15፣ 31፡11፣ 13፣ 48፡15-16 ዘፀ 3፡2-4፣ 13፡21፣ 14፡19፣ መሳ 2፡1፣ 6፡22-24፣ 13፡3-23፣ዘካ 3፡1-2 ሉቃስ ብዙ ጊዜ ሐረግን ይጠቀማል ( ሉቃ 1፡11፣ 2፡29

ሉቃስ ብዙ ጊዜ ይህን ሐረግ ይጠቀማል (ሉቃ 1፡11-12፣ 2፡9፣ ሐዋ 5፡19፣ 7፡30፣ 8፡26፣ 12፡7፡11፡23፣ 10፡3፣ 27፡23) ነገር ግን በቁጥር 1 ላይ ባለው ሁኔታ ነው፡፡ በሐዋርያት ስራ 8፡26 እና 29 ላይ "የጌታ መልአክ" ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በተንዳኝነት ከተጠቀሰበት ውጪ አዲስ ኪዳን የቁ. 2ን ትርጓሜ አይጠቀምም፡፡

▣ **"የወህኒውን ደጅ ከፍቶ"** ይህ ጳውሎስና ሲላስ በፊሊጶዩስ ከገጠማቸው ልምምድ ጋር ተመሳሳይነት አለው ( ሐዋ 16፡26)፡፡ በብዙ ሁኔታዎች የጴጥሮስ ሕይወት ከጳውሎስ ሕይወት ተመሳሳይነት አለው፡፡ ይህ ምን አልባት በፅሑፋዊ አቀራረቡ ሆን ተብሎ የተደረገ ሊሆን ይችላል፡፡

**5፡20 "ሒድና ቆማችሁ .... ንገሩ"** እነዚህ የሚያገለግሉት እንደ ሶስት ትዕዛዞች ነው

1. ሒድ
2. ቆማችሁ
3. ንገሩ አሁን የሚለውም አድራጊነትን የሚገለፅ ትዕዛዛ

መልአኩ ለሐዋርያት ወንጌልን የመስበክ ተልዕኮ ነበረው

▣ **"ለሕዝብ ንገሩ"** ይህ የሐዋርያት ዋናው የአገልግሎት ግፊት ነበር፡፡ በመንፈስ የተሞላው አዲሱ ሕይወት ፍርሃት ሳይሆን ድፍረት መለያ ባህሪው ነው፡፡

▣

| | |
|---|---|
| NASB | **"የዚህን የሕይወት ቃል ሁሉ"** |
| NKJB | **"የዚህን የሕይወት ቃል ሁሉ"** |
| NRSV | **"ስለዚህ የሕይወት ቃል መልዕክት ሁሉ"** |
| TEV | **"ስለዚህ አዲስ ሕይወት ሁሉ"** |
| NJB | **"ስለዚህ አዲስ ሕይወት ሁሉ"** |

ይህ ሐረግ የሚናገረው በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ውስጥ ብቻ ስላለው አዲስ ሕይወት ነው (የዘላለም ሕይወት)፡፡ በመንፈስም (ደህንነት አግኝተው) በስጋም (ከእስር ወጥተው) ነፃ ወጥተው አሁን ሁሉንም ለሁሉ እየተናገሩ ነው፡፡

**5፡21** በመለኮት ኃይል ነፃ ወጡ ማለት ዳግመኛ አይታሰሩም ማለት እንዳልሆነ አስተውል፡፡ የእግዚአብሔር አቅርቦት እንኳ በአገልግሎት ውስጥ ሁሉንም ችግሮች ያስወግዳል ወይም ይፈታል ማለት አይደለም (ማቴ 5፡10-12፣ መሜ 8፡17፣ 1ጴጥ 4፡12-16)

▣ **"ሸንጎውንና .... የእስራኤል ልጆች ሽማግሌዎች"** በምዕ 4፡15 ላይ ስለ የተሰጠውን ማብራሪያ ተመልከት ለማን ነው "ሽማግሌዎች" የሚልኩት? ኩርትስ ቮውጋን Acts በሚለው መፅሐፍ ገጽ 39-40 ላይ ሲናገር በኢየሩሳሌም ያሉ መሪዎች ነገር ግን የሸንጎው አባል ያልሆኑ (በዚያን ጊዜ) (ኤም.ኤር.ቪ.ንስንት Word Studies ቁ. 1፣ ገፅ 234) ነገር ግን NASB እና አዲሱ መደቦች ትርጉም ሽማግሌዎች እና ሸንኮ ልዩነት እንደሌላቸው ይገለጣሉ፡፡

**5፡23 "ተዘግቶ"** የድርጊቱን መፈፀም የሚያሳይ ነው፡፡ ሐሳቡ የሚያመለክተው የወህኒው በሮች በጥንቃቄ ተዘግተውና ጠባቂዎቹም በደጅ ፊት ቆመው እንደነበሩ የሚያሳይ (የድርጊቱን መፈፀም የሚያሳይ) ነገር ግን እስረኞቹ ግን ሔደዋል፡፡

**5፡24 "አመነቱ"** ሉቃስ ይህንን ቃል ብዙ ጊዜ ይጠቀማል፡፡ aporio (ሉቃ 24፡4፣ ሐዋ 25፡20) Via ከሚለው ቃል ጋር (ሉቃ 9፡7፣ ሐዋ 2፡12፣ 5፡24፣ 10፡17) በጠንካራ አገላለፅ ሲተላለፍ ነው፡፡ መሠረታዊ ትርጉሙም መጠራጠር፣ እርግጠኛ ያለመሆን ወይም ግራ መጋባት ነው፡፡

▣ "እንጃ ይህ ምን ይሆን" የዚህ ሐረግ የሰዋሰው ቅርፅ አራተኛው መደብ ነው፡፡ የዚህ ግስ ሁኔታ የሚያሳየው ግራ መጋባትን (ሉቃ 1:61-62፣ 3:15፣ 8-9፣ 15:26፣ 22:23፣ ሐዋ 5:24፣ 8:31፣ 10:17፣ 21:23) በዚህ ጉዳይ ላይ የጀምስ አለን ሕይወትን New Testament (ገፅ 195) ን ተመልከት፡፡

5:26 "ሕዝቡ እንዳይወግሩአቸው ይፈሩ ነበርና" ይህ የሚያመለክተው የቀደመችው ቤተክርስትያን ለመጥሮ መሆኗን (ቁ 13፣ 2:47፣ 4:21) እና የአይሁድ መሪዎች በቅንአት እየተቃጠሉ ለመሔዳቸው ምክንያት እንደነበረች ነው፡፡

**NASB (የተሻሻለው) መፅሐፍ ቅዱስ ምዕ 5:27-32**

**አምጥተውም በሸንጐ አቆሙአቸው ሊቀካህናቱም በዚህ ስም እንዳታስተምሩ አጥብቀን አላዘዝናችሁምን እነሆም ኢየሩሳሌምን በትምህርታችሁ ሞልታችኋል የዚያንም ሰው ስም በእኛ ታመጡብን ዘንድ ታስገባላችሁ ብሎ ጠየቃቸው ጴጥሮስና ሐዋርያትም መልሰው አሉ ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልትታዘዙ ይገባል፡፡ እናንተ በእንጨት ላይ ሰቅላችሁ የገደላችሁትን ኢየሱስን የአባቶቻችን አምላክ አስነሳው ፤ ይህን እግዚአብሔር ለእስራኤል ንስሐን የሐጢአትንም ስርዓት ይሰጥ ዘንድ ሁሉም መድኃኒትም አድርጐ በቀኙ ከፍ ከፍ አደረገው፡፡ እኛም ለዚህ ነገር ምስክሮች ነን ደግሞም እግዚአብሔር ለሚታዘዙት የሰጠው መንፈስ ቅዱስ ምስክር ነው፡፡**

5:28
NASB NRSV
TEV "ጥብቅ ትዕዛዝ"
NKJV "በጥብቅ አዘዝን"
NJB "ጠንካራ ማስጠንቀቂያ"

የኪንግ ጀምስ ትርጓሜ "በጥብቅ አላዘዝንም" የሚል እሳቤ አለው፡፡ ይህም የግሪክ ፅሑፍ ሆኖ በተለያዩ ትርጉሞች ይገኛል፡፡ ለምሳሌ በግሪክ ትርጉሞች በ$N^2$፣ በD እና በE ነገር ግን በP74፣ በA ወይም በB አይገኝም፡፡ አፍራሽ ቃሉ በኋላ በፀሐፍት የተጨመረ መሆን አለበት፡፡

አወቃቀሩ የሴሜቲክ አባባል ይመስላል (ሉቃ 22:15) በዚህም ግሱ (ኘሪንጀሎ) እና ቀጥተኛ ተሳቢው (ኘሪንጀልያ) መሠረታቸው አንድ ነው፡፡ አወቃቀሩ የሚያጠናክረው የቃሎቹን መሠረታዊ ትርጉም ነው፡፡ በጣም የሚያስደንቀው የዚህ ቃል በግብፅ መገኘት ማለት ወደ ፍርድ ቤት የሚያስወስድ ወይም ትዕዛዛ የሚያስመጣ ነው፡፡

▣ "የዚህን ሰው" ይህ የሚያሳየው የአይሁድ መሪዎችን ንቀት ነው፡፡ የኢየሱስን ስም በፍፁም አይገልፁትም፡፡ ታልሙድ የሚባለው ማብራሪያ ብሎት ይጠራዋል (ኤም .ኤር.ቪንሰንት Word studies ቁ.1 ገፅ 234)

▣ "ደም በእኛ ላይ" ጴጥሮስና ዮሐንስ የአይሁድ መሪዎች የኢየሱስን መሞት እንዳቀነባበሩ በማስረገጥ ተናገሩ፡፡ ይህም ሁኔታ በእስጢፋኖስ ወቀሳ የታየ ነበር (7:52)::

5:29 "ይገባል" dia የሚለው ቃል የግብረ ገብ አስፈላጊነትን ያመለክታል ይህም የሚያሳየው ወንጌል የትኛውንም ችግር ቢያስከትልም ሐዋርያት እውነቱን የመስበክ ግዴታ እንዳለባቸው ነው (4:19)::

5:30 "የአባቶቻችን አምላክ" ቀደምት ክርስትያኖች በብሉይ ኪዳን የሚገኙት የእግዚአብሔር ሕዝቦች እውነተኛ መንፈሳዊ ዘሮችና ወራሾች መሆናቸውን ያምኑ ነበሩ (ሮሜ 2:28-29፣ ገላ 6:16፣ 1ጴጥ 3:5-9 ራዕ 1:6)::

▣ "ኢየሱስን አስነሳው" አዲስ ኪዳን አብ ኢየሱስን እንዳስነሳው ያረጋግጣል (ሐዋ 2:24፣ 32፣ 3:15፣ 26፣ 4:10፣ 5:30፣ 10:40፣ 13:30፣ 33:34፣37፣ 27:31፣ ሮሜ 6:4-9) ይህም የኢየሱስን ሕይወትና ትምህርት እውነተኝነት ለማረጋገጥ ነው፡፡ ይህም ዋናው የሙታን ትንሳኤ አቅጣጫ ነው (1ቆሮ 15)::

▣ "እናንተ በእንጨት ላይ ሰቅላችሁ የገደላችሁትን" ይህ በዘዳ 21:23 ላይ ከተሰጠው የመርገም ቃል ጋር የሚገናኝ ነው፡፡ እነዚህ የኃይማኖት መሪዎች መሲሁን ኢየሱስ የይሕዌን መርገም እንዲሸከም ፈለጉ፡፡ ኢየሱስም የብሉይ ኪዳንን ሕግ ተሸከመ (ኃጢአት የምትሰራ ነፍስ እርስዋ ትሞታለች) (ሕዝ 18:4፣ 20) ሁሉም ሰዎች ኃጢአትን ሰርተዋል (ሮሜ 1:15፣ 2ቆሮ 2:14) ስለ እኛ ሲል (ገላ 3:13፣ ቆላ 1:14)፡፡ ኢየሱስም ሐጢአት የሌለበት የእግዚአብሔር በግ ነበር (ዮሐ 1:29፣ 2ቆሮ 5:21)::

5:31 "እግዚአብሔር በቀኙ ከፍ ከፍ አደረገው" ከፍ ከፍ አደረገው የሚለው ቃል በዮሐ 3:14 ላይ "ወደ ላይ ተነሳ" ተብሎ ሲተረጐም በፊልጰ 2:9 ደግሞ "ያለልክ ከፍ ከፍ" ተብሎ ተተርጉሟል፡፡ መስቀሉ የክርስቶስ ከፍ የሚልበት እና ድል የሚነሳበት መንገድ ነው (ቆላ 1:15፣ 2ቆሮ 2:14) "በቀኙ ከፍ ከፍ አደረገው" የሚለው አገላለፅ የሐይልና የስልጣን ተምሳሌት ነው (ማቴ 26:64) እግዚአብሔር ዘላለማዊ መንፈስ ነው፤ የሚዳሰስም አካል የለውም፡፡

▣ "ራስም" ይህ ጥቅስ በግልፅና ልዩ በሆነ ሁኔታ የኢየሱስን መሲህነት ያረጋግጣል፡፡ ይህ ቃል ራሱ በምዕ 3:5 ላይ "ደራሲ" ተብሎ ተተርጉሟል፡፡ ዋና ፈር ቀዳጅ ወይም "ልዑል" የሚል ትርጉም ሊኖረው ይችላል፡፡ የአንድ ት)ቤት ወይም ቤተሰብ መስራች በሚል ሐሳብ ጥቅም ላይ ውሏል (ዕብ 2:10፣ 12:2)::

▣ **“መድኃኒት”** ይህ ቃል በቂሳር የግሪኩ ሮም አገዛዝ በአንኛው ክ)ዘመን በስራ ላይ ወሎ ነበር፡፡ ቄሳር ራሱን የዓለም ባህልና ሰላም መድኃኒት አድርጐ ይመለከት ነበር፡፡ ሌላው ቃል ቄሳሮች ለራሳቸው የሚጠቀሙት ፤ ነገር ግን ክርስትያኖች ለየት ባለ ሁኔታ የሚጠቀሙት ቃል ጌታ (ኩርዮስ) የሚለውን ነው፡፡ ሌላው “መድኃኒት” የሚለው ቃል ሌላው አቅጣጫ ደግሞ ያህዌ ለሚለው በብሉይ ኪዳን የሚጠቀሙት ነው (2 ሳሙ 22፡3፣ መዝ 106፡21 ኢሳ 4፡4፣ 11፣ 45፡15፣ 21፣ 49፡26፣ 60፡16፣ 63፡8) የአዲስ ኪዳን ፀሐፊዎች የኢየሱስን አምላክነት የሚያረጋግጡት በብሉይ ኪዳን ለያህዊህ የተሰጡትን ስዎች በመስጠት ነው፡፡ ጳውሎስ በመልዕክቱ ለጢሞቲዎስ እንዴት ይህን እንደገለፀ ተመልከት፤

1. 1፡3 “መድኃኒታችን እግዚአብሔር”
2. 1፡4 “ከመድኃኒታችንም ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ”
3. 2፡10 “መድኃኒታችን እግዚአብሔር”
4. 2፡13 እግዚአብሔር “ታላቁ አምላካችንና መድኃኒታችንን ኢየሱስ ክርስቶስ
5. 3፡4 “እግዚአብሔር መድኃኒታችን”
6. 3፡6 “መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ”

▣ **“ለእስራኤል ንስሐን፣ የኃጢአትንም ስርሃት ይሰጥ ዘንድ”** ይህ የሚያመለክተው የኢየሱስን መሞት ዓላማ ነው (ሉቃ 24፡47 እና ሐዋ 2፡38) ለአዲስ ኪዳን ፀሐፊዎች ንስሐ እንደ እግዚአብሔር ስጦታ ለማመልከት ያልተለመደ ነገር ነው (ሐዋ 11፡18፣ 2ጢሞ 2፡25 እንዲሁም ምናልባት 1ጢሞ 2፡4) በተለምዶ ይህ የአዲሱ ቃል ኪዳን አንዱ መስፈርት ነው (ማር 1፡15 እና ሐዋ 3፡16፣ 19፣ 20፡21)::

በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔር ያለበትን ድርሻ ላይ ትኩረት የሚያደርጉ አማኞች ይህንን ጥቅስ በመጠቀም ደህንነት ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር ስራ ነው ብለው ያምናሉ፡፡ ይሁን እንጂ ይህ አንድ ሰው አስቀድሞ ያለውን የስነ መለኮት አወቃቀር ለማረጋገጥ በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በግልፅ የእግዚአብሔርን አነሳሽነትና አስፈላጊነት ያስቀምጣል፡፡ ነፃነት እግዚአብሔር መጀመሪያ ሲፈጥር የሰጠው ነገር ነው፡፡ እግዚአብሔር ይህን ስጦታ) ኃላፊነት አይጥስም (ሮሜ 2፡4፣ 2ቆሮ 7፡10) እግዚአብሔር እኛን ይስበናል፣ ያባብለናል፣ ከእኛ ጋር ይሰራል እንዲሁም የምንድንበትን መንገድ ያዘጋጃል (ዮሐ 6፡44-65)፡፡ ነገር ግን የወደቀው የሰው ዘር ምላሽ መስጠትና በምላሹም በንሰሐ፣ በእምነት፣ በመታዘዝ እና በመፅናት ሊሆን ይገባል፡፡

በጣም ደስ የሚያሰኝ ጥቅስ (ፍራንክ ስታግ New Testamet Theology ገጽ 119)::

“ሰዎች ንሰሐን በራሳቸው ሊያመጡ አይችሉም ነገር ግን ንሰሐን ብቻ ሊቀበሉ ይችላሉ አንድ ሰው ክርስቶስን ወደ ልቡ ይቀበላል በአንፃሩም ክርስቶስ ደግሞ ያንን ሕይወት በመለወጥ ራሱን ከማመን ወደ በእግዛአብሔር ወደ መታመን ያመጣዋል ራስን ከማፅደቅ ወደ ራስን ወደ መካድ ያመጣዋል፡፡ ይህ መለወጥ የሰው ልጅ ውድቀት በተቃራኒው ነው ይህም ሰው የሕይወትን ትርጉም ከራሱ የሚያገኝበት ነው፡፡

5፡32 በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ጴጥሮስ ሐዋርያትና ደቀመዛሙርት የኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት፣ ሞትና ትንሳኤ ምስክሮች መሆናቸውን ብዙ ጊዜ ገልጾታል፡፡ በዚህ አገባብ ላይ እርሱ ሲጨምር “መንፈስ ቅዱስን” እንዲመሰክር አድርጐ ይጠቅማል፡፡ ይህ ምናልባት በብሉይ ኪዳን አንድን ነገር ለማረጋገጥ የሚያስፈልጉ ሁለት አስፈላጊ ነገሮችን የማረጋገጫ መንገድ ነው (ዘሕል 35፡30፣ ዘዳ 17፡6)::

▣ **“እግዚአብሔር ለሚታዘዙት”** መታዘዝ የሕይወት ዘይቤ ምርጫ ነው ወንጌልን በማመን መታዘዝ አለብን፡፡ መታዘዛችንን በመፈፀም የውጤቱ ተጠቃሚዎች መሆን አለብን (ሉቃ 6፡46)፡፡ ብዙ ጊዜ የማንጠቀመው ቃል መታዘዝ (Peithomai Plus Auche 27፡21፣ ቲቶ 3፡1) የሚለው ቃል በቁ 29 እና 32 ላይ “ruler” (archi) እና መታዘዝ የሚለው ቃል ጥምረት ነው፡፡

**NASB (የተሻሻለው) መፅሐፍ ቅዱስ ምዕ 5፡33-39**

**እነርሱም ሲሰሙ በጣም ተቆጡ ሊገድሉአቸውም አሰቡ፡፡ ነገር ግን በህዝብ ሁሉ ዘንድ የከበረ የሕግ መምህር ገማልያል የሚሉት አንድ ፈሪሳዊ በሸንጐ ተነስቶ ሐዋርያትን ጥቂት እንዲያደርጓቸው አዘዘ እንዲህም አላቸው የእስራኤል ሰዎች ሆይ ስለእነዚህ ሰዎች ምን እንደምታደርጉ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፡፡ ከዚህ ወራት አስቀድሞ ቴዎዳል እኔ ታላቅ ነኝ ብሎ ተነስቶ ነበርና ፤ አራት መቶ የሚያህሉ ሰዎችም ከእርሱ ጋር ተባበሩ ፤ እርሱም ጠፋ የሰሙትም ሁሉ ተበተኑ እንደምናምንም ሆኑ፡፡ ከዚህ በኂላ ሰዎች በተፃፊበት ዘመን የገሊላው ይሁዳ ተነሳ ብዙ ሰዎችንም አሸፍቶ አስከተለ እርሱም ጠፋ የሰሙትም ሁሉ ተበታተኑ፡፡ አሁንም እላችኂለሁ ከእነዚህ ሰዎች ተለዩ ተውአቸውም፡፡ ይህ ሐሳብ ወይም ይህ ሥራ ከሰው እንደሆነ ይጠፋልና ከእግዚአብሔር እንደሆነ ግን ታጠፋአቸው ዘንድ አይቻላችሁም በእርግጥ ከእግዚአብሐር ጋር ስትጣሉ ምናልባት እንዳትገኙ፡፡**

5፡33

| | |
|---|---|
| NASB | “በጣም ተቆጡ” |
| NKJV | “በጣም ተናደዱ” |
| NRSV | “በጣም ተቆጡ” |
| TEV | “በጣም ተናደው ነበር” |
| NJB | “ይህ በጣም አናደዳቸው” |

ይህ ቃል በጥሬ ትርጉሙ "በመጋዝ መቁረጥ" ወይም "ጥርስን ማፋጨት" ነው፡፡ ይህ ቃል በተመሳሳይ አይነት (መልክ) በምዕ 7፡54 ላይ ተገልፆል፡፡ እዚህ ላይ የተጨመረው "በልባቸው በጣም ተቆጡ" የሚለው ሐረግ ሙሉውን ተምሳሌታዊ ትርጓሜ ያሳያል (ሉቃ 2፡35ን ተመልከት)፡፡ ይህ ጠንካራ ቃል (ማለት diaprie) በምዕ 2፡31ሀ ላይ ካለው ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው፡፡

▣ **"ሊገድሉአቸውም አሰቡ"** ይህ ያላለቀ ዓ)ነገርን የሚያመለክት ነው፡፡ ይህም ማለት (1) በሚናገሩበት ጊዜ ለመግደል ሙከራ ጀምረዋል (2) ይህ የታቀደና የተቀነባበረ መሻት ነው ከቀደመችው ቤተክርስትያን እድገት ካለን ግንዛቤ አንፃር የመጀመሪያው ተስማሚ ነው፡፡ ይህን የመግደል ሐሳብ ያንፀባረቁት ሰዱቃዊያን እንደሆኑ ልብ በል፡፡ ፈሪሳዊያን (ገማልያ) የቀደመችው ቤተክርስትያን ሰዶቃውያን በትንሳኤ ሙታን ላይ ያላቸውን አቋም እንደ ልዩ ማርከሻ አድርገው ይመለከቷቸዋል፡፡ ፈሪሳዊያን ማረጋገጥ የሚፈልጉት የትንሳኤ ጉዳይ አይደለም፡፡

በአሁን ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነቡ የሐይማኖት መሪዎች ነፍስ ለማጥፋት ሲያቅዱ ሲያይ ሊደነቅ ይችላል፡፡ እነዚህ ሰድቃዊያን ለሙሴ ሕግ ራሳቸውን የሰጡና ሕግን የሚሳደብ በድንጋይ ተወግሮ ይሙት ባይ ናቸው፡፡ እነዚህም መሪዎች እግዚአብሔርን ወክለው የሚያረጉና እንደቃሉ መሆናቸውን ያምናሉ፡፡ (ዘሌ 24፡10-16)፡፡

5፡34 **"ፈሪሳዊያን"** የሚከተለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት

---

**ልዩ ርዕስ: ፈሪሳዊያን**

ቃሉ የሚከተሉት ምንጮች የነበሩት ይመስላል፡፡
ሀ. "የተለዩ" ይህ ቡድን የተለያየው በመቃብያን ዘመን ነው፡፡
(ይህ ከሁሉም በስፋት ተቀባይነት ያገኘ አመለካከት ነው)
ለ. "የተካፈሉ" ይህ ተመሳሳይ የዕብራይስጥ የቃሉ ምንጭ ሌላው ትርጉም ነው (2ጢሞ 2፡15)
ሐ. "ፈርሳዊ" ይህ ተመሳሳይ የአራማይክ የቃሉ ምንጭ ሌላው ትርጉም ነው፡፡ አንዳንዶች የፈሪሳዊያን አስተምህሮቶች ከፔርሺያን ዞሪስትሪያን ዱዋሊዝም ጋር ብዙ ተመሳሳይነት አላቸው፡፡

ፈሪሳዊያን መስፋፋት የጀመሩት በመቃብያን ዘመን ከ "ሐሲደም" (Piousenes) ብዙ የተለያዩ ቡድኖች እንደ "ኢሳንስ" የመሳሰሉት የመጡት በአንቲከስ 4ኛ ኤፒፓኔስ ላይ በተነሳው ፀረ-ሔሌኒስትክ እንቅስቃሴ ውስጥ ነው፡፡ ፈሪሳዊያን ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሱት ፍሴፊል Antiquities of the Jews በሚለው መጽሐፍ ምዕራፍ 8፡5፡1-3 ላይ ነበር፡፡

ዋና ዋና አስተምህሮቶቻቸው
ሀ. በመሲሑ መምጣት
ለ. እግዚአብሔር በዕለታዊ ሕይወት በስራ ላይ ነው፡፡ ይህ በቀጥታ ከሰዱቃዊያን አስተምህሮት ጋር የሚቃረን ነው፡፡ አብዛኛው የፈሪሳዊያን አስተምህሮ ለሰዱቃዊያን አስተምህሮ የተሰጠ ሥነ-መለኮታዊ ምላሽ ነው፡፡
ሐ. በምድር ላይ ሕይወት የተመሰረተ ይህም ሽልማትንና ቅጣትን ያካተተ ነው፡፡ እነዚህም ምናልባት ኪዳን 2፡2 የመጡ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
መ. የብሉይ ኪዳንን የትውፊት ባህል ስልጣን በረቢ የሃይማኖት ሊቃውንት እንደተተረጐሙትና በስራ ላይ እንደዋሉት ለብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ትዕዛዛትከፍተኛ አፅንኦት በመስጠት ይታዘዛሉ፡፡ ("ሻማይ" ወግ አጥባቂዎች "ሄሰል" ለዘብተኞቹ) የረቢዎች ትርጓሜ የተመሰረተው በሁለት ረቢዎች መካከል በሚደረግ ክርክር ነው፡ አንድ ወግ አጥባቂ ሌላው ለዘብተኛ አቋም ያለው፡፡ እነዚህ በቅድስት መምህርት ላይ የሚደረጉ የቃል ውይይቶች በሁለት መንገዶች ይፃፋሉ፤ የባቢሎናዊያን ታልሙድ እና ያልተሟላው የፍልስጥኤም ታልሙድ በመባል ሙሴ እነዚህን ያልተፃፉ (የቃል) ትርጓሜዎችን በሲና ተራራ ላይ ተቀብሏል ብለው ያምናሉ፡፡ የእነዚህ ታሪካዊ ውይይት የተጀመሩት በእዝራ እና "የተዳቁ ምኩራብ" ሰዎች ነው (በኗላም የተባሉት)፡፡
ሠ. በጣም የተጠናከረ የስነ-መለኮት ትምህርት ይህም ሁለቱን መልካም እና ክፉ መንፈሳዊ አካላትን የሚያካትት ነው፡፡ ይህም የተስፋፋው ከፋርሳዊያን ዲሞሊዝም እና ከአይሁዶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስነ ዕሁፍ ነው፡፡

---

**ልዩ ርዕስ፡ ገማልያል**

I. ስሙ
ሀ. የስሙ ትርጉም "እግዚአብሔር ሽላሚዬ ነው" ማለት ነው
ለ. በአይሁድ አመራር ውስጥ ተሳታፊ ከነበረው ዘውዱ ለመለየት ሲባል "ቿስማግሌው" ወይም ገማልያል ፤ ተብሎ ይታወቃል፡፡
II. የሰውየው ማንነት
ሀ. ትውፊት እንደሚለው እርሱ የሒስል የልጅ ልጅ እንደሆነ ነው
ለ. ሌሎች ትወፊቶች ደግሞ እንደሚሉት ከሔሮድስ ንጉሳዊ ቤተሰብ ጋር ትስስር አለው (ማለትም ኢግሪጳ)

ሐ. ትውፊት እንደሚለው እርሱ የኾሮዝዳንት እንደነበር ነገር ግን ይህ ምናናልባት የሚያመለክተው ገማልያል II ሊሆን ይችላል፡፡
መ. በጣም ስመ ጥር ከሆኑት ከ7ቱ ረቢዎች የተከበረና ረቢ የተሰኘውን ማዕረግ የተቀበለ ነበር
ሠ. በሰባ (70) ዓመተምህረት ነበር የሞተው
III. ሥነ መለኮቱ
ሀ. በጣም ሥመ ጥር ረቢ ነበር
ለ. በሌሎች አገሮች ከተበተኑት አይሁዶች እንክብካቤና ቁጥጥር በማድረግ የሚታወቅ ሰው ነው፡፡
ሐ. በማህበረሰቡ ለተገፋ ሰዎች ትኩረት በመስጠት ይታወቃል (የእርሱ Takkont ብዙውን ጊዜ ለሰው ዘር ጥቅም በሚል የሚጀምር ነው)
1. ወላጅ አልባ ሕፃናት
2. መበልቶች (ባሎች የሞቱባቸው)
3. ሴቶች
መ. በኢየሩሳሌም የጳውሎስ ረቢ ነበር (ሐዋ 22፡3)
ሠ. በሐዋ 5፡39 የቀደመችውን ቤተክርስትያን በፍልስጥኤም ምድር እንዴት መያዝ እንዳለባት የሊቃውንት ጥበብን በመስጠት ይታወቃል፡፡
ረ. ይህ ረቢ ሲሞት በብዙዎች ዘንድ የተሰበው እንደውም ረቢ ገማልያል ሽማግሌው ሲሞት የሙሴ የሕግ መጽሐፍት ክብር አቁሟል እንዲሁም ደግሞ ንፅህናና ቅደስና ጠፍቷል (”መለየት”) ተብሎ ነበር (Sot. ከ*Eccyclopedia Judiaica* ቁ. 7 ገጽ 296 ላይ የተወሰደ)
ሰ. በዚህ ሁኔታ ውስጥ የገማልያል ሐሳብ ምን እንደሆነ እንደማይታወቅ ማወቅ ይገባል፡፡ ከሰዱቃውያን ጀብደኝነት ይልቅ የፈሪሳዊያንን ጥበብ የደገፈ ይመስላል፡፡ ስለዚህ ሁለቱ ኃይል የአይሁድ የኃይማኖት ክፍሎች በማንኛውም አጋጣሚ አንዱ ሌላውን ያጠቃ ነበር፡፡

**5፡36-37 ቴዎዳስ …** የገሊላው ይሁዳ ጆሴፊል እነዚህ ሁለቱን ስሞች ይጠቅሳል (Antiq 20፡5-1)፡፡ ይሁን እንጂ የዘረዘራቸው በተቃራኒው መልኩ ነው፡፡ ተጨማሪ ታሪካዊ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በዚህ ስም የተጠቀሱ በሮም ቅኝ አገዛዝ ላይ ተቋውሞ ያደረጉ ሁለት የአይሁድ ቀናተኞች (ተቃዋሚዎች) ነበሩ፡፡ ስለዚህ አዲስ ኪዳንና ጆሴፈስ ሁለቱም ትክክል ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በገማልያል የተጠቀሰው በሮም ላይ ያመፀው በ6ኛው ዓ.ም. ሲሆን በጆሴፈስ የተጠቀሰው ደግሞ በ44ኛው ዓ.ም. ነበር፡፡

**5፡37 "ሰዎች በተፃፉበት ዘመን"** ጆሲፊስ (Antiq 18፡1፡1) ላይ እንደሚነግረን አርኪላዊስ ከንግስናው ከወረደ በኂላና ኩዕይል (ከ6-7 ዓ.ም. አካባቢ) አውግስጦስ ቄሳር አይሁድ ቀረጥ እንዲከፍሉ ትዕዛዝ ሰጥቶ ነበር፡፡ ይህ ለቁርጥ ዓላማ የሚደረግ የሕዝብ ቆጠራ በየ14 ዓመት የሚካሄድ ሲሆን ለመጠናቀቀም አመታትን ይወስዳል፡፡

▣ **"የገሊላው ይሁዳ"** ብዙ ጊዜ በጆሲፊስ ተጠቅሷል (Antiq 18፡1 1-6፣ 26፡5-2) እንዲሁም በwors 2፡8፡1፣ 2፡17፣ 8-9) የእሱ አመት የተጀመረው በ6ኛው ወይም በ7ኛው ዓ.ም. ነው፡፡ የቀናተኛ አይሁድ እንቅስቃሴ መስራች ነበር፡፡ ቀናተኞቹ (ጆሴፊስ እንደሚለው አራተኛው ፍልስፍና) እና ዘ "ሲካሪ" (ማለትም assaaaing) ምናልባትም ተመሳሳይ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ነበራቸው፡፡

**5፡38 "ከእነዚህ ሰዎች ተለዩ ተዋአቸውም"** ምን አይነት አስደናቂ ምክር ነው
1. *aphistemi,* ተለዩ፣ ለዩ
2. *aphiomi* ላከው፣ አጥፋው

▣ **"እንደ ሆነ"** ይህ ሶስተኛው ዓረፍተ ነገር ሲሆን ሊፈፀም የሚችል መሆኑን አመልካች ነው፡፡

**5፡39 "እንደሆነ"** ብዙውን ጊዜ የሚያመለክተው ስለውነትን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ ስፍራ ላይ እውነት ሊሆኝ አይችልም፡፡ ይህም የሚያሳየው የሰዋሰው መልኩ ሥነፅሑፋዊ አጠቃቀምን ነው፡፡

▣ **"ምናልባት ከእግዚአብሔር ጋር ስትጣሉ እንዳትገኙ"** ሊታወቅ የሚገባው እነዚህ የሐይማኖት መሪዎች እግዚአብሔርን ወክለው እንደሚከራከሩ ነው፡፡ ሊሳሳቱ እንደሚችሉ ገማልያል የተናገረው በጣም አስደንጋጭ ነበር (11፡17)

**5፡40 "ሰሙትም"** ይህ ሐረግ በአንዳንድ ትርጉሞች በቁ. 39 ውስጥ ነው የተካተተው (NRSV) በሌሎች ደግሞ በቁ. 40 ውስጥ ተካቷል (NASB, NKJV) TEV እና NJB በቁ. 39 ውስጥ አካተው አዲስ አንቀፅ ይጀምራሉ፡፡

**NASB (የተሻሻለው) መፅሐፍ ቅዱስ ምዕ 5፡40-42**
**ሰሙትም ሐዋርያትንም ወደ እነርሱ ጠርተው ገረፋአቸው በኢየሱስም ስም አእንዳይናገሩ አዝዘው ፈቱአቸው፡፡ እነርሱም ስለ ስሙ ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለተቆጠሩ ከሸንጐው ፊት ደስ እያላቸው ወጡ ፤ ዕለት ዕለትም በመቅደስና በቤታቸው ስለኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ ማስተማርና መስበክን አይተውም ነበር፡፡**

▣ *"ገረፏአቸው" ይህ የሮማዊያን አይነት ግርፋት አልነበረም*)mastic *ሐዋ* 22:24-25) *ልክ ኢየሰስ የተገረፈበት። ይህ የሚያመለክተው የአይሁዳዊያንን በበትር መምታት ያመለክታል።* (ዘዳ 25:3 *ማለትም* deror *ሉቃ* 12:47-48፣ 20:10-11፣ 22:63) *የሚያሳምም ቢሆንም ለሕይወት የሚያሰጋ አልነበረም።*

*ያለው የአተረጓጐም ችግር እነዚህ ሁለቱ የግሪክ ቃላት እየተለዋወጡ ጥቅም ላይ ይውላሉ። የዘዳግ* 25:3 *ሰብትዋጀንት አለው ነገር ግን የአይሁዶችና የቅጣት ዘይቤ የሚያመለክት ነው። ሉቃስ በተለምዶ የሚለውን ቃል አይሁደ በምኩራብ የሚያሳዩትን የእምነት ዘይቤ ለመግለፅ ተጠቅሟል።* (በጥሬ *ትርጉሙ አንሶላን መግፈፍ" ማለት ነው*)።

▣ **"በኢየሱስም ስም እንዳናገሩ አዝዘው"** *ይሔው ሸንጐ ከዚህ ቀደም ተመሳሳይ የሆነ እርምጃ ወሰደው ነበር* (4:17፣ 21) *በዚህ ጊዜ መቷቸው ማስጠንቀቂያውንም ደገሙት*

5:41 *ኢየሱስም ስለዚህ ጉዳይ አስቀድሞ ተናግሮ ነበር* (*ማቴ* 10:16-23፣ *ማር* 13:9-13፣ *ሉቃ* 12:1-12፣ 21:10-19፣ *ዮሐ* 15:18-27፣ 16:2-4)

▣ **"እነርሱም ስለሰው ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለተቆጠሩ"** *ይህ ዛሬ ለእኛ በጣም የሚያስደንቀን ጉዳይ ነው ምክንያቱም እኛ የምንኖረው አካላዊ ለደት የማይታይበት ስደት ማህበረሰብ ውስጥ ነው። ነገር ግን ለዘመናት ለአብዛኞዎቹ አማኞች ጉዳዩ ይህ አልነበረም።*

*ኢየሱስ በግልፅ የእረሱ ተከታዩች መከራ እንደሚደርስባቸው ተናግb*ል። *ማቴ* 5:10-12፣ *ዮሐ* 15:18-21፣ 16:1-2፣ 27:14፣ *ሐዋ* 14:22 *ሮሜ* 5:3-4፣ 8:17 2*ቆሮ* 4:16-18፣ *ፊሊ*. 1:29፣ 1*ተሰ* 3:3 2*ጢሞ* 3:12፣ *ያዕ* 1:2-4 *እንዲሁም* በ1*ኛ ጴጥ የኢየሱስ መከራ እንዴት እንደነበር ተመልከት* (1:11፣ 2:21፣ 23፣ 3:18፣ 4:1፣ 13፣ 5:1) *እንዲሁም የእርሱ ተከታዮች የእርሱን ፈለግ ሲከተሉ እንደሚገባቸው* (1:6-7፣ 2:1-9፣ 3:13-17፣ 4:1-12-19፣ 5:9-10)።

5:42 **"ዕለት ዕለትም በመቅደስ"** *እነዚህ ቀደምት የኢየሱስ ምስክሮች የአይሁድ እምነት እምብርት በሚገኝበት በቤተመቅደሱ እንኳ ዝም ለማለት እምቢ ብለው ይመሰክሩ ነበር።*

▣ **"በቤታቸው"** *የቀደመችው ቤተክርስትያን ሰብሳቢዎቻቸውን የሚያካሂድት በከተማው ውስጥ በሚገኙ የግለሰብ ቤቶች ውስጥ ነበር* (2:46) *እስከ ብዙ መቶ ዓመታት ድረስ የቤተክርስትያን ሕንፃ የሚባል አልነበረም።*

**የውይይት ጥያቄዎች**

*ይህ የጥናት* <u>*መመሪያ*</u> *ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።*

*እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ለመርዳት ነው የተሰናዱት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋነኞቹን ጉዳዮች ለማጤን እንዲረዳ ነው። ሐሳብ ለማጫር እንጂ መደምደሚያ አይደሉም።*

1. *ሐዋርያው ለምንድን ነው በይሁዲነት ውስጥ ለዚህ ያህል ጊዜ የቆየው?*
2. *በምዕራፍ* 3 *ውስጥ ለኢየሱስ የተሰጡ አርዕስቶችንና ትርጉማቸውን ዘርዝር*
3. *ለደህንነት አስፈላጊ የሆኑ ሁለት ነገሮችን ግለፅ*
4. *በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሙሴ መጻሕፍት ለምንድነው በብዛት የሚጠቀሱት?*
5. *የአብርሃም ኪዳን ለአዲስ ኪደንዋ ቤ/ክን ምን ጠቀሜታ አለው?*
6. *ጴጥሮስና ዮሐንስ ለምንድነው የታሰሩት?*
7. *የጴጥሮስን ስብከት ዝርዝር ይዘት ፃፍ*
8. *የሐዋ* 4:24-31 *የፀሎት ጥቅም ምንድን ነው?*
9. *በእውነት ከሆነ አዲስ ኪዳን አንዱ ኮሚኒስታዊ ነገር ነው* (4:32)
10. *ሉቃስ ሃናንያንና ለጵራን ስራ ለምን እንደጻፈ ምክንያቶቹን ግለፅ*
11. *ሃናነያ በሰይጣን እንደተሞላ ያውቅ ነበር ወይ? እግዚአብሔርን እየዋሸ እንዳለ ያውቅ ነበር ወይ?*
12. *እግዚአብሔር ለምን ይሆን ጨካኝ የመሠለው?*
13. *በዘመናችን የፈውስ አገልግሎት እንዴት ነው?*
14. *ሰዱቃውያን ለምንድን ነው የተናደዱት?*
15. *መልዕክቶች ለምንድን ነው ሐዋርያትን ከእስር ቤት ያስወጡት?*
16. *የጴጥሮስን አራተኛውን የስብከት ዝርዝር ግለፅ። በሌሎች የሐዋርያት ስራ መጻሕፍት ያሉት ዝርዝር ጉዳዮች ጻፍ።*
17. *ገማልያ ማን ነበር?*
18. *ክርስቲያኖች ለምንድን ነው በመከራ ወቅት መደሰት ያለባቸው?*

# ሐዋርያት ሥራ 6

## የተሻሻሉ ትርጓሜዎች የአንቀፅ አከፋፈል

| UBS[4] | NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| የሰባቱ መሾም | ሰባቱ ለማገልገል መሾማቸው | የሰባቱ ምርጫ | ሰባቱ ረዳቶች | የሰባቱ ተቋም |
| 6:1-6 | 6:1-7 | 6:1-7 | 6:1-4 | 6:1-6 |
| | | | 6:5-6 | |
| 6:7 | | | 6:7 | 6:7 |
| የእስጢፋኖስ መያዝ | እግዚአብሔርን ተሳደብክ ተብሎ መከሰሱ | የእስጢፋኖስ ስብከትና ሰማዕትነት | የእስጢፋኖስ መያዝ | የእስጢፋኖስ መያዝ |
| | | )6:8-7:2ሀ) | | |
| 6:8-15 | 6:8-15 | 6:8-7:2ሀ | 6:8-15 | 6:8-15 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (ከ "**መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ**" **ገጽ** vii)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ሐተታ)ትርጓሜ ነው፡፡ በመሆኑም መጽሐፍ ቅዱስን በሚመለከት ለምትሰጠው የራስህ አተረጓጐም ኃላፊነት አለብህ፡፡ እያንዳንዳችን መሔድ ያለብን ባለን መረዳት መሠረት ነው፡፡ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ በአተረጓጐም ሒደት ውስጥ ቅድሚያ የሚሰጣችሁ ናችሁ፡፡ ይህን ጉዳዩ ማብራሪያውን ለሚያቀርበው ብቻ መተው የለብንም፡፡

በአንድ ጊዜ ተቀምጠህ ምዕራፍን አንብበው፡፡ የአንተን የርዕስ አከፋፈልና አሁን ከምንጠቀማቸው አምስቱ ትርጓሜዎች ጋር አነፃፅር፡፡ አንድን ምዕራፍ በአንቀፅ መከፋፈል በመንፈስ ቅዱስ ትዕዛዝ የተደረገ አይደለም፡፡ ነገር ግን የመጀመሪያውን ፅሑፍ ዋጋ ሐሳብ መከተል ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ እያንዳንዱ አንቀፅ ሁል ጊዜ አንድ ሐሳብ ይይዛል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀፅ

2. ሁለተኛው አንቀፅ

3. ሶስተኛው አንቀፅ

4. ወ.ዘ.ተ

ሀ. ምዕ 6 እና 7 ወደ አህዛብ የተደረገውን የሚሊዮናዊነት ጉዞ ለመወያየት የሉቃስ ስነ ፅሑፋዊ)ታሪካዊ አጀማመር ነው፡፡

ለ. በዚህ ጊዜ በኢየሩሳሌም የነበረችው ቤተክርስትያን በፍጥነት አድጋ ነበር (6:1)

ሐ. ቤተክርስትያን የተዋቀረችው)የተመሰረተችው በፍሊስጥኤም ከሚገኙ የአራማይክ ቋንቋ ተናጋሪ አይሁዶችና ከተበተኑት አይሁዶች የግሪክን ቋንቋ ከሚናገሩ ነው፡፡

**የቃላትና የሐረግ ጥናት**

**NASB (የተሻሻለው) ትርጉም ምዕ** 6:1-6
**በዚህም ወራት ደቀመዛሙርት እየበዙ ሲሔዱ ከግሪክ አገር መጥተው የነበሩት አይሁድ በይሁዳ ኖረው በነበሩት አይሁድ አንጐራጐሩባቸው በየቀኑ በተሰራው አገልግሎት መበለቶቻቸውን ችላ ይሉባቸው ነበርና፡፡ አስራ**

ሁለቱም ደቀመዛሙርት ሁሉን ጠርተው እንዲህ አሉአቸው፡- የእግዚአብሔርን ቃል ትተን ማዕድን እናገለግል ዘንድ የሚገባ ነገር አይደለም። ወንድሞች ወይ በመልካም የተመሰከረላቸውን መንፈስ ቅዱስና ጥበብም የሞላባቸው ሰባት ሰዎች ከእናንተ ምረጡ ለዚህም ጉዳይ እንሾማቸዋለን እና ግን ለፀሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን። ይህም ቃል ሕዝብን ሁሉ ደስ አሰኛቸው። እምነትና መንፈስ ቅዱስም የሞላበትን ሰው እስጢፋኖስን፣ ፊሊጶስምንም፣ ሮአወስንም፣ ኒቃሮናንም፣ ጢሞናንም፣ አርሜናንም ወደ ይሁድነት ገበቶ የነበረው የአንጾኪያዊውንም ኒቆላውስንም መረጡ። በሐዋርያትም ፊት አቆሟቸው ከፀለዩ በኋላ እጃቸውን ጫኑባቸው

6፡1 "*ደቀመዛሙት*" ይህ በጥሬ ትርጉሙ "*ተማሪ*" ማለት ነው (manthano)።አዲስ ኪዳን እንዲያው ዝም ብሎ ውሳኔ ማድረግን ሳይሆን ትኩረት የሚያደርገው "*ደቀመዝሙር መሆን*" በሚለው ላይ እንደ ሆነ ማስተዋል ይጠቅማል (ማቴ 28፡19) ይህ ለአማኞች የተሰጠ ስያሜ በወንጌላትና በሐዋርያት ስራ ውስጥ መጠቀሱ ልዩ ያደርጋቸዋል። በደብዳቤዎች ደግሞ "ወንድሞች" እና "ቅዱሣን" የተባሉ ቃላት የኢየሱስን ተከታዮች ለመሰየም ተጠቅመዋል።

▣ "**እየበዙ ሲሔዱ**" ይህ እየተካሔደ ያለ ድርጊትን የሚገልፅ ነው። ዕድገት ሁል ጊዜ አለመግባባትን ያመጣል።

▣ "**እንጐራጐሩባቸው**" ይህ ቃል ማለት "ድምፅን ዝቅ አድርጐ ለብቻ ማውራት" (ሞልተን፤ Analztical hexicon ገጽ 81)። በዘፀአት ውስጥ በምድረበዳ የመንከራተትን ጊዜ ለማመልከት ብዙ ጊዜ ተጠቅሷል። (ዘፀ 16፡7፣ 8፣17፡3 እንዲሁም 11፡1፣14፡27)። የተዳፈነ ችግር ወይም አለ መስማማት ነበር። ተመሳሳይ ቃል በሉቃ 5፡30 ላይ እና በዮሐንስ ወንጌል ላይ ብዙ ጊዜ ተጠቅሷል (6፡41፣ 43፣ 61፣ 7፡12፣ 32)

▣ "**ከግሪክ አገር መጥተው የነበሩት አይሁድ በይሁዳ ኖረው በነበሩት አይሁድ**" ይህ የሚያመለክተው ከፍልስጥኤም ምድር የሆኑትና በይበልጥ የአራማይክን ቋንቋ የሚናገሩ አይሁድና በሌሎች ሐገራት ያደጉና በይበልጥ የግሪክ ቋንቋን የሚናገሩ መሆናቸውን ነው። ከባህልና ከዘር የተነሳ በመካከላቸው ውጥረት እንደነበሩ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል።

▣ "**በየቀኑ በተሰራው አገልግሎት**" የቀደመችው ቤተክርስትያን የምኩራብን ስርዓት የተከተለች ነበረች። በየሳምንቱ ድሆችን ለመመገብ ገንዘብ (መባ) ይዋጣ (ይሰበሰብ ነበር። ገንዘቡ ምግብ ለመግዛት የሚጠቅም ነበር ፤ ይህም በምኩራቦች በየሳምንቱ በድሆች ሲሰጥ በቀድሞዋ ቤተክርስትያን ግን በየዕለቱ ይደረግ ነበር። ልዩ ርዕስን ተመልከት ፤ ምፅዋት በምዕ 3፡2 ላይ ወደ ፍልስጤኤም ምድር የሚመለሱት በኋለኛው የአባቶቻቸው የሕይወት ዘመናቸው ነበር። ይህም አባታቸው በተስፋይቱ ምድር መቀበር እንዲችል በማሰብ ነው። ስለዚህም በፍልስጥኤም በተለይም በኢየሩሳሌም አከባቢ ብዙ መበልቶች ነበሩ።

የአይሁድ እምነት በተቋም ደረጃ (የሙሴ ቃል ኪዳን) ለድሆች፣ ለመፃተኞች እና ለመበለቶች እንክብካቤ ያደርግ ነበር (ዘፀ 22፡21-24፣ ዘዳ 10፡18፣ 24፡17)። የሉቃስም ፅሑፍ እንደሚያስረዳው ኢየሱስ ለመበለቶች ግድ እንደሚለው ያሳያል (ሉቃ 7፡11-15፣ 18፡7-8፣ 21፣ 1-4)። በመሆኑም የቀደመችው ቤተክርስትያን ራጰን በምኩራብ ማህበራዊ አገልግሎቶችን በኢየሱስ ትምህርቶች ላይ ምሳሌ በመሆን በቤተክርስትያን ውስጥ ሳሉ መበለቶች ግልፅ የሆነ ትኩረትና እንክብካቤ አድርጋለች።

6፡2 "**አስራ ሁለቱ**" ይህ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ለሐዋርያት የተሰጠ የስብሰባ መጠሪያ)ማህረግ ነው። እነዚህ ከገሊላ ጀምሮ በኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎት አብረውት የነበሩ የመጀመሪያዎች በተለየ ሁኔታ የተጠሩ ነበሩ።

▣ "**ደቀ መዛሙርት ሁሉን ጠርተው**" በትክክል እዚህ ላይ ምን ለማለት እንዲፈለገ ግልፅ አይደለም ምክንያቱም ቤተክርስትያን የተመሰረተችው በብዙ ሺህ በሚቆጠሩ ምዕመናን ነው። በመሆኑም ይህን ያህል ትልቅ ስብሰባ የሚይዝ ምንም አይነት ቤት ሊኖር አይችልም። ይህ ምናልባትም በሰለሞን ደጅ መመላለሻ ላይ የተካሄደ መሆን አለበት (3፡11፣ 5፡12)።

ይህ የመጀመሪያው የተደራጀ ማህበር (ቁ 3፣5፣15፡22) ነው። ይህ የዘመኑ ቤተክርስትያን ከምትኩላቸው ሶስት መፅሐፍ ቅዱሳዊ የቤተክርስትያን አስተዳደር አንዱ ነው፤ (1) ኤጶስቆጶሳዊ (አንድ የበላይ መሪ ያለው) (2) የሽማግሌዎች አመራር (የሽማግሌዎች)የማሪዎች ስብሰብ) እና (3) የብዙሐኑ አመራር (ሁሉም አማኞች) እንዚህ ሁሉም በሐዋ 15 ላይ ይገኛሉ።

▣ "**የእግዚአብሔርን ቃል ትተን ማዕድን እናገለግል ዘንድ የሚገባ ነገር አይደለም**" ይህ አገልገሎትን የሚያንኳስስ አይደለም ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ኃላፊነትን ለመከፋፈል አስፈላጊነቱን ለማሳየት ነው። እነዚህ ቢሮዎች (የአገልግሎት) ሳይሆኑ የውክልና ስራዎች ናቸው። አስፈላጊ ከሆኑ አንዳንድ አገልግሎቶች ይልቅ ወንጌልን ማወጃ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ነው። ሐዋርያት በተለየ ሁኔታ የተጠሩ እና ለዚያም ኃላፊነት ብቃት የነበራቸው ነበሩ። ከዚህ ተግባር ምንም አይነት ነገር ሊወስዳቸው አይገባም። ይህ አማራጭ ያለው ሁኔታ ሳይሆን የግድ መሆን የነበረበት ነው።

▣ "**ማገልገል**" የሚለው ቃል የግሪኩ ቃል ለማገልገል ከሚጠቀመው "diakonia" ከሚለው የመጣ ነው። እንዳለመታደል ሆኖ ብዙዎች ኮሚንታተሮች በኋላ የተነሳውን የድቁና ቢሮ (ፊልጵ 1፡1፣ 1ጢሞ 3፡8*10፣ 12-13) ለማስረዳት ሲሉ ይህንን ጥቅስ መጠቀማቸዋ ነው)ተጠቅመዋል። ይሁን እንጂ እነዚህ ዲያቆናት ሳይሆኑ ተራ አገልጋዬች ወይም ሰባኪዎች ናቸው። የራስን ትርጓሜ ወደ መፅሐፍ ቅዱስ የሚያስገባ የዳያቆንነትን ቢሮ በሐዋ 6

ውስጥ ሲያገኝ የሚችለው የቀደመችው ቤተክርስትያን ያለምንም ሕንፃ አገልግሎቱን ማካሄድ መቻሏ ለእኔ በጣም አስደሳች ነገር ነው፡፡

1. ሁሉም ሲገናኙ በቤተ መቅደስ ውስጥ መሆን አለበት
2. በሰንበት ቀናት በምኩራቦች ሲገናኝ እሁድ እሁድ ግን በቤት ውስጥ ባሉ ቤተክርስትያናት ይገናኛሉ፡፡
3. በሳምንቱ (በየዕለቱ) ሐዋርያት ከአንዱ አማኝ ቤት ወደ ሌላው ቤተ ይሔዳሉ (2፡46)፡፡

6፡3

| | |
|---|---|
| NASB,NRSB | **"ምረጡ"** |
| NKJV | **"ፈልጉ"** |
| JEV | **"ምረጡ"** |
| NJB | **"መምረጥ አለባችሁ"** |

ይህ ትዕዛዝ አዘል ሃሳብ አለው፡፡ አንድነትን ለመጠበቅ የሆነ ነገር መሠረት አለበት፡፡ ይህ ትንሽ ነገር አጠቃላይ የወንጌል መልዕክት ላይ ተጽዕኖ ሊያመጣ ይችላል፡፡

▣ **"ሰባት ሰዎች"** ለዚህ ቁጥር መጠቀስ በቂ ምክንያት የለም የፍፁምነትን መገለጫ መሆኑንና የፍጥረት ስራ በሰባት ቀናት ውስጥ መጠናቀቁን ከማመልከቱ ውጪ (ዘፍ 104)፡፡ በብሉይ ኪዳን መሪነት በማዘጋጀት ሒደት ውስጥ ምሳሌነትን ለማሳየት መገለፁን ያሳያል (ዘሕል 18)፡፡

6፡3

| | |
|---|---|
| NASB, NJB | **"በመልካም የተመሰከረላቸውን"** |
| NKJ | **"መልካም ምስክርነት"** |
| NRSV | **"መልካም አቋም ያላቸው"** |
| TEV | **"የሚታወቁ ሰዎች"** |

በእነዚህ የእግግሊዘኛ ትርጉሞች መካከል ያለው ልዩነት የዚህን ቃል ሁለት የተለያዩ አጠቃቀሞችን ያሳያል፡፡

1. "የተመሰከረላቸውን" ወይም ስለ አንድ ሰው) ነገር መረጃ መስጠት (TEV፣ NIV)
2. "ስለ አንድ ሰው መልካም መናገር" (ሉቃ 4፡22)

▣ **"መንፈስ ቅዱስ የሞላባቸው"** በመንፈስ መሞላት በሐዋርያት ስራ ውስጥ ብዙ ጊዜ ተጠቅሷል በተለምዶ ከአስራ ሁለቱ ጋር እና ከትምህርታቸው ወይም ከስብከታቸው ጋር በተያያዘ ተጠቅሷል፡፡ ለአገልገሎት የሚያስፈልገውን ኃይል ያመለክታል፡፡ በአንድ ሰው የመንፈስ ቅዱስ መኖር ተለይቶ ሊታወቅ የሚችል ነው፡፡ በአማለካከት፣ በድርጊት እንዲሁም በውጤታማነት አንፃር ማረጋገጫ አለ፡፡ ቤተክርስትያን የመረጠቻቸው ሰዎች በዚህ አገልገሎት ላይ እያገለገሉ እንደሆነ የተገለፀ ነገር የለም ነገር ግን ወንጌልን የሚሰብኩ ሰዎች ናቸው፡፡ መበለቶች መዳት አስፈላጊ ነገር ነው ነገር ግን ወንጌልን መስበክ ቅድምያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው (ቁ 4)፡፡ "በመሞላት" ላይ ሙሉውን ማብራሪያ በምዕ 2፡4 ላይ እና ምዕ 3፡10 ላይ ተመልከት፡፡

▣ **"እና ጥበብ የሞላባቸውን"** ሁለት የጥበብ አይነቶች አሉ

1. እውቀትን መጨበጥ
2. የጥበብ አኗኗር

እነዚህ ሰባት ሰዎች ሁለቱም ነበራቸው፣

▣ **"ለዚህም ጉዳይ እንሾማቸዋለን"** ተግባር ተኮር ኃላፊነት ነበረባቸው፡፡ ይህ ምንባብ ዲያቆናት በቤተክርስትያን ያሉትን ንግድ ነክ ጉዳዮችን መከታተል አለባቸው ማለት <u>አይደለም</u> (KJV: "this business' ስለሚል ነው) 'task' (Chraoma) የሚለው ቃል "ፍላጐት" የሚለውን ያሳያል እንጂ "ቢሮን" አያመለክትም፡፡ (አልፍሬድ ማርሻል ፣ RSV)nterlinear ገጽ 468

6፡4 **"እንተጋለን"** ይህ የግሪክ ቃለ በተለያዩ ትርጓሜዎች ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

1. ከአንድ ሰው ጋር በቅርቦት ኃብረት ማድረግ ሐዋ 8፡13
2. አንድን ሰው በግል ማገልገል ሐዋ 10፡7
3. ለአንድ ነገር ወይ ሰው በፅናት መስጠት
   ሀ. የመጀመያዎቹ ደቀመዛሙርት አንዳቸው ለሌላውና ለፀሎት ሐዋ 1፡14
   ለ. የቀድሞዎች ደቀመዛሙርት ለሐዋርያት ትምህርት ሐዋ 2፡42
   ሐ. የቀድሞዎቹ ደቀመዛሙርት አንዳቸው ለሌላው ሐዋ 2፡46
   መ. ሐዋርያት ለፀሎትና ለቃሉ አገልግሎት ሐዋ 6፡4 (ጳውሎስ አማኞች በፀሎት ፅኑ እንዲሆኑ ጥሪ ሲያደርግ ተመሳሳይ ቃል ይጠቀማል ሮሜ 12፡12፣ ቆላ 4፡2

▣ **"ለፀሎትና ቃሉን ለማገልገል"** ይህ ሐረግ በግሪክ ዓረፍተ ነገር ቅድሚያ ወይም ትኩረት መስጠቱን ለማሳወቅ ከፊት ተቀምጧል፡፡ ሐዋርያት ሳይሆኑ እነዚህ "ሰባቱ" ሰዎች የአለም አቀፍ የወንጌል ተልዕኮን ራዕይ ለመቀበል የመጀመሪያዎቹ መሆናቸው ግራ የሚያጋባና የሚያነጋግር ነው፡፡ የእነዚህ "ሰባቱ" ስብከት ነው በአይሁድ ኃይማኖት ላይ ተፅዕኖ ያመጣው እንጂ ሐዋርያት አይደሉም፡፡

6፡5 **"እስጢፋኖስ"** የሰው ትርጉም "የድል ነሺ አክሊል" ማለት ነው ሁም "ሰባቱ" የግሪክ ስም ነበራቸው ነግር ግን አብዛኛዎቹ በስደት ያሉ አይሁዶች የእብራይስጥና የግሪክ ስሞች አሏቸው፡፡ ስሞቻቸው ብቻ ሁሉም የግሪክ ቋንቋ ተናጋሪ አይሁዶች መሆናቸውን አያሳዩም፡፡ አመክና ግን የሚለው ምናልባት ሁለቱ ቡደኖች ነበሩ የሚል ነው፡፡

▣ **"እምነት የሞላባቸው"** እምነት የሚለው ቃል የመጣው ከብሉይ ኪዳን ቃል ነው ( ማለትም ( ቃሉ ከመነሻው የሚያመለክተው አገሮቹ ፀንተው የቆመ ሰውን ለማመልከት ነው፡፡ በተምሳሌትነት አንድ ሰው ሊታመን የሚችል፣ ታማኝ፣ ሊደገፊበት የሚችሉት እና እውነተኛ መሆኑን ለመግለፅ ጥቅም ላይ መዋል ጀመረ፡፡ በአዲስ ኪዳን ይህ ቃል እግዚአብሔር በክርስቶስ ስለሰጠው ተስፋ አንዱ አማኝ የሚሰጠውን ተስፋ ያሳያሉ፡፡ ታማኝነቱን እናምናለን አደራ ጠባቂነቱን እናምናለን፡፡ እሰጢፋኖስ የእግዚአብሔርን እውነተኝነት አመነ ፤ ስለዚህ እርሱም በእግዚአብሔር ባሕርይ ተለያዩ ታወቀ (ሙሉ እምነት፣ ታማኝነት)

▣ **"መንፈስ ቅዱስ ….. የሞላባቸው"** የመፈስ ቅዱስን አገልግሎት የሚገለፁ ብዙ የተለያዩ ሐረጐች አሉ፡፡

1. የመንፈስ ቅዱስ ማባበል (ዮሐ 6፡44፡65)
2. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት (1ቆሮ 12፡13)
3. የመንፈስ ፍሬ (ገላ 5፡22-23)
4. የመንፈስ ስጦታዎች (1ቆሮ 12)
5. የመንፈስ ቅዱስ መሞላት (ኤፌ 5፡18)

በመንፈስ መሞላት ሁለት ነገሮችን ያሳያል (1) ግለሰቡ መዳኑን (ሮሜ 8፡9) (2) ግለሰቡ በመንፈስ መመራቱን (ሬሜ 8፡14)፡፡ የአንድ ሰው "ሙላት" አንድ ሰው በየዕለቱ ከመሞላቱ ጋት የተያያዘ ነው (የማያቋርጥ ሒደትን በትዕዛዝ መግለፅ ኤፌ 5፡18)፡፡

▣ **"ፊሊጶስ"** በአዲስ ኪዳን ብዙ ፊሊጶሶች አሉ፡፡ ይህኛው ከሰባቱ አንዱ ነው፡፡ የሰው ትርጉም "ፈረሶችን የሚወድ" ማለት ነው፡፡ አገልግሎቱም በሐዋርያ ውስጥ ተነግbል በሰማርያ ለተነሳው ሪቫይባል በመሳሪያነት ያገለገለን ከኢትዮጳያ ለመጣው ጃንደረባ ወንጌልን መስክ bል፡፡ በሐዋ 21፡8 ላይ "ወንጌላዊው" ተብሎ ተጠርቷል፤ እንዲሁም ሴቶች ልጆቿ በአገልግሎት የሚሳተፍ ነበር (ነቢያቶች ሐዋ 21፡9)፡፡

▣ **"ጴሮክሮስ"** ስለዚህ ሰው የሚታወቀው ትንሽ ነው፡፡ በ(International Standard Bible Encyclopedia ቁ 4 ጀምስ ኦር) ሲናገር የኒቆሚዲያ ጳጳስ እንደሆነና በአንፃኪያ ሰማዕት እንደሆነ ያሳያል፡፡

▣ **"ኒቃሮናን"** በቤተክርስትያን ታሪክ ስለዚህ ሰው የሚታወቀ ነገር የለም፡፡ ስሙ የግሪክ ሲሆን ትርጓሜውም "ድል ነሺ" (የተከበረ) ማለት ነው፡፡

▣ **"ጢሞናን"** በቤተክርስትያን ታሪክ ስለዚህ ሰው የሚታወቅ ነገር የለም ስሙ የግሪክ ሲሆን ትርጓሜውም "የተከበረ" ማለት ነው፡፡

▣ **"ጰርሜናን"** ይህ ጰርሜናይደስ የሚለው ቃል በማሳጠር ሲጠራ ነው፡፡ የቤተክርስትያን ታሪክ (ትውፊት) የሚለው ትራጃን ንጉስ በነበረበት ጊዜ በፊሊጶስዮስ ሰማዕት ሆኗል ይላል፡፡ (*The international Standard Bible Encyclopedia* ቁ 4፣ ገጽ 2248)፡፡

▣ **"ወደ ይሁዳነት ገብቶ የነበረው የአንጾኪያው ኒቆላዎስ"** ስለዚህ ሰው የበለጠ መረዳ ሊሰጥ ይችል ነበር ምክንያቱም የሚኖርበት ከተማ የሉቃስ መኖሪያ ሊሆን ይችላል፡፡ ወደ ይሁዲነት የሚገባ ሰው ሶስት ስርዓቶችን መፈፀም ይኖርበታል (1) ግለሰቡ በምሥክሮች ፊት ማጥመቅ (ራስን) አለበት (2) ወንድ ከሆነ መገረዝ አለት (3) እድል ካገኘ በቤተመቅደስ መስዋት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ይህን ሰው በሚመለከት በቤተክርስትያን ታሪክ ውስጥ የተወሰነ ግራ መጋባት አለ ምክንያቱም ተመሳሳይ ስያሜ ያለው ቡድን በራዕ 2፡14-15 ላይ መኖሩ ነው፡፡ አንዳንድ የቀድሞ ቤተክርስትያን አባቶች (ኢራንየስና ሂፖሊተስ) የስህተት ትምህርት ቡድን መስራች እንደሆነ ያስባሉ፡፡ አብዛኛዎቹ የቤተክርስትያን አባቶች ግንኙነት እንዳለ የሚያስቡት ቡድን ስሙን በመጠቀም መስራች በኢየሩሳሌም ቤተክርስትያን መሪ እንደነበር ለማሳየት ተጠቅመዋል ይላሉ፡፡

6፡6 **"እጃቸውን ጫኑባቸው"** የሰዋሰው ስርዓቱ የማያመለክተው መላው ቤ)ክ እጆቻቸውን እንደጫኑባቸው ነው፡፡ (13፡1-3) ምንም እንኳ ተውላጠ ሰውን የሚያመለክተው ግልፅ ባይሆንም፡፡

የሮማ ካቶሊካዊት ቤተክርስትያን የሐዋርያትን ቀጣይነትን ለመደገፍ እንዲህ አይነት ፅሑፎችን ትጠቀማለች፡፡ በመጥምቃዊያን ሕይወት እንዲህ አይነት ፅሑፎችን ለአገልገሎት ሹመት እንጠቀማለን (ሰዎችን ለተለየ አገልግሎት ለመስጠት)፡፡ ሁሉም አማኞች የተጠሩና ስጦታን የተቀበሉ መሆናቸው እውነት ከሆነ (ኤፊ 4፡11-12) በአዲስ ኪዳን በተጠሩና ባልተጠሩ መካከል ልዩነት የለም ማለት ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተደገፊ የቤተክርስትያን ትውፊቶች አማካኝነት ቁንጮ ወይም የበላይ የመሆን አካሄድ በአዲስ ኪዳን ቅዱሳት መፅሐፍት አማካኝነት እንደገና መመርመርና መታየት አለባቸው፡፡ እጆችን መጫን ተግባርን ሊያመለክት ይችላል ነገር ግን የተለየ ማንነትን ወይም ስልጣንን አያመለክትም፡፡ አብዛኞዎቹ የዲናሚኔሽናል ልማዶቻችን በታሪክና በልማድ ላይ እንጂ ግልፅ በሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ወይም ትዕዛዝ ላይ አይደለም፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስን ስልጣን እስካልተጋፋ ድረስ ልማድ ችግር ሊሆን አይችልም፡፡

ልዩ ርዕስ፡ እጆቹን መጫን በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ

ይህ የሰውነት እንቅስቃሴ በመጽሐፍ ቅድስ ውስጥ በተለያዩ መንገዶች ጥቅም ላይ ውሏል፡፡
1. የቤተሰብ መሪነትን ለማስተላለፍ (ዘፍ 48፡18)
2. መስዋዕት ለመሆን የሚሞት እንዳለን እንደምትክ ለማሳየት
ሀ. ካህናት (ዘፀ 29፡10፣ 15፣ 19 ዘሌ 16፡2፣ ዘሕ 8፡12)
ለ. ተራ ሰዎች (ዘሌ 14፡31፡4፣ 3፡2፣8፣4፣25፣24 2ዜና 29፡23)
3. እግዚአብሔርን እንዲያገለግሉ ሰዎችን ለመለየት
)ዘሕል 8፡10፣ 27፡18፣ 23፣ ዘዳ 34፡9 ሐዋ 6፡6፣ 13፡3 1ጢሞ 4፡14 5፡22፣ 2ጢሞ 1፡6)
4. አንድን የተፈረበደትን ኃጢአተኛ በድንጋይ ለመውገር ተሳትፎ ሊደረግ (ዘሌ 24፡14)
5. ለጤንነት፣ ለደስታ እና ለቅድስና በረከትን መቀበል (ዘሌ 24፡14)
6. ከአካላዊ ፈውስ ጋር በተገናኘ (ማቴ 9፡18፣ ማር 5፡23፣6፡5 7፡32፣ 8፡23፣ 16፡18፣ ሉቃ 4፡40፣ 13፡13፣ ሐዋ 9፡17፣ 28፡8
7. መንስ ቅዱስን ለመቀበል (ሐዋ 8፡17-19፣ 9፡17፣ 19፡6)

የቤተክርስትያን መሪዎችን ሹመት በሚመለከት ለመደገፍ የምንጠቀማቸው የመፅሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ውስጥ ለማመን የሚያስቸግር ወጥነት የሌለው ሁኔት ይስተዋላል፡፡
1. በሐዋ 6፡6 በቤተክርስትያን ውስጥ ላለው አገልግሎት ሰባቱ ሲሾሙ እጅ የጫኑት ሐዋርያት ናቸው፡፡
2. በሐዋ 13፡13 በርናባስንና ጳውሎስን ለሚሲዮናዊነት አገልግሎት ሲላኩ እጅ የጫኑት ነብያትና አስተማሪዎች ነበሩ፡፡
3. በ1ጢሞ 4፡14 በጢሞቲዎስ የመጀመሪያ የአገልግሎት ጥሪና ሹመት የተሳተፊት የአጥቢያ ቤ)ከ ሽማግሌዎች ነበር፡፡
4. በ2ጢሞ 1፡6 በጢሞቲዎስ ላይ እጁን የጫነው ጳውሎስ ነበር፡፡

ይህ ልዩነት እና ግራ መጋባት የሚያመለክተው በቀደመችው ቤተክርስትያን ውስጥ የአደረጃደት ችግር እንደነበር ያሳያል፡፡ የቀደመችው ቤተክርስትያን ኃይለኛና በአማኞች ውስጥ ያለውን መንፈሳዊ ስጦታዎች ሁል ጊዜ የምትጠቀም ነበረች (1ቆሮ 14) አዲስ ኪዳን የተፃፈው እንዲሁ ዝም ብሎ ለአንግስታዊ ሞዴል ወይም የሹመት ሒደት ጥብቅና ለመቆም አይደለም፡፡

6፡7 **"የእግዚአብሔር ቃል"** ይህ የሚያመለክተው የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ነው፡፡ ሕይወቱ፣ ሞቱ፣ ትንሳኤው እና ስለ እግዚአብሔር ያስተማረው ብሉይ ኪዳንና በአዲስ መንገድ ለማየት ያስቻለ ነው፡፡ (ማቴ 5፡17-48) ቃሉ ኢየሱስ ነው (ዮሐ 1፡1፣ 14፡6)፡፡ ክርስትና ስብእና ነው፤

▣ **"እየሰፋ ሄደ"** በቁ 7 ላይ ያሉት ሶስቱም ግሶች ያላለቁ በሂደት ላይ ያሉ ድርጊቶችን ያመለክታሉ፡፡ ይህ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ማዕከላዊው ሐሳብ)ጭብጥ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል እየተስፋፋ ያለው ክርስቶስን ማመኑ አዲስ የቃል ኪዳን ሕዝቦች እና የአዲስ የእግዚአብሔር ሕዝብ ክፍል በሆኑት ነው (6፡7፣ 12፡24፣ 19፡22) ይህ ለአብርሃም የቤተሰቡ ቁጥር መጨመርን በሚመለከት እግዚአብሔር ከሰጠው ተስፋ ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ ይህም ቤተሰብ የብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ ሊሆን የቻለ ነው (17፡17፣ ዘፍ 17፡4-8፣ 18፡18፣ 29፡3፣ 35፡11)፡፡

▣ **"ከካህናትም ብዙ ሰዎች ለሐይማኖት የታዘዙ ሆኑ"** ይህ ከክርስትና የተነሳ ለአይሁድ የሐይማኖት አመራር ስጋት ሊሆን የቻለ ነበር (ማለትም ሰዱቃዊያን) ቀደም ሲል ብሉይ ኪዳን የሚያውቁት የናዝሬቱ ኢየሱስ በእውነት ተስፋ (የሚጠበቀው) መሲህ እንደሆነ ሊያምኑ ቻሉ፡፡ ውስጠኛው የአይሁድ ኃይማኖት መሰንጠቅ እየመጣበት ነበር ፤ ስለቤተክርስትያን ዕድገት የተሰጡት ማጠቃለያ ዓረፍተ ነገሮች ለመፅሐፍ ቅርፅ ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው፡፡ (9፡31፣ 12፡24፣ 16፡5፣ 19፡20፣ 28፡31)፡፡

▣ **"ለሐይማኖት"** ይህ ቃል የተወሰኑ ለየት ያሉ ማሳሰቢያዎች አሉት፤
1. የብሉይ ኪዳን የኂላ ታሪኩ የሚለው ፡- "ታማኝነት"፣ "እውነተኛነት" ማለት ነው፡፡ ስለዚህ የእግዚአብሔርን ታማኝነት ማመን ወይም የእግዚአብሔርን እውነተኛነት ማመን ማለት ነው፡፡
2. በክርስቶስ ያለውን የእግዚአብሔርን ነፃ ምረጫ መቀበላችንን
3. ታማኝና እግዚአብሔርን የመምሰል ኑሮ
4. ስለ ክርስትያን እምነት አጠቃላይ የሆነ ትርጉም ወይም ስለኢየሱስ የአስተምህሮ እውነታ (ሮሜ 1፡5 ገላ 1፡23 ይሁዳ 3 እሃ 20) በተወሰኑ ምንባቦች ለምሳሌ በ2ተሰ 3፡2 ጳውሎስ የትኛው ትርጓሜ በአእምሮው ለማወቅ ያስቸግራል፡፡

NASB (የተሻሻለው) ትርጉም ምዕ 6፡8-15

**እስጢፋኖስም ድጋንና ኃይልን ተሞልቶ በሕዝቡ መካከል ድንቅንና ተአምራትን ታላቅ ድንቅን ያደርግ ነበር፡፡ የነፃ አውጪዎች ከተባለችው ምኩራብም ከቀሬና ከእስክንድርያም ሰዎች ከኪልቅያና ከእስያም ከነበሩት አንዳንዶቹ**

ተነስተው እስጢፋኖስን ይከራከሩት ነበር። ይናገርበት የነበረውንም ጥበብና መንፈስ ይቃወሙ ዘንድ አልቻሉም። በዚያን ጊዜ በሙሴ ላይ በእግዚአብሔርም ላይ የስድብን ነገር ሲናገር ሰምተነዋል የሚሉ ሰዎችን አስነሱ። ሕዝቡንና ሽማግሌዎችንም ፃፎችንም አናደዱ ቀርበውም ያዙት ወደ ሸንጉም አወጡትና ይህ ሰው በዚህ በተቀደሰው ስፍራ በሕግም ላይ የስድብን ነገር ለመናገር አይተውም ፤ ይህ የናዝሬቱ ኢየሱስ ይህን ስፍራ ያፈርሰዋል ፤ ሙሴም ያስተላለፈልንን ስርዓት ይለውጣል ሲል ሰምተነዋልና የሚሉ የሐሰት ምስክሮችን አቆሙ። በሸንጉም የተቀመጡት ሁሉ ትኩር ብለው ሲመለከቱት እንደመልአክ ፊት ሆኖ ፊቱን አዩት።

6፡8 **"ፀጋንና ኃይልን ተሞልቶ"** "ፀጋን ተሞልቶ" የሚያሳየው በሕይወቱና በአገልግሎቱ የእግዚአብሔርን በረከት ነው። ይህ "ኃይል" የተባለው ቃል የሚያመለክተው)የሚገናኘው ከሚቀጥለው ሐረግ ነው፡- "ድንቅንና ታላቅ ምልክትን ያደርግ ነበር" ከሚለው ነው።

▣ **"ድንቅንና ታላቅ ምልክትን ያደርግ ነበር"** ይህ ያላለቀ ጊዜ አመልካች ነው (እንደ ቁ 7) ይህ ምናልባት የተከሰተው ከሰባቱ አንዱ ለማገልገል ከመሾሙ በፊት ነው። የእስጢፋኖስ የወንጌል መልዕክት በማያቋርጥ ሁኔታ የሚታጀበው በፀጋ ሙላትና በኃይል (ምልክትና ድንቆች) ነበር።
6፡9 **"አንዳንድ ሰዎች ከ .... አንዳንዶች ከ"** ስንት ቡድኖች በእስጢፋኖስ ላይ እንደተነሱ የተሰጠው አተረጓጉም ላይ ጥያቄ ያስነሳል።

1. አንድ ምኩራብ (ከሁሉም አገሮች የሆኑ ሰዎች ተዘርዝረዋል)
2. ሁለት ሙኩራቦች
3. ከቀሬናና ከአሌክሳንደሪያ የሆኑ አይሁዶች
4. ከሰልሰያ እና ከእስያ የመጡ አይሁዶች (ጳውሎስ ከሰደስያ ነበር)
5. አንድ ምኩራብ ግን ሁለት ቡድኖች
6. አምስት የተለያዩ ምኩራቦች

የግሪኩ የብዙ የወንድ ጾታ መስተአምር (ሁለት ጊዜ ተደግሟል።

▣ **"ከተባለችው"** የዚህ ሐረግ ምክንያቱ "ነፃ አውጪዎች" የሚለው ቃል የላቲን ቃለ ስለሆነ ነው። ስለዚህ ግልፅ ለማድረግ መተርጎም ነበረበት። እነዚህ እንደባሪያ ወደ ሌላ አገር የተወሰዱ አይሁዶች መሆናቸው ግልፅ ነው። ነገር ግን ወደ ፍልስጥኤም የወጡት እንደ ነፃ አውጪዎች ሆነው ነው ነገር ግን አሁንም ግሪክ የመጀመሪያ ቋንቋቸው ነው።

6፡10 የእስጢፋኖስ የወንጌል መልዕክት የተረጋገጠው በምልክት ብቻ አይደለም ነገር ግን በግልፅ አሳማኝ በመሆኑ ጭምር እንጂ። ምዕ 7 የስብከቱ ምሳሌ ነው።

▣ **"መንፈስ"** በግሪክ መፅሐፍ የመጀመሪያ ፊደሎች ካፒታል መሆን አለመሆናቸውን የሚለዩበት መንገድ የለም ፤ ይህ የተርጓሚዎች ተግባር ነው። "S" ካፒታል ሲሆን የሚያመለክተውም መንፈስ ቅዱስን ነው ፤ ትንሹ "s" ለሰው መንፈስ ነው (7፡59፣17፡16፣ 18፡25 ሮሜ 1፡9፣ 8፡16 1ቆሮ 2፡11፣ 5፡4፣ 16፡18 2ቆሮ 2፡13፣12፡18 ገላ 6፡18፣ ፊል 4፡23) ይህ ምናልባት ከምሳ 20፡27 ጋር ይመሳሰላል።

6፡11 **"የሚሉ ሰዎችን አስነሱ"** የሚለው ቃል (1) በሚስጢር ለማድረግ ጉቦ መስጠት (louw and Nida: Lexiconl vol 1. PP 577-578) (2) በሚስጢር ማቀነባበር (Baur, Arndt, Ginzrich, and Danker A Greck English lexieon Vol PP 843)። ይህ በኢየሱስ ላይም የተጠቀሙት ተመሳሳይ ዘዴ ነው (ማቴ 26-61)፣ በጳውሎስ ላይም (ሐዋ 21፡28)። ክሳቸው የሞት ቅጣት የሚያስከትለው ዘፀ 20፡7 ትዕዛዝ የሚጥስ ነው።

6፡12 **"ሕዝቡ ሽማግሌዎችን ፀሐፊዎች"** "ሽማግሌዎችና ፀሐፊዎች" የሚለው ሐረግ ብዙውን ጊዜ ሸንጐ ለሚለው ቃል የሚሰጥ አጭር መጠሪያ ነው። በዚህ አገባብ ሸንጐ ተብሎ ይጣራል። ይህ በሮማዊያን ጊዜ የአይሁድ የኃይማኖት የስልጣን አካል ነበር (ከ70 ዓ.ም. በፊት) የተዋቀረውም (1) ከሊቀካህኑና ከቤተሰቡ (2) ሐብታም የመሬት ባለቤቶችና የሲቪል መሪዎች (3) ከታች ያሉ ፀሐፊዎች። ባጠቃላይ ከኢየሩሳሌም ጋር ሰዎችን ይይዛል። ልዩ ርዕስ በሚለው ሸንጐ የሚለውን ይመርጣል፡

6፡13 **"ይህ ሰው"** ይህ በሴሜቲክ ንቀትን ለማሳየት ነው። ሐረጉ ብዙ ጊዜ ለኢየሱስ የዋለ ነው።

▣ **"በተቀደሰው ስፍራ በሕግም ላይ ይናገራል"** ይህ ሐረግ በቁ 11 ላይ ለቀረበው ክስ ቀጣዩ ነው። ይህ ምናልባት የሚያመለክተው ኢየሱስ በሉቃ 19፡44-48 ላይ ስለተጠቀሰው መቅደስ የተናገራቸውን ቃላት ለማረጋገጥ ይመስላል። ምናልባት ማቴ 26፡61፣ ማር 14፡58፣ 15፡29 ዮሐ 2፡1 (ቁ 14) ኢየሱስ ራሱን ያየው እንደ "አዲሱ መቅደስ" አዲሱ የአምልኮ ማዕከል፣ አዲሱ እግዚአብሔርና ሰው የሚገናኙበት ቦታ (ማር 8፡31፣ 9፡31፣ 10፡34)።

"በሕግም ላይ ይናገራል" ለተባለው ምክንያቱ ስለኢየሱስ ሙሉ ምህረትና ነፃ ይቅርታ ማድረግ መስበኩ ነው።

ለመጀመሪያው ክፍለ ዘመን አይሁዶች ይህ አስተምህሮች ፍፁም ስድብ ነው። ይህ በእርግጥ በአንድ አምላክ ማመን፣ ደህንነት፣ እና የእስራኤል ልዩ ስፍራ ለየት አድርጐ ከሚያምነው ብ)ኪ. እንግዳ ነገር ነው።

**6፡14** በእርግጥ ክሳቸው ትክክል ነበሩ፤ እነዚህ ሁለቱ ክሶች የተቀነባበሩት ሰዱቃዊያንን ለማነሳሳት ነበር ("ይህን ስፍራ ያፈርሰዋል") እንዲሁም ፈሪሳዊያንንም ጭምር (ሙሴ ያስተላለፈልንን ስርዓት ይለውጣል)፡፡

**6፡15 "ትኩር ብለው ሲመለከቱት"** ይህ ሉቃስ የተጠቀመው ስነ ፅሑፋዊ ዘይቤ ነው፡፡ ያልተቋረጡ ትኩረትን ያሳያል (ሉቃ 4፡20፣22፡56፣ ሐዋ 1፡10፣ 3፡4፣ 12፣ 6፡15፣ 7፡55፣ 10፡4፣ 11፡6፣ 13፡9፣ 14፡9፣ 23፡1)፡፡

▣ **"እንደመልአክ ፊት ሆኖ አዩት"** ይህ ምናልባት ተመሳሳይነት ያለው (1) ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ከተገናኘ በኂላ ፊቱ አንፀባረቀ (ዘፀ 34፡29-35፣ 2ቆሮ 3፡7) (2) ኢየሱስ ፊቱና አካሉ በተራራው ላይ እንደተለወጠው (ማቴ 17፡2፣ ሉቃ 9፡29 ወይም (3) ለዳንኤል መልዕክት ያመጣው መልአክ (10፡5-6) ይህ አንድ ሰው በእግዚአብሔር ሕልውና ውስጥ እንደ ነበር ለማሳየት የሚጠቅም ተምሳሌታዊ አነጋገር ነው፡፡

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት _መመሪያ_ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ለመርዳት ነው የተሰናዱት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋነኞቹን ጉዳዮች ለማጤን እንዲረዳ ነው፡፡ ሐሳብ ለማጫር እንጂ መደምደሚያ አይደሉም፡፡

1. ማዕድን ያገለግሉ ዘንድ ለምንድን ነው? የቀደመችው ቤ/ክን በመንፈሳዊ ነገር የበሰሉትን የመረጠችው?
2. እየሆነ ባለው እድገት ለምንድን ነው የተጨነቁት?
3. እጅን የመጫን ዓላማው ምንድን ነው?
4. እስጢፋኖስ የተገደለው?

# የሐዋርያት ሥራ 7

## የተሻሻሉ የመፅሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀፅ አከፋፈል

| የተየመቅሰ[4] | አኪጆት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የእሰጢፋኖስ ንግግር | የእሰጢፋኖስ ንግግር የአብርሃም መጠራት | የእስጢፋኖስ ብስከትና ሰማዕትነት | የእስጢፋኖስ ንግግር | የእስጢፋኖስ ንግግር |
| | | (6፡8፣ 8-10) | | |
| 7፡1-8 | 7፡1-8 | | 7፡1 | 7፡1-8 |
| | አባቶች በግብፅ | 7፡2ለ-8 | 7፡2-8 | |
| 7፡9-16 | 7፡9-16 | 7፡9-16 | 7፡9-16 | 7፡9-16 |
| 7፡17-22 | 7፡17-36 | 7፡17-22 | 7፡17-22 | 7፡17-22 |
| 7፡23-29 | | 7፡23-29 | 7፡23-29 | 7፡23-29 |
| 7፡30-43 | | 7፡30-34 | 7፡30-34 | 7፡30-34 |
| | በእግዚአብሔር ላይ አመፁ | 7፡35-43 | 7፡35-38 | 7፡35-43 |
| | 7፡37-43 | | | |
| | እውነተኛው የእግዚ-ሐብሔር ማደሪያ | | | |
| 7፡44-50 | 7፡44-50 | 7፡44-50 | 7፡44-47 | 7፡44-50 |
| | እስራኤል መንፈስ ቅዱስን ተቃወመ | | | |
| 7፡51-53 | 7፡51-53 | 7፡51-53 | 7፡51-53 | 7፡51-53 |
| የእስጢፋኖስ መወገር | የእስጢፋኖስ ሰማዕትነት | | የእስጢፋኖስ መወገር | በጳውሎስ አማካኝነት የእስጢፋኖስ መወገር |
| 7፡54-8-1ሀ | 7፡54-60 | 7፡54-8፡1ሀ | 7፡54-8፡14 | 7፡54-8፡1 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (ከ **"መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ" ገጽ** vii)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

*ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡*

*ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡*

1. *የመጀመሪያው አንቀፅ*

2. ሁለተኛው አንቀፅ

3. ሶስተኛው አንቀፅ

4. ወ.ዘ.ተ

**የአገባብ/ውዳዊ መረዳቶች**

ሀ. በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ረጅም ንግግር ተብሎ የእስጢፋኖስ ንግግር ነው፡፡ ጳውሎስ ወንጌል ከብሉይ ኪዳን ጋር ያለውን ትስስር ያለውን ሥነ-መለኮታዊ አቋም ያፈርሰዋል፡፡ በእሱ ላይ ለተመሰረቱ ሁለት ክሶች ምላሽ በመስጠት
1. እግዚአብሔር ከመቅደሱ ውጪ እንደተናገረ
2. እግዚአብሔር ከአሕዛቦች ጋር ይሰራል፡፡
3. አይሁዳዊያን ሁል ጊዜ የእግዚአብሔርን መልዕክት እንደሚቃወሙ አሁንም ደግሞ መሲሁን እየተቃወሙ እንዳሉ

ለ. እስጢፋኖስ የሰጠው ምላሽ የጠርሲሱን ጳውሎስ ልብ እና ሥነ-መለኮት ላይ ተፅዕኖ ማምጣቱ፡፡

ሐ. እስጢፋኖስ የአይሁዳውያን በተደጋጋሚ ቃል ኪዳን የማፍረስ ተግባራቸውንና የእግዚአብሔር ከተስፋይቱ ምድር ውጪ መገለጥ እንዲሁም በኢየሩሳሌም ካላቸው ቤተመቅደስ፡፡ ይህም በአንደኛው ክ/ዘ የነበረው የአይሁድ አምልኮ ያተኮረበት ነበር፡፡

መ. አይሁዶች ሁል ጊዜ እግዚአብሔርን ወክለው የሚናገሩትን እንደተቃወሙ አሁንም ደግመው እንዳደረጉት፡፡ እስጢፋኖስ በድንጋይ እየተወገረ ስለ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሆኖ ያለውንና ያደረጋቸውን ነገሮች በተደጋጋሚ ብዙ ነገሮችን አለ፡፡ ይህ ሆነ ተብሎ በሉቃስ የተደረገ ሥነ-ፅሑፋዊ አቀራረብ ነው ብቻ ይመስላል፤

ሠ. እስጢፋኖስ በአይሁድ እና በእስራኤላዊያን መካከል ያለውን ግንኙነት በሚመለከት ያለው አመለካከት ለስደት ሁኔታን ሲያመቻችና (8፡1-3) ለሁለቱ ቡድኖች ምክንያት ሆኗል፡፡

ረ. እስጢፋኖስ ያደረገው (ንግግር) መከላከል (ስብከት ከዕብራዊያን ብሉይ ኪዳን በተለየ ብዙ ዝርዝሮች አሉት (ከሰብትዋጀንት ነበር የጠቀሰው) የሥነ መለኮት ሊቃውንት የእስጢፋኖስን አባባል መከላከል አለባቸው፣ የአይሁድ ባህሎች አድርገው መቀበል አለባቸው ወይስ እንደታሪካዊ ስህተት ማየት አለባቸው ይህ ጥያቄ የሚያሳየው የተርጓሚዎችን የስሜትና የእውቀት ግራ መጋባት ወይም አቋም አለመያዝን ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛ ታሪክ እንዲሆን ክርስትናም የሚቆመው ወይም የሚወድቀው በመፅሐፍ ቅድስ ባሉት ክስተቶች እንደሆነ አምናለሁ፡፡ ይሁን እንጂ የመፅሐፍ ቅዱስ ጅማሮ (ዘፍ 1፡11) እና የመፅሐፍ ቅዱስ ፍፃሜ (የራዕይ መፅሐፍ) "መሳጭ ታሪኮች" አይደሉም፡፡ ትክክልና እውነተኛ ናቸው እንጂ፡፡ ይህም ሁኔታ አንዳንድ ጊዜ
1. የቁጥር ልዩነት እንዳሉ
2. የስነፅሑፍ ልዩነት
3. የገለፃ ልዩነቶች እንዳሉ
4. ረቢያዊ የአተረጓጎም ቴክኒኮች (ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ትርጉሞችን ማጣመር)

ይህ ሁኔታ ግን ለመፅሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኮች ያለኝን ታሪካዊ አፅንኦት ላይ ለውጥ አያመጡብኝም፡፡ እስጢፋኖስ ምናልባት በምኩራብ ውስጥ የተማሪውን እየዘረዘረ ትርጉሞችን ለራሱ ዓላማ በሚመች ሁኔታ አሻሽሎ አቅርቦ ሊሆን ይችላል ወይም በዝርዝር ነገሮች ግራ ተጋብቶ ሊሆን ይችላል በአንድ ወይም ሁለት ዝርዝሮች ብቻ ትኩረት አድርገን የእስጢፋኖስን መልዕክት መሳት የአሁኑ የዘመናችን የታሪክ ትርጓሜ ብሔል እንጂ የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የታሪክ ትርጓሜ አይደለም፡፡

ሰ. እግዚአብሔር በምዕ 7 ከእስራኤል ጋር ያደረገውን ነገር የሚያሳይ የእስጢፋኖስ ታሪካዊ ምልከታ ዝርዝር
1. አባቶች ቁ. 2-16
2. ከግብፅ መውጣትና የምድረበዳ ጉዞ ቁ 17-43
3. የማደሪያው ድንኳን እና ቤተመቅደሱ ቁ 44-50
4. ማጠቃለያውን የብሉይ ኪዳን በስራ ላይ ማዋል ቁ 51-53

**NASB (የተሻሻለው) ትርጉም ምዕ 7፡1-8**
**ሊቀ ካህናቱም፡- ይህ ነገር እንዲህ ነውን? አለው እርሱም እንዲህ አለ ወንድሞችና አባቶች ሆይ ስሙ የክብር አምላክ ለአባታችን ለአብርሃም በካራን ሳይቀመጥ ገና በሁለት ወንዝ መካከል ሳለ ታየና፡- ከአገርህና ከዘመዶችህም ወጥተህ ወደ ማሳይህ ወደ ማንኛውም ምድር ና አለው በዚያን ጊዜ ከከላዲዊያን አገር ወጥቶ በካራን ተቀመጠ። ከዚያም አባቱ ከሞተ በኋላ እናንተ ዛሬ ወደምትኖሩባት ወደዚች አገር አወጣው። በዚችም የእግር ጫማ እንኳ የሚያክል ርስት አልሰጠውም፤ ነገር ግን ደጅ ሳይኖረው ለእርሱ ከእርሱም በኋላ ለዘሩ ርስት አድርጐ ይሰጠው ዘንድ ተስፋ ሰጠው። እግዚአብሔርም ዘሩ በሌላ አገር መፃተኞች እንዲሆኑ አራት ልዩ አመትም ባሪያዎች እንዲደያደርጉአቸው እንዲያስጨንቋቸውም እንዲሁ ተናገረ ደግሞም እግዚአብሔር እንደባሪያዎች በሚገዙአቸው ሕዝብ ላይ እኔ እፈርድባቸዋለሁ ከዚህም በኋላ ይወጣሉ በዚህም ስፍራ ያመልኩኛል አለ። የመገረዝንም ኪዳን ሰጠው እንዲሁም ይስሐቅን ወለደ በስምንተኛውም ቀን ገረዘው ይሳሐቅም ያዕቆብን ያዕቆብም አስራ ሁለቱን የአባቶችን አለቆች።**

7፡1 **"ሊቀካህናቱም"** ይህ ቀያፋ ነበር በ4፡6 ላይ የተሰጠውን ማስታወሻ ይመገብ አለው።

7፡2 **"እርሱም እንዲህ አለ"** የእስጢፋኖስ መከላከል ከዕብራዊያን መፅሐፍ ጋር በጣም ተመሳሳይነት አለው። ለክሱ ምላሽ የሰጠው በሁለት መንገዶች ነው፤ (1) የአይሁድ ሕዝብ ባለፊት ጊዜያት ሙሴን ባለማቋረጥ ሲቃወሙት ነበር (2) ቤተመቅደሱ እግዚአብሔር እስራኤልን ለማነጋገር ከሚጠቀምባቸው መንገዶች አንዱ ነበር ይህ በምዕ 6፡3 ለቀረበበት ክስ የተሰጠ ቀጥተኛ ምላሽ ነበር።

▣ **"ስሙ"** ጥቅም ላይ የዋለው ዝነኛውን የአይሁድ ፀሎት የሆነውን (*Shema*) ከሰብትዋጀንት ለመተርጐም ነው (ዘዳ 6፡4-5) እንዲሁም በነብያት መፃህፍት "ለማድረግ ስሙ" የሚል ትርጓሜ በያዘ መልኩ ለማስተላለፍ ነው (ሚክ 1፡2፣ 6፡1) እነዚህ አይጆች የአይሁድ አሳቦቻቸውን በግሪክ ቃላት እያስተላለፊ እንዲህ አይነቱ ቴክኒካዊ የቋንቋ አካሄድ አለ ለማለት ያስቸግራል ነገር ግን እንደዚህ ባሉ ፁሑፎች እውነትነት ሊኖረው ይችላል።

▣ **"የክብር አምላክ"** ይህ የክብር አምላክ ለአብርሃም ተገለጠለት (ዘፍ 12፡1፣ 15፡1፣42 17፡1፣ 118፡1፣ 22፡1) በዚያም የአይሁድ ሕዝብ ተጀመረ። በ3፡13 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።

▣ **"ለአብርሃም"** አብርሃም የአይሁዶች አባት ተብሎ ነው የሚታወቀው። የመጀመሪያው አባት ነው። ጥሪውን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገው ጉዞ በዘፍ 12፡1-25-11 ላይ ተጠቅሷል። በሮሜይ ላይ በእምነት ስለመውደቅ እንደ ሐዋርያ ይመለከተዋል።

▣ **"በካራን ሳይቀመጥ ገና በሁለት ወንዝ መካከል ሳለ"** ዘፍ 11፡31 የሚያሳየው እግዚአብሔር አብርሃምን ሲናገረው በካራን ከተማ ነበር። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር የተገናኘበት ትክክለኛው ጊዜ አልተገለፀም። አብርሃም ከዑር ነበር (ዘፍ 11፡28፣ 31) ከዚያም በኋላ ወደ ካራን ተጓዘ (ዘፍ 11፡31፣ 32፣ 29፡4) የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ በመከተል። ዋናው ነጥብ ግን እግዚአብሔር አብርሃምን የተናገረው ከካነዓን ምድር ውጭ ነው። ከተሰፋይቱ ምድር ምንም የያዘው ወይም የራሱ የሆነ ነገር የለም (ቁ 5) በህይወቱ ዘመን ሁሉ (ቤተሰቡን ለመቅበር ከገዛው ዋሻ በስተቀር)። "በሁለት ወንዞች" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የተለያዩ የብሔር ቡድኖችን ወይም (2) በጢግሮስና በኤፍራጥስ ወንዞች ማነሻ ላይ ያሉ ህዝቦችን።

7፡3 **"ከአገርህና ከዘመዶችህም ወጥተህ ወደ ማሳይህ ወደ ማንኛውም ምድር ና አለው"** ይህ ከዘፍ 12፡1 የተወሰደ ነው። እግዚአብሔር ይህን ለአብርሃም ሲናገረው በዚህ ጥቅስ ውስጥ ያለው ሥነ መለኮታዊ ጉዳይ (1) አባቱን ታራንና ሎጥን ወደ ካራን ከመውሰዱ አስቀድሞ በዑር እያለ ነበር (2) በካራን እያለ አባቱ እስኪሞቱ ድረስ እንደጠበቀና የእግዚአብሔርን ጥሪ ተቀብሎ ወደ ከነአን ገባ

7፡4 **"ከከለዳዊያን አገር ወጥቶ"** ይህ ቦታ ምናልባት በጠግሮስና በኤፍራጥስ ወንዞች መውጫ አካባቢ ያለ ቀበሌ ሊሆን ይችላል (በ7፡2 ላይ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ)። ባቢሎን መነሻዋ ከዚህ አካባቢ እንደሆነ ይታመናል። ይህ አገር በምሽት የሚንቀሳቀሱ ከዋክብት እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ የሥነ-ቀመር ሊቃውንት የወጡባት ሥፍራ ናት (ኘላኔቶችን፣ ከዋክብትን፣ ከሜዮችን ወዘተ) እነዚህ የጠቢባን ስብስብ (አስትሮሎጂስዮች) ከለዳዊያን በሚል ስያሜ ይታወቃሉ። (ዳን 2፡2፣ 4፡7፣ 5፡7-11)

▣ **"ካራን"** ካራን ታራ፣ አብርሃምና ሎጥ የተጓዙበት ከተማ ናት (ዘፍ 11፡31-32) ሌሎች የአብርሃም ወንድሞች የሰፈሩበት እንዲሁም የቦታው ስም በአብርሃም የተጠራ ነበር (የናሆር ከተማ ዘፍ 24፡10፣ 27፡43)። ይህች ከተማ በኤፍራጥስ የላይኛው ክፍል የሚገኝ (ባሊክ፣ ገባር ወንዝ)፣ በሶስተኛው ሺህ ዓመት (ከክርስቶስ ልደት በፊት) የተቀረቀረችና እስከ ዛሬ ይህን ስም ይዛ የምትገኝ ናት ነገር ግን የአብርሃም ወንድም ካራ በእብራይስጥ ከተማው እንደሚጠራበት አጠራር አይጠራም።

▣ **"አባቱ ከሞተ በኋላ"** ብዙዎች በዘፍ 11:26፣ 32 እና በዘፍ 12:4 *መካከል ተቃርኖዎችን ያጤናሉ። ለዚህ ቢያንስ ሁለት መፍትሔዎች* አሉ። (1) አብርሃም ምናልባት ትልቁ ልጅ ሳይሆን ምናልባት ተወዳጅ ልጅ ሊሆን ይችላል (2) የሳምራዊያን ፔንታቱክ የታራ *ዕድሜ* 145 እንዲሆን እንጂ እንደዕብራዊያን *መፅሐፍ* 205 አይልም። Gleason L. Archer : Encyclopedia of Bible Diffeculties *ገጽ* 378።

**7:5 "ለእርሲ ከእርሱም በኋላ ለዘሩ ርስት አድርጐ ይሰጠው ዘንድ ተስፋ ሰጠው"** ይህ ዘፍ 12:7 ወይም 17:8ን *የሚያመለክት ነው ሥነ-መለኮታዊ ፍሬ ነገር* የእግዚአብሔር ተስፋ ብቻ አይደለም ነገር ግን አብርሃም እግዚአብሔር ለእርሱ ዘርና ርስት ሊሰጥ እንደሚችል *ማመኑ* ነው። ይህ እምነት በዘፍ 15:6 ላይ ትኩረት ተሰጥቶታል (ሮሜ 4)።

7:6 ይህ የወደፊቱን ለይቶ የሚናገረው ትንቢት በዘፍ 15:13፣ 14 ላይ እንዲሁም ዘፀ 3:12 በድ*ጋሚ ተረጋግጧል*። ይሁን እንጂ ዘፀ 12:40 "400 *ዓመታት*" ከማለት "430 *ዓመታት*" ይላል። ሰብትዋጀንት ዘፀ 12:40ን የሚተረጉመው የእስራሔል ልጆች በግብፅ ምድርና በከነዓን ምድር ያደረጉት ጉዞ 430 *ዓመታት* ናቸው ይላሉ።

ረቢዎች "400 *ዓመታት*" የሚለው ቁጥር የሚጀምረው አብርሃም ይስሐቅን ለመስዋዕትነት ካቀረበ ጀምሮ ነው ይላሉ። ካልቪን 400 ውን *ዓመት ዙሪያ ገብ ቀመር* ይለዋል። ምናልባት 100 *ዓመት* ያላቸው አራት ትውልዶችን ያሳያል (ዘፍ 15:6)።

**7:7 "በሚገዙአቸው ሕዝብ ላይ"** ይህ ከሰብትዋጀንት የተወሰደ ጥቅስ ነው። ዘፍ 15:4 ይህም አጠቃላይ የሆነ ዓረፍተ ነገር ነው። ሕዝብ ግብፅ እንሆነ ለመገመት አያስቸግርም። ይሁን እንጂ ሌሎች ሕዝቦች (ፍልስጥኤም፣ ሶሪያ፣ አሦር፣ ባቢሎን) የእስራኤል መቋኖች ሊሆኑ ይችላሉ፣ እግዚአብሐርም ይፈርድባቸዋል።

▣ **"ከዚህም በኋላ"** ይህ ሙሉው ሐረግ የተወሰደው ከዘፀ 3:12 ነው። እስጢፋኖስ እንዲያው የእስራኤል ታሪክ ላይ ላዩን እየጠቀሰ ነው። ጽሑፍ የሚያረጋግጠው ከነአንና እየሩሳሌም ልዩ በሆነ ሁኔታ የያሕዊህ ለየት ያለ ነው ይህ ሁኔታ በዘዳግም ከተሰጠው ትኩረት ጋር የሚስማማ ነው።

▣ **"በዚህም ስፍራ"** ከዘፀ 3:12 በተወሰደው ጥቅስ አውድ ይህ የሚያመለክተው ከተስፋይቱ ምድር ውጪ ስለሆነው የሲና ተራራ እንደሆነና በእስራኤል ሕይወት ከታዩ ክስተቶች ዋናው እንደሆነ ነው (ሕግ ለወገኔ የተሰጠበት)

**7:8 "ኪዳን"** በ2:47 ላይ በልዩ ርዕስ የተሰጠውን ማራርያ ይመልከቱ

▣ **"መገረዝ"** ይህ ከፍልስጥኤማዊያን በስተቀር የእስራኤል ጐረቤት በሆነ ሌሎች አገሮች ሁሉ በስራ ላይ የዋለ ነበር (የግሪክ ኤጅያን ሕዝቦች) ለብዙዎቹ ባሕሎች አንድ ሰው ወደ ጐልማሳነት ሕይወት የሚሸጋገርበት ልምምድ ነው ነገር ግን ለእስራኤል አይደለም ፤ ይህውም የቃል ኪዳን ሕዝቦች መሆናቸው ማረጋገጫ ነውና። ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ለየት ያለ የእምነት ሕብረት የሚደረግባት ምልክት ነው (ዘፍ 17:9-14)። እያንዳንዱ አባት የራሱን ወንድ ልጅ ይገርዝ ነበር (ለቤተሰቡ እንደካሕን በመሆን)። ሮቨርት ገርድልስቶን ፤ Synonyms of the old testament ገጽ 214 በሚለው መፅሐፍ ላይ ሲናገር የመገረዝ ልማድ ለመገረዝ ሲባል ደምን ከማፍሰስ ጋር የተያያዘ ነው። ደም ቃል ኪዳን ከማድረግ ጋር (ዘፍ 15:17)) ቃል ኪዳን ከመስበር ጋር (ዘፍ 2:17) እና ኪዳንን ከመዋጀት ጋር የተያያዘ ነው (ኢሳ 53)።

▣ **"በዚህም ስፍራ"** ከዘፀ 3:12 በተወሰደው ጥቅስ አውድ ይህ የሚያመለክተው ከተስፋይቱ ምድር ውጪ ስለሆነው የሲና ተራራ እንደሆነና በእስራኤል ሕይወት ከታዩ ክስተቶች ዋናኛው እንዲሆን ነው (ሕግ ለሙሴ የተሰጠበት)።

▣ **"አስራ ሁለቱ አባቶች"** ይህ በተለምዶ አብርሐምን፣ ይስሐቅንና ያዕቆብን የሚያመለክት ነው ነገር ግን በዚህ ስፍራ የሚያመለክተው የእስራኤል ነገድ ስለሚሆኑት አስራ ሁለቱ ወንድ ልጆች ነው (የያዕቆብ)።

> **NASB (የተሻሻለው) ትርጉም ምዕ 7:9-10**
> **የአባቶችም አለቆች በዮሴፍ ቀንተው ወደ ግብፅ ሸጡት ፤ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነበር ከመከራውም ሁሉ አወጣው በግብፅ ንጉስ በፈርኦንም ፊት ሞገስንና ጥበብን ሰጠው በግብፅና በቤቱ ሁሉ ላይም ቢተወደደ ምድር ላይ ሾመው።**

7:9 "ዮሴፍ" ይህ ክፍል)ታሪክ የሚገኘው በዘፍ 37:11 ፤ 25፤ 45:4 ላይ ይገኛል። እስጢፋኖስ ለማሳየት የሞከረው የአይሁድ ሕዝብና መሪዎቻቸውን በእግዚአብሔር የተመረጠውን መሪ በተደጋጋሚ መቃወማቸውን ነው (ሙሴ በቁ 35 ላይ)።

> **NASB (የተሻሻለው) ትርጉም፡ 7:11-16**
> **በግብፅና በከነአን አገር ሁሉ ራብና ጭንቅ መጣ። አባቶችንም ምግብ አላገኙም። ያዕቆብም በግብፅ እህል መኖሩን ሰማ ጊዜ በመጀመሪያ አባቶቻችንን ሰደዳቸው በሁለተኛውም ዮሴፍ ለወንድሞቹ ታወቀ። የዮሴፍም ትውልድ በፈርኦን ዘንድ ተገለጠ። ዮሴፍም አባቱን ያዕቆብንና ሰባ አምስት ነፍስ የነበረውን ቤተዘመድ ሁሉ ልኮ አስጠራ። ያዕቆብ ወደ ግብፅ ወረደ እርሱም ሞተ አባቶቻችንም ወደ ሴኬም አፍስሰው አብርሃም ከኤኮም አባት ከኤምር ልጆች በብረ በገዛው መቃብር ቀበሩአቸው።**

7፡10 ይህ ታሪክ የሚገኘው በዘፍ 39፡12 ፤ 41፡40-46 ላይ ነው፡፡

7፡11 ይህ ታሪክ የሚገኘው በዘፍ 41፡54-55፣42፡5 ላይ ነው

7፡12 ይህ ታሪክ የሚገኘው በዘፍ 42፡4 ላይ ነው፡፡

7፡13 ይህ ታሪክ የሚገኘው በዘፍ 45፡1-4 ላይ ነው፡፡

7፡14 "ሰባ አምስት" ይህ የሰብትዋጀንት እና የሙት ባሕር ጥቅስ መፅሐፍትን ተከትሎ የመጣ ሲሆን የማዞሬቲክ መፅሐፍ "ሰባ" ይላል (ዘፍ 46፡27፣ ዘፀ 1፡5) በመጀመሪያ ይህ የፅሑፍ ምንም ችግር ይመስላል፡፡ ይህም ችግር ያለው እስጢፋኖስ በጠቀሰው በሰብትዋጀንትና ዘፀ 1፡53 በያዘው የአይሁድ መፃፍ መካከል ነው፡፡ በተጨማሪነት ይህ ምናልባት ሁለት አይነት የያዕቆብን ዘሮች የመቁጠር አካሄድ ሊሆን ይችላል፡፡ ችግሩ የሚከሰተው በዘፍ 42፡26 እና 27 መካከል ሲሆን (1) የማዞሬትስ ትርጉም ለዮሴፍ የተወሰዱት ሁለት ልጆች ናቸው ሲል የሰብትዋጀንት ትርጉም ደግሞ 9 ይላል ይህም ኤፍሬምና ምናሴ በመካከላቸው ብዙ ልጆች ነበራቸው ወይም (2) በዕብራዊያን ያዕቆብና ሚስቱ ተቆጥረዋል ነገር ግን የኤፍሬምና ምናሴ ተጨማሪ ልጆች አልተቆጠሩም፡፡ በግሪክ ትርጉም (Lxx) ያዕቆብና ሚስቱ አልተቆጠሩም ነገር ግን የኤፍሬምና የምናሴ ተጨማሪ ልጆች ተቆጥረዋል፡፡ ሁለቱም ትክክል ናቸው ነገር ግን በተለያዩ የያዕቆብ ሕይወት ጊዜያቶች ዘሮቹን ቆጥሮ በተለያዩ መንገዶች ይደምራቸዋል፡፡ የሙት ባህር ጥቅሎች ተብለው የሚታወቁት የዕብራዊያን መፃሐፍት "ሰባ አምስት ሰዎች" የሚል በዘፍ 46፡27 እና በዘፀ 1፡5 ላይ አላቸው፡፡ የአሌክሳንደሪያው ሎሌ ስለ እነዚህ ቁጥሮች ቅርበት አለው፡፡

ሁላችንም የዘመናዊው ዕውቀት ተጠቃሚዎች ነን በተለይም አስቸጋሪ ፅሑፎችና የቁጥር ችግሮች ሲኖሩ፡፡ ለእነዚህ ችግሮች ምላሽ የሚሰጡ አዲስ መፅሐፍ ቅዱሳዊ የሆኑ ምንጮች አሉ እነዚህም ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉ ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል፤

1. *Hard Saying of the Bible*, IVP
2. *More Hard Sayings of the Bible* IVP
3. *Encyclopedia of Bible Difficulties by* Gleason Archer.

በሐዋ 7፡14-15 ላይ ያለውን ለመወያየት #1 ገጽ 521-522 ን ይመልከቱ

7፡15 ይህ ታሪክ የሚገኘው በዘፍ 46፡5፣ 49፡33 ዘፀ 1፡6 ላይ ነው፡፡

7፡16 "ወደ ሴኬም" ከዘፍጥረት ታሪክ (1) የዮሴፍ መቀበር በኢያ 24፡32 ላይ ተመዝግቧል (2) የያዕብ መቃብር በዘፍ 50፡13 ላይ ተጠቅሷል ፤ ነገር ግን በእስጢፋኖስ ንግግር አሻሚ የሆነ ነገር አለ፡፡ የዚህ ምክንያት (1) ከተማው ፡- ሴኬም ሳይሆን ኬብሮን መሆን አለት (2) የዕምነት አባት፡- አብርሃም ሳይሆን ያዕቆብ መሆን አለበት፡፡ ይሁን እንጂ አብርሃምና ያዕቆብ ሁለቱም መሬት ገዝተዋል፡፡ (ዘፍ 23፡16፣ 33፡19) በኬብሮን ሳራና አብርሃም ተቀብረዋል፡፡ (ዘፍ 23፡19፣ 24፡9) ልክ ይሳቅና ርብቃ (ዘፍ 49፡29-31) እንዲሁም ያዕቆብ (ዘፍ 50፡13) እንደተቀበሩት፡፡ ምንም እንኳን በሴኬም ስላለው የቀብር ቦታ እርግጠኛ መሆን ባይቻልም (ዘፍ 12፡6-7) ስናይ አብርሃም ቀደም ብሎ የቀብር ቦታ እንደገዛ ማየት ይቻላል፡፡ በኋላም ያዕቆብ ያንን መሬት ዋጀው (ዘፍ 33፡19፣ ኢሳ 24፡32)፡፡ ይህ ግምት ነው ነገር ግን እስጢፋኖስ ስለ ብሉይ ኪዳን ታሪክ ጠለቅ ያለ ዕውቀት ያለው ስለሚመስል ይህ ብቻ ነው የተለያዩ ታሪኮችን የማስታረቂያ መንገድ ሊሆን የሚችለው፡፡

**NASB (የተሻሻለው) ትርጉም ምዕ 7፡17-29**

***እግዚአብሔርም ለአብርሃም የማለለት የተስፋው ዘመን ሲቀርብ ዮሴፍን የማያውቀው ሌላ ንጉስ በግብፅ እስኪነሳ ድረስ ህዝቡ እየተጨመሩ በግብፅ በዙ እርሱም ወገናችንን ተተንኩሎ ህፃናትን በህይወት እንዳይጠብቁ ወደ ውጭ ይጥሉ ዘንድ አድርጐ አባቶቻችንን አስጨነቀ፡፡ በዚያ ጊዜ ሙሴ ተወለደ በእግዚአብሔር ፊት ያማረ ነበር በአባቱ ቤትም ሶስት ወር አደገ በተጣለም ጊዜ የፈርኦን ልጅ አነሳችው ልጅም ይሆናት ዘንድ አሳደገችው፡፡ ሙሴም የግብጾችን ጥበብ ሁሉ ተማረ በቃሉና በስራውም የበረታ ሆነ ነገር ግን አርባ አመት ሲሞላው ወንድሞቹን የእስራኤል ልጆች ይጐበኝ ዘንድ በልቡ አሰበ፡፡ አንዱም ሲበድል አይቶ ረዳው የግብፅም ሰው መጥቶ ለተገፋ ተበቀለ፡፡ ወንድሞቹም እግዚአብሔር በእጁ መዳንን እንዲሰጣቸው የሚያስተውሉ ይመስለው ነበር፡፡ እነርሱ ግን አላስተዋሉም በማግስቱ እርስ በእርሳቸው ሲጣሉ አገኛቸው፤ ሊያስታርቃቸውም ወዶ ሰዎች ሆይ እናንተስ ወንደማማች ናችሁ ስለምን እርስ በእርሳችሁ ትበዳደላላችሁ አላቸው፡፡ ያን ባልንጀራውን የሚበድል ግን አንተ በእኛ ላይ ሹምና ፈራጅ እንድትሆን የሾመህ ማን ነው ወይስ ትናንትና የግብፅን ሰው እንደገደልከው ልትገድለኝ ትወዳለህን ብሎ ገፋው፡፡ ሙሴም ከዚህ ነገር የተነሳ ሸሽቶ በሚዲያም ሀገር መፃተኛ ሆኖ ኖረ ከዚያም ሁለት ልጆች ወለደ፡፡***

7፡17 ይህ የሚያመለክተው ዘፍ 15፡12-16 ነው (የተሰጠው ተስፋ) እንዲሁም ዘፍ 1፡7 (በቁጥር መብዛታቸውን)

7፡18 **"ሌላ ንጉስ በግብፅ እስኪነሳ ድረስ"** ይህ ከዘፀ 1፡3 የተወሰደ ጥቅስ ነው እስራኤላዊያን ከግብፅ የሚወጡበት ጊዜ ላይ በምዕመናን መሃከል የማይቋረጥ ክርክር እስከ ዛሬ አሉ፡፡ ባለመስማማቱ ላይ አንደኛው ችግር የዚህ ንጉስ ማንነት ጉዳይ ነው፡፡ አንድ ሰው ይህንን ንጉስ ከ18ኛው ስረወ መንግስት (ከ1445- ከክ.ል.በፊት) ወይም ከ19ኛው ሰረወ መንግስት (1290 ከክ.ል.በፊት) መካከል ሊኖር ይችላል፡፡ አንዱ ንዑስ ሃሳብ የመጀመሪያው ግብፃዊና ሴማንቲክ የተባሉትን የግብፅ ገዢዎችን ያስወገደ ነው በማለት የሚያዛምድ ነው፤ ይህም HETRAS በቁጥር 18 ጥቅም ላይ መዋሉ የሚያስረዳ ነው፡፡ ተወላጅ ግብፃዊ እንደ እብራዊያን ያሉ የሴም ዝርያዎች በብዛት በግዛቱ እንዲኖሩ አይፈልግም ምክንያቱም እንደ አይክሴሶች ሌላ ወረራ ሊከሰት ይችላል ብሎ ስለሚፈራ ነው፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ በእስራኤላዊያን ከግብፅ በመጡበት ቀን**

በእስራኤላዊያን ከግብፅ በመጡበት ቀን ላይ ያለው ክርክር እስካሁን ድረስ ከግብፅ በመጡበት ዕለት ዙሪያ ሁለት የምሁራን አስተያየቶች አሉ፡፡

ሀ. ከ1ነገ 6፡12
1. ሰለሞን መንገስ የጀመረው በ970(ከክ.ል.በ) ነው፡፡ ይህም የተሳለወ የ ጦርነትን (ስምንት መቶ ሃምሳ ሶስት ከክ.ል.በፊት) እንደመነሻ ቀን በመውሰድ ነው፡፡
2. ቤተመቅደሱ የተገነባው በነገሰ በአራተኛው ዓመት ነው (965 ከክ.ል.በፊት ነው) ስለዚህ ከግብፅ በወጡበት ጊዜ 1445)6 ከክ.ል.በፊት
3. ይህም በ18ኛው የግብፅ ስረው መንግስት እንዲከሰት ያደርገዋል
   ሀ. የፈረኦን አገዛዝ (1490 -1436(ከክ.ል.በፊት)
   ለ. ሲወጡ የነበረው ፈርኦን ከ1436-1407ከክ.ል.በፊት)
      1. AMONHOTEP III (1413-1377 ከክ.ል.በፊት) እንደሆነ እንደሚያነብት ምንም አይነት የዲኘሎማቲክ ግንኙነት በኢያሪኮና በግብፅ እንዳልነበረ ነው
      2. AMARMA መፅሐፍት እንደሚዘግቡት AMONHOTEP III የአገዛዝ ዘመን HABIRU ከነሃንን ስለመግዛቱ በአስተርያ ላይ የዲኘሎማቲክ ግንኙነት እንደተፃፈ ይናገራሉ፡፡
      3. 13ኛው ክፍለ ዘመን የእስራኤል መውጣት ሲሆን የመሳፍንት ዘመን እረጅም አይደለም ማለት ነው፡፡
4. እነዚህ ቀናት በሚመለከት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮች
   ሀ. የሰብትዋጀንት 480 ሳይሆን 440 ማለቱ
   ለ. 480 ዓመታት እያንዳንዳቸው 40 ዓመታት ያላቸው 12 ትውልዶች ማለት ይቻላል (ስለዚህ ስዕላዊ ቁጥር ነው
   ሐ. ከአሮን እስከ ሰለሞን ድረስ 12 የካህናት ትውልዶች አሉ (1ዜና 6) ከዚያም ከሰለሞን እስከ ሁለተኛው ቤተመቅደስ 12 ትውልዶች አይሁድ እንደ ግሪኮች አንድን ትውልድ 40 ዓመታት ብለው ይቆጥራሉ፡፡ ስለዚህ ወደኂላ ወደፊት 480 ዓመት አሉ (ቁጥሮችን ለምልክት መጠቀም (*Bunonson Redating the Exodus and conquest*)
5. ስለቀናት መግለጫ የሚሰጡ ሌሎች ሶስት መፃሐፍት አሉ
   ሀ. ዘፍጥረት 15፡13-16 (ሐዋ 7፡6 ፤ 400 የባርነት ዓመታት ከግብፅ መውጣት
   ለ. ዘፀአት 12፡40-41 (ገላ 3፡17)
      (1) የማዘቴቲክ መጽሐፍ 430 ዓመታት በግብፅ
      (2) የሰብትዋጀንት መጽሐፍ 215 ዓመታት በግብፅ
   ሐ. መሳ 11፡26-300 ዓመታት በዮፍታሔ ዘመንና በኢያሱ (የ1445 ቀንን የሚደግፍ)
   መ. ሐዋ 13፡19 መውጣት፣ የምድረ በዳ ጉዞ፣ ርስት መያዝ 450 ዓመታት
6. የነገሡት ፀሐፊ ውስን የሆኑ ታሪካዊ መረጃዎችን ተጠቅሟል ቁጥሮችን በማጠጋጋት አልተጠቀመም Edwin Thiele Achronology of the Hebrew Kings PP 33-85)

ለ. ከአርኪዋሎጂ ጥናት በጊዜያዊነት ያለው መረጃ ወደ 1290 (ከክ.ል.በፊት) ወዳለው ያመለክታል ወይም 19ኛውን የግብፅ ሥረው-መንግስት፡፡
1. ዮሴፍ አባቱንና ፈርኦንን የጐበኘው በተመሳሳይ ቀን ነው፡፡ የመጀመሪያው ግብፃዊ የግብፅን ዋና ከተማ ከረቤስ ወደ ናይል ዴልታ ወደ ሚገኘው ልዩ ስሙ Avaris (Zoaa (Tanis (ጣዕዋል) የወሰደው ፈርኦን Seti (ሴቲ) (1309 -1290) በክ.ል.በፊት) ይህ ንጉስ በጭቆናው ዘመን የግብፅ ንጉስ ሊሆን ይችላል፡፡
   ሀ. ይህም ሃይክቢሶች በግብፅ ለመንገላቸው ሁለት መረጃዎችን ይሰጠናል
      (1) ከራምሴ 2ኛ ጀምሮ የAvaris (ጣዕዋል) መመስረት ከ400 ዓመታት በፊት ጡብ መገኘቱ (በሃይክሊሶች 1700ከክ.ል.በፊት)
      (2) በዘፍ 15፡13 የተነገረው ትንቢት የ400 ዓመታት አገዛዝ ይናገራል፡፡
   ለ. ይህ የሚያሳየው ዮሴፍ ወደ ስልጣን የወጣው ሐይክሊስ (ሴሜቲክ) ፈርኦን ዘመን ነው፡፡ አዲሱ የግብፅ ሥረወ-መንግስት በዘፀ 1፡8 ተጠቅሷል፡፡
2. ሐይክሲሶች ግብጾች እንደሚሉት (የባዕድ ሀገራት ገዢዎች) ግብፃዊ ያልሆኑ ሴማዊ ገዢዎች የሆኑ ግብፅን የገዟት በ15ኛውና በ16ኛው ሥር መንግስት ነበር (1720-1570 ከክ.ል.በፊት) አንዳንዶች እነርሱም ከዮሴፍ ስልጣን ላይ መውጣት ጋር ያቆራኛሉ፡፡ ከዘፀ 12፡40 ያለውን 430 ዓመታት

ከ1720 (ከክ.ል.በፊት) ላይ ብንቀንስ የምናገኘው ቁጥር 1290 (ከክ.ል.በፊት) ነው፡፡

3. የSet I ወንድ ልጅ ራምሴ 2ኛ ነበር (1290 — 1224) ከክ.ል.በፊት ይህ ስም የተገለፀው በዕብራዊያን የተገነባ ከተማ እንደሆነ ይታወቃል (ዘፀ 1፡11) ይህ በጌሴም ግብ ያለ ተመሳሳይ ቦታ ራምሴ ተብሎ ይጠራል (ዘፍ 47፡11)፡፡ ጠኤዋስም "የራምሴዎች ቤት" ተብሎ ይታወቃል፡፡ (ከ1300 - 1100 ከክ.ል.በፊት)
4. Thumoses 3ኛ ታላቅ መስራች ነበር ልክ ራምሴ 2ኛ እንደነበረው
5. ራምሴ 2ኛ በተለያዩ ቤተመንግስቶች የሚኖሩ 47 ሴት ልጆች ነበሩት፡፡
6. የአርኪዎሎጂ ጥናት እንደሚያሳየው አብዛኞዎቹ የከነዓን ጠንካራ ቅጥሮች (ሐዘር፣ ዳብር፣ ለኪስ) ወድመው ነገር ግን ወዲያውኑ በ1250 (ከክ.ል.በፊት) አካባቢ እንደገና ተገነቡ፡፡ የ38 ዓመቱን የምድረ በዳ ጉዞን ስንመለከት ይህ ከ1290 (ከክ.ል.በፊት) ጊዜ ጋር የሚስማማ ነው፡፡
7. የአርኪዎሎጂ ጥናት እስራኤላዊያን በደቡባዊ ከነዓን እንደነበሩ ማረጋገጫ አግኝቷል ይህም ከራምሴ ቀጥሎ የነገሰውን Merneptalን የሚመለከት ነው (1224-1214 ከክ.ል.በፊት) ይህም የ Merneptal ጠብ ቀኑ የሚያሳየው 1220 ነው፡፡
8. ኤዶምን ሞአብ ጠንካራ ብሔራዊ ማንነትን ያገኙት በኃለኛው 1300 ዓመታት ነበር፡፡ እነዚህ ሐገሮች በ15ኛው ክ)ዘ አልተደራጁም ነበር
9. በJohn J. Bimson የተፃፈውን በመፈልድ ዩኒቨርስቲ የታተመው መፅሐፍ በእስራኤል መውጣት በሚመለከት ሁሉንም የአርኪዋሎጂ ማስረዳዎተን ይከራከራል፡፡

7፡19 ይህ ታሪክ የሚገኘው በዘፀ 1፡10 ላይ ነው

7፡20 **"ሙሴ ተወለደ"** ይህ ታሪክ የሚገኘው በዘፀ 2 ላይ ነው

**"በእግዚአብሔር ፊት ያማረ ነበር"** ይህ የዕብራዊያን የቁንጅና አገላለፅ ነው ዘፀ 2፡2፡፡ ይህውም በሙሴ ቁንጅና ላይ ማብራሪያ ሰቶበታል፡፡

7፡21 ይህ ታሪክ የሚገኘው በዘፀ 2፡5 ላይ ነው

▣ **"በተጣለም ጊዜ"** ይህ የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙም ማጋለጥ (ቁ . 19) ወይም በውጭ ማኖር ማለት ነው፤ ግብፃውያን የእስራኤላዊያንን ቁጥር ህዝብ ብዛት ለመቆጣጠር ወንድ ልጆቻቸውን እንዲጥሉ ያስገድዱአቸው ነበር፡፡

▣

| | |
|---|---|
| NASB, NKJV | **"የፈርኦን ልጅ ወለደችው"** |
| NRSV, NJB | **"የፈርኦን ልጅ አሳደገችው"** |
| TEV | **"የንጉስ ልጅ አሳደገችው"** |

*Anaireo* የሚለው ቃል ትርጉሙ ወደ ላይ ማንሳት ማለት ነው፡፡ ሙሴ በትክክልም ቃል በቃል ከውሃ ውስጥ ነው እንዲወጣ የተደረገው ከዚያም ሙሴ የፈርኦን ልጅ በጉዲፈቻ አሳደገችው፡፡

7፡22 ሙሴ በፈርኦን አደባባዮች በጊዜው ምርጥ የተባለውን የቀለም ትምህርትና የሚሊተሪ ስልጠና አግኝቷል፤

▣ **"በቃሉና በስራው የበረታ ነበር"** ይህ ስለኗላኛው የህይወት ዘመኑ የተሰጠ ማጠቃለያ ነው ምክንያቱም እግዚአብሔር ሲገለፅለት መናገር አይችልም ነበር (ዘፀ 4፡10-17)፡፡

7፡23-24 **"አርባ ዓመት"** ይህ ታሪክ የሚገኘው በዘፀ 2፡11 ላይ ነው፡፡

7፡23 **"አርባ ዓመት ሲሞላው"** ዲ.ኤል ሙሴ ሳይሆን ሙሊ የሙሴ ህይወትን በሶስት ሊከፍለው ችሏል፡፡ (1) መጀመሪያዎቹ 40 ዓመታት እንደማንኛውም ሰው ነበር (በፈርኦን ቤት የተማረ (2) ሁለተኛው 40 ዓመታት ማንም እንዳልሆነ ያለፈበት ወቅት (ወደ ሚዲያም የተሰደደበትና ስለ ሲና ምድረ በዳ የተማረበት (3) በሶስተኛው 40 ዓመታት ምንም ባልሆነ ሰው ውስጥ እግዚአብሔር ምን ሊሰራ እንደሚችል የተማረበት ነው፡፡ (የእግዚአብሔርን ሕዝብ ወደ ተስፋይቱ ምድር የመራበት ነው፡፡

7፡25 ይህ ጥቅስ የእስጢፋኖስ ግምት ነው (ምናልባት የህብራውያን ባህል) እንጂ በዘፀአት ውስጥ አልተፃፈም፡፡

7፡26-29 ይህ ታሪክ የሚገኘው በዘፀ 2፡13 ላይ ነው፡፡

7፡29 **"ከዚህ ነገር የተነሳ ሙሴ ሸሸ"** ይህ ታሪክ የሚገኘው በዘፀ 2፡15 ላይ ነው፡፡ ሙሴ ግብፃዊውን በመግደሉ የተሰማው የፍርሃት ስሜት የፈርኦን የማደጉ ልጅ በመሆኑ ላይ ድጋፍ እንዳልነበረ ያሳያል፡፡ ከዚህ በላይ ዕብ 11፡27 ግልፅ ያደርገዋል፡፡

▣ *"በሚዲያም ሀገር ምፃተኛ ሆኖ ኖረ"* እግዚአብሔር ለሙሴ የተገለጠው በሚዲያም ምድር ነበር (ዘፀ 3፡4) እንዲሁም ህጉን የገለጠበት ሀገር ነበር፤ (ዘፀ 19፡20) ይህ የሚያሳየው እግዚአብሔር እራሱን ለመግለፅ በስፍራ አይወሰንም፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ እግዚአብሔር ከመቅደሱ ውጪ እራሱን የገለፀበት ሁኔታ ነበር (ሐዋ 7፡36፣ 44፣ 48፣ 53)

▣ *"በዚያ ሁለት ልጆች ወለደ"* ይህ ታሪክ የሚገኘው በዘፀ 18፡3 ላይ ነው፡፡

**NASB (የተሻሻለው) ትርጉም ምዕ 7፡30-34**
***ዓርባ ዓመትም ሲሞላው የጌታ መልአክ በሲና ተራራ ምድረ በዳ በቁጥቋጦ መካከል በእሳት ነበልባል ታየው፡፡ ሙሴም አይቶ ባየው ነገር ተደነቀ፡፡ ሊመለከትም ሲቀርብ የጌታ ቃል፡- እኔ የአባቶችህ አምላክ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምለክ ነኝ ብሎ ወደ እርሱ መጣ፡፡ ሙሴም ተንቀጥቅጦ ሊመለከት አልደፈረም፡፡ ጌታም የቆምክባት ስፍራ የተቀደሰች ምድር ናትና የእግርህን ጫማ አውልቅ በግብፅ ያሉትን የሕዝቤን መከራ ፈፅሜ አይቼ መቃተታቸውንም ሰምቼ ላድናቸው ወረድኩ አሁንምና ወደ ግብፅ እልክሃለሁ አለው፡፡***

7፡30 ይህ ታሪክ የሚገኘው በዘፀ 3 እና 4 ውስጥ ነው፡፡

*"የጌታ መልአክ"* በብሉይ ኪዳን ይህ መልእክት በተለምዶ ያህዌ ተብሎ ይጠራል፡፡ ሙሉ ማስታወሻውን በ5፡19 ላይ ተመልከት ፤ እንዴት አይነት ስያሜ ይህ መልአክ እንደተሰጠው አስተውል፡፡

1. ዘፀ 3፡2 "የጌታ መልአክ በእሳት ነበልባል ታየው"
2. ዘፀ 3፡4 "እግዚአብሔርም (ያህዌ) ሊያዩ እንደመጣ ባየ ጊዜ"
3. ዘፀ 3፡4 "እግዚአብሔር (ኤሎሒም) ከቁጥቋጦው ውስጥ እርሱን ጠርቶ"

▣ *"የሲና ተራራ"* ቀጥሎ ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት

**ልዩ ርዕስ፡ የሲና ተራራ አቀማመጥ**

ሀ. ሙሴ ፈርኦንን የሶስት ቀን መንገድ ብሎ የጠየቀበት (3፡18፣ 5፡3፣ 8፡27) ቀጥተኛ ንግግር ከሆነ ያ ወደ ደቡባዊው ከነአን ለመድረስ ረጅም ጊዜ አይሆንም፡፡ ስለዚህም አንዳንድ ምሁራን ተራራውን በቃዲስ በርኔ የሚገኝ ምንም አጠገብ ነው ይላሉ፡፡

ለ. በሲና ምድረ በዳ የሚገኘው የተለመደው "የቤል ሙላ" የሚባለው ብዙ ነገሮች አሉት

1. በተራራው የሚገኝ (ፊት ለፊት) ሰፊ ሜዳ
2. ዘዳ 1፡2 የሚለው ከሲና ተራራ እስከ ቃዲስ በርኔ የአስራ ሁለት ቀናት ጉዞ እንዲሆን ያስረዳል
3. "ሲና" የሚለው ቃል የዕብራይስጥ ቃል አይደለም፡፡ ምናልባትም ከሲና ምድረ በዳ ጋር የሚገናኝ ነው ይህም በምድረ በዳ የሚገኝ ትንሹ ቁጥቋጦ ነው፡፡ የዚህ ተራራ የእብራይስጥ ሰው ኮሬብ ይባላል (ምድረ በዳ ማለት ነው)
4. የሲና ተራራ ከ4ኛው ክ/ዘ ጀምሮ ታሪካዊ/ባህላዊ ቦታ ሆኖ ቆይቷል፡፡ "የምድያም ምድር" የሲናን ስርጥ እና አረቢያን የሚያካትት ነው፡፡
5. የአርኬዎሎጂ ጥናት በዘፀአት ታሪክ ውስጥ የሚገኙትን አንዳንድ ከተሞች (ኤለም፣ ይኝካ፣ ራፊሊም) አቀማመጣቸውን በሲና ሰርጥ በስተ ምዕራብ በኩል እንደሆነ አረጋግጧል፡፡

ሐ. አይሁዶች ስለ ሲና ተራራ ጂኦግራፋያዊ አቀማመጥ እምብዛም ፍላጐት አልነበራቸውም፡፡ እግዚአብሔር ሕጉን እንዲሰጣቸውና ተስፋውን እንዲፈፀም ብቻ ነው ያመኑት (ዘፍ 15፡12-21)

መ. የሲና ተራራ የተለመደው ቦታ "የስልቪያ ጉዞ" በ385-8 ዓ.ም. እስኪ. ተደረገበት ጊዜ ድረስ አይታወቅም ነበር (ኤፍ .ኤፍ. ብሩስ ፤Comentary on the Book of the Acts) ገጽ 151፡፡

ሠ. በአርቢያ በሚገኘው የአካባ ባህረ ሰላጤ ማይ ያለው ቦታ ብዙ ሊመስሉ የሚችሉ ግምቶችን እያስነሳ ነው፡፡ ይህ አቋም የሚያመለክተው

1. የምድያም ምድር ያለጥርጥር የሚገኘው በአረቢያ ነው
2. በገላ 4፡25 ጳውሎስ በአረቢያ እንደሆነ ይጠቅሳሉ
3. የሳተላይት ካርታ እንደሚያመለክተው ከግብፅ ወደ ሲና ሲሮጥ የተዘረጋ የጥንት መንገድ እንዳለ ይህም የሚያልፈው የአካባን ባህረ ሰላጤ አቋርጦ እንደሆነ
4. በዚህ አካባቢ ያለው ከፍተኛው የተራራ ጫፍ በከባድ ጢስ የተሸፈነ እንደሆነ (ዘፀ 19፡16፣ 18)

አሁንም ደግመን መግለፅ ያለብን ትክክለኛውን የተራራውን አቀማመጥ አሁንም እናውቅም ብለን ነው፡፡

7፡32 ይህ ታሪክ የሚገኘው በዘፀ 3፡6 ላይ ነው፡፡

▣ *"አባቶች"* በሁሉም የእብራይስጥ መፅሐፍና የግሪክ ትርጉም) ሰብትዋጀንት) ቃሉ ነጠላ ነው፡፡ በሌላው የሐረጉ አገባብ ላይ ግን የብዙ ቁጥርን ያመለክታል፡፡ እግዚአብሔር ባሪያ የነበረውን የሙሴን አባት ያወቀ ነበር፡፡

7:33 ይህ ታሪክ የሚገኘው በዘፀ 3:6 ላይ ነው

▣ "አባቶች" በሁለቱም የእብራይስጥ መፅሐፍና የግሪክ ትርጉም ቃሉ ነጠላ ነው፡፡ በሌላው የሐረጉ አገባብ ላይ ግን የብዙ ቁጥርን ያመለክታል፤ እግዚአብሔር ባሪያ የነበረው የሙሴን አባት ያውቅ ነበር፤
7:33 ይህ ታሪክ የሚገኘው በዘፀ 3:5 ላይ ነው ሙሴ ቁጥቋጦውን የጠረበው በመደነቅ እንጂ ከመንፈሳዊነት አንፃር አልነበረም

1. ጫማ ሊቆሽሽ የሚችል ነው (የከብት እበት ወዘተ)
2. ጫማን ማውለቅ ምናልባት በጣም የመቅረብ ምልክት ሊሆን ይችላል (ማለትም በቤት ውስጥ)
3. የአባቶች ባህላዊ ድርጊት ወይም የግብፃዊያን ስርዓት ሊሆን ይችላል፡፡

7:34 ይህ ታሪክ የሚገኘው በዘፀ 3:7 ላይ ነው ይህ ጥቅስ ከነገረ መለኮት አንፃር በጣም ጠቃሚ ነው የምለው ያህዌ ፀሎታቸውን የሰማበት መከራቸውን ያየበትና ምላሽ የሰጠበት ነው፡፡ ሊያድናቸው ወረደ ነገር ግን የርሱ ማዳን በሰው በኩል ውጤታማ እንዲሆን አስተውል እግዚአብሐር ፈቃደኛ ያልነበረውን ሙሴን ላከ እግዚአብሔር ሰዎችን ለማግኘት በሰው በኩል ይመጣል፡፡

**NASB (የተሻሻለው) ትርጉም ምዕ 7:35-43**

*ሹምና ፈራጅ እንድትሆን የሾመህ ማነው? ብለው የካድትን፦ ይህን ሙሴን በቁጥቋጦው በታየው በመልአኩ እጅ እግዚአብሐር ሹምና ቤዛ አድርጐ ላከው፡፡ ይህ ሰው በግብፅ ምድርና በኤርትራ ባህር በምድረ በዳም አርባ አምስት ድንቅና ምልክት እያደረገ አወጣቸው፡፡ ይህ ሰው ለእስራኤል ልጆች፦ እግዚአብሔር ከወንድሞቻችሁ እንደ እኔ ነቢይ ያስነሳላችኋል እርሱን ስሙት ያላቸው ሙሴ ነው፡፡ ይህ ሰው በሲና ተራራ ከተናገረው መልአክና ከአባቶቻችን ጋር በምድረ በዳ በማህበሩ ውስጥ የነበረው ነው፡፡ ይሰጠንም ዘንድ ሕይወት ያላቸውን ቃላት ተቀበለ ለእርሱም አባቶቻችን ሊታዘዙት አልወደዱም ነገር ግን ገፉት በልባቸውም ወደ ግብፅ ተመለሱ አሮንንም በፊታቸው የሚሄድ አማልዕክት ስራልን ይህ ከግብፅ ምድር ያወጣን ሙሴ ምን እንደሆነ አናውቅምና አሉት፡፡ በእጃቸውም ስራ ደስ አላቸው፡፡ እግዚብሔር ግን ዘወር አለ የሰማይንም ጭፍራ ያመልኩ ዘንድ አሳልፎ ሰጣቸው በነቢያትም መፅሐፍ እናንተ የእስራሔል ቤት አርባ አመት በምድረ በዳ የታረደውን ከብትና መስዋዕትን አቀረባችሁልኝን? ትሰግዱላቸውም ዘንድ የሠራችኋቸውን ምስሎች እነርሱንም የሞሎክን ድንኳንና ሬምፋም የሚሉትን የአምላክችሁን ኮከብ አነሳችሁ፤ እኔም ከባቢሎን ወዲያ አሳድዳችኃለሁ ተብሎ እንዲህ ተፅፎአል፡፡*

7:35 "የካዱትን ይህን ሙሴን" የእግዚአብሔር ሕዝብ ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔር መልዕክተኞችን ይቃወማሉ (ቁ . 51-52) ይህ ምናልባት የቁ 27 ዓላማ እንዲሁም ሊሆን ይችላል፡፡

▣ "በቁጥቋጦው በታየው በመልአኩ እጅ" አሁንም እግዚአብሔር ከተስፋይቱ ምድር ውጪ ያልሆነው እስራኤላዊ መጣ የእግዚአብሔር ስራ በስፍራ አይወሰንም፡፡ አብዛኛው የእስራኤል ታሪክ የተከሰተው ከከነዓን ውጪና በኢየሩሳሌም የነበረው ቤተመቅደስ ቀደም ብሎ ነው፡፡ በእስራኤላዊያን ታሪክ በሙሉ የእግዚአብሔር መሪዎች ተገፍተዋል (ቁ 9 ፤ 27-28 ፤ 35:39) ይህ በተደጋጋሚ የታየ ጉዳይ ነው፡፡

መልአኩ እንዲመለከት ነበር የታየው (ዘፀ 3:2-4) ይህ የመለኮት አካላዊ መገለጥ በዘፍ 16:7-13፣ 22:11-15፣ 31:11፣ 13፣ 48:15-16፣ ዘፀ 13:21፣ 14:19፣ መሳ 2:1፣ 6:22-23፣ 13:3-22፣ ዘካ 3:1-2፡፡ ይሁን እንጂ "የጌታ መልአክ" የሚለው የመለኮት አካላዊ መገለጥ እንዳልሆነ መታወቅ አለበት፡፡ አንዳንድ ጊዜ መልዕክተኛ መልአክ ነው (ዘፍ 24:7፣ 40 ዘፀ 23:20-23፣ 32:34 ዘሕል 22:22፣ 2ሳሙ 24:16 ዮሐ 5:23 1ቆሮ 21:15፣ ዘካ 1:11፣ 12-13)

7:36 ይህ የእግዚአብሔር ተአምራታዊ ኃይል ማጠቃለያ ዓረፍተ ነገር ነው፡፡ (የሙሴ በትር) ይህም የተገለጠው በሙሴና በአሮን በኩል ነው፡፡

7:37-38 ይህ በዘዳ 18:15 የተወሰደ መሲሐዊ ጥቅስ ነው፡፡ እስጢፋኖስ ከግብፅ ሲወጡ እና በምድረ በዳ ጉዞአቸው የታየውን የእግዚአብሔር አብሮነት እንደ እግዚአብሔር መልአክና ሙሴን ከሚተጋው የእግዚአብሔር ነቢይ ጋር ያገናኘዋል (መሲሑ፣ ነቢይ) እስጢፋኖስ ሙሴን ዝቅ እያደረገው አይደለም በእርግጥ እየሰማው እንጂ፡፡

7:38 "ማሕበር" ይህ ኤክሌሽያ የሚለው የግሪክ ቃል ነው፡፡ ነገር ግን እዚህ ላይ እንደ ጉባኤ እንጂ እንደ ቤተክርስትያን አይወክል፡፡

▣ "በሲና ተራራ ከተናገረው መልአክ" የረቢዎች ሥነ መለኮት እንደሚያረጋግጠው መልዕክት በያህዌህ እና በሕጉ መሰጠት መካከል አገናኝ ናቸው (በ7:53 ላይ ያለውን ማስተወሻ ተመልከት)፡፡ መልአኩ ያሕዊን ያመለክታል ማለት ይቻላል (ዘፀ 3:21፣ ከ14:19 ጋር አነፃፅር እንዲሁም ዘፀ 32:34 ዘሕል 20:16 መሳ 2:1)

7:39 "አባቶቻችን ሊታዘዙት አልወደዱም" እስጢፋኖስ የብሉይ ኪዳን አመፅን እያሳያቸው ነበር፡፡ አሉ ማለት የፈለገው ዕብራዊያን ሁል ጊዜ የእግዘአብሔርን መሪዎች እንደተቃወሙ አሁንም መሲሁን እየተቃወሙ እንዳሉ ለማሳየት ነው፡፡

▣ *"ገፋት"* ይህ ክፍል የሚገኘው በዘሕ 14፡3-4 ላይ ነው፡፡

7፡40-41 ይህ ክፍል የሚገኘው በዘፀ 32 ላይ ነው፡፡ ይህ ማመንዘር ሳይሆን የእግዚአብሔርን አካላዊ ምስል መስራት ነው፡፡ በኂላም ከልምላሜ አምልኮ ጋር በተያያዘ ተቀየረ፡፡

7፡41 እስጢፋኖስ የወርቁን ጥጃ እንደ ጣኦት ነው የተረጐመው ፤ ከአሞፅ 5 በመጥቀስ ይህን ታሪካዊ ክስተት በመጠቀም እስራኤል ከግብፅና ከምድረ በዳ ጀምሮ አመንዝራና አመፀኛ ትውልድ እንደሆነች አሳዩ፡፡

**7፡42 "እግዚአብሔር ግን ዘወር አለ"** ቁ.42 እና 43 ከአሞ 5፡25-27 የተወሰዱና እስራኤል ሁል ጊዜ ለአሕዝብ አማልእክት መስዎዕትን እንደምታቀርብ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ቀደምት፣ የተለመደና የሕይወታቸው ስርዓት ነበር (ኢያሱ 24፡20)፡፡ ይህ የሚያስታውሰን በእግዚአብሔር ስለመጣል ጥብቅ የሆነ ማሳሰቢያ ነው ሮሜ 1፡24፣ 26፣ 28)፡፡

▣ **"የሰማይንም ጭፍራ"** ይህ የሚያሳየው የአሶሪዊያንና የባቢሎናዊያንን የከዋክብት አምልኮ ነው (ዘዳ 17፡3 2ነገ 17፡16፣ 27፡3 2ዜና 33፡3፣ 5 ኤር 8፡2፣ 19፡13)፡፡ ብዙ የቴክስት ችግሮች አሉ፡፡ በዕብራዊያን መፅሐፍ (ማዞሬቲክቴክስት)ስለ አሞ 5፡25-27፣ የግሪኩ ትርጉም (Lxx) እና እስጢፋኖስ የጠቀሰው፡ (1) የሚመለከው ኮከብ ስም የማዞሬቲክ ትርጉም ለኘላኔት ሳተርን የአስር ስያሜ ሲሰጠው Kywn ወይም Kaiwann ይለዋል፡፡ የሰብትዋጅንት ትርጉም raiph ወይም "raiphaa" ምናልባትም "rapa" አምላክ ለሚመለከው የሳተርን ኮከብ (ኘላኔት) የግብፅ ስያሜው ነው፡፡ (2) የዕብራዊያን መፅሐፍ (ማዞሬትክ) እና የሰብትዋጀንት ትርጉም "ከደማስቆ ወዲያ" ሲሉ እስጢፋኖስ ደግሞ "ከባቢሎን ወዲያ" ይላል፡፡ ስለ አሞፅ ምንም የታወቀ የተፅፈ መረጃ የለም፡፡ እስጢፋኖስ ምናልባት የአሥርን ምርኮ (አሞፅ የሚናገረውን) ከኃለኛው ይሁዳ ወደ ባቢሎን የሔደበትን ምርኮ አጣምሮ ሊሆን ይችላል፡፡ የልደት ቦታውን በመቀያየር፡፡
የከዋክብት አምልኮ የተጀመረው በሚሰፐተሚያ ሲሆን ነገር ግን ወደ ሶርያና ከነአን ተሰራፍቷል (ኢዮ 31፡26-27) በቴልኤል አማሮና የተገኙት አርኪዮሎዲካዊ ግኝቶች በ14ኛው ክ)ዘ (ከክ.ል.በፊት) ከከነዓን ወደ ግብፅ የተፃፉ ደብዳቤዎችን ያቀፈው እነዚህን የክዋክብት አማልክት እንደ ቦታ ስያሜዎች ይጠቀማቸዋል፡፡

▣ **"በነቢያት መፅሐፍ"** ይህ የሚያመለክተው አስራ ሁለቱን ደቂቃ ነብያትን የያዘውን ጥቅስ ነው (13፡40) በቁ 42-43 ላይ የተጠቀሰው ከአሞፅ 5፡25-27 የሰብትዋጀንት ትርጓሜ ላይ ነው፡፡

**7፡43 "ሞሎክ"** ንጉስ ለሚለው ቃል የዕብራይስጥ ቋንቋ ተነባቢዎች "mlk" ናቸው፡፡ ብዙ ተነባቢዎቻቸው ከዚህ ጋር የሚገናኙ ብዙ የከናአን አማልዕክት አሉ፤ ሚልኮም፣ ምሌክ፣ ወይም ምሎክ ምሎክ የአምራዊያን አምላክ የለምላሜ ሲሆን ለዚህም የማህበረሰብ ወይም የሐገሩን ጤንነትና ብልፅግና ለማረጋገጥ ልጆች በመስዋዕትነት የሚቀርብለት ነው (20፡2-5፣ 12፡31፣ 1ነገ 11፡5፣ 7፡33፣ 2ነገ 23፡10፣ 13፡14 ኤር 32፡35 7፡31) ኤ.ቲ .ሮቨርትስን፤ *Wood Pictures la the New Testament* ቁ. 3 ገጽ 93 ሲናገሩ "ሞልክ በሬ የሚመስል ቅርፅ ያለው (የበሬ ራስ) ሕፃናትን ለመውሰድ የተዘጉ ሁለት አይችያሉት ከስሩ ክፍት ቦታ ያለውን እሳት የሚቃጠልበት ነው"፡፡ በዘሌዋዊያን 18፡21 ስለሞሎክ የተሰጠው መግለጫ ተገቢ ካልሆነ የወሲብ ግንኙነት ጋር ስለሚያገናኘው ምሁራን ሕፃናቱ ለሞልኮ ለመሰዋዕነት የሚቀርቡ ሳይሆን ለዝሙት ተግባር በቤተ መቅደስ እንዲያገለግሉ የተሰጡ ናቸው ወደሚል ድምዳሜ አድርሷቸዋል፡፡ሐሳቡ ግን ከልምላሜ አምልኮ ጋር ከሚለው የሚስማማ ነው፡፡

▣ **"ምስሎች"** ቀጣዩን ሰንጠረዥ ይመልከቱ፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ ቅርጽ (*Tupos*)**

*Tupos* የሚለው ችግሩ ይህ ቃል በብዙ ቦታዎች ለተለያዩ ግልጋሎቶች ውሏል፡፡

1. ሙልቶንና ሚሊገን (*The vocabulary of the Greek New Testament* p 645)
   - ሀ. ሂደት
   - ለ. ዕቅድ
   - ሐ. ቅርጽ ወይም የጽሑፍ ሂደት
   - መ. ሕግ
   - ሠ. ዓረፍተ ነገር
   - ረ. የሰውነት አካል ቅርጽ
   - ሰ. አንድ ሰው ሕግን እንዲጠብቅ የሚደረግ ግፊትን ያጠቃልላል፡፡
2. ሎው እና ኒዳ *Greek Engilish Lexicon*, vol. 2, p 249
   - ሀ. ጠባሳ (ዮሐ 20፡25)
   - ለ. ቅርፅ/ምስል (የሐዋ 7፡43)
   - ሐ. ሞዴል (ዕብ 8፡5)
   - መ. ምሳል (1ቆሮ 10፡6, ፊሊ. 3፡17)
   - ሠ. ዋና አመልካች (ሮም 5፡14)
   - ረ. አይነት (የሐዋ 23፡25)

ሰ. ይዘት (የሐዋ 23፡25)

3. ሀሮልድ ኬ.ሙልቶን

ሀ. መልክት (ዮሐ 20፡25)

ለ. የምልክት ማሳያ

ሐ. ቅርጽ (የሐዋ 7፡43)

መ. ፎርሙሳ (ሮማ 6፡17)

ሠ. ቅርጽ (ሐዋ 23፡25)

ረ. ምስል (1ቆሮ 10፡6)

ሰ. ዓይነት (ሮሜ 5፡14, 1ቆሮ 10፡11

ሸ. ሞዴል (ዋና መንገድ) (የሐዋ 7፡44, ዕብ 8፡5)

ቀ. ሂደታዊ መንገድ (ፊሊ 3፡17, 1ተሰ 1፡7, 2ተሰ 3፡9 1ጢሞ 4፡12, 1ጴጥ 5፡3)

በዚህ ዓውድ ውስጥ (ቁጥር አንዱ) እጅግ በጣም የተሸለው ነው፡፡ ወንጌል ሁለቱንም ትምህርትንና የአኗኗር ዘይቤ አመልካች ነው፡፡ በክርስቶስ በነፃ የተሰጠን የደህንነት ስጦታ እንደ ክርስቶስ መመላለስም ይጠይቃል፡፡

**NASB (የተሻሻለው) ትርጉም ምዕ 7፡44-50**

**እንዳየው ምስል አድርጐ ይሰራት ዘንድ ሙሴን ተናግሮ እንዳዘዘው ፤የምስኮ ድንኳን በአባቶቻችን ዘንድ በምድረ በዳ ነበረች ፤ አባቶቻችንም ደግሞ በተራ ተቀብለው እግዚአብሔር በፊታቸው ያጣቸውን የአህዛብን አገር በያዙት ጊዜ ከኢያሱ ጋር አገቡአት እስከዳዊት ዘመንም ድረስ ኖረች፡፡ ኢያሱም በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ አግኝቶ ለያዕቆብ አምላክ ማደሪያ ያገኝ ዘንድ ለመነ፡፡ ነገር ግን ሰለሞን ቤት ሰራለት ነገር ግን ነቢዮ ሰማይ ዙፋኔ ነው ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት ለእኔ ምን አይነት ቤት ትሰራላችሁ ? ይላል ጌታ ወይስ የማርፍበት ስፍራ ምንድነው? ይህንንስ ሁሉ እጄ የሰራችሁ አይደለምን? እንዲሉ ልሁል የሰው እጅ በሰራችው አይኖርም፡፡**

7፡44 ይህ ክፍል የሚገኘው በዘፀ 25፡31፣ 36፡40 ላይ ነው፡፡ እነዚህ የማደሪያው ድንኳን ዝርዝር ዕቅዶች ለሙሴ የተገለጡት በሲና ተራራ ላይ ነው፡፡ የአዲስ ኪዳኑ የዕብራዊያን መልዕክት ስለሰማርያዊቱ ማደሪያ ወይም መቅደስ ይናገራል (8፡5-6፣ 9፡11፣ 23) በዚህም የምድራዊው መቅደስ የሰማያዊው ግልባጭ እንደሆነ ያሳያል፡፡ 7፡45 ይህ የሚሸፍነው እስራኤላዊያን ድል አድርገው በያዙበት (በኢያሱ ዘመን) (1400 ወይም 1250 ከክ.ል.በፊት) እስከ ዳዊት ዘመን ድረስ (1011 -971) 70 ከክ.ል.በፊት ይሪስን 973 ከክ.ል.በፊት የንግ 961 ከክ.ል.በፊት ብራይት)፡፡

▣ *"መንገዱ"* የ7፡43 የልዩ ርዕስ ሰንጠረዥ ይመልከቱ፡፡

7፡45 ይህ ጊዜ የሚያጠቃልለው ድል ከማድረግ እስከ ዳዊት ዘመን ድረስ ነው፡፡ (ይህም 1400 ወይም 1250) ወይም (1011 ዓ.ም እስከ 971/70 ዓ.ም Harrison, 973 ዓ.ም, Young; 961 ዓ.ም)

7፡46 ይህ የሚያንፀባርቀው 2ሳሙ 7ን ነው ይህም በጣም ወሳኝ መልዕክት ነው፡፡ የዳዊት ንጉሳዊነት መለኮታዊ መመስራትን ያሳያል፡፡

7፡47 "ሰለሞን ቤት ሰራለት" ይህ ክፍል የሚገኘው በ1ኛ ነገ 6፡8 እና በ2ኛ 1፡6 ላይ ነው፡፡

7፡48 ይህ ዓረፍተ ነገር ሰለሞን በ1ኛ ነገ 8፡27 እና 2ዜና 6፡18 ላይ ከሰጠው ዓረፍት ነገር ጋር ተመሳሳይ ነው

7፡49-50 ይህ ጥቅስ የተወሰደው ከኢሳ 66፡1-2 የሰብትዋጀንት ትርጉም ነው፡፡ ዋናው ነጥብ ግን ሰለሞን ህንፃው የፍጥረት አምላክ የሆነውን እግዚአብሔርን ሊይዘው እንዳልቻለ እንዳስተዋለ ነው፡፡

እነዚህ ጥቅሶች አህዛብ መካተት እንዳለባቸው ያመለክታሉ ከሆነም በመጠኑ የተሸፈነ ወይም የተጋረደ ይመስላል፡፡ ይሁን እንጂ ቤተ መቅደሱ ከእስራኤል ያልሆኑ ወገኖች ወደ ያህዌ የሚመጡበት እንደሆነ አይቷል (1ነገ 8፡41-43) ዓለም አቀፍ የወንጌል ተልኮ ለመጀመሪያ ጊዜ ያዩትና የሰበኩት ግሪክ ተናጋሪ አይሁዶች ሐዋርያት እንኳን የኢየሱስን ትምህርት ከመገንዘባቸው በፊት (ማቴ 28፡18-20፣ ሐዋ 1፡8)፡፡ እስጢፋኖስም ይህንን ሁኔታ በቁጥር 50 ላይ ያረጋገጠ ይመስላል፤

**NASB (የተሻሻለው) ትርጉም ምዕ 7፡51-53**
***ለእናንተ አንገተ ደንዳኖች ልባችሁና ጆሮአችሁ ሳልተገረዘ እናንተ ሁል ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ትቃወማላችሁ አባቶቻችሁ እንደተቃወሙት እናንተ ደግሞ ከነብያት አባቶቻችሁ ያላሳደዱት ማነው የፃድቁንም መምጣት አስቀድሞ የተናገሩትን ገደሉአቸው በመላእክት ስርዓት ሕግን ተቀበላችሁ ያልጠበቃችሁት እናንተም አሁን እርሱን አሳልፋችሁ ሰጣችሁት ገደላችሁትም፡፡***

7፡51 ***"አንገተ ደንዳኖች"*** እስጢፋኖስ የሚያነሳው ሙሴ ያዕቆብ ልጆች እንዴት እንደመሰላቸው ነው (ዘፀ 32፡9)፡፡

▣ ***"ልባችሁ ያልተገረዘ"*** ይህ የእብራዊያን ፈሊጣዊ አባባል አለመታመንን፣ እውነተኛ አለመሆን፣ እንዲሁም ዋጋ ቢስነትን ያሳያል (ዘሌ 26፡41፣ ኤር 4፡4፣ 9፡25-26፣ ሕዝ 44፡7)፡፡

▣ ***"ዶሮአችሁ ያልተገረዘ"*** ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን መልእክተኞች ለመስማትና ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆንን ያሳያል (ኤር 6፡10)፡፡

▣ ***"ሁል ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ትቃወማላችሁ"*** ይህ ከኢሳ 63፡10 ጋር በጣም ተመሳሳይነት አለው፡፡ በኢሳያስ ውስጥ የእግዚአብሔር ፍቅርና ታማኝነት ከልዩ ይታያል፡፡ 63፡9፣11-14 ነገር ግን የሕዝቡ ምላሽ ግን አለመታመን ነበር፡፡

7፡51ለ-52 ልክ እንደ ቀድሞው የእስራኤላዊያን አመራር ይህ አሁን ባለው የአይሁድ ሕዝቦች የእግዚአብሔርን መልዕክተኞች ገድለው እንደ ነበር አሁንም ደግሞ የአይሁዶቹ መሲሑን ገደሉት (3፡14፣ 5፡28)

7፡52 ***"የፃድቁንም"*** ይህ ለኢየሱስ እንደ ማዕረግ ስም ጥቅም ላይ የዋለ ነው 3፡14 እና 22፡14 ሙሉውን ማብራሪያ በ3፡14 ላይና በልዩ ርዕስ ላይ ይመልከቱ

7፡53 ***"በመላዕክት ስርዓት"*** ይህ የሚያመለክተው ከሰብትዋጀንቱ የተወሰደው በዘዳ 33፡2 ላይ ረቢዎች የሰጡት ትርጓሜ ነው፡፡ በዚህም እግዚአብሔር ለሙሴ በመልዕክት አማካኝነት ሕጉን እንዲሰጠ የሚያሳይና ገላ 3፡19 እና ዕብ 2፡2 ማረጋገጫ የሚሰጡበት ነው፡፡

▣ ***"ያልጠበቃችሁት"*** እስጢፋኖስ ምላሽ መስጠቱን "ስሙ" በማለት ይጀምራል ፤ ይህም የሚያሳየው በእብራይስጥ "Shema ፤ "እስራኤል ወይ ስማ" (ዘዳ 6፡4) የተባለውን ሐረግ ለማሳየት ነው፡፡ እስጢፋኖስ በኂላም ያዕቆብ (የኢየሱስ ወንድም) ሁለቱም አስረግጠው የሚናገሩት "ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ የምትሰጡ ብቻ አትሁኑ" በማለት ነው (ያዕ 1፡22-23) ኢየሱስ ማቴ 7፡24-27፤ ሉቃ 11፡48 ፤ ዮሐ 13፡17 ጳውሎስ ሮሜ 2፡13)፡፡

**NASB (የተሻሻለው) ትርጉም ምዕ 7፡54-60**
***ይህንም በሰሙ ጊዜ በልባቸው በጣም ተቆጡ ጥርሳቸውንም አፋጩበት መንፈስ ቅዱስንም ተሞልቶ ወደ ሰማይ ትኩር ብሎ ሲመለከት የእግዚአብሔርን ክብር ኢየሱስንም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየና እነሆ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየዋለሁ አለ በታላቅም ድምፅ እየጮሁ ጆሮአቸውን ደፈኑ በአንድ ልብ ሆነው ወደ እርሱ ሮጡ ከከተማውም ወደ ውጭ አውጥተው ወገሩት ምስክሮችም ሰብስበው ሳኦል በሚሉት በአንድ ጉበዝ እግር አጠገብ አኖሩት እስጢፋኖስም ጌታ ኢየሱስ ሆይ ነፍሴን ተቀበል ብሎ ሲጠራ ይወግሩት ነበር ተንበርክኮም ጌታ ሆይ ይህን አጥያት አትቁጠርባቸው ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮህ፡፡ ይህን ብሎ አንቀላፋ ሳኦልም በእርሱ መገደል ተስማምቶ ነበር፡፡***

7፡54 ***"በሰሙ ጊዜ"*** ይህ የሚያመለክተው ሸንጎውን መሆን አለበት (6፡15)

▣ .

| | |
|---|---|
| NASB | "በልባቸው በጣም ተቆጡ" |
| NKJV | "ከልባቸው በጣም ተቆጡ" |
| NRSV | "በጣም ተናደዱ" |
| TEV | "በጣም ተናደዱ" |
| NJB | "ተናደዱ" |

ይህ ያላለቀ ድርጊት ገላጭ ግስን አመልካች ነው፡፡ ቃል በቃል ሲተረጐም በጣም መቆጣት የሚል ትርጓሜ አለው (5፡33) የእስጢፋኖስ መልዕክት በእርግጠኝነት ለእንዚህ ሰዎች ደርሿቸዋል ነገር ግን ንሰሐ ከመግባት ይልቅ እንደተለመደው ወደ መጋፋትና ወደ መግደል ተሸጋገሩ (5፡33)፡፡

▣ ***"ጥርሳቸውንም አፋጩበት"*** ይህ የንዴት ምልክት ነው (ኢዮ 16፡9፣ መዝ 35፡16)፡፡

7፡55 ***"መንፈስ ቅዱስ . . . እግዚአብሔር ኢየሱስ"*** የስላሴ አካላት መጠቀሳቸውን ልብ በሉ 2፡32-33 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከቱ፡፡

▣ **"መንፈስ ቅዱስን ተሞልቶ"** ወንጌልን ለማወጅ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት የሚለው ሃሳብ የሐዋርያት ስራን ልዩ ያደርገዋል፡፡

በመንፈስ ቅዱስ ጉዳይ ላይ የመፅሐፍ ቅዱስ እውነት የሚታወቅባቸው፡-

4. የመንፈስ ስብዕና (ዮሐ 14፡16)
5. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት (1ቆሮ 12፡13)
6. የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ (ገላ 5፡22-23)
7. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች (1ቆሮ 12)
8. የመንፈስ ቅዱስ ሙላት (ኤፌ 5፡18)

እነዚህ ሁሉ ይልቅ የሐዋርያት ስራ የሚያተኩረው በቁጥር 5 ላይ ነው፡፡ የቀደመችው ቤተክርስትያን መሪዎች ወንጌልን በድፍረትና በኃይል ለመስበክ በግልፅ በተደጋጋሚ ኃይልን ተቀብለዋል፡፡ በእስጢፋኖስ ሁኔታ የስብከቱ ስኬት ህይወትን አስከፍሎታል፡፡ በሙላት ላይ ሙሉ ማብራሪያ ለማግኘት 2፡4 እና 3፡10 ይመልከቱ፡፡

▣ **"ትኩር ብሎ ሲመለከት"** ሉቃስ ይህንን ቃል ይወዳል (ሉቃ 4፡20፣ 22፡56፣ ሐዋ 1፡10፣ 3፡4፣ 6፡15፣ 7፣55፣ 10፡4፣ 11፡6፣ 13፡9፣ 14፡9፣ 23፡1) አይሁዶች ሲፀልዩ እንደሚያደርጉት እስጢፋኖስ ወደ ላይ ተመለከተ ነገር ግን ከመፀለይ ይልቅ እግዚአብሔር ሰማያትን ከፍቶ አሳየው፡፡

▣ **"የእግዚአብሔርን ክብር አየ"** እስጢፋኖስ ያየው እግዚአብሔርን ሳይሆን የእግዚአብሔር ክብር ነው፡፡ ማንም እግዚአብሔርን አይቶ በህይወት መኖር አይችልም (ዘፀ 33፡20)፡፡ (ኢዩ 19፡25-27) ልበ ንፁሐን አንድ ቀን እግዚአብሔርን የሚያዩት ኢየሱስ ተስፋ ሰጥቷል (ማቴ 5፡8) ልዩ ርዕስን ተመልከቱ ክብር 3፡13

▣ **"ኢየሱስንም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ"** ኢየሱስ በእግዚአብሔር ቀኝ መሆኑ መለኮታዊ ሃይሉንና ስልጣኑን ለማሳየት የተጠቀመበት ትምሳላዊ አነጋገር ነው፡፡ በዚህ ዘመን ያለው ሁሉንም ምንባብ ቃል ለቃል የመውሰድ ችግር ለመፅሐፍ ቅዱስ ያላቸውን እምነት ወይም መሰጠት እንዳለባቸው መታየቱ የሚያሳዝን ነው እግዚአብሔር በፍጥረቱ እራሱን የሚገልጥ አምላክ ነው ነገር ግን ይህን የሚያደርገው ሰዎች ሊረዱት በሚችሉት በመድራዊ ቋንቋ ነው፡፡ የእውቀት ውስን የሆነ የሰው ልጅ መንፈሳዊ ዓለም ሙሉ በሙሉ ሊረዳ አይችልም፡፡

እግዚአብሔርም ምሳሌዎችን ዘይቤዎችን ከባህላችንና ከልምምዳችን ጋር የሚገናኙ ነገሮችን ለመጠቀም ከእኛ ጋር ግንኙነት ያደርጋል፡፡ እነዚህ ነገሮች በእርግጠኝነት እውነት ናቸው ነገር ግን አሰልቺ አይደሉም

1. ያ መንግስተ ሰማይም 'ወደላይ' ነው፡፡
2. ያም እግዚአብሔር በዙፋኑ ላይ የተቀመጠበት ነው፡፡

የኢየሱስን እንክብካቤ እና ሃሳብ ለመግለፅ ነው፡፡ ባህላዊ ለሆኑ አገላለፆች በጣም መጠንቀቅ ይኖርብናል፡፡ በዚህ ዘመን ያሉ ምዕራባውያን ሁሉንም የተጻፋን ነገር ቃል በቃል ይቀበላሉ፡፡ ወይም በባህላዊው መንገድ መጽሐፉን ይረዱታል፡፡ እግዚአብሔር በፍጥረት በኩል ገልፆአል፡፡ ግን ይህንንም በምድር ላየ ባለው ሁኔታ በኩል ነው ራሱን የገለፀው፡፡ ይህ በትክክል የተካተተበት ነገር ነው፡፡ ውድቀት የሰው አፈጣጠር ሁሉም መንፈሳዊውን ዓለም አይገለጹትም፡፡ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ለመነጋገር ያመቸው ዘንድ የዚህን ዓለም ልምምዶችንና ባህላችንን ተጠቅሞበታል፡፡ እነዚህ ነገሮች እውነት ናቸው፣ ሁሉንም የሚያጠቃልሉ ባይሆኑም፡፡

7፡56 **"የሰው ልጅ"** እስጢፋኖስ ኢየሱስን ፃዲቁ (5፡52) ከሚለው ጋር ነው ያገናኘው፡፡ አድማጮቹም የኢየሱስን መሲህነት ሊያጡት (ሊስቱት) አይገባም (1) የሰው ልጅ የሚለው ቃል ሁለት የብሉይ ኪዳን አጠቃቀሞች አሉት ለአንድ ሰው የተለመደ ሃረግ ነው (ሕዝ 2፡1) (2) መለኮታዊ ስብዕናን ለመግለፅ (መሲሁን) ዳን 7፡13-14፡፡ ስለዚህ ለሰውም ሆነ መለኮትን የማመልከት አካሄድ አለው ለዚህ ነው ኢየሱስ ራሱን ለማስታወቅ የተጠቀመበት እንዲሁም ደግሞ ረቢዎች ቃሉን ለብሔራዊና ለወታደራዊ ጥቅም አልተጠቀሙበትም፡፡ ይህ እስጢፋኖስ የተጠቀመበት ኢየሱስ ከተናገረው ውጪ (ዮሐ 12፡34) ከሁለት መንገዶች አንደኛው አጠቃቀም ነው፡፡

7፡57-58 **"በአንድ ልብ ሆነው ወደርሱ ሮጡ"** እነዚህ አድማጮች ኢየሱስ የሚመጣው የሰው ልጅ ነው ብለው ተሳለቁበት እንደተሳደበ አመኑ (ዳን 7፡13) በአንድ አምላክ ብቻ ለሚያምኑት ለእንዚህ አይሁዶች እጅግ ሲበዛ ነው ሙሴ ስለመሳደብ እንደደነገገው በእስጢፋኖስ ላይ አደረጉበት (ዘሌ 24፡14-16፣ ዘዳ 13፡9) የእስጢፋኖስ ማረጋገጫ ወይ ትክክል ነው አልያም ሞት የሚገባው ተሳዳቢ ነው፡፡ ኢየሱስ ስለሚያስቀምጠው እውነት ምንም አይነት መካከለኛ ስፍራ የሚባል ነገር የለም (ይሐ 14፡6-9)፡፡

7፡57 **"በአንድ ልብ ሆነው ወደ እርሱ ሮጡ"** ሉቃስ የቀድሞዎቹን አማኞች ለመግለፅ የተጠቀመበት ቃል ነው (1፡14፣ 2፡46፣ 5፡12፣ 15፡25) በእስጢፋኖስ ላይ በመቆጣትና እርሱን በመቃወም ሸንጐ አንድ ሆኖ ነበር (18፡22ን ተመልከቱ) በአካያ የሚኖሩ አይሁዶች ጳውሎስን ተቃወሙት (19፡29) በኤፌሶን የሚገኙት አረማውያን በክርስትያን ላይ መነሳታቸው፡፡

7፡58 **"ከከተማ ወደ ውጭ አውጥተውት"** ኢየሩሳሌም ቅድስት ከተማ ስለነበረች ማንም ሰው በዚህያ አይገደልም፡፡

▣ **"ወገሩት"** በሮም ቅኝ አገዛዝ የነበሩት አይሁዶች የገንዘብ ቅጣት የማድረግ መብት አልነበራቸውም ይህ የሚያሳየው ሁል ጊዜ እውነት መፈፀም እንዳለባቸው ነው፡፡ የህዝብ አመፅ ወዲያው ሊቆም አይችልም ነበር፡፡

▣ **"ሳኦል በሚሉት በአንድ ጐበዝ"** በአብራውያን አካባቢ አንድ ሰው ዕድሜው እስከ 40 ዓመት ያለው ከሆነ ጐበክ ይባላል። ይህ የጠርሴሱን ሳኦል በኋላም ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ የተባለውን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየንበት ታሪክ ነው። ጳውሎስ እስጢፋኖስ ያደረገውን የብሉይ ኪዳንን ዳሰሳ የሰማ ምናልባትም በኢየሩሳሌም የሚገኘው በሲቪሲያውያን ምዕራብ ውስጥ ሰምቶት ሊሆን ይችላል (6፡9) አንድ ሰው ምናልባት ይህ ሁኔታ ሳኦል መጠራጠር የጀመረበትና ያንንም ለማስወገድ ክርስትያኖችን ለማሳደድ እነደሆነ ሊያስብ ይችላል።

7፡59 **"ጌታ ኢየሱስ ሆይ ነፍሴን ተቀበላት"** የኃላፊን ጊዜ ለማመልከት የተጠቀመበት ግስ ነው። እስጢፋኖስ ከኢየሱስ ጋር ለመኖር እንደሚሄድ ማመኑ ልብ በሉ እስጢፋኖስ ስለ ኢየሱስ መሰቀል ሰምቶ ይሆናል ወይም በዝርዝር ሰምቶ ሊሆን ይችላል ምክንያቱም ሁለት ተመሳሳይ ሃረጐችን ይጠቀማል (ቁ. 59 እና 60፣ ሉቃ 23፡34-46)።

ደቀመዛሙርት እንደፀለዩት እስጢፋኖስም ወደ ኢየሱስ ሲፀልይ ማስተዋሉ የሚያስደስት ነው (1፡24) ይሁን እንጂ በቀረው በአዲስ ኪዳን ፀሎት በኢየሱስ አማካኝነት በእግዚአብሔር አብ የሚቀርበው።

7፡60 **"ተንበርክኮም"** በድንጋይ መወገር በፍጥነት የሚካሄድ ድርጊት አልነበረም ክፍሉ እንደሚያስረዳው መውገሩ ብዙ ደቂቃዎችን እንደወሰደ ነው።

▣ **"በታላቅ ድምፅ ጮሀ"** ይህ እንግዲህ የኢየሱስን የመስቀል ላይ ልምምድ ይመስላል እነዚህ ቃላት ለህዝቡም ለያህዊም የተደረጉ ነበር። እነዚህ ቃላት በሳኦል ጆሮች ውስጥ አስተጋብቶ መሆን አለባቸው

▣ **"አንቀላፋ"** ይህ በመፅሐፍ ቅዱስ ያሉ መስዋት የሆኑትን የሚገልፅ ነው። ኢዮ 3፡13-14፣ መዝ 76፡5፣ 2ሳሙ 7-12፣ 1 ነገ 2-10፣ ኤር 51-39፡57፣ዳን 12፡12፣ ማቴ 27፡52፣ ዮሐ 11፡11፣ ሐዋ 7፡60፣ 13፡36፣ 1ቆሮ 15፡6 ፡18፡20፣ 1ተሰ 4፡13፣ 2ጴጥ 3፡4)።

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ለመርዳት ነው የተሰናዱት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋነኞቹን ጉዳዮች ለማጤን እንዲረዳ ነው። ሐሳብ ለማጫር እንጂ መደምደሚያ አይደሉም።

1. የእስጢፋኖስ ንግግር ዓላማው ምንድን ነው?
   ስለአይሁድ ምን ያሳያል?
   እነርሱ ለምንድን ነው የተናደዱት?
2. በቁጥር 37, ላይ በምን መልኩ ነበር ኢየሱስ ሙሴን የሚመስለው?
3. በኢሳያስ 66፡1-2 ያለው ጥቅስ 49-50 ባለው ላይ ለምንድን ነው? የተጠቀሰው? ጥቅሙስ ምንድን ነው?
4. እስጢፋኖስ ስለ ኢየሱስ ያው ራዕይ ጠቀሜታው ምንድን ነው?

# የሐዋርያት ሥራ 8

## የምንባቡ ክፍፍል በአዳዲሶቹ ትርጉሞች

| የተየመቅሶ[4] | አኪጀት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ሳኦል የቤ)ክርስቲያን አሳዳጅ | ሳኦል የቤ)ክርስቲያን አሳዳጅ | የወንጌል ስርጭት በሰማሪያ እና በባህር ዳርቻ ባሉ ሀገሮች | ሳኦል የቤ)ክርስቲያን አሳዳጅ | የእስቲፋኖስ መወገር እና የሳኦል አሳዳጅነት<br>7:55-8:3 |
| 8:1b-3 | 8: 1-3 | 8:1b-3 | 8:1b-2 | |
| | | | | 8:2 |
| | | | 8:3 | 8:3 |
| ወንጌል ለሰማሪያ ሰዎች ተሰበከ | ክርስቶስ ለሰማሪያ ተሰበከ | | ወንጌል ለሰማሪያ ሰዎች ተሰበከ | ፊሊጶስ በሰማሪያ |
| 8:4-8 | 8:4-8 | 8:4-8 | 8:4-8 | 8:4-8 |
| | የጠንቋዩ እምነት | | | የስምኦን ጥንቆላ |
| 8:9-13 | 8:9-13 | 8:9-13 | 8:9-13 | 8:9-13 |
| | የጠንቋዩ ሃጢያት | | | |
| 8:14-24 | 8:14-24 | 8:14-24 | 8:14-17 | 8:14-17 |
| | | | 8:18-19 | |
| | | | 8:20-24 | |
| 8:25 | 8:25 | 8:25 | 8:25 | 8:25 |
| ፊሊጶስ እና ኢትዩያዊው ጃንደረባ | ክርስቶስ ለኢትዩጵያውያን ተሰበከ | | ፊሊጶስ እና ኢትዩጵያዊው ባለስልጣን | ፊሊጶስ ኢትዩጵያዊውን አጠመቀው |
| 8:26-33 | 8:26-40 | 8:26-40 | 8:26-30 | 8:26-33 |
| | | | 8:31-33 | |
| 8:34-40 | | | 8:34-37 | 8:34-40 |
| | | | 8:38-40 | |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (ከ "**መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ**" **ገጽ** vii)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

*ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።*

*ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።*

1. ምንባብ አንድ
2. ምንባብ ሁለት
3. ምንባብ ሦስት
4. ወ.ዘ.ተ…

**የቃልና እና የጥምር ቃል ጥናት**

> **NASB (የተሻሻለው) ትርጉም፡ 8፡1a**
> [1]**ሳኦልም በእርሱ መገደል ተስማምቶ ነበር፡፡**

**8፡1 ሳኦል በእርሱ መገደል ተስማምቶ ነበር"** ይህ ዓረፍተ ነገር የምዕራፍ ሰባት ማጠቃለያ ነው፡፡ ሐዋራያው ጳውሎስ ይህንን የራሱን የቀደመ ታሪክ በእፍረት ያስታውሰዋል፡፡ (ሐዋ 22፡20፣1ቆሮ 15፡9፣ ገላ 1፡13-23፣ ፊሊ. 3፡6፣1ጢሞ 1፡13 ይህንን ምዕራፍ ከሐዋርያት ሥራ 26፡10 ጋር ያዛምዱት፡፡ ይህም ሐዋርያው ጳውሎስ ክርስቲያኖች ለሞት አልፈው እንዲሰጡ የተባበረበት ምንባብ ነው፡፡

> **NASB (የተሻሻለው) ትርጉም፡ 8፡1-3**
> [1b]**በዚያን ቀንም በኢየሩሳሌም ባለች ቤተክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ሆነ ሁሉም ከሐዋርያትም በቀር ወደ ይሁዳና ወደ ሰማሪያ አገሮች ተበተኑ፡፡ በፀሎትም የተጉ ሰዎች እስጥፋኖስን ቀበሩት ታላቅ ልቅሶም አለቀሱለት ሳውል ግን ቤተክርስቲያንን ያፈርስ ነበር ወደ ሁሉም ቤት እየገባ ወንዶችንም ሴቶችንም እየጐተተ ወደ ወህኒ አሳልፎ ይሰጥ ነበር፡፡**

▣ **"በዚያን ቀንም በኢየሩሳሌም ባለች ቤተክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ሆነ"** ይህ የሚያመለክተው በእየሩሳሌም ያለችው ቤተክርስቲያን በፍጥነት ከማደጓ የተነሣ የአይሁድ መሪዎች ይልቁንም ሰዱቃውያን ያስነሱትን ስደት ለማመላከት የተፃፈ ነው፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ ይህንን ስደት ቤተክርስቲያኑን ለማሳደግ ተጠቅሞበታል፡፡ (ሐዋ.ሥ 1፡8) ያንብቡ፡፡ ሐዋርያት ስራ 1፡8 የሚፈፀመው በሐዋርያት ሥራ 1፡8 ላይ በሚገኘው መንገድ ነው፡፡

የሐዋርያት ሥራን የፃፈው ሉቃስ "ኤክሌሽያ" የሚለውን የግሪኩን ቃል በክርስቶስ አካል ውስጥ ያሉትን የአማኞችን ስብስብ አብራርቶበታል፡፡ ይህም እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን የገባውን ቃል ኪዳን ተፈፃሚነት እንዳለው ያሳያል፡፡ ኤክሌሽያ የሚለው ቃል ("ጉባኤ") በሚል በግሪኩ ቃል ተተክቷል በዕብራይስጡ "ኳል" የሚል ስያሜ አለው፡፡ (ሐዋ. 7፡ 38) በመሆኑም ይህ ቃል በኢየሩሳሌም ለነበሩ ለአማኞች ስብስብ ሲያገለግሉ መመልከት ይቻላል፡፡

ፀሐፊው ሉቃስ "ታላቅ" የሚለውን ቃሉ በፃፋቸው ሁለት መፅሐፍቶች ውስጥ ተጠቅሞአል፡፡ ይህም ሃያ አምስት ጊዜ በሉቃስ ወንጌል እና ሃያ ዘጠኝ ጊዜ በሐዋራያት ስራ መፅሐፍ ውስጥ እናገኛለን፡፡ በዚህ በሐዋርያት ሥራ ስምንት "ታላቅ" የሚለውን ቃል የተጠቀመበትን ቦታ እንመልከት፡፡

1. ታላቅ ስደት ቁ.1
2. ታላቅ ሃዘን ቁ.2
3. ታላቅ ድምፅ ቁ.7
4. ታላቅ ነኝ ቁ.9
5. እስከ ታላላቆች ድረስ ቁ.10
6. ታላቅ ተአምራቶች ቁ.13

▣ **"ሁሉም ከሐዋርያት በቀር"** በኢየሩሳሌም የነበሩ አማኞች በስደት በአራቱም አቅጣጫ መበተናቸውን ያመለክታል፡፡ ነገር ግን ሐዋሪያቶች በአይሁድ ሐይማኖት ተፅእኖ ሥር በመሆን መንፈስ ቅዱስ ከወረደ በኃላም ወንጌል ያደርሱ የነበረው በኢየሩሳሌም፣ እግዚአብሔርን ለሚፈሩ ለተባሉ እና ለአይሁድ ብቻ መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡

▣ **"ወደ ይሁዳና ወደ ሰማርያ ሀገሮች ተበተኑ"** ይህ በሐዋራያት ሥራ 1፡8 ላይ የተነገረውን የታላቁ ተልዕኮ የትንቢት ቃል ፍፃሜ ነበር፡፡ እግዚአብሔር በስደት ቤተክርስቲየን እንድትፈርስና እንድታድግ እና ወንጌልን እንድታደርስ ፈቃዱ ነበር፡፡ ነገር ግን ቤተክርስቲያን ይህንን ለመቀበል መቸገሯን እንገነዘባለን፡፡

**8፡2 "በፀሎት የተጉ እስቲፋኖስን ቀበ\ት"** እነዚህ በአይሁድ መቅደስ በየዕለቱ በፀሎት የሚተጉትን ሰዎች ለማመልከት ነው፡፡ (ሉቃ 2፡25) ወይም እነዚህ ሰዎች የአይሁድ ክርስቲያን ሆነው ነገር ግን ያለአግባብ የሆነውን የሮማውያንን ጭቆና እና ስደት የሚቃወሙ መንፈሳዊ ሰዎች ናቸው፡፡ እነዚህ መንፈሳዊ ሰዎች ሰማዕት የሆነወን እስቲፋኖስን ለመቅበር ፈቃድ ቢያገኙም ነገር ግን ድምፃቸውን አሰምተው ሊያለቅሱ አልተፈቀደላቸውም ነበር፡፡ ይህን የቀብር ሥነ ሥርዓት በማድረግ፡- (1) ተቃውሞአቸውን አሰምተዋል (2) የመንግስት ሕግ እንደተጣሰ አመልክተዋል፡፡

8፡3 **“ሳኦል ግን ቤተክርስቲያንን ያፈርስ ነበር”** በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተፃፈው ግስ የሚያመለክተው ጠቅለል ያለን ሃሳብ ነው፡፡ ይህ ማለት ቀድሞ የተጀመረን ድርጊት ያሳያል (NKSV,NRSV,NSB) ወይም በአሁኑ ጊዜ የተደረገ ድርጊትን ያመለክታል (NKSV, NRSV, TEV)

▣ **“ያፈርስ ነበር”** የሚለው ቃል የሚያመለክተው በአውሬ የተቀደደ ሰውነትን ለማመልከት የሚጠቅም ቃል ነው፡፡
ይህ ቃል በግርኩ እንስሳትን ያመለክታል መዝ 79፡13 እና በጦርነት መሸነፍ ኤር 28፡2 እና 31፡18 እንደሁም ሐዋሪያው ጳውሎስ እስቲፋኖስ የተናገረውን የእውነት ቃል ለማሸነፍ ትግል ቤተክርስቲያንን ያፈርስ ነበር፡፡ (ሐዋ 9፡1, 13, 21; 22፡ 4, 19፡ 26፡10-11; 1ቆሮ15፡9, ገላት 1፡13 ፊሊ.3፡6፡ 1ጢሞ1፡13)

▣ **“ወደ ሁሉም ቤት እየገባ”** ይህንን ሐረግ በሁለት መንገድ መረዳት ይቻላል፡፡ (1) ሐዋርያው ጳውሎስ ሐዋርያቱ የሚገኙበትን ያወቀ ይመስላል (2) ቤተክርስቲያን በዚህ ጊዜ በግለሰቦች ቤት እንደነበረች ያሳያል፡፡
እንግዲህ በዚህ በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ክርስቲያኖች ስብሰባቸውን በሦስት በተለያዩ ቦታዎች ያደርጉ ነበር፡፡ (1) በምኩራብ በየሰንበቱ (2) በመቅደስ በበዓልና በመባቻ የፀሎት ቀኖች (3) ቤታቸውን ለሰንበት አምልኮ በሰጡ መንፈሳዊ ሰዎች ቤት አምልኮ ይካሄድ ነበር፡፡

▣ **“ወንዶችም ሰቶችንም እየጐተቱ”** እየተጐተተ የማለው ግስ የሚያመለክተው ሰይጣን አንድ ሦስተኛ የሚያህሉ ክዋክብትን ከሰማይ ወደ ምድር እየጐተተ መጣሉን ከሚያመለክት ሃሳብ ጋር አንድ ዓይነት ነው፡፡ በሐዋርያት ሥራ መፅሐፍ ይህ ሃሳብ ብዙ ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ (ሐዋ 8፡3 14፡19 17፡6) ሐውርያው ጳውሎስ ቀድሞ አሳዳጅ መሆኑን በቁጭር ይተርካል (ሐዋ 26፡10) ወንዶችንም ሰቶችንም የሚለው ሐረግ ቤተሰብን መበተኑ ከዚያም ባለፈ በማሰር፣በመግደል ሥራ ላይ የተሰማራ እንደነበር የሚናገር ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ከሁሉ የማንስ በማለት ስለ ራሱ ተናግሮአል፡፡ “ከቅዱሳን ሁሉ በማንስ” (ሐዋ 9፡1, 21; 22፡4,19፡ 26፡10,11; 1ቆሮ 15፡9; ገላ 1፡13 23 1ጢሞ 1፡13) በዚህም ምክንያት ነው ራሱን “ከቅዱሳን ሁሉ በማንስ” ብሎ የጠራው (1ቆሮ 15፡9, ኤፌ 3፡8)፡፡

> **NASB (የተሻሻለው) ትርጉም፡ 8፡4-8**
> ***የተቀሩትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ ፊሊጶስም ወደ ሰማሪያ ከተማ ወረደ ክርስቶስን ሰበከላቸው ሕዝቡም የፊሊጶስን ቃል በሰሙ ጊዜ የተናገረውንም ምልክት ባዩ ጊዜ በአንድ ልብ አደመጡ፡፡ እርኩሳን መናፍስት በታላቅ ድምፅ እየጮኹ ከብዙ ሰዎች ይወጡ ነበርና ብዙም ሽባዎችና አካሶች ተፈወሱ በዚያችም ከተማ ታላቅ ደስታ ሆነ፡፡***

8፡4 **“የተበተኑትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ”** ይህንን ወንጌል በመዞር የሰበኩትን በዚህ ምንባብ ሐዋርያት ሳይሆኑ የአይሁድ ክርስቲያኖች መሆናቸው ግልፅ ነው፡፡ እንግዲህ ወንጌልን ሚሲዮናዊ በመሆን የሰበኩት ሐዋርያት ሳይሆኑ የተሰደዱ ክርስቲያኖች ናቸው፡፡) እስቲፋኖስ፣ፊሊጶስ ወዘተ…
*ቃሉን እየሰበኩ የሚለው ወንጌሉን ቢባል የትርጉም ለውጥ አይኖረውም (ይህ ታላቁን ተልዕኮ ነው፡፡ ማቴ 28-20)*

8፡5 **“ፊሊጶስ”** ይህ ሰው ከተመረጡት ሰባት ዲያቆናት መሃከል አንዱ ነበር (ሐዋ 6፡5) በሦስት የተለያዩ የወንጌል ስርጭት ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ (1) ለሰማሪያ ሰዎች ወንጌልን ሰብኳል፤ (2) ለኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ወንጌልን ሰብኳል፤ (3) በፋልስጎኤም የባህር ዳር አገሮች ወንጌልን አድርሷል፡፡

▣ **“ወደ ሰማሪያ ከተማ ወረደ”** ይህች ከተማ ባሁኑ ጊዜ በቀድሞ ስሟ አትታወቅም ነገርግን “ሴኤባአስተኢ” በመባል ትታወቃለች፡፡ ይህች ከተማ ሮማውያን በሚገዙበት ዘመን የዚህች ከተማ ስም የአውራጃ ስም ነበረች፡፡ ዋና ከተማዋም ሴኬም ነበር፡፡ ይህች ከተማ የጥንት አጠራb የስምኦን ማአጉስ ቤት ትባል ነበር፡፡ ይህም የዚህ አገር ነዋሪ የነበረው ጀስቲን ማርቲን የተባለው ሰው በፃፈው ፅሑፍ የሚገኝ ነው፡፡

▣ **“ክርስቶስን ሰበከላቸው”** ሰማሪያውያን በአይሁድ ሕዝብ የተጠሉ ነበሩ፡፡ ምክኒያቱም ከአህዛብ ጋር ዘራቸው ተዳቅሏል፡፡ ይህ 722 ከክ.ልደት በፊት በአሶር ንጉሥ ተማርከው በነበረንት ጊዜ በሰሜን ከነበሩት አስሩ ነገዶች እነዚህ ሰማሪያውያን ከአህዛቦች ጋር ጋብቻ ፈፅመው ነበር (2ነገ 17፡24-41)፡፡
ኢየሱስ እነዚህን ሰማሪያውያንን አገልግሏል (ዩሐ 4፡) ኢየሱስ መሲህ መሆኑን ሰማሪያዊት ለሆነች ሴት ገልጧል፡፡ ፊሊጶስም ለሰማሪያ ሕዝብ መሲሁን ሰብኳል፡፡ ይህ መሲህ አዲስን መንግስትና አሰራርን የሚመሰርት መሆኑን አሳይቷል፡፡ (የኢየሱስ የመጨረሻ ቃሉ ለሰማሪያ ወንጌል እንዲሰብክ ነበር (ሐዋ 1፡8)፡፡

8፡6 **“በአንድ ልብ”** ሉቃስ ይህንን ቃል በብዛት ይጠቀምበታል (ሐዋ 1፡14)፡፡

▣ **“ቃሉንም በሰሙ ጊዜ ያደርጋት የነበረውንም ምልክት ባዩ ጊዜ”** እነዚህ ተዓምራቶች የፊሊጶስን ስብከት የሚያረጋግጡ ነበሩ፡፡ እነዚህም ተዓምራቶች ኢየሱስ፣ሐዋሪያቱ፣የተላኩት ሰባዎቹ ሰዎች አድርገውት ነበር፡፡

8፡7 *አጋንንቶች በሰው ውስጥ ማደራቸውን ይህ የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል ያረጋግጥልናል፡፡ ለተጨማሪ ግንዛቤ የሚከተለውን ያንብቡ* (Merrill F. unger's two books: [1] *Biblical Demonology* and [2] *Demons in world Today*) *ሐዋ* 5፡16

> **NASB (የተሻሻለው) ትርጉም፡ 8፡9-13**
> ***ሲሞን የሚሉት አንድ ሰው ግን እኔ ታላቅ ነኝ ብሎ እየጠነቆለ የሰማሪያን ወገን እያስገረመ ቀድሞ በከተማ ነበር ከታናናሾች ጀምሮ እስከ ታላላቆች ድረስ ታላቁ የእግዚአብሔር ኃይል ይህ ነው እያሉ ሁሉ ያደምጡ ነበር፡፡ ነገር ግን ስለ እግዚአብሔር መንግስትና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም እየተሰበከላቸው ፊልጶስን ባመኑት ጊዜ ወንዶችም ሴቶችም ተጠመቁ፡፡ ሲሞንም ራሱ ደግሞ አመነ ተጠምቆም ከፊሊጶስ ጋር ይተባበር ነበር የሚደረገውንም ምልክትና ድንቅ ተአምራት ባየ ጊዜ ተገረመ፡፡***

8፡9 “*ሲሞን የሚሉት አንድ ሰው*” *ሲሞን በጥንቆላ ስራ ለይ ተሰማርቶ የነበረ ሰው ነበር በኃላ ግን ፊሊጶስ በሰበከው ወንጌል ተማርኮ አማኝ ሆኖአል ነገር ግን ከልቡ አማኝ ለመሆን ማረጋገጫ የለም ወይም ትርፉን ለማግኘት የእግዚአብሔርን ኃይል ፈልጉ ሊሆን ይችላል፡፡)ሐዋ* 8፡24) *ለተጨማሪ ገለፃ የሚከተለውን አንብቡ* (The zondervan pictorial Encyclopedia of the Bible, vol 6, pp. 442-444)፡፡

▣

| | |
|---|---|
| NSSB, NRSV | **"ጥንቆላ"** |
| NKKSV, TEV | ***"መናፍስት ጠሪ"*** |
| NIB | **"የጥንቆላ ተግባር"** |

> **ልዩ ርዕስ፡ "ጥንቆላ"**
>
> በጥንት አባቶቻችን ጊዜ ሰዎች በጣምራና በግል በመሆን የተለያየ የጥንቆላ ስራ ይሰሩነበር፡፡
> 1. ከለዳውያን በክዋክብት ቆጠራ የጥንቆላ *ሥራ* ይሰሩ ነበር፡፡)ዳንኤ 1፡20 2፡2 10 27 4፡7 9 5፡11 *ማቴ* 2፡1 716)፡፡ ሄሮድስ ክዋክብት ቆጣሪዎችን ያስጠንበት ምክኒያት የክዋክብትን እንቅስቅሴ በማንበብ ስለ ወደፊት ትንቢት ይናገራሉ የሚል ከፍተኛ እምነት በሕብረተበቡ ውስጥ ስለነበር ነው፡፡
> 2. በዚያን ጊዜ በግሪክ የፍልስፍና ምጥቀት ብዙዎች የሚያምኑበት ፓይታጐረስ የሚባል የሂሣብ ፍልስፍና የተጀመረበት ወቅት ነበር
> 3. በትውልዶች መሐከል የጥንቆላን *ሥራ* የሚሰሩ ሰዎች ይኖራሉ (ዘፍ 41፡8፤24 ዘፀ 7፡11፤22 8፡7፤19፤ 9፡11) እነዚህ ሰዎች የእርኩስ መንፈስን ኃይል ለችግሮቻቸው እንደሚጠሩ ይናገራሉ፡፡
>    *ሀ.* የወደፊቱን ክስተት ይተነቢያሉ፡፡
>    ለ. የወደፊቱን ክስተት እንበሚቆጣጠሩ ይናገራሉ፡፡
>    ሐ. ስለወደፊቱ የሚነገረውን ይተረጉማሉ
>    *መ.* እርግማንንና በረከት በግለሰቦችና በሀገር ላይ ይናገራሉ
> 4. የጥንቆላ *ሥራ* ለማህበረሰብ አጠቃላይ ኑሮ ላይ አደገኛ ጫናን ይፈጥራሉ)ሐዋ 8፡9-11
> 5. እውነተኛ ጠንቋዮች ሃላፊነታቸውን የማይወጡ ሌሎች ጠንቋዮችን ይቀጣሉ፡፡ ሐዋ. 13፡ 6፣ 8፣ 19፡13
> 6. የወንጌል ሃይል በጳውሎስ አገልግሎት ተገልጧል፡፡ (ሐዋ 19፡19) ጠንቋዮችም ወደ ክርስቲያን ልባቸውን አዘንብለዋል፡፡
> 7. ለተጨማሪ ዕውቀት የሚከተለውን አንብቡ
>    *ሀ. Susan Garrett, The Demise of the Devil*, Fortress, 1989
>    **ለ.** *Merrill unger, Biblical Demonology*, Scripture press, 1967
>    *ሐ. Hendrik Berkhof, Christ and the powers*, Herald Press, 1977
>    *መ. Waller wink, Naming the power*, Fortress press, 19184
>    *ሠ. Clinto Arnold, Three crucial questions About spiritual warfare*, Baker 1997

8፡10 "***ታላቁ የእግዚአብሔር ሐይል እያሉ ያዳምጡት ነበር***" ይህ ሰው እንደ አምላክ "ዙስ" በመባል የሚታወቀውን የጣኦት ስያሜ አግኝቶ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ በአረማውያን ቋንቋ “ታላቅ የአምላክ ኀይል” በመባል ይታወቃል፡፡ ሲሞን በጥንቆላ ስራው በዙሪያው ያሉተን ሁሉ አስደንቋቸው ነበር፡፡ በተጨማሪም ራሱን ያሳተ ሰው ነበር፡፡

8፡12 “***አመነ***” ልዩ ትኩረት የሚያሻው የሚለውን ይመልከቱ ዮሐ“3፡16”

▣

| | |
|---|---|
| NAIB | ***“የምስራቹ ቃል መሰበክ”*** |
| NKJS | ***“የተሰበኩት ነገሮች”*** |
| NRSV | ***“የምስራቹ ቃል እየታወጀ ነበር”*** |
| NRSV | ***“የምሰራቹ ቃል መልእክት”*** |

ወንጌል የግሪኩ ቃል "ኢቫንጀላይዞ" evangelize ይህም የሁለት ቃላት ጥምር ነው መልካም (ev) እና መልእክት (angelizo) ከዚህም የእንግሊኛው ቃል ኢቫንጀሊዝም ( evangelism ) የሚለው ተገኝቷል፡፡ ፊሊጶስ ይህንን ወንጌል ለሰማሪያ ነዋሪዎች በማወጁ ብዙዎች ሊያምኑ ችለዋል፡፡

▣ **"ስለ እግዚአብሔር መንግስት"** ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርዕስ ሐዋ 1፡3 ይመልከቱ፡፡

▣ **"የኢየሱስ ክርስቶስ ስም"** ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርዕስ ሐዋ 2፡21 ይመልከቱ፡፡

▣ **"ተጠመቁ"** ሐዋ 2፡38 ያንብቡ፡፡

▣ **"ሴቶችንም ወንዶችንም"** በሁለት መንገድ ልንተረጉመው እንችላለን፡፡
1. ጳውሎስ ያስድድ የነበረው ጸታ ሳይለይ ነበር፡፡ ይህም ወንጌል ሴቶችንም ወንዶችንም ያድን እንደነበረ አመልካች ነው፡፡
2. በአይሁድ እምነት የወንዶችን ግርዘት ሥነ ሥርዓት በማክበር ቀዳሚዎች ነበር፡፡ ነገር ግን በወንጌል ወንዶችም ሴቶችም ተሳታፊዎች መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

8፡13 "ሲሞን አመነ" በርካታ አብያተክርስቲያናት "አመነ" ወይም "እምነት" የሚለውን ቃላ በግርድፉ ሳይተረጉሙ ይናገሩታል፡፡ ነገር ግን በአዲስ ኪዳን (ዮሐ. 8፡13) ፊፅሞ የተለወጠ ህይወት ከመያዝ ጋር ያነሰ እንድምታ ተሰቶት እናነባለን፡፡
የመጀመሪያው እምነታቸውን ሁሉን ማሟላታችንን አይናገርም (ማቴ 13፡1-9፣ 10-23፣ 24፡13) ነገር ግን ቀጣይነት ያለው መታዘዝ ከክርስቶስ ጋር ያለንን እውነተኛ ሕብረት ያመለክታል፡፡
ከፊሊጶስ ጋር የተባበር ነበር"
1. ሰምቷል ቁ. 6-7፣ 12
2. አይቷል ቁ. 6-7፣ 13
3. አምኗል ቁ. 13
4. ተጠምቋል ቁ. 13
5. ከፊልጶስ ጋር ተባበረ ቁ. 13

**NASB (የተሻሻለው) ትርጉም፡ 8፡ 14-24**

**በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያት የሰማሪያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንደተቀበሉ ሰምተው ጴጥሮስንና ዮሐንስን ሰደዱላቸው፡፡ እነርሱም በወረዱ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ እንጂ ከእነርሱ በአንድ ላይ እንኳ ገና አልወረደም ነበርና በዚያን ጊዜ እጃቸውን ጫኑባቸው መንፈስ ጫኑባቸው መንፈስ ቅዱስም ተቀበሉ ሲሞንም በሐዋርያት እጅ መጫን መንፈስ ቅዱስ እንዲሰኝ ባየ ጊዜ ገንዘብ አመጣላቸውና እጄን የምጭንበት መንፈስ ቅዱስን ይቀበል ዘንድ ለኔ ደግሞ ይህን ስልጣን ስጡኝ አለ ጴጥሮስ ግን እንዲህ አለው የእግዚአብሔርን ስጦታ በገንዘብ እንድታገኝ አስበሃልና ብርህ ከአንተ ጋር ይጥፉ፡፡ ልብህ በእግዚአብሔር ልት የቀና አይደለምና ከዚህ ነገር ዕድል ወይም ፈንታ የለህም እንግዲህ ስለዚህ ክፋትህ ንሰሃ ግባ ምናልባትም የልብህን አሳብ ይቅር ይልህ እንደሆነ ወደ እግዚአብሔር ለምን በመራራ መርዝና በዓመፅ አስራት እንዳለህ አይሃለሁና፡፡ ሲሞንም መልስ ካላችሁት አንዳች እንዳይደርስብኝ እናንተው ወደ ጌታ ለምኑልኝ አላቸው፡፡**

8፡14 **"በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያት የሰማሪያም ሰዎች የእግዚአብሔርን ጊዜ ልቀመዛሙርቱ ቃላ እንዳትቀበሉ ሰምተው ጴጥሮስንና ዮሐንስን ሰደዱላቸው"** ኢየሱስ በምድር በነበረበት ጊዜ ለደቀ መዛሙርቱ ለሰማሪያም ሰዎች ወንጌል መስበክ ክልክሉ ነበር፡፡ (ማቴ 10፡5) በተመሳሳይም ሐዋርያትም ቢሆን ከመንፈስ ቅዱስ መውረድ በኋላም ለሰማሪያ ሰዎች ወንጌልን ከመስበክ አይፈቀዱም ነበር ምክንያቱም ከዚህ ቀደም የነበረው የዘር መድሎ ጥላቻ በአይምሮአቸው ስለነበረ ነው፡፡ ነገር ግን በሐዋ 1፡8 ላይ ወንጌል በኢየሩሳሌም በይሁዳ ብቻ ሳይሆን በሰማሪያም ቢሆን መስበክ እንዳለበት ኢየሱስ ከተናገረው የመጨረሻ ቃሎቹ መሃከል ነበር፡፡ ይህንን የተስፋ ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ ፊሊጶስ በሰማሪያ ወንጌል በመስበክ አከናውኗል፡፡

በኢየሱስ ማመን የእግዚአብሔርን ቃል እንደመቀበል ይቆጠራል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል የሚለው ሐረግ ደግሞ ብዙ ነገሮችን ይወክላል፡፡
1. እግዚአብሔር የሰውን ልጅ የሚገናኝበትን መንገድ ያሳያል፡፡
2. የእግዚአብሔርን ሕግ እርሱም መፅሐፍ ቅዱስን ያመለክታል፡፡
3. የእግዚአብሔርን ልጅ)ቃል ነበር… ዩሐ 1፡1) እርሱም እግዚአብሔር ራሱን ለአለም የገለጠበትን መንገድ ያሳያል (ዕብ 1፡3)፡፡

ሐዋርያው ጴጥሮስ እና ዩሐንስ ለሰማሪያ ሰዎች መላካቸው ትልቅ ፋይዳ ነበረው ጴጥሮስ የሐዋርያት መሪ በመሆን የታወቀ ሰው ነበር፡፡ዩሐንስ ደግሞ በሰማሪያ ሰዎች ላይ የሰማይን እሳት ለመጥራት የፈለገ ሰው ነበር፡፡ (ሉቃ 9፡54)

8፡15 **"እነርሱም በወረዱ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ ፀለየላቸው"** ከሐዋርያት ሥራ መፅሐፍ ስለደህንነት የስነ መለኮት ትንተና ለመስጠት አስቸጋሪ ነው፤ የሚከተሉትን ምክንያቶች እንመልከት፤ አንዱ ምንባብ ውስጥ ያለው

ክስተት ክሌላኛው በመለየቱ፣ መንፈስ ቅዱስ በዚህ ምዕራፍ ማረጋገጫውን የሰጠ በመሆኑ እርሱም እግዚአብሔር የሰማሪያን ሰዎች እንደተቀበላቸው።

እኔ እንደማስበው የጴንጤ ቆስጤ ቀን እግዚአብሔር የተለያዩ ነገዶችንና በተለያዩ ስፍራ ያሉትን ህዝቦች በማገናኘት የአይሁድ አማኞች ቤ/ክን ለሆነችው ህብረት አንድ አዲስ ሕዝብ እየተቀበለ ያለ ይመስላል።

8:16-17 በዚህ ምንባብ ላይ የሚገኘውን ክስተት ይመልከቱ)ሐዋ 2:38) የመንፈስ ቅዱስ ልዩ አሰራሩን መመልከት ይቻላል። (1) ሐዋ 2:38 የመንፈስ ቅዱስ ስራ በደህንነት ስራ ላይ ይመልከቱ፤ (2) ሐዋ 8:16 የመንፈስ ቅዱስ ስራ በመንፈስ እንቅስቃሴ በሆኑ ልምምዶች ይመልከቱ።

በሐዋርያት ሥራ 2 ላይ የተከሰተው ዓይነት የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ዓይነት ነው በሰማርያም የተከናወነው። ይህ ለእነርሱ ጥቅም ብቻም አልነበረም። ግን በይበልጥ ለአይሁድ ማህበረሰብ ነበር። ይህም እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ ሰማሪያውያንን መቀበሉን ሲያሳያቸው ነው። ይህ ማለት ደህንነት ሁለት ደረጃዎች አሉት ማለት ግን አልነበረም።

ፊሊጶስ በሰማሪያ የመንፈስ ቅዱስን ስራ ከመስበኩ በፊት ጴጥሮስና ዮሐንስ ለዚህ ልምምድ ጀማሪዎች መሆናቸውን እንገነዘባለን። ይህ ደግሞ የፊሊጶስን ስብከት እውነት ስላልነበር ምንም አይነት ምልክት አልተከተለውም ማለት አይደለም። (ቁ 13) ጴጥሮስና ዮሐንስ የሰማርያውን ጴንጤቆስጥ ፈልገውታል። ይህ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። ምክንያቱም የመሮ አለቃው ቆርኔሌዎስም ተመሳሳይ ነገር ገጥሞታል። ጴጥሮስ እግዚአብሔር የሮማውን መቶ አለቃ እና ቤተሰቡን መቀበሉን አረጋግጦለታል። ወንጌል ለሁሉም ሰዎች ነው። ይህም ታላቅ ነገር ነው በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የተገለጠው።

8:16 ይህ የሰማሪያውያን ባለሃምሳ ሊባል ይችላል።

8:17 እጅን በሌሎች ላይ መጫን እንዳለብን በዝርዝር የሚያስረዳ ምንባብ አይደለም። ነገር ግን የስልጣን እና የሃይል መቀበያ መንገድ ሆኖ በዚህ ሐረግ ላይ ይገኛል።

8:20 የስነመኮት ጥያቄ የሚያስነሳ ዐረፍተ ነገር ነው። የጴጥሮስን ንግግር እንደእርግማን ወይም ማስጠንቀቅያ ሊወሰድ ይችላል አዳዲስ አማኞች በዚህ ጥቅስ ይሰናከሉ ይሆናል፤ ነገር ግን ጴጥሮስ ከራሱ አንዳች አልጨመረም ሰው በእንዲህ አይነት ሁኔታ እያለ ሊድን ይችላልን?

▣ **"የእግዚአብሔር ስጦታ"**የእግዚአብሔርን አጠቃላይ ስራ የሚያመለክት ዐረፍተ ነገር ነው።) ኢሳ 55:1-2; ኤር 31:31-34; ሕዝ 36:22-28; ሉቃ11:13; ሐዋ 2:38)

8:21 **"ከዚህ ነገር ዕድል ወይም ፈንታ የለህም"** አሉታዊ ትርጉም አለው (2ቆሮ 6:15) ዕድል ወይም "ክፍል" የለህም ማለት ነው።

ሁለተኛው "ፈንታ" ማለት በብሉይ ኪዳን "ዕጣ" የሚለው የተካዋል። (ኢያ 12:19) በዚህ ምንባብ ቃሉ አንድን ነገር ለመውረስ የሚጠቅም ነው። የእንግሊዘኛው ቃል ለዚህ ሐረግ የሚሰጠው ትርጉም "የላቀ መንፈሳዊ ነገር ላሳየ ሰው የሚሰጥ ስያሜ ነው። በአዲስ ኪዳን ግን ለሁሉም አማኞች ስያሜው ተሰጧል።

▣ **"ልብህ በእግዚአብሔር ፊት የቀና አይደለም"** መዝ 78:37 ይመልከቱ። የቀና እና ትክክል የሚለው ቃል የመጣው በእግዚአብሔር ስነምግባር በተሰየመው ከሜሶፓታሚያ። ያም ከአስራ አምስት እስከ ሃያ ጫማ ያህል ቁመት ነበረው። እንዲሁም ቀጥ ያለ ነበር። እግዚአብሔር ይህንን ቃል ወሰዶአል። በግንባታ ውስጥ የሚጠቀሙበት ቃል እርሱ የራሱን ስነ ምግባር ባህርይ ሊያሳይ። እግዚአብሔር መለኪያችን ነው ገዥ፣ ቀጥተኛ የሆነና በሰው ልጆች ሁሉ ላይ በትክክል የሚፈርድ። በዚህም መሠረት ሁሉም ፈተናውን አላለፉም (ሮሜ 3:9-18,23)።

8:22 **"ንስሃ ግባ"** ትዕዛዝ ያለበት ፍጥነትን የሚጠይቅ ንግግር ነው።

▣ **"ፀሎት"** ይህም ትዕዛዝ ነበር። ወደ እግዚአብሔር መናገር ከእርሱ ጋር ላለን ግንኙነት ማስረጃ ነበር። ወደ ንስሐ የሚመራና የመንፈስን ሙላት የሚያመጣ።

▣ **"ቢሆንም"** ይህም ቃል እውነት እንደሆነ የሚታመንና በዓላማ የተባለ ነገር ነው ወይም ከእርሱ እይታ አንፃር። በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ የሲሞንና ለንስሐ ፈቃደኛ መሆንና ለሃጢአት ይቅርታ መፀለይን ያጠቃልላል። የእርሱ አስተሳሰብና ተግባር ከሌሎቹ ክርስቲያኖች በጣም የተለየ ነገር ነው።

▣ **"የልብህን ክፋት"** ሃጢአት የሚፀነሰው በሐሳብ ውስጥ ነው። በመሆኑም የአይሁድ መምህራን አእምሮ የዘር ፍሬን እንደሚቀበል እርሻ ነው። ከፈቀድንለት በቅሎ ስሮቹ በአይናችንና በጆሮአችን በማውጣት ምግብን ከገሃዱ ዓለም ይወስዳል ይላሉ (1ጴጥ 1:13፣ ሮሜ 12:12)። በዚህም ነው አዲስ ኪዳን በትኩረት የልቦናችንን ወገብ መታጠቅ (ጴጥ 1:13) ወይም "በአእምሮ መታደስ" (ሮሜ 12:2, ኤፌ 4:23) እንዳለብን የሚናገረው።

8:23

| | |
|---|---|
| NASB, NRSV | **"በመራርነት"** |
| NKJV | **"በመታረዝ መራራ"** |

TEV "በመራራ ቅናት በተሞላ"
NJB "በመራራ እሬት

እሬት "*chole*" እና መራርነት "*Pikros*" ሁለቱም ቃሎች የተማረረን መንፈስ ለማመልከት ሆኖ ነገር ግን ቁጣ እና ክደት የተደባለቀበትም ነው።) ዘዳ. 29፡18፤ 32፡28-33፤ ዕብ 12፡15) ሐዋሪያው ጳውሎስ ይህንን ቃል ብዙ ጊዜ ይጠቀምበታል (ሮሜ3፡14፣ ኤፌ. 4፡31).

▣
NASB "በበደል እስራት"
NKJV "በበደል ቀንበር"
NRSV "በጠማምነት ሰንሰለት"
TEL በሐጢያት እስረኛ"
NJB "በሐጢያት ሰንሰለት"

ይህ የመሲሁ ወደ ምድር የመምጣቱ ዓላማ በዋናነት ከላይ የተዘረዘሩትን ለማስወገድ ነው። ኢየሱስ ሲሞንን ከዚህ ከሚያስቀጣ ከሐጢያት እስራት ሊፈታው ይችላል። ሐጢአት ሁለት ገፅታ አለው። (1) ሞት ስጋዊና መንፈሳዊ ነው እና (2) በሐጢያተኛው ላይ የሚሰለጥነው የትኛው ነው። (ይህ ሐጢያት የደላውን እና ያልደላውን ያጠቃል (1ቆሮ 3፡1-3) በመሆኑም ሐጢያት በአሁን ጊዜና በዘላለም የጊዜ አቆጣጠር ቅጣቱን ያገኛል።

8፡24 እናንተው ወደ ጌታ ለምኑልኝ አላቸው ይህ ልመና በሚሿዮናዊነት ወደ ሰማርያ የመጡትን ሐዋርያት የሚመለከት ነው። ሲሞን ጴጥሮስ በቁ.22 ላይ የተናገረው በመፍራት ጠይቋል እንደሚገመተው ሲሞን እንደ አዲስ ህፃን ልጅ አዲስ አማኝ ነበር።

> **NASB (የተሻሻለው) ትርጉም፡ 8፡25**
> **[25]እነርሱም ከመሰከሩና የጌታን ቃል ከተናገሩ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ በሳምራውያን በብዙ መንደሮች ወንጌልን ሰበኩ።**

8፡25 መሰከሩ ሐዋ 2፡40 ይመልከቱ።

▣ "በሳምራውያን በብዙ መንደሮች ወንጌልን ሰበኩ" ይህ የሚያመለክተው የሐዋርያቱ የአይምሮ መቀየር እርሱም ለሰማርያ ሰዎች በድፍረት ወንጌል ለማድረስ መወሰናቸውን ያመለክታል።
የጌታ ቃልና ወንጌል አንድ አይነት ትርጓሜ ነው ያላቸው

> **NASB (የተሻሻለው) ትርጉም፡ 8፡26-40**
> **የጌታም መልአክ ፊሊጶስን ተነስተህ በደቡብ በኩል ከእየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደሚያወርደው ምድረ በዳ ወደ ሆነ መንገድ ሂድ አለው ተነስቶም ሄደ። እነሆም ህንዳኬ የተባለች የኢትዮጵያ ንግስት አዛዥና ጃንበረባ የነበረ በገንዘብም ሁሉ የሰለጠነ አንድ የኢትዮጵያ ሰው ሊሰግድ ወደ እየሩሳሌም መጥቶ ነበር ሲመለስም በሰረገላ ተቀምጦ የነብዩን የኢሳያስን መፅሐፍ ያነብ ነበር መንፈስም ፊሊጶስን ወደዚህ ሰረገላ ቅረብና ተገናኘው አለ ፊሊጶስም ሮጠ የነብዩ ኢሳያስን መፅሐፍ ሲያነብ ሰማና በውኑ የምታነበውን ታስተውላለህን አለው እርሱም የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል አለው ወጥቶም ከእርሱ ጋር ይቀመጥ ዘንድ ፊሊጶስን ለመነው ያነበው የነበረ የመፅሐፍ ክፍል ይህ ነበረ እንደ በግ ለመታረድ ተነዳ የበግ ጠቦትም በሸላቶቹ ፊት ዝም እንደሚል እንዲሁም አፉን አልከፈተም በውርደት ፍርዱ ተወገደ ህይወቱም ከምድር ተወገደች ትውልዱንስ ማን ይናገራል ጃንደረባውም ለፊሊጶስ መልስ እባክህ ነብዩ ሰለሞን ይናገራል። ስለ ራሱ ወይስ ስለ ሌላ አለው ፊሊጶስም አፉን ከፈተ ስለዚህም መፃፍ ጀምሮ ስለ ኢየሱስ ወንጌልን ሰበከለት በመንገድም ሲሄዱ ወደ ውሃ ደረሱ እነሆ በውሃ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድነው አለኝ ፊሊጶስም በፍፁም ልብ ብታምን ተፈቅዷል አለው መልስም ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ አለ ሰረገላውም ይቆም ዘንድ አዘዘ ፊሊጶስና ጃንደረባው ወደ ውሃ ወረዱ አጠመቀውም ከውሃም ከወጡ በኋላ የጌታ መንፈስ ፊሊጶስን ነጠቀው ጃንደረባውም ሁለተና አላየውም ደስ ብሎት መንገዱን ይሄድ ነበረና።**

8፡26 "የጌታ መልአክ ፊሊጶስን ተናገረው" እዚህ ምንባብ ላይ የኔታ መልአክ እና መንፈስ ቅዱስ ተመሳሳይነት ያላቸው ይመስላል ሐዋ 8፡29 እና ሐዋ 5፡19 ይመልከቱ።

▣ "ተነስተህ በደቡብ በኩል" ይህ መንገድ የሚያመለክተው ወደ ግብፅ ከሚወስደው ሁለት መንገድ አንዱ ነው። ይህ የእግዚአብሔር ንግግር በሚሰማ በድምፅ ለፊሊጶስ መምጣቱ ነገሩን ትክክለኛ እንዲሆን አድርጐታል።

▣
NASB "ይህ የበረሃ *መንገድ* ነው"
NKJV "ይህ በረሃ ነው"
NRSV "ይህ የምድረ በዳ መነገድ ነው"
TEV "ይህ መንገድ በአሁኑ ጊዜ አገልግሎት አይሰጥም"
NJB "የበረሃ መንገድ"

ይህ መንገድ በፀሐፊው በሉቃስ የሚታወቅ ይሆንን? ሉቃስ ደግሞ ከየት እንዳገኘው አልፃፈልንም ወይም ሉቃስ ሲፅፍ ከፊሊጶስ ማስረጃን አግኝቶ ይሆንን? እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ አይቻልም ነገር ግን እግዚአብሔር የዚህ መፅሐፍ ጠባቂ እንደሆነ እናውቃለን፡፡

8፡27 **"የመንግስት ባለስልጣን"** የመንግስት ባለስልጣን የሚለው አቻ ቃሉ ጃንደረባ የሚለው ሊተካው ይችላል ነገር ግን ይህ ሰው በአካሉ ጃንደረባ ወይም ባለልጣን መሆኑ በግልፅ የተቀመጠ ዓረፍተ ነገር አናገኝም፡፡ በብሉይ ኪዳን ጰጢፍራ ዳንደረባ ቢሆንም ነገር ግን ትዳር ነበረው (ዘፍ 39፡1 በቡሉይ ኪዳንም ጃንደረባ የሆነ ሰው ከህዝቡ ጋር ህብረት እንዲኖረው አይፈለግም ነበር፤ ነገር ግን በኢሳ 56፡3 ይህ አስተሳሰብ ተወግዷል፡፡ ይህ የሚያመለክተው የአዲሱን ኪዳን ስርዓት ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ጃንደረባ ጣኦትን የሚያመልክ ይሁን ወይም እግዚአብሔርን የሚፈራ መሆኑን ማረጋገጫ የለም ነገር ግን ከዓረፍተ ነገር በግርድፍ የምንረዳው የመንግስት ባለስልጣን መሆኑን ነው፡፡

▣ **"ህንዳኪ የኢትዮጵያ ንግስት"** ሕንዲኬ እንደ ፈርኦን እና ቄሳር የማዕረግ ስም ነው፡፡ በዚህ ምንባብ የንግስቲቱ ስም የተጠቀሰበት ዋና ምክንያት የኢትዮጵያ ነገስታቶች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው የሚል አድምታ አለው፡፡

8፡28 **"የኢሳያስን መፅሐፍ ሲያነብ"** ይህ ጃንደረባ ሃያ ዘጠኝ ጫማ ርዝማኔ ያለውን የቆዳ ብራና ወይም የመፅሐፍ ጥቅልል ይዞ ነበረ፡፡ በመንፈስም ምሪት የኢሳያስን መፅ 53፡7-8 እያነበቡ ነበር ይህም ስለ መሲሂ ኢየሱስ የሚናገር የመፅሐፍ ቅዱስ ምንባብ ነው፡፡

8፡29 **"የጌታ መንፈስ ፊሊጶስን ወደዚህ ሰረገላ ቅረብና ተናገር አለኝ"** ይህ የትዕዛዝ ንግግር ነው፤ መንፈስ ቅዱስ ፊሊጶስን በግልፅ ምሪት ይሰጠው ነበር፡፡

8፡30 **"ፊሊጶስም ሮጠ የነብዩን የኢሳያስን መፅሐፍ ሲያነብ"** በዚያ ዘመን ሰዎች ብቻቸውን ሲሆኑ ድምፃቸውን አውጥተው የማንበብ ልምድ ነበራቸው፡፡

▣ **"የምታነበውን ታስተውለዋለህን"** ይህ ሰው ከባድ ጥያቄ ተጠየቀ፡፡ ምክንያቱም ሰዎች የመፅሐፍ ቅዱስ አላማ ሳይገባቸው ጮኸው ሊያነቡ ይችላሉና መንፈስም ፊሊጶስን እየመራው ነው፡-

1. ይህም አዲስ ኪዳን መምጣቱን አመላካች ነው
2. የወንጌል ምስክርነት በመንፈስ እና በመረዳት የሚነገርበትን ዘመን የሚያመለክት ነው፡፡

8፡31 **ለተጨማሪ ግንዛቤ** (A.T. Roberson's *word pictures in the new testament*) የማጠቃለያ ሐረግ ነው ተመሳሳዩን ሉቃ 19፡40 ይመልከቱ፡፡ ይህ የተደበቀ ሁኔታ ነው፡፡ የመጨረሻው ማጠቃለያ ወደ አራተኛው ክፍል ነው የሚመጣው ሉቃ 19፡40 ሁንታውም በሙድ ተገልፆአል በግንባታ ሳይሆን ሉቃ 19፡40፡፡

8፡32-33 ከኢሳ 53፡7-9 የተጠቀሰ ነው፡፡ ይህንን የሚተካ ስለመሲሁ የሚናገር የዚህ አይነት ተመሳሳይ ቃል በብሉይ ኪዳን የለም፤ ይሁን እንጂ ፊሊጶስ የጀመረው እርሱ ያነበበት ከነበረው ምዕራፍ ላይ ነው፡፡ በሕይወት ብርሃን እና አገልግሎት፣ ሞት እና የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ፡፡ ብሉየ ኪዳን ነቢያት በክርስቶስ መስዋዕትነት ሙሉነት አግኝቶአል፡፡ እንዲሁም በእያንዳንዱ የሚሆን የሃጢአት ይቅርታ፡፡

8፡35 **"ፊሊጶስም አፋን ከፈተ"** ፊሊጶስ የመፅሐፍ ቅዱስን ዋና መልዕክት ለመናገር መዘጋጀቱን ያመለክታል ኢሱስን አምናለሁ እርሱ ራሱ የቀደሙት የነቢያት ቃል ምን ያህል ስለ እርሱ እንደሚናገር አሳይቷል (ሉቃ 24፡27)፡፡

8፡36 **"ወደ ውሃ ደረሱ --- እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድነው"** ፊሊጶስ የሚሰብከው ወንጌል ጥምቀትንም የሚያጠቃልል ነበር፡፡ ( ማቴ 28፡ 19 ሐዋ 2፡38 ሮሜ 6፡1-11 ቆላ 2፡12) ነገር ግን ፊሊጶስ ለማጥመቅ ከሐዋርያት ስልጣን አልተቀበለም ፤ ጥምቀት የሰው ሳይሆን የእግዚአብሔር መንግስት ትዕዛዝ መሆኑን ያሳያል፤ በመሆኑም የቤተክርስቲያናችን አስተምሮት የመፅሐፍ ቅዱስ መሆኑን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡
ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ላለመቀበል የሚነሱ ጥያቄዎች ምንድናቸው

1. የዘር ጥያቄ (አህዛብ መሆኑ)
2. የስልጣን ማዕረጉ
3. የሚኖርበት ማዕበረሰብ
4. የዕምነቱ ልዩ መሆን

ነገር ግን እነዚህ ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ልዩነታቸው ተሽሯል፡፡ (ኤፌ 2፡11-3፡13)

8፡37 የጃንደረባው ንግግር በጥንት የግሪክ ፓቲረስ ፅሑፍ አልተገኘም (Chester Beatty papyri) ያንብቡ እንዲሁም በጥንት ላቲን፣ ኮፓቲክ እና የኢትዮጵያ ትርጉም በሚባለውም መፅሐፍት ላይ ፅሑፍ አልተፃፈም በመሆኑም ቁ. 37 ሉቃስ አልፃፈውም በተጨማሪም በUSB እና NASB ላይ አልተገኘም ነገር ግን በ1995 ዓ.ም. መጨመሩን ማስረጃ ተገኝቷል፡፡

8፡38-39 **"ወደ ውሃ ወረዱ --- ከውሃም ከወጡ በኂላ"** ይህ በውሃ ውስጥ አመቀው የሚል ትርጉም አይሰጥም ነገር ግን ወደ ወንዙ መግባታቸውንና መውጣታቸውን የሚያመለክት ብቻ ነው፡፡

8፡39 **"የጌታ መንፈስ ፊሊጶስን ነጠቀው"** የኤልያስን ተመልከቱ (1ነገ 18፡12፤ 2ነገ 2፡16) የዚህ ተመሳሳይ መንፈስ ቅዱስ ያደርግ እነደነበር አመላካች ቃል ነው ወይም (እዝ 3፡14፣ 8፡3)። መንፈስ ቅዱስ በመለወጥ ሂደት ውስጥ ተሳትፎአል። የክትትል ትምህርትም ብዙ አልነበረም በዚያን ወቅት ግን የኢሳያስን መጽሐፍ ያነብ ነበር። እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ነበር።

▣ **"ደስ ብሎት መንገዱን ይሄድ ነበር"** ወንጌል ደስተኛ ያደርጋል (8.8) በሆኑም ይህ ጃንደረባ ለአገሩ ሚሲዮናዊ ሆኖአል። መንፈስ ራሱ የክትትሉን ሥራ ይሠራ ነበር ደቀመዝሙር ለማድረግ።

8፡40 ፊሊጶስም የወንጌል ሥራውን ቀጥሎበት ነበር። በፍልስጤም ምድር አሻዶድ በሚባል ወደ ቂሳርያ በሚወሰደው ባህር ላይ። ፊሊጶስ በሰማርያዊያንና በኢትዮጵያውያን ላየ ሲሆን የሚገባውን የወንጌል አገልግሎት ተረድቶታል። ወንጌል ፍልስጤማውያንንም ሳይቀር እንደሚያጠቃልል ያምናል።

### የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጐመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ለመርዳት ነው የተሰናዱት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋነኞቹን ጉዳዮች ለማጤን እንዲረዳ ነው። ሐሳብ ለማጫር እንጂ መደምደሚያ አይደሉም።

1. እግዚአብሔር ስደት በጥንቲቱ ቤተክርስቲያን ላይ እንዲሆን ለምን ፈቀደ
2. ወንጌል ለሰማርያ ሰዎች መሰበክ ለምን አስፈላጊ ሆነ
3. ሲሞን አማኝ ሆኖአልን
4. የሰማርያ ሰዎች በአመኑ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ለምን አልተቀበሉም
5. ጃንደረባ የሚወክለው ምን አይነትን ሰው ነው
6. በቁ.37 ላይ የሚገኘው በሁሉም የመፅሐፍ ቅዱስ አስተምሮዎች ላይ ለምን አይሰራም።

# ሐዋርያት ሥራ 9

## የምንባቡ ክፍፍል በአዳዲሶቹ ትርጉሞች

| የተየመቅሰ[4] | አኪጀት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የሳኦል መለወጥ | በደማስቆ መንገድ ሳኦል ተቀየረ | የጠርሴሱ ሳኦል መቀየር | የሳኦል መቀየር | የሳኦል መቀየር |
| 9:1-9 | 9:1-9 | 9:1-9 | 9:1-2 | 9:1-2 |
| | | | 9:3-4 | 9:3-9 |
| | | | 9:5a | |
| | | | 9:5b-6 | |
| | ሃናኒያ ሳኦልን አጠመቀው | | 9:7-9 | |
| 9:10-19a | 9:10-19 | 9:10-19a | 9:10a | 9:10-12 |
| | | | 9:10b | |
| | | | 9:11-12 | |
| | | | 9:13-14 | 9:13-19a |
| | | | 9:15-16 | |
| | | | 9:17-19a | |
| ሳኦል በደማስቆ ሰበከ | ሳኦል ክርስቶስን ሰበከ | | ሳኦል በደማስቆ ሰበከ | የሳኦል ስብከት በደማስቆ |
| 9:19b-22 | | 9:19-22 | 9:19b-20 | 9:19b-22 |
| | | | 9:21 | |
| | 9:20-22 | | 9:22 | |
| ሳኦል ከአይሁዶች አመለጠ | ሳኦል ሞትን አመለጠ | የሳኦል ለመጀመሪያ ጊዜ ኢየሩሳሌም መጉብኘት | | |
| 9:23-25 | 9:23-25 | 9:23-25 | 9:23-25 | 9:23-25 |
| ሳኦል በኢየሩሳሌም | ሳኦል በኢየሩሳሌም | | ሳኦል በኢየሩሳሌም | ሳኦል በኢየሩሳሌም |
| 9:26-30 | 9:26-30 | 9:26-30 | 9:26-30 | 9:26-30 |
| | የቤተክርስቲያን ባለጠግነት | | | |
| 9:31 | 9:31 | 9:31 | 9:31 | 9:31 |
| የኤንያስ መፈወስ | የኤንያስ መፈወስ | የጴጥሮስ ጉብኝት በበልሳ እና በኢዩጴ | ጴጥሮስ ዶርቃን በኢዩጴ ተመለከተ | ጴጥሮስ በኢዩጴሽባ ፈወሰ |
| 9:32-35 | 9:32-35 | 9:32-35 | 9:32-35 | 9:32-35 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የዶርቃ በሕይወት መኖር | የዶርቃ በሕይወት መኖር | | | ጴጥሮስ የሞተች ሴት በኢዩጴ አስነሳ |
| 9፡36-43 | 9፡36-43 | 9፡36-43 | 9፡36-43 | 9፡36-38 |
| | | | | 9፡39-42 |
| | | | | 9፡43 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (ከ "**መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ**" **ገጽ** vii)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. ምንባብ አንድ

2. ምንባብ ሁለት

3. ምንባብ ሦስት

4. ወዘተ-----

**የአውዱ እይታ**

ሀ. የሐዋርያት ሥራ ሽግግርን የሚናያሳይ መፅሐፍ ነው፡፡ ከጴጥሮስ አገልግሎት ወደ ጳውሎስ፣ ለወንጌል ከፍልስጤም ምድር ወደ ሚዲትራኒያን፣ከአይሁድ ወደ አሕዛቦች በፍጥነት የተስፋፋበት መፅሐፍ ነው፡፡

ለ. የሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ክርስቶስ መምጣት በቤተክርስቲያን ታሪክ አስፈላጊ መሆኑን ለማመልከት በሐዋርያት ሥራ ላይ ሦስት ጊዜ ተፅፏል፡፡
   1. በሉቃስ ፅሑፍ ላይ ይገኛል፡- ሐዋ 9፡1-3
   2. በሐዋርያው ጳውሎስ ፅሑፍ ላይ ይገኛል፡- ሐዋ 22፡3-16
   3. በሐዋርያው ጳውሎስ ፅሑፍ ላይ በአግሪፓ ፊት በቂሳሪያ አገር፡- ሐዋ 26፡4-18
   4. ጳውሎስ የተብራራ ገለፃውን ያንብቡ፡- ገላ 1፡13-17 እና 2ኛ ቆሮ11፡32-33

ሐ. በሰማዕት እስቲፋኖስ እና በጳውሎስ መልዕክቶች መሃከል ግልፅ የሆነ አንድነት ይታያል ጳውሎስ ለግሪኮች ወንጌልን ሰብኳል እንዲሁም እስቲፋኖስ፡፡ ሐዋሪያው ጳውሎስ የእስቲፋኖስን ስብከት ሰምቷል፡፡) ሐዋ 7፡58; 8፡1; 22፡20) እስቲፋኖስ በምኩራብ ክርክር በነበረው ጊዜ ጳውሎስ አንዱ የምኩራብ መሪ እና ተከራካርም ነበር፡፡

መ. ለሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ክርስቶስ መምጣት የሆኑት ምክንያቶች፡-
   1. የአይሁድ ሐይማኖት ለውስጥ ሰላም እና ደስታ ለመስጠት ባለመቻሉ፡፡
   2. የኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት በብዙዎች ዘንድ ጥያቄ በመፈጠሩ፡፡)በተለይ በኢየሩሳሌም)
   3. የእስቲፋኖስን ስብከት በመስማቱ፡፡)በተለይ በፍርድ ወንበር ፊት በቀረበ ጊዜ (
   4. የክርስቲያኖች ዕምነንት በስደት ውስጥ ጠንካራ ነበር፡፡
   5. ሐዋርያው ጳውሎስ በደማስቆ ክርስቶስን በመገናኘት ህይወቱ ፈፅሞ ሊቀየር ችሏል፡፡

ሐዋ 9፡1-9
**ሳኦል ግን የጌታን ሲቃ መዛውርት እንዲገልፅላቸው ገና እየዛተ ወደ ሊቀ ካህናት ሄዶ በዚህ መንገድ ያሉትንም ሰዎች ወንዶችንም ሴቶችንም ቢያገኝ እየሰራ ወደ ኢየሩሳሌም ያመጣቸው ዘንድ በደማስቆ ላሉት ምኩራቦች ደብዳቤ ከእርሱ ለመነ ወደ ደማስቆም በቀረበ ጊዜ ድንገት በእርሱ ዙሪያ ከሰማይ ብርሃን አንፀባረቀ በምድርም ላይ ወድቆ ሳለ ሳውል ሳውል ስለምን ታሳድደኛለህ የሚለውን ድምፅ ሰማ ጌታ ሆይ ማን ነህ አለው እርሱም አንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ለአንተ ይብስብሃል አለው። እየተንቀጠቀጠና እየተደነቀ ጌታ ሆይ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ አለው ጌታም ተነስተህ ወደ ከተማ ግባና ታደርገው ዘንድ የሚያስፈልግህን ይነግሩሃል አለው ከእርሱም ጋር በመንገድ የሄዱ ሰዎች ድምፁን ግን ሲሰሙ ማንንም ሳያዩ እንደ ዲዳዎች ቆሙ ሳውልም ከምድር ተነሳ ዓይኖቹ በተከፈተ ጊዜ ምንም አላየም እጅንም ይዘው እየመሩ ወደ ደማስቆ አገቡት ሳያይም ሶስት ቀን ኖረ አልበላምም አልጠጣምም።**

9.1 **"ሳኦል ግን የጌታን ደቀ መዝሙርት እንዲገድላቸው ገና እየዛተ"**

▣ **"የጌታ ደቀ መዝሙርት"** የጌታ ተማሪዎች የሚለው አቻ ቃሉ ነው ይህ ሐረግ በወንጌላትና በሐዋርያት ስራ ላይ ብቻ ነው የሚገኘው ነገር ግን ይህ ቃል ብዙም ሳይቆይ ቅዱሳን በሚለው ተተክቷል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የእግዚአብሔር ልጆች መጠሪያ የሆነውን እንመልከት፡-

1. ደቀ መዝሙርት፡- ቁ. 1፣ 10፣ 19፣ 25፣ 26፣ 36፣ 38
2. በዚያ መንገድ ያሉትን፡- ቁ. 2
3. ቅዱሳን፡- ቁ. 13፣ 32፣ 41
4. ወንድሞች፡- ቁ. 17

▣ **"ወደ ሊቀ ካህናት ሄዶ"** ሐዋ 26፡10 እና ሐዋ 4፡5 ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው

9፡2 **"በደማስቆ ላሉት ምኩራቦች ደብዳቤ"** ይህ የሚያመለክተው ሮማውያን ለሊቀ ካህናት የሰጡትን ገደብ ያለው ስልጣን ነው መቃብያን 15፡16-21 ወይም ጆሴፊስ አንቲክ 14፡10፡2 በማንበብ ተጨማሪ ዝርዝር ማግኘት ይቻላል። የአይሁድ ሃይማኖት በግሪኮ ሮማ ጊዜ እውቅና የነበረው ሃይማኖት ነበር።

በመሆኑም ይህ ደብዳቤ ክርስቲያኖችን ለመጨቆን አይነተኛ መንገድ ነበር (የሐዋ 9፡14፣ 21፣ 25፡5፣ 26፡10)።

▣ **"ቢሆንም"** የሚለው ዓረፍተ ነገር የመፈፀም ሃይል እንዳለውም ያመለክታል።

▣ **"በዚያ መንገድ"** ይህ ለአማኞች የተሰጠ ስያሜ ነበር (ሐዋ 19፡9፣ 23፣ 22፡4፣ 24፡14፣ 22 እና 18፡25፣ 26) ይህ በብሉይ ኪዳን የተለመደ ንግግር ነው (መዝ 1፡1፣119፡105 ምሳ 4፡10፣ 19) በተጨማሪ በዮሐ 14፡6 ይመልከቱ።

▣ **"ሴቶች"** ሐዋርያው ጳውሎስ አሳዳጅ በነበረ ጊዜ ያሳድዳቸው የነበሩትን የሕብረተሰብ ክፍሎች በግልፅ ለመናገር የተደረገ ጥረት ነው። (ሐዋ 8፡3 22 4)

9፡3 **"ደማስቆ"** ይህች ከተማ የጥንት እንደሆኗ የሮም አውራጃ የነበረችው የሲሪያ ዋና ከተማ ነበረች፤ የምትገኘውም በሰሜን ምስራቅ ገሊላ ነው ከኢየሩሳሌም መቶ ሃምሳ ማይክ ትርቃለች።

▣ **"በድንገት"** - ባልተጠበቀ ጊዜ የሚለው ይተካዋል።

▣ **"ከሰማይ ብርሃን"** ሐዋርናያው ጳውሎስ የዚህ አይነት ሶስት ልምምዶቹን እንመልከት፡-

1. "ከሰማይ ብርሃን አንፀባረቀ" (ሐዋ 9፡3)
2. "ከሰማይ ታላቅ ብርሃን በዙሪያዬ አንፀባረቀ" (ሐዋ 22፡6)
3. "ከፀሐይ ብሩህነት የበለጠ ብርሃን ከሰማይ ሲበራ አየሁ" (ሐዋ 26፡13)

ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ክስተት በተክክል አስታውሶ ይተርከዋል።

ይህ የተሰጠው ድምፅ እስራኤሎች በምድረ በዳ በነበሩ ጊዜ ከሰሙት ጋር ተመሳሳይነት አለው የሚያንፀባርቅ ብርሃን በእግዚአብሔር ክብር ይመስላል። ሐዋ 3፡13 ይመልከቱ። ይህንን ብርሃን ሐዋርያው ጳውሎስ ብቻ ማየቱ እግዚአብሔር የግል አምላክ መሆኑንም የሚያስገነዝብ ነው።

9፡4 **"ድምፅ ሰማ"** ከሠማይ ድምፅን በመማት ለአይሁዳውያን አዲስ ልምምድ አይደለም። ይህንን በተለምዶ ባዝኮል ይሉታል፤ ለአይሁዳውያን ከእግዚአብሔር የሚሰሙበትና የሚመልሱበት የመገናኛ አንዱ መንገድ ነበር በተለይ ይህ የዝምታ ጊዜ በሚባለው ዘመን ሕዝቡ በዚህ መንገድ የእግዚአብሔርን ድምፅ ይሰማ ነበር፤ ምክንያቱም በዚህ ዘመን ነብይ ስላልነበረም ነው።

▣ **"ሳኦል ሳኦል"** ይህ በዕብራውያን ትኩረት መስጠቱን የሚያመለክት ነው

▣ **"ስለምን ታሳድደኛለህ"** ይህ በቤተክርስቲያንና በኢየሱስ መሃከል የነበረውን ጥብቅ ግንኙነት የሚያመለክት ነው)ማቴ 10፣ 40፣ 45፣ 25፣ 40፣ 45) ጳውሎስ የሚያሳድደው ቤተ ክርስትያንን ነበር ነገር ግን ኢየሱስን እንደሚያሳድድ ተነገረው ሐዋ 26:14 ኢየሱስ በአራማክ ቋንቋ እንደተናገረው መላምት አለ

ይህ የሚያመለክተው ኢየሱስ እና ቤተክርስትያኑ የማይለያዩ መሆናቸው ክርስቲያኖችን የሚያስደስት ነው። በመሆኑም ለቤተክርስቲያን የተሰጣትን ስያሜ እንመልከት:-

1. አካል
2. ቤተሰብ
3. ሕንፃ
4. ቅዱሳን

የክርስቲያኖች ሕብረት የአካል ጥምረት ይታይበታል፣ ይህ መተሳሰብን የሚያመለክት ነው የአንድ ብልት መጠቃት የሁሉም መጠቃት ነው (1ቆሮ 12:7) ያንብቡ። ይህም ግለሰብ ጳውሎስ ስለ አዳምና ክርስቶስ ከተናገረው ነገር ጋርም ይነፃፀራል። ሮሜ 5:12-21፣ አንዱ የሁሉም አካል ነው። አንዱም በሌሎች ላየ ተጸዕኖ ይፈጥራል (ኢያሱ 7)።

9:5a **"ጌታ ሆይ ማንነህ"** ሐዋርያው ጳውሎስ ጌታ በማለት ምንን ለማመልከት ነው

1.ጌታዬ ማለትም የአክብሮት ማዕረግ ነው (ኢያ 4:11)

2. ያሕዌ በብሉይ ኪዳን ጌታ የሚለውን ቃል ይተካል (ዘፍ 2:4)

በጳውሎስ ሁኔታ ሁለት ነገሮችን መገንዘብ ይቻላል የመጀመሪያው ከሰማይ ብርሃን ማንፀባረቁ የእግዚአብሔር ስራ መሆኑን ያሳያል ሁለተኛው ሐዋርያው ጳውሎስ የተማሪው የአይሁድ መምህራን ሰነመለኮት ያሕዌ (ጌታ) ብሎ እንዲናገር አድርጎታል።

9:5b-6b ይህ ጥቅስ በግሪኩ ፅሁፍ ላይ አይገኝም። በአንድ የላቲን ጽሑፍ ብቻ ውስጥ ነው የሚገኙት። ኤራስመስ የተባለውና ቨልግት ከሚለው የተተረጎመው በመጀመሪያው በግሪኩ አዲስ ኪዳን በ1516 በታተመው ላየ ተጽፏል። እነዚህም ቃላቶች በሐዋ 26:14 ላይ የሚገኙ ናቸው። በዚህም ስፍራ በፀሐፊዎች የሚደረገውን ንጽጽር እና አጠቃላይ ነገሮችን ያሳያል።

9:5 **"አንተ የምታሳድደኝ ኢየሱስ ነኝ"** ሐዋርያው ጳውሎስ ኢየሱስን አየሁት የሚለው ከዚህ የተነሳ ነው (ሐዋ 22:14 1ቆሮ 9:5፣ 15:8-9) ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን የኢየሱስ መገለጥ ከአገልግሎት ጥሪው ጋር ያገናኘዋል።

9:6 ይህ ጥቅስ በቁ. 10-19 ተብራርቷል።

9:7 **"ከእርሱ ጋር በመንገዱ የሄዱ ሰዎች"** ሶስት የተለያዩ መላምቶች አሉ፤ (1) የመቅደስ ጠባቂዎች (2) በምኩራብ ለእግዚአብሔር የሚቀኑ (3) በኢየሩሳሌም የሚኖሩ የስነ መለኮት ተማሪዎች

▣ **"ድምፁን እየሰሙ ማንንም ሳያዩ"** በሐዋ 9:7 እና 22 9 መሐከል ልዩነት አለ የሚከተሉትን መላምቶች እንመልከት:-

1. የዐረፍተ ነገሩ አመሰራረት ልዩነት አምጥቷል ፤ መስማስ የሚለው በስም ወይም በተውላጣ ስም ወይም በቅፅል መልክ በመቀመጡ ቋንቋውን ማንም እንዳሻው እንዲተርጉመው ሆኖአል ሐዋ 9:7) ወይም 22 9 በተመሳሳይ ዕረፍተ ነገሩ ትርጉሙን ሊቀይር ችሏል። የግሪኩ ፅሁፍ በዙሪያው ከሰዋሰው ድርድር ካለመስተካከል ያሉ ድምፁን እየሰሙ የሚነገረውን ቃል አልሰሙም በሚል አስቀምጦታል።
2. ሌላው መላምት በዮሐ 12:29-30 ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜ የተሰማው አይነት ድምፅ ነው።
3. ሌላው መላምት የተሰጠው ድምፅ የኢየሱስ ሳይሆን የራሱ የጳውሎስ ነው። በዙሪያው የነበሩት የሰሙት የጳውሎስን እንጂ የኢየሱስን ንግግር አይደለም የሚል ምልከተ ዓለም ነው።
4. ሌሎች ደግሞ የሚሉት ይህ ችግር በወንጌላት መሃከል ያለው ችግር ነው

የተለያዩ የወንጌላት ፀሐፊዎች ክስተቶችን፣ ስብከቶች፣ የኢየሱስ ስራዎችን ሲዘግቡ በራሳቸው መንገድ መሆኑ አገላለፃቸውም የተለየ እንዲሆን አድርጎታል።

9:8 **"አይኖቹ በተከፈቱ ጊዜ ምንም አላየም"** ሐዋርያው ጳውሎስ ከዚህ ነገር በኂላ ችግር ነበረበት ምክንያቱ ባይታወቅም (ገላ 4:13-15፣ 6:11) ቅሪፊት መውደቅ አይኑ አካባቢ ያለው ስጋው መቀደዱ አያጠራጥርም ከዚህም የተነሳ የአይን በሽተኛ ሆኖ ሊሆን ይችላል (2ቆሮ 12:7-10) መንፈሳዊውንም ዓለም ደግሞም በስጋም ባለው አይኑ እንደሚያይ ያስብ ይሆናል ነገር ግን ዕውር ሆኖ ነበር በእርግጥ መንፈሳዊ አይኑ ተከፍቶ ነበር (ዮሐ 9) ያንብቡ።

9:9 **"ሰያይ ሶስት ቀን ኖረ"** በዚህ ጊዜ የሰማይ ራዕይ ይመለከት ነበር የሚል መልከተ ዓለም አለ (2 ቆሮ 12:1-4)

▣ **"አልበላም አልጠጣም"** ጳውሎስ ይጾምና ይፀልይ ነበር ቁ. 11 ይመልከቱ የሐዋርያው ጳውሎስ ከአሳደጅነት ወደ ወንጌል ሰባኪነት ለመቀየር ቁርጠኛ አቋም መውሰዱን የሚያመለክት ሐረግ ነው።

አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 9፡10-19a

በደማስቆም ሐናንያ የሚሉት አንድ ደቀ መዝሙር ነበረ ጌታም በራዕይ ሐናንያ ሆይ እያለ እርሱም ጌታ ሆይ እነሆኝ አለ ጌታም ተነስተህ ቅን ወደ ሚባለው መንገድ ሂድ ባይሁድ ቤትም ሳውል የሚሉትን አንድ የጠርሴስ ሰወ ፈልጐ እነሆ እርሱ ይፀልያልና ሐናንያ የሚሉት ሰው ገብቶ ደግሞ እንዲያዩ አጅን ሲጭንበት አይቶአልና አለው ሐናንያም መልሶ ጌታ ሆይ በኢየሩሳሌም በቅዱሳንህ ላይ ስንት ክፉ አንዳደረገ ስለዚህ ሰው ከብዙዎች ሰምቼአለሁ በዚህም ስምህን የሚጠሩትን ሁሉ ለማሰር ከካህናት አለቆች ስልጣን አለው አለ ጌታም ይህ በአህዛም በከስታትም በእስራኤልም ልጆች ፊት ስሜን ይሸከም ዘንድ ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነውና ሂድ ስለ ስሜ ስንት መከራ ሊቀበል እንዲያስፈልገው እኔ አመለክተዋለሁና አለው ሐናንያም ሄዶ ወደ ቤቱ ገባእጅንም ኸኖበት ወንድሜ ሳውል ሆይ ጌታ እርሱም በመጣህበት መንገድ የታየህ ኢየሱስ ነው ደግሞ ታይ ዘንድና መንፈስ ቅዱስ ይሞላብህ ዘንድ ላከኝ አለ፡፡ ወዲያው እንደ ቅርፊት ያለ ከአይኑ ወደቀ ያን ጊዜም ደግሞ አየ ተነስቶም ተጠመቀ መብልም በልቶ በረታ፡፡

9፡10 “ሃናንያ” የሰሙ ትርጉም “እግዚአብሔር ባለጠጋ” የሚል ነው እውነተኛ አማኝ ነበር (ሐም 22፡12)
“ጌታ ሆይ እነሆኝ አለ” የአይሁድ የተለመደ ምላሽ ነው (ኢሳ 6፡8)

▣ “እነወኝ ጌታ ሆይ” ይህ አይሁዶች መገኘታቸውን ለመግለጽ የሚጠቀሙበት ቋንቋ ነው (ኢሳያስ 6፡8)፡፡ ቁጥር 11 የንግግር ምክንያቱም በጣም የተለየ ትዕዛዝ ነው፡፡

9፡12 “ሐናንያ የሚሉትም ሰው ገብቶ እንዲያይ እጅን ሲጭንበት አይቷል አለው” በግሪኩ ፅሑፍ ላይ አልተፃፈም ነገር ግን MSS B እና C ላይ ተፅፎ ይገኛል፡፡ ሃናኒያ የመጣው ኢየሱስ የተናገረውን በድርጊት ለማከናወን ነው፡፡

▣ “እጅን ሲጭንበት” ሐዋ 6፡6 ይመልከቱ፡፡

9፡13 “ከብዙዎሀት እስማለሁ” ሐናኒያ ከአይሁድ ክርስቲያኖችን በኢየሩሳሌም ከሚኖሩ ነዋሪዎች የጳውሎስን ጨካኝነት መስማቱን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

▣ “ቅዱሳንህን” የሚለው ቅዱስ በግሪኩ “hagios” የሚል ነው የብሉይ ኪዳኑ “Kadosh” ለእግዚአብሔር ሰውን፣ ቦታን መቀደስ ወይም መለየት ማለት ነው “ቅዱሳን” የሚለው ቃል በመፅሐፍ ቅዱስ በብዙ ቁጥር ተቀምጧል ከፊሊጱስዩስ 4፡21 በስተቀር ነገር ግን በዚህም ቢሆን ዓውዱ ስለብዙ ቁጥር የሚናገር ነው፡፡ ክርስቲያን መሆን ከአካሉ ጋር ጥምረት መፍጠር ማለት ነው፡፡ በብቸኝነት ጉዳና አማኝ መሆን አይቻልም፡፡

**ልዩ ርዕስ: “ቅዱሳን”**

የዕብራይስጡ አቻ ቃሉ “ከዳሽ” ነው ትርጉሙ አንድን ቦታ፣ ሰውን፣ አንድ ነገርን ለያህዊ መለየት ማለት ነው፡፡ በእንግሊዘኛው ቃል “የተቀደሰ” ይህም ከፍጥረቱ የተለየ የሚያደርጉት ፈጣሪ መሆኑና መለኮታዊ ባህሪው ነው እርሱ ቅዱስ እና ብቻውን የሚኖር ነው፡፡

እግዚአብሔር ከሰው ጋር ሕብረት ማድረግ ይፈልጋል ነገር ግን በዙፋን የሰው ልጅ የሐጢያት ውድቀት ሰውን ከቅሉ እግዚአብሔር ጋር ሕብረት እንዳይኖረው አድርጓል፡፡ እግዚአብሔር ይህንን የፈረሰውን ሕብረት ለመመለስ ሕዝቡን ቅዱስ ሕዝብ በማለት ጠርቷቸዋል ዘሌ 11፡44 19፡2፣ 20፡7፣ 26፣ 21፡8) ሕዝቡ ለእግዚአብሔር የተለየ በመሆኑ ቅዱስ ተብሏል ነገር ግን በቅድስና እንዲኖር ታዟል ማቴ 5፡48

በቅድስና መኖር ይችላል ምክንያቱም አማኞች በክርስቶስ የመስቀል ስራ ሃጢያታቸው ይቅር ተደምስሷል የመንፈስ ቅዱስ ማደሪም ሆነዋል፡፡ ሁለት የሚጋጭ የሚመስል ሃሳብ እንመልከት

1.ክርስቶስ ፅድቃችን ነው

2.መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ስላደረ በቅድስና እንኑር

አማኞች “ቅዱሳን” በመባል ተጠርተዋል “hagios” ምክንያቱም፡- የቅዱሱ እግዚአብሔር ፈቃድ ህይወታችንን ስለሚመራው (2) ከቅዱስ ከእግዚአብሔር ልጅ ስራ የተነሳ (3) ቅዱሱ መንፈስ ማደሪያ ስለሆንን ቅዱሳን መባል ችለናል፡፡

ከፊሊ 4፡12 በስተቀር ቅዱሳን የሚለው ቃል በብዙ ቁጥር ተፅፎ ይገኛል መዳን ማለት አንድ ቤተሰብ አካል ወይም ህንፃ ውስጥ መጠለል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም እያንዳንዱ የዳነ ሁሉ ስራ በአካሉ ውስጥ አለው 1ቆሮ 12፡11 ይህም ለአካሉ እድገትና ጤንነት ጠቃሚ ነው፡፡ 1ቆሮ 12፡7 የዳንነው ለማገልገል ነው ቅድስና የዚህ አካል የአነEነEEር ዘይቤው ነው፡፡

9፡14 “የካህናት አለቆች” የብሉይ ኪዳን ሊቀ ክህነት እስከ የሕይወት ፍፃሜ ነው ከዚያም ለልጅ ልጅ ይተላለፋል (ዘሌዋ 8፡10) ነገር ግን ሮማውያን ይህንን የእግዚአብሔርን ስርዓት በገዛ ስልጠናቸው አበላሽተውት ነበር፤ በመሆኑም በአንድ ጊዜ ብዙ ሊቀ ካህናቶችን ይሸጡ ነበር ፤ ለምሳሌ ከሰዱቃውያን ቤተሰብ የሆነውን ሃናን ሾመውት ነበር፡፡

▣ "ስምህን የሚጠሩትን" በስነመለኮት አስፈላጊ ሐረግ ነው ሉቃስ በሐዋርያት ስራ መፅሐፍ ላይ ብዙ ጊዜ ተጠቅሞበት እንመለከታለን

1. የኢየሱስን ስም ለመጥራት (ሐዋ፡59)
2. ኢየሱስን እንደግል አዳኝ አድርጐ ለመቀበል (ሐዋ 9፡14-21)
3. የያህዌን ስም ለመጥራት (አሞፅ 9)12)
4. አንድ ሰው አማኝ መሆኑን በሰው ፊት ለመመስከር ይጠቀምበታል (ሐዋ 22፡16)

ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ስም ስለ እስራኤል ልመና ያቀረበበት ነው ( ኢዮ 2፡32፣ ሮሜ 10፡9-13፣ 2ጢሞ 2፡22) ጴጥሮስም ተመሳሳይ ምንባብ ተጠቅሟል ኢዩ 2፡28-32 ጴጥሮስ በስብኩ መሃከለኛ የነበረው ይህ ስም ነበር፡፡

9፡15 "ሂድ" ይህ የትዕዛዝ ቃል ነው፡፡ ሃናኒያ ወደ ጳውሎስ ላለመሄድ ባመነታ ጊዜ የደረሰው የትዕዛዝ ቃል ነው፡፡

▣ "ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነውና" የእግዚአብሔርን ነፃ ምርጫ የሚያሳይ ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ለወንጌል ስራ አእይምሮ የተዘጋጀ አልነበረም፡፡

▣

| | |
|---|---|
| NASB, NKSV | "በአሕዛብ ፊት" |
| NRSV, NJB | "ስሜን ለአሕዛብ የሚናገር" |
| TEV | "ስሜ ለአሕዛብ እንዲታወቅ የሚያደርግ" |

አይሁዶች ወንጌል ለአሕዛብ ማድረስ የሚለው ሃረግ ተቀባይነት የሌለው ነበር (ኤፌ 3፡7) ነገር ግን ከፍጥረት መጀመሪያ የእግዚአብሔር የዘላለም አላማ ነበር (ዘፍ 12፡31፣ ዘፀ 19፡5-6፣ ኤፌ 2፡11-3፣13) እስራኤል የእግዚአብሔር ብቸኛ መጠቀሚ በማድረግ የእግዚአብሔር አምሳል አድርጐት ነበር (ዘፍ 1፡26-27) ነገር ግን ውድቀት ተከሰተ ዘፍ 3፡15፡፡

▣ "በነገስታት" ሐዋርያው ጳውሎስ ለነገስታትና ለመንግስት ባለስልጣናት ደግሞም ለቄሳሮች ወንጌል እንዲሰብክ መሾሙን ያመለክታል፡፡

▣ "ለእስራኤል ልጆች" ሐዋርያው ጳውሎስ ወንጌልን በመጀመሪያ ያደረሰው በእየሩሳሌም ለሚገኙ ምኩራቦች ነበር (ሮሜ 1፡1) ከዚያ በመቀጠል ለአህዛብ ወንጌል አድርሷል፡፡

9፡16 "ስለ ስሜ ስንት መከራ ሊቀበል እንዲየስፈልገው እመለከተዋለሁና" መከራን ሁል ጊዜ እግዚአብሔር የሚያዘው አይደለም፡፡ ነገር ግን በሃጥያት በወደቀ ዓለም ውስጥ ክርስቲያኖች የሚያጋጥማቸው አንድ ክስተት ነው፡፡ ማቴ 5፡10-12፣ ዮሐ 15፡18-21፣ 16፡1-2፣ 17፡14፡ ሐዋ 14፡22፣ ሮሜ 5፡3-4፣ 8፡17-18፣ 2ቆሮ 4፡7-12፣ 6፡3-10፣ 11፡24-33፣ ፊሊ 1፡29፣ 1ተሰሎ 3፡3 2ጢሞ 3፡12፣ ያዕቆ 1፡2-4፣ 1ጴጥ 4፡12-16)

በክርስቶስ ስቃይ እና በአማኞች ስቃይ መሃከል የጠበቀ የስነመለኮት ግንኙነት አለ፡፡ በ1ጴጥ መፅሐፍ ውስጥ የሁለቱን ንፅፅር እንመልከት፡-

1. የኢየሱስ መሰቃየት 1ጴጥ 1፡11፣ 2፡21፣23፣3፡18፣ 4፡1፣ 13፣5፡1
2. የአማኞች ስቃይ፡- 1ጴጥ 1፡6-7፣ 2፡19፣ 3፡13-17፣ 4፡1፣ 12-19፣ 5፡9-10፣ዩሐ 7፡7፣ 15፡18-19፣ 17፡14

9፡17 "እጁንም ጭኖበት" እጆቹን በመጫን መንፈሳዊ ስጦታን እንዲቀበሉ ማድረግ እንደሚቻል የሚናገር "የሐርያት" ትምህርት አልተፃፈም ሃናኒያ በብዙዎች የማይታወቅ አማኝ ነው ነገር ግን፡- (1) የእግዚአብሔር ድምፅ ወኪል ሆነ (2) ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞላ ፀለየ (ቁ. 17)፣ (3) ከሰውነት በሽታው እንዲድን ፀለየ (ቁ.18) እና (4) ጳውሎስ እንዲጠመቅ አደረገ፡፡ (ቁ.18)

▣ "ወንድሜ ሳውል" አስገራሚ ፍቅር እና መታዘዝ የሞላበት ሐረግ ነው፡፡

9፡18 "ወዲያውም እንደ ቅርፊት ያለ ከአይኑ ወደቀ" ፀሐፊው ሉቃስ የሕኮም ቋንቋ ተጠቅሟል እርሱም የቆዳ መሰንጠቅ በአይኑ አካባቢ እንደነበር የሚናገር ምልክት አለው፡፡ ቅርፊት የአሳን ቅርፊት አይነት እንደሆነ የግሪኩ ፅሑፍ ያወሳል፡፡ ዘሌ 11፡9፣10፣12፣ ዘዳ 14፡9) ዘኃ 16፡38) እንግዲህ ከጳውሎስ አይን የወደቀው በአይኑ ላይ የነበረ የደረቀ ቆዳ ወይም የሚገፈፍ ሞራ ሊሆን ይችላል፡፡

▣ "ተጠመቀ" ሃናንያ ጳውሎስን በሚከተለው ተሞክሮ መሠረት የአዲስ ኪዳን ጥምቀት ከኢየሱስ መታዘዝ ያሳያል ማቴ 3፡13-17 ማርቆ 1፡9-11 ሉቃ 3፡21-22 እና ትዕዛዝም ነው (ማቴ 28፡19)

አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 9፡19b-22

**በደማስቆም ላሉት ደቀ መዛሙርት ጋር ጥቂት ቀን ኖረ ወዲያውም ስለ እየሱስ ክርስቶስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ በምኩራቦቹ ሰበከ፡፡ የሰሙትም ሁሉ ተገረመና ፤ ይህ በኢየረሳሌም ይህንን ስም የሚጠሩትን ያጠፋ አይደለምን? ስለዚህስ ታስረው ወደ ካህናት አለቆች ይወስዳቸው ዘንድ ወደዚህ አልመጣምን አሉ፡፡ ሳውል ግን እየበረታ ሄደ በደማስቆም ለተቀመጡት አይሁድ ይህ ክርስቶስ እንደሆነ አስረድቶ መልስ ያሰጣቸው ነበር፡፡**

9፡19a **“በልቶም በረታ”** ከሶስት ፍፁም ጾም በኋላ ጳውሎስ መበርታቱን እናነባለን፡፡

9፡20 **“ወዲያውም ስለ እየሱስ ክርስቶስ በምኩራቦች ሰበከ”** በሁለት መንገዶች መመልከት ይችላል፡፡ 1. የአገልግሎቱ መጀመሪያ ሊሆን ይችላል 2. በተደጋጋሚ የሚያደርገውን ጳውሎስ በሚገልበት ምኩራት ወንጌልን እንዴት ሊሰብክ ይችላል፡፡ (ሐዋ 9፡21) ይመልከቱ፡፡

▣ **“የእግዚአብሔር ልጅ ነው”** በሐዋርያት ስራ መፅሐፍ ውስጥ ይህ ሐረግ በዚህ ቦታ ላይ ብቻ ተፅፎ ይገኛል፤ ከመዝ 2፡7 የተጠቀሰው በሐዋ 13፡33) ይገኛል፡፡ የብሉይ ኪዳን አስተምርሆት በግልፅ ይታያል፤ (1) የእስራኤል ህዝብ (ሆሴ 11፡1)፤ (2) የእስራኤል ንጉስ (2 ሳሙ 7፡14)፤ (3) መሲሁ (ማቴ 2፡15) ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሔር አንድ አምላክ መሆኑን የሚያሳይ የስላሴን ስነመለኮት አብራርቷል፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ “የእግዚአብሔር ልጅ”**

በአዲስ ኪዳን የኢየሱስ ክርስቶስ መጠሪያ “የእግዚአብሔር ልጅ” የሚል ነው፡፡ እግዚአብሔር እንደ አባት ኢየሱስ ደግሞ “ልጅ” እና “ልጅ” በሚል መጠሪያ ይጠራል፡፡

በአዲስ ኪዳን ብቻ መቶ ሃያ አራት ጊዜ ተፅፏል የሰው ልጅ የሚለው መለኮታዊ ትርጉም ተስቶታል ዳንኤ 7፡13-14

“ልጅ” የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን ሶስት ነገሮችን ያመለክታል፡-

1. መለአክቶችን (ዘፍ 6፡2፣ ኢዮ 1፡6፣ 2፡1
2. የእስራኤል ነገስታትን ( 2ሳሙ 7፡14 መዝ 2፡7፣ 89፡26-27)
3. ሕዝበ እስራኤልን (ዘፀ 4፡22-23፣17 ዳ 14፡1፣ ሆሴ 11፡1 ማልክ 2፡10)
4. የእስራኤል መሳፍንትን)መዝ 82፡6)

በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ልጅ የሚለው በቀጥታ ለመሲሂ የተፃፈ አይደለም ነገር ግን ትንቢቶቹ ሲተረጉሙ ለመሲሁ መፃፋቸው ያመለክታሉ፡፡ የዳዊት መዝ 89 ለተጨማሪ ገለፃ ያንብቡ፡፡ በተጨማሪ የእግዚአብሔር ልጅ የሚለው ሐረግ በአይሁድ ድርሳናት የመሲሁን የሚወጣውን ስራውን የሚገልፁ ሆነው ተገኝተዋል፤ (2 Esdras T:28፣13:32፣37፣52፣14:9 እና Enoch 105:2)

የአዲስ ኪዳን መፅሐፍት የእግዚአብሔር ልጅ የሚለውን ሐረግ በግልፅ አስቀምጠው ቃል፡-

1. አለም ሳይፈጠር መኖሩን ዮሐ 1፡1-18
2. ከድንግል መወለዱን፡- ማቴ 1፡23 ሉቃ 1፡31-35
3. ጥምቀቱን፡- ማቴ 3፡17 ማርቆ 1፡11 ሉቃ 3፡22 (የሰማይ ድምፅ አረጋገጠ እርሱም የተወደደ ንጉስ መሆኑን መዝ 2 ደግሞም ለአለም ሃጢያት ሊሰዋ መሆኑን ኢሳ 53)
4. በሰይጣን መፈተኑ፡- (ማቴ 4፡1-11 ማርቆ 1፡12፣13፣ ሉቃ 4፡1-13 (በሰይጣን የተፈተነው ልጅነቱን እንዲጠራጠር ነበር)
5. ማረጋገጫን አግኝቷል፡-
   ሀ. ከአጋንንት፡- ማርቆ 1፡23-25፣ ሉቃ 4፡31-37 ማርቆ 3፡11-12
   ለ. ካላመኑ ሰዎች፡- ማቴ 27፡43፣ ማርቆ 14፡16፣ ዮሐ 19፡7
6. ከደቀ መዛሙርቱ ማረጋገጫ አገኘ
   ሀ. ማቴ 14፡33፣16፡16
   ለ. ዮሐ 1፡34፣49፣6፡69፣11፡27
7. የራሱ ማረጋገጫ
   ሀ. ማቴ 11፡25-27
   ለ. ዮሐ 10፡36
8. እግዚአብሔርን እንደ አባት መጥራቱ፡-
   ሀ. “አባት ሆይ” የሚል ሐረግ ይጠቀማል
      1. ማርቆ 14፡36
      2. ሮሜ 8፡15
      3. ገላ 4፡6
   ለ. አባት ሆይ የሚለው ሐረግ የእግዚአብሔር ጋር ያለው የጠበቀ ግንኙነት ያመለክታል፡፡

በአጠቃላይ የብሉይ ኪዳን መፅሐፍት ዕውቀት ላላቸው የሃይማኖት ሰዎች የእግዚአብሔር ልጅ የሚለው ስያሜ በስነ መለኮት ትምዕርታቸው ውስጥ ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡ ነገር ግን የአዲስ ኪዳን ፀሐፊዎች ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው የሚለውን ሃረግ ለአህዛብ፤ በጣኦት አምልኮ ውስጥ ለነበሩ ሰዎች ለመተንተን እና ለመግለፅ ቀላል አይሆንላቸውም ምክንያቱም ተመሳሳይ ድርጊቶችን ያደርጉ ስለነበር ነው ለምሳሌ አምላኪዎቹ አንድ ሴት የወለደችውን ልጅ የጣኦቱ ልጅ ተደርጐ ይቆጠር ስለነበር ለአዲስ ኪዳን ፀሐፊዎች ይህን ለይተው ማስረዳት ቀላል አልነበረም፡፡

9፡21 ይህ ጥቅስ በጥያቄ የተቀመጠ ሆኖ ፤ ነገር ግን አዎንታዊ መልስ የሚፈልግ ይመስላል፡፡

▣ “ያጠፋ” ይህ ቃል ከፍተኛ ጥፋት ወይም በቃል የሚለውን ሐሳብ ይተካል፡፡ ቃሉ በዚህ ክፍል እና በገላ 1፡13፣23 እና (መቃብ 4፡23 ላይ ብቻ ይገኛል፡፡

9፡22

| | |
|---|---|
| NASB | “ሳኦልም እየጠነከረ ሄደ” |
| NKJV | “ሳኦልም ጥንካሬ እየጨመረ ሄደ” |
| NRSV | “ሳኦልም በሃይል እየጨመረ ሄደ” |
| TEV | “የሳኦል ስብከት ሃይል እየጨመረ መጣ” |
| NJB | “የሳኦል ሃይል ጨመረ” |

በዓውዱ መሠረት ጳውሎስ እየጨመረ የነበረው አገልግሎቱ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ (በስብከት እና በመልሶቹ በጥበብ መጨመሩን ያመለክታል)

▣ “መልስ ማሳጣት” በሐዋርያው ጳውሎስ በተደጋጋሚ በአገልግሎቱ የሚያረገውን የሚናገር ሐረግ ነው፡፡ ቃሉ ከሁለት ጥምር ቃል የተሰራ ነው “በአንድ ላይ” እና “የሚፈስስ” ይህ ቃል በሐዋርያት መፅሐፍ ብቻ የሚገኝ ነው፡፡

1. ሐዋ 2፡6 ፡- ግራ መጋባት
2. ሐዋ 9፡22፡- መልስ ማሳጣት
3. ሐዋ 19፡32፡- መጨነቅ እና ግራ መጋባት
4. ሐዋ 21፡32፡- ማወክ
5. ሐዋ 21፡32፡- መጨነቅ እና ግራ መጋባት

አይሁዳውያን ሐዋርያው ጳውሎስ የሚሰብከውን ኢየሱስን ሊቋቋሙት እና ሊመልሱለት አይችሉም ነበር፡፡

▣ “ማረጋገጥ” (ሐዋ 16፡10፣19፡33) ይመልከቱ፡፡ የሐዋርያው ጳውሎስ የስብከት ዘዴ ከእስቲፋኖስ ጋር ይመሳሰላል፡፡ ሁለቱም የብሉይ ኪዳንን ትምዕርት እና የኢዲስ ኪዳንን የትንቢት ፍፃሜ የሆነው መሲሁን ኢየሱስን ይሰብካሉ፡፡

▣ “ክርስቶስ” መሲሁን ለማመልከት የሚጠቅም ስያሜ ነው (የተቀባ ይም የሚመጣው የተስፋው ቃል) ጳውሎስ ክርስቴስ ስለ ሃጢያተኞች በኢየሩሳሌም መሰቀሉን በግልፅነት ሰብኳል ነገር ግን አይሁዶች ስላልተረዱት ተቃውመውታል፡፡ (ሐዋ 4፡27) ይመልከቱ፡፡

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 9፡23-25**
**ብዙ ቀንም ሲሞላ አይሁድ ሊገድሉት ተማከሩ ሳውል ግን አሳባቸውን አወቀ፡፡ ይገድሉትም ዘንድ በሌሊትና በቀን የከተማይቱን በር ሁሉ ይጠብቁ ነበር ደቀ መዛሙርት ግን በሌሊት ወስደው በቅጥር ላይ አሳልፈው በቅርጫት አወረዱት**

9፡23 **“ብዙ ቀን ሲሞላ”** (በገላ 1፡15-24) ያንብቡ፡፡ በዚህ ጊዜ በአረብ ምድረ በዳ ነበረ፡፡ የአረብ ምድረ በዳ የሚያመለክተው የናባቲያንን ስርወ መንግስት እርሱ በአገረ ገዢው በአርተስ አራተኛ የሚመራ ነበር፡፡ ይህ አገር ገዢ ከክ.ል.በፊት 9 እስከ 10 ከክ.ል.በኋላ ድረስ መሪ ሆኖ ቆይቷል፡፡ የሶስት አመት ጊዜ በአይሁድ አቆጣጠር ለስምንት ወራቶች ገዢ ነበር፤ በአይሁድ ጊዜ አቆጣጠር የአንዱን ቀን ክፍል እንደ ሙሉ ቀን ይቆጥሩ ስለነበረ ነው፡፡ (ማቴ 26፡61፣27፡40፣63)

▣ **“አይሁድም ሊገሉት ተማከሩ”** አይሁድ ነገስታቶችን ያነሳሱ ነበር (2 ቆሮ 11፡32-33) ምክንያቱም ጳውሎስ እውነቱን በመናገሩ (2ቆሮ 11)

9፡25 **“በቅጥር ላይ”** የአንድ ግለሰብ ቤት መስኮት ከከተማው ውጪ ማሻገሪ ሆኖ ተጠቅሷል፡፡ 2ቆሮ 11፡33 ኢያ 2፡15 1 ሳሙ 19፡12

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 9፡26-30**
**ሳውልም ወደ ኡየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ ከደቀ መዛሙርት ጋር ይተባበር ዘንድ ሞከረ ሁሉም ደቀ መዝሙር እንደ ሆነ ስላላመኑ ፈሩት፡፡ በርናባስ ግን ወሰደ ወደ ሐዋርያት አገባውና ጌታን በመንገድ እንዴት እንዳየውና እንደተናገረው በደማስቀ በኢየሱስ ስምደፍሮ እንዴት እንደነገረ ተረከላቸው፡፡ በጌታም በኢየሱስ ስም ደፍሮ እየተናገረ በኢየሩሳሌም ሲወና ሲገባ ከእነርሱ ጋር ነበረ ከግሪክ አገርም መጥተው ከነበሩት አይሁድ ጋር ይነጋገርና ይከራከር ነበር እነርሱ ግን ሊገድሉት ፈለጉ፡፡ ወንድሞችም ይህን ባወቁ ጊዜ ወደ ቂሳሪያ ወሰዱት ወደ ጠርሴስም ሰደዱት፡፡**

9፡26 **“ወደ ኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ”** ይህ በዓመት ከአስራ ስመንት እስከ ሰላሳ ስድስት ወር ቢኋላ ሲሆን ነው፡፡ (ገላ 1፡15-25) በኢየሩሳሌም የነበሩ አማኞች ለብዙ ጊዜ በጳውሎስ አማኝነት አይተማመኑም ነበር፡፡
ጳውሎስ ግን በርካታ ጊዜ ኢየሩሳሌምን በወንጌል ጉደይ ጐብኝቷል፡፡

1. ሐዋ 9፡26፡- የመጀመሪያው ጉብኝቱ
2. ሐዋ 11፡30፡- ለእርዳታ ያደረገው ጉብኝት
3. ሐዋ 12፡25፡- ከሚሲዮናዊነት አገልግሎት በኋላ ያደረገው ጉብኝ ነው

4. ሐዋ 15፡2፦ በኢየሩሳሌም በነበረው ስብሰባ ላይ ጳውሎስ ተገኝቷል
5. ሐዋ 18፡22፦ የቤተ ክርስቲያን ጉብኝት ጳውሎስ አደረገ፡፡
6. ሐዋ 21፡17፦ ከያዕቆብ እና በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር በመሆን ጉብኝት አደረገ፡፡

9፡27 **"በርናባስ"** ስርው ቃሉ የመፅናናት ልጅ **"ማለት ነው"** እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ነው፤ ሐዋ 4፡36፤ከዚያ በኋላ የሐዋርያው ጳውሎስ በመጀመሪያው ሚሲዮናዊነት ባልንጀራው ነበር ሐዋ 4፡36 ይመልከቱ፡፡

▣ **"ወደ ሐዋርያት አመጣው"** ለተጨማሪ ማብራሪያ ገላ 1፡18 ያንብቡ፡፡

▣ **"ተረከላቸው"** በርናባስ ያውቃል እንዲሁም የጳውሎስን ምስክርነት ተከፍሎአል፡፡ ለሐዋርያው ጳውሎስ በር ከፋች መተዋወቂያ ምስክርነት ነበር፡፡

9፡28
NASB **"በነፃነት ሲንቀሳቀስ"**
NKJV **"ሲወጣና ሲገባ"**
NRSV **"ወቶ ገብቷል"**
TEV **"ሁሉ ቦታ ሄዷል"**
NJB **"ዞሮአል"**

በብሉይ ኪዳን የሕዝቡን የየዕለት እንቅስቃሴን ለሚመለከት በተለምዶ የሚጠቀሙበት ሐረግ ነው)ዘኊ 27፡17፣ 1ነገ 3፡7)

9፡29 **"ከግሪክ አገር መተው ከነበሩ አይሁድ ይነጋገርና ይከራከር ነበር"** እንዚህ አይሁዳዊ ሆነው የግሪክ ቋንቋ ተናጋሪዎች፣ እስቲፋኖስንም የገደሉት እንዚሁ ናቸው ፤ አሁንም ጳውሎስን ሊገድሉት ይፈልጋሉ፡፡ እስቲፋኖስ ከሞተ ተነስቷል የሚል አስተሳሰብ ነበራቸው፡፡

9፡30 **"ወንድሞች ይህንን ባወቁ ጊዜ"** ከሐዋ 22፡17-21 የምንረዳው ኢየሱስ ጳውሎስን ከዚያ ቦታ እንዲሄድ ነግሮታል፡፡ እየሱስ ለሐዋርያው ጳውሎስ አገልግሎቱን ለማበርታት እና ምሪትን ለመስጠት ይገለጥለት ነበር (ሐዋ 18፡9-11፣22፡17-21፣እና የጌታ መልአክም ተገልጦለታል ሐዋ 27፡23)

▣ **"ቂሳርያ"** በሜድትራኒያት የባህር መንገድ ያለውን የሮማውያንን የባሕር በር የሚያመለክት ነው፡፡ ሮማውያን በዚህ ስፍራ የአስተዳደር ቢሮዎሀት ነበሩአቸው፡፡

▣ **"ተርሴስ"** ሐዋርያው ጳውሎስ ከሚኖርበት ከተማ ለብዙ ዓመታት ተሰዷል፡፡ ተርሴስ ከግብፅ አሌክሳንደሪያ እና ከአቴንስ ቀጥሎ የትምህርት ማዕከል ነበረች፡፡ በፍልስፍና፣ በመምህር ማሰልጠኛ እና በህግ የታወቁ ዩኒበርስቲዎች የሚገኙባት ከተማ ነበረች፡፡ የግሪኮች ጥበብ፣ ፍልስፍና እና የአይሁድ መምህራን ለከፍተኛ ትምህርት የሚመሩበት ቦታ ነው፡፡

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 9፡31**
**በአይሁድም ሁሉና በገሊላ በሰማርያም የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት በሰላም ኖሩ ታነፁም በእግዚአብሔርም ፍርሃትና በመንፈስ ቅዱስ መፅናናት እየሄዱ ይበዙ ነበር፡፡**

9፡31 ይህ ጥቅስ የሐዋርያው ጳውሎስ መለወጥ ያመጣውን ውጤት በአጠቃላይ የሚያመለክት ነው፡፡

▣ **"ቤተክርስቲያን"** ሐዋ 5፡11 ያንብቡ፡፡ ቤተ ክርስቲያን በነጠላ ቁጥር ቢቀመጥም የቅዱሳን መሰባሰቢያ ቦታን የሚወክል ነው፡፡ በተጨማሪም አንድን የቅዱሳን ጉባኤ ሊሆን ይችላል፡፡ ቆላ 1፡18፣24፣4፡15፣16) ወይም በየቦታው ያሉ አብያተ ክርስቲያናትን (ኤፌ1፡22፣3፡10፣21፣5፡23፣24፣25፣27፣29፣32) ወይም አለማቀፋዊ የሆነችዋን ቤተክርስቲያን (ማቴ 16፡18)፡፡

▣ ሉቃስ የተጠቀመበትን ዝርዝር እንመልከት፦
1. በአብያተክርስቲያናት ሰላም ሆነ
2. አብያተ ክርስቲያናት እያደጉና እየጨመሩ መጡ
3. አብየተ ክርስቲያናት በመንፈስ ቅዱስ ተፅናኑ

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ለመርዳት ነው የተሰናዱት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋነኞቹን ጉዳዮች ለማጤን እንዲረዳ ነው፡፡ ሐሳብ ለማጫር እንጂ መደምደሚያ አይደሉም፡፡

1. ሐዋርያው ጳውሎስ ክርስቲያኖችን ከልቡ ጨክኖ ለምን ያሳድድ ነበር?
2. የሐዋርያው የጳውሎስን መቀየር ሉቃስ ሶሶት ጊዜ ደጋግሞ በሐዋርያት ስራ ውስጥ ለምን ፃፈው፡፡
3. የሐዋርያው ጳውሎስ ለወንጌል መላክ፣ እጅ መጫን እና በአናኒያ መጠመቁ ለምን አስፈላጊ ሆነ?
4. ሐዋርያው ጳውሎስ ኢየሱስን "የእግዚአብሔር ልጅ በሚል መጠሪያ መጠቀሙ ፋይዳው ምንድ ነው?
5. ሉቃስ የሐዋርያው ጳውሎስን የሶስት ዓመት የአረብ ቆይታውን ለምን አልፃፈም?

## የአውዱ እይታ ሐዋ 9፡32-10፡48

ሀ. የሐዋርያት ስራ መፅሐፍ ከጴጥሮስ አገልግሎት ወደ ጳውሎስ የሚያመራ ነው ምዕራፍ 9፡32-12፡25 የሚያመለክተው የጴጥሮስን የቅብብሎሽ አገልግሎት ነው፡፡

ለ. ጴጥሮስ በደርባን ሐዋ 9፡32-35 በኢዮጴ 9፡36-43፣10፡9-23 በቂሳሪያ 10፡1-8፣23-48 እና በኢየሩሳሌም ሐዋ 11፡1-18፣21-17፡፡

ሐ. ይህ አስፈላጊ ምዕራፍ የሚያመለክተው ለአሕዛብ ወንጌልን ለመስበክ የነበረውን ጥረት እና የጴጥሮስን ከፍተኛ ሚና የሚያያወሳ ነው፡፡ ሉቃስ የቆርኖሊዎስን ታሪክ ሶስት ጊዜ በመድገም የታሪኩን አስፈላጊነትን ፅፏል፡፡

## የቃል እና የጥምር ቃል ጥና

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 9፡32-35**

**ጴጥሮስም በየስፍራው ሁሉ ሲዞር በልዳ ወደሚኖሩት ቅዱሳን ደግሞ ወረደ በዚያም ከስምንት ዓመት ጀምሮ በአልጋ ላይ ተኝቶ የነበረውን ኤንያ የሚሉትን አንድ ሰው አገኘ ፤ እርሱም ሽባ ነበር ጴጥሮስም ኤንያ ሆይ ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈውስሃል ተነስ ለራስህም አንጥፍ አለው፡፡ ወዲያውም ተነሳ በልዳና በሰሮናም የሚኖሩ ሁሉ እርሱን አይተው ወደ ጌታ ዘወር አሉ፡፡**

9፡32 "**ጴጥሮስም በየስፍራው ሁሉ ሲዞር**" ይህ ሐዋርያቱ ሁሉ የሚያደርጉት የወንጌል ስራን ያመለክታል፡፡

▣ "**ቅዱሳን**" ቃሉ የክርስቶስን ቤተክርስቲያንን የሚያመለክት ነው፡፡ ሐዋ 9፡13 ያንብቡ፡፡ ደቀ መዝሙር የሚለው ቃል "ቅዱሳን" በሚለው ተተክቷል፡፡ በብሉይ ኪዳን "ቅዱስ" ማለት "የተለየ" ለእግዚአብሔር አገልግሎት ሊሆን ይችላል፡፡ ከፊሊ 4፡21 በስተቀር ቃሉ በብዙ ቁጥር ተፅፏል፡፡ ቅዱሳን የሚለው ቃል በሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን "ልዩ ክርስቲያን" የሚል ስያሜ አለው በአዲስ ኪዳን አማኞች ሁሉ "ቅዱሳን" ተብለዋል ይህም በክርስቶስ ፊት እውቀት የሚሰጠን ማዕረግ ነው፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ መንፃት**

በአዲስ ኪዳን ሃጢያተኞች ክርስቶስን በንስሃ እና በእምነት ሲቀበሉ ወዲያውኑ ይነፃሉ ደግሞ ይፀድቃሉ፡፡ ይህም በክርስቶስ ፊት የሚኖራቸው አዲስ ህይወት ነው፡፡ (ሮሜ 4)

ነገር ግን አዲስ ኪዳን አማኞች በቅድስናና በንፅህና መኖር እንዳለባቸው ያስገነዝባል፡፡ ይህም ማለት በክርስቶስ መስቀል ባለቀ ስራ ብንኖርም ክርስቶስን በመምሰል የየዕለት ሕይወታችንን መምራት እንዳለብን ያስጠነቅቀናል፡፡ ምንም እንኳን የዘላለም ሕይወት ነፃ ስጦታ ቢሆንም በሕይወት ውስጥ ዋጋ የሚያስከፍል መሆኑን፦

| <u>የመጀመሪያ ምላሽ</u> | <u>በቆይታ ክርስቶስን መምሰል</u> |
|---|---|
| ሐዋ 20፡23፣26፡18 | ሮሜ 6፡19 |
| ሮሜ 15፡16 | 1 ተሰሎ 3፡13፣4፡3-4፣7፣5፡23 |
| 1ቆሮ 1፡2-3፣6፡11 | 1ጢሞ 2፡15 |
| 2 ተሰሎ 2፡13 | 2ጢሞ 2፡21 |
| ዕብ 2፡11፣10፡10፣14፣13፡12 | ዕብ 12፡14 |
| | 1ጴጥ 1፡15-16 |

▣ "**በልዳ**" የበልዳ ከተማ የሚገኘው የንግዶች መንገድ በሆነው በባቢሎን እና በግብፅ መሃከል ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን "ሎድ" ትባል ነበር (1ዜና 8፡12) ከሜድትራኒያን ባህር አስራ አንድ ማይል ላይ ትገኛለች፡፡ ወንጌላዊው ፊሊጶስ የጐበኛት ቦታ ነች (ሐዋ 8፡40)

9፡33 “**ኤንያ የሚባል ሰው**” በግሪኩ “ምስጋና” ማለት ነው ይህ ሰው አማኝ መሆኑን የሚያረጋግጥ ፅሁፍ የለም ነገር ግን ጴጥሮስ በፊሊጶስ የተጀመረውን የቤተክርስቲያንን ስራ እንደገና መጐብኘቱን ያመለክታል፡፡

◘ “**ከስምንት አመት ጀምሮ በአልጋ ላይ ተኝቶ የነበረውን**” በሁሉም ትርጉሞች አንድ አይነት ሐረግ ነው (NASB, NKJV, NRJV, TEV, እና NJB) የግሪኩ ፅሁፍ ከስምንት ዓመት ዕድሜው ሀደምሮ ሽባ ነበር በማለት ያብራራዋል፡፡ )Newman and Nida, A Translator’s Hand book on The Acts of the Apostles, P. 199)

9፡34 “**ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈውስሃል**” የተለመደ አባባል ነው፡፡ ይህም መሲሁ ይህንን ፈውስ አሁን ያከናውናል በሚል ትርጉም አለው፡፡

◘ “**ተነሳና ለራስህ አንጥፍ አለው**” እነዚህ ሁለት ትዕዛዞች ትኩረት የተሰጠበት እና አስቸኳይም ነበር፡፡

◘ “**ወዲያውም ተነሳ**” ይህ የሰውየውን የጠለቀ እምነቱን እርሱም ጴጥሮስ የተናገረውን ተግባራዊ በማድረግ ሊፈወስ ችሏል፡፡

9፡35 “**በልዳና በሰሮናም የሚኖሩ ሁሉ እርሱን አይተው ወደ ጌታ ዘወር አሉ**” “ሁሉ” አማኝ መሆናቸው በመፅሐፈ ቅዱስ ውስጥ በምሳሌነት የሚጠቀስ ቦታ ነው

◘ “**ሶሮና**” በሰሜን ፊልስጤም በባህር ዳር ያለን ቦታ የሚያጠቃልል ነው፤ ከኢዮጴና ከቂሳሪያ ሰሮና አስራ ሶስት ማይል ትርቃለች፡፡

◘ “**ወደ ጌታ ዘወር አሉ**” ዘወር የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን ንስሃን የሚያመለክት ቃል ነው በተለይ ከሐጢያት ተመልሶ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እምነት መምጣትን ያመለክታል (ሐዋ 11፡21) ይመልከቱ፡፡
በሐዋርያው ጴጥሮስ እና በጳውሎስ የተደረገው ተዓምራት ብዙዎችን ወደ ወንጌል ዘወር እንዲሉ አድርጓአቸዋል፡፡

| |
|---|
| **አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 9፡36-43**<br>**በኢዮጴም ጣቢታ የሚሉአት አንዲት ደቀ መዝሙር ነበረች ትርጓሜውም ዶርቃ ማለት ነው፡፡ እርስዎም መልካም ነገር የሞላበት ምፅዋትም የምታደርግ ነበረች በዚያም ወራት ታመመችና ሞተች አጥበውም በሰገነት አኖሩአት፡፡ ልዳም ለኢዮጴ ቅርብ ናትና ደቀ መዛሙርት ጴጥሮስ በዚያ እንዳለ ሰምተው ወደ እነርሱ ከመምጣት እንዳይዘገይ እየለመኑ ሁለት ሰዎች ወደ እርሱ ላኩ፡፡ ጴጥሮስም ተነስቶ ከእነርሱ ጋር ሳለች ያደረገቻቸውን ቀሚሶችንና ልብሶችን ሁሉ እያሳዩት በፊቱ ቆሙ፡፡ ጴጥሮስም ሁሉን ወደ ውጭ አስወጥቶ ተንበርክኮ ፀለየ ወደሬሳውም ዞር ብሎ ጣቢታ ሆይ ተነሺ አላት እርስዋም አይኖችዎን ከፈተች ጴጥሮስንም ባየች ጊዜ ተቀመጠች፡፡ እጁንም ለእርሷ ሰጥቶ አስነሳት ቅዱሳንና መበልቶችንም ጠራ ህያውም ሆና በፊታቸው አቆማት፡፡** |

9፡36 “**ኢዩጴ**” ይህች ከተማ በአሁኑ ስያሜዋ “ጃፋር” ነው ለኢየሩሳሌም የወደብ ከተማ ሆና ታገለግል ነበር፡፡

◘ “**ደቀ መዝሙር**” በአዋርያት ስራ መፅሐፍ በብዛት ተጠቅሷል ትርጉሙም “ተማሪ” ማለት ነው ነገር ግን በሐዋርያት ስራ መፅሐፍ ውስጥ የተፃፈው አማኞች በሚል ትርጉም ነው፡፡

◘ “**ጣቢታ. . . ዶርቃ**” በአራማይክ “ጣቢታ” ሲሆን በግሪክ “ዶርቃ” ትባላለች በርካታ አይሁዳውያን በማህበራዊ ኑሮና በንግድ ግንኙነታቸው የሰፋ ስለነበር ስማቸው በግሪክና በአራማክ ነበር፡፡ በመሆኑም ጣቢታም ቢሆን ዶርቃ የስሙ ትርጉም የፀጋ እና የውበት ተምሳሌነት አለው፡፡ (መሃልየ መሃልየ 2፡9፣ 17፣4፡5፣7፡3)

◘ “**መልካም ነገር የሞላበት ምፅዋትም የምታደርግ**” የአይሁዳውያንን ምፅዋት ስጦታ ያሟላች ነበረች፡፡ ይህ በየሳምንቱ ለድሆች በምኩራብ ይሰጥ የነበረውን የገንዘብ ስተታ ይመለከታል፡፡ በኢየሱስ ዘመን በነበሩ ፈሪሳውያን የዚህን አይነቱ ገንዘብ በየሳምንቱ የሚሰጥ ሰው መንፈሳዊ ሰው ተደርጐ ይመሰገን ነበር ከዚያም በኋላ ቤተ ክርስቲያን ይህንን ምሳሌ ተከትላለች፡፡ (ሐዋ 6) በተጨማሪ ሐዋ 3፡2 ይመልከቱ፡፡

9፡37 “**አጥበውም በሰገነት አኖሩአት**” በአይሁድ ባህል አስክሬን ከመቀበሩ በፊት ይታጠብ ነበር በኢየሩሳሌም ሰው ሲሞት በዕለቱ መቀበር አለበት ነገር ግን ከኢየሩሳሌም ውጪ እስከ ሶስት ቀን ሊዘገይ ይችላል፡፡ (ሐዋ 5፡6) ያንብቡ

9፡38 “**ሁለት ስሞችን ወደ እርሱ ላኩ**” እነዚህ አማኞች እግዚአብሔር በጴጥሮስ እንደሚሰራ በማመን ሊያስጠሩት በሙሉ ልብ ፈቃደኞች መሆናቸው ያስገነዝባል፡፡

9፡39 “**መበልቶቹ በፊቱ ቆሙ**” እነዚህ መበልቶች ደርቃ በውስጥ እና በውጭ የምትለብሳቸውን አልባሶች በመልበስ ያለቅሱ ነበር፡፡

9፡40 “**ጴጥሮስም ሁሉን ወደ ውጭ አስወጥቶ**” አባረራቸው የሚል ትርጉም አለው በተመሳሳይ ኢየሱስም አድርጓል፡፡ (ማርቆ 5፡40) በእርግጥም ኢየሱስ ያደረገው የነበረው ተሃምራት እና በዚህ መፅሐፍ ላይ የተደረገው ታዕምራቶች

ተመሳሳይነት አላቸው የኢየሱስ የተዓምራት አገልግሎት ለሐዋርያቱ አገልግሎት ቀድሞ መሳሌ አላቸው የኢየሱስ የተዓምራት አገልግሎት ለሐዋርያቱ አገልግሎት ቀድሞ ምሳሌ በመሆን መልክ እንዳይዝ ያደረገ ነው፡፡

በዚህ ምንባብ ውስጥ የማነሳው ጥያቄ ጴጥሮስ ስሞቹን ማስወጣት ለምን አስፈለገው ኢየሱስ ይህንን ያደረገው ወንጌል ሳይሰበክ ፈዋሽነቱ ብቻ ታውቆ ወንጌል ዋጋ እንዳያጣ በመጠንቀቅ ነበር፡፡ ነገር ግን ጴጥሮስ ስሞቹን ከክፍሉ ውስጥ ማስወጣት አስፈለገው? ሊሆን የሚችለው በዚህ ተዓምራት ለወንጌል በር እንዲከፈት ሆኖ ሰዎች የእግዘአብሔርን ታዓምሪት ለማየት እንዲጓጓና እንዲነሳሱ እንጂ እንደተራ ነገር እንዳይቆጥሩበት ለመጠበቅ ይሆናል፡፡

▣ **"ተንበርክኮ"** በአይሁድ የፀሎት ባህል እጅን ዘርግቶ ወደ ሰማይ አይኑን በመክፈት ነው ነገር ግን በሐዋርያት መፅሐፍ ውስጥ ሐዋርያት ተንበርክከው ይፀልዩ ነበር ( ሐዋ 7፡60፣20፡36፣21፡5) ኢየሱስ በጌታ ሴማኔ በተመሳሳይ መልኩ ተንበርክኮ ፀልዮአል፡፡ (ሉቃ 22፡41)

▣ **"ጣቢታ ተነሺ"** ጴጥሮስ ይናገር የነበረው በአራማይክ ቋንቋ ነበር ኢየሱስ እና በእርሱ ዘመን የነበሩ አይሁድ ሁሉ አራማይክ ቋንቋ ይናገራሉ እንጂ በዕብራሲጥ ቋንቋ በቻ አልነበረም በነህምያ እና በዕዝራ ዘመን የአራማይክ ቋንቋ የተለመደ ነበር፡፡ (ነህ 8፡4-8)

9፡41 **"ቅዱሳን"** ሐዋ 9፡13 ይመልከቱ፡፡

9፡42 **"ብዙ ሰዎችም በጌታ አመኑ"** ይህ የጴጥሮስን ታአምራዊ አገልግሎት በማየት እና ስብከት በመስማት የመጣ ውጤት በመሆኑ ፀሐፊው እንደማጠቃሊያ አድርጐ ሐረጐቹን አስቀምጧቸዋል፡፡

9፡43 **"በኢዮጴም ስምኦን ከሚሉት ከአንድ ቁርበት ፋቂ ጋር አያሌ ቀን ኖረ"** ጴጥሮስ በዚህ ድርጊቱ የአይሁዳውያንን ወግና ስርዓት በመጣስ ንፁህ ከማይባል ቆዳ ፋቂ ጋር መኖሩን ያረጋግጥልናል፡፡ (ይህ ስምኦን የሞቱ እንስሶችንም እንኳን ሳይቀር ቆዳ ይፍቅ ነበር)

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ለመርዳት ነው የተሰናዱት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋነኞቹን ጉዳዮች ለማጤን እንዲረዳ ነው፡፡ ሐሳብ ለማጫር እንጂ መደምደሚያ አይደሉም፡፡

1. የሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ክርስቶስ መምጣት እና መለወጥ በሐዋርያት ስራ ላይ ሶሶት ጊዜ ትኩረት ተሰቶት ለምን ተፃፈ?
2. በሶስት ቦታ የተፃፊት የሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ክርስቶስ መምጣት እና መለወጥ በመጠኑ ልዩነት ያላቸው ለምንድነው?
3. ለሐዋርያው ጳውሎስ መለወጥ አስተዋፅኦ ያደረጉትን ዘርዝር?
4. አይሁዳውያን ጳውሎስ ሊገሉት ለምን ፈለጉ?
5. ጴጥሮስ እና ጳውሎስ ተአምራትን በማድረግ ወንጌልን ለማድረስ ምቹ በሮችን ከፍተዋል፤ እግዚአብሔር ይህንን አይነት ተዓምራት ዛሬ በብዛት ለምን አያደርግም?

# የሐዋርያት ስራ 10
## የምንባብ ክፍፍል በአዳዲሶቹ ትርጉሞች

| የተየመቅሰ[4] | አኪጀት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጲጥሮስ ቆርኖሌምስ | ቆርኖሌምስ መልክቶች ላከ | የቆርኖሌሞስ መሰወጥ | ጳጥሮስ እና ቆርኖሌሞስ | ጳፐሮስ መቶ አለቃውንጎበኘ |
| 10:1-8 | 10:1-8 | 10:1-8 | 10:1-3 | 10:1-2 |
| | | | | 10:3-8 |
| | | | 10:4a | |
| | የጴጥሮስ ራዕይ | | 10:4b-8 | |
| 10:9-16 | 10:9-16 | 10:9-16 | 10:9-13 | 10:9-16 |
| | | | 10:14 | |
| | ስምኦን በቂሳርያ | | 10:15-16 | |
| 10:17-23 | 10:17-23 | 10:17-23a | 10:17-18 | 10:17-23a |
| | | | 10:19-21 | |
| | | | 10:22-23a | |
| 10:23b-33 | ጳጥሮስ ቆርኖሌምስን ተገናኘው | 10:23b-29 | 10:23b-33 | 10:23b-33 |
| | 10:24:33 | | | |
| | | 10:30-33 | 10:30-33 | |
| ጵጥሮስ በቆርኖሊሞስ ቤተ የተናገረው | የቆርኖሌሞስ ቤተሰዎች የተሰበከው | | ጴጥሮስ ንግግር | ጴጥሮስ ቆርኖሌምስ ቤተ ተናገረ |
| 10:32-43 | 10:34-43 | 10:34-43 | 10:34-43 | 10:34-35 |
| አህዛቦች መንፈፈስ ቅዱስን ተቀበሉ | በመንፈስ ቅዱስ በአህዛቦች ላይ ወረደ | | አህዛቦች መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ | የመጀመሪያው በመንፈስ ቅዱስ መጠበቅ |
| 10:44-48 | 10:44-48 | 10-44-48 | 10-44-48 | 10-44-48 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (ከ "**መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ**" **ገጽ** vii)
***የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል***

*ይህ የጥናት* *መመሪያ* *ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።*

*ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።*

1. *ምዕራፍ አንድ*

2. ምንባብ ሁለት

3. ምንባብ ሦስት

4. ወዘተ. . .

**የቃል እና የጥምር ቃል ጥናት**

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 10፡1-8**
**በቂሣርያም ኢጣሊቄ ለሚሉት ጭፍራ የመቶ አለቃ የሆነ ቆርኔሎምስ የሚሉት አንድ ሰው ነበረ እርሱም ከቤተሰቦቹ ሁሉ ጋር እግዚአብሔርን የሚያመልክና የሚፈራ ለሕዝብም እጅግ ምፅዋት የሚያደርግ ወደ እግዚአብሔርም ሁልጊዜ የሚፀልዩ ነበር ከቀኑመ በዘጠኝ ሰዓት ያህል ቆርኔሊምስ ሆይ የሚለው የእግዚአብሔር መልአክ ወደ እርሱ ሲገባ በራዕይ በግልፅ አየው እርሱም ትኩር ብሎ ሲመለከተው ደንግጦ ጌታ ሆይ ምነድር ነው አለ መልአኩም አለው ፀሎትህና ምፅዋትህ በእግዚአብሔር ፊት ለመታሰቢያ እንዲሆን ዐረገ አሁንም ወደ ኢዮጴ ሰዎህትን ልከህ ጴጥሮስ የሚባለውን ስምኦንን አስመጣ እርሱ ቤቱ በባሕር አጠገብ ባለው በቁርበት ፋቂው በስምኦን ዘንድ መልአክ በሄደ ጊዜ ከሎሌዎቹ ሁለቱን ከማይለዩትም ጭፍሮቹ እግዚአብሔርን የሚያመልክ አንዱን ወታደር ጠርቶ ነገሩን ሁሉ ተረከላቸው ወደ ኢዮጴም ላካቸው፡፡**

10፡1 በቂጣሪያ አንድ ሰው ነበረ የቆርኖሊዮስ መለወጥ አስደናቂ ክስተት ነው:: ይህ ሰው ከወንጌል የራቀ አልነበርም ወንጌል የነበረውን ልዩነት በማጥፋት ልዩ ልዩ የሆኑ ሕብረተሰቦችን እያሸነፈ ያለበት ወቅት ነው፡፡ (1) የሰማያን ሰዎች ወንጌል አሸንፋቸዋል (2) የኢትዮጰያውን ጃንደረባ ወንጌል አሸንፎታል (3) የመቶ አለቃ የሆነውን ቆርኖሊዎስን ወንጌል አሸንፎታል፡፡ ይህ መቶ አለቃ እግዚአብሔርን የሚፈራ መሆኑን ፀሐፊው መስክሮለታል ከዚህም የተነሳ በዙሪያው የነበሩትን የስጋ ዘመዶቹን ጌታ እንዲያምኑ ግድ ብሏቸዋል ሐቁ 10፡1 24 27 44 48) ሐዋርያው ጴጥሮስ በእየሩሳሌም በነበረው ስብሰባ ላይ ተናግሮታል (ሐዋ 15፡7-9) ከዚህም የተነሳ ለአሕዛቦች ወንጌልን መስበክ እንዲፈቀድ መንገድን አመቻችቷል፡፡

▣ "**ቆርኖሊዎስ**" (FF Bluce's *Commentary on the book of the Acts*, p. 214) ያንብቡ፡፡ ቆርኖሊዎች የሚለው ስያሜ በሮማውያን ዘንድ የተለመደ ስም ነው ለምሳሌ (ፑቡለስ ቆርኖሊዎስ ሱላ በ82 ከክርስቶስ ልደት በፊት አስር ሺ የሚያህኩሉ ባሪያዎትን በነፃ ለቅቋዋቸል እነዚህም ባራያዎች ጂንስ ቆርኖሊዎስ ለተባለው ንጉስ የሚገብሩ ነበሩ፡፡ የመቶ አለቃ በአዲስ ቢዳን ይህ ቃል ብዙ ጊዜ ተጠቅሷል ማቴ 8፡5 ሉቃ 7፡2፣ 23፡47 ሐዋ 10፡1፣ 22፡5 27፡3 ወዘተ) መቶ አለቆች ማለት የመቶ ሰዎች አስተዳደሪ ማለት ነው፡፡

▣ "ደጣሊቄ ለሚሉት የኢጣሊያን አንድ ጭፍራ" ስድስት ሺ ወንዶች ያህሉ ነበር እዚህ ምንባብ ውስጥ ባልተለመደ ሁኔታ አንድ ሺ ፈቃደኛ ወታደሮች ያሉበት ምድብ ተከማችቶ ነበር የሮማውያን ወታደሮች በኢየሩሳሌም ዙሪያ በብዛት ይሰፍሩ ነበር የአይሁድን አመፅ ይፈሩ ስለነበር::

10፡2 "የሚያመልክና የሚፈራ" ሶስት መግለጫዎተን መስጠት ይቻላል፡፡
1. እግዚአብሔርን የሚያከብር (ቁ 22)
2. ለሕዝቡ እርዳታን ቸርነትን የሚያደርግ ነበር
3. የፀሎት ሕይወት የነበረው ሰው መሆኑን ያረጋግጥልናል ቁ. 22 13 16 26)

ቆርኖሌዎስ የመንግስት ባለስልጣን ቢሆንም ከምኩራብ ጋር የተቆራኘ ግንኙነት ነበረው ነገር ግን የዳነ መሆኑን ምልክቶቹን የፈፀመ አልነበረም፡-
1. አልተገረዘም ነበረ
2. ምስክሮች ባሉበት የውሃ ጥምቀት አልወሰደም
3. በመቅደስ መስዋት ማድረግ

እነዚህ ዝርዝርሮች አህዛቦችን ወደ አይሁዳውያን ዕምነት እንዳይመጡ የሚከለክሏቸው ዋና ዋና ምክንያቶች ነበሩ፡፡

▣ "**ከቤተሰቦቹ ጋር**" በሐዋርያት ስራ መፀሐፍ የቆርኖሌዎስ ቤተሰቦች አማኞች በመሆን የመጀመሪያዎቹ ናቸው (ሐዋ 10፡2፣ 11፡14፣ 16፡15፣31፣ 18፡8)፡፡ በአይሁድ ባህል የአባት ሃይማኖት የቤተሰቦቹ ይሆናል፡፡ ከዚህም ባለፈ ዘሮቹም ሳይቀር ይከተሉት ነበር፡፡

▣ "**እጅግ ምፅዋት**" ለእግዚአብሔር ስጦታን መስጠተን ያመለክታል ለአይሁዳውያን ቆርኖሊዎስ የምኪራብ ተሳታፊ እና እግዚአብሔርን መፍራቱን አረጋጋጭ የሆነውን ምፅዋት በመስጠቱ ተቀባይነት ነበረው ( **ምፅዋት** ሐዋ 3፡2) ለተጨማሪ ግንዛቤ ያንብቡ፡፡

▣ **"ወደ እግዚአብሔር ሁል ጊዜ የሚፀልይ"** ከዚህ ሃረግ ውስጥ ሶስት የአሁን ጊዜ ቀጣይነት ያለውን አመልካች ጊዜያት ያሳያል፡፡

1. እየፈራ
2. ምፅዋት እያደረገ
3. ዘወትር እየፀለየ

የቆርኖሊዎስ ሕይወት ለእግዚአብሔር በየቀኑ የመስጠት እና እርሱን በመፍራት ቤተሰቦቹን መምራት ነበር የአይሁድ መምህርት ከደነገጉት ሕገ ደንብ ሁለቱን ያደረግ ነበር እነርሱም ምፅዋት መስጠት እና ፀሎት ናቸው፡፡

10፡3 **"ሰጠኝ ሰዓት"** ይህ የማታ መስዋት የሚቀርብበት ሰዓት ነው ( ዘፀ 25፡39 41 1ነገ 18፡29 መዝ 5፡11 ዳንኤ 6፡10) ለአይሁድ የፀሎት ሰአታቸው ነው፡፡

▣

NASB, NRSV

| | |
|---|---|
| TEV | "በግልፅ አየ" |
| NKJV | "አየ በግልፅ" |
| NJB, NIV | "አረጋግጦ አየ" |

በወንጌላት ለማረጋገጫ እናንብብ (ማርቆ 1፡45 ዮሐ 7፡10) ሌላው የዚህ አይነት ክስተት የሚገኘው በዚህ ምህራፍ ውስጥ ነው ራዕዩ የታየው በቀን መሆኑን ከምንባቡ መገንዘብ ይቻላል፡፡

▣ **"በራዕይ የእግዚአብሔር መልአክ"** ሐዋርያው ጳውሎስ በደማስቆ ካየው ጋር ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል:: እግዚአብኤር ቆርኖሊዎስን ማናገሩ በፈቃድ ለድነት ምርጫ ጣራው እንጂ የሰው ምርጫ እንዳልታከለበት መረዳት ይቻላል፡፡

10፡4 የመልአኩ ንግግር ሁለት ግልፅ መልእክቶችን የያዘ ነው ዐረገ እና በእግዚአብሔር ፊት ለመታሰቢያ እግዚአብሔር ቆርኖሊዎስ ወንጌልን ከመቀበሉም በፊት ፀሎቱን እና ምፅዎቱን እና አምልኮውን እንደተቀበለው ምንባብ ያስረዳናል፡፡

▣ **እርሱም ትኩር ብሎ ሲመለከት** (ሐዋ 1፡10) ይመልከቱ

▣ **"ጌታ ሆይ ምንድነው"** የዚህን ሐረግ ፍቺ በቀላሉ ማግኘት አይቻልም
ነገር ግን መላምቶቹን እንመልከቱ ፡- (1) ጌታዬ ማለት አንድ ሰው ለማክበር ከእድሜ ወይም ከኑሮ ደረጃ የተነሳ (2) ጌታ ማለት ገዥ እና ሉአላዊ የሚል ትርጉም ይሰጣል:: ተከታዩን ጥቅስ በማንበብ ተጨማሪ ግንዛቤ ማግኘት ይቻላል ( ዮሐ 4፡1 11፡15፣ 19፡49)፡፡

በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ተጨማሪ አማራጮች ያሉ ይመስላል፡፡ ቆርኔልዮስ መላዕክቱን እንደ ግታ ነበር ያሰበው (ራዕይ 7፡14)፡፡ እናም እንግዲህ ይሻላል የሚለው ከተፈጥሮ ሃይል በላይ የሆነውን ያሳያል በተለይም ኢየሱስን በማመልከት፡፡ በ8፡26 እና 29 የጌታ መልዓክም እንደ መንፈስ ተገለፆአል፡፡ ይህም ተነፃፃሪነጽ በድምፅ እና በመንፈስ መሃከልም ተገልፆአል (10፡13,14,15 እና 19,20)፡፡

10፡5 **ሰዎችን ወደ ኢዮጴ ልከህ** በመልአኩ የተነገረው ትዕዛዝ ያለበት ንግግር ነው፡፡ መልአክ ወንጌልን ለቆርኖሊዎች አልመሰከረለትም ነገር ግን ጴጥሮስን ወንጌልን እንዲነግረው ሲልከው እንመለከታለን፡፡ እግዚአብሔር ሰዎችን ይጠቀማል (ዘፀ 3፡7-10)፡፡

10፡7 **ከሎሌዎቹ ሁለቱን ከማይለዩትም ጭፍሮች እግዚአብሔርን ከሚያመልክ** እነዚህ ሎሌዎች የቆርኖሊዎች ቤተሰቦች መሆናቸው ግልፅ ነው፡፡

10፡8 ቆርኖሊዎስ እና ቤተሰቦቹ ጌታን አመኑ እምነቱን በስራ ላይ የሚያው ሰው ብዙዎችን የሚማርክ ይሆናል፡፡

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 10፡9-16**

**እነርሱም በነገው ሲሄድ ወደ ከተማም ሲቀርቡ ጴጥሮስ በስድስት ሰዓት ያህል ይፀልይ ዘንድ ወደ ጣራው ወጣ ተርቦም ሊበላ ወደደ ሲያዘጋጅለት ሳሉም ተመስጦ መጣበት ሰማይም ተከፍቶ በአራት ማዕዘን የተያዘ ታላቅ ሻማ የሚመስል ዕቃ ወደ ምድር ሲወርድ አየ በዚያውም አራት እግር ያላቸው ሁሉ አራዊትም በምድርም የሚንቀሳቀሱት የሰማይ ወፎችም ነበሩባት ጴጥሮስ ሆይ ተነሳ አርደህ ብላ የሚልም ድምፅ ወደ እርሱ መጣ ጴጥሮስ ግን ጌታ ሆይ አይሆንም አንዳች ርኩስ የሚያፀይፋም ከቶ በልቼ አላዉቅምና አለ፡፡ ደግሞም ሁለተኛ እግዚአብሔር ያነፃውን አንተ አታርክሰው የሚል ድምፅ ወደ እርሱ መጣ ይህም ሶስት ጊዜ ሆነ ወዲያውም ዕቃው ወደ ሰማይ ተወሰደ፡፡**

10፡9 **በስድስት ሰዓት ያህል** በአይሁድ ህብረተሰብ በየዕለቱ ስድስት ሰዓት ላይ የሰርክ መስዋትና ፀሎት የሚቀርብበት ሰዓት ነው የዚህ ሰዓት ፀሎት ፈርሳውያን በጠዋት እና በማታ ለማይችሉ ከርቀት ለሚመጡ ሰዎች የጨመሩት

የፀሎት ጊዜ ነው ጴጥሮስ ይህንን የፀሎት ባህል የሚከተል ነበር:: በዚህ ምንባብ ደግሞ ይህ የፀሎት ጊዜ ከመድረሱ በፊት እንዳንቀላፋ እንገነዘባለን።

10፡10 **ተርቦም** ጴጥሮስ ራዕዩን ያየበትን ሁኔታ ስናጤን ተርቦና በስምኦን ቆዳ ፋቂው የላኛው ቤት ሆኖ የሚድትራኒያንን ውቅያኖስ ማየት በሚችልበት ቦታ ሆኖ ነበር።
*ረሃብ ሚለው ቃል በግሪክ ፅሁፎች ውስጥ በዚህ ስፍራ ጥቅም ላይ እንደዋለበት ዓይነት ነው። በቀጥታ የተጠቀሰበትን ማወቅ አስቸጋሪ ነው። ግን በተጨማሪም ከባድ ረሃብ ሊሆን ይችላል። ቢሆንም ግን በዚህ ያለው ዓውዱ አስደናቂ ነው። ሉቃስ ለምን የህንን እንደተጠቀመ ማንም እርግጠኛ መሆን አይችልም ግን ያም ቢሆን የአውዱ መንፈስ አጠቃላይነት ያለው ነገር ነው።*

▣ ***"ተመስጦ መጣበት"*** ይህ ልምምድ ከጴጥሮስ ቁጥጥር በላይ ነው (ማርቆ 5፡42 16፡8፤ ሉቃ 5፡26)። እና በግሪክ ፅሁፍ ውስጥ የተለመደ ንግግር ነው የእንግሊዘቃው ሐሴት ወይም ከፍተኛ ደስታ የሚል ትርጉም ከግሪኩ አለው።ይህ ማለት አይምሮአችን እየሰራ ነገር ግን በሰመመን በመሆን እግዚአብሔር ለመንፈሳችን እንዲናገር መፍቀድ ማለት ነው በሐዋ 10፡3 ጋር ካለ የማይመሳሰል ነው።

10፡11

| | |
|---|---|
| NASB | ***"ሰማይ ተከፈተ"*** |
| NKJV , TEV | ***"ሰማያት ተከፍተው"*** |
| NKJV | ***"የሚታየው ሰማይ ተከፍቶ"*** |
| NJB | ***"ሰማያት በግልፅ ተከፍተው"*** |

*ሐረጉ በጥቅሉ ሲተረጉም ሰማያት ባለማቋረጥ እየተከፈቱ ነው የሚል ትርጉም ይሰጣል። በብሉይ ኪዳን ሰማያት በብዙ ቁጥር ተፅፈዋል በመሆኑም በዚያ ጊዜ ለነበሩት የሰማይ መከፈት መንፈሳዊው ዓለም ገሃዱን አለም በማለፍ ለሰዎች መታየቱን የሚያበስር ነው (ሕዝ 1፡1 ማቴ 3፡16 ማርቆ 1፡10 ሉቃ 3፡21 ዮሐ 1፡51 ሐዋ 7፡56 10 11 ራዕይ 4፡1 19 11)።*

▣ ***"ታላቅ ሸማ"*** *መርከበኞች የሚጠቀሙበት ቋንቋ ነው።*

10፡12 **"አራት እግር ያላቸው ሁሉ አራዊትም በምድርም የሚንቀሳቀሱት የሰማይ ወፎችም ነበሩበት"** *ተመሳሳይ ሃሳብ ይመልከቱ* (ዘፍ 1 እና 6፡20) እነዚህ እንስሳት በአይሁድ ባህል የነፁ ያልነፁ በመባል ይታወቃሉ።

10፡13 "**ድምፅ ወደ እርሱ ወጣ**" በብሉይ እና በአዲስ ኪዳኖች መሃከል የእግዚአብሔርን ድምፅ በግልፅ እንደነበረ የሚያረጋግጥ አንድም ንባብ የለም አይሁዳውያን በዚህ ወቅት አንድ ነገር እውነተኝነቱ ለማረጋገጥ Bath kol የሚባለውን ይጠቁም ነበር ከሚከተሉት ጥቅሶች መረዳት ይቻላል (ማቴ 3፡17 17 5 17 5 እና ሐዋ 9፡7 እና ሐዋ 10፡1

10፡14 **"ጌታ ሆይ አይሆንም አንዳች ርኩስ የሚያፀይፊም ከቶ በልቼ አላውቅም"** አይሆንም የሚለው ቃል በግሪክ ጠንካራ ተቃውሞ ያለበት ነው; ጴጥሮስ የአይሁድን ባህል ላለመልቀቅ ከጌታ ጋር እየታገለ ነው። የጴጥሮስ እያንዳንዱ ሐይማኖታዊው ድርጊቶቹ በዘሌ 11 መሠረት ነው:: ተመሳሳይ ሃሳብ ይመልከቱ (ማርቆ 7፡14)

10፡15 **"እግዚአብሔር ያነፃውን አንተ አታሪክሰው"** ይህ የትዕዛዝ ቃል አሁኑኑ እንዲፈፀም የሚጠይቅ ነው።

10፡16 **"ይህም ሶስት ጊዜ ሆነ"** በመፅሐፍ ቅዱስ ሶስት ጊዜ አንድን ነገር መደጋገም የተለመደ ነው በዚህም ትኩረት መስጠቱን ያመለክታል። (1) ኢየሱስ በጌቴ ሴማኒ የአትክልት ስፍራ ፀልዩአል (ማርቆ 14፡36 39)፣ (2) ኢየሱስ ከትንሳኤ በኋላ ጴጥሮስን አናግሮታል (ዮሐ 21፡17) (3) የጳውሎስ የስጋው እሾክ ከእርሱ ላይ እንዲነቀል ፀልዩአል (2 ቆሮ 12፣8) ለተጨማሪ ግንዛቤ (ኢሳ 6፡3 ኤር 7፡4) ያንብቡ
A.T Roberston, *Word Pictures In the New Testement* has an incisike word at this point
*የጌታ የሆነውን ድምፅ ችላ በማለት ወደ ተሳሳተ መንገድ ሰዎች መሄዳቸው የተለመደ ሆኖአል:: ጴጥሮስ ሶስት ጊዜ የመጣውን የጌታን ድምፅ ችላ ብሎት ቢሆን ኖሮ ወንጌል ለቆርኖሊዎስ ቤት ባልተሰበከ ነበር።*

> *አአመመቅ* (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 9፡17-23a
> ***ጴጥሮስም ስላየው ራዕይ ምን ይሆን ብሎ በልቡ ሲያመነታ እነሆ ቆርኔሌዎስ የላካቸው ሰዎች ስለ ስምኦን ቤት ጠይቀው ወደ ደጁ ቀረቡ ድምፃቸውንም ሰፋ አድርገው ጴጥሮስ የተባለው ስምኦን በዚህ በእንግድነት ተቀምጦአልን ብለው ይጠይቁ ነበር ጴጥሮስም ስለ ራዕዩ ሲያወጣ ሲያወርድ ሳለ መንፈስ እነሆ ሶስት ሰዎች ይፈልጉአል ተነስተህ ውረድ እኔም ልከአቸዋለሁና ሳትጠራጠር ከእርሱ ጋር ሂድ አለው ጴጥሮስም ወደ ሰዎቹ ወርዶ እነሆ የምትፈልጉት ምንድነው አላቸው እነርሱም ፃድቅ ሰው እግዚአብሔርን የሚፈራ በአይሁድም ህዝብ ሁሉ የተመሰከረለት የመቶ አለቃ ቆርኔሌዎስ ወደ ቤቱ ያስመጣህ ዘንድ ከአንተም ቃልን ይሰማ ዘንድ ከቅዱስ መልአክ ተረዳ አሉት እርሱም ወደ ውስጥ ጠርቶ እንግድነት ተቀበላቸው::***

**10፡17 ጴጥሮስ ስላየው ራዕይ ሲያመነታ** በፀሐፊው ሉቃስ ይህ ሐረግ በአይምሮ መወሰን አለመቻልን ለማመልከት ይጠቀምበታል ሉቃ 9፡7 ሐዋ 2፡12፣ 5፡24 10፡17)፡፡

ጴጥሮስ እና ቆርኖሊዮስ ራዕዩን ያዩበት መንገድ ተመሳሳይ ነው ሐዋ 10፡3 እና ቁ 19) ይመልከቱ::

10፡19 ***መንፈስም አለው*** በዚህ ዓውድ ውስጥ ያለው መንፈስ ቁ. 19 እና መልአክ ቁ. 3፡22 ተናገረ የሚለው ሃሳብ ዝምድናውን ለመለየት አስቸጋሪ ነው፡፡ መልአኩ መንፈስ ቅዱስን ወክሎ ተናግሯል ወይም ሁለቱም በብሉይ ኪዳን እንደነበረው የስላሴዎች በሌላ ስያሜ መገለጥ ሊሆን ይችላል፡፡ (ዘፀ 3፡2,4 ሐዋ 8፡26,29)፡፡

10፡20 ግልፅ የሆነ ንግግር ነው

1. ተነሳ ፡- ትዕዛዝ ነው
2. ውረድ ፡- ወዲያ እንዲፈፀም የተላለፈ ትዕዛዝ ነው
3. ልኬአቸዋለሁ ፡- በሌላ አካል የተነገረ ነው እንጂ በሰዎቹ ፍላጐት አይደለም
4. ሳትጠራጠር፡- አትጠራጠር የሚል እዎቅ ትዕዛዝ አለው
5. ከእነርሱ ጋር ሂድ ፡- ትዕዛዝ ነው

ይህ ለሐዋርያው ጴጥሮስ ምርጫ የተሰጠበት ምንባብ አይደለም ነገር ግን ትዕዛዙን እንዲፈፀም የተጠየቀበት ነው

10፡22 በታማኝነት እና የንፁው ልብ የሆነውን ሁሉ የተናገሩበት ነው፡፡

▣

| | |
|---|---|
| NASB | **"ፃድቅ"** |
| NKJV | **"ትክክለኛ ሰው"** |
| NKJV NJB | **"ቅን"** |
| TEV | **"መልካም ሰው"** |

እነዚህ ከላይ በዝርዝር የምንመለከታቸው ቃላቶች በብሉይ ኪዳን መፅሐፋት አንድን ከወቀሳ ነፃ የሆነን ሰው ለማመልከት የሚገለገሉበት ቋንቋ ነው ዘፍ 6፡1፣ አዮ 1፡1፣ ሉቃ 1፡6፣ 2፡25) ወይም የክርስቶስን ፅድቅ ለመግለጥም አገልግሏል (ሮሜ 4)

▣

| | |
|---|---|
| NASB, NRSV | |
| NJB | **"እግዚአብሔርን የሚፈራ"** |
| NKJV | **"ፈረሃ እግዚአብሔር ያለው"** |
| TEV | **"እግዚአብሔርን የሚያመልክ"** |

ቆርኖሌዎስን ለመግለፅ የጠቀመ ዓረፍተ ነገር ነው (ሐዋ 10፡2 22፡35) በሐዋ 13፡16፣ 26፡43,50 ላይ የተጠቁሰት ሰዎች በዘር አይሁድ ወይም አክራሪ ቀናተኞች የሚባሉ አይደሉም ነገር ግን እግዚአብሔርን ይፈራሉ የሚባሉ ከምኩራብ የማይለዩ መንፈሳዊ ሰዎት ናቸው (ሐዋ 16፡14) ቁ 17፡4,17፣ 18,7)

10፡23 **"እርሱም ወደ ውስጥ ጠርቶ እንግድነት ተቀበላቸው ሐዋርያው ጴጥሮስ"** በዚህ ሐረግ መሠረት የአይሁድ አባቶችን ህገ ደንብ መጣሱን ያረጋግጣል፡፡ ጴጥሮስ ከአህዛቦች ጋር በእንግድነት መቀመጡም የባህል ጥሰት አድርጐ ወንጌልን ማስበለጡን ያሳያል (ሐዋ 10፡48)፡፡

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 10፡23 — 29**

**በነገውም ተነስቶ ከእነርሱ ጋር ወጣ በኢዮጴም ከነበሩት ወንድሞች አንዳንዶቹ ከእነርሱ ጋር አብረው ሄዱ በነገውም ወደ ቂሳሪያ ገቡ ቆርኔሌዎስም ዘመዶቹንና የቅርብ ወደጆቹን በአንድነት ጠርቶ ይጠባበቃቸው ነበር ጴጥሮስም በገባ ጊዜ ቆርኔሌዎስ ተገናኝቶ በእግሩ በታች ወደቀና ሰገደለት ጴጥሮስ ግን ተነሳ እኔ ራሴ ደግሞ ሰው ነኝ ብሎ አስነሳው ከእርሱም ጋር እየተነጋገረ ገባ ብዙዎችም ተከማችተው አግኝቶ አይሁዳዊ ሰው ከሌላ ወገን ጋር ይተባበር ወይም ይቃረብ ዘንድ እንዳልተፈቀደ እናንተ ታውቃላችሁ ለእኔ ግን እግዚአብሔር ማንንም ሰው ርኩስና የሚያፀይፍ ነው እንዳልል አሳየኝ ስለዚህ ደግሞ ብትጠሩኝ ሳልከራከር መጣሁ አሁንም በምን ምክንያት አስመጣችሁኝ ብሎ እጠይቃችኂለው አላቸው፡፡**

10፡24 **"በኢዮጴም ከነበሩት ወንድሞች ከእርሱ ጋር አብረው ሄዱ"** ሐዋ 11 እና 12 የሰዎቹ ብዛት በቁጥር ስድስት ነበሩ ሐዋርያው ጴጥሮስ ይሄ ክስተት ከአይሁድ ስደት እንደሚያመጣበት ያውቃል በመሆኑ ከእርሱ ጋር የአይን እማኞች አብረውት እንዲሄድ አድርጓል (ሐዋ 11፡12)፡፡

▣ **"ቂሳርያ"** ባህር ዳር አጠገብ የምትገኝ የተዋበች ከተማ ነበረች የስሙ መገኛ ቂሳር ከሚለው የክብር ስያሜ ነው:: በዚህች ከተማ ሮማውያን የጦር ወታደሮቻቸውን አስፍረው ነበር እንዲሁም የባህር በሩን ለንግድ ይጠቀሙበት ነበር፡፡

▣ "ዘመዶቹን እና የቅርብ ጓደኖቹን ጠርቶ ቆርኖሊዎስ" እግዚአብሔር የሚናገረውን እንዲሰሙ ቤተሰቡን፣ ባልጀሮቹን፣ አገልጋዬቹን ጠርቷል ጴጥሮስን ተሰብስበው ለሰአታት ጠብቀውት ሊሆን ይችላል በዚህ የተሰበሰቡት ጉጉታቸውን በአይነ ሕሊና ማሰም ሁሉ ይቻላል። እነዚህ ሁሉ ቆርኖሌዎስ ያየውን ራዕይ እየተነጋገሩበት እንደነበር እንገምታለን።

ይህ በአይሁዳዊ አዕምሮ የማይታሰብ ነው እንደውም አህዛብ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ የሚለው አመፅ ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል።

10:25,27 "በገባ ጊዜ. . .እየተነጋገረ ገባ" በግሪኩ ፅሁፍ ላይ ሁለቱን ገባ የሚለውን ቃል የመጀመሪያው ገባ ቁ 25 የግቢው በር እና የሁለተኛ ገባ ቁ 27 የሚለው ደግሞ :- የቆርኖሊዎስ የቤቱን በር መሆኑን በግልፅ አስቀምጦታል) ነገር ግን በምንም መንገድ ይሁን ጴጥሮስ ይህንን በማድረጉ የአይሁድን የመንፃት ህግ ተላልፎ ተገኝቷል።

10:25 "ከእግሩ በታች ወደቀና ሰገደለት" በዕብራይስጡ ፅሁፍ የተለመደ አባባል ሲሆን በወንጌላት ግን ከአምልኮ ጋር ይገናኛል። በዚህ ዓውድ ግን የአክብሮት ስግደትን ያመለክታል (NJB) የጴጥሮስን መምጣት ያሰናዳው መልአኩ ነው በመሆኑም ቆርኖሌዎስ የአክብሮት ሰግደት አቅርቧል (ራዕ 19:10፣ 22:8-9)።

10:28 "አይሁዳዊ ሰው ከሌላ ወገን ጋር ይተባበር ወይም ይቃረብ ዘንድ እንዳልተፈቀደ እናንተ ታውቃላችሁ" ጴጥሮስ በምኩራብ ትምህርት ቤተ የተማረውን እየተናገረ ነው። ይህ የብሉይ ኪዳን ትምህርት አይደለም ነገር ግን የአይሁድ መምህራን ህገ ደንብ ነው።

▣ በሌላ ወገን ይህ ሐረግ በአዲስ ኪዳን የሚገኝበት በዚህ ቦታ ብቻ ነው ሉቃስ በተመሳሳይ እንግዳ ቃላትን በርካታ ጊዜ ይጠቀማል።

1. *Prsebēs* ቁ. 27 መስጠት (2ጴጥ 2:9)
2. *Prospernes* ቁ. 10 ረሃብ
3. *dien thumeomai* ቁ. 19 ማንፀባረቅ
4. *sunomileō* ቁ. 27 ንግግር
5. *athomiton* ቁ. 28 ያልተፈቀደ
6. *allophkō* ቁ. 28 ሌላ ወገን
7. *anantirrētos* ቁ. 29 ሳልከራከር (ሐዋ 19:36)
8. *prosōporemptēs* ቁ. 34 ማክበር (ሮሜ 2:11 ኤል 6:9 ያዕቆ 2:19)
9. *katacrunasenō* ቁ. 38 መቃወም (ያዕቆ 2:6)
10. *procheirotoneō* ቁ. 41 አስቀድመው የተመረጡ

ፀሐፊው ሉቃስ በሐዋርያት ስራ መፅሐፍ ያሉትን ስብከቶች እና ክስተቶች ሁሉ ከሌሎች ምንጮች ወይም በቃሉ መጠየቅ አግኝቶ መፃፍን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማግኘት ያስቸግራል።

▣ "ለኔ ግን እግዚአብሔር ማንንም ሰው እርኩስ የሚያፀይፍ ነው እንዳልል አሳየኝ" ጴጥሮስ ከእግዚአብሔር ተማረ ጴጥሮስ የተመለከታቸው በሻማ ላይ የነበሩት እንስሳት የሰው ዘርን ሁሉ በእግዚአብኤር አምሳል የተፈጠሩ መሆናቸውን የሚያስገነዝብ ነው (ዘፍ1:26-27) እግዚአብሔር የቆርኖሊዎስን ቤተሰቦች እና ባልንጀሮቹን እንደሚወዳቸው ለጴጥሮስ አሳየው። ይህ የእስቲፋኖስን እና የፊሊጶስን አገልግሎት የሚያረጋግጥ ነው።

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 10:30 -33**

**ቆርኔሌዎስ እንዲህ አለው በዚች ሰዓት የዛሬ አራት ቀን የዘጠኝ ሰዓት ፀሎት በቤቴ እፀልይ ነበር እነሆም የሚያንፀባርቅ ልብሜ የለበሰ ሰው በፊቴ ቆመና ቆኔልወስ ሆይ በእግዚአብሔር ፊት ፀሎትና ተሰማ ምጎዋተሀም ታሰበ እንግዲስ ወደ የዮጴ ልከህ ጴጥረስ የተባለውን ስምኦንን አስጠራ እርሱ በቁርበት ፋቂው በስምኦን ቤት በባህረ አጠገብ እንግድነት ተቀምአል አለኝ። ስለዚህ ያን ጊዜ ወደ አንተ ላክን አንተም በመምጣትህ መልካም አድርገሃል። እንግዲህ አንተ ከእግዚአብሔር ዘንድ የታዘዝኸውን ሁሉ እንድንሰማ እኛ ሁላችን አሁን በእግዚአብሔር ፊት በዚህ አለን።**

10:30 "የሚያንፀባርቅ ልብስ" መልክቶች በዚህ መንገድ ለሰዎች መገለጣቸው የተለመደ ነበር። (ማቴ 28:3 ማርቆ 16:5፣ ዮሐ20:17፣ ሉቃ 24:4)

10:31 ቆሮሊሞስ ሦስተኛ ጊዜ ማረጋገጫ አግኝቶዋል (ሐዋ 4,22) ቆሮኖሊዋስ ብቻ ሳይሆን ባልንጀሮቹ፣አገልጋዮቹ፣ቤተሰቦቹ በክርስቶስ አምነዋል። በሐዋርያት ስራ ይህ አንዱ የቤተሰብ ድነት የታየበት ምንባብ ነው።

በምዕራቡ ዓለም ስነመለኮት ትምህርት የኖረ ሰው በህብረት ውሳኔ ውስጥ ለመሳተፍ ላይፈልግ ይችላል ነገር ግን ብዙ የዓለም ክፍሎች ውስጥ ያሉ ባህሎች ማዕበራዊ ኑሮን እና ውሳኔን የለዱ ናቸው:: በመሆኑም እግዚአብሔር በወደደው መንገድ ወይም ሰዎች ባሉበት ባህል ሁኔታ ወንጌልን ሊያቀርብላቸው ይችላል። ወንጌል የሚሰበክበት አንድ አይነት ቅርፅ የለውም።

10:33 በቆርኖሌዎስ ቤት የተሰበሰቡት ሰዎች ለመስማት የተዘጋጀ ነበሩ ምክንያቱም የሚነገረው መልዕክት ከእግዚአብሔር እንደሆነ በማመናቸው ነው፡፡

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 34-43**
**ጴጥሮስም አፋን ከፍቶ እንዲህ አለ እግዚአብሔር ለሰው ፊት እንዳያዳላ ነገር ግን በአሕዛብ ሁሉ አሕዛብ ሁሉ እርሱን የሚፈራና ፃድቅን የሚያደርግ በእርሱ የተወደደ እንደ ሆነ በእውነት አስተዋልሁ፡፡ የሁሉ ጌታ በሚሆን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እየሰበከ ይህን ቃል ወደ እስርኤል ልጆች ላከ ዩሐንስ ከሰበከው ጥቅምት በኃላ ከገሊላ ጀምሮ በይሁዳ ሁሉ የሆነውን ነገር እናንተ ታውቃላችሁ፡፡ እግዚአብሔር የናዝሬቱ ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በሃይልም ቀባው እርሱም መልካም እያደረገ ለዲያብሎስም የተገዙትን ሁሉ እየፈወሰ ዞረ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበርና እኛም በአይሁድ አገርና በኢየሩሳሌም ባደረገው ነገር ሁሉ ምስክሮች ነን እርሱን በእንጨት ላይ ሰቅለው ገደሉት እርሱን እግዚአብሔር በሦስተኛው ቀን አስነጣው ይገለኝም ዘንድ ሰጠው ይኸውም ለህዝብ ሁሉ አይደለም ነገር ግን በእግዚአብሔር አስቀድሞ የተመረጡ ምስክሮች ለሆንን ለእኛ ነው እንጂ ከሙታንም ከተነሣ በኃላ ከእርሱ ጋር የበላን የጠጣንም እኛ ነን ለህዝብም እንድንሰብክና በህያዋንና በሙታን ሊፈርድ በእግዚአብሔር የተወሰነ እርሱ እንደ ሆነ እንመሰክር ዘንድ አዘዘን በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የሃጢአቱን ስርየት እንዲቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል፡፡**

10:34 **"በእግዚአብሔር ለሰው ፊት እንዳያደላ"** የመጀመሪያው የሐዋሪያው ጴጥሮስ ስብከት ለቆርኔሌዎስ ቤተሰቦች ይህን ይመስል ነበር፡፡ ይህ በአዝዛቦች ወንጌል በሚሰበክበት ቦታ ሁሉ እንደ ምሳሌ ይህ ዐረፍነገር ይነገር ጀመር ዘዳ (0:17, 2 ዜና 19:7) እና ለሕዝቡ (ዘዳ 1:17 :10:19) በእግዚአብሔር ባህሪ መግለጫ ተደርጎም ተፅፏል (ሮማ 2:11፣ ገላ 2:6፣ ኤል 6:9፣ ቆላ 3:24-25፣ 1ጴጥ 1:17)፡፡ በብሉይ ኪዳን ቃሉ ፊትን መመለስ የሚል ፈቺ ይሰጣል፡፡ በመሆኑም እግዚአብሔር ለሁሉም በእኩል የሚፈርድ ከሆነ እስራኤልን ልዩ የሚያደርጋት የለም ስለዚህ በዚህ ርዕስ ትንታኔ የተሰጠባቸውን ስነመለኮቶች መጠንቀቅ ይኖርብናል፡፡ እግዚአብሔር ምንም ሌላ ተወዳጅ (ሕዝቦችን፣ ዘሮችን ወይም ግለሰቦች) የሉትም፡፡ ይህ እውነት ከሆነ ታዲያ እንዴት ነው የተለየ ሊሆን የሚችለው? ዘመናዊ ቅርጽ ያለውን የስና መለኮት በጥንቃቄ ተመልከቱት፡፡

10:35 **"እግዚአብሔር ለሰው ፊት እንዳያደላ ነገር ግን በአህዛብ ሁሉ እርሱን የሚፈራና ፅድቅን የሚያደርግ በእርሱ የተወደደ"** ዐረፍተ ነገሩ ስለ ነፈስ ድነት የሚናገር ሳይሆን ለእግዚአብሔር ምፅዋትን፣ፀሎትን እና ልመናን ስለማድረግ ነው፡፡ (ሐዋ 3:2) ይመልከቱ፡፡ ይህ ዐረፍተ ነገር በስነ መለኮት መነፅር መታየት ይገባዋል (ዩሐ 1:12፣ 3:16; ሮሜ 10:9-13)፡፡

እግዚአብሔር አይሁድን የተቀበላቸው ስለሚፈሩ አይደለም፤ ነገር ግን ስለ ወደዳቸው ነው፡፡ ይህ በእየሩሳሌም ስብሰባ ጭብጥ ሃሳብ ነበር፡፡

10:36 **"ይህን ወደ እስራኤል ልጆች ላከ"** ይህ የሚያመለክተው የኢየሱስን እና የሐዋርያቱን ስብከት ነው እንጂ ብሉይ ኪዳንን አይደለም፡፡

▣ **"በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እየሰብከ"** ከኢሳ 52:7 የተጠቀሰ ነው፡፡ በአዲስ ኪዳን "ሰላም" የሚለው ቃል ሶስት ፍቺ አለው፡ (1) በእግዚአብሔር እና በሰዎች መሃከል ያለውን ሰላም ያመለክታል፣ (2) አማኞች (ቆላ 1:20) ያገኙትን ሰላም ያመለክታል (ዮሐ14:27; 16:33 ፊሊ. 4)፡፡ (3) ሰዎች ለክርስቶስ መልካም ምላሽ በመስጠታቸው ያገኙትን ሰላም ያመለክታል፡፡ (ኤል 2:14-3:6; ቆላ 3:16)፡፡ ሁሉም ሰዋዊ የሆነ መሰናክል በሙሉ ተወግዶአል (ገላ 28፣ ቆላ 3:11)፡፡

▣ **"የሁሉ ጌታ በሚሆን"** የአለምን ህዝብ ሁሉ ወደ እውነተኛው ወንጌል የሚጠራ ቃል ነው፡፡ (ሐዋ 2:36፣ ማቴ 28:18; ሮማ 10:12፡ኤፌ 1:20-22; ቆላ 2:10, 1 ጴጥ3:22) ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሁሉም አምላክ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ በወረዳ ቀን የሰበከውን ዓይነት የቃላት አጠቃቀም በቆርኖሌዎስ ቤተ ተጠቅሞበት እናነባ፡፡

10:37,39 **"የሆነውን ነገር እናንተ ታውቃላችሁ"** ሐዋሪያው ጴጥሮስ መንፈስ ቅዱስ በወረደ ቀን ከተናገረው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡(ሐዋ 2:22, 33)

በቆርኒሌሞስ ቤተ የተሰበሰቡ ሁሉ በእርግጥ በቂ የሆነ ግንዛቤ ስላላቸው ይሆን እናንተ ታውቃላችሁ ያላቸው? ወይስ ጳጥሮስ እያገነነ ነው? ወይስ የቆርኔሌሞስ ሰራተኞች አይሁዳውያን ናቸውን? ሉቃስ ስለፃፋፈው ፅሁፍ መላምቶች አሉ፡፡

አንዳንዶቹ ይህንን ስብከት ለመግለጽ እንደሚከተለው ተጠቅመዋል፡፡

1.ሉቃስ ሁሉንም ስብከቶች በሐዋርያት ስራ ውስጥ ጽፏል (ግን ሉቃስ ኮይኔ በሚባለው የጽሑር አይነት ጥሩ ቢሆንም 36-38 ያሉት ግን መልካም አይደሉም፡፡
2.ሉቃስ ደካማ የሆኑ የሰዋሰው አገባባቸውን እንኳን ሳያስተካክል ጽሁፎቹን በታማኝነት ተጠቅሞበታል፡፡
3.ይህም ዓረፍተ ነገር በቀጣዮቹ የሐዋርያት ስራ አንባቢዎች ዘንድ የተረዱት ነው፡፡ (*The Jerome Commentary*, Voll, 11 p. 189)፡፡

**10:37 "ዮሐንስ ከሰባኪው ጥምቀት"** ኢየሱስ የተጠመቀው ጥምቀት ለምንድን ነው ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው? ምክንያቱም የዮሐንስ ጥምቀት የንሰሐ ጥምቀት ነበርና፡፡ ኢየሱስ ንሰሐ ወይም ይቅርታ አያስፈልተውም፡፡ እርሱ ሃጢአት የሌለበት ስለነበር፡፡ (2ቆሮ 5:21፣ ዕበ 4:15፣ 7:26፣ 1ጴጥ 2:22፣ 1ዮሐ 3:5) ቲዮሪውም እንደሚታየው

1. ለአማኞች ምሳል ነው የእርሱን አርአያ ይከተሉ ዘንድ
2. የአማኞች መግለጫ በመሆኑ
3. ለአገልግሎት የሚያጭበት አንድ መንገድ ስለሆነ
4. የመዳን ምሳሌ በመሆኑ
5. የዩሐንስን አገልግሎት እውነተኝት ለመመስከር
6. ሰለሞቱ ቀብሩ እና ትንሳኤው ትንቢታዊ ተምሳሌት ስላለው (ሮማ 6:4)

የዮሐንስ ጥምቀት የኢየሱስ አገልግሎት በመንፈስ ተሞልቶ እንደ ጀምር ያደረገ ስርአት ነው፡፡ ሁሉም የወንጌልን ፀሐፊዎች ይህንን ፅፈዋል በኢየሱስ ላይ መንፈስ ሲወርድ በ ህዝብ ፊት ለመጀመሪይቱ ቤተክርስቲያን የአዲስ ነገር ጅማሬ ሆኖላታል፡፡

**10:38 "እግዚአብሔር የናዝሬት ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በሃይል ቀባው"** ጴጥሮስ የማረጋገጫ ቃል ለቆርኔሌዎስ ቤተሰቦች ተናገር፡፡

1. እግዚአብሔር ቀብቶታል (መሲህ ሆኖአታል)
2. በንፈስ ቅዱስ (አዲሱን ዘመን ያመለክታል)
3. በሃይል (ውጤታማ አገልግሎትን ያመለክታል)
   ሀ. መልካም በመስራት
   ለ. በመንፈስ እስራት በመፍታት
4. እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበር (እግዚአብሔር ፈንታ መሆን ይችላል ማለት ነው)

(F.F Brucc *Answers to Questions*, pp 171-172) ያንብቡ፡፡

"Xpiele" የሚለው ግስ አምስት ጊዜ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተፅፏል፡፡ አራቱ የሚያመለክቱት ክርቶስ በእግዚአብሔር እንደተቀባ ነው ሉቃ 4.18፣ ከኢሳ 61፡፡ 1ዕብራ 1:9 ደግሞ ከመዝ 45:7 ጠቅሷል፡፡ ሐዋ 4:27 ከመዝሙረ ዳዊት ውስጥ ከተወሰደበት ስፍራ ከዚያም በፍጥነት ከወሰደበት ስፍራ እንዲሁም በሐዋ 10:38 እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን በመንፈስ እንደቀባው በተገለጸበት ስፍራ፡፡

ክሪይጋማ የሚለውን ልዩ ሰንጠረዥ ይመልከቱ በ2:14 ላየ ያለውን ይመልከቱ፡፡

**10:39 "እነርሱም በእንጨት ላይ ሰቅለው ገደሉት"** እነርሱ የሚያመለክተው የአይሁድ ሃይማኖት መሪዎችን፣ሕዝቡን፣የሮማውያን ባለስልጣኖችን ነው፡፡ (ሐዋ 2:23) በእንጨት ላይ የሚለው ቃል በሐዋ 5:30፣ ዛዳ 21:23 ተጠቅሳል፡፡ የእንጨት ላይ ስቅላት በአይሁድ ማህበረሰብ የውርደት መትን ለማመልከት ነው፤ ነገር ግን በጊዜው የነበሩ መምህራን ይህንን የሮማውያን ስቅላት አድርገው ተርጉመውታል፡፡ በብሉይ ኪዳን የተባለውን እርግማን ኢየሱስ በእንጨት ላይ በመስቀል ሃጢያት ሆኖ እርግማኑን አሰወገደው፡፡ (ኢሳ 53) (ገላ 3:13)፡፡

**10:40 "እግዚአብሄር አስነሳው"** በአዲስ ኪዳን በኢየሱስ ትንሳኤ ጊዜ የስላሴ ተግባር በግልፅ ታይቷል፡፡ መንፈስ ቅዱስ (ሮማ 8:11) (1) ኢየሱስ ክርስቶስ ዩሐ 2:19-22;10:17-18 (2) አባት(እግዚአብሔር) 2:24,32; 3:15,25; 4:10; 5:30; 10:40; 13:30,33,34,37; 27:31; ሮማ 6:4-9) (3) ይህ ከላይ ያየነው የተጨበጠ ማስረጃ የኢየሱስ ክርስቶስ ህይወት፣ሞቱ እና ስለ አብ ያስተማረው ትምዕርቱ እውነቱ መሆኑን የበለጠ ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡ የሐዋርያት ስራ ዋና ጭብጥ ሃሳብም ይሄው ነው፡፡

▣ **"በሦስተኛው ቀን" ከ1 ቆሮ 15:4 ጋር መዝ 16:10** የሚያነፃፅሩ ሰዎች አሉ ነግር ግን በይበልጥ ዮሐ 1:17 ማቴ 12:40 ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡

**10:40-41 "ይገለጥም ዘንድ ሰጠው ይሄውም በሰው ሁሉ አይደለም"** ኢየሱስ ለተለያዩ አይነት ሰዎች ተገልጧል፤(ዩሐ 14:19,24; 15:27; 16:16,22; 1ቆሮ 15:5-9)፡፡

**10:41 "ከእርሱ ጋር የበላን የጠጣንም እኛ ነን"** የኢየሱስ የትንሳኤ አካል ለተለያዩ አይነት ሰዎች ተገልጧል፤ (ዩሐ 14:19,24; 15;27; 16:16; 2:1 ቆሮ 15:5-9)

**10:42 "እንድንሰብክ አዘዘን"** ማቴ 28:18-20; ሉቃ 24:47-48; ሐዋ 1:8,ዩሐ 15:27) ይህ ወንጌል በኢሩሳሌም ተጀምሮ እስከ ምድር ዳርቻ እንደደረስ በታቀደው መሰረት ሊሳካ ችሏል፡፡

▣ **"በሕያዋንና በሙታን በሚፈርድ"** ክርስቶስ በእግዚአብሔር ለፍርድ ተሹሞአል፡፡ 1 ዳንኤ 7:13-14;ዩሐ 5:22,27; ሐዋ 17:31, 2 ቆሮ 5:10 2ጢሞ 4:1;1 ጳጥ 4:5 ኢየሱስ በፍጥረት ላይ ታሹምአል (ዮሐ 1:3; ቆላ 1:16; ዕብ 1:2)፡፡ ኢየሱስ ለማዳን እንጂ ለፍርድ አልመጣም ነበር (ዮሐ 3:17-19)፡፡

"ህያውና ሙት" የሚለው ሀረግ ወደፊት ያለውኝ የመጨረሻውን ፍርድ ያመለክት ነበር፡፡ አንዳንድ አማኞች በህይወት የሚኖሩ ናቸው (ተሰ 4:13-18)፡፡

**10:43 "ነብያቱ ሁሉ ይመሰክሩለታል"** ኢየሱስ ለሁለቱ ደቀ መዛሙርቶች በኤማአስ ታይቷል (ሉቃ 24:13-35) ለአይሁድ ታአማኒነትን ያገኘው ደግሞ ኢየሱስ በሰገነቱ ቤት ላይ ለደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ተገልጧል (ሐዋ 3:18)

▣ "በስሙ" (ኢዩ 2:32 እና ሉቃ 24:47) ለተጨማሪ ግልፅ ትንተና ጥቅሶቹን ያንብቡ።

▣ "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የሐጢያቱን ስርየት እንዲቀበል" የወንጌል መልእክት ነው።

1. እያንዳንዱ
2. በስሙ በኩል
3. የሚያምን ሁሉ
4. የሐጢያት ይቅርታ ይቀበላል

እያንዳንዱ ሰው ለመዳን ማድረግ የሚጠበቅበት ዝርዝር ነው። እግዚአብሔር በሃጢያት የወደቀውን የሰውን ልጅ እንደገና እያነሣው ያለው በቃል ኪዳን ነው። እግዚአብሄር የድንቅ ጥሪ ጀማሪ ቢሆንም የሰው ልጆችን ፈቃደኝነት እና የልብ ምርጫ አጥብቆ ይፈልገዋል። እርሱም በንስሃ፣በእምነት፣ በመታዘዝ እና በትዕግስት ወደ እርሱ እንዲቀርቡ ነው።

በይቅርታና በንስሃ መሃከል ያለውን ግንኙነት የሚያብራራ መፅሐፍ ማንበብ ጠቃሚ ይሆናል። (Frank stag, New Testament theology,) በመፃፍ የሚከተለውን ቀንፅል ሐሳብ እንመልከት፡-

የእግዚአብሔር ይቅርታ ሰዎችን ስለ ሃጢያት ንቁ እንደሆኑ እና ከክፉ ስራቸው የሚመለስ ነው። ይህ የእግዚአብሔር ይቅርታ ማረጋገጫ ሰዎች ንስሃ ከገቡ በኃላ የሚሆን ነው። (1 ዩሐ1:9) ንስሃ በሌለበት ይቅርታ ይኖራል። የሚል ማስረጃ አይገኝም በቆርኖሌዎስ ቤት ጴጥሮስ ንስሃ መግባት በማመን እንደሚከናወን ተናግራል። (ሐዋ 10:43) በማመን ሰው ሐጢያቱ እንደሚሰረይ መፅሐፉ ያስተምራል። ይህ ማለት ንስሃ ከይቅርታ በላይ ነው ማለት አይደለም በተጨማሪም ንስሃ ስለተገባ ብቻ በዘላቂነት ይቅርታ እናገኛለን ማለት አይደለም። ሃጥያተኛው ሃጥያተኛ እንደሆነ መረዳት ይኖርበታል። ሃጥያተኛው ሃጥያቱ ይቅር እንስኪባል ድረስ ሃጥያተኛ ነው። የእግዚአብሔርን አሉታዊ ምላሽ በመቀበል አውንታዊ ምላሽ ይሰማል።

| |
|---|
| **አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 10:44-48**<br>***ጴጥሮስ ይህን ነገር ገና ሲናገሩ ቃሉን በሰሙት ሁሉ ላ መንፈስ ቅዱስ ወረደ ጴትሮስም ጋር የመጡት ሁሉ ከተገረዙት ወገን የሆኑ ምዕመናን በሕዝብ ላይ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በለፈሰስ ተገረሙ በልሳኞች ሲናገሩ እግዚአብሔርንም ሲያከብሩ ሰምተዋቸዋልና በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ መልሶ እነዚህ እንደ እኛ ደግሞ መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉ እንዳይጠመቁ ዉሃን ይከለክላቸው ዘንድ የሚችል ማጥ ነው አለ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምም ይጠመቁ ዘንድ አዘዛቸው። ከዚህ በኃላ ፅቂጽ ቀን እንዲቀመጥ ለመኑት።*** |

10:44 ሐዋሪያው ጴጥሮስ ስብከቱን ሳይጨርስ *መንፈስ ቅዱስ* መውረዱን ያሳያል።

▣ "*ቃሉን በሰው ሁሉ ላይ*" በስነ መለኮት ትኩረት የተሰጠው ለቆርኔሌዎስ ሳሆን ነገር በእርሱ ቤት ተሰብስባው ለነበሩት ባልንጀረቹ ነው፤ እግዚአብሔር ግን ሁሉንም ተቀብሏቸዋል። ይህ የአሕዛብ ወደ እግዚአብሔር መንግስት ቅበላ የአዲስ ዘመን መምጣት አመላካች ነው።

በሐዋርያት ስራ መፅሐፍ ክስተቶቹ ቅድመ ተራቸውን ሳይጠብቁ በተገላቢጦሽ መምጣታቸው አስደናቂ ሆኖአል፤ ይህም ሰዎች በውሃ ሳይጠመቁ መንፈስ ቅዱስ በላያቸው ይሰስስ ነበር (ሐዋ 2:28 እና ሐዋ 8:17) ሉቃስ የፃፋ መሆን የነበረበትን ሳሆን የሆነውን ነው።

10:45 በሐዋ 10:46 አንድ አይነት የመንፈስ ቅዱስን ስራ መመልከት ይችላል። ይህ ምልክት ለቆርኔሌዎች ቤተሰቦች ብቻ ሳይሆን ከጴጥሮስ ጋር ሄደው ለነበሩ ለተገረዙም አይሁዳውያ ጭምር ነበር (ሐዋ 10:47)

ሐዋርያው ጳውሎንም እና ጴጥሮስ በእየሩሳሌም በነበረው ስብስብ ላይ እግዚአብሔር በክርስቶስ አህዛብን እንዲቀበላቸው ማስረዳት ችለዋል።

▣ "*የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ*" የመንፈስ ቅድስ አገልግሎት በግልፅ (በዮሐ ወ 16:8-14) ተቀምጧል። የመንፈስ ቅዱስ ስራ አንድ ስለሃጢያት መውቀስ ሌላው ስለደህንነት መናገር በፍፃሜውም በልባችን መኖሩ ከክፍ እንድንጠበቅ ያደርጋል። ይህ የአዲስ ኪዳን ዋና አጀንዳ ነው በመሆኑም ያለ መንፈስ ቅዱስ ሃይል በመንፈሳዊዉ አለም ምንም መሆን አይችልም።

▣ "*መንፈስ ቅዱስ ወርዶ*" ወርዶ የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን የነበረውን መስዋት ያመለክታል። በአዮኤል 2:28 ተተንብዮአል፤ ጴጥሮስም በስብከቱ ጠቅሶታል (ሐዋ 2:17,33) መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ለአማኞች የሚሰጥ ስጦታ ነው።

10:47 ይህ የንግግር ጥያቄ ነው፤ አሉታዊ መልስ የሚፈለግም ነው። የአይሁድ አማኞች ጴጥሮስ ወደ ኢዩጴ ለመሸት ስምምነት ላይ መድረሳቸውን ያስገነዘበናል።

10:48 "በኢየሱስ ክርስቶስ ስምም ይጠመቁ ዘንድ አዘዛቸው" በዚህ ቦታ የተጠቀሰው ጥምቀት በአመኑ ጊዜ ወዲያው የተከናወነ ነው። በሐዋ 2:28 እና 19:5 እንደተፃፈው ጥምቀቱ የተከናወነው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንጂ በአብ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም አልነበረም ነገር ግን ሐዋርያቱ ይመለከቱ የነበረው ቅርፁን መጠበቁ ሳይሆን የሰዎቹን ልብ በማየትቸ ጥምቀቱን ያከናውኑ እንደነበር ለመረዳት አያዳግትም።

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጐመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ለመርዳት ነው የተሰናዱት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋነኞቹን ጉዳዮች ለማጤን እንዲረዳ ነው። ሐሳብ ለማጫር እንጂ መደምደሚያ አይደሉም።

1. የቆርኔሌዎስ መዳን አስፈላጊ ሆኖ ለምን ተፃፈ?
2. የጳውሎስን እና የቆርኔሌዎስን የመዳን ልምምድ አብራራ?
3. ጴጥሮስ የተመለከተው በሸማ የወረዱት እንስሳት እና የሰጠውን ትንታኔ በስነ መለኮት ያለውን ፋይዳ አስረዳ።
4. ቆርኔሌዎስ እና የባልንጀሮቹ መዳን ችግር የሚያመጣ ይመስልሃል?
5. የሐዋሪያው ጴጥሮስን ስብከት በዝርዝር አውጡና በሐዋርያት ስራ መፅሐፍ ውስጥ ካሉት የደህንነት ስብከቶች ጋር አዛምድ።

# የሐዋርያት ስራ 11

## የምንባቡ ክፍፍል በአዲሶቹ ትርጉሞች

| የተየመቅሰ[4] | አኪጆት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የጴጥሮስ መረጃ ለኢየሩሳሌም ቤ)ክርስቲያን | ጴጥሮስ ስለ እግ)ር ፀጋ ተናገረ | የጴጥሮስ መከላከያ | የጴጥሮስ መረጃ ለኢየሩሳሌም ቤ/ክርስቲያን | የጴጥሮስ ባህሪ በኢየሩሳሌም |
| 1፡1-18 | 1፡1-18 | 11፡1-18 | 11፡1-4 | 11፡1-10 |
| | | | 11፡5-17 | |
| | | | | 11፡11-14 |
| | | | | 11፡15-17 |
| | | | 11፡18 | 11፡18 |
| ቤተክርስቲያን በአንፃኪያ | በናባስ እና ጳውሎስ በአንፃኪያ | በአንፃኪያ ለክረኮች ወንጌል ተሰበከ | ቤተክርስቲያን በአንፃኪያ | በአንፃኪያ የቤተክርስቲያን ምስረታ |
| 11፡19-26 | 11፡19-26 | 11፡19-26 | 11፡19-26 | 11፡19-21 |
| | | | | 11፡22-44 |
| | | | | 11፡25-26 |
| | እርዳታ ለአይሁድ | ለኢየሩሳሌም ላሉት ቤተክርስቲያን እርዳታ ተላከ | | በርናባስ እና ጳውሎስ ተሾሙ |
| 11፡27-30 | 11፡27-30 | 11፡27-30 | 11፡27-30 | 11፡27-30 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (ከ "**መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ**" **ገጽ** vii)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. ምንባብ አንድ
2. ምንባብ ሁለት
3. ምንባብ ሦስት
4. ወ.ዘ.ተ……

አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 11፡1-18

ሐዋርያትና በይሁዳም የነበሩት ወንድሞች አህዛብ ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ተቀበሉ ሰሙ፡፡ ጴጥሮስም ወደ ኢየሩሳሌም በወጣ ጊዜ ከተገረዙት ወገን የሆኑት ሰዎች ከእርሱ ጋር ተከራክረው ወዳልተገረዙት ሰዎች ገብተህ ከእነርሱ ጋር በለህ አሉት ጴጥሮስ ግን ከመጀመሪያው ጀምሮ በተራ ገለጠላቸው እንዲህም አለ እኔ የኢዮጴ ከተማ ስፀልይ ሳለሁ ተመስጬ ራዕይን አየሁ ታላቅ ሸማ የመሰለ ዕቃ በአራት ማዕዘን ተይዞ ከሰማይ ወረደና ወደ እኔ መጣ ይህንም ትኩር ብዬ ስመለከት አራት እግር ያላቸው የምድር እንሰሶች አራዊትንም ተንቀሳቃሾችንም የሰማይ ወፎችንም አየሁ፡፡ ጴጥሮስ ሆይ ተነሣ አርደህ ብላ የሚለኝንም ድምፅ ሰማሁ፡፡ እኔም ጌታ ሆየ አይሆንም ርኩስ ወይም የሚያፀይፍ ከቶ ወደ አፌ ገብቶ አያውቅምና አልሁ፡፡ ሁለተኛም እግዚአብሔር ያነፀውን አንተ አታርክሰው የሚል ድምፅ ከሰማይ መለሰልኝ፡፡ ይህም ሦስት ጊዜ ሆነ እንደ ገናም ሁሉ ወደ ሰማይ ተሳበ፡፡ እነሆም ያን ጊዜ ሦስት ሰዎች ከቂሣርያ ወደ እኔ ተልከው ወዳለሁበት ቤት ቀረቡ፡፡ መንፈስም ሳልጠራጠር ከእነርሱ ጋር መጡ ወደዚያ ሰውም ቤት ገባን፡፡ እርሱም መልአክ በቤቱ ቆሞ እንዳየና ወደ ኢዮጴ ሰዎች ልከህ ጴጥሮስ የተባለውን ስምኦንን አስመጣ እርሱም ለመናገርም በጀመርሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ለእኛ ደግሞ በመጀመሪያ እንደወረደ ለእነርሱ ወረደላቸው ዮሐንስ በውሃ አጠመቀ እናንተ ግን በመፈንቀሰ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ ያለውም የገታ ቃል ትዝ አለኝ፡፡ እንግዲህ እግዚአብሔር በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ላመነው ለእኛ ደግሞ እንደ ሰጠን ያን ስጦታ ለእርሱ ከሰጠ እግዚአብሔርን ለመከልከል እችል ዘንድ እኔ ማን ነበርሁ ይህ በሰሙ ጊዜ ዝም አሉና እንኪያስ እግዚአብሔር ለአሕዛብ ደግሞ ለህይወት የሚሆን ንስሐን ሰጣቸው እያሉ እግዚአብሔርን አከበሩ፡

11፡1 ይህ የሚያመለክተው የቤተክርስቲያን አመራር በግዜው በነበረው ክስተት መለወጡን ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ የታላቁ ተልኮን አላማ ለመገንዘብ ያዳግታል (ማቴ 28፡18-20 ሉቃ 24፡47፣ ሐዋ 1፡8)፡፡

▣ "ወንድሞች" የአማኞች መጠሪያ ነው፡፡ (ሐዋ 1፡15፣ 6፡3፡ 9፡30 10፡23፣ 11፡1 12 29፣12፡17፣14፡2፣5፡1,3,2,23,32,33,40; 16:2, 40;17:6,10,14,18:18,27;21:7,17,22:5;28:14-15) ክርስቲያን መሆን የአንድ ቤተሰብ አባል መሆን ማለት ነው፡፡

▣ "በይሁዳም የነበሩት" ቤተክርስቲያን የነበራትን ውስን የራዕይ ስፋቷን የሚያሳይ ነው፡፡ ከባህል እስራት የተነሣ ቤተክርስቲያን ለብዙ ለማይቆጠሩ አመታት ወንጌልን ለሌሎች አላደረሰችም ነበር፡፡ ኢየሱስ የተናገረውን አላከበረችም (ሐዋ 1፡8)፡፡

▣ "አህዛብ የእግዚአብሔርን ቃል ተቀበሉ" ወንጌል ሰዎች የሚቀበሉት ስጦታ መሆኑን ያመለክታል 1ዮሐ 1፡12 3፡16፣ ሮሜ 10፡9-13፣ ኤፌ 2፡8-9)፡፡

የእግዚአብሔር ቃል አቻ ቃሉ ወንጌል ሊሆን ይችላል ይህም የብሉይ ኪዳን የትንቢት ፍፃሜ ነው፡፡

11፡2 "ጴጥሮስ ወደ ኢየሩሳሌም በወጣ ጊዜ" ለሕዛቦች ወንጌልን መስበክ እስከ ምዕራፉ አስራ አምስትና ምዕራፉ ቀጥሎ ይታያል፡፡ ይህም በኢየሩሳሌም ለነበረው የቤተክርስቲያን አመራር ችግር ሆኖም ነበር፡፡ ክርስቲያኖች የሆኑ አይሁዳውያን የዘረኝነት መድልዎ ያደርጉ ነበር፡፡

▣

| | |
|---|---|
| NASB | "እነዚያ የተገረዙ" |
| NKJV | "የተገረዙ" |
| NRSV, NIG | "የተገረዙ አማኞች" |
| TEV | "እነዚያ የአህዛቦችን መገረዝ የማፈልጉ" |
| Williams | "የመገረዝ ደስታ" |

ይህ ሐረግ የተለያዩ ትርጉሞች ተሰተውታል፡ (1) ከጴጥሮስ ጋር የሄዱትን ሰዎች ያመለክታል (ሐዋ 10፡45) (2) በኢየሩሳሌም ያሉትን አማኞች የሚያመለክት ነው (ሐዋ 11፡18) (3) የኢየሩሳሌም አማኞች እና የማያምኑ አይሁድን ያመለክታል (ሐዋ 1፡7፣2፡4፡5፡10፡12)፡፡

የእነዚህ ሰዎች እምነት ጥያቄ የሚነሣበት አልነበረም ነገር ግን ወንጌል ሁሉን ለመቀበል የተከፈተ በር መሆኑ ከነበራቸው ባህል ጋር በመገጨቱ የሙሴ ሕግ ፈፅሞ የሚሻር አስመስሎት ነበር፡፡ ይህ ጽነት በስራ ሳይሆን በፀጋ መሆኑ ሁሉን አዲስ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

▣

| | |
|---|---|
| NASB | "አጥብቆ መያዝ" |
| NKJV | "ክርክር" |
| NRSV, TEV | "ትችት" |
| NIB | "ተቃውሞ" |

የሰዋሰው ህጉ በድግግሞች የኃላፊውን ጊዜ ያመላክታል፡፡ ሃይማኖተኛ አይሁዳውያን ከወንጌል ጋር ሳይሆን ከጴጥሮስ ጋር ንትርክ ይዘዋል፡፡ ነገር ግን የወንጌል ቃል መመርመር አይፈልጉም፡፡

11፡3 **“ወዳልተገረዙት ገብተህ ከእነርሱ ጋር በላህ አሉ”** በሰዋሰው ህግ ይህ አረፍተ ነገር በሐተታ ወይም በጥያቄ መልክ የተቀመጠ ሊሆን ይችላል፡፡

በአይሁድ ባህል አብሮ መመገብ የተለመደ ነበር፡፡ ይህ በዘሌዋውያን መፅሐፍ ትዕዛዙ ተፅፎ ይገኛል፡፡ (ዘሌ 11) አይሁድ ከከነአናውያን ጋር በማዕድ አብረው አይቀመጡም ነበር፡፡ በመሆኑም በጥንት ቅርብ ምስራቅ አብሮ መመገብ የቃል ኪዳን ምልክት ነበር፡፡
ኢየሱስ ክርስቶስ አብሮ በመመገቡ ተወቅሷል፡፡ (ማቴ 9፡11፣ 11፡19 ሉቃ5፡30፣ 15፡2)፡፡

ጴጥሮስም ተመሳሳይ ችግር ገጥሞታል (ገላ 2፡12) በመጀመሪያ ምህተ ዓመት ለነበሩ ሰዎች ባህልን፣ ልማዶችን በማክበር ካልሆነ በቀር ወንጌልን መስበክ የማይቻል ነበር፡፡ (1ቆሮ 12፡13፣ ገላ 3፡23-29፣ ቆላ 3፡11)፡፡

11፡4-18 ሐዋርያው ጴጥሮስ በስምኦን እና በቆርቆሌዎች ቤት ያሳለፈውን በግልፅ ለአይሁድ መሪዎች በኢየሩሳሌም ተናገረ (ሐዋ 10) በኢየሩሳሌም በነበረው ስብሰባም ላይ ተናገረ (ሐዋ 15)፡፡ ይህ የሚያሳየው ጉዳዩ ለወንጌል ስራ አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡

11፡4
NASB **“ደረጃውን ጠብቆ”**
NKJV **“በደረጃ ከመጀመሪያ ጀምሮ”**
NRSV **“አንድ በአንድ”**
TEV **“ሙሉ ታሪኩን”**
NJB **“ነጥብ በነጥብ በዝርዝር”**

*Kathexes* የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን በሉቃስ ብቻ ነው የተፃፈው (ሉቃ 1፡3 8፡1፣ ሐዋ 3፡24፣11፡4፣18፡23) የሉቃስ አፃፃፍ ግልፅ የሆነ የሂሳብ ፋስቱን የጠበቀ ነው፡፡ ይህ ሉቃስ ምርምሩን ያደረገበትን ዘዴውን ያመለክተናል (ሉቃ 1፡1-4)፡፡

11፡6 **“ትኩር ብዬ ስመለከት”** (ሐዋ 1፡10) ይመልከቱ፡፡

11፡12
NASB **“ያለ ፍርሃት”**
NKSV **ልጠራጠር”**
TEV **“ሳይለያይ”**
NIB **“ሳላወላውል”**

በግሪክ ፅሁፎች ውስጥ ድምፅ ከሚለው ነገር ጋር የተያያዘ ነገር አለው፡፡ እንዲያውም p45 እና D በተባለው የጽሁፍ አይነት ላይም እነደማይገኝ ይናገራሉ፡፡ አንዱ ችግር በሐዋርያት ስራ 10፡20 ላይ ተገልፆ ነበር፡፡ ከዚህ ምዕራፍ ጋር ፈፅሞ ተነፃፃሪ የሆነ ነው፡፡ ፀሐፍትም በተነፃፃሪነት እንዲሆን አድርገውታል፡፡ በአዲስ ኪዳን ውስጥ እንደገባው በምንም ሁኔታ ትርጉሙን አያፋልስም፡፡

11፡14 **“የምትድኑበትን”** ቆርቆሌዎስ ቅንነቱ እና ለጋስ መሆኑ ድነትን ሊሰጠው አልቻለም፡፡

11፡15 የባለ ሃምሳ ዕለት በስነ መለኮት ትምህርት ትኩረት የሚሰጠው ርዕሰ ጉዳይ መሆኑን የምናውቅ በተደጋጋሚ በመፃፍ ነው፡፡ እግዚአብሔር ይህንን በማድረግ ሁሉን እንደተቀበለ የገለፀበት ታሪካዊ ክስተት ነው፡፡ (ቁ.17) በመሆኑም ልምምዱ አህዛብ ለሆነው ለቆርቆሌዎስ ቤተሰብ ብቻ ሳይሆን፡ (1) ለጴጥሮስ (2) ለአይሁድ አማኞች (3) በኢየሩሳሌም ላሉት ቤተክርስቲያን ነበር፡፡

11፡16 **“የጌታ ቃል ትዝ አለኝ”** የቀደሙ አባቶች ስብከታቸውን የሚያቀርቡበት የተለመደ መንገድ ነው፡፡ ኢየሱስን እንደ ምሳሌ በመጥቀስ፣ የኢየሱስን ምሳሌዎች በመጠቀም እና የብሉይ ኪዳን መፅሐፍ በመጥቀስ ስብከታቸውን ያከናወኑ ነበር፡፡ (ማቴ 3፡11፣ሐዋ 1፡5)

11፡17 **“እንግዲህ”** ፀሐፊውን የራሱን ሃሳቡ የጨመረው ይህንን ቃል ተጠቅሞ ነው፡፡

▣ **“ያው ስጦታ ለእነርሱ ተሰጠ”** (ሐዋ 11፡15) የሚያመለክተው (ሐዋ 2) ነው፡፡ ደህንነት እንደ መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ነው፡፡ ሮሜ 3፡24፣ 5፡15-17፣6፡23፣ ኤፌ 2፡8

▣ **“በጌታ በኢየሱስ ስም ላመኑ”** ደህንነት ከእግዚአብሔር የሚቀበሉት ነው፡፡ (ሐዋ 11፡1፣ ዮሐ 1፡12 ኤፌ 2፡8-9) በአዲስ ኪዳን ወደ ክርስቶስ ኢየሱስ መተው ላመኑ ሰዎች የተሰጡ ምላሾችን እንመልከት፡፡

1. *epi* = እዚህ
2. *eis* = ወደ
3. *en* = ውስጥ
4. *hoti* = ስለ ኢየሱስ መናገር
5. ቦታን ሳይቀይሩ የመለወጥ ቀጠሮ መያዝ

ይህ ልዩነት ማመን በሚለው ቃል ላይ ምንም ዓይነት የሰዋሰው ግንኙነት እንደሌለ ነው፡፡ በተለይም ትኩረት የተደረገበት ዋና ግላዊ በሆነ ነገር ላይ ነው፡፡ መቀበል የሚገባን ኢየሱስ ክርስቶስን ነው በ2:40 እና 3:16 ላይ የተዘረዘሩትን የልዩ ርዕስ ሰንጠረዥ ተመልከት፡፡

11:18 "ዝም አሉና እግዚአብሔርን አከበሩ" የሐዋርያው ጴጥሮስ ምስክርነት ዝም ማሰኘት ብቻ ሳይሆን ለእግዚአብሔር ክብርን አምጥቷል፡፡ በዚህ ምንባብ የሚነኙት አድማጮች የአይሁድ መምህራ በመሆናቸው ስነ መለኮታቸውን አሻሽለዋል፡፡

▣ "እግዚአብሔር ለአህዛብ ደግሞ ለህይወት የሚሆን ንስሃን ሰጣቸው" የአዲስ ኪይን መፅሐፍቶች ሁሉ እግዚአብሔር የንስሃንና የፀጋ አምላክ መሆኑን ያረጋግጣሉ፡፡ (ሐዋ 5:31፣ 8:21፣ 2ጢሞ 2:25)፡፡

በዚህ በተለምዶ የሚነሳው የስነ መለኮት ጥያቄ ደህንነትን የሚሰጠው እግዚአብሔር እንዴት የሰዎችን ምላሽ ይጠብቃል የሚል ነው፡፡ እምነት እና ንስሃ የሰው ምላሽ ወይስ የእግዚአብሔር ስጦታ (ማርቆ 1:15) ሐዋ 3:16 19፣ 20:21) የሚከተሉት ጥቅሶች የሚያመለክቱት እምነት እና ንስሃ ከእግዚአብሔር እንደሚሰጡ ነው፡፡ (ሐዋ 5:31፣ 11:18 ሬሜ 2:4 እና 2ጢሞ 2:25) በመሆኑም ሁሉንም ጥቅሶች በመመልከት እውነተኛው ሃሳብ ማግኘት ይቻላል እንጂ ቃሉ እርስ በእርሱ የሚጣረዝ አይደለም፡፡ ነገር ግን ሁሉን የሚችል አምላክ የሁሉ ተቆጣጣሪ እንደሆነ እናውቃለን፡፡ እግዚአብሔር ለደህንነት የመጀመሪያውን ቅድሚ ያወስዳል ነገር ግን የሰዎች ምላሽም ከግዴታ ነፃ መሆኑን ያሳያል፡፡ ቃል ኪዳን (2:46) ንስሃ (2:38) ለተጨማሪ ግንዛቤ ያንብቡ፡፡

11:19-30 ይህ ሐረግ የቀደመውን ታሪክ የሚያስታውስና የስነ መለኮት የመደምደሚ ሃተታ የተሰጠበት ነው፡፡

> ሐዋ 11:19-26
>
> **በእስቲፋኖስ ላይ በተደረገው መከራ የተበተኑት እስከ ልንቄ እስከ ቆጵሮስም እስከ አንፃኪያም ድረስ ዞሩ ቃሉንም ለአይሁድ ብቻ እንጁ ለአንድ ስንኳ አይናገሯም ነበር፡፡ ከእነርሱ ግን የቆጵሮስና የቀሬና ሰዎች የነበሩት አንዳንዶቹ ወደ አንፃኪያ መጥተው የጌታን የኢየሱስን ወንጌል እየሰበኩ ለግሪክ ሰዎች ተናገሩ፡፡ የጌታም እጅ ከእነርሱ ጋር ነበረ ቁጥራቸውም እጅግ የሚሆን ሰዎች አምነው ወደ ጌታ ዘወር አሉ፡፡ ወሬውም በኢየሩሳሌም ባለችው ቤተክርስቲያን ስለ እነርሱ ተሰማ በርናባስንም ወደ አንፃኪያ ላኩት እርሱም መጥቶ የእግዚአብሔርን ፀጋ ባየ ጊዜ ደስ አለው ሁሉንም በልባቸው ፈቃድ በጌታ ፀንተው ይኖሩ ዘንድ መከራቸው ደግ ሰውና መንፈስ ቅዱስ እምነትዎ የሞላበት ነበረና፡፡ በርናባስም ሳውልን ሊፈልግ ወደ ጠርሴስ ወጣ ባገኘውም ጊዜ ወደ አንፃኪያ አመጣው፡፡ በቤተክርስቲያንም አንድ ዓመት ሙሉ ተሰበሰቡ ብዙ ህዝብንም አስተማሩ ደቀ መዛሙርትም መጀመሪያ በአንፃኪያ ክርስቲያን ተባሉ፡፡**

11:19 "በመከራ የተበተኑት" በሐዋርያት ስራ መፅሐፍ መከራ የተለመዶ የህይወት ዘይቤ ነው፡፡ (ሐዋ 5:17፣ 6:8-15፣ 8:1-3፣ 9:1-2) የእስጢፋኖስ የስብከት ቃል ብዙ አክራሪ አይሁዶችን እምነታቸውን እንደገና እንዲፈትኑት አድርጎቸዋል፡፡

▣ "አንፃኪያ" የአንፃኪያ ከተማ ከሮም እና ከኤክሳንደሪያ በመቀጠል የምትገኝ ትልቋ ከተማ ነች፤ የሦርያ ዋና ከተማ በመሆን አይሁዳውያን የዝሙት ስራ የሚሰሩባት ከተማ በመሆን ትታወቃለች በተጨማሪም በሰረገላ ውድድር በአለም አቀፍ ደረጃ ትታወቃለች፣ የክርስትናም ደሴት ነበረች፡፡

▣ "ቃሉን ለአይሁድ ብቻ እንጂ ለአንድስ እንኳን አልተናገርም ነበር" የጥንቲቲ ቤተክርስቲያን ለአህዛቦች ወንጌል መስበክ፣ ትክክለኛ ነው ብለው አይቀበሉትም ነበር፡፡ አክራሪዎቹ ኢየሱስ ዝም አስኝቷቸው ነበር፡፡ (ማርቆ 10:5) ይህ የስነ መለኮት ንትርክ እስከ አስራ አምስተኛ ምዕራፍ ደርሶ ይታያል፡፡

11:20 "እርሱ ግን የቆጵሮስና የቀሬና" በሐዋ 6-8 ያሉት ግሪክ ተናጋሪ የሆኑ አይሁዳውያንን የሚያመለክት ነው፡፡ እነዚህም በኢየሩሳሌም ወንጌልን በመስበክ ይታወቃሉ በርናባስ የዚህ አገር ተወጅ ነው፡፡

▣ "ለግሪኮች" ሄለና የሚለው ቃል የሚያመለክተው አህዛቦችን ነው (ሐዋ 14:1፣16:1:3፣ሐዋ 19:10:17፣ ሐዋ 20:21:21:28)፡፡ ነገር ግን በሐዋ 17:4 ያሉት አህዛብ ከሙኩራብ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያላቸው ናቸው፡፡

በመሆኑም ሉቃስ በዚህ የጠቀሳቸው ግሪኮች የትኞቹ ናቸው፡፡ (1) ግሪክ ቋንቀ ተናጋሪ አይሁዶችን (ሐዋ. 6:1 እና 9:29) (2) ግሪክ ቋንቋ ተናጋሪ አህዛቦችን ይህ ጥቅስ የሚያመለክተው፡ (1) ሌሎች አይሁዳውያንን (2) ከምኩራብ ጋር ህብረትን የሚያደርጉ አህዛቦች (ሄለን) (3) አህዛቦች ከዚህ ዓረፍተ ነገር በግርድፍ የምንረዳው እነዚህ የተበተኑት ግሪክ ተናጋሪ አይሁድ እና ሌሎች አህዛቦችን ያመለክታል፡፡

▣ "የኢየሱስን ወንጌል እየሰበኩ" የእንግሊዘኛው በአሁን ጊዜ ዓረፍተ ነገር በማስቀመጥ "የወንጌል ስርጭት" የሚል ትርጉም ሰቶታል፡፡

11:21 "የጌም እጅ ከእነርሱ ጋር ነበረች ቁጥራቸውም እጅግ የሚሆን ሰዎች አምነው ወደ ጌታ ዘወር አሉ" በወንጌል አገልግሎት የተደረገውን የሚያወሳ ዝርዝር የማጠቃለያ ሐሳብ ነው፡፡ በሐዋ 1:8 ላይ የተፃፈው መፈፀሙን መገንዘብ እንችላለን፡፡

ጌታ ወይም (ኪውርዮስ) የሚለው ቃል በዚህ ቁጥር ላይ ያሕዌን ተክቶ መመልከት ይቻላል፡፡ (ዘፀ 3፡14፣ 2ሳሙ 3፡12 ፡ኢሳ 59፡1) በቀጣዩ ይህ ስልታዊ ንግግር በአዲስ ኪዳን በተለዋዋጭነት ያገለግላል፡፡ ይህም የኢየሱስን አምላክነት ለመግለፅ ፀሐፊው ተጠቅሞበታል፡፡

በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር እጅ የሚለው ሐረግ ተምሳሌያዊ ንግግር ነው፡፡ ምክንያቱም ሰውን ለመርዳት ስዕላዊ በሆነ መግለጫ ፀሐፊዎቹ ሊፅፉ ይገደዳሉ እንጂ ሁሉን የሚችለው አምላክ እጅ እና እግር አለው ማለት አይደለም የራሳችንን ፍጥረት መረዳት አለብን እኛ ጊዜያዊ፣ በሀጢያት የወደቀን እና በምድር ዕውቀት እና ቋንቋ የምንጠቀም ስለዚህ የሰማዩን አለም ለመግለፅ ምድራዊ ቋንቋዎች፣ መግለጫዎች፣ ምሳሌዎች አስፈላጊ ናቸው፡፡ እነዚህ እውነትን በአጭር መንገድ የሚያብራሩ ናቸው፡፡ መፅሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር መሆኑን ማመን አለብን ነገር ግን እግዚአብሔር ከዚህም በላይ ታላቅ ነው፡፡ የሰው ቋንቋ ውስን እና የተብራራ መሆኑን ማወቅ ይገባናል፡፡

11፡22 **"በርናባስ"** በሐዋርያ ስራ መፅሐፍ ይህ ስም የታወቀ ስም ነው (ሐዋ 4፡36-37፣9፡27) የስሙ ትርጉም "የመፅናናት ልጅ" ነው፡፡

11፡23 በርናባስ የእግዚአብሔር ፀጋ ተገልጦ ሲመለከት በመበረታታት ሌሎችንም በእምነት እንዲፀኑ ያደረግ ነበር፡፡ ለእግዚአብሔር ህዝብ መትጋት ዋነኛ መሳሪያ ነው፡፡ አይሁድ እና በዚያ ዘመን የነበረች ቤተክርስቲያን የጦኦት አምላኪዎችን አስተምርሆት በጥንቃቄ ይመለከቱት ነበር፡፡ ምክንያቱም ነፃ ስጦታ የሆነው ደህንነት ነፃ ብቻ ሳይሆን የቅድስናና የንፅህና ኑሮ የሚጠይቅ በመሆኑ ነዉ፡፡ (ማቴ 5፡48፡ ሮሜ 8፡28-29፣ 2ቆሮ 3፡18፣ ገላ 4፡19 ኤፌ 4፡1፣ 1ተሰሎ 3፡13 4፡3 1ጴጥ 1፡15) እግዚአብሔር ባህሪውን እንድናፀባረቅ ይፈልጋል፡፡ ክርስትና መንግስተ ሰማይ መግባት ብቻ ሳይሆን በምድር ላይ ክረስቶስን መልክ መምሰልና መመስከር ነው፡፡

11፡24 **"ደግ ሰውና መንፈስ ቅዱስ እምነትም የሞላበት ሰው ነበር"** የዚህ ዓረፍተ ነገር ትንተና የግሪክ ተናጋሪ ደቀ መዛሙርት በሚናገሩት ጋር ተመሣሣይ ነው (ሐዋ 6፡3፡5)

11፡25 **"በርናባስም ሳውልን ሊፈልግ ወደ ጠርሴስ መጣ"** በግብፅ ፖሪረስ ላይ ይህ የሚለው ሳውልን ማግኘት ቀላል አለመሆኑን ነው፡፡ የግሪኩ ፅሑፍ ላይ አልተፃፈም በአዲስ ኪዳን ሉቃስ የዚህ ቃል ብቸኛ ተጠቃሚ ነው፡፡ (ሉቃ 2፡44 45፣ ሐዋ 11፡25) የዝምታ ጊዜ የሚባለው ተመልክቱ (ገላ 1፡21) እነዚህ አመታት አስር እንደሆኑ ይገመታል፡፡

11፡26 **"ወደ አንፃኪያም አመጣው. . .መጀመሪያ በአንንኪያ ክርስቲያን ተባሉ"** ክርስቲያን የሚለው ስያሜ እምነት የለሽ በሆኑ ሰዎች ትርጉም አልባ ነበር፡፡ ክርስቲያን የሚለው ስያሜ ለሄሮድስ ደጋፊዎች ሄሮድያን ከሚለው የሄሮድስ ስም ጋር የመጨረሻውን የፊደላት ድምፀት የሁለቱም "ያን" በሚለውን ያመሳስሉ ነበር፡፡ 1ማርቆ 3፡6፣ 12፡13 ማቴ 22፡16) ነገር ግን የመሲሁ (የክርስቶስ) አማኞች ስያሜአቸው በእርሱ በማድረግ የኢየሱስ ተከታዮች ለመሆን በቅተዋል፡፡

በሄለናይዜሽን ስልጣኔ የሮማ መንግስት በአይሁድና በክርስቲያኖች መሐከል ለመለየት የራሳቸውን ስያሜ ይሰጡአቸው ነበር፡፡

**ሐዋ 11፡ 27-30**

**በዚያም ወራት ነቢያት ከኢየሩሳሌም ወደ አንፃኪያ ወረዱ ከእነርሱም አጋበስ የሚሉት አነድ ሰው ተነስቶ በዓለም ሁሉ ታላቅ ራብ ሊሆን እንዳለው በመንፈስ አመለከተ ይህም በቀላውዴዎስ ቄሣር ዘመን ሆነ ደቀመዛሙርትም እያንዳንዳቸው እንደ ችሎታው መጠን አዋጥተው በይሁዳ ለሚኖሩት ወንድሞች እርዳታን ይልኩ ዘንድ ወሰኑ እንዲህም ደግሞ አደረጉ በበርናባስና በሳውልም እጅ ወደ ሽማግሌዎቹ ሰደዱት፡፡**

11፡27 **"ነቢያት"** በአዲስ ኪዳን ነብያት የሚለው ቃል በርካታ ቦታ ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ (ሐዋ 13፡1፣ 15፡32፣ 21፡10፣1ቆሮ 12፡28፣ 14፡1-5፣ 29-33 ኤፌ 2፡20፣ 4፡10)፡፡ ነብያቶች የሚመጣውን በግልፅ የሚናገሩ ናቸው፡፡ (1ቆሮ 14 እና ሐዋ 2፡17) (ሐዋ 13፡1፣ 15፡32፣ 21፡10፣1ቆሮ 12፡28፣ 14፡1-5፣ 29-33 ኤፌ 2፡20፣ 4፡10)፡፡

የብሉይ ኪዳን ነብያቶተ እግዚአብሔር በመወከል የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ የአዲስ ኪዳን ነብያት በእግዚአብሔር በሰዎች መሃከል የሚቆሙ አይደሉም፡፡ ይህ ትምህርት በአዲስ ኪዳን ፀሐፊዎች አልተጠቀም፡፡ ስጦታው ወሰንነት ይታይበታል፡፡ የአዲስ ኪዳን ነብያቶች እንደ ብሉይ ኪዳን ነብያቶች መፅሐፍ ቅዱስ እንዳይፃፍ ተከልክለዋል፡፡ (ይሁዳን እና 20) ለተጨማሪ ግንዛቤ ያንብቡት፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ የአዲስ ኪዳን ትንቢት**

I. የአዲስ ኪዳን ትንቢት የብሉይ ኪዳን አይነት አይደለም(ሐዋ 3፡18 2) ሮሜ 16፡26 ነብያቶች ብቻ መፅሐፍ ቅዱስን ይፅፉ ነበር፡፡
   ሀ. ሙሴ ነብይ ተብሎ ተጠርቷል (ዘዳ 18፡15-21)
   ለ. የታሪክ መፅሐፍት (ከኢያሱ-ነገስት (ከሩት በስተቀር) ነብያቶች ተብላዠው ተጠርተዋል (ሐዋ 3፡24)
   ሐ. ነብያት የሊቀ ካህናቱን ቦታ በመተካት መልእክትን ከእግዚብሔር ለሰዎች ያስተልፍል (ሐዋ 3፡24)
   መ. የዕብራውያን መፅሐፍ ‹‹የነብያት መፅሐፍት›› ተብለው ተጠርተዋል፡፡ (ማቴ 5፡17፡22፤40 ሉቃ

116፡16፣16፡24፡25፡27 ሮሜ 3፡21

II. በአዲስ ኪዳን ‹‹ነቢያት›› የሚለው የተለያየ መገለጫዎች አሉት፡-

ሀ. በብሉይ ኪዳን ነብያቶች መፅሐፉ ላይ የተመሠረተ መልእክተ የአዲስ ኪዳን ነብያቶች ይናገራሉ። (ማቴ 2፣23 5፡12፣11፡13፣ሮሜ 1፡2)

ለ. የብሉይ ኪዳን ነብያቶች ለእስራኤል ሲናገር የአዲስ ኪዳን ነብያቶች ለተለያዩ ለህብረቶች (ሰዎች ይናገራሉ።

ሐ. መጥምቁ ዮሐንስና ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን መንግስት አዋጅ በመናገር ነብያቶች ሆነዋል። (ማቴ 13፡57፣21፡11፣46፣ሉቃ 4፡24፣ማቴ 11፡9፣12፡41፣ሉቃ7፡26)

መ. የአዲስ ኪዳን ሌሎች ነብያቶች፡-

1. ኢየሱስ በተወለደ ጊዜ የነበሩ ነብያቶች እንደ ሉቃስ ፅሐፍ፡-
   - ሀ. ኤልሳቤጥ (ሉቃ 1፡41-42)
   - ለ. ዘካርያስ (ሉቃ 1፡67-79)
   - ሐ. ስምኦን (ሉቃ 2፡25-35)
   - መ. ሐና (ሉቃ 2፡30)
2. ትንቢታዊ (ዮሐ 11፡51)

ሠ. ወንጌልን የሚያውጭ ነብይ የሚል መጠሪያ ተሰቶታል (1ቆሮ 12፡28-29፣ ኤፌ 4፡11)

ረ. ለቤተክርስቲያን የሚሰጥ ስጦታ ነው (ማቴ 23፡24 ሐዋ 13፡1፣ 15፡32፣ ሮሜ 12፡6፣ 1ቆሮ 12፡10፣28-29፣13፡2፣ ኤፌ 4፡11 አንዳንድ ጊዜ የሴቶችንም አገልግሎት ያመለክታል (ሉቃ 2፡30፣ ሐዋ 2፡17፣ 21፡9 1ቆሮ 11፡4-5)

ሸ. የራዕይ መፅሐፍ የነብያት መፃፉ የሚል ስያሜም ተሰቶታል (ራዕ 1፡3፣ 22፡7፣ 10፣ 18፣ 19)

III. የአዲስ ኪዳን ነብያቶች

ሀ. የአዲስ ኪዳን ነብያቶች እንደ ብሉይ ኪዳን ነብያቶች መፅሐፍ ቅዱስን አይፅፉም (ሐዋ 6፡7፡13፡8፡14፡22 ገላ 1፡23፡2፡23፣6፡10 ፊሊ 1፡27 ይሁዳ 3፡20)

በይሁዳ ምዕራፍ ሦስት ያለው ንባብ ግልፅ ያደርገዋል ‹‹ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ስለተሰጠው እምነት›› የሚለው እምነት የሚያመላክተው እውነትን፣ አስተምህሮችን፣ ሃሳብን፣ የክርስትና ትምህርት መላምቶችን ያጠቃልላል። በመሆኑም መፅሐፍ ቅዱሳዊ ገደብ ያላቸውን ትምህርቶች በራሳችን ጊዜ በመጨመር በማስፋፋት እና መለወጥ አንችልም በአዲስ ኪዳን በርካታ ግልፅ ያልሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች መኖራቸው ግልፅ ነው። አማኞች መርዳት ያለባቸው ከበቂ በላየ ለእምነታችን መሠረታዊ የሆኑ ነገሮችን በመፅሐፍ ቅዱስ ግልፅ ሆነው መቀመጣቸውን መገንዘብ አለብን።

1. እግዚአብሔር በዘመናት ሁሉ ራሱን ይገልጣል።
2. እግዚአብሔር ፀሐፊዎችን በመምረጥ ስራውን ለትውልድ እንዲገልጡ ያደርጋቸዋል።
3. እግዚአብሔር የተፃፈውን ሰዎች መረዳት እንዲችሉ አእምሮን በመክፈት ስለድነት እና ስለ ክርስትና ህይወት አጠቃላይ ዕውቀት እንዲኖራቸው ያደርጋል።

በመሆኑም ከእንግዲህ ወዲህ በተፃፈው ላይ ለመጨመር ለመቀነስም ሌላም ለመፃፍ ስልጣን የለው ሰው የለም። መፅሐፍ ቅዱስ ተፃፎ ተዘግተል። የሚያስፈልገን እውነት ሁሉ ተፅፏል፡ ስለሆነም ይህንን እውነት መተግበር በቂ ነው።

ለ. የአዲስ ኪዳን ነብያቶች ከብሉይ ኪዳን ነብያቶች ጋር የሚያመሳስላቸው ነጥቦች እንመልከት።

1. ሁለቱም የወደፊቱን ይተነብያሉ (ጳውሎስ ሐዋ 27፡22 አጋቦስ ሐዋ 11፡27-28፣ሌሎችም ስማቸው ያልተጠቀሱ ነብያት አሉ ሐዋ 20፡23)
2. ሁለቱም ፍርድን ይናገራሉ። (ሐዋ 13፡11፣28፡25-28)
3. ሁለቱም በምሳሌ ይናገራሉ። (አጋበስ ሐዋ 21፡11)

ሐ. የአዲስ ኪዳን ነብያቶች ወንጌልን በትንቢት መልክ ያውጁታል። (ሐዋ 11፡27-28፣20፡23፣21፡10-11) ነገር ግን ቅድሚየ የሚሰጠው አይደለም። ትንቢትን ለመናገሪ ወንጌልን ለማሰራጨተ የራሱ የሆነ ድርሻ ይኖረዋል። (1ቆሮንቶስን ያንብቡ) (ሐዋ 14፡24፣39)

መ. ፀጋ ስጦታዎች የእግዚብሔርን የአሁን ጊዜ አሰራሩን የምናይበት ነው። (1ቆሮ 14፡3) የእግዚአብሔርን የተገለጠ እውነት እና እውቀት የምናደንቅበት ነው።

ሠ. በጳውሎስ ዘመን የፀጋ ስጦታዎች በስፋት ይገለጡ ነበር። (1ቆሮ 11፡4-5 1ቆሮ 12፡28፣29 13፡29፡14 ፡1፡3፡4፡5፡6፡22፡24፡29፡31፡32፡37፡39 ኤፌ2፡20 3፡5፡4፡11፣ ተሰሎ5፡20) ይህም በ‹‹ዲዳች›› ተፅፎ ይገኛል።

IV. በአዲስ ኪዳን የነብያት አገልግሎት አቁሞአልን

ሀ. ይህንን ጥያቄ መመለስ ቀላል አይሆንም ነገር ግን የስጦታዎችን አላማ በማጤን ግልፅ ማድረግ ይቻላል። ወንጌል እውነተኛ መሆኑን የሚያረጋግጡል ናቸው ወይም ቤተክርስቲያን በአገልግሎቷ እግረ መንገዷን የጠፉትን ለማዳን የምታደርገው ነው?

ለ. አንድ ሰው ጥያቄውን ለመመለስ የቤተክርስቲያን ታሪክ ወይስ አዲስ ኪዳን ማንበብ ይኖርበታል? በአዲስ ኪዳን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ጊዜያዊ ናቸው የሚል ማስረጃ አናገኝም። (1ቆሮ 13፡8-13) ነገር ግን ስጦታዎች ሁሉ ሲያልፉ ፍቅር ግን ለዘላለም ይኖራል።

ሐ. የአዲስ ኪዳን መፃህፍት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች እንደሚሰሩ ካረጋገጠ አማኞች ይህንን ቃል

መቀበል ይኖርብናል። በመሆኑም አማኞች በማህበረሰቡ ወይም በቤተክርስቲያናቸው አስተምህሮትና ባህል መያዝ የለባቸውም። በመፅሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ በርካታ በእኛ ዘመን ልንተገብራቸው ርዕሰ ጉዳዮች አሉ ምሳሌ:- የሴቶች መሸፋፈን፣ የተቀደሰ አሳሳም፣ የቤተክርስቲያን በግለሰብ ቤት መሆን እና ወዘተ....

መ. በመንፈስ ቅዱስ የፀጋ ስጦታዎች ላይ በሁለት በኩል ጐራ ለይተው ይከራከራሉ። በመሆኑም መልሱ ይሄ ነው ለማለት አስቸጋሪ ሆኖአል በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የአማኞች ልብ ቁልፉ ቦታ ነው። በዚህ ርዕስ ላይ አዲስ ኪዳን ግልፅ አይደለም በተጨማሪም የባህል ተፅእኖ ይታይበታል። (Fee and Stuart's How to read the Bible for all its worth, pp. 14-19 and 69-77) እንግዲህ በርዕሰ ጉዳዩ ለማውራትም ነፃነት እና ሃላፊነት በመውሰድ መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው። (ሮሜ 14:1-15:13 እና 1ቆሮ 8-10)

ይህንን ርዕሰ ጉዳይ በሁለት መንገዶች መመለስ እንችላለን።

1. እያንዳንዱ አማኝ በእምነት እና በተሰጠው ብርሃን መሃድ አለበት። ምክንያቱም እግዚአብሔር ልባችንን እና የመነሻ ሀሳባችንን ይመለከታል።
2. እያንዳንዱ ክርስቲያን ሌላኛውን አማኝ በራሱ መረዳት እንዲሄድ መፍቀድ አለበት።

ሠ. በማጠቃለያም የክርስትና ህይወት በእምነት እና በፍቅር እንጂ ስህተት በሌላው ስነመለኮት ሙሉ ነው ማለት አይደለም። ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ከየትኛውም ከምናወጣቸው ዶክትሪኖች የበለጠ ማወቅ አለብን።

1:28 **"በዓለም ሁሉ ታላቅ ረሃብ.... በቀላውዴዎስ"** የሮምን ግዛት የሚያመላክት ነው። (ሐዋ 17:6:31፣ 19:27፣ 24:5) **<u>ከዜሮ</u>** ቀጥሎ ቀላውዴዎስ ከ41-54 AD የነገሰ ንጉስ ነው። በዚህ ሰው ዘመነ መንግስት ታላላቅ ረሃቦች ተከስተዋል (Suetonius, Life of caludius 18:2) በማንበብ ተጨማሪ ግንዛቤ ይገኛል። ከ44-48 ዓ.ዓለም የተከሰተው ረሃብ በታሪክ ትልቁ ረሃብ እንደነበረ ታሪክ ዘግቦታል።

11:29 **"ደቀመዛሙርትም እንደ ችሎታቸው መጠን አዋተው"** ይህ የገንዘብ መዋጮ የአህዛብ አብያተ ክርስቲያናት ከኢየሩሳሌም ካለችው እህት ቤተክርስቲናትን ሲያደረጅ ይህንን ታሳቢ በማድረግ ነበር። (ሐዋ 24:17፣ሮሜ 15:2 1ቆሮ 16:1-4፣2ቆሮ 8-9 ገላ 2:10)

11:30 **"ወደ ሽማግሌዎች ሰደዱ"** በዚህ ቦታ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች የሚል ተጠቅሶ፣ (ሐዋ 14:23፣ 15:2፣2:4:6:22:23:16:4፣20:17:21:18) "ሽማግሌዎች" የሚለው ስያሜ አቻ ቃሉ

▣ **"የበላይ ተቆጣጣሪ" ወይም "የበላይ ተመልካች"** ወይም "መጋቢ" ወይም "ቄሶች" ማለት ነው። (ሐዋ 20:17:28 እና ቲቶ 1:5:7) "ሽማግሌ" የሚለው ደግሞ የግሪኮች ባህል ይዘት አለው። ነገር ግን በግልፅ አንደተቀመጠው እነዚህ ሽማግሌዋች በኢየሩሳሌም ክርስቲያንን እየመሩ የነበሩ መሆናቸው በግልፃ ተቀምጧል።

▣ **"በርናባስና በሳኦል"** የኢየሩሳለምን ጉብኝ የሚያመላክት ሐረግ፤ (ሐዋ 15) የጳውሎስ የቀደመ ሕይወትና አገልግሎት ለብዙዎች ጥያቄ የሚፈጥ ነው በመሆኑም በኢየሩሳሌም ለሚደረገው ጉብኝት ብዙ ውይይት ተደርጐበታል። (ገላ 2:2:10)

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት <u>*መመሪያ*</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ለመርዳት ነው የተሰናዱት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋነኞቹን ጉዳዮች ለማጤን እንዲረዳ ነው። ሐሳብ ለማጫር እንጂ መደምደሚያ አይደሉም።

1. አህዛቦች ኢየሱስ ክርስቶስን መቀበላቸው እንደችግር ለምን ሆነ
2. ንስሃ የእግዚብሔር ስጦታ ነውን? (ቁ: 18) ወይስ ቃል ኪዳኑ የሚጠይቀው ግዴታ ነው? (ማርቆ 1:15 ሐዋ 3:16:19:20:21)
3. በርናባስ ጳውሎስን መፈለግ ለምን አስፈለገው?

# የሐዋርያት ስራ 12

## የምንባቡ ክፍፍል በአዳዲሶቹ

| የተየመቅሰ[4] | አኪጀት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ያዕቆብ ተገደለ ጴጥሮስ ታሰረ | የሄሮድስ ቁጣ በቤተክርስቲያን ላይ | የሄሮድስ አግሪጳ ስደት | የበለጠ ስደት | የጴጥሮስ ተአምራዊ መዳን |
| 12፡1-5 | 12፡1-5 | 12፡1-5 | 12፡1-5 | 12፡1-5 |
| የጴጥሮስ ከእስር ተፈታ | ጴጥሮስ ከእስር ነፃ ሆነ | | ጴጥሮስ ከእስር ነፃ ሆነ | |
| 12፡6-17 | 12፡6-19 | 12፡6-11 | 12፡6-10 | |
| | | 12፡12-17 | 12፡11 | |
| | | 12፡18-19 | 12፡12-15 | |
| | | | 12፡16-17 | |
| 12፡18-19 | | | 12፡18-19a | 12፡18-19 |
| | | | 12፡19b | |
| የሄሮድስ መሞት | የሄሮድስ አደገኛ አሟሟት | የሄሮድስ አግሪጳ ሞት | የሄሮድስ ሞት | |
| | | | 12፡20 | 12፡20-23 |
| 12፡20-23 | 12፡20-24 | 12፡20-23 | 12፡21-23 | |
| | | በርናባስና ሳኦል ቆጵሮስ (12፡24-13፡12) | | የባርናባስ የሳኦል ወደ አንፃኪያ መመለስ |
| 12፡24-45 | | 12፡24-25 | 12፡24 | 12፡24 |
| | በርናባስ እና ጳውሎስ ተሾሙ | | | |
| | 12፡25-13፡3 | | 12፡25 | 12፡25 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (ከ "**መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ**" **ገጽ** vii)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. ምንባብ አንድ

2. ምንባብ ሁለት

3. ምንባብ ሦስት

4. ወዘተርፈ

**የአውዱ እይታ**

የሄሮድስት የዘር ግንድ (Index of Flavius Josephus in Antiquities of the Jews)
I. ንጉስ ሄሮድስ
 ሀ. የይሁዳ ንጉስ ነበር። (37-4 ከክርስቶስ ልደት በፊት)
 ለ. ማቴ 2፡1-19፣ ሉቃ 1፡5
II. የሄሮድስ ወንድ ልጆቹ፡-
 ሀ. ሄሮድስ ፊሊጶስ (ከስምኦን ልጅ ከማሪና የሚወለድ)
  1. የሄሮዲያ ባለቤት
  2. የገዛበት ዘመን (ከ4 ክ)ል)በፊት - 34 ዓ.ዓ)
  3. ሜቴ 14፡3፣ ማርቆ 6፡17
 ለ. ሄሮድስ ፊሊጶስ (ከኪሊዮፖትራ የሚወለድ)
  1. በሰሜን እና በምሥራቅ የገሊላ ባህር ግዛቱ ነበር (4ከ.ክ.ል.በፊት 34 ዓ.ዓ)
  2. ሉቃ 3፡1
 ሐ. ሄሮድስ አንቲጳስ
  1. የገሊላ ገዥ (4ከ.ክ.ል በፊት 39 ዓ.ዓ)
  2. የመጥምቁ ዮሐንስን አንገት አስቆርጦታል
  3. ማቴ 14፡1-12፣ማርቆ 6፡14 ሉቃ3፡19፣9፡7-9፣ 13፡31፣ 23፡6-12፡15፣ ሐዋ 4፡27፡13)
 መ. ሄሮድስ አርኬላዎስ
  1. የይሁዳ የሰማርያ እና የኤዶምያስ ገዥ ነበር (4 ከክ.ልበፊት 7-6 ዓ.ዓ)
  2. ማሜ 2፡22
 ሠ. ሄሮድስ አርስተቡላስ
  1. አንድ ልጅ ሄሮድስ አግራጳ
  2. የፋልስጥኤምን ምድር ይገዛ ነበር። (41-44 ዓ.ዓ)
  3. ያዕቆብን ገድሉታል፣ ጴጥሮስን አሳስሮታል
  4. ሐዋ 12፡1-24፣ 23፡35
   ሀ. ልጁ ሄሮድስ አግሪጳ (50-70 ዓ.ዓ)
   ለ. ሴት ልጁ ቤርናይስ ትባላለች
    (1) ወንድሟን አግብታለች
    (2) ሐዋ 25፡13-26-32
   ሐ. ሴት ልጁ ድሩሲላ ትባላለች
    (1) የፊሊክስ ባለቤት ነች
    (2) ሐዋ 24፡24

**የቃል እና የጥምር ቃል ጥናት**

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 12፡ 1-5**
**በዚያም ዘመን ንጉሡ ሄሮድስ መከራ ያፀናባቸው ዘንድ ከቤተክርስቲያኒ በአንዳንዶች ላይ እጁን ጫነባቸው። የዮሐንስም ወንድም ያዕቆብን በሰይፉ ገደለው አይሁድንም ደስ እንዳሰኛቸው አይቶ ጨምሮ ጴጥሮስን ደግሞ ያዘው። የቂጣ በዓልም ወራት ነበረ በያዘውም ጊዜ ወደ ወህኒ አገባው ከፋሲካም በኃላ ወደ ህዝብ ያመጣው ዘንድ አሰበ እያንዳንዱ አራት ወታደሮች ሆነው እንዲጠብቁት ለአራት ጭፍራ ክፍል አሳልፎ ሰጠው።**
**ጴጥሮስም በወህኒ ይጠበቅ ነበር። ነገር ግን በቤተክርስቲያን ስለ እርሱ ወደ እግዚአብሔር ፀሎት አጥብቆ ይደረግ ነበር።**

12፡1 "ሄሮድስ" ይህ ስያሜ የሄሮድስ አግሪጳ የሚያመላክት ነው። ከ37-44 ዓ.ዓ በፍልስጥኤም ግዛት ውስጥ የተለያዩ ቦታዎችን ያስተዳድር ነበር። ይህ ሰው በሮም ከተማ ያደገና የንጉስ ጢባሪዮስ ተከታ ከሆነው ከጋዮስ ጋር ባልንጀራ ነበረ። ይህን ሄሮድስ አይሁድ ይቀበሉት ነበር። ምክንያቱም አያቱ መሪማ ከመቃባውያን ወገን ነበረች። (ለአይሁድ ተከራካሪ ሴት ነበረች) በመሆኑም ይህ ሰው የአይሁድ ሀይማኖት ተከታይ ሆኖ ነበር ለፖለቲካው ከለላ በማሰብ። (Josephs Antiq 19.7.3፣ 19.8.2) ይመልከቱ።

▣ **"በቤተክርስቲያን"** ሐዋ 5፡11 ለተጨማሪ ግንዛቤ ያንብቡ።

▣ **"መከራ ያፀናባቸው ዘንድ"** ሄሮድስ ከአይሁዳውያን መሪዎች መወደድን ለማግኘት ቤተክርስቲያንን ያሳድድ ነበር። (ቁ.3፡11) እንዲሁም ሌሎቹ የሮማውያን ባለስልጣናት ተመሳሳይ ነገር ይፈፅሙ ነበር። (ሐዋ 24፡27፡25፡9) ፀሐፊው ሉቃስ ሐረጉን ሁል ጊዜ ይጠቀምበታል (ሐዋ 7፡6፣19፡1፣14፡2፣18፡10) ይህ የግሪክ ቃል ሆኖ ለታማሚ የሚሰጥ ህክምና የሚያንፀባርቅ አንድምታ አለው።

12፡2 **"የዮሐንስንም ወንድም ያዕቆብን በሰይፉ ገደለው"** ይህ ያዕቆብ ደቀ መዝሙሩን ማለቱ ነው። እርሱም የዮሐንስ ወንድ ነው (ማቴ 17፡1፣26፡37 ማርቆ 5፡37፣9፡2 14፡33 ሉቃ 9፡28) በሮማውያን ሰው የሞት ፍርድ ሲወሰንበት በሰይፍ ስለት አንገቱ ይቆረጥ ነበር።
የጥንቱቱ ቤተክርስቲያን ይሁዳን በሌላ እንድተካቸው ያዕቆብን ግን በሌላ ለመተካት እንዳልፈለገች እንገነዘባለን (ሐዋ 1፡15-26)

12፡3 **"ጴጥሮስን ደግሞ ያዘው"** ጴጥሮስ ለሦስተኛ ጊዜ ሲታሰር ነው። (ሐዋ 4፡3፣5፡18)

▣ **"የቂጣ በዓልም ወራት ነበረ"** የፋሲካ በዓልን ያመለክታል (ቁ.4 ይህም) ከቂጣ በዓል ጋር በጋራ የሚከበር ነው። (ዘፀ 12፡18፣23፡15፣ሉቃ 22፡1) በዓሉ የሚያስታውሰው የእስራኤልን ከግብፅ ባርነት ነፃ መውጣት ነው። በተለምዶ ኒሲያ በሚባል ወር ከ14-21 ይቆያል ይህ ወር ለእኛ መጋቢት ወይም ሚያዚያ ነው።

12፡4 **"እያንዳንዱም አራት ወታደሮች ሆነው"** ይህ ማለት አራት ጭፍራ ሆኖ በቀን አራት ጊዜ እየተፈራረቁ የሚጠብቁ በቁጥር ስድስት ወታደሮች ይሆናሉ። የሄሮድስ ትዕዛዝ በጴጥሮስ ላይ ጥብቅ እንደነበር ያሳያል።

12፡5 **"በቤተክርስቲያን ስለ እርሱ አጥብቆ ይፀለይ ነበር"** ቤተክርስቲያን እየፀለየት ቢሆንም ነገር ግን ጴጥሮስ ተፈትቶ ሲመጣ አስደንግጧቸዋል። አጥብቆ የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ሦስት ጊዜ ብቻ የተፃፈ ቃል ነው። (1ጴጥ 1፡22)

**ልዩ ርዕስ፡ የምልጃ ፀሎት**

I. መግቢያ
   ሀ. ኢየሱስ በፀሎት ምሳሌአችን ነው።
      1. የግል ፀሎት ማርቆ 1፡35፣ሉቃ 3፡21፣6፡12፣ 9፡29፣22፡29-46
      2. መቅደስ የመንፃት ፀሎት ማቴ 21፡13፣ ማርቆ 11፡17 ሉቃ 19፡46
      3. ምሳሌያዊ ፀሎት ማቴ 6፡5-13 ሉቃ 11፡2-4
   ለ. ፀሎት ተጨባጭ ድርጊቶችን በእግዚብሔር ፈቃድ ስለራስ እና ስለ ሌሎች እንዲደረግ ልመና ማቅረብ ነው።
   ሐ. እግዚአብሔር የልጆቹን ፀሎት ሰምቶ እንዳይመልስ የሚያደርጉት ዝርዝር ጉዳዮች አሉ። (ያዕቆ 4፡2)
   መ. የፀሎት ዋናው ዓላማ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ማድረግ ነው።
   ሠ. የፀሎታችን ስፋት እና ጥልቀት ሳይሆን የሚወስነው በማመን በተደጋጋሚ ሲሆን ይችላል። አጥብቀን የምንፀልየው ፀሎት ተሰሚነት ይኖረዋል።
   ረ. ፀሎት የሚያጠቃልላቸው፡-
      1. እግዚአብሔር ማመስገን
      2. ውዳሴ
      3. ንስሃ
      4. ልመና ማቅረብ
      5. ስለሌሎች መማለድን ያጠቃልላል።
   ሸ. የምልጃ ፀሎት ምስጢር ነው። እግዚአብሔር እኛ ልንፀልይላቸው ለሚገና ሰዎችም ትልቅ ፍቅር አለው። ፀሎት የእኛን ሕይወና ነገር ብቻ አይደለም የሚለውጠው በምንፀልይላቸው ሰዎች ህይወትም ውስጥ ለውጥን ያመጣል።

II. መፅሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ፡-
   1. የምልጃ ፀሎት ምሳሌዎች፡-
      ሀ. አብርሃም ስለ ሶዶም ማለደ (ዘፍ 18፡22)
      ለ. ሙሴ ስለ እስራኤል ማለደ
         1. ዘፀ 5፡22-23
         2. ዘፀ 32፡31
         3. ዘዳ 5፡5
         4. ዘዳ 9፡18,25
      ሐ. ሳሙኤል ለእስራኤል ፀለየ

(1) 1ሳሙ 7፡5-6; 8-9
(2) 1ሳሙ 12፡16-23
(3) 1ሳሙ 15፡11
መ. ዳዊት ለልጁ ፀለየ 2ሳሙ 12፡16-18
2. እግዚአብሔር በምልጃ የሚቃትቱትን ያያል ኢሳ 59፡16።
3. የታወቀ፣ ንሰሐ ያልገባንበት ሃጠአት ወይም ሃሳብ በፀሎታችን ላየ ተፅዕኖ ይፈጠራል።
ሀ. መዝ 66፡1
ለ. ምሳ 28፡9
ሐ. ኢሳ 59፡1-2፣ 64፡7

2. አዲስ ኪዳን
1. ወልድና መንፈስ በምልጃ አገልግሎት
ሀ. ኢየሱስ
1. ሮም 8፡34
2. ዕብ 7፡25
3. ዮሐ 2፡1
2. የጳውሎስ የምልጃ አገልግሎት
ሀ. ጳውሎስ ለአይሁድ ፀለየ
(1) ሮሜ 9፡1
(2) ሮሜ 10፡1
ለ. ለቤተክርስቲያን የተደረገ ፀሎት
(1) ሮሜ 1፡9
(2) ኤፌ 1፡16
(3) ፊሊ 1፡3-4፣9
(4) ቆላ 1፡3፡9
(5) 1ተሰሎ 1፡2-3
(6) 2ተሰሎ 1፡11
(7) 2ጢሞ 1፡11
(8) ፊሊሞ 4
ሐ. ሐዋርያው ጳውሎስ ቤተክርስቲያን እንድትፀልይላት ጠየቀ፡-
(1) ሮሜ 15፡30
(2) 2ቆሮ 1፡11
(3) አፌ 6፡9
(4) ተሰሎ 31
(5) ቆላ 4፡3
(6) 1ተሰሎ 5፡25
3. የቤተክርስቲያን የምልጃ አገልግሎት
ሀ. እርስ በእርስ የሚደረግ ፀሎት
1. ኤፌ 6፡18
2. 1ጢሞ 2፡1
3. ያዕቆ 5፡16
ለ. ፀሎት የሚደረግላቸው ሌሎች አካላት፡-
1. ለጠላቶቻችን ማቴ 5፡44
2. ለክርስቲያን ሰራተኞች ዕብ 13፡18
3. ለባለስልጣናት 1ጢሞ 2፡2
4. ለታመሙ ያዕቆ 5፡13-16
5. ከጌታ ወደኃላ ለተመለሱ 1ዮሐ 5፡16
ሐ.

III. ፀሎትን መልስ የሚያዘገዩ፡-
ሀ. ከክርስቶስ እና ከመንፈስ ቅድስ ጋር ያለን ህብረት
1. በእኛ አድሯል ዮሐ 15፡7
2. በስሙ ፀሎት ይዳረጋል ዮሐ 14፡13፣14፣15፡16 16፡23-24
3. በመንፈስ ይፀለያዪ ኤፌ 6፡18፣ይሁዳ 20
4. እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ፀሎት ይደረጋል። ማቴ 6፡10፣1ዮሐ 3፡22
ለ. የውስጣችን ፍላጐት
1. ባለማመን መፀለይ ማቴ 21፡22 ያዕቆ 1፡6-7
2. ራስን ገላቅ በማድረግና በንስሃ ሉቃ 78፡9-14
3. በተሳሳተ መንገድ መጠየቅ ያዕቆ 4፡3

4. ራስ ወዳድነት ያዕቆ 4፡2-3

ሐ. ሌሎች ዝርዝሮች፡-

1. ትዕግስት፡-
   ሀ. ሉቃ 18፡1-8
   ለ. ቆላ 4፡2
   ሐ. ያዕቆ 5፡16
2. ባለመታከት እንጠይቅ
   ሀ. ማቴ 7፡7-8
   ለ. ሉቃ 11፡5-13
   ሐ. ያዕቆ 1፡5
3. በቤታችን ያለ ያለመስማማት
1. ጴጥሮ 3፡7

4. ከሚታወቅ ሃጢያት ነፃ መሆን፡-
   ሀ. መዝ 66፡18
   ለ. ምሳ 28፡9
   ሐ. ኢሳ 59፡1-2
   መ. ኢሳ 64፡7

IV. የሥነ መለኮት መጠቃለያ
   ሀ. ፀሎት ከእግዚአብሔር የተሰጠን ትልቅ ስጦታ እና እድል ነው፡፡ ይህም ኃላፊነት ያለበትም ነው፡፡
   ለ. ኢየሱስም በመፀለይ ምሳሌ ሆኖናል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ሊመራን ተዘጋጅቷል፡፡ አብ ደግሞ የእኛን መፀለይ ይጠብቃል፡፡
   ሐ. ይህ አንተን፣ ቤተሰብህን፣ ጓደኛህን እና አለምን ሊለውጥ ይችላል፡፡

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 12፡6-17**
**ሄሮድስም ሊያወጣው ባሰበ ጊዜ በዚያች ሌሊት ጴጥሮስ በሁለት ሰንሰለት ታስሮ ከሁለት ወታደሮች መካከል ተኝቶ ነበር፡፡ ጠባቂዎችም በደጁ ፊት ሆነው ወህኒውን ይጠብቁ ነበር፡፡ እነሆም የጌታ መልአክ ቀረበ በቤትም ውስጥ ብርሃን በራ ጴጥሮስንም ጎድኑን መትቶ አነቃውና ፈጥነህ ተነሣ አለው፡፡ ሰንሰለቶቹም ከእጁ ወደቁ፡፡ መልአኩም ታጠቅና ጫማህን አግባ አለው፡፡ እንዲሁም አደረገ፡፡ ልብስህንም ልበስና ተከተለው ራዕይንም የሚያዩ ይመስለው ነበር እንጂ በመልአኩ የሚደረገው ነገር እውነት እንደሆነ አላወቀም፡፡ የመጀመሪያውንና የሁተኛውንም ዘብ አልፈው ወደ ከተማ ወደሚያወጣው ወደ ብረቱ መዝጊያ ደረሱ፡ እርሱም አውቆ ተከፈተላቸው መጥተውም አንዲት ስላች አለፉ ወዲያውም መልአኩ ከእርሱ ተለየ፡፡ ጴጥሮስም ወደ ልቡ ተመልሶ ጌታ መልአኩን ልኮ ከሄሮድስ እጅና የአይሁድ ህዝብ ይጠብቁት ከነበረው ሁሉ እንደ አዳነኝ አሁን በእውነት አወቅሁ አለ፡፡ ባስተዋለም ጊዜ እጅግ ሰዎች ተከማችተው ይፀልዩበት ወደ ነበረው ማርቆስ ወደ ተባለው ወደ ዮሐንስ እናት ወደ ማርያም ቤት መጣ፡፡ ጴጥሮስም የደጁን መዝጊያ ባንኳኳ ጊዜ ሮዴ የሚሉአት አንዲት ገረድ ትሰማ ዘንድ ቀረበች፣ የጴጥሮስ ድምፅ መሆኑንም ባወቀች ጊዜ ከደስታዋ የተነሣ ደጁን አልከፈተችም ነገር ግን ወደ ውስጥ ሮጣ ጴጥሮስ በደጁ ፊት ቆሞ እንዳለ አወራች፡፡ እነርሱም አብደሻል አሉአት፡፡ እርስዋ ግን እንዲሁ እንደሆነ ታደርግጥ ነበር፡፡ እነርሱም መልአኩ ነው አሉ፡፡ ጴጥሮስ ግን ማንኳኳቱን አዘወተረ፡፡ ከፍተውም አዩትና ተገረሙ፡፡ ግን ዝም እንዲሉ በእጁ ጠቅሶ ጌታ ከወህኒ እንዴት እንዳወጣው ተረከላቸውና ይህን ለያዕቆብና ለወንድሞች ንገሩ አላቸው፡፡ ወጥቶም ወደ ሌላ ስፍራ ሄደ፡፡**

12፡6 "በዚያች ሌሊት" ሉቃስ ጊዜ ጠቋሚ የሆኑ ቃላትን ተጠቅሟል ሐዋ 12፡3፣4፣5፣6፡7፡8፡10፡18)

▣ "ከሁለት ወታደሮች መሐከል" በእስር ቤት ያለውን የተለመደ ጥበቃ ለማስገንዘብ ነው፡፡ እስረኞች ያመልጣሉ የሚል ጥርጣሬ ስለሌለ ይህንን ለማስወገድ የተደረገ ነው (ሐዋ 5፡19)፡፡

12፡7 "የጌታ መልአክ ቀረበ በቤቱም ውስጥ ብርሃን በራ" በዚህ ዓይነት ሁኔታ የመላእክት መለኮታዊ ጣልቃ ገብነት ያልተለመደ ነው፡፡ ሐዋ 5፡19፣7፡30፣35፣38፣53፣8፡26፡10፡3፡7፡22) እና የመንፈስ ቅዱስ (ሐዋ 8፡29,39፣10፡19) እነዚህ ሁለቱ በሐዋርያት ስራ መፅሐፍ ውስጥ ስማቸውን እርስ በእርስ በመለዋወጥ እናገኛቸዋለን፡፡

▣ "ፈጥነህ ተነሣ" የትዕዛዝ ቃል ነው፡፡ መልአኩ ፈጣን ለምን ሆነ? ሁሉን ነገር ተቆጣጥሮ የለም እንዴ?

12፡8 "ጣጠቅ እና ጫማህን አግባ" የትዕዛዝ ቃሎች ናቸው፡፡

▣ **"ልብህንም ልበስና ተከተለኝ አለው"** መልአኩ ይህንን ጉዳይ ለመፈፀም የተጣደፈ ይመስላል፣ አስቸኳይ ትዕዛዝን ሲያስተላልፍ ከሐረጉ ለመረዳት ይቻላል።

12፡9 ጴጥሮስ ራዕይ፣ ህልም ወይም እውነት መሆኑን አላረጋገጠም ነበር። (ሐዋ 11-12፣10፡17፡19፡11፡5)

12፡11 **"ጌታ መልአኩን ልኮ"** ሉቃስ የጣፈውን ልጅ ለመግለፅ የተጠቀመበት ተመሳሳይ ሐረግ ነው። (ሉቃ 15፡17)

12፡12 **"የማርያም ቤት"** ማርያም የሚለው ስም በአይሁድ ማዕበረሰብ የተለመደ ስያሜ ነው። በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱትን እንመልከት፡-

1. የኢየሱስ እናት (ሉቃ 1፡27)
2. መግደላዊት ማርያም (ሉቃ 8፡2፣24፡10)
3. የያዕቆብ እና የዮሐንስ እናት (ሉቃ 24፡10)
4. የማርታ እና የአልአዛር እናት (ሉቃ 10፡39፣42)
5. የቀለዮጳ ሚስት (ዮሐ 19፣25 )
6. ማርቆስ የተባለው የዮሐንስ እናት (ሐዋ 12፡12)

▣ **"የዮሐንስ እናት"** ይህች ሴት ማርቆስ የተባለው የዮሐንስ እናት ነች። የጥንቲቱ ቤተ ክርስቲያን በግለሰቦች ቤት አምልኮ በኢየሩሳሌም ታደርግ ነበር። (ሐዋ12፡12) ጌታ ኢየሱስ ከሙታን በተነሣ ጊዜ ለሦስት ተደጋጋሚ ጊዜያት በቤት ውስጥ ለተሰበሰቡ ሰዎች ተገልጧል።

ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ የበርናባስ የወንድ ልጅ ነው። እርሱም ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር አብሮ ወንጌልን አገልግሏል። (ቆላ 4፡10 ሐዋ 12፡25-13፡19) ነገር ግን ይህ ማርቆስ ዮሐንስ በምክንያት ከወንጌል አገልግሎት ተመልሰል (ሐዋ 15፡38) በርናባስ በሁለተኛው የሚሲኒዮን ጉዞአቸው ማርቆስን ቢፈልግም ጳውሎስ በዚህ ሃሳብ አልተስማማም። (ሐዋ 15፡36-41) ይህ ያለመስማማት ከጳውሎስ እና በርናባስ መሃከል መለያየትን ፈጥሮአል በመሆኑም በርናባስ ማርቆስን ይዞ ወደ ቆጵሮስ ወረደ። (ሐዋ 15-39) ነገር ግን ጳውሎስ በእስር በነበረ ጊዜ ማርቆስን በመልካም ነገር አመስግኖታል (ቆላ 4፡30) በተጨማሪም ጳውሎስ በእስር ቤት በነበረ ጊዜ የማርቆስ ዮሐንስን ስም ጠቅሶ እናገኛለን። (2ጢሞ 4፡11)

ማርቆስ ዮሐንስ የጴጥሮስ የወንጌል አጋር መሆን ችሎ ነበር። (1ጴጥ 5፡13) የሚከተለውን ያንብቡ (ሐዋ 3፡39፡12)።

ፀሐፊው ፖፒስ "የኢየሱስን ትምህርት ከእርስቶን አግንኝ ወይም ከሽማግሌው በመማር፣ በመፅሐፉ ላይ ፅፎት ይገኛል። ይህ የብዙ የመፅሐፍ ቅዱስ ምሑራንን ትኩረት የሳበ መፅሐፍ ነው። የጴጥሮስ ፀሐፊ የነበረው ማርቆስ የሚያስታውሰውን በኢየሱስን ትምህርት የጊዜ ደረጃውንና የሃሳብ ፍሰቱን ሳይጠብቅ ፅፎታል።

የኢየሱስን ትምህርት በቀጥታ መስማት እድሉ አልነበረውም በተጨማሪም ከደቀ-መዛሙርቱ መስማማትም አልቻለም ነገር ግን የጴጥሮስ ባንጀራ እና ፀሐፊው ስለነበረ ታሪኮችን ማግኘት ችሏል። ማርቆስ ጴጥሮስ የነገረውን ኢየሱስ ያስተማረውን ትምህርት የሚያስታውሰውን ብቻ ለመፃፍ ተገዷል። ይህንን ያደረገበት ምክንያቶቹ ከቃሉ ምንም እንዳይጉድል እና በተሳሳተ ትርጉም እንዳይፅፈው በመፈለግ አንፃር ነው" ( P. 152)።

በፅሑፉ ፖፒስ ሽማግሌው ዮሐንስን ይጠቅሳል (in Against 5:33:4)ኢራኒየስ ደግሞ እነዚህ ዝርዝሮች ከፓፒስ የአይን እማኝነት የመጡ ምስክሮች ናቸው ይላል። ይህ ፖፒስ የፖሊካርፕ ባልጀራ ነበር። በፍፃሜውም ፖፒስ ከሐዋርያው ዮሐንስ ዝርዝር ታሪኮችን እንዲሰማ ያመለክታል።

▣ **"ተከማችተው ይፀልዩ ወደነበረበት"** ይህ የሰዋሰ ህግ እንደሚያስገነዝበን ሰዎች ለፀሎት ለተሰበሰበው ባሉበት ቦታ እንደሚቆዩ ነው።

12፡13 **"የደጁ መዝጊያ"** የደጁ መዝጊያ በመንገዱ ዳር ያለው የቤቱ የውጭው በር ሲሆን የጣራው ቤት ደግሞ ሌላ ትልቅ በር አለው።

▣ "ሮዴ" የስሟ ትርጉም "ሮዝ" የሚል ነው። ሮዴ የቤታቸው ሰራተኛ መሆንዋን ወይም ፀሎት ለማድረግ የመጣች ሴት መሆንዋን በግልፅ አይታወቅም።

12፡15 **"አብደሻል"** ቤተክርስቲያን ስራውን እንዲሰራ ወደ እግዚአብሔር እየፀለየች ነበር። ግን በሚገርም ሁኔታ እግዚአብሔር ሲሰራ በጣም ተደንቀዋል (ቁ 16)።

▣ **"መልአኩ ነው አሉ"** በሉቃስ ፅሑፉ ውስጥ መላእክቶች ትልቅ ሚና የሚጫወቱ ናቸው። በአይሁድ እምነት የእያንዳንዱ ሰው ጠባቂ መልአክ የሚጠብቀው ሰው መልክ እንደሚመስል ይናገራሉ። ለተጨማሪ ግንዛቤ (*Encyclopida Judaica*, Vol 2,p.963) ማንበብ ይቻላል። ነገር ገን ለዚህ ልማዳዊ አስተሳሰብ ተጨባጭ የሆነ ማስረጃ አናገኝም። ለዚህ የመልአክ አስተምሮት ከዘሪአስተሪዝም እንደሆነ የታወቀ ነው። የብዙ አይሁድ ስለ መላእክት ያላቸው አስተምሮት የሶሪያውያን አስተምሮ ተፅኖ አለበት። በአዲስ ኪዳን ያለውን ማስረጃ ተመልከቱ (ማቴ 18፡10)

12፡17 "በእጁ ጠቅሶ ዝም እንዲሉ" ሐረጉ የሚያስረዳው የአይን ምስክርነቱ የተረጋገጠ መሆኑን ነው፣ ሉቃስም ይህንን ደጋግሞ ፅፎታል። (ሐዋ 13፡16፣ 19፡33፣21፡40)

▣ **"ይህን ለያዕቆብና ለወንድሞቹ ንገሩ አላቸው"** ያዕቆብ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንድም ነው፣ በዚህ ጊዜ ደግሞ በኢየሩሳለም ባለችው ቤተክርስቲያን በመሪነት ያገለግል ነበር (ሐዋ 15፡13-21)።

**ልዩ ርዕስ፡ የኢየሱስ ወንድም ያዕቆብ**

ሀ. ያዕቆብ የስሙ መጠሪያ "ፃድቁ ያዕቆብ" ይሉት ነበር፣ በኃላም "የግመል ጉልበት" የሚል ቅፅል ስም ነበረው። ይህም የተባለበት ምክንያት የፀሎት ሰው ስለነበር ነው።
ለ. ያዕቆብ አማኝ የሆነው ከትንሳኤ በኃላ ነበር (ማርቆ 3፡21፣ ዮሐ7፡5) ነገር ግን ኢየሱስ በግሉ ከትንሳኤ በኃላ ተገልጦለታል (1ቆሮ 15፡7)
ሐ. በሐዋ 1፡14 "በነበረው ስብሰባ ውስጥ ነበር፣ ደግሞ በጴንጤቆስጤ ወይም ባለሀምሳ በተባለው ቀን ተሳታፊ እንደነበር ይገመታል"
መ. ያዕቆብ ትዳር የነበረው ሰው ነው። (1ቆሮ 9፡5)
ሠ. ሐዋርያው ጳውሎስ ያዕቆብን "አህማድ" ብሎታል (ገላ 1፡19) ነገር ግን ከአስራ ሁለቱ ደቀ-መዛሙርት አንዱ አልነበረም። (ገላ 2፡9፣ ሐዋ 12፡17፣15113)
ረ. ጆሰፈስ የተባለው የታሪክ ፀሐፊ ያዕቆብ በሰዱቃውያን ትዕዛዝ በ62 ዓ.ዓ በድንጋይ ተወግሮ እንደሞተ ቢናገርም ነገር ግን የጥንት ታሪክ ደግሞ ክሌመንተ አሌክሳንደሪያን በመጥቀስ ከመቅደስ ቅጥር ላይ ተወርውሮ እንደሞተ ዘግቧል።
ሰ. ከኢየሱስ ሞት በኃላ ለብዙ አብያተ ክርስቲያና የኢየሱስ ዘመድ የሆነውን በመሪነት እንዲያስተዳድር ይሾሙ ነበር።
ሸ. በአዲስ ኪዳን አንድ መፅሐፍን ፅፏል "የያዕቆብ መፅሐፍ"

▣ **"ወጥቶም ወደ ሌላ ስፍራ ሄደ"** ጴጥሮስ ወዴት እንደሄደ ለማወቅ ያዳግታል። ነገር ግን ወደ ሮም እንዳልሄደ የምናውቀው በኢየሩሳሌም ስብሰባ ላይ በመገኘቱ ነው (ዮሐ 15)።

እግዚብሔር ጴጥሮስን በተዓምራት መታደጉ ተመሳሳይ ተዓምራት በየጊዜው ይሆናል ተብሎ እንዳ ህግ የምንወስደው መሆን የለበትም:: በዚሁ ምዕራፍ ላይ ትልቁ ያዕቆብ እንደተገደለ እናጤናለን። በመሆኑም ጴጥሮስ ለቅዱሳን በፃፈው ፅሑፍ በመዳናቸው ብዙ መከራ እንደሚፈራረቅባቸው ተናግሯል።

**ሐዋ 12፡18-19**

**በነጋም ጊዜ ጴጥሮስን ምን አግኝቶት ይሆን ብለው በጭፍሮች ዘንድ ብዙ ሁከት ሆነ። ሄሮድስም አስፈልጎ ባጣው ጊዜ ጠባቂዎችን መረመረ ይገድሉአቸውም ዘንድ አዘዘ። ከይሁዳም ወደ ቂሣርያ ወርዶ በዚያም ተቀመጠ።**

12፡18 **"በጭፍሮች ዘንድ ብዙ ሁከት ሆነ"** የሉቃስ የስነ ፅሑፍ ስልቱ ነው ሐዋ 14፡28፣15፣2፣17፡4፡12፣19፡23፡24፣27፡20)

12፡19 **"ጠባቂዎችም መረመረ ይገድሉአቸውም ዘንድ አዘዘ"** አረፍተ ነገሩ ፍፃሜን በግልፅ አያሳይም። በግሪኩ ፅሑፍ ይህ አልተገኘም። ነገር ግን አንድ ጠባቂ የእስረኛው ቢያመልጥ ጠባቂው የእስረኛውን ቅጣት እንዲፈፅም ይገደድ ነበር (ሐዋ 16፡27፣27፣42)።

**ሐዋ 12፡20-23**

**ከጤሮስና ከሲዶና ሰዎችም ጋር ተጣልቶ ነበር። በአንድ ልብ ሆነውም ወደ እርሱ መጡ። የንጉስንም ቢትወደድ ቢነስጦስን እሹ አሰኝተው ዕርቅ ለሙኑ። አገራቸው ከንጉስ አገር ምግብ ያገኝ ነበርና። በተቀጠረ ቀንም ሄሮድስ ልብሰ መንግስቱን ለብሶ በዙፋን ተቀመጠ እነርሱንም ተናገራቸው ህዝቡም የእግዚብሔር ድምፅ ነው። የሰውም አይደለም ብለው ጮኹ፡ ለእግዚአብሔር ክብር ስላልሰጠ ያን ጊዜ የጌታ መልአክ መተው በትልም ተበልቶ ሞተ።**

12፡20 **"ከጢሮስና ከሲዶና ሰዎችም ጋር ተጣልቶ ነበር"** ሄሮድስ ከእነዚህ ሀገራት ጋር ሰላም አልነበረም። በገሊላ ካሉ ሀገሮች ሲዶና እና ጢሮስ በእርሻ ምርት የታወቁ አገራት መሆናቸውን እንጂ ሌላ ታሪካዊ ክንዋኔዎቻቸው በግልፅ ማስረጃ የሚታወቅ አይደለም (1ነገሰ 5፡11፣ ዕዝ 3፡7 እና ሕዝ. 27፡17)።

12፡21 **"በተቀጠረ ቀንም ሄሮድስ ልብሰ መንግስቱን ለብሶ"** ታሪኩ የተከናወነው በ44 ዓ.ዓ) ነበር። ተጨማሪ ግንዛቤ ለማግኘት ቀጣዩን መፅሐፍ ያንብቡ (Josephus 19.8-2)።

የአውራጃው ታላቅነት እንዲታይ ብዙ ባለስልጣናት እና የተከበሩ ሰዎች የተገኙበተ በአል ነበር። ሄሮድስም በበዓሉ በሁለተኛው ቀን ክብር የተሰራ ልብስ መንግስቱን ለብሶ በሚያንፀባርቀው የማለዳ ፀሐይ ሲታይ በእርግጥም የሚያስገርም ውበት ነበር። በመሆኑም ለሚያየው ሁሉ እጅግ የሚያስፈራ ነበር። በበዓሉ የተሰበሰቡትም ሰዎች "እነሆ ምህረትን አድርግልን እንደሰው ብቻ አመስግነንህ ነበር አንተ ግን አምላክ በመሆንህ ክብርን እንሰጥሀለን"

በማለት ሲያሞግሱት እርሱ ግን ንግግራቸውን አልተቃወማቸውም ነበር፡፡ ሄሮድስም ቀና ብሎ በተመለከተ ጊዜ ገመድ በራሱ ላይ ተጠምጥሞ ነበር፣ ገመዱንም ያመጣችው ወፍ ቀድሞ መልካም ነገር የምታመለክተው ወፍ ነበረች አሁን ግን ክፉ ገመድን ከሰማይ እንዳመጣች በማወቁ እጅግ አዘነ፡፡ ወዲያውም ከባድ ህመም በሆዱ ውስጥ ተከሰተ በዚህ ጊዜ ወደ ባልንጀሮቹ እየተመለከተ እንዲህ አለ፡- እኔ እናንተ እንደ አምላክ የጠራችሁኝ በአሁኑ ጊዜ ይህንን ህይወት እለያለሁ እናንተ ያላችሁኝን ቃል የሚሽር ቃል ተነግሯል፤ ሟች አይደለህም ያላችሁኝ ቃል በፍጥነት በሞት ተተክቶ ይሰወራል" (P.412)፡፡

12፡23 **"የጌታ መልአክ"** የሞት መልአክ የተባለውን ያመለክታል (ዘፀ 12፡23 2ሳሙ 24፡16፣ 24፡16፣2ነገ 19፡35) ሞት በእግዚአብሔር እጅ እንጂ በሰይጣን መዳፍ ውስጥ አይደለም፡፡ ይህም ጊዜያዊ ፍርድን ያመክታል፡፡

12፡24 የማጠቃለያ ሐተታ ነው (ሐዋ 6፡7፣9፡31፣12፡24፣16፡5፣19፡20፣28፡31)

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 12፡24**
**የእግዚአብሔር ቃል ግን ያድግና ይበዛ ነበር፡፡**

12፡25 ምንባቡ የሐዋርያው ጳውሎስን የሚሲዮናዊነት የመጀመሪያ ጉዞውን ይተርካል፡፡ በዚህ ስፍራ ወደ ኢየሩሳሌም እየተመለሱ እያለ ወይም ከኢየሩሳሌም እየሄዱ እንዳለ በስነመለኮት ተመራማሪዎች ዘንድ ልዩነት አለ፡፡ ምዕራፍ 13 በበርናባስና በሳኦል በአንፆኪያ መሆን የጀምራል፡፡

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 12፡25**
**በርናባስና ሳውልም አገልግሎታቸውን ፈፅመው ከኢየሩሳሌም ተመለሱ ማርቆስ የተባለውን ዮሐንስንም ከእነርሱ ጋር ይዘውት መጡ፡፡**

### የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ለመርዳት ነው የተሰናዱት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋነኞቹን ጉዳዮች ለማጤን እንዲረዳ ነው፡፡ ሐሳብ ለማጫር እንጂ መደምደሚያ አይደሉም፡፡

1. እግዚአብሔር ያዕቆብን እንደ ጴጥሮስ ከሞት ለምን አላዳነውም
2. ስለ ጴጥሮስ የሚፀልዩ ሰዎች ከእስር ተፈቶ ባዩት ጊዜ ስለምን ተገረሙ? ግለፅ፡፡
3. አማኞች መንፈስ ቅዱስን ከተሞሉ በኃላ መላእክት ያስፈልጋቸዋልን?

# የሐዋርያት ስራ 13

## የምንባቡ ክፍፍል በአዲሶቹ ትርጉሞች

| የተየመቅሶ[4] | አኪጀት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የባርናባስ እና ሳኦል ተልእኮ | በርናባስና ኦልስ ተሾሙ | በርናባስና ሳኦል በቆጳሮስ | በርናባስና ሳኦል የተመረጡና የተላኩ ናቸው፡፡ | የሚሲዮናዊነት ተልዕኮ |
| | (12፡25-13፡3) | (12፡23-13፡12) | | |
| 13፡1-3 | | 13፡1-3 | 13፡1-2 | 13፡13 |
| | | | 13፡3 | |
| በሐዋርያት በቆጵሮስ ሰበኩ | በቆጳሮስ ስብከት | | በቆጳርስ | ጥንቆላ በጳሮስ |
| 13፡4-12 | 13፡4-12 | 13፡4-12 | 13፡4-5 | 13፡4-5 |
| | | | 13፡6-11a | 13፡6-12 |
| | | | 13፡11b-12 | |
| ጳውሎስና በርናባስ በአንፃኪያ | በአንፃኪያ | ጉዞ ወደ አንፃኪያ እና አቆንዮስ | በአንፃኪያ | አንፃኪያ ደረሱ |
| 13፡13-16a | 13፡13-41 | 13፡13-16a | 13፡13-16a | 13፡13-16a |
| 13፡16b-25 | | 14፡16b-25 | 13፡16b-20 | 13፡16b-25 |
| | | | 13፡20-25 | |
| 13፡26-41 | | 13፡26-41 | 13፡26-41 | 13፡26-31 |
| | | | | 13፡32-37 |
| | | | | 13፡38-39 |
| | | | | 13፡40-41 |
| | በረከትና ክርክር በአንፃኪያ | | | |
| 13፡42-43 | 13፡42-52 | 13፡42-43 | 13፡42-43 | 13፡42-43 |
| 13፡44-52 | | 13፡44-47 | 13፡44-47 | 13፡44-47 |
| | | 13፡48-52 | 13፡48 | 13፡48-49 |
| | | | 13፡49-52 | |
| | | | | 13፡50-52 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (ከ "መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ" ገጽ vii)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. ምንባብ አንድ

2. ምንባብ ሁለት

3. ምንባብ ሦስት

4. ወዘተ…

**የዓውዱ እይታ**

ሀ. ምዕራፍ የሚያወሳው ስለሐዋርያው ጳውሎስና በርናባስ የመጀመሪያ የሚሲዮናዊነት ጉዞ ነው።

ለ. የሐዋርያት ስራን ምዕራፍ አስራ ሦስት እና አስራ አራትን የሚያጠና ሁሉ አገሮችን የሚያመላክት ካርታ ቢመለከት ግልፅ ግንዛቤን ያገኛል።

ሐ. በዚህ ምዕራፍ ላይ በርናባስ አገልግሎቱን ለሐዋርያው ጳውሎስ ያሸጋገረበት ምዕራፍ ነው።

**የቃል እና የጥምር ቃል ጥናት**

> **አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ: 13:1-3**
> **በአንፃኪያ ባለችው ቤተክርስቲያን ነቢያትና መምህራን ነበሩ። እርሱም በርናባስ ኔገር የተባለው ስምኦንም የቀሬናው ሉክዮስም የአራተኛው ክፍል ገዥ የሄሮድስም ባለምዋል ምናሔ ሳውልም ነበሩ። እነዚህ ጌታን ሲያመልኩና ሱጠሙ መንፈስ ቅዱስ በርናባስንና ሳውልን ለጠራነቸው ስራ ለዩልኝ አለ። በዚያን ጊዜም ከጠሙ ከፀለዩ እጃቸውንም ከጫኑ በኃላ አሰናበቷቸው።**

13፡1 "**አንፃኪያ**" ሐዋ 11፡19 ይመልከቱ።

▣ "**ቤተክርስቲየን**" ሐዋ 5፡11 ይመልከቱ።

▣ "**ነብያትና መምህራን**" እነዚህ ሁለት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በ1ቆሮ 12፡28 እና በኤፌ 4፡11 ተፅፈው ይገኛሉ። በዚህ ጥቅስ የተፃፉት ስሞች የመጀመሪዎቹ አምስት ነብያት እና አስተማሪዎች ወይም የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ ነብያቶች የሚቀጥሉት ሁለት ደግሞ አስተማሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

በዚህ ምንባብ የሚነሳው ጥያቄ የአዲስ ኪዳን ነብያቶች ከብሉይ ኪዳን ነብያቶች የሚዛመዱት በምንድነው? በብሉይ ኪዳን የነበሩ መፅሐፍ ቅዱስን የፃፉ ሲሆን ይህ በአዲስ ኪዳን ለሐዋርያት እና ለረዳቶቻቸው የተሰጠ ስራ ነበር። የሐዋርያነት ስጦታ አስራ ሁለቱ ከሞቱ በኃላ በተለየ በተለወጠ ስራ ስጦታው ቀጥሎአል። ነብያትም በዚሁ መልክ ስራቸው ተቀይሯል። (ኤፌ 4፡11) ይህ ማለት መፅሐፍ ቅዱስ ከእንግዲህ በሐዋርያትና በነብያት ስራቸው ወንጌልን ማወጅ ነው።

የአስተማሪነተ ስጦታ ከነብያት ስጦታ ጋር (በሐዋ 13፡1) ተጠቅሶ ይገኛል። በኤፌ 4፡11 ከመጋቢ ስጦታ ጋር ተጣምሮ ይገኛል። በ2ጢሞ 1፡11 ጳውሎስ አስተማሪ፣ ሐዋርያ እና አስተማሪ መሆኑን ይገልፃል። በመሆኑም ሁሉም ራሱን የቻለ ስጦታ መሆኑን ያሳውቀናል። (ሮሜ 12፡7 ያዕቆ 3፡1) በጥንቲቱ ቤተክርስቲያን ወንጌልን ለመስበክ በሚያስችላቸው መንገድ ሁሉ በመጠቀም ወንጌልን ያውጁ ነበር።

▣ "**ኔገር የተባለው ስምኦንም**" "**ኔገር**" በላቲን "ጥቁር" ወይም "ጨለማ" ማለት ነው። ይህ ስምኦን በማርቆ 15፡21 ላይ የሚገኘው ማርቆስ ሳይሆን አይቀርም።

▣ *"የቀሌናው ሉክዮስ"* ሉክዮስ የግሪክ ቋንቋ ተናጋሪ የሆነ አይሁዳዊ ነው። ወንጌልን ለህዛቦች የሰበከ ሰው ነው። (ሐዋ 11፡20) ይህ ሉክዮስ በሮሜ 16፡21 የተጠቀሰው አይደለም።

▣ *"የአራተኛው ክፍል ገዥ የሄሮድስም ባለምዋል ምናሔ"* በግሪክ "ምናሔ" ማለት "አፅናኝ" ነው። ምናሔ የሔሮድስ አንቲጳው ወንድም ወይም አብሮ አደጉ እንደሆነ ይገመታል።

13፡2
NASB *"ሲያገለግሉ"*
NKJV *"አገለገሉ"*
NRSV *"ሲያመልኩ"*
TEV *"ሲያገለግሉ"*
NJB *"መስዋት ሲሰዎ"*

ከሁለት ጥምር ቃል የተቃኘ ነው("ህዝብ እና ስራ") የግሪኩ "ሊተርጂያ" ወደ እንግሊዘኛው ሲተረም በራሱ ገንዘብ እና ጉልበት ህዝብ የሚያገለግል ማለት ነው። በዚህ በአምልኮ ጊዜ ለእግዚአብሔር በመስዋት በመስዋት እርሱን መፈለጋቸው ያሳያል። ነገር ግን ይህ ግስ አምስቱን ሰዎች ወይስ ቤተክርስቲያኒቱን የሚወክል ቃል ይሆን

▣ *"ሲጦሙ"* በብሉይ ኪዳን በአመት አንድ ጊዜ ብቻ የፃም ጊዜ ነበር። ዘሌ 16፤ ነገር ግን ኢየሱስ በነበረበት ዘመን የአይሁድ መምህራን በስምንት ሁለት ጊዜ የፃም እወጃ አድርገው ነበር። ፃም የእግዚአብሔር ፈቃድ ለመለየት አይነተኛ መንገድ ነው። (ሐዋ 14፡23)

> **ልዩ ርዕስ: *ፆም***
>
> በአዲስ ኪዳን ፃም እንዲደረግ አያዝም ነገር ግን የኢየሱስ ደቀመዛሙርት በግዜው ለነበረው ሁኔታ መፃም ነበረባቸው። (ሐዋ2፡19፣ ማቴ6፡16.17፣ሐዋ 9፡15፣ ሉቃ 5፡35) በኢሳ 58 አግባብ የሆነ ፃም ይደረግ እንደነበረ አመላካች ቃል ነው። ኢየሱስ ክርስቶስም ፃሚል (ማቴ 4፡2)
>
> የጥንቲቱም ቤተክርስቲያን ፃምን ትለማመድ ነበር። (ሐዋ 13፡2-3) ሐዋ 14፡23፣ 2ቆሮ 6፡5፣ 11፡27) በእርግጥ የፃም አይነቱ እና የቀኑ ብዛት እንደግለሰቡ ይወሰናል። የብሉይ ኪይን ፃም ለአዲስ ኪዳን አማኞች ግዳጅ አይደለም (ሐዋ 15) ፃም ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ እንጁ መንፈሳዊነትን አያሳይም። የጥንቲቱ ቤተክርስቲያን ራስን ለእግዚአብሔር ለማስገዛት ትፃም ነበር (1ማቴ 17፡21፣ ማርቆ 9፡29፣ ሐዋ 10፡30፣ 1ቆሮ 7፡5)።

▣ *"መንፈስ ቅዱስ.... ለዩልኝ አለ"* ይህ ሐረግ የመንፈስ ቅዱስን ምልአተ ስብዕና የሚያረጋግጥልን ነው። በዚህ ዓረፍተ ነገር የተነገረው በሚሰማ ድምፅ ወይም በነብያት በኩል መሆኑን ግልፅ አይደለም (ሐዋ 8፡29፣ 10፡19፣ 11፡12፣ 20፡23፣ 21፡11)። ይህ ክፍል በጣም የተለየ መልዕክት እንዳለው የታወቀ ነው (16፡7-7)።

▣ *"ለዩልኝ"* (*aphonzō*) የሚለው ቃል 'ቅዱስ' (*hagiazō*) ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ሃሳብ ያለው ነው። ለመለኮታዊ ስራ መለየትንና መዘጋጀትን ያመለክታል (ሮሜ 1፡1፣ ገላ 1፡15)።

▣ *"ለዩልኝ"* ከሚለው ከግሪኩ ቃል መቀራረብ እንዳለ እናይበታለን (ሉቃ 2፡15፣ 1ቆሮ 6፡20)። ለመንፈስ ጥሪ ከፍተኛ ስፍራ ሲሰጥ እናያለን። ይህ በ15፡36 ላይ ከተገለፀው ሀሳብ ጋር የጎንዮሽ ሀሳብ ያለው ይመስላል።

▣ *"እኔ ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ"* የጠራቸው እና ብቃትን የሰጣቸው ራሱ እግዚአብሔር ነው (1ቆረ 12፡7,11)።

13፡3 *"እጃቸውንም ጫኑባቸው"* በዚህ ጥቅስ ላይ ነው በዚህ ዘምን ያለንም አገልጋዮችን የመሾም አገልግሎት የተመሠረተው። ነገር ግን በአብያተ ክርስቲያናት የሚደረገው እጅ መጫን እንደ እግዚአሔብር ቃል መሆኑን ያጠራጥራል። በመፅሐፍ ቅዱሳችን ስለ እጅ መጫን በርካታ ምሳሌዎች አሉ፡-

1. በብሉይ ኪዳን፡-
   ሀ. የሚሰዋውን ለመለየት (ዘሌ 1፡4፣ 3፡2፣ 4፡4፣ 16፡21)
   ለ. ለመባረክ (ዘፍ 48፡1፣ ማቴ 19፡13.15)
   ሐ. ለተተኪ መሪዎች (ዘኁል 27፡23፣ ዘዳ34፣9)
2. በአዲስ ኪዳን እጅ መጫን፡-
   ሀ. ለፈውስ (ሉቃ 4፡40፣ 13፡13 ሐዋ 9፡17፣ 28፡8)
   ለ. ለልዩ ስራ ለመለየት (ሐዋ 6፡6፣ 13፡3)
   ሐ. መንፈሳዊ ሃይልና ስጦታን ለመቀበል (ሐዋ 8፡17፣ 1ጢሞ 4114)
   መ. የአይሁድን ሃይማኖት ለማመልከት (ሐዋ 616፣ 13፡3)

እጅ መጫን የአንድ ፕሮግራም ወይም ነገር ማስጀመሪያ አይደለም። በዚህ ክፍል ያሉት እጅ የሚጫንላቸው ሰዎች በአገልግሎት የቆዩ ናቸው እንጂ አዲሶች አይደሉም።

ነገር ግን ሹመት አማኞችን የሚያበረታታ ነው። በካቶሊክ ቤተክርስቲያን ተራውን ክርስቲያን ከጳጳሶቹ የሚለኝ ስርዓት ነው። የግሪኩ ጳጳስ(ክሌሮስ) ማለት በእጣ መጣጣል መወረስ (ላኦስ) ህዝብ ማለት ነው። አዲስ ኪዳን ይህንን ቃል ለአማኞችን ሁሉ ለመግለፅ ይጠቀምበታል አማኞች ሁሉ ከእግዚአብሔር ስጦታን ተቀብለዋል። (ኤፌ 4፡11-12) በአማኞች መሃከል የስልጣን ተዋረድ እንዳለ መፅሐፍ ቅዱስ አይናገርም። ነገር ግን ሁሉም አማኝ የክርስቶስን አካል ለመገንባት ማገልገል ይችላል (1ቆሮ 12፡17,11)።

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 13፡4-12**

**በእርሱም በመንፈስ ቅዱስ ተልከው ወደ ሴሌውቅያ ወረዱ ከዚያም በመርከብ ወደ ቆጵሮስ ሄዱ። በስልማናም በነበሩም ጊዜ በአይሁድ ምኩራቦች የእግዚአብሔርን ቃል ሰበኩ አገልጋይ ዮሐንስ ነበራቸው። ደሴቲቱንም ሁሉ እስከ ጳፉ በዞሩ ጊዜ ባርያሱስ የሚሉትን ጠንቀይና ሐሰተኛ ነብይ የሆነውን አንድ አይሁዳዊ ሰው እርሱም አስተዋይ ሰው ከሆነው ሰርግዮስ ጳውሎስ ከሚባለው አገረ ገዢ ጋር ነበር። ይህም በርናባስንና ሳኦልን ወደ እርሱ ጠርቶ የእግዚአብሔርን ቃል ሲሰማ ፈለገ። ጠንቋዩ ግን ኤልማስ ስሙ እንዲህ ይተረጐማልና አገረ ገዢውን ከመስማት ሉያጣምም ፈልጐ ተቃወማቸው። ጳውሎስ የተባለው ሳኦል ግን መንፈስ ቅዱስን ተሞልቶ ትኩር ብሎ ሲመለከተው አንተ ተንኰል ሁሉ ክፋትም ሁሉ የሞላብህ የዲያቢሎስ ልጅ የፅድቅም ሁሉ ጠላት የቀናውን የጌታን መንገድ ከማጣመም አታፍርምን አሁንም እነሆ የጌታ እጅ በአንተ ላይ ዕውርም ትሆናለህ እስከ ጊዜውም ፀሐይን አታይም አለው። ያን ጊዜም ጭጋግና ጨለማ ወደቀበት በእጁም የሚመራውን እየዞረ ፈለገ በዚያን ጊዜ አገረ ገዢው የተደረገውን ባየ ጊዜ ከጌታ ትምህርት የተነሣ ተገርሞ አመነ።**

13፡4 **"በመንፈስ ቅዱስ ተልኮው"** በቤተክርስቲያን ስልጣን ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ መላካቸውን ያመለክታል። በሐዋርያት ስራ መፅሐፍ የስላሴን ትምህርት በግልፅ ማግኘት ይቻላል። የመሲሁ ዓመት የመንፈስ ዘመን በመባል ተሰይሟል እንግዲህ ይህ መንፈስ ይጠራል፣ ስጦታን ይሰጣል፣ ከመንፈስ ቅዱስ ሀይል በቃር ማንም ምንም ማድረግ አይቻለውም።

▣ **"ሴሌውቅ"** በሲሪያ ልሳነ ምድር ያለ የአንጾኪያ የወደብ ከተማ ነበር በደቡብ ምዕራብ አስራ አምስት ማይል ርቀት ላይ ይገኛል። አሌክሳደር ከሞተ በኃላ ጀነራል ሆኖ አካባቢውን ይመራ በነበረው በሴለውቅ ከተማይቱ ተሰይማለች።

▣ **"ቆጵሮስ"** የባርናባስ ከተማ ሲሆን በርካታ አይሁዳውያን ይኖሩ የነበረበት ከተማ ነበር። በብሉይ ኪዳን ከተማው ኪታም ይባል ነበር። በዚህ ክፍል የተጠቀሱት ክርስቲያኖች የደሴቲቱ የመጀመሪያ አማኞች አልነበረም (ሐዋ 11፡19-20)

13፡5 **"ስልማና"** በምስራቅ ቆጳሮስ በባህር ዳርቻ የምትገኝ ከተማ ነች። የንግድ ማዕከል ነበረች።

▣ **"በአይሁድ ምኩራቦች የእግዚአብሔርን ቃል ሰበኩ"** በምኩራብ የእግዚአብሔርን ቃል መስበክ ለምን አስፈለገ፡ (1) አይሁድ የብሉይ ኪዳን መፅሐፍ ስለሚያውቁ (2) አይሁድ የተመረጡ በመሆናቸው የመጀመሪያውን ዕድል እንዲያገኙ በማሰብ ነው። (ዘፍ 12፡1-3 ሐዋ3፡26 ሮሜ 1፡16፣ሐዋ17፡2) (3) በአይሁድ ምኩራብ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ አህዛቦች በመኖራቸው ወንጌል እንዲሰሙ የጳውሎስ አላማ ነበር።

▣ **"ዮሐንስ"** ደቀ መዛሙርቱ ለፀሎት የሚሰበሰቡት ማርቆስ በተባለው በዮሐንስ ቤት ነበር። (ሐዋ 12፡12) ይህ ማርቆስ ከወንጌላት መሀከል አንዱን ፅፏል የሐዋርያው ጴጥሮስም የአይን እማኝ ምስክርነት በማግኘት መፅሐፉን የፃፈ ሰው ነው። በጳውሎስና በበርናባስ መሃከል የነበረው ጥርልና ክርክር በማርቆስ ዮሐንስ የተነሳ ነበር። የሐዋ 15፡35-41 ነገር ግን ዘግይቶ ጳውሎስ በአዎንታዊ መልክ ዮሐንስን ስሙን ጠቅሶታል (ቆላ 4፡10፣ 2ጢሞ 4፡11 እና ፊሊ ቁ.24)

13፡6 **"ደሴቲቱንም ሁሉ በዞሩ ጊዜ"** ይህ ሊሆን የሚችለው በደረሱበት ደሴት ሁሉ በምኩራብ እየሰበኩ እንደነበር ያመለክታል።

▣ **"ጳፉ"** ይህች ከተማ ከቀድሞይቱ ከፊንቃውያን ከተማ በሰባት ማይል ላይ የምትገኝ ነች። እነዚህ ሁለቱም ከተሞች በፊንቃውያን ጣኦት ስያሜ የተሰየሙ ናቸው (ጳፊያን) ይህ የፍቅር አምላክ ሲሆን በሌላም መጠሪያም ይጠራሉ አፍሮዳይት፣ አስታሮች እና ቬነስ ወዘተ... ከተማይቱ የቆፐሮስ የፖለቲካ ማዕከል ነበረች።

▣ **"በርያሱስ"** ይህ ሰው አይሁዳዊ ሆኖ የሃሰት ትንቢትን የሚሰማ ነበር። የስሙ ትርጉም የኢያሱ ልጅ ማለት ነው። በቁጥር ስምንት ላይ ኤልማስ ወደ ተባለ ጠንቋይ ይሄድ እንደነበር ተፅፏል። በግሪክ ማጂክ የሚለው ቃል በአራማክ ጠንቋይ በማለት ፍቺ ይሰጣል። (ሐዋ 8፡9)

13፡7 **"አገረ ገዥው ሰርግዮስ ጳውሎስ"** የሉቃስን ፅሑፍ እርግጠኛ ካደረጉት መሃከል ይህ ዓረፍተ ነገር አንዱ ነው። ይህንን ሰው ሉቃስ አገረ ገዥ በማለት ጠርቶታል። በመሆኑም ቆጵሮስ የሮማ መሆንዋን ያረጋግጥልናል። ከአገስቲን አዋጅ መረዳት እንችላለን። (22 ከክርስቶስ ልደት በኂላ) በላቲኒ ትርጉም ውስጥ ደግሞ ሰርግዮስ ጳውሎስ መሪነቱን የተረከበው መሆኑን ይገልፃል (በ53 ከክርስቶስ ልደት በኂላ) በሚዲትራኒያን ዓለም የተገኘው የቅሪት አካል ምርምር ለዚህ ማስረጃን አቅርቧል።

▣ "አስተዋይ ሰው" የተለያየ ትርጉም ሊሰጠው የሚችል ሐረግ ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ ዓውድ መሠት ትርጉሙ በመሪነት የተዋጣለት ነበር ለማለተ ተፈልጐ ነው፡፡ በተጨማሪም ወንጌል ድሆችን እና ያልተማሩትን ብቻ ሳይሆን ባለጠጐችንና የተማሩትንም እንደሚማርክ ለማስገንዘ ተፈልጐ ነው፡፡ የፀሐፊው ሉቃስ ትኩረት የክርስትና ሃይማኖት ለሮማውያን ፍርሃት እንዳይደለ ለመግለፅ መፈለግ ተቀዳሚ አላማው ነበር፡፡

13፡8 "ኤልማስ" ይህ የግሪክ ስም በአረብኛ ትርጉሙ ጠቢብ ማለት ነው (ይህም ማለት መለኮታዊ፣ የማይታዮትን የመንፈስ አካላት በማስገደድ የወደፊቱን የሚናገር ማለት ነው)፡፡

▣ "ጠንቋይ" ይህ ማጂ የሚል ቃል ይተካዋል፡፡ ትርጉሙም የከለዳዊያን እና የሚዲያውያን ጥበበኛ ሰዎችን የሚያመለክት ነው ዳንኤልም ጠቢብ ተብሏል፡፡ (ዳንኤ 2፡2 4፡9፣ ማቴ2፡1) በጳውሎስ ዘመን በግሪኮ ሮማ ዓለም የጥንቆላ ስራ የሚሰሩ እንደነበሩ ይታወቃል፡፡

▣ "ማመን" በአዲስ ኪዳን እምነት በሦስት መንገዶች ይገለፃል፡፡ (1) ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ግል አዳኝ አድርጎ መቀበል፡፡ (2) በቅድስና ታማኝ ሆኖ መኖርን ያመለክታል፡፡ (3) የወንጌል ዋና መልእክት ነው (ይሁዳ 3፡20) በሐዋ 6፡7 የተፃፈፀውን በጥልቀት ይመልከቱት፡፡

13፡9 "ጳውሎስ" የሮማ ባለስልጣንነትን ከተወ በኃላ በዚህ ስም ሲጠራ የመጀመሪያ ነው፡፡ ጳውሎስ የግሪክ ስም ነው ትርጉሙም ትንሽ ማለት ሲሆን አንዳንዶች የስሙ ፍቺ የጳውሎስን ሰውነት ያመለክታል የሚል ግምት አላቸው ሌሎች ደግሞ ጳውሎስ ስለ ራሱ የነበረውን ግምት ያሳያል በማለት አስተያየታቸውን ይሰጣሉ፡፡ (ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ) ይህን ያለበት ምክንያቱ የቤተክርስቲያን አሳዳጅ ስለነበረ ነው፡፡ ይህ ሁለተኛ ስሙ ወላጆቹ የሰየሙለት ስም ሳይሆን አይቀርም፡፡

▣ "ጳዎሎስ ግን መንፈስ ቅዱስን ተሞልቶ" በጥንቲቱ ቤተክርስቲየን የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ለመግለፅ ተሞልቶ ወይም ሙላት የሚለውን ቃል ይጠቁሙ ነበር፡፡ (ሐዋ 2፡4፣4፡8,31፣ 6፡3፣ 7፡55፣ 9፡17፣ 13፡9,52) በየፅሉቱ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት የጥንቲቱ ቤተክርስቲያን ልምምድ ነበር፡፡ (ኤፌ 5፡18) በሐዋርያት ስራ መፅሐፍ ድፍረትን እና ወንጌል ለመስበክ መዘጋጀትን ያመለክታል፡፡

▣ "ትኩር ብሎ" ሐዋ 1፡10 ይመልከቱ፡፡

13፡10 ጳውሎስ ሐሰተኛ ነብያቶችን የሚለይበትን ባህሪያት እንመልከት፡-

1. በውሸት የተሞሉ መሆናቸው (በሉቃስ ፅሑፍ ላይ ብቻ ይህ ቃል ይገኛል)
2. በማታለል የተሞሉ ናቸው፡፡ የግሪክ ፍቺው በማይታወቅ ሁኔታ አንድ ነገርን ማድረግ ማለት ሲሆን ነገር ግን ክፉ አጀንዳ ከበስተጏላው ያለው ነው፡፡ (ሐዋ 13፡10፣ ዮሐ 8፡38,4,44)
3. የፅድቅ ጠላት በመባል ተለይተዋል፡፡ በፀሐፊው ሉቃስ የተለመደ የአፃፃፍ ስልቱ ነው፡፡ (ሉቃ 1፡71,74፣ 20፡43፣ ሐዋ 2፡35)
4. በዚህ ቁጥር ውስጥ ጳውሎስ ሦስት ጊዜ "ሁሉ" የሚለውን ቃል የተጠቀመው የሰውን ክፉ ስራ ለማመልከት ነው፡፡

▣ "የቀናውን የጌታን መንገድ ከማጣመም አታርፍምን" ዓረፍተ ነገሩ አዎንታዊ ምላሽ የሚያሻው ነው፡፡ ቀና ወይም ቀጥተኛ የሚለው ቃል ከብሉይ ኪዳን የተወሰደ ነው፡፡ ፍቺውም ትክክለኛነት ወይም ፅድቅ ማለት ነው፡፡ በአዲስ ኪዳን ማጣመም በብሉይ ኪዳን ሃጢያት በእግዚአብሔር ላይ መስራት የሚል ሰፊ ትርጉም አለው፡፡ ሰው የሚሰራው ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት የፅድቅ ተቃራኒ የሆነውን የተጣመመ ነገርን ነው፡፡

13፡11 "የጌታ እጅ" የሰውን አካል በተምሳሌት በመጠቀም የያህዌን ሀይል የሚገልፅ ሐረግ ነሉ፡፡ (ሉቃ 1፡66፣ ሐዋ 11፡21) በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔርን ፍርድ ያሳያል፡፡ (ዘፀ 9፡3፣ 1ሳሙ 5፡6፣ኢዮ 19፡21፣ 23፡2፣መዝ 32፡4፣ 38፡2 መዝ 39፡10)

▣ "ዕውር ትሆናለህ" ጳውሎስ የቀደመውን የራሱን ህይወት በመመልከት የቀናውን የጌታን መንገድ የሚያጠምመውን ይህን ጠንቋይ ለመለከት ቅጣት አሳልፎ ሲሰጠው ማጤን ይቻላል፡፡ (ሐዋ 9፡8)
የአይን መጨለም በምሳሌነት የሚያገለግለው መንፈሳዊ ጨለማን ለመገለፅ ነው፡፡

13፡12 "የተደረገውን ባየ ጊዜ ከጌታ ትምህርትየተነሳ ተገርሞ አመነ" ከግሪኩ ቃል ፒስቲዮ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ፍቺውም ማመን፣ እምነት ወይም መደገፍ የሚል ትርጉምን ይሰጣል፡፡ በአዲስ ኪዳን እውነተኛ ከልብ የሆነን እምነት ያሳያል፡፡ በመሆኑም ይህ ባለስልጣን ለወንጌል አዎንታዊ ምላሽ መስጠቱን አሳይቷል፡፡ በዚህ ምንባብ የአንድ ሰው አይን ሲታወር የአንድ ሰው አይን ደግሞ ተከፍቷል፡፡ (በምሳሌ የቀረበ ነው) (የሐ 9) ሐዋ 3፡16 ይመልከቱ፡፡

ሐዋ 13፡13-16
**ጳውሎስም ከጓደኞቹ ጋር ከጳፍ ተነስቶ የጵንፍልያ ወደምትሆን ወደ ጴርጌን መጣ፣ ዮሐንስም ከእነርሱ ተለይቶ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ። እነርሱ ግን ከጴርጌን አልፈው የጲስድያ ወደምትሆን ወደ አንፃኪያ ደረሱ። በሰንበትም ቀን ወደ ምኵራብ ገብተው ተቀመጡ ህግና ነብያትም ከተነበቡ በኃላ የምኩራብ አለቆች ወንድሞች ሆይ ህዝብን የሚመከር ቃል እንዳላችሁ ተናገሩ ብለው ላኩባቸው ጳውሎስም በእጁ ጠቅሶ እንዲህ አለ።**

13፡13 **"ጳውሎስም ከጓደኞቹ ጋር"** *የአመራር ስልታቸው ተቀይሮ እንመለከታለን። ከዚህ ምዕራፍ በኃላ የጳውሎስ ስም በመጀመሪያ ተፅፎ እናገኛለን።*

▣ **"ከጳፍ ተነስቶ የጵንፍልያ"** *የጳፋ ከተማ በሮማ አውራጃ በሆነችው በጰንፍልያ የምትገኝ ትልቅ ከተማ ነች። (የዛሬይቱ የደቡብ መካከለኛ ቱርክ) ከተማይቱ ከባህር ዳር የራቀች ነበረች ምክንያቱም ከባህሩ ወደብ ላይ የሚነሳውን ዘረፍ ለመግታት ነው።*

*ጳውሎስ በዚህ ጊዜ ሳይሆን ዘግይቶ በከተማይቱ ወንጌልን ሰብኳል። (ሐዋ. 14፡25) በዚህች ከተማ የነበሩትን ክርስቲያኖች ታሪክ ለማወቅ አዳጋች ሆኖአል ነገር ግን ጳውሎስ በዚህ አካባቢ አልፏል።*

▣ **"ዮሐንስም ከእነርሱ ተለይቶ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ"** *ሉቃስ እና ሌሎችም የአዲስ ኪዳን ፀሐፊዎች ዮሐንስ ወደ ኢየሩሳለም የተመለሰበትን ምክንያት አልፃፍም።*

13፡14 **"የጲስድያ አንፃኪያ"** *ይህ ማለት ከአንፃኪየ ወደ የጲስድያ ያለውን አቅጣጫ ለማመልከት የተፃፈ ሐረግ ነው። እነዚህ በሮማውያን ግዛት በገላትያ የሚገኙ ልዩ ዘሮች ናቸው። ምናልባት የአውሮፖ ዙር ሳይሆኑ አይቀሩም።*

▣ **"በሰንበት ቀን"** *አርብ ማታ ፀሐይ ከጠለቀች ጀምሮ እስከ ቅዳሜ ፀሐይ እስከምትጠልቅ ያለውን ጊዜ ያመለክታል። አይሁዳውያን ቀን የሚቆጥሩት ከማታ እስከማቀጥለው ማታ ነው። (ዘፍ 1)*

▣ **"ተቀመጡ"** *በምኩራብ ተናጋሪ የሆነውን ሰው ለማመልከት የሚያገለግል የተለመደ ቃል ነው። የአይሁድ መምዕራን ተቀምጠው የማስተማር ባህል አላቸው (ማቴ 5፡1፣ ሉቃ4፡20) እንግዶች በምኩራብ ከተገኙ እንድናገር ይፈቀድላቸው ነበር (ቁ.15)።*

13፡15 **"ህግና ነብያት ከተነበቡ በኃላ"** *በኢየሱስ ዘመን የነበረው የምኩራብ ስርዓት የሚያካትታቸው ዝርዝሮች ናቸው፡ በመጀመሪያ የሙሴ ህግ ብቻ ይነበብ ነበር ነገር ግን አንቲዮከስ IV አፒፋኒስ ይህንን ከልክሏል በ16ን ከክ)ል)በፊት። በመቀጠልም አይሁድ ይህንን የነብያትን መፅሐፍ ብቻ በማንበብ ተክተውት ነበር። አሁንም በመቃብያን አመፅ ጊዜ አይሁድ የሙሴና መፅሐፍ እንዲነበብ አድርገዋል (ቁ.27)።*

**ልዩ ርዕስ: የዕብራውያን ህግ**

*የዕብራውያን መፅሐፍ ቅዱስ በሦስት ክፍል የተከፈለ ነው(የእንግዚኛው መፅሐፍ ቅዱስ የግሪኩን ተከተሎ የተፃፈ ነው)*

1. *ቶራ (ፔንታቱክ) ከዘፍ - ዘዳ*
2. *ነብያቶች*
   *ሀ. የቀደሙ ነብያቶች ከኢያሱ - ነገስታት (ከሩት በስተቀር)*
   *ለ. የኃለኞች ነብያቶች ከኢሳያስ - ሚልክያስ (ከዳንኤልና ከሰቆቃ.ኤ በስተቀር)*
3. *የስነ ግጥም መፅሐፍት፡-*
   *ሀ. ከጥበበ መፅሐፍት (ከኢዮብ-ምሳሌ)*
   *ለ. ከግዞት በኃላ የተፃፉት መፅሐፍ (ከዕዝራ-አስቴር)*
   *ሐ. አምስቱ ብራናዎች፡-*
      (1) *መክበብ (በዳስ በዓል የማነበብ)*
      (2) *መክብብ (በዳስ በዓል የሚነበብ)*
      (3) *መኃልየ መሃይል (በፋሲካ የሚነበብ መፅሐፍ)*
      (4) *ሰቆቃው ኤርምያስ (የኢየሩሳሌም መፍረስ ለማስታወስ በ586 ከ)ክ)ል)በፊት)*
      (5) *አስቴር*
   *መ. 1 እና 2 ዜና*
   *ሠ. ዳንኤል*

▣ **"የምኩራብ አለቆች"** *የምኩራብን ህንፃ ማደስ እና የአምልኮውን ስርዓት መቆጣጠር የምኩራብ አለቆች ስራ ነው። (ሉቃ 8፡41.49) በተጨማሪም በምኩራብ የሚያገለግል አገልጋይ የሚያብዙም እነርሱ ነበሩ።*

▣ "ህዝብን የሚመክር ቃል" በምኩራብ አምልኮ ማንም ሰው ህዝብን የሚያንፅ ቃል እንዲናገር ይፈቀድ ነበር፡፡ በመሆኑም ጳወሎስ ይህንን ዕድል ወንጌልን ለመናገር ይጠቀምበት ነበር፡፡

13፡16 "ጳውሎስ ተነሳና" በአይሁድ መምህራን ቆሞ ማስተማር ያልተለመደ ነበር ነገር ግን በግሪኮ ሮማ ባህል ለህዝብ ንግግር የሚያደርግ ማንም ሰው ቆሞ ይናገር ነበር፡፡ በመሆኑም ጳውሎስ ያደረገው ከአይሁድ ባህል በተለየ መንገድ ነበር፡፡

▣ "በእጁ ጠቅሶ" ጳውሎስ የእጁ ምልከታ ፀጥ ለማሰኘት ነው፡፡ ሉቃስ የአይን እማኝነቱን ይጠቅሳል (ሐዋ 12፡17፣ ሐዋ13፡16፣ 19፡33፣ ሐዋ 21፡40)፡፡

---

አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 13፡16-25

የእስራኤል ሰዎችና እግዚአብሔርን የምትፈሩ ሆይ ስሙ፡፡ የዚህ የእስራኤል ህዝብ አምላክ አባቶቻችንን መርጦ በግብፅ ሀገር በእንግድነት ሳሉ ከፍ ከፍ አደረጋቸው ከፍ ባለችውም ክንዱ ከዚያ አወጣቸው፡፡ በበረሃም አርባ አመት ያህል መገባቸው፡፡ በከነዓንም አገር ሰባት አህዛብን አጥፍቶ ምድራቸውን አወረሳቸው ከዚህም በኃላ እስከ ነብዩ እስከ ሳሙኤል ድረስ አራት መቶ ሃምሳ አመት ያህል መሳፍንትን ሰጣቸው፡፡ ከዚያም ወዲያ ንጉስን ያነግስላቸው ዘንድ ለመኑ እግዚአብሔርም ከቢንያም ወገን የሚሆነውን ሰው የቂስን ልጅ ሳኦልን አርባ ዓመት ሰጣቸው፡፡ እርሱንም ከሻረው በኃላ ዳዊትን በእነርሱ ላይ እንዲነግስ አስነሳው ሲመሰክርለትም እንደ ልቤ የሆነ ሰው ፈቃዴን ሁሉ የሚያደርግ የእሰይ ልጅ ዳዊትን አገኘሁ አለ፡፡ ከዚህም ሰው ዘር እግዚአብሔር እንደተስፋው ቃል ለእስራኤል መዳኒትን እርሱም ኢየሱስን አመጣ፡፡ ከመምጣቱ በፊት ዮሐንስ አስቀድሞ ለእስራኤል ህዝብ ሁሉ የንስሃን ጥምቀት ሰብኮ ነበር፡፡ ዮሐንስም ሩጫውን ሲፈፅም ሳለ እኔ ማን እንደሆንኩ ታስባላችሁ እኔስ እርሱን አይደለም ነገር ግን የእግሩን ጫማ እፈታ ዘንድ የማይገባኝ ከእኔ በኃላ ይመጣል ይል ነበር፡፡

---

13፡16b "የእስራኤል ሰዎችና እግዚአብሔርንም የምትፈሩት" እነዚህ ሁለት ዓይነት ሰዎች ናቸው፡፡(1) አይሁዳውያን (2) እግዚአብሔርን የሚፈሩ አይሁድ (ቁ. 26፣10፡2.22.35)፡፡ በዚህ ቁጥር ላይ ያለው ሀሳብ ከእስቲፋኖስ ስብከት ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ (ጠዋት) በአንድ መንገድ ይሁን በሌላ ጳውሎስ በእስቲፋኖስ ስብከት አዎንታዊ ተፅኖ እንዳለበት ከፅሑፉ መረዳት ይቻላል፡፡

13፡17 ጳውሎስ የብሉይ ኪዳን መፅሐፍ ከአብርሃም መጠራት ጀምሮ ይተርካል፡፡ (አብርሃም፣ ይስሐቅ እና ያዕቆብ) እና የግብፅን የባርነት ታሪክ እና የግብፅ ነፃ የሆኑበትን እያስታወሰ ይተርካል፡፡

▣ "ህዝቡን ከፍ ከፍ አደረጋቸው ከፍ ባለችው ክንዱ ከዚያ አወጣቸው" ምሳሌያዊ ንግግር ነው፡፡ (ዘፀ 6፡1.6) በተመሳሳይ መልኩ በቀኝ እጁ በማለት እግዚአብሔርን በሰውኛ ቋንቋ በመናገር ሰዎች እንዲረዱት ፀሐፊዎች ያደርጉ ነበር፡፡ ነገር ግን እንደሚታወቀው እግዚአብሔር ዘላለማዊ፣ መንፈስ፣ የስጋ አካል የሌለው መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ በእርግጥ እንደዚህ ዓይነት ተምሳሌያዊ ንግግር በቀጥታ ከተወሰዱ የተሳሳተ ትርጉም ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ መፅሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ከሰው የተለየ፣ በጊዜ ያልተገደበ በመሆኑ ሰው ሊረዳው በሚችለው ምሳሌና ተምሳሌት እግዚአብሔርን ለሰው ሁሉ ለመግለፅ ይጥራል፡፡

13፡18 "በበረሃ አርባ ዓመት ያህል መገባቸው ከዛዳግም 1፡31 የተወሰደ ነው፡፡ ዓረፍተ ነገሩን እንደ ተንከባካቢ መጋቢያቸው በማለት ተከታዩ ትርጉም ሰቶታል (Mss A.C) በአጠቃላይ ሃሳቡ የሚያንፀባርቀው የዘኋልቁ እና የዘፀአትን መፅሐፍቶች ነው፡፡

በእስራኤል አርባ ቁጥር የተለመደ ቁጥር ነው ነገር ግን ከሲና እስከ ስጥና የወሰደባቸው አመታት ሰላሳ ስምንት ዓመታት ቢሆኑም በሲና ለሁለት ዓመት ተቀምጠው ነበር፡፡

13፡19 "ሰባቱን የአህዛብ ነገስታት አጥፍቶ" ፍልስጥኤማውያን በብዙ መንገድ ሊገለፁ ይችላሉ፡-

1. የጋራ ስያሜአቸው ከነአናውያን ሊባሉ ይችላሉ፡፡ (ረባዳ ስፍራ ያሉት ዘፍ. 10፡18.29፣ መሳ1፡1) ወይም አሞራውያን (ተራራማ ስፍራ ያሉት ዘፍ15፡16)
2. ሁለት ነገስታቶችን ይወክላሉ (ከነአናውያን እና ፈርዛውያን ዘፍ.13፡7፣ 7፡34፡3 መሳ.1፡4-5)
3. ሦስት ነገስታቶችን ይወክላሉ (ዘፀ. 23፡28)
4. አምስት ነገስታቶችን ይወክላሉ (ዘፀ. 3፡17፣ ዘኃ 23፡29)
5. ስድስት ነገስታቶችን ይወክላሉ (ዘፀ 3፡8.7 33፡2፣ 34፡11፣ ዘዳ 20፡17፣ ኢሳ20፡17፣ ኢሳ 9፡1፡ 12፡8)
6. ሰባት ነገስታቶችን ይወክላሉ (ዘዳ 7፡1፣ ኢያ 3፡10፣ 24፡11
7. አስር ነገስታቶችን ይወክላሉ፡፡ (ዘፍ 15፡19-21)

▣ "አወረሳቸው" ከሦስት ጥምር ቃል የተሰራ ቃል ነው፡፡ ካታተኪሮስ ተኒሞ በግሪኩ ፅሑፍ በአዲስ ኪዳን ብቻ ተፅፎ ይገኛል፡፡ (በሌላ አውድ ዳግም ካታ ተሊሲሮስ ዲዲዮሚ) ትርጉሙም እጣን በመጣል የመሬትን ርዕስት መከፋፈል ማለት ነው (ኢያ 13-19)

▣ "አራት መቶ ሃሳም ዓመታት" የእነዚህ ዓመታት ቁጥር የሚከተሉት ተደምሮ የተገኘ ውጤት ነው፡-
1.400 ዓመት በግብፅ ባርነት የነበሩበት ዓመታት ናቸው፡፡ (ዘፍ 15፡13)

2.40 ዓመታት በምድረ በዳ ጉዞ ያሳለፍበት ነው። (ዘፀ 16:35፣ ዘኍ 14:33)

3.ከ7-10 ዓመታት የድል ዓመታት ነበሩ። (ኢ.ያ 1417.10)

የKJV ትርጉም ወደ ቁጥር ሃያ ድረስ በማድረስ በዚህ ላይ የመሳፍንትን ታሪክ ሲጨመር ያስባል ይመስላል። (Josephus, Antiq 8:3:1) ነገር ግን በጥንቱም በአዲሱም የግሪክ ፁሑፍ ላይ እንዲሁም በNASB ፈፅሞ አልተፃፈም።

13:20 በዚህ ቁጥር ላይ የሚገኙት መሳፍንት 1ሳሙ 7 ያሉትን የሚያመሳክሩ ናቸው።

13:21 ይህም 1 ሳሙ 8-10 ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው።

▣ **"ለአርባ አመታት"** በዚህ ምንባብ የተጠቀሰው አርባ በብሉይ ኪዳን አልተጠቀሰም ነገር ግን ምንናልባት የግሪኩ ፅሑፍ ከ1ሳሙ 13:1 ጋር ካላገናኘው በስተቀር። በግሪኩ ፅሑፍ ላይ አርባ ቁጥር ተፅፎ አይገኝም። በመሆኑም አርባ ቁጥር የአይሁድ መምህራን የጨመሩት ነው።

13:22 **"እንደልቤ የሆነውን ሰው ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርገ የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ አለ"** ከ1ሳሙ 13:14 እና ከመዝ 89:20 የተወሰደ ጥቅስ ነው። ጳውሎስ እስቲፋኖስ በተጠቀመበት የመስበክ ስልክ መሠረት በተመሳሳይ እያደረገ ነው። (ሐዋ7) ዳዊት ሐጢያተሃ ሳለ እንደ ልቤ ተብሏል። (መዝ 32.51፣ 2ሳሙ 11)

ይህ ጥቀስ የሚያመክተው፡-

1. የአይሁድ መምህራን እንዲህ አይነት ያልተለመዱ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን ይጠቀሙ እንደነበር አመላካች ነው።
2. በተጨማሪም ጥቅስ ከብሉይ ኪዳን መጥቀስ የክርስቲያኖች ልማድ መሆን ጀምሮ ጳውሎስ ከቆዩ የክርስቲያኖች መዝሙር እና ሌሎች ፅሑፎ ይጠቅስ ነበር።
3. ለሐዋርያው ጳውሎስ ይህ ጥቅስ እንደ እንግዳ ነው። ነገር ግን ሉቃ ከጳውሎስ ስብከት በማጠቃለያ መልክ ፅፎታል።

▣

| | |
|---|---|
| NIB | *"ፈቃዴን የሚያደርግ"* |
| NRSV, TEV | *"ምኞቴን ሁሉ የሚፈፅም"* |
| NKJV | *"ያዘዝሁትን ሁሉ ፈቃዴን የሚያደርግ"* |
| NASB | *"ፈቃዴን ሁሉ የሚያከናውን"* |

ይህ ቁጥር ከብሉይ ኪዳን ጥምር ቃል ሆኖ የተጠቀሰ ነው። ይህ ዓረፍተ ነገር በብሉይ ኪዳን አልተፃፈም። በብሉይ ኪዳን ሳኦል ባለመታዘዝ ተንቋል ዳዊትም እግዚአብሔርን ያልተዘዘበት ጉዳይ ነበረው። እግዚአብሔር ታንሽና ደካማ የሆነውን ይመርጣል።

13:23 ይህ ቁጥር ከሐዋ 7:52 ጋር ተመሳሳይ ነው። የብሉይ ኪዳንን ቃል ኪዳኖች የሚያስታውስ ነው።

1. ከሴቲቱ ዘር አዳኝ ይወጣል፣ ዘፍ 3:15።
2. ከይሁዳ ገዢ ይነሳል፣ ዘፍ 49:10።
3. እንደ ሙሴ ያለ ይነሣል፣ ዘዳ 18:15,18።
4. ከዳዊት ቤት መሪ ይወጣል፣ 2ሳሙ 7፣ መዝ 132:11፡ ኢሳ 11:1,10፣ ማቴ 1:1።
5. መከራ የሚቀበል መሪ ይነሳል፣ ኢሳ 52:13-53:12።
6. አዳይ ይመጣል፣ ሉቃ 2:11፣ ማቴ1:21፣ዮሐ 1:29፡ 4:42 ሐዋ 5:31።

ሉቃስ ተራ ቁጥር አራትን ተጠቅሞበታል። (ሉቃ 1:32፣69:2:4:3:3) ሐዋ 2:29-31፣2:29-31፣ 13:22-23) መሲሁ የእሰይ ዘር ነው። (ኢሳ 9:7፣ 11:11:1.10፣16:5)

13:24 የመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት እና መልእክት በዝርዝረ ተፅፏል። (ማርቆ 1:1-8 ማቴ 3:1-11፣ ሉቃ 3:2-17፣ ዮሐ 1:6-8.19-28) ዮሐንስ በማቴ 3:1፡ 4:5-6 የተነገረውን ትንቢት ፈፅሞታል። ዮሐንስ የንስሃ ይሰብክ ልክ እንደ ኢየሱስ ይሰብክ ነበር (ማቴ 4:17፣ ማርቆ 1:14-15)።

ነገር ግን ዮሐንስ ከእርሱ የበለጠ እንደሚመጣ አበክሮ ይናገር ነበር (ማቴ 3:11፣ ማርቂ 1:7፣ ሉቃ 3:16 ዮሐ 1:27.30፣ ሐዋ 13:25)።

13:25 **"ዮሐንስ ተልዕኮውን በማጠናቀቅ ሳለ"** እግዚአብሔር ለዮሐንስ የተለየ ተልዕኮ ሰጥቶት ነበር። የዮሐንስ አግልሎት በ18 ወራት ውስ ብቻ ነበር የተከናወነው። ግን ለአንድ አመት ተኩል ብቻ ነበር በመንፈስ ቅዱስ ሃይል ተሞልቶ ለመሲሁ መንገዱን ያዘጋጅ የነበረው።

ጳውሎስ በገማልያ እግር ስር እና በምኩራብ የብሉይ ኪዳን መፅሐፍ በጥንቃቄ የተማረ ሰው ነበር። መጀመሪያ ጳውሎስ ወንጌልን የሰማው ከእስቲፋኖስ ነበር። ከዚያም ከሚያሳድዳቸው ክርስቲያኖች በመቀጠልም ከራሱ ከኢየሱስ በተጨማሪም በአረብ ምድር በዳ በነበረ ጊዜ ከኢየሱስ በፈፃሚውም ከአማኞች ጋር ህብረት ማድረግ ጀመረ። ስለዚህ በሚናገርበት ርዕስ ሁሉ ኢየሱስን የማከለ ንግግር ያደርግ ነበር። የህይወቱ መቀየር ምክንያቱ ወንጌል መሆኑን ያውጅ ነበር።

ሐዋ 13፡26-41
*እናንተ ወንድሞቻችን የአብርሃም ዘር ልጆች ከእናንተ መካከልም እግዚብሔርን የምትፈሩ ሆይ ለእህንተ የዚህ መዳን ቃል ተላከ፡፡ በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎችና አለቆቻችሁ እነርሱንና በየሰንበቱ የሚነበቡትን ነብያትን፣ ድምፃቸውን ስላላወቁ በፍርዳቸውን ፈፅመዋልና ለሞትም የሚያደርስ ምክንያት አንድስከ ባይገኝበት ይገድለው ዘንድ ጲላጦስን ለመኑት ስለእነርሱ የተፃፈው ሁሉ በፈፀመ ጊዜ ከእንጨት አውርደው በመቃብር አኖሩት እግዚአብሔር ግን ከሙታን አስነሳው በዚህም ዘንድ ምስክሮቹ ለሆኑት ከእነርሱ ጋር ከገሊላ ወደ ኢየሩሳሌም ለወጡት ብዙ ቀን ታያቸው እኛም ለአባቶች የተሰጠውን ተስፋ የምስራች ለእናንተ እንሰብካለን፡፡ ይህንን ተስፋ እግዚአብሔር በሁለተኛ መዝሙር ደግሞ አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ ተብሎ እንደ ተፃፈ ኢየሱስን አንስቶ ለእኛ ለልጆቻቸው ፈፅሞአልና፡፡ እንደገናም ወደ መበስበስ እንዳይመለስ ከሙታን እንዳስነሳው እንዲህ የታመነውን የዳዊትን ቅዱስ ተስፋ እሰጣችኃለሁ ብሎአል፡፡ ደግሞ በሌላ ስፍራ ቅዱስህን መስበስን ያይ ዘንድ አትሰጠውም ይላልና፡፡ ዳዊትም የእግዚአብሔረን ሃሳብ ከገላገለ በኃላ አንቀላፋ ከአባቶቹም ጋር ተጨምሮ መበስበስን አየ ይህ እግዚአብሔር ያስነሳው ግን መበስበስን ያይ ዘንድ አትሰጠውም ይላልና፡፡ ዳዊትም የእግዚአብሔርን ሃሳብ ካገለገለ ግን በኃላ አንቀላፋ ከአባቶቹም ጋር ተጨምሮ መበሰበስን አየ ይህ እግዚብሔር ያስነሳው ግን መበስበስን አለየም እንግዲህ ወንድሞች ሆይ በእርሱ በኩል የሃጢያት ስርየት እንዲነገርላችሁ በሙሴም ህግ ትፀድቁበት ዘንድ ከማይቻላችሁ ያመነ ሁሉ በእርሱ እንዲፀድቅ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን፡፡ እንግዲህ፡- እናንተ የምትንቁ እዩ ተደነቁም፣ ጥፍም አንድ እንክ ቢተረክላችሁ፣ የማታምኑትን ስራ በዘመናችሁ እኔ እሠራለሁ፡፡ ተብሎ በነቢያት የተነገረው እንዳይደርስባችሁ ተጠንቀቁ፡፡*

13፡26 **"የአብርሃም ዘር ልጆች ከእናንተ መካከል እግዚአብሔርን የምትፈሩ"** አይሁድን እና እግዚአብሔርን የሚፈሩትን አህዛብን የሚያመላክት ዐረፍተ ነገር ነው፡፡

▣ **"የመዳን ቃል"** በመሲሁ በኩል የሚመጣውን የእግዚአብሔርን ማዳን ለመግለፅ ነው፡፡ (ዘፍ 3፡15) አህዛበንም ያጠቃልላል፡፡ (ዘፍ 12፡5፣ ዘፀ19፡5-6 እና ሐዋ 28፡28 እና 12፡46)

13፡27 በኢየሩሳሌም የሚኖሩ አይሁድ በየጊዜው መፅሐፍትን እያነበቡ ስለ መንፈሳዊ ነገር ያለማወቃቸው አሳዛኝ ነው፡፡ የነብያትን መልእክተ አላስተዋሉም (መዝ. 22፡ ኢሳ 53፣ ዘካ. ሚል) ትንቢቶችን ዋጋ አልሰጡም (ኢሳያስ እና ዮናስ) ኢየሱስ ወደ ገዛ ወገኖቹ መጣ ነገር ግን የገዛ ወገኖቹ አልተቀበሉትም (ዮሐ 1፡11-12)፡፡

13፡28 በሐዋርያት ስራ መፅሐፍ በኢየሩሳሌም ያሉት አይሁድ መንፈሳዊ ኃላፊነት እንዳለባቸው በተደጋጋሚ ትኩረት ሰቶት ሉቃስ ፅፎታል (ሐዋ 2፡23-36 ሐዋ 3፡13-15፣ 4፡10 5፡30 ሐዋ7፡82፣10፡39፣ 13፡27-28)፡፡

13፡29 **"በፈፀመ... አውርደው"** የተለያዩ ቡድኖችን ያመለክተናል፡፡ የመጀመሪያዎቹ በጲላጦስ ፊት የነበረሩት የአይሁድ መሪዎች እነርሱ የሰቀሉት ሲሆኑ የሁለተኞች ከመስቀል አውርደው በክብር የቀበሩት ናቸው፡፡ እነዚህ ታማኝ አይሁዳውያን ናቸው (ሐዋ 19፡38-42)፡፡

▣ **"ስለ እርሱ የተፃፈው ሁሉ"** የኢየሱስ ህይወት የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች የተፈፀመበት ህይወት ነው፡፡ መፅሐፍ ቅዱስ እውነተኛ እና በመንፈስ የተፃፈ መሆኑ አንዱ ማረጋገጫ የመሲሁ የኢየሱስ በተባለው ዘመን መገለጡ ነው፡፡ (ሉቃ 22፡22፣ሐዋ3፡18፣ ሐዋ 4፡28፣ 10፡43)

ስለ ኢየሱስ ህይወት የተፃፉት ትንቢቶች የምንላቸው ሁሉ በምሳሌ የተፃፉ ናቸው፡፡ በእስራኤል የተከሰተው በኢየሱስም ተከስቶ እንመለከታለን፡፡ (ሆሴ 11፡1) የተፃፈት ትንቢቶች የኢየሱስን የምድር ኑሮውን እና አገልግሎቱን በቀጥታ የሚያሳዩ ናቸው (መዝ 22 ኢሳ.53)፡፡ የብሉይ ኪዳን መፅሐፍት የኢየሱስን ህይወት በሩቅ በማሳየት እን ደጥላ አገልግለዋል፡፡

▣ **"መስቀሉ"** ሐዋ 5፡30 እና 10፡29 ይመልከቱ፡፡

13፡30.33.34.37 **"እግዚአብሔር ግን ከሙታን አስነሳው"** የአዲስ ኪዳን መፅሐፍ ስላሴ በትንሳኤው ስራ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ፡፡

1. መንፈስ ቅዱስ (ሮሜ 8፡1)
2. ልጁ (ዮሐ2፡19-22፣ 10፡17-18)
3. አባት (ሐዋ2፡24.32. ሐዋ3፡15.26፣ሐ፣ 4፡10 ሐዋ 5፡30 ሮሜ 6፡4.9፣1ቆሮ 6፡14፣2ቆሮ 4፡14፣ ገላ1፡1)

እንግዲህ የአባት ምስክርነት እርሱም ልጁ እውነተኛ መሆኑን የገለፀበት መንገድ ትንሳኤው ነው፡፡ በመሆኑም የሐዋርያት ስራ መፅሐፍ ዋና ትምህርት ያተኮረው በዚህ ርዕስ ጉዳይ ነው፡፡ ልዩ ርዕስ 2፡14 ያለውን ይመልከቱ፡፡

13፡31 **"ብዙ ቀን"** ሐዋ 1፡3 አርባ ቀናት በማለት ብዙ ቀንን ይተረጉማል ነገር ግን ይህ አርባ ዓመት አይሁድ ብዙ ቀናትን ለመናገር የሚጠቀምበት ነው፡፡

▣ **"ታያቸው"** ቀጥሎ ያለውን ልዩ ርዕስ ያለውን ይመልከቱ፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ ኢየሱስ ከትንሳኤው በኋላ**

ኢየሱስ ትንሳኤውን ለሌሎች ለማረጋገጥ ለብዙዎች ታይቷል፡፡

1. በመቃብር ቦታ ለነበሩ ሴቶች ታይቷል፣ ማቴ 28፡9
2. ለአስራ አንዱ ደቀ-መዛሙርት፣ ማቴ 28፡16
3. ለስምኦን ታይቷል፣ ሉቃ 24፡34
4. ለሁለት ወንዶች፣ ሉቃ 24፡15
5. ለደቀመዛሙርት፣ ሉቃ 24፡36
6. ለመግደላዊት ማርያም፣ ዮሐ 20፡15
7. ለአስሩ ደቀ መዛሙርት፣ ዮሐ 20፡17
8. ለአስራ አንዱ ደቀመዛሙርት፣ ዮሐ 20፡26
9. ለሰባቱ ደቀመዛሙርት፣ ዮሐ 21፡1
10. ለኬፋ፣ (ጴጥሮስ) 1ቆሮ 15፡5
11. ለአስራ አንዱ ሐዋርያት፣ 1ቆሮ 15፡5
12. ለአምስት መቶ ወንድሞች፣ 1ቆሮ 15፡6፣ ማቴ 28፡16-17
13. ለያዕቆብ፣ (ለወንድሙ) 1ቆሮ 15፡7
14. ለሁሉም ሐዋርያት፣ 1ቆሮ 15፡7
15. ለጳውሎስ፣ 1ቆሮ 15፡8 (ሐዋ 9)

እነዚህ ነገሮች ተመሳሳይ አቀራረቦችን እንደሚያመለክቱ የታወቀ ነው፡፡ ኢየሱስ እርሱ ሕያው እንደሆነ ያውቁ ዘንድ ይፈልጋል፡፡

**13፡32 "እኛም ለአባቶች የተሰጠውን ተስፋ"** እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን የተስፋ ቃል የሚያስታውስ ነው፡፡ (ዘፍ 12፡1-3፣ ሮሜ4) የአብርሃም የተስፋ ቃል ለሌሎቹም አባቶች በተመሳሳይ መንገድ ተነግሯል፡፡ (ኢሳ 44፡3፣ ኢሳ 54፡13፣ ኢዮ 2፡32) የብሉይ ኪዳን ትኩረት መሬት ላይ ሲሆን የአዲስ ኪዳን ደግሞ ዘር ላይ ነው፡፡ ጳውሎስ በሮሜ 1፡2-3 ጠቅሶታል፡፡

**13፡33** ይህ ጥቅስ ከመዝ 2፡7 የተወሰደ ለመሲሁ የተዘመረ የውጊያ እና የድል ዝማሬ ነው፡፡ ኢየሱስ በሰው እና በሰይጣን ክፉ ተቃውሞ ተገድሎ ነበር ነገር ግን እግዚአብሔር ከሙታን በሃይል አስነስቶታል (ሮሜ 1፡4)፡፡

በዚህ ጥቅስ እና በሮሜ 2፡7 ላይ ባለው ሂሳብ ሐሰተኛ አስተማሪዎች የራሳቸውን ትርጉም በመስጠት ኢየሱስ በትንሳኤ ቀን የእግዚብሔር ልጅ መሆን እንደጀመረ ያስተምሩ ነበር፡፡ በእርግጥ ኢየሱስ በመታዘዙ እንደከበረ ቢገለፅም ይህ ማለት ከመወለዱ በፊት ክብር አልነበረውም ማለት አይደለም (ዮሐ 1፡1-5,9-18፣ ፊሊ.2፡6-11፣ ቆላ1፡13-18፣ ዕብ1፡2-3)፡፡

ይህ 'ተነስ' (*anistimi*) የሚለውን ቃል በሐዋ 3፡26 ተጠቅሞበታል፡፡ እግዚአብሔር 'አገልጋዩን አስነሳ' በሚለው ስፍራም በሐዋ 3፡22፣ እግዚአብሔር ነቢያቱን ያስነሳል (7፡37፣ ዘዳ 18፡19) ይህም ከሙታን መነሣት ከሚለው የተለየ ነው (ቁጥር 30,34,37)፡፡ ኢየሱስ ከመሞቱ በፊት ነው "የተነሣው"!

**13፡34 "ወደ መበስበስ እንዳይመለስ"** ስለ ኢየሱስ ሞትና ትንሳኤ የሚናገር ነው፡፡ ኢየሱስ ከፍጥረት የመጀመሪያ ሆኖአል፡፡ ከሞት በመነሳት (ተነስቶ በሚሞት አካል አይደለም) 1ቆሮ 15፡20 በመፅሐፍ ቅዱስ ብዙዎች ከሞት ተነስተዋል፡፡ ነገር ግን ዳግመኛ ሞተዋል፡፡ ሄኖክ እና ኤልያስ ወደ ሰማይ ተነጥቀዋል እንጂ ከሙታን አልተነሱም፡፡

▣ **"የታመነውን የዳዊትን ቅዱስ ተስፋ እሰጣችኃለሁ"** በግሪኩ ፅሑፍ ከኢሳ 55፡3 የተጠቀሰ ነው፡፡ በዚህ ክፍል በውስንነት ሳይሆን ለብዙ ቁጥር በሚሆን መንገድ ግሶቹ ተፅፈዋል፡፡ ይህም ማለት ከእግዚአብሔር ወደ ዳዊት ከዚያም ወደ ኢየሱስ በመቀጠልም ወደ ተከታዮቹ በመተላለፍ በረከቱ ቀጣይነት እንዳለው ማረጋገጫ ነው፡፡ በመሆኑም የብሉይ ኪዳን መፅሐፍት እኛ ትኩረት እንደተሰጠንም ያስገነዝበናል፡፡ (ኢሳ 55፡4-5) የሚከተለውን መፅሐፍ ያንብቡ (Zondelvan, 1976, P.890)፡፡

የዳዊት በረከት እና ቃል ኪዳን የአህዛብ ሁሉ ቃል ኪዳን ሆኖአል፡፡

**13፡35-37** በሐዋ 2፡24-34፣መዝ16 ተመሳሳዩን ተመልከቱ ይህ የስብከት አቀራረብ የጥንቲቱ ቤተክርስቲያን ልማድ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ነገር ግን የኢየሱስ መነሳት እና የዳዊት ሞት መበስበስ የሐዋርያት ስራ ዋና አንኳር መልእክት መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

**13፡38** ጳውሎስ የብሉይ ኪዳንን መፅሐፍት ጴጥሮስ እንደጠቀሶ ይጠቅስ ነበር፡፡ (ሐዋ 2 እና ሐዋ7) ይህንን የሚያደርግበት ምክንያት በምኩራብ የነበሩትን ሰዎች በወንጌል ለመድረስ በማሰብ ነው፡፡

ጳውሎስ ንስሃ ለሚገባ እና ኢየሱስን ለሚያምን ማንም ሰው ሙሉ ምህረት ከእግዚብሔር እንደሚቀበል ይናገር ነበር፡፡ ነገር ግን በአይሁዳውያን ሀይማኖት ይህ ፈፅሞ የተከለከለ ነው፡፡

**13፡39 "በእርሱ በኩል"** እግዚአብሔር ሰውን ሁሉ ይወዳል በመሆኑም ሰው ሁሉ ለዚህ ፍቅር ምላሽ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡ (ሐዋ 10፡43፣ ኢሳ 42፡1 ሕዝ18፡32፣ ኢዩ 2፡28.32፣ዮሐ 3፡16፣ ሮሜ3፡22,29,30፣ 1ጢሞ 2፡4)

▣
NASB, NKJV　　"ያመነ ሁሉ" ሐዋ 3፡16 ይመልከቱ
NRSV　　"ከሁሉ ነገር ነፃ ነው"
TEV　　"ከነዚያ ሃጢያቶች ነፃ ነው"
NJB　　"ከሃጢያቶች ፃድቅ ነው"

ይሄ ቃል በቃል 'ፀድቋል' በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ባገኘነው ጽድቅ በእግዚአብሔር ፊት መቆም መብቃታችንን የሚያሳይ ነው (2ቆሮ 5፡21)፡፡ በእብራይስጡ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር የግንባታ ምሳል ተጠቅሞ በጻድቅ መፍረዱንና መዳኙቱን የሚያሳይ ሃሳብ አለው፡፡

▣ **"ሙሴም ህግ ትፀድቁበት ዘንድ ከማይቻላችሁ"** ይህ የሐዋርያው ጳውሎስ ስነመለኮት ዋና ሃሳብ ነው (ሮሜ 3፡21-30) የሙሴ ህግ ወደ ክርስቶስ የማወስደን እና መረዳትነ የሚሰጠን ሞግዚት ነው(ገላ 3፡23-29) የብሉይ ኪዳን ህግ የድነት ማግኛ ዋና መሳሪያ አይደለም (ሮሜ 3፡9-18.23፣ ገላ3፡22) ይህም ሞትን እርግማንን የሚያስከትል ህግ ነው፡፡ (ገላ 3፡13፣ ቆላ 2፡14)

13፡40-41 ጳውሎስ አድማጮቹ ኢየሱስ እርሱ መሲህ እና የሃጢያትን ስርየት መቀበያ መንገድ መሆኑን ገብቷቸው ምላሽ እንዲሰጡ ያደርግ ነበር፡፡ (ዮሐ14፡6፣ ሐዋ4፡12፣ 1ጢሞ 2፡5)
ከግሪኩ ፅሑፍ ከዕብ 1፡5 ላይ የተጠቀሰ ነው፡፡ ጳውሎስም ከዕብ 2፡4 ጠቅሶት እናያለን፡፡ (ሮሜ 1፡17፣ ገላ3፡11) ጳውሎስ ይሰብክ የነበረው ለውሳኔ በሚያደርስ መልኩ ነው፡፡ እውቀተ ብቻ ሳይሆን ኢየሱስን ለማመነ የግል ውሳኔ የሚጠይቅ ነው፡፡ ኢየሱስን ማመንና ንስሃ ክርስቶስን ለመምሰል በየቀኑ ከሚደረግ ኑሮ ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት፡፡ (ቁ. 41 ይመልከቱ)

> አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 13፡42-43
> **በወጡም ጊዜ ይህን ነገር በሚወጣው ሰንበት ይነግሩአቸው ዘንድ ለመኑአቸው፡፡ ጉባኤውም ከተፈታ በኃላ ከአይሁድና ወደ ይሁዲነት ገብተው ከሚያመልኩ ብዙዎች ጳውሎስንና በርናባስን ተከተሉአቸው እነርሱም ሲነግሩአቸው በእግዚአብሔር ፀጋ ፀንተው እንዲኖሩ አስረዷቸው፡፡**

13፡42 ይህ የሚያሳየው የመንፈስን ሃይል ነው፡፡ (1) በጳውሎስ ስብከት የመንፈስ ሃይል ይስተዋላል፡፡ (2) ሰዎችን ወደ እግዚብሔር ይቅርተ የማምጣት ሂደት በመንፈስ ሃይል የሚደረግ ነው፡፡

13፡43
NASB　　**"እግዚአብሔር የሚፈሩ አህዛብ"**
NKJV　　**"የተሰጡ አህዛብ"**
NRSV　　**"ወደ ይሁዲነት የተለወጡ የተሰጡ"**
TEV　　**"ወደ ይሁዲነት የተለወጡ አህዛብ"**
NJB　　**"ወደ ራሳቸው የሰጡ የተለወጡ"**

ይህ ሐረግ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ የሚፈሩን አህዛቦችን ይመለከታል፡፡ (ቁ. 16.26) (ሐዋ 10፡22.35) ቁ.43 አይሁድ የሆኑ አህዛቦችን ይጠቅሳል፡፡ አይሁድ ለመሆን የሚከተሉትን አሟልተዋል፡-

1. በምስክሮች ፊት ጥምቀትን ወስደዋል፡፡
2. ወንዶቻቸው ተገርዘዋል፡፡
3. በኢየሩሳሌም ወዳለው መቅደስ መስዋታቸውን ወስደዋል፡፡ በአዲስ ኪዳን አይሁድ ሆነው እግዚብሔርን እንደነበሩ ጥቂት ማስረጃ አለ (ማቴ 23፡15፣ ሐዋ2፡11፣ 6፡5፣ሐዋ 13፡43)፡፡

▣ **"በእግዚአብሔር ፀጋ ፀንተው እንዲኖሩ አስረዷቸው"** በዚህ ዓውድ ያለውን ይህን ዐረፍተ ነገር ትርጉሙን ለመስጠተ አስቸጋሪ ነው፡፡ (1) በዚህ ክፍል የሚገኙት አድራጮች ለወንጌል አዎንታዊ ምላሽ የሰጡ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ (2) ለብሉይ ኪዳን መፅሐፍት ታማኝ የነበሩ አሁንም የጳውሎስን ስብከት ለመስማት ፈቃደኞች ሆነዋል ማለት ነው (ቁ.44)፡፡

> አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 13፡44-47
> **በወጡም ጊዜ ይህን ነገር በሚወጣው ሰንበት ይነግሩአቸው ዘንድ ለመኑአቸው፡፡ ጉባኤውም ከተፈታ በኃላ ከአይሁድና ወደ ይሁዲነት ገብተው ከሚያመልኩ ብዙዎች ጳውሎስንና በርናባስን ተከተሉአቸው እነርሱም ሲነግሩአቸው በእግዚአብሔር ፀጋ ፀንተው እንዲኖሩ አስረዷቸው፡፡ በሁለተኛውም ሰንበት ከጥቂቶቹ በቀር የከተማው ሰው ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ይሰሙ ዘንድ ተሰበሰቡ፡፡ አይሁድም ብዙ ህዝብ ባዩ ጊዜ ቅናት ሞላባቸው እየተሳደቡም ጳውሎስ የተናገረውን ቃል ተቃወሙ፡፡ ጳውሎስና በርናባስም ገልጠው የእግዚአብሔርን ቃል አሰቀድሞ ለእናንተ ይነገር ዘንድ ተሰበሰቡ፡፡ አይሁድም ብዘ ህዝብ ባዩ ጊዜ ቅናት ሞላባዠው እየተሳደቡም ጳውሎስ የተናገረውን ቃል ተቃወሙ፡፡ ጳውሎስና በርናባስም ገልጠው፣ የእግዚአብሔርን ቃል አስቀድሞ ለእናንተ ይነገር ዘንድ ያስፈልጋል፡፡ ከገፋችሁትና የዘላለም ህይወት እንዳይገባችሁ በራሳችሁ ከፈረዳችሁ ግን ወደ አህዛብ ዘወር እንላለን፡፡**

13፡44 በፀሐፊው ተጋኖ የተፃፈ ነው፡ በእርግጥ እያንዳንዱ የከተማው ነዋሪ ተገኝቷል ለማለት አያስደፍርም፡፡

13፡45 **"አይሁድም ብዙ ህዝብ ባዩ ጊዜ ቅንዓት ሞላባቸው"** አይሁድን ያስቀናው የህዝቡ መብዛተ ወይስ የአህዛብ መብዛት በዚህ ዓውድ ይህንን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ በኢየሩሳለም እና ተበትነውም ያሉ አይሁድ ቀናተኞች ናቸው (ማቴ. 27፡18፣ ማርቆ 15፡10፣ ሐዋ 17፡5)፡፡

ጳውሎስ በሮሜ መፅሐፍ ውስጥ የአይሁድን አለማመን እና የስነመለኮት ስህተታቸውን በዝርዝር ፅፎታል፡፡ (ሮሜ 9፡11) በመሆኑም እግዚአብሔር እስራኤልን ለጥቂት በማሳወር አህዛብ እንዲድኑ አድርጓል፡፡ እግዚአብሔር አህዛብን በማዳን እስራኤልን በማስቀናት ለወንጌል ምላሽ እንዲሰጡ አድርጓል አለው ግን ሁለቱም በወንጌል አንድ እንዲሆኑ ነው፡፡ ነገር ግን ጥያቄ ይህ መቼ ይሆናል (ዘካ 2፡10) ይህ ጥቅስ የቀደመችውን ቤተክርስቲያን ወይም የወደፊቱን የሚያሳይ ሊሆን ይችላል፡፡ (ሮሜ 10፡19፣ ሮሜ 11፡11.14)

▣ **"ቅንዓት ሞላባቸው"** ሐዋ 3፡10 ይመልከቱ፡፡

▣ **"እየተሳደቡም"** እነዚህ አይሁዳውያን ባህላቸውን ለመጠበቅ ጳውሎስን በመናቀቅ እና በመሳደብ ሃጢያትን እየሰሩ መሆናቸውን አልተገነዘቡም፡፡ በአይሁዳውየን እና በክርስትና መሃከል ልዩነት ነበር፡፡ በመሆኑም መሃል ሰፋሪ መሆን አይቻልም ነበር፡፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔር እውነት ያለው ከሁለት አንዱ ጋር ነበርና!

13፡46 **"ገልጠው"** በመንፈስ የመሞላት አንዱ ምልክተ በድፍረት ነገሮችን መናገር ነው፡፡

▣ **"እግዚአብሔር ቃል አስቀድሞ ለእናንተ ይናገር ዘንድ ያስፈልጋል"** በመጀመሪያ ምዕተ ዓመት የነበሩ ሚሲዮናውያን አስቀድመው ወንጌል ለአይሁዳውያን የመናገር ዕቅድ ነበራቸው፡፡ (ሮሜ 9-11) ነገር ግን እግዚአብሔር አህዛቦችንም ወደ ወንጌል ጠርቷቸዋል፡፡ በምኩራብ በየለቱ የሚተገ የብሉይ ኪዳንን መፅሐፍት ቢያነቡም ትንቢቶቹን አላስተዋሉአቸውም ነበር፡፡ የሐዋርያት ስራ የሚተርከው የትንቢቶቹን ፍፃሜ ነው፡፡ (ሐዋ 3፡26፣9፡20፣ 13፡5.14 ሐዋ16፡13 ሐዋ17፡2)

▣ **"ከገፋችሁት"** በክሪኩ ፅሑፍ በጠንካራ ግስ በርካታ ጊዜ ተፅፎ ይገኛል፡፡ ትርጉሙም አለመቀበል ወይም ማሽቀንጠር የሚል ጠንካራ ትርጉም ይሰጣል፡፡ (ሐዋ 7፡39) (ሮሜ 11፡1-2) እግዚአበሔር ህዝቡን አልናቃቸውም ነገር ግን ህዝቡ የእግዚአብሔርን ልጅ ደህንነትን እና መገለጡን ንቀዋል፡፡

▣ **"የዘላለም ህይወት እንዳይገባችሁ በራሳችሁ ከፈረዳችሁ"** በሐዋርያት ስለ መጨረሻው የሰው ዕድል መገንዘብ አስቸጋሪ የሚሆነው በግለሰቡ ምላሽ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ነው፡፡ እግዚአብሔር ወደ እርሱ ያላመጣው ማንም ወደ እርሱ መምት አይችልም፡፡ (ዮሐ 6፡44.65) የጳውሎስን ወንጌል መቃወማቸው እነሱ እነማን እንደሆኑ ያሳየ ነበር፡፡ (ዮሐ 3፡17-21) እግዚአብሔር ያዘጋጀውን የመዳን መንገድ ኢየሱስን ካልተቀበሉ አይድኑም በመሆኑም በማንም ላይ ሰበብ ማድረግ አይችሉም፡፡

▣ **"ወደ አህዛብ ዘወር እንላለን"** በወንጌል እወጃቸው ስራ በተደጋጋሚ የሚያደርጉተን የሚገልፅ ነው፡፡ (ሐዋ 18፡6፣ ሐዋ26፡20፣ 28፣28)

13፡17 ከግሪኩ ፅሑፍ ከኢሳ 49፡6 የተወሰደ ጥቅስ ነው፡፡ ስምኦነ ኢየሱስነ ለመባረክ የተጠቀመበተ ዐረፍተ ነገር ነው፡፡ (ሉቃ 2፡32) በመሆኑም ጳውሎስ እና በርናባስ ለአህዛብ ወንጌልን መስበካቸው ብርሃን እንደወጣላቸው የሚያስገነዝብ ነው፡፡ (use of the old testament in the new, by dareill borach, p.97 in foundations for biblical interpretation, Broadman)፡፡

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 13፡48-52**

**አህዛብም ሰምተው ደስ አላቸው የእግዚብሔርም ቃል አከበሩ ለዘላለም ህይወትም የተዘጋጁ ሁሉ አመኑ የጌታም ቃል በአገሩ ሁሉ ተስፋፋ፡፡ አይሁድ ግን የሚያመልኩትን የከበሩትንም ሴቶችንና የከተማውን መኳንንት አወኩ በጳውሎስና በበርናባስም ላይ ስደትን አስነሰተው ከአገራቸው አወጡአቸው፡፡ እነርሱ ግን የእግራቸውን ትቢያ አራግፈውባቸው ወደ ኢቆንዮስ መጡ፡፡ በደቀ መዛሙርትም ደስታና መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፡፡**

13፡48 **"አህዛብ ሰምተው ደስ አላቸው የእግዚአብሔርንም ቃል አከበሩ"** እነዚህ በምኩራብ እግዚአብሔርን ሲያመልኩ የነበሩ፡፡ አህዛብ ለመጀመሪያ ጊዜ እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ሁሉን ፍቅር በማሳየት ይቀበላል፡፡ ይሚለውን መልእክት በመስማታቸው ደስ ተሰኝተዋል በመሆኑም በሙሉ ልብ ተቀብለውታል (ሐዋ 28፡28)

▣ **"ለዘላለም ህይወትን የተዘጋጁ አመኑ"** ስለ ሰው መጨረሻ ዕድል ፈንታ በግልፅ የሚናገር ዐረፍተ ነገር ነው፡፡ በዝምታ ዘመን የዚህ አይነት ስነ ፅሑፍ የተለመደ ነበር፡፡ በአዲስ ኪዳን ይህ ርዕሰ ጉዳይ የእግዚአብሔር ቅድመ ምርጫ እና የሰው የመምረጥ ነፃነት እነዚህ ሁለቱ የሚጋጩ ይመስላሉ፡፡ (ፊሊ 2፡12.13) ይህ አረፍተ ነገር ወታደሮች የሚጠቀሙበት ሐረግ ነው፡፡ ይኸውም ታሶ ወይም መመዝገብ ወይም መሾም የሚል ትርጉም አለው፡፡ መመዝገብ የሚለው ቃል ሁለት መፅሐፍትን እንድናነብ ያመለክተናል (ዳን 7፡10፣ ራዕ 20፡12)፡፡ በመጀመሪ የሳውን ስራ

በሚገልፀው መጽሐፍ ላይ (መዝ 56፡8፣ 139፡16፣ ኢሳ 65፡6 እና ሚልክ 3፡16) ሌላኛው የሕይወት መጽሐፍ ነው (ዘው 32፡32፣ መዝ 69፡28፣ ኢሳ 4፡3፤ ዳን 12፡1፣ ሉቃ 10፡20፣ ፊሊ 4፡3፣ ዕብ 1፡23፣ ራዕ 3፡5፣ 13፡8፣ 17፡8፣ 20፡12-15፣ 21፡27)፡፡ ምርጫ እና የስነ መለኮት ሚዛናዊነት ተብሎ በ2፡47 ላይ የተገለፀው ልዩ ርዕስ ተመልከት፡፡

**13፡50 "አይሁድ ግን የሚያመልኩትንም የከበሩትንም ሴቶች አወኩ"** በትንሹ እስያ የነበረውን የሴቶች ክብረ እና ነፃነታቸውን የሚናገር ታሪክ ጠቃሽ ዐረፍተ ነገር ነው (ሐዋ 16፡14፣ 17፡4)፡፡

በዚህ ክፍል የሚገኙት ሴቶች እግዚአብሔርን የሚፈሩ በህብረተሰቡ መሃከል የተከበሩ የህዝብ መሪዎች ወይም የህዝብ መሪ የሆኑ ወንዶች ሚስቶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡(A.T Roberson, *Word Pictures in the New Testament* vol.3.p.201) በተጨማሪም አህዛብ ሴቶች ወደ አይሁድ ሃይማኖት መማረካቸውን ያመለክታል፡፡ (*Strabo* 7:2 *Juvenal* 6:542) ሃይማኖቱ የተወደደበት ምክንያት መልካም ስነምግባርን ያስተምር ስለነበረ ነው፡፡

▣ **"ጳውሎስ ላይ ስደተነ አስነስተው"** 2ጢሞ 3፡11 ይመልከቱ፡፡

**13፡51 "እነርሱ ግን የእግራቸውን ትቢያ አራገፌውባቸው"** በአይሁድ ባህል የተቃውሞ ምልክት ነው፡፡ (ማቴ. 10፡14፣ ሉቃ9፡5፡ 10፡11) ትቢያን ማራገፍ ሊያመለክተ የሚችለው፡-

1. በአዋራ የተሸፈነን እግር ማራገፍን ያመላክት ይሆናል፡፡
2. በልብስ ላይ ያለውን አዋራ ማራገፍ ሊሆን ይችላል፡፡

▣ **"ኢቆንዮን"** በሮማውያን አውራጃ በገላትያ ግዛተ የሊቆኒዮ ዋና ከተማ ነች፡፡ በምስራቅ እና በደቡብ ምስራቅ አንፃኪያ እና በሰሜን ስልጥራ የምትገኝ ከተማ ነች፡፡

**13፡52 "ደስታና መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው"** ደስታው ተደጋጋሚ መሆኑ የሚገልፅ የሰዋሰው ህግ በዐረፍተ ነገሩ ይታያል፡፡ መንፈስ ቅዱስ በእንዲህ ባለ ስደት እና መከራ ደስታን ይሰጣል፡፡ (ያዕ 1፡22፣ 1ጴጥ 4፡12)
በዚህ ቁጥር ውስጥ ደቀ መዛሙርት የትኞቹ መሆናቸውን ማወቅ አይቻልም፡፡ ምናልባት አዳዲስ አማኞች ሊሆኑ ይችላሉ ወይም የሚሲዮናዊያን ቡድን ሊሆን ይችላል ወይም ሁለቱም ሊሆን ይችላል፡፡

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ለመርዳት ነው የተሰናዱት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋነኞቹን ጉዳዮች ለማጤን እንዲረዳ ነው፡፡ ሐሳብ ለማጫር እንጂ መደምደሚያ አይደሉም፡፡

1. በሐዋ 13፡2 የተደረገው ሹመት መርህ ሆኖ ለምን አልቀጠለም?
2. ጳውሎስ በመጀመሪያ በምኩራብ የሚሰብክበት ምክንያቱ ምንድነው?
3. ዮሐንስ የሚሲዮን ቡድኑን ለምን ተለየ? (ቁ.13)
4. ቁ.39 ከገላ 3 ጋር የሚዛመደው በምን መንገድ ነው?
5. ቁ.48 ከእግዚአብሔር አስቀድሞ መምረጥ እና ከሰው ነፃ ምርጫ ጋር በማነፃፀር ግለፁ?

# የሐዋርያት ስራ 14

## የምንባቡ ክፍፍል በአዲሶቹ ትርጉም

| የተየመቅሰ[4] | አኪጀት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጳውሎስና በርናባስ በኢቆንዮስ | በኢቆንዮስ | አገልግሎት ክልል | በኢቆንዮስ | የምስራቹ ቃል በኢቆንዮስ |
| 14:1-7 | 14:1-7 | 14:1-7 | 14:1-4 | 14:1 |
| | | | | 14:2 |
| | | | | 14:3 |
| | | | | 14:4-7 |
| | | | 14:5-7 | |
| ጳውሎስና በርናባስ በበልስጥራን | የጣኦት ምልኮ በበልስጥራን | | በልስጥራና ደርባ | የሽባ ፋውስ |
| 14:8-18 | 14:8-18 | 14:8-18 | 14:8-13 | 14:8-10 |
| | | | | 14:11-18 |
| | ከድንጋይ ወገራ ከደርባን አመለጡ | | | |
| 14:19-20 | 14:19:20 | 14:19-20 | 14:19-20 | 14:19-20 |
| ከአንፃኪያ የተደረገ ጉዞ | አዳዲስ አማኞች ማፅናት | | ከአንፃኪያ የተደረገ ጉዞ | |
| 14:21-28 | 14:21-28 | 14:21-23 | 14:21-23 | 14:21-23 |
| | 14:24-28 | 14:24-26 | 14:24-26 | 14:24-26 |
| | | | 14:27-28 | 14:27-28 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (ከ "**መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ**" **ገጽ** vii)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. ምንባብ አንድ
2. ምንባብ ሁለት
3. ምንባብ ሦስት
4. ወ.ዘ.ተ

**የሐዋርያው ጳውሎስ የወንጌል አገልግሎት በገላትያ**
**እንዴት ማዛመድ ይቻላል?**

ሀ. በገላትያ የነበረውን አገልግሎቱን የሚያወሱ ሁለት ምልከተዓለሞች አሉ።

ለ. ሁለቱ መላምቶች የሚከተሉት ናቸው።

1. የመጀመሪያው እስከ ስምንተኛም ዓመት ምህረት የነበረው አመለካከት ነው።
   ሀ. የሰሜን ገላትያ መላምት
   ለ. የሰሜን ዋልታ የቱርክ ሜዳማ ቦታ የነበሩ የገላትያ ገተያር የነበራቸው ሰዎች ናቸው። እነዚህም በሦስተኛው ዓመት ምህረት ይህንን ቦታ በመውረር የራሳቸው አደረጉት፤ ከምዕራፍ አውሮፓ በመለየት "ጋሎ ክሪሽያንስ የሚል መጠሪያ ያዙ፤ ነገር ግን በንጉስ አታቱስ በ230 ከክ)ል)በፊት ተሸንፈዋል። ከዚያ ቀድም ግዛታቸው እስከ ሰሜን መካከለኛ እስያ እና የአሁኑ ታርክ ይደርስ ነበር።"
   ሐ. ከላይ በዝርዝር ላየናቸው ዘሮች ጳውሎስ ከሲላሶ እና ከጢሞቲዎስ ጋር በሁለተኛውና በሦተኛውም የሚሲዮናዊት ጊዞው ያገኛቸው ሰዎች ናቸው።
   መ. አንዳንዶች የጳውሎስን ሕመም ከወባ በሽጣታ
2. ሁለተኛው መላምት በኤም ራምሴ "st Paul the trakeler and Roman citizen, New York G.P Putom's sons, 1996" የተሰኘ መፅፍ በማንበብ ተጨማሪ ግንዛቤ ማግኘት ይችላል።
   ሀ. በአፈታሪክ ገላትያ ራሷን የቻለች ሃገር መሆንዋን ይነገራል ነገር ግን ጳውሎስ የሮማውያንን አውራጃዎች ስያሜ በብዛት ይጠቀማል እንገዲህ በዘር ገላትያ የሀኑ እንዳሉ ሆነው ነገር ግን ገላትያ የሚባለው የሮማ ግዛት ትልቅ ታን የሚያካልል ነው። እነዚህ የገላትያ ሰዎች ሮማውያንን በመደገፍ በመንግስት ተመስግዋል። ጳውሎስ የመጀመሪያ የሚሲዮናዊነት ጉዞውን ወደ ደቡብ ገላትያ ወደ ልስጥልን፣ አንድኮኪያ፣ አቆንዮን አድርጓል። ይህም በሐዋ 13-14 ተፅፏል፡ አብያተክርስቲያናት በዚህ አካባቢ እንደነበሩ ጠቋሚ ማስረጃዎች ተፅፈዋል።
   ለ. የደቡብ መላምት የሚባለው የጳውሎስ የሚሽነሪ ጉዞው በኢየሩሳሌም ስብስብ ከመደረጉ በፊት የተከናወነ እንደሆነ ይናገራሉ። (ሐዋ፡15) ስብሰባው የተካሄደው በ48-49 ነው። በመሆኑም የገላትያ መፅሐፍ የተፃፈው በዚሁ ጊዜ ነው። ይህም የጳውሎስ የመጀመሪያው ደብዳቤ ነው።
   ሐ. በደቡብ ገላትያ ያሉ መላምቶች ማስረጃዎች፡-
      (1) ከበርናባስ በስተቀር ከጳውሎስ ጋ በመሆን የመጀመሪያውን የሚሲዮናዊነት ጉዞ የሄደ የማንም ስም አልተጠቀሰም (ሐዋ 2፡19,19)
      (2) ቲቶ አለመገረዙ ተፅፏል (ቲቶ 2፡1-5) ከሐዋ 15 በፊት የተከናወነው ከኢየሩሳሌም ስብስባ በፊት ነው።
      (3) የጴጥሮስ ከአህዛብ ጋር ህብረት ማድረግ ከኢየሩሳሌም ስብስባ በፊት የሆነ ነው (ሐዋ 2፡11-14)
      (4) ከተለያዩ የአህዛብ አብያተክርስቲያናት ለኢየሩሳሌም ቤክርስቲያን የእርዳታ ገንዘብ ተሰብስባል (ሐዋ 20፡4)

   እነዚህን ዝርዝሮች በማቅረብ የደቡብ መላምቶች ተቀባይነት እንዲኖራቸው ይጥራሉ ነገሀር ግን ሌሎች ማመሳከሪያ መፅሐፎችን መመልከት ተገቢ ነው።

ሐ. የገላትያ መፃፍና የሐዋርያት ስራ ያላቸው ዝምድና፡-

1. ሐዋሪያው ጳውሎስ አምስት ጊዜ ኢየሩሳሌምን ጉብኝቷል ይህም በሐዋርያት ስራ ውስጥ በሉቃስ በግልፅ ተፅፏል።
   ሀ. ሐዋ 9፡26-30 ጳውሎስ ከተለወጠ በኃላ
   ለ. ሐዋ 11፡30;12፡25 ከአህዛብ አብያተ ክርስቲያናት እርዳታ
   ሐ. ሐዋ 15፡1-30 የኢየሩሳሌም ስብሰባ
   መ. ሐዋ 18፡18 የተብራራ ጉብኝት
   ሠ. ሐዋ 21፡15 በአህዛብ መሃከል
2. ሐዋርያው ጳውሎስ ሁለት ጊዜ ኢየሩሳሌምን መጉብኘቱ በገላትያ መፃህፍ ተፅፏል።
   ሀ. ገላ 1፡18 ከሦስት አመት በኃላ
   ለ. ገላ 2፡1 ከአስራ አራት አመት በኃላ
3. ሐዋርያት ስራ 9፡26 እና ገላትያ 1፡18 ይዛመዳሉ። ሐዋ 11፡30 እና ያልተጠቀሰ ስብሰባ ነው ነገር ግን በገላትያ 2፡1 ተዘግቧል።
4. በሐዋ 15 እና በገላ 2 መሃከል ልዩነት አለ ምክንያቱም
   ሀ. የተለያዩ አመለካከት ስለነበረ ነው
   ለ. የተለያየ ዓላማ በጳውሎስና በሉቃስ መሃከል ስላነበረ ነው
   ሐ. በእርግጥም ገላ 2 የተፀፈው ከሐዋ 15 በፊት በመሆኑም ነው።

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 14፡1-7**
**በኢቆንዮንም እንደ ቀድም አይሁድ ምኩራብ ገብተው ከአይሁድና ከግሪክ ሰዎች ብዙ እስኪያምኑ ድረስ ተናገሩ ያላመኑት አይሁድ ግን የአህዛብን ልብ በወንድሞች ላይ አነሣሡ አስከፉም። ምልክትና ድንቅ በእጃቸው ይደረግ ዘንድ እየሰጠ ለፀጋው ቃል ስለ መሰከረው ስለ ጌታ ገልጠው እየተኛገሩ ረጅም ወራት ተቀምጡ። የከተማውም ህዝብ ተከፍለው እኩሌቶቹ ከሐዋርያት ጋር ሆኑ አሕዛብን አይሁድ ግን ከአለቆቻቸው ጋር ሊያንገላቱአቸውና ሊወግሩአቸው ባሰቡ ጊዜ አውቀው ልስጥራንና ደርቤን ወደ ተባሉት ወደ ሊቃኦንያ ከተማዎች በእነርሱም ዙሪያ ወዳለው አገር ሸሹ በዚያም ወንጌልን ይሰብኩ ነበር።**

**14፡1 "ኢቆንዮን"** ይህ በሁለተኛ ምዕተ ዓመት "የጳውሎስ ክንዋኔዎች እና ተክላ" በሚል ስያሜ ጳውሎስ በኢቆንዮስ የነበረውን ታሪክ የሚያወሳ መፅሐፍ ነው፤ ይህም የጳውሎስ ተክለ ሰውነቱን ሁሉ የሚገልፅ መፅሐፍ ነው፤ ጳውሎስ አጭር፣ ራሰ በርሃ፣ብራኬት እግር፣ብዙ ፀጉር ቅንድብ የለው እና አይኑ ጎላ ያለ ሰው እንደነበር ይገልፃል። እነዚህ ዝርዝሮች በመፅሐፍ ቅዱስ አልተጠቀሱም ነገር ግን ጳውሎስ የትንሹ እስያ የኑሮ ዘይቤና ተክለ ሰውነት ይታይበታል። በሮም ግዛት የነበሩ እንደ ገላትያ ያሉ ሃገሮች የሚገኙት በዚሁ አካባቢ ነው።

▣ **"ምኩራብ ገብተው"** የጳውሎስና የበርናባስ የተለመደ ተግባራ ቸው ነው። በምኩራብ አይሁድ እና ግሪኮች ነበሩ እነርሱም የብሉይ ኪዳንን ትንቢቶች እና ቃል ኪዳኖች ጠንቅቀው የሚያውቁ ናቸው።

▣ **"ከአይሁድና ከግሪክ ሰዎች ብዙ እስኪያምኑ ድረስ"** ይህ የሐዋርያት ስራ መፅሐፍ ዓላማ በዚህ ዓረፍተ ነገር በአጭሩ ተቀምጧል። ወንጌል ዘር እና ቀለም ሳይለይ በርካታ ቦታዎች መድረሱን ያመለክታል ይህም በብሉይ ኪዳን የተነገረ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ተፈፅሟል (ዘፍ 3፡15;12፡3)

**14፡2 "ያላመኑ አይሁድ"** የድነት ሥራ የሚከናወነው "በሚመን" ብቻ ነው፤ መንፈሳዊ ዕውርነት እና ማወላወል ያለመታዘዝ እና ያለማመን አይነተኛ ምልክቶች ናቸው። ወንጌል የሚቃወም ማንም የታወረ የእርሱ መቃወም ወንጌል ወደ ብዙዎች እንዲሄድ በር ከፈተ። (ሮሜ 9፡11)

▣ **"አነሣሡ"** በግሪኩ ፅሐፍ ላይ **"አመፅ"** በሚል በተለመደ ቃል ተተክቷል።
(1 ሳሙ 3፡12; 22፡8;2 ሳሙ 18፡31;22፡49;1 ዜና 5፡26) በአዲስ ኪዳን (ሐዋት 13፡50 እና 14፡2) ብቻ ይገኛል።

▣ **"አስከፉም"** በግሪኩ ፅሐፍ ላይ "ክፋት" በሚል በተለመደ ቃል ተተክቷል። ይህም በሌሎች ላይ ክፍ እንዲያደርጉ ማነሳሳት የሚል ትርጉም ይሰጣል። (ሐዋ 7፡6;19;12፡114፡2;18፡10)
**14፡3** እግዚአብሔር የተዳምራት ምልክቶችን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል እውነተኛ መሆኑን ለማረጋገጫ ተጠቅሞበታል።

**14፡4 "የከተማው ሕዝብ ተከፍለው"** የእውነት ቃል በማጣ ጊዜ ሰዎች መከፋፈላቸውን ያስገነዝባል። (ሐዋ 17፡4-5;19፡9;28፡24;ማቴ 10፡34-36) በምዕኩራብ የነበሩ አይሁድ ብዙዎቹ ሲያምኑ ሌሎቹ ደግሞ በወንጌል ላይ ጦራቸውን መስበቃቸውን ያሳያል።

▣ **"ሐዋርያትም"** ጳውሎስን እና በርናባስን የሚያመለክት ቃል ነው። ሉቃስ ከአስራ ሁለቱ ደቀመዛሙርት ሌላ ለጳውሎስና ለባርናባስ ሐዋርያት የሚል ስያሜ ሲሰጥ የመጀመሪያው ነው። በርናባስ ሐዋሪያ ተብሏል (ቀ.14) ይመልከቱ። ከአስራ ሁለቱ ሌላ ሐዋርያ የሚል ስያሜ ሲሰጥ የመጀመሪያው ነው። በርናባስ ሐዋሪያ ተብሏል (ቁ.14) ይመልከቱ። ከአስራ ሁለቱ ሌላ ሐዋርያ የሚል ስያሜ መሰጠቱን እንገነዛባለን። በገላ 1፡9 ላይ የኢየሱስ ወንድም ያዕቆብ ሐዋርያ ተብሏል፣ ሲላስ እና ጢሞቲዮስ ሐዋርያ ተብለዋል። (1 ተሰሎ 1፡1,2፡6 ሮሜ 16፡6-7 እና አጳሎስ ሐዋሪያ ተብሏል (1 ቆሮ 4፡6-9)።
አስራ ሁለቱ ደቀመዛሙርት የተለዩ ሐዋሪያ ናቸው፤ በመሆኑም በሞቱ ጊዜ እነርሱን የሚተካ የለም (ከማቴዎስ በስተቀር ሐዋ 1) ነገር ግን የሐዋርያነት ስጦታ ቀጣይ መሆኑን እንመለከታለን። (1 ቆሮ 12፡28 እና ኤፌ 4፡11)

**ልዩ ርዕስ ፡ መላክ (አፖስቴሎ)**
*ይህ መላክ ለሚለው ተለመደ የግሪክ ቃል ነው (ማለትም አፖስቶሎ)። ይህ ቃል ልዩ ልዩ ሥነ መለኮታዊ ጥቅሞች አሉት።*

1. ረቢዎች ቃሉን የተጠቀሙት ሌላውን በኦፌኒስ ተክቶ የተላከ በሚለው ሲሆን ይህም ልክ የእንግሊዝ አመባሳደሮችን እንደማለት ነው (1ቆሮ 5፡20)።
2. ወንጌላት ይህን ቃል ኢየሱስ በአባቱ እንደተላከ ለማመልከት ይጠቀሙታል። በዮሐንስ ወንጌል ቃሉ መሲሐዊ ትርጓም (ቃና) አለው (ማት 10፡40፣ 15፡24፣ ማር 9፡37፣ ሉቃ 9፡48 እና በተለይ ዮሐ 4፡34፣ 5፡24፣ 30፡36,37,38፣ 6፡29,38,39፣ 40፡47፣ 7፡29፣ 8፡42፣ 10፡36፣ 11፡42፣ 17፡3፣

8:18,21፣ 23:25፣ 20:21) ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን መላኩን ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል (ዮሐ 17:18፣ 20:21)።

3. አዲስ ኪዳን ለደቀመዛሙርት ተጠቅሞበታል።
   ሀ. የመጀመሪያዎቹ አስራሁለቱ ደቀመዛሙርት (ሉቃ 6:13፣ ሐዋ 1:21-22)
   ለ. ከሐዋርያት ጋር አብረው የሚሠሩና ረዳቶችን ለማመልከት
      1. በርናባስ (ሐዋ 14:4,14)
      2. አንዲራኒቆስና ዩልያን (ኪንገጀምስ ዩልያን ሮሜ 16:17)
      3. አጵሎስ (1ቆሮ 6-9)
      4. ያዕቆብ የጌታ ወንድም (ገላ 1:19)
      5. ሲልባኖስና ጢሞቴዎስ (1ተሰ 2:6)
      6. ምናልባት ቲቶ (2ቆሮ 8:23)
      7. ምናልባት አፍሮዲጡ (ፊሊጵ 2:25)
   ሐ. በቤተክርስቲያን ውስጥ ቀጣይነት ያለው ስጦታ (1ቆሮ 12:28፣ ኤፌ 4:11)
4. ጳውሎስ ይህን ማዕረግ የክርስቶስ ወኪል መሆኑን ለማስረገጥና ሥልጣኑ ከእግዚአብሔር መሆኑን ለማሣወቅ በብዙ መልዕክቶቹ ለራሱ ተጠቅሞታል (ሮም 1:1፣ ቆሮ 1:1፣ 2ቆሮ 1:1፣ ገላ 1፣ ኤፌ 1:1፣ ቆላ 1:1፣ 2ጢሞ 1:1፣ ቲቶ 1:1)።

14:5 **"ከአለቆቻቸው ጋር"** የከተማው መሪዎች ወይም የምኩራብ መሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ። የጥንት ፀሐፊዎችና የአሁን ፀሐፊዎች እንደሚስማሙበት አሳዳጆቹ ሁለት ናቸው፦ (1) በቁ 2 እና (2) በ ቁ 5 ላይ ሚገኙት ናቸው።

▣
NASB, NRSV
TEV **"አልተቀበሉአቸውም"**
NKSV **"መዳፈር"**
NJB **"አጠቋቸው"**

የግሪኩ ፅሑፍ "hubrizo" አለመቀበል ከሚለው ቃል ሌላ ትርጉም አለው እርሱም "ማሳመፅ" ወይም "የአመፅ ተግባርን ማድረግ" የሚል ነው። በአዲስ ኪዳን በግሪኩ ፅሁፍ የተለመደ ቃል ነው፤ ቃል ነው፤ ሉቃስ የፃፈውን የዚህን ቃል ፍቺ እንመልከት፦

1. መሳደብ ሉቃ 11:45
2. የአመፅ ተግባር ሉቃ 18:32; ሐዋ 14:5
3. ንብረትና ማጣት ሐዋ 27:10, 21

▣ "ወገራ" የተቃውሞ ዓይነት ጠንካራ እና ጭካኔ የተሞላበት መሆኑን ያመለክታል። ከብሉይ ኪዳን የመውገር ባህል ተላልፎ የመጣ ነው።

14:6 **"ልስጥራንና ደርቤን ወደሚባሉት ወደ ሊቃኦንያ"** ይህ በዘር የተለዩ ወደ ሆኑት ሰዎች አገር መድረሳቸውን ያመለክታል

14:7 በተደጋጋሚ የተሰበከበት ቦታ ነው። ይህም የሐዋርያው ጳውሎስ የሚሲዮናዊው ጉዞውን የሚያወሳ ዋና ሃሳብ ያለበት ሐረግ ነው (ሐዋ 14:21; 16:10)።

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 14:8-18**

**በልስጥራንም እግሩ የሰላለ ከእናቱም ጀምሮ አንካሳ የሆነ ከቶ ሄዶ የማያውቅ አንድ ሰው ተቀምጦ ነበር። ይህም ሰው ጳውሎስ ሲናገር ይሰማ ነበር እርሱም ትኩር ብሎ ተመለከተው ይድን ዘንድ እምነት እንዳለው ባየ ጊዜ በታላቅ ድምፅ ቀፅ ብለን በእግርህ ቁም አለው። ብድግ ብሎ ይመላለስ ነበር። ሕዝቡም ጳውሉስ ያደረገውን ባዩ ጊዜ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በሊቃአንያ ቋንቋአማልክት ሰዎችን መስለው ወደ እኛ ወርደዋል አሉ በርናባስንም ድያ አሉት፤ ጳውሉስንም እርሱ በመናገር ዋና ስለ ነበረ ሄርሜን አሉት። በከተማውም ፊት መቅደስ ያለው የድያ ካህን ኮርማዎችንና የአበባን አክሊሎች ወደ ደጃፍ አምጥቶ ከህዚቡ ጋር ሆኖ ሊሰዋላቸው ወደደ። ሐዋርያት በርናባስና ጳውሉስ ግን ይህን በሰው ጊዜ ልብሳቸውን ቀደው ወደ ሕዝቡ መካከል እየጮኹ ሮጡ እንዲህም አሉ እናንተ ሰዎች ይህን ስለምን ታደርጋላችሁን እኛ ደግሞ እንደ እናንተ የምንሰማ ሰዎች ነን ከዚህም ከንቱ ነገር ሰማይንና ምድርን ባህርንም በእነርሱም ያለውን ሁሉ የፈጠረውን ወደ ሕያው እግዚአብሔር ዘወር ትሉ ዘንድ ወንጌልን እንስካለን። እርሱ ባለፉት ትውልዶች አህዛብን በ ገዛ ጎዳናቸው ይሄዱ ዘንድ ተዋቸው። ከዚህም ሁሉ ጋር መልካም ስራ እየሰራ ከሰማይ ዝናብን ፍሬ የሚሆንበትን ወራት ሲሰጥ ልባችንን በመብል እና በደስታ ሲሞላው ራሱን ያለ ምስክር አልተወም። ይህንንም ብለው እንዳይሰውላቸው ህዝቡን በጭንቅ አስተውአቸው።**

14:8 **"በልስጥራን"** የጢሞቴዎስ የመኖሪያ ከተማ ነች። (ሐዋ 6:1) የተመሰረተችው በሮማዊው ኮኖሊስት በአነስቲያ በ6 ዓ.ዓ ነው። በዚህች ከተማ ምኩራብ ስላልነበረ ጳውሎስና በርናባስ በየመንገድ ወንጌልን ይሰብኩ ነበር።

▣ **"የሰለለ"** የቃሉ ፍቺ **"የማይቻል"** ወይም **"ያልቻለ"** የሚል ቀጥተኛ ትርጓሜ አለው (ሉቃ 18:27;ዕብ 6:4,18;10:4;11:6) የሕክምና ቃል በመጠቀም ደካማ የሚል ስሜት ያለው ቃል ተጠቅሟል፡፡ (ሮሜ 8:3;15:1) በዓረፍተ ነገር ድርደራው ይገልፃል፡፡

**14:9 "ትኩር ብሎ ተመለከተና"** ሉቃስ ይህን ሐረግ ብዙ ጊዜ ይጠቀምበታል (ሐዋ 3:4;10:4) ጳውሎስ ሰውየው እየሰማው እንደነበር በመገንዘብ እምነቱን አይቶ ፈውስ ያከናወነበት ቦታ ነው፡፡

▣ **"ይድን ዘንድ እምነት እንዳለው"** የብሉይ ኪዳን "መዳን" የሚለውን ቃል ተጠቅሟል፤ ይህም ከበሽታ መዳንን ያመለክታል፡፡ ጳውሎስ ፈውሱን ያከናወነው በሰውየው ዕምነት ላይ መሰረት አድርጎ ነው ነገር ግን ሁል ጊዜ ላይሆን ይችላል ሉቃ 5:20;ዮሐ 5:5-5-9፡፡ የተዓምራት ምልክቶች ለተለያዩ ዓላማዎች ሊደረጉ ይችላሉ፡ (1) የእግዚአብሔርን ፍቅር ለመግለፅ (2) የእግዚአብሔርን ሃይል እና የወንጌልን እውነት ለማሳየት (3) አማኞችን ለማበረታታት፡፡

**14:11 "በሊቃኦንያ ቋንቋ"** ይህ ቋንቋ የአገሩ ህዝብ ቋንቋ በመሆኑ ጳውሎስና በርናባስ የሚባለውን በዚህ ቦታ መስማት አልቻሉም ነበር፡፡

**14:11-12 "በርናባስንም ድያ አሉት ጳውሎስንም እርሱ በመናገር ዋና ስለነበር ሔርሜን አሉት"** በግዜው የነበረው ባህል የግሪክ ጣኦታት በሰዎች መልክ ይገላጣሉ የሚል አስተሳሰብ ነበር፡፡ (Ovid, Methamot phoses 8:626) በዚህ ቦታ ዙስ እና ሄርመስ የሚባሉ ጣኦታት የሚመለኩበት ቦታ ነበር፡፡ (ሐዋ :14:13)

የበርናባስ ስም መጀመሪ ተጠቅሷል፤ ይህም የሆነበት ምክንያት ተናጋሪ የነበረው ጳውሎስ ሄርመስ (ሜሪኩሪ) በሚባለው ጣኦት የታወቀ በመሆኑ ነው ነገር ግን ዝም ያለው በርናባስ በታላቅ በመመሰል የመጀመሪያ ለመሆን በቅቷል፡፡

**14:13 "በከተማውም ፊት"** ይህ የከተማው በር ሆኖ በቅደሱ ያለው ከከተማው በር ውጭ በመሆን ወደ ውስጥ ሲመለከት የሚያሳየን ገፅታን ያሳያል፡፡

**14:14 "ሐዋርያት"** ሐዋ 14:4 ይመልከቱ፡፡

▣ **"ልብሳቸውን ቀደው"** ለአይሁዶች ልብስን መቅደድ የሃዘን ወይም የውርደት ምልክት ነው፡፡ (ማቴ 26:65;ማርቆ 14:63) ይህ ሁኔታ ለአሕዛቦችም ቢሆን ችግር መኖሩን የሚያመላክት ነው፡፡

▣ **"ሮጡ"** በአዲስ ኪዳን የግሪኩ ፅሑፍ ላይ ተመሳሳይ ወይም አንድ ዓይነት ትርጓሜ ተሰቶታል፡፡ ጳውሎስ እና በርናባስ በሮጣቸውን ያመለክታል፡፡
14:15-17 ይህ ምንባብ የጳውሎስን የመጀመሪያ ለአህዛብ የሰበከበትን ማጠቃለያ ያሳያል፡፡ ስብከቱ ከማርስ ሂል ጋር ተመሳሳይነት አለው (ሐዋ 17:22-33)

**14:15**

| | |
|---|---|
| NASB, NKJV | **"የእናንተው ዓይነት ተፈጥሮ ያለን ሰዎች ነን"** |
| NRSV | **"እኛም እንደእናንተው የምንሞት ነን"** |
| TEV | **"እኛ ራሳችን እንደ እናንተው ሰዎች ነን"** |
| NJB | **"ሰዎች ብቻ ነን እንደ እናንተ እንሞታለን"** |

የግሪኩ **"ሆሚዮዝ"** ከሁለት ጣምራ ቃል የመጣ ነው "አንድ ዓይነት" እና "ፍላጎት" የባህሉ ተፅኖ ሰዎች ጳውሎስና በርናባስ አማልክት እንደሆኑ አድርገው እንዲያስቡ አድርጓቸዋል፡፡ ነገር ግን "ሆሚዮቴንተሽ" ቁ.11 ማለት "ተመሳሳይ አሰራር" በሚል የቃል ፍቺ አለው፡፡ በመሆኑም ጳውሎስ እነዚህን የግሪክ ቃሉችን በመጠቀም እነርሱም ሰው መሆናቸውን ይገልፃል፡፡

▣ **"ከዚህ ከንቱ ነገር. . . ዘወር እንድትሉ"** ፀሐፊው ሉቃስ በዚህ ሐረግ የጳውሎስን እና የበርናባስን ትህትና ገልፃበታል በተለይ ከሄሮድስ አንቲፓስ ጋር ሲያዛምደው (ሐዋ 20:20:23) **"ከንቱ"** የሚለው ቃል ፍቺው "ባዶ" "ምንም" እና "ረብ የሌለው" ትርጉም ይሰጣል፡፡

▣ **"ወደ ሕያው እግዚአብሄር"** ከዕብራይስጡ ፅሑፍ የተወሰደ ነው፤ እርሱም ሕያው የሚለው "መሆን" ከሚለው ስርወቃል የተወሰደ ነው፡፡ (ዘፀ 3:14) ወይም በቀጥታ "ያሕዌ" ማለት "ለዘላለም የሚኖር" እና "ብቻውን ሕያው" የሚል ትርጉም ይሰጣል፡፡

▣ **"ፈጠረ"** ከዘፀ 20:11 እና መዝ 146:6 የተወሰደ ነው፡፡ የዕብራይስጡ ኤሎሂም፤ ዘፍ 1:1 እግዚአብሐርን ፈጣሪና የፍጥረቱ መጋቢ እንደሆነ ይገልፃል፡፡ (The expositor's Bible commentary; vol 1, pp -468-469) ያህዌ አዳኝና የሚዋጅ (The expositor's Bible commentary V.1 pp 471 -472) እና ያህዋ ቃል ኪዳን አድራጊ መሆኑን ይገልፃል፡፡

**14:16 "እርሱ ባለፉት ትውልዶች አህዛብን በገዛ ራሳቸው ጎዳና ይሄድ ዘንድ ተዋቸው"** በዘዳ 3a:7-8 ላይ ያህዌ ለህዝቡ ወሰንን እንደበጀ ሙሴ ፅፏል፤ ይህ በስነመለኮት መነፅር እግዚአብሄር ለአህዛቡ ጥንቃቄ እና ትኩረት እንደሚሰጥ

ለማስገንዘብ ነው:: (Gentiles Girdlestone, synonyms of the old Testament, pp 258-259) እግዚአብሔር ሰው ሁሉ እርሱን እንዲያውቀው ዕቅድ ነድፎ ሳለ ነገር ግን የሰው ዘር ጣኦታትን በማምለክ እግዚአብሔርን አስከፍቶአል፡፡ (ሮማ 1፡18-2፡29) ነገር ግን አግዚአብሔር አሁንም ሰውን እየፈለገ ነው (ሐዋ 14፡17)

አህዛቦች ስለ እግዚአብሔር የሚያውቁት ነገር አልነበረም ነገር ግን አይሁድ ስለ እግዚአብሔር ዕውቀት ነበራቸው፡፡ ይሄ ምዕት አህዛቦች ለእግዚአብሔር ወንጌል በዕምነት ምላሽ ሲሰጡ አይሁዶች ግን ወንጌልን በቃወም ብቻ ሳይሆን አሳዳጆችም ሆነዋል፡፡ (ሮሜ 9-11)

ነው፡፡ (መዝ 19፡1-6;ሮማ 1፡19-20;2፡14-15) የሰው ዘር በሁሉ እግዚአብሔር እንደሆነ

14፡17 **"ራሱን ያለ ምስክር አልተወም"** ፍጥረታት የእግዚአብሔር መሆናቸውን እያስገነዘበ የተናገረበት ምንባብ ነው፡፡ (ዘዳ 27-29)

እነዚህ አህዛብ ጣኦት ማምለካቸው ከእግዚአብሔር ዘንድ እርግማንን እንደሚያመጣባቸው አላስተዋሉም፡፡ እግዚአብሔር ጳውሎስን ለልዩ ለራሱ አላማ መርጦታል (መዝ 45፡15-10;147፡8፡ኤር 5፡24;ዮና1፡9) እነዚህን ተመሳሳይ የእግዚአብሔር ምርጫዎች ይመልከቱ፡፡

ጳውሎስ በአቴና እንዳደረገ ተመሳሳይ ነገር ማድረጉን ልናጤን እንችላለን፡፡ እንግዲህ ፀሐፊው ሉቃስ ይህንን የጳውሎስን የስብከት ሃተታ ለሌሎች ወይም ከራሱ ከጳውሎስ መስማቱን መገመት ይቻላል፡፡

14፡18 የእማኞች ምስክርነት የቀረበበት ዝርዝር ነው፡፡

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 14፡19-23**

**አይሁድ ግን ከአንፃኪያ ከኢቆንዮን መጡ፤ ሕዝቡንም አባብለው ጳውሉስን ወገሩ የሞተም መስሎአቸው ከከተማ ወደ ውጭ ጎተቱት ደቀ መዛሙርት ግን ከበውት ሳሉ ተነስቶ ወደ ከተማ ገባ ነበነገው ከበርናባስ ጋር ወደ ደርቤን ወጣ፡፡ በዚያች ከተማ ወንጌልን ሰብከው እጅግ ደቀ መዛሙርትን ካደረጉ በኃላ የደቀ መዛሙርቱን ልብ እያፀኑ በሃይማኖትም ፀንታ እንዲኖሩ እየመከሩና ወደ እግዚአብሔር መንግስት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል እያሉ ወደ ልስጥራን ወደ ኢቆንዮንም ወደ አንፃኪያም ተመለሱ በየቤተ ክርስቲያኑም ሽማግሎዎችን ከሾሙላቸው በኃላ ጠመውም ከፀለዩ በኃላ ላመኑበት ለጌታ አደራ ሰጡአቸው፡፡**

14፡19 አይሁድ ጳውሎስን በሚሰብክበት ቦታ ሁሉ ከእርሱ ጋር እየተዘዋወሩ በተደጋጋሚ ይቃወሙት ነበር፡፡ ጥቃቱ ያነጣተረው ጳውሎስ ላይ እንጂ በርናባስ ላይ አልነበረም ጳውሎስና ባርናባስ እንደአማልክት ተከብረው ነበር፤ ነገር ግን በቀጣዩ ቀን ይወግሯቸው ነበር፡፡

▣ **"ጳውሎስን ወገሩት"** ሐዋርያው ጳውሎስ የትንሳኤ ሃይል ያገና ይመስል ከሞት ከሚያክል ወገራ ተርፎ ማገልገሉ ለአገልግሎት መቁረጡን ያሳያል፡፡ (ሐዋ 14፡20-21) 2 ቆሮ 11፡25 እና ገላ 6፡17 ይመልከቱ፡፡

14፡20 **"ደቀ መዛሙርት ግን ከበውት ሳሉ** ሁኔታው በዝርዝር የተቀመጠ አይደለም ነገር ግን ጳውሎስ ከሞት ድኖ መነሳቱ የደቀ መዛሙርቱ ፀሎትም ይሆናል ብዬ አምናለሁ ወንጌል በዚህ ዓይነት ስደት ያድግና ይሰፋ ነበር"፡፡

14፡21 **"በዚያች ከተማ ወንጌልን ሰብከው"** ከተማይቱ ደርባን (ቁ .20) በኢቆንዮን የሮማውያን አውራጃ የሆነች የገላትያ ክፍል ናት ብዙ ሰዎች የጳውሎስን ስብከት በመስማት የዳኑበት ከተማ ነች፡፡

14፡21 **"በዚያች ከተማ ወንጌልን ሰብከው"** ከተማይቱ

14፡22 ይህ ጥቅስ የጳውሎስ አገልግሎት ማጠቃለያ ሃሳብ ነው፡፡ (1) በጽናት እና (2) በመከራ ላይ እንዳተኮረ ልብ በል፡፡ አማኞች በመከራ ውስጥ ይጠነክራሉ (ሮሜ 5፡3-4፣ 8፡17-18፣ 1ተሰ 3፡3፣ 2ጢሞ 3፡12፣ ያዕ 1፡2-4 (ጴጥ 4፡12-16)፡፡

▣ **"ወደ ልስጥጥራን ወደ አቆንዮንም ወደ አንፃኪያም ተመላሱ"** በዚህ ጊዜ በግልፅ እየሰበኩ ሳይሆን ያመኑበትን በመጎብኘት እያፀኑ የተመላለሱበትን ታሪክ እያብራራ ነው (ሐዋ 14፡22-23)፡፡
መፅናት
መከራ (ሮማ 5፡3-4;8፡17-18;1 ተሰሎ 3፡3;2 ጢሞ 3፡12 ያዕቆ 1፡2-4,1 ጴጥ 4፡12-16)፡፡

▣ **"እያፀኑ"** በግሪኩ ፅሁፍ "የሰውን ማንነት" "የአእምሮ ድርጊቶች" የሚል ቀጥተኛ ትርጉም አለው፡፡ በግሪኩ ፅሁፍ እያንዳንዱ ሰው ያልተቀደሰ ነፍስ አለው የሚል ትርጉም አናገኝም ነገር ግን በዕብራይስጡ ፅሁፍ ላይ የሚያመለክተው የሰውን አጠቃላይ ምልዓተ ስብዕናውን ነው፡፡

▣ **"በሐይማኖት ፀንተው"** ትዕግስት የሚለውን ርዕስ ይመልከቱ፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ መፅናት**

*የመፅሐፍ ቅዱስን አስተምርሆት ከክርስትና ሕይወት ጋር ለማዛመድና ለመግለፅ አስቸጋሪ ነው ምክንያቱም የምዕራባውያን የአነጋገር ስልት ከመፅሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር የሚጋጭ ስለሚመስል ነው፡፡ የምዕራባውያን ክርስትና አንድን እውነት የሚመርጥ ሆኖ ነገር ግን ሌላኛውን እውነት የሚሽር ነው፡፡ በምሳሌ እነመልከት፡-*

1. *ደህንነት ክርስቶስን ለማመን በመወሰን ወይስ በሕይወት ዘመን ሁሉ በመስጠት ደቀ መዝሙር በመሆን የሚገኝ ሕይወት ነው?*
2. *ደህንነት የእግዚአብሔር ነፃ ምርጫ ወይስ የሰው የንስሃና የእምነት ፈቃድ ማሳያ ነው?*
3. *ደህንነትን ካገኙ በኃላ ሊያጡት ይችላሉ? ወይስ በቀጣይነት በትጋት የሚጠበቅ ሕይወት ነው?*

*በጥንቲቱ ቤተክርስቲያን የትጋት ጥያቄ ዋና ነገር ነበር፡፡ የችገሩ ጅማሬ የተነሣው በአዲስ ኪዳን ምንባቦች መለያየት ነው፡፡*

1. *የማረጋገጫ ዓውዶች*
   - *ሀ. የኢየሱስ ዓረፍተ ነገሮች* (ዮሐ 6፡37;10፡28-29)
   - *ለ. የጳውሉስ ዓረፍተ ነገሮች* (ሮማ 8፡35-39; ኤፌ 1፡13;2፡5,8-9; ፊሊ 1፡6;2፡13; 2 ተሰሎ 3፡3,2፣ ጢሞ 1፡12;4፡18)
   - *ሐ. የጴጥሮስ ዓረፍተ ነገሮች* (1ጴጥ 1፡4-5)
2. *የመፅናት አስፈላጊነት የሚናገሩ ዓውዶች፡-*
   - *ሀ. የኢየሱስ ዓረፍተ ነገሮች* (ማቴ 10፡22;13፡1-9-24-30 ማርቆ 13፡13;ዮሐ 8፡31;15;4-10;ራዕ 2፡17,)
   - *ለ. የጳውሉስ ዓረፍተ ነገሮች* (ሮማ 11፡22;1 ቆሮ 15፡2;2 ቆሮ 13፡5 ገላ 1፡6;3፡4;5፡4;6፡9;)ፊሊ 2፡12;3፡18-20;ቆላ 1፡23)
   - *ሐ. የዩሐንስ ዓረፍተ ነገሮች* (1 ዮሐ 2፡6; 2 ዮሐ 9)
   - *መ. የዕብራውያን መፅሐፍ* (ዕብ 2፡1;3፡6,14;4፡14;6፡11)
   - *ሠ. የአባት ዓረፍተ ነገር* (ራዕ 21፡7)

*መፅሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው "ድነት" የእግዚአብሔር ፍቅር፣ ምህረት እና የፀጋው መገለጫ መሆኑ ለሁሉ መታወቅ አለበት፡፡ ያለ መንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት ማንም ሰው ወደ ደህንነት ሊመጣ አይቻለውም* (ዮሐ 6፡44,65) *የመለኮት ጥሪ ቅድሚ ሲሰጠው የሰው ምላሽ በሁለተኛ ደረጃ የሚቀመጥ ነው፡፡ ሁሉ መብቱን እና ሃላፊነቱን ማወቅ ይጠበቅበታል፡፡*

*ደህንነት ለሁሉ የተቸረ የአምላክ ስጦታ ነው፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ መሞት የዓለምን ሃጢያት ለማስወገድ ችሏል ይህም እግዚአብሔር ለሰው ዘር ሁሉ ለመዳኛ ያዘጋጀው የደህንነት በር ነው፡፡*

*የሚከተሉት መፃህፍቶች በማንበብ ተጨማሪ ግንዛቤ በዚህ ርዕስ ጉዳይ ላይ ይቻላል፡፡*

1. dale moody, *The word of Truth*, Eerdmans, 1981 (pp 348-365)
2. Howard marshall, *Kept by the Power of God*, Bethany fellow ship, 1969
3. Robert shank, *Life in the Son*, Westcott, 1961

*መፅሐፍ በዚህ ርዕስ ላይ ሁለት ሃሳቦችን ያነጣል፡* (1) *ማረጋገጫ አገኘን የሚሉ ነገር ግን የተሳሳተ ኑሮ የሚኖሩ የማስጠንቀቂ ቃል የተነጋገራቸው ነገር ግን የሚያገለግሉ፡፡* (2) *በራሰው ሕሞትና አግልግሎት ውስጥ የሚታገሉትን አበረታቱ፡፡ ችግሩ ትክክለኛ ያልሆነ ቡድን ስህተት የሆነ ትምህርት ይቀበላል እነዲሁም በተወሰኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ብቻ ላይ በመደገፍ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮን ይገነባሉ፡፡ አንዳንድ ክርስቲያኖች የዋስት መልዕክትን የፈልጋሉ፡፡ አንዳንዶች የማስጠንቀቂያ ደወልን አንተ በየትኛው ቡድን ውስጥ ነህ?*

▣ **"የእግዚአብሔር** *መንግስት" ይህን ሐረግ ለመተርጎም አስቸጋሪ ነው፡፡ ኢየሱስ በአገልግሎቱ ሐረጉን በብዛት ይጠቀምበታል ነገር ግን ደቀመዛሙርቱ በተሳሳተ መንገድ ተረድተውታል፡፡* (ሐዋ 1፡3,6) *በሐዋርያት ስራ መፅሐፍ ይሐረጉ ወንጌል የሚለው ቃል ተክት ይታያል፡፡* (ሐዋ 8፡12;19፡8;20፡25,28፡23፡31) *በሐዋ* 14፡22 *ስለመጨረሻው ዘመን ያመለክታል፡፡ "የተፈፀመ መንግስት"* (ማቴ 12፡28;ማርቆ 16፡6 *እና ገና የሚመጣ መንግስት* (ማቴ 24፡14,36-37; 25፡30,3); (2ጴጥ 1፡11) *የእግዚአብሔር መንግስት ወደ ምድር መታለች* (የኢየሱስ መምጣት) *ነገር ግን ደግሞ የአለም ፍፃሜ ሁለተኛው እንደሚመጣ ያመላክታ፡፡*

**14፡23 "ሽማግሌዎችን ከሾው በኃላ"** *ሽማግላች* (*presbuteros*) *"ጳጳሶች"* (*episkopos*) *እና መጋቢዎች ተመሳሳይነት አላቸው* (ሐዋ 20፡17,28 *እና ቲቶ* 1፡5,7)፡፡ *ስማግሌ የሚለው የአይሁድ ባህላዊ ንግግራቸው ነው፡፡* (Girdlestone *synonyms of the old testament*, pp 244-246 and frank stage, new testament theology, pp 262-264) *"ጳጳስ" እና "የበላይ ጠበቃ" የግሪለክ ሰዎች ቋንቋ መነጋገር ናቸው፡፡ የቤተክርስቲያን ቋንቋ መገልገያ የሆኑ ሁለት ቃሎች ብቻ ናቸው፡፡ በጋቢዎች እና ዲያቆናት* (ፊሊ 1፡1)፡፡

*"የሹመት" ፍቺ እጅን በማንሳት የሚደረግ ምርጫ የሚል ቀጥተኛ ትርጉም አለው፡፡* (2 ቆሮ 8፡19 እና louw and Nida, Greek English lexicon pp363,484) *ዘግይቶ በቤተክርስቲያን አባቶች ሹመት የሚለው ቃል በሰፊው አገልግሎት ላይ መዋል ጀመረ ነገር ግን ሹመት በእጅ ምርጫ የሚለው ትርጉም ለዚህ ዓውዱ እንዴት ለጠቅም ይችላል? በአዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት የነበረው የመሪዎች ምርጫ ቢደረግም ልምድን የማከለ አልነበረም* (በአንፃሩ በኢየሩሳሌም ባለች ቤተክርስቲያን እና የጳውሎስን በአህዛብ መካከል ያለውን አገልግሎቱን በመሾም ታፀድቅ ነበር)፡፡

"FF Bruce, *answers to questions*, p 79" በዚህ መፅሐፍ ላይ ሹመት ማለት እጅን በመዘርጋት ወይም በማሳየት መሆኑን በማስረጃ ተፅፎል። ነገር ግን በአዲስ ኪዳን ይህንን መመሪያ ባልጠበቀ መልኩ ሹመት ይደረግ እንደነበር የቤተክርስቲያን ታሪክ ይናገራል።

ጳውሎስ ቲቶን ሽማግሌዎችን እንዲሾም ነግሮታል ነገር ግን ጢሞቲዮስን የቤተክርስቲን መሪዎችን እንዲሾሙ አስጠንቅቆታል (ጢሞ 3)። በአዳዲስ ሥፍራዎች ላይ መሪዎች ይሾሙ ነበር። ግን በተደራጁ ስፍራዎች መሪዎች የመገኘት እድል ስላላቸው በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ዕውቅና ማግኘት ይኖርባቸዋል።

የጳውሎስ የሚስዮናዊነት አላማው የሚያተኩረው በሁለት ነገሮች ላይ ነው። ወንጌል መስበክ፣ ደቀ መዛሙርት ማድረግ ይህ የእግዚአብሔር የተመረጠ መንገድ ነው።

▣ **"ቤተክርስቲያን"** ልዩ ርዕስ 5:11 ላይ ያለውን ይመልከቱ።

▣ **"ጾመው ከፀለዩ በኃላ"** ከሐዋ 13:2-3 ጋር ተነፃፃሪ ነው። ጳውሎስ የዚህ ዓይነት የመንፈስን ሃይል እና ምሪትን የመቀበል ልምድ በአንፃኪያ ነበረው የዚያ ዓይነት ተመሳሳይ ልምምድ በዚህ ምዕራፍ ላይ ይታያል። እግዚአብሔር ፈቃዱን እንዲያመለክታቸው ዓይነተኛው መንገድ መፃምና መፀለይ ነበር።

▣ **"ለመኑበት"** እነዚህ አዲስ መሪዎች አማኞች ናቸው ነገር ግን እምነታቸው በስራቸው የሚፈተንበት ጊዜ በመድረሱ በፃምና በፀሎት ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ ተገቢ ነበር።

▣ **"ለጌታ አደራ ሰጡአቸው"** በግዜው የነበረውን የሹመትን አካሄድ የሚያወሳ ሐረግ ነው። በሐዋ 14:26 ላይ ተመሳሳይ ሹመት እንመልከት በሐዋ 20:32 መሪዎች ሆነው የተሸሙትን እንመልከት። እግዚአብሔር ለመሪነት የመረጣቸውን ሰዎች ማስተማር ተገቢ ነው። አማኞች መሃከል ማበላለጥ አፍራሽ እና መፅሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም ምክንያቱም እያንዳንዱ አማኝ ከእግዚአብሔር የተሰጠው ስጦታ አለው። (ኤፌ 4:11-12) በአዲስ ኪዳን የካህን እና የተራ ክርስቲያን ግንኙነት የሚባል የለም።

> **አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 14:24-28**
>
> **በጵስድያም አልፈው ወደ ጵንፋልያ መጡ በጴርጌንም ቃሉን ከተናገሩ በኃላ ወደ አጣሊያ ወረዱ ከዚያም ስለ ፈፀሙት ስራ ለእግዚአብሔር ፀጋ አደራ ወደ ተሰጡበት ወደ አንፃኪያ በመርከብ ሄዱ። በደረሱም ጊዜ ቤተክርስቲያኑን ሰብስበው እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ያደረገውን ሁሉ ለአሕዛብም የሃይማኖትን ደጅ እንደ ከፈተላቸው ተናገሩ ከደቀ መዛሙርትም ጋር አያሌ ቀን ተቀመጡ።**

14:24 ጲስድያ በከፍታ ቦታ የምትገኝ ሆና በሰሜን የባህር መንገድ በሆነው በጵንፋልያ አጠገብ ነች ጴርጌንም የዚህ አካባቢ የክልሉ ዋና ከተማ ነች። ሐዋሪያው ጳውሎስ በዚች ከተማ አልፋል (ሐዋ 13:13) ነገር ግን በዚህ ምንባብ ውስጥ ወንጌልን ለመስበክ እንደተመለሰ እንገነዘባለን።

12:25 **"ኢጣልያ"** የጴርጌን የባህር በር ነበረች።

14:26 **"ወደ አንፃኪያ በመርከብ"** ወደ ቆብሮስ አልተመለሱም፤ ነገር ግን በርናባስ ከጳውሎስ ጋር ሚርቆስ በተባለው በዮሐንስ ጉዳይ ከተከፋፈ በኃላ ወደዚች ከተማ መቶ ወንጌልን ሰብኳል። (ሐዋ 15:36-39)

▣ **"ለእግዚአብሔር ፀጋ አደራ ወደ ተሰጡበት"** ተደራጊ ግስን የሚያመለክት ሐረግ ነው፣የመጀመሪያው የሚሲዮናዊነት ተልኮ የተሳካ ነበር።

14:27 **"ቤተ ክርስቲያኑን ሰብስበው እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ያደረገውን ... ተናገሩ"** ስልጣን መገዛታቸውን ያመለክታል፤ ይህም ለአሕዛብ አብያተ ክርስቲያን ሁሉ እንደሆነ መገንዘብ አያዳግትም በተጨማሪም የስራ ባለቤት የሆነውን እግዚአብሔርን በሰው ሁሉ ፊት ያመሰግኑ ነበር።

የሐርያቱ የሰሩትን የወንጌል ስራ ለመሪዎች ብቻ ሳይሆን ለህዝቡ ሁሉ በማስረጃ የቀረቡ ነበር። (ሐዋ 15:4) ሐዋርያቱን ወደ ወንጌል ስራ እጅ በመጫን ለጌታ አደራ በመስጠት የቅዱሳን ሁሉ አስተዋፅኦ በቀላሉ የሚገመት አልነበረም።

▣ **"ለአሕዛበው የሃይማኖት በር እንደከፈተላቸው"** ጳውሎስ ይህንን በር "የእምነት በር" በማለት ስያሜ ሰቶታል። 1 ቆሮ 16:9;2 ቆሮ 2:12;ቆላ 4:3; እና እዕ 3:8 እግዚአብሔር ለሰው ዘር ሁሉ የወንጌልን በር መክፈቱን የሚያሳይም ነው፤ በመሆኑም ማንም ሊዘጋው አይችልም ኢየሱስ በሐዋ 1:8 ላይ የተነገረው ፍፃሜነቱን አገኙ።

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ለመርዳት ነው የተሰናዱት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋነኞቹን ጉዳዮች ለማጤን እንዲረዳ ነው። ሐሳብ ለማጫር እንጂ መደምደሚያ አይደሉም።

1. በጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ የጳውሎስን የመጀመሪያ የወንጌል ጉዞ በዝርዝር አስቀምጥ።
2. ለአይሁድና ለአሕዛብ ጳውሎስ ያቀረበው ስብከት በዝርዝር አስቀምጥ።
3. ያም በእንዴት አይነት መልኩ ነው ከዚህ ዘመን ክርስትና ጋር የሚገናኘው?
4. ለምንድነው ዮሐንስ ማርቆስ ከሚሽነሪ ቡድኑ የተገለለው?

# ሐዋርያት ሥራ 15

## የምንባቡ ክፍፍል በአዲሶቹ ትርጉሞች

| የተየመቅሰ[4] | አኪጀት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የኢየሩሳሌም ስብሰባ | በግርዛት ርዕስ ያለመስማማት | በአሕዛብ መግባት ላይ ክርክር | በኢየሩሳሌም ስብሰባ | በአንፃኪያ የነበረ ክርክር |
| 15፡1-5 | 15፡1-5 | 15፡1-5 | 15፡1-2 | 15፡1-2 |
| | | | 15፡3-5 | 15፡3-4 |
| | | | | በኢየሩሳሌም የነበረ ክርክር |
| | በእየሩሳሌም የነበረ ስብሰባ | | | 15፡5-7 |
| 15፡6-11 | 15፡6-21 | 15፡6-21 | 15፡6-11 | የጴጥሮስ ንግግር |
| | | | | 15፡7b-11 |
| | | | 15፡12-18 | 15፡12 |
| | | | | የያዕቆብ ንግግር |
| | | | | 15፡13-18 |
| | | | 15፡19-21 | 15፡19-21 |
| የስብሰባው ምላሽ | በኢየሩሳሌም የነበረ አዋጅ)ድንጋጌ | | ለአህዛብ የተፃፈ ደብዳቤ | ሐዋርያዊ ደብዳቤ |
| 15፡22-29 | 15፡22-29 | 15፡22-29 | 15፡22-29 | 15፡22-29 |
| | በሲሪያ የቀጠለው አገልግሎት | | | በአንፃኪያ ተወካዬች |
| | 15፡30-35 | 15፡30-35 | 15፡30-34 | 15፡30-35 |
| | | | 15፡35 | |
| ጳውሎስና በርናባስ ተለያዩ | በማርቆስ ዮሐንስ ምክንያት የመጣ ክፍፍል | በሁለተኛው የሚሽን ጉዞ ተለያዩ | ጳውሎስና በርናባስ ተለያዩ | ጳውሎስ ሲላሰን መረጠ |
| 15፡36-41 | 15፡36-41 | 15፡36-41 | 15፡36-41 | 15፡36-38 |
| | | | | 15፡39-40 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (ከ "**መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ**" **ገጽ** vii)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

*ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።*

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. ምንባብ አንድ

2. ምንባብ ሁለት

3. ምንባብ ሶስት

4. ወ.ዘ.ተ ……

**የአውዱ ዕይታ**

ሀ. ይህ ምዕራፍ "የኢየሩሳሌም ስብሰባ" በመባል ይታወቃል።

ለ. በዚህ ምዕራፍ በግልፅ የሚታየው የጥንቲቱ ቤተ ክርስቲያን የስነ መለኮት አቋሟን የገለፀችበት ምንባብ ነው፤ በተለይ በኢየሩሳሌም እና በአንፃኪያ ሁለት የእግዚአብሔር መንግስት ተቋሙ የተመሰረተበት ቦታም ነው።

ሐ. አይሁዳያውያን ያልሆኑ ወደ ክርስቶስ መምጣታቸው ሁሉን ግራ የሚያጋባ አንገብጋቢ ርዕስ ነበር (ሐዋ 8-11)።

መ ይህ ምዕራፍ ከገላትያ ሁለት ጋር ዝምድና ስላለው አጨቃጫቂ ርዕስ ጉዳይ ነው። ሐዋ 15 እና 11፡30 የገላትያ ምዕራፍ ሁለት ዋና ሃሳብ የተፃፈበት ምዕራፎች ናቸው።

ሠ. የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ በተለይ በልሳን መናገር የተለመደ መሆኑ ለአህዛብ ድነት ምልክት ሆኖ አገልግሏል (ሐዋ 2፣8 እና 10)።

**የቃል እና የጥምር ቃል ጥናት**

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 15፡1-5**
**አንዳንዶችም ከአይሁድ ወረዱና እንደ ሙሴ ስርዓት ካልተገረዛችሁ ትድኑ ዘንድ አትችሉም ብለው ወንድሞችን ያስተምሩ ነበር። በእነርሱና በጳውሎስ በብርናባስም መካከል ብዙ ጥልና ክርክር በሆነ ጊዜ ስለዚህ ክርክር ጳውሎስና በርናባስ ከእነርሱ አንዳንዶች ሌሎች ሰዎች ወደ ሐዋርያት ወደ ሽማግሌዎችም ወደ ኢየሩሳሌም ይወጡ ዘንድ ተቋረጠ። ቤተ ክርስቲያኑም በመንገድ እየረዳቸው እነርሱ የአህዛብን መመለስ እየተረኩ በፊንቂና በሰማርያ አለፉ ወንድሞችንም ደስ አሰኙአቸው። ወደ ኢየሩሳሌም በደረሱ ጊዜ ቤተ ክርስቲያንና ሐዋርያት ሽማግሌዎችም ተቀበሉአቸው እግዚአብሔርም ከእነርሱ ጋር ያደረገውን ሁሉ አወሩ ከፈሪሳውያን ወገን ግን ያመኑት አንዳንዶቹ ተነስተው ትገርዛቸው ዘንድና የሙሴን ሕግ እንዲጠብቁ ታዙአቸው ዘንድ ይገባል አሉ።**

**15፡1 "አንዳንዶች ከአይሁድ ወረዱና"** እነዚህ አይሁዶች አማኞች ሆነው ለአይሁድ ሃይማኖት እና ለኢየሱስ ምስክር ለመሆን ታማኞች ነበሩ:: ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን ትንቢት ፍፃሜ እንደሆነ የሚያምኑ ናቸው (ሐዋ 11፡2፣፡15፡5 ገላ 2፡12) እነዚህ አይሁዶች በኢየሩሳሌም ካላቸው ቤተክርስቲያን ጋር የጠበቀ ግንኙነት ነበራቸው። (ሐዋ 15፡24) ነገር ግን መሪዎች ወይም ቤተክርስቲያን የወከለቻቸው ሰዎች አልነበሩም በካርታ ይሁዳ ከኢየሩሳሌም በከፍታ ቦታ አትገኝም ነገር ግን ለአይሁድ ከኢየሩሳሌም ከፍ ያለች ሌሎች ከተሞች ግን ዝቅ ያሉ እንደሆነ ይቆጠር ነበር።

▣ "ያስተምሩ ነበር" ሁለት ሃሳብን ያንፀባርቃል።
1. ማስተማር ጀምረዋል
2. በተደጋጋሚ እያስተማሩ ነው።

▣ **"ካልተገረዛቹ"** ለአብረሃም እና ለዘሮቹ የተሰጠ የቃል ኪዳን ምልክት ነው (ዘፍ 17፡10-11) ለአይሁዳውያን ይህ ስርዓት ቀላል ዓመት የሚሰጠው አይደለም፤ ለደህንነትም አስተዋጾኦ እንዳለው ያስባሉ እነዚህ ሰዎች በክርስቶስም ለሙሴም በተሰጠው ሕግ ያምናሉ (ሐዋ 15፡5) በመሆኑም መዳን የሚገኘው እነርሱ በሚያደርጉት መልካም ስራ እንደሆነም ያስተምራሉ የአንድ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረው ግንኙነቱ የሚመዘነው ሃይማኖተኛ በመሆኑና የምኩራብ ስርዓት አክባሪ በመሆኑ እንደሆነ በስፋት ያስተምራሉ።

**15፡2 "በጳውሎስና በብርናባስም መሃከል ብዙ ጥልና ክርክር በሆነ ጊዜ"** ፀሐፊው ሉቃስ የነበረውን አለመስማማት **"ብዙ ጥልና ክርክር"** የሚለውን ሐረግ ተጠቅሟል። (ሉቃ 23፡19፣25፣ ሐዋ 15፡2፣ 40፣23፡7፣ 10፣ 24፡5) ይህ አለመስማማት ለወንጌል አስተዋጾኦ ነበረው እርሱም፡ (1) የእግዚአብሔር ወገንተኛ በመሆን ወንጌልን ለመስበክ የተቆረጠበት ቦታ ነው (2) የሙሴ ህግጋት ሳይሻሩ አዲሱን ኪዳን ለመናገር የወሰኑበት ቦታም ነው።

▣ **"ወንድሞች ---- ቆረጡ"** የቤተክርስቲያን ውሳኔ የምታስተላልፍ አካል እንደሆነች የሚያረጋግጥ ዐረፍተ ነገር ነው። በሐዋርያት ምዕራፍ 15 ላይ የተለያዩ የአመራር አይነቶች እንደነበሩ መገንዘብ ይቻላል። በዚህ ምዕራፍ ቁ. 2፣3፣12 እና 22 ላይ የቤተክርስቲያን አባላት ስልጣን ተፅፏል። ይህም የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን እና የአንግሊካል ቤተክርስቴያን የምትተዳደርበት ነው። በቁጥር 6 እና 22 ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ስልጣን ተጠቀሷል። አዲስ ኪዳን መፅሐፍት የእነዚህን ሁሉ የአመራር አይነት ተጠቅሶ እናነባለን። ሐዋርያቶች ባንቀላፉ ጊዜ ቀጣዩን አመራር ሌሎች ተረክበዋቸዋል።

▣ **"ሌሎች ሰዎች"** (A.T. Robertson, *Word Pictures in the New Testament*, P. 224, በዚህ ጥቅስ ላይ ሃሳብ የሚሰጥ በመሆኑ ማንበቡ ጠቃሚ ነው። ሌሎች ሰዎች የተባሉት ቲቶ እና የሉቃስ የስጋ ወንድሙ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ መላምታ ነው፤ እንጂ በሐዋርያት ስራ የተጠቀሰ አይደለም። (ገላ 2:1፣3)

▣ **"ወደ ሐዋርያት"** በዚህ ጊዜ በኢየሩሳሌም የነበረው የአመራር መዋቅር ገና አልተደራጀም ነበር። ነገር ግን ሌሎች ትርጉሞች የኢየሱስ ወንድም ያዕቆብ በኢየሩሳሌም ላላቸው ቤተክርስታያን በዚህ ጊዜ መሪ እንደነበር ያወሳሉ። በመሆኑም አንድ የተዋቀረ የመሪዎች ቡድን እንደነበር ይታሰባል።
(ሐዋ 15:4፣22) እነርሱም፡

1. አስራ ሁለቱ ሐዋርያቶች
2. የቤተ ክርስቲያኒቱ ሽማግሌዎች
3. የቤተ ክርስቲያኒቱ አማኞች

የኢየሱስ ወንድም የሆነው ያዕቆብ በዚህ ምንባብ ከተጠቀሱት ሐዋርያት ጋር መመደቡን አልተረጋገጠም፤ ነገር ግን ሐዋርያም ደግሞም የቤተ ክርስቲያን መሪ ተብሎ ተጠቅሷል። (ገላ 1:19) ሌሎችንም እንመልከት፡- ጴጥሮስ ራሱን "መሪ" በማለት ስያሜ ሰቷል 1 ጴጥ 5:1 እና ዮሐንስም እንዲሁ 1ዮሐ እና 3ዮሐ) ይመልከቱ።

▣ **"ሽማግሌዎች"** እነዚህ መሪዎች በእድሜአቸው ያረጁ ልምድ አላቸው የሚባሉ ከምኩራብ አገልግሎት ይመረጣሉ። (ሐዋ 11:30 ወይም 14:23)

15:3 **"ቤተክርስቲያን"** ልዩ ርዕስ 5:11 ላይ ያለውን ይመልከቱ።

▣ **"በፋንቄ እና በሰማርያ አለፈ"** ፊንቄያውያን አህዛቦች ሲሆኑ ነገር ግን ሰማርያውያን የአህዛቦች እና የአይሁዳውያን ውህደት የሆኑ ህዝቦች ናቸው። ከዚህ ቀደም የሰማርያ ከተማ ሰዎች ወንጌልን ለመስማት ዕድል አግኝተዋል።)ሐዋ 8:5፣ 11:19)

▣ **"የአሕዛብን መመለስ እየተረኩ"** ጳውሎስ እና በርናባስ እግዚአብሔር በአህዛብ መሃከል ያደረገውን ስራ ለየቤተክርስቲያን ይመሰክሩ ነበር፤ ከእነዚህም መሐከል የብሉይ ኪዳንን የተስፋ ቃል ጠንቅቀው የሚያውቁ ይገኙበታል።

በመሆኑም በኢየሩሳሌም ያለችው ቤተክርስቲያን ይህንን የአህዛብ ወደ እግዚአብሔር በፀጥታ እና በሚስጥር ታሰራጭ ጀመር (ሐዋ 21:18-20)

▣ **"ወንድሞችን ደስ አሰኙአቸው"** ይህ የአህዛብ መንደር ቢሆንም አብያተ ክርስቲያናት ግን አይሁድን እና አህዛቦችን በጋራ እንዳያመልኩ አዲስ ስርዓት አዋቅረው ነበር። ይህ በኢየሩሳሌም ለምትገኘው ቤተክርስቲያን የብሉይ ኪዳኑ ትንቢት ፍፃሜ አመልካች ነበር። አለም አቀፍ ቤተክርስቲያን የግሪኮች ቤተክርስቲያንን በመክፈት አዲስ ኪዳን መምጣቱን አበሰረች።

15:4 **"ቤተክርስቲያንና ሐዋርያት ሽማግሌዎችም"** የቤተ ክርስቲያን የአመራር ስብስቡን ያመለክታል። (ሐዋ 15:22)

▣ **"እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ያደረገውን አወሩ"** ይህ አደራረግ የጥንቲቱ ቤተክርስቲያን የምትከተለው ህግ ሆነ።

15:5 **"ከፈሪሳውያን ወገን ግን ያመኑት"** በዚህ ዘመን በአይሁድ ሃይማኖትና በክርስትና መሃከል የነበረው ልዩነት የተራራቀ አልነበረም፤ በኢየሱስ ማመን ማለት በአይሁድ ሃይማኖት በመሲሁ እንደማመን ነው። ነገር ግን በቤተክርስቲያን የተለያዩ ሃሳቦች በክርስትና ሃይማኖት ላይ ስለነበሩ ይህም ለእስራኤል በተሰጠው የተስፋ ቃል ላይ ብዙ ግልፅ ያልሆነ ነገር የነበረበት ዘመን ነበር እነዚህ በዚህ ምዕራፍ ላይ ያሉ የዳኑ አይሁድ የብሉይ ኪዳን ህግጋት መጠበቅ እንዳለበት አጥብቀው የሚያምኑ ናቸው፤ ይህም ማለት በኢየሱስ ማመን እና ሙሴን መታዘዝ የሚል አቋም ነበራቸው የሙሴ ስርዓቶችም እንዲጠበቁ ያስተምራሉ እነዚህም፡ [1] ግርዘት [2] ለቤተክርስቲያን ገንዘብ መስጠት [3] ህጉችን መጠበቅ እና ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል።

አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 15፡6-11

*ሐዋርያትና ሽማግሌዎችም ስለዚህ ነገር ለመማከር ተሰበሰቡ ከብዙ ክርክርም በኃላ ጴጥሮስ ተነስቶ እንዲህ አላቸው ወንድሞች ሆይ አህዛብ ከአፌ የወንጌልን ቃል ሰምተው ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር በመጀመሪያው ዘመን ከእናንተ እኔን እንደ መረጠኝ እናንተ ታውቃላችሁ። ልብንም የሚያውቅ አምላክ ለእኛ ደግሞ እንደ ሰጠን መንፈስ ቅዱስን በመስጠት መሰከረላቸው ልባቸውንም በእምነት ሲያነፃ በእኛና በእነርሱ መሃከል አንዳች አልለየም። እንግዲህ አባቶቻችንና እኛ ልንሸከመው ያልቻልነውን ቀንበር በደቀ መዛሙርት ጫንቃ ላይ በመጫን እግዚአብሔር አሁን ስለ ምን ትፈታተናላችሁ? ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋ እንደ እነርሱ ደግሞ እንድን ዘንድ እናምናለን።*

15፡6 **"ሐዋርያትና ሽማግሌዎችም"** በመጀመሪያ በመሪነት ላይ ያሉ ተገናኝተው ከተወያዩ በኂላ ውሳኔ ያስተላልፉ ነበር፤ ይህ የፕሪስፔትሪያን ወግና ስርዓት ነው።

15፡7 **"ከብዙ ክርክር በኂላ"** የቤተክርስያኒቱ መሪዎች አለመስማማታቸውን የሚገልፅ ዐረፍተ ነገር ነው። ከእነዚህ አንዳንዶቹ በቁጥር 5 ላይ የተፃፈውን ይስማሙበታል ሌሎቹ ደግሞ በለመዱት ወግና ሰርዓ መኖር ይፈልጋሉ። ሐዋርያትም በሐዋ 8፡1 ላይ የተፃፈው ምክንያቱን አላስተዋሉም ነበር። በአይሁድ መሃከል ህግጋት የሚፀድቁት በሶስት መንገዶች ነው። (1) በመሪዎች ውይይት (2) ግልፅ በሆነ ውይይት (3) ከህዝቡ ጋር በግልፅ በመወያየት ህጐች ይቀርፁ ነበር።

▣ **"ጴጥሮስም ተነስቶ"** ሰዎች በተሰበሰቡ ጊዜ ንግግር የሚያደርግ ማንም ሰው ቆሞ የመናገር ልማድ ነበር በቆርኖሊዮስ ቤት የነበረው ይሄው አይነት ልምምድ ነው (ሐዋ 10-11)።

▣ **"አሕዛብ የወንጌልን ቃል ሰምተው ያምኑ ዘንድ"** እግዚአብሔር ጴጥሮስን ፍቅሩን ለአህዛብ ለማሳየት ተጠቀመበት።

1. በመጀመሪያ ለሰማሪያ ሰዎች ምዕራፍ ስምንት
2. በሁለተኛ ደረጃ ለኢትዮጰያዊው ጃንደረባ ምዕራፍ ስምንት
3. ለቆርኖሊዎስ ቤተሰቦች (ምዕራፍ 10-11)

እነዚህ ሙሉ በሙሉ የአህዛብ ስራዎች አይለማመዱም ነበር። ከአይሁዶች ጋር ይቀራረቡ ነበር። ይሁን እንጂ 1 እና 3 በጴንጤቆስጤው ልምምድ ተካተዋል። እግዚአብሔር ሌሎችን ሕዝቦች እንደተቀበለ በሚያረጋግጠው ክፍል ላይ።

15፡8 **"ልብን የሚያውቅ አምላክ"** የእግዚአብሔርን ፍፁም አዋቂነት የሚናገር ነው። (1 ሳሙ 16፡7፣ ምሳ 24፡12፣ ኤርም 17፡10፣ ሐዋ 1፡24፣ ሮሜ 8፡27፣ ራዕ 2፡23)

▣ **"መንፈስ ቅዱስን በመስጠት"** በሐዋርያት ስራ ምዕራፍ ሁለት ያለው ተመሳሳዩ ልምምድ ነው (በእኛም ዘመን ተመሳይ ልምምድ አለ) ይህ ልምምድ በኢየሩሳሌም፣ በሰማርያ እና በቂሳሪያ በስፋት ታይቷል። የአመኑ አይሁድ ከሌሎች አይሁዶች የሚለዩት በዚህ ነው።

15፡9 **"በእኛና በእርሱ መሃከል አንዳች አልለየም"** የጴጥሮስ የተቀየረው የስነ መለኮት አስተሳሰቡ ነው፤ የሐዋ 10፡28፣34፣11፡12) የሰው ዘር ሁሉ በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥሮአል (ዘፍ 1፡26-27) እግዚአብሔር ሰው ሁሉ እንዲድን ይፈልጋል። (ዘፍ 12፡3፣ ዘፀ 19፡5-6፣ 1ጢሞ 2፡4፣ 4፡10፣ ቲቶ 2፡11፣ 2ጴጥ 3፡9)

▣ **"ልባቸውንም በእምነት ሲያነፃ"** የሌዋውያንን የመንፃት ስርዓት ያመለክታል ፤ ከእግዘአብሔር የሚለየን በደል መወገዱን ይገልፅል።

የጴጥሮስን ልምምድ በመመልከት ግንዛቤ ማየት እንችላለን (ሐዋ 10፡15 እና 11፡19፣ ዘፍ 7፡2፣8፡8፡20)።

በሉቃስ ወንጌል ላይ የለምፅ መንፃትን ይናገራል (ሐዋ 4፡27፣5፡12፣13፣7፡22፣17፡14፣17) ከሃጢያት መንፃት (ዕብ 9፡22፣23፣1ዮሐ 1፡7)።

ልክ በብሉይ ኪዳን የሚያመለክተው መላይ ስብዕናን ነው። እንዚህ አህዛቦች በእግዚአብሔር ሙሉ ለሙሉ ተቀባይነትን አግኝተዋል። በእግዚአብሔር መንፃታቸው እና ተቀባይነት ማግኘታቸው የወንጌልን አላማ ግልፅ አድርጐ ያሳየ ነው።

15፡10 **"እግዚአብሔርን አሁን ስለ ምን ትፈታተኑታላችሁ"** ዘፀ 17፡2፣7 እና ዘዳ 6፡16 ጋር ተመሳሳይ ነው። የግሪኩ ፅሑፍ "ትፈታተኑታላችሁ" የሚለውን እንዲያጠፋን ስለምን ትፈትኑታላችሁ" በሚል ተክቶታል። ይህ ተጨማሪ ውይይት የሚያስፈልገው በመሆኑ "ፈተና" የሚለውን ልዩ ትኩረት የሚያሻው በሚለው ርዕስ ስር ተመልከቱ።

▣ **"ቀንበር"** ቃሉ የህግን ክብደት ለሚመለከት ነው (ዘዳ 6፡4-፣ ማቴ 23፡4፣ ሉቃ 11፡46፣ ገላት 5፡1)።

15፡10 **"አባቶታችንና እኛ ልንሸከመው ያልቻልነውን"** በሉቃ 14፡46 የሚገኘውን የኢየሱስን ትምህርት የሚያንፀባርቅ ሐረግ ነው፤ በተጨማሪም ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች በምዕራፍ ሶስት ላይ ጠቅሶታል።

የሰው ዘር ህግጋትን በመጠበቅ ወደ ደህንነት መምጣት አልቻለም ምክንያቱም በሃጢያት የተሸነፈው የሰው ሰውነት የእግዚአብሔርን ቅዱስ ህግ መጠበቅም እና መፈፀም አቅም የለውም (ሮሜ 7) በተጨማሪም በህግ ስራ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቸር ስጦታ በሆነው በኢየሱስ፣ በእምነት እና ለእግዚአብሔር በቅድስና ለመኖር በመወሰን ብቻ ደህንነት ማግኘት ይቻላል። (ማቴ 11:30፣ ኤፌ 1:4፣2:10) ክርስቶስን መምሰል የክርስትና ህይወት የመጀመሪያው ግብ ነው በመሆኑም ይህ እውነተኛ ኑሮ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግስት ይጠራል።

15:11 ይህ ጥቅስ በፀጋ በኩል በእምነት ስለመዳን የሚያወሳ የማጠቃለያ ሃሳብ ነው። (ሐዋ 2-3፣ ሮሜ 3-8፣ ገላ 3፣ ኤፌ 1-2) የድነት መንገድ ለአይሁድ እና ለአህዛብ አንድ አይነት መሆኑን እንገነዘብ (ሮሜ 4 ኤፌ 2:1-10)።

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 15:12-21**

**ሕዝቡም ሁሉ ዝም አሉ በርናባስና ጳውሎስም እግዚአብሔር በእጃቸው በአህዛብ መካከል ያደረገውን ምልክትና ድንቅ ሁሉ ሲተርኩላቸው ይሰሙ ነበር። እነርሱም ዝም ካሉ በኂላ ያዕቆብ እንዚህ ብሎ መለሰ ወንድሞች ሆይ ስሙኝ። እግዚአብሔር ለስሙ የሚሆንን ወገን ከአህዛብ ይወስድ ዘንድ አስቀድሞ እንዴት እንደ ጐበኘ ስምኦን ተርኮአል። ከዚህም ጋር የነቢያት ቃል ይስማማል እንዲህ ተብሎ እንደ ተፃፈ፡ ከዚህ በኂላ የቀሩቱ ሰዎችና በስሜ የተጠሩት አህዛብ ሁሉ ጌታን ይፈልጉ ዘንድ እመለሳለሁ የወደቃችውንም የዳዊትን ድንኳን እንደ ገና እሰራታለሁ፤ ፍራሻ*ንም እንደ ገና እሰራታለሁ፤ እንደ ገናም አቆማታለሁ ይላል፤ ይህን የሚያደርግ ጌታ ከጥንት ጀምሮ ስራው ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቀ ነው። ስለዚህ ከአሕዛብ ወደ እግዚአብሔር የዘሩትን እንዳናስቸግራቸው ነገር ግን ከጣኦት ርኩሰትና ከዝሙት ከታነቀም ከደምም ይርቁ ዘንድ እንድንፅፍላቸው እቆርጣለሁ። ሙሴስ ከቀደሙት ትውልድ ጀምሮ በሰንበት በምኩራቦቹ ሲያነቡ በየከተማው እርሱን የሚሰብኩ አሉት።**

15:12 "**ሕዝቡም ሁሉ ዝም አሉ --- ይሰሙ ነበር**" የሐዋርያው ጴጥሮስ ንግግር የመሪዎችን እና የህዝቡን ልብ አሳርፏል። በዚህ ጊዜ የጳውሎስ እና የበርናባስ ሁለተኛው የሚሲዮናዊነት ጉዞ ምስክርነት በቤተክርስትያን መሪዎች እየተደመጠ ያለበት ጊዜ ነው። ነገር ግን በዚህ ጊዜ የሚባለውን ሁሉ ለማድመጥ መሪዎች ዝም ያሉበት ጊዜ ነው።

▣ "**በርናባስና ጳውሎስ**" መጀመሪያ የበርናባስ ስም የተፃፈበት ምክንያት እርሱ የሚያገግልባት ቤተ ክርስቲያን በመሆኑዋ ነው።

▣ "**ያደረገውን ምልክትና ድንቅ**" በሐዋርያት ስራ ምዕራፍ ሁለት የተከሰተው ከፍተኛ የመንፈስ ቅዱስ መውረድ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ሰውን መቀበሉን በግልፅ ለማስገንዘብ ነው።

በሐዋርያት እና በኢየሱስና በሰባቱ ዲያቆናት ተደጋጋሚ የሆነ ተአምራት ተደርጓል (ሐዋ 2:22፣ 2:43፡3:7፣4:16፣30፣5:12፣6:8፣8:6፣13፣14:3፣15:12) እግዚአብሔር በሚደረጉ ተዓምራት የሰዎች ልብ ለወንጌል እንዲከፈት በአገልጋዩቹ ይጠቀማል። እንዚህ ተዓምራቶች ለአይሁድ የሃይማኖት ፅንፈኞች እግዚአብሔር አህዛብን እንደተቀበላቸው የሚያሳይ ግልፅ የሚታይ ማስጠንቀቂያ ያለበት የሚስማማ ምልክት ነው።

15:13 "**ያዕቆብ**" ይህ ሐዋርያው ያዕቆብ አይደለም ምክንያቱም በሐዋ 12:1-2 ያዕቆብ ተገድሏል። ይህ ያዕቆብ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንድም ነው። እርሱም በኢየሩሳም ባለች ቤተክርስቲያን መሪና የያዕቆብ መፅሐፍ ፀሐፊ ነው። "ያዕቆብ ፃድቁ" ወይም "የግመል ጉልበት" የሚል ቅፅል ስያሜ ነበረው። በኢየሩሳሌም ያዕቆብና ጴጥሮስ ዋና መሪዎች ነበሩ። (ሐዋ 12:17)

15:14 "**ስምኦን**" በአራማይክ ቋንቋ "**ሳይመን**" ማለት ጴጥሮስ ማለት ነው (2 ጴጥ 1:1)።

▣ "**በእግዚአብሔር ለስሙ የሚሆንን ወገን ከአሕዛብ ይወስድ ዘንድ**" የቡሉይ ኪዳን ነብያቶች የዓረፍተ ነገር አገላለፅን ያመለክታል። (ኢሳ 45:20-23፣ 49:6፣ 52:10) የእግዚአብሔር ሕዝቦት አሕዛብንም አይሁድንም ያጠቃልላሉ። (ዘፍ 3:15፣ 12:3፣ ዘፀ 9:16፣ ኤፌ 2:11-3:13) "**ለስሙ**" የሚለው ቃል የተወሰደው ከኤር 13:11 እ 32:20 ወይም ኢሳ 63:12፣14) ነው።

15:15-18 "**ተብሎ እንደ ተፃፈ**" ከአሞፅ 9:11-12 የተጠቀሰ ነው። የሰው ዘር የሚለው ቃል በቁ.17 ላይ "**ኤዶም**" ወይም (አለማት) በማለት የዕብራይስጡ መፅሐፍ ላይ ይገኛል። ነገር ግን በግሪኩ ፅሑፍ ላይ ደግሞ "**አንትሮፖስ**" ይላል በመሆኑም ያዕቆብ ሃሳቡን በዚህ ምንባብ ሲናገር የፈለገው የእግዚአብሔር ፍቅር ለሁሉ እንዲሆን ለመናገር ነው።

15:16 ምንባቡ የሚያመለክተው ያዕብ ከብሉይ ኪዳን መፅሐፍ በመጥቀስ ጥቂትና ግልፅ ማሻሻያ በማድረግ የአሕዛብን ወደ እግዚአብሔር መንግስት መቀላቀል የተናገረበት ነው። ያዕቆብ ከብሉይ ኪዳን መፅሐፍ በመጥቀስ ጥቂትና ግልፅ ማሻሻያ በማድረግ የአህዛብን ወደ እግዚአብሔር መንግስት መቀላቀል የተናገረበት ነው። ያዕቆብ ጥቅሱን የጠቀሰው የብሉይ ኪዳን የሙሴ የሃይማኖት ስርዓት አያመለክተ ይሆንን? አዲሱ ኪዳን በእርግጥ አዲስ እንደሆነ በሚከተሉት ማስረጃ መመልከት ይቻላል።

1. መዳን በስራ ሳይሆን በፀጋ ሆኖአል።

2. መሲሁ ተኮር እንጂ መቅደስ ተኮር አይደለም (ኢየሱስ አዲሱ መቅደስ ነው)
3. መዳን ለአይሁድ ብቻ መሆኑ ቀርቶ ለህዝብ ሁሉ ሆኖአል፡፡

ይህ ያልተጠበቀ የኪዳን ለውጥ ብዙ ሃይማኖተኛ አይሁድን ያስደነገጠ ቢሆንም ነገር ግን ከሐዋርያት ዋና የሆነው ጴጥሮስ፣ የአይሁድ መምህር የነበረው ጳውሎስ እና በኢየሩሳሌም ላለችው ቤተክርስትያን መሪ የነበረው ያዕቆብ ይህንን አዲስ አሰራር ተቀብለውት ነበር፡፡

15፡18 አህዛቦች ወደ እግዚአብሔር መንግስት መጠቃለላቸው የእግዚአብሔር የቀድሞ የዘላለም ሃሳቡ ነው፡፡ (ገላ 3፡26-29፤ኤፌ 3፡3-6) የደህንነት የዘፍ ግንድ በዳዊት ቤተሰብ ዘር የመጣ ነው፡፡ (ሐዋ 15፡16)

15፡19 ይህ ጥቅስ የሚገልፀው የያዕቆብን የመደምደሚያ ንግግር ነው፡፡

15፡20 በሁለት መንገዶች ጥቅሱን ማጤን ይቻላል፡ (1) አህዛቦችና አይሁድን በአንድ ላይ መመገብ ጀምረዋል፡፡ (2) ወንጌል ለአይሁድ እየተዳረሰ የነበረበት ጊዜ ነው፡፡

በዘሌዋውያን መፅሐፈ የሙሴ ህግ በአይሁድ እና በከነዓናውያን መሃከል የማህበራዊ ኑሮ እና የሃይማኖት ሕብረት እንዳይኖር ያዛል ነገር ግን በዚህ ምዕራፍ የሚታየው ስርዓቶች ህብትን ለማድረግ ሲያገለግሉ በግልፅ ይታያሉ፡፡ (አይሁድንና አህዛቦችን)

ከዚህ የሃይማኖት ስርዓቶችና ወጐች በኋላ የሐዋርያት ህግጋት የሚባለው ህግ ተቀርፃ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ ለተጨማሪ ገለፃ የሚከተለውን መፅሐፍ አንብቡ (Bruce M-Metzger's *A Textual Commentary on the Greek New Testament*, PP 429-434)፡፡

▣ "ከታነቀም ከደምም ይርቁ ዘንድ" አብዛኞቹ የመፅሐፍ ቅዱስ አዋቲዎች ከሙሴ የምግብ ስርዓት ጋር ያቆራኙታል፡፡ (ዘሌ 17፡8-16) በሙሴ ሕግ "ደም" የሚያመለክተው ግድያን ነው፡፡

15፡21 ይህ ጥቅስ ትርጉሙ፡ (1) አህዛቦች የሙሴን መፅሐፍት እየተማሩት ነበር፣ (2) አይሁድ በነበሩበት ቦታ ሁሉ ይህንን ቃል ያስተምሩት ነበር (2ቆሮ 3፡14-15)፡፡

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 15፡22-29**

***ያን ጊዜ ሐዋርያት ሽማግሌዎች ከቤተክርስቲያኑ ሁሉ ጋር ከእነርሱ የተመረጡትን ሰዎች ከጳውሎስ እና ከበርናባስ ጋር ወደ አንፃኪያ ይልኩ ዘንድ ፈቃድ ፤ እነርሱም በወንድሞች መሃከል ዋናዎች ሆነን በርስያን የተባለው ይሁዳና ሲላስ ነበሩ እንዲህም ፅፈው በእነርሱ እጅ ላኩ ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ወንድሞችም በአንፃኪያና በሶሪያ በኪልቅያም ለሚኖሩ ከአህዛብ ወገን ለሆኑ ወንድሞች ሰላምታ ያቀርባሉ፡፡ ያላዘዝናቸው ስዎች ከእኛ ወተው ትገረዙ ዘንድና ሕግና ትጠብቁ ዘንድ ልገባችኋል ብለው ልባችሁን እያወኩ በቃል እንዳናወጡአችሁ ስለ ስማን ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቴስ ስም ነብሳቸውን ከሰጡት ከምንወዳቸው ከበርናባሰና ከጳውሎስ ጋር የተመረጡትን ሰዋች ወደ እናንተ እንልክ ዘንድ በአንድ ልብ ሆነን ፈቃድን ራሳቸውም ደግሞ በቃላቸው ያንኑ ይነግሩአችሁ ዘንድ ይሁዳንና ሲላስን ልከናል፡፡ ለጣኦት ከተሰዋ ከደምም ከታነቁም ከዝሙትም ትርቁ ዘንድ ከዚህ ከሚያስፈልገው በቀር ሌላ ሸክም እንዳንጭንባችሁ እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናልና ከዚህም ሁሉ ራሳችሁን ብትጠብቁ በመልካም ትኖራላችሁ ጤና ይስጣችሁ፡፡***

15፡22 መልእክተኞች የተላኩበት ዓላማ አንድነትን ለማሳወቅ ነው እንጂ ጥያቄን ለመመለስ አይደለም፡፡

▣ "በርስያን የተባለው ይሁዳንና" በአዲስ ኪዳን ታማኝ መሪዎች ከሚባሉት አንዱ ነው ነገር ግን ሰው ብዙ የሚታወቅ አይደለም፡፡

ይህ ሰው አስቆርቱ ይሁዳን ሊተካው ለነበረው በርስያን ዮሴፍ ለሚባለው ወንድም ነው (ሐዋ 1፡23)

▣ "ሲላስ" በኢየሩሳሌም ባለችው ቤተ ክርስቲያን መሪ ነበር ይህ ሰው በጳውሎስ"ሲልሳነስ"_የሚል ስያሜ መቶለታል በኂላም በርናባስን በመተካት ከጳውሎስ ጋር ሁለተኛውን የሚስተናዊነት ጉዞ አድርጓል፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ ሲላሰን የመረጠበትን ምክንያት እንመልከት፡ (1) ከአስራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት በተለይ መንገድ ወንጌልን ይሰብክ ስለነበር፡፡ (2) ከሌሎች አብያተ ክርስቲያን ጋር ልምድ ስለነበረው የሚጠየቀውን ጥያቄ ለመመለስ ብቁ እንደሆነ ጳውሎስ ስላሰበ ነበር፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ "ሲላስ"**

ሲላስ በጳውሎስ ሁለተኛ የሚስቶናዊነት ጉዞው አብሮት የሄደ ሰው ነው፡፡

ሀ. በመፅሐ ቅዱስ "ሲላስ" የተጠቀሰው በወንድሞች መሃከል ዋና ተደርጐ ተመርጦ ቤተ ክርስቲያንም ሃላፊነትን በመስጠት አደራ የሰጠችው ነው (ሐዋ 15፡22)፡፡

ለ. ነብይ ነበር (ሐዋ 15፡32)፡፡

ሐ. የሮማውያን ዜግነት እንደ ጳውሎስ ነበረው (ሐዋ 16፡37) ሲላስ እና ይሁዳ በአንፃኪያ ያለውን ችግር ለማረጋገጥ ከኢየሩሳሌም ተልከው ነበር (ሐዋ 15፡22፤30፡35)፡፡

መ. ሲላስ እና ይሁዳ በአንፃኪያ ያለውን ችግር ለማረጋጋት ከኢየሩሳሌም ተልከው ነበር (ሐዋ 15፡22፣30፡35)፡፡
ሠ. ጳውሎስ ሲላስን እንደ ወንጌል አጋር ባልንጀራ ይቆጥረው ነበር (2ቆሮ 1፡19)፡፡
ረ. ሲላስ ከጴጥሮስ ጋር ፀሐፊ እንደነበር ተጠቅሷል (1ጴጥ 5፡12)፡፡
ሸ. ጳውሎስና ጴጥሮስ ሲላስን "ስልዋኖስ" በማለት ይጠሩታል፡፡ ነገር ግን ሉቃስ በአራማይክ ቋንቋ "ሲላስ" ብሎ ይጠራዋል፡፡ "ሲላስ" የአይሁድ ስም ሊሆን ይችላል ፤ "ስልዋኖስ" ደግሞ የላቲን ስያሜ ነው (F.F Bruce (pan) *Apostle of the Heart set free*, P. 213)

15፡23 **"ኪልቅያ"** የሐዋርያው ጳውሎስ የመኖሪያ መንደሩ ነው (ሐዋ 22፡3)፡፡

15፡24 በኢየሩሳሌም ካለችው ቤተክርስቲያን አንዳንድ የቤተክርስቲያኒቱ አባላት ከቤተክርስቲያን ስልጣንን ሳይቀበሉ ነገር ግን በራሳቸው ፈቃድ ሁለት ነገሮችን ያደረጉ ነበር፡ (1) ወደ አብያ ክርስቲያናት ሚሲዮናዊ ሆነው ይሄዱ ነበር፣ (2) የሙሴን ህግ አማኞች እንዲያከብሩ ያለአግባብ ያስገድዱ ነበር፡፡
"አስገደዱ" (anaskeuazo ( የወታደራዊ ቃል ነው ፤ ይህም ማለት "ከተማን ወዝረፋ "የሚል ድብቅ ትርጉም አለው፡፡

15፡25

| | |
|---|---|
| NASB | **"አንድ ሃሳብ ሆነን"** |
| NKSV | **"ተሰብስበን በአንድ ስምምነት"** |
| NRSV,NJB | **"በአንድነት ወስነናል"** |
| TEV | **"ተሰብስበን ተስማምተናል"** |

የአማኞች አንድ መሆን የመንፈስ ቅዱስን መገኘትን ማክበር ነው (ቁ . 25) ይህ ማለት በአማኞች ስብሰባ የሃሳብ አለመስማማት አለመታየቱ ሳይሆን ነገር ግን ከውይይቶች በሌላ ወደ ስምምነት መምጣት እንዳለባቸው የሚያስገነዝብ ነው፡፡

እርስ በእርስ መስማማት ተገቢ የሆነበት ምክንያት ወደ አላስፈላጊ ፅንፈኝነትና አፈንጋጭነትና እልክኝነት ውስጥ ያለአግባብ ሊገባ ስለሚችል ከወዲህ ጥንቃቄ ለመውሰድ ያስችላል፡፡

15፡26 ጳውሎስ እና በርናባስ መልካሙን ብቻ ሳይሆን ክፋውንም አብረው ተጋርተዋል፡፡ የተጠሩበት መጠራት ዘላለምን ከልብ መሰጠትን የሚጠይቅ ነው እንጂ በስሜት ላይ የተመሰረተ አይደለም፡፡

15፡28 **"እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናል"** እግዚአብሔር በዚህ የመሪዎች ስብሰባ ዋነኛ መሪ ነው በመሆኑም በእነርሱ ውይይት ፈቃድን ገልጦላቸዋል ይህ የእነርሱ አንድነት የመጣው ከመንፈስ ቅዱስ ነው ነገር ግን የመንፈስ ቅዱስ አዛዥነት እና የሰው ተባባሪነት አስፈላጊ እንደሆነ የሚያሳይ አይነተኛ ጥቅስ ነው፡፡ ወንጌል የበላይ መሪ ህግ ቢሆንም የሰዎች ትሁት መሆንና ታዛዥ ልብ መያዝ ለስራው ቅለትን ያመጣል፡፡

▣ **"ከዚህም ሁሉ"** እነዚህ የተባሉትን በመጠበቅ ድነትን ማግኘት አይቻልም ነገር ግን ባመኑ አይሁድና ባመኑ አህዛብ መሃከል ልዩነት እንዳይፈጠር ነው፡፡

15፡29 አህዛብን ከጣኦት አምልኮ እንዲለዩ የሚያደርግ ትዕዛዝ ነው፡፡ በክርስትና ነፃነት እና ሃላፊነት በጋራ ማዋደድ እጅግ ከባድ ነገር ነው (ሮሜ 14፡1-5፣ 1ቆሮ 8፡1-13፣ 10፡23-28) እምላክ የሌላቸው እምነት የለሽ የሚባሉ ሰዎች በሶስት ነገሮች ይታወቃሉ፡፡
እነዚህ ሶስቱ በግሪኩ ፅሁፍ ላይ በተለያየ መንገዶች ተፅፈዋል፡፡

1. ስጋ ለጣኦት የታረደ መሆኑ ተገልጾበታል (1ቆሮ 8፡10፡23-33)
2. ደም ደግሞ የሚያመለክተው
   ሀ. ያልነፃ ስጋ
   ለ. የተገደለ
3. የታነቀ የሚለው ካልነፃ ከተባሉት እንስሶች መሃከል የስጋ ለመብልነት ሲቀርብ በአይሁድ ሃይማኖት ተቀባይነት የለውም
4. ከዝሙት ትርቁ ዘንድ ማለት፡-
   ሀ. በጣኦት አምልኮ አለመሳተፊን ያመለክታል (ዘሌ 7፡10-14)
   ለ. ደምን ለመብላት መጓጓት ክልክል ነው (ዘሌ 7፡10-14)

እነዚህ የብሉይ ኪዳን ትምህርቶች ለደህንነት ሳይሆን የሌሎችን ህግ ለማክበር ይጠቅማል፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ የክርስቲያን ነፃነት እና ሃላፊነት**

ሀ. ይህ ምዕራፍ በክርስቲያን ነፃነት እና ሃላፊነት መሃከል ያለውን ግጭት እልባት የሚሰጥ ነው፡፡ (ሐዋ 15፡13)

ለ. በዚህ ምዕራፍ የሚገኘው ትልቁ ችግር በአህዛብ እና በአይሁድ አማኞች የተፈጠረው አለመግባባት ነው፡፡ አይሁድ አማኝ ከመሆናቸው በፊት ወግ አጥባቂዎች ነበሩ አህዛቦች ጣኦት አምላኪዎች በመሆናቸው ሁለቱም የቀደመውን ስርዓታቸውን ፈፅሞ አላስወገዱትም ነበር ይህ ምዕራፍ እውነተኛ ስለሆነ አማኞች እንደሚናገር ማስተዋል ይገባናል (1ቆሮ 3፡1) ነገር ግን በሁለቱ መሃከል ፅንፈኝነት በግልፅ ይታያል፡፡

ሐ. አማኞች የራሳቸውን ደንብ በማውጣት የሌሎችን ስነመለኮት እና የኑሮ ዘይቤ መቆጣጠር የለባቸውም፡፡ (2ቆሮ 10፡12) አማኞች በተሰጣቸው መረዳት መኖር ይጠበቅባቸዋል እንጂ የእነርሱ መረዳት ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር ስነመለኮት ነው በማለት ሌላውን መጨቆን አይገባቸውም፡፡ አማኞች በሃጢያት ሊጠቁ ይችላሉ በመሆኑም በፍቅር እርስ በእርስ መማማርና መበረታታት ይገባቸዋል፡፡ ለማወቅ የሚጥር ቀድሞ ከሚያውቀው የበለጠ እንደሚያውቅ መዘንጋት የለብንም (1ቆሮ 13፡12) ነው፡፡ ክርስቲያኖች ከሌሎች ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት በእግዚአብሔር ፊት ፍርድን ወይም በረከትን በህይወታቸው ሊያመጣባቸው ይችላል፡፡ (2ቆሮ 5፡10)

መ. የአንድ ሰው የውስጡ የልቡ ፍላጐትና የመነሻ ሃሳቡ ማንነቱ የሚፈተሸበት ቁልፍ ቦታ

ሠ. ማርቲን ሉተር እንዲህ አለ "ክርስቲያን ለማንም ባሪያ ሳይሆን ሙሉ ነፃነት አለው ፤ ክርስቲያን የሁሉ አገልጋይ ሆኖ ሃላፊነት የተሸከመ ነው"

ረ. ይህ ርዕስ ጉዳይ (የሮሜ 14፡1-15፡13 እና የ1 ቆሮ 8-10 እና የቆላስያስ 2፡8-23) ዋና ሃሳብ ነው፡፡

ሸ. አንዳንድ ክርስቲያኖች ስለመንትያ ሃሳቦች መኖር ያምናሉ ይህም ማለት እያንዳንዱ አማኝ ብርቱ እና ደካማ ጐን እንዳለው ይናገራሉ ይሄ ደግሞ እውነትነት አለው እያንዳንዱ አማኝ ከእግዚአብሔርና ከመፅሐፍ ቅዱስ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ካለው በብርሃን ይሄዳል የዚህን ተቃራኒ ላደረገ ደግሞ ክጨለማ ይሄዳል ማለት ነው፡፡

ቀ. ደካማና ብርቱ የተባሉት ክርስቲያኖች ቢሆኑም ነገር ግን ጳውሎስ ከእንርሱ የተነሣ ብርቱ ብሎም ደካማ እንደሆኑ ለእኛ (ለአንባቢዎቹ) መግለፅ እንደሌለብን አመላካች ቃል ነው በክርስቴስ ሁላችንም እርስ በእርስ መቀባበል አለብን፡፡

በ. ርዕስ ጉዳዩ በዝርዝር ሲቀመጥ፡-

1. እርስ በእርሳቹ ተቀባበሉ እግዚአብሔር ተቀብሏችኋልና (ሐዋ 14፡10፣3፡15፡7
2. ክርስቶስ ፈራጅ ነውና እርስ በአርሳችሁ አትፈራረዱ፡፡ (ሐዋ 14፡3፡12)
3. ፍቅር ከነፃነት ይልቅ አስፈላጊ ነው (ሐዋ 14፡13-23)
4. የክርስቶስን ምሳሌ በመከተል መብቶቻችሁን መተው ይጠበቅባችኋል፡፡ (ሐዋ 15፡1-13)

▣ "ብትጠብቁ" የNJB ትርጉም "ይህን አስወግዳችሁ ትክክለኛውን አድርጉ በሚል ተክቶታል፡፡

▣ "ጤና" በአይሁድ ባህል የመሰነባበቻ ቃል ሆኖ ያገለግላል፡፡

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 15፡30-35**
**እነርሱም ተሰናብተው ወደ አንፃኪያ ወረዱ ህዝቡንም ሰብስበው ደብዳቤውን ሰጡአቸው፡፡ ባነበቡትም ጊዜ ከምክሩ የተነሳ ደስ አላቸው፡፡ ይሁዳና ሲላስም ደግሞ ነብያት ደስ አላቸው፡፡ ይሁዳና ሲላስም ደግሞ ነቢያት ነብሩና ወንድሞችን በብዙ ቃል መክረው አፀኑአቸው፡፡ አያሌ ቀንም ከተቀመጡ በኋላ ከወንድሞች በሰላም ተሰናብተው ወደ ሐዋርያት ሄዱ፡፡ ሲላስ ግን በዚያ ይኖር ዘንድ ፈቀደ፡፡ ጳውሎስና በርናባስም ከሌሎች ከብዙ ሰዎት ጋር ደግሞ የጌታን ቃል እያስተማሩና ወንጌልን እየሰበኩ በአንፃኪያ ይቀመጡ ነበር፡፡**

15፡30 ሐረጉ የሚያሳየው የክርስቲያኖች መሰብሰብ እጅግ ጠቃሚ መሆኑን ነው፡፡

15፡31 በአንፃኪያ የነበረው ሁለተኛው የእማኞች ስብሰብ ጉዳዩን በአዎንቲዊ ገፅታው ተመልክቶታል፡፡

15፡32 በዚህ ምንባብ የምንመለከተው የብሉይ ኪዳን መፅሐፍት የትንቢት ቃሎች የታመኑ መሆናቸውን ነው፡፡ ልዩ ርዕስ የሚለውን የአዲስ ዲን ትንቢት (ሐዋ 3፡18) በማንበብ የጠለቀ ግንዛቤ ማግኘት ይቻላል፡፡

15፡33 "በሰላም" የዕብራውያንን "ሻሎም" ወየም የስንብት ቃል ያመለክታል፡፡ በዚህም በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ለመርዳት ያላቸውን አዎንቲዊ መልስ ያሳያል፡፡

15:34 ይህ ጥቅስ በግሪኩ ፅሁፍ እና በላቲኑ ፅሑፍ ላይ አይገኝም በተጨማሪም በ NRSU፣ TEV፣ NSB እና NIV አልተፃፈም፡፡ ነገር ግን በሌሎች የግሪክ ፅሑፎች ላይ ቃሉን በማሻሻል ፅፈውታል ፤ ጥቅሱ ዘግይቶ የተጨመረ ሊሆን ይችላል፡፡

15:35 ጳውሎስና በርናባስ እያስተማሩና እየሰበኩ ነው፡፡ ነገር ግን ሌሎቹ አገልጋዬች በምን አይነት ስራ ላይ እንደነበሩ ዝርዝር ሃሳብ አናገኝም፡፡ አዲስ ኪዳን በተወሰኑ ሰዎች አገልግሎት እና ህይወት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ: 15:36-41**

**ከጥቂት ቀንም በኋላ ጳውሎስና በርናባስን ተመልሰን የጌታን ቃል በተናገርንበት በየከተማው ሁሉ ወንድሞችን እየጐበኛቸው እንዴት እንዳሉም እንወቅ አለው፡፡ በርናባስም ማርቆስ የተባለውን ዮሐንስን ደግሞ ይወስዱ ዘንድ አሰበ ጳውሎስ ግን ይህን ከእነርሱ ጋር ሊወስድ አልፈቀደም ከእነርሱም ዘንድ ከጵንፋልያ ተለይቶ ነበርና ወደ ስራም ከእነርሱ ጋር አልመጣም ነበርና ስለዚህም እርስ በርሳቸው እስኪለያዩ ድረስ መከፋፋት ሆነ በርናባስም ማርቆስን ይዞ በመርከብ ወደ ቆጵሮስ ሄደ፡፡ ጳውሎስ ግን ሲላስን መረጠ ወንድሞችም ለእግዚአብሔር አደራ ከሰጡት በኋላ ወጣ አብያተ ክርስቲያናትንም እያፀና በስርያና በኪልቅያ ይዞር ነበር፡፡**

15:36 **"ተመልሰን"** የጳውሎስ እና የበርናባስ ሃሳብ አብያት ክርስቲያናትን ማጠንከርና ማፅናት ነበር ነገር ግን ልዩ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ተሰቷቸው አልነበረም፡፡

15:38 **"ጳውሎስ ግን ይህንን ከእነርሱ ጋር ሊወስድ አልፈቀደም"** በዚህ ዓረፍተ ነገር ላይ ጳውሎስ ፈፅሞ መወሰኑን አያሳይም፡፡

▣ **"ተላይቶ ነበርና"** ማርቆስ የተባለው ዮሃንስ በመጀመሪያው የሚሲዮናዊነት ተልዕኮ ላይ ያልተሳተፈበት ምክንያት በርግጠኝነት አልታወቀም፡፡

15:39 **"ስለዚህም እርስ በእርሳቸውም እስኪለያዩ ድረስ መከፋፋት ሆነ"** መከፋፋት የሚለው ፍቺው "ስላታም" ወይም "እንደ ምላጭ የሚቆረጥ" የሚል አቻ ትርጉም ይሰጣል፡፡ በዕብራውያን መፅሐፍ በአዎንታዊ ገፅታ ተፅፏል፡፡ (ዕብ 10:24፣ ሐዋ 17:6 እና 1ቆሮ 13:5) ይመልከቱ፡፡

▣ **"በርናባስም ማርቆስን ይዞ በመርከብ ወደ ቆጵሮስ ሄደ"** በዚህ ጊዜ ዑለት የሚስዮን ቡድን ተፈጠረ፡፡

15:40 **"ጳውሎስ ሲላስን መረጠ"** ሐዋርያው ጳውሎስ በሌላው ጉኑ በእየሩሳሌመ ቤተ ክርስቲያን መሪ የሆነውን መረጠ ማለት ይቻላል፡፡

▣ **"ለእግዚአብሔር ፀጋ አደራ ከሰጡት በኋላ"** ሰዎችን ለእግዚአብሔር የመስጠት የአደራ ፀሎት ነው (ሐዋ 6:6፣13:3፣14:26፣20:32) ይህንን አብያተ ክርስቲያኑ ይጠቀሙበት ነበር፡፡

15:41 **"ኪልቅያ"** ቤተ ክርስቲያን በዚህች ከተማ እንዴት እንደተጀመረች የሚጠቅስ ዝርዝር የለም፤ ነገር ግን ጳውሎስ በጠርሲስ በነበረው የዝምታ አመታት ቤተ ክርስቲያኒቷን መስርቷት ሊሆን ይችላል፡፡ ከልቅያ የጳውሎስ የመኖሪያ አውራጃ ነች፡፡

▣ **"ቤተክርስቲያን"** ልዩ ርዕስ 5:11 ላይ ያለውን ይመልከቱ፡፡

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ለመርዳት ነው የተሰናዱት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋነኞቹን ጉዳዮች ለማጤን እንዲረዳ ነው፡፡ ሐሳብ ለማጫር እንጂ መደምደሚያ አይደሉም፡፡

1. የአይሁድ ክርስቲያኖች የሚባሉት እነማን ናቸው?
2. ያዕቆብ የሚያቀርበው ሃሳብ ተቀባይነት ይኖረው የነበረ ለምንድ ነው?
3. ሽማግሌዎች እነማን ናቸው?
4. በዚህ ምዕራፍ ቁጥር 28 እና 29 ደህንነትን ወይም ህብረትን ያመለክታሉን?

# የሐዋርያት ስራ 16

## የምንባቡ ክፍፍል በአዲሶቹ ትርጉሞች

| የተየመቅሰ[4] | አኪጆት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጢሞትዮስ የጳውሎስ እና የሲላስ ባልንጀራ ነው | ጢሞትዮስ የጳውሎስ እና የሲላስን ተደባለቀ | ጢሞቴዎስ ጳውሎስን አገኘ | ጢሞቴዎስ ከጳውሎስ እና ሲላስ ጋር ሄደ | በኢቆንዮን ጳውሎስ ጢሞቴዎስን መለመለው |
| | | | | 15፡41-16፡3 |
| 16፡1-5 | 16፡1-5 | 16፡1-5 | 16፡1-5 | |
| | | | | 16፡4 |
| | | | | 16፡5 |
| ጳውሎስ የመቄዶንያ ሰው ሲጠራው በራዕይ አየ | የመቄዶንያ ጥሪ | ከትንሹ እስያ ወደ ጢሮአዳ | በጢአዳ የጳውሎስ ራዕይ | ወደ ትንሹ እስያ ተሻገሩ |
| 16፡6-10 | 16፡6-10 | 16፡6-10 | 16፡6-10 | 16፡6-8 |
| | | | | 16፡9-10 |
| የሊድያ መለወጥ | በፊሊጲሲዮስ ሊድያ ተጠመቀች | ጳውሎስና ሲላስ በፊሊጵስዮስ | በፊሊጵስዮስ የሊድያ መለወጥ | ፊሊጵስዮስ ደረሱ |
| 16፡11-15 | 16፡11-15 | 16፡11-15 | 16፡11-15 | 16፡11-15 |
| በፊጵስዮስ እስር ገጠማቸው | ጳውሎስና ሲላስ ታሰሩ | | በፊሊጵስዮስ እስር ቤት | የጳውሎስ ሲላስ መታሰር |
| 16፡16-24 | 16፡16-22 | 16፡16-22 | 16፡16-22 | 16፡16-18 |
| | የፊሊጵስዮስ ዘብ መዳን | | | 16፡19-24 |
| 16፡25-34 | 16፡25-34 | 16፡25-34 | 16፡25-28 | 16፡25-18 |
| | | | 16፡29-30 | 16፡29-34 |
| | ጳውሎስ በስውር በእስር መውጣቱን ተቃወመ | | 16፡31-34 | |
| 16፡35-40 | 16፡35-40 | 16፡35-40 | 16፡35 | 16፡35-37 |
| | | | 16፡36 | |
| | | | 16፡37 | |
| | | | 16፡38-40 | 16፡38-40 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (ከ "**መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ**" **ገጽ** vii)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. ምንባብ አንድ

2. ምንባብ ሁለት

3. ምንባብ ሦስት

4. ወ.ዘ.ተ

**የሃውዱ ዕይታ**

1. ሁለተኛው የሚሲዮናዊነት ጉዞ (ሐዋ 15፡36-18፡38)

   ሀ. ይህ ሁለተኛው ተልዕኮ ከሌሎቹ ረጅም ጊዜ ወስዷል፤ ከ3-4 ዓመታት ይሆናል።

   ለ. ጉዞው የሚያተኩረው በሜቄዶኒያ እና በአቻ ማለት (የአሁኑዋ ቱርክ) ነው።

   ሐ. የተብራራ ገለፃ፡-
      1. በርናባስ እና ጳውሎስ ተለያዩ ሐዋ 15፡36-40
      2. በሶርያና በኪልቅያ ሐዋ 15-41 (በእነዚህ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት እንዴት እንደተመሠረቱ ዝርዝር መረጃ የለም)
      3. ደርቤንና ልስጥራን ሐዋ 16፡1-5 (ጢሞቲዮስ አገልግሏል)
      4. ፋርግያ ሐዋ 16፡6-10 (ጳውሎስ ወደ ምዕራብ ለመሄድ ራዕይ የተቀበሉበት ቦታ ነው።
      5. ፊልጵስዮስ ሐዋ 16፡11-40
      6. ተሰሎንቄ ሐዋ 17፡1-9
      7. ቤርያ ሐዋ 17፡10-14
      8. አቴና ሐዋ 17፡15-34
      9. ቆሮንቶስ ሐዋ 18-1-17
      10. በማጠቃለያውም ወደ አንፃኪያ ወደ ሶርያ ተመለሱ ሐዋ 18፡18-22

**በሚሲዮናዊነት የተጠቀሱ ሰዎችን ዝርዝን እነመልከት**

ሀ. ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ (ዮሐንስ የአይሁድ ስም ነው፤ ማርቆስ የሮማውያን ስም ነው)
   1. ማርቆስ ዮሐንስ ያደገረ ኢየሩሳሌም ነው፤ የእናቱም ቤት ተጠቅሷል (ሐዋ 12፡12) ቤተክርስቲያን የምትሰበሰበው በዚህ ቤት ነበር።
   2. ብዙዎች እንደሚስማሙበት አብዛኛውን ጊዜ አማኞች የጌታን እራት የሚወስዱበት ቤት ነው።
   3. ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ የበርናባስ የአጐቱ ልጅ ነው (ቆላ 41፡10)
   4. ይህ ሰው የጳውሎስና የበርናባስ ባልንጀራ ነበር (ሐዋ 13፡5)
   5. ዮሐንስ የሚሲዮናዊነት ተልዕኮውን በመተው ተለይቶ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ነበር (ሐዋ 13፡13)
   6. በርናባስ ዮሐንስን ሊወስድ ፈልጐ ነበር ጳውሎስ ግን ተቃሞአል። (ሐዋ 13፡13)
   7. ጳውሎስና ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ ዕርቅን አድርገዋል። (2ጢሞ 4፡11)
   8. ይህ ሰው ከጴጥሮስ ጋር የጠበቀ ወዳጅነት ፈጥሮ ነበር። (1ኛ ጴጥ 5፡13)
   9. የጴጥሮስን ስብከት በመስማት ማርቆስ ዮሐንስ የማርቆስ ወንጌልን እንደፃፈ የሚጠቁሙ መላምቶች አሉ። የማርቆስ ወንጌል ከሌሎቹ የአዲስ ኪዳን መፅሐፍቶች በበለጠ የላቲንን ቃላቶችና ሳሳቦች በመጠቀም ይታወቃል።
   10. የጥንት ፅሑፎች እንደሚያስረዱት ይህ ዮሐንስ አሌክሳንድሪያ ያለችው ቤተክርስቲያን ስትመሠርት ትልቅ ማና ተጫውታል።

ለ. ሲላስ
   1. በሐዋርያት ስራ መፅሐፍ "ሲላስ" የሚል ስያሜ አለው ነገር ግን ጳውሎስና ለሎችም በፃፏቸው መፃህፍት ላይ ሲልዋኖስ የሚል መጠሪያ አለው።

2. በኢየሩሳሌም በነበረች ቤተክርስቲያን መሪ ነበር (ሐዋ 15፡22-23)
3. ሲላስ የጳውሎስ የቅርብ ወዳጁ ነበር፡፡ (1ሐዋ 15፡40 16፡19 17፡1-15 1ተሰሎ 1፡1)
4. ሲላስ ነብይ ነበር፡፡ (ሐዋ 15፡30)
5. ሲላስ ሐዋርያ የሚል ማዕረግም ተሰጥቶታል (1ተሰሎ 2፡6)
6. ሲላስ የሮማውያን ዜግነት ያለው ነበር (ሐዋ 16፡37፡38)
7. ሲላስ እንደማርቆስ ዮሐንስ ከጴጥሮስ ጋር መፅሐፍትን በመፃፍ ትብብር ያደርግ ነበር፡፡

ሐ. ጢሞትዮስ
1. ጢሞትዮስ የሰሙ ትርጉም "እግዚአብሔርን የሚያከብር" ማለት ነው፡፡
2. ጢሞትዮስ እናቱ አይሁዳዊት ነች አባቱ ግን ግሪካዊ ነበር፣ የሚኖሩትም በስልጥሬን ነበር፡፡ (ሮሜ 16፡21) ጢሞቲዮስ የዳርቤን ዜግነት ነበረው፡፡ (ሐዋ 20፡4) ነገር ግን ሚሞቲዎስ ሕይወቱን ይመራ የነበረው በእናቱ እምነትና በአያቱ ትምህርት ነበር፡፡ (2ጢሞ 1፡5፡3 14-15)
3. በሁለተኛው የሚሲዮናዊነት ጉዞአቸው ላይ ጢሞቲዎስ ተሳታፊ እንዲሆን በጳውሎስና በሲላስ ጥያቄ ቀርቦለታል፡፡ (1ጢሞ 1፡18፡4፡14) በነብያት የማረጋገጫ ቃል አግንቶ ነበር፡፡
4. ጢሞትዮስ በጳውሎስ እጅ በመገረዙ ከአይሁድና ከአህዛብ ጋር (ከግሪኮችም) ይሠራ ነበር፡፡
5. በሐዋርያው ጳውሎስ ልቡን የሰጠ የወንጌል አጋሩ ጢሞቲዎስ ነበር፡፡ ከጳውሎስ ባልንጀሮች በበለጠ ሁኔታ የጢሞቲዎስ ስም ተጠቅሶ እናገኛለን፡፡ ይህም 17 ጊዜ በ10 ደብዳቤዎች ውስጥ ተፅፏል፡፡ (1ቆሮ 4፡17 16፡10፤ ፊሊ 1፡1፤ 2፡10፤ ቆላ 1፡5 ፤ 1ተሰሎ 1፡1፤ 2፡6፤ 3፡2 1ጢሞ 1፡2 18)
6. ይህ ሰው ሐዋርያ የሚል ማዕረግ ተሰቶታል (1ተሰሎ 2፡6)
7. የመጋቢያን መፅሐፍት ከሚባሉት ሦስት መፃህፍት ሁለቱ የተፃፉት ለጢሞቲዎስ ነው፡፡
8. የጢሞቲዎስ ስም በማጠቃለያው የተጠቀሰው በዕብ 13፡23 ላይ ነው፡፡

***የቃል እና የጥምር ቃል ጥናት***

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 16፡1-5**

***ወደ ደርቤንና ወደ ልስጥራንም ደረሰ፡፡ እነሆም በዚያ በአንዲት ያመነች አይሁዳዊት ልጅ ጢሞቲዎስ የሚባል አንድ ደቀ መዝሙር ነበር፡፡ አባቱ ግን የግሪክ ሰው ነበረ፡፡ ለእነርሱም በልስጥራንና በኢቆንዮን ያሉ ወንድሞች መስከሩለት፡፡ ጳውሎስ ይህ ከእርሱ ጋር ይወጣ ዘንድ ወደደ በእነዚያም ስፍራዎች ስለ ነበሩ፡፡ አይሁድ ይዞ ነረዘው አባቱ የግሪክ ሰው እንደሆነ ሁሉ ያውቁ ነበርና፡፡ በከተሚዎችም ሲዘሩ በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያትና ሽማግሌዎች የቁረጡትን ስርዓት ይጠብቁ ዘንድ ሰጡአቸው፡፡ አብያተ ክርስቲያናትም በሃይማኖት ይበረቱ ነበር፡፡ በቁጥርም ዕለት ዕለት ይበዙ ነበር፡፡***

**16፡1 *"ደርቤን እና ልስጥራን"*** *እነዚህ ከተሞች የሚገኙተ የሮማውያን አውራጃ በሆነችው በገላትያ በስተደቡብ ነው፤ (የዛሬዋ ቱርክ) ሐዋርያው ጳውሎስ እንደሚታወቀው በመጀመሪያው የሚሲዮናዊነት ጉዞው እነዚህን ከተሞች ጐብኝቶአቸዋል፡፡*

▣ ***"አንድ ደቀመዝሙር ነበር"*** *ሉቃስ ሐረጉን ለመግለፅ "" የሚል ግሪክ ቃል ተጠቅሟል፤ ይህም ሰው ከጳውሎስ ጋር የወንጌል አጋር የሚሆን ሰው እንደሆነ ስለወደፊት የሚያመለክት ሐረግ ነው፡፡*

▣ ***"እናቱ ያመነች አይሁዳዊት አባቱ የግሪክ ሰው"*** *2ጢሞ 1፡5 ያንብቡ ከዚህ ምንባብ አያቱም አማኝ እንደነበሩ ስማቸውም "ሊዮስ" የእናቱም ስም "ኢዩኒስ" ይባሉ ነበር፡፡ እናቱ እና አያቱ አማኞች ነበሩ፤ ይህም ምናልባት በጳውሎስ የመጀመሪያ የሚሲዮናዊነት አገልግሎት ጽነትን አግኝተው ሊሆን ይችላል፡፡*

**16፡2 *"ወንድሞች መሠከሩለት"*** *ሰዎች ደጋግመው ጢሞትዮስን ያበረታቱት ነበር፤ የጥንቲቱ ቤተክርስቲያን መሪዎች አንዱ የሚመሰረኑት ሌሎችን በማበረታታቸው ነው፡፡ ይህን የሚያደርጉት ለሚያምኑም ብሎም ለማያምኑም አህዛብ ነበር (1ጢሞ 3፡2 7 10)፡፡*

▣ ***"በሊስጥራ"*** *የጢሞቴዎስ ሃገር ሊስጥራ ይባላል፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ የግሪክ ጽሑፎች የእርሱ ሀገር ድስራ እንደሆነ ያመለክታሉ፡፡*

**16፡3 *"ጳውሎስ ይህ ከእርሱ ጋር ይወጣ ዘንድ እንደወደደ"*** *የጢሞቲዎስ ምርጫ ብቻ አልነበረም፤ ነገር ግን ጳውሎስም የመረጠው ምርጫ ነበር (1ጢሞ 3፡1)፡፡ በዚህም ጢሞቲዎስ የጳውሎስ ተወካይ ለመሆን እንኳን በቅቷል፡፡*

▣ ***"ገረዘው"*** *ሐዋርያው ጳውሎስ ጢሞቲዎስን ከአይሁዶች ጋር መስራት እንዲችል ያደረገው ነው፡፡ (1ቆሮ 9፡20፤ ሐዋ 15፡27-29)፤ ለአይሁዳውያን መገረዝ ዋና ስርዓት ነው፡-*
1. *ይህ ርዕስ ጉዳይ የኢየሩሳሌም የስብሰባው ውጤት ነው (ሐዋ 15)*
2. *ቲቶ የግሪክ ሰው ሆኖ አልተገረዘም ነበር፤ ነገር ግን ጳውሎስን በመገረዙ ለደህንነት ሰዎች እንዳይሰናከሉ ቅድሚያ መስጠቱን አመላካች ድርጊት ነው፡፡*

▣ "አባቱ የግሪክ ሰው… ነበርና" ሐረጉ የሚያመለክተው አባቱ በሕይወት እንደሌለ ነው፡፡

16፡4 ጳውሎስና ሲላስ በኢየሩሳሌም በነበረው ስብሰባ ላይ ውጤቱን አብራርተዋል፡፡ 1ሐዋ 15፡22-29 የአይሁድን "ስርዓቶች" መፈፀም ያስፈለጉበት ምክንያቶቹ፡ (1) ህብረትን በቤተክርስቲያን ለመጠበቅ ነው፣ (2) አይሁድን በወንጌል ለመድረስ ነው (የጢሞቴስ መገረዝ ምሳሌ ነው)፡፡

16፡5 ይህ ሐረግ የሉቃስ የማጠቃለያው ሐተታው ነው፡፡ (ሐዋ 6፡7፤ 9፡31፤ 12፡24፤ 16፤15፤ 19፤20፤28፤31)

▣ "ቤተክርስቲያን" ልዩ ርዕስ 5፡11 ላይ ያለውን ይመልከቱ፡፡

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 16፡6-10**
**በእስያም ቃሉን እንዳይናገሩ መንፈስ ቅዱስ ስለ ከለከላቸው በፋግያና በገላትያ አገር አለፉ በሚስያም አንፃር በደረሱ ጊዜ ወደ ቢታንያ ይሄዱ ዘንድ ሞከሩ፡፡ የኢየሱስ መንፈስም አልፈቀደላቸውም በሚስያም አጠገብ አልፈው ወደ ጢሮአዳ ወረዱ፡፡ ራዕይም ለጳውሎስ በሌሊት ታየው አንድ የመቄዶንያ ሰው ወደ መቄዶንያ ተሻገርና እርዳን እያለ ቆሞ ሲለምነው ነበር፡፡ ራዕዩንም ካየ በኃላ ወዲያው ወደ መቄዶንያ ልንወጣ ፈለግን ወንጌልን እንሰብክላቸው ዘንድ እግዚአብሔር እንደ ጠራን መስሎናልና፡፡**

16፡6 **"በፍርግያና በገላትያ አገር አለፉ"** ሉቃስ ለመግለፅ የፈለገው በሮማውያን ቅኝ ግዛተ የተከፋፈሉትን አገሮች ለማመልከት ሳይሆን በመሃከላቸውም የነበረውን የዘር እና የቋንቋ ልዩነት ለመግለፅ የተጠቀመበት ሐረግ ነው፡፡

▣ **"ከለከላቸው"** በግሪኩ ፅሑፍ እና በአዲስ ኪዳን የተለመደ ቃል ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ በቀደመችው ቤተክርስቲያን ቀጥተኛ ትዕዛዝ እና ተሳትፎ ያደርግ እንደነበር ያመለክታል፡፡ (ሐዋ 2፡4፤ 8፡20 30 10፡10፤ 19፡11 12 28 15፡28፤ 16፡6 7 7፡21 ፡4 ሮሜ 1፡13)

▣ **"በእስያ"** የሮማውያን አውራጃ የሆነውን ትንሹን እስያ ያመለክታል፡፡

16፡6 ,7 **"መንፈስ ቅዱስ"** ልዩ ትኩረት የሚያሻው የሚለውን ይመልከቱ፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ ኢየሱስና መንፈስ**

በኢየሱስ እና በመንፈስ ቅዱስ ስራ መሐከል ተያያዥነት ይታያል፡፡ ጂ.ካምፔኤል ምርነን ‹‹የመንፈስ ቅዱስ ስሙ›› ለሌላኛው ኢየሱስ ነው በማለት የስራቸውን ተያያዥነት ለማሳየት ሞክሯል፡፡ የሚከተለው ዝርዝር ስለኢየሱስና ስለመንፈስ ቅዱስ ስራ እያነፃፀርን እንመለከታለን፡-

1. መንፈስ ቅዱስ ‹‹የኢየሱስ መንፈስ›› የሚል ስያሜ ተሰቶታል፡
   ሮሜ 8፡9 ፤ 2ቆሮ 3፡17፤ ገላ 4፡6 ፤ 2ጴጥ 1፡11
2. ሁለቱም በአንድ አይነት ስያሜ ተጠርተዋል፡፡
   ሀ. ‹‹እውነት››
      1. ኢየሱስ (ዮሐ. 14፡6)
      2. መንፈስ ቅዱስ (ዮሐ 14፡17 ፤ 16፡13)
   ለ. አፅናኝ
      1. ኢየሱስ (1ዮሐ 2፡1)
      2. መንፈስ ቅዱስ (ዮሐ 14፡16፣26 ፤ 15፡26 16፡7)
   ሐ. ‹‹ቅዱስ››
      1. ኢየሱስ (ሉቃ 1፡35 ፤ 14፡26)
      2. መንፈስ ቅዱስ (ሉቃ 1፡35)
3. ሁለቱም በአማኞች ውስጥ ያድራሉ፡፡
   ሀ. ኢየሱስ (ማቴ 28፡20 ፤ ዮሐ 14፡20፡ 15፡4-5 ሮሜ 8፡10 2ቆሮ 13፡5 ገላ 2፡20 ኤፌ 3፡17 ቆላ 1፡27)
   ለ. መንፈስ ቅዱስ (ዮሐ 14፡16-17፤ ሮሜ 8፡9 11 1ቆላ 3፡16፣ 6፡19 2ጢሞ 1፡14)
   ሐ. አባትም በተመሳሳይ አማኞተ ውስጥ ይኖራል (ዮሐ 14፡23 2ቆሮ 6፡16)

16፡17 **"ሚስያ"** በትንሹ እስያ በሰሜን ምዕራብ የምትገኝ የሮማውያን አውራጃ ነበረች፡፡ ከተማይቱ ተራራማ ነበረች ይሁን እንጂ ሮማውያን ያሰሩአቸው መንገዶች ነበሩ፡፡

▣ **"ቢታንያ"** በሰሜን ምዕራብ በትንሹ እስያ የምትገኝ አገር ነች፤ ለሚስያ በሰሜን ምስራቅ በመሆን ቅርብ ከተማ ነች፡፡ ይህች ከተማ የሮማውያነ ቅኝ ግዛት አልነበረችም፤ ነገር ግን ከፖኦንተስ ጋር የፖለቲካ አንድነት ፈጥረው ነበር፡፡

ሐዋርያው ጴጥሮስ በዚህ አካባቢ ወንጌልን ማድረሱን ማስረጃ አለ፡ (1ጴጥ 1፡1) ከዚህ የምንረዳው በቅኝ ታገዝተው የነበሩ አይሁድ የሚኖሩበት ቦታ መሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

16፡8 **"በሚስያ አጠገብ አልፈው"** ማለት "በከተማው መሀከል" ወይም "በዙሪያው" የሚል ትርጉም ይሰጣል፡፡

▣ **"ጢሮአዳ"** ከጥንታዊቱ ከተማ ከቶሬ በአራት ማይል ርቀት ላይ የምትገኝ ከተማ ነች፡፡ ከተማይቱ ለአራት መቶ አመት ሮማውያን ቅኝ እስከሚገዙአት ድረስ የግሪክ ነፃ ከተማ ነበረች፡፡

16፡9 **"ራዕይም ለጳውሎስ በሌሊት ታየው"** እግዚአብሔር ጳውሎስን በእንዲሁ አይነት መለኮታዊ ምርት ይመራው ነበር፡፡

1. የሚያፀባርቅ ብርሃን እና የኢየሱስን ድምፅ በመስማት ይመራው ነበር (ሐዋ 9፡3-4)
2. ራዕይን በማሳየት (ሐዋ 9፡10)
3. ራዕይን በማሳየት (ሐዋ 16፡9፡10)
4. ራዕይን በማሳየት (ሐዋ 18፡9)
5. በተመስጦ ተናግሮታል (ሐዋ 22፡17)
6. የእግዚአብሔር መልአክ ተገልጦለታል፡፡ ሐዋ 27፡23

▣ **"የመቄዶንያ ሰው"** ጳውሎስ በራዕይ የተመለከተው ሰው የመቄዶንያ ሰው መሆኑን እንዴት እንዳወቀ የሚያብራራ ማስረጃ የለም፣ ነገር ግን ምናልባት በአለባበሱ፣ በአነጋገር ዘይቤው አውቆት ሊሆን ይችላል፡፡ የመፅሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች በራዕይ የታየው ሉቃ እንደሆነ ያትታሉ፡፡ ነገር ግን ይህ የወንጌል አቅጣጫን ወደ አውሮፖ ያዞረ ራዕይ ነው፡፡

▣ **"ተሻገር እና እርዳን"** ራዕዩ ግልፅ እና የተረጋገጠ ነው፡፡

16፡10 **"ልንወጣ ፈለግን እኛ"** ሉቃስ ከጳውሎስ ጋር ያሉትን ሲላስ እና ጢሞቲዎስ ለመጥቀስ ያደረገው ጥረት ነው፡፡ ሐዋ 16፡10-17፡20፡5-15፤21፡1-18፡27፡1-28 1-28፡16) አንዳንድ መላምቶች ጳውሎስ በራዕይ ያየው ሰው ሉቃስ ባለመዳኒቱ ወይም የሐዋርያት ስራ ፀሐፊ የሆነውን የሚል ሕሳቤ አላቸው፡፡

▣ **"ሜቄዶንያ"** የአሁኑዋ ግሪክ ሁለት የሮማውያን አውራጃ ሆና ተከፋፍላ ነበር፡፡ እነርሱም፡-

1. አቼያአ በደቡብ በኩል አቴናን፣ ቆሮቶስን እና ስፖርታን ያጠቃልላል፡፡
2. ሜቄዶንያ በሰሜን በኩል ፊሊጺሲዮስን፣ ተሰሎንቄን እና ቤርያን ያጠቃልላል፡፡

▣ **"ራዕዩን ካየን በኃላ"** የሚለው "አንድ ላይ በማሰባሰብ" የሚልትርጉም ይሰጣል፡፡ (የመንፈስ ቅዱስ በእስያ እንዳይሰብኩ ከላከላቸው፣ በቢታንያ አገልግሎት አልፈቀደላቸውም ቁ.7 የእግዚአብሔር ምሪት ግን ወደ መቄዶንያ ሆኖአል፡፡)

▣ **"እግዚአብሔር ጠራን"** የእግዚአብሔር ተነሳሽነት የተደረገ ነው፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ለጥንቃቄ አይደለም ነገር ግን ወንጌልን ለማሰራጨት በማሰብ ነው፡፡ ይህም ሁል ጊዜ የእግዚብሔር ፈቃድ ነው፡፡

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 16፡11-15**
**ከጢሮአዳም ተነስታ በቀጥታ ወደ ስምትራቂ በነገውም ወደ ናዱሌ በመርከብ ሄድን ከዚያም ወደ ፊልጰስዮስ ደረስን እርስዋም በመቄዶንያ ከተማ ሆና የወረዳ ዋና ከተማና ቅኝ አገር ናት በዚህችም ከተማ አንዳንድ ቀን እንቀመጥ ነበር፡፡ በሰንበት ቀንም በከተማው በር ውጭ የፀሎት ስፍራ በዚያ መሆኑን ስላሰብን ወደ ወንዝ አጠገብ ወጣን ተቀምጠንም ለተሰበሰቡት ስቶች ተናገርን፡፡ ስትያጥሮን ከተማም የወጣች ቀይ ሐር ሻጭ እግዚአብጠርን የምታመልክ ልድያ የሚሉአት አንዲት ሴት ትሰማ ነበረች፡፡ ጳውሎስም የሚናገረውን ታዳምጥ ዘንድ ጌታ ልብዋን ከፈተላት፡፡ እርስዋም ከቤተ ሰዎችም ጋር ከተጠመቀች በኃላ በጌታ የማምን እንድሆን ከፈረዳችሁብኝ ወደ ቤት ገብታችሁ ኑሩ ብላ ለመነች በግድም አለችን፡፡**

16፡11 **"ተነስተን በቀጥታ"** ይህ ሐረግ የመርከበኞችን ቋንቋ ያመለክታል (ሐዋ 27) በመሆኑም ጳውሎስና ሰዎች በመርከብ እንደተጓዙ ያረጋግጥልናል፡፡

▣ **"ሳሞትራቂ"** ከኤጂያ ባህር አምስት ሺ የባህር ወለል በላይ ይምትገኝ አለታማ ደሴት ነች፡፡ የምትገኘውም በፊሊጵስዮስ እና በጢሮአዳ መሀከል ነው፡፡

▣ **"ናጱሌ"** የከተማው ስያሜ ትርጉሙ "አዲስ ከተማ" ማለት ነው፤ ነገር ግን በሜድትራንያን በዚህ ስም የሚጠሩ በርካታ ከተሞች ነበሩ፡፡ ይህች ከተማ አስር ማይል ብቻ በመራቅ ለፊሊጵስዮስ የወደብ አገልግሎት ትሰጥ ነበር፡፡

16፡12 **"ፊሊጺስዮስ"**የግሪኩ ፅሑፍ በብዙ ቁጥር አስቀምጦአታል፤ ምናልባት የብዙ ቅዬዎች ብስብስብ ሊሆን ይችላል፡፡ የከተማይቱ አቅጣጫ ወደ ግብፅ በሚወስደው መንገድ ላይ ነው፤ የቀድሞ መጠሪያዋ "ኬሪንዲስ" ወይም "የውሃ

ጉድጓድ" ተባል ነበር፤ ንጉስ ሰሊፐ ሁለተኛ የወርቅ ክምችት ከተማይቱ ስለነበራት በቅኝ ግዛት ይዞት ነበር። በኃላም የከተማይቱ ስም በስሙ ተሰየመች።

▣
NASB *"የሚቆዶንያ ዋና መሪ ከተማ"*
NRSV *"የሚቄደንያ ቀዳሚ ከተማ"*
TEV *"የመጀመሪያ የሚቆዶንያ ዋና ከተማ "*
NJB *"የወረዳው ዋና ከተማ"*

*ሐረጉ በውል ፍቺው አይታወቅም፤ ነገር ግን አምልፖኦሰስ የሚቄዶንያ ዋና ከተማ እንደሆነች ይነገራል፤ ነገር ግን ሉቃስ አጨቃጫቂ ሃሳብን ፅፏል።*

▣ *"**የሮማውያን ቅኝ**"* በ42 ከክ)ል)በፊት ኦክታቭን እና ማርክ አንቶኒ ከስስን እና ብሩተስን ከጦርነት አሸንፈዋል። ይህንን በማስመልከት ኦክታቭን ስለጵስዮስን የሮማ ቅኝ አድርጎ ወታደሮቹን በዚያ በነጎ አሰናብቶአቸዋል። በመቀጠል በ31 ከክ)ል)በፊተ አንቶኒዮ እና ኪሎፖትራ በአተም ከተሸነፉ በኃላ ኦክታሽን ብዙ ሠራዊት በዚያ አግኝቶ ነበር። እንዲሁም ሌሎቹን ቅኝ ግዛቶች ከመፅሐፍ ቅዱስ ማግኘት ይቻላል። ሁሉም ቅኝ ግዛቶች፡ (1) የራሳቸው መንግስት ነበራቸው፣ (2) ታክስ አይከፍሉም ነበር። (3) ልዩ መብት ተሰጥቷቸው ነበር። በመሆኑም ጳውሎስ በሮማውያን ቅኝ ግዛት በርካታ አብያተ ክርስቲያናትን መመስረት ችሎ ነበር።

16፡13 "በሰንበት በፊሊጵስዮስ ምኩራብ አልነበረም ይህ የሚያመለክተው ለምኩራት ምስረታ አስር የሚያህሉ የአይሁድ ወንዶች አልነበሩም ማለት ነው፣ ነገር ግን እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች ይኖሩ ነበር። (ሐዋ 16፡14 ፤ 13፡43፤ 17፡4 17 ፤ 18፡7)" በፊሊጵስዮስ ከተማ የነበሩ ሴቶች በአይሁድ የሃይማኖት ስርጭትና የአኗኗር ዘይቤ ተማርከው ነበር።

▣ *"**በወንዝ አጠገብ ተቀምጠን**" ይህ ቦታ የሀይማኖት አምልኮ የሚካሄድበት የተለመደ ቦታ ነው።*
*የአይሁድ መምህራን ለማስተማር የሚጠቀሙበትን የሰዎች አደራደር ያመለክታል።*

16፡14 "**ከትያጥሮን ከተማም የመጣች..... ልድያ የሚሉአት አንዲት ሴት**" *ከሮማውያን ቅኝ ግዛቶች ሁሉ ሜቄዶንያ የሴቶችን መብት በማክበር በሚድትያኒያን ከነበሩ ከተሞች ሁሉ በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት የተሻለች ነበረች። ልድያ ከትንሹ እስያ ሀገር ነበረች። (ራዕ 2 17) በሮማውያን የታወቀ የሐር ምርት የሚገኘው ከዚህ አካባቢ ነበር። በልድያ ከተማ የምኩራብ አምልኮ እንደነበር ማስረጃዎች አሉ። የልድያ ስም የተወሰደው ከጥንት ከተሞች በነበሩት ከአንዳ ከተማ ስም ነበር፤ ስሟ በጳውሎስ ደብዳቤዎች ላይ አንድም ጊዜ ያመለጠቀሷ ምክንያቱ በህይወት ሳትኖር በመቅረቷ ነው። የሚል ህሳቤ አለ።*

▣ *"**ጌታን የምታመልክ**" እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት መሆንዋን እና በአይሁድ ሀይማኖት ልቧ እንደተማረከ መገንዘብ ይቻላል።*

▣ *"**ጌታ ልቧን ከፈተላት**" መፅሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር በሰው መካከል ያለውን የቃል ኪዳን ዝምድና የሚገልፅ መፅሐፍ ነው። እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ባለቤት እንደሆነ እና የሰው ልጅ ፈላጊ እንደሆነ መረዳት አያዳግትም በመሆኑም ደህንነት የእግዚአብሔር ለሰው የተሰጠ የቃል ኩዳን ዝምድና ነው። እግዚአብሔር ለሰው ራሱን ካልገለጠለት ሰው ወደ እግዚአብሔር መምጣት አይችልም። (ዮሐ 6 44 65) ነገር ግን እግዚአብሔር ሰው ሁሉ እንዲድን ይፈልጋል። (ዮሐ 3፡16 1ጢሞ 2፡4 2ጴጥ 3 9) ራሱን በፍጥረት ገልጧል። (መዝ 19፡7-14) ሰው ሁሉ በኃጢያቱ ምክንያት በፍርድ ወንበር ፊት ይቆማል (ሮሜ 1 2) በመሆኑም አንዳንዶች ወንጌልን ለማመን ሲታዘዙ ሌሎች ግን አየታዘዙም። ይህ አንዳንዶች እንደሚሊት የእግዚአብሔር ምርጫ ስለሆነ በቻ አይደለም። ነገር ግን የሰው ምላሽ አስፈላጊ መሆኑን ያስገነዝበናል። ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥሮአል (ዘፍ 1፡26) እግዚአብሔር ሰው ሁሉ እንዲድን ይፈልጋል (ዘፍ 3፡15)*

16፡15 "**ከነቤተሰዎቿ ተጠመቀች**" *የሊዲያን ቤተሰብ ሰራተኞችዋን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው (ሐዋ 16፡33) እንደሌሎቹ በአዲስ ኪዳን እንዳሉት ምሳሌዎች ሊዲያም ባመነች ጊዜ ወዲያው የውሃ ጥምቀት ወስዳለች።*
*በዚህ ምንባብ የስነ መለኮት ጥያቄ ይነሳል ይህም የቤተሰብ ጥምቀቱ ህፃናቶችንን ያጠቃለለ ከሆነ የህፃናት ጥምቀት እንዳለ ያሳያል ነገር ግን ግልፅ የሆነ ዝርዝር ሃሳብ አልተፃፈም።*
*በእስራኤል ማህበረሰብ የተደጋገመ ታሪክ ይታያል እርሱም ከአንድ ቤተሰብ አንድ ሰው ወደ ክርስቶስ ከመጣ ቤተሰቡ ሁሉ ወደ ክርስቶስ የመምጣትና የመዳን ፍላጎት ይታያል። ነገር ግን ይህ በሌሎች አገር ባህሎች የተለመደ ይሆን ነገር ግን በአዲስ ኪዳን በጅምላ ሳይሆን በተናጥል ሰው ሁሉ ሀጢያተኝነቱ ተሰምቶት ወደ እግአብሔር ለንስሀ በጅምላ ሳይሆን በተናጥል ሰው ሁሉ ሃጢያተኝነቱ ተሰምቶት ወደ እግዚአብሔር ለንስሃ መቅረብ እንዳለበት ግልፅ ነው። አንድ ሰው በግሉ ድነት እንደሚያስፈልገው ከልቡ ማመን አለበት። ጥያቄው ግን ሰው ሁሉ በአዳም ሃጢያት አለበትን እግዝአብሔር ሳያውቁ ባይታዘዙ ሃጢያት ይሆንን የእስራኤል ልጆቻቸውን ህግ ያስተምሮአቸው ነበር። ለወንድ 13 ለሴቶች 12 ዓመት ሲደርሱ የህጉን መፅሐፍ ይማሩ ነበር።*

▣ *"በጌታ የማመን እንድሆን ከፈረዳችሁብኝ"* ፀሐፊው ሉቃስ በራሱ *ዕይታ ሊድያ* እውነተኛ *አማኝ መሆን ግን ለማረጋገጥ* ይህን ዓረፍተ ነገር ተጠቅሞበታል፡፡ በተጨማሪም ወደቤቷ እንዲገቡና እንዲኖሩ ማድረጓ ኢየሱስ ለሰባዎቹ ደቀመዛሙርት ለተናገረው መልእክት ምላሽ የሚሆን ነው፡፡ (ሉቃ 10 5-7)

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 16:16-18**

**[16]ወደ ጸሎት ስፍራም ስንሄድ፥ የምዋርተኝነት መንፈስ የነበረባት ለጌቶችዋም እየጠነቈለች ብዙ ትርፍ ታመጣ የነበረች አንዲት ገረድ አገኘችን፡፡ [17]እርስዋ ጳውሎስንና እኛን እየተከተለች፡፡ የመዳንን መንገድ የሚነግሩአችሁ እነዚህ ሰዎች የልዑል አምላክ ባሪያዎች ናቸው ብላ ትጮኽ ነበር፡፡ [18]ይህንም እጅግ ቀን አደረገች፡፡ ጳውሎስ ግን ተቸገረና ዘወር ብሎ መንፈሱን፡፡ ከእርስዋ እንድትወጣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዝሃለሁ አለው፤ በዚያም ሰዓት ወጣ፡፡**

16:16 *"ወደ ፀሎት ስፍራ ስንሄድ"* ጳውሎስ እና ሲላስ በየትኛው ቀን ለመፀለይ ምኩራብ እየሄዱ እንዳለ አይታወቅም የእግዚአብሔር ሙሉ ሃይል የስራ ስለነበረ የሰዎችን አእምሮ ለመማረከ የእነርሱን ፀሎት በመስማት ጌታ ታምራቱን አድርጓል፡፡

▣ *"የሟርተኝነት መንፈስ"* በዚህ ምንባብ ውስጥ ይህ ሐረግ በሁለት መንገዶች ሊብራራ ይችላል፡፡ የመጀመሪያው "ሟርተኛ" ይህ የብሉይ ኪዳን መፅሐፍ የሚሰጡት ተመሳሳይ ትርጉም አለው፡፡ ሁለተኛው በአዲስ ኪዳን በግሪኩ ፅሑፍ ደግሞ "በአጋንንት የተያዘ የሚጠነቁል፣ የሚራገም እና ተፈጥሮን በመመልከት የወደፊቱን የሚናገር (ለምሳሌ፡- የእንስሳትን ጉበት በማየት፣ ደመናንን በመመልከ፣ የወፎችን አበራረር በመመልከት እና የሲነን ጭላጭ በመመልከት) " ይተነብያሉ፡፡

በግሪክ ባህል "ፑዝ ኦን" የሚለው ቃል የወጣው በግሪክ ታሪክ አፖሎ የሚባል ጦኦት ትልቅ እባብ በመግደሉ ሰው ወደዚህ ጣኦት በመምጣት የወደፊት ዕጣ ፈንታውን እና የሚደርስበትን ክፋ ነገር በመስማት መጠንቀቅ እንደሚያስፈልገው በአፈ ታሪክ ይነገር ነበር፡፡

▣ *"እየጠነቆለች"* በአዲስ ኪዳን ቃሉ የተጠቀሰው በዚህ ስፋራ ብቻ ነው፡፡ በግሪኩ ፅሑፍ መንፈስን ዓለም የማያውቅ ነብይ በማለት በአሉታዊ መንገድ ይገልፀዋል፡፡ በዚህ ምንባብ እንደምረዳው ይህች ሴት በእርኩስ መንፈስ እንደተያዘች ነው፡፡

16:17 *"ይህን እጅግ ቀኝ አደረገች… ትጮህ ነበር"* ይህ የሚያሳየው ድርጊቱ በተደጋጋሚ የተደረገ መሆኑን ነው፡፡

▣ *"እነዚህ ሰዎች የልኡል አምላክ ባሪያዎች ናቸው"* ኢየሱስ የክፉ መናፍስትን ምስክርነተ አይቀበልም ነበር፡፡ ሉቃ 8:28 ማርቆ 1:24፤ 3:11 ፤ ማቴ 8፣29) ጳውሎስም እንዲሁ አይቀበልም ነበር፡፡ "የልኡል አምላክ" የሚለው ቃል "ያሕዌ" ማለት ነው (ዘፍ 14 18-19) ነገር ግን በእነዚህ ጣኦት አምላኪዎችም ዘንድ ለራሳቸው ትርጉም በሚሰጥ መንገድ ቃሉን ይጠቀሙበት ነበር፡፡

▣ *"የመዳንን መንገድ የሚያሳዩአችሁ"* በዚች ሴት ውስጥ ያለው አጋንንት የጳውሎስን አገልግሎት እየደገፈ አይደለም፡፡ ነገር ግን የዚህ አላማ ሁለት ነው፡፡ (1) ጳውሎስ ሟርተኛ መሆኑን ለማስመሠል፡፡ (2) የመዳን መንገድ የተለያየ እንጂ አንድ እንዳይደለ ለመናገር የታደቀ ነበር፡፡

16:18 *"ጳውሎስም እጅግ ተቸገረና"* ጳውሎስ እጅግ በመሰሳጨት ምላሽ መስጠቱን ያመለክታል፡፡ በመክ 10:9 ተመሳሳይ ቃል አለ፡፡ በአዲስ ኪዳን ይህ ቃል በዚህ ምንባብ እና በሐዋ 4:2 ላይ ብቻ ተጠቅሶ ይገኛል፡፡

▣ *"መንፈሱን"* ጳውሎስ የቆጣው ወይም እንዲወጣ ያዘዘው መንፈሱን እንጂ ሴትየዋን አለመሆኑን ይገልፃል፡፡ ጳውሎስ በሌሎቹ በአዲስ ኪዳን በኢየሱስ እና በሌሎች ይደረግ እንደነበረው በተመሳሳይ መልኩ አድርጓል፡፡

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 16:19-24**

**ጌቶችዋ የትርፋቸው ተስፋ እንደወጣ ባዩ ጊዜ ጳውሎስንና ሲላስን ይዘው ወደ ገበያ በሹማምት ፊት ጐተቱአቸው ወደ ገዢዎችም አቅርበው እነዚህ ሰዎች አይሁድ ሆነው ከተማችንን እጅግ ያናውጣሉ፡፡ እኛም የሮሜ ሰዎች ሆነን እንቀበላቸውና እናደርጋቸው ዘንድ ያልተፈቀደልንን ልማዶች ይናገራሉ አሉ፡፡ ሕዝቡም አብረው ተነሡባቸው ገዢዎቹም ልብሳቸውን ገፈው በበትር ይመቱአቸው ዘንድ አዘዙ ብዙም ከደበደቡአቸው በኃላ ወደ ወህኒ ጣሉአቸው የወህኒው ጠባቂ ተጠንቅቆ እንዲጠብቃቸው አዘዙት እርሱም የዚህን ዓይነት ትዕዛዝ ተቀብሎ ወደ ውስጠኛው ወህኒ ጣላቸው እግራቸውንም በግንድ አጣብቆ ጠረቃቸው፡፡**

16:19 *"የትርፋቸው ተስፋ እንደወጣ ባዩ ጊዜ"* እነዚህ ጌቶች ሰው ከክፉ ባርነት ነፃ መሆንና አለመሆን ሳይሆን የሚያሳስባቸው ትርፍ ማግኘታቸው ብቻ ነበር፡፡

▣ *"ጳውሎስና ሲላስን ይዘው"* ሉቃስ እና ጢሞቴዎስ ነበሩ፤ ነገር ግን ለምን እነርሱን ወደ እስር ቤት እንዳልወሰዱአቸው የሚያብራራ መረጃ የለም፡፡

16፡20 *"ገዢዎች"* ሉቃስ የሮማውያን መሪዎችን ማዕረግ ጠንቅቆ የሚያውቅ ነው፡፡

16፡20, 21 *"አይሁድ ሆነው.... የሮሜ ሰዎች ሆነን"* የሮማውያንን የዘር ብልጫ ለማሳየት የተጠቀሙበት ንግግር ነው፡፡ ገላውዲዮስ ከሮም ፊፅሞ እንዲወጣ ትዕዛዝ አውጥቶ ነበረ ከ49-50 ዓ.ም በተጨማሪም ማንኛውንም የአይሁድ የሀይማኖት እንቅስቃሴ እንዲታገድ አድርጎ ነበር፡፡ (Clcero's profiasco 28 እና Javenal 14:96.106 ) በማንበብ ተጨማሪ ግንዛቤ ያግኙ፡፡

▣ *"እናደርጋቸው ዘንድ ያልተፈቀደልንን ልማዶች ይናገራሉ"* የማርተኝነት መንፈስ ከነበረባት ሴት ጉዳይ ጋር የሚያገናኝ አይደለም ነገር ግን ወንጌልን በመስበካቸው ተቃውሞ ደርሶባቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ክርስትና በሮማ መንግስት ዕውቅና ቢሰጠውም ነገር ግን ተቃውሞው እንደቀጠለ ነበር፡፡ ለአይሁድ ሮማውያን በምኩራባቸው መቀበል ህብረት ማድረግ ለአይሁድ ህገወጥ መሆን ነው፡፡ ለጳውሎስም ይህ ድርጊታቸው ህገወጥ ነው ነገር ግን በራሳቸው ፈቃድ የወደዱትን ስለሚያደርጉ ያለ ህግ ሁሉን ያደርጉ ነበር፡፡

16፡22 *"ልብሳቸውን ገፈው በበትር ይመቱአቸው ዘንድ አዘዙ"* ሮማውያን ከሚያከናውኑት ቅጣት ቀላል የሚባለው ነበር፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ በእንዲህ አይነት ሁኔታ ሦስት በተለያዩ ጊዜአት ድብደባ ደርሶበታል (2ቆሮ 11፡25 1ተሰሎ 2፡2)፡፡

16፡24 *"ውስጠኛው እስር ቤት"* ይህ ማለት ከፍተኛው ጥበቃ ያለበት ሥፍራ ማለት ነው፡፡ የፍርሃት መንስኤዎች አሉ (ቁ 29)፡፡ ጳውሎስ አጋንንትን የማስወጣቱ አገልግሎት ሀሳባቸውን ተቆጣጥሮታል፡፡

▣ *"እግራቸውንም በእንጨት ማሰር"* በዚያን ዘመን የነበሩት እስር ቤቶች በብዛት ግድግዳቸው ላይ የሚታሰር ሰንሰለት ነበራቸው፡፡ እናም እንግዲህ በሮቹ ትንሽ ብቻ ይዘጉ ነበር እንጂ አይቆለፉም፡፡ እነዚህ ማሰሪያዎች እግራቸውን በሰንሰለት ይዘው ይቆያሉ፡፡ ይህም ደግሞ ጥበቃው ዋስትና እንዲኖረው ያደርጋል፡፡

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡** 16፡ 25 -34
**በመንፈቀ ሌሊት ግን ጳውሎስና ሲላስ እየፀለዩ እግዚአብሔርን በዜማ ያመሰግኑ ነበር፡፡ እስረኞችም ያደምጡአቸው ነበር፡፡ ድንገትም የወህኒው መሠረት እስኪናወጥ ድረስ ታላቅ የምድር መንቀጥቀጥ ሆነ በዚያን ጊዜም ደጆች ሁሉ ተከፈቱ የሁሉም እስራት ተፈታ፡፡ የወህኒውም ጠባቂ ከእንቅልፉ ነቅቶ የወህኒው ደጆች ተከፍቶ ባየ ጊዜ እስረኞቹ ያመለጡ መስሎት ራሱን ይገድል ዘንድ አስቦ ሰይፉን መዘዘ፡፡ ጳውሎስ ግን በታላቅ ድምፅ ሁላችን ከዚህ አለንና በራስህ ክፉ ነገር አታድርግ ብሎ ጮኸ፡፡ መብራትም ለምኖ ወደ ውጪም አውጥቶ ጌቶች ሆይ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል አላቸው፡፡ እነሱም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እመን አንተና ቤተሰዎችሁ ትድናላችሁ አሉት፡፡ ለእርሱና በቤቱ ላሉ ሁለት ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ተናገሩአቸው፡፡ በሌሊትም በዚያች ሰዓት ወስዶ ቁስላቸውንም አጠበላቸው ያን ጊዜውንም እርሱ ከቤተሰዎቹ ሁሉ ጋር ተጠመቀ ወደ ቤቱም አውጥቶ ማዕድ አቀረበላቸው በእግዚአብሔርም ስላመነ ከቤተሰዎቹ ጋረ ሃሴት አደረገ፡፡**

16፡25 *"በመንፈቀ ሌሊት"* ጳውሎስና ሲላስ ከህማማቸው የተነሳ መተኛት የተሣናቸው ይመስላል፡፡

▣ *"እየፀለዩ እግዚአብሔርን በዜማ ቃል ያመሰግኑ ነበር"* የሚዘምሩት መዝሙር ሌሎች እስረኞችን ወደ ክርስቶስ ልባቸውን እንዲያቀኑ የሚያደርገ መሆኑን የሚያጠራጥር አይሆንም፣ የምድር መንቀጥቀጥ በሆነም ጊዜ ማንም እስረኛ አላመለጥም (ሐዋ 16፡25 28)፡፡

▣ *"እስረኞቹም ያደምጧቸው ነበር"* ጳውሎስን እና ሲላስን ያለማቋረጥ እስረኞቹ ያደምጡአቸው ነበር፡፡ ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን እና በግሪኩ ፅሑፍም ላይ የተለመደ አይደለም፡፡ የዚህን ተመሳሳይ በብሉይ ኪዳን መፅሐፍት በሆነ በ1ሳሙ 15፡22 ላይ በዝርዝር ተቀምጧል፣ ይህ በዚህ ክፍል ላይ ያለው መስማት ደስታ የተንፀባረቀበት ነበር፤ እንዲሁም እስረኞቹ በደስታ ውስጥ ሆነው መዝሙሩን መስማታቸው ዓረፍተ ነገሩ ያስረዳናል፡፡ እነዚህ እስረኞች ይህንን መዝሙር በመስማት ለእግዚአብሔር ፍቅርና ርህራሄ ልባቸውን መስጠታቸው ምንም ጥርጥር የሌለው ክስተት ነው፡፡

16፡26 *"የምድር መንቀጥቀጥ"* የምድር መንቀጥቀጥ የተፈጥሮ ክስተት ቢሆንም ነገር ግን በመለኮት አድራጊነት በተወሰነ አላማ የተደረገ መሆኑን ከውጤቱ መገንዘብ ይቻላል፡ (ማቴ 27፡51 54 ፤ 28፡2) እግዚአብሔር መልአኩን በመላክ ጴጥሮስን ከእስር ቤት አድኖታል፤ (ሐዋ 4፡31) ነገር ግን ጳውሎስን ለማዳን እግዚአብሔር የተጠቀመበት ሌላ አሰራር ነው፡፡

16፡27 *"ሰፍፉ"* ሮማውያን የሞት ቅጣት የሚያከናውኑበት መሳሪያቸው ነው፤ የእስር ቤቱ ዘብ እስረኞች ቢያመልጡ የእነሱን ቅጣት በዚህ ሰይፉ ይቃጣ ነበር፡፡

16:28 ሐዋርያው ጳውሎስ በሌሎች እስረኞች አእምሮ ላይ መልካምን ተፅኖ አሳድሮባቸው፡፡

16:29 **"መብራትም ለምኖ"** በብዙ ቁጥር የተቀመጠ ቃል ነው ይህም የሚያመለክተው ሌሎች ዘቦች ከእርሱ ጋር እንደነበሩ ያስገነዝበናል፡፡

16:30 **"ጌቶች ሆይ እድን ዘንድ ምን ማድረግ አለብኝ"** ጥያቄው የሰው ዘር ሁሉ ጥያቄ ነው፡ (1) የእግዚአብሔርን በመፍራት የሚደረግ ጥያቄ ነው፡፡ (2) የእግዚአብሔርን እውነተኛ ሰላም ከመፈለግ የሚመጣ ጥያቄ ነው፡፡

16:31 **"በጌታ በኢየሱስ ስም እመን"** እመን የሚለው ግስ ትርጉሙ "ታመን፣ እምነት፣ ተደገፍ" የሚል ፍቺ ይሰጣል፡፡ ይህ ሰው የሚያምነው የቤተክርስቲያንነ ዶክትሪን ወየም የመፅሐፍ ቅዱስን ስነመለኮት ሳይሆን በኢየሱስ እንዲያምን መጠየቁ የዴህንነት መንገድ ቀላል እንደሆነ ያስገነዝበናል፡፡

▣ **"አንተና ቤተሰቦችሁ ትድናላችሁ"** የጥንት ዘመን የቤተሰብ መሪ የሆነው ሰው ሃይማኖት ቤተቦቹ ያንን ሐይማኖት ይከተሉ ነበር፡፡ (ሐዋ 10:2 11:4:16:15)

16:33 **"ያን ጊዜውንም እርሱ ከቤተዎቹ ሁሉ ጋር ተጠመቀ"** የጥምቀትን አስፈላጊነት ይናገራል፡፡ (ሉቃ 3:21) እና ትዕዛዝም ነው፤ (ማቴ 28:19) በሐዋርያት ስራ መፅሐፍ ተመሳሳይ ታሪክ አለ፡፡ (ሐዋ 10:47-48) ለተጨማሪ ግንዛቤ ይህንን ጥቅስ ያንብቡ፡፡

16:34 **"በእግዚአብሔርም ስላመነ ከቤተሰዎቹ ሁሉ ጋር ሐሴት አደረገ"** ሁለቱ ግሶች ሰውየውን የሚያመላክት ነው፣ "ስላመነ" እና "አደረገ" አመነ የሚለው ቃል እርግጠኛ የሆነ ነገር እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 16:35-40**
**በነጋም ጊዜ ገዢዎቹ እነዚያን ሰዎች ፍታቸው ብለው ሎሌዎቻቸውን ላኩ፡፡ የወህኒው ጠባቂ ትፈቱ ዘንድ ገዢዎች ልከዋል እንግዲህ አሁን ወጥታችሁ በሰላም ሂዱ ብሎ ለጳውሎስ ነገረው፡፡ ጳውሎስ ግን እኛ የሮሜ ሰዎች ስንሆን ያለ ፍርድ በሕዝብ ፊት ደብድበው በወህኒ ጣሉን አሁንም በስውር ይጥሉናል አይሆንም ራሳቸው ግን መጥተው ያወጡን አላቸው፡፡ ሎሌዎቹም መጥተው ለገዢዎች ነገሩ፡፡ የሮሜ ሰዎችም እንደሆኑ በሰሙ ጊዜ ፈሩ መጥተውም ማለዱአቸው አውጥተውም ከከተማ ይወጡ ዘንድ ለመኑአቸው፡፡ ከወህኒውም ወጥተው ወደ ልድያ ቤት ገቡ ወንድሞችንም ባዩ ጊዜ አፅናኑአቸውና ሄዱ፡፡**

16:35 **"ሎሌዎቻቸውን"** እነዚህ በትርን ይዘው የሚዞሩ ስርዓት አስከባሪዎች ናቸው፡፡ (ሐዋ 16:26) የኢጣሊያን ፋሺስት ይህንን መጠሪያ ይጠቀሙበት ነበር፤ የሚይዙአቸውም በትሮች የስልጣን ተምሳሌቶች ነበሩ፡፡

16:37 **"የሮሜ ሰዎች ስንሆን"** ፊሊጲስዮስ የሮማውያን ቅኝ ግዛት ነበረች፤ በመሆኑም በዚህች ከተማ ሮማዊ ተጨኑአል የሚል ተጨባጭ ማስረጃ ቢገኝ ከፍተኛ ቅጣት ያሰጣል፡፡

16:39 ሐዋርያው ጳውሎስ ተቃውሞ ያደረገበተ ዋናው ምክንያት የተሻለ መብትን የፊሊጵስዮስ ቤተክርስቲያን እንድትለማመድ በማሰብ ነው፡፡ የፊሊጵስዮስ ቤተክርስቲያን መሪዎች ወንጌልን መስበክ ህገወጥ እንዳይደለ ማሳየት እንዳለባቸው ምሳሌ ለመሆን ጳውሎስ ተቃውሞውን አድርጓል፡፡

16:40 **"እና ሄዱ"** ሉቃ በዚህ ከተማ ቀርቶ ነበር (ሐዋ 20:5-6)፡፡

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ለመርዳት ነው የተሰናዱት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋነኞቹን ጉዳዮች ለማጤን እንዲረዳ ነው፡፡ ሐሳብ ለማጫር እንጂ መደምደሚያ አይደሉም፡፡

1. መንፈስ ቅዱስ የኢየሱስ መንፈስ የሚል ስያሜ የተሰጠበት ምክንያት ምንድነው
2. እግዚአብሔር ሚሲዮናውያኑን ተቃውሞ እንዲገጥማቸው ለምን ይፈቅዳል
3. ጳውሎስ የሟርተኝነት መንፈስ የነበረባትን ሴት ምስክርነት ለምን አልተቀበለም
4. በፊሊጵስዮስ የዳኑትን ሰዎች ስም ዝርዝር ጥቀስ
5. ጳውሎስ እና ሲላስ ብቻ ለምን ታሰሩ
6. እስረኞች ከእስር ስለምን አላመለጡም

7. የድነት መንገዶች ጥቀስ ከሌሎቹ ምዕራፎች ጋር አነፃፅር።
8. የእስር ቤቱ ዘብ የአይሁድ ወይም የክርስትና ሃይማኖት እውቀት ይኖረው ይሆን
9. ቤተሰዎቹ ዳኑ የሚለውን እንዴት ትገለፁታላችሁ
10. ጳውሎስ ገዢዎች ይቅርታ እንዲያደርጉ የተጠቀመበትን መንገድ አስረዱ።

# የሐዋርያት ስራ 17

## የምንባቡ ክፍፍል በአዳዲሶቹ ትርጉሞች

| የተየመቅሶ[4] | አኪጀት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የተሰሎንቄ አመፅ | በተሰሎንቄ ክርስቶስ ተሰበከ | ከተሰሎንቄ ወደ አቴንስ | በተሰሎንቄ | በተሰሎንቄ አይሁድ ተቸገሩ |
| 17፡1-9 | 17፡1-4 | 17፡1-4 | 17፡1-4 | 17፡1-4 |
| | አመፅ በኢያስን ቤት ላይ | | | |
| | 17፡5-9 | | 17፡5-9 | 17፡5-9 |
| ሐዋርያት በቤሪያ | አገልግሎት በቤሪያ | | በቤሪያ | አዲስ ችግር በቤሪያ |
| 17፡1015 | 17፡10-15 | 17፡10-15 | 17፡10-15 | 17፡10-12 |
| | | | | 17፡13-15 |
| ጳውሎስ በአቴና | ፈላስፎች በአቴና | ጳውሎስ በአቴና | በአቴና | ጳውሎስ በአቴና |
| 17፡16-21 | 17፡16-21 | 17፡16-21 | 17፡16-21 | 17፡16-18 |
| | | | | 17፡19-21 |
| | በአርስፋዬስ ተናገሩ | | | |
| 17፡22-28a | 17፡22-34 | 17፡22-31 | 17፡22-31 | 17፡22a |
| | | | | የጳውሎስ ንግግር በአርስፋጐስ ፊት |
| | | | | 17፡22b-23 |
| | | | | 17፡24-28 |
| 17፡28b-31 | | | | |
| | | | | 17፡29 |
| | | | | 17፡30-31 |
| 17፡32-34 | | 17፡32-34 | 17፡32-34 | 17፡32-34 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (ከ "**መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ**" **ገጽ** vii)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

*ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።*

*ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።*

1. ምንባብ አንድ

2. ምንባብ ሁለት

3. ምንባብ ሶስት

4. ወ.ዘ.ተ

**የአውዱ ዕይታ**

በአቴና የነበረውን የጳውሎስን መልዕክት ይዘረዝራል (17፡15-34) ከሐዋ 14፡15-18 ተመሳሳይ ነው።

ሀ. አንድ እግዚአብሔር አለ፣ አንድ የሰማይ ፈጣሪ (መንፈስ) እና የምድር ፈጣሪ (የሚታየውን)

1. ህይወት የላቸውም ነገር ግን በእርሱ ተፈጥረዋል።
2. ሰው በሰራው መቅደስ አይኖርም
3. እግዚአብሔር ከእነዚህ ፍጥረታትን ከሰው ዘር ምንም አይፈልግም።
4. ይህ እግዚአብሔር የህይወት ሁሉ ምንጭ ነው።

ለ. እግዚአብሔር በሰው ታሪክ ላይ ይሰለጥናል።

1. የሰው ዘርን ሁሉ ከአንድ ሰው ፈጥሮአቸዋል
2. የሰውን መኖሪያ ወስኗል

ሐ. በሰው ልብ ውስጥ እርሱን መፈለግ አኑሮአል።

መ. ሐጢያት ሰውን ከእግዚአብሔር ለይቶታል።

1. ሳናውቅ ከእግዚአብሔር ላይቶታል
2. ሰው ሁሉ ንሰሃ መግባት አለበት

ሠ. እግዚአብሔር በፍጥረቱ ላይ ይፈረዳል

1. ለፍርድ የተቀጠረ ቀን አለ
2. ፍርድ በመሲሁ ይከናወናል
3. መሲሁ ከሙታን ተነስቷል በዚህም ስራው ህያው መሆኑን አሳይቷል።

**የተሰሎንቄ ከተማ**

ሀ. የተሰሎንቄ ከተማ የታሪክ ዳራ፡-

1. ተሰሎንቄ በቴራሚክ የባህር ወሽመጥ የምትገኝ ከተማ ነበረች ከዚህም የተነሳ የወደብ ከተማ ሆናለች። የተሰሎንቄ ከተማ በትልቅነቱ፤ በንግድ እና በመቂዶንያ ካሉ ከተሞች በፖለቲካ ማዕከልነቷ ዝና የነበራት ከተማ ነበረች።
2. ተሰሎንቄ "ተርማ" ከሚለው በአከባቢው ከሚገኝ የተፈጥሮ ፋል የውሃ ምንጭ የተገኘ ስያሜ ነው። ከጥንት ፀሐፊዎች ሽማግሌው ፒሊኒ ተሪማ እና ተሰሎንቄ ከተማ የታሪክ ዳራ ከሆነ ከተማይቱ በተፈጥሮ የፍል ውሃ የተከበበች ነበረች ማለት ነው። (Lean Morris The first and second Epistles to the Theualoniand grand Rapids WM.B Eerdmans publishing company, 1991 P.11#) ክርስትና እየተስፋፋ በነበረበት ወቅት የተሰሎንቄ ከተማ ቅፅል ስያሜ "የኦርቶዶክስ ከተማ" ትባል ነበር ምክንያቲም የክርስቲያኖች መናሃሪያ በመሆንዋ ነው። ( ( ዛሬም ተሰሎንቄ የግሪክ ሳሎኔካ የምትባል ከተማ ነች።
3. ተሰሎንቄ ልክ እንደ ቆሮንቶስ የብዙ ሰዎች መሰብሰቢያ ነበረች፤
   ሀ. በሰሜን  ተሰሎንቄ ባርቤሪክ ጀርሚክ የሚባሉ ህዝቦች በራሳቸው የጣኦት ሃይማኖት እና ባህል የሚኖሩበት ከተማ ነች
   ለ. በርካታ የግሪክ ሰዎች ከደቡብ እና ከሰሜን ኤጄሪያ ባህር ደሴቶች ለመኖር ይመጡ ነበር በመሆኑም ባህላቸውንና ፍልስፍናቸውን ይዘው ይመጡ ነበር።
   ከምዕራም የመጡ ሮማውያንም ይኖሩ ነበር ከእንዚህም መሃከል ጡረታ የወጡ ወታደሮች ያላቸው ጥረትና ሃብት ይዘው ወደዚህች ከተማ ለመኖር ይመጡ ነበር
   ሐ. ከምዕራብ የመጡ ሮማውያንም ይኖሩ ነበር ከእንዚህም መሃከል ጡረታ የወጡ ወታደሮች ያላቸው ኀሪትና ሃብት ይዘው ወደዚህች ከተማ ለመኖር ይመጡ ነበር።
   መ. በመጨረሻ በርካት አይሁዳውያን ከምስራቅ በመምጣት የከተማውን ህዝብ ቁጥር አነድ ሶስተኛ ሆነዋል። በተጨማሪም የአይሁድ ሃይማኖትን ከነስርዓቱ ያከብሩ እና ይፈፅሙ ነበር።
4. የተሰሎንቄ ነዋሪዎች ሁለት መቶ ሺ ይሆናሉ ነገር ግን ከተማይቱ የብዙ እንግዳ ሰዎች መሰብሰቢያ ነበረች። በዚህች ከተማ ከተፈጥሮ ፋል ውሃ የተነሳ የመዝናኛ እና የሕክምና ማዕከል ነበረች። በተሰሎንቄ ካለው የባህር ወደብ የተነሳ የንግድ እንቅስቃሴአቸው ከፍተኛ ነበር።
5. ተሰሎንቄ ልክ እንደ ዋና ከተማ የሚቄዶንያ የፖለቲካ ዋና መሰራያ ቤት የሚገኝበት ከተማ ነበረች። በዚህም ከተማ በርካታ ጡረታ የወጡ የሮማ ወታደሮች ይኖሩባት ነበር። በተሰሎንቄ ከተማ የሚኖሩ ሁሉ ሮማውያን ስለነበሩ ለመንግስት ግብርን አይከፍሉም ነበር። በዚህች ከተማ የሚገኙ ገዥዎች ፓሊትረችስ

በመባል የታወቁ ነበር፡፡ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይህንን ስያሜ አናገኘውም፤ ነገር ግን “Vardar Gate, Farrar, P.37)” በዚህ መፅሐፍ ፋቺው ይገኛል፡፡

ለ. ጳውሎስን ወደ ተሰሎንቄ ያመጣው ምክንያት፡-

1. ጳውሎስን ወደ ተሰሎንቄ እንዲሄድ ያደረጉ ምክንያቶች ቢኖሩም ነገር ግን የእግዚአብሔር ጥሪ ነበረበት፡፡ በመጀመሪያ ጳውሎስ ወደ አውሮፓ ለመሄድ አቅዶ ነበር፡፡ የጳውሎስ ፍላጐት በመጀመሪያው የሚሲዮናዊነት ጉዞው የመሠረታቸውን አብያተ ክርስቲያናት በዚህ በሁለተኛው ጉዞው መጐብኘት በመቀጠልም ወደ ምስራቅ መሄድ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ግን በሰሜን ምስራቅ ያለውን የወንጌል በር ሲዘጋ ጳውሎስን በሚያሳየው ሪዕይ ወደ ሚቄዶኒያ ሊያመጣው በመፈለጉ ነበር (ሐዋ 16፡6-10) ስለዚህ ሁለት ነገሮችን መዘርዘር ይቻላል፡፡ በአውሮፓ አህጉር ወንጌል ደርሶ ነበር፡፡ ጳውሎስ በሜቄዶንያ ለነበረው ሁኔታ ደብዳቤ መፅሐፍ ነበረበት፡፡ (Thomas Carter, *life and letters of Paul*, Nashville: Cokesbury Press, 1921, P112)፡፡
2. ጳውሎስ ወደ ተሰሎንቄ እንዲሄድ ያደረገውን የሚታዩ ምክንያቶች እንመልከት፡-
   ሀ. ጳውሎስ ወደ ፊሊጲሲዮስ ምኩራብ ወደ ሌሰበት ቦታ መሄዱ ይታወሳል፡፡ ነገር ግን የሟርተኝነት መንፈስ የነበረባት ሴት በመፈወስ እና የጌቶችዋ ትርፊ በመነካቱ በጳውሎስ ላይ ከፍተኛ እስራትና ድብደባ ደርሶበት ነበር፡፡ በዚሁም ምክንያት ያሰበውን የቤተ ክርስቲያን ምስረታ ከፈፀመ በኋላ ከተማውን ለመልቀቅ ተገዷል፡፡
   ለ. ጳውሎስ በቀጣይነት የት ሄደ? ጳውሎስም ምኩራብ ወደ ሌሰበት ወደ አንፊጶልና አጶሎንያ አምርቷል፡፡
   ሐ. ጳውሎስ ታላቅ ከተማ ወደ ሆነችው ወደ ተሰሎንቄ በመምጣት በመጀመሪያ አይሁድን በዚያ አግኝቷቸዋል፡፡ ይህን ያደረገበትን ምክንያት እንመልከት፡፡
      (1) የብሉይ ኪዳን መፅሐፍ ዕውቀት ስላላቸው ነበር
      (2) በእነርሱ ምኩራብ የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተማርና ለመስበክ ምቹ መንገድ ስለሚሆንለት ነበር
      (3) የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ህዝቦች ስለሆኑ ነው (ማቴ 10፡6፣ሮሜ 1፡16-17፣ 9-11)
      (4) ኢየሱስ በመጀመሪያ ራሱን ለአይሁድ በመቀጠልም ለአለም ሁሉ ሰቷል፤ በመሆኑም ጳውሎስ የእርሱን ፈለግ ለመከተል በማሰብ ነው፡፡

**የጳውሎስ ባልንጀሮች**

ሀ. ጳውሎስ በተሰሎንቄ ከጢሞቲዎስ እና ከሲላስ ጋር ይሰራ ነበር፡፡ ሉቃስ በፊሊጶሲዮስ ከጳውሎስ ጋር ነበር ነገር ግን በዚያው ተርታል፡፡ ይህንን እኛ በሚለው ቃል ማወቅ እንችላለን (ሐዋ 16 እና 17) ሉቃስ በፊሊጶኒዮስ ነበረሩ ጊዜ በማለት ሲገልፅ ነገር ግን ወደ ተሰሎንቆ ሲሄዱ እነርሱ በማለት ፅፏል፡፡

ለ. ሲላስ (ሲልዳና) ማርቆስና በርናባስ ተለይተውት ወደ ቆጥሮስ በሄዱ ጊዜ ጳውሎስ ደግሞ ከሲላስ ጋር በመሆኑና የሁለተኛውን የሚሊዮናዊነት ጉዞውን አድርጓል፡፡

1. በመጀመሪያ የሲላስ ስም የተጠቀሰው በሐዋ 15፡22 ላይ ነው፤ እርሱም በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን የወንድሞች መሪ ነበር፡፡
2. ነብይ ነበር (ሐዋ 15፡32)
3. እንደ ጳውሎስ የሮም ዜግነት ነበረው (ሐዋ 16፡37)
4. ሲላስ እና ይሁዳ በርሲሳ ከኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን በወቅቱ ለነበረው ችግር ወደ አንፃኪያ ተልከዋል፡፡ (ሐዋ 15፡22፣30-35)
5. ጳውሎስ በፃፈው መፅሐፍ ስሙ ብዙ ጊዜ ተጠቅሷል በተጨማሪም በ2ቆሮ 1፡19 ላይ ሲያመሰግነው ይታያል፡፡
6. ከሐዋርያው ጴጥሮስ ጋር በፀሐፊነት ተሳትሮ ነበር) 1ጴጥ 5፡12)
7. ጳውሎስ እና ጴጥሮስ ሲላስን ሲልቫና በሚል ስያሜ ሲጠሩት ሉቃስ ግን ሲላስ በማለት ይጠራዋል፡፡

ሐ. ጢሞቲዎስ የጳውስ የወንጌል አጋሩ ነበር፡፡

1. በጳውሎስ የመጀመሪያ የሚሲዮናዊነት ጉዞው የጢሞቲዎስ ልብ ተቀይbል ፤ እርሱም በልስጥሬን ይኖር ነበር፡፡
2. ጢሞቴዎስ በአባቱ ግሪካዊ እና በእናቱ አይሁዳዊ ነበር፡፡ ጳውሎስ ይህ ወጣት ለአህዛብ ወንጌልን እንዲሰብክ በብረቱ ፈልጓል፡፡
3. ለአይሁድ ወንጌልን እንዲሰብክ ጳውሎስ ይህን ወጣት ገርዞታል፡፡
4. ጢሞቲዎስ በጳውሎስ ደብዳቤዎች መጀመሪያ ሰላምታ ተልኮለታል፡፡ (12ቆሮ፣ ቆላ፣ 1 እና 2 ተሰሎን እና ፊልሞና)
5. ጳውሎስም ጢሞቲዎስን ልጄ በማለት ይጠራዋል (1ጢሞ 1፡2፣ 2ጢሞ 1፡2፣ ቲቶ 1፡4)
6. በጳውሎስ ደብዳቤዎች ውስጥ ጢሞቲዎስ ወጣት እና የሚፈራ ባህሪ እንዳለው ያሳያል፡፡ ነገር ግን የጳውሎስ ልብ የሚታመንበት ሰው ነበር (ሐዋ 19፡27፣ 1ቆሮ 4፡17፣ ፊሊ. 2፡19)፡፡

መ. በተሰሎንቄ ጳውሎስ በነበረው አገልግሎት ከእርሱ ጋር ይተባበሩ የነበሩት ሰዎች ስም ተጠቅሷል እነርሱም፡- አርስጎርኮስ (ሐዋ 19፡29፣ 20፡4፣ 27፡2) ደማስ ከተሰሎንቄ ከተማ (ፊሚሞ 24፣ 2ጢሞ 4፡10) እነዚህ ጳውሎስ በተሰሎንቄ የነበረውን የሚሲዮናዊነት አገልግሎቱን ያገዙ ናቸው፡፡

በከተማ የጳውሎስ አገልግሎት

ሀ. በተሰሎንቄ ጳውሎስ ዘወትር እንደሚያደርገው ወንጌልን በመጀመሪያ ለአይሁዳውያን በመቀጠልም ለአህዛቦች በስኳል። ጳውሎስ በተሰሎንቄ ለሶስት ሰንበታት ኢየሱስ እርሱ መሲህ እንደሆነ በማስተማር የብሉይ ኪዳንን መፅሐፋት ይጠቅስ ነበር። ( ዘፍ 3:15 2 ኢሳ 53) በተጨማሪም ለሁሉም ፈፅሞ ስለተሰጠው ድነት እና ትንሳኤ ያስተምር ነበር በብሉይ ኪዳን የተነገረው የመሲሁ ትንቢት መፈፀሙን ያበሰረ ነው።

ለ. በተሰሎንቄ ለጳውሎስ መልእክት ምላሽ ከሰጡት መሃከል አይሁዶች፣ የተሰጡ አህዛቦች፣ ኢየሱስን እንደግል አዳኛቸው አድርገው የተቀበሉ ይገኙበታል።

ሐ. አህዛቦች የቤተክርስቲህየን አባል መሆናቸውን ሁለቱ የአዲስ ኪዳን መፅሐፍት የብሉይ ኪዳንን ጥቅስ ሳይጠቅሱ አፅድቀውት ይነበባል። አህዛቦች ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛቸው አርገው የተቀበሉበት ምክንያቶች፡-

1. በተሰሎንቆ የሚገኘው የጣኦት አምልኮ (ኦሎንፕስ እና ሌሎችም) ሃይል እንደሌላቸው በመረዳት ወደ ክርስቶስ መተዋል።
2. ወንጌል ለሁሉም ነፃ ስጦታ በመሆኑ አህዛብ ወደ ክርስቶስ መተዋል።
3. ክርስቲያን ለመሆን አየሁዳዊ መሆን አይጠይቅም የአይሁድ ሃይማኖት በብዙ ስርዓት እና ዘረኝነት የተመሠረተ በመሆኑ ማንም ወደዚህ ሃይማኖት መገባት አይችልም ነበር።

መ. በርካታ ሴቶች ክርስትናን ተቀብለው ነበር። በግሪክ ሮማ ዓለም ከሚገኙት ሃራት በሜቂዶንያ እና በትንሹ እስያ ሃገራት ሴቶች ነፃነት ነበራቸው። (sit WM.M Ramsay, st. paul the Traveller and Roman citizen, New york: G.P putnam's sons, 1896, P.227) በአነስተኛ የኑሮ ደረጃም የሚገኙ ሴቶች የጣኦት አምልኮን እና ብዙ ጣኦታትን የማምለክ ነፃነት ነበራቸው። (Ramsay, P. 229)

ሠ. ጳውሎስ በተሰሎንቄ በነበረው ረጅም ቆይታ ችግሮች ተፈጥረዋል፡፡

1. በተሰሎንቄ ምኩራብ ሶስት ጊዜ ጳውሎስ አመክኖ ያለው ተጨባጭ ንግግር አድርጓል (ሐዋ 17:2)
2. ጳውሎስ በተሰሎንቄ የራሱን የድንኳን ስራ ወይም አንዳንዶች እንደሚሉት የቆዳ ስራውን ይሰራ ነበር (1 ተሰሎ 2:7-11)
3. ጳውሎስ በተሰሎንቄ በነበረ ጊዜ ከፊሊጳስዩስ ቤተክርስቲያን ሁለት የገንዘብ ስጦታዎች ተቀብሏል። በሁለቱ ከተሞች መሃከል የነበረው ርቀት 100 ማይል ነው። ጳውሎስ በዚህች ከተማ የቆየው ሁለት ወይም ሶስት ሳምንታት ብቻ መሆኑን የሚያሳየው በምኩራብ ሶስት ጊዜ ብቻ ማገልገሉ ነበር። (Shepard, P. 165#
4. በሐዋ 17:4 እና 1ተሰሎ 1:9፣ 2:4 መሃከል ያለው የሰዎች ልብ መለወጥ ልዩ የሚያደርገው አህዛቦቹ የጣኦት አምልኮን መካዳቸው ነው። ነገር ግን በሐዋርያት ስራ ላይ የሚገኙት አህዛቦች እግዚአብሔርን የሚፈሩ የጣኦት አምልኮን የሚያመልኩ ናቸው በዚህ ዓውድ መሠረት ጳውሎስ ከአይሁድ ይልቅ ጣኦትን በሚያመልኩ አህዛብ መካከል ያገለገለው  አገልግሎት ይበልጣል።
5. ጳውሎስ በአንድ ከተማ ታላቅ አገልገሎትን ለማገልገል ሲያስብ በመጀመሪያ በዚያ ከተማ ወዳሉት አይሁድ ይሄድ ነበር መልእክቱን ከተቃወሙ በመቀጠል ወደ አህዛብ ፊቱን ያዞር ነበር። አህዛብ ለጳውሎስ አምንታዊ ምላሽን ከሰጡ አይሁድ በከተማ ውስጥ ሁከትን ማስነሳት ልማዳቸው ነበር።

ረ. ከአይሁድ ሁከት የተነሳ ጳውሎስ የአሶንን ቤት ለመልቀቅ ተገዶ ከጢሞቴዎስና ከሲላስ ጋር ተደብቆ ነበር አይሁድ የኢሶንን ቤት ሲከቡ ጳውሎስ ግን በዚያ አልነበረም። እንግዲህ ይህ የአይሁድ አላስፈላጊ ሁከት ጳውሎስ በጨለማ ከተማይቱን ለቆ ወደ ቤሪያ ለመምጣት ተገዷል።

የቃል እና የጥምር ቃል ጥናት

**አእመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 17:1-9**
**በአንፊሊጳና በአጶሎንያ ካለፊ በኋላ ወደ ተሰሎንቄ መጡ በዚያም የአይሁድ ምኩራብ ነበር። ጳውሎስም እንደልማዱ ወደ እነርሱ ገባ ሶሶት ሰንበትም ያህል ከእነርሱ ጋር ከመፃሐፍት እየጠቀሰ ይነጋገር ነበር። ሲተረጉምም ክርስቶስ መከራ እንዲቀበልና ከሙታን እንዲነሳ ይገባው ዘንድ እያስረዳ ይህ እኔ የምሰብክላችሁ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ ነው ይል ነበር። ከእነርሱም አንዳንዶቹ ተረድተው ከሚያመልኩ ከግሪክ ሰዎች ብዙ ከከበሩትም ሴቶች ጥቂቶቹ ያይደሉ ከጳውሎስ እና ከሲላስ ጋር ተባበሩ። አይሁድ ግን ቀንተው ከስራ ፈቶች አገሩ ሰዎችን አመጡ ህዝብንም ሰብስበው ከተማውን አወኩ ወደ ህዝብም ያወጧቸው ዘንድ ፈልገው ወደ ኢያሶን ቤት ቀረቡ ባላገኙአቸውም ጊዜ ኢያሶንና ከወንድሞች አንዳንዶችን ወደ ከተማው አለቆች ጐትተው አለምን ያወኩ እነዚህ ወደዚህ ደግሞ መተዋል ኢያስንም ተቀብሏቸዋል። እነዚህም ሁሉ ኢየሱስ የሚሉት ሌላ ንጉስ አለ እያሉ የቄሳርን ትዕዛዝ ይቃወማሉ ብለው ጮሁ ህዝቡና የከተማውም አለቆች ይህን ነገር በሰሙ ጊዜ ታወኩ።**

17:1 "በአንፊጶልና በአጶሎንያ ካለፊ በኋላ" እነዚህ ሁለት ከተሞች የሚገኙት በምስራቅ ወደ ምዕራብ ሮም በሚወስደው አምስት መቶ ማይል ባለው የርቀት መንገድ ላይ ነው ይህ መንገድ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ አገሪቱን ለሁለት የሚከፍል ነው የተሰራውም ወደ ተሰሎንቄ እንዲወስድ ተደርጐ ነው።

▣ "ተሰሎንቄ" የዚህን ምዕራፍ መግቢያ ይመልከቱ።

▣ *"ምኩራብ ያለበት"* ይህ የሐዋርያው ጳውሎስ የእወጃ የደረጃ አቀማመጥ ነው፡፡ (ሐዋ 17፡2፣ 3፡26 ሐዋ 13፡46፣ ሮሜ 1፡16፣ 2፡9፣10 ሐዋ 9፡20፣ 13፡5፣ 14፡1፣17፡2፣10፣17፡18፡4፣19፣19፡8) ምኩራብ ያለበትን የመረጠው የብሉይ ኪዳንን መፅሐፍ መሠረት በማድረግ ለሌሎች ወንጌልን ለመስበክ እንዲያመቸው ነበር፡፡

17፡2 **"ለሶስት ሰንበቶች"** ጳውሎስ በተሰሎንቄ ቆይተው ለሶስት ሰንበቶች ብቻ ነው በምኩራብ ንግግር ማድረግ የቻለው ነገር ግን ከተማ ውስጥ ከዚያ በላይ ቆይታ ነበረው፡፡

▣ *"ከመፅሐፍት እየጠቀሰ ይነጋገር ነበር"* ጳውሎስ በብሉይ ኪዳን የተነገሩትን ትንቢቶች ከኢየሱስ ህይወት፣ ትምህርት፣ ሞት እና ትንሳኤ ጋር በማገናኘት ይሰብክ እና ያስተምር ነበር፡፡

17፡3

| | |
|---|---|
| NASB | *"እየገለፀ እና ማስረጃ እየሰጠ"* |
| NKJV | *"እየገለፀ እና እያሳየ"* |
| NKJV, NJB | *"እየገለፀ እና እያረጋገጠ"* |
| TEV | *"መፅሐፋትን እየገለፀ እና ከእነርሱ ማረጋገጫ እያገኘ"* |

በዚህ ቁጥር ላይ ቃል የሚተካው ፍቺ (ዲያኖጕ) ይህም ኢየሱስ በኤማኦስ መንገድ ላይ ለደቀመዛሙርቱ ከመፅሐፍት እየገለፀ ያስረዳበት ተመሳሳዩ ነው፡፡ (ሉቃ 24፡32፣ 45፣ ሉቃ 24፡31) በተጨማሪም የሊድያ ልብ እግዚአብሔር ከፈተላት የሚለውም ተመሳሳዩ ነው፡፡ (ሐዋ 16፡14)

ሁለተኛው በዚህ ቁጥር ላይ ያለውን ቃል የሚተካው ፍቺ (ፓራቲየቲማ) በአንድ ሰው ፊት ምግብ ማቅረብን ያመለክታል፡፡ ነገር ግን በዚህ ዓውድ መሠረት እውነትን ማቅረብ በሚል ሊተካ ይችላል፡፡ (ሐዋ 14፡23፣ 30፡32) ጳውሎስ ወንጌልን ለሰዎች በጥንቃቄ ያቀርብ ነበር፡፡ (1ጢሞ 6፣20፣ 2ጢሞ 1፡12፣14) አንዳንድ አይሁድ፣ እግዚአብሔርን የሚፈሩ አህዛብ እና ሴቶች አዎንታዊ ምላሽ ይሰጡ ነበር፡፡

▣ *"ክርስቶስ መከራ መቀበል ነበረበት"* በሰዋሰው ህግ መሠረት ቀድሞ የተወሰነ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በብሉይ ኪዳን ትንቢቶችም መሠረት መሲሁ ክርስቶስ መከራን መቀበል ይገባው ነበር፡፡ (ዘፍ 3፡15፣ መዝ 22፣ ኢሳ 52፡13-53፡12) ነገር ግን ሚስጥሩ ከአይሁድ መምህራን ተሰውbል፡፡ በሐዋርያት ስብከት እውነቱ ተገልጧል፡፡ (ሐዋ 3፡18፣ 26፡33፣ 1ጴጥ 1፡10-12) ይህ እውነት ለአይሁድ የማሰናከያ አለት ሆኖባቸዋል፡፡ (1ቆሮ 1፡22-25)

▣ *"ከሙታን ይነሳ ዘንድ እንዲገባው"* ይህ በሐዋርያት ዋነኛ የስብከታቸው አንኳር ሃሳብ ነበር፡፡ የወንጌል መካከለኛ እና ምሰሶ የሆነ መልእክት ነው፡፡

▣ *"የምሰብከው ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ"* በግሪኩ ፅሑፊ ላይ የዚህ ዓረፍተ ነገር የመጨረሻ ቃል እንደሚከተለው ተፅፎ እናገኛለን፡፡

1. ክርስቶስ ኢየሱስ (MSB)
2. ክርስቶስ ኢየሱስ (Vulgate እና Coptic translation)
3. ክርስቶስ ኢየሱስ (Mss P 74, A.D)
4. ኢየሱስ ክርስቶስ (MS)
5. ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ (MSE እና Bahaitic Coptic version)
6. "ክርስቶስ" (the Georgean version)

በርካታ የመፅሐፍ ቅዱስ ምሁራን ተራ ቁጥር አነድን ይመርጡታል ምክንያቱም ያልተለመደ በመሆኑ፡፡

በምኩራብ ክርስቶስ የሚለው ስም ያለው ትርጉም የተቀባው መሲህ ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ሶሶት የአገልግሎት ቢሮዎች ነበሩ፡፡ ንጉስ፣ ነብይ እና የክህነት አገልግሎት ኢየሱስ ሁሉንም ፈፅሞታል (ዕብ 1፡1-3) ይህ ቅባት ከእግዚአብሔርን ምርጫ የሚያመለክት ነው፡፡ (ሐዋ 4፡27) ይመልከቱ፡፡

17፡4

| | |
|---|---|
| NASB, NKJV | |
| NRJV | *"መረታት"* |
| TEV,NJB | *"ማመን"* |

ይህ የግሪክ ቃል የሚገኘው በአዲስ ኪዳን ብቻ ነው፡፡ ቀጥተኛ ትርጉሙ (በእባ መለየት) ነው፡፡ በዚህ ዓውድ ደግሞ መከተል ወይም መደባለቅ ሲሆን ይችላል፡፡ በብሉይ ኪዳን እጣ የእግዚአብሔር ፈቃድ መለያ ነበር፡፡ ሶስት መሠረታዊ ነገሮተን ማየት ተገቢ ነው፡፡ መስተዋድዱን፡ስርወ ቃሉን እና መለኮታዊ ሃንላፊነትን፡፡ እግዚአብሔር የሊዲያን ልብ እንደከፈተ ለእኛም ሊደርግልን ይችላል፡፡

▣ *"ከሚያመልኩም ከግሪኮች"* እነዚህ የአይሁድን ሃይማኖት የሚከተሉ ነገር ግን ሙሉ ለሙሉ ያልተለመዱ አህዛብ ናቸው እነዚህ ግሪኮች ሶስት ስርዓቶችን ያደርጉ ነበር፡ (1) እንደ አይሁድ ህግ ተገርዘው ነበር፣ (2) ተጠምቀው ነበር፣ (3) በመቅደስ መሰዋትን ያቀርቡ ነበር፡፡

▣ *"ሴቶችም --- ይተባበሩ ነበር"* በሚቄዶንያ ለስቶች ነፃነት ተሰጥቶ ነበር፡፡ (በሐዋ 13፡43፣45፣50) ተመሳሳዩን ተመልከቱ በግሪኩ ፅሑፍ ላይ እንዚህ ሴቶች የመሪ ወንዶች ሚስቶች መሆናቸውን ይገልፃል፡፡ ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ ያሉ ምሁራን የሴቶችን መብት ለማሳነስ ይህንን ዓውድ የራሳቸውን ትርጉም ይሰጡታል፡፡

17:5 **"አይሁድ ግን ቀንተው"** የአይሁድ አለማመን ያሳዝናል፡፡ (ሐዋ 14:2) ነገር ግን ቀናተኛ ናቸው (ሐዋ 5:17) ሳውልም ልቡ ሳይቀየር እንዲሁ ነበር የተለወጡት ሰዎች ቁጥር ተመልከቱ (ሐዋ 13:45)፡፡
ሉቃስ እንደ ጳውሎስ አይሁድን ሲጠቅስ በአሉታዊ ስሜት ነው (1ተሰሎንቄ 2:15-16)፡፡ ይህም ወንጌል ከሚቃወሙና ከሚገዳረሩት ጋር ያመሳስለዋል፡፡

▣ **"ከገቢያ የመጡ አንዳንድ ክፉ ሰዎች"** እነዚህ ሰዎች በገቢያ ስፍራ ስራ የሌላቸው ዘራፊዎች ናቸው፡፡

17:6 **"ወደ ኢያሶን ቤት ቀረቡ"** በሮሜ 16:21 የተጠቀሰው ሰው እንደሆነ ይገመታል፡፡

▣ **"ከወንድሞች አንዳንዶች"** በዚህ ሐረግ መሠረት ኢያሶን ገና አማኝ አልሆነም ነበር፡፡ ነገር ግን ኢያሰን እንዴት ወደ ወንጌል ስራ እንደገባ ግልፅ ማስረጃ የለም፡፡ ነገር ግን ያለው ማስረጃ፡ (1) ጳውሎስ ሲላስ ከእርሱ ጋር በጋራ ሰርተዋል፣ (2) ከኢየሱስ ቤት በመከራየት ቆይታ አድርገዋል (3) በቤቱም ሰንብተዋል፡፡
በዚህ ምዕራፍ ቁጥር ሰባት ላይ ያለው ግስ "እንደ እንግዳ መቀበል" የሚል ፍቺ አለው፡፡ (ሉቃ 10:38፣ 19:6፣ ያዕቆ 2:25)

▣ **"ወደ ከተማው አለቃ"** ይህ የከተማው ከንቲባ ነው፡፡ በመቄዶንያ ግዛት በሮማውያን የሚሰጥ የማዕረግ ስም ነው፡፡ ይህ ስያሜ በዚህ ክፍልና በቁ. 8 ላይ ብቻ ተፅፎ የሚገኝ ነው፡፡ ሉቃስ አካባቢውን ጠንቅቆ የሚያውቅ መሆኑን ያሳያል፡፡ ሉቃስ ፅሑፍቹ ሁሉ ትክክለኛ ማስረጃ እንዲያቀርቡ አድርጐ በተቻለው መጠን ተጠንቅቋል፡፡

▣

| | |
|---|---|
| NASB | **"አለን የሚያበሳጭ"** |
| NKJV,NRSV | |
| NJB | **"አለምን የሚገለብጥ"** |
| TEV | **"በየቦታው ችግር የሚፈጥር"** |

በገዥዎች ላይ አመፅን ለማነሳሳት የሚል ፍቺ ይሰጣል፡፡ (ሐዋ 21:38) ይህ በጣም ጠንካራ ቃል ነው፡፡ ጳውሎስ በገላትያ 5:12 ተጠቅሞበት እናነባለን፡፡ ከዚህ ምንባብ እንደምንረዳው የተሰሎንቆ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ስደት እንደገጠማት ነው፡፡

17:7 **"የቄሳርን ትዕዛዝ"** በሮም አይሁድ ያላቸውን የሃይማኖት ስርዓት የሚያስተካክል ትዕዛዝ ነበር፤ በተጨማሪም አይሁድ ከሮም እንዲወጡ የሚያስገድድ ትዕዛዝ ነበር፡፡ ይህ ግልፅ የሮማውያን ጣልቃ ገብነት ነበር እርሱም ወንጌል እንዳይሰብክ ሮማውያንም ወደዚህ እምነት እንዳይመጡ በመፍራት የተደረገ ነበር፡፡

▣ **"ኢየሱስ የሚባል አንድ ንጉስ አለ እያሉ"** ይህ ክስ በሁለት ምክንያቶች ነው፡ (1) ጳውሎስ በተሰሎንቄ አማኞች ስለ መጨረሻው ዘመን ዘርዝሮ በማስተማሩ ነበር፣ (2) ክርስቲያኖች በኢየሱስ የሚጠቀሙበት ቃል ለቄሳሮች ያገለግል ስለነበረ ዓመፅ እና ክስ ሊመሰረቱ ችለዋል (ንጉስ፣ ጌታ እና አዳኝ)፡፡

17:9 **"መሃላ"** በክርስቶስ ያመነ አዲስ ሰዎች ገንዘባቸውን ለመስጠት ፈቃደኞች ሆነዋል፡፡

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 17:10-15**
**ወዲያውም ወንድሞች ጳውሎስንና ሲላስን በሌሊት ወደ ቤርያ ሰደዱአቸው በደረሱም ጊዜ ወደ አይሁድ ምኩራብ ገቡ እነዚህም በተሰሎንቆ ከሚኖሩት ይልቅ ልበ ሰፊዎች ነበሩና ነገሩ እንዲህ ይሁንን? ብለው ዕለት ዕለት መፅሐፉትን እየመረመሩ ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ፡፡ ስለዚህም ከእነርሱ ብዙ ከግሪኮችም የከበሩት ሴቶችና ወንዶች ጥቂት ያይዳሉ አመኑ፡፡ በተሰሎንቄ ያሉት አይሁድ ግን ጳውሎስ በቤሪያ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል እንደ ሰበከ ባወቁ ጊዜ ወዲዚያው ደግሞ መጡና ህዝቡን አወኩ፡፡ በዚያን ጊዜ ወንድሞች ወዲያው ጳውሎስን እስከ ባህር ድረስ ይሄድ ዘንድ አቴና አደረሱት እንደሚቻላቸውም በፍጥነት ወደ እርሱ ይመጡ ዘንድ ወደ ሲላስና ወደ ጢሞቴዎስ ትዕዛዝ ተቀብለው ሄዱ፡፡**

17:10 **"ቤርያ"** በጳውሎስ ዘመን ቤርያ ስልሳ ማይል ወደ ሮም በሚወስደው መንገድ የተጠጋ ነበር፡፡ በዚህም ከተማ አይሁድ ስለነበሩ ጳውሎስ ከብሉይ ኪዳን መፅሐፍት በመጥቀስ ወንጌል ማስተማር ተችሎት ነበር፡፡

▣ **"ወደ አይሁድ ምኩራብ ገብተው"** ይህ የሚያመለክተው ጳውሎስና ሰዎች ረጅም ጉዞ በለሊት እንኳን ቢያደርጉም ነገር ግን በደረሱ ጊዜ ወደ ምኩራብ ሄደዋል፡፡ ምናልባት የደረሱበት ቀን ሰንበት ሊሆን ይችላል፡፡ በእርግጥ በአሁኑ ጊዜ ምዕራባውያን በፍጥነት ወንጌልን ለመስበክ እንደነጳውሎስ ፍቃደኞች አይደሉም፡፡

17:11 **"ልበ ሰፊዎች ነበሩ"** ይህ ሐረግ የሚያገለግለው ለባለጠጐች፣ ለተማሩ ሰዎች፣ በህዝቡ ለተከበሩ ሰዎች መግለጫ ሐረግ ነው፡ (LXX ኢዮ 1:3፣ ሉቃ 19:12) ለዚህ ዓውድ ይህ ትርጉም አይሰጥም ነገር ግን ምክንያቱም የቤሪያ ሰዎች

የተማሩ መሆናቸውን ለመግለፅ ሳይሆን አዲስ ነገር ለማወቅ የተዘጋጁ መሆናቸውን ለመግለፅ ሉቃስ የተጠቀመበት ዐረፍተ ነገር ነው (ቁ 12)፡፡

"ነገሩ እንደዚሁ ይሆንን? ብለው ዕለት ዕለት መፃህፋትን እየመረመሩ ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ" እውነተን ለማወቅ የሚጠቅም መንገድ ነው፡፡ የጳውሎስ አገልግሎት የብሉይ ኪዳንን መፅሐፍት ትንቢታቸው መፈፀሙን የሚጠቁም ነበር፡፡ ግን የተፈፀመውን ትንቢት እርሱም ክርስቶስን ለመቀበል ሰዎች ያንገራግሩ ነበር፡፡

17፡2 **"ብዙዎች አመኑ"** ከእነዚህ መካከል አይሁዶችና እግዚአብሔርን የሚፈሩ ከተባሉት ግሪኮችንም ያጠቃለለ ስብሰብ ነው፡፡ 1ሐዋ 8፡12 እና 4፡4)

▣ **"ዋና"** በሁለት ጥምር ቃል የተፈጠረ ነው "መልካም" እና "ቅርፅ" ወይም ገፅታ ከሚለው ቃል የመጣ ነው፡፡ ቃሉ ክብርን፣ ተቀባይነትን እና በህዝቡ ላይ መልካም ተፅህኖ በሚያሳድሩ ሰዎችን ለመግለፅ ይጠቀሙበታል፡፡ (ሐዋ 13፡50 እና ማርቆ 15፡43 እና ጆሴፍ አርማቲያስ)

17፡13 የጳውሎስ ተቀናቃኞች አላማቸው የተገለጠበት ክፍል ነው፡፡ ከእነዚህ መካከል ቀጥተኛ የሚባሉ አይሁዳውያን ይገኙበታል (ምሳሌ ሳውል)፡፡ በዚህ ክፍል የሚያሳዩት ስነ ምግባር መንፈሳዊ ደረጃቸውን ያመለክታል፡፡

17፡16 "አቴና" የግሪክ ባህላዊ ቅርስ የነበረባት ታላቅ ከተማ ነበረች፡፡ አሁንም ቢሆን ቢሮም ዓለም የትምህርት ማዕከል የሆነች ድንቀኛ ከተማ ነች፡፡

> **አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 17፡16-21**
> **ጳውሎስም በአቴና ሲጠብቃቸው ሳለ በከተማው ጣኦት መሙላቱን እየተመለከተ መንፈሱ ተበሳጨበት፡፡ ስለዚህም በምኩራብ ከአይሁድና እግዚአብሔርን ከሚያመልኩ ሰዎች ጋር በየቀኑም በገቢያ ከሚያገኛቸው ጋር ይነጋገር ነበር፡፡ ከኢፊቆሮስ ወገንና አስጢአኮችም ከተባሉት ፈላስፎች አንዳቸቹ ከእርሱ ጋር ተገናኙ፡፡ እያንዳንዶቹም ይህ ለፍላፊ ምን ሊናገር ይወዳል? አለ ሌሎችም የኢየሱስንና የትንሳኤውን ወንጌል ስለ ሰበከላቸው አዲሶችን አማልክት የሚያመራ ይመስላል አሉ፡፡ ይዘውም ይህ የምትናገረው አዲስ ትምህርት ምን እንደ ሆነ እናውቅ ዘንድ ይቻለናልን? በጆሮአችን እንግዳ ነገር ታሰማናለህና እንግዲህ ይህ ነገር ምን እንደ ሆነ እናውቅ ዘራድ እንፈቅዳለን ብለው አርዮስፋጎስ ወደ ተበለው ስፍራ ወሰዱት የአቴና ሰዎች ሁሉና በዚያ የኖሩ እንግዶች አዲስ ነገርን ከመናገርና ከመስማት በቀር በሌላ ጉዳይ አይውሉም ነበርና፡፡**

▣ ***"መንፈሱን"*** በግሪክ ፅሑፍ ላይ በቃሎቹ መሃከል ክፍተት የላቸውም፡ (1) የስርዓት ነጥብ ምልክቶች አይታዩም፣ (2) በካፒታል ፅዳነት የተፃፈ አይደለም (ሁሉም የግሪክ ፅዳነት የተፃፊት በካፒታል ፅዳነት ነው)፡፡ (3) የቁጥርና የምዕራፍ ክፍፍል አይታይም፡፡ በመሆኑም የዳውዱ ትርጉም በካፒታል ፅዳነቱ የሚወሰን ይሆናል፡፡ በተለምዶ የካፒታል ፅዳነት የሚጠቀሙት፡ (1) ለመለኮት ምልዕት ስብዕና ስያሜዎችን ለመስጠት (2) ቦታንና ስሞችን ለመጥቀስ (3) የግለሰብ ሰዎችን ለመግለፅ
መንፈስ የሚለው ስያማ የሚያመለክተው፡ (1) መንፈስ ቅዱስን ሊሆን ይችላል (ማርቆ 1፡5)፣ (2) የሰውን መንፈስ ሊሆን ይችላል (ማርቆ 8፡12፣14፡38)፣ (3) የመንፈሳዊውን ዓለም ሊሆን ይችላል (እርኩሳን መናፍስትን (ማርቆ 1፡23)
በመሆኑም ጳውሎስ በዚህ ዓውድ ውስጥ አንድ ስብዕና ያለውን እያመለከተ ነው፡፡
ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ አይነቱን የሰዋሰው የቃላት አመሰራረት መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ውስጠ የሚያፈራውን ፍሬ ለመግለፅ ይጠቀምበታል፡፡

1. የባርነት መንፈስ ሳይሆን የልጅነት መንፈስ ሰቶናል (ቁ. 15)
2. የየዋት መንፈስ (1ቆሮ 4፡21)
3. የእምነት መንፈስ (2 ቆሮ 4፡13)
4. የጥበብና የመገለጥ መንፈስ (ኤፌ 1፡17)

በዚህ አውድ መሠረት ጳውሎስ መንፈስ የሚለውን ቃል ራሱን ለማመልከት ተጠቅሞበት እንመለከታለን (ሐዋ 2፡11፣5፡4፣2ቆሮ 2፡13፣7፡13፣ሮሜ 1፡9፣8፡16፣ ፊሊ. 4፡23)፡፡

▣

| | |
|---|---|
| NASB | "ውስጡን አነሳሱት" |
| NKJV | "ውስጡ ተነሳሳ" |
| NRSV | "ከልቡ ተጨነቀ" |
| TEV | "እጅግ ተበሳጨ" |
| NJB | "አመፀ" |

ይህ ቃል ቀጥተኛ ትርጉሙ ስለታም ሲሆን በዚህ ዓውድ ግን ያለውን ትርጉም መነሳሳት ማለት ነው፡፡ በጳውሎስና በበርናባስ መሃከል የነበረው ግጭት የተገለፀበት ቃል ይህ ነው (ሐዋ 15፡39)

17፡17 ሐዋርያው ጳውሎስ በአገልግሎት የሚደርሳቸውን ሰዎች እንመልከት፣ አይሁድን፣ አህዛቦች፣ እግዚአብሔርን የሚፈሩ አህዛብ፣ ጣኦት አምላኪዎች (በገበያ ስፍራ ያሉትን) ጳውሎስ አይሁድንና እግዚአብሔርን የሚፈሩ ለሚባሉ የብሉይ ኪዳን መፅሐፍ ሲጠቀም ለጣኦት አምላኪዎች ደግሞ ሌላ መንገድ ይጠቀም ነበር፡፡

17፡18 “ኢፊቆሮስ” እነዚህ ቡድን አስተምርሆት ደስታና ሐሴት የህይወት የመጨረሻ አላማ ነው በማለት ይናገራሉ፡፡ ከሞት በኂላ ህይወት መኖሩን ይክዳሉ የእነርሱ መፈክር ዛሬን ደስ ይበልህ የሚል ነው፡፡ አማልክት ከሰው ጋር አይገናኙም ነገር ግን ታላላቅ የአቴና ፈላስፋ ስም በአማልክቶቻቸው ያስባሉ እንደተሰየመ ያስባሉ፡፡ (341-270 ከክ)ል)በፊት) ነገር ግን ኤፌቆሮስ የሚባለው ፈላስፋ ደስታ የሰውነት ብቻ ሳይሆን የአእምሮ መሆኑን ይናገር ነበር፡፡ ይህ ሰው ሰውን ደስ ለማሰኘት ባለው ላይ መጨመር ብቻ ሳይሆን መቀነስም ደሰታን ይሰጠዋል ብሏል፡፡

▣ “ኢስጦኢኮችም” ይህ የሰዎች ስብስብ እምነታቸውን ያደረጉት በሁለት ነገሮች ላይ ነው፡ (1) አማልክት የአለም ነብስ ናቸው፣ (2) እግዚአብሔር በፍጥረቱ መሃከል ይኖራል፡፡ የእነዚህ ደግሞ አስተምርሆት መረጋጋት፣ የሰውነት ደስታ፣ እራስን መግዛት፣ ለራስ መብቃት እና የስሜት መረጋጋት የሕይወት ዋና አላማቸው ነው፡፡ ከሞት በኂላ ህይወት እንዳለ አያምኑም የእምነቱ መስራች ፈላስፋ ዚኖ የቆጰሮስ ሰው ሆኖ ወደ አቴና መቶ ኑሮውን መስርቷል (300 ከክ/ል)በፊት)

▣ “ለፍላፊ” ይህ ቃል ምሳልያዊ ሲሆን አንዳንድ መምህራን ትንሽ መረጃ ወይም ወሬ ብቻ ይዘው ከስፍራ በመዞር ለመሸጥ ሲሞክሩ የሚያወሩትን ወሬ አመልካች ነው፡፡ በአልፍርድ ማርሻል የተተረጎመው R.S.V interlinear የተባለው መጽሐፍ ‘የአላዋቂ ወሬ’ ብሎታል፡፡

▣ “አዲሶች አማልዕክትን ሚያወራ ይመስላል” እነዚህ አማልክት እንግዳ አምልኮት በማለት ይጠራቸዋል፡፡ በመሆኑም ጳውሎስ ስለኢየሱስ በመስበኩ እንደ አዲስ መንፈሳዊ ሃይል እና ጣኦት ትምህርቱ ይታይ ነበር፡፡ (1ቆሮ 10፡20-21) እነዚህ የአቴና ሰዎች በርካታ ጣኦትን በማምለክ የታወቁ ነበሩ፡፡ (የአሎንፒክ ሁሉ ገብ የማምለኪያ ቦታ የሚባል መቅደስ ነበር) በዚህ መቅደስ ሁሉም የሮማ ጣኦታት ይመለኩ ነበር፡፡
በመሆኑም እነዚህ የግሪክ ሰዎች የጳውሎስን ትምህርት ሁለት ጣኦታት አድርገው ተቀብለውት ነበር፡-

1. የጤንነት ጣኦት
2. የትንሶኤ ጣኣት

ጳውሎስ የሚሰብከውን ኢየሱስን እነዚህ የግሪክ ሰዎች ኢየሱስን ወንድ ጾታ እና ከትንሳኤ በኂላ ያለውን አካል በሴት ጾታ በማድረግ ትምህርቱን በተሳሳተ ትርጉም ተቀብለውት ነበር፡፡

▣ “የኢየሱስንና የትንሳኤውን ወንጌል ስለሰበከላቸው” ለአይሁድ የኢየሱስ ክርስቶስ መሰቃየት የመሰናከያ ርዕስ ሲሆን ለግሪኮች ደግሞ የኢየሱስ ትንሳኤ የሚሰናከሉበት ትምህርት ሆኖ ቆይቷል (1ቆሮ 1፡18-25) በግሪኮት ፍልስፍና ትምህርት ከሞት በኂላ ህይወት አለ ለማለት ተአማኒነትን አያስገኝም ሰው በስጋው እስር ቤት እንደሚኖር ይናገራሉ፡፡ ድነት ለግሪኮች በሰጋ ነፃነት ማግኘትና በግማሽ የራስን ፍጥረት መረዳት ማለት ነው፡፡

17፡19 “ኢርዮስፋጉስ ወደ ተባለው ስፍራ ወሰዱት” አርዮስፋጉስ ማለት የአርስ ተራራ ነው ትርጉሙም የጦርነት አምላክ ማለት ነው፡፡ ወርቃማ ቀን በተሰኘው የአቴና በዓል ላይ የፍልስፍና ውይይቶች በዚህ ከተማ ይካሄዳል፡፡ ይህ ውይይት ሁሉንም አይነት ሰዎች የሚያካትት ነው፡፡ ጳውሎስም የራሱን መልእክት መናገር የቻለው በዚህ አይነቱ ስብሰባ ላይ ነበር፡፡

▣ “ይህ የምትናገረው አዲስ ትምህርት ምን እንደሆነ እናውቅ ዘንድ” እንግዲህ በመንፈሳዊ መገለጥ እና በአእምሮ ዕውቀት መሃከል ልዩነት እንዳለው መመልከት ይቻላል፡፡ እግዚአብሔር እርሱን የምናውቅበትን ማስተዋል ሰቶናል ነገር ግን የሰው አእምሮ ሰላምንና ደስታን ሊያመጣ አይችልም ወንጌል ሁሉን የማድረግ ብቃት አለሙ፡፡ ጳውሎስ በሰው እና በእግዚአብሔር ጥበብ መሃከል ከፍተኛ ልዩነት እንዳለ ተናግbል፡፡ (1ቆሮ 1፡4)

17፡21 በዚህ ክፍል የሚናገሩት ሰዎች በእርግጥ እውቀትን ለማግኘት ፈልገው አይመስልም ነገር ግን በመስማት እና በመጠራጠር ደስታ ያገኙ ነበር፡፡ በተጨማሪም የአቴናን የቀድሞ ታሪክ ገናና አድርገው በንግግራቸው መሃል ጣልቃ ማስገባት የተለመደ ነበር፡፡ ከሁሉ በላይ የሚያሳዝነው የምድሩንና የመለኮትን ጥበብ ለይተው አያውቁም ነበር፡፡

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 17፡22-31**

ጳውሎስም በአርዮስፋጉስ መካከል ቆሞ እንዲህ አለ፡- የአቴና ሰዎች ላይ እናንተ በሁሉ ነገር አማልክትን እጅግ እንደምትፈሩ አመለክታለሁ፡፡ የምታመልኩትን እየተመለከትሁ ሰልፊ ለማይታወቅ አምላክ የሚል ፅሑፊት ያለበተ መሰዊያ አግኝቼአለሁና፡፡ እንግዲህ ይህን ስታውቁ የምታመልኩትን እኔ እነግራችኂለሁ፡፡ ዓለሙንና በእርሱ ያለውን የፈጠራ አምላክ እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነውና እጅ በሰራው መቅደስ አይኖርም እርሱም ህይወትንና እስትንፋስም ለሁሉ ይሰጣልና አንዳች እንደሚጉድለው በሰው እጅ አይገለገልም፡፡ ምናልባትም እየመረመሩ ያገኙት እንደሆነ እግዚአብሔርን ይፈልጉት ዘንድ በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩ የሰውን ወገኖች ሁሉ ከአንድ ፈጠረ የተወሰኑትንም ዘመኖችና ለሚኖሩበት ስፍራ ዳርቻ መደበላቸው ቢሆንም ከእያንዳንዳችን የራቀ አይደለም፡፡ ከእናንተ ከባለ ቅኔዎች አንዳንዶች ደግሞ እኛ ዘመዶቹ ነንና ብለው እንደ ተናገሩ በእርሱ ህያዋን ነን እንቀሳቀሳለን እንኖርማለን፡፡ እንግዲህ የእግዚአብሔር ዘመዶች ከሆንን አምላክ በሰው ብልሃትና አሳብ የተቀረፀውን ወርቅ ወይም በር ወይም ድንጋይ እንዲመስል እናስብ ዘንድ አይገባንም፡፡ እንግዲህ እግዚአብሔር ያለማወቅን ወራት አሳልፎ አሁን በየቦታቸው ንስሃ ይገቡ ዘንድ ሰው ሁሉ ያዛል ቀን ቀጥሮአልና ስለዚህ እርሱን ከሙታን በማስነሳቱ ሁሉን አረጋግጦአል፡፡

17፡22 “*አማልክትን እንደምትፈሩ*” ቀጥተኛ ትርጉሙ የጣኦት ፍርሃት (የአጋንንት) ይህን በሁለት መንገድ ልንተርጉመው እንችላለን፡ (1) በአሉታዊ ስሜት (እርሱም መንፈሳዊ ሃያላትን መፍራት)፣ (2) በአዎንታዊ ስማት (የሃይማኖት አክብሮት NKJV ሐዋ 25፡19)፡፡ እነዚህ ሰዎች የማወቅ ፍላጐት እና ሃይማኖትን የማክበር የራሳቸው የሆነ ልማድና ወግ የነበራቸው ናቸው፡፡

▣ **“በሁሉ” ጳውሎስ በስብከቶቹ በርካታ ጊዜ ቃሉን ይጠቀማል**

1. በሁሉ ነገር ቁ. 22
2. አለሙንና በእርሱ ያለውን ሁሉ ቁ. 24
3. ሕይወትንና እስትንፋስንም ሀሉንም ቁ. 25
4. ለሁሉ ይሰጣልና ቁ .25
5. በምድር ሁሉ ቁ .26
6. የሰው ወገኖች ሁሉ ቁ. 26
7. እያንዳንዶችን ቁ . 27
8. እኛ (ሁለት ጊዜ) ቁ . 28
9. በየቦታቸው ቁ . 30
10. በዓለሙ ላይ ቁ . 31
11. ሰውን ሁሉ ቁ. 31

ጳውሎስ እግዚአብሔር ለሁሉ ሰው ዕድል መስጠቱን የሚያመለክት ቃሎች ናቸው፡፡

17፡23 “**ለማይታወቅ አምላክ የሚል ፅሑፍ**” ግራኮች እነርሱ የዘነጉት ሌላ አምላክ እንዳለ በማመን ይህ አምላክ አደጋ እንዳያደርስባቸው በመፍራት ይህን አይነት ፅሑፍ የፅፍ ነበር፡፡ (Pausanias, *Description of Greece* 1:1:4 and philostraths, *life of Apollonius* 63:5) ግሪኮች የብዙ አማልክት አምላኪዎች እና እንደሚፈሩአቸውም ያስገነዝበናል፡፡

▣ “**እንግዲህ ይህን ሳታውቁ የምታመልኩትን**” ከግሪኩ ፅሑፍ የተገኘው ይህ ሃሳብ አግኖስቲክ በሚል የእንግሊዘኛ ቃል ተተክቷል ጳውሎስ ለጣኦት አምላኪዎች ወንጌልን የሰበከበት መንገዶች አንዱ በእንዲህ ባለው ዐረፍተ ነገር መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡

▣ “**እኔ እነግራችኋለሁ**” ጳውሎስ ግልፅ ተናገረ እንጂ ሞኛ ሞኝ ሰባኪ አልነበረም (ቁ. 18) በመሆኑም እነርሱ እውቀት ያጡበትን እውነተኛውን አምላክ እርሱ እንደሚያውቀው በድፍረት የተናገረበት ቦታ ነው፡፡

17፡24 “**አለሙንና በእርሱ ያለውን ሁሉ የፈጠረ**” የጳውሎስ የመጀመሪያው የስነ መለኮት ትምህርቱ እግዚአብሔር ፈጣሪ መሆኑን የሚያስረዳ ነው፡፡ (ዘፍ 1-2፣ መዝ 104፣ 146፡6፣ኢሳ 42፡5) ግሪኮት መንፈስ (እግዚአብሔር) እና ነገር (ግኡዝ አለም) በመተባበር የሚኖሩ እንደሆኑ ያስባል፡፡ ነገር ግን ጳውሎስ ሰማይና ምድር ከአላማው የተፈጠሩ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

▣ “**እጅ በሰራው መቅደስ አይኖርም**” ከብሉይ ኪዳን የተጠቀሰ ጥቅስ ነው፡፡ 1ነገ 8፡27፣ ኢሳ 66፡1-2 እና ከግሪኮች የፍልስፍና መፅሐፍት፣ Euripides፣ ፍራግመንት 968 በግሪኩ ፅሑፍ ይህ አነጋገር የተለመደ በመሆኑ ጳውሎስ አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀምበታል፡፡

17፡25 “**ሁሉንም ለሁሉ ይሰጣልና**” የዚህን ተመሳሳይ ሐረግ በሚከተሉት ውስጥ ታገኛላችሁ፡ (1) Euripides *Herocles* 1345፣ (2) Plato's *Euthyphro፣ (3)* Aritobulus, Flagment፣ (3) መዝ 50፡9-12 የግሪክ መቅደሶች ሁሉ ጣኦታቱ የሚመገቡበት እና እንክብካቤ የሚያገኙበት ቦታ እንደሆነ ይታሰብ ነበር፡፡

▣ “**እርሱ ህይወትና እስትንፋስን ሁሉንም ለሁሉ ይሰጣልና**” ከኢሳ 42፡5 የተወሰደ ሊሆን ይችላል፡፡ የጳውሎስ የስነ መለኮት ትንተናው ነው፡ (1) የእግዚአብሔርን ፍቅር ያመለክታል፣ (2) የእግዚአብሔርን ለፍጥረቱ ያለውን ረድኤት ያስገነዝባል፡፡

የዚህን ትምህርት ተመሳሳይ በፈላስፎች ኢስጦኢኮስ ትምህርት ቤት በፈላስፋ በዜኖ ተፅፎ ይገኛል፡፡ (clement Alexanaria, *Stromateis* 5:76:1)

በመሆኑም አህዛብ ጣኦት አምላኪዎች የእግዚአብሔርን ፍቅር እና ረድኤት ማውቃቸው እንዴት የሚያስደስት ነው፡፡

17፡26 “**ከአንድ ፈጠረ**” የምዕራቡ ቤተሰብ የሚባለው የግሪኩ ፅሑፍ ከአንድ ደም የሚል ጨምbል ነገር ግን ሌሎቹ የግሪክ ፅሑፎች ላይ ከአነድ ደም የሚለውን አልፃፈትም ይህ ሐረግ መገኛን የሚያመለክት ከሆነ ስለ አዳም ይናገራል በመሆኑም የግሪኩ ፅሑፍ ይህንን የሚያንፀባርቅ ከሆነ የሰው ፍጥረት ከአንድ ዘር መምጣቱን መናገሩ ግልፅ ነው፡፡ የዚህ ሐረግ ዋና ፍሬ ሃሳብ የሰው ዘር በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረ መሆኑን ይገልፃል፡፡ (ዘፍ 1፡26-27) የሰው ዘር ሁሉ ፍሬያማ እና ምድርን እንዲሞላ ታዟል፡፡ (ዘፍ 1፡28፣9፡1-7) ነገር ግን የሰው ልጅ በፍጥነት ከእግዚአብሔር ለመለየት እና ምድርን በሐጢያት ለማቆሸሽ የሄደበት መንገድ ፈጣሪን የሚያስቆጣ ነው (ዘፍ 10-11)፡፡

▣ **"የተወሰኑትንም ዘመኖችና ለሚኖሩበት ስፍራ ዳርቻ መደበላቸው"** እግዚአብሔር ሰውን መፍጠር ብቻ ሳይሆን ፍጥረቱንም የሚመራ አምላክ ነው ከዘዳ 32፡8 የተወሰደ ሊሆን ይችላል፡፡ ሌሎችንም እንመልከት፡ (ኢዮ 12፡33፣ መዝ 47፡7)፡፡

17፡27 ከግሪክ የግጥም ስነ ፅሑፍ የተወሰደ አባባል ነው፡፡

▣ **"እንደ ሆነ"** እውነቱን ለማግኘት እሩቅ መሆኑን የሚያመለክት ሐረግ ነው፡፡

▣

NASB,NKJV,

NRSV **"ያገኙት እንደሆነ"**

TEV **"በዙሪያው እንዳሉ ይሰማቸዋል"**

NJV **"በቀና ስሜት ወደ እርሱ"**

የቃሉ ትርጉም "መንካት" ወይም "መስማት" (ሉቃ 24፡39) ከብርቱ ጨለማ የተነሳ ማግኘት ቀላል አይሆንም የሚል አንድምታ በዓውዱ ውስጥ ይታያል፡፡ እግዚአብሔርን ለማግኘት ቀላል አልሆነላቸውም ጣኦት አምላኪነት ሰይጣንን በመስማት በአጋንንት የሚሰራ ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በፈቃዱ የሚገኝ ነው (ሮሜ 1-2)፡፡

▣ **"ቢሆንም ከእያንዳችን የራቀ አይደለም"** ይህ የሚያስደንቅ እውነት ነው፡፡ እግዚአብሔርን እኛን ፈጥሮናል፣ እግዚብሔር የእኛ ነው፣ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው፡፡ (መዝ 139) ሐዋርያው ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ፍቅር፣ ጥበቃ እና ከፍጥረቱ ጋር መገኘቱን በግልፅ ለሰው ሁሉ ይናገር ነበር፡፡ ይህ የወንጌል ዋናኛ መልእክት ነው፡፡ (ኤፌ 2፡11-2፡13)

ጳውሎስ ከዘዳ 4፡7 የጠቀሰው ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ለሰው ሁሉ የተፃፈ መሆኑ ተረድቷል፡፡ በእርግጥ የአዲስ ኪዳን የተሰወረው የቃል ኪዳን ሚስጥር ይህ ነው፡፡

17፡28 **"ከእናንተ ባለቅኔዎች አንዳንዶች"** ከዚህ ቁጥር በፊት ያለውን ጥቅስ እንመልከት ይህ የተጠቀሰው፡-

1. Cleanthes Hymn to Zens ወይም (ለዙስ ጣኦት የሚዘመር የመንፃት ዝማሬ ይባላል) ይህ የትምህርት ቤቱ ርዕስ አለቃ ነበር፡፡ (ከ263-232B.C)
2. አርተስ ከጠርሴስ አጠገብ የምተገኝ ከተማ ነዋሪ የነበረ ሰው ነበር
   ይህ ሰው ከ315-240 ከክ)ል)በፊት ነበር፡፡ በመሆኑም ይህ ጥቅስ የሚያመለክተው፡-
   ሀ. የእግዚአብሔርን ከፍጥረቱ ጋር ያለውን ቁርኝት ያሳያል (ቁ. 27)
   ለ. እግዚአብሔር የሁሉ ፈጣሪ መሆኑን ያስገነዝበናል 1ቁ. 26)

ጳውሎስም በ1ቆሮ 15፡32 እና በ1ቆሮ 15፡33 ዝርዝር ሃሳቡን ጠቅሶትል ጳውሎስ ጠርሴስ በሚገኘው ዩኒቨርስቲ የግሪክን ስነ ፅሑፍ እና የንግግር ችሎታን ተምሯል፡፡

▣ **"እኛ ደግሞ ዘመዶቹ ነን"** ይህ ሐረግ የተጠሰው (ከ Erimenides quoted by Diogenes laertins in *Lives* of the *Philosophers* 1:112) ይህን መፅሐፍ በማንበብ ዐረፍተ ነገሩን በዝርዝር መረዳት ያስችላል፡፡

17፡29 ጳውሎስ የጣኦት አምልኮን በግልፅ መቃወሙን ያሳያል፡፡ (መዝ 115፡1-8፣ ኢሳ 40፡18-20፣ 44፡9-20፣ 46፡1-7፣ ኤር 10፡6-11፣ ዕብ 2፡18-19) በሐጢያት የወደቀው ሰው ለማይናገሩና ለማይሰሙ የሰው እጅ ስራ ጣኦቶች ስግደትን ማቅረቡና መንፈሳዊ እውነትን እና ህብረትን መፈለጉ የሚያሳዝን ነው፡፡

17፡30 **"ያለማወቅን ወራት"** ይህ የሚያስገርም የእግዚአብሔርን ምህረት ያሳያል (ሮሜ 3፡20፣ 25፣ 4፡15፣ 5፡13፣20፣7፡5፣7-8፣ 1ቆሮ 15፡56) ነገር ግን አሁን ወንጌልን ሰምተዋልና መንፈሳዊ ተጠያቂነት አለባቸው!

▣ **"አሁን በየቦታው ንሰሃ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል"** በዚህ ዐረፍተ ነገር መሰረት እግዚአብሔር እያንዳንዱ ሰው እንዲድን መፈለጉን ያሳያል የእግዚአብሔርን ፍቅር እና ምህረት ያሳያል (ዮሐ 3፡16፣ 1ጢሞ 2፡4፣ 2ጴጥ 3፡9) ሰው ሁሉ ይድናል ሳይሆን (ቁ . 22-23) ነገር ግን እግዚአብሔር የሰው ዘር ሁሉ እንዲድን መፈለጉን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህም ኢየሱስን በማመን የሚገኝ ድነት ነው ኢየሱስ በመስቀል ለሁሉም ሞቷል ሁሉም ሊድኑ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ክፉ ነገሩ ሁሉም መዳን አለመቻላቸው ነው፡፡

▣ **"ንሰሃ"** የዕብራይስጡ "የድርጊት ለውጥ" የግሪኩ ደግሞ የሃሳብ ለውጥ በማለት ፍቺ ይሰጣል ለንሰሃ ሁለቱም ነገሮች አሰፈላጊ ናቸው፡፡ ነገር ግን በሐዋ 17፡18 ላይ የሚገኙት ሁለቱ የፍልስፍና ትምህርት ቤቶች ይህንን የንሰሃ ትርጉም የራሳቸውን አመክኖ በማቅረብ ይቃወማሉ፡፡ ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርዕስ ስር ንሰሃ (ሐዋ 2፡38) ተመልከቱ፡፡

17፡31 **"ቀን ቀጥሮአልና በዚያም ቀን ባዘጋጀው ሰው እጅ በዓለሙ ላይ በፅድቅ ሊፈርድ አለው"** ጳውሎስ በመልእክቱ የእግዚአብሔርን ምህረትና ርህራሄ በግልፅ ይናገራል፡፡ ነገር ግን ይህ ግማሽ መልእክት ነው ምክንያቱም እግዚአብሔር የፍቅርና የርህራሄ አምላክ እንደሆነ ሁሉ ፍርድንም የሚያደርግ ፃድቅ ጌታ ነው፡፡ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረው ሰው የተሰጠውን ህይወት መንከባከብ ይጠበቅበታል፡፡ አዲስ ኪዳን እግዚአብሔር በአለም ላይ እንደሚፈርድ በግልፅ ያስተምራል፡፡ (ማቴ 10፡158፣ 11፡22፣24፣16፡27፣ 22፡36፣ 25፡31-46፣ ራዕ 20፡11-15)

▣ "ባዘጋጀው ሰው እጅ" በተቀጠረው ቀን ፍረዱ መሠረት የሚያደርገው በትንሳኤ ከተነሳው ከናዝሬቱ ከኢየሱስ ጋር ያለንን እምነት በመመልከት ነው። ይህ ለግሪክ ምሑራንና የፍልስፍና ሰዎች አደናጋሪ እና የማይታመን ሃሳብ ነው። (1ቆሮ 1፡23) ነገር ግን ወንጌል ይህንን በግልፅ በተብራራ መልክ ገልጾታል (ሐዋ 10፡42፣ ማቴ 25፡31-33)

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 17፡32-34**
**የሙታንን ትንሳኤ በሰሙ ጊዜ እኩሌቶቹ አፌዘበት እኩሌቶቹ ግን ስለዚህ ነገር ሁለተኛ እንሰማለን አሉት። እንዲሁም ጳውሎስ ከመካከላቸው ወጣ። አንዳንዶች ወንዶች ግን ተባብረው አመኑ ከእነርሱ ደግሞ በአርዮስፋጎስ ያለው የፍርድ ቤት ፈራጅ ዲዮናስዮስ ዶማሪስ የሚሉአትም የሚሉአትም እንዴት ሴት ሌሎችም ከእነርሱ ጋር ነበሩ።**

**17፡32 "የሙታንን ትንሳኤ በሰሙ ጊዜ"** ከኤልቆሮስ በስተቀር ግሪኮች በነብስ ሞት እንዳለ ያምናሉ ነገር ግን ትንሳኤን አያምኑም ነበር። (ቁ. 18፣ 1ቆሮ 1፡23)

▣ **"አፌዙበት"** በአዲስ ኪዳን ይህ ቃል የተፃፈው በዚህ ስፍራ ብቻ ነው። ነገር ግን (በሐ 5፡30 እና 26፡21) በስፋት ተብራርቶ እናገኘዋለን። በግሪኩ ፅሑፍ "ቀልደኛ የሚያፌዝ" የሚል ፍቺ ይሰጣል። (ኢዮ 12፡4፣ መዝ 79፡4፣ ኤ 20፡8)

▣ **"ነገር ግን ሌሎች እንደገና ልንሰማ እንወዳለን አሉ"** እነዚህ አድማጮች ጳውሎስ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር በሰበከ ጊዜ ልባቸው ተማርኳል ነገር ግን በፍፁም አላመኑም ነበርና ደግመው መስማት መፈለጋቸውን እንመለከታለን።

**17፡34 "አንዳንዶች ወንዶች ግን ተባብረው አመኑ ከእነርሱ ደግሞ በአርዮስፋጎስ ያለው የፍርድ ቤት ፈራጅ ዲዮናስዮስ"** ለወንጌል ሰዎች ያደረጉ የነበረውን ምላሽ እንመልከት፡ (1) ተቃውሞ (አንዳንዶች ያፌዙ ነበር) ቁ.32፣ (2) ዘግይቶ መወሰን (እንደገና ልንሰማ እንወዳለን) ቁ. 32፣ (3) የሚያምኑ ነበሩ። (አንዳንዶች ጳውሎስን ተባብረው አመኑ) ቁ. 34 ( 1ተሰሎ 1፡9-10) የዞረውን ምሳሌ መመልከቱ ተገቢ ነው (ማቴ 13)።

▣ **"ዲዮናስዮስ አርዮስፋጎስ"** ይህ የፍልስፍና ውይይት የሚያደርግበት ቦታ ነው። በዚህም ውይይት ወደ ክርስቶስ እምነት የሚመጡ ምሁራን ነበሩ። (Eusebius, Eccl, His 3:4, 6-7 and 4:23:6) በዚህ መፅሐፍ ላይ ይህ ሰው የአቴና የመጀመሪያው ጳጳስ እንደነበረ ፅፏል። በእርግጥ ይህ እውነተኛ ማስረጃ ከሆነ የወንጌልን ሰው የመቀየር ሃይሉን ማጤን እንችላለን።

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ለመርዳት ነው የተሰናዱት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋነኞቹን ጉዳዮች ለማጤን እንዲረዳ ነው። ሐሳብ ለማጫር እንጂ መደምደሚያ አይደሉም።

1. ጳውሎስ በታላላቅ ከተሞች ለምሳሌ በአንፊጶልና በአጶሎንያ ያልፍ የነበረው ለምንድ ነው?
2. አይሁድን የክርስቶስ መከራና ስቃይ መስማት ስለምን ያበሳጫቸዋል?
3. የቤርያ ሰዎች ለወንጌል በአዎንታ የመለሱበት ምክንያቶች ምንድናቸው?
4. ጳውሎስ በአቴና መንፈሱ ስለምን ተበሳጨበት?
5. ጳውሎስ በአርዮስፋጎስ ያደረገውን ንግግሩ አስፈላጊነቱ ምንድነው?

# የሐዋርያት ሥራ 18

## የምንባቡ ክፍፍል በአዲሶቹ ትርጉሞች

| የተየመቅሶ[4] | አኪጀት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጳውሉስ በቆሮንቶስ | በቆሮንቶስ አገልግሎት | የቤተክርስቲያን ምስረታ በቆንቶስ | በቆሮንቶስ | የቤተክርስቲያን ምስረታ በቆሮንቶስ |
| 18፡1-4 | 18፡1-17 | 18፡1-4 | 18፡1-4 | 18፡1-4 |
| 18፡5-11 | 18-5-11 | 18፡5-8 | 18፡5-8 | |
| | | | 18፡9-11 | አይሁድ ጳውሉስን ወደ ፍርድ ወሰዱት |
| 18፡12-17 | | 18፡12-17 | 18፡12-13 | 18፡12-13 |
| | | | | 18፡14-17 |
| ጳውሎስ ወደ አንፃኪያ ተመለሱ | ጳውሉስ ወደ አንፃኪያ ተመለሰ | የሁለተኛው አልቆ የሶስተኛው የሚሰድ ናዊነት ጉዞ ጀማሬ | ወደ አንፃኪያ ተመለሱ | ሦስተኛውን ጉዞ በመጨርስ ወደ አንፆኪያ ተጓዙ |
| 18፡18-23 | 18፡18-23 | 18፡18-21 | 18፡18-21 | 18፡18 |
| | | | | 18፡19-21 |
| | | 18፡22፡23 | 18፡22-23 | 18፡22-23 |
| ጳውሎስ በኤፌሶን ሰበከ | የጳውሎስ አገልግሎት | ጳሎስ በኤፌሶን | ጳሎስ በኤፌሶን እና በቆሮንጦስ | ጳውሉስ |
| 18፡24-26 | 18፡24-28 | 18፡24-28 | 18፡24፡28 | 18፡27-28 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (ከ "*መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ*" **ገጽ** vii)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. ምንባብ አንድ
2. ምንባብ ሁለት
3. ምንባብ ሦስት
4. ወ.ዘ.ተ . . .

> አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 18፡1-4
> ከዚህም በኃላ ጳውሎስ ከአቴና ወጥቶ ወደ ቆሮንቶስ መጣ፡፡ በወገኑም የጳንጦስ ሰው የሚሆን አቂላ የሚሉትን አንድ አይሁዳዊ አገኘ እርሱም ከጥቂት ጊዜ በፊት ከሚስቱ ከጳርስቅላ ጋር ከኢጣልያ መጥቶ ነበር፡፡ አይሁድ ከሮማ ይወጡ ዘንድ ቀላውዴዎስ አዞ ነበርና ወደ እነርሱ ላይ ሰሩ ስራቸውም ድንኳን መስፋት ነበርና በየሰንበቱም ሁሉ በምኩራብ ይነጋገር አይሁድንና የግሪክም ሰዎች ያስረዳ ነበር፡፡

18፡1 **"ጳውሎስ ከአቴና ወጥቶ ወደ ቆሮንቶስ መጣ"** የቆሮንቶስ ከተማ በስተ ምዕራብ ሃምሳ ማይል ከአቴና ትርቃለች እንግዲህ ጳውሎስ ሃምሳ ማይል ተጉዞ ወደ ቆሮንቶስ መድረስ ችላል (ቁ 5) ጳውሎስ ብቻውን ነበር፡፡ የአይን ችግር ያለበት ሰው ብቻ መሆን ከባድ ነው (2 ቆሮ 12)፡፡

> **ልዩ ርዕስ፡ የቆሮንቶስ ከተማ**
>
> ሀ. በበጋ ወራት በሰሜን ግሪክ በኬፕ ማአሊአ በመርከብ መሄድ ለጉዳት ይደረጋል፡፡ በመሆኑም ቅርብ የነበረው ይህ መንገድ አስፈሪ በመሆኑ ሰዎች በሌላ በኩል መሄድ በኤጀርያ በህር መሃከል ነው፤ ከዚህም የተነሣ ከተማይቱ የንገድ ከተማ ነበረች፡፡ ይህም በሸክላ ስራና በአልማዝ ማዕድን ንግድ ትታወቅ ነበር፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የወታደሮች መናኸሪ ነበረች፡፡
>
> ለ. የቆሮንቶስ ከተማ በየአመቱ የሚከበሩት በአላቶችም የግሪክ ሮማን ባህል የሚያንፀባርቅ ነበሩ፤ይህም በባህላቶቹ የሚደረጉ የተለያዩ ሃይማኖታዊ እና እስፓርታዊ ጨዋታዎች ፓሊሲዮን በሚባል መቅደስ ይደረግ ነበር፡፡ ነገር ግን ኦሎምፒክ በየአራት አመቱ በአቴንስ ይደረግ ነበር፡፡
>
> ሐ. በ14 ከክ)ል)በፊት ቆሮንቶስ በሮማውያን ላይ ሲያምፁ በሮማ ጀነራል በሉዮሴስ በጦርነት ተሸንፈዋል፤ ከዚያም በኃላዳ ሌሎች ነገሮች ለመበተን ተገዷዋል፡፡ ነገር ግን ከኢኮኖሚ እና ከፖለቲካ ጠቃሜታ አንፃር ከተማይቱ በጁሊየሽ ቄሳር በ46 ወይም ከክ)ል)በፊት እንደገና ተገንብታለች በ15 ዓ.ዓ. ላይ የሮማውያን ሕግ ግዛት ሆናለች፡፡
>
> መ. የቀድሞይቱ ቆሮንቶስ ከባህር ወለል በላይ 1880 ጫማ ላይ ትገኛለች በዚህች ከተማ አፍሮዳይት የሚባለወው መቅደስ እስከ 1000 የሚደርሱ ሰትኛ አዳሪዎች የሚገኙበት ነበር፡፡ የቆሮንቶስ ስያሜ ተመሳሳይ መባከን እና ያልተረጋጋ ህይወት ማለት ነው፡፡ ይህ መቅደስ ጳውሉስ ወደ ቆሮንቶስ ከመሄዱ ከ150 ዓመት በፊት በመሬት መንቀጥቀጥ አደጋ ፈርሷል፡፡ ነገር ግን ነበአዲስቱ ቆሮንቶስ በመቅደስ የነበረው ስራ መቀጠሉን የሚያረጋግጥ ግልፅ ማስረጃ የለም ሮማውያን በ146 ከክ)ል)በፊት ከተማይቱን በማቃጣላቸው ሁለተኛ የተገነባቸው ቆሮንቶስ የሮማውያን እና የግሪሎች ባህል የሚንፀባረቅበጽ ሆኖአል፡፡

18፡2 **"አቂላና ጶርስ ቅላ"** ጳርሶቅላ "ጵርስቃ" የሚል ስያሜ አላት በስም ተርታ ብዙ ጊዜ መጀመሪያ ትፃፋለች (ሐዋ 18፡18, 26 ;) ቆሮ፡16፡19 2 ጢሞ 4፡19 ይህ በመፅሐፍ ቅዱስ የስም አደራደርን ያልጠበቀ ያልተለመደ አቀማመጥ ነው፡፡ የዚህች ሴት ስም የሮም ባለጠጋ ቤተሰብ ከሆነችው ከጂን ድርቅላ ጋር ተመሳሳይነት አለው በዘር አይሁዳዊ መሆንምን የሚገልፅ ግልፅ ማስረጃ የለም፡፡

▣ **"በቅርብ"** ይህንን ረዳት ግስ ለመረዳት የሚከተለውን መፅሐፍ ያንብቡ "In a *Translators Hand Book on the Acts of the Apostles*, P.347,Newman and nida" የቃሉ ትርጉም "በቅርብ የተገደለ" የሚል ፍቺ እናገኛለን ይህ ለዚህ ዓውደ ትርጉም አይሰጥም በመሆኑን ቀጥተኛውን ፍቺ መጠቀም የተሻለ ነው፡፡ ቃላት በማህበረሰብ ውስጥ የራሳቸው የሆነ ትርጉም እንዳላቸው መዘንጋት የለብንም ብዙ የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በተሳሳተ ትርጉም የሚቀርቡት በግዜያው የነበረውን የቃላት ፍቺ አሰጣኝ ባለማወቅ የሚከሰት ነው፡፡

▣ **"ለጳርስቅላ ጋር ከኢጣልያ መጥቶ ነበርና አይሁድ ከሮማ ይመጡ ዘንድ ቀላውዴዎስ አዞ ነበርና"** ይህንን ሐረግ ለመረዳት የሚከተሉትን ያንብቡ (historia contra pagnus 7. 6.15 suetonius, in life of cassius 25.4 Tacitus, annais 25:44:3 Dio cassius in histories 60.6) ቀላውዴምስ ያወጣው ህግ አይሁዳውያን በሮማ በቀጣይነት እንዳይኖር የሚደነግግ ሕግ እንደሆነ ከሰዋሰው ሕግ አፃፃፍ እንረዳለን፡፡

18፡3 **"ስራቸውም አንድ ስለነበረ"** ይህ ስራ የድንኳን መስፋት ስራ ቢሆንም ነገር ግን አረፍተ ነገሩ የቆዳ ንግድ ስራንም ሊያመለክት ይችላል፡፡ ሐዋሪያው ጳውሎስ በሚኖርበት መንደር የምኩራብ መምህር የሆነ አይሁዳዊ ሁሉ ገንዘብ በመስራት እንጂ ከሌላ ሰው አይቀበልም ነበር፡፡ በመሆኑም የስራ ባህል የነበረው ሰው ነው፡፡

18፡4 **"በየሰንበቱም ሁሉ በየምኩራቡ ይነጋገር ነበር"** ጳውሎስ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት አሳማኝ አመክሮዎችን በመናገር በየምኩራቡ ያገለግል ነበር፡፡ ጳውሎስ ለአይሁድ ወንጌልን ለመናገር ቅድሚ የሰጠባቸውን ዋና ምክንያቶች እንመልከት፡ (1) ኢየሱስ የተናገረውን ትዕዛዝ ስለሆነ (ማቴ 10፡5-6)፣ (2) የብሉይ ኪዳን መፅሐፍትን አይሁድ ስለሚያውቁ፣ (3) እግዚአብሔርን የሚፈሩ የግሪክ ሰዎች በምኩራብ ለወንጌል በጎ ምላሽ በመስጠታቸው ጳውሎስ

ወንጌልን ለመስበክ ትችል የምኩራብ አገልግሎት የተጀመረው በባቢሎን ሲሆን ይህም የአይሁን ባህል ለመጠበቅ የተደረገ ነው፡፡

> **አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ *18፡5-11***
> **ሲላስና ጢሞቲዎስም ከመቄዷንያ በወረዱ ጊዜ ጳውሎስ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ ለአይሁድ እየመሰከረ ለቃሉ ይተጋ ነበር ነገር ግን በተቃውሙትና በተሳደቡ ጊዜ ልብሱን እያራገፈ ደማችሁ በራሳችው ነው እኔ ንፁህ ነኝ ከእንግዲህ ወዲህ ወደ አህዛብ እሄዳለሁ አላቸው ከዚያም ወጥቶ ኢየስጦስ ወደ ሚባል እግዚአብሔርን ወደሚያመልክ ሰው ቤት ገባ ቤቱም በምኩራብ አጠገብ ነበር፡፡ የምኩራብ አለቃ ቀርስቶስም ከቤተ ሰዎቹ ጋር ጌታ አመነ ከቆሮንቶስ ሰዎችም ብዙ በሰሙ ጊዜ አምነው ተጠመቁ ጌታም ሌሊት በራዕይ ጳውሎስን እኔ ከአንተ ጋር ነኝ ማንም ክፍ ሊያደርግብህ የሚነሳብህ የለምና አትፍራ ነገር ግም ተናገር ዝምም አትበል በዚህ ከተማ ብዙ ህዝብ አሉኝና አለው፡፡ በመካከላቸውም የእግዚአብሄርን ቃል እያስተማረ ዓመት ከስድስት ወር ተቀመጠ፡፡**

18፡5 ***"ሲላስና ጢሞቴዎስም ከመቄዶንያ ወረዱ"*** ጳውሎስን በሙሉ ጊዜውን እንዲሰጥ የሚያስችለውን ገንዘብ ከፊሊጲሲዩስ አማኞች አግኝተዋል፡፡ (2 ቆሮ 11፡9ፊሊ 4፡15) ጢሞቲዎስ ከተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን መልእክትን በማምጣት ጳውሎስ ደግሞ አንደኛ እና ሁለተኛን ተሰሎንቄ በመፃፍ ምላሽ መስጠቱን እንገነዘባለን፡፡ (ሐዋ 17፡14) ሉቃስ ወንጌልን ለማስተማር በፊሊጳሲዮስ እንደቀረ ጢሞትዮስም በተሰሎንቄ እንዲሁም ሲላሶ በቤርያ ነበሩ፡፡ ጳውሎስ አዳዲስ አማኞች የእግዚአብሄር ቃል እንደማሩ አጥብቆ ይጥር ነበር፡፡

▣

| | |
|---|---|
| NASB | **"ጳውሎስ ፍፁም ራሱን ለቃሉ ሰጠ"** |
| NKJV | **"ጳውሎስ በመንፈስ ታዘዘ"** |
| NRSV | **"ጳውሎስ ቃሉን በማወጅ ላይ ነበር"** |
| TEV | **"ጳውሎስ ሙሉ ጊዜውን ቃሉን ይሰብክ ነበር"** |
| NJB | **"ጳውሎስ ሙሉ ጊዜውን ለስብከት አድርጎ ነበር"** |

በግሪክ ፅሁፍ ላይ የተለያዩ የትርጉም አንድ ሃረግ ይሰጣል፡፡ ለምሳሌ (mss P74 N, A, B,D እና የሦሪያው እና የላቲኑ እና የኮፓቲኩ ትርጉም ጳውሎስ ለቃለ እግዚአብሔር ንባብ ጊዜውን ሰጠ የሚል ፍቺ አለው፡፡ በመንፈስ መታዘቱንም ያመላክታል ይህም መንፈስ በወንድ ፃታ ተቀምጦ በግሪኩ ላይ ይነበባል፡፡)

▣ ***"ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ ለአይሁድ እየመሰከረ"*** ሐዋ 9፡22 እና 17፡3 እነዚህን ጥቅሶች በማወዳደር አጥኑአቸው፡፡ ሱኒቶ የሚለው የግሪኩ ቃል "ጫና መፍጠር" በማለት ተርጎሞታል፡፡ ከእስቲፋኖስ የስብከት ዘዴ ጋር ተመሳሳይ ነው (ሐዋት) ይህ የስነ መለኮት ትንተና ለሁሉ ጠቃሚ ሆኖአል

18፡6 በታቃወሙት እና በተሳደቡ ጊዜ የሐረጉ ሰዋሰው ህግ እንደሚያመለክተው ድርጊቱ ቀጣይነት እንደነበረው ያሳያል፡፡ ይህ ተቃውሞ እና ስድም የተበተኑ አይሁድ የሚሰጡት የተለመደ ምላሽ ነበር፡፡

▣ ***"ልብሱን እያራገፈ"*** ይህ የተለመደ የአይሁድ የንቀት ምልክት ነው፡፡ (ነህ 5፡13 ሐዋ 13፡51 ሉቃ 9፡5፤10፡11)

▣ ***"ደማቸው በራሳችሁ ነው"*** የብሉይ ኪዳንን ገለፃ እንመልከት

1. የቅጥር ጠባቂው ሃላፊነት ነው ሕዝ 3፡16 33፡1-6
2. የግል ሃላፊነት ነው አያ 2፡19፣ 2ሳሙ 1፡16,33፡1-6
3. የሕዝብ ሃላፊነት ነው 2 ሳሙ 3፡28-29;2 ነገስ 2፡33
4. ተራ ቁጥር 2 እና 3 በአዲስ ኪዳን ተጠቃሏል፤፡ ማቴ 27፡25

ሕይወት የሚገኘው በዳም ውስጥ ነው (ዘሌ 17, 11, 14) አንድ ሰው የሰውን ደም በማፍሰሱ በገዳይነት በእግዚአብሔር ይጠየቃል (ዘፍ 4፡10;9;4-6)፡፡

▣ ***"ንፁህ ነኝ"*** የብሉይ ኪዳን በግል የመንፃትን ስርዓት ያመለክታል፡፡ ሐዋሪያው ጳውሎስ ለአይሁድ ወንጌልን በመናገር ከደማቸው ነፃ እንደሆነ እየተናገረ የሚገልፅ ነው፡፡ (ህዝ 33) ናስ ንፁህ ነን?

▣ ***"ከእንግዲህ ወዲህ ወደ አህዛብ እሄዳለሁ"*** ወንጌልን አልቀበልም ሚል ማዕበረሰብ የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚያገኘው ጳውሎስ ጠንቅቆ ያውቃል (ሐዋ 13፡46;18፡6;26;28፡28) ጳውሎስ ለአይሁድ በመጀመሪ መስበክ እንዳለበት ያውቃል (ማቴ 10፡6;15፡24;ማርቆት፡27፡ሮማ 1፡3,5) ሐዋ 9;15;22 ሮሜ 11፡13;5፡16፡ገላ 1፡16 ኤፌ 3፡2,8,) ጢሞ 2፡7፡2 ጢሞ 4፡17

18፡7 ***"ኢየስጦስ ወደሚባል"*** ይህ ሰው እግዚአብሔርን የሚፈራ እና ቤቱን ለምኩራብ ጎን የሰራ ነው፡፡ ዝርዝሩን እንመልከት፡-

1. *ሙሉ ስሙ "ጋዮስ ቲቶ ኢዮስጦስ ይባላል፤የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን በእርሱ ቤት ነበረች (ሮማ 16፡23)"*
2. *በ1 ቆሮ 1፡14 የተጠቀሰው ጋዮስ በጳውሎስ የተጠመቀው ሊሆን ይችላል፡፡*
3. *የግሪኩ ፅሁፍ ስለዚህ ስያሚ ዝርዝር ገለፃ አለው*

*ሀ. ታይቶስ ሉስቶስ*, Mass B.D[2]
*ለ. ታይቶስ ሉስቶስ*, Mass N, E, P
*ሐ. ሉስቶስ* Mass A, B, D
*መ. ታይቶስ ፊሺታ*, *በኮፕቲክ ትርጉም*

▣ **"እግዚአብሔርን የሚያመልክ** *በሦስተኛ መቶ ክፍለ ዘመን የነበረ አፍሮዲሲስ የሚባለው የታሪክ ፀሐፊ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ የሚባሉት አሕዛብ ሆነው ነገር ግን ወደ አይሁድ ምኩራብ የሚመጡ እንደሆነ በመፅሐፍ ፅፎት ተገኝቷል።"* (*ሐዋ* 10፡1-2,22;13፡16,26)

*ይህ ሐረግ በተለያዩ የአዲስ ኪዳን መፅሐፎች ውስጥ በብዛት ተፅፏል ለምሳሌ ሊዲያን ለመግለፅ ቃሉን ፀሐፊው ሉቃስ ተጠቅሟል* (*ሐዋ* 16፡14 *እና በተሶሎንቄ* 17፡4 *ለግሪክ ሰዎች*) *እና ለቤርያ ለሚገኙ* (*ሐዋ* 17፡7) *እነዚህ የግሪክ ሰዎች ከአይሁድ ምኩራብ አይቀሩም ነገር ግን ደህንነት ያገኙ አልነበረም። ይሁን እንጂ 'ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለባቸው አሕዛብ' ሙሉ በሙሉ አሕዛብ የነበረና በምኩራብ በጆረጊያ ይኖር የነበረውን ያመለክታል* 13፡43።

18፡18 **"ቀርጳስም"** *በምኩራቡ ስራ ላይ እንዲያስተባብር የተሾመ መንፈሳዊ ሰው ነበር* (1 *ቆሮ* 1፡14)

▣ **"ከቤተሰቦቹ ሁሉ ጋር በጌታ አመነ"** *በሐዋርያት ስራ መፅሐፍ ውስጥ የቤተሰቡ መሪ ስላመነ ቤተሰቡ ሁሉ የዳኑ የብዙዎች ታሪክ ተፅፎ ይገኛል።* (*ሐዋ* 11፡14;16፡15,31-34;18፡8) *የጥናት የሜዲትራኒያን ምዕራብ አገሮች ለቤተሰብ ትኩረት አይሰጡም ነበር ነገር ግን ቤተሰብ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል። በመሆኑም አሁን ከሚታየው ከግለኝነትና ራስን መውደድ ጋር በእጅጉና የሚጣረዝ ሃሳብ ነው።*

*ይህ ማለት የቤተሰቡ አባላት ሁሉ ድነትን አግኝቶ ላይሆን ይችላል፡ አናሲምስ በክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ ቢኖርም ጳውሎስ እስከ ሚያገኘው ሕይወቱ አልተለወጠም ነበር።*

▣ **"ከቆርንቶስ ሰዎቹ ብዙ በስሙ ጊዜ አምነው ተጠመቁ** *አብዛኞቹ የቆሮንቶስ ሰዎች የጳውሎስን መልእክት ተቀብለውታል ነገር ግን ጳውሎስ ተስፋ የሚያስቆርጠው ነገር ገጥሞታል። ነገር ግን ጌታ ባሳየው ራዕይ በርትቷል* (*ሐዋ* 18፡10) *የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን የሚወዳት ቤተክርስቲያን ብትሆንም ነገር ግን በእርሱም ሰዎቹ አስቸጋሪዎች መሆናቸውን መገንዘብ እንችላለን።* (1 *እና* 2 *ቆሮንቶስን*) *በማንበብ ተጨማሪ ዝርዝር እናገኛለን።*

*ተመሳሳይነት ያለውን አውድ ከዚህ በታች እንመክከት* (1 *ቆሮ* 1፡14-17) 1፡17

"1፡17 **"ክርስቶስ እንዳጠምቅ ሳይሆን እንድሰብክ ልኮኛል"** *ይህ የጥምቀትን ስርዓት ለመቃወም ሳይሆን ለቆሮንቶስ መሪዎች በጊዜው ለነበረው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ነው ከዚህም በተጨማሪ ጥምቀት የቤተክርስቲያን ስርዓት ሆኖ በፀጋ እንዳይተካ ለማስገንዘብ ነው። አንዳንድ መላምቶች የጌታ ዕራት አንድ ጊዜ ብቻ በመጠቀሱ* (1 *ቆሮ* 11) *ነገር ግን ጥምቀት ሁለት ጊዜ በመጠቀሱ አስፈላጊነቱን ያመለክታል የሚል ክርክር አላቸው* (*ሮማ* 6፡1-11,*ቆላ* 2፡12) *በመሆኑም ጥምቀት የእግዚአብሔር ፈቃድ ለአማኝ ሁሉ ነው።*

1. *ኢየሱስ ያደረገው ነው*
2. *የኢየሱስ ትዕዛዝ ነው*
3. *በአማኞች ሁሉ የተሰጠ በረከት ነው።*

*ጥምቀት የእግዚአብሔር ፀጋ እና መንፈስ ለመቀበለ ዋና ስርዓት ነው ብዬ በግሌ አላምንም። ነገር ግን እምነትን በሰው ሁሉ ፊት ለመመስከር የሚጠቅም ስርዓት ነው። ኢየሱስ ለቤተ ክርስቲያን ከሰጣት ትዕዛዝ መካከል ጥምቀት አንዱ ቢሆንም በአዲስ ኪዳን የለም።*

18፡9 **"አትፍራ"** *ትዕዛዝ ያለው ነገር ግን ድርጊቱ ክፍም ሊሆን እንደሚችል የሚናገር ጠቋሚ ቃል ነው። ጳውሎስ በልቡ ፍርሃት ስለገባ የጌታ ማፅናናት ያስፈልገው ነበር። ጳውሎስ ያለፈበትን ተመሳሳይ ይህወት የሚያልፍ ሰው ሊፈራ ይችላል ነገር ግን ሉቃስ መፅናናትን ፅፏል* (*ሐዋ* 22፡17-18;23፡11;27፡23-24)።

▣ **"ተናገር ዝምም አትበል"** *ትዕዛዝ ያለበት ንግግር ነው። ይህ ሐረግ የሚያሳየው የሰው ስሜት ለመለዋወጥ እንደሚችል ነው፤ ነገር ግን ሐዋ* 1፡8 *የማይለወጥ ቃል እርሱ የሚመራ ብርሃን ነው* (2 *ጢሞ* 4፡2-5)

18፡10 **"እኔ ከአንተ ጋር ነኝ"** *ከዚህ የሚበልጥ ቃል ኪዳን የለም* (*ዘፍ* 26፡24;*ዘፀ* 3፡12፤33፡4;*መዝ* 23፡4;*ማቴ* 28፡20;*ዕብ* 13፡5) *እርሱ ከእኛ ጋር ስሆነ ሰላም እና ወንጌል ለመስበክ ድፍረት እናገኛለን።*

▣ **"በዚህ ከተማ ብዙ ሰዎች አሉኝ"** *የእግዚአብሔርን ቅድመ ምርጫ ከሚያመለክቱ ምንባቦች መሃከል አንዱ ነው።* (*ሮማ* 9; *ኤፌ*1) *በሕይወት መፅሐፍ ላይ የተፃፉ ሳች አሉ።* (*ራዕ* 13፡8) *በወንጌል ፀንቶ ለመኖር ያለ ተጋድሎ እርግጠኝንትን ያመጣል እንጂ አማኝ በመሞቱ መንግስተ ሰማይ ይገባል የሚል ማረጋገጫ አልተሰጠንም።*

18፡11 *ይህ ጥቅስ የጳውሎስን የሚሲዮናዊነት ጉዞውን በቅደም ተከተል በማስቀመጥ ግልፅ አድርጎታል። በቆሮንቶስ የነበረውን የአስራ ስምንት ወራት አገልግሎት በዝርዝር አስቀምጧል።*

**አእመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 18፡12-17**

*ጋልዮስም በአካይያ አገረ ገዥ በነበረ ጊዜ አይሁድ በአንድ ልብ ሆነው በጳውሎስ ላይ ተነሡ ወደ ፍርድ ወንበርም አምጥተው ይህ ህግን ተቃውሞ እግዚአብሔርን ያመልኩት ዘንድ ሰዎችን ያባብሳል፡፡ አሉ ጳውሎስም አፍን ሊከፍት ባሰበ ጊዜ ጋልዮስ አይሁድን አይሁድ ሆይ ዓመፃ ወይም ክፉ በደል በሆነ እንድታገሳችሁ በተገባኝ ስለ ቃልና ስለ ሰዎች ስለ ሕጋችሁም የምትከራከሩ ከሆነ ግን እራሳችሁ ተጠንቀቁ እኔ በዚህ ነገር ፈራጅ እሆን ዘንድ አልፈቅድምና አላቸው፡፡ የግሪክ ሰዎችም ሁሉ የምኩራብ አለቃ ሶስቴንስን ይዘው በወንበሩ ፊት መቱት በእነዚህም ነገሮች ጋልዮስ ግድ የለውም ነበር፡፡*

18፡12 "*ጋልዮስ*" ከመፅሐፍ ቅዱስ እና ከሌሎች መፅሐፍት እንደምንረዳ ይህ ሰው የተዋጣለት የፓለቲካ መሪ ነበር፡፡ ሴኒሳ የሚባለው ወንድሙ "በስልጣን ላይ ያሉ ባለስጣናት ወንድሜን አይወዱትም" እና "ለህዝቡ እንደ ጋልዮስ ያለ የለም በማለት የራሱን ወንድም አምካሽቷል፡፡" ይህ ሰው በጳውሎስ የሚሲዮናዊነት ጉዞው ረድቶታል፡፡ ጋልዮስ ለሁለት ዓመት ተኩል አገር ገዥ ነበር፡፡ (51 መቶ (ክ/ዘመን)

▣ "*ጋልዮስም በአካይያ አገረ ገዥ ነበር*" ፀሐፊው ሉቃስ ጠንቅቆ የሮማውያንን የስልጣንን ማዕረግ መጠሪያ ያውቃል በእርግጥም ከ44 ዓ.ም በኃላ የሮማውያን የስልጣን መጠሪያ ይህን ነበር፡፡ (ሐዋ 13፡7,19፡38)

"*አይሁድ በአንድ ልብ*" ሉቃስ አማኞች አንድ መሆናቸው ለመግለፅ ይህን ዐረፍተ ነገር በተለመጠ ይጠቀምበታል፡፡ (ሐዋ 1፡14; 2፡14; 2፡1, 46; 4፡24; 5፡12) ነገር ግን በዚህ ምንባብ ውስጥ የወንጌል ተፃራሪ አይሁድ ለክፋት አንድ መሆናቸውን ዓውዱ በዝርዝር ያስረዳል፡፡ በሌሎች ምዕራፎች ውስጥ ተመሳሰዩን ተመልከቱ (ሐዋ 7፡57; 12፡20 እና 19፡29)፡፡ 'አይሁድ' የሚለው ቃል በሉቃስ አፃፃፍ ተቀናቃኝ አይሁዶችን በሙሉ የሚያመለክት ነው፡፡

▣ "*ወደ ፍርድ ወንበርም አምጥተው*" የቃሉ ትርጉም አወጡት የሚል ቀጥተኛ የትርጉም አለው፡፡ በሮማውያን የፍርድ ቤት "ወንበሩ ከፍ ባለ መድረክ" የተቀመጠ ነበር (ማቴ 27፡19;ዮሐ 19፡3;ሐዋ 25፡6,10,17;2 ቆሮ 5፡10) ፡፡

18፡13 "*ሕግን ተቀውሞ እግዚአብሔርን ያመልኩ ዘንድ*" አይሁዶች የክርስትናን እምነት የሚመለከቱት ሕጋቸውን እና ስርዓታቸው የሚያረክስ እንግዳ የኑፋቄ ትምህርት እንደሆነ ያስባሉ፡፡ ጋልዮስ በስልጣን ላይ ቆይቶ ቦሆን ኖሮ ክርስትና ሕጋዊ ሃይማኖት በዚህ ጊዜ ይሆን ነበር፡፡ ነገር ግን በሮማውያን ዘንድ ክርስትና የአይሁድ ሃይማኖት ተቀፅላ በመሆን እውቅናን አግኝቶ ነበር ይህም ኔሮ በክርስቲያኖች ላይ ስደት እስካመጣበት ጊዜ ቆይቷል፡፡ (በግምት ከ10-12 አመታት በኃላ ይሆናል)

18፡14 "*በሆነ*" ይህ የሐይማኖት ንትርክ ነው እንጂ ወንጀል አይደለም ለማለት ቃሉ አገልግሏል፡፡ በዚህ አለመስማማት መሃከል ለየትኛውም ፍርድ መስጠት አስቸጋሪ መሆኑም ተብራርቷል፡፡

18፡15 "*በተገባኝ*" ይህ አገር ገዥ የማይገባውን ነገር ማድረግ እንደሌለበት አስታውቋል፡፡

18፡16 "*አስወጣቸው*" በአዲስ ኪዳን ይግሱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተፃፈ ነገር ግን በግሪኩ ፁሁፍ ውስጥ በርካታ ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ (1 ሳሙ 6፡8 ሕዝ 34፡12) "*elaunō*" የሚለው በግድና በሐይል ማሶጣት የሚል ቀጥተኛ ትርጉም አለው፡፡

18፡17 "*ሶስቴንስ ይዘው*" ግሪኮች ወይም አይሁድ ይህን የምኩራብ አለቃ ይዘው ደብድበውታል፡፡ ሶስቴንስ በ1 ቆሮ 1፡1 ጠቅሷል ነገር ግን ይሄው ሰው መሆኑን ማረጋገጫ የለም በተጨማሪም በዚህ ክፍል በፍርድ ወንበር ፊት ለምን እንደተደበደበ በግልፅ ዝርዝር አልተፃፈም፡፡

▣ "*በነዚህም ነገሮች ጋልዮስ ግድ የለውም ነበር*" ከጴላጦስ የተለየ አመል የነበረው ሰው ነበር፡፡

**አእመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 18፡18-21**

*ከዚያ በኃላ ጳውሎስ እጅግ ተቀምጦ ወንድሞችንም ተሰናብቶ በመርከብ ወደ ሶሪያ ሄደ ስለትም ነበረበትና ራሱን በክንክራኦስ ተላጨ ጳርስቅላና አቂላም ከእርሱ ጋር ነበሩ ወደ ኤፌስንም በደረሱ ጊዜ እነዚያን ከዚያ ተዋቸው ራሱ ግን ወደ ምኩራብ ገብቶ ከአይሁድ ጋ ይነጋገር ነበር፡፡ እነርሱም ብዙ ጊዜ እንዲቀመጥ ስለምኑት እሺ አላለም ነገር ግን ሲሰናበታቸው የሚመጣውን በዓይ በኢየሩሳሌም አደርግ ዘንድ ይገባኛል እግዚአብሔር ቢፈቅድ ግን ወደ እናንተ ደግሞ እመለሳለሁ፡፡ አላቸው ከኤፌሶን በመርከብ ተነሣ፡፡*

18፡18 "*በክንክራኦስ*" በኤጳሪያ ባህሪ አጠገብ የምትገኝ የቆሮንቶስ የወደብ ከተማ ነበረች በቤተክርስቲያን አቅጣጫም እንደምትገኝ መመልከት ይቻላል፡፡ (ሮማ 16፡1)

▣ "*ስዕለትም ነበረበት*" በብሉይ ኪዳን የተፃፈውን መሃላ ለማክበር ጳውሎስ ያደረገው ነው፡፡ (F.F Bruce, *answers to questions*, p 52) ሐዋሪያው ይህንን በድጋሚ አድርጎታል፡፡ (ሐዋ 21፡24) ፀጉርን መላጨት ቃል ኪዳትን እንደፈፀሙ የሚያመለክት ነው፡፡

ኤ.ቲ ሮበርሰን እና ኤም. አር.ቪ.ንሰንት ስዕለቱ የፃፈው መፅሐፍ የተጠሰው ሳይሆን የአይሁድ ባህል ነው። የሚል መላምት አላቸው ጳውሎስ ሰው ወደ ክርስቶስ ለማምጣት ሁሉን ለማድረግ የተዘጋጀ ነበር። (1 ቆሮ 9፡19-23) ይህን ያደረገበት ምክንያት ስርዓትን ለማክበር ሳይሆን ወንጌልን ለመስበክ እንዲያመቸው ነበር።

18፡19 "ኤፌሶን" በሚልተስ ከተማ የነበረውን ወደብ ካፈረሰ በኃላ በምዕራብ ትንሹ እስያ የምትገኘው የኤፌሶን ወደ ከተማይቱን የንግድ ከተማ እንድትሆን አድርጓት ነበር። በአዲስ ኪዳን ዘመን ኤፌሶን ባለጠጋ ከሚባሉ አገሮች ትመደብ ነበር አሁን ግን የቀድም ዓይነት ሳይሆን በአዲስ አመሰራረት ከተማይቱ ትገኛለች።

1. በትንሽ እስያ ከሚገኙ ከሮማውያን አውራጃዎች ትልቋ ከተማ ነበረች ዋናው ከተማ ባይሆንም የሮማ መንግስታት በዚህ ከተማ ይኖሩ ነበር ምክንያቱም ባለጠጋ እና የባህር በር የነበራት ዘመናዊ ከተማ በመሆንዋ ነው።
2. የኤፍሰን ከተማ ለሁሉም ሰው የተመቸች ነፃ ከተማ ነበረች
3. ከትንሹ እስያ ከሚገኙ ከተሞች ይልቅ በየአመቱ የሚከበር የእስፖርት ፊስቲቫል የሚደረግበት ስቴዲየም ነበር።
4. ከሰባቱ ታላላቅ የአለም አስደናቂ ከተሞች በዚያ ጊዜ በኤፌሶንም የአርጤምስ ቤተመቅደስ የነበረበት ከተማ ነበር። ይህ መቅደስ 425x220 የሆነ እና 127 የቤቱ ምሰሶዎች ያለው ሰፊ ህንፃ ነበር። የመቅደሱ ምስስዎች ርዝመታቸው 60 ክንድ ሲሆን ከ127ቱ በወርቅ የተለበጡ ነበሩ። (pliny's hist nat 36:95) የአርጤምስ መቅደስ በብዙ ሴቶች ጡቶች ይመስል ነበር። ይህ የሚያሳየው ከተማይቱ የዝሙት ጣኦት አምልኮት የነበረባት መሆኑን ነው። (ሐዋ 19)
5. በኤፌሶን ጳውሎስ ለሦስት ዓመታት ተቀምጧል (ሐዋ 18፡18;20፡13)
6. ማርያም ከሞተች በኃላ ዮሐንስ በኤፌሶን ሲኖር እንደመጣ ይናገራል።

▣ *"ራሴ ግን ወደ ምኩራብ ገብቶ ከአይሁድ ጋር ይከራከር ነበር"* ጳውሎስ የራሱን ህዝብ ይወዳል። (ሮማ 9፡1-5) በወንጌል እነርሱን ለመድረስ ብዙ ጥረቶችን አድርጓል።

18፡20 እነዚህ አይሁድ ቤርያምችን ይወዷቸዋል ልባቸውም ለመስማት የተከፈተ ነበር ጳውሎስ በዚህ መቀመጥ ያልፈለገበት ምክንያት በምንባቡ አልተጠቀሰም ምናልባት በእግዚአብሔር ምሪት በሌላ ጊዜ መምጣት አስቦ ሊሆን ይችላል።

▣ *"እግዚአብሔር ቢፈቅድ ወደ እናንተ ደግሞ እመለሳለሁ"* ጳውሎስ ሕይወቱን ለእግዚአብሔር የሰጠ ሰው ነው፡ (ሮማ 1፡10;15፡32;1 ቆሮ 4፡19;16፡7) ጳውሎስ በሦስተኛ የሚሲዮናዊነት ጉዞውን ወደ ኤፌሶን በማድረግ ተመልሶ ወደ ኤፌሶን መምጣቱን መረጋገጥ ይቻላል።

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡** 18፡22-23
**[22]ወደ ቂሳርያም በደረሰ ጊዜ ወጥቶ ለቤተ ክርስቲያን ሰላምታ ከሰጠ በኃላ ወደ አንፃኪያ [23]ወረደ ጥቂት ቀንም ቆይቶ ወጣ ደቀ መዛሙርትንም እያፀና በገላትያ አገርና በፍርሚያ በተራ አለፈ።**

18፡22 በቁጥር 21 ላይ ጳውሎስ ኤፌሶን መድረሱን ያሳያል ነገር ግን ቁጥር 22 ደግሞ በቂሳርያ በመድረስ በኢየሩሳሌም መጥቶ (በስነ መለኮት ወጣ የሚለው የኢሩሳሌምን ታላቅነት የሚያሳይ ነው) አብያተ ክርስቲያናት ይጎበኝ ነበር በተጨማሪም ወደ አንፃኪ. ወረደ (ወረደ በመሬት አቀማመጡ ሳይሆን ከኢየሩሳሌም ያነሰ ክብር ለመስጠት የተፃፈ ነው) ሉቃስ እያንዳንዱን የጳውሎስን የመንገድ ክስተት አልፃፈው ነገር ግን ለስነመለኮት ጠቃሚና አስፈላጊ የሆኑ ነጥቦችን ፅፏል። ቁጥር 22 ሁለተኛው የሚሲዮን አገልግሎት አብቅቶ ቱ. 2 ሦስትተኛው ጀምሮአል።

18፡23 *"ደቀ መዛሙርትን እያፀና"* ሐዋርያው ጳውሎስ የታላቁን ተልዕኮ ትዕዛዝ እያከናወነ ነው (ማቴ 28፡19-20) አገልግሎት ወንጌልን ማዳረስ የማቴ 28፡19) እና ደቀ-መዛሙርትን ማስተማር ነበር። (ሐዋ 15፡36; ማቴ 28፡20)

▣ *"ቤተክርስቲያን"* ልዩ ርዕስ 5፡11 ላይ ያለውን ይመልከቱ።

*"በገላቲያ አገርና በፍርግያ"* በአሁኑም ቱርክ ግዛት ገላትያ የትኛው አካባቢ እንደሆነ ባለመታወቁ በምሁራን መሃከል አነታሪኪ ጉዳይ ሆኖአል።

ፊርግያ በመጀመሪያ የተጠቀሰችው በሐዋ 2፡10 ላይ ነው። አንዳንዶች የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ የተቀበሉት የፍርግያ ሰዎች ነበሩ። በሐዋ 16፡6 ላይ ጳውሎስ በዚህ አገር ወንጌል እንዳይሰብ መንፈስ ቅዱስ ከልክሎት ነበር።

ደቀ መዛሙርትን እያፀና የሚለው ዐረፍተ ነገር የሚያሳየው በመንፈስ ቅዱስ መውረድ ቀን የነበሩትን አማኞች ወይም በጳውሎስ ስብከት በደርባንና በልስፕራ ልባቸው የተቀየረ ወይም በአቆንዮን የነበሩትን አማኞች የሚያሳይ ነው እነዚህም ጳውሎስ የሰበከባቸው ቦታዎች በደቡብ ገላትያ የሚገኙ የሮማ አውራጃዎች ናቸው።

እንግዲህ ይህ የጳውሎስ ሦስተኛ የሚሲዮናዊነት ጉዞው መጀመሪያ ነው (5፡36፣ ማቴ 28፡20)።

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 18፡24-28**

**በወገኑም የእስክንድርያ ሰው የሆነ ነገር አዋቂ የነበረ አጳሎስ የሚሉት አንድ አይሁዳዊ ሰው ወደ ኤፌሶን ወረደ እርሱም በመፅሐፍት እውቀት የበረታ ነበር። እርሱ የጌታን መንገድ የተማረ ነበር የዮሐንስም ጥምቀት ብቻ አውቆ በመንፈስ ሲቃጠል ስለ ኢየሱስ ይናገርና በትክክል ያስተምር ነበር። እርሱም በምኩራብ ገልጦ ይናገር ጀመር ጳርስቅላ እና አቂላ በሰሙት ጊዜወስደው የእግዚአብሔርን መንገድ ይልቅ ባለሙልት እርሱም ወደ አካይያ ማለፍ በፈቀደ ጊዜ ወንድሞቹ አፅናኑት ይቀበሉትም ዘንድ ወደ ደቀ መዛሙርት ፃፍለት በደረሰም ጊዜ አምነው የነበሩትን በፀጋ እጅግ ይጠቅማቸው ነበር። ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ ከመፅሐፍት እየገለጠ ለአይሁድ በሁሉ ፊት በፅኑ ያስረዳቸው ነበርና።**

18፡24 **"ጳሎስ የሚሉት አይሁዳዊ"** ለአይሁዳዊ ሰው በግሪክ ጣኦት ስም መጠራት አልተለመደም ነገር ግን ይህ አጳውሎስ የተማረ እና የመናገር ችሎታ የነበረው (ሐዋ 18፡24-19፡1) ለቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን አገልግሎት አስፈላጊ ቢሆንም ነገር ግን እርስ በእርስ በነበረው ክፍፍል እርሱን አንድ ቡድን መሪ አድርገውት ነበር። (1 ቆሮ 1-4) ከዚያ በኃላ አጳሎስ ወደ ቆሮንቶስ መመለስ ፈቃደኛ አልሀሆነም (1 ቆሮ 16፡12)

▣ **"በወገኑም የእስክንድሪያስ ሰው"** በሮም ከሚገኙ ትላልቅ ከተሞች በሁለተኛ ደረጃ የምትገኝ ከተማ ነች፤ ከተማይቱም በትምዕርት እና በቤተ መፅሐፍት ትልቅነትን ካተረፉት መሃከል የሚመደብ ነው አይሁድዳውያን በብዙ ቁጥር በዚህ ከተማ ይኖራሉ፤ መፅሐፍ ቅዱስ ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ የተተረጎመውም በዚሁ ከተማ ነበር በተጨማሪም የፍልስፍና የታላላቅ አይሁዳውያን መፍለቂያ ነበረች።

▣ **"ወደ ኤፌሶን ወረደ** በሐዋርያት ስራ በዝርዝር ታሪኩ በቅደም ተከተል አልተፃፈም በዚህ ጊዜ ጳውሎስ ከተማይቱን ለቆ ሄዶ ነበር (ሐዋ 18፡23)"

▣ **"አዋቂ"** የግሪኩ "koine" ፍቺው **"ተናጋሪ"** ወይም "የተማረ" ማለት ነው። አጳውሎስ ከጳውሎስ ይልቅ የመናገር ወይም የመስበክ ክህሉት ነበረው (1 ቆሮ 1፡17,2፡1;2፡1;2 ቆሮ 10፡10 እና 11፡6)

▣ **"በመፅሐፉም ዕውቀት የበረታ ነበር"** መፅሐፍት የሚያመለክተው የብሉይ ኪዳንን መፅሐፍት ነው። (1 ተሰሎ 2፡13;2 ጢሞ 3፡16,1 ጴፕ 1፡23-25; 2 ጳፕ 1፡20-21) አጳሎስ የብሉይ ኪዳንን መፅሐፍ ጠንቅቆ ያውቅ ነበር።

የበረታ የሚለው ቃል "dunatos" ይህም ማለት ኢየሱስ በቃል እና በስራ ብርቱ ነበር ከሚለው የዐረፍተ ነገር ትርጉም ጋር አንድ አይነት ነው።

18፡25 **"እርሱ የጌታን መንገድ የተማረ ነበር"** አጳሎስ የኢየሱስን ትምዕርት በመስማት ሰልጥኖ ሊሆን ይችላል። (curtis Vaughan, acts p 118,footnote#2,) አጳሎስ ሚሰብከው ስለማን ነበር፡-

1. ዮሐንስ መጥምቁ የመሲሁ መንገድ ጠራጊ ነበር
2. የእግዚአብሔር ልጅ የሆነውን ኢየሱስ የአለምን ሃጢያት የሚያስወግድ መሆኑን
3. ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ መሲህ እንደሆነ አጳውሎስ ገልጦ ያስተምር ነበር።

▣ **"የእግዚአብሔርን መንገድ"** መንገድ የሚለው ቃል ለአማኞች የተሰጠ ስያሜ ነበር። (ሐዋ 9፡2;19፡9,23;22፡4;24፡14,22;ዮሐ 14፡6) በብሉይ ኪዳን ቃሉ የተለመ ነው (ዘደ 5፡32-33;3) ፡29;መዝ 27፡11; ኢሳ 35፡8) የአማኝን የሕይወቱን መመሪያ የሚወስን ነው። (ሐዋ 18፡26)

አጳሎስ የክርስቶስን አገልግሎት ያውቃል ነገር ግን ከትንሳኤ በኃላ ያለውን አገልግሎቱን ታሪኩን በሚገባ ያውቅ አልነበረም ጳውሎስ ሃርቬ የሚባል ፀሐፊ "የቀረውን ታሪክ ማወቅ ነበረበት" በማለት ፅፏል።

▣ **"በመንፈስ ሲቀጥል"** ይህ የሚያመለክተው አጳሎስ በኢየሱስ ትምዕርት እና በተረዳው ዕምነት የጋለ ፍላጎት እንደነበረው ያስገነዝበናል።

▣ **"የዮሐንስ ጥምቀት ብቻ አውቆ"** ይህ ሐረግ የዮሐንስ ደቀመዛሙርት የተተዋወቀበትን አይነት አገላለፅ ሉቃሽ በድጋሚ የአጳሎስን ሁኔታ ለመግለፅ ተጠቅሞበታል። (ሐዋ 19፡1-7) በመጥምቁ ዮንስ ትምዕርትና ስብከት መሰረት ለማድረግ በመጀመሪያው መቶ ምዕተ ዓመት ብዙ የስህተት ትምህርቶች ነበሩ።

መጥምቁ ዮሐንስ የመጨረሻው የብሉይ ኪዳን ለመሲሁ መንገድን የሚያዘጋጅ ነብይ ነበር እንጂ የአዲስ ኪዳን የመጀመሪያው ወንጌል ሰባኪ አልነበረም። አጳሎስ በዮሐንስ ትምህርት ላይ ብቻ አተኩሮ ከሆነ የመሲሁን አጠቃላይ አላማ መሳቱን መገንዘብ ይቻላል። ኢየሱስና ዮሐንስ ትኩረት የሰጡአቸው ጉዳዮች ንስሃ፣እምነት፣የቅድስ ህይወት ላይ ነው። አይሁድ በቃል ኪዳን የራሳቸው ዕምነት ነበራቸው በተጨማሪም በያህዌ በግል ያምኑ ነበር። ነገር ግን ኢየሱስ (የሐ 18እና 14) በማስገባቱ ችግር በዙዎች ዘንድ ሆኖአል። እንግዲህ አጳሎስ የጎደለው በዚህ ጥቅስ ላይ ያለው ሃሳብ ነው።

18፡26 **"በምኩራብ ገልጦ ይናገር ጀመር"** ለጳውሊስም በተመሳሳይ ተጠቅ ይገኛል (ሐዋ 13፡46;14፡3፡19፡8) አጳውሎስ የተሳካለት ሰባኪ እና አስተማሪ ነበር።

▣ **"በምኩራብ"** አቂላ እና ጵርስቅላ ያሉበት ምኩራብ የነበሩበት ነው። ይህ ደግሞ የጳውሎስም ልማድ ነው።

▣ **"ጵርስቅላ እና አቂላ"** የጵርስቅ ስም መጀመሪያ መጠቀሱ በአዲስ ኪዳን የተለመደ ሆኖአል (ሐዋ 18፡18፡26 ሮሜ 16፡3፤2 ጢሞ 4፡19) ይህ የሚያመለክተው ይህች ሴት ይህ የሚያመለክተው ይህች ሴት መልካም ስዕብና ያላት መሆኗን ይገልፃል። አቂላ አይሁዳዊ ሲሆን ጵርስቅላ አይሁዳዊ መሆንዋን የሚያረጋግጥ ፅሁፍ የለም። እነዚህ ባልና ሚስት ከጳውሎስ ጋር ድንኳን በመስፋት ይተዳደሩ ነበር።

▣ **"ወስደው"** አንድን ሰው ባልንጀራ አድርጎ መቀበልን ያመለክታል። አቂላና ጳርስቅላ አጳሎስን መቼ እንደተቀበሉት አይታወቅም ነገር ግን ምናልባት በግል አናግረውታል እቤታቸውም ወስደውት ሊሆን ይችላል። አጳሎስን በህዝብ ፊት በምንም መንገድ ከክፉ አልተናገሩትም:: አጳሎስ ምንም እንኳን የተማረ ቢሆንም ለመማር የተዘጋጀ ልብ ነበረው።

▣ **"የእግዚአብሔርንም መንገድ ይበልጥ ገልጠው አስረዱት"** እርሱ ለመማር ፈቃደኛ ነበር። ለተማሩ ሰዎች እጅግ አስቸጋሪ ነበር መማር። እርሱ ስለ ኢየሱስ ለሰማው ነገር ሙሉ መልስ ነው የሰጠው።

18፡27 **"ወደ አካይያ ማለፍ በፈቀደ ጊዜ"** የግሪኩ ፅሐፊ የቆሮንቶስ ሰዎች እንዲሄድ እንገፋፉት ይገልፃል።

▣ **"ወንድሞች . . . ፃፍለት"** በአብያተ ክርስቲያናት መሃከል ለማረጋገጫ ደብዳቤ ለግለሰቦች ይፃፍ ነበር። (ሮማ 16፡1፡2 ቆሮ 3፡1)

▣ **"አምነው የነበሩትን በፀጋ ይጠቅማቸው ነበር"** ይህንን ሐረግ በሁለት መንገዶች መረዳት ይቻላል።

1. አንድ ጊዜ ፈፅመው የዳኑትን አማኞቸው ያመለክታል (NASB,NKJV,NRSV,TEU)
2. እግዚአብሔር አጳውሎስን በሃይል እንደሞላውና ለብዙዎች በረከት እንዳደረገው ማጤን ይቻላል። አጳውሎስ በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን የሚያደርገው ወንጌል ስርጭት ሳይሆን አማኞች ደቀ- መዝሙር ማድረግ ነበር።

18፡28 አጳሎስ የብሉይ ኪዳንን መፅሐፍት ጳጥሮስ፣ጳውሎስ እና እስቲፋስ እንደተጠቀሙበት ይጠቅስ ነበር። የብሉይ ኪዳንን መፅሐፍት መጥቀስ አይሁዳውያን ስለ መሲሁ ለመናገር የሚያገልግል አይነተኛ መንገድ ነበር።

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ለመርዳት ነው የተሰናዱት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋነኞቹን ጉዳዮች ለማጤን እንዲረዳ ነው። ሐሳብ ለማጫር እንጂ መደምደሚያ አይደሉም።

1. የጵርስቅላ ስም በመጀመሪያ ተርታ በአዲስ ኪዳን የተፃፈበት ምክንያት ምንድነው።
2. ጳውሎስ ጵርስቅላን እና አቂላን እንዴት እና ለምን ተዋወቃቸው?
3. ጵርስቅላ እና አቂላ ወደ ሮም መመለሳቸውን ማስረጃ ማግኘት ይቻላልን?
4. የጳውሎስንና የአጳሎስን የስብከት ዘዴ አነፃፅሩ።
5. አጳሎስ ጵርስቅላንና አቂላ ሳያገኝ እንዴት ክርስቲያን ሊሆን ቻለ?

# የሐዋርያት ስራ 19

## የምንባቡ ክፍፍል በአዲሶቹ ትርጉሞች

| የተየመቅሶ[4] | አኪጀት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጳውሎስ በኤፌሶን | ጳውሎስ በኤፌሶን | የጳውሎስ ረጅም አገልግሎት በኤፌሶን | ጳውሎስ በኤፌሶን | የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት በኤፌሶን |
| 19:1-7 | 19:1-10 | 19:1-7 | 19:1-2 | 19:1-7 |
| | | | 19:2 | |
| | | | 19:3 | |
| | | | 19:3 | |
| | | | 19:4 | የቤተክርስቲያን ምስረታ በኤፌሶን |
| | | | 19:5-7 | |
| 19:8-10 | | 19:8-10 | 19:8-10 | 19:8-10 |
| የአስቄዎ ልጆች | የክርስቶስ የክብር ተዓምራት | | | አጋንንት የሚያስወጡ አይሁድ |
| 19:11-20 | 19:11-20 | 19:11-20 | 19:11-14 | 19:11-12 |
| | | | | 19:13-17 |
| | | | 19:15 | |
| | | | 19:16-20 | |
| | | | | 19:18-19 |
| | | | | 19:20 |
| አመፅ በኤፌሶን | አመፅ በኤፈሶን | | አመፅ በኤፌሶን | የጳውሎስ ዕቅድ |
| 19:21-27 | 19:21-41 | 19:21-22 | 19:21-22 | 19:21-22 |
| | | | | በኤፌሶን የብር አንጥረኞቹ አመፅ |
| | | 19:23-27 | 19:23-27 | 19:23-31 |
| 19:28-41 | | 19:28-41 | 19:28-34 | |
| | | | | 19:32-41 |
| | | | 19:35-41 | |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (ከ "**መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ**" **ገጽ** vii)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

*ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።*

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. ምንባብ አንድ
2. ምንባብ ሁለት
3. ምንባብ ሦስት
4. ወ.ዘ.ተ.....

**የቃል እና የጥምር ቃል ጥናት**

| |
|---|
| አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ: 19:1-7<br>**አጵሎስም በቆሮንቆስ ሳለ ጳውሎስ በላይኛው ሀገር አልፎ ወደ ኤፌሶን መጣ አንዳንድ ደቀ መዛሙርትንም አገኘ። በመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁ? አላቸው።እነርሱም አልተቀበልንም መንፈስ ቅድስ እንዳለ እንኳ አልሰማንም አሉት። እንኪያስ በምን ተጠመቃችሁ? አላቸው። እነርሱም በዮሐንስ ጥመቀተ አሉት። ጳውሎስም ዮሐንስስ ከእርሱ በኃላ በሚመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ ያምኑ ዘንድ ለህዝብ እየተናገረ በንስሃ ጥምቀት አጠመቀ አላቸው። ይህንም በሰሙ ጊዜ በጌታ በኢየሱስ ስም ተጠመቁ ጳውሎስም እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው በልሳኖችም ተናገሩ ትንቢትም ተናገሩ። ሰዎቹም ሁሉ አስራ ሁለት ያህሉ ነበር።** |

**19:1 "በላይኛው አገር"** ይህ በደቡብ ገላትያ ጳውሎስ ገላትያ ጳውሎስ ወንጌልን ያገለገለበት አካባቢን ያመለክታል።

**19:2 "በመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን"** በዚህ ምንባብ ላይ የሚገኙት ክርስቲያኖች ደቀ-መዛሙርት ተብለዋል። ባመናችሁ ጊዜ የሚለው አማኞች እንደሆኑ ይናገራል። ይህ ጥያቄ የሚያስከትል ነው፡ (1) እነዚህ ሰዎች ባመኑ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን አልተቀበሉም ማለት ነው። (2) እግዚአብሔር ካልገለጠ አይታወቅም ማለት ነውን? (ዮሐ 6:44.65) የመንፈስ ቅዱስ ስራዎች ደረጃ በደረጃ የሚከናወኑ ናቸው። የሐዋርያት መፅሐፍ በደህንነት ላይ ስለሚያተኩር ተርጓሚዎች ፅንፈኞች እንዳይሆኑ ይከለክላል። የሐዋርያት ስራ መፅሐፍ በአንድ ወቅት የሆነውን ይናገራል እንጂ ተመሳሳይ ነገር እንዲሆን የሚያስገድድ መመሪያ የለውም ድነት በአንድ መንገድ ሳይሆን በጊዜው በተፈጠረው ክስተት ሊከናወን ይችላል።

▣ **"መንፈስ ቅዱስ እንዳለ እንኳን አልሰማንም"** የመጥምቁ ዮሐንስ ስብከት ያለመንፈስ ቅዱስ ሃይል ዋጋ እንደሌለው ያመለክታል። (ሮሜ 5:6-11፣ 1ቆሮ 12:3፣ 1ዮሐ 4:2) ዮሐንስ በስብከቱ ስለ መንፈስ ቅዱስ ተናግሯል። (ማቴ 3:11፣ ማርቆ 1:8፣ ሉቃ 3:10፣ ዮሐ 1:32-33) ነገር ግን ይህ የእርሱ መልእክት ሰዎችን የሚያዘጋጅ ነበር። (ኢሳ. 40:3፣ ማቴ 3:3) መጥምቁ ዮሐንስ የመጨረሻው የብሉይ ኪዳን ነብይ በመሆን ለሚመጣው መሲህ መንገድ የሚጠረግ ነበር። ይህ ሰው ሁሉን ወደ ኢየሱስ እንዲመለከቱ ይናገር ነበር (ዮሐ 1:19-42)።

**19:13 "እንኪያስ በምን ተጠመቃችሁ"** እነዚህ ሰዎች የመጥምቁ ዮሐንስ ተከታዮች ናቸው በመሆኑም ስለኢየሱስ ክርስቶስ ህይወት፣ ሞት እና ትንሳኤ እና ወደ ሰማይ ማረግ ሊማሩ ይገባል (ሐዋ 18:24-28)።

**19:3-4 "በዮሐንስ ጥምቀት"** የመጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት የሚያካትተው ንስሃን እና የወደፊት ምልክታን ነው። (ማቴ3:11፣ ማርቆ 1:15) በመሆኑም በመመርከዝ በርካታ የስህተት ትምህርቶች ተፈጥረዋል። (*Recongnitions of Clement*, chapter 60) ሉቃስ እነዚህን ሰዎች ለይቶ ፅፏቸዋል። የመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት ከእርሱ ይልቅ ወደ ኢየሱስ የሚያመለክት ነበር።

▣ **"በርሱ ያመኑ"** ልዩ ርዕስ 3:16 ላይ ያለውን በርሱ ያመኑ የሚለውን ርዕስ ይመልከቱ።

▣ **"ተጠምቀው ነበር"** ልዩ ርዕስ 2:38 ላይ ያለውን ይመልከቱ።

**19:5 "በጌታ በኢየሱስ ስም"** ፀሐፊው ሉቃስ ጥምቀተ በጌታ በኢየሱስ ስም እንደተደረገ የገለፀበት ቦታ ነው። (ሐዋ 2:38 ሐዋ 8:12:16 ሐዋ 10:48) ማቴዎስ እንደፃፈው ጥምቀት የሚካሄደው በአብ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም ነው (ማቴ 28:19) የጥምቀት ቅርፅ መለዋወጥ ለድነት ዋስትና አይሰጥም። ነገር ግን የልብ መለወጥ እጅግ አስፈላጊ ነው። ደህንነት የሚያስገኝልን የመስዋት ትክክለኛነት ሳይሆን የግል እምነታችን እና ንስሃ መግባታችን ነው።

አጵሎስ በመጥምቁ ዮሐንስን ጥምቀት ብቻ ቢጠመቅም መንፈስ ቅዱስ በሚያስተምረው እና በሚሰብከው ቃል ሰዎችን ያገለግል ነበር።

**19:6 "ጳውሎስ እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው"** እጅን መጫን ከመንፈስ ቅዱስ ስራ ጋር የተገናኘ ነው። (ሐዋ 8:16-17፡ ሐዋ 9:17) ነገር ግን ሁል ጊዜ ላይሆን ይችላል። (ሐዋ 10:44) መፅሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ህይወት እንደሚከተለው ይገለፃል፡ (1) አንድ ሰው አማኝ በሆነ በቅስበት መንፈስ ቅዱስ ከእርሱ ጋር ይሆናል፣ (2) የውሃ ጥምቀት በሚወስድ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ይወት መስራት ይጀምራል፣ (3) በእጅ መጫን በተፀለየ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ሙላት ይሆናል።

የሐዋርያት ስራ መፅሐፍ ህግጋት ለማስተማር ሳይሆን የመንፈስ ቅዱስን ስራዎች የሚናገር መፅሐፍ ነው። የዮሐንስ ደቀ-መዛሙርት በመንፈስ ቀዱስ በልሳን መናገራቸው የሚያስደንቅ ነው። በአዲስ ቋንቋ-መናገር ለአማኞች ምልክት ነው። ሉቃስ ለምን ይህንን ታሪክ መዝገብ አስፈላጊው? ምክንያቱም በሐዋርያት ስራ 1.8 ላይ ያለውን የአጳሎስን ታሪክ ከዚህ ጋር ለማስተያየት ይመስላል።

▣ **"ትንቢትም ተናገሩ"** የብሉይ ኪዳን አማኞች ንግግር ነው። (1ሳሙ 10110-122 19:23-24) ነገር ግን ይህ ሐረግ በ1 እና 2 ቆሮንቶስ መሠረት የወንጌል እወጀን ያመለክታል። (ሐዋ 11:4.5.24.31.39) በአዲስ ኪዳን የትንቢትን ትርጉም ማግኘት አይቻልም። በመንፈስ ቅዱስ መሞላት የመጀመሪያው አላሚው ወንጌልን ለመስበክ ነው።

**19:7 "ሰዎቹም ሁሉ አስራ ሁለት ያህሉ ነበር"** በመፅሐፍ ቅዱስ አስራ ሁለት ቁጥር ለብዙ ተምሳሌታዊ ንግግር ያገለግላል። ነገር ግን በዚህ ሐረግ ውስጥ የሰዎቹ ቁጥር አስራ ሁለት ብቻ መሆናቸው ለመናገር ተፈልጐ ነው።

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 19:8-10**
**ወደ ምኩራብ ገብቶ ስራ እግዚአብሔር መንግስት እየተነጋገረና እያስረዳቸው ሦስት ወር ያህል በግልፅ ይናገር ነበር። አንዳንዶች ግን እልኞች ሆነው በህዝቡ ፊት መንገዱን እየሰደቡ ባላመኑ ጊዜ ከእርሱ ርቆ ደቀ መዛሙርትን ለየ ጢሮስም በሚሉት በትምህርት ቤት ዕለት ዕለት ይነጋገር ነበር። በእስያም የጌታን ቃል እስኪሰሙ ድረስ ሁለት ዓመት ያህል እንዲህ ሆነ።**

**19:8 "ወደ ምኩራብ ገብቶ"** የጳውሎስ ወደመኛ ስራው ነበር (ሐዋ 9:20 ሐዋ13:5.14፣ ሐዋ17:2.10፣ ሐዋ 8:4.19.26)።

▣ **"በግልፅ ይናገር ነበር"** በመንፈስ የመሞላት የመጀመሪያው ምልክት ይህ ነው። (ሐዋ 4:13.29.31 ሐዋ9:28.29፣ ሐዋ 14:3፣ ሐዋ18:26) ጳውሎስ በግልፅ መናገር እንዲችል ይፀልያል። (ኤፌ 6:19)

▣ **"ሦስት ወራቶች"** በኤፌሶን የሚገኙ ምኩራቦች ጳውሎስ እንዲያስተምር፣ እንዲሰብክ እና አመክንዮዎቹን በየሰንበቱ እንዲያቀርብ ፈቅደውለት ነበር። ይህ የሚያመላክተው ለወንጌል በራቸውን መክፈታቸውን ነበር።

▣ **"የእግዚአብሔር መንግስት"** በኢየሱስ አገልግሎት መካከለኛ መልእክቱ ስለ እግዚአብሔር መንግስት ነበረ። የእግዚአብሔር መንግስት በሰው ልብና በሰማይ በሚል ባለሁለት ይከፈላል። (ማቴ 6:10)

**19:9 "አንዳንዶች ግን እልከኛ ሆነው"** ወንጌልን የሚሰሙ ሁሉ የመምረጥ ሙሉ ፈቃድ አላቸው (ሐዋ 17:32.34)። የዘር ዘሪውን ምሳሌ ተመልከቱ (ማቴ 13፣ ማር 4)።

እልከኛ ወይም *ስክልሩኖ* የሚያመለክተው ድርጊቱ በሃላፊ ጊዜ በተደጋጋሚ የተፈፀመ ወይም ድርጊቱ ገና መጀመሩን ሊያመለክት ይችላል። በሬሜ 19:18 እስራኤል በእግዚአብሔር ላይ ልቧን ክፉ አድርጋ ነበር። እግዚአብሔር በመልኩ የፈጠረውን ሰው ልብ ድንጋይ አያደርግም ነገር ግን በልባቸውን አመፅ የክብሩ መገለጫ ሁኔታ ያደርገዋል። (ሮሜ 1124.26.28) ነገር ግን የሰዎች ክፋት ጥፋትን የሚያመጣ መሆኑ የታወቀ ነው (ኤፌ 2:1-3፣4:14፣6:10-18)።

▣ **"በህዝብ ፊት መንገዱን እየሰደቡ"** ወንጌል በአይሁዳውያን ሃይማኖት ፊፅሞ የተለየ ከመሆኑ የተነሣ ከፍተኛ ተቃውሞ ይገጥመው ነበር።

ፀሐፊው ሉቃስ የአይሁድን ተቃውሞ በዓፊው መፅሐፍ ውስጥ በግልፅ ዘግቦት እንመለከታለን። (ሐዋ 13:46-48፣ ሐዋ 18-5-7. ሐዋ 19:8-10፣ 28:23-28)

▣ **"መንገዱን"** ሐዋ 18:25 ይመልከቱ።

▣ **"ጢራኖስም የሚሉት ትምህርት ቤት"** የስብሰባው ህንፃ ነፃ በሚሆንበት ከጠዋቱ አምስት ሰዓት እስከ አስር ሰዓት ጳውሎስ ያስተምር ነበር። ይህ በእርግጥ አፈ ታሪክ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ የግል ስራውን ከስራ በኃላ በእረፍት ሰዓቱ ወንጌልን ያስተምር ነበር (ሐዋ 20:34)።

ስለ ጢራኖስ ትምህርት ቤት የተለያዩ ምልከታ ዓለሞችን እንመልከት።

1. በፀሐፊው ሳዱስ በአስረኛው ምዕተ ዓመት በዝርዝር ተፅፏል። ይህ ጢራኖስ እንደ ፓለቲካል ኢንሳይክሎፒዲያ፣ የስነፅሑፍ ማዕከል እና ዘመናዊ ሰዎችን ማሰልጠኛ ተደርጐ ይወሰድ ነበር።
2. ጢራኖስ የአይሁድ መምህር ነበር እርሱም ይህንን የግል ትምህርት ቤት በመክፈት የሙሴን ህግ ያስተምር ነበር። ነገር ግን የፅሐፊ ማስረጃ ለዚህ ዝርዝር አናገኝም።

3. ትምህርት ቤት የሆነው ህንፃ በመጀመሪያ የአስፖርት ማሰልጠኛ ነበር፡፡ ነገር ግን ዘግይቶ ጢራኖስ ህንፃውን የራሱ አድርጎታል፡፡

ጳውሎስ በኤፌሶን ቤትን በመከራየት ያስተምር ነበር፡፡

19፡10 "*ሁለት ዓመታት*" በሐዋ 20፡31 በዚህ ጥቅስ ውስጥ ጳውሎስ በአውራጃው የነበረውን ቆይታ ገልፃል፡፡ (*ለሦስት ዓመታት*)

▣ "*በእስያም የሚኖሩት ሁሉ*" በፀሐፊው ተጋኖ የተፃፈ ቁጥር ነው፡፡ በምስራቁ የስነ ፅሑፍ የተለመደ አፃፃፍ ስልት ነው፡፡

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 19፡11-20**

**እግዚአብሔር በጳውሎስ እጅ የሚያስገርም ተዓምራት ያደርግ ነበር፡፡ ስለዚህም ከአካሉ ጨርቅ ወይም ልብስ ወደ ድውዮች ይወስዱ ነበር፡፡ ደዌያቸውም ይለቃቸው ነበር፡፡ ክፍዎች መናፍስትም ይወጡ ነበር፡፡ አጋንንትንም እያወጡ ይዞሩ ከነበሩት አይሁድ አንዳንዶች ጳውሎስ በሚሰብከው በኢየሱስ እናምላችኃላን እያሉ ክፍዎች መናፍስት ባሉባቸው ላይ የጌታን የኢየሱስን ስም ይጠሩባቸው ዘንድ ሞከሩ፡፡ የካህናትም አለቃ ለሆነው አስቄዋ ለሚሉት ለአንድ አይሁዳዊ ይህን ያደረጉ ሰባት ልጆች ነበሩት፡፡ ክፉ መንፈስ ግን መልሶ ኢየሱስንስ አውቀዋለሁ እናንተማ እነማን ናችሁ አላቸው፡፡ ክፉ መንፈስም ያለበት ሰው ዘለለባቸው ቁስለውም ከዚያ ቤት ዕራቁታቸውን እስኪሸሹ ድረስ በረታባቸው አሸነፋቸውም ይህም በኤፌሶነ በሚኖሩት ሁሉ በአይሁድና በግሪክ ሰዎች ዘንድ የታወቀ ሆነ በሁላቸውም ላይ ፍርሃት ወደቀባቸው የጌታም የኢየሱስ ስም ተከበረ፡፡ አምነውም ከነበሩት እጅግ ሰዎች ያደረጉትን እየተናዘዙና እየተናገሩ ይመጡ ነበር፡፡ ከአስማተኞችም ብዙዎቹ መፅሐፋቸውን ሰብስበው በሰው ሁሉ ፊት አቃጠሉት ዋጋውም ቢታሰብ አምሳ ሺ ብር ሆኖ ተገኘ፡፡ እንዲህም የጌታ ቃል በሃይል ያድግና ያሸንፍ ነበር፡፡**

19፡11 በዚህ ምንባብ ያለው የእግዚአብሔር ተዓምራቶች ለመጀመሪ የተደረገ አይደለም ነገር ግን የወንጌልን እውነት የሚያረጋግጡ፡ የተለመዱ የእግዚአብሔር ራሰዎች ናቸው፡፡ (ሐዋ3፡1-10፣ ሐዋ5፡15፣8፡6፡13 ሐዋ9፡40-42 ሐዋ13፡11-12) በአፌሶን ከተማ የጥንቆላ አሠራር በግልፅ ይታይ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ አምላክ እና የምህረት አምላክ መሆኑን በጳውሎስ ይገልጥ ነበር፡፡

19፡12 "*ከአካሉ ጨርቅ*" ይህ ጨርቅ የጳውሎስ የላብ መጥረጊያው ሳይሆን እንደማይቀር ይገመታል፡፡

▣ "*ልብስ*" ይህ የግሉ ልብስ ቢሆንም እግዚአብሔር በዚህ ልብስ ተጠቅሞ ፈውስ ያከናውን ነበር ይህ የእግዚአብሔርን ርህራሄ ያሳያል፡፡

▣ "*ክፉ መናፍስት ይወጡ ነበር*" የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከቱ (*ሉቃ* 10፡17 *ሐዋ* 8፡2) *አጋንንት ተብለዋል*፤ *ማቴ* 12፡45፣ *ሉቃ* 7፡21 *እርኩስ መናፍስት ተብለዋል*፤ *ነገር ግን ሉቃስ ያልነፁ መናፍስት በሚል ስያሜ* ተጠቅሟል (*ሐዋ* 5፡16፣8፡7) በሐዋ 16፡16 *አጋንንት የሚርተኝነት መንፈስ ተብለዋል*፡፡ ጳውሎስ (በኤፌ 1፡21፣ ኤፌ 3፡10፣ ኤፌ 6፡12) የተናገረውን እንመልከት፣ በመፅሐፍ ቅዱስ ስለ ሁሉም ዝርዝር ማስረጃ አናገኝም፡፡ ነገር ግን በኢየሱስ ሃይል በአጋንንት ላይ የበላይ መሆኑን፣ በዝርዝር ተፅፎልናል፡፡ የኢየሱስ ስም ከስሞት በላይ በመሆን ድነትን፣ ሰላምን፣ ተሃድሶን እና ጤንነትን እንደሚሰጥ ተገልፆል፡፡

19፡13-16 "*አጋንንት ያውጡ... አይሁድ*" በአይሁድ መሃከል የተለመደ መንፈሳዊ ልምምድ ነበር፡፡ (*ሉቃ* 11፡19) በዚህ ክፍል ያሉት አይሁድ በሚርት መንፈስ ሳይሆን በኢየሱስ ስም አጋንንት ያውጡ ነበር፡፡ የሚከተለውን መፅሐፍ በማንበብ ዝርዝር ማስረጃ ያገኛሉ፡፡ (Josephus Jewish exorcism rite in Antiq 8.2.5 by one eleazar)

19፡13 "*ክፉዎች መናፍስት*" የዲያቢሎስ ሰራተኞች የሚያመለክት ነው፡፡ በአዲስ ኪዳን ስለክፉ መናፍስት ተፅፎ እናገኛለን፡፡ ነገር ግን በዝርዝር ስለ ቅድመ ክፉ ስራቸው አልተፃፈም፡፡ አጋንንትን ማስወጣት የሚል ስጦታ በአዲስ ኪዳን የለም ነገር ግን አስፈላጊ ነው፡፡ የሚከተሉትን መፅሐፍት በማንበብ ተጨማሪ ዕውቀት ማግኘት ይቻላል፡፡

1. *Christian Counseling and the Occult* by kouch
2. *Biblical Demonology and Demons in the World Today* by unger.
3. *Principalities and Powers* by montgomety
4. *Christ and the powers* by hendrik Berkh of and
5. Crucial *Questions about spiritual warfare* by clinfom E. mold

19፡14 "*ለካህናት አለቃ ለሆነ አስቄዋ*" የዚህ ሰው ስም በሌሎች ፅሑፎች ውስጥ አልተጠቀሰም፡፡ በአይሁድ ሀይማኖት የካህናት አለቃ ሆኖ በኤፌሶን መኖር ያልተለመደ ነበር፡ ምክንያቱም ቤተመቅደሱ የሚገኘው በኢየሩሳሌም በመሆኑ ነው፡፡

አስቄዋ የሊቀ ካህናቱ የስጋ ዘመድ ወይም በዳዊት ከተሾሙት ሃያ አራቱ ካህናት መሃከል የሚመደብ ሳይሆን እንደማይቀር ይገመታል፡፡ (1ዜና 24፡7-19)

አስቄዋ እና ልጆቹ ካህናቶች ናቸው። ነገር ግን የያህዌን ስም በመጥራት የሠይጣኑን ሃይል መቋቋም አቅቷቸው ይታያል።

19:15 **"ኢየሱስንስ አውቀዋለሁ፣ ጳውሎስንም አውቀዋለሁ"** የመጀመሪያው ሐሳብ (ጊኒዮስክ) የሁተኛው ደግሞ (ኢፒስታሚያ) እነዚህ ሁለቱ በመጠኑ ተመሳሳይ ናቸው ነገር ግን በዚህ ዓምድ ውስጥ የመጀመሪያው አጋንንት ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን የማወቀ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ጳውሎስ የእርሱ አገልጋይ መሆኑን ጠንቅቆ የማወቅ ነው።

19:17 ሉቃስ የእርኩስ መንፈሱ ኢየሱስን እንዴት አድርጎ እንዳከበረው ፅፏል።

19:18 **"አምነውም ከነበሩት"** በዚህ ሐረግ ውስጥ እነዚህ ሰዎች ያመኑት ኢየሱስን (ወንጌል) ወይስ ሌላ የጣኦት ስራን? በእርግጥ አዳዲስ አማኞች በቀድሞ ክፉ ልምምዳቸው ተፅኖ ሊደርስባቸው ይችላል።

አጋንንትን የሚያወጡ የነበሩ አይሁድ (ቁ. 13-16) በዚህ ምንባብ የሆነውን በመመልከት የኢየሱስ ስም ከስሞች በላይ መሆኑን ያረጋገጡበት ነው። ይህም የወንጌል የመጀመሪያው መልእክት ነው።

▣ **"እየተናዘዙ እና እየተናገሩ"** በጥንት የሚዲትራኒያን ሃገሮች ጣኦትን ማምለክ የተለመደ ነበር። በመሆኑም ይህ የጣኦት አምልኮ የእያንዳንዱን ሰው ስኬት መለኪያ ነበር። ነገር ግን በዚህ ምንባብ ወንጌል የሁሉ የበላይ መሆኑ የተገለፀበት ቦታ ነው። (ቁ. 20)

**ልዩ ርዕስ፡ መናዘዝ**

ሀ. መናዘዝ ለሚለው የግሪኩ ስርወ ቃል ከሁለት ቃላት የተሰራ ነው። ‹‹ሆሞሎጆ እና ኤክሶሞሎጆ›› ሆሞ የሚለው አንድ አይነት ሲሆን ሎጂ ደግሞ መናጋር እና ኤክሶ የሚለው ደግሞ መውጣት የሚል ፍቺ ይሰጣል። ስለዚህ የቃሉ ፍቺ አንድ አይነት ነገር ወይም መስማማት በተጨማሪም ኤክሶ ደግሞ በሰው ፊት መናገርን ያጠቃልላል።

ለ. በእንግሊዘኛው ተመሳሳዮቹን ፍቺዎች እንመልከት
1. ማመስገን
2. መስማማት
3. ማወጅ
4. መናገር
5. መናዘዝ

ሐ. ቃሉ በሁለት ተቃራኒ አጠቃቀም ሊኖረው ይችላል።
1. ማመስገን (እግዚአብሔርን)
2. ሐጢያትን ማመን

መ. በአዲስ ኪዳን መናዘዝ ማለት፡-
1. መሃላ ማድረግ (ማቴ 14:7፣ሐዋ 7:17)
2. መስማማት (ዮሐ 1:20፣ ሉቃ 22:6 ሐዋ24:14፣ ዕብ 11:19)
3. ማመስገን (ማቴ 11:25፣ ሉቃ10:21፣ሮሜ 14:11፣ 15:9)
   ቃሉ የሚያመለክተው፡-

19.19 **"አስማተኞች"** ሐዋ 8:9 ይመልከቱ።

መፅሐፊ (ባአይቡለስ) እርግማንን እና መሃላ የተፃፈበት ትልቅ መፅሐፍ ወይም አነስተኛ ጥቅልል መፅሐፍ ሊሆን ይችላል። የመፅሐፉም ዋጋ ታላቅ ነበር። ከዚህ የምንረዳው፡- (1) እነዚህ ሰዎች በጥልቀት በአስማትና በጥንቆላ ስራ ውስጥ እንደሆኑ ይናገራል፣ (2) ወንጌል ነፃ አውጪ መሆኑን ያስገነዝበናል።

▣ **"በሰው ሁሉ ፊት አቃጠሉት"** እነዚህን ውድ መፅሐፍ በሰው ሁሉ ፊት በእሳት ማቃጠላቸው የሚያሳየው ንስሃ መግባታቸውን እና ክርስቶስን ማመናቸውን የሚያረጋግጥ ነው።

19:20 የወንጌል መልእክተ አሸናፊ ነው። የሉቃስ የማጠቃለያ ሃሳብ የሐዋርያት ስራ መፅሐፍን ለስድስት እንዲከፈል ያደርገዋል። (ሐዋ 6:7፣ ሐዋ 9:31፣ ሐዋ12:24፣ ሐዋ 16:5፣ ሐዋ 19:20፣ ሐዋ 28:31)

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 19:21-22**

**ይህም በተፈፀመ ጊዜ ጳውሎስ ወደዚያ ደርሴ ሮሜን ደግሞ አይ ዘንድ ይገባኛል ብሎ በመቄዶንያና በአካዲያ አልፎ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሄድ በመንፈስ አሰበ። ከሚያገለግሉትም ሁለቱን ጢሞቴዎስንና ኤርሰጠንን ወደ መቄዶንያ ልኮ ራሱ በእስያ ጥቂት ቀን ቆየ።**

19:21
NASB **"ጳውሎስ በመንፈስ አለመ"**

NKJV "ጳውሎስ በመንፈስ አለመ"
NRSV "ጳውሎስ በመንፈስ መፍትሄውን አሰበ"
TEV, NJB "ጳውሎስ አእምሮውን ቀና አደረገው"
TEV (footnote) "ጳውሎስ በመንፈስ ተመርቶ ወሰነ"

ይህ የሚያመለክተው የእግዚብሔርን ሉዓላዊነት እና የሰውን ነፃነት ነው፡፡ በዚህ ምንባብ የሚገኘው መንፈስ የሚያመለክተው፡-

1. መንፈስ ቅዱስን ወይም
2. የሰው መንፈስን ሊሆን ይችላል፡፡ (ሐዋ 7፡59፣ ሐዋ 17፡16፣ ሐዋ18፡25 ሮሜ 1፡9፣8፡16፣ 1ቆሮ 2፡11፡5፡4፣16፡18፣2ቆሮ 2፡11 ገላ6፡18)

በዚህም ምንባብ ያለው መንፈስ ቅዱስ ከሆነ የመለኮተ መሪነትን በመንፈስ ምላሽ ጋር ያለውን ቁርጠኝነት በግልፅ መመልከት ይቻላል፡፡

ሉቃስ የጳውሎስን እያንዳንዱን ታሪክ ፅፏል፡፡ ጳውሎስ በመንፈስ በመመራት ከአገር አገር መዞርን ጭምር ተረድቶ ፅፏል፡፡

▣ "ሬሜን ደግሞ አይ ዘንድ" ጳውሎስ በሮም የምትገኘውን ቤተክርስቲያን መጐብኘት ተመኝቷል፡፡ (ሮሜ 1፡10፣ ሐዋ 9፡15) ጳውሎስ የሮሜ ክርስቲያኖች እንዲያውቁት እና የገንዘብ ስጦታ ሊያበረክትላቸው ፈልጓል፡፡

19፡22 "ኤርስጦንን" በሮሜ 16፡23 ውስጥ ተመሳሳይ ስም ተጠቅሷል፡፡ ይህ ሰው የቆሮንቶስ አገር ባለሃብት ይባል ነበር፡፡ በ2ጢሞ 4፡20 ስሙ ተጠቅሷል ነገር ግን ተመሳሳዩ ሰው መሆኑን አልተረጋገጠም፡፡

▣ "በእስያ እጥፍ ቀን ቆዩ" ወንጌል የብዙ ሰዎችን ልብ እየለወጠ እየተስፋፋ የነበረበት አውራጃ ነበር፡፡ (1ቆሮ 16፡9)

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 19፡23-27**

**በዚያም ጊዜ ስለዚህ መንገድ ብዙ ሁከት ሆነ፡፡ ብር ሠራ የሆነ ድሜጥሮስ የሚሉት አንድ ሰው የአርጤስን ቤተ መቅደስ ምስሎች በብር እየሠራ ለአንጥረኞች እጅግ ትርፉ ያገኝ ነበርና፡፡ እነዚህንም የሚመስለውን ስራ የሠሩትን ሰብስቦ እንዲህ አላቸው፡፡ ሰዎች ሆይ ትርፋችን በዚህ ስራ እንደ ሆነ ታውቃላችሁ ይህም ጳውሎስ በእጅ የተሰሩት አማልእክት አይደሉም ብሎ በኤፌሶን ብቻ ሳይሆን ከጥቂት ክፍል በቀር በእስያ ሁሉ ብዙ ህዝብን እንደ አስረዳና እንደ አሳተ አይታችኃል፡፡ ሰምታችሁማል፡፡ ስራችንም እንዲናቅ ብቻ አይደለም እስያ ሁሉ ዓለሙም የሚያመልካት የታላቂቱ አምላክ የአርጤምስ መቅደስ ምናምን ሆኖ እንዲቀጠር እንጂ ታላቅነትዋም ደግሞ እንዳይሻር ያስፈራል፡፡**

19፡23 "መንገድ" ለክርስቲያኖች የተሰጠ ስያሜ ነበር፡፡ ይህ የብሉይ ኪዳን ሐሳብ ነው (መዝ 1፡1.6፣5፡8፣25፡4.8.9.12) የእምነት መገለጫ ነው (ሐዋ 9፡2፣ ሐዋ19፡9.23፣ ሐዋ 18፡25-26)፡፡

19፡24 "ብር ሠሪ" ከብር የተሰሩ ምስሎችን (1) የአርጢምስ መቅደስ ምስል ያለበት ነበር (2) የሴት መልክ ከብዙ ጡቶች ጋር የተሳለ ነበር፡፡ የቅሪት አካል ተመራማሪዎች በርካታ ከብር የተሰሩ ቅርፃ ቅርፃችን አግኝተዋል፡፡ በእርግጥ የአርጤምስ መቅደስ ምስል ያለበትን ሊያገኙ አልቻሉም፡፡

▣ "ይህን የሚመስል ስራ" (ሐዋ 25.27) የስደቱን አይነት ያጢኑ፡፡

▣ "አንጥረኞች" የእንግሊዘኛው ተመሳሳዩ ፍቺ "ቴክኒሻን" ነው፡፡ በሜዲትራኒያን ሃገሮች ከእነዚህ ሰራተኞች ጋር ባልንጀርነት መፍጠር ታዋቂ ያደርጋል፡፡ ጳውሎስ ይህን ከሚሰሩ መሃከል በመሆን ድንኳን ይሰፋ ነበር፡፡

19፡26-27 ጳውሎስ በእስያ የነበረውን መጠነ ሰፊ አገልግሎቱን የሚያበራራ ምንባብ ነው፡፡

▣ "በእጅ የተሰሩ አማልክት አይደሉም" የብሉይ ኪዳኑን ህግ ያስታውሰናል (ዘዳ 4፡28፣ መዝ 115፡4-8፣ 135፡15-18፤ኢሳ 44፡9-17፡ ኤር 10፡3-11)፡፡

19፡27 ስለ አርጢምስ የሚናገሩ በርካታ ፅሑፎች በመጀመሪያው ምዕተ አመት ተፅፈዋል፡፡ በሚድትራኒያን አገሮች መሃከል ሰላሳ ዘጠኝ የሚያክሉት ከተሞች በዚህች የአርጤምስ አምልኮ ተይዘው ነበር፡፡

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 19፡28-41**

**ይህንም በሰሙ ጊዜ ቁጣ ሞላባቸው የኤፌሶን አርጤምስ ታላቅ ናት እያሉም ጮኹ ከተማውም በሙሉ ተደባለ የመቄዶንያም ሰዎች የጳውሎስን ጓደኞች ጋዲዮስንና አርስጥከሰን ከእነርሱ ጋር ነጥቀው በአንድ ልብ ሆነው ወደ ጨዋታ ስፍራ ሮጡ፡፡ ጳውሎስም ወደ ህዝቡ ይገባ ዘንድ በፈቀደ ጊዜ ደቀ-መዛሙርት ከለከሉት፡፡ ከእስያም አለቆች ወዳጆቹ የሆኑተ አንዳንዶቹ የሆኑት አንዳንዶች ደግሞ ወደ እርሱ ይጮኹ ነበር፡፡ በጉባአው ድብልቅልቅ ሆኖ የሚበልጡት እንከን ስለምን እንደተሰበሰቡ አላወቁም ነበርና፡፡ አይሁድም ሲያቀርቡት እስክንድሮስን ከህዝቡ**

መካከል ወደ ፊት ገፋት እስክንድሮስን በእጁ ጠቅሶ በህዝብ ፊት እንደምዋገትላቸው ወደደ፡፡ አይሁዳዊ ግን እንደ ሆነ ባወቁ ጊዜ ሁሉ በአንድ ድምፅ የኤፌሶን አርጤምስ ታላቅ ናት እያሉ ሁለት ሰዓት ያህል ጮኹ፡፡ የከተማይቱም ፀሐፊ ህዝቡን ፀጥ አሰኝቶ እንዲህ አለ፡፡ የኤፌሶን ሰዎች ሆይ የኤፌሶን ከተማ ለታላቂቱ አርጤምስ ከሰማይም ለወረደው ጣኦትዋ የመቅደስ ጠባቂ መሆንዋን ከተማ ለታላቂቱ አርጤምስ ከሰማይም ለወረደው ጣኦትዋ የመቅደስ ጠባቂ መሆንዋን የሚያውቀ ሰው ማን ነው ይህንም የሚክደው ከሌለ ፀጥ እንድትሉና አንዳች በችኩላ እንዳታደርጉ ይገባል፡፡ የመቅደስን ዕቃ ያልሰረቁ አምላካችንንም ያልሰደቡ እነዚህ ሰዎች አምጥታችኃቸዋልና፡፡ ድሜጥሮስና ከእነርሱ ጋር ያሉት አንጥረኞች ግን በሰው ላይ ነገር እንዳላቸው የመጋቢያ ቀንና አገረ ገዢዎች አሉ፡፡ እርስ በርሳቸው ይምዋገቱ ስለ ሌላ ነገር እንደ ሆነ ግን አንዳች ብትፈልጉ በተደነገገው ጉባኤ ይፈታል፡፡ ዛሬ ስለ ተደረገው ሁከት ነው፡ ሲሉ እንዳይከሱን ያስፈራልና ስለዚህም ስብሰባ ምላሽ መስጠት አንችልም ምክንያት የለምና ይህንም ብሎ ጉባኤውን ፈታው፡፡

19፡28 ይህ ጥቅስ የሚያስገነዝበን በጥንት ዘመን ሰዎች ከሃይማኖት እና ከብዙ መንፈሳዊ ልምምዶች ጋር የተቆራኘ ልምምድ እንደነበራቸው ነው፡፡ ይህም የጣኦት አምልኮ ነው፡፡

▣ **"የኤፌሶን አርጤምስ ታላቅ ናት"** ይህ በረከትን የሚያዛ አምላክ ይባላል፡፡ እርሱም ታላቅ ይባላል፤ የቤተ መቅደሱ መፋክር ሊሆንም ይችላል፡፡

19፡29 **"ወደ ጨዋታ ሰፍራ ሮጠ"** ይህ የቲያትር አይነት አሁንም በሮም ይካሄዳል፡ ከሃያ አምስት እስከ ሃምሳ ስድስት ሺ ሰዎች ጨዋታውን ለመመልከት ይገኙ ነበር፡፡

▣ **"በአንድ ልብ"** የሐዋርታ ስራ መፅሐፍ የአማኞችን ህብረት እና በአንድነት መስማማት ለመግለፅ ይህንን ቃል ይጠቀማል፡፡ (ሐዋ1፡14፣ ሐዋ 2፡1.46፣ሐዋ 4፡25) ሰዎች በክምፎ አንድ ሊሆኑ ይችላሉ (ሐዋ 7፡57፣ ሐዋ 12፡20፣ ሐዋ 18፡12)፡፡

▣ **"ጋዲዮስ"** የደርቤ አገር ሰው ነበር፡፡ (ሐዋ20፡4) እንግዲህ በዚህ ስያሜ የሚጠሩ በርካታ ሰዎች ስለነበሩ የትኛው ጋዮስ መሆኑ ለመለየተ አስቸጋሪ ነው (1ቆሮ 1፡14፡3 3ዮሐ 3)፡፡

▣ **"አርስጥሮኮስ"** የተሰሎንቄ አገር ሰው ነበር (ሐዋ 20፡4፣27፡2 ቆላ 4፡10-11፣ ፊሊ 2፡4)፡፡

19፡30 **"ደቀ-መዝሙርት ከለከሉት"** ጳውሎስ አማኞች በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ለመታዘዝ ቅን ልብ ያለው ሰው ነበር፡፡

19፡31 **"ከእስያ አለቆች አንዳንዶች"** እነዚህ የአንድ አካባቢ የመንግስት ባለስልጣን ናቸው፡፡ ነገር ግን በዚህ ስያሜ የተለያዩ ባለስልጣናት የሚጠሩበትም ማዕረግ ነበር፡፡ ከእነዚህ መከል አማኝ ሆነው የጳውሎስ ባልንጀሮችም ነበሩበት፡፡ ሉቃስ ማንፀባረቅ የፈለገው በዚህ ደረጃ ለሚገኙ ባለስልጣናት ክርስትና አስፈሪ እምነት ያለመሆኑን ነው፡፡ ቤተክርስቲያን በተደጋጋሚ ከአይሁድ ጋር ግጭት ስትፈጥር ነገር ግን ከመንግስት ጋር ሰላም ነበረች፡፡

19፡32 **"ጉባኤው"** ቃሉን የሚተካው የግሪኩ (ኤክሊሺያ) ይህ ቃል የቤተክርስቲያን ስብሰባ ለመግለፅ የሚጠቅም ቃል ነው (ሐዋ 19፡32.39 እና 41)፡፡

የጥንቲቱ ቤተክርስቲያን *ኤክሌሺያ* የሚለውን ቃል ትጠራበታለች፡፡ ስያሜውም የመጣው ከብሉይ ኪዳን ከህዝበ እስራኤል ነው፡፡

▣ **"ስለምን እንደተሰበሰቡ አላወቁም ነበር"** የሰዎች ከፍተኛ ቁጥር መሰባሰብ ያመላክታል፡፡

19፡33 **"እስክንድሮስ"** አይሁዶች ራሳቸውን ከክርስትና ለማግለል የሚያደርጉት ተንኮል እራሳቸውን ይጐዳ እንደነበር፡ ይህ ቁጥር በማንበብ መረዳት ይቻላል፡፡ ስም በመፅሐፍ ቅዱስ ተጠቅሶ እናገሃለን ነገር ግን አንዱን ከአንዱ ለይቶ ለማወቀ አስቸጋሪ ነው፡፡ (2ጢሞ 4፡14፣ጢሞ 1፡20)

▣ **"በእጁ ጠቅሶ"** በአይሁድ ባህል ፀጥ ለማሰኘትና በንግግር ለማድረግ የሚደረግ የእጅ ምልክት ነው፡፡

▣ **"መሟገት"** የእንግሊዘኛው ቃል (አፖሎጂ) ይህም ቃል ከግሪኩ ሲገኝ ትርጉሙሙ ህጋዊ ሙግት ማድረግ ማለት ነው፡፡ (ሉቃ12፡11፣21፡14፣ሐዋ19፡32፣ሐዋ 24፡10 ሐዋ25፡8) እና (ሐዋ 22፡1 ፤ና 25፡16)

19፡34 ይህን ሐሳብ በሁለት መንዶች መረዳት ይቻላል፡ (1) የግሪክ ሮማን ዓለም ፊፅሞ መቃወምን ያሳያል፣ (2) ህዝቡ የጳውሎስን አገልግሎት መቃወሙን ያመለክታል፡፡

19.35 **"የከተማይቱ ፀሐፊ"** በታወቀው መቅደስ ውስጥ የህዝብ ዋና አስተባባሪ የነበረ ሰው ነው፡፡ ይህ ቃል የአይሁድ ፀሐፊዎች ስያሜም ነበር፡፡ (ሐዋ4፡5 ሐዋ6፡12) የግብፅ መሪዎችንም የመላክታል (ዘፀ 5፡6፣ ዘዳ 20፡5)፡፡ "የኤፌሶን

ከተማ.... የመቅደስ ጠባቂ መሆንዋን" ጠባቂ የሚለው ቃል ፍቺው (የመቅደስ ጠራጊ) ነው። እነዚህ በመቅደስ ዝቅተኛውን ስራ የሚሰሩ ሰራተኞች ነበሩ።

▣ **"ከሰማይ ለወረደው ጣኦትዋ"** የሴት መልክ ከብዙ ጡቶች ጋር አርጤምስ ትመሰል ነበር። ይህ የበረከት ወቅት፣ የብዜት ጣኦተ ለመባል አይነተኛ መገለጫዋ ነበር። ሰማይ የሚወክለው ዙስ የተባለው ጣኦት ነው።

**19፡37** የህዝቡ አመፅ መሠረት የሌለው በመሆኑ ባለስልጣናቱ ስብሰባውን መበተን ችለዋል።

**19፡38-39 "እርስ በእርሳቸውም ይምዋገቱ"** በአግባቡ ሙግታቸውን እንዳያደርጉ የተፈቀደላቸው ይመስላል።

**19፡38 "አገረ ገዢዎች"** ሁለት አይነት የሮማ ግዛቶች ነበሩ። የመጀመሪያው በነገስታቱ የሚመራ ሲሆን ሁለተኛው በሴኔት የሚመራ ግዛት ነው። (Augusths, acts of settlement, 27 B.C) የሮማ አውራጃዎች የሚመሩት፡-

1. በገዢዎች የሚመራ የህግ አውጪ አካል
2. ንጉሳዊ አገዛዝ እና የጦሩ መሪ
3. የአውራጃ አነስተኛ ስልጣን ያላቸው መሪዎች
4. በሽማግሌዎች የሚመራ አመራረ ነገር ግን በሮማውያን ቁጥጥር የማደረግበት
5. የጉረቤት አገሮች ሆነው ለአንድ አካባቢ በተሾሙ መሪዎች የሚገዛ።

የኤፌሶን ከተማ የምትመራው በሴኔት እና በአገረ ገዢዎች ነበር። አገረገዢዎቹ ሦስት ጊዜ ተጠቅሰዋል፡-

1. ሰርግዮስ ጳውሎስ (ሐዋ 13፡7-8.12)
2. ጋልዮስም በአካይያ (ሐዋ 18፡12)
3. ስሙ ያልተጠቀሰው ሰው (ሐዋ 19138)

**19፡39-41**

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ለመርዳት ነው የተሰናዱት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋነኞቹን ጉዳዮች ለማጤን እንዲረዳ ነው። ሐሳብ ለማጫር እንጂ መደምደሚያ አይደሉም።

1. ሐዋ 19፡2-6 ያለው ዓውድ እንዴት ይተረጉማል
   ሀ. የአማኞችን ዳግም ጥምቀተ ያሳያል?
   ለ. እጆችን በመጫን በልሳን የመናገር ስጦታ ያገኛልን?
2. የትንቢት ስጦታን አብራራ (ቁ.6)
3. ጳውሎስ ከአጵሎስ እና ከአስራ ሁለቱ የዮሐንስ ደቀመዛሙርት ጋር የገጠመውን ችግር መፃፍ ለምን አስፈለገ
4. በሐዋ 19፡11-12 ያለው በጳውሎስ ጨርቅ የተደረገው ተዓምራት በእኛም ዘመን በተመሳሳይ መልክ ይሰራል? ወይስ ለምን አይሰራም?
5. አጋንንትን ማስወጣት ከመንፈሳዊ ፀጋ ስጦታዎች ዝርዝር ውስጥ ለምን አልተፃፈም?
6. ለአማኞች በዚህ ርዕስ ጉዳይ ዝርዝር መግለጫ መፅሐፍ ቅዱስ ለምን አልሰጠም?
7. በሐዋ 19፡17 ላይ የሚገኘው ተዓምራት ዓላማው ምን ነበር?

# የሐዋርያት ስራ 20

## የምንባቡ ክፍፍል በአዲሶቹ ትርጉሞ

| የተየመቅሰ[4] | አኪጆት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የጳውሎስ ጉዞ ወደ መቄንያ | ጉዞ ወደ ግሪክ | የመጨረሻው ጉብኝት ወደ ግሪክ | ወደ መቄዶንያ ጉዞ | ጳውሎስ ኤፌሶንን ተወ |
| 20፡1-6 | 20፡1-6 | 20፡1-6 | 20፡1-6 | 20፡1-6 |
| የጳውሎስ ጉዞ ጢሮአዳ | አገልግሎት በጢሮአዳ | ጳውሎስ ወደ ፍልስጥኤም ተመለሰ | ጳውሎስ በጢሮአዳ የመጨረሻ ጉብኝት | በጢሮአዳ የሞተ ወደ ሰው አስነሳ |
| 20፡7-12 | 20፡7-12 | 20፡7-12 | 20፡7-12 | 20፡7፡-12 |
| ገዞ ከጢሮአዳ ወደ መሳጢያ | ከጢሮአዳ ወደ መሳጢያ | | ከጢሮአዳ ወደ መሳጢያ | ከጢሮአዳ ወደ መሳጢያ |
| 20፡13-16 | 20፡13-16 | 20፡13-16 | 20፡13-16 | 20፡13-16 |
| ጳውሎስ ከኤፌሶን መሪዎች ጋር ተነጋገረ | የኤፈሶን መሪዎች ምክር | | የጳውሎስ የመሰናበቻ ለኤፌሶን መሪዎች | የመሰናበቻ ሰላምታ ለኤፈሶን |
| 20፡17-24 | 20፡17-38 | 20፡17-18 | 26 ፡17-24 | 20፡17-18 |
| | | 20፡18b-24 | | 20፡18b-21 |
| | | | 20፡22-24 | |
| 20፡25-35 | | 20፡25-35 | 20፡25-31 | 20፡25-27 |
| | | | | 20፡28 |
| | | | | 20፡28-32 |
| | | | 20፡32-35 | |
| | 20፡33-35 | | | |
| 20፡36-38 | | 20፡36-38 | 20፡36-38 | 20፡36-36 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (ከ **"መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ" ገጽ** vii)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. ምንባብ አንድ

2. ምንባብ ሁለት

2. ምንባብ ሦስት

3. ወ.ዘ.ተ

**የአውዱ ዕይታ ከቁጥር 1-6**

*ሀ. የጳውሎስ ሦስተኛው የሚሲዮናዊነት ጉዞውን በመጠኑ በተብራራ መልክ የማጠቃለያ የተሰጠበት ምዕራፍ ነው፡፡*

*ለ. የጳውሎስን አገልግሎት ለመረዳት 1 እና 2 ቆሮንቶስን ማንበብ ተገቢ ነው፡፡*

*ሐ. ፀሐፊው ሉቃስ ጊዜ በመውስድ ጳውሎስ ያደረጋቸውን ክንዋኔዎች የሄደበትን ቦታ ሰዎች እና እንዲሁም ሌሎች ዝርዝሮችን ፅፏል፡፡*

**የቃል እና የጥምር ቃል ጥናት**

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 20፡1-6**
**ሁከቱም ከቀረ በኃላ ጳውሎስ ደቀ መዛሙርቱን አስመጥቶ መከራቸው ተሰንብቶአቸውም ወደ መቄድኒያ ይሄድ ዘንድ መጣ፡፡ ያንም አገር እያለፈ በብዙ ቃል ከመከራቸው በኃላ ወደ ግሪክ አገር መጣ በዚያም ሶስት ወር ተቀምጦ ወድ ሶሪያ በመርከብ ሊሄድ ባሰበ ጊዜ አይሁድ ሴራ ካላደረጉበት በመቄዶንያ አልፎ ይመለስ ዘንድ ቆረጠ፡፡ የሸኙትም የቤርያው ሱሲዳፐሮስ ከተሰሎንቄ ሰዎችም ቲኪቆስ ፕሮልሞስም ነበሩ፡፡ እነዚህም ወደ ፊታችን አልፊው በጢሮአዳ ቆዩን እኛ ግን ከቂጣ በዓል ቀን በኃላ በፊሊጵስቶስ በመርከብ ተነስተን በአምስት ቀን ወደ ጢሮአዳ ወደ እነርሱ ደርሰንና በዚያ ሰባት ቀን ተቀመጥን፡፡**

20፡1 "*ሁከትም ከቀረ በኃላ*" *ሐረጉ ያልተለመደ ንግግር የሚንፀባርቅበት ነው፡፡ ጳውሎስ በኤፌሶን ሁከት ስለተነሳ ከተማይቱን ጥሎ አልወጣም ነገር ግን ወንጌልን ለመስበክ እንደሄደ በአንደበቱ ተናግሯል፡፡* (ሐዋ 19፡20)

▣ "*ጳውሎስ ደቀ መዛሙርቱን አስመጥቶ መከራቸው*" *ጳውሎስ ወንጌልን መስበክ ብቻ ሳይሆን ደቀ መዛሙርትን በማፍራት ላይ ያተኮረ አገልግሎት ነበረው፡፡* (ቁ 2; *ማቴ* 28፡18-20) *የምኩራብ አገልግሎት በሚኖርበት ቦታ ሁሉ ወንጌልን መስበክ የተለመደ እየሆነ መጣ* (1 *ቆሮ* 12፡7)፡፡

20፡2 "*ያንም አገር እያለፈ*" *ይህ የሚያመለክተው*፡(1) *እልዋሪቆንን እና* (*ሮሜ* 15፡19)፣ (2) *ከፊሊጵሲዮስ ከተሞች ከሆኑት የሜቄዶንያ አገርን ለማመልከት ነው፡፡*

▣ "*ወደ ግሪክ መጡ*" *ግሪክ* (*ሄላስ*) *የሮማውያን አውራጃ የሆነችው አካያይ ነች፡፡* (*ሐዋ* 19፡21) *ብዙ ጊዜ ይህ የቆሮንቶስ ከተማን ለማመልከት ነው፡፡ የጳውሎስ የአገልግሎት አቅጣጫ እዚህም መድረሱን እንገነዘባለን በመሆኑም ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሲጨነቅ እናነባለን* (*ቆሮ* 16፡5-9 *እና* 2 *ቆሮ* 2፡12) *እንግዲህ በዚህ ጊዜ ጳውሎስ የሮሜን መልእክ መፃፍን ይነገራል፡፡*

20፡3 *የጳውሎስን የጉዞ ዕቅድ ያሳያል በዚህ ወቅት በመርከብ መሄድ አደጋ ስለሚያስከትል እቅዱን በመቀየር በእግር ለመሄድ የቆረጠበት ጊዜ ነው፡፡*

▣ "*አርስጥሮ ኮስ የደርቤኑም፣ጋይዮስ፣ፕሮልምስ፣ቲኪቆስ፣ፕሮፊም*" *ጳውሎስ የገንዘብ ስጦታ ከአብያተ ክርስቲያናት የተባበሩት ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡* (*ቆሮ* 16፡1-3,2 *ቆ* 8-9) *የእነዚህ ዝርዝር ስሞች በሚከተለው የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል አንብቡ* (*ሮማ* 16፡2 *ሐዋ* 19፡29;27 *እና ቆላ* 4፡10, *ኤፌ* 6፡21-22;*ቆላ* 4፡7-8;2 *ጢሞ* & ፡12 *እና ቲቶ* 3፡12; *ሐዋ* 19፡29; *እና* 2 *ጢሞ* 4፡20)፡፡ *የሚከተለው ፅሑፍ ከቆሮንቶስ የማመስካሪያ መፅሐፍ የተወሰደ ነው፡፡*

*የእነዚህ ስብስብ በግዜው ለነበረው የገንዘብ ማሰባሰብ ፕሮግራም አገለገሉ እንጂ ከህዝቡ በቀጣይነት ቀረጥን ለማሰባሰብ የተሾመ ሰዎች አይደሉም፡፡* (Moulton, milligan, The *vocabulary of the Greek Testament* p.377) *ይህ የገንዘብ ስጦታ በተደጋጋሚ የተደረገ ይሁን ወይም ከህዝቡ በግብር መልክ ይሰበሰብ በዓውዱ ውስጥ የተብራራ አይደለም፡፡ ጳውሎስ ከጴጥሮስ፣ከያዕቆብ፣ከዮሐንስ እና ከበርናባስ ጋር በዚህ ጉዳይ ከተስማማ በኃላ በይሁዳ ለነበሩት ድሆች ገንዘብ መርዳቱን ቀጥሎ ነበር፡፡* (*ሐዋ* 11፡27-30) *ይህ ስጦታ በአዲስ ኪዳን መፅሐፍ በብዙ ቦታ ተጠቅሶ እናገኛለን* (*ሮሜ* 15፡26;2 *ቆሮ* 8-9;1 *ቆሮ* 16፡1) *ይህ ስጦታ በአይሁድ እናት ቤተክርስቲያን እና በአህዛብ አብያ ክርስቲያናት መሃከል ያለውን ግንኙነት የሚያጠናክር ነበር፡፡ በዚህም አህዛቦች ወደ አይሁድ ህብረት ለመምጣት መንገድን የጠረገም ነበር፡፡*
*ጳውሎስ ይህንን የአንድ ጊዜ የገንዘብ እርዳታ በተለያየ ስያሜ ሰቶታል፡፡*
1. *ምዕዋት ሐዋ* 24፡17

2. ህብረት ሮሜ 15፡26,27;2ቆሮ 8፡4; 9፡13
3. ከዕዳ ነፃ መሆን ሮሜ 15፡27
4. አገልግሎት ሮሜ 15፡27;2 ቆሮ 9፡12

በ2 ቆሮ 8፡6፣16 እንደንመለከተው ትቶ የቤተክርስቲያን ተወካይ መሆኑን ነው፡፡ ነገር ግን ሉቃስ በሐዋርት ስራ የዚህን ሰው ስም አልጠቀሰም ምናልባት ወንድሙ ስለሆነ ስሙን አልጠቀሰውም ይሆናል፤፡ በ2 ቆሮ 8፡16 ስሙ ያልተጠቀሰው ወንድም ሊሆን ይችላል (Eusebius his, Eccl 6, 25, 6; A.T Roberson's *Word Pictures in the New Testament*, P .245)፡፡

F.F Bruce, Paul *Apostle of the Heart Set Free*, comments on titus and being brothers.
"ፀሐፊው ሉቃስ ቲቶን ያለመጥቀሱ ወንድሙ መሆኑን ያሳያል" "W.M. Ramsay, st *Paul theTtraveler and the Romas ncitizen* (London, 1895), P. 390 *Luke the Physician and Other Studies* (London 1908), PP 17) ሉቃስ በ2 ቆሮ 8፡18 የተጠቀሰው ሰው ነው፡፡

20፡5 **"እኛ"** ሉቃስ የአይን እማኝ እራሱ እንደሆነ ለማመልከት ቃሉን ተጠቅሞበታል (ሐዋ 16; 10-17; 20፡5-15; 21፡1-18 እና 27፡1-28)፡፡

20፡6 **"የቂጣ በዓል"** በሚያዝ መካከል ከሰባቱ የበዓል ቀናት የቂጣ በዓል ሲሆን ከነዚህ አንዱ ቀን ደግሞ የፋሲካ በዓል ነው፡፡ (ዘፀ 13) ጳውሎስ የአይሁድ የቀን አቆጣጠር ተፅኖ እንዳሳደረበት እንመለከታለን፡፡ በፊሊጲሲዮስ ስለነበሩ አይሁድና ምኩራብ በዝርዝር የምናውቀው ነገር የለም ነገር ግን ጳውሎስ ይህን የቂጣ በዓል መናገሩ ለእነዚህ ሰዎች እና ለወንጌል ከሚያደርገው አላማ ጋር የሚሄድ አይደለም (1 ቆሮ 9፡19) የሚደረገውን ስርዓት ለመተረክ ሊሆን ይችላል፡፡

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡** 20፡7-12
**ከሳምንቱም በመጀመሪያ ቀን እንጀራ ለመቁረስ ተሰብስበን ሳለን ጳውሎስ በነገው ሊሄድ ስላሰበ ከእነርሱ ጋር ይነጋገር ነበር፡፡ እስከ መንፈቅ ለሊትም ነገሩን አስረዘመ ተሰብሰበንም በነበረበት ሰገነት እጅግ መብራት ነበር፡፡ አውጤኪስ የሚሉትም አንድ ጎበዝ በመስኮት ተቀምጦ ታላቅ እንቅልፍ አንቀላፍቶ ነበር ጳውሎስም ነገርን ባስረዘመ ጊዜ እንቅልፍ ከብዶት ከሦስተኛው ደርብ ወደ ታች ወደቀ ሞቶም አነሱት፡፡ ጳውሎስም ወርዶ በላዩ ወደቀ ብዙ አቅፎም ነፍሱ አለችበትና አትንጫጩ አለችው ወቶም እንጀራ ቆርሶ በላ ብዙ ጊዜ እስኪነጋ ድረስ ተነጋገረ እንዲህም ሂዶ ብላቴናውንም ደህና ሆኖ ወስዱት እጅግም ተፅናኑ፡፡**

20፡7 **"በሳምንቱም** *መጀመሪያ ማዕድን ስንቆርስ ሳለን"* ይህ የሚያስገነዝበት የጭንቀቱ ቤተ ክርስቲያን በየሰንበቱ በማዕድ ቅዱሳን ህብረታቸው እንዲያጠነክሩ ታደርግ ነበር፡፡ (ቁ.11) እና ማዕድ የሚለው በአዲስ ኪዳን የጌታን እራትም ያመለክታል ከሙታን ከተነሳ በኃላ ኢየሱስ የመጨረሻው እራት ከደቀመዛሙርቱ ጋር በመብላት ለስርዓቱ ያለውን አክብሮት አሳይቷል፡፡ ዮሐ 20፡19 ሉቃ 24፡36 1 ቆሮ 16፡2)

(*The acts of the Apostles* by Newman and Nida p 384) በዚህ መፅሐፍ ላይ ሉቃስ የአይሁድን ሰንበት እርሱም ቅዳሜ ምሽትን ለመጥቀስ ነው፡፡ (TEV) በሐዋርያት ስራ መፅሐፍ ላይ ብቻ ይህ ሐረግ ተፅፎ እናገኛለን፡፡ ጳውሎስ በሳምንቱ የመጀመሪያው ቀን የሚለው እሁድን ነው (1 ቆሮ 6፡2)

▣ **"ስብከቱን ባስረዘም ጊዜ"** ጳውሎስ ሰዎችን ለመረዳት የሚይታክት ሰው በመሆኑ ባለመድከም ረጅም ሰዓት እንደሚያስተምር ያሳያል ፡፡

20፡8 **"እጅግ መብራት ነበር"** የተቀመጡበት ቤት በብርሃን የተሞላ፣ ሞቃት፣ የታፈነ እና በጭስ የተሞላ አየር በመኖሩ አውጢኪስ የተባለው ጎበዝ በእንቅልፍ ከደርብ ላይ ሊወድቅ ችሏል፡፡

20፡9 **"አንድ ጎበዝ"** ወጣትነት ለመግለፅ የሚያገለግል ቃል በቁ. 12 ላይ በተለየ ሁኔታ ተፅፏል፡፡ ይህም በዕድሜ ህፃን ልጅ የሆነን ሰው ይጠቁማል፡፡

▣ **"አውጤኪስ የሚሉትም አንድ ጎበዝ በመስኮት ተቀምጦ ታላቅ እንቅልፍ አንቀላፍቶ ነበር ጳውሎስም ነገርን ባስረዘመ ጊዜ"** በዚህ ምንባብ የሚገኙት አድማጮእ ከጳውሎስ ረጅም ስብከት የተነሣ መተኛታቸውን አመላካች ምሳሌ ነው፡፡

▣ **"ሞቶም አነሡት"** ይህ ወጣት ሰው በእንቅልፍ ምክንያት ከደረብ ላይ ወድቆ ህይወቱ ማለፍን የሚገልፅ ቃል ነው፡፡ (ሐዋ 20፡12)

20፡10 **"ጳውሎስም ከላይ ወደቀ"** ጳውሎስ በብሉይ ኪዳን እንደነበሩት እንደ ነብዩ ኤልያስ እና ኤልሳዕ በተመሳሳይ መንገድ የሞተውን አስነስቷል (1 ነገሰ 17፡21,2 ነገ 4፡34) ጳውሎስ በተፈጠረው ሁኔታ ሳይደናገጥ አይቀርም ፤ ቢሆንም ስዎቹ እንዳይረበሹ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረጉን ያመለክታል፡፡

▣ **"አትንጫጩ አላቸው"** ጳውሎስ ድርጊቱን የማስቆም የውሳኔ ንግግር ማድረጉን ያሳያል፡፡

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 20፡13-16**
**እኛ ግን ጳውሎስን እንቀባለው ዘንድ ስላለን እንቀበለው ዘንድ ስላለን ወደ መርከብ ቀድመን ሄድንና ወደ አሶን ተነሳን እርሱ በመሬት ይሄድ ዘንድ ስላሰበ እንደዚህ አዞ ነበርና በአሶንም ባገኝን ጊዜ ተቀብለነው ወደ ሚጢሊን መጣን በማግስቱ ከዚያ በባህር ተነስተነን በኪዮ ፊት ለፊት ደርሰን በነገውም ወደ ሰሞን ተሻገርን በትወጊሊዮን አድርገን በማግስት ወደ ሚሊጢን መጣን በማግስቱም ጳውሎስ በእስያ እጅግ እንዳይቀመጥ ኤፌስንን ይተው ዘንድ ቆረጠ ነበርና ቢቻለውም በባለዓምሳን በኢየሩሳሌም ይውል ዘንድ ይቸኩል ነበር፡፡**

20፡13 **"መርከብ"** ጳውሎስ የአይሁድን ሴራና ተንኮል በመረዳት የባህር ጉዞውን በመቀየር ከጢሮአዳ መርከብ አግኝቶ ወደ አሶን ለመምጣት ተገዷል (ቁ.4)

20፡14 **"ሚጢሊን መጣን"** የሊስቦስ ዋና ከተማ ነች፡፡ ከቱርክ በስተምዕራብ ከሚገኙት ከትንሽ እስያ ደሲቶች ትልቋ ነች፡፡

20፡15-16 ሉቃስ የባህርን ጉዞ ጠንቅቆ የሚያቅ መሆኑን ያሳያል በሐዋርያት ስራ መፅሐፍ በርካታ ቦታ ላይ መርከበኞች የሚጠቀሙበትን ቋንቋ ይጠቀማል:: ይህ ሰው የተማረ በመሆኑ ለራሱም ጉዳዩ የመርከብ ጉዞ ያደርግ ነበር፡፡

20፡15 **"ኪዮ"** ከኤጀርያ ባህር ደሴቶች አንዷ ደሴት ነች በባህሩ ላይ በጣም ቀጭን በሆነ የመሬት አቀማመጥ የምትገኝ ነች፡፡

▣ **"ሳሞን"** በምዕራብ ትንሹ እስያ የምትገኝ ደሴት ናት፡፡

▣ **"ሚሊጢን"** በኤፌሶን በደቡብ የባህር ዳርቻ የሚትገኝ ከተማ ነበረ:: ጳውሎስ በዚህ አርፎ የኤፌሶንን ሽማግሎዎች አስጠርቷቸዋል፡፡ጳውሎስ ኤፌሶንን ይተው ዘንድ ቁርጦ ነበር: (1) ጳውሎስ በመርከቡ ጉዞ ላይ የተቆጣጣሪነት ምልክቶች ይታይበት ነበርጳውሎስ መርከቡን ተከራይቶት ሊሆን ይችላል፣ (2) ወይም ጳውሎስ በኤፌስን መርከቡ እንዳይቆም ተናግሮ ሊሆን ይችላል፡፡

20፡16 **"ጳውሎስ ኤፌሶን አልፎ መሄድ ወስኖ ነበር"** ይህ የሚያመለክተው ጳውሎስ በመርከቦቹ ላይ የመወሰን ስልጣን እንደነበረው ነው፡፡ ይህ እንዲህ ከሆነ 1ኛ ወይ ለራሳቸው መርከብ ተከራይተው ሊሆን ይችላል፡፡ ወይም 2ኛ ኤፌሶን ላይ መቆም የማይችል መርከብ ተሳፍረዋል፡፡

▣ **"ቢቻላቸውም"** ምኞትን ለመግለፅ ያገለገለ ቃል ነው፡፡

▣ **"ጴንጤቆስጤ"** ይህ ፋሲካ ካለፈ በኋላ የሚከበር የአይሁድ በዓል ነው፡፡ ጳውሎስ በቁጥር 3 ላይ ባለው ምክንያት ፋሲካን አላከበረም፡፡

**የዓውዱ ዕይታ ሐዋ 20፡17-21፡16**

ሀ. ይህ ምዕራፍ የጳውሎስን ዝርዝርና ውስብስ በሚቄዶንያና በግሪክ የነበረውን ሦስተኛውን የሚሲዮናዊነት ተልዕኮውን ይገልፃል፡፡

ለ. በተጠቀሱት አገሮች የጳውሎስን አገልግሎት ዝርዝር ለመረዳት 1 ቆሮን እና 2 ቆሮን ማንበብ ጠቃሚ ነው፡፡

ሐ. ፀሐፊው ሉቃስ የጳውሎስን እያንዳንዱ እንቅስቃሴውን ለመዘገብ የጊዜ፣ የቦታ ስሞችን በመጥቀስ የታሪክ ቅደም ተከተሎችን ለመጠበቅ ከፍተኛ ጥረት አድርጋል፡፡

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 20፡17-18a**
**[17]ከሚሊጢንም ወደ ኤፌስን ልክ የቤተ ክርስቲያንን ሽማግሌዎች አስጠራቸው፡፡ [18]ወደ እርሱም በመጡ ጊዜ እንዲህ አላቸው፡፡**

20፡17 **"ሚሊጢ"** ይህቺ ደሴት 30 ከ/ሜ ያህል ከደቡባዊ ኤፌሶን ትርቅ ነበር፡፡

▣ **"ሽማግሌዎች"** 'ፐሬሲቡተሮስ' ከሚለው ቃል 'ፐረስቢተር' ወይም 'ፐረስፐተሪያን' የሚለውን እናገኛለን፡፡ ምክንያቱም በሐዋ 20፡17,18 እና በቲቶ 1፡5,7 ሽማግል (ፐሮስፐተር) እና "ኤጲስቆዶስ" የሚለው ተመሳሳይ ነው፡፡ መጋቢ (ፐአይሞን ኤፌ 4፡11) ላይ ካለው ጋር 'ሽማግሌ' የሚለው ቃል የአይሁድ ታሪካዊ ዳራ አለበት፡፡ (የአይሁድ

ነገዶችን መሪዎችን ያሳያል)። እንዲሁም "ኤጲስቆዶስ" ወይም 'መጋቢ' የሚለው ደግሞ የግሪክ ፖለቲከኞች ወይም አስተዳደር ታሪካዊ ዳራ አለው።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሁለት ቡድኖች ብቻ ናቸው በአጥቢያ ደረጃ የተነገረባቸው። መጋቢ እና ዲያቆናት (በፊሊ 1:1) ምናልባትም ሦስት ቡድኖች ተጠቅሰዋል በ1ጢሞ 3 ላይ። የመበለቶችን እና የዲያቆናትንም ጭምር በጻፈው ላይ (ሮሜ 16:1)። ማስተዋል ያለብህ ነገር እነዚህ ነገሮች በብዙ ቁጥር ነው የተጠቀሱት ይህም ምናልባት የቤተክርስቲያናት መሪዎችን ሊያመለክት ይችላል (11:30፣ 14:23፣ 15:2,4፣6፣22-23፣ 16:4፣ 21:18 1ጢሞ 5:17፣ ቲቶ 1:5፣ ያዕ 5:14፣ 1ጴጥ 5:1)።

▣ "ቤተክርስቲያን" የግሪኩ ቃል (እክሌሺያ) በአንድ ከተማ ውስጥ የሚደረገውኝ ጉባኤ ያመለክታል (19:39)። የሁን እንጂ በብሉይ ኪዳን የነበሩት የእስራኤልን ጉባኤ መሰባሰብም ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል። የቀደመችው በ/ክን የክርስቶስ አካል የሆኑትን አዲሱን የአማኞችን ጉባኤ ለመግለጽ ተጠቅመውበታል በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከነበሩት ከእግዚአብሔር ሕዝቦች ጋር በማነጻጸር። የአዲስ ኪዳን ቤ/ክን የብሉይ ኪዳን ተስፋ የተፈፀመባቸው አድርገው ራሳቸውን ይቆጥራሉ። ምክንያቱም የናዝሬቱ ኢየሱስ እውነተኛው መሲህ በመሆኑ ነው። ልዩ ርዕስ 5:11 ላይ ያለውን ተመልከት።

> አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 20:18b-24
>
> *ወደ እስያ ከገባሁበት ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ በትህትና ሁሉና በእንባ ከአይሁድ ሴራ በደረሰብኝ ፈተና ለጌታ እየተገዛው ዘመኑን ሁሉ ከእናንተ ጋር እንዴት እንደኖርሁ እናንተው ታውቃላችሁ። [19]ከአስማተኞችም ብዙዎቹ መጽሐፋቸውን ሰብስበው በሰው ሁሉ ፊት አቃጠሉት፤ ዋጋውም ቢታሰብ አምሳ ሺህ ብር ሆኖ ተገኘ። [20]እንዲህም የጌታ ቃል በኃይል ያድግና ያሸንፍ ነበር። [21]ይህም በተፈጸመ ጊዜ ጳውሎስ ወደዚያ ደርሼ ሮሜን ደግሞ አይ ዘንድ ይገባኛል ብሎ በመቄዶንያና በአካይያ አልፎ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሄድ በመንፈስ አሰበ። [22] ከሚያገለግሉትም ሁለቱን ጢሞቴዎስንና ኤርስጦንን ወደ መቄዶንያ ልኮ ራሱ በእስያ ጥቂት ቀን ቆየ። [23]በዚያም ጊዜ ስለዚህ መንገድ ብዙ ሁከት ሆነ። [24]ብር ሠሪ የሆነ ድሜጥሮስ የሚሉት አንድ ሰው የአርጤምስን ቤተ መቅደስ ምስሎች በብር እየሠራ ለአንጥረኞች እጅግ ትርፍ ያገኝ ነበርና፤*

20:18 "ዘመኑን ሁሉ ከእናንተ ጋር" ጳውሎስ ከክርስቶስ ጋር የጠበቀ ሕብረት እንደነበረው የሚያሳይ እና በእርሱ ዘመን አገልጋዮች ይወቀሱ እንደነበረም የሚያመለክት ሃሳብ ነው።

20:19 "ለጌታ እየተገዛው" ክርስቲያኖች መፈፀም ከሚገባቻ አንዱ ጉዳይ ነው። (ኤፌ 4:2-3) በግሪኩ ፅሐፍ ላይ ባይገኝም ነገር ግን መገዛት የክርስቲያን ስነ ምግባር መሆን አለበት መገዛት የትህትና ምልክት ነው። ሙሴ እና ኢየሱስ በዚህ ተመስግነዋል (ዘኋ 12:3; ማቴ11:29) የጳውሎስ ፅሑፍ በዚህ ቃል የታጀበ ነበር (ኤፌ 4:2;ፊሊ 2:3;ቆላ 2:18,23;3:12)

▣ "በእንባ ከአይሁድም ሴራ" ጳውሎስ በስጋው እና በስነልቦናው የከፈለውን ዋጋ በዝርዝር እየተናገረ ነው። (2 ቆ 4:7-12; 6:3-10; 11:24-28) ይህ የከፈለው ዋጋ ለአገልግሎት የከፈለው ዋጋ ነው።

▣ "ከአይሁድ ሴራ" በሐዋርያት ስራ መፅሐፍ በስፋት የዚህን አይነት ተመሳሳይ ተንከለክ መመልከት እንችላን:: (ሐዋ.9:24;ሐዋ13:45,50:ሐዋ 14:2,4,5,19;ሐዋ17:5,13 ሐዋ 18:12 ሐዋ 20:3;21:27;30 ሐዋ 24 5-9)

20:20 "አላስቀረሁባችሁም" መርከብ በውሃ ስትሰጥም የሚያመለክት ቃል ነው (ሐዋ 20:27)።

▣ "ከሚጠቅማችሁ ነገር አንዳች" ጳውሎስ ወንጌልን በተመለከተ የሚያውቀውን ሁሉ አስተምራቸዋል። እርሱም እንዴት መቀበል፣መኖር፣መከላከል እና ማደግ እንደሚቻል በዝርዝር አስተምሯቸዋል።

▣ "በጉባኤም በየቤታችሁም አወራሁላችሁና አስተማርኳችሁ" ጳውሎስ የአደባባይ ሰባኪ ብቻ ሳይሆን በግለሰቦች ቤትም የሚሰበሰቡትን ሰዎች ያገለግል እንደነበር ግልፅ መረጃ ነው። እነዚህ የኤፌስን ሽማግሌዎች ጳውሎስ እንደደከመላቸው ተገንዝበዋል።

ጳውሎስ በዚህ ከተማ ባልተገለፁ ሳዎች ጥቃት እንደደረሰበት ከንግግሩ ይታወቃል።

20:21 "ለአይሁድና ለግሪክ ሰዎች እየመሰከረሁ" ለሁለቱም አካላት መልእክቱ አንድ ነው:: ነገር ግን አቀራረቡ የተለያየ ሊሆን ይችላል (በሐዋ መፅሐፍ እንደምንመለከተው) ጳውሎስ ለአይሁድ ህዝብ ወንጌልን መስበክ ቅድሚያ ሰቶ ነበር (ሮሜ 1:16;1 ቆሮ 1:18;24)።

▣ "ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ንስሃንና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን" በግሪኩ ንስሃ "የሃሳብ ለውጥ" ሲሆን በዕብራይስጡ የድርጊት ለውጥ ማለት ነው። ለድነት ሁለት መሰረታዊ ነገሮችን ማድረግ ተገቢ ነው። የመጀመሪያው ከሃጢያት ክፍ ስራ መመለስ ሲሆን ሁለተኛ ኢየሱስ ክርስቶስን ማመን ነው (ማርቆ 1:5;ሐዋ 3:16,19) በአዲስ ኪዳን የሰው ድርሻ እንዳለ መዘንጋት የለብንም እነርሱም ንስሃ፣እምነት፣አሁንም፣ንስሃ፣እምነት፣መታዘዝ እና መታገስ አስፈላጊ ነገሮች ናቸው።

በአንዳንድ የግሪክ ፅሑፎች ላይ ክርስቶስ የሚለው ስያሜ ባይጠቀስም ነገር ግን በዓውዱ ላይ የትርጉም ልዩነት አይፈጥርም፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ፀሐፊዎቹ ዐረፍተ ነገሩን በአጭር ለማድረግ ቃላቶችን ላለመድገም የሚደረግ አፃፃፍ መሆኑ እርግጥ ነው፡፡

20፡22
NASB "ታስሬ በመንፈስ"
NKSV "በመንፈስ ታስሬ"
NRSV "በመንፈስ ምርኮኛ ሆኜ"
TEV "በመንፈስ ታዝዤ"
NJB "በመንፈስ ምርኮኛ ሆኜ"

ይህ የሚያመለክተው ጳውሎስ መለኮታዊ መሪነት እንደተሰማው ያሳያል (18፡21፣ 19፡21፣ 20፡23፣ 1ቆሮ 4፡19፣ 7፡40፣ 16፡7)፡፡ በ19፡21 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት፡፡ መንፈስ ቅዱስ በቁጥር 23 ላይ ተጠቅሶአል፡፡

20፡23 **"ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ እስራትና መከራ ይቆይሃል ብሎ በየከተማው ሁሉ ይመሰክርልኛል"** ይህ የተነገረው በተለያዩ ነቢያት ሊሆን ይችላል፡፡ (ሐዋ 9፡16;21፡4,10-12) የነበያቱ ንግግር አሉታዊ ቢሆንም የእግዚአብሔር ለጳውሎስ ያለው አላማው የሚፈፀምበት መንገድ ነው፡፡ (ኢሳ 55-፡-8-11) ጳውሎስ በምንም መከራ የሚበገር ያለሆነበት ምክንያት የእግዚአብሔርን አላማ ጠንቅቆ በማወቁ ነው፡፡

20፡24 **"ነፍሴን በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እንደ ከንቱ ነገር እቁጥራለሁ"** የሰው ልጅ በሃጢያት ከወደቀ ጀምሮ ከሚያስበው ተቃራኒ ንግግር ጳውሎስ ሲናገር ይታያል:: ይህ የሚያሳየው የክርስትና ዕምነት ከሌለው የተለየ የሚያደርገው ራስን ማኖር እና መሞት የሚል መርህ ያለው ነው፡፡ ለሃጢያት ሞተን ለእግዚአብሔር ህያው እንድንሆን የእግዘአብሔር ቃል ያዘናል (ሮማ 6፡2 ቆሮ 5፡14-15፡ገላ 2፡20 1ዮሐ 3፡16)

▣ **"ሩጫውን ጨርሻለሁ"** ለእስፓርት ውድድር የሚያገለግል ቋንቋ ነው ጳውሎስ የአትሌቲክስ ቋንቋዎችን መጠቀም ይወዳል የራሱን የህይወት ጉዞ በሯጮች ይመስላል፡፡ (1 ቆሮ 9፡24-27;ገላ 2፡2;5፡7 ፊሊ 2፡16;3፡14 2 ጢሞ 2፡5;4፡7) ጳውሎስ እግዚአብሔር ለእርሱ ያለውን አላማ ጠንቅቆ የተገነዘበ ሰው ነው፡፡

▣ **"ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልኩትን አገልግሎት"** ጳውሎስ ይህንን አገልግሎቱን የተቀበለው በደማስቆ ነበር፡፡ (ሐዋ 9) አማኞች ሁሉ ከጌታ የተቀበሉት አገልግሎት አላቸው (ኤፌ 4፡11-12)

ይህንን ጠንቅቀን ካወቅን ሁላችን በወንጌል ስራ ላይ መሆናችንን እንገነዘባለን፡፡ 12 ቆሮ 5፡18-20) የዳንበት አላማ ሌሎችን ለማዳን መሆኑን ልናውቅ ይገባል፡፡

▣ **"የእግዚአብሔር ፀጋ ወንጌልን ለመመስከር"** በሐጢያት የወደቀው የሰው ዘር ተስፋ የሚያደርገው የማይለወጠውን የእግዚአብሔርን ፀጋ ብቻ ነው፡፡ ተስፋችን በእርሱ እና እርሱ ለእኛ በሰራው ስራ ብቻ ነው፡፡

ፀሐፊው ሉቃስ ወንጌል የሚለውን ቃል በግስ መልክ በሁለቱም መፅሐፎቹ ውስጥ በብዛት ተጠቅምአል ነገር ግን በስም መልክ ሐዋርያት ስራ ውስጥ ሁለት ጊዜ ብቻ ተጠቅሞ እናገኛለን፡፡ (ሐዋ 15፡17,20፡24)

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 20፡25-35**

***አሁንም እነሆ እኔ የእግዘአብሄርን መንግስት እየሰበክሁ በመካከላችሁ የዘርሁ ሁላችሁ ከእንግድህ ፊቴን እንዳታዩም አውቃለሁ፡፡ ስለዚህ እኔ ከሰው ሁሉነ ደም ነፃ እንደሆንሁ ዛሬ በዚህ ቀን እመሰክርላችኃለሁ፡፡ የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ ነግሬአችኃለሁና ምንም አላስቀረሁባችሁም በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቃት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባጽ ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ ከሄድሁ በኃላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች እንደገቡባችሁ ደቀ-መዛሙርትንም ወደ ኃላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሱ እኔ አውቃለሁ፡፡ ስለዚህ ሦስት ዓመት ሌሊት እና ቀን በእንባ እያንዳንዳችሁን ከመገሰፅ እንዳላቋረጥሁ እያሳባችሁ ትጉ አሁንም ለእግዚአብሔር እና ያንፃችሁ ዘንድ በቅዱሳንም ሁሉ መካከል ርስትን ይሰጣችሁ ዘንድ ለሚችለው ለፀጋ አደራ ሰጥቻችኃለሁ፡፡ ከማንም ብር ወይም ወርቅ ወይም ልብስ አልተመኘሁም እነዚህ እጆቼ በሚያስፈልገኝ ነገር ለእኔና ከእኔ ጋር ላሉት እንዳገለገሉ እናንተ ታውቃላችሁ፡፡ እንዲሁም እየደከማችሁ ድውዮችን ልትረዱና እርሱ ራሱ ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁህ ነው እንዳለ የጌታን የኢየሱን ቃል ልታስቡ ይገባችሁ ዘንድ በሁሉ አሳየኃችሁ፡፡***

20፡25 **"ከእንግዲህ ወዲህ ፊቴን እንዳታዩ አውቃለሁ"** ጳውሎስ ወደ እስፔን ለመሄድ አቅዷል፡፡ ነገር ግን ይህ ንግግር በኢየሩሳሌም ስለሚገኘው እስራት እና ሞት ያመለከተበት ንግግሩ ነው፡፡ በመጋቢያን ደብዳቤዎች ውስጥ ስለአራተኛው የጳውሎስ የሚሲዮናዊነት ጉዞው ዘግበው ቢሆን ኖሮ የሚከተሉትን ከተሞች ይጠቅሱ ነበር፡-

1. ኤፌሶን 1 ጢሞ 1፡3;14;4፡13
2. ሚሊጢን 2 ጢሞ 4፡20
3. ጢሮስ 2 ጢሞ 4፡13

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለወደፊቱ የሚሆነውን ሳያውቅ እግዚአብሔርን በማመን የተደገፈ ሕይወት በመምራት ያገለግል ነበር፡፡ እርሱ ራሱ ወደ እስፔን ለመሄድ ቢያቅድም ነገር ግን በኢየሩሳሌም እስራት እና ሞት እንደሚገጥመው በዓውድ ውስጥ በግልፅ ይታያል፡፡

▣ **“የእግዚአብሔር መንግስት”** ሐዋ 2፡34 ይመልከቱ ፡፡

**20፡26 “ከሳው ሁሉ ደም ንፁህ ነኝ”** በሐዋ 18፡6 እንደሚገኘው ሐረግ በተመሳሳይ መልክ የተፃፈ የአይሁድ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፡፡ (ህዝ 3፡16 እና 33፡1) ጳውሎስ ወንጌልን በታማኝነት ማገልገሉን የተናገረበት ዐረፍተ ነገር ነው፡፡ (1 ቆሮ 2፡17) በመሆኑም ለወንጌሉ አምንታዊ እና አሉታዊ ምላሽ በሚሰጡት ላይ ሽክሙ ይሆናል (2 ቆሮ 2፡15-16)፡፡

**20፡27 “ምንም አላስቀሁባችሁም”** ሐዋ 20፡20 ይመልከቱ፡፡

▣ **“የእግዚአብሔር ምክር”** የእግዚአብሔርን ፈቃድ መስበክ እንጂ የራሳችንን ፍላጎትና ምኞት መናገር ተገቢ አይሆንም፡፡ ይህ የአይሁዳውያን ሃይማኖት ዋና መገለገያ ሐረግ ነው እንዲሁን በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ አማኞች ሁሉ የሚያምኑበት ዐረፍተ ነገር ነው፡፡ (2 ቆሮ 12 የእግዚአብሔር ዓላማ የሰው ዘር ሁሉ ወደ ቀደመው የእግዚአብሔር ሃሳብ እርሱም ህብረት ወደ ሚያደርግበት፣ህልውናው ወዳለበት እንደመጣ ነው፡፡

**20፡28 “ለራሳቸው ተጠንቀቁ”** የአሁን ጊዜ ትዕዛዝ ያለበት አመልካት ሐረግ ነው፡፡ ተመሳሳዩን ተመልከቱ (1 ቆሮ 16፡13,ቆላ 4፡2;1 ተሰሎ 5፡6,10) ክርስቲያኖች የስጋ እና መንፈሳዊ ህይወት እንዳላቸው ማጤን ተገቢ ነው፡፡ እግዚአብሔር ለሰው ዓላማ ቢኖረውም ሰው ግን ሃላፊነቱን መወጣት ያስፈልገዋል፡፡ ይህ ማለት ለመንፈሳዊ ህይወታችን ጥንቃቄ ማድረግ አለብን፡፡ (1 ቆሮ 3)

▣ **“ለመንጋው”** የእግዚአብሔርን ህዝብ የሚያመለክት ነው፡፡ (መዝ 23;ሉቃ 12፡32;ዮሐ 21፡15-17) መጋቢ የሚለው ቃል የተገኘው ከዚህ ሃረግ ነው፡፡ (ሐዋ 20፡17) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለራሳቸው፣ለእግዚአብሔር እና ለመንጋው መጠንቀቅ ይገባቸዋል፡፡ (1 ቆሮ 3)

▣ **“መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመበት”** በቤተ ክርስቲያን በአመራር ላይ ሰዎችን መንፈስ ቅዱስ እንደሚሾም የተገለፀበት ግልፅ ምንባብ ነው፡፡

▣ **“ጳጳሳት”** ሐዋ 20፡17 ይመልከቱ፡፡

▣ **“የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን”** በጥንቱ የግሪክ ፅሑፍ P[74] A,C,D እና E እግዚአብሔር ሲሆን ነገር ግን በዕብራይስጡ N እነ B ላይ “ጌታ” የሚል ተጠቅሷል፡፡ ጳውሎስ ሁል ጊዜ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን የሚለውን ሐረግ ይጠቅማል እንጂ የጌታ ቤተክርስቲያን አይልም ነገር ግን ቀጣዩ ቁጥር በገዛ ደሙ በማለት የጌታ ቤተክርስቲያን የሚለው ሐረግ የዐረፍተ ነገሩን ፈሰት የሚጠብቅለት መሆኑን ያሳያል:: እንዲህ አይነቱ ስህተት የፀሐፊዎች በጥንቃቄ አለመፃፍ መሆኑን ያሳያል፡፡ በመሆኑም ለንባብ አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡

ይህ ንባብ ፀሐፊዎች ለራሳቸው የስነ መለኮት ትንትና ያመቻቸው ዘንድ ፅሑፎችን፣ቃሎችን ይቀይሩ እንደነበር አመለካች ምሳሌ ነው፡፡ (D.Ehrman’s ‘The *Orthodox Corruption of Scripture*, pp,87-89) ይህ የሚያሳየው ፀሐፊዎቹ በጊዜያቸው የነበረውን የስህተት ትምህርቶች ለመቃወም የሚፅፋትን በዚያ መልክ ይቃኙት እንደነበር ያሳያል (ሐዋ 20፡28)፡፡

ማንኛውም ሰው ሃሳብ ከመስጠቱ በፊት እያንዳንዱ የአዲስ ኪዳን መፅሽፍት አውዶቻቸውን የባህል ነፀብራቅ እንዳለባቸው መዘንጋት የለብንም፡፡ በተጨማሪም ከዚህ የተነሣ የአንዳንድ ቃላትን ትርጉም በትክክል ሳንረዳ እንችላለን ነገር ግን የመፅሽፍ ቅዱሳን አላማ አንስተውም (*RethInkling New Testament Textual Criticism* ed David Alan Black)፡፡

▣ **“በገዛ ደሙ የዋጃትን”** የብሉይ ኪዳንን የመስዋት ስርዓት ሚያስታውስ ነው፡፡ (ዘሌዋ 1-7; ኢሳ 2፡53)፡፡ ምናልባትም የኢየሱስን አምላክነተ ለመግለጽ ጠንካራ መረጃ ሊሆን የሚችል ነው፡፡ ጳውሎስ በተደጋጋቢ የሽንን እውነት ሊያሳይ የሚችል ሀረግን ይጠቀማል (ሮሜ 9፡5፣ ቆላ 2፡9፣ ቲቶ 2፡13)፡፡

በግሪኩ ፅሑፍ ውስጥ ይህንን **“በእርሱ በኩል”** የሚል አቻ ትርጉም እናገኛለን፡፡ (F.F Bruce, *Commentary on the Book of the Acts*, p 416፡59) ይህ የማመሰካሪያ መፅሐፍ ደግሞ “በእርሱ ደም በኩል” በማለት ተርጉሞታል፡፡

**20፡29 “ለመንጋው የማይራሩ ጨካኝ ተኩላዎች”** በእርኛ እና በመንጎች መሃከል የሚኖረውን ግንኙነት የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ የተጠቀሱት እረኞች ሃሰተኞች በመሆናቸው መንጋውን የሚያጎሳቁሉ ናቸው እነዚህም በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ እና ወጪ የሚኖሩ ሊሆኑ ይችላሉ (ቁ 29 እና 30) ይመልከቱ ሃሰተኞቹ የበግ ለምድ ይለብሳሉ (ማቴ 7፡15)፡፡ አማኞች ስለ እግዚአብሔር የሚናገሩ ሰዎችን መመርመር ይችላሉ (ዮሐ 4፡1)፡፡ ለወንጌል ባላቸው ታማኝነት ፈትኑአቸው በቃልና በስራ (ቁጥር 18-24፣ ሮም 16፡17-18)፡፡

**20፡30 “ጠማማ ነገርን የሚናገሩ”** ቀጥተኛ ትርጉም “ነገሩን የሚያጠማዝዙ” የሚል ፍቺ አለው በሰዎች መሃከል ያለውን ማዕበራዊ ኖሩ የሚመለከት ዐረፍተ ነገር ነው (ሉቃ የ 41; ፊሊ 2፡15)፡፡ ይህም ክንውን በሌላ ቦታ በተለየ ሁኔታ ተገልያአል በ2ጴጥ 3፡15-16፡፡

▣ **"ደቀ-መዛሙርትን ወደ ኃላቸ ይስቡ ዘንድ"** ወደ ኋላ የተመለሱት ደቀ-መዛሙርት ከጌታ ወደ ኃላ የሚመለሱ ናቸው ወይስ የተደነጋገሩ ለማለት ተፈልጎ ነው? (ማቴ 24፡24) እውነተኛ አማኝ በማንም የሽንገላ ቃል ወደ ኃላ መመለስ የለበትም (1ዮሐ 2፡18)፡፡

20፡31 **"ትጉ"** የአሁን ጊዜ አመልካች ቃል ሆኖ ትዕዛዝም ያለበት ነው፡፡ (ማርቆ 13፡35) ከ ቁጥር ሃያ ስምንት ጋር ተመሳሳይት አለው የቤተክርስቲያን መሪዎችና ቤተክርስቲያን በሐተኞች አስተማሪዎች ቤተክርስቲያን እንዳትጠቃ የነቁ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡

▣ **"ለሦስት ዓመታት"** ጳውሎስ ኤፌሶን ለሦስት አመታት በመቆየት የእግዚአብሔርን ስራ ሰርቷል ጳውሎስ ከሌሎቹ ከተሞች ይልቅ በዚህች ከተማ ቆይታ አድርጓል፡፡ በኤፌሶን የሚገኙ አማኞች ወንጌልን ጠንቅቀው የሚያውቁ ሆነዋል፡፡

20፡32 **"ለእግዚአብሔር አደራ"** (ሐዋ 14፡23) አማኞች ለተጠሩበት ወንጌል ታማኝ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ (1ጢሞ1፡18) በተጨማሪም ይህን የመዳን ወንጌል ለሌሎች የማስተላለፍ ግዴታ አለብን (2 ጢሞ 2፡2)

እግዚአብሔር የሚለው በ Mss, ℵ, A, C, D እና E ላይ ሲገኝ በዚህ ፈንታ ጌታ የሚለው በ MSB, USB[4], ላይ ተፅፎ ይገኛል፡፡

▣ **"ለፀጋ ቃል"** በዚኀ ምዕራፍ በቁጥር ሃያ አራት የሚገኘውን ተመልከቱ፡፡

▣ **"ያንፃችሁ ዘንድ"** ሰውን ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ሙላት የሚያደርሰው የወንጌል ትምህርት መሆኑን ያስገነዝበናል (ሐዋ 9፡31)፡፡ የግሪኩ ቃል "መገንባት" ወይም "ማነፅ" ይላል፡፡ (1 ቆሮ 14)፡፡ የወንጌል አለማ በግለሰቦች ዕድገት ላይ ያተኮረ ብቻ ሳይሆን በማዕበረሰብ አቀፍ የሆነም ነው፡፡

▣ **"ርስትን ይሰጣችሁ ዘንድ"** እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ለሌዋውያን እና ለካህናቱ ርስታቸው ነበር በአዲስ ኪዳን ደግሞ እግዚአብሔር ለአማኞች ሁሉ ርስታቸው ሆኖአል ምክንያቱም ሁሉም ልጆቹ ናቸውና (ሮሜ 8፡15, 17 ገላ 4፡1-7 ቆላ 1፡12)፡፡

▣ **"በቅዱሳን ሁሉ መካከል"** መንፃት የሚለውን ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርዕስ በሚለው ስር ተመልክቱ (ሐዋ 9፡32)

20፡33 **"ከማንም ብር ወይም ወርቅ ወይም ልብስ"** የባለጠግነት መለኪያ ቁሳቁሶች ናቸው በአዲስ ኪዳን ሃሰተኛ አስተማሪዎች ምልክታቸው ገንዘብን መውደዳቸው እና መስገብገባቸው ነው (1 ቆሮ 3፡10-17)፡፡

20፡34 **"ለእኔና ከእኔ ጋር ላሉ እንዳገለገሉ"** በሃሰተኛ አስተማሪዎች ጳውሎስ ይከሰስ ስለነበር ከቤተክርስቲያን የስጦታ ገንዘብን መቀበል አቁሞ ነበር፡፡ በዚህ ፈንታ ጳውሎስ ራሱን የእየረዳ ያገለገል ነበር፡፡ (1 ቆሮ 4፡12;9፡3-7;2 ቆሮ 11፡7-12;12፡13;1 ተሰሎ 2፡9;2 ተሰሎ 3፡6-19) ጳውሎስ በዚህ ጊዜ መምህራንን ሊያሰለጥን ነበር እርሱ ባይቀበልም ነበር ግን አገልጋዬች ገንዘብ እንዲከፈላቸው ያስተምር ነበር (1 ቆሮ 9፡3-18፡1 ጢሞ 5፡17)፡፡

ጳውሎስ ባደረጋቸው ሦስት ታላላቅ የሚሲዮናዊነት ጉዞው ራሱን እየረዳ አገልግሏል፡፡ (James J. Jeffers, *The Greco-Roman world of the New Testament* Era p28)

1. የመጀመሪያው ጉዞ 1 ቆሮ 4፡12; 9፡6; 1ተሰሎ 2፡9
2. ሁለተኛው ጉዞ ሐዋ 18፡3
3. ሦስተኛው ጉዞ ሐዋ 19፡11-12; 20፡34 2ቆሮ 12፡14

20፡35 የአማኞች ተግቶ መስራትና ባለጠጋ መሆን ለራስ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም እንደሆነ እንድናጤን የሚያደርግ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ነው፡፡ (2 ቆሮ 9፡8-11) ይህ ሃሳብ ጳውሎስ በኢየሱስ የሰማው አይደለም ምክንያቱም ይህ ሃሳብ በየተኞቹ የወንጌላዊት መፅሐፍት አናገኛቸውም፡፡ በመሆኑም በቤተክርስቲያን በአፈታሪክ የሚታወቅ መሆኑ ግልፅ ና፡፡

በዚህ ጥቅስ ውስጥ ደካማ የተባሉት አክራሪ ክርስቲያኖች ለማለት ተፈልጎ አይደለም 1 ሮማ 14፡1; 15፡1;1 ቆሮ 8፡9-13;9፡22) ነገር ግን በስጋ ድሆች የሆኑትን ለማመልከት ነው በመሆኑም ጳውሎስቸ ራሱ እና ሌሎች ክርስቲያኖች በመስራት እነዚህን እንደረዱ ማሳሰቢያ የተሰጠበት ምንባብ ነው፡፡

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 20፡36-38**
**ይህንንም ብሎ ከሁላቸው ጋር ተንበርክኮ ፀለየ ሁሉም እጅግ አለቀሱ ጳውሎስንም አንገቱን አቅፈው ይስሙት ነበር፡፡ ይልቁንም ከእንግዲህ ወዲያ ፊቴን አታዩትም ስላላቸው ነገር እጅግ አዘኑ እስከ መርከቡም ድረስ ሸኙት፡፡**

20፡36 **"ተንበርክኮ"** በአይሁድ ሃይማኖት የሃይማኖት ሰርዓት ውስጥ ተንበርክኮ መፀለይ የተለመደ አይደለም ይህ ምናልባት የተለየ መስጠትን ለማመልከት ይሆናል፡፡ (ቁ 32; 21፡5)

20፡37 **"ጳውሎስን አቅፈው"** የNKJV ትርጉም ይህን ቃል አንገቱ ላይ ተጠምጥመው" በማለት ፍቺ ይሰቶታል፡፡ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን በእንዲህ አይነት ሁኔታ የሚወዱ ሰዎች መኖራቸው እንድናመሰግን ያነሳሳናል፡፡

20፡38 “*ፊቴን አታዩትም ስላላቸው ነገር እጅግ አዘኑ*” *በዚሁ ምዕራፍ ቁጥር ሃያ አምስትን ይመልከቱ*።

***የውይይት ጥያቄዎች***

*ይህ የጥናት* *<u>መመሪያ</u>* *ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።*

*እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ለመርዳት ነው የተሰናዱት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋነኞቹን ጉዳዮች ለማጤን እንዲረዳ ነው። ሐሳብ ለማጫር እንጂ መደምደሚያ አይደሉም።*

1. *ጳውሎስ በሚሄድበት ከተማ ሁሉ ከብዙ ሰዎች ጋር ለምን ጉዞ ያደርጋል* (ቁ.4)?
2. *የሐዋ* 20፡7-10 *የስነመለኮት አላማ ምንድ ነው*?
3. *የዚህ ምዕራፍ ቁጥር* 13 *ለምን በቀላሉ መረዳት አልተቻለም*?
4. *ጳውሎስ የኤፌስንን የቤተክርስቲያን መሪዎች ሃሳብ ለምን አልተቀበለም*?
5. *ጳውሎስ በነብያቶች በኢየሩሳሌም ችግር እንደሚገጥመው እየተነገረው ለምን ለመሄድ ወሰነ*? (ቁ 22-23)
6. *ሐሰተኛ ነብያቶች በየዘመኑና በየቦታው ተመሳሳይ ችግሮች አሏቸው። ይህ ማለት ሃሳባቸውን ይቀባበላሉ ማለት ነው*? *ደግሞስ የሚከተሏቸው እነማን ናቸው*? *ሃሰተኛ ነብይ ማለት ምን ማለት ነው*?
7. *ለቤተክርስያናችን መሪዎች መፀለይ ለምን ይጠቅማል*? (ቁ 36-38)

# የሐዋርያት ስራ 21

## የምንባቡ ክፍፍል በአዲሶቹ ትርጉሞች

| የተየመቅሰ[4] | አኪጀት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የጳውሎስ ጉዞ ወደ ኢየሩሳሌም | መስጠንቀቂያ ወደ ኢየሩሳሌም ለሚሄደው | ጳውሎስ ወደ ፍልስጥኤም ተመለሰ<br><br>(20፡7-21፡4) | ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ | ወደ ኢየሩሳሌም የተደረ ጉዞ |
| 21፡1-6 | 21፡1-4 | 21፡1-6 | 21፡1-6 | 21፡1-6 |
| 21፡7-14 | | 21፡7-14 | 21፡7-14 | 21፡7-14 |
| | ጳውሎስ ሰላምን ፈለገ | ጳውሎስ አይሁድን አረጋገጠላቸው | 21፡12-13 | የጳውሎስ ኢየሩሳሌም መድረስ |
| 21፡15-16 | 21፡15-25 | 21፡15-16 | 21፡15-16 | 21፡15-16 |
| ጳውሎስ የዕቆብን ጎበኘው | | | ጳውሎስ ያዕቆብን ጎበኘው | |
| 21፡17-26 | በመቅደስ መታሰር | 21፡17-26 | 21፡17-25 | 21፡17-25 |
| | 21፡26-36 | | 21፡26 | 21፡26 |
| ጳውሎስ በመቅደስ ታሰረ | | የጳውሎስ እስራት እና የመከላከያ ሃሳብ<br><br>(21፡27-22፡29) | ጳውሎስ በመቅደስ ታሰረ | ጳውሎስ ታሰረ |
| 21፡27-36 | | 21፡27-36 | 21፡27-29 | 21፡27-29 |
| | | | 21፡27-36 | 21፡27-36 |
| ጳውሎስ ራሱን ተከላከለ | በኢየሩሳሌም ላለው ብጥብጥ ምላሽ ሰጠ | | ጳውሎስ ስለ ራሱን ተከላከለ | |
| 21፡37-22፡5 | (21፡37-22፡21) | 21፡37-40 | (21፡37-22፡5)<br>21፡37a | 21፡37-40 |
| | | | 21፡37b-38 | |
| | | | 21፡39 | |
| | | | 21፡40-22፡2 | |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (ከ "**መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ**" **ገጽ** vii)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. ምንባብ አንድ

2. ምንባብ ሁለት

3. ምንባብ ሦስት

4. ወ.ዘ.ተ

**የቃል እና የጥምር የቃል ጥናት**

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ: 21:1-6**
**ከእነርሱም ተለይተን ተነሣን በቀጥታም ሄደን ወደ ቆስ በነገው ወደ ሩድ ከዚያም ወደ ጳጥራ መጣን ወደ ፊንቂም የሚሸገር መረከብ አግኝተን ገባንና ተነሣን ቆጵሮስንም ባየናት ጊዜ በስተ ግራችን ተውናት ወደ ስርያም ሄደን ወደ ጢሮስ ደርሰን መርከቡ ሸክውን በዚያ የሚያርፈው ነበርና። ደቀ መዛሙርትን በያዘ ባገኘን ጊዜ ሰባት ቀን ተቀምጥን እነርሱም ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይወጣ በመንፈስ አሉ። ጊዜውንም በፈፀምን ጊዜ መጥተን ሄድን ሁላቸውም ከሚስቶቻቸውና ከልጆቻቸው ጋር እስከ ከተማው ውጭ ድረስ ሸኙን በባህሩም ዳር ተንበርክከን ፀለይን እርስ በእርሳችንም ተሰነባብተን ወደ መርከብ ወጣን ከዚያም ወደ ቤታቸው ተመለሱ።**

21:1 **"በቀጥታ ሄድን"** የባህር መርከበኞች የሚጠቀሙበት የተለመደ ቃል ነው። (ሐዋ 16:11) ፀሐፊው ሉቃስ የመርከበኞችን ቋንቋ ጠንቅቆ ያውቃል እኛ የሚል የብዙ ቁጥር ስሞች ወይም ተውላጦ ሰዎች የመርከብ ጉዞን የሚያመለክቱ ናቸው በዚህ ምዕራፍ በቁጥር 3 ላይ ተመልከቱ።

▣ **"ቆስ"** የቃሉ ትርጉም "ጥሪ" ማለት ነው። ይህ ስያሜ ደሴቲቱን እና የትልቁ ከተማ ስም ነው። ከክርስቶስ ልደት በፊት የሃይፓክራት መኖሪያ ነበር። በዚህች ከተማ ዝነኛ የሆነ የህክምና ማዕከል የነበረበት ቦታ ነው። ከመላጢያ አርባ ማይል ርቀት ላይ የሚገኝ ሃገር ነው።

▣ **"ሩድ"** የደሴትዋ እና የዋናው ከተማ ስያሜ ነው። ይህች ደሴት በሁለት ነገሮች ትታወቃለች የመጀመሪያው በአበባ ንግዷ ሲሆን ሁለተኛው በዩኒቨርሲቲ ማዕከልነቷ ነው። በኃላም በ29 ከክ)ል)በፊት በተገነባው የባህር ዳር የአልማዝ የወንድ ምስል ሃውልት ታዋቂ በመሆን ችላለች። ሃውልቱ የብርሃን ቤት በመባል ይታወቅ ነበር።

▣ **"ጳጥራ"** የምዕራቡ ቤተሰብ የግሪክ ፅሐፊ ላይ (p[41], D) "እና ሜራ" የሚል ተጨማሪ ቃል ተፅፎ ይገኛል። ይህች ከተማ የሶሪያ የወደብ ከተማ ነበረች። ጳጥራ ግን የሊዛ የወደብ ከተማ ነበረች በዚህ ከተማ አፖሎ የሚባለው ጣኦት አፈተሪክ በስፋት የሚነገርበት ቦታ ነበር።

21:2 **"ወደ ፊንቂም የሚሻር መርከብ አግኝተን"** ትናንሽ መርከቦች በየወደቡ ስለሚቆሙት አልመረጡአቸውም ነገር ግን ይህ ትልቅ መርከብ የቀጥታ ጉዞ ስለሚሄድ ጊዜን እንደሚቆጥብላቸው ስላወቁ ሊመርጡት ችለዋል።

21:3 **"ወደ ሶሪያ ለመሄድ ባሰበ ጊዜ"** የበርናባስ ሃሳብ ይመስላል ይህም ከመጀመሪያው የሚሲዮናዊነት ጉዞው ያገኘው ተሞክሮ ነበር።

▣ **"ጢሮስ"** የፊንቂ ከተማ የባህር በር ከተማ ነበረች።

21:4 **"ደቀ መዛሙርት"** በዚህች ከተማ አከእስቲፋኖስ ሞት በኃላ ቤተክርስቲያን ተመስርታለች (ሐዋ 8:4;11:19) በዚህ ጊዜ አማኞች ህብረት ለማድረግ አጥብቀው የሚፈልጉበት ጊዜ ነበር (ሐዋ 21:7,16)።

▣ **"እነርሱም ጳውሎስን ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይወጣ በመንፈስ አሉት"** በዚህች ቤተክርስቲያን ነብያቶች እንደነበር ያሳያል (ሐዋ 20:23;21:23;21:10-12) ነብያት የሚናገሩት እውነት ቢሆንም የእግዚአብሔር ፈቃድ ለጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲወጣ ነበር። (ሐዋ 21:14) ኢየሱስ በገዥዎች ፊት እንደሚቆም ለጳውሎስ ተናግሮት ነበር፡ (ሐዋ 9:15-16)ለጳውሎስ ስደትና መከራ የጠለመደ የኑሮው ዘይቤን ሆአል ነገር ግን በዚህም ሁኔታ ለነገስታት ክርስቶስን ለመመስከር የተዘጋጀ ነበር።

21:5 **"በባህሩም ተንበርክከን ፀልየን"** የክርስቲያኖችን የጠበቀ መተሳሰብ እና ፍቅርን በግልፅ ያመለክታል። (ሐዋ 20:32,36)

አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 21፡7-14

እኛም የባህሩን መንገድ ጨርሰን ከጢሮስ ወደ አካ ደርሰን ለወንድሞችም ሰላምታ ሰጥተን ከእነርሱ ዘንድ አንድ ቀን ተቀመጥን በነገውም ወተን ወደ ቂሳሪያ መጣን ከሰባቱም አንዱ በሚሆን በወንጌላዊ ፊሊጶስ ቤት ገብተን በእርሱ ቤት ተቀምጠን። ለእነርሱም ትንቢት የሚናገሩ አራት ደናግል ሴቶች ልጆች ነበሩት። አያሌ ቀንም ተቀምጠን ሳለን ነቢይ የነበረ አጋቦስ የሚሉት አንድ ሰው ከይሁድ ወረደ ወደ እኛም መጣና የጳውሎስን መታጠቂያ ወሰደ የገዛ እጁንና እግሩን አስሮ እንደሁ መንፈስ ቅዱስ ይህ መታጠቂያ ያለውን ሰው አይሁድ በኢየሩስሌም እነደዚህ ያስሩታል በአህዛብም እጅ አሳልፈው ይሰጡታል ይላል አለ።
ይህንም በሰማን ጊዜ እኛም በዚያ የሚኖሩትን ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይወጣ ለመነው ጳውሎስ ግን እኛም በዚያ የሚኖሩትን ወደ እየሩሳሌም እንዳይወጣ ለመነው ጳውሎስ ግን መልስ እየለቀሳችሁ ልቤን እያሰበራችሁ ምን ማድረጋችሁ ነው? እኔ ስለ ጌታ ስለ ኢየሱስ ስም ለመሞት እንኳን ተሰናድቼአለሁ እንጂ ለእስራት ብቻ አይደለም አለ። ምክርንም ሊቀበል እንቢ ባለ ጊዜ ፈቃድ ይሁን ብለን ዝም አልን።

21፡7 "አካ" ከቶሎሚ II ቀጥሎ በተሾመው በታላቁ የግብፅ መሪ በአሌክሳንደሪያ ስም ከተማይቱ ተሰይማለች ከተማይቱ ቀድም የተገነባቸው በቶለሚ II በ26 ከክ)ል)በፊት ነበር። በብሉይ ኪዳን የከተማይቱ ስም አኮበሚል ትጠራ ነበር (መሳ 1፡31) በአሁኑ ጊዜ ደግሞ አክራ በመባል ትታወቃለች።

▣ *"ወንድሞች"* ተመሳሳይ (በሐዋ 21፡4,16) ያንብቡ።

▣ *"ከእነርሱ ተቀመጥን"* ቁጥር 4 ይመልከቱ።

21፡8 *"መጣን"* የተጠቀሙበት የትራንስፖርት ዓይነት በውል አልተጠቀሱም።

▣ *"ቂሣሪያ"* የሮማውያን ዋና ቦታ ነው የሚገኘውም በባህር አጠገብ ነበር የሰው ሰራሽ ግድብ ስለነበር የንግድ መስመር በዚያ ተዘርግቶ ነበር። ፊሊጳስ በዚህ ከተማ ኖሯል (ሐዋ 8፡40)

▣ *"ወንጌላው"* በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሦስት ጊዜ ብቻ ይህ ቃል ተጠቅሶ ይገኛል። (ኤፌ 4፡11,2 ጢሞ 4፡5 እና በዚህ ቦታ) ይህ ስጦታ በውል ምንና ምንን እንደሚያጠቃልል ማወቅ አይቻልም። ነገር ግን የስሙ ጥሬ ትርጉም "ወንጌልን የሚያውጅ" ነው።

▣ *"ከሰባቱም አንድ በሚሆን"* በኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ግሪክ ተናገር በሆኑ መበለቶች ላይ ይደረግ የነበረውን የምግብ ጭቆና የሚያሳይ ዓውድ ነው። በመሆኑም ሰባኪዎች እና የግሪክ ሰዎች የነበራቸው ነበሩ። እነዚህ የወንጌልን አለማቀፋዊነት ያበሰሩ የወንጌል አርበኞችም ናቸው (ሐዋ 6)

21፡9 *"አራት ድንግሎች. . ."* የሴቶችን አመራር አስፈላጊነት እንደገና እንድናስብ ያደርገናል (ኢዮ 2፡28-32; ሐዋ 2፡16-21) እነዚህን እና ሌሎችንም የአዲስ ኪዳን መፅሐፍ ቅዱስ የሚለውን ተመልከቱ (ሐዋ 2፡17) ይህ ርዕስ ጉዳይ አጨቃጫቂ ነው። እነዚህ አራት ደናግሎች ወደ እስያ በሚሄድ እግዚአብሔር በስፋት ማገልገላቸውን የሚጠቅስ የቤተክርስቲያን የጥንት ታሪክ ያወሣል። ኢሱባስ የሚባለው የታሪክ ፀሐፊ ፓሊካርፕና ፓፒስን በመጥቀስ ፅፎ እናገኛለን (ECCL hist 3:31:2-5)

21፡10 *"ነቢይ የነበረ አጋቦስ"* ይህንን ዐረፍተ ነገርተ ነገር በሁለት መንገዶች መረዳት እንችላለን፡ (1) ለቆሮንቶስ ሰዎች በተፃፈው ደብዳቤ መሰረት ይህ የወንጌል እወጃ መንገድ እንደሆነ እንገነዘባለን። (ሐዋ 14፡1)፣ (2) የሐዋርያት ስራ መፅሐፍ የወንዶች ብቻ ሳይሆን የሴቶችም ነብያቶች እንዳሉ አስገንዝበናል። (ሐዋ 21፡9)።

የአዲስ ኪዳን እና የብሉይ ኪዳን ነብያት የሚለዩበትን ማወቅ ተገቢ ነው የብሉይ ኪዳን እና የብሉይ ኪዳን ነብያቶች መፅሐፍ ቅዱስን የፃፉ ሲሆኑ በአዲስ ኪዳን ግን ይህ ስራ ለአስራ ሁለት ሐዋርያት የተሰጠ ነበር። ነገር ግን ሐዋርያት ከሞቱ በኃላ ነብያት የእነርሱን ስራ በመተካት ሰርተዋል ይህ ማለት መፅሐፍ ቅዱስን እንደገና ፅፈዋል ማለት አይደለም ምክንያቱም ከዚህ በኃላ መፅሐፍ ቅዱስ አይፃፍም (ይሁ 20) የአዲስ ኪዳን ነብያቶች ተቀዳሚ ስራ ወንጌልን ማፅበረሰቡ ባለበት ሁኔታ ማድረስና ማወጅ ነው (ሐዋ 11፡27)።

21፡11 አጋቦስ በብሉይ ኪዳን እንደነበሩ ነብያት የወደፊቱን የሚናገር አውነተኛ ነብይ ነበር።

21፡12 *"ለመንነው"* ሁለት ነገሮችን ያመለክታል፡ (1) ድርጊቱ መጀመሩን ያመለክታል፣ (2) ቀደም በተደጋጋሚ የተከናወነ ድርጊትን ያሳያል።

21፡13 የነብያቶችን ቃል ከራሱ ስሜት ጋር ማስማማት የጳውሎስ ቁቀዳሚ ተግባር ሆኖ ነበር።

21፡14 *"የጌታ ፈቃድ ይሁን ብለን ዝም አልን"* የፀሎት ስሜት ያልው ንግግር ነው። እግዚአብሔር በነብያቱ በኩል ለጳውሎስ በኢየሩሳሌም መከራ እንደሚገኘው መናገሩ ሊያስፈራራው ሳይሆን የአእምሮ ዝግጅት እንዲያደርግ ነው ለጳውሎስ ሕይወት ላይ ያቀደው የራሱ ግልፅ የሆነ አላማ

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 21፡15-16**

**ከዚያ ቀን በኃላ ተዘጋጅተን ወደ ኢየሩሳሌም መጣን፡፡ በቂሳሪያም የነበሩት ደቀ መዛሙርት አንዳንዶች ደግሞ ከእኛ ጋር መጡ እነርሱም ወደ ምናድርበት ወደ ቀድሞው ደቀ መዝሙር ወደ ቆጵሮሱ ወደ ምናሶን ወደሚሉት ቤት መሩን፡፡**

21፡15 **"ተዘጋጅተን"** p ""king james verstion" ይህ ትርጉም ቃሉን "ደፋር መሆን" በማለት ተርጉሞታል በ NKJV ላይ ደግሞ መታጠቅ "በማለት ፍቺ ሰጥቶታል፡፡" ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን ብቻ የተፃፈ ነው፡፡

▣ **"ኢየሩሳሌም"** 64 ማይል ትርቃለች፡፡

21፡16 **"ምናሶን"** የቆፕሮስ ሃገር አይሁዳዊ ክርስቲያን የነበረ ሰው ነው፡፡ በሐዋ 6 ላይ እንደሚገኙት ሰባት ሰዎች ይህም ሰው የግሪክን ቋንቋ ጠንቅቆ የሚያውቅ ነበር፡፡ ምናሶን የጥንት ክርስቲን እንደሆነ እና ሉቃስ ለፅሑፍ ይጠቅመው ዘንድ ይህን ሰው መጠይቆችን አድርጎለት ነበር፡፡ የአውዱ ዕይታ (ሐዋ 21፡17-23፡30)

### ሀ. የሐዋ 21፡17-26፡32 ዝርዝር ማውጫ (ጳውሎስ በኢየሩሳሌም እና በቂሳርያ በእስር ቀይቶል)

1. በመቅደስ እስራት እና አመፅ 21፡17-40
2. የጳውሎስ የመከላከያ ሃሳብ በህዝብ ፊት 21፡1-22
3. የሮማውያን መጠይቅ 22፡23-30
4. የሸማግሌዎች መጠይቅ 23፡1-10
5. የጳውሎስ ጉዳዮች ሴራ 23፡11-35
6. ጳውሎስ በፊላክና ፊት 23፡1-23
7. ጳውሎስ በፊሊክስና በዱራሴል ፊት 24፡24-27
8. ጳውሎስ በፍስተስ ፊት 25፡1-12
9. ጳውሎስ በአግሪጳ II እና 25፡13-26፡32

### ለ. የሐዋርያው ጳውሎስ የተለመዱ የመከላከያ ሃሳቦች

| ዝርዝር | ጳውሎስ በሽማግሌዎች ፊት | ጳውሎስ በፊሊክስ | ጳውሎስ በፊስተስ ፊት | ጳውሎስ በአግሪጳ II |
|---|---|---|---|---|
| 1. የአይሁዳዊነት የቀድሞ ህይወት | 22፡3 | | 24፡14, 17-18 | 26:4 |
| 2. የፈራሳዊነት ቅናቱ | 22፡3 | 23፡6-9 | 24፡15,21 | 26:5-8 |
| 3. አሳዳጅነቱ | 22፡4-5 | | | 26:9-11 |
| 4. የግል ምስክርነቱ | | | | |
| 5. የአገልግሎት ጥሪው | 22፡6-16 | | | 26:12-16 |
| | 22፡17-22 | | | 26:17-23 |

ሐ. ፈርሳውያን እና ሰዱቃውያን በንፅፅር ሲቀመጡ

| | ሰዱቃውያን | ፈሪሳውያን |
|---|---|---|
| መገኛ | በመቃብያን ጊዜ | በመቃብያን ጊዜ |
| የስያሚያቸው ትርጉም | ዛዱካሮትስ | የተለየ |
| የኑሮ ደረጃ | የካህናት ደረጃ ኑሮ | መካከለኛ የኑሮ ደረጃ |
| የመፅሐፍ ቅዱስ አስተምርሆታቸው | የሕጉን መፅሐፍ ብቻ (ከዘፋጥረት እስከ ዘዳዓም) | የሕጉን ሌሎች የብሉይ መፅሐፍትን እና አፌ ታሪኮችን |
| ስነመለኮታቸው | ወግ አጥባቂ የፈረሳዉያን የሆነው ሁሉ ለእነርሱ ተቃራኒ ነው (ሐዋ 23:8) | ተራማጅ<br>- በመላእክት ያምናሉ<br>- ከሞት በኃላ ስላለው ትንሳኤ ያምናሉ።<br>- በየዕለቱ ስለሚኖራቸው ሕይወት ህግጋት አላቸው። |

አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ: 21:17-26

ወደ ኢየሩሳሌም በደረሰን ጊዜ ወንድሞች በደስታ ተቀብሉን በነገውም ጳውሎስ ወደ ያዕቆብ ዘንድ ገባ ሽማግሌዎችም ሁሉ መጡ። ሰላምታም ካቀረቡላቸው በኃላ በእርሱ ማገልገል እግዚአብሔር በአህዛብ መካከል ያደረገውን በእያንዳንዱ ተረከላቸው እነርሱም በሰሙ ጊዜ እግዚአብሔርን አመሰገኑ አሉትም ወንድም ሆይ በአይሁድ መካከል አምነው የነበሩት ስንት አእላፍት እንደ ሆኑ ታያለህ ሁላቸውም ለህግ የሚቀት ናቸው። ልጆቻቸውም እንዳይገረዙ በስርዓትም እንዳይሄዱ ብለህ በአህዛብ መካከል ያሉት አይሁድ ሁሉ መሴን ይክዱ ዘንድ እንድታስተምር ስለ አንተ ነግረዋቸዋል። እንግዲህ ምን ይሁን? የአንተን መምጣት ይሰማሉና ብዙዎች የግድ ሳይሰበሰቡ አይቀሩም እንግዲህ ይዘህ ከእነርሱ ጋር ንፃ ራሳቸውንም እንዲላጩ ገንዘብ ክፈልላቸው ሁሉም ስለአንተ የተማሩት ከንቱ እንደሆነና አንተ ራስህ ደግሞ ህጉን እየጠበቅህ በስርዓት እንድትመላለስ ያውቃሉ። አምነው ስለነበሩ አህዛብ ግን ለጣኦት ከተሰዋ ከደማም ከታነቀም ከዝሙትም ነፍሳቸውን እንዲጠብቁ ፈርደን እኛ ፅፈንላቸዋል። በዚያን ጊዜ ጳውሎስ ሰዎችን ይዞ በማግስቱ ከእነርሱ ጋር እየነፃ መንፃታቸውን የሚፈፅሙበትን ቀን አስታውቆ ወደ መቅደስ ገባ በዚያም ቀን ስለ እያንዳንዳቸው መስዋትን አቀረቡ።

21:17 በአየሩሳሌም የነበሩ አማኞች ጳውሎስንና የተለወጡ አህዛብን በመልካም ልብ ተቀብለዋቸዋል (ሉቃ 8:40;9:11;ሐዋ 2:41; 18:27;21:17;24:3;28:30) በኢየሩሳሌም ሳሉ አብያተ ክርስቲያናት ግሩም ምስክርነት ሆኖአል።

21:18-19 **"ጳውሎስ ከእኛ ጋር ወደ ያዕቆብ ቤት መጣ"** ከአህዛብ አብያተ ክርስቲያናት የተሰበሰበውን የገንዘብ ስጦታ ያሳያል (ሐዋ 24:17) ጳውሎስ ለያዕቆብ የተከናወነውን ዘገባ አቅርቧል። (ሐዋ 15:12) ያዕቆብ የኢየሱስ ወንድምና በኢየሩሳሌም ላለች ቤተክርስቲያን መሪ ነበር። (ሐዋ 12:17;15:13)

21:18 **"ሽማግሌዎቹ በሙሉ ተገኝተው ነበር"** በዚህ ምንባብ ውስጥ ሐዋርያት አልተጠቀሱም እነዚህ ሐዋርያት በዚህ ጊዜ በወንጌል አገልግሎት ላይ ወይም በሕይወት ላይኖሩ ይችላሉ። ሽማግላች የሚለው ስያሜ አይሁድ መሪዎቻቸውን የሚጠሩበት ስያሜ ነበር። (ሐዋ 4:5, 8,23,6:12;11:30;15:2,4,22,23) 6:4;23:14;24:1,25:15;ዕብ 11:12;ያዕቆ 5:14) ይህ ስያሜ ለቤተ ክርስቲያን በጋቢዎች አገልግሎት ሲሰጥ ይታያል (ሐዋ 14:23;ቲቶ 1:5:1 ጴጥ 5:1)

21:19 አንዳንድ የመፅሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ጳውሎስ አስደሳች የሆነ የገንዘብ ስጦታ አለተቀበለም በማለት የሚያቀርቧቸውን ምክንያቶች እንመልከት:-

1. ጳውሎስ የግሪክ ሰው በሆነው አንድ አማኝ ቤት ቆይቷል እንጂ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከነበሩት በአንዳቸውም ቤት አላረፈም ነበር።
2. ጳውሎስ ስለተሰጠው ስጦታ ሲያመሰግን አይታይም።
3. በኢየሩሳሌም የሚገኙ መሪዎች ለጳውሎስ ያላቸውን ጥላቻቸውን አንፀባርቋል።
4. ቤተክርስቲያን ጳውሎስን በእስር ቤት እና በፍርድ ላይ ሆኖ አልረዱትም ነበር።

ስለጳውሎስ ትምህርትና አገልግሎት ትልቅ መጋጨትና ግራ መጋባት ነበረ ማለት ይቻላል። ይሁን እንጂ በቁጥር 19 ላይ ያለው ለኔ አዎንታዊ ሃሳብ አለው።

21:20 **"በአይሁድ መሃከል አምነው ከነበሩ ስንት አእላፋት እንደሆኑ ታየለህ"** ይህ እጅግ የሚያስደስት ምስክርነት ነው። በኢየሩሳሌም የሚገኙ አይሁዳውያን ወደ ክርስቶስ መምጣት ለሁሉም አስገራሚ ነው።

▣ **"ያመኑት"** ይህ የመፅሐፍ ቅዱስ እውቀት ድነት የሚናገር ነው። ነገር ግን አንድ ሰው ሙሉ የመፅሐፍ ቅዱስ እውቀት እና ሙሉ መረዳት ሳይኖረው ሊድን ይችላል (ሐዋ 1:6 ሉቃ 19:11)። ጳውሎስ እነዚህን ክርስቲያኖች መሆናቸው ወንጌልን መቃወማቸውን አያመለክትም።

▣ **"ለህጉ የሚቀኑ"** እነዚህ የተለወጡ ፈረሳውያን፣ ቀናተኞች ወደ ክርስቶስ ቢመጡም ነገር ግን ከዚህ ቀደም ያደረጉት የነበረውን የሃማኖት ስርዓት አልተውም ነበር። ዐረፈተ ነገሩ የገላትያ አማኞች እንደሆኑ የሚናገር ይመስላል።

21:21 **"በስርዓትም እንዳይሄዱ ብለህ በአህዛብ መካከል ያሉት አይሁድ ሁሉ ሙሴን ይክዱ ዘንድ እንድታስተምር ስለ አንተ ነግረዋቸዋል"** ዐረፍተ ነገሩ የዕብራይስጥ የንግግር ዘይቤ በግልፅ ይታይበታል። የሰዋሰው ህጉ የሚያመለክተው በአሁን ጊዜ ግሶች የተፀፈ መሆኑ ጳውሎስ ወቀሳ በቀረበበት ጊዜ በማስተማር ላይ እንደሚገኝ ያሳያል። ይህ ተቃውሞ ጳውሎስ ለአህዛብ ወንጌልን ሲሰብክ ከደረሰበት የበለጠና የጠነከረ ተቃውም ነበር። (ሐዋ 15) "መካድ" የሚለው ቃል የእግሊዘኛው (Apostary) በማለት ይተርጉመዋል የተሳሳተ መሆኑን የሚጠቁም ነው።

21:23 **"ስዕለት ያለባቸው አራት ሰዎች በእኛ ዘንድ አሉ"** የሚጠቁም ነው አባል የነበሩ ሰዎች ናቸው ይህ የሚያመለክተው የናዝራዊነት ቃል ኪዳን ውስን እነደነበሩ ነው (ዘኃል 6:1-8) ሐዋርያው ጳውሎስ ተመሳሳይ መሃላ አድርጎ ነበር። (ሐዋ 18:18) በመሆኑም ውስን ስለሆነው የናዝራዊነት መሃላ ዝርዝር ማስረጃ አናገኝም።

21:23 -25 ጳውሎስ የአይሁድ ክርስቲያኖች አመለካከት የገመገመበት ምንባብ ነው። አይሁዳውያንን ወንጌል በሚደርስበት ጊዜ የሃይማኖት ስርዓታቸውን በማክበር ነበር። (ሐዋ 18:18;20:6) ቆሮ 9:19-23 ይህ አሁን በእኛ ጊዜ ለሚገኙት መሲሁን እንጠብቃለን ለሚሉ አይሁዳውያን መልስ ነው።

21:24 **"ገንዘብ ክፈልላቸው"** ጳውሎስ በዚህ ጊዜ ይህን አይነቱን መሃላ አድርጎ ላይሆን ይችላል። ነገር ግን የሚያስፈልገውን የመስዋት ክፍያ ለሌሎች መክፈሉን ዐረፍተ ነገሩ ያስገነዝበናል። የአይሁድ መምህራን ለናዝራዊነት መሃላ የሚከፍል ትልቅ ክብር እንደሚገባው ያስተምሩ ነበር።

**ልዮ ርዕስ: "የናዝዊነት መሃላ"**

I. **አላማው**
   ሀ. የሌዋዊ ዘር ያልሆነ እስርኤዊ ሁሉ ናዝራዊ በመሆን ለእግዚአብሔር የተለየ መሆን ይችላል። (ዘኃ 6:1) ናዝራዊ ማለት "የተለየ" ወይም "መቀደስ ነው።
   ለ. የብሉይ ኪዳን መሃላ የሕይወት ሙሉ ኪዳን ሆኖናል።
      1. ሳምሶን (መሳ 13:7)
      2. ሳሙኤል (1 ሳሙ 1:21)
      3. ዮሐንስ መጥምቁ
   ሐ. የአይሁድ ሃይማኖት የተመሰረተው ውስን ከሆነው የናዝራዊነት መሃላ ከሚለው ሐሳብ ሊሆን ይችላል (ዘኃ 6:5) ውስን መሃላው የሚያጠቃልለው ራስን መላጨት እና በእሳት ማቃጠል ነው።
   መ. መሟላት ያለባቸው ዝርዝሮች (ዘኃ 6:1-8)
      1. ከወይን ጠጅ እና ከወይን አትክልት ውጤቶች አንድ ናዝራዊ መለየት አለበት።
      2. የሰውን ፀጉር ናዝራዊ አይቆርጥም
      3. የሞተ ሰው አስከሬንን ናዝራዊ እንደነካ አይፈቅድም። ይህ ማለት በአይሁድ የቀብር ስነስርዓት ላይ እንዳይገኝ በህግ የተከለከለ ነው።
      4. ባለማስተዋል በረክስ ምህረት አለው (ዘኃ 6:9) በግልፅ የጳውሎስን ሁኔታ መመልከት እንችላለን (ሐዋ 21:23-25) የመንፃትና መስዋትን የማድረግ ትዕዛዝ አለ (ዘኃ 6:9-12)

▣ **"እራሳቸውን እንዲላጩ"** የዘኃ 6 ላይ ስለናዝራዊ በግልፅ ተፅፏል። በህይወታቸው ሁሉ ናዝራውያን የሆነ ሁሉ ፀጉራቸውን እንዲላጩ ይገዳዳሉ ነገር ግን ለአጭር ጊዜ መሐላ የሚገቡ ምልክታቸው ፀጉራቸውን መላጫታቸው ነው። በዚህ ምንባ ሐዋርያው ጳውሎስ ለባህሉና ለህጉ ተገዥ መሆኑን ያሳያል። (1 ቆሮ 9:19-23;10:23-33)

21:25 **"ፅፈንላቸዋል"** በኢየሩሳሌም ስብስባ የተወሰነው ሕጋዊ ደብዳቤ ያመለክታል (ሐዋ 15:19,-20,28-29):: ይህ ደብዳቤ በአህዛብ አማኞችና በአይሁድ አማኞች መሃከል ያለውን ስርዓት በአንድነት እንደሆኑ ያወደደ ደብዳቤ ሲሆን አይሁድ ከሙሴ ህግጋት ጋር ይህ ፅሑፍ እንዳይደባለቅ ይከራከሩ ነበር።

21:26 **"ወደ መቅደስ ገባ"** የጳውሎስ ወደ መቅደስ መግባት ችግርን አስነሳ እንጂ ሰላምን አያመጣም ነበር።

አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 21፡27-36

ሰባቱ ቀንም ይፈፀም ዘንድ ሲቀርብ ከእስያ የመጡ አይሁድ በመቅደስ አይተውት ህዝብን ሁሉ አወኩና የእስራኤል ሰዎች ሆይ እርዱን ህዝብን ህግንም ይህንም ስፍራ ሲቃወም ሰውን ሁሉ በየስፍራው የሚያስተምረው ሰው ይህ ነው። የግሪክ ሰዎችን ወደ መቅደስ አግብቶ ይህን የተቀደሰ ስፍራ አርክሷል ብለው እየጮኹ እጃቸውን ጫኑበት በፊት የኤፌሰምን ፐሮፉምስን ከእርሱ ጋር በከተማ አይተውት ነበርና ጳውሎስም ወደ መቅደስ የገባው መስሏቸው ነው ከተማውም ሁሉ ታወከ ሕዝቡም ሁሉ ተሰበሰቡ ጳውሎስንም ይዘውት ከመቅደሱ ውጪ ጎተጎቱት ወዲያውም ደጁቹ ተዘጉ ሊገሉትም ሲፈልጉ ኢየሩሳሌም ፈፅማ ታውካት የሚል ወሬ ወደ ጭፍራው አለቃ ወጣ እርሱም ያን ጊዜ ወታደሮችን ከመቶ አለቆቹ ጋር ይዘው እየሮጠ ወርደባቸው እነርሱም የሻለቃውንና ወታደሮችን ባየ ጊዜ ጳውሎስን መምታት ተው በዚያን ጊዜ የሻላቃው ቀረበ ያዘዘውና በሁለት ሰንሰለት ይታሰር ዘንድ ማን እንደሆነና ምን እንዳደረገ ጠየቀ ህዝቡም እኩሌቶች እንዲህ እያሉ ይጮሁ ነበር ስለጫጫታውም እየሮጡ ማወቅ ባልተቻለ ጊዜ ወታደሮቹ ሰፈር ይወስዱት ዘንድ አዘዘ። ወደ ደረጃውም በደረሰ ጊዜ ስለህዝቡ ግፊያ ወታደሮች እንዲሸከሙጽ ሆነ ብዙ ሕዝብ አሰወግደው እያሉና እየጨሁ ይከተሉ ነበርና።

21፡27 ከእስያ የመጡ አይሁድ የጳውሎስ የቀደሞ ጠላቶቹ አሁን ደግሞ ወደ ኢየሩሳሌም የመጡበት ጊዜ ነው።

21፡28 "የሚያስተምረው ሰው ይህ ነው" የእስያ የመጡት አይሁድ የጳውሎስ ትምህርት የብሉይ ኪዳን የትንቢት ፃሜን የሚናገር ሳይሆን የአይሁድን ሃይማኖት ለመቃወም የሚያስተምር ይመስላቸው ነበር። እስቲፋኖስ ከተከሰሰበት ክስ ጋር ተመሳሳይነት አለው። (ሐዋ 6፡13) ጳውሎስ የአይሁድን ወግ በማክበር የታወቀ ነበር። በዚህ በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረውን ይህን የአይሁዳዊነት ወገና ስርዓት ኢየሱስ በግልፅ ትምህርቱ ተቃውሞታል። አድልኑ በሌለበት ሁኔታ መዳን ለሁሉም መሆኑን ለህዝብ ሁሉ አብስሯል።

▣ "የግሪክ ሰዎችንም ወደ መቅደስ አግብቶ" ጳውሎስ በደባብ ምስራቅ በነበረው ምከራብ የናዝራውያን መሃላ በሚፈፀም ጊዜ የግሪክ ሰዎችን ወደ መቅደስ ይዞ መግባቱ እንደወንጀል ተቆጥሮበታል። አሕዛቦች ወደ መቅደስ ውስጥ መግባቱ አይፈቀድላቸውም ነበር። (ሐዋ 21፡29)

21፡29 "የኤፌሶችን ፐሮፊሞስን" እነዚህ የእስያ አይሁድ (ኤፌስናውያን) ጳውሎስና ፐሮፊሞስን ለመግደል እቅድ አውጥተው የነበሩ ናቸው (ሐዋ 20፡3) በመሆኑም ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ጳውሎስን ለመግደል ብርቱ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ።

21፡30 "ደጆች ተዘጉ" እነዚህ ዳጆች የሚገኙት በእስራኤል መሰብሰቢያ እና በሴቶች መሰብሰቢያ በሚባሉት አዳራሾች መሃከል ያለ መዝጊያ ነው። መቅደሱ የሚጠብቁ ዘቦች ነበሩ እነርሱም፡ (1) መቅደሱ እንዳይረክስ ይጠብቁት ነበር፣ (2) ጳውሎስን ወደ መቅደስ አጅበው የሚመልሱት ነበሩ።

በኤፌሶን ተመሳሳይ ድርጊት እንመለከታለን (ሐዋ 19)።

21፡31 "የጭፍራው አለቃ" የአንድ ሺ ወታደሮች የበላይ ተቆጣጣሪ ነው። በሮማውያን የስልጣን ተዋረድ ይህ ትልቅ የስልጣን ተዋረድ ይህ ትልቅ የስልጣን እርከን ነው። የጭፍራ አለቃው በኢየሩሳሌም በመሆን ስርዓት እንደከበር ትዕዛዝን የሚያወጣ ባለስልጣን ነው።

▣ "ወረደባቸው" መቅደሱን የሚጠብቁ በምሽግ የሚኖሩ ወታደሮች ናቸው። ይህ የመቅደስ የተገነባው በታላቅ ሄሮድስ ነው አገልግሎቱም ለቤተመንግስትነት እና ለወታደራዊ ቀጠና እንዲሆን ነው (Josephns, wars 5.5.8)

21፡32 "ጥቂት ወታሮችና ጭፍሮች አለቋ" የጭፍራ አለቃ የመቶ ሰዎች የበላይ ተቆጣጣሪ ማለት ነው። እነዚህ ወታደሮች መቅደሱን ቤተመንግስትን የሚጠብቁ ናቸው በተለይ በበዓላት ቀናት ጥብቅ ቁጥጥርን ያደርጋሉ።

21፡33 "በሁለት ሰንሰለት ታስሮ" ይህ ማለት፡ (1) እግርና እጅ ማለት ነው፣ (2) በሁለት የሮማውያን ወታደሮች መካከል ማለት ነው። የሮማውያን ወታደሮች ጳውሎስን እንደ ነገሰ ገዳይ ይመለከቱት ነበር።

21፡34-35 ይህ ሐረግ የሚያስገነዝበን ከፍተኛ ተቃውሞ እና ብጥብጥ እንደነበር ነው (ቁ.30)።

21፡35 "ደረጃዎች" እነዚህ ደረጃዎች ወታደሮች ከምሽጋቻ በማውጣት ወደ መቅደስ የሚያመሩበት መንገዳቸው ነው (ቁ.32) መቅደሱ ሁለት የተለያዩ መተላላፊያዎች ነበሩት በበዓላት ቀናት የሚነሳው አመፅ ሮማውያን" በፍጥነት ለማቆም አቅደው የሰሩት የወታደሮች መሄጃ መንገድ ነው።

አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 21፡37-40

**ወደ ሰፈርም ሊያገቡት በቀረቡ ጊዜ ጳውሎስ የሻለቃውን አንድ ነገር ንነግርህ ትፈቅዳለህን አለው እርሱም የግሪክ ቋንቋ ታውቃለህን አንተ ከዚህ ዘመን አስቀድሞ ከነፋስ ገዳዮቹ አራቱን ሺ ሰዎች አሸፍተህ ወደ ምድረ ባዳ ያወጣህ የግብፅ ሳ አይደለህምን? አለ ጳውሎስ ግን እኔስ አይሁዳዊ በኪልቅያ ያለው የጠርሴስ ሰው ሆኜ ስመ ጥር በሆነ ከተማ የምኖር ነኝ ለህዝቡ እናገር ዘንድ እንድትፈቅድልኝ እለምንሃለሁ አለው በፈቀደለት ጊዜ በደረጃው ላይ ቆሞ በእጁ ወደ ህዝቡ ጠቀሶ እጅግም ፀጥታ በሆነ ጊዜ በእብራይስጥ ቋንቋ እየተናገረ እንዲህ አለ፡፡**

21፡37 **"የግሪክ ቋንቋ ታውቃለህ"** የሻለቃው በጳውሎስ የግሪክ ቋንቋ ተናጋሪ መሆን ተደንቃል ምክንያተቱም እርሱ የሚመስለው ግብጣ ሽፍታ እንደሆነ ነበር፡፡ (ቀ 38 እና Josephns Antiq 2:13:5; 20:8:6) የግብፆች አመፅ በ52-57 ዓ.ዓ ተከናውኖ ነበር፡፡

21፡38 **"ነፍስ ገዳዮች የላቲኑ ፅሁፍ"** መሬት ቆፋሪ በማለት ለዚህ በቃል ፍቺ ይሰጣል፡፡ በአዲስ ኪዳን በተለመደ "ቀናተኞች" የሚባሉት ናቸው፡፡ (ሉቃ 6፡15;ሐዋ 1፡13) እነዚህ ቀጥተኞች አይሁድ ሆነው የሮምን መንገስት በአመፅ ለመገልበጥ የሚጥሩ ናቸው፡፡ የሚከተለውን መፅሐፍ አንብቡ፡-
(A.T Roberson, word picture in the NT, VO13, P382)

21፡39 **"ስመ ጥር በሆነ ከተማ የምኖር ነኝ"** በአለም የታወቀ ዝነኛ ዩኒቨርሲቶቲ ያለበትን ከተማ ለመጥቀስ ፈልጎ ጳውሎስ ረፍተ ነገሩን ተጠቅሞ እናነባለን፡፡ ከጳውሎስ ዘመን በፊት ሮማዊ ያልሆነ የሮም ግዛት ባልሆነ ከተማ የሮም ዜግነት ይህ መኖር አይፈቀድም ነበር እንዲሁም ሮማዊ ያልሆነ ሁሉ ዜግነት ለማግኘት አይቻልም ነበር፡፡ ነገር ግን በጳውሎስ ጊዜ የሮም መንግስ ህግጋት በመቀየሩ ባለስልጣናቱን ይህ የጳውሎስ ንግግር የሚያስቆጣም የሚያስደንቅም አልነበረም፡፡

21፡40 **"ፈቀደለት"** በዚህ ዓውድ ውስጥ የሚታየው ባለስልጣን የጳውሎስን ነገር በትኩረት ማወቅ ይፈልጋል፡፡

▣ **"በዕብራውያን ቋንቋ እየተናገረ"** አይሁዳውያን በአሦራውያን ምርኮ በነበሩበት ጊዜ የአራማይክን ቋንቋ ስለሚያውቁ ጳውሎስ ሕዝብ በተሰበሰበ ጊዜ በዚህ ቋንቋ ይጠቀም ነበር፡፡ (ሐዋ 22፡2)

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ለመርዳት ነው የተሰናዱት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋነኞቹን ጉዳዮች ለማጤን እንዲረዳ ነው፡፡ ሐሳብ ለማጫር እንጂ መደምደሚያ አይደሉም፡፡

1. ነብያቶች በየከተማው ለጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይሄድ እየተናገሩ ጳውሎስን ለምን መሄድ አስፈለገው?
2. ያመኑት አይሁድ የሙሴን ህግ እንዴት ይመለከቱታል?
3. ከእስያ የመጡ አይሁድ ጳውሎስን ላይ ክስ ነበራቸው?
4. የሻለቃው ንግግር የሚያመለክተው ብዙ አይሁዶች ግሪክ አይናገሩም ማለት ነው? ወይስ ጳውሎስ የግብፅ ሽፍታ አድርጎ ቆጥሮታል (ቁ.39)?

# የሐዋርያት ስራ 22

## የምንባቡ ክፍፍል በአዲሶቹ ትርጉሞች

| የተየመቅሰ[4] | አኪጀት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጳውሎስ የመከላከያ ሃሳብ አቀረበ | በኢየሩሳሌም የነበረውን ብጥብጥ ተናገረ | የጳውሎስ እስራት እና መከላከያው | ጳውሎስ ስለራሱ ተከራከረ | ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ለነበሩ አይሁድ መሰከረ |
| | | (21:27-22:29) | (21:37-22:5) | |
| 21:37-22:5 | 21:37-22:21 | 21:37-22:1 | | |
| | | | | 22:1-5 |
| | | 22:2 | | |
| | | 22:3-5 | 22:3-5 | |
| ጳውሎስ ስለመለወጡ ተናገረ | | | ጳውሎስ ስለመለወጡ ተናገር | |
| | | | 22:6-11 | |
| 22:6-11 | | 22:6-11 | 22:12-16 | 22:6-11 |
| | | 22:12-16 | ጳውሎስ ለአህዛብ ወንጌል ለመሰበክ ተጠርቷል | 22:12-16 |
| ጳውሎስ ወደ አህዛብ ተላከ | | | | |
| | | 22:17-21 | 22:17-21 | |
| 22:17-21 | | | | |
| | | | | 22:17-21 |
| ጳውሎስ እና የሮማዊ ዜግነቱ | የጳውሎስ ሮማዊ ዜግነት | | | |
| | | | | ጳውሎስ የሮማዊ ዜግነት አለው |
| 22:22-29 | 22:22-29 | | 22:22-25 | |
| | | 22:22-29 | | 22:22-29 |
| | | | 22:26 | |
| | | | 22:27 | |
| | | | 22:28 | |
| | | | 22:29 | |
| ጳውሎስ በሸንጐ ፊት | ሽማግሌዎቹ ተከፋፈሉ | | ጳውሎስ በፍርድ ፊት | በሽማግሌዎች ታየ |
| (22:30-23:11) | | | (22:30-23:11) | (22:30-23:11) |
| 22:30-23:5 | 22:30-23:10 | 22:30 | 22:30 | 22:30 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (ከ **"መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ" ገጽ** vii)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. ምንባብ አንድ

2. ምንባብ ሁለት

3. ምንባብ ሦስት

4. ወ.ዘ.ተ. . .

**የቃል እና የጥምር ቃል ጥናት**

| |
|---|
| **አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 22፡1**<br>**እናንተ ወንድሞች አባቶችም አሁን ለእናንተ ነገሬን ስገልጥ ስሙኝ፡፡** |

22፡1

| | |
|---|---|
| NASB | **"ወንድሞችና አባቶች"** |
| NKJV | **"ወንዶች፣ ወንድሞች እና አባቶች"** |
| NRSV | **"ወንድሞችና አባቶች"** |
| TEV | **"ወዳጅ አይሁዳውያን"** |
| NJB | **"ወንድሞቼና አባቶቼ"** |

(*A Translator's Handbook on the Apostles*, by Newman and Nida) በዚህ ምንባብ በጳውሎስ እድሜ እኩዮቹ የሆኑ እና ከእርሱ የሚበልጡትን ለመጥራት ወንዶችና አባቶች በማለት ይጠራቸው ነበር፡፡ (ሐዋ 7፡2) በዚህ ጊዜ ጳውሎስ ወደ ስልሳ ዓመት እንዲምላው ይገመታል፡፡ በዚህ ጉባኤ ውስጥ አንዳንድ አማኞች መኖር ይገባቸዋል፡፡ በተለይም 'ወንድሞች' የሚለው ቃል እነርሱን አመልካች ነው፡፡ ይሁን እንጂ ጳውሎስ ሁልጊዜ ራሱን ከዘሩና ከዜግነቱ ጋር ያገናኘዋል (ሮም 9፡1-5፣ ፊሊ. 3፡5)፡፡

▣ **"ነገሬን ስገልጥ"** የእግዚአብሔር "aplogy" ወይም ከግሪኩ "apologia" ትርጉሙም በቃላት መከራከሪያ ሃሳብ ማቅረብ ማለት ነው፡፡ በሐዋርያት ስራ መፅሐፍ በጳውሎስ በቃላት የመከራከሪየ ሃሳብ ማቅረብ ማለት ነው፡፡ በሐዋርያት ስራ መፅሐፍ በጳውሎስ ጉደይ ይህ ቀል በተደጋጋሚ ተጠቅሷል (ሐዋ 25፡16፣ 2ጢሞ 4፡6)፡፡

| |
|---|
| **አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 22፡2**<br>**በዕብራይስጥ ቋንቋ በሰው ጊዜ ከፊት ይልቅ ዝም አሉ፡፡ እርሱም አለ፡፡** |

22፡2 **"የዕብራይጥ ቋንቋ"** የአራማይክን ቋንቋ ያመለክታል፡፡ በወንጌላት ውስጥ ኢየሱስ የሰበከት በአብዛኛው በአራማይክ ቋንቋ ነው፡፡ በጥንት ዕብራውያን መሃከል ይህ ቋንቋ የመግባቢ ቋንቋቸው ነበር፡፡ የአራማይክ ቋንቋ የሦሪያዎች ቋንቋ ነው፡፡ በአሥር ቅኝ ግዛት አይሁዶች በነበሩ ጊዜ ቋንቋቸውንም መማር ችለዋል፡፡ ለምሳሌ ነህም 8 ዕዝራ መፅሐፍ በዕብራይስጥ ሲያነብ ለዋውያኑ ደግሞ ለህዝቡ ወደ አራማይክ ይተረጉሙ ነበር (ነህም 8፡7)፡፡

▣ **"ከፊት ይልቅ ዝም አሉ"** ጳውሎስ በተከበረው በአይሁድ መምህር በገማልያ መማሪ ህዝቡን ዝም እንዲህ አድርጓል፡፡ በተጨማሪም የጳውሎስ አቀራረብ በአራማክ ቋንቋ መናገር የህዝቡን ቀልብ በመግዛቱ ፀጥታ ከመሆኑ የተነሳ ጳውሎስ ወንጌልን ለመናገር እድል አግኝቷል፡፡

| |
|---|
| አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 22፡3-5<br>**እኔ የኪልቅያ በምትሆን በጠርሴስ የተወለድሁ በዚችም ከተማ በገማልያ እግር አጠገብ የደግሁ የአባቶችንም ህግ ጠንቅቄ የተማርሁ ዛሬውንም እናንተ ሁሉ እንድትሆኑ ለእግዚአብሔር ቀናተኛ የሆንሁ አይሁዳዊ ሰው ነኝ፡፡ ወንዶችንም ሴቶችንም እያሠርኩ ወደ ወህኒም አሳልፌ እየሰጠሁ ይህን መንገድ እስከ ሞት ድረስ አሳደድሁ፡፡ እንዲህም ሊቀ ካህናቱ ወደ ሽማግሌዎቹም ሁሉ ይመሰክሩልኛል ከእነርሱ ደግሞ መልእክትን ተቀብዬ በደማስቆ ያሉትን ደግሞ ታስረው እንዲቀጡ ወደ ኢየሩሳሌም ለመጣ ወደዚያ እሄድ ነበር፡፡** |

22፡3 **"እኔ የኪልቅያ በምትሆን በጠርሴስ የተወለድሁ"** የጳውሎስ የራሱን ማንነት ለህዝቡ እያሳወቀ ነው፡፡ በተለይ አይሁዳዊ መሆኑን በአንክሮ እየተናገረ ነው፡፡ (2ቆሮ 12፡22፣ ፊሊ. 3፡5-6) ምክንያቱም ጳውሎስ ለብዙዎች ግሪክ ተናጋሪ ምዕአተኛ ተጠርጐ ይቆጠር ነበር፡፡

በዚህ ምንባብ ጳውሎስ በጠቀሰው ከተማ እንዳደገ ይናገራል ነገር ግን ከተማው በውል አይታወቅም ምናልባት ጠርሴስ ወይም ኢየሩሳለም ልትሆን ትችላለች፡፡ ነገር ግን ከአወዱ መረዳት እንደሚቻለው በኢየሩሳሌም በተጨማሪ በሌላ በታም ተምሯል ማለት ነው፡፡

▣ **"በገማል እግር ስር"** ይህ የተከበረ የአይሁድ መምህር ነበር (ሐዋ 5፡34-40) ጳውሎስ ሂሊል በሚባባል የአይሁድ መምህራን የሚማሩበት ትምህርት ቤት ተምሯል፡፡ በመሆኑም የተሰበሰቡት ሰዎች ሲሰሙ ልባቸው ተነካ ገማልያ የሚለውን ርዕስ ተመልከቱ (ሐዋ 5፡34)

▣ **"የአባቶችንም ህግ ጠንቅቄ የተማርሁ"** ይህ የሚያሳየው ጳውሎስ ፈሪሳዊ ነበር ማለት ነው፡፡ (ሐዋ 23፡6፣ 26፡5) በተጨማሪም ቀናተኛ ነበር፡፡ (ቁ.4) እንደሚታወቀው ፈሪሳዊያን ታልሙድ ወይም በአፈ ታሪኮች ላይ የተጠቀ እምነት እና ለህግጋቱም ይታዘዙ ነበር፡፡

▣ **"ዛሬውንም እናንተ እንድትሆኑ"** ጳውሎስ እነዚህ አይሁድ የሚቀኑትን ቅናት እርሱም ይቀና እንደነበር እየነገራቸው ነው፡፡

22፡4 **"አሳድድ ነበር"** ጳውሎስ በአገልግሎት ሁሉ የቀደመውን ህይወቱን በመፀፀት ይተርክ ነበር፡፡ (ሐዋ 9፡1፡13፡2) ሐዋ 22፡4.19 ሐዋ 26፡10-11፣ ገላ1፡13.23፣ፊሊ. 3፡6 1ጢሞ 1፡13) ጳውሎስ ከሁሉ ያነስኩ ነኝ የሚልበት ምክንያቱ በዚህ በቀደመ ድርጊቱ በመቆጨት ነበር (1ቆሮ 15፡9፣ 2ቆሮ 12፡11፣ ኤፌ 3፡8፣ 1ጢሞ 1፡15)፡፡

▣ **"ይህ መንገድ"** በጥንቲቱ ቤተክርስቲያን የክርስቲያኖች ስም መንገድ ነበር፡፡ (ሐዋ 9፡2፣ ሐዋ 19፡9፡23፣ ሐዋ22፡4፣ሐዋ 28፡14፣22) መንገድ የሚያመለክተው፡ (1) ኢየሱስ የህይወት መንገድ መሆኑን (ዮሐ 14፡6)፣ (2) መፅሐፍ ቅዱሳዊ የክርስትና መገለጫ ነው፡፡ (ዘዳ 5፡32-33፣ (ዘዳ 31፡29፣ መዝ27፡11፣ ኢሳ35፣3)

▣ **"እስከ ሞት"** ጳውሎስ የክርስቲያኖችን ነብስ አጥፍቶአል፡፡ (ሐዋ 8፡1.3 ሐዋ 26፡10) በእስቲፋኖስ ሞት ጳውሎስ በቀጥታ ተሳታፊ ነበር (ሐዋ 7፡58.81)፡፡

▣ **"ወንዶችንም ሴቶችንም እያሰርኩ"** ጳውሎስ ይኽንን ለስቲየዋ ያሳየው የእርሱ መከራ ምን ያህል ከባድ እንደነበር ያሳያል፡፡

2፡5 ጳውሎስ ወደ ደማስቆ የሄደበትን አላማ ይተርካል (ሐዋ 9)

▣ **"ሽማግሌዎች"** በሉቃ 22፡66 ተመሳሳዩን መመልከት ይቻላል፡፡ እነዚህ መሪዎች በኢየሩሳሌም የሚገኙትን የአይሁድ መሪዎች ወይም በቁጥር ሰባ የሚደርሱትን ሳይሆን ነገር ግን በዚህ ዓውድ እነዚህ ሽማግሌዎች የአንድ አካባቢ የህዝብ መሪዎች መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡

▣ **"መልእክትን ተቀብዬ"** (F.F Bruce, paul: *Apostle of the Heart set Free*) ይህንን መፅሐፍ የሰባዎቹን ስልጣን በግልፅ መመልከት ይቻላል፡፡ ለተጨማሪም ዝርዝረ መቃበያን 15፡21 እና የጆሲፈንስን መፅሐፍ ማንበት ጠቃሚ ነው፡፡
"በዚያ ያሉትን" በኢየሩሳሌም የነበሩ አይሁድ ከፍተኛ ስደት ደርሶባቸው እንደነበር መመልከት ይቻላል፡፡

> **አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 22፡6-11**
> **ስሄድም ወደ ደማስቆ በቀረብሁ ጊዜ ቀትር ሲሆን ድንገት ከሰማይ ታላቅ ብርሃን በዙሪያዬ አንፀባረቀ በምድር ላይ ወድቄ ሳውል ሳውል ስለምን ታሳድደኛለህ የሚለኝን ድምፅ ሰማሁ፡፡ እኔም መልሼ ጌታ ሆይ አንተ ማን ነህ አልሁ፡፡ እርሱም አንተ የምታሳድደኝ፡ የናዝሬቱ ኢየሱስ እኔ ነኝ አለኝ፡፡ ከእኔ ጋር የነበሩትንም ብርሃኑን አይተው ፈሩ የሚናገረኝንም የእርሱም ድምፅ ግን አልሰሙም ጌታ ሆይ ምን ላድርግ አልሁት፡፡ ጌታም ተነስተህ ወደ ደማስቆ ሂድና ታደርገው ዘንድ ስለ ታዘዘው ሁሉን በዚያ ይነግሩሃል አለኝ፡፡ ከዚያ ብርሃንም ክብር የተነሣ ማየት ባይሆንልኝ ከእኔ ጋር የነበሩት ሰዎች እጄን ይዘው እየመሩኝ ወደ ደማስቆ ደረስሁ፡፡**

22፡6 **"ቀትር ሲሆን"** ሐዋ 9፡3 ይመልከቱ

22፡7 የሐዋርያት ስራ 9፡4 ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

22፡8
NASB, NJB **"ኢየሱስ ናዝራዊው"**
NKJV, NRSV
TEV **"ኢየሱስ የናዝሬቱ"**
ሐዋርያው ጳውሎስ የራሱን የግል ምስክርነት በሐዋርያት ስራ መፅሐፍ ሦስት ጊዜ መስክሮአል በመሆኑም በዚህ ቁጥርና በሐዋ 26፡9 የናዝሬቱ ኢየሱስ የሚለውን ሐረግ ተጠቅሟል፡፡ በሐዋ 24፡5 የአንድ ቡድን መሪ አድርገውታል፤

በማቴ 2:23 በትንቢት ድምፅ የተሰየ ስም ነው። ይህ የአንድ የናዝሬት መሪ ብቻ ሳይሆን የመሲህነት ስያሜው ነው (ኢሳ 11:1፣ ኢሳ 53:2፣ ኤር 23:5፣ ኤር 33:15፣ ዘካ 3:8፣ ዘካ 6:12)።

▣ **"የምታሳድደኝ"** ሐዋ 9:4 ይመልከቱ።

22:9 **"የእርሱን ድምፅ ግን አልሰሙም"** በሐዋ 9:7 እና 22:9 መሃከል የታሪክ ስህተት የለም። የግሪኩ ሰዋሰው ድምፁን ሰምተው ነገር ግን ቃሎቹን አላወቋቸውም ይባላል። (ሐዋ 9:7)

22:10 **"ስለ ታዘዘው ሁሉን በዚያ ይነግሩሃል"** ኢየሱስ ለሃናንያ ያለውን ንግግር የሚያንፀባርቅ አገልግሎት ነው። (ሐዋ 9:15-16) ጳውሎስ እጅግ አስቸጋሪ የሆነ የአገልግሎት የፈፀመ አገልጋይ ነበር። የጳውሎስ አገልግሎት ብሉይ ኪዳን ተከር ሆኖ ነገር ግን የትንቢቶቹን ፍፃሜ በግልፅ ይናገር ነበር (ኢሳ6፣ ኤር1፣ ህዝ2-3)።

22:11 በዚህ ምንባብ ውስጥ የጳውሎስ የህይወት እሾክ የሆነውን ነገር የመፅሐፍ ቅዱስ ምሑራን እንደሚከተለው ይዘረዝራሉ፦

1. የቤተክርስቲያን አባቶች የሆኑት ካልቪን እና ሉተር ጳውሎስ ከተፈጥሮ ስጋው ድክመት የተነሳ መንፈሳዊ ችግር እንደነበረው ይናገራሉ።
2. ክርሶስተም ደገሞ የጳውሎስ የስጋው እሾክ ሰዎች ናቸው ይላል። (ዘላ 33:55፣ መሳ2:3)
3. ሌሎች ደግሞ የጳውሎስ የስጋው እሾክ የሚጥለው በሽታ መሆኑን ይናገራሉ።
4. ዊሊያም ራምሴ የተባሉት ምሁር ደግሞ ጳውሎስ የወባ በሽታ እንደሚያጥለው በሽታ እንደሚያስቀየው ይናገራሉ።
5. ጳውሎስ በደማስቆ መንገድ ብርሃን ከበራበት በኃላ የአይን ህመምተኛ በመሆኑ የስጋው እሾክ የስጋው እሾክ ይሄው ህመሙ መሆኑ ይነገራል። (ሐዋ 9: ኢሳ. 23:13 )

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 22:12-16**
**[12]በዚያም የኖሩት አይሁድ ሁሉ የመሰከሩለት እንደ ሕጉም በጸሎት የተጋ ሐናንያ የሚሉት አንድ ሰው ነበረ። [113]እርሱም ወደ እኔ መጥቶ በአጠገቤም ቆሞ። ወንድሜ ሳውል ሆይ፥ እይ አለኝ። እኔም ያን ጊዜውን ወደ እርሱ አየሁ። [14]እርሱም አለኝ። የአባቶቻችን አምላክ ፈቃዱን ታውቅ ዘንድና ጻድቁን ታይ ዘንድ ከአፉም ድምፅን ትሰማ ዘንድ አስቀድሞ መርጦሃል፤ [15]ባየኸውና በሰማኸው በሰው ሁሉ ፊት ምስክር ትሆንለታለህና። [16]አሁንስ ለምን ትዘገያለህ? ተነሣና ስሙን እየጠራህ ተጠመቅ ከኃጢአትህም ታጠብ።**

22:12 በሐዋ 9:10 ከተፃፈው ይልቅ የሐናንሃ ዝርዝ ተፅፎ ይገኛል። ሃናኒያ ፈሪሳዊ የነበረ ነገር ግን ህይወቱን ለምኩራብ አገልግሎት በመስጠት የፀሎት ሰው ነበር።
ፀሐፊው ሉቃስ ህፃኑን ኢየሱስን ላቀፈው ስምኦን (ሉቃ 2:25) እና በባለሃምሳ ዕለት ወደ ኢየሩሳሌም ለመጡ አይሁድ (ሐዋ 2:25) እና እስቲፋኖስን ሊቀበሩት ሰዎች የተጠቀመበት የዐረፍተ ነገር አመሠራረቱ ተመሳሳየ ነው (ሐዋ 8:2)። በዚህ ምንባብ መሠረት ሃናኒያ አማኝ እና የአይሁድ ሃይማኖት ተከታይ አልነበረም ነገር ግን ደቀ መዝሙር ተብሎ ተጠርቷል። ሐዋ 9:10 በኃላ ግን ክርስቲያን ሆኖአል።

22:13 ሐናኒያ በአገልግሎቱ ለጳውሎስ ያደረገውን በመመልከት በአዲስ ኪዳን በአማኞች መሃከል በጳጳሳት እና በምዕመናን መሃከል ክፍፍል እንደሌለ መረዳት ይቻላል። ኢየሱስ ያዘዘውን እንመልከት፦

1. እጁን ጫነበት (ሐዋ 9:10)
2. የኢየሱስ ፈቃድ መገለጠ ለጳውሎስ አገልግሎት እጅግ ጠቃሚ ነበር። (ቁ. 15)
3. የጥመቀት ስነ ስርዓት እንዲፈፅም አዘታል።
4. በመንፈስ እንዲሞላ አዟል (ሐዋ 9:17)

ሐናንያ በጌታ እንዲፅም የታዘዘው ሁሉ አሳዳጅ እና ነፋሰ ገዳይ ለሆነ ለጳውሎስ ጌታን በመታዘዝ ፈፅሞታል (ሐዋ 9:13-14)።

22:14 **"የአባቶቻችነ አምላክ"** በአይሁድ አምልኮ ይህ ዐረፍተ ነገር የተለመደ ንግግር ነበር። በመሆኑም ጳውሎስ የሚሰብከብ ወንጌል ያህዌ የላከው ኢየሱስን እንደሆነ እንጂ ሌላ እንግዳ ትምህርት አለመሆኑን ለመግለፅ ያደረገው ጥረት ነው።

▣ **"ፈቃዱን ታውቅ ዘንድ"** የእግዚአብሔር የመጀመሪያው ፍላጐቱ እያንዳንዱ ሰው ልጁን ኢየሱስን እንዲያውቅ ነው። (ዮሐ 6:29.40) የእግዚአብሔር ለጳውሎስ ያለው ፈቃድ ለአህዛብ ወንጌልን እንዲያደርስ ነበር። (ሐዋ 9:15፣ 22:15፣26:16)

▣ **"ፃድቁን ታይ ዘንድ"** ለመሲሁ ለኢየሱስ የተሰጠ ስያሜ ነው። (መዝ 45፡ ሐዋ3:14፣ 7:52፣1ዮሐ 2:1) ጳውሎስ ኢየሱስን ፊት ለፊት የማየት ዕድል ነበረው። (ሐዋ 7:55-56) ፅድቅ የሚለው ርዕስ በተጨማሪ አንብቡ (ሐዋ 3:14)

▣ **"ከአፉ ድምፁን ትሰሙ ዘንድ"** ከሰማይ የወጣውን ድምፅ ያመላክታል፣ (ቁ.8) ነገር ግን በዝርዝር ከቁ.17-21 ተገልፆአል። በእርግጥ ጳውሎስ በአገልግሎቱ በርካታ ራዕዮችን ተመልክቶአል (ቁ.17-21)።

የእግዚአብሔር ድምፅ በትንቡት ሚልኪያስ ዘመንና እስከ መጥምቁ ዮሐንስ ዘመን ድረስ የዝምታ ጊዜ በነብያት ሳይሆን እግዚአብሔር ከሰማይ ውስጥ ሆኖ ወደ ምድር ይናገራል የሚል አፈ ታሪክ ነበር። በመሆኑም ይህንን የአይሁድ አፈ ታሪክ እግዚአብሔረ በዮርዳኖስ ወንዝ በነበረው ስርዓት ተግባራዊ አድርጎታል። (ሉቃ 9:35፣ ማቴ 17:5) ኢየሱስም ለጳውሎስ የተገለጠበት ምክንያት በአንድ ዓላማ ነበር።

22:15 **"በሰው ሁሉ ፊት ምስክር ትሆኑታላችሁና"** የኢየሱስ ወንጌል ሁሉም መካሪ እንዲሆኑ የሚጠራ በመሆኑ አስደናቂ ነው (ዮሐ 3:15፣ 1ጢሞ 2:4፣ 4:10፣ቲቶ 2:11፣ 2ጴጥ 3:9፣ 1ዮሐ 2:2)። ነገር ግን ይህ ማለት ሁሉም ይቀበላሉ ሁሉም ድምፁን አጥርተው ይሰማሉ ማለት አይደለም ነገር ግን ሁሉ ኢየሱስ በከፈለው ማስዋትነት አማካይነት የእግዚአብሔር ፍቅር ተካዮች ናቸው (ቁ. 22)።

ሃናንያ ኢየሱስ ለጳውሎስ የተናገረውን አንድም ሳያስቀር ነግሮታል (ሐወ 9:15)። በአይሁዳውያን ወግና ስርዓት ተይዞ ለነበረ ለጳውሎስ ወደ አህዛበ ሁሉ ሂድና ወንጌል ተናገር የሚለው ቃል ተአማኒነት የሌለው ድምፅ ነበር።

▣ **"በየኸውና በሰማነው"** ጳውሎስ የሰማው እና ያየው ነገር በፍፁም ከህይወቱ የማይጠፋ ነው። በሐዋርያት ስራ ዝርዝር ታሪኩን ሦስት ጊዜ ጠቅሶታል። ጳውሎስ ምናልባት በእያንዳንዱ ምኩራብ የግል ታሪክ እንደናገረ ይገመታል።

22:16 **"ተጠመቅ ከሐጢያትህም ታጠብ"** ከዘሌ 11:25.28.40፣ዘሌ 13:6.34.58 ዘሌ 14:8-9፣ዘሌ 15:5-13.21-22.27፣ ዘሌ 17:15-16፣ዘኃ 8:7.21፣ 19:19፣ ዘዳ 23:11)። የተወሰደ የብሉይ ኪዳን ዐረፍተ ነገር ነው። በዚህ ስፍራ የተጠቀመበት በክርስቶስ በኩል ያገኘውን መንፈሳዊ መንጻታችንን ለመግለጽ ነው (1ቆሮ 6:11፣ ኤፌ 5:26፣ ቲቶ 3:5፣ ዕብ 10:22)። ጥምቀት በቀደመችው ቤተክርስቲያን ውስጥ የእምነት መመለኪያ ተደርጎ ይቆጠር ነበር። ለስነመለኮታዊ ውይይት በ2:38 ላይ ያለውኝ ልዩ ርዕስና ማስታወሻ ተመልከት።

መሃከለኛው ድምፅ ለሁለቱም ማለትም ለጥምቀትና መንጻት አመልካች ነው። ጳውሎስ የራሱን ሃጢአት በማጠብ ሊያስወግደው አይችልም ነገር ግን መጠመቅ ይችላል። (ይህም አይሁዶች ወደ ይሁዲነት ለሚመጡት አሕዛብ የሚያደርጉት ልማድ ነው። በዚህ በአዲስ ኪዳን ይህ ጥቅስ የሚያመለክተው በክርስቶስ በማመናችን ከሃጢያት መንፃታችንን የማየመለክት ነው (1ቆሮ 6:11፣ ኤፌ 5:26፣ ቲቶ315፣ ዕብ 10:22)። በ1ጴጥ 3:21 መሠረት ጥምቀት ምሳሌ ነው እንጂ የሃይማኖት ስርዓት አይደለም።

አዳዲስ ትርጉሞች ይህንን ሃሳብ በጥንቃቄ መተርጉም አለባቸው በተጨማሪም ዐረፍተ ነገሮቹ የተፃፉበትን የግሪኩን ፁሑፍ ሰዋሰዎን ማወቅ ትክክለኛውን ትርጉም ለማግኘት ይረዳል።

▣ **"ስሙን እየጠራህ"** የኢየሱስ ስም በፎርሙላ የሚጠራ ሳይሆን በህዝብ ሁሉ ዘንድ ለምስክርነት የሚጠራ የክርስቲያን ልዩ ምልክት ነው። በጥንቲቱ ቤተክርስቲያን አዳዲስ አማኞችን በውሃ ጥምቀት ስታጠምቅ ኢየሱስ ጌታ ነው በማለት ተጠማቂዎች በሰው ሁሉ ፊት እንዲመሰክሩ ታደርግ ነበር። (ሮሜ 10:19-13፣ 1ቆሮ 1:2፣ 2ጢሞ 2:22) የኢየሱስን ስም መጥራት ብቻ ሳይሆን የአማኞች ልብ ለመንፈሳዊ አለም ቁልፉ ቦታ ነው። (ሐዋ 2:38)

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 22:17-21**

**ወደ ኢየሩሳሌም ከተመለስሁ በኃላ በመቅደስ ስፀልይ ተመስጦ መጣብኝ እርሱም ፈጠን ከኢየሩሳሌም ቶሎ ውጣ ስለ እኔ የምትመሰክረውን አይቀበሉህምና ሲለኝ አየሁት። እኔም ጌታ ሆይ በአንተ፣ የሚያምኑትን በምኩራብ ሁሉ እኔ በወህኒ አገባ እደበድብ እንደ ነበርሁ። እነርሱም ያውቃሉ የሰማዕትህንም የእስቲፋኖስን ደም ባፈሰሱ ጊዜ ራሴ ደግሞ በአጠገባቸው ስቆም ተስማምቼ የገዳዮችን ልብስ እጠብቅ ነበር አልሁ እርሱም ሂድ እኔ ወደ አህዛብ ከዚህ ወደ ሩቅ እልክልሃለሁ አለኝ።**

22:17-21 የሐዋርያው ጳውሎስን ግልፅ ራዕይ ያሳያል። (ሐዋ 18:9-11፣ ሐዋ 23:11፡ ሐዋ 27፣23-24)

22:17 **"ወደ ኢየሩሳሌም ከተመለስኩ በኃላ"** ከጳውሎስ ምስክርነት እንደሚነበበው ወደ ክርስቶስ መቶ ልብ እንደተቀየረ ወደ ኢየሩሳሌም መምጣቱን እንገነዘባለን። ገላ 1:11-24 ነገር ግን ሳይመለስ ለሦስት ዓመታት ቆይቷል።

▣ **"ተመስጦ መጣብኝ"** ሐዋ 10:10 ይመልከቱ።

22:18 ኢየሱስ ጳውሎስን በቀጥታ ንግግር ተነሳና ሂድ በማለተ ከአይሁድ ተንኮልና ሴራ ሲያድነው እንመለከታለን (ሐዋ 9:29)።

22:19 **"ጌታ"** ሁለት ነገሮችን ለማመልከተ ተፈልጐ ሊሆን ይችላል። የአባቶቻችን አምላክ (ቁ. 14)፣ ፃድቁ (ቁ. 14) በዚያ የተሰበሰቡ ሰዎች ስለ ያህዌ ያውቃሉ ነገር ግን በዚያ የነበሩ ክርስቲያኖች ስለ ኢየሱስ ጠንቅቀው አውቀዋል። በኢየሱስ በብሉይ መፅሐፍት ይጠቀሱ ነበር። በእርግጥ አንድ አምላክ የሚለው ለመረዳተ አዳጋች ነው።

▣ **"እኔ በወህኒ አገባና እደበድብ ነበር"** ጳውሎስ ይህንን ክፉ ድርጊት በተደጋጋሚ ያደርግ እንደነበር ከሰዋሰው ስርዓቱ ለመረዳት ይቻላል (ሐዋ 22:4)።

22፡20 ሐዋ 7፡58-59 እና 8፡1 ይመልከቱ ጳውሎስ ከዚህ ቀደም ያሳለፈውን ታሪክ በሐዘን በመተረክ ያደረጋቸውን ሦስት ነገሮች ዘርዝሮአል፡-

1. ከህዝቡ አድማ ጋር ተባብሬ ነበር፡፡
2. በድንጋይ ወገራው ተስማምቼ ነበር፡፡
3. የእስቲፋኖስን ገዳዮች ልብስ እጠብቅ ነበር፡፡

በመሆኑም ጳውሎስ በእስቲፋኖስ ህይወት እና ስብከት አዎንታዊ ተፅኖ ተደርጐበታል፡፡

▣ ማፍሰስ" የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ የሚናገረው ልዩ ርዕስ ተመልከት፡፡

ልዩ

22፡21 "ወደ አህዛብ ወደ ሩቅ እልክሃለሁ አለኝ" ይህ የጳውሎስን ግልፅ ተልእኮ ያሳያል እርሱም የሚሲዮናዊነት ጉዞውን፣ በሮማውያን ነገስታት ፊት እንደሚቆም እና በሮም በቄሳሮች ፊት እንደሚመሰክር የሚያመለክት ነው፡፡

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 22፡22-29**
**እስከዚህም ቃል ድረስ ይሰሙት ነበር፡፡ ድምፃቸውንም ከፍ አድርገው እንደዚህ ያለውን ሰው ከምድር አስወግደው በህይወት ይኖር ዘንድ አይገባውምና አሉ፡፡ ሲጮኹና ልብሳቸውን ሲወረውሩ ትቢያንም ወደ ላይ ሲበትኑ የሻለቃው ወደ ሰፈሩ እንዲያገቡት አዘዘ እንደዚህም የጮኩበትን ምክንያት ያውቅ ዘንድ እየገረፋችሁ መርምሩት አላቸው፡፡ በጠፈርም በገተሩት ጊዜ ጳውሎስ በአጠገቡ የቆመውን የመቶ አለቃ የሮሜን ሰው ያለ ህግ ትገርፉ ዘንድ ተፈቅዶላችኃልን አለው፡፡ የሻለቃውም ቀርቦ አንተ ሮማዊ ነህን ንገረኝ አለው፡፡ እርሱም አዎን አለ የሻለቃው መልሶ እኔ ይህን ዜግነት በብዙ ገንዘብ አገኘሁት አለ፡፡ ጳውሎስም እኔ በእርሷ ተወለድሁ አለ፡፡ ስለዚህ ሊመረምሩት ያስቡት ከእርሱ ወዲያው ተለዩ የሻለቃውም ደግሞ ሮማዊ መሆኑን ባወቀ ጊዜ ፈራ አሳስሮት ነበርና፡፡**

22፡22 በዚህ ቁጥር ውስጥ አይሁድ የራሳቸውን ወግ እና ሃይማኖት ለማስጠበቅ ከፍተኛ ተቃውሞ ያደረጉበት ቦታ ነው፡፡

22፡23

| | |
|---|---|
| NBSB | "ልብሳቸው እየወረወሩ" |
| NKJV | "ልብሳቸውን እየቀደዱ" |
| NRSV | "ልብሳቸውን እየወረወሩ" |
| TEV | "ልብሳቸውን እያወዛወዙ" |
| NJB | "ልብሳቸውን እያርገበገቡ" |

ልብስን መቅደድ፣ ልብስን ማወዛወዝ እና ልብስን ወደ ላይ መወርወር የተቃውሞ ምልክት ነበር፡፡

▣ "ትቢያንም ወደ ላይ ሲበትኑ" በአካባቢው የአለት ድንጋይ ባመኖሩ ጳውሎስ ከድንጋይ ወገራ ሊድን ችሏል፡፡ ትቢያን በራስ ላይ መነስነስ በብሉይ ኪዳን የዘን ምልክት ነበር፡፡ (ኢያ 7፡6፣ 1ሳሙ 1፡2፣ኢዮ 2፡12) በዚህ ዓውድ ደግሞ የተቃውሞ ምልክት ነው፡፡ (ኢሳ 47፣ ሰ.ቆ ኤር2 ሚል1፡10)

22፡24 "ሻለቃው" የአንድ ሺ ወታደሮች መሪ ነው፡፡ (ቁ. 27-29) ይመልከቱ እንዲሁም (ቁ.26-27) የመቶ አለቃው ማለት የመቶ ወታደሮች መሪ ነው፡፡ ነገር ግን የወታደሮቹ ቁጥር አንዳንዴ ሊለየይ ይችላል፡፡ ነገር ግን ይህ ሻለቃ በኢየሩሳሌም ከተማ ፀጥታ ጥበቃ ላይ የተሾመ ነበር፡፡

▣ "ወደ ሰፈሩ" ከመቅደሱ ጋር የተገናኘ የአንቶኒዮ እልፋኝ ወይም ምሽግ ነው፡፡ ይህ ህንፃ የተገነባው በሦርያውያን ዘመን በነህምያ ዕድሜ ነበር፡፡ (ነህ 2፡8፣7፡2) ታላቁ ሄሮድስ ስሙን በመቀየር በማርክ አንቶኒ ስም ሰይሞታል ኢየሩሳሌም በበዓላት ቀናት የነዋሪዋን ሦስት እጥፍ ህዝብ ታስተናግድ ነበር፡፡ በመሆኑም ሮማውያን በዚህ ጊዜ በርካታ ወታደሮችን ከቂሳርያ ወደ አንቶኒዮ ሰፈር ለደህንነት ጥበቃ ያሰማሩ ነበር፡፡

▣ "እየገረፋችሁ መርምሩት" ይህ ሰዎችን ምስጥር ለማሰወጣት የሚደረግ የግርፋት አይነት ነበር፡፡ ከአይሁድ የድንጋይ ወገራ እና ከሮማውየን የበትር ድብደባ ይልቅ የበለጠ የቅጣት አይነት ነበር፡፡ ይህ የመግረፊያ ጅራፍ በመግረፊያው ጫፍ ላይ ብረት ወይም ድንጋይ ወይም አጥንታ የታሰረበት ነበር፡፡

22፡25 "በጠፈርም በገተሩት ጊዜ" የሚገረፉ እስረኛ በቆዳ ገመድ ይታሰር ነበር፡፡

▣ "ያለ ህግ" እነዚህ ወታደሮች የሮማውያንን ህግ ለመተላለፍ እየሞከሩ መሆኑን ያሳያል፡ (1) የሮም ዜግነት ያለው ማንም አይታሰርም ነበር፡፡ (ሐዋ 21፡33 እ 22፡29)፣ (2) የሮም ዜግነት ያለው ማንም አይገረፉም ነበር፡፡ (Livy, History 10:9:4;Cicero,pro Rabirio 4:12-13)፣ (2) በተጨማሪም ጳውሎስ ወንጀል አልሰራም ነበር፡፡ (ሐዋ 16፡37)

22፡27 **"ሮማዊ ነህን"** ይህ ጥያቄ የሚያመለክተው በዚህ ምንባብ የሚያው የሮም ባለስልጣን ጳውሎስ ሮማዊ መሆኑን ተጠራጥሮች ነበር፡፡

22፡28 **"ይህን ዜግነት በብዙ ገንዘብ አገኘሁት"** የሮም ዜግነት ለማግኘት ሦስት መንገዶች ነበሩ፡ (2) ከሮማዊ ቤተሰብ በመወለድ ዜጋ መሆን ይቻላል፣ (2) የአገሪቱን መንግስት በማገልገል ዜግነት ይገኝ ነበር፣ (3) በገንዘብ በመግዛት ዜጋ መሆን ይቻል ነበር (Dio Cassius, Rom, Hist 60:17:15-60)፡፡ በመሆኑም ይህ ባለስልጣን ግሪካዊ ነበር፡፡ ነገር ግን ገላውዲዮስ በሚገዛበት ዘመን በገንዘብ ዜግነቱን ገዝቶታል፡፡ (Claudius lysias, ሐዋ 23፡26) የገላውዲዮስም ባለቤት የሮማዊያንን ዜግነት በብዙ ገንዘብ ገዝታለች፡፡

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 22፡30**
**በማግስቱም አይሁድ፡ የከሰሱ ት በምን ምክንያት እንደሆነ እርግጡን ያውቅ ዘንድ አስበ ፈታው የካህናት አለቆችና ሸንጐውም ሁሉ ይሰበሰቡ ዘንድ አዘዘ ጳውሎስንም አውርዶ በፊታቸው አቆመው፡፡**

22፡30 **"የካህናት አለቆችና ሸንጐውም ሁሉ ይሰበሰቡ ዘንድ አዘዘ"** የሮማውያን ስልጣን ከፍተኛ መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡ ሮማውያን ያለ ቀጠሮ የካህናት አለቆችን የመብሰብ ስልጣን እንደነበራቸው ያሳያል፡፡

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ለመርዳት ነው የተሰናዱት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋነኞቹን ጉዳዮች ለማጤን እንዲረዳ ነው፡፡ ሐሳብ ለማጫር እንጂ መደምደሚያ አይደሉም፡፡

1. ጳውሎስ ለህዝቡ ራሱን ለማሳወቅ ለምን ጥረት አደረገ?
2. ሉቃስ የጳውሎስን የግል ምስክርነቱን ሦስት ጊዜ በተደጋጋሚ መፃፍ ለምን አስፈለገው? (ይህም የደማስቆ መንገድ ታሪክ ነው)
3. ጳውሎስ በሐዋርያት አገልግሎት እንዲቀጥል መንፈስ ቅዱስ ሃናኒያን እንዴት እንደተጠቀመበት አብራሩ?
4. የጳውሎስን ራዕዮች ዝርዝር ለምን ራዕዮቹ አስፈለጉት?
5. ጳውሎስ በህዝቡ ፊት በመቅደስ ከተናገረ በኋላ ያገኘው ውጤት ምን ነበር?

# ሐዋርያት ስራ 23

## የምንባቡ ክፍፍል ለአዲሶቹ ትርጉሞች

| የተየመቅሶ[4] | አኪጆት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጳውሉስ በስብሰባውፊት | የሽማግሌዎች ክፍፍል | ጳውሉስ በሸንጎ ራት | ጳውሎስ በስብሰባው | የጳውሉስ ገፅጻ በሽማግላች ፊት ራት |
| | | (22:30-23:10) | (22:30-23-11) | (22:30-23:11) |
| 22:30-25:5 | 22:30-23:10 | 22:30-23:5 | | |
| | | | 21:1-3 | 23:1-5 |
| | | | 23:4 | |
| | | | 23:5 | |
| 23:6:10 | | 23:6-10 | 23:6 | 23:6-10 |
| | | | 23:7-9 | |
| | በጳውሉስ ላይ ሴራ ተደረገ | ጳውሎስ ወደ ቂሳሪያ ተላከ | 23:10 | |
| 23:11 | 23:11-22 | 23:11 | 23:11 | 23:11 |
| በጳውሎስ ሕይወት ላይ ሴራ ተደረገ | | | በጳውሎስ ሕይወት ላይ ሴራ ተደረገ | በጳውሎስ ላይ አይሁድ፡ሴራ አደረጉ |
| 23-12-22 | | 23:12-15 | 23:12-15 | 23:12-15 |
| | | 23:16-22 | 23:16-18 | 23:16-15 |
| | | | 23:19 | |
| | | | 23:20-21 | |
| | | | 23:22 | |
| ጳውሉስ ወደ ገዥው ፊሊክስ ተላከ | ወደ ፊላክስ ተላክ | | ጳውሎስ ወደ ፊሊክስ ተላከ | ጳውሎስ ወደ ቂሳሪያ፡ ተላለፈ |
| 23:23-36 | 23:23-35 | 23:23-25 | 23:23-25 | 23:23-25 |
| | | 23:26-30 | 23:26-30 | 23:26-30 |
| 23:31-35 | | 23:31-35 | 23:31-35 | 23:31-35 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (ከ **"መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ" ገጽ** vii)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

*ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።*

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. ምንባብ አንድ

2. ምንባብ ሁለት

4. ምንባብ ሦስት

5. ወዘተ. . .

**የቃለ እና የጥምር ቃል ጥናት**

> **አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 23፡1-5**
> **ጳውሎስም ሸንጎውን ትኩር ብሎ ተመልክቶ ወንድሞች ሆይ እስከዚች ቀን ድረስ በመልካም ህሊና ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ፍሬ አለው አለ። ሊቀ ካህናቱም ሐናንያ አፉን ይመቱት ዘንድ በአጠገቡ ቆመው የነበሩትን አዘዘ። በዚያን ጊዜ ጳውሎስ አንተ በኖራ የተለሰነ ግድግዳ እግዚአብሔር አንተን ይመታ ዘንድ አለው አንተ በሕግ ልትፈርድብኝ ተቀምጠህ ሳለህ ያለ ህግ እመታ ዘንድ ታዛለህን? አለው። በአጠገቡ የቆሙትም የእግዚአብሔርነገረ ሊቀ ካህናት ትሳደባለህን? አሉት ጳውሎስም ወንድሞች ሆይ ሊቀ ካህናት መሆኑን ባላውቅ ነው። በሕዝብህ አለቃ ላይ ክፉ ቃል አትናገር ተብሎ ተፅፎአልና አላቸው።**

23፡1

| | |
|---|---|
| NASB, NRSV | **"በትኩረት ሲመለከት"** |
| NKJU | **"አጥብቆ ሲመለከት"** |
| TEV | **"በቀጥታ አየ"** |
| NSB | **"በትኩረት ተመለከተ"** |

ይህን ቃል ፀሐፊው ሉቃስ በተለምዶ ይጠቀበታል፤ ጳውሎስ ቃልን የተጠቀመበት በ2ቆሮ 3፡7፣13 ብቻ ነው።

▣ **"ሸንጎው"** ሐዋ 4፡5 ይመልከቱ።

▣ **"ወንድሞች"** ሐዋሪያው ጳውሎስ አይሁድን ወንድሞች ብሏቸዋል። ሐይ 13፡26፣38;22፡1፣5;6) አይሁድም ጳውሎስን ወንድም ብለውታል። ሃናኒያም "ወንድሜ ሳውል" ብሎታል። (ሐይ 9፡17) እና በእየሩሳሌም ያለችው ቤተ ክርስቲያን ተመሳሳይ ስያሜ ሰቷዋለች። የአይሁድ አማኞች ሁሉ ወንድሞች ተብለዋል (ሐዋ 9፡3010፡23;11፡1,12;12;17;15፡3,13,22)። ደቀ መዛሙርት እና የግሪክ አማኞች በዚህ ስያሜ ተጠርተዋል (ሐዋ 11፡29;18:27;ሐይ 16፡2,40)።

▣ **"በእግዚአብሔር ፊት ኖሬአለሁ"** ይህ በትክክል አመልካች ነው። *ፖሊቲየስ* ከሚለው ቃል ነው በእግዚአብሔር *ፖ*ለቲካ ወይም *ፖ*ሊሲ የሚለውን ቃል ያገኘነው። ይህም ጥቅስ ከዜግነት ጋር የተዛመደ ነው። ፊሊ 1፡27 ጳውሎስ በአይሁድ ስርዓት የነበረበትን ሃላፊነት ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ፊት እንደተወጣ ይናገር ነበር።

▣

| | |
|---|---|
| NASB | **"ፍፁም መልካም ሕሊና"** |
| NKJV | **"በመልካም ሕሊና"** |
| NRSV | **"ንፁህ ህሊና"** |
| TEV | **"ህሊናዬ በፍፁም ንፁህ ነው"** |
| NJB | **"ፍፁም ንፁህ ህሊና"** |

ሐዋሪያው ጳውሎስ "ሕሊና" የሚለውን ቃል ለቆሮንስ ሰዎች በፃፋ ደብዳቤ ላይ ደጋግሞ ተጠቅሞበታል (ሐዋ 4፡4;8፡7,10,12;10፡25,27,28,29 2 ቆሮ1፡12;4;2;5፡11) ሕሊና መልካሙን እና ክፍን እንድለኝ እግዚአብሔር ለሰው የሰጠው ነው (ሐዋ 23፡1) ሕሊናችን በቀደመው ሕይወታችን፣ በተሳሳተ ምርጫ ወይም በጌታ መንፈስ ተፅኖ ስር ሊሆን ይችላል።

የአይማኖት ሕሊና በእግዚአብሔር ቃል ሊታነፅ ይገባል። (1ጢሞ 3፡9) እግዚአብሔር ሕሊናችን ባወቀው መጠን ነው፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ቃል እና በመንፈስ ቅዱስ ብርሃን በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ባለ ዕውቀት ለማደግ እራሳችን መስጠት ይጠበቅብናል።

▣ **"እስከዚች ቀን ድረስ"** ጳውሎስ ተመሳሳይ ንግግር ተጠቅሟል። (2 ቆሮ 1፡12፡ 2 ጢሞ 1፡13) የጳውሎስ ምኞት ነው (ሮማ 7፡23) የጳውሎስን ስንመለከት ትንታኔውን ይመልከቱ (ሮማ 1-8) እግዚአብሔር በስሞች ላይ የሚፈርደው ህጉን በመተላለፋቸው እና በህሊናቸው ዕውቀት ነው። (ሐይ 3፡20; 4፡15; 5፡20)

23፡2 **"ሊቀ ካህናቱ ሃናኒያ** በዕብራይስጡ ስሙ **"ሃናኒያ"** ነው፡፡ ይህ በሉቃ 3፡2 ዮሐ 18፡13 ወይም ሐይ 4፡7 የሚገኘው አናኒያ አይደለም፤ ነገር ግን ይህ ሃናኒያ በሮድስ የተሾመው ነው፤ እርሱም ከ 47-59 ዓ.ም ነግሷል፡፡

የታሪክ ፀሐፊው ጆሴፈስ ስለ ሊቀናህናቱ የፃፈውን እንመልከት፡-

1. ሊቀ ካህን ተደርጎ ሲሾም፡- (Antiq 20:5:2; wars 2.12.6)
2. ሊቀ ካህኑን ልጁ ወይም የሮም እስረኛ ሆነዋል (Antiq 20.6.2)
3. በአይሁድ አክራሪዎች ሊቀ ካህኑና ወንድሙ ተገድለዋል (wars, 2:17.9)፡፡

ጆሴፈስ የአይሁድን ታሪክ በመዘገብ የታወቀ የታሪክ ፀሐፊ ነው፡፡

▣ **"አፉን ይመቱት ዘንድ"** የውርደት ምልክት ነው፡፡ (ዮሐ 18፡22)

23፡3 **"እግዚአብሄር አንተን ይመታ ዘንድ"** ጆሰፈስ በፃፋ መፅሐፍ ላይ ዝርዝር ታሪኩ ይገኛል wars 2.17.9

▣ **"በኖራ የተለሰነ ግድግዳ"** ቃሉ ስለምን እንደሚናገር ግልፅ አይደለም፡፡ ይህ ዓረፍተ ነገር ሁለት መላምቶች አሉት፡ (1) አይሁድ ግብዝነትን ለመግለፅ ይጠቀሙበታል (ጣቱ 23.27)፣ (2) ቃሉ የተወሰደው (ከሕዝ 13፡10-15)፡፡

▣ **"በህግ ልትፈርድብኝ"** ለዘሌ 19፡15 የተጠቀሰ ነው፡፡ እንደገና ዮሐ 7፡51 ላይ ይመልከቱ፡፡

23፡5 **"ወንድሞች ሆይ ሊቀ ካህን መሆኑን ባላውቅ ነው፡፡"** ጳውሎስ ሊቀ ካህኑን ያላወቀበት ምክንያቶች፡ (1) የአይን ችግር ስላነበረበት፣ (2) በኢየሩሳሌም ብዙ አመት አልኖረም፣ (3) ሊቀ ካህኑ የማዕረግ ልብሱን ባለመልበሱ፣ (4) ተናጋሪውን አልለየውም፣ (4) የሊቀ ካህኑ ክፍ ተግባሩ፡፡

▣ **"ተብሎ ተፅፎአልና"** ጳውሎስ የብሉይ ኪዳን ህግጋት የሚያከብር መሆኑን አሳይ (ዘፀ 22፡28)፡፡

> **አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 23፡6-10**
> **ጳውሎስ ግን እኩሌቶቹ ሰዱቃውያን እኩሌቶቹም ፈረሳውያን መሆናቸውን አይቶ ወንድሞች ሆይ እኔ ፈሪሳዊ ልጅ ነኝ ስለ ተስፋና ስለሙታን መነሣት ይፈርዱብኛል ብዬ በሸንጎው ጮሀሁ፡፡ ይህን ባለ ጊዜ በፈሪሳዊያን እና በሰዱቃውያን ጥል ሆነ ሸንጎውም ተለያየ፡፡ ሰዱቃውያን ትንሳኤም መላእክም መንፈስም የለም የሚሉ ናቸውና ፈሪሳውያን ግን ሁለቱን ያምናሉ ታላቅ ጩኸትም ሆነ ከፈሪሳውያንም ወገን የሆኑት ፃፎች ተነስተው በዚህ ሰው ላይ ምንም ክፍ ነገር አላገኘንበትም መንፈስ ወይም መላእክ ተናግሮት ይሆን ብለው ተከራከሩ ብዙ ጥልም በሆነ ጊዜ የሻለቃው ጳውሎስን እንዳይገነጣጥሉት ፈርቶ ጭፍሮቹ ወርደው ከመካከላቸው እንዲነጥቁት ወደ ሰፈሩም እንዲያገቡት አዘዘ፡፡**

26፡6 "ጳውሎስ ግን" ጳውሎስ በሊቀ ካህናቱ ተደማጭነት እንዲያገኝ የዘየደው መፍትሄን ያሳያል

▣ **"ሰዱቃውያን"** (ሐይ 4፡1) ይመልከቱ

▣ **"ፈሪሳውያን"** ጳውሎስ ፈርሳዊ ነበር፡፡ (ሐዋ 2፡5፤ፊሊ.3፡5-6)

▣ **"ስለ ተስፋና ስለሙታን ትንሳኤ"** ጳውሎስ በሳዱቃውያ እና በፈሪሳውያን መሃከል ያለውን የስነ መለኮት ልዩነት በማንሳት የሁለቱን ልዩነት ገልጦ አሳያ (ኢዮ1፡14,19፡23-27,ዳን 12፡2)፡፡ ይህም ክፍል ጉባኤው በሁለቱ ሃሳቦች ላይ ያለውን የእርስ በርስ መቃረን የሚያሳይ ነው (ቁጥር 7-10)፡፡

23፡7 **"ሸንጎውም ተለያየ"** የቃሉ ቀጥተኛ ትርጉም "መቀደድ" (ሉቃ 5፡36,23፡45) በአንድ ቡድን መሃከል የተነሳውን ክፍፍል ያሳያል (ሐይ 14፡4,23፡7) እነዚህ የአይሁድ ሁለት የሃይማኖት ፅንፈኞች በመሃከላቸው ልዩነት ነበር፤ በመሆኑም ጳውሎስ ይህንን ልዩነታቸውን ተጠቀመበት፡፡

23፡8 **"መንፈስ ወይም መልአክ"** ሐረጉ የሚያመለክተው በመንፈስ ዓለም ስለሚገኙ ሁለት ምልአት ስብእና ስላላቸው አካላት ነው፡፡ (ዕብ 1፡5,13 እና 14)

ሰዱቃውያን የክፍን እና የእግዚአብሔርን መልካሙን መንፈሳዊ ዓለም መኖር አያምኑም (Loroastrian dualism) ነገር ግን ፈሪሳውያን የብሉይ ኪዳንን የመንፈስ ዓለምን ትምዕርት ከፋርስ የመንፈስ ዓለም እምነት የራሳቸውን ስነ መለኮት እንደሰሩ ብዙ አስረጂዎች አሉ፡፡

23፡9 **"ፃፎች"** የሙሴን መፅሐፍ እና በንግርት የተናገሩትን ታሪኮች በመፃፍ የታወቁ ናቸው፤ አብዛኞቹ ፈሪሳውያን ናቸው፡፡

▣ **"ይህ ሰው"** ሐረጉ ግልፅ የሆነን ስሙ የታወቀን ሰው የሚያመለክት ነው፡፡

▣ "ይሆናል" ቃሉ አንድ ነገር ያልተረጋገጠ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ሶዱቃውያን ጳውሉሽ መልአክ ወይም መንፈስ ተናግሮኝ ይሆናል፡ አሉ እንጂ እርግጠኞች አልነበሩም እነዚህ ሰዎች መፅሐፍ እውቀት አለ የሚሉ ቢሆኑም ነገር ግን እነርሱ ግራ የገባቸው ነበሩ፡፡

23፡10 "**ጭፍሮቹ ወርደው ከመካከላቸው እንዲነጥቁት ወደ ሰፈሩም እንዲያገቡት አዘዘ**" የሮም መንግስት ሁለት ጊዜ የጳውሎስን ይህወት ታድጓል ጳውሎስ መንግስትን የእግዚአብሔር አገልጋዮች እንደሆኑ ተናግሯል፡፡ (ሮማ 13) ለተጨማሪ ግንዛቤ ሁለተኛ ተሰሎንቄን ያንብቡ፡፡

> **አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 23፡11**
> [11]**በሁለተኛውም ሌሊት ጌታ ባጠገቡ ቆሞ ጳውሎስ ሆይ በኢየሩሳሌም ስለ እኔ እንደመስከርህ እንዲሁ በሮማ ትመሰክርልኝ ዘንድ ይገባሃልና አይዞህ አለው፡፡**

23፡11 "ጌታ ባጠገቡ ቆሞ" ጳውሎስን ለማበረታት ጌታ በራዕይ እንደገና ተገለጧ፡፡ (ሐዋ 18፡9-10, 22፡17-19,27፡23-24) ጳውሎስ የሚጠራጠርና ተስፋ የሚቆርጥ ማንነት አይታይበትም፡፡

▣ "አይዞህ" በሉቃስ ፅሁፍ ውስጥ ቃሉ የተፃፈው ለመጀመሪያ ጊዜ ነው፡፡ ኢየሱስ ይህንን ቃል በርካታ ጊዜ ተጠቅምበት መመልከት ይቻላል ማርቴ 9፡2, 22, 14፡27, ዮሐ 16፡33)

▣ "**በሮሜ ትመሰክርልኝ ዘንድ ይገባልና**" ጳውሎስ እንዲታሰርና በቄስር ፊት እንዲቆም የጌታ ፈቃድ ነበር የእግዚአብሔር ወንጌል በሮም ሊሰበክ ይገባ ነበርና፡፡ (ሐዋ 19፡21; 22፡21)

> **አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 23፡12-15**
> [12]**በጠባም ጊዜ አይሁድ ጳውሎስን እስኪገድሉ ድረስ እንዳይበሉና እንዳይጠጡ በመሃላ ተስማሙ፡፡ ይህን ሴራ ያደረጉት ሰዎች ከአርባ ይበዙ ነበር፡፡ እነርሱም ወደ ካህናት አለቆችና ወደ ሽማግላቹ መታ ጳውሉስን እስክንገድል ድረስ ምንም እንዳንቀምስ ተረጋግመን ተማምለናል እንግዲህ እናንተ ከሸንጎው ጋ ር ሆናችሁ ስለ እርሱ አጥብቃችሁ እንደምትመረምሩ መስላችሁ ወደ እናንተ እንዲያወርደው ለሻለቃው አመልክቱት እኛም ሳይቀርብ እንድንገድለው የተዘጋጀን ነን አሉአቸው፡፡**

23፡12-15 በዚህች ምንባብ ውስጥ የአይሁድን ስውር የሆነነ የግድያ እቅድ እንመለከታለን፤ በኢየሱስ ሕይወት እና አገልግሎት ላይ ተመሳሳይ ነገር ተደርጓል፡፡

23፡13 "ከአርባ የሚበልጡ" አርባ ቁጥር ርዝመትን ለማመልከት አይሁዶች የሚጠቀሙበት ቁጥር ነው፤በዚህ ምንባብ ውስጥ ለሰዎች በመሆኑ በቁጥር ልክ የሰዎጨ ብዛት አርባ ሊሆን ይችላል፡፡

23፡14 የካህናት አለቆችና ሽማግሎዎች የእስራኤልን የዋኩራብ ስብስብ የሆነውን ሸንጎ ለማመልከት ነው፡፡ (ሐዋ 4፡5)

▣

| | |
|---|---|
| NASB | "በእርግማን መሃላ እራሳችንን አስረናል" |
| NKJV | "በትልቅ መሃላ እራሳችንን አስረነዋል" |
| NRSV | "ጥብቅ በሆነ መሃላ እራሳችንን አስረናል" |
| TEV | "የእርግማን ኪዳን ወስደናል" |
| NIB | "የእርግማን ኪዳን አድርገናል" |

የእንግሊዘኛው ቃል "በእርግማን እራሳችንን ረግመናል" የሚል ትርጉም ተሰቶታል፡፡ ነገር ግን ጳውሎስን ሊገድሉት አልቻሉም፤ እስከሚገድሉት ድረስ ምግብ ያለመመገባቸው ወደ ሞት ቢያደርሳቸው መሃላ የገቡበት ጉዳይ የሚቋረጠው ግባቸው ሲፈፅሙ ብቻ ነበር፡፡

> **ልዩ ርዕስ፡ መርገም (Anathema)**
> በዕብራይስጥ ቋንቋ ውስጥ 'መርገም' ለሚለው ቃል ብዙ ዓይነት ትርጉሞች ይኖራሉ፡፡ (ሄሬም) የሚለው ቃል አንዳንዴ ለእግዚአብሔር ለሚሰጥ ነገር ተጠቅሞበታል (በሰባዎቹ ሊቃውንት በተተረጎመው ዘሌዋ 27፡28)፡፡ በተለይም ለጥፋት (ዘዳ 7፡26፣ ኢያሱ 6፡17-18፣ 17፡12) 'በቅዱስ ጦርነት' ሀሳብ ነበር ጥቅም ላይ የዋለው፡፡ እግዚአብሔር ከንዓንና እና ኢያሪኮን ተናግሮአቸዋል፡፡ ይህም ደግሞ እንደ 'በኩር ፍሬ' ይታይ ነበር፡፡
> በአዲስ ኪዳን ውስጥ አናቴማ (Anathema) የሚለው ቃል ተዛማጅ የሆኑ ሀረጎች በተለያዩ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡
> 1. ለእግዚአብሔር የሚቀርብ መስዋዕት ወይም ስጦታ (ሉቃ 21፡5)
> 2. ለመግደል የሚደረግ መሀላ (መረጋገም) የሐዋ 23፡14
> 3. መርገም እና መማል ማር 14፡71
> 4. ኢየሱስን በሚመለከት የተደረገ ንጽጽር 1ቆሮ 12፡3
> 5. ለእግዚአብሔር ፍርድ ወይም ጥፋትን በተመለከተ የተሰጠ ስጦታ (ሮም 9፡3፣ 1ቆሮ 16፡22፣ ገላ 1፡8-9)

አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 23፡16-25
**የጳውሎስ የእህቱ ልጅ ግነረ ደባቸውን በሰማ ጊዜ መጥቶ ወደ ሰፈሩ ገባና ለጳዉሎስ ነገረው፡፡ ጳውሎስም ከመቶ አለቆች አንዱን ጠርቶ ይህን ብላቴና ወደ ሻለቃው ውሰድ የሚያወራለት ነገር አለውና አለው እርሱም ይዘት ወደ ሻለቃው ወሰደውና ይህ ብላቴና የሚነግርህ ነገር ስላለው እስረኛው ጳውሎስ ጠርቶ ወደ አንተ እንድወስደው ለመነኝ አለው የሻለቃውም እጅን ይዞ ፈቀቅ አለና ለብቻው ሆኖ የምታወራልኝ ነገር ምንድነው? ብሎ ጠየቀው እርሱም ጳውሎስ ከፊት ይልቅ አጥብቀህ እንደምትመረምር ነገ ወደ ሸንጎው ታወርደው ዘንድ ሊለምኑህ ተስማምተዋል፡፡ እንግዲህ አንተ በጅ አትበላቸው እስኪገሉት ድረስ እንዳይበሉና እንዳይጠጡ ተማምለው ከእነርሱ የሚበዙት ሰዎች ያደቡበታልና አሁንም ተዘጋጅተዋል፡፡ የአንተን ምላሽ ይጠብቃሉ አለው፡፡ የሻለቃውም ይህን ነገር ለእኔ ማመልከትህን ለማንም እንዳትገልጥ ብሎ ካዘዘ በኃላ ብላቴናን አሰናበተው፡፡**
**ከመቶ አለቆቹም ሁለት ጠርቶ ወደ ቂሳሪያ ይሄዱ ዘንድሁለት መቶ ወታደሮችንና ሰባ ፈረሰኞችን ሁለት መቶም ባለ ጠር መሣሪያዎችን ከለሊቱ በሦስተኛው ሰዓት አዘጋጁ አላቸው ጳውሎስንም ወደ አገር ገዥዳ ልሊክስ በደህና እንዲያድሱት የሚያስቀምጡበትን ከብት ያዘጋጁ ዘንድ አዘዛቸው፡፡ ደብዳቤዎ ፃፈ እንዲህ የሚል፡**

23፡16 "ጳውሎስ ቤተሰብ የሚታወቅ ዝርዝር ማስረጃ የለም በመሆኑም የእህቱ ልጁ ሴራቸውን እንዴት እንዳወቀ፡ አይታወቅ፤ ምናልባ የፈረሳውያን ወገን ሊሆን ይችላል፡፡"

23፡21 የግዳያው ሴራ የሮማውያንንም ዘቦች የሚያቃጠልል ነበር፡፡

23፡23 ጳውሎስን የሚጠብቁ ሁለት መቶ ወታደሮች፣ ሰባ ፈረሰኞች ሁለት መቶ ባለጦር መሳሪያዎች ነበሩ፡፡

▣ "በሦስተኛው ሰዓት" በሮማውያን ሰዓት አቆጣተር ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ነው፡፡ "ቂሳሪያ" በፍልስጥኤም ምድር ሮማዉያን ይህችን ከተማ ወና ቦታ አድርገዋት ነበር፡፡

▣ "ባለ ጦር መሳሪያዎች" የቃሉ ቀጥተኛ ፍቺ "በቀኝ በኩል መሣሪያ የሚታጠቁ" ማለት ነው፡፡ NEB የሚለው ቀላል ያለ መሳሪያ የታጠቁ፤ NSB ደግሞ የሚለው በቀኝ በኩል የታሰረ እስረኛ ወይም ሌላ ፈረስ የያዘ ወታደር የሚል ቀጥተኛ ፍቺ ይሰጣል፡፡

23፡24 "ፈሊክስ" የሮማውያን ፀሐፊ ታይተስ (histories 5:9 Annals 12:54) ፈሊክስ ጨካኝ እና ረብ የሌለው ሰው ነበር፡፡ ስልጣኑን ያገኘው ከገላውዲዮስ ባልንጀራ በነበረው በወንድሙ በኩል ነበር፤ ከ52-59 ዓ.ም ነገሰ፡፡

አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 23፡26-30
**ከቀላውዲዮስ ሉስዮስ ወደ ክቡር አገር ገዥ ወደ ፊልክስ ሰላም ለአንተ ይሁን ይህን ሰው አይሁድ ይዘው ሊገሉት ባሰቡ ጊዜ ከጭፍሮቹ ጋር ደርሼ አዳንኩት ሮማዊ እንደሆነ አውቄ ነበርና የሚከሰስበትንም ምክንያት አውቅ ዘንድ አስቤ ወደ ሸንጎአቸው አወርድሁት በህጋቸውም ስለመከራከር እንደከሰሱት አገኘው እንጂ ለሞት ወይም ለእስራት የሚያደርስ ክስ አይደለም በዚህ ሰው አይሁድ ሴራ እንዲያደረጉበት ባመለከቱኝ ጊዜ ያን ጊዜውን ወደ አንተ ሰደድሁት ከሳሾቹንም በፊትህ ይከሱት ዘንድ አዘዝቸው፡፡ ደህና ሁን**

23፡26-30 ጳውሎስ በስልጣን ላይ ባሉት ሰዎች ነገሩ እየታየለት መሆኑን የሚያወሳ ምንባብ ነው (ሐዋ 25፡12)

23፡26 በጊዜው የነበሩት የባለ ስልጣኖች የስም ዝርዝር ነው፡፡

23፡29 ሉቃስ ለማሳየት የፈለገው ክርስቲያኖች በፍርድ ፊት ያደረጉት የነበረውን ክርክር ነበር፤ ከዚህም የተነሣ ሮማውያን አይሁዶችን ይንቁአቸው ነበር፡፡

አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 23፡31-35
**ወታደሮቹም እንደ ታዘዙት ጳውሉስን ይዘው በሌሊት ወደ አንቲጳፕሪስ አደረሱት በነገውም ከእርሱ ጋር ይሄዱ ዘንድ ፈረሰኞችን ትተው ወደ ሰፈር ተመለሱ፡፡ እነዚያም ወደ ቂሳሪያ ገብተው ደብዳቤውን ለአገር ገዥ በሐጡ ጊዜ ጳውሎስንም በፊቱ አቆሙት፡፡ ካነበበውም በኃላ የወዴት አውራጃ እንደ ሆነ ጠየቀው የኪልቅያ ሰው መሆኑንም ባወቀ ጊዜ ከሳሾችህ ደግሞ ሲመጡ እሰማሃለሁ አለው፡፡ በሄሮድስ ግቢ ውስጥ ይጠብቁት ዘንድ አዘዘ፡፡**

23፡31 "በሌሊት ወደ አንቲጳፕሪስ አደረሱት" ይህች ከተማ የተገነባችው በታላቁ ሄሮድስ ሆኖ የከተማይቱ ስም የተሰየመው በአባቱ በአንቲጳስ II ነበር፡፡ ጳውሎስን ወደዚህች ከተማ ሲያመጡት ረጅም ጉዞ ተጉዘው ነው፤ ከ30 -40

ማይልስ፡፡ በአሁኑ ጊዜ ከተማይቱ አትታወቅም፡፡ እግረኛ ወታደሮች እዚህ ቦታ ተመልሰዋል (ቁ 32) ምክንያቱም፡ (1) የአሕዛብ ክልል ስለነበረ ነው፣ (2) የመሪቱ አቀማመጥ ገላጣ እና ሜዳ በመሆኑን ለጥቂት እንዳይገለጡ በመፍራት በፈረስ ጉዛአቸውን ያደረጉ ዘንድ ተገዳዋል፡፡

23፡33 **"አገር ገዥ"** የሮማውያን የስልጣን ማዕረግ ስያሜ ነው፡፡

23፡34 "የወዴት አውራጃ እንደሆነ ጠይቀው" በሮማውያን ግዛት ሦስት የተለያዩ ክፍፍሎች ነበሬ፡ (1) መንገስት (ቄሳሮች)፣ (2) ሸንጎ፣ (3) የአውራጃ አገሮችን የሚገዛ (ምሳሌ፡- ሄሮድስ)፡፡

23፡35 **"ከሳሾችህ ደግሞ ሲመጡ"** የጳውሎስ ከሳሾች ከእስያ የመጡ አይሁዳውያን ናቸው፤ ጳውሎስ በዚያ ሃገራቸው በተከለከሉ የአይሁድ ምኩራቦች የሰበክ ነበርና ነገር ግን በዚህ ክስ ላይ አልተገኙም፡፡

▣ **"በሄሮድስም ግቢ ውስጥ"** ሮማውያን ለጳውሎስ ርህራሄአቸውን እያሣዩት ነው፡፡ (ሐዋ 24፡23) ሐዋሪያው ጳውሎስ ቀድሞ አስዳጅ ሆኖ የሚኖርበትን የቤተመንግስት ግቢ አሁን ደግሞ ስለክርስቶስ ተከሶ እንዲያርፍ ተፈቀደከለት፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ የፐራይቶሪየም ጠባቂ/የአገረ ገዢው ወታደሮች**

ይህ ቃል ከመጀመሪያ የሚያመለክተው የሮም ጀነራል ድንኳን ነው (ፐራይተር) ነገር ግን ሮም ከተቆጣጠረች በኋላ ቃሉ አስተዳደራዊ ትርጉሙን በያዘ መልኩ ተጠቅሷል፡፡ ይህም የፖለቲካ ወይም የወታደራዊ አስተዳደር መምሪያን ለማመልከት ነበር (ማቴ 27፡27፣ ዮሐ 18፡28,33፣ 19፡9 ሐዋ 23፡35)፡፡

ይሁን እንጂ በመጀመሪያው የሮማውያን ዓለም (ዘመን) ቃሉ ጥቅም ላይ የዋለው የኢምፔሪያል ወታደሮች መኮንኖችን ለማመልከት ነበር፡፡ ይህ የተማረ ወገን (ወታደር) የተጀመረው በአውግስጦስ ሲሆን በኋላ ግን የከተመው (በሮም) በጢባርዮስ ነበር፡፡ እነርሱም (1) ተመሳሳይ ማዕረግ ነበራቸው (2) እጥፍ ክፍያ ይቀበሉ ነበር (3) ልዩ መብት ነበራቸው (4) ኃያል በመሆናቸው አፄ ለመሆን ያላቸው ምርጫ ሁልጊዜ ይከበራል፡፡ ይህ ከኮንስተንቲን ይህ ቡድን እስከ ኮንልታንቴን አገዛዝ ዘመን ይህ የተማረ ቡድን በፖለቲካ ኃያል ሆኖ ቆይቶ ነበር፡፡

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ለመርዳት ነው የተሰናዱት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋነኞቹን ጉዳዮች ለማጤን እንዲረዳ ነው፡፡ ሐሳብ ለማጫር እንጂ መደምደሚያ አይደሉም፡፡

1. ጳውሎስ በሸንጎ ፊት ያቀረበውን የመከላከያ ሃሳብ ዝርዝርህ አስረዳ
2. ጳውሎስ ለአይሁድ ወግ እና ህግጋት ታማኝ ነውን?
3. የጳውሎስን ቤተሰብ ለማወቅ የሐዋርያት ስራ መፅሐፍ ያለው ድርሻ ምንድነው?

# የሐዋርያት ስራ 24

## የምንባቡ ክፍፍል በአዲሶቹ ትርጉሞች

| የተየመቅሰ[4] | አኪጀት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጳውሎስን የተቃወሙበት ምክንያት | የሰዱቃውያን ክስ | ጳውሎስ በለሊክስ ፊት | ጳውሎስን የተቃወሙበት ምክንያት | በለሊክስ ፊት ምክንያት |
| 24፡1-9 | 24፡1-9 | 24፡1-2a | 24፡1-2a | 24፡1-9 |
| | | 24:2b-8 | 24:2b-9 | |
| | | 24:9 | | |
| የጳውሉስ የተቋውሞ ሃሳብ በፊሊክስ | ተቃውሞ በልሊክስ | | የጳውሉስ የተቋውሞ ሃሳብ በፊሊክስ | |
| 24፡10-21 | 24፡10-21 | 24፡10a | 24፡ 10a | 24፡10a |
| | | | | የጳውሉስ ንግግር በሮም መንግስት ፊት |
| | | 24፡10b፡21 | 24፡10b-16 | 24፡10b-13 |
| | | | | 24፡14-61 |
| | | | 24፡17-21 | 24፡17-21 |
| | የፊሊክስ ውሳኔ | | | ጳውሉስ በቂሣሪያ ግዞተኛ ሆነ |
| 24፡22-23 | 24፡22-27 | 24፡22-23 | 24፡22-23 | 24፡22-23 |
| ጳውሉስ በክስ ተያዘ | | | ጳውሎስ በለሊክስ እና በዱርሲላ ፊት | |
| 24፡24-26 | 24፡24-26 | 24፡24-26 | 24፡24-26 | 24፡24-26 |
| 24፡27 | | 24፡27 | 24፡27 | 24፡27 |

‹

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (ከ **"መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ" ገጽ** vii)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

*ይህ የጥናት* *<u>መመሪያ</u>* *ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።*

*ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።*

1. ምንባብ አንድ

2. ምንባብ ሁለት

3. ምንባብ ሦስት

4. ወዘተ…

*የቃል እና የቃል ጥናት*

> **አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 24፡1-2**
> **1ከአምስት ቀንም በኃላ ሊቀ ካህናቱ ሐናንያ ከሽማግሌዎች እና ጠርጠሉስ ከሚሉት ከአንድ ጠበቃ ጋር ወርዶ እነርሱም ስለ ጳውሉስ ለአገር በገዥ አመለካከቱ በተጠራም ጊዜ ጠርጠሉስ ይከሰው ዘንድ ጀመር እንደህ እያለ፡-**

24፡1 “**ሊቀ ካህናቱ ሐናንያ**” ሐይ 23፡2 ይመልከቱ፡፡

▣ “**ወርዶ**” ለአይሁድ ሁሉ ኢየሩሳሌም ከፍ ያለች ነች ነገር ግን ሌሎቹ ከተሞች እታች እንዳሉ ይቆጠራሉ፡፡

▣ “**ሽማግሌዎች**” በብሉይ ኪዳን በእድሜ ሽማግሎዎች የሆኑት የነገድ መሪዎችን ነው፤ከባቢሎን ምርኮ በኃላ ይህ ቃል ለባለጠጎች እና በኢየሩሳሌም ለነበሩ በሕዝብ ለታወቁ ሰዎች ስያሜው አገልግላል፤በአዲስ ኪዳን ሊቀ ካህናት፣ ፀሐፍት፣ እና የቤተክርስቲያን መሪዎች ስያሜውን አግኝተው ነበር (ሐይ 23፡6-10)፡፡

▣ “**ጠርጠሉስ**” ይህ ሰው በልምድ ጠበቃ የሆነ ነበር (NKJU) የግሪኩ “ሬማ” ወይም “የተገለጠ ቃል” የሚል ስያሚ ተሰቶታል የሽማግሌዎቻችን ጉዳይ ለሮማዉያን ገዥዎች ስርዓት ባለው መንገድ በፍርድ ቤት የቀረብ ነበር፡፡

> **አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 24፡2-9**
> **ክቡር ፊሊክስ ሆይ በአንተ በኩል ብዙ ሰላምናገኝ ለዚህም ሕዝብ በአሳብህ በየነገሩ በየስፍራውም መልካም መሻሻል ስለሚሆንለት በፍፁም ምስጋና እንቀበለዋለን፡፡ ነገር ግን እጅግ እንዳላቆይህ በቸርነትህ በአጭሩ ትስማን ዘንድ እንለምንሃለን ይህ ሰው በሽታ ሆኖ በአለም ባሉ አይሁዶች ሁሉ ሁከት ሲያስነሣ የመናቀፍቃን የናዝራውያን ወገን መሪ ሆኖ አግኝተናል መቅደስንም ደግሞ ሊያረክስ ሲሞክር ያዝነው፡ እንደ ሕጋችንም እንደፈርድበት ዘንድ ወደድን ነገር ግን የሻለቃ ሉስዩክ መቶ ከእጃችን ወስደው ከሳሾቹንም ወደ አንተ ይመጡ ዘንድ አዘዘ አንተም ራስህ እርሱን መርምረህ እኛ ሰለምንካሰበት ነገር ሁሉ ልታውቅ ትችላለህ አይሁድም ደግሞ ይህ ነገር እንዲሁ ነው እያሉ ተስማሙ፡፡**

24፡2b-4 ይህ መሰረት የሌለው ክስ መሆኑን ከክሱ ጭብጥ መረዳት አያዳግትም ነገር ግን ለሊክስ ጨካኝ ሰው ነበር (Tacitus, histories 5:9 እና 12፡12) ልሊክስ ወንድሙ በመተካት ነበር ወደ ስልጣን የመጣው እርሱም “ፓላስ” የሚባለው ነው፡፡ በህዝቡ ጥያቄ በኔሮ ከስልጣን ሊወገድ ይችል (Josephus, war 2,12,8-13,17)

24፡2b “**ብዙ ሰላም ስለምናገኝ**” የአይሁድ ፅንፈኝነት የነበረውን አመፅ ልለክሸ መቆጣጠሩን እየመሰከሩለት እና እያመሰገኑት ነው፡፡

24፡5 “**ይህ ሰው አገኘነው**” የፀሐፊው የሉቃስ አንዱ አላማው ይህንን የሮማውያንን የወንጌል ተቃውሞ ለማሳወቅ ነው፡፡ ከዚህም የተነሣ ሉቃስ በፍርድ ቤት የተከናወኑትን ክስተቶች በጥንቃቄ ፅፍል ጳውሎስ በሦስት ምክንያቶች ይከሰስ ነበር፡ (1) አዋኪ በመባል፣ (2) የናዝራውያን መሪ በመባል፣ (3) የመቅደስ ስርዓት ያስክሳል በመባል

▣

| | |
|---|---|
| NASB | “ አዋኪ” |
| NKSU | “ መቅሰፍት” |
| NRSV | “በሽታን የሚያስከትል” |
| TEV | “አደገኛ” |
| NSB | “በትክክል በሽታ የሆነ” |

ይህ ቃል “መቅሰፍት” የሚል የቃል ትርጉም አለው (ሉቃ 21፡11) በብሉይ ኪዳን በግሪኩ ፅሁፍ ላይ መቅሰፍት የሚል ተመሳሳይ ፍቺ ይሰጣል፡፡ ነገር ግን ክፍ ስነ ምግባር የለውንም ሰው ያመለክታል (ምሳ 19፡25)፡፡

▣ “**በዓለም ሁሉ**” የጳውሎስ አገልግሎት የደረሰበትን የሮማውያን ግዛት እና ሌሎችንም ለማመልከት ነው፡፡ “መሪ” የግሪኩ ፅሐፍ

▣ *"መጀመሪያ"* እና ተጠባባቂ "የሚል ፍቺ አለው" (ኢዩ 15፡24) ይመልከቱ በአዲስ ኪዳን ቃሉ በዚህ ምንባብ ውስጥ ብቻ ተፅፎ ይገኛል፡፡

▣ **"ወገን" ይህ ቃል** "ሄረሲስ" ወይም "ክፍፍል" ወይም "የራስን ምርጫ ማድረግ" የሚል ቀጥተኛ ፍቺ አለው ከግሪክ የተገኘው የእንግሊዘኛ "ሄርሲ" አሉታዊ የትርጉም ፍቺ አለው ሐዋ 5፡17 እና ሐይ 15፡5 ነገር ግን ጳውሎስ ክርስትና ሄርሲ ሳይሆን የአይሁድ የአዲሱ ኪዳን ዕምነት እንደሆነ ይገልፃል፡፡

▣ **"ናዝራውያን"** ሐረጉ የሚያመለክተው የኢየሱስ ተከታይ የሆኑትን ነው፡፡ ቃሉ ናዝሬት ከሚለቃ የመጣ ነው ነገር ግን አንዳንዶቹ "ነዘር" ወይም "ቅርንጫፍ" የሚለውን ለመሲሁ ስያሜ ከሆነው የመጣ እንደሆነ ይፅፈዋል (አሳ 11፡1;53፡2)፡፡

24፡7 በዚህ ምዕራፍ ቁ 6,7, እና 8 በግሪኩ ፅሑፍ ላይ አልተፃፈም በተጨማሪም ሉቃሽ በሐዋርያት ስራ መፅሐፍ እነዚህን ቁጥሮች አልፃፋቸውም፡፡

> **አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 24፡10-21**
> **ገዥም በጠቀሰ ጊዜ ጳውሉስ መለስ እንደህ አለ ከብዙ ዘመን ጀምሮ አንተ ለዚህ ህዝብ ፈራጅ እንደሆንክ አውቃለሁና ደስ እያለኝ ስለ እኔ ነገር እመልሳለሁ እሰግድ ዘንድ ከኢየሩሳሌም ከመጣሁ አስራ ሁለት ቀን እንዳይበልጥ ልታውቀው ትችላለህ ከአንድም ስንኳ ስነጋገር ወይም ሕዝብን ስሰበስብ በመቅደስ ቢሆን በምኩራብም ቢሆን በከተማም ቢሆን አላገኙኝም አሁንም ስለሚከሱኝ ያስረዱህ ዘንድ አይችሉም ነገር ግን ይህን እመሰክራልሃለሁ በሕጉ ያለውን በነብያትም የተፃፉትን ሁሉ አምኜ የአባቶቼን አምላክ እነርሱ ኑፋቄ ብለው እንደሚጠሩት መንገድ አመልካለሁ እነዚህም ደግሞ ራሳቸው የሚጠብቁት ፃድቃንም አመፀኞችም ከሙታን ይነሱ ዘንድ እንዳላቸው ተስፋ በእግዚአብሔር ዘንድ አለኝ ስለዚህ እኔ ደግሞ በእግዚያአብሔር እና በሰዎች ፊት ሁልጊዜ ነውር የሌለባት ህሊና ትኖረኝ ዘንድ እተጋለሁ፡ ከብዙ አመት በኃላ ለህዝቤ ምፅዋትና መስዋት አደርግ ዘንድ መጣሁ ይህንም ሳደርግ ሳለሁ ሁከትም ሳይሆን በመቅደስ በነፃ አገኙኝ ነገር ግን በኔ ላይ ነገር ያላቸው እንደሆነ በፊትህ መተው ይከሱኝ ዘንድ የሚገባቸው ከእስያ የመጡ አንዳንድ አይሁድ አሉ፡፡ ወይም በመካከላቸው ቆሜ ስለ ሙታን መነሳት በፊታችሁ በእኔ ይፈርዱብኛል ብዬ ከመጮሄ ከዚህ ከአንድ ነገር በቀር በሸንጎ ፊት ቆሜ ሳለሁ በእኔ አንድ አመፅ ያገኙ እንደሆነ እነዚህ እራሳቸው ይናገሩ፡፡**

24፡10 ሽማግሌዎቹ የተጠቀሙበትን የፍርድ ስርዓት ጳውሎስ ተጠቀምበታል፡፡

▣ *"መከላከያ"* የእንግሊዘኛ ቃል ነው ትርጉሙም የመከላከያ እና የማጥቂያ ሃሳብ ማቅረብ የሚል አቻ ትርጉም አለው፡፡

24፡11-12 ሐዋሪያው ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ያደረገው ሁሉ የአይሁድን ሃይማኖታዊ ስርዓት የጠበቀ ተቀባይነት የነበረው ነው፡፡

24፡14 **"መንገድ"** ይህ መጠሪያ ለክርስትያኖች ያገለግል ነበር (ዮሐ 14፡6) ህብረት የማድረጊያ ስያሜም ነበር (ሐዋ 9፡2፡19፡9,23;22፡4;24፡22 እና 18፡25-26)

▣ **"በህግ እና ... በነብያት"** እነዚህ ከሦስቱ የብሉይ ኪዳን መፅሐፍት ዓይነቶች ሁለቱ ናቸው፡፡
1. የህጉ መፅሐፍ (ከዘፍጥረት -ዘዳግም)
2. የነበያት መፅሐፍት
   ሀ. ከቀደሙት ነቢያት (ኢያሱ ነገስታት)
   ለ. ከታላላቆች ነብያት -(ኢሳያስ-ሚልክያስ)
   (ከዳንኤል እና ከሶቆቃው ኤርምያስ)
3. የተለያዩ መፅሐፍት
   ሀ. የታሪክ መጽሐፍቶች
   ለ. የስነ ግጥም መፅሐፍት (ኢዮብ መዝሙር እና ምሳሌ)
   ሐ. ከምርኮ በኃላ ያለ ታሪክ (1 እና 2 ቆሮንጦስ, ህዝራ እና ነህምያ)

24፡15 **"እነዚህ እራሳቸው ከሚጠብቁት"** ጳውሎስ ሃይማኖታዊ ትንታኔ ለከሳሾቹ እየሰጠ ነው፡፡ (ሐይ 24፡16) ጳውሎስ የሃይማኖት ክስ መሆኑን እየተናገረ ነው ይህም የሮም መንግስት በአይሁድ ሃይማኖት ጣልቃ መግባት የማይፈልግበት ጉዳይ ነው፡፡

▣ **"ፃድቃንም አመፀኞችም ከሙታን ይነሱ ዘንድ እንዳላቸው ተስፋ ለእግዚያብሔር ዘንድ አለኝ"** ይህ የሰዱቃውያንን ሳይሆን የፈሲጺውያንን ስነ መለኮት ያመለክታል፤ ምክንያቱም አንዳንድ ፈሪሳውያን አመፀኞች ከሙታን አይነሱም የሚል ትምህርት እያስፋፉ ነበር መፅሐፍ ቅዱስ ይህንን ትምህርት ይቃወማል፡፡ (ኢሳ 25፡8;ዳንኤ 12፡2;መቴ 25፡4b; ዮሐ 5፡29 ሮማ 2፡6-11;ራዕ 20፡11-15)

የእኔ ጓደኛ እና አብሮኝ ሠራተኛ የሆነ ዶ/ረ ዳዊት ኪንግ እኔ የሠራሁትን ይኸንን ቅዱስ ሀተታ አንብቦ አስተያየቱን ሰጥቶኛል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እርሱ እንዲህ ሲል ጽፎአል። "አንድ ፍሬ፣ ብዙ ክፍልፍሎች እንደብርቱኳን" ብሎ።

▣ 24:26 **"ነውር የሌለበት ሕሊና ትኖረኝ ዘንድ እተጋለሁ"** የሊቀካህኑን ቁጣ የቀሰቀሰ ዓረፍተ ነገር ነበር (ሐይ 23:1-2) ጳውሎስ ይህንኑ ቃል ይሄው ሊቀካህን በተገኘበት ደግሞታል (1 ቆሮ 9: 24-27) ራስን ስለመግዛት ለልሊክስ መናገር አስፈላጊ ነበር እርሱም የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነው (ሐይ 24:25)።

24:17 **"ለህዝቤ ምፅዋትን እሰዋ ዘንድ መጣሁ"** (ሐይ 3:2) ያንብቡ ይህ ከአህዛብ አብያተ ክርስቲያናት ለአየሩሳሌም ቤተክርስቲያን የተሰጠውን የገንዘብ ዕርዳታ ለማመልከት ነው (ሮማ 15:25-27; 1ቆሬ 16:1-4;2 ቆሮ 8-9) በሐዋ 21:15 አልተጠቀሰም ይህ ስጦታ በኢየሩሳሌም ለሚገኙ የአይሁድ አማኞች ለመቀበል አጨቃጫቂ ነበር።

24:18 **"በመቅደስ ስነፃ አገኙኝ"** ይህ የአይሁድ የሃይማኖት ስርዓት ነው (ሐዋ 21:17-26)። ይህ የተደረገበት ምክንያት የአይሁዶችን ስርዓት በቤተክርስቲያን ውስጥ ለማስገባት ነበር። ግን ይህ ደግሞ በተጨባጭ ከእሲያ የመጡትን አይሁድ አስቸገራቸው።

24:18-19 **"ከእስያ የመጡ አንዳንድ አይሁድ አሉ"** በጳውሎስ ንግግር ሐረጉ በጣም አስፈላጊ ነው፤ ከሳሾቹ የአይን እማኞች አልነበሩም (ሐይ 24:20)።

24:19b **"እንደ ሆነ"** ከእውነት የራቀ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ነው። (A.T Roberston, word picture in the New Testament, P420) ሉቃ 17:6, እና ሐዎ 8:31) ያነፃፅሩ።

> **አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ: 24:22-23**
> **[22]ፊልክስ ግን የመንገዱን ነገር አጥብቆ አውቆአልና። የሻለቃው ሉስዮስ በወረደ ጊዜ ነገራችሁን እቆርጣለሁ ብሎ ወደ ፊት አዘገያቸው። [23]የመቶውንም አለቃ ጳውሎስን ሲጠብቅ እንዲያደላለት፥ ከወዳጆቹም ማንም ሲያገለግለው ወይም ወደ እርሱ ሲመጣ እንዳይከለክልበት አዘዘው።**

24:22 ራሊክስ ስለ ኢየሱስ እና ስለ ክርስቶስትና በቂ የሆነ ግንዛቤ አለው፤ በተጨማሪም ባለቤቱ አይሁዳዊት ነበረች (ሐዋ 24:24) በመሆኑን የአይሁዳውያንን ሃይማኖት ስርዓቶቻቸውንም ጠንቅቆ ያውቃል።

24:23 የክርስትና ሃይማኖት ለሮማውያን ገዥዎች የፓለቲካ ጥያቄ ባለመሆኑ ትኩረት አይሰጡትም ነበር።

> **አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ: 24:24-27**
> **[24]ከጥቂት ቀንም በኋላ ፊልክስ አይሁዳዊት ከነበረች ድሩሲላ ከሚሉአት ከሚስቱ ጋር መጥቶ ጳውሎስን አስመጣ፥ በኢየሱስ ክርስቶስም ስለ ማመን የሚናገረውን ሰማው። [25]እርሱም ስለ ጽድቅና ራስን ስለ መግዛት ስለሚመጣውም ኵነኔ ሲነጋገር ሳለ፥ ፊልክስ ፈርቶ። አሁንስ ሂድ፥ በተመቸኝም ጊዜ ልኬ አስጠራሃለሁ ብሎ መለሰለት። [26]ያን ጊዜም ደግሞ እንዲፈታው ጳውሎስ ገንዘብ ይሰጠው ዘንድ ተስፋ አደረገ፤ ስለዚህ ደግሞ ብዙ ጊዜ እያስመጣ ያነጋግረው ነበር። [27]ሁለት ዓመትም ከሞላ በኋላ ጶርቅዮስ ፊስጦስ በፊልክስ ፈንታ ተተካ። ፊልክስም አይሁድን ደስ ያሰኝ ዘንድ ወዶ ጳውሎስን እንደ ታሰረ ተወው።**

24:24 "ድሩ ሲላ" የሄሮድስ አግሪጳ መልከ መልካም ልጅ የአናዳ II እህት ነበረች። ይህችም ሴት የፌሊክስ ሶስተኛ ሚስቱ ሆና ነበር።

(Josephus, antiq 20:7:2) ባለ ታሪክ ፀሐፊው ጆሴፈስ እንደፃፈው ፌሊክስ ለሚስትነት ሊወስዳት ዕድሜዋ አስራ ስድስት ብቻ ነበር።

24:24-25 ሐዋርያው ጳውሎስ ለፌሊክስ እና ለድሩሲላ ወንጌልን በግልፅ ለመስበክ ዕድል አግኝቷል (ሐይ 24:26) ኢየሱስም የሚፈልገውን ነገር አድርጓል (ሐይ 9:15) ይህ ፌሊክስ በልቡ አውነት እንደሆነ ቢረዳም ነገር ግን ገንዘብ ከጳውሎስ ለመቀበል መፈለጉ በስልጣን መባለጉን ያሳያል።

24:26 በዚህ ጊዜ ጳውሎስ ጥቂት የገንዘብ ዕርዳታ አግኝቷል፣ (1) ከራሱ የመሬት ጥሪት፣ (2) ከአብያት ክርስቲያናት (ከተሰሎንቄና ከልሊጵሲዮስ ፌሊክስ ጳውሎስን በየጊዜው ወደ እርሱ የሚያስጠራው ወንጌል ሊሰማ ብቻ ሳይሆን ገንዘብን ሊቀበለው ስላሰበ ነበር።

24:27 **"ከሁለት አመት በኃላ"** ፀሐፊው ሉቃስ ፅሑፎቹን ሁሉ ያሰባሰበው በዚህ ጊዜ ውስጥ እንደሆነ ይታመናል። (ሉቃ 1:1-4) ለሐዋሪያው ጳውሎስ እነዚህ ዓመታት ተስፋውን የሚጠባበቅ ወቅት ነበር።

▣ **“ጵርቅዮስ ፊስጦስ”** በሮማውያን እና በሌሎች ፀሐፊዎች መሃከል የነገሱበትን አመት ለመገመት አስቸጋሪ ሆኖአል:: ፊሊክስ በ55 ዓ.ም በሞት ፍርድ ክስ ላይ ነበር ነገር ግን ከዚያ በኃላ ያለው ታሪኩ አይታወቅም ፊስጦስ በ62 ዓ.ም በስልጣኑ ላይ እንዳለ ሞቷል (josephus, antiq 20:9.1) ስለ ፊስጠስ በዝርዝር የሚታወቅ ታሪክ የለም (josephus, antiq 20:8.9.10 wars 2:14:1)

▣ **“ፊሊክስ … ጳውሎስን እንደታሰረ ተወው”** በሮም ግዛት ሁሉ በአስተዳደር ላይ የነበሩ ገዥዎች ሲቀየሩ እስረኞች ይለቀቁ ነበር ነገር ግን በዚህ ምንባብ የሚታየው የሮም መንግስት ሕግጋት መላላቱን እና የአይሁድ ሽማግሎዎች ደካማ መሆንን ነው፡፡

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ለመርዳት ነው የተሰናዱት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋነኞቹን ጉዳዮች ለማጤን እንዲረዳ ነው፡፡ ሐሳብ ለማጫር እንጂ መደምደሚያ አይደሉም፡፡

1. ናዝራውያን የሚለው ቃል ትርጉም ምንድነው?
2. “መንገድ” የሚለው ስያሜ ለክርስቲያኖች መሰጠቱ ምንን ለማመልከት ነበር?
3. የሐዋ 24፡15 ጭብጡን ሃሳብ ግለፁ

# ሐዋርያት ስራ 25

## የምንባቡ ክፍፍል በአዲሶቹ ትርጉሞች

| የተየመቅሶ[4] | አኪጀት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጳውሉስ ቂሳርን ይግባኝ | ጳውሉስ ቂሳርን ይግባኝ ጠየቀ | ንጉስ ነገስቱን ይግባይ ጠየቀ | ጳውሎስ ነጉሱን ይግባኝ ጠየቀ | ጳውሉስ ቂስረን ይግባይ ጠየቀ |
| 25፡1-5 | 25፡1-12 | 25፡1-5 | 25፡1-5 | 25፡1-5 |
| | | 25፡6-12 | 25፡6-8 | 25፡6-12 |
| | | | 25፡9 | |
| | | | 25፡10-11 | |
| | | | 25፡12 | |
| ጳውሉስ በአግሪጳ ራት | ጳውሉስ በአግሪጳ ራት | የጳውስ ክርክር በአግርጳ ፊት (25፡13-26፡32) | ጳውሎስ በአግርጳ ራት | ጳውሉስ ለንጉስ አግራጳ ታየ |
| | | 25፡13-22 | 25፡13-21 | 25፡13-22 |
| | | | 25፡22a | |
| | | | 25፡22b | |
| 25፡23-27 | | 25፡23-27 | 25፡23-27 | 25፡23-16፡1 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (ከ **"መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ" ገጽ** vii)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. ምንባብ አንድ

2. ምንባብ ሁለት

3. ምንባብ ሦስት

4. ምንባብ ወ.ዘ.ተ

አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 25፡6-12
[1]ፊስጦስም ወደ አውራጃው ገብቶ ከሦስት ቀን በኂላ ከቂሣርያ ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ። [2]የካህናቱ አለቆችና የአይሁድም ታላላቆች በጳውሎስ ላይ አመለከቱ፥ [3]ጳውሎስንም ሲ ቃወም እንዲያደላላቸው እየለመኑ፥ በመንገድ ሸምቀው ይገድሉት ዘንድ አስበው ወደ ኢየሩሳሌም እንዲያስመጣው ማለዱት። [4]ፊስጦስ ግን ጳውሎስ በቂሳርያ እንዲጠበቅ እርሱም ራሱ ወደዚያ ፈጥኖ ይሄድ ዘንድ እንዳለው መለሰላቸው፤ [5]እንግዲህ በዚህ ሰው ክፋት ቢሆን ከእናንተ ዘንድ ያሉት ባለ ስልጣኖች ከእኔ ጋር ወርደው ይክሰሱት አላቸው።

25፡1 *"ፊስጦስም ከፊሊክስ ወጥሎ የነገሰው ሰው ነው፤"* ልዩ ምክቱ መልካም ምልአተ ስብዕያ የነበረው ቢሆንም ነገር ግን በሮማውያን የፖለቲካ አመራር ይመራ ነበር። ለሁለት ዓመት ከነገሠ በኃላ በ62 ዓ.ም ሞቷል።

▣ *"ከሶስት ቀን በኃላ"* ይህ የጳውሎስ ጉዳይ የአይሁድ መሪዎች ምን ያህል ሃሳብ እንደያዛቸውና እረፍት እንዳጡ ያሳያል። ፊሊስጤም ደግሞ መልካም ተጽዕኖ ለመፍጠር አስቦ ነበር በመጀመሪያው ጊዜ።

25፡2 *"የካህናት አለቆችና የአይሁድ ታላላቆች"* እነዚህ በቁጥር ሰባ የሚያህሉ በኢየሩሳሌም የሚኖሩ የአይሁድ መንገዶች የሃማኖት ስብስብ ነው። በአይሁዳውያን በፓለቲካ እና በሃይማኖት ጉዳይ ላይ ከመንግስት ጋር ጉዳይ አስፈፃሚ በመሆን አዝባቸውን ያገለግላሉ። (ሐዋ 4፡5) በተጨማሪም ከነዚህ መሐከል ባለጠጎችና የተማሩ ሰዎች በመኖራቸው በሮማውያን ተደማጭነት እንደኖራቸው አድርጓል። ከሁለት ዓመታት በኃላ እስማኤል የሚባል ሊቀ ካህን ተሹሞአል እርሱም ከሮማውያን ጋ የጠበቀ ግንኙነት ነበረው።

▣ *"አጥብቀው ለመኑት"* ይህ ትዕዛዛዊ ሃሳብ ያለው ነገር ይመስላል። ደጋግመው አጥብቀው ለመኑት።

25፡3 እነዚህ የሃይማኖት መሪዎች ጳውሎስን እንደጠላት ይመለከቱት ስለነበር ጥላቻቸውን የገለበጡበት ቦታ ነው።

▣ ***"በተመሳሳይ ወቅት፣** **እርሱን በመንገድ ላይ ለመግደል ያሴሩ ነበር"*** የአይሁድ መሪዎች ሴራ አልተቀየረም (23፡12-15)።

25፡5 *"እንግዲህ…"* ከፀሐፊው ዕይታ አንፃር በዚህ የተነገረው እውነተኛ መሆኑን የሚያሣይ ሐረግ ነው። (A.T Roberson. *Word Picture in the New Testament* No 13, & 429) ሰባዎቹ የአይሁድ ሽማግሌዎች አጥብቀው ጳውሎስን በከሰሱት ጊዜ ንጉስ ፊስጠስም ጳውሎስን እንደወንጀለኛ ተመልክተው በኢየሩሳሌም የሚገኙ ሰባ ሽማግሎዎች ጳውሎስን በእንዲህ ዓይነት ክስ እስከ መጨረሳ ለምን ጨከኑበት?

አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 25፡6-12
[6]በእነርሱም ዘንድ ከስምንት ወይም ከአስር የማይበልጥ ቀን ተቀምጦ ወደ ቂሳርያ ወረደ፤ በነገውም በፍርድ ወንበር ተቀምጦ ጳውሎስን ያመጡት ዘንድ አዘዘ። [7]በቀረበም ጊዜ ከኢየሩሳሌም የወረዱት አይሁድ ከበውት ቆሙ፥ ይረቱበትም ዘንድ የማይችሉትን ብዙና ከባድ ክስ አነሱበት፤ [8]ጳውሎስም ሲምዋገት። የአይሁድን ህግ ቢሆን መቅደስንም ቢሆን ቄሳርንም ቢሆን አንዳች ስንኳ አልበደልሁም አለ። [9]ፊስጦስ ግን አይሁድን ደስ ያሰኝ ዘንድ ወዶ ጳውሎስን። ወደ ኢየሩሳሌም ወጥተህ ስለዚህ ነገር ከዚያው በፊቴ ትፋረድ ዘንድ ትወዳለህን? ብሎ መለሰለት። [10]ጳውሎስ ግን። እፋረድበት ዘንድ በሚገባኝ በቄሳር ፍርድ ወንበር ፊት ቆሜአለሁ። አንተው ደግሞ ፈጽመህ እንደምታውቅ አይሁድን ምንም አልበደልሁም። [11]እንግዲህ በድዬ ወይም ሞት የሚገባውን ነገር አድርጌ እንደ ሆን ከሞት ልዳን አልልም፤ እነዚህ የሚከሱኝ ክስ ከንቱ እንደሆነ ግን ለእነርሱ አሳልፎ ይሰጠኝ ዘንድ ማንም አይችልም፤ ወደ ቄሳር ይግባኝ ብዬአለሁ አለ። [12]በዚያን ጊዜ ፊስጦስ ከአማካሪዎቹ ጋር ተማክሮ። ወደ ቄሳር ይግባኝ ብለሃል፤ ወደ ቄሳር ትሄዳለህ ብሎ መለሰለት።

25፡6-9 በዚህ ምንባብ እንደምናነበው ጳውሎስ በፊስጦስ ፍርድ ወንበር ፊት ተስፋ እንደሌለው እንመለከታለን። ጳውሎስ በኢየሩሳሌምን ምን እንደሚቆየው አውቆታልና ቁ.3) ጌታም ጳውሎስን ወደ ሮም ትሄዳለህ ብሎታል (ሐዋ9፡15)

25፡6 *"በእነርሱ ዘንድ ከስምንት ወይም ከአስር የማይበልጥ ቀን"* እነዚህ የአይሁድ ሽማግሌዎች የሮማውያንን ባለስልጣኖች ረብ በሌለው ነገር ያለህን በራሳቸውም ህዝብ ላይ ቢሆን እንዲፈርዱ ይገፋፋ ነበር።

25፡10-11 ጳውሎስ በባለስልጣኖች ፊት እና በተገቢው ቦታ መሆኑን በንግግሩ ትቅሷል በመሆኑን ጳውሎስ ወደ ቄሳር ይግባኝ ብሏል ለቄሳር ይግባይ ማለት የተጀመረው በአክተቫውያን በ30 ክክ)ል)በፊት ነበረ። (Dio cassius history,

51.19) ይህም ሕግ የሮማውያንን የዜግነት መብት ለመጠበቅ የወጣ ነበር፤ ሮማውያንን ማሰቃየት፣በግርፍ፣ማንገላታት የተከለከለ ነበር፡፡ (Paulus sententiae 5.26.1)

በመጀመሪያ ምዕተ አመት በሮማውያን ህግና የተለያዩ ህግና የተለያዩ ሰንቦች ላይ ብዙ ውይይት ይደረግ ነበር (N.S Sherwin-white's Roman Society and roman law in the New Testament, "lectrutre four Paul before felix and fesths pp 48-70)፡፡

25:11 **"እንግዲህ. . ."** በፀሐፊው በሉቃስ አንፃር ከዚህ ቃል በኃላ የተዘረዘረው ሐተታ እውነተኛ እንደሆነ ለማመልከት ቃሉን ተጠቅሞበታል፡፡ የዚህን ተመሳሳይ (ሐዋ 25:5) ይመልከቱ፡፡

▣ **"ከሞት ልዳን አልልም"** ጳውሎስ የመንግስት ስልጣን ማክበሩን ያሣያል፡፡ (ሮሜ 13:4) በብሉይ ኪዳን የነበረውን የሞት ቅጣት በተከታተ ጥቅስ ይመልከቱ (H4 9:6) ለተጨማሪ ግንዛቤ የሚከተለውን መፅሐፍ ያንብቡ (hard sayings of the Bible, pp.114-116)

▣

| | |
|---|---|
| NASB, TEV | **"ለእነርሱ አሳልፎ ማንም ሊሰጠኝ አይችልም"** |
| NKJV | **"ለእነርሱ አሳልፎ ማንም ሊያስረክበኝአይችልም"** |
| NRSV | **"ማንም ለእነርሱ ሊመልሰኝ አይችልም"** |
| NJB | **"ማንም ለእነርሱ ሊሰጠኝ መብት የለውም"** |

"*charizoma*" ማለት "ማመስገን" ወይም "ስጦታን መስጠት" ነው፡፡ ፊሲጠስ የአይሁድ መሪዎችን ለማመስገን ራሱን አሳልፎ ሰጣቸው፡፡ ጁሊያስ ቄሳር ሊሰጠን የማዘዝ ሙሉ መብት የነበረው ቢሆንም ነገር ግን የአይሁድ መሪዎችን ምኞት የሚፅም እንደሆነ የታወቀ ነው፡፡

ይሁን እንጂ ፍስጦስ ከጁሊያስ ጋር ሕግን ማክበር መፈለጉ የታወቀ ነው (ጂሲፊስ፣ አንቲያክ 14:1.2)፡፡ ለሊቀካህናት በፍልስጤም ውስጥ ሃሳባቸው እንዲከበር ባለስልጣናት እንዲያበረታቱአቸው ያመለክታል፡፡

▣ **"ወደ ቄሳር ይግባኝ"** የሮማዊ ዘግነት ያለው ሁሉ ይህንመብት ተጎናፅፏል፡፡

25:12 **"ከአማካሪዎቹ"** የፊሰጠስን የህግ ባለሙያዎች ያመለክታል፡፡

**የዓውዱ ዕይታ ሐዋ 25:13-26-32**

ሀ. ሄሮድስ አግሪጳ II (ማርኮስ ጁሊስ አግራጳ)
1. የሄሮድስ አግርጳ I ልጅ ነው (ሐዋ 12) የይሁድ ገዥ እና መቅደሱን ሊቀካህናትን የሚቆጣጠር ነበር (ቆ 1:44 ዓ.ም)
2. የተማረ ሰው ነበር፤ ከአይሁዳውያን ጦርነት በኃላ ወደ ሮማ ተመልሷል (በ70 ዓ.ም) እና በዚያው በ100 ዓ.ም ሞቷል፡፡
3. በአስራ ሰባት ዓመቱ ላይ አባቱ ሞቷል ነገር ግን ወጣት ስለነበር በትረ መንግስቱን መያዝ አልቻለም፡፡
4. በ50 ዓ.ም ሄሮድስ አገረዳ I ከአጎቱ ቀጥሎ እንዲገዛ በንጉስ ገላውዲዮስ ተሹሞአል፡፡ እርሱም የመቅደሱን ስርዓት እና ሊቀ ካህናቱን እንዲቆጣጠር ተደርጓል፡፡
5. በ53 ዓ.ም በግዛቱ የምትገኘውን ከተማ ለሄሮድስ ፊሊጶስ እንዲያተዳድሯት ሰጠው፡፡
6. ከዚያ በኃላ ንጉስ ኔሮ ከገሊላ ባህር ዳር ያሉ ከተሞችና እና መንደሮችን በግዛቱ ላይ ጨምሯል፤ ዋና ከተማውንም ቂሣሪያ ፊሊጲ በማለት ሰይሟል ዘግይቶም በራሱ ስም ኔሬኒየስ የሚል ስያሜ ሰቶታል፡፡
7. ታሪክ ጠቃች ምስክሮችን እንመልከት፡-
   ሀ. ጆሰፌስ "Jewish war 2.12.1, 7-8; 15.1; 16.4; 7.5.1"
   ለ. ጆሶፊስ Antiquities of the Jews 19.9.2; 20, 5.2; 6.5; 7.1;8.4;9.6.

ለ. በርነቄ
1. የሄሮድስ አግሪጳ I የመጀመሪያ ልጁ ነኝ፡፡
2. በርኒቄ የአግራጳ II የስጋ እህቱ ብትሆንም የፍቅር ግንኙነት እንደነበራቸው ይነገር ነበር፡፡ ከሮማዊው የጦር ጀነራል ኮቲቶ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ነበራ ይህም ቲቶ የኢየሩሳሌምን መቅደስ በ70 ዓ.ም ያፈረሰ ነው፡፡
3. የድሩሲላ የስጋ እህት ነች፡፡ (ሐዋ 24:24)
4. ሄሮድስ ቻልሲንን አግብታ ነበር (የሄሮድስ አግረጳ I ወንድም I የእርሷ ደግሞ አጎት ነው) በሞት ጊዜ ወንድሟን አግብታለች፡፡
5. በርነቄ ፓሎሚን አግብታ ነበር ነገር ግን ጋብቻውን በማፍረስ ወደ ወንድሟ መሄዷን ታሪክ ይናገራል፡፡
6. በርኒቄ ከንጉስ ቪስፓሲን እና የጀነራል ቲቶ ባልንጀራ ነበረች፡፡
7. ታሪክ ጠቃሽ ምስክሮችን እንመልከት፡-
   ሀ. ጆስፌስ Jewish wars 2.1.6; 15; 17.1
   ለ. ጆሰፍስ 'Antiquities of the Jew 19.9.; 15.1; 20.1.3
   ሐ. ታይክስ Life of Titus 7

ሠ. ዲዮ ካሰዮስ Histories 65:15; 66.18
ረ. ጁቨነአል Satire 61.156-157

**የቃል እና የጥምር ቃል ጥናት**

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 25፡13-22**
**[13]ከጥቂት ቀንም በኂላ ንጉሡ አግሪጳ በርኒቂም ለፊስጦስ ሰላምታ እንዲያቀርቡ ወደ ቂሳርያ ወረዱ። [14]በዚያውም ብዙ ቀን ስለተቀመጡ ፊስጦስ የጳውሎስን ነገር ለንጉሡ እንዲህ ብሎ ገለጠ። ፊልክስ አስሮ የተወው አንድ ሰው በዚህ አለ፤ [15]በኢየሩሳሌምም ሳለሁ የካህናት አለቆችና የአይሁድ ሽማግሌዎች እፈርድበት ዘንድ እየለመኑ ስለ እርሱ አመለከቱኝ። [16]እኔም። ተከሳሹ በከሳሾቹ ፊት ለፊት ሳይቆም ለተከሰሰበትም መልስ ይሰጥ ዘንድ ፈንታ ሳያገኝ፥ ማንንም ቢሆን አሳልፎ መስጠት የሮማውያን ሥርዓት አይደለም ብዬ መለስሁላቸው። [17]ስለዚህም በዚህ በተሰበሰቡ ጊዜ፥ ሳልዘገይ በማግሥቱ በፍርድ ወንበር ተቀምጬ ያንን ሰው ያመጡት ዘንድ አዘዝሁ። [18]ከሳሾቹም በቆሙ ጊዜ እኔ ያሰብሁትን ክፉ ነገር ክስ ምንም አላመጡበትም፤ [19]ነገር ግን ስለ ገዛ ሃይማኖታቸውና ጳውሎስ፦ ሕያው ነው ስለሚለው ስለ ሞተው ኢየሱስ ስለ ተባለው ከእርሱ ጋር ይከራከሩ ነበር። [20]እኔም ይህን ነገር እንዴት እንድመረምር አመንትቼ። ወደ ኢየሩሳሌም ሄደህ በዚህ ነገር ከዚያ ልትፋረድ ትወዳለህን? አልሁት። [21]ጳውሎስ ግን አውግስጦስ ቄሣር እስኪቈርጥ ድረስ እንዲጠበቅ ይግባኝ ባለ ጊዜ፥ ወደ ቄሣር እስክሰደው ድረስ ይጠበቅ ዘንድ አዘዝሁ። [22]አግሪጳም ፊስጦስን። ያንንስ ሰው እኔ ደግሞ እኮ እሰማው ዘንድ እወድ ነበር አለው። እርሱም፦ ነገ ትሰማዋለህ አለው።**

25፡13 “ንጉስ አግሪጳ” ንጉስ አግሪጳ II ያመለክታል። ይህ ሰው የድሩሲላ እና የበርላቂ ወንድም ነው ለሮማውያን የፖለቲካ ህግጋት በታማኝነት የሚገዛ የተማረ ሰው ነበር።

25፡13ff የፀሐፊውን የሉቃስን የስነ መለኮት ጥልቅ አላማ የጠገለፀበት አንዱ ቦታ ነው ይህም ለሮማውያን ክርስትና የፓለቲካቸው እንቅፋት እንዳይደለ ያመለክታል። (ሐዋ 25፡25) ይልቁንም ክርስትና በሮማውያን አይን የአይሁድ ሃይማኖት ክርክር ውስጥ መግባት ኤፌልጉም ነበር።

**25፡18 “ከሳሾቹም በቆሙ ጊዜ እኔ ያሰብኩትን ክፍ ነገር ክስ ምንም እንጂ ታለታካዊ ክስ አለመሆኑን ያመለክታል።”**

25፡19 **“ሃይማኖት”** ከሁለት ጣምራ ቃሉች የተመሰረተ6 ነው፤“ፍርሃት” እና “ጣኦታት” ቃሉ በግርድፍ ትርጉሙ “መንፈሳዊ ዓለም” ይህ የሮማውያን የአይሁድ ህዝብ ጣኦት አምላኪ እንደሆነ ያስኩ ነበር ነገር ግን ፊሊክስ የአይሁድን ሃይማኖትን አይንቅም ነበር።

▣ **“ሕያው ነው ስለሚለው ስለሞተው ኢየሱስ”** የሐዋርያት ዋነኛ ስብከታቸው ያተኮረው በትንሳኤው ላይ ነው። (Kelygma ሐዋ 2፡13)፣ (ሐዋ 26፡8) ክርስትና በትንሳኤ ትምህርት ላይ የተመሰረተ ሃይማኖት ነው (1 ቆሮ 15)።

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 25፡23-27**
**በነገውም አግሪጳና በርኒቄ በብዙ ግርማ መጥተው ከሻለቆችና በከተማው ታላላቆች ጋር ወደ ፍርድ ቤት ገቡ ፊስጠስም ባዘዘ ጊዜ ጳውሎስን አመጡት ፈስጠስም አለ፦ አግርጳ ንጉስ ሆይ እናንተም ከእኛ ጋር ያላችሁ ሰዎች ሁሉ ከእንግዲህ ወዲህ በሕይወት ይኖር ዘንድ እንዳይገባው እየጮኩ የአይሁድ ህዝብ ሁሉ በኢየሩሳሌም በዚህም ስለ እርሱ የለለመኑኝም ይህን ሰው ታዩታላችሁ። እኔ ግን ሞት የሚገባውን ነገር እንዳላደርግ አስተዋልሁ እርሱም ወደ አውግስጠስ ይግባኝ ስላለ እሰደው ዘንድ ቁርጥሁ ስለ እርሱም ወደ ጌታዬ የምፅፈው እርግጥ ነገር የለኝም ስለዚህ ከተመረመረ በኃላ የምፅፈውን ነገር አገኝ ዘንድ በፊታችሁ ይልቁንም በፊትህ ንጉስ አግሪጳ ሆይ አመጣሁት ደግሞ አለማመከት ሞኝነት መስሎኛል።**

25፡23 ሐዋርያው ወንጌልን ለመስበክ ትልቅ እድል ማግኘቱን ያረጋግጥልናል።

▣ **“ሻለቆች”** የአንድ ወታደሮች አለቆችን ያመለክታል። (ጆስፈስ *Antiq* 19 19.2) በቂሳሪያ አምስት የተለያዩ ሰረገላ የሚነዱ የመንግስት ስርዓት አስከባሪ ዘርፎች ነበሩ።

**25፡26 “ስለ እርሱም ወደ ገታዬ የምፅፈው እርግጥ ነገር የለኝም”** ፈስጠስ ስለ ጳውሎስ የሚፅፈውን በማጣት ግራ መጋባቱን ያሣያል ምክንያቱም ተጨባጭ ማስረጃ ባለመገኘቱ ነው።

▣ **“ጌታ”** በግሪኩ “ኪዮረዮስ” ፍቺው “ጌታ” “አለቃ እና ገገር” ማለት ነው። በዚህ ስያሜ የሮም ጀነራል የሆነ ኔሮ ይጠራ ነበር። ይህ ስያሜ በአክታቫውያን በአገስቲን ታቃውሞ ተደርጎበታል ምክንያቱም ወደ ላቲኑ ትርጉም “ንጉስ” የሚል ፍቺ በመስጠቱ ነበር ይህም በሮማውያን የስልጣን መዋቅር ስያሜው ተቀባይነት ስሌለው ነበር ነገር ግን ከኔሮ ዘመን መንግስት በኃላ ብዙዎቹ የሮማውያን ገዥዎች ንጉስ ተብለው ተጠርዋል። ቫስፓሬን እና ቲቶ ራሳቸውን አዳኝ

በማለት ሰይመዋል እና ደሜቱን ደግሞ "አምላክቸ በሚል መጠሪያ ተሰይሟል" (James s. suffers, the Greco-roman world P.101) ክርስቲያኖት "ጌታ" የሚለውን ቃል ለኢየሱስ ክርስቶስ በመስጠታቸው በሮማውያን ገዥዎች ዘንድ ከፍተኛ ስደት ደርሶባቸዋል፡፡ "ከመረመረው በኃላ" ቤባስቶስ የላቲኑ "ኦገስተስ" ነው፡፡ የስረው ቃሉ ትርጉም "ማክበር" ወይም "ማምለክ" የሚል ነው፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ቃሉን የተጠቀሙት በአክታቪያን ስብሰባ ላይ በ27 ከክ)ልደት)በፊት ነው፡፡ ለዚህ ክፍል ደግሞ ለኔሮ ስያሜው አገልግሏል ይህም ሰው የነገስታትን አምልኮ በሮም ያስፋፋ ሰው ነው፡፡

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ለመርዳት ነው የተሰናዱት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋነኞቹን ጉዳዮች ለማጤን እንዲረዳ ነው፡፡ ሐሳብ ለማጫር እንጂ መደምደሚያ አይደሉም፡፡

1. የአይሁድ መሪዎች አብዝተው ጳውሎስን ለምን ፈሩት? ለምንስ ጠሉት?
2. ፀሐፊው ሉቃስ ይህንን ምዕራፍ ሲፅፍ አጠቃላይ አላማው ምንድነው?
3. ጳውሎስ በአግራጳ ፊት የመከላከያ ሃሳብ ያቀረበበት ዓላማው ምንድ ነው?

# የሐዋርያት ስራ 26

## የምንባብ ክፍፍል በአዲሶቹ ትርጉሞች

| UBS | NKJS | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|---|
| ጳውሎስ የመከላከያ ሃሳብ በአግሪጳ ፊት አቀረበ | የጳውሎስ የቀድመው ታሪኩ | ጳውሎስ በአግጳ ፊት ተከራከረ (25፡13-26፡32) | ጳውሎስ የመከላከያ ሃሳብ በአግሪጳ አቀረበ | ጳውሎስ በንጉስ አግሪጳ ፊት ለመነ |
| 26፡1-11 | 26፡1-11 | 26፡1 | 26፡1 | የጳውሎስ ንግግር በንጉስ አግሪጳ ፊት |
| | | 26፡2-3 | 26፡2-3 | 26፡2-3 |
| | | 26፡4-8 | 26፡4-8 | 26፡4-8 |
| | | 26፡9-11 | 26፡9-11 | 26፡9-11 |
| ጳውሎስ መለወጡን ተረከ | ጳውሎስ መለወጡን አብራራ | | ጳውሎስ ስራውን ተናገረ | |
| 26፡12-18 | 26፡12-18 | 26፡12-18 | 26፡19-18 | 26፡19-18 |
| ጳውሎስ ለአይሁድና ለአህዛብ መሰከረ | የጳውሎስ የቀድሞ ሕይወት | | ጳውሎስ አግሪጳ እንዲያምነው ተማፀነ | |
| 26፡19-23 | 26፡19-23 | 26፡19-23 | 26፡19-23 | 26፡19-23 |
| | | | የአድማጮቹ ተቃውሞ | |
| 26፡24-29 | 26፡24-32 | 26፡24-29 | 26፡24 | 26፡24-29 |
| | | | 26፡25-27 | |
| | | | 26፡28 | |
| | | | 26፡29 | |
| 26፡24-32 | | 26፡30-32 | 26፡30-32 | 26፡30-32 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (ከ **"መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ" ገጽ** vii)
***የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል***

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. ምንባብ አንድ

2. ምንባብ ሁለት

3. ምንባብ ሦስት

4. ወ.ዘ.ተ . . . .

**ሐዋ 26፡1**
**[1]አግሪጳም ጳውሎስን። ስለ ራስህ ትናገር ዘንድ ተፈቅዶልሃል አለው። በዚያን ጊዜ ጳውሎስ እጁን ዘርግቶ መለሰ እንዲህ ሲል፦**

26፡1 **"እጁንም ዘርግቶ"** የሰላምታ እና የንግግር መጀመሪ ምልክት ነው። (ሐዋ 12፡27; 13፡16 እና 21፡40) የሰዎችን ትኩረት ለማሰብ ይጠቀሙበት ነበር።

**ሐዋ 26፡2-3**
**ንጉስ አግሪጵ ሆይ የአይሁድን ስርዓት ክርክርንም ሁሉ አጥብቀህ አውቀሃልኛ በአይሁድ በተከሰሰሁበት ነገር ሁሉ ራሴን እንደተመረቀ አድርጌ እቆጥረዋለሁ ስለዚህ በትዕግስት ትሰማኝ ዘንድ እለምንሃለሁ።**

26፡2-3 ጳውሎስ በፊሊክስ ፊት እንዳደረገው ወጉን የጠበቀ ንግግር አደረገ (ሐዋ 24፡10) በአይሁድ ሽማግሌዎች መሃከል በነበረ ጊዜ የሚደረገውን ስርዓት ማወቁኝ ያሳያል።

26፡2 **"በአይሁድ በተከሰስኩበት ነገር ሁሉ"** አግሪጳ ii በመቅደስና በሊቀ ካህናቱ ላይ ተሹሞ ነበር። አግሪጳ II ሮማዊ ቢሆንም የአይሁድን የሃይማኖት ስርዓት ጠንቅቆ የሚያውቅ ነበር (ሐዋ 26፡3)

▣ **"እንደተመረቀ"** በማቴስ እና በመዝሙር 1፡1 ላይ የለውን ዝርዝር በመመልከት ስፊ ግንዛቤ ማግኘት ይችላል።

26፡3

| | |
|---|---|
| NASB, NKJV | "ስርዓቱን ሁሉና ጥያቄዎቹን" |
| NRSV | "ስርዓቱን ሁሉና ክርክሮቹን" |
| TEV | "የአይሁድን ስርዓትና ክርክሮቻቸውን" |
| NJB | "ስርዓትና ክርክሮቹን" |

የግሩሪኩ "Ethon" የእግሊዘኛው "ዘር" የሚል ፍቺ አለው በአይሁድ ሃይማት መሪዎች ክርክር እና ጭቅጭቅ ነበር (ሐዋ 15፡2; 18፡15; 23፡19; 25፡19;25፡19;26፡3) በሃሁድ ሃይማኖት ውስጥ የተለያየ ወገን ስለነበረ ፈረሳውያን፣ሰዱቃውያን፣ፃፍች እና ሌሎችም ስለነበሩ ብዙ ንትርክ ነበረ።

**ሐዋ 26፡4-8**
**ከመጀመሪያ አንስቶ በህዝቤ መካከል በኢየሩሳሌም የሆነውን ከታናሽነቴ ጀምሮ የኖርኩትን ኑሮዬን አይሁድ ሁሉ ያውቃሉ ሊመስክሩ ይወዱ እንደሆነ በአምልኮአችን ከሁሉ ይልቅ ህግን በመጠንቀቅ እንደሚተጋ ፈረሳዊ ሆኜ እንደኖረሁ ከጥንት ጀምሮው አውቀውኛልአሁንም ከእግዚአብሔር ዘንድ ለአባቶቻችን ስለተሰጠው ስለ ተስፋ ቃል አለኝታ ልፈርድ ቆሜአለሁ። ወደዚህም ወደ ተስፋ ቃል አስራ ሁለቱ ወገኖቻችንም በሌሊትና ቀን በትጋት እያመለኩ ይደርሱ ዘንድ አለኝታ አላቸው ስለዚህም አለኝታ ንጉስ አግሪጳ ሆይ ከአይሁድ እከሰሳለሁ እግዚአብሔር ሙታንን የሚያስነሣ እንደ ሆነ ስለምን በእናንተ ዘንድ የማይታመን ነገር ሆኖ ይቆጠራል?**

26፡4 **"ኑሮዬን አይሁድ ሁሉ ያውቃሉ"** ጳውሎስ ቃሉን በተደጋጋሚ ተጠቅሞበታል። (ሐዋ 22፡3-5 23፡1;24፡16፡25፡8) ጳውሎስ ምሳሌነት ያለው ኑሮ በኢየሩሳሌም የነበረው መሆኑን ያረጋግጣል፤ (ሐዋ 26፡5)

▣ **"በሕዝቤ መካከል"** ጳውሎስ በግልፅ የት እንዳደገ ማስረጃ የለም ነገር ግን በጠርሴስ ወይም በኢየሩሳሌም ሊሆን ይችላል።

26፡5 **"ለመስክሩ ይወዱ እንደሆነ"** በዚህ ምንባብ የሚታዩት ሰዎች ስለ ጳውሎስ የሚያውቁት ነገር አለ ነገር ግን እውነቱን ለመናገር ፍቃደኛ መሆን ይኖርባቸዋል።

▣ **"ሕግን በመጠንቀቅ እንደሚተጋ ወገን ፈሪሳዊ ሆኜ"** በመካብያን ጊዜ የተደነገገውን የአይሁድ ሃይማኖት ስርዓት ያመለክታል፤ ይህም በቃል እና በፅሁፍ የተገኘ ማስረጃ አለ። (ሐዋ 5፡34 እና 15፡15) ያንብቡ።

26፡6 **"ከእግዚአብሔር ዘንድ ለአባቶቻችን ስለ ተሰጠው ስለ ተስፋ ቃል"** በብሉይ ኪዳን የተባለውን ሁለት ነገር ያመለክታል።

1. የመሲሁ መምጣት፡-
2. የሙታን መነሳት፡- (ሐዋ 23፡6;24፡15፡ኢዮ 14፡14-15;19፡25-27) ዳንኤ 12፡2) ጳውሎስ የተስፋ ቃሉ የተፈፀመበትን መንገድ ተመልክቶታል። (ማቴ 5፡17-19፤ገላ 3)

27:7 **“አስራ ሁለቱ ወገኖቻችን”** ለአይሁዳውያን አስራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች ታሪካቸው ዘወትር ይወሳል፡፡ አብዛኞቹ የሰሜኑ አስር ነገዶች ከአሥር ግዞት ወደ አገራቸው አልተመለሱም (722 ከክ)ላ)በፊት) ከአዲስ ኪዳን አንዳንድ ማስረጃዎችን እናገኛለን፡፡ (1) ማርያም፣ ዮሴፍ እና ኢየሱስ ከይሁድ ወገን ነበሩ (ማቴ 1፡2-16፣ ሉቃ 3፡23-33፤ ራዕይ 5፡5)፣ (2) ሃና የአሲር ወገን ነው (ሉቃ 2፡36)፣ (3) ጳውሎስ የቢኒያም ወገን ነው (ሮማ 11፡1 ፊሊ. 3፡5)

ሄሮድስ በቅንነት አይሁድን ሁሉ በየወገናቸው እንዲመዘገቡ ትዕዛዝን አውጥቶ ነበር አስራ ሁለቱ የሚለውን ልዩ ትኩረት የሚሻው በሚለው ርዕስ ስር ይመልከቱ፡፡

▣ **“ተስፋ”** ጳውሎስ የሚናገረው ተስፋ በዚህ ዓውደ መሰረት ስለሙታን ትንሳኤ በመሆኑ ከቀጥታ ንባቡ መረዳት ይቻላል፡፡

▣ **“ሌሊት እና ቀን በትጋት እያመለኩ”** ጳውሎስ የራሱን ዘር ይወዳል (ሮማ 9፡1-3) አይሁድ ያህዌን ለማገልገል ያላቸውን ፍላጎት ጳውሎስ ያውቃል፡፡ በተጨማሪም ሕጋቸውን፣ስርዓታቸውን እና ትምህርቶቻቸውን ጠንቅቆ ተምሯል፡፡

ቀንና ለሊት የሚለው ሐረግ ትጋትን ለማመልከት ነው፡፡

26:8 **“በእናንተ ዘንድ የማይታመን ነገር ሆኖ ይቆጠራል”** ጳውሎስ ለሁለት አካላት እየተናገረ ነው፡ (1) ለአግሪጳ እና ለአይሁድ፣ (2) ለአህዛቦች ምሳሌ ፊስጦስ፡፡

▣ **“እንደ ሆነ”** ከፀሐፊው ከሉቃስ ዕይታ ግምቱ ልክ እንደሆነ ያመለክታል፡፡

▣ **“እግዚአብሔርን ሙታንን የሚያስነሣ እንደሆነ”** ለአይሁድ ቃሉ በፍፃሜው ሰው ሁሉ ከሞት ይነሳል ሲሆን ነገር ግን ጳውሎስ የክርስቶስን ትንሳኤ በማሰብ የተናገረው ነበር፡፡ (1 ቆሮ 15) ሰዱቃውያን በዚህ ንግግር ከፍተኛ ተቃውሞ እንዳላቸው የታወቃ ነው (ሐዋ 23፡1-10)፡፡

> ሐዋ 26:9-11
> **እኔም ራሴ የናዝሬቱን የኢየሱስን ስም የሚቃወም እጅግ ነገር አደረግ ዘንድ እንደገባኝ ይመስለኝ ነበር፡፡ ይህንም ደግሞ በኢየሩሳሌም አደረግሁ፡፡ ከካህናት አለቆችም ስልጣን ተቀብዬ እኔ ከቅዱሳን ብዙዎችን በወህኒ አሳስረኃቸው ሲገድሏቸውም አብሌ ተቸው በምኩራብም ብዙ ጊዜ እየተቀጣሁ ይሰድቡት ዘንድ ግድ አልኃቸው ያለ ልክ ስቁጣባቸውም እስከ ውጭ ሃገር ከተማምች ድረስ እንኳን አሳድድ ነበር፡፡**

26:9 እኔ (ኢጎ) ራሴ (ኢማቱ) በሚል ጳውሎስ የራሱን ፍላጎት በመፈፀም የእግዚአብሔርን መንገስት ይቁወም እንደነበር ተናገረ፡፡ (1 ጢሞ 1፡13) አማኞችን በማሳደድ እግዚአብሔርን የሚያገለግል እና የሚያስደስት ይመስለው ነበር፡፡ ነገር ግን በደማስቆ መንገድ ላይ የጳውሎስ አስተሳሰብ ተቀየረ (ሐዋ 9)

▣ **“የናዝሬት ኢየሲስ”** (ሐዋ2፡21 እና 2፡27) ልዩ ርዕስ ከሚለው በታች ያለውን ይመልከቱ፡፡

26:10 **“ቅዱሳን”** ጥሬ ትርጉሙ **“ቅዱስ”** ማለት ነው፡፡ ጳውሎስ የተገነዘበው የእግዚአብሔርን ሕዝብ እያስቀየ እና እየገደለ እንደነበር አሁን በመረዳት ይን ስያሜ ለሕዝቡ ተጠቅሟል፡፡ በደመስቆ መንገድ ላይ የታየው ራዕ የጳውሎስን ሕይወት በቅስበት መቀየር አስገራሚ ነው፡፡

▣ **“ስልጣን ተቀብዬ”** ጳውሎስ ከሰባዎቹ የእስራኤል ሽማግሌዎች መሃከል ተመራጭ ባለስልጣን ነበር፡፡
“ሲገድሉአቸውም” በክርስቲያኖች ላይ የነበረውን መጠን ሰፊ ስደት የሚያሳይ አመልካች ነው፡፡

▣ **“አብሬ ተቸው”** በግሪክ ፅሁፍ ቃሉ ባለስጣን የሆነ ሰው ለአንድ ጉዳይ ድምፁን መስቱን የሚናገር ስለታዊ ቋንቋ ነው፡፡ ምክንያቱም የትኞቹ አጥቢያ ምኩራቦች ሰው እንደሞት ድምፃቸውን አልሰጡም ምናልባት የአይሁድ ሃይማኖት መሪዎች ይህንን ያደረጉ ነበር፡፡ እንግዲህ ጳውሎስ የሰባምቹ ሽማግሌዎች አባል ከሆነ ትዳር እንደነበረው አመላካች ነው፡፡ አብሬ ታቸው የሚለው በእጣ በጣል ድምፅን መስጠት ሊሆን ይችላል፡፡ (ራዕ 2፡17)

26:11 **“ግድ አልኃቸው”** በ ግሪኩ ፅሁፍ ቃሉ “በሃይል ወይም በግዳጅ” በማለት አብራርቶታል፡፡ (ሐዋ 28፡19) ነገር ግን በዚህ ዓውደ በአውንታዊ መልክ ተቀምጧል::

▣ **“እየቀጣሁ”** በግሪኩ **“በሃይል እና በግፊት”** መሆኑን ይገልፃል ሐዋ 28፡19 በመሆኑም በዚህ ምንባብ ውስጥ ቃሉ ተደጋጋሚ ድርጊት መሆኑነ እንመለከታለን፡፡

▣ **“ይሰድቡት ዘንድ”** ሳውል በህዝብ ሁሉ ፊት ኢየሱስን ይሰድቡት ዘንድ ሰዎችን ያስገድድ እንደነበር የተረከቡት የመፅሐፍ ቅዱሽ ምንባብ ነው፡፡

▣

| | |
|---|---|
| NASB | *"እንዲሰደዱ"* |
| NKSV | *"ከመጠን ባለፈ እንዲሰደቡ"* |
| NRSV | *"እኔ በጣም እሳደብ ነበር"* |
| TEV | *"ጨካኝ ነበርኩ"* |
| NJB | *"ለእነርሱ ያለኝ ጥላቻ ከመጠን በላይ ነበር"* |

*ንጉስ ፈስጠስ ተመሳሳይ ቃል ለጳውሎ ተጠቅሞ እንደነበር በተከታዩ ጥቅስ ውስጥ ተፅፎ እናገኛለን፡፡* (ሐዋ 26፡24)

> *ሐዋ* 26፡12-18
> **ስለዚህ ነገር ከካህናት አለቆች ስልጣንና ትዕዛዝ ተቀብዬ ወደ ደማስቆ ስሄድ ንጉስ ሆይ በመንገድ ሳለሁ እኩል ቀን ሲሆን በዙሪያዬና ከእና ጋር በሄዱት ዙሪያ ከፀሐይ ብሩህነት የበለጠ ብርሃን ከሰማይ ሲበራ አየሁ ሁላችንም በምድር ላይ በወደቅን ጊዜ ሳውል ሳውል ስለምን ታሳድደኛለህ የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ለአንተ ይብሰብሃል የሚል ድምፅ በይብራይስጥ ቋንቋ ሲናገር ሰማሁ፡፡ እርሱም አለኝ አንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ፡፡ ነገር ግን ተነሣና በእግርህ ቁም ስለዚህም እኔን ባየህበት ነገር አገልጋይ እና ምስክር ትሆን ዘንድ ልሾምህ ታይቼሃለሁና፡፡ የሃጢያትንም ስርየት በእኔ በማመን በተቀደሱት መካከል ርስትን ያገኙ ዘንድ ከጨለማ ወደ ብርሃን ከሰይጣን ስልጣን ወደ እግዚአብሔር ዘወር እንዲሉ ዓይናቸውን ትከፍት ዘንድ ከህዝቡና ወደ እነርሱ ከምልክህ ከአህዛብ አድንሃለሁ፡፡**

26፡12 *በሐዋርያት ስራ መፅሐፍ ጳውሎስ ግል ሕይወቱ ሦስት ጊዜ መስክሯል፡፡* (ሐዋ 9፡1-31; 22፡3-21) *እና በዚህ ምዕራፍ፤ የእግዚአብሄር ምርጫ ግልፅ በሆነ ሁኔታ ስለመጣ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ይቅርታ እና ምርጫ በደጋጋሚ ይመሰክራል፡፡*

26፡13 (ከ*ሐዋ* 9፡3) *የተሻለ መረዳት ማግኘት ይቻላል፡፡*

26፡14 ከ*ሐዋ* 9፡4) *የተሻለ መረዳት ማግኘት ይቻላል፡፡*

Frank stag, New Testament theology *ይህ መፅሐፍ በኢየሱስ እና በቤተክርስቲያን መሃከል ያለውን የጠበቀ ግንኙነት ያብራራል፡፡*

*እኛ ከኢየሱስ እና ከሰዎች ጋር በሚኖረን የትኛውም ግንኙነት የሚፈርደው ክርስቶስ ብቻ ነው፡፡ ከእርሱ ጋር የሚኖረን ፍቅር የሚለካው ለወንድሞቻችን በምናሳየው ፍቅር ነው፡፡ በተጨማሪም ሰውን ማገልገል እርሱን እንደምናገለግል ነገር ግን ሰዎችን መናቅ እርሱን እንደመናቅ ይቆጠራል፡፡* (ማቴ 25፡31-46, *ሐዋ* 9፡1-2,4-5;22፡4,7-8;26፡10-11,14-15) *ወንድሞችን መበደል ክርስቶስን መበደል ነው* (1ቆሮ 8፡12)፡፡ *እኛ ምንም እንኳን በስራ የዳን ባይሆንም ግን በእርሱ ይፈረድብናል፡፡ ከክርስቶስ እና ከፀጋው ጋር ያለንን ግንኙነት ስለሚያስረዱ፡፡ ፍርድን በተቀበሉ ላይ ምህረት ያለው ፍርድ ይሆንባቸዋል እናም ለፍርድ ምህረትን ለሚያደርጉ ለእነርሱም ምህረት ይደረግላቸዋል* (ማቴ 5፡7)፡፡

▣ **"ዕብራዊ"** *በጳውሎስ ሦስት የግል ምስክርነቶች ውስጥ ይህ ቃል ትኩረት ተሰቶት መመልከት ይቻላል፡፡*

▣ **"ሳውል፣ ሳውል"** *በዚህ ምዕራፍ በቁጥር* 14፣15 *እና* 16-18 *የተጠቀሰው ኢየሱስ ለጳውሎስ የተናገረው ትኩረት የሚያስፈልገው መሆኑን ለማስገንዘብ ነው፡፡*

▣ **"የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ለአንተ ይብሰብሃል"** *ይህ ሐረግ ለዚህ ዓውድ የተለየ ነው፤ ምክንያቱም ሐረጉ የግሪክ እና የላቲን የአነጋገር ዘይቤ እንጂ የአይሁድ አይደለም ጳውሎስ በሚገባው መንገድ ነበር ጌታ የተናገረው በመሆኑም ሐረጉ የሚያመለክተው ሁለት ነገሮችን ነው፡፡* (1) *ይህ ብረት ሰረገላን የሚጎትት ብረት ነው፣* (2) *ብረት ፈረሱ ወደ ኃላ እንዳይራገጥ የሚከለክለው በማንኛውም ሰርጋ ላይ ከብረት የሚሰራ ዘንግ ነው፡፡ ይህ እንግዲህ በምሳሌ የቀረበ መንፈሳዊ ስልጣንን መቃወም አደገኛ እንደሆነ የጠገለፀበት ቦታ ነው፡፡*

26፡15 ከ*ሐዋ* 9፡5 *የተሻለ መረዳት ያግኙ፡፡*

▣ **"የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ"** *ይህ የሚያመለክተው ኢየሱስ ከቤተክርስቲያን ያለውን የጠበቀ ግንኙነት ነው፡፡* (ማቴ 10፡40;45) *ቤተክርስቲያን መንካት ኢየሱስን እንደመንካት ይቆጠራል፡፡*

26፡16 **"ተነስና በእግር ቁም"** *ከነአብዩ ኤርምያስ የነብይነት አገልግሎት ጥሪ ጋር ተመሳሳይነት አለው* (ኤርም 1፡7-8 *እና* አዝ 2፡1,3)፡፡

▣ **"ስለዚህ እኔን ባየህበት ነገር"** *እግዚአብሔር ለጳውሎስ የተለየ አላማ እንዳለው በግልፅ ራዕይ ለጳውሎስ መታየቱን አመላካች ዐረፍተ ነገር ነው፡፡ የጳውሎስ ጥሪ ከሌሎች ሐዋርያት በተለየ ነው፡፡ እግዚአብሔር ቸርነቱ እና ነፃ ምርጫ በዚህ ምዕራፍ ጳውሎስን ለአገልግሎትና ለህይወት በመመጥራት አሳይቷል፡፡*

▣ **"እኔን ባየህበት ነገር. . . ለአንተም በምታይበት ነገር"** የመጀመሪያው የሃላፊ ጊዜን ሲያመለክት ሁለተኛ ግን የወደፊቱን ያመለክታል። ኢየሱስ የወደፊቱን ለጳውሎስ እየተናገረው ነው። ሐዋሪያው ጳውሎስ በርካታ መለኮታዊ ራዕዮችን ስለ አገልግሎቱ ተመልክቷል (ሐዋ 18፡9-10;22፡17-21;23፡11:27፡23-24) ጳውሎስ ምድረባዳ በነበረው ቆይታ በኢየሱስ ብዙ ነገሮችን ተምሯል። (ገላት 1፡12,17,18 ፍፃሜን ጭምር የሚያሳይ ቃል ነው (ሐዋ 22፡14;26፡16)

▣ **"አገልጋይ እና ምስክር"** የመጀመሪያው ቃል "ከስር የሚሽከረከር" ለመርከብ ሲሆን ቀጥተኛ ትርጉም ለጌታው በታች ሆኖ የሚያገለግል ማለት ነው፤ ሁለተኛው ቃል "Martus" ወይም የእንግሊዘኛው ትርጉም "ሰማዕት" ነው።
ይህ ሁለት ትርጉም አለው
1. ምስክር (ሉቃ 11፡48;24፡48; ሐዋ 1፡8,22;5፡32;10፡39,41፡22፡15)
2. ሰማዕት (ሐዋ 22፡20)
እነዚህ ሁለቱ በየዘመናቱ ያሉ አማኞች የሚያልፉበት ጉዳይ ነው ይህም ወንጌል የሚጠይቀው ህይወት ነው።

**26፡17 "አድንሃለሁ"** ቃሉ የእግዚአብሔርን ምርጫ የሚያመለክት ነው፤ ጥሬ ትርጉም ደግሞ መታደግ ወይም "ማዳን" የሚል ቀጥተኛ ፍቺ አለው (ሐዋ 7፡10; 34; 12፡11;23፡27) በጳውሎስ አገልግሎት የእግዚአብሔር ጥበቃ በእያንዳንዱ አገልግሎት ውስጥ በመላጥ ድፍረትን ሲሰጠው እናነባለን። ይህ ጥቅስ የተወሰደው ከኢሳ 48፡10 እና ከኤር 1፡7-8,19 ነው።

▣ **"ከቡ እና ከአህዛብ"** ጳውሎስ በሁለቱም ከፍተኛ ስደትና ተቃዉሞ ደርሶበታል (2 ቆሮ 11፡23-27)።

▣ **"ወደ እነርሱ ከምልክህ"** "እኔ" ማለቱ "ኢጎ" ከሞለው ከቁጥር አስራ አምስት ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው። "አፓስቲሎ" የሚለው የእንግሊዘኛው ቃል "ሐዋርያ" ትርጉም እግዚአሐሔር ኢየሱስን መላኩን ያሳያል (የሐ 20፡21)።

**26፡18 "ዘወር እንዲሉ አይናቸውን ትከፍት ዘንድ"** ከኢሳ 42፡7 የተወሰደ ነው። መሲሁ ዕውራንን ያመራል፤ ይህም መንፈሳዊ ዕውርነትና ነው። (ዮሐን) ወንጌል እውቀት እና መረዳትን በመስጠት በሃጢያታችን ንስሃ እንድንገባና አማኝ እንድንሆን ይጠራናል። በተቃራኒው ሰይጣን አዕምሮአችንን እና ልባችንን ለማጨለም ይጥራል (2 ቆሮ 4፡4) መንፈስ ቅዱስ የጨለመውን።

▣ **"ከጨለማ . . . ከሰይጣንም ግዛት"** ጎንዮሹን አስተውል። ግዛት በግሪክ ቋንቋ "ኤክሶዚ" በተለየ ሁኔታ ከስለጣንና ከሃይል ጋር ይተረጎማል። (NKJV, NRSV, TEV) ይህቺ ዓለም በክፉው ቁጥጥር ስር ናት ያለችው (ኤፌ 2፡2፣4፡14፣ 6፡10-18፣ 2ቆሮ 4፡4)።
በብሉይ ኪዳን ውስጥ በተለይም በኢሳያስ ትንቢት ውስጥ፣ መሲሁ የሚመጣው ለታወሩት ማየትን ሊሰጥ ነው። ይህ ደግሞ አካላዊውንና ምሳሌያዊ የሆነ ነገርን አመልካች ነው (ኢሳ 29፡18፣ 32፡3፣ 35፡5፣ 42፡7፣16)።

▣ **"ወደ ብርሃንና . . . ወደ እግዚአብሔር"** ንፅፅሩን በመመልከጽ መረዳትን ማግኘት ይቻላል። ጨለማ የክፍ ነገር ምሳሌ በመሆኑ በጥንት ሰዎች ጨለማን ይፈሩ ነበር። ብርሃን ደግሞ የመልካም ነገር፣ የፈውስ፣ የሰላም መግለጫ ነው። (ዮሐ 3፡17-21) በዚህ ምንባብ ውስጥ ጨለማንና ብርሃንን በመግለፅ ማነፃፀር ይችላል።

▣ **"ያገኙ ዘንድ"** የእንግሊዘኛ "ምናልባት ያገኙ ዘንድ" ነገር ግን በግሪኩ "ምናልባት" የሚለው "በእኔ በማመን" በሚለው ተተክቷል። የእግዚአብሔር በረከቶች የሚገኙት በእምነት ምላሽን በመስጠት ነው። (ኤፌ 2፡8-9) ይህም የአዲስ ኪዳን ዋነኛ ትምህርት ነው።

▣ **"የሃጢትንም ስርየት"** ሉቃስ "aphesis" የሚል ቃል ይጠቀማል፤ ይህም ማለት፡-
1. በሉቃ 4፡18 የተጠቀሰው ከኢሳ 61፡1 የተወሰደ ነው። በግሪኩ ደግሞ በዛው 18፡2 እና ዘሌ 16፡26 ያለውን ያንፀባርቃል።
2. በሉቃ 1፡77;3፡3;24 መንፃትን ያመለክታል በግሪኩ ፅሁፍ በዘፀ 15፡3 "የእዳ ዝርዛ" የሚለል ሐሳብ አለው።

▣ **"ርስትን"** የግሪኩ *"ኬልሮስ"* ይህም ማለት ዕጣን መጣል በሚል ፍቺ ይሰጣል። (ዘሌ 16፡8 ዮና 1፡7;ሐዋ 1፡26) ዕጣ የሚጣለው ርስትን የራስ ለማድረግ ነበር (ዘፍ 48፡6;ዘፀ 6፡8 እና አያሱ 13፡7-8) በብሉይ ኪዳን ካህናት የሆኑት ሌዋውያን ርስታቸው እግዚአብሔር ነበር (ዘዳ) 10፡9;12፡12 ዘኑ 18፡20) በአዲስ ኪዳን ደግሞ አማኞቸ ሁሉ ካህናቶች ናቸው (1 ጳጥ 2፡5,9 ሮሜ 8፡15-17)።

▣ **"በተቀደሱት መካከል"** የሰዋሰው ህሀጉ ተደራጊ ሃላፊ ጊዜን ያሳያል። አማኞች በክርስቶስ በሚኖረው ዕምነት ይነፃሉ። (ሐዋ 20፡21) ሐዋ 9፡32 ይመልከቱ። ሰይጣን እና አጋንንቱ ይህንን ከእኛ መውሰድ አይችሉም (ሮማ 8፡31-39)።

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፥ 26፡19-23**
**ንጉስ አግሪጳ ሆይ ስለዚህ ከሰማይ የታየኝ ራዕይ እምቢ አላልሁም። ነገር ግን አስቀድሜ በደማስቆ ላሉት በአየሩሳሌምም በይሁዳም ሃገር ሁሉ ለአህዛብም ንስሃ ይገቡ ዘንድና ለንስሃ የሚገባ ነገር እያደረጉ ወደ እግዚአብሔር ዘወር ይሉ ዘንድና ለንስሃ የሚገባ ነገር እያደረገ ወደ እግዚአብሔር ዘወር ይሉ ዘንድ ተናገርኩ። ስለዚህ አይሁድ በመቅደስ የዙኝ ሊገድሉኝም ሞክሩ። ከእግዚአብሔርም ዘንድ ረድኤት ተቀብዬ ለታናሹም ለታላቁም ስመሰክር እከዚች ቀን ድረስ ቆሜአለሁ። ነብያትና ሙሴ ይሆን ዘንድ ያለውን ክርስቶስ መከራ እንዲቀበል በሙታንም ትንሳኤ ለህዝብና ለአህዛብ ብርሃንን በመጀመሪያ ሊሰብክ እንዳለው ከተናገሩት በቀር አንድ እንኳ የተናገርኩት የለም።**

26፡19 **"ንጉስ አግሪጳ ሆይ"** ጳውሎስ ይህን ሰው በወንጌል ለመድረስ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል (ሐዋ 26፡2-29)

▣ **"እንቢ አላልሁም"** በግሪክ "ፒዛ" ቃሉ "አሳማኝ አምላክ" ከሚባል ከጣኦት ስም የተገኘ ነው በዓውዱ ውስጥ እንደምናየው የአምላክን ጥራ እንቢ ማለት ይቻል እንደነበር ያሳያል። (ሉቃ 1፡17፡ሮማ1; 30, 2 ጢሞ 3፡2; ቲቶ 1፡16; 3፡3) በሌላ ጳውሎስ በፍላጎቱ ሲታዘዝ ማጤን ይቻላል።

▣ **"ከሰማይ የታየኝን ራዕይ"** ጳውሎስ በደማስቆ መንገድ የታየውን ኢየሱስን እየመሰከረ ነው።

26፡20 **"ደማስቆ. . . ኢየሩሳሌም"** (ሐዋ 9፡19-25,27) የጳውሎስን አገልገግሎት በደማስቆ፣(ሐዋ 9፡26-30) የጳውሎስን አገልግሎት በደማስቆ፣ (ሐዋ 9፡26-30) የጳውሎስን አገልግሎት በኢየሩሳሌም እና (ሐዋ 9፡31) የጳውሎስን አገልግሎት በይሁዳ በማንበብ በእነዚህ ከተሞች ያደረገውን ተግባራት ማየት እንችላለን።

▣ **"ንስሃ ይገቡ ዘንድ እና ወደ እግዚአብሔር ዘወር ይሉ ዘንድ"** የጳውሎስ መልዕክት ከመጥምቁ ዩሐንስ ስብከት ጋር ተመሳሳይነት አለው። (ማቴ 3፡1-12; ማርቆ 1፡4-8) እና በኢየሱስ ትምህርት (ማርቆ 1፡15) መመልከት ይቻላል።

"በግሪኩ ንስሃ "የአምሮ ሃሳብ ለውጥ ማድረግ" ሲሆን፤በዕብራይስና "የድርጊት ለውጥ" ማለት ነው። ሁለቱም አውነተኛ መመለስን ይጠይቃሉ። (ሐዋ 2፡38) ሁለቱ ኪዳኖች የሚጠይቁት ለድነት ንስሃ መግባትንና እምነትን ነው (ማርቆ 1፡15;ሐዋ 3፡16,18;20፡21፡26፡18,20)።

▣ **"ለንስሃ የሚገባ ነገር እያደረጉ"** የአማኞች የአኗኗር ዘይቤ የተሰጡላትን እምነት ሊያንፀባርቅ ይገባል። (ማቴ 3፡8;ሉቃ 3፡8,ኤፌ. 2፡8-10 ያዕቆብ እና 1 ዮሐ) አማኞች ክርስቶስን መምሰል አለባቸው (ሮማ 8፡28-29;ገላ 4፡19;ኤፌ 1፡4;2፡10)

26፡21 በዚህ ምንባብ ያለው ሃሳብ የጳውሎስ የስነመለኮት አስተያየት አይደለም ነገር ግን አህዛቦችን ወደ ክርስቶስ ለማስጠጋት የተጠቀመበት ስልት ነው። በመሆኑም ንግግሩ በመቅደስ አነታራኪ ሆኖአል።

▣ **"ሊገድሉኝም ሞከሩ"** በዚህ ዓረፍተ ነገር ላይ የሚገኘው ግስ የሚያመለክተው ድርጊቱ ተደጋጋሚነት እንዳለው ነው። አይሁዶች (ሐዋ 9፡24) እና ከእስያ የመጡ (ሐዋ፡3,19;21፡27,30) ጳውሎስን ለመግደል ብዙ ጊዜ ጥረት አርገው አልተሳካላቸውም።

26፡22 **"ለታናሹም ለታላቁም ስመሰክር"** ይህ የሴሜቲክ ቋንቋ ዘይቤ ያለው ይመስላል። የጳውሎስ ማረጋገጫ ነው (እንደ ጴጥሮስ 10፡38 ይመልከቱ)። እርሱም እንደ እግዚአብሔር ለሰው ፊት እነደማያደላ (ዘዳ 10፡17፣ 2ዜና 19፡7፣ በ10፡34 ላይ ያለውን ሙሉ ማስታወሻ ይመልከቱ) እርሱ ለሰው ልጆች በሙሉ ነው የሰበከው።

▣ **"ነብያትና ሙሴ ሊሆን ዘንድ ያለውን"** ጳውሎስ አድማጮቹን በንግግሩ ለመማረክ ከራሱ ሳይሆን ከብሉይ ኪዳን መፃዕፍት እየጠቀሱ ያስረዳ ነበር። ስለዚህ ጳውሎስ በብሉይ የተላገሩትን ትንቢተቶች እና ቃል ኪዳኖች መፈፀሙን የሚናገር ሰባኪ ነበር።

26፡23 የሐዋሪያው ጳውሎስ መልክት ሦስት አንኳር ነገሮችን ያዘለ ነው፡ (1) መሲሁ ስለ ሰው ልጁ ሃጢያት መሰቃየቱን ይናገራል: (2) የኢየሱስ ትንሳኤ የአማኞች መሰረት መሆኑን ይሰብካል: (3) ወንጌል ለአህዛብና ለአይሁድ መሆኑን ይናገር ነበር። እነዚህ መሰረታዊ ሦስት ነገሮች በቁ 20 ላይ ተጠቃለዋል። በመሆኑም በግላችን በክርስቶስ ፊት በንስሃ ከሃጢያታችን በእምነት ወደ እግዚአብሔር መመለስ እንደሚኖርብን ያመለክታል።

▣ **"ክርስቶስ መከራን እንዲቀበል"** ለአይሁድ የማሰናከያ ትምህርት ነበር (1 ቆሮ 1፡23) ነገር ግን የብሉይ ኪዳን ትንቢት ነበር። (ዘፍ 3፡15; መዝ 22 እና ኢሳ 53)

የግሪኩ "ክርስቶስ" በዕብራይስጡ "መሲህ" የሚል ስያሜ አለው። ጳውሎስ የሰበከው ኢየሱስ የተሰቀለው፣የተቀባው፣በነብያት የተነገለትን ነው (ሐዋ 2፡36;3፡6,18,20;4፡10,26;13፡33;17፡3;26፡23)

▣ "በሙታንም ትንሳኤ ለህዝብና ለአህዛብ" በዚህ ጥቅስ እና የማደን ልጅ መሰረት አድርገው የስህተት ትምህርቶች አንድ የኢየሱስ የማደን ልጅ በመሆኑ መልካም ስነምግባር ስለነበረው እግዚአብሔር እርሱን ከሞት በማስነሳት ሸልሞታል የሚል ነበር። ይህ የተጣመመ ስነመኮት ኢየሱስ ወድሞ አምላክ እንደነበረ የሚክድ ነው (የሐ 1፡1;ፊሊ.2፡6-11;ቆላ1፡15-17,እና ዕብ 1፡2-3)።

▣ "ብርሃን" ቃሉ የሚመሰው በእውነት እና በንፅህና ነው (ቁ.18 እና ኢሳ 9፡2; 42፡6-7)

▣ "ለሕዝብና ለአሕዛብ" ለእነዚህ ለሁለቱም አንድ ወንጌል ተሰጥቷል፤ (ኤፌ 2፡11-3፡13) ይህ በብዙ ዘመናት ከትውልድ ተሰውሮ የነበረ ነው። ነገር ግን አሁን በክርስቶስ ተገልጧል። የሰው ዘር ሁሉ በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥሮአለወ (ዘፍ 1፡26-27) እግዚአብሄር በሃጢያት የሰው ልጅ ከወደቀ በኃላ ኪዳን ገብቶላታል። (ዘፍ 3፡15) ኢሳያስ ኢየሱስ ለአለም ሁሉ እንደተሰጠ ተንብይል (ኢሳ 42፡4,6,10-12;45፡20-25;49፡6;51፡4;52፡10;60፡1-3 እና ሚልክ 5፡4-5)።

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 26፡24-29**

**እንዲህም ብሎ ስለ ራሱ ሲመለስ ፊስጦስ በታላቅ ድምፅ ጳውሎስ ሆይ አብደሃል እኮ ብዙ ትምህርትህ ወደ ዕብደት ያዙርሃል አለው።ጳውሉስ ግን እንዲህ አለ ክብር ፊስጠስ ሆይ የእውነትንና የአዕምሮን ነገር እናገራለሁ እንጂ እብደትስ የለብኝም። በእርሱ ፊት ደግሞ በግልጥ የምናገረው ንጉስ ይህን ነገር ያውቃል ከዚህ ነገር አንዳች እንደይሰወርበት ተረድቼአለሁና አውቃለሁ። አግሪጳም ጳውሎስን በጥቂቱ ክርስቲያን ልታደገኝ ትወዳለህ አለው።ጳውሎስም በጥቂት ቢሆን በብዙ አንተ ብቻ አይደለህም ነገር ግን ዛሬ የሚሰሙኝ ሁሉ ደግሞ ከዚህ እስራት በቀር እንደ እኔ ይሆኑ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር እለምናለሁ አለው።**

26፡24 "ፊስጦስ በታላቅ ድምፅ" የጳውሎስ መልእክት ከጠበቀው በላይ ስሆነበት ንጉስ ፊስጦስ ሊያነውና ሊቀበለው አልተቻለም።

▣ "ብዙ ትምህርትህ ወደ ዕብደት ያዙርሃል" ይህ የሚያሳየው የጳውሎስ የመከላከያ ሂሳት ጥልቅ፣ግልፅ እና አሳማኝ እንደሆነ ነው።

26፡25 "የእውነትንና የአምሮን" ከግሪኩ ሁለት ጥምር ቃል የተሰራ ነው "የሚሰማ" እና "አእምሮ" ይህም ማለት ለህይወት ሚዛናዊ አስተሳሰብን መያዝ የሚል ቀጥተኛ ትርጉም አለው።

▣ "እውነት" ልዩ ትኩረት የሚለው ርዕስ ይመልከቱ።

**ልዩ ርዕስ: "እውነት" በጳውሉስ ደብዳቤዎች**

ጳውሎስ "እውነት" የሚለውን ቃል የብሉይ ኪዳን "ኢሚት" "ታማኝ" የሚል አቻ ትርጉም ተጠቅሟል ከዚህም በበለጠ "እውነት" የሚለው ቃል ከሙት ባህር የተገኙት መፅሐፍት ውስጥ ቀጥተኛ ትርጉሙ "የውዳሴ መዝሙራት" በማለት ያብራራዋል። እውነተኞች ደግሞ የእውነት ምስክሮች ናቸው።

በሐዋሪያው ጳውሎስ ቃሉን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ለመግለፅ ተጠቅሞበታል፡-

1. ሮሜ 1፡18,25;2፡8,20;3፡7;15፡8
2. 1 ቆሮ 13፡6
3. 2 ቆሮ 4፡2;6፡7;11;10;13፡8
4. ገላ 2፡5,14;5፡7
5. ኤፌ 1፡13;6፡14
6. ቆላ 1፡5,6
7. 2 ተሰሎ 2፡10,12,13
8. 1 ጢሞ 2፡4;3፡15;4፡3;6፡5
9. 2 ጢሞ 2፡15,18,25;3፡7,8;4፡4
10. ቲቶ 1፡1,14

ጳውሎስ "እውነተን" እርግጠንነቱን የገለፀበት ቃል ነው።

1. ሐዋ 26፡25
2. ሮማ 9፡1
3. 2 ቆሮ 7፡14;12፡6
4. ኤፌ 4፡25
5. ፊሊ 1፡18
6. 1 ጢሞ 2፡7

ጳውሎስ "እውነትን" የራሱን የውስጥ ፍላጎት ንፅኅና ገልፃበታል 1 ቆሮ 5፡8 በተጨማሪም "እውነት" የአማኝ ሁሉ መገለጫ መሆን አለበት እንዲሁም የሚከተለውን አንብቡ

1. የእግዚአብሔር ምልዳተ ስብዕና መግለጫ ነው። (ኤፌ 4፡21 እና ዮሐ 14፡6)

2. ለኢየሱስ የተሰጠ የመሰከሩት ስለ እውነት ነበር። (ሮሜ 3፡4 ዮሐ 14፡6)
3. ሐዋሪያቶች የመሰከሩት ስለ እውነት ነበር።(ቲቶ 1፡13)
4. ጳውሎስ እውነተኛ ነበር (2 ቆሮ 6፡8)

*ሐዋሪያው ጳውሎስ ብቻ የቃሉን ግስ ተጠቅሟል* (ለምሳሌ aletheuo) ገላ 4፡16 እና ኤፌ4፡15። በተጨማሪም ገለፃ "Colin Brown (ed), *The New international Dictionary of New Testament* theology, Vol 3, pp 784-902"

26፡26-28 **"ንጉስ ይህን ነገር ያውቃል"** ጳውሎስ አግሪጳን የተጠቀመበት ወንጌልን ለመስበክ ነው ቦሆን እርሱንም ወደ ክርስቶስ ለማምጣት ብርቱ ጥረት አድርጓል። በዚህ ምዕራፍ በቁጥር ሃያ ስምንት የተፃፈው የክርስትና መስካሪ እንድሆን ትፈልጋለህን? በማለት ሊተረጎም ይችላል።

26፡26 **"በእርሱ ፊት ደግሞ በግልጥ የምናገረው"** ፀሐፊው ሉቃስ ይህንን ቃል የጳውሎስን ድፍረት ለመግለፅ ይጠቀምበታል። (ሐዋ 9፡27፡28; 13፡46; 14፡3; 18፡26; 19፡8) "በድፍረት መናገርን" ያሳያል። (1 ተሰሎ 2፡2) ይህም ድፍረት በመንፈስ የመምላት አንዱ ምልክት ነው። (ኤፌ 6፡20) የጳውሎስም ፀሎት ጌታ ድፍረት እንዲሰጠው ነው። የወንጌል እወጃ የሚከናወነው ከመንፈስ ቅዱስ ባገናነው ድፍረት መሆኑን መዘንጋት የለብንም።
"ይህ በስውር የተደረገ አይደለምና" ጳጥሮስ በኢየሩሳሌም ለነበሩ አድማጮቹ ይህን አረፍተ ነገር በመደጋገም ተናግሯቸዋል። (ሐዋ 2፡22, 33) ወንጌል ጭብጡና አላማው በግልፅ የሚታወቅ መሆኑን ያስገነዝባል።

26፡27 ጳውሎስ አግሪጳ የብሉይ ኪዳን መፅሐፍቶች ዕውቀት እንዳለሁ ተረድቷል። የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክቶች በሙሉ መሰረት ያደረጉት በብሉይ ኪዳን መፅሐፍትና ትንቢቶች ላይ ነበር።

26፡28

| | |
|---|---|
| NASB | **"በአችር ጊዜ ክርስቲያን ልታደርገኝ ነው"** |
| NKJV | **"ክርስቲያን ልታደርገኝ ምንም አልቀረህ"** |
| NRSV | **"በቶሎ ክርስቲያን የምታደርገኝ ይመስልሃል"** |
| TEV | **"በአጭር ጊዜ እኔን ክርስቲያን እንደምታደር"** |
| NJB | **"ያነሳኸው ጭብጥ እኔን ለጥቂት ክርስቲያን ሊያረገኝ"** |

የቃላት ምርጫ በዚህ ዐረፍተ ነገር ላይ ይታያል፣ "Oligo" ማለት ትንሽ ወይም "ያነሰ"፣ በNASB, NRSV እና TEV ትርጉሞች ላይ ደግም "ባጭር" ጊዜ በ NKJV,NJB ትርጉምች ላይ ደግሞ "በትንሽ ጥረት" በማለት ፍቺ ተሰቷል። በቁ-29 ላይ ተመሳሳዩን እናገኛለን።

በዓውዱ ላይ የትርጉም ሲውጥ ከሚያመጡት አንድ "ልታደርገኝ" (poier) ይህንን (በግሪኩ P,N,A) እናገኛለን፤ ወይም "ለመሆን" ይህን ደግሞ በዕብራይስጡ፣በሦሪያ እና በላቲኑ ትርጉሞች ላይ ማግኘት ይቻላል። የጳውሎስ አላማ ግልፅ ነው እርሱም የሚሰብከው ወንጌል በብሉይ ኪዳን ተያይዞ የመጣ መሆኑን ነው።

▣ **"ክርስቲያን"** የክርስቶስ ተከታዮች በመጀመሪያ ክርስቲያን የተባሉት በአንፃኪያ ነው። (ሐዋ 11፡26) ይህ ስም ከአግሪጳ II አንደበት ተሰምቷል። ይህ የሚያሳየው ስያሜ በዚያ ሰፋት እየታወቀ መምጣቱን ነው።

26፡29 **"ወደ እግዚአብሔር እለምናለሁ"** የጳውሎስ ፀሎቱን እና ምኞቱን የገለፀበት መንገድ ነው፤ ይህም አድማጮቹ ሁሉ ሮማውያን፣አይሁዶች ወደ ክርስቶስ እንደመጡ የተመኘው ጥልቅ ፍላጎቱ ነው።

ሐዋ 26፡30-32

**ንጉሱ አገር ገዢም በርነቄም ከእነርሱም ጋር ተቀምጠው የነበሩት ተነሡ ፈቀቅ ብለውም እርስ በእርሳቸው ይህ ሰው እንኳንስ ለሞት ለእስራትም የሚገባ ምንም አላደረገ ብለው ተነጋገሩ። አግሪጳም ፊስጦስን ይህ ሰው እኮ ወደ ቄሣር ይግባኝ ባይል ይፈታ ዘንድ ይቻል ነበር አለው።**

26፡30 ይህ የባለስጣኖች የግል ንግግር ቢሆንም ሉቃስ ምናልባት ከባለዋላቸው ይህንን ንግግር ሰምቶ ይሆን? ወይስ ንግግራቸው በግምት ፅፎት ይሆን? ነገር ግን ፀሐፊው ሉቃስ አለውን አንፀባርቆበታል እርሱም ጳውሎስም ክርስትናም ለሮማውያን ቅንጣት ያህል ጉዳት እንዳልሆነ አብራርቶበታል።

26፡31፡32 **"ይህ ሰው እኮ ወደ ቄሣር ይግባኝ ባይል ይፈታ ዘንድ ይችል ነበር አለው"** የፀሐፊው የሉቃስ አንዱ ዓላማው ክርስቲያን መሆን አገር መክዳት ባለመሆኑ ለሮማውያን እንደ ትልቅ ችግር የሚታይ አልነበረም።

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት _መመሪያ_ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ለመርዳት ነው የተሰናዱት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋነኞቹን ጉዳዮች ለማጤን እንዲረዳ ነው። ሐሳብ ለማጫር እንጂ መደምደሚያ አይደሉም።

1. ጳውሎስ በዚህ ምዕራፍ ያቀረበው የመከላከያ ሃሳቡ በፊሊክስና በፊስጦስ ፊት ካቀረበው በምን ይለያል?
2. የጳውሎስ የግል ምስክርነቱ ከተከሰተበት ክስ ጋር አብሮ እንዴት ሊሄድ ይችላል።
3. ለአይሁድ የመሲሁ መከራ ለመቀበል መምጣት እንግዳ ነገር ለምን ሆነባቸው?
4. የዚህ ምዕራፍ ሃያ ስምንተኛው ቁጥር ለመተርጎም ለምን ከባድ ሆነ?
5. የፊስጦስ፣የፊሊክስ እና የበርኒቄ እርስ በእርስ ስለ ጳውሎስ መነጋገር ፀሐፊው ሉቃስ ዋነኛ ትኩረት ያደረገበት ለምን ሆነ?

# የሐዋርያት ስራ 27

## የምንባቡ ክፍፍል በአዲሶቹ ትርጉሞች

| የተየመቅሰ[4] | አኪጀት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጳውሎስ ወደ ሮም ሄደ | ወደ ሮም ጉዞ | ወደ ማላታ ጉዞ | ጳውሎስ በመርከሰት ወደ ሮም ሄዶ | ወደ ሮም የተደረገ ጉዞ |
| 27፡1-8 | 27፡1-8 | 27፡1-8 | 27፡1-6 | 27፡1-3 |
| | | | | 27፡4-6 |
| | የጳውሎስ ማስጠንቀቂያ ተናቀ | | 27፡7-8 | 27፡7-8 |
| 27፡9-12 | 27፡9-12 | 27፡9-12 | 27፡9-12 | 27፡9-12 |
| የባህር ላይ ወጀብ | ወጀብ | | በባህሩ ላይ ወጀብ | ወጀብ እና ነፋስ |
| 27፡13-20 | 27፡13-38 | 27፡13-20 | 27፡13-26 | 27፡13-20 |
| 27፡21-26 | | 27፡21-26 | 27፡21-26 | 27፡21-26 |
| 27፡27-32 | | 27፡27-32 | 27፡27-32 | 27፡27-32 |
| የመርከብ መስብር | መርከቡ ተሰበረ | | | |
| 27፡39-44 | 27፡39-44 | 27፡39-44 | 27፡39-41 | 27፡39-41 |
| | | | 27፡42-44 | 27፡42-44 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (ከ "**መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ**" **ገጽ** vii)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

*ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡*

*ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡*

1. ምንባብ አንድ
2. ምንባብ ሁለት
3. ምንባብ ሦስት
4. ወ.ዘ.ተ….

***የዓውዱ ዕይታ***

*ሀ. ሉቃስ የባህር ላይ ጉዞ የጠለቀ እውቀት ነበረው* (A.T Robertson, word pictures in he New Testament, Vol, 3, p, 456) *በዚህ መፅፍ ላይ ሉቃስ መርከበኛ፣ ሃኪም፣ ታሪክ ፀሐፊ እና የስነ መለኮት ሰው መሆኑን ይገልፃል ሉቃስ የሚጠቀምበትን ቋንቋ ጥቂት ዝርዝሮችን እንመልከት፡-*
1. እየቀዘፍን (ሐዋ 13፡4፣14፡20፣20፡15፣27፡1)
2. ተተግነን (ሐዋ 27፡4 7)

3. ጥግ ጥጉን (ሐዋ 27፡13)
4. መርከቡም ተነጥቆ (ሐዋ 27፡15)
5. ነፋሱን ሲቃወም (ሐዋ 27፡15)
6. በተተገንን ጊዜ (ሐዋ 27፡16)
7. አስታጥቀው አፀኑ (ሐዋ 27፡17)
8. አስታጥቀው አፀኑ (ሐዋ 27፡17) የመርከብ ዕንቅፋት (ሐዋ 27፡19)
9. የሰው ቁመት (ሐዋ 27፡28) ሁለት ጊዜ
10. የመለኪያ ገመድ ሐዋ 27፡28 ሁለት ጊዜ
11. አራት መልህቅ አወርዱ (ሐዋ 27፡29 40)
12. የመቅዘፊያው ማሰሪያ (ሐዋ 27፡40)
13. ታናሹ ሸራ (ሐዋ 27፡40)
14. የማዕበል የመርከቡን አቅጣጫ ማስቀየር ( 28፡13 )

ለ. በዚህ ምዕራፍ ላይ ትንታኔ ያለውን መፅሐፍ ያንብቡ ()

ሐ. በመርከብ ወደ ሮም ለመሄድ ጊዜው አስቸጋሪ ነው፡፡ (ሐዋ 27፡1 4 7 9 10 14) ከህዳር እስከ የካቲት የባህር ጉዛ ማድረግ ለከፍተኛ አደጋ ሊያጋልጥ ይችላል፡፡ በተጨማሪም ከእነዚህ ወራት ሁለት እና ሦስት ሳምንት በፊት እና በኃላም የባህር ጉዞ ማድረግ አደገኛ ነበር፡፡ የእህል ማመላለሻ መርከቦች የአስራ አራት ቀን ጉዞ አድርገው ወደ ሮም ይደርሱ ነበር፡፡ ነገር ግን ከማዕበሉ ኀይል የተነሳ በአስራ ስድስተኛው ቀን ሊደርሱ ነበር፡፡ ነገር ግን ከማዕበሉ ኃይል የተነሳ በአስራ ስድስተኛው ቀን ሊደርሱ ይገደዱ ነበር፡፡

መ. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሦስት የተለያዩ የመርከብ አይነቶች መመልከት ይቻላል፡፡
1. በየወደቡ የሚቆም የመርብት አይነት ነበር፡፡
2. ከግብፅ ወደ ጣሊያን የሚያመላልሱ የእቃ ማጓጓዣ መርከቦች ነበሩ፡፡
3. ከደቡብ ሮም እስከ ኔፖል አርባ ሦስት ማይል የሚሄድ ትልቅ ጀልባ አንዱ መጓጓዣ ነው፡፡

**የቃል እና የጥም ቃል ጥናት**

**ሐዋ 27፡1-8**
**ወደ ኢጣሊያም በመርከብ እንሄድ ዘንድ በተቋረጠ ጊዜ ጳውሎስንና ሌሎችን እስረኞች ከአውግስጦስ ጭፍራ ለነበረ ዮልዮስ ለሚሉት ለመቶ አለቃ አሳልፈው ሰጡአቸው፡፡ በእስያም ዳርቻ ወዳሉ ስፍራዎች ይሄድ ዘንድ ባለው በአድራሚጢስ መርከብ ገብተን የመቄዶንያም ሰው የሆነ የተሰሎንቄው አርስጥሮኮስ ከእኛ ጋር ነበረ፡፡ በነገውም ወደ ሲዶና ስንደርስ ዩልዮስ ለጳውሎስ ቸርነት አድርጎ እርዳታቸውን ይቀበል ዘንድ ወደ ወዳጆቹ እንዲሄድ ፈቀደለት፡፡ ከዚያም ተነስተን ነፋሱ ፊት ለፊት ነበረና በቆጀሮስ ተተግነን ሄድን በኪልቅያና በጳንፋልያም አጠገብ ያለውን ባህር ከተሻገርን በኃላ በሉቅያ ወዳለ ወደ ሙራ ደረስን፡፡ የመቶ አለቃውም በዚያ ወደ ኢጣሊያ የሚሄድ የእስክንድርያውን መርከብ አግኝቶ ወደ እርሱ አገባን፡፡ ብዙ ቀንም እያዘገምን ሄደን በጭንቅም ጥግ ጥጉን አልፈን ለሳሲያ ከተማ ወደ ቀረበች መልካም ወደብ ወደሚሉአት ስፍራ መጣ፡፡**

27፡1 "ወደ ኢጣሊያ በመርከብ እንሄድ ዘንድ በተቆረጠ ጊዜ" እንሄድ ዘንድ የሚለው በብዙ ቁጥር የተቀመጠው ተውላጠ ስም የሚያመለክተው ጳውሎስንና ሉቃስ ሌሎችንም የመርከብ ተሳፋሪዎችንም ይጨምራል፡፡ ሐዋ 16፡10-17 20፡5፡151-18፣27፡1-28፡16

▣ "ሌሎችም እስረኞች" የሮም የመንግስት እስረኞች መሆናቸው እንጂ ሌላ የሚታወቅ ነገር የለም፡፡

▣ "ጭፍራ" በአዲስ ኪዳን ቃሉ በአዎንታዊ ሃሳብ ተፅፏል፡፡ (ማቴ 8፣ ሉቃ 7፡23፡47፣ ሐዋ 10 እና ሐዋ 21-28)

▣ "የአውግስጦስ ጭፍራ" በሮም እና በአውራጃዎቿ ላይ የተሾሙ አለቆች ነበሩ፡፡ (W.Ramsay, St. Paul the Traveler and Roman citizen, PP 315,348) ይህ በማስረጃነት ይቅረብ እንጂ የተረጋገጠ አይለም፡፡

27፡2 "በአድራሚጢስ መርከብ" ይህ በትንንሽ የባህር ወደቦች የሚቆም መርከብ ነው፡፡ የመርከቡ መቆሚያ በትንሹ እስያ በመሲያ ነው፡፡ እንግዲህ ይህ የመርከብ ጉዞ ወደ ሮም ለመሄድ ረጅምና አደገኛ ነው፡፡

▣ "አውግስጦስ" ይህ ሰው የሚኖረው በተሰሎንቄ ከተማ ነው፡፡ በዚህ ምንባብ ደግሞ ወደ ቤቱ እየተመለሰ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሐዋ 19፡29፣ 20፡4 ቆላ 4፡10 እና ፊሊ 24)

27፡3 "ሲዶና" ከሰሜን ቂሳርያ በ67 ማይል ርቀት ላይ የምትገኝ፡ የፊንቃውያን ከተማ ነች፡፡

▣
**NASB "በመርዳት"**

NKSV, NRSV "በትህትና"
TEV "ትሁት ነበር"
NSB "ተረድቶ ነበር"

ይህ ከሁለት ጥምት ቃሎት የተሰራ ነው "ፍቅር" (*Philos*) እና የሰው ፍጥረት (*Anthropos*) በሐዋርያት ስራ መፅሐፍ ሁለት ጊዜ ተፅፏል፡፡ (ሐዋ 28፡2) በቲቶ 3፡4 እና ሐዋ 27፡3 ላይ በተውላጠግስ ተቀምጧል፡፡ ዩልዮስ የጳውሎስን በመስማት ርህራሄ አድርጎለታል፡፡

▣ **"ባልንጀሮቹ"** ክርስቲያኖችን ለማመለከት ነው፡፡

▣ **"ይቀበል ዘንድ"** ምንባቡ ምን እንደተቀበለ በግልፅ አያሳያም፡፡

27፡4 **"በቆጵሮስ ተተግነን"** ይህ ሐረግ በእንግሊዘኛው ሲነበብ በደቡብ ቆጵሮስ ሲያመለክት ነገር ግን በሰሜን ለማለት እንደሆነ ከንባቡ እናገኛለን፡፡ በተጨማሪም ሌሎቹ ትርጉሞች በደቡብና በምዕራፉ የባህር መንገድ በማለት ተርጉመውታል፡፡

27፡6 **"የእስክንድሪያውን መርከብ"** ይህ 276 ሰዎችን እና ከባድ ክብደት ያላቸውንም ዕቃዎች የሚጭን ከግብፅ ወደ ጣሊያን የሚሄድ መርከት ነበር፡፡ የመርከቡን ምስል ፖፒስ በሚባል ግድግዳ ላይ በግብፅ ሃገር ተስሎ ይገኛል፡፡ እንድሁም በሉሲያን ፅሑፎች ውስጥ በዘርዝር ተዘግቦ ይገኛል፡፡ (Thucydides, Hist.) የዚህ ትልቅ መርከብ ወደብ ሜራ ይባላል፡፡

27፡7 **"ቀኒዶስ"** በደቡብ ምዕራፍ የሮም አውራጃ በእስያ ነፃ የሆነ የባህር በር ያለበት ቦታ ነበር፡፡ የሮም በርካታ መርከቦች የሚቆሙበት ወደብ ነበር፡፡ (Thucydides, Hist. 8.35) በዚህ የባህር ወሽመጥ ሁለት ወደቦች ይገኙ ነበር፡፡

▣ **"ሰልሙና"** በምስራቅ ጫፍ በክሪት ደሴት የሚገኝ መከተማ ነው፡፡ ይህ ወደብ ሳይሆን መለስተኛ የውሃ አካል ያለበት ቦታ ነው፡፡ በመሆኑም በበጋ እዚህ አካባቢ መሆን አይቻልም፡፡

27፡8 **"መልካም ወደብ"** የባህር በሩ የሚገኘው በደቡብ ለሳሲያ ከተማ በክሪት ነው፤ በቦታው በረዶአማ በመሆኑ ለረጅም ጊዜ መቆየት ለህይወት አደገኛ ነው፡፡

| |
|---|
| **አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 9፡12**<br>**ብዙ ጊዜም ካለፈ በኃላ የጦም ወራት አሁን አልፎ ስለነበር፡ በመርከብ ለመሄድ አሁን የሚያስፈራ ነበርና ጳውሎስ እናንተ ሰዎች ሆይ ይህ ጉዞ በጥፋትና በብዙ ጉዳት እንዲሆን አያለሁ ጥፋቱም በገዛ ህይወታችን ነው፡፡ እንጂ በጭነቱና በመርከቡ ብቻ አይደለም ብሎ መከራቸው የመቶ አለቃው ግን ጳውሎስ ከተናገረው ይልቅ የመርከብ መሪውንና የመርከቡን ባለቤት ያምን ነበር፡፡ ያም ወደብ ይከርሙበት ዘንድ የማይመች ስለሆነ የሚበዙቱ ቢቻላቸው በሰሜንና በደቡብ ምዕራብ ትይዩ ወዳለው ፋንቄ ወደሚሉት ወደ ቀርጤስ ወደብ ደርሰው ይከርሙ ዘንድ ከዚያ እንዲነሡ መከሩ፡፡** |

27፡9 የአየሩ ፀባይ መለዋወጥ የመርከብ ጉዞውን ማሰናከሉን ይህ ዓረፍተ ነገር ይናገራል፡፡ በሜዲትራኒያን ባህር በዚህ ወራት የሚሳነው ነፋስ በባህሩ ላይ ወጀብ ያስነሣል፤ ይህ የተለመደ ነው፡፡

▣ **"ፆም"** ሌዋ 16 ያመለክታል፡፡ ሙሴ በፃፈው መፅሐፍት ውስጥ ከዚህ ፃም የተለመደ አይደለም፡፡
እንግዲህ ይህ የባህር የመርከብ ጉዞ የተደረገው በመስከረምና በጥቅምት መሃከል ነው፡፡

▣ **"ጳውሎስም ጀመረ"** ሁለት ነገሮችን ያመለክታል፡ (1) ጳውሎስ ከመጀመሪያው ጀምሮ ሲናገር ሰሚ አላገኘም፣ (2) ጳውሎስ ገና ሲናገር ጀምሯል የሚል ትርጉም አለው፡፡

27፡10 ጳውሎስ የማስጠንቀቂያ ንግግር ቢናገርም የሚሰማው አልነበረም፡፡ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያሉትን ሰዎች ሊሰጠው ስለነበረ ይሆን ያልሰሙት ወይስ ጳውሎስ የራሱን ምክር በመለገሱ አድማጭ ሳያገኝ ቀርቶ ይሆን (ቁ 24)

27፡11
NASB "መሪው እና ነጂው"
NKJV "ነጂው እና ባለቤቱ"
NRSV "ነጂው እና ባለቤቱ"
TEV,NSB "መሪው እና ባለቤቱ"

ይህ ሐረግ ሁለት የተለያዩ ሰዎችን ያመለክታል፡-

1. የመጀመሪያው ፖይለቱ የመርከቡ ነጂ ነው (ራዕ 18፡17)
2. ባለቤቱ የሚለው የመርከቡ ባለንብረት ለማለት ተፈልጎ ነው፡፡ (F.F Bruce, *The Book of Acts*, P507, Quotes Ramsay, St. *Paul the Traveler*, P.324, Who Quotes *Inscriptiones Graecae*, 14,918) ነገር ግን በተከታዩ መፅሐፍ ላይ የሁለቱ ትርጉም በውል እንደሚታወቅ ይናገራል፡፡ (Louw and Nida,

*Greek-English Lexicon*, vol.1, P.548 Vs Harold Moulton The Analytical *Greeak Lexicon Revised*, P.275) የአሌክሳንዲሪያ መርከብ ከትልቅነቱ የተነሳ በርካታ የመርከብ አስተባባሪዎችና መሪዎች እንደሚኖሩ ይገመታል፡፡

27:12 **"ቢቻላቸው"** መርከበኞቹ በዚህ ጊዜ በባህር መጓዝ አደገኛ እንደሆነ እያወቁ መሄዳቸው ስህተት ነበር፡፡

▣ "ፋንቄ" በደቡብ ባህር በቀዳ የሚገኝ ወደብ ነው፡፡ የዚህን የባህር በር ትክክለኛ ቦታ ለማወቅ በምሁራን መሃከል ክርክር አለ፡፡ (Strabo, *Geography*, 10:4.3 Vs Ptolemy, An *Egyptian Geography* 3.17.3) በአሁኑም ጊዜ ይህ ወደብ ግልጋሎት ይሰጣል፡፡

▣ **"በሰሜን እና በደቡብ ምዕራብ ትይዩ"** በፋንቄ ሁለት ከተሞችን ያመለክታል ከአንዱ ከተማ ወደብ ከአንድ አቅጣጫ የሚመጣውን ነፋስ ሲያስተናግድ ሌላኛው ወደብ ከተማ ደግሞ ከተቃራኒ አቅጣጫ የሚመጣውን ያስተናግዳል፡፡ በመሆኑም የባህር ጉዞአቸው ባነፋሱ አቅጣጫ ይወሰናል፡፡

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 27:13-20**
**ልከኛም የደቡብ ነፋስ በነፈሰ ጊዜ እንዳሰቡት መስሎአቸው ተነሡ በቀርጤስም አጠገብ ጥግ ጥጉን አለፉ፡፡ ነገር ግን እጅግ ሳይዘገይ አውራቂስ የሚሉት ዓውሎነፋስ ከዚያ ወረደባቸው መርከቡም ተነጥቆ ነፋሱን ሲቃወም መሄድ ስላልቻለ ለቃነው ተነዳን ቄዳ በሚሉአት ደሴት በተተገንን ጊዜ ታንኳይቱን ለመግዛት በጭንቅ ቻልን ወደ ላይም ካወጡአት በኃላ መርከቱን በገመድ አስታጥቀው አፀው ስርቲስም ወደሚሉት ወደ አሸዋ እንዳይወድቅ ፈርተው ሸራውን አውርደው እንዲሁ ተነዱ ነፋሱም በርትቶ ሲያስጨንቀን በማግስቱ ከጭነቱ ወደ ባሕር ይጥሉ ነበር፡፡ በሦስተኛውም ቀን የመርከቡን ዕቃ በእጃችን ወረወርን ብዙ ቀንም ፀሐይን ከዋክብትንም ሰናይ ትልቅ ነፋስም ሲበረታብን ጊዜ ወደ ፊት እንድናለን የማለት ተስፋ ሁሉ ተቋረጠ፡፡**

27:14
NASB, NRSV **"አመፀኛ ነፋስ"**
NKSV **"መቆጣጠር የማይቻል ነፋስ"**
TEV **"በጣም ጠንካራ ነፋስ"**
NJB **"አውሎ ነፋስ"**
የግሪኩ ፅሑፍ "በጣም አመፀኛ ነፋስ" በሚል ተርጉሞታል፡፡ ይህ ነፋስ በክሪት ሰባት ሺ እግር ጫማ ያህል ከፍታ ቦታዎችን ይሸፍናል፡፡

▣
NASB **"አውራቂስ"**
NKJV **"አሮክራዶን"**
NRSV, TEV **"የደቡብ ምስራቃዊ"**
NJB **"የደቡብ ምስራቃዊ"**

የዚህ ባህር መርከበኞች ወቅቱን በማገናዘብ ለነፋሱ ያወጡለት ስያሜ ነው ቃለ የተሰራው፡ (1) ከግሪኩ ቃል "የምስራቅ ነፋስ" (*euros*) ማለት ነው፣ (2) ከላቲኒ ቃል "ከሰሜን ነፋስ" (*quilo*) ከሚለው አውቃቂስ ተሰይሟል፡፡
የመርከበኞች ቋንቋ (*eukakulon*) ከመሆኑ የተነሣ፡ ፀሐፊዎች የዳውዱን ትርጉም ለመጠበቅ የራሳቸው የአፃፃፍ ስልት መጠቀም ፅሑፍ ስሜት እንዲሠኝ አድርገዋል፡፡

27:15 **"ነፋሱን ሲቃወም መሄድ ስላልቻለ"** የጥንት መርከቦች በጐንና በጐን የአይን ምስል ይሳልባቸው ነበር፤ በኃላ ደግሞ የሰው እና የሌሎች እንስሳት ምስል ይቀረፅ ጀመር፤ (ሐዋ 28:11) በመሆኑም ይህ ሐረግ ቀጥተኛ ትርጉሙ "መቃወም" የሚል ነው፡፡

27:16 **"ቄዳ"** በደቡብ ክሪት ሃምሳ ማይል ላይ የምትገኝ ደሴት ነች፡፡ በዚህ ወቅት በሰሜን ምስራቅ ነፋስ ወደሴቲቱ የምትመታበት ጊዜ ነው፡፡ በመሆኑም ከማዕበሉ የሚያመልጡበትን ዘዴ ቀይሰው ነበር፡፡
በግሪኩ ፅሑፍ የዚህን ደሴተ ስያሜዎች እንመልከት፡-
1. *ካዳአ*, MSS P.B
2. *ካልዳአ*, MSS , A
3. *ካልደን*, MSS H.L.P
4. *ጋደን*, የጀሬም መፅሐፍ ቅዱስ
5. *ካልዲዮን*, some minucle manuscripts

▣ "ታንኳይቱን ለመግዛት በጭንቅ ቻልን" ሐረጉ የሚያመለክተው ትንሿን የመርከቡን ታንኳ ለመቆጣጠር የነበረውን ትግል ያሳያል (ሐዋ 27:30 32)፡፡

27:17 **"መርከቡን በገመድ አስተጥቀው አፀኑ"** ይህ መርከበኞች ለማሰር የሚጠቀሙበት ጠንካራ ገመድ ነው፡፡

▣ **“ሽራውን አውርደው”** በዚህ አውድ ውስጥ አውርደው የሚለው ቃል ትኩረት ተሰቶታል። በመሆኑም እነዚህ ሰዎች ያወረዱት ምንድነው።

▣ **“የባህሩን መልህቅ”** ይህንን ዓውድ በትክክል ለመተርጎም “መቀነስ” የሚለውን ቃል በትክክል መረዳትን ይጠይቃል። እነርሱ ምንን ነበር የቀነሱት፡ (1) የባህሩን መልህቅ፣ (2) ከመርከቡ እቃዎች አንዳንዶቹን ይህን ያደረጉበት ዓላማ የመርከቧን ጭነት ለመቀነስ እና ለመቆጣጠረ እንዲያመቻቸው ነው።

ይህ የባህር መልህቅ እንደፖራሹት የሚዘረጋ ፍጥነቱን እና አቅጣጫውን የሚቀይር ነው በመሆኑም ይህንን ፖራሹት በመዘርጋት አቅጣጫቸውን መቀየር ችለዋል። (Old Latin text and NASB, NRSV እና NJB እና የሦሪያ ትርጉም በእንግሊዘኛ የተፃፈው) የግሪኩ ቃል “ነገር” ፅፎታል ነገር ግን በዓውዱ መሠረት መተርጎም አለበት። (Louw & Nida, *Greek-English Lexicon*, vo12, P.223) (Moulton እና Milligan, *The Vocabulary of the Greek Testament*, P.577) በመሆኑም የመርከቡን ክብደትና ፍጥነት በመቀነስ መርከቡን መቆጣጠር ችለዋል።

27፡18-19 የማዕበሉን ሃይለኝነት የሚያመለክት ዓረፍተ ነገር ነው።

27፡18 **“የመርከቡን ዕቃ ወረወርን”** እነዚህ መርከበኞች በእውነት ለህይወታቸው እጅግ ሰግተው እንደነበር አረጋጋጭ ቃል ነው።

27፡19 **“የመርከቡን ዕቃ”** በዚህ ሐረግ ላይ የተጠቀሰው ዕቃ ምን እንደሆነ አልተገለፀም። በቁ.17 ላይ ተመሳሳይ ቃል በመጠቀሱ የሚያሻማ ትርጉም ይሰጣል።

27፡20 **“ፀሐይንም ክዋክብትንም ሳናይ”** ይህ ሐረግ የሚያሳየው የት ቦታ እንዳሉ አለማወቃቸው ነው። የሰሜን አፍሪካን የባህር ጠረፍ ጠንቅቀው ስለሚያውቁት እጅግ ይፈሩታል። በመሆኑም ምን ያክል ርቀት ለወደቡ እንደቀራቸው መናገር አልፈለጉም ነበር። (ቁ. 29) ፀሐይንና ክዋክብትን ሳያዩ መርከበኞች አቅጣጫቸውን ማወቅ አይችሉም ነበር።

▣ **“ወደፊት እንድናለን የማለት ተስፋ ሁሉ ተቆረጠ”** ጳውሎስ ወደፊት የመኖሩ ተስፋ የተመሠረተው በእግዚአብሔር ለእርሱ ባለው ራዕይ ላይ ነው (ሐዋ 27፡21-26)።

> **አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 27፡ 21-26**
> **ሳይበሉም ብዙ ቀን ከቆዩ በኃላ ያን ጊዜ ጳውሎስ በመካከላቸው ቆሞ እንዲህ አለ እናንተ ሰዎች ሆይ ሰምታችሁኝስ በሆነ ኖሮ ከቀርጤስ እንዳትነሱ ይህንም ጥፋትና ጉዳት እንዳታገኙ ይገባችሁ ነበር። አሁንም አይዞአችሁ ብዬ እመክራችለሁ። ይህ መርከብ እንጂ ከእናንተ አንድ ነፋስ እንኳ አየጠፋምና የእርሱ የምሆንና ደግሞ የማመልከው የእግዚአብሔር መልአክ በዚች ሌሉት በአጠገቤ ቆሞ ነበርና እርሱም ጳውሎስ ሆይ አትፍራ በቄሣር ፊት ልትቆም ይገባሃል እነሆም እግዚአብሔርም ከአንተ ጋር የሚሆዱትን ሁሉ ሰጥቶሀል አለኝ። ስለዚህም እናንተ ሰዎች ሆይ አይዞአችሁ እንደ ተናገረኝ እንዲሁ እንዲሆን እግዚአብሔርን አምናለሁና። ነገር ግን ወደ አንዲት ደሴተ እንድወድቅ ያስፈልገናል።**

27፡21 **“ሳይበሉም ብዙ ቀን ከቆዩ በኃላ”** ይህን ዐረፍተ ነገር በሦስት መንገዶች መመልከት ይቻላል። (1) ከወጀቡ ፍርሃት የተነሳ ምግብ አልበላ ብሏቸው ሊሆን ይችላል፣ (2) በመርከብ ውስጥ ያሉ ሁሉ በየሀይማኖታቸው እየፀለዩና እየፃመ ሊሆን ይችላል (ቁ. 29)፣ (3) መርከቡን ለማዳን ጥረት ያደረጉ ስለነበር ለምግብ ትኩረት ላይሰጡ ይችላል።

▣ **“ሰምታችሁኝ በሆነ ኖሮ”** ጳውሎሰ ከመንፈሰ ዓለም የተረዳውን ባለመስማታቸው ለከፋ ችግር ተጋልጠዋል።

27፡22 **“ይህ መርከብ እንጂ”** ሐዋ 27፡26 ይመልከቱ።

27፡23 **“የጌታ መልአክ”** ጳውሎስን በተለያዩ ጊዜያት ኢየሱስ እና መላእክት እየተገለጡ ጳውሎስን ያፅናኑትና ያበረታቱት ነበር። (ሐዋ 18፡9-10፡22፡17-19፣ 23፡11፣ 27፡23-24) እግዚአብሔር የወንጌል አገልግሎትአላማ ለጳውሎስ ነበረው። (ሐዋ 27፡26፡9፡15)

27፡24 **“አትፍሩ”** በድርጊት ላይ ያለን ማንኛውንም እንቅስቃሴ የሚገታ ቃል ነው (ሐዋ 23፡11፣ ምሳ 3፡5-6)

▣ **“ካንተ ጋር የሚሄዱትን በሙሉ ሰቶሃል”** በዓረፍተ ነገሩ ላይ የሚገኘው ዓስ የተደመደመን ውሳኔ ያሳያል። እግዚአብሔር በጳውሎስ አገልግሎት ዓላማ እንዳለው በግልፅ ማየት ይቻላል። (ሐዋ 9፡15፣ ሐዋ 19፡21፣ 23፡11) በሮማውያን ባለስልጣናት ፊት ስለኢየሱስ እንዲመሰክር የጌታ ፈቃድ ነበር።

የጳውሎስ ህይወት እና የእምነት ጀግንነት ለባልንጀሮቹ ምሳሌ ነበር። (በ ዘዳ 5፡10፣7፡9 1ቆሮ 7፡14) ተመሳሳይ ታሪክ እናገኛለን። ጳውሎስ በዚህ ድርጊቱ በአማኞች፣ በባልንጀሮቹ እና አብረውት በሚሰሩ ሁሉ ላይ መልካም ተፅኖን ያሳደረ ሰው ነበር።
27፡25 በዚህ ቁጥር ላይ የሚታየው የጳውሎስ ንግግር በዚህም ዘመን ያሉትን አማኞች የሚያበረታ ነው።

▣ "እግዚአብሔርን አምናለሁ" ጳውሎስ ከክርስቶስ ጋር በደማስቆ መገናኘቱ እግዚአብሔርን እንዲያምነው አስችሎታል። እምነት ደህነነትን የምንቀበልበት ብቻ ሳይሆን የዛሬውንም በረከት ከእርሱ የምንቀበልበት መሣሪያ ነው።
Rober B. Girdlestone, Life of faith በሚለው መፅሐፍ ያሰፈረውን እንመልከት።
አዲስ ኪዳን በእምነት እና በተስፋ መሃከል ልዩነት እንዳለ ያስተምራል። እምነት የእግዚአብሔር ቃል እንዳለ መቀበል ሲሆን ትዕግስ ወይም ተስፋ ግን አማኞች እንደማሆን ሳይጠራጠሩ ጊዜ በመስጠት የሚያሳዩት የኑሮ ዘይቤ ነው። ከፈጣሪ መልእክት ሲመጣልኝ አስደንጋጭ፣ ቃልኪዳን ወይም ትዕዛዝ ሊሆን ይችላል። ይህንን የመጣልኝን ቃል በእምነት ከተቀበልኩት በረከት ይሆንልኛል። እምነት እንደ መፅሐፉ ቅዱስ አስተምርሆት ቃልን፣ መልእክትን ወይም እውነተኛ የእግዚአብሔርን ቃል በእውነት መቀበል እና በተነገረው ቃልና የተስፋ ቃል መደገፍ ነው። በመሆኑም የተቀበለው ሰው እምነቱን በተግባርና በተነገረው መሠረት በተግባር ሲያውል እምነት አለው ሊባል ይችላል። እንዲሁም ፍሬውም የተቀበለው መልእክት ውጤት መሆኑን መዘንጋት የለብንም ኖህ በእምነት መርከብ ይሰራ ነበር፣ አብርሃም በእምነት ልጁ ሊሰም ነበር፣ ሙሴ የፈርኦን የልጅ ልጅ እንዳይባል በእምነት እንቢ ብሎአል፣ የእስራኤል ልጆች የኢያሪኮነ ግንብ በመዞር እንደሚፈርስ አምነዋል እንደተናገረኝ እንዲሁ እንዲሆን እግዚአብሔርን አምናለሁ፤ ይህን መፅሐፍ ቅዱስ እምነት ብሎ ይጠራዋል። (P.P 104-105)

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 27፡ 27-32**

**በአስራ አራተኛውም ሌሊት በአድርያ ባህር ወዲህና ወዲያ ስንነዳ መርከበኞች በእኩል ሌሊት ወደ አንድ ምድር የቀረቡ መሰላቸው መለኪያ ገመድን ቢጥሉ ሀያ በሰው ቁመት አገኙ ጥቂትም ቆይተው ሁለና ቢጥሉ አስራ አምስት በሰው ቁመት አገኙ ድንጋያማ ወደ ሆነው ስፍራ እንዳይወድቁ ፈርተው ከመርከቡ በስተኃላ አራት መልህቅ አወረዱ ቀንም እንዲሆን ተመኙ። መርከበኞቹም ከመርከቡ ይሸሹ ዘንድ ፈልገው ከመርከቡ በስተለተ መልህቅ መጣል እንዳላቸው አመካኝተው ታንኳይቱን ወደ ባህር ባወርዱ ጊዜ ጳውሎስ ለመቶ አለቃውና ለወታደሮች ወታደሮቹ የታንኳይቱን ገመድ ቆርጠው ትወድቅ ዘንድ ተዋት።**

27፡27 "በአስራ አራተኛውም ሌሊት" የሄዱበትን የባህር መንገድ ርቀት በቀን ብዛት ለክተውት እናያለን። የመንገዱ ርቀተ 476 ማልይ ሲሆን በሃያ አራት ሰዓት ጊዜ ውስጥ ሰላሳ ስድስት ማይል ተጉዘዋል።

▣ "አድርያቲክ ባህር" በደቡ መካከለኛ ሜዲትራኒያን የሚገኝ ቦታ ነው። ነገር ግን የአሁኑን አድርያ ባህር የሚያሳይ አይደለም።

▣ "ወደ አንድ ምድር የቀረቡ መሰላቸው" በባህር ዳር የሚታዩትን ወፎችና አሶችን አይተው ዳር የደረሱ መስሏቸው ሊሆን ይችላል።

27፡28 "መለኪያ ገመድ" ይህ ክብደት ያለው ገመድ ነው በመሆኑም ገመዱን ወደ ባህር ውስጥ በመክተት ጥልቀቱን ማወቅ ይቻል ነበር።

▣ "አስራ አምስት በሰው ቁመት" መርከበኞች ጥልቀትን ለመለካት የሚጠቀሙበት የተለመደ የንግግር ስልት ነው። (በሌላው ትርጉም ሁለተ የሰው ክንድ ያህላል የሚል አለ ወይም ስድስት ጫማ)

27፡29 በዚህ ቁጥር ላይ ጳውሎስና ሰዎቹ በጨለማ ውስጥ ከመሆናቸው የተነሣ የት እንዳሉ እንኳን አያውቁም። መርከቢቱን በቀስታ በመንዳት ወደብ መፈለጋቸውን የሚያሳይ ነው።

27፡30 እነዚህ መርከበኞች እምነት የላቸውም ነገር ግን እራሳቸው ለማዳን ማንኛውንም ነገር ከማድረግ ወደ ኃላ የማይመለሱ ናቸው።

27፡31 ሐዋርያው ጳውሎስ በተመለከተው ራዕይ እና በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን መሃከል በቀጥታ የተገናኘ ሁኔታ በዚህ ቁጥር ላይ ይታያል።

▣ "ትድኑ ዘንድ" በብሉይ ኪዳን ከሞት መዳንን ያመለክታል። (ያዕቆ 3፡15) በአዲስ አበባ ኪዳን ደግሞ መንፈሳዊ መዳንን ያመለክታል ምክንያቱም በመርከቡ ላይ የጳውሎስን ስብከት መንገደኞቹ፣ ወታደሮቹ፣ መርከበኞቹ፣ እና ሌሎች እስረኞች በመስማማታቸው ነው። ነገር ግን ከስጋ ሞት ሰው ድኖ መንፈሳዊ ሞት ከሞተ አሳዛኝ ነው።

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 27፡33-38**

**ቀንም ሲነጋ ጳውሎስ ምግብ ይበሉ ዘንድ ሁሉን ይለምን ነበር እንዲህም አላቸው እየጠቃችሁ ምንም ሳትቀበሉ ጠማችሁን ከሰነበታችሁ ዛሬ አስራ አራተኛ ቀናችሁ ነው። ስለዚህ ምግብ ትበሉ ዘንድ እለምናችኃለሁ።ይህ ለደህንነታችሁ ይሆናልና ከእናንተ ከአንዱ የራስ ጠጉር እንኳ አትጠፉምና ይህም ብሎ እንጀራ ይዞ በሁሉ ፊት እግዚአብሔርን አመሰገነ ቁርሶም ይበላ ዘንድ ጀመረ። ሁሉም ተፅናንተው ራሳቸው ደግሞ ምግብ ተቀበሉ። በመርከቡም ያለን ሁላችን ሁለት መቶ ሰባ ስድስት ነበር። በልተውም ባጠገቡ ጊዜ ስንዴውን ወደ ባህር እየጣሉ መርከቡን አቃለሉት።**

27:34 ከእናንታ መካከል ከራሱ ፀጉር አንዲት እንኳ የሚነካነት ማንም የለምና ጳውሎስ ኢየሱስ እንደተጠቀመው ዓይነት ቃል ነበር፡፡ በትክክል የተጠቀመው (ሉቃ 12:7፣ 21:18) ይህ የእብራውያን የመተማመን መግለጫ ነው (1ሣሙ 14:45፣ 2ሳሙ 14:11፣ 1ነገ 1:52)፡፡

27:35 ይህ የግታን እራት አመልካች አይደለም ግን የጳውሎስን እምነት ያሳያል፡፡ በመከራ መሃከል እንኳን የጳውሎስም እምነት በሌሎች ላይ ተጽ ዕኖን ፈጥሮአል (ቁጥር 36)፡፡

27: 37 ***ሁለት መቶ ሰባ ስድስት"*** ይህ ሁሉንም ተጓዦችን ጨምሮ ነው፡፡ በ4ኛው ከ/ዘመን የነበረው ፅሁፍ ለ76 ሲል ሌሎቹ ግን '276' በማለት ይተልጻሉ፡፡ በ4ኛው ከ/ዘመን የነበረው ሌላኛው ፅሁፍ ሀ ደግሞ 275 ይለዋል፡፡ ሁሉም የእንግሊዘኛ ዘመናዊ ትርጉሞች '276' የሚለውን ይዘዋል፡፡

27:38 ይህ ከግብፅ የሚነሣ ትልቁ መርከብ ነው፡፡ እነርሱ አስቀድመው ብዙ ዕቃዎችን ወደ ባሕር በመጣል አቅለውት ነበር (ቁ 18)፡፡

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 27:33-38**
***[39]በነጋም ጊዜ ምድሩን አላወቁትም፥ ነገር ግን የአሸዋ ዳር ያለውን የባሕር ስርጥ ተመለከቱ፥ ቢቻላቸውም መርከቡን ወደዚያ ይገፉ ዘንድ ቈረጡ፡፡ [40]መልሕቆቹንም ፈትተው በባሕር ተዉአቸው፥ ያን ጊዜም የመቅዘፊያውን ማሠሪያ ፈቱት፤ ታናሹንም ሸራ ለነፋስ ከፍ አድርገው ወደ ዳር አቅንተው ይሄዱ ዘንድ ጀመሩ፡፡ [41]ነገር ግን ሁለት ባሕር በተገናኙበት ስፍራ ወድቀው መርከቡን በዲብ ላይ ነዱ፤ በስተ ፊቱም ተተክሎ የማይነቃነቅ ሆነ፥ በስተ ኋላው ግን ከማዕበሉ ግፊያ የተነሣ ይሰበር ነበር፡፡ [42]ወታደሮቹም ከእስረኞች አንድ ስንኳ ዋኝቶ እንዳያመልጥ ይገድሉአቸው ዘንድ ተማከሩ፡፡ [43]የመቶ አለቃው ግን ጳውሎስን ያድነው ዘንድ አስቦ ምክራቸውን ከለከለ፤ ዋና የሚያውቁትም ከመርከብ ራሳቸውን እየወረወሩ አስቀድመው ወደ ምድር ይወጡ ዘንድ፥ [44]የቀሩትም እኵሌቶቹ በሳንቃዎች ላይ እኵሌቶቹም በመርከቡ ስባሪ ይወጡ ዘንድ አዘዘ፡፡ እንዲሁም ሁሉ በደኅና ወደ ምድር ደረሱ፡፡***

27:39 በዚህም ርቀት ላይ ሆነው መርከቡን ሙሉ ለሙሉ ሊቆጣጠሩተ አልቻሉም ነበር፡፡ (ቁ.40)
በግሪኩ ፅሐፍ "መርከብን መንዳት" እና ወደ ወደብ በሰላም መድረስ በግሪኩ ፅሐፍ እነዚህ ምንባቦች በግሪክ ሁል ጊዜ አደናጋሪ ናቸው፡፡

27:40 እነዚህ በባህር ዳር የሚገኙ ትክል ድንጋዮች ለብዙ መርከቦች መሰበር የሚያደርጉ ናቸው፡፡

▣
NASB, NKJV
NJV "መቅዘፊያ"
NRSV,TEV "የመቅዘፊያ ዘንግ"
ለትልልቅ መርከቦች መጠቀሚያ የሆነ ባለሁለት ዘንግ መቅዘፊያን የሚያመለክት ነው፡፡ (ያዕቆ 3:4)

▣ **"በስተፊቱም ተተክሎ የማይነቃነቅ ሆነ"** መርከቡን በቀስታ ፍጥነት እየነዱ መሆናቸውን ያስገነዝበናል፡፡ (Juvenas, Sat 12.69)

27:42 **"ወታደሮቹ ከእስረኞች አንድ እንኳ ዋኝቶ እንዳያመልጥ ይገሉአቸው ዘንድ ተማከሩ"** እነዚህ እስረኞች ቢያመልጡ በአገሩ መንግስት መሠረት የእስረኞቹን ቅጣት ወታደሮቹ ይቀበላሉ፡፡

27:43 የጳውሎስ ድርጊት እና እምነት የመቶ አለቃውን ስላሳመነው ሊንከባከበው እና ሊተማመንበት ችሏል፡፡

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች ለመርዳት ነው የተሰናዱት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋነኞቹን ጉዳዮች ለማጤን እንዲረዳ ነው፡፡ ሐሳብ ለማጫር እንጂ መደምደሚያ አይደሉም፡፡

1. በሉቃስ ፅሑፍ ውስጥ የመርከበኞች ስልታዊ የቋንቋ አጠቃቀም በብዛት ይታያል፡፡ ይህ ምንን ያመለክታል?
2. በዚህ ምዕራፍ በቁጥር ሃያ ላይ ያለው ዐረፍተ ነገር የስነመለኮት ፋይዳው ምንድነው?

# የሐዋርያት ስራ 28

## የምንባቡ ክፍፍል በአዲሶች ትርጉሞች

| የተየመቅሰ[4] | አኪጀት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጳውሎስ በማላታ ደሴት ላይ | የጳውሎስ አገልግሎት በማለት | ጳውሉስ በማለት | በማላታ | በማለታ ጠበቃ |
| 28፡1-10 | 28፡1-10 | 28፡1-6 | 28፡1-6 | 28፡1-6 |
| | | 28፡7-10 | 28፡7-10 | 28፡7-10 |
| ጳውሎስ ሮም ደረሰ | ሮም ደረሰ | ወደ ሮም ጉዞ | ከማላታ ወደ ሮም | ከማላታ ወደ ሮም |
| 28፡11-15 | 28፡11-16 | 28፡11-15 | 28፡11-15 | 28፡11-14 |
| | | | በሮም | 28፡15-16 |
| 28፡16 | | 28፡16 | 28፡16 | |
| ጳውሉስ በሮማ ሰበከ | የጳውሉስ አገልግሎት በሮም | ጳውሉስና አይሁድ በሮም | | ጳውሎስ ከሮማ አይሁዶች ጋር ግንኙነት ፈጠረ |
| 28፡17-22 | 28፡17-31 | 28፡17-22 | 28፡17-20 | 28፡17-20 |
| | | | 28፡21-22 | 28፡21-22 |
| | | | | የጳውሉስ |
| | | ምስክርነት | | |
| | | | | በሮም ለሚገኙ አይሁድ |
| 28፡23-29 | | 28፡23-29 | 28፡23-27 | 28፡23-27 |
| | | | | (26-27) |
| | | | 28፡28 | 28፡28 |
| | | ማጠናቀቂያ | 28፡29 | መደምደሚያ |
| 28፡30-31 | | 28፡30-31 | 28፡30-31 | 28፡30-31 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (ከ "**መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ**" **ገጽ** vii)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. ምንባብ አንድ

2. ምንባብ ሁለት

3. ምንባብ ሦስት

4. ወ.ዘ.ተ . . .

**የቃል እና የጥምር ቃል ጥናት**

---

አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 28፡1-6

**በደህና ከደረስን በኃላ በዚያ ደሴቲቱ መላጥያ እንድትባል አወቅን አረማውያንም የሚያስገርም ቸርነት አደረጉልን ዝናብ ስለሆነ ስለብርዱም እሳት አንደው ሁላችንን ተቀበሉን ጳውሎስ ግን ብዙ ጭራሮ አከማችቶ ወደ እሳት ሲጨንር እፍኝት ከሙቀት የተነሣ ወጥታ እጁን ነደፈችው፡፡ አረማውያንም እባብ በእጁ ተንጠላጥላ ባዩ ጊዜ እርስ በእራሳቸው በእርግጥ ይህ ሰው ነፋስ ገዳይ ነው፡፡ ከባህር እነወኳን በደህና ቢወጣ የእግዚያአብሔር ፍርድ በሕይወት ይኖር ዘንድ አልተወውም አሉ፡፡ እርሱ ግን እባቢቱን ወደ እሳት አራገፍት አንዳችም አልጎዳቸውም እነርሱም ሊያብጥ ወይም ሞቶ ሊወድቅ ነው፤ ብለው ይጠባበቁት ነበር፡፡ ብዙ ጊዜ ግን ሲጠባበቁ በእርሱ ላይ የሚያስገርም ነገር ባላዩ ጊዜ ይህስ አምላክ ነው፡፡ ብለው አሳባቸውን ለወጡ፡፡**

---

28፡1 "በደህና ከደረስን በኃላ" "ሐረጉ" "SOZO" (ሐዋ 27፡31) በግሪኩ "dia" የሚል ግልፅ ትርጉም ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በደህና መድረስና ያመለክታል፡፡ (ሐዋ 23፡2427፣ 44፡28፡1፡4) በተጨማሪ ሉቃስ ድውያን ጤንነትን ሲያገኙ ለመግለፅ ተጠቅሞበታል (ሉቃት ፡3)

ሉቃስ መግለፅ የፈለገው የመርከብ ጉዞው በእግዚአብሔር ጥበቃ መሆኑን ለመግለፅ ነው፡፡ (ሐዋ 27፡21-26)

▣ "መላጥያ" ፊንቃውያን ከተማይቱ መላጥያ ይሏት ነበር፤ ይህም የከናአናውያን ቋንቋ ነው፤ ትርጉሙም "የመማፀኛ ከተማ" ወይም "ጊዜያዊ ማረፊያ"፤ ይህች ከተማ የፊንቃውያን ቅኝ ግዛት ሆና በሰሜን አፍሪካ እና በሲሲሊ መካከል ትገኛለች ይህም ማለት ከባህሩ የንግድ ቦታ አስራ ስምንት ማይል ብቻ ትርቃለች በዚያም በርካታ የባህር ወደቦች ያሉበት ቦታ ነው፡፡

28፡2 "አረማውያን" ቀጥተኛ ትርጉም "ያልታመኑ" ናቸው፤ የግሪክን ወይም የላቲን ቋንቋ የማይናገር ሰው ሁሉ አረማውያን ስያሜ ተሰቶታል፡፡

▣

| | |
|---|---|
| NASB | "ያልተለመደ ትህትና" |
| NKJV, NRSV | |
| NJB | "ልዩ ትህትና" |
| TEV | "ወዳጆች ነበሩ" |

Philanthropos የሚለው "የወንዶች ፍቅር" የሚሎ ፍቺ አለው (ሐዋ 27፡3) ጳውሎስን በተለየ መንገድ ለማየት የተገደዱት እፋኝቷ በጳውሎስ ላይ ጉዳት ባለማድረሷ ነበር፡፡ ይህ እና ሌሎችም የታምራት ክንዋኔዎች ለወንጌል ትልቅ በርን ይከፍታሉ፡፡ ጳውሎስ ዘወትር ለወንጌል በር የሚያገኝበትን ያስብ ነበር (1 ቆሮ 9፡19-23)

28፡3 "ጳውሎስ ግን ብዙ ጭራሮ አከማችቶ" ጳውሎስ እንደሌሎቹ የማገዱ እንጨት መሰብሰቡ ትህትናውን ያሳያል፡፡

▣ "እፉኝት . . . በእጁ ተንጠላጥላ" ቀጥተኛ ትርጉም ተጣብቃ የሚል ነው፤ ይህም ማለት ጳውሎስን እባቧ መንደፏን ያሳያል፡፡

28፡4 "እባብ" መርዛማውን እባብ የሚያመለክት ነው (ሐዋ 10፡12)

▣ "የእግዚአብሄር ፍርድ በህይወት ይኖር ዘንድ አልተወውም" ፍርድ ወይም ዕጣ ፋንታ የአርማውያን የተለያዩ ጣአታትን የሚያመልኩ ናቸው፡፡

28፡6 በባህር ዳርቻ የሚኖሩ እነዚህ ሰዎች የእባብ ዝርያዎችን ያውቃሉ ነገር ግን ጳውሎስ በእፍኝት ተነድፎ

---

አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 28፡7-10

**በዚያም ስፍረ አጠገብ ፑፕልዮስ የሚሉት የደሴት አለቃ መሬት ነበር እርሱም እንግድነት ተቀብሎን ሦስት ቀን በፍቅር አሳደረን፡፡ የፐኘልዮስ አባት በንዳድና በተቅማጥ ታሞ ተኝቶ ነበር ጳውሎስም ወደ እርሱ ገብቶ ፀለየለት እጁንም ጭኖ ፈወሰው፡፡ ይህም በሆነ ጊዜ የቀሩት ደግሞ በደሴቲቱ ደዌ የነበረባቸው እየመጡ**

እንዳልሞተ ሲመለከቱ ሃሳባቸውን ቀይረዋል፡፡ ተመሳሳዩን ሌላ ይመልከቱ፡፡ ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን በዚህ ምንባብ ውስጥ ብቻ ተፅፎ ይገኛል፡፡

28፡7 **"የደሴት አለቃ"** ይህ ቃል ጥሬ ትርጉም የመንግስት ባለስልጣን ያመለክታል፡፡ (ሐዋ 13፡50፣ሉቃ 19፡47፣16፡12) ሮማውያን ከተማይቱ በራሷ አገር ሰዎች እንድትመራ አድርገዋት ነበር፡፡

28፡8 **"በንዳድና በተቅማጥ ታሞ ተኝቶ ነበር"** የዚህ ከተማ ሰዎች በፍየል ወተት ውስጥ ባለው ባክቴሪያ ይጠቁ ነበር፡፡ ይህ ንዳድ እና ተቅማጥ ከዚህ የበሽታ ባክቴሪያ የነሣ ነው፡፡

▣ "እጁን ጭኖ ፈውሰው" ሐዋ 6፡6 ያንብቡ የእጁ መጫን ልምምድ ምን እንደሆነ ከምንባቡ ይረዱ፡፡

28፡9 እግዚአብሔር በጳውሎስ አገልግሎት ሕዝቡን በቀጣይነት እየፈወሰ እንዳለ አመልካች ቃል ነው፡፡
 የግሪኩ "therapeno" ወይም የእንግሊዘኛው "therapy" ቀጥተኛ ትርጉም "መዳን" የሚል ፍቺ ይሰጣል ቃሉ ለአገልግሎት እና ለፈውስ የሚያገለግልም ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ትርጉሙ በዓውዱ ይወሰናል፡፡

> አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 28፡11-15
> **ከሦስት ወርም በኃላ በደሴቲቱ ከርሞ በነበረው በእስክንድርያው መርከብ ተነሣን በእርሱም የዲዮስቆሮስ አላማ ነበረበት ወደ ስራኩስም በገባን ጊዜ ሦሥት ቀን ተቀምጠን ከዚያም እየተዛወርን ወደ ሬጊዩም ደረስን፡፡ ከአንድ ቀን በኃላም የደቡብ ነፋስ በነፋስ ጊዜ በሁለተኛው ቀን ወደ ፑቲዮስ መጣን፡፡ በዚያም ወንድሞችን አግኝተን በእነርሱ ዘንድ ሰባ ቀን እንድንቀመጥ ለመኑን እንዲሁም ወደ ሮማ መጣን፡፡ ከዚያም ወንድሞችን ስለእኛ ሰምተው እስከ አፋዩስ ፈረሱን ሦስት ማደሪያ እስከሚባለው ሊቃበሉን መጡ ጳውሉስ ባያቸው ጊዜ እግዚአብሔርን አመሰገነ ልቡም ተፅናና፡፡**

28፡11 **"በደሴቲቱ ከርሞ በነበረው ሜዲትራኒያን ባህር በዝናብ ወቅት በመርከብ ለመጓዝ አስቸጋሪ ነበር፡፡** የመርከብ ጉዞ የሚቻለው የካቲት ወይም በመጋቢት ወር መጨረሻ ላይ ነበር፡፡

▣ **"የአሌክሳንደሪያ መርከብ"** ይህ ከኔፓል ወደ ግብፅ እህልን የሚያጓጉዝ ትልቅ መርከብ እንደሆነ ይታመናል፡፡

▣ **"የዲዮስቆሮስ አላማ"** የዙስን ሁለቱን ልጆች ያመለክታል ካስተር እና ፓኦሎክስ እነዚህ በሮማውያን መርከበኞች ዘንድ የታወቁ ጀግኖች ነበሩ በአፈታሪክ የባህር አምላክ የሆነው ፓሲዶን ንፋስን፣ማዕበልን እና ወጀብን ለመቆጣር ሃይል ለነዚህ ለሁለቱ እንደሰጣቸው ይነገር ነበር፡፡

28፡12 "ስራኩስ" የምስራቅ ባህር አጠገብ የምትገኝ የሲሲሊ ዋና ከተማ ነበረች፡፡ ይህ የባህር ወደብ ከሰላፐያ ሰማንኛ ማይል ርቀት ላይ ይገኛል

28፡13 **"እየተዘዋወርን"** በሌሎች የጥናት ፅሑፎች በተለይ በሲንታክስ እና ቫቲካኒዮስ ቃሉ መልዕቅን መጣል በሚል ተክቶታል ነገር ግን በሌሎች የጥናት ፅሑፎች ላይ ደግሞ "እያለፍን" በሚል ፍቺ ተሰቶት እናገኛለን

▣ **"ሬጊዮም"** በደቡብ ምዕራብ ጫፍ ኢጣሊያን የምትገኝ ከተማ ነች፡፡

▣ **"ፑቲዮሉስ"** ኢጣሊያን ከኔፓል የባህር ወሽመጥ እህል የሚራገፍበት ከተማ ነው፡፡ መቶ ሰማኒያ ማይል ርቀት የባህር ጉዞ ይርቃል፡፡

28፡14 **"በዚያ ወንድሞችን አግኝተን"** በኢጣሊናን እና የነበሩትን የክርስቲያን ምዕመናንን ያመለክታል (ሐዋ 28፡15)፡፡

28፡15 **"አፋዩስ"** ይህ ቦታ የሚገኘው በደቡብ ኢጣሊያናን እና ወደ ሮም በሚያስኄደው አውራ ጎዳና ላይ ነው፤ ስያሜውም "የአፋዩስ መንገድ" ይባላል፤ ከሮም በአርባ ሦስት ማይልስ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡

▣ **"ሶስት ማደሪያ"** ይህ ቦታ ሰዎች በመንገድ የሚያርፍበት ቦታ ነው፤ ከሮም በሰላሳ ሦስት ማይል ርቀት ላይ ይገኛል፡፡

▣ **"ጳውሎስ . . . በርትቶ"** ጳውሎስ ተስፋ መቆረጥ ገጥሞታል ወንድሞች ብዙ ጊዜ አበርትተውታል፡፡

> አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 28፡16
> [16]**ወደ ሮማም በገባን ጊዜ ጳውሎስ ከሚጠብቀው ወታደር ጋር ለብቻው ይቀመጥ ዘንድ ተፈቀደለት**

28፡16 “ወደ ሮማም በገባን ጊዜ” ጳውሎስ ወደ ሮማ እንደሚመጣና ወንጌልን ለሮም ባለስልጣናት፣ለአለቆች፣ለሃይማኖት መሪዎች ወንጌል እነደሚናገር ጌታ ቢናገረውም ነገር ግን በዚህ መንገድ እንደሚመጣ አላወቀም ነበር፡፡

▣ **“ጳውሎስ ከሚጠብቀው ወታደር ጋር ለብቻው ይቀመጥ ዘንድ ተፈቀደለት”** ጳውሎስ በእስር ላይ ሆኖ በተሻለ ሁኔታ ለብቻው እንዲቀመጥ መደረጉን ያመለክቷል፡፡

**አአመት (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 28፡17-22**

**[17]ከሦስት ቀን በኃላ ጳውሎስ የአይሁድን ታላላቆች ወደ እርሱ ጠራ በተሰበሰቡም ጊዜ እንዲህ አላቸው ወንድሞች ሆይ እኔ ሕዝቡን ወይም የአባቶችንን ስርዓት የሚቃወም አንዳች ስላደረግ ከኢየሩሳሌም እንደታሰርኩ በሮማውያን እጅ አሳልፈው ሰጡኝ እነርሱም መርምረው ለሞት የሚገባ ምክንያት ስላልነበረብኝ ለፈቱኝ አሰቡ አይሁድ ግን በተቃወሙ ጊዜ ወደ ጌሳር ይግባን እንድል ግድ ሆነብኝ እንጂ ህዝቤን የምከስበት ነገር ኖሮኝ አይደለም፡፡ ስለዚህም ምክንያት አያችሁ እና እነግራችሁ ዘንድ ጠራኃችሁ ስለ እስራኤል ተስፋ ይህን ሰንሰለት ለብሻለሁና እነርሱም እኛ ከአይሁድ ስለ አንተ ደብዳቤ አልተቀበለንም ከወንድሞችም አንድ እንኳን መጥቶ ስለ አንተ ክፍ ነገር አላወራልንም ወይም አልተናገረብህም፡፡**

28፡17 **“ጳውሎስ የአይሁድን ታላላቆች ወደ እርሱ ጠራ”** ጳውሎስ የደረበትን ደረጃ ያመለክታል (ሮማ 1፡16 2፡9) ጳውሎስ የራሱን ታሪክ በመዘርዘር ለወንጌል በር እንዲከፍት እያመቻቸ መሆኑን አንባቦ መረዳት ይችላል፡፡

28፡18-19 ፀሐፊው ሉቃስ ለማመልከት የፈለገው ክርስትና በሮማውያን ዘንድ ፈፅሞ ክብር እንደሌለው ነው፡፡

29፡19 “አይሁድ” ተቃወሙ “በሮም በአይሁድ መሪዎች እንዲህ አይነት ተቃውሞ” በራሳቸው ወገን ላይ ያልተለመደ ነው፡፡ ነገር ግን የታቃሞአቸውን ምክንያቶች እንመልከት፡-

1. ብሔራዊፍቅር(ሐዋ2፡5፡119፡22,10፡22,28,11፡19፡13፡56፡14፡1,16፡116፡1,20,17፡ 10,17,18,4,5,19,፡10,17,34)
2. ኢየሲስን ተቃውመው የነበሩ ናቸው (ሐዋ 2፡15,10፡39)
3. በኡታዊ ስሜት ታቃወሙ (ሐዋ 9፡23,12፡3,11,13፡45,50,14,2,4,5,19,17፡5, 13,፡18,12,14,28,19፡13,14,33, 20፡3)
4. በአውንታዊ የተቀበሉት ነበሩ (ሐዋ 13፡43፡14፡1-18፡2,24,21፡20)

የዚህን ቃል ፍቺ የሚያብራራውን ይመልከቱ (ሐዋ 14፡1-2)፡፡

28፡20 “ስለ እስራኤል ተስፋ” ጳውሎስ ከአድማጮቹ ጋር በቀላሉ ህብረትን ለመፍጠር ይህ ዓረፍተ ነገር አስፈልጎታል፡፡ የእስራኤል ተስፋ የአይሁድን ቀልብ የሚስብ ርዕስ ነው፡፡ ለጳውሎስ ይህ ሐረግ ኢየሱስን ሲያመለክት አይሁድን ግን ገና የሚመጣውን መሲህ ወይም የትንሳኤ ቀን በማለት ትርጉም ይሰጡታል፡፡ 28፡21 ስለ ጳውሎስ የሚሲዮናዊነት አገልግሎቱ በሌሎች ዘንድ አለመሰማቱን የሚጠቁመን ጥቅስ ነው፡፡

28፡22 የአየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በሁሉም ቦታ ተሰራጭቷል ይህም ለአይሁድ የምስራች ቃል አልነበረም፤ አሁን ግን በዚህ ሐረግ ላይ አይሁድ የጳውሎስን ንግግር መስማት ፈልገዋል፡፡

**ሐዋ 28፡23-29**

**ቀንም ቀጥረውለት ብዙ ሆነው ወደ መኖሪያው መጡ ስለ እግዚአብሔርም መንግስት እየመሰከረ ስለ ኢየሱስም ከሙሴ ህግና ነቢያት ጠቅሶ እያስረዳቸው ከጥዋት ጀምሮ እስከ ማታ ይገልጥላቸው ነበር፡፡ እኩሌቶቹም የተናገረውን አመኑ እኩሎቶቹ ግን አላመኑም እረስ በእርሳቸውም ባልተስማሙ ጊዜ ጳውሉስ አንዲት ቃል ከተናገረ በኃላ ሄዱ እንዲህም አለ መንፈስ ቅዱስ በነብዩ በኢሳያስ ለአባቶቻችን፡-**

**ወደዚህ ሕዝብ ሂድና መስማትን ትሰማላችሁ አታስተውሉም ማየትን ታያላችሁ አትመለከቱም በአይናቸው እንዳያዩ በጆራቸውም እንዳይሰሙ በልባቸውም እንዳያስተውሉ ተመልሰውም እንዳልፈውሳቸው የዚህን ሕዝብ ልብ ደንድኖአል ኑሮቸውም ደንቁሮአል ዓይናቸውንም ጨፍነዋል በላቸው፡፡**

**ሲል በመለካም ተናገረ እንግዲህ ይህ የእግዚአብሔር ደግነት ለአህዛብ እንደ ተላከ በእናተ ዘንድ የታወቀ ይሁን እነርሱ ደግሞ ይሰሙታል፡፡ ይህንም በተናገረ ጊዜ አይሁድ እርስ በእርስ እጅግ እየተከራከሩ ሄዱ፡፡**

28፡23 **“ወደ እርሱ መጡ… ብዙ ሆነው… ከጥዋት ጀምሮ እስከ ማታ”** ጳውሎስ ስለ ክርስትና እምነት ቀኑን ሙሉ ለአይሁድ ይመሰክር ነበር፡፡

▣ **“የእግዚያአብሄር መንግስት”** ይህ የኢየሱስ ክርስቶስ የስብከቱ እና የትምህርቱ መካከለኛ መልእክት ነበር ለእኛ ለአማኞችም ደግሞ ስለሚመጣውም መንግስት የሚያመለክት ሐረግ ነው፡፡ (ማቴ 6፡10) ሐረጉ ስለ እስራኤል ብቻ ሳይሆን ስለሚወጣው ተስፋ የሚናገር ነው፡፡

▣ **"ከሙሴ ህግና ከነቢያት ጠቅሶ"** ከዕብራውያን መፅሐፍ (ብሉይ ኪዳን) ከሦስት ክፍፍል ሁለቱ ናቸው። ማቴ 5:17, 7:12, 22:40, ሉቃ 16:16, 24:24, ሐይ 13:15, 28:23) ጳውሎስ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመስበክ የብሉይ ኪዳን መፅሐፍትን ምንባቦች ለአይሁድ ይጠቅስ ነበር።

28:24 የወንጌልን ምስጢርን የሚናገር ነው፤ አንዳንዶቹ ማመናቸው ሌሎቹ ደግሞ አለማመናቸው በሰው ፍቃድ በእግዚአብሔር ሉአላው ፈቃድ ላይ መዳን እንደሆነ በቀላሉ ማረጋገጥ ከዚህ ዓረፍተ ነገር ይቻላል።

የጳውሎስ አገልግሎት በአይሁድ መረምች የሚታየው በትልቁ ከተማ በሮም እንደትንሽ መንደር ምስረታ ነበር የብሉይን ኪዳን ለመፈፀም ጳውሎስ በመጀመሪያ ለአይሁድ ወንጌልን ሰበከ (ኢሳ 6:9:10)።

28:25-27 **"በነብዩ ኢሳያስ መንፈስ ቅዱስ እንደተናገረ"** (ከኢሳ 6:9-10) የተጠቀሰ ነው፤ ኢየሱስ የስምችን አለማመን ለመግለፅ ቃሉን ይጠቀምበታል። (ማቴ 13:14-15 ማርቆ 4:12 ሉቃ 8:10 ዮሐ 12:39-40) ጳውሎስ በዚህ ጊዜ ታስሮ ነበር። (ሮማ 9-11) እስራኤሎች መሲሁን ለምን ተቃወሙት? ያመኑ ቅሬታዎች አሉ ነገር ግን ብዙሃኑ አላመኑም።

28:28 **"የእግዚአብሔር ደኅንነት ለአሕዛብ እንደተላከ"** መዝ 67:2 የተወሰደ ነው። ይህ የአህዛብ አለማቀፍ የእግዚአብሄር ደህንነት በአይሁድ ለብዙ አመታት ችግር ሆነ የቆየ ነው። (ዘፍ 1:26, 27, 3:15, 12:3) የእግዚአብሔር እቅድ በልጁ የሰው ዘርን ለማዳን ነው ኤፌ 2:11-3:13)።

▣ **"እነርሱ ደግሞ ይሰሙታል"** ሮማ 9-11 ያንብቡ አይሁድ መሲሃን አልተቀበሉትም ምክንያም ግምታቸውን ያሟላ አልነበረም በተጨማሪም ወንጌሉ ለአህዛቦችም የመዳን መንገድን ከፈተ።

የአዲስ ኪዳን ጭብጥ አይሁድን ብቻ ሳይሆን ሁሉን ወደ እግዚአብሔር መንግስት ማስገባት ነው። የአዲስ ኪዳን ጥያቄ ዘርህ ምንድነው ሳይሆን በልጁ አምነሃል ወይ? የሚል ነው።

28:29 በጥንቱ የግሪክ ጽሁፍ ላይ ይህ ጥቅስ አልተፃፈም።

| |
|---|
| ሐዋ 28:30-31<br>**ጳውሉስም በተከራየው ቤት ሁለት ዓመት ሙሉ ተቀመጠ ወደ እርሱም የሚመጡትን ሁሉ ይቀባል ነበር። ማንም ሳይከፍለው የእግዚአብሔርን መንግስት እየሰበከ ስለ ጌታ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እጅግ ገልጦ ያስተምር ነበር።** |

28:30 **"ሁለት ዓመት ሙሉ"** ጳውሎስ በእነዚህ ዓመታት ለምን በዚህ ተቀመጠ? (1) ወደ ቄስራ ለመግባት ሁለት ዓመት ያስፈልግ ስለነበረ፣ (2) የባለስልጣን የማዘዣ ወረቀት እስከሚቀበል ድረስ ሁለት አመት መቆየት ግድ ነበረበት፣ (3) በእስያ እና ከእየሩሳሌም መስካሪዎችን ለማቅረብ የሚታዘዘው ሁለት ዓመት ነበር፣ (4) ሕጋዊ ለሆን እንዲያስችለው።

▣ **"በተከራየው ቤት"** ጳውሎስ የተወሰነ የገቢ ምንጭ ነበረው፡ (1) በድንኳን መስፋት ስራ ተሰማርቶ ነበር፣ (2) በቤተክርስቲያን ይረዳ ነበር፣ (3) የራሱ የሃብት ጥሪት ሽያጭ ነበረው።

▣ **"እየተቀበለ"** ቀጥተኛ ትርጉምና ልባዊ መስተንግዶ" ያደርግ ነበር። (ሐዋ 18:27, 28:30 እና 15:4) ሉቃ 8:40 እና 9:11 ተመሳሳይ ድርጊት ተፅፏል።

▣ **"የመጡትን ሁሉ"** የጳውሎስ ወንጌል የመጡትን ሁሉ የሚያስተናግድ በመሆኑ ለአይሁድ **ሃይማሮተኞች** ችግር ነበር።

28:31 **"ይሰብክ . . . ያስተምር"** በሐዋርያት ዘመን እነዚህ ሁለት የተለያዩ ስጦታች ናቸው። በሐዋርያት ስራ መፅሐፍ ውስጥ ጳፕሮስና እስቲፋኖስ ሰብከዋል "keryama" እወጃ አድረገዋል። (ሐዋ 20:25, 28:31, ሮሜ 10:8, ገላ 2:2, 1 ቆሮ 9:27, 2 ጢሞ 4:2) ትምህርት ደግሞ "Didache" ይባላል (ሐዋ 2:28, 5:28,13:12, ሮማ 16:17,1 ቆሮ 14:20)።

23:31 **"የእግዚአብሔር መንግስት"** ይህ የኢየሱስ ዋነኛ ትምህርቱ ነው። ይህ ማለት የእግዚአብሔር ግዛት በሰው ልብ ውስጥ ሲሆን ማለት ሆኖ ደግምም በፍፃሜው የምድር ኑሮ የሚያበቃበትን ሃሳብ ያንፀባርቃል።

▣ **"ጌታ"** በዕብሪይስጡ "አዶን" ማለት ባለቤት፤ ባል፤አለቃ፤ገዥ ማለት ነው። አይሁድ ያህዊ የሚለውን የእዚአብሔርን ስም አይጠሩም ነበር ምክንያቱም ከሙሴ ትዕዛዛት አንድ የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ በመሆኑ ስለሆነም ያሐዌ የሚለውን አዶን በሚለው ተክተውታል። ከዚህ የተነሣ በእንግሊዘኛው የመጀመሪያው ቋንቋ ጌታ የሚለውን የመጀመሪያው ፊደል በካፒታል ፊደል በብሉይ ኪዳን ተፅፎ እናገኛለን። በአዲስ ኪዳን የግሪኩ ፅሑፍ ለኢየሱስ "ኪዮርዎዮስ" በማለት ጌታ መሆኑ ተፅፎ እናገኛለን።

▣ **"ኢየሱስ"** ስያሜው የተሰጠው በመልአኩ ነው (ማቴ 1:21)። ከሁለት የዕብራይስጥ ጣምራ ቃል የተገኘ ነው "ያህዌ" የቃል ኪዳን ስም ነው እና "ደህንነት" ኢያሱ ከሚለው ከዕብራዉያን ስያሜ ጋር አንድ አይነት ፍቺ ያለው ነው። በአዲስ ኪዳን ደግሞ ለመሲሁ የተሰጠ ስያሜ ነው (ሜቴ 1:16,25,2,1:3:13,15,16)።

▣ **"ክርስቶስ"** በዕብራይስጡ "መሲህ" (የተቀባ) ይህም እግዚአብሔር የላከው የሚያድን አዳኝ መሆኑን የሚያረጋግጥ ቃል ነው፡፡

▣

NSAB **"በግልፅነት ያለቅንቅፍት"**
NKJV **"በልበሙሉነት ማንም ሳይከለክለው"**
NRSV **"በድፍረት እና ያለ እንቅፋት"**
TEV **"በድፍረት እና በነፃነት ተናገረ"**
NJB **"ያለፍርሃት እና ከማንም ተቃውሞ ሳይደርስበት"**

ይህም ምንባብ የሚያመለክተው ሮማውያን ክርስትናን ፓለቲካቸውን የማይጎዳ አድርገው ይቆጥሩ ስለነበር ትኩረት አይሰጡትም ነበር የግሪኩ ፅሁፍ የሚያደናቅፍ ወይም "ያልታሰረ" የሚል ትርጉም ይሰጣል፡፡ ይህ በእርግጥ ወንጌል የተፈታ እና ሉቃስ ከሁለት መፅሐፍቶች በላይ ፅፏል ሦስተኛውም መፅሽፍ 1 ጢሞ፣2ጢሞ እና የቲቶ መፅሐፍት ናቸው በማለት የራሳቸውን ማስረጃ ያቀርባሉ፡፡

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (ከ **"መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ" ገጽ** vii)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የሐዋርያት ስራ መፅሐፍ ጳውሎስ በእስር ቤት እንዳለ ፅሁፍ ማለቁ ለምንድነው?መፅሐፍ በቅስፈት ለምን ተፈፀመ?
2. ፀሐፊው ሉቃስ የጳውሎስን ጉዞ እና የሮም ቆይታው ትኩረት ሰጥቶ ለምን ፃፈ?
3. ሐዋሪያው ጳውሎስ ለአይሁድ ወንጌል ለመስበክ የሚጥረው ለምንድን ነው?
4. የ "kerygma" (ስብከት) እና "*Didache*" (ትምህርት) ልዩነታቸውን አስረዱ፡፡

# ተጨማሪ መግለጫ አንድ
# የግሪክ ሰዋሰዋዊ ቃላት አጭር መግለጫዎች

የኮኔ ግሪክ፣ ዘወትር ሔለናዊ ግሪክ የሚባለው፣ በሜዲትራኒያን የዓለም ክፍል አካባቢ ከታላቁ አሌክሳንደር ጀምሮ (336-323 ቅልክ) ዋነኛ ቋንቋ በመሆን አገልግሏል፤ ለ800 ዓመታት ገናና ሆኖ አክትማል (300 ቅልክ – 500 ዓም)። እሱም ቀለል ያለ የጥንታዊ ግሪክ አልነበረም፣ ነገር ግን በብዙ መንገዶች አዲሱ ግሪክ ሆኖ በጥንታዊው ቅርብ ምስራቅና በሜዲትራኒያን የዓለም ክፍል ሁለተኛ ቋንቋ ሆኖ ነበር።

የግሪኩ አዲስ ኪዳን በአንዳንድ መንገዱ የተለየ ነበር፣ ምክንያቱም ተጠቃሚዎቹ ከሉቃስና ከዕብራውያን ጸሐፊ በተቀር፣ ምናልባት አራማዊን እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተጠቅመው ይሆናል። ስለዚህ፣ ጽሑፎቻቸው የአራማዊ ፈሊጦችና መዋቅራዊ ቅርጾች ስላሉባቸው ነው። በተጨማሪም፣ ከሴፕቱዋጊንት (የግሪኩ የብሉ ትርጉም) ያነቡም ይጠቅሱም ነበር፣ ይህም ደግሞ በኮኔ ግሪክ የተጻፈው። ነገር ግን ሴፕቱዋጊንት ደግሞ የተጻፈው የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ግሪክ ባልሆነ የአይሁድ ሊቃውንት ነው።

ይህም አዲስ ኪዳንን ወደ ጥብቅ ሰዋሰዋዊ መዋቅር ወዳለው እንዳንገፋው እንደ ማስታወሻ ያገለግላል። እሱ የተለየ ያልሆነና ብዙ የሚጋራው ያለው ነው (1) ሴፕቱዋጊንት፤ (2) የግሪክ ጽሑፎች ለአብነትም የጆሴፈስ፤ እና (3) በግብፅ የተገኘው የወረቀት ጽሑፍ። ታዲያ እንዴት አድርገን የአዲስ ኪዳንን ሰዋሰዋዊ ትንታኔ እናካሂዳለን?

የኮኔ ግሪክ ሰዋሰዋዊ ባሕርይና የአዲስ ኪዳን ኮኔ ግሪክ ተወራራሽ ናቸው። በብዙ መንገዱ ሰዋሰውን በቀላል መልክ የማቅረብ ጊዜ ነበር። ጽሑፉ ዋነኛው መመሪያችን ይሆናል። ቃላቶች ትርጉም የሚኖራቸው በሰፊ ጽሑፍ ነው፤ ስለሆነም፣ ሰዋሰዋዊ መዋቅርን መረዳት የሚቻልበት ብርሃን (1) የጸሐፊው የተለየ ያጻጻፍ ስልት፤ እና (2) የተለየ የጽሑፍ አካል ነው። በግሪክ ቅርጾችና መዋቅሮች ላይ ለድምዳሜ የሚሆን ተስማሚ መግለጫ የለም።

ኮኔ ግሪክ በመጀመሪያ ግሣዊ ቋንቋ ነበር። ዘወትር ለትርጓሜው ቁልፉ የግሡ ዓይነትና ቅርጽ ነው። በብዙ ዋነኛ ሐረጎች ግሡ በመጀመሪያ ይመጣና፣ ዋነኛ ጠቀሜታውን ያስከትላል። የግሪክን ግሥ ለመተንተን ሦስት የሚሆኑ መረጃዎች የግድ ያሻሉ፡ (1) መሠረታዊ አጽንኦት የሰጠው ጊዜ፣ ድምጸት (ገቢር/ተገብሮ) እና ሁኔታው (ገጠመኙ ወይም የግሡ ርባታ)፤ (2) የተለየው ግሥ መሠረታዊ ፍቺ (ሥርወ ቃል)፤ እና (3) የጽሑፉ አወራረድ (አገባብ)።

I. ጊዜ

ሀ. ጊዜ ወይም ገጽታ የሚያካትተው የግሥን የተጠናቀቀ ድርጊትና ያልተጠናቀቀ ድርጊትን ግንኙነት ነው። ይህም ዘወትር “የተጠናቀቀ” እና “ያልተጠናቀቀ” በመባል ይታወቃል።

1. የተጠናቀቀ ጊዜ የሚያተኩረው የድርጊትን መከናወን ነው። አንድ ነገር ከመሆኑ ውጪ ተጨማሪ መረጃ አይሰጥም! አጀማመሩ፣ አካሄዱ ወይም ማብቃቱ አይካተትም።
2. ያልተጠናቀቀ ጊዜ የሚያተኩረው የአንድን ድርጊት ቀጣይነት ነው። linear action (ተሻጋጋሪ ድርጊት፣ በመካሄድ ላይ ያለ ድርጊት፣ ቀጣይ ድርጊት፣ ወዘተ።

ለ. ጊዜያቶች፣ ጸሐፊው ድርጊቶች እንዴት እንደተካሄዱ በተመለከተበት አግባብ ሊመደቡ ይችላሉ

1. ሆኗል = ያልተጠናቀቀ ግሥ
2. ሆኖአል እናም ውጤቱም ይገኛል = የተጠናቀቀ
3. ባለፈው ጊዜ ተጠናቋል እናም ውጤቱ ይኖራል፣ አሁን ግን አይደለም = በኃላፊ ጊዜ የተጠናቀቀ
4. እየሆነ ነው = የአሁን
5. ሆኗል = ያልተጠናቀቀ
6. ይሆናል = የወደፊት

እነዚህ ጊዜያቶች ለትርጓሜ እንዴት እንደሚረዱ ተጨባጭ ምሳሌ ሊሆነን የሚችለው “መዳን” የሚለው ቃል ነው። እሱም በበርካታ የጊዜያት ዓይነቶች ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን ከሂደቱንም ሆነ ፍጻሜውን ያመላክታል።

1. የድርጊት ግሥ – “ድኗል” (ሮሜ. 8፡24)
2. የተጠናቀቀ – “ድኗል እናም ውጤቱ ይቀጥላል” (ኤፌ. 2፡5፣8)
3. የአሁን – “የዳነ” (1ኛ ቆሮ. 1፡18፤ 15፡2)
4. የወደፊት (የትንቢት) – “ይድናል” (ሮሜ. 5፡9፣ 10፤ 10፡9)

ሐ. በግሥ ጊዜያቶች ላይ በማተኮር፣ ተርጓሚዎች፣ ዋናው ጸሐፊ ራሱን ለመግለጽ የመረጠበትን ምክንያት ይቃኛሉ። መደበኛው “ከስም በፊት የሚመጣ ግሥ” ጊዜያቱ ያልተጠናቀቀ የተግባር ግሥ ነበር። እሱም መደበኛው “ያልተወሰነ፣” “ያልተለየ፣” ወይም “ዘወትር ከስም በፊት” የሆነ ግሥ ነው። በበርካታ የተለያዩ መንገዶች ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል ጽሑፉ በሚወስነው መሠረት። እሱም አንድ ነገር መሆኑን ያሳያል። የኃላፊ ጊዜው ገጽታ ጥቅም ላይ የዋለው በአመላካች ተግባር ነው። ሌላ ጊዜ ጥቅም ላይ ከዋለ አንድ ልዩ ነገር አጽንዖት ተሰጥቶታል ማለት ነው። ግን ምን?

1. የተጠናቀቀ ጊዜ። ይህ የሚናገረው የተጠናቀቀ ድርጊትን ከሚኖረው ውጤት ጋር ነው። በአንዳንድ አገባቦች ያልተፈጸመ ጊዜ (የድርጊት ግሥ) እና የአሁን ጊዜን የደባለቀ ነው። ብዙውን ጊዜ የሚያተኩረው

የተገኘው ውጤት ላይ ወይም የድርጊት መጠናቀቅ ላይ ነው። ለምሳሌ፡ ኤፌ. 2፡5 እና 8፣ "ድናችኋል፣ በመዳናችሁም ቀጥላችኋል።"

2. በኃላፊ ጊዜ የተጠናቀቀ። ይህም እንደ ተጠናቀቀ ጊዜ ሆኖ የሚኖረው ውጤት ያበቃበት ነው። ለምሳሌ፡ "ጴጥሮስ ከበሩ በስተውጭ ቆሞ ነበር" (ዮሐንስ 18፡16)።
3. የአሁን ጊዜ። ይህ የሚያሳየው ያላበቃለት ወይም ያልተጠናቀቀ ድርጊትን ነው። ትኩረቱም ብዙውን ጊዜ በሁኔታው ቀጣይነት ላይ ነው። ለምሳሌ፡ "በእርሱ የሚኖር ሁሉ ኃጢአትን በመሥራት አይቀጥልም፣" "ማንም ከእግዚአብሔር የተወለደ ኃጢአትን በመፈጸም አይቀጥልም" (1ኛ ዮሐንስ 3፡6 እና 9)።
4. ያልተጠናቀቀ ጊዜ። በዚህ ጊዜ ከአሁን ጊዜ ጋር ያለው ግንኙነት ከተጠናቀቀ እና በኃላፊ ጊዜ ከተጠናቀቀው ጊዜ ጋር ያለው ግንኙነት ተመሳሳይ ነው። ያልተጠናቀቀው የሚያሳየው ያላበቃለትን ድርጊት ማለትም ተጀምሮ አሁን ያበቃለትን ወይም ባለፈው ጊዜ የነበረውን ድርጊት መጀመሪያ ነው። ለምሳሌ፡ "ከዚያም ሙሉው ኢየሩሳሌም ወደ እሱ መውጣታቸውን ቀጠሉ" ወይም "ከዚያም ሞላው ኢየሩሳሌም ወደ እሱ መውጣት ጀመሩ" (ማቴ. 3፡5)።
5. የትንቢት ጊዜ። ይህ የሚያሳየው ዘወትር በመጪው ጊዜ የሚፈጸምን ንድፍ አመላካች ነው። የሚያተኩረውም አሁን በተፈጠረው ሁኔታ ሳይሆን ወደፊት ሊፈጠር በሚችለው ላይ ነው። ዘወትር የሚናገረውም የሁኔታዎቹን እውነነት ነው። ለምሳሌ፡ "ብፁዓን ናቸው… እነሱ ወደፊት…" (ማቴ. 5፡4-9)።

II. የግሥ ጊዜያት (ድምጸት)

ሀ. የግሥ ጊዜያት የሚገልጸው የግሥን ድርጊትና የባለቤቱን ግንኙነት ነው።

ለ. የአሁን ጊዜ ተራ፣ የሚጠበቅ፣ ያልተጋነነ መንገድን ይዞ ለማለት የሚፈልገውን ባለቤቱ የግሡን ድርጊት ሲከውን ነው።

ሐ. ተገብሯዊ ጊዜ ማለት ባለቤቱ የድርጊቱ ተቀባይ ሲሆን ማለት በውጭ አካል የተደረገውን። በውጭ አካል የሚፈጸመው ድርጊት በግሪክ አኪ. ሲመለከት በሚከተለው መስተጻምራት እና አግባቦች ላይ ይታያል፡

1. ቀጥተኛ ሰዋዊ አድራጊ በ(hupo) ሲፈጸምና በስም፣ በተውላጠ ስምና በቅጽል የሚታይበት አግባብ ስከሰት (ማቲ. 1፡22፣ ሐዋ. 22፡30)።
2. ሰዋዊ መካከለኛ ፈጻሚ በ(dia) በስም፣ በተውላጠ ስምና በቅጽል የሚታይበት አግባብ ሲከሰት (ማቲ. 1፡22)።
3. ሰዋዊ ያልሆነ ፈጻሚ፣ ዘወትር በ(en) በቁሳቁሳዊ አግባብ።
4. አንዳንድ ጊዜ በሰዋዊ ሆነ ሰዋዊ ባልሆነ ፈጻሚ፣ በቁሳዊ አግባብ ብቻ።

መ. መካከለኛ ጊዜ ማለት ባለቤት የግሡን ተግባር ሲፈጽም እና እንዲሁም በቀጥታ በግሡ ድርጊት ላይ በቀጥታ ሲገባ ነው። ዘወትር ከፍ የተደረገ ሰዋዊ ፍላጎት የግሥ ድምጸት ተብሎ ይጠራል። ይህ አወቃቀር በተመሳሳይ መንገድ ለሐረጉ ወይም ለዓረፍተ ነገሩ ባለቤት አጽንዖት ይሰጣል። ይህ አወቃቀር በእንግሊዝኛ አይገኝም። እሱም ሰፋ ያለ የግሪክ ፍቺ እና ትርጉም አግባብ አለው። ለዚህ ዓይነት የሚሆኑ ጥቂት ምሳሌዎች፡

1. አነጻጻሪ – የባለቤቱ ቀጥተኛ ድርጊት በራሱ ላይ። ምሳሌ፡ "ራሱን ሰቀለ" (ማቲ. 27፡5)።
2. የታሰበበት – ባለቤት ድርጊቱን ለራሱ ይፈጽማል። ምሳሌ፡ "ሰይጣን ራሱን እንደ ብርሃን መልአክ ይለውጣል" (2ኛ ቆሮ. 11፡14)።
3. ባለ ሁለት ወገን – የሁለት ባለቤቶች ውስጣዊ ድርጊት። ምሳሌ፡ "እርስ በርሳቸው ተመካከሩ" (ማቲ. 26፡4)።

III. አኳኋን (ወይም አገባብ)

ሀ. በኮኔ ግሪክ አራት አገባቦች አሉ። እነርሱም የግሥን እውነታዊ ግንኙነት ይጠቁማሉ፣ ይሄውም በተቻለ መጠን ጸሐፊው በራሱ ሐሳብ። አገባቦች በሁለት ሰፋፊ ምድቦች ይከፈላሉ፤ እውነታን የሚጠቁሙ (ጠቋሚ) እና በውስጥ ያለ አቅም ጠቋሚዎች (መሻታዊ ሁኔታ (አጠራጣሪ)፣ ትዕዛዝ አንቀጽ እና አማራጫዊ ናቸው።)

ለ. አመላካች አገባብ ሁነኛ አገባብ ሲሆን የተከናወነን ወይም ተከናውኖ የነበረን ማለትም ቢያንስ በጸሐፊው ልቦና የነበረን ለመግለጽ የሚያገለግል ነው። ይህም <u>ብቸኛው</u> የግሪክ አገባብ ሆኖ ትክክለኛን ጊዜ የሚገልጽ ነው፣ እዚህም ቢሆን ይህ ገጽታ ሁለተኛ ነው።

ሐ. ተያያዥ አኳኋን የሚገለጠው በምናልባታዊ የትንቢት ድርጊት ነው። አንድ ነገር ገና አልሆነም፣ ነገር ግን የመሆን ዕድል አለው። ከትንቢታዊ አመላካች ጋር በርካታ የሚጋራው አለው። ልዩነቱ መሻታዊው የሚገልጸው የተወሰነ ደረጃ ያለው አጠራጣሪነትን ነው። በእንግሊዝኛ ይህ ዘወትር "ይችላል፣" "ነበር፣" "ምናልባት፣" "ምናልባት።"

መ. አማራጫዊ ሁኔታ የሚገልጸው በንድፈ ሐሳባዊ ደረጃ ሊሆን የሚችለውን ነው። ከመሻታዊው አንድ ደረጃ ከእውነታ ቀደም ብሎ ይገኛል። አማራጫዊው አጠራጣሪነትን የሚገልጸው በተወሰኑ ሁኔታዎች ነው። አማራጫዊው በአዲስ ኪዳን አልፎ አልፎ ነው የሚገኘው። በጣም የታወቀው ድግግሞሻዊ አጠቃቀሙ

የሚገኘው በታወቀው የጳውሎስ ሐረግ፣ “እንዲህስ አይሁን” (ኪጀቅ፣ “እግዚአብሔር አያርገው”)፣ የሚለው አስራ አምስት ጊዜ (ሮሜ. 3:4፣ 6፣ 31፤ 6:2፣ 15፤ 7:7፣ 13፤ 9:14፤ 11:1፣ 11፤ 1ኛ ቆሮ. 6:15፤ ገላ. 2:17፤ 3:21፤ 6:14) ጥቅም ላይ ውሏል:: ሌሎች ምሳሌዎችም ተሰ. (?) 1:38፣ 20:16፣ ሐዋ. 8:20፣ እና 1ኛ ተሰ. 3:11::

*ሠ. ትዕዛዛዊ ሁኔታ አጽንዖት የሚሰጠው ሊሆን የሚችል ትዕዛዝ ላይ ሆኖ አጽንዖቱ ግን በተናጋሪው ፍላጎት ላይ ነው:: እሱም በፍቃድ ላይ የተመሠረተውን ብቻ አማራጭ አመላክቶ እንዲሁም በሌላው ሁኔታዊ አማራጭ ላይ ነው:: ትዕዛዛዊ ሁኔታ በጸሎት እና በሦስተኛ መደብ ጥያቄዎች ላይ ልዩ አጠቃቀም አለው:: እነዚህ ትዕዛዛት በአኪ የሚገኙት በአሁን እና በግብር ግሦች ነው::*

*ረ. አንዳንድ ሰዋሰዎች ቦዝ አንቀጽን እንደሌለኛው ሁኔታዊ ዕይነት ይመድቧቸዋል:: እነዚህም በግሪክ አኪ የተለመዱ ናቸው፣ ብዙውን ጊዜ ግሳዊ ቅጽል በሚል:: ከሚቀራረቡት ከዋናው ግሥ ጋር ተጣምረው ይተረጎማሉ:: ቦዝ አንቀጽን ለመተርጎም የተለያየ ሰፋ ያለ አማራጭ አለ:: እዚህ ላይ በርካታ የእንግሊዝኛ ትርጓሜዎችን መቃኘቱ ይበጃል:: መጽሐፍ ቅዱስ በሃያ ስድስት ትርጉሞች* በቤከር የታተመው ደኅና አድርጎ *ይረዳል::*

*ሰ. የድርጊት አንቀጽ አመላካች፣ ሁነኛ ወይም “ያልተለየ” አንድን ሁኔታ (ድርጊት) ለመመዝገብ ይሆን ነበር:: ማንኛውንም ጊዜ፣ ድምጸት ወይም የተለየ ትርጓሜያዊ ጠቀሜታ ያለው ሲሆን ይህም ዋነኛው ጸሐፊ ለማለት የፈለገውን ነው::*

IV. *የግሪክኛ ችሎታ ለሌለው ሰው የሚከተሉት የጥናት መርጃዎች አስፈላጊውን መረጃ ሊሰጡት ይችላሉ፡*

*ሀ.* ፍሪበርግ፣ ባርባራ እና ጢሞቲ:: *የተተነተነ የግሪክ አዲስ* ኪዳን:: ግራንድ ራፒድስ፡ ቤከር፣ 1988::

*ለ. ማርሻል፣ አልፍሬድ:: ኢንተርላይነር (መስመራዊ) የግሪክ እንግሊዝኛ አዲስ ኪዳን:: ግራንድ ራፒድስ፡* ዞንደርቫን፣ 1976::

*ሐ. ሞውንሲ፣ ዊሊያም ዲ. የግሪክ አዲስ ኪዳን ቃላታዊ ትንታኔ:: ግራንድ ራፒድስ፡* ዞንደርቫን፣ 1993::

*መ. ጭምቅ ሐሳቦች፣ ሬይ. የግሪክ አዲስ ኪዳን ጠቀሜታዎች::* ናሽቪሊ፡ ብሮድማን፣ 1950::

*ሠ.* በከፍተኛ ትምህርት ተቀባይነት ያለው የኮኔ ግሪክ የተልእኮ ኮርስ ከሞዲ መጽሐፍ ቅዱስ ተቋም፣ ቺካጎ፣ IL *ይገኛል::*

V. *ስሞች*

*ሀ.* ከአገባብ *አኳያ፣ ስሞች የሚመደቡት በየጉዳዩ ነው:: ጉዳዩ ከስሙ አኳያ መልኩ የተቀየረ ሲሆን ይህም ከግሡ እና ከሌሎቹ የዓረፍተ ነገሩ ክፍሎች ጋር ያለውን ግንኙነት ያመለክታል:: በኮኔ ግሪክ ብዙዎቹ የጉዳዮ ተግባራት የሚጠቀሙት በመስተጻምሮች ነው:: የጉዳዩ መልክ የተለያዩ በርካታ ግንኙነቶችን እንደመግለጡ መጠን፣ መስተጻምሮች ለእነዚህ ተግባራት የሚሆኑ ግልጽ መለያዎችን ያስቀምጣሉ::*

*ለ. የግሪክ ጉዳዮች በሚከተሉት ስምንት መንገዶች ይመደባሉ፡*

1. *ሳቢዎቹ ጉዳይ ጥቅም ላይ የሚውሉት ለስያሜ ሲሆን ዘወትርም የዓረፍተ ነገሩ ወይም የሐረጉ ባለቤት ይሆናሉ:: በተጨማሪም ስም አመልካች ግሦችን እና ቅጽሎችን ከአያያዥ ግሦች ጋር “የመሆን” ወይም “የመኖር” ለመጠቀም ያስችላል::*
2. *አገናዛቢ ጉዳይ ጥቅም ላይ የሚውሉት የተለየ ባሕርይ ወይም ይዘት ለቃሉ እና ከእሱም ጋር ለተጎዳኙት የሚሰጥ መሆኑን ለመግለጽ ነው:: “ምን ዓይነት?” የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል:: ብዙውን ጊዜም የእንግሊዝኛውን መስተጻምር “የ”ን በመጠቀም ይታወቃል::*
3. *የስም፣ የተውላጠ ስምና የቅጽል ጉዳዮች ተመሳሳይ የሆነ መልኩ የተቀየረ እንደ አገናዛቢ ያለ ይጠቀማል፣ ነገር ግን መለያየትን ነው የሚያሳየው:: ዘወትር የሚገለጸውም በጊዜ፣ በቦታ፣ በምንጭ፣ በመነሻ ወይም በደረጃ ያለውን ልዩነት ለማሳየት ነው:: ብዙውን ጊዜም የእንግሊዝኛውን መስተጻምር “ከ”ን በመጠቀም ይታወቃል::*
4. *ቀጥተኛ ያልሆነ ተሳቢ (የስም) ጥቅም ላይ የሚውለው ግላዊ መሻትን ነው:: ይህም አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ግጽታዎችን ያሳያል:: ይህም ዘወትር ቀጥተኛ ያልሆነ ተሳቢ ነው:: ብዙውን ጊዜም የእንግሊዝኛውን መስተጻምር “ወደ”ን በመጠቀም ይታወቃል::*
5. *አቅጣጫዊ ጉዳይ ቀጥተኛ ያልሆነ ተሳቢ ተመሳሳይ የስም፣ የተውላጠ ስምና የቅጽል ጉዳዮች ዓይነት ሲሆን፣ ነገር ግን የሚያሳየው አቅጣጫን በቦታ፣ በጊዜ፣ ወይም በአመክኖአዊ ወሰን ነው:: ብዙውን ጊዜም በእንግሊዝኛው መስተጻምር “በውስጥ፣ በላይ፣ በ፣ በመሐል፣ በጊዜ፣ በ፣ በላይ እና በላይ”ን በመጠቀም ይታወቃል::*

6. *መገልገያዊ ጉዳይ ቀጥተኛ ካልሆነው ተሳቢ እና ለመገልገያዊ ጉዳዮች መልኩ የተቀየረ ተመሳሳይ ነው። እሱ የሚገልጸው ምንነቱንና መስተጋብሩን (ተያያዥነቱን) ነው። ብዙውን ጊዜም የእንግሊዝኛውን መስተጻምር "በ"ን ወይም "ጋር"ን በመጠቀም ይታወቃል።*
7. ቀጥተኛ ባለቤታዊ ጉዳዮች ጥቅም ላይ የሚውሉት የአንድን ድርጊት ድምዳሜ ለመግለጽ ነው።ዋናው ጠቀሜታው ለቀጥተኛ ባለቤት ነው። "ምን ያህል ሩቅ?" ወይም "እስከ ምን ድረስ?" የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል።
8. የስም መልኮች ጉዳይ ጥቅም ላይ የሚውለው ቀጥተኛ ባለቤትን ነው።

VI. *መስተዋድድ እና አያያዦች*

1. *ግሪክ በጣም ቁልጭ ያለ ቋንቋ ነው፣ ምክንያቱም በርካታ አያያዦች ስላሉት። እነሱም ሐሳቦችን ያያይዛሉ (ሐረጎች፣ ዓረፍተ ነገሮች፣ እና አንቀጾችን)። በጣም የተለመዱ ስለሆኑ፣ በሚቀሩበት ጊዜ በተለይ በትንታኔ ጊዜ ትርጉም ይኖረዋል። እንደ እውነቱ ከሆነ እነዚህ መስተዋድዶች እና አያያዦች የጸሐፊውን ሐሳብ አቅጣጫ ያመላክታሉ። ብዙውን ጊዜ ጸሐፊው በትክክል ምን ለማለት እንደፈለገ ለመወሰን በጣም ጠቃሚ ናቸው።*
2. ከዚህ ቀጥሎ የጥቂት መስተዋድዶች እና አያያዦች እና ትርጉሞቻቸው ይቀርባል፣ (ይህ መረጃ ባብዛኛው የተገኘው ከ ኤች. ኢ. ዳና እና ጁሊየስ ኬ. ማንቲ *የግሪክ አዲስ ኪዳን የሰዋሰው መመሪያ)* ላይ ነው።

*ሀ. ጊዜ አያያዦች*

1) epei, epeid e, hopote, hote, hotan (ተሳቢ) - "*መቼ*"
2) *hoes*, - "በ... ጊዜ"
3) *hotan, epan* (ተሳቢ) — "*መቼም* ቢሆን"
4) *hoes, achiri, mechri* (ተሳቢ) — "እስከ... *መቼ*"
5) *priv* (ንዑስ አንቀጽ) - "በፊት"
6) *hos* - "ከ... ጀምሮ" "*መቼ*" "እንደ"

**ለ.** *አመክኖአዊ አያያዦች*

1) *ተግባር*
   a) *hina* (ተሳቢ), *hopos* (ተሳቢ), hos - "እንደ...*መሆኑ*" "እንደ"
   b) *hoste* (አቀላጣፊ ንዑስ አንቀጽ ተሳቢ) "እንደ"
   c) *pros* (አቀላጠፊ ንዑስ አንቀጽ ተሳቢ) ወይም eis (አቀላጠፊ ንዑስ አንቀጽ ተሳቢ) "እንደ"
2) ውጤት (በሰዋሰዋዊ ቅርጾች ተግባርና ውጤት መካከል የቀረበ ተወራራሽነት አለ)
   a) (ንዑስ አንቀጽ ይህ በጣም የተለመደ ነው) - "እንደ...*መሆኑ*" "እንደ"
   b) *hiva* (ተሳቢ) - "ስለሆነም"
   c) *ara*- "ስለዚህ"
3) *መንሥኤ* ወይም ምክንያት
   a) (ምክንያት/*መነሻ* ወይም ሳቢያ/ድምዳሜ) — "ለ፣" "*ምክንያት*"
   b) *dioti, hotiy* - "*ምክንያቱም*"
   c) *epei, epeide, hos*- "ከ... ጀምሮ"
   d) (ከ ተሳቢ) እና (አቀላጣፊ ተሳቢ ንዑስ አንቀጽ) "*ምክንያት*"
4) ተገቢ አስተያየት
   a) *ara, poinum, hoste*-"ስለሆነም"
   b) *dio* (ጠንካራው ምርመራዊ ተገቢ አስተያየት) — "በዚህም ምክንያት)
   c) *oun* "ስለሆነም" "ስለዚህ" "ከዚያም" "በዚህም ሳቢያ"
   d) *toinoun* "በ*መሠረቱ*"
5) *ተጻራሪ* ወይም *ተቃርኖ*
   a) *alla* (ጠንካራ ተቃርኖ) - "ግን፣" "በተቀር"
   b) *de* - "ግን፣" "ቢሆንም፣" "ገና፣" "በሌላ በኩል"
   c) *kai* - "ግን"
   d) *mentoi, oun* - "ቢሆንም"
   e) *plên* "ቢሆንም ግን" (በአብዛኛው ሉቃስ ላይ)
   f) *oun* - "ሆኖም"
6) አወዳዳሪ
   a) *hôs*, (አወዳዳሪ ሐረጎችን ያሳያል)
   b) *kata* (በድብልቆች katho, kathoti, kathôsper, kathaper)
   c) *hosos* (በዕብራይስጥ)
   d) ê — "ከ...ይልቅ"
7) ተከታታይ ወይም ተለጣጣቂ
   a) *de* - "እና" "አሁን"
   b) *kai* - "እና"
   c) *tei* - "እና"
   d) *hina, oun* - "እንደ"
   e) *oun* "ከዚያም" (በዮሐንስ)

ሐ. ግነታዊ አግባብ

1) *alla* - "በርግጠኝነት" "አዎን" "በእውነቱ"
2) *ara* - "በርግጥ" "በእውነቱ " "በርግጥ "
3) *gar* - "ግን በርግጥ" "በርግጠኝነት" "በርግጥ "
4) *de* - "በርግጥ"
5) *ean* - "እንኳን"
6) *kai* - "እንኳን" "በርግጥ" "በእውነቱ "
7) *mentoi* "በርግጥ"
8) *oun* "በርግጥ" "እንደ ምንም"

VII. ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገሮች

ሀ. ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር አንድ ወይም ከዚያም በላይ የሆኑ ሐረጎችን የያዘ ነው፡፡ ይህ ሰዋሰዋዊ መዋቅር ለትርጓሜ ይረዳል፡፡ ምክንያቱም እሱ ነባሩ ግሥ ድርጊቱን ያደረገበትን ወይም ያላደረገበትን ሁኔታዎች፣ ምክንያቶች ወይም መንሥኤዎች ስለሚያሳይ ነው፡፡ አራት ዓይነት ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገሮች አሉ፡፡ አካሄዳቸውም ከጸሐፊው አስተሳሰብ ወይም ሊል ለፈለገው እውነት ወደ ሆነው መሻት ነው፡፡

ለ. አንደኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር የሚገልጸው ድርጊትን ወይም ከጸሐፊው አስተሳሰብ አኳያ ትክክል ይሆናል ተብሎ የሚታመንበትን ወይም ሊል ከፈለገው አንጻር ነው— ምንም እንኳ "እንደሁ" በሚል ቢገለጥም፡፡ በብዙ ጽሑፎች "ከ… ጀምሮ" በሚል ቢተረጎምም (ማቴ. 4:3፤ ሮሜ.8:31)፡፡ ቢሆንም ይህ ግን ሁሉም አንደኛ መደቦች ከእውነታ ጋር ትክክል ናቸው ማለት አይደለም፡፡ ብዙውን ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውሉት አንድን ነጥብ በክርክራዊ መንገድ ወይም ስህተት ያለበትን አጉልቶ በማሳየት ነው (ማቴ. 12:27)፡፡

ሐ. ሁለተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ብዙውን ጊዜ "ከሐቅ ጋር ተጻራሪ" በመባል ይታወቃል፡፡እሱም ነጥቡን ለመጥቀስ ትክክል ያልሆነን ነገር ወደ እውነት ያመጣል፡፡ ለምሳሌ፡

1. "በርግጥ ነቢይ ቢሆን ኖሮ፣ አይደለም እንጂ፣ ማን እና እንዴት ያለች ሴት እንደያዘችው ባወቀ ነበር፣ ግን አይደለም" (ተሰ. 7:39)፡፡
2. "ሙሴንስ ብታምኑት፣ አታምኑትም እንጂ እኔን ታምኑኝ ነበር፣ ግን አታምኑም" (ዮሐንስ 5፣46)፡፡
3. "ሰዎችን ባስደስት ኖሮ ግን፣ አላደርገውም እንጂ የኢየሱስ ክርስቶስ ባርያ ጨርሶ ባልሆንኩን ነበር፣ ነገር ግን ነኝ" (ገላ. 1:10)

መ. ሦስተኛ መደብ ሊሆን የሚችል የትንቢት ድርጊትን ያመላክታል፡፡ ዘወትር የድርጊቱን የመሆን ግምት ያስቀምጣል፡፡ ዘወትርም ሊደርስ የሚችልን ያሳያል፡፡ የነባሩ ግሥ ድርጊት ርግጠኛ ባልሆነ መልኩ በሐረጉ ላይ ተመልክቷል፡፡ ምሳሌዎች ከ1ኛ ዮሐንስ፡ 1:6-10፤2:4፣6፣15፣20፣21፣24፣29፤ 3:21፤ 4:20፤ 5፣14፣16፡፡

ሠ. አራተኛው መደብ ሊደርስ ከሚችል ራቅ ያለ ነው፡፡ በአኪ. እምብዛም አይገኝ፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ የተሟላ አራተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር አይገኝም፣ ሁለቱንም የሁኔታዊ ክፍሎች መግለጫ ሊያሟላ የሚችል፡፡ ለከፊል አራተኛ መደብ ምሳሌ የሚሆን የመክፈቻ ሐረግ በ1ኛ ጴጥ. 3:14፡፡ ለከፊል አራተኛ መደብ መዝጊያ ሐረግ የሚሆን ምሳሌ ሐዋ. 8:31፡፡

VIII. ክልክሎች

ሀ. የአሁን ጊዜ ያልተጠናቀቀ፣ እኔ በሚል አገባብ (ግን የተለየ ያልሆነ) በሂደት ላይ ያለ ድርጊት መቆሙን አጽንዖት ይሰጣል፡፡ ጥቂት ምሳሌዎች፡ "ሀብታችሁን በምድር ላይ ማከማቻታችሁን አቁሙ…" (ማቴ. 6:19)፤ "ስለ ሕይወታችሁ መጨነቃችሁን አቁሙ…" (ማቴ. 6:25)፤ "ሥጋችሁን ለኃጢአት በመስጠት ክፉ የመፈጸሚያ መሣርያ አታድርጉ…" (ሮሜ. 6:13)፤ "የእግዚአብሔርን ቅዱስ መንፈስ ማሳዘን አይኖርባችሁም…" (ኤፌ. 4:30)፤ እና "በወይን ጠጅ አትስከሩ…" (5:18)

ለ. ያልተጠናቀቀ ድርጊት እኔ በሚል አገባብ "አንድን ድርጊት ወይም አትጀምር ወይም አትፈልም" ለሚለው አጽንዖት ይሰጣል፡፡ ምሳሌዎች፡ "እንደዛለማድረግ እንኳ አታስቡ…" (ማቴ. 5:17)፤ "አትጨነቁ…" (ማቴ. 6:31)፤ "አሳፋሪ መሆን አይኖርባችሁም…" (2ኛ ጢሞ. 1:8)፡፡

ሐ. ጥንድ አሉታ በተያያዥ አኳኋን የሚገለጠው በእጅጉን አጽንዖታዊ አሉታ ነው፡፡ "ፈጽሞ በፍጹም" ወይም "በምንም ምክንያት ቢሆን" ምሳሌዎች፡ "እሱ ፈጽሞ፣ በፍጹም ሞትን አያይም" (ዮሐንስ 8:51)፤ "እኔ በፍጹም፣ ፈጽሞ…" (1ኛ ቆሮ. 8:13)፡፡

IX. መስተአምር

ሀ. በኮኔ ግሪክ የተወሰነ መስተአምር "ው" (the) ከእንግሊዝኛው ጋር ተመሳሳይ ጠቀሜታ ነው ያለው፡፡ ዋነኛው ተግባሩ "አመላካችነት" ሆኖ ለሚመለከተው ቃል፣ ስም ወይም ሐረግ አጽንዖት ማስጠት ነው፡፡ አጠቃቀሙ በአዲስ ኪዳን ከጸሐፊ ጸሐፊ ይለያያል፡፡ የተወሰነው መስተአምር ለሌሎች ተግባራትም ሲውል፡

1. እንደ አመላካች ተውላጠ ስም ለተቃርኗዊ አግባብ፤

2. ቀደም ሲል ለተጠቀሰ ባለቤት ወይም ሰው እንደ ማጣቀሻ ምልክት
3. የዓረፍተ ነገሩን ባለቤት በአያያዥ ግሥ በሚገልጽ በሆነ መንገድ። ምሳሌዎች፡ "እግዚአብሔር መንፈስ ነው፣" ዮሐንስ 4፡24፤ "እግዚአብሔር ብርሃን ነው፣" 1ኛ ዮሐንስ 1፡5፤ "እግዚአብሔር ፍቅር ነው፣" 4፡8፣16።

ለ. የኮኔ ግሪክ እንደ እንግሊዝ "አንድ" (a እና an) ዓይነት የተወሰነ መስተአምር የለውም። የዚህ ያልተወሰነ መስተአምር አለመኖር ማለት፣
1. በአንድ ነገር ባሕርይ ወይም ዓይነት ላይ ያተኩራል።
2. በአንድ ነገር ምድብ ላይ ያተኩራል።

ሐ. የአኪ ጸሐፍት በስፋት የሚለያዩት በመስተአምር አጠቃቀማቸው ነው።

X. በግሪክ አዲስ ኪዳን አጽንዖት የሚታዩባቸው መንገዶች
ሀ. በአዲስ ኪዳን አጽንዖት የሚሰጥባቸው ስልቶች ከጸሐፊ ጸሐፊ ይለያያሉ። ከሁሉም የተሻሉት ቋሚ እና መደበኛ ጸሐፍት ሉቃስ እና የዕብራውያን ጸሐፊ ናቸው።
ለ. ቀደም ሲል ያልተጠናቀቀ ድርጊት የአሁን አመላካች መደበኛና ለአጽንዖት ያለተለየ ዳሩግን ሌላ ማንኛው ግሥ፣ ድምጸት ወይም አኳኋን ትርጉማዊ ጠቀሜታ እንዳለው ተመልክተናል። ይህም ማለት ያልተጠናቀቀ ድርጊት የአሁን አመላካች ተገቢያዊ በሆነ የሰዋሰው ሁኔታ ጥቅም ላይ አይውልም ማለት አይደለም። ለምሳሌ፡ ሮሜ. 6፡10 (ሁለት ጊዜ)
ሐ. በኮኔ ግሪክ የቃላት ቅደም ተከተል
1. የኮኔ ግሪክ ተለዋዋጭ የሆነ የቃላት ቅርጽ ያለው ቋንቋ ሲሆን እንደ እንግሊዝኛው የቃላት ሥርዓት ሳይሆን ራሱን የቻለ ነው። ስለዚህም ጸሐፊው መደበኛውን የቃላት ቅደም ተከተል እነዚህን ለማሳየት ይለዋውጠዋል…
   ሀ. ጸሐፊው ለአንባቢው አጽንዖት እንዲሰጥ የፈለገውን
   ለ. ጸሐፊው ለአንባቢው ያስገርማል ብሎ ያሰበውን
   ሐ. ጸሐፊው በጥልቀት የተሰማውን ጉዳይ
2. ተገቢው የግሪክ የቃላት ቅደም ተከተል ጉዳይ ገና እልባት አላገኘም። ቢሆንም፡ ይሆናል የብሎ የታሰበው ተገቢ ቅደም ተከተል
   ሀ. ለአያያዥ ግሦች
      (1) ግሥ
      (2) ባለቤት
      (3) ማሟያ
   ለ. ለተሻጋሪ ግሦች
      (1) ግሥ
      (2) ባለቤት
      (3) ተሳቢ
      (4) ቀጥተኛ ያልሆነ ተሳቢ
      (5) መስተጻምራዊ ሐረግ
   ሐ. ለስማዊ ሐረጎች
      (1) ስም
      (2) አጎላማሽ
      (3) መስተጻምራዊ ሐረግ
3. የቃላት ሥርዓት ለማብራራት (ለትርጓሜ) ፍጹም ጠቃሚ ነጥብ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ፡
   ሀ. "ለእኔና ለበርናባስ የኅብረት ቀኝ እጃቸውን ሰጡን" (ገላ. 2፡9)። "የኅብረት ቀኝ እጃቸውን" ተከፍሎ ጠቀሜታውን ለማመልከት ከፊት ለፊት ሆኗል።
   ለ. "ከክርስቶስ ጋር" (ገላ. 2፡20)፣ ከፊት ሆኗል። ሞቱ ማዕከላዊ ነው።
   ሐ. "ጥቂት በጥቂት እና በበርካታ የተለያዩ መንገዶች ነበር" (ዕብ. 1፡1)፣ ከፊት ሆኗል። ይህም እግዚአብሔር ራሱን እንዴት እንደገለጠ ነው አከራካሪ የሆነው እንጂ የመገለጥን እውነት በመቃረን አይደለም።
መ. ዘወትር የተወሰነ መጠን ያለው አጽንዖት ያሳያል
1. የተውላጠ ስሞች መደጋገም፣ በግሡ በተለያየ መልኩ ቀደም ሲል የነበረው። ምሳሌ፡ "እኔ፣ ራሴ፣ ከእናንተ ጋር በርግጥ እሆናለሁ…" (ማቴ. 28፡20)።
2. በቃላት፣ በሐረጋት፣ በዐቢይ ሐረጋት ወይም በዓረፍተ ነገሮች መካከል መኖር የሚገባው መስተጻምር ወይም ሌሎች አያያዥ ቃላት አለመኖር። ይህም (asyndeton) ("ያልታሰረ") በመባል ይታወቃል። አያያዥ ቃል እንዲኖር ተጠብቆ መቅረቱ ትኩረትን ይስባል። ለምሳሌ፡
   ሀ. የብፁአን ትሩፋቶች (ሰባቱ)፣ ማቴ. 5፡3 (ዝርዝሩን ለማግነን)
   ለ. ዮሐንስ 14፡1 (አዲስ ርዕስ)
   ሐ. ሮሜ. 9፡1 (አዲስ ክፍል)
   መ. 2ኛ ቆሮ. 12፡20 (ዝርዝሩን ለማግነን)

3. በተመለከተው ጽሑፍ ውስጥ የሚገኝ የቃላት ወይም የሐረጎች መደጋገም። ምሳሌ፡ "ለክብሩ ምስጋና" (ኤፌ. 1፡6፣ 12 እና 14)። ምስጋናው ጥቅም ላይ የዋለው የእያንዳንዱን የሥላሴ አካል ሥራ ለማሳየት ነው።
4. ጥቅም ላይ የዋለ ፈሊጥ ወይም ቃል (ድምጽ) በቃላት በካከል የሚኖረው ሚና
   ሀ. ተለዋጭ ቃል - ስም አይጠሬ ቃላትን ቀይሮ በሌላ መጠቀም ለምሳሌ "እንቅልፍ" ን ለሞት (ዮሐንስ 11፡11-14) ወይም "እግሮች" ለወንድ ብልት (ሩት 3፡7-8፤ 1ኛ ሳሙ. 24፡3)።
   ለ. ጎናዊ አገላለጽ - ለእግዚአብሔር ስም ቃላትን መለወጥ፣ ምሳሌ "የሰማይ መንግሥት" (ማቲ. 3፡21) ወይም "ከሰማይ የሆነ ድምፅ" (ማቲ. 3፡17)።
   ሐ. ዘይቤያዊ አገላለጾች
      (1) የማይቻል ግነት (ማቲ. 3፡9፤ 5፡29-30፤ 19፡24)።
      (2) የተለዩ ግነታዊ አገላለጾች (ማቲ. 3፡5፤ ሐዋ. 2፡36)።
      (3) ሰዋዊ ዘይቤዎች (1ኛ ቆሮ. 15፡55)።
      (4) ውስጠ ወይራ (ገላ. 5፡12)
      (5) ቅኔያዊ አንቀጾች (ፊሊ. 2፡6-11)።
      (6) በቃላት መካከል ያሉ ድምፆች
         (ሀ) "ቤተ ክርስቲያን"
            i. "ቤተ ክርስቲያን" (ኤፌ. 3፡21)
            ii. "ጥሪ" (ኤፌ. 4፡1፣4)
            iii. "የተጠራ" (ኤፌ. 4፡1፣4)
         (ለ) "ነጻ"
            i. "ነጻ ሴት" (ገላ. 4፣31)
            ii. "ነጻነት" (ገላ. 5፡1)
            iii. "ነጻ" (ገላ. 5፡1)
   መ. ዘይቤአዊ ቋንቋ - ብዙውን ጊዜ ባህላዊ እና የተለየ ቋንቋን (ዘዬ) የሚያሳይ ነው፡
      1) ይህ የ "ምግብ" ዘይቤአዊ አጠቃቀም ነበር (ዮሐንስ 4፡31-34)።
      2) ይህ የ "መቅደስ" ዘይቤአዊ አጠቃቀም ነበር (ዮሐንስ 2፡19፤ ማቲ. 26፡61)።
      3) ይህ የዕብራይስጥ የማወዳደሪያ ፈሊጥ ነው፡ "ጠላ" (ዘፍ. 29፡31፤ ዘዳ. 21፡15፤ ተሰ. 14፡36፤ ዮሐንስ 12፡25፤ ሮሜ. 9፡13)
      4) "ሁሉም" ወይም (በተቃርኖ) "ብዙ።" ኢሳ. 53፡6 ("ሁሉም")ን ከ53፡11 እና 12 ("ብዙ") ጋር አነጻጽር። ቃላቶቹ እንደ ሮሜ. 5፡18 እና 19 እንደታየው ተመሳሳይነትን ያመለክታሉ።
5. በነጠላ ቃል ምትክ ሙሉ ሐረጋዊ ቋንቋ መጠቀም። ምሳሌ፡ "ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ።"
6. የስሞች፣ የቅጽሎች፣ የተውሳከ ግሦች (የርስ በርሱ) ልዩ አጠቃቀም
   ሀ. መስተአምሩ (ጠባያዊ ቦታ) ሲይዝ "አንድ ዓይነት" በሚል ይተረጎማል።
   ለ. ያለ መስትአምር (በአንቀጹ ቦታ) ሲይዝ አረጋጋጭ አገናዛቢ ተውላጠ ስም በሚል ይተረጎማል– "ራሱ፣" "ራሷ፣" ወይም "ራሱ።"

ሠ. ግሪክኛ ያልሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ አጽንዖትን በተለያየ መንገድ ሊረዳ ይችላል፡
   1. በትንተናዊ ቃላት አጠቃቀም፣ ማለትም በግሪክኛውና በእንግሊዝኛው ጽሁፍ በየመስመሩ በተጻፈው።
   2. የእንግሊዝኛን ትርጓሜዎች በማነጻጸር፣ በተለይም ከተለያዩ የትርጓሜ ንድፈ ሐሳቦች አኳያ። ምሳሌ፡ "የቃል በቃል" ትርጓሜዎችን በማነጻጸር (ኪጀት፣ አኪጀት፣ አመት፣ አአሶመቅ፣ የተመት፡ አየተመት) ከ "ታደሰው አቻ" (ዊሊያምስ፣ አዓአት፣ አእመቅ፣ የተእመቅ፣ ኢበቅ፣ አኢመቅ፣ TEV ?እት)። ሻል ያለ *ማብራሪያ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ በሃያ ስድስት ትርጉሞች* በቤከር የታተመው ላይ ይገኛል።
   3. ባለ *አጽንዖታዊ መጽሐፍ ቅዱስ* በጆሴፍ ብራያንት ሮዘርሃም (ክሪገል፣ 1994)
   4. የጥሬ ትርጉም አጠቃቀም
      ሀ. *የአሜሪካ መደበኛ ትርጉም* የ1901
      ለ. *ለወጣቶች ተስማሚ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም* በሮበርት ያንግ (ጋርዲያን አሳታሚ፣ 1976)።

ለተገቢ ትርጓሜ ሰዋሰዋዊ ጥናት አስፈላጊ ነው፣ አስቸጋሪ ቢሆንም። እነዚህ አጠር ያሉ መግለጫዎች፣ አስተያየቶች እና ምሳሌዎች የተፈለጉት ግሪክኛ አንባቢ ያልሆኑ ሰዎችን ለማበረታታትና በቅጹ ውስጥ የተመለከቱትን ሰዋሰዋዊ መግለጫዎች እንዲያገናዝቡ ነው። በርግጥ እነዚህ መግለጫዎች ቀለል ብለው ነው የቀረቡት። ቀኖናዊና ሊተጣጠፍ በማይችል መልኩ ጥቅም ላይ መዋል አይኖርባቸውም፤ ዳሩግን ወደ አዲስ ኪዳን አገባብ የተሻለ መረዳት የሚወስዱ ደረጃዎች ናቸው። እነዚህ መግለጫዎች አንባቢዎች የሌሎችን የጥናት መርጃዎች አስተያየቶችን ለምሳሌም፣ የአዲስ ኪዳን ስልታዊ ሐተታዎችን ለመረዳት ያስችሏቸዋል።

የራሳችንን ትርጓሜ ከመጽሐፍ ቅዱስ በምናገኛቸው ጽሑፎች ላይ በመመሥረት ልንመረምረው ይገባል። ሰዋሰው በጣም ከሚረዱን ዓይነቶች መካከል አንዱ ነው፤ ሌሎች ዓይነቶች ደግሞ እንደ ታሪካዊ መቼት፣ ሥነጽሑፋዊ ጽሑፎች፣ የየዘመኑ የቃላት አጠቃቀም፣ እና አቻዊ አንቀጾች ይገኙበታል።

# ተጨማሪ መግለጫ ሁለት
# ጽሑፋዊ ትንተና

ይህ ርዕሰ ጉዳይ በዚህ መልኩ የቀረበው በዚህ ሐተታ ውስጥ የሚገኙትን ጽሑፋዊ ማስታወሻዎች ለማብራራት ነው:: ቀጣዩ ማውጫ ጥቅም ላይ ይውላል::

I. የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱሳችን ጽሑፋዊ ምንጮች
   ሀ. ብሉይ ኪዳን
   ለ. ሐዲስ ኪዳን
II. "የመለስተኛ ትንተና" ወይም "ጽሑፋዊ ትንተና" ተብሎ የሚጠራው ንድፈ- ሐሳባዊ ችግሮች አጭር ማብራሪያ
III. ለተጨማሪ ንባብ የተጠቀሱ ምንጮች

I. የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱሳችን ጽሑፋዊ ምንጮች

ሀ. ብሉይ ኪዳን

1. ማሶረቲክ ጽሑፍ (ማጽ) - የዕብራይስጥ ተናባቢ ጽሑፍ የተቀናበረው በራቢ አቂባ በ100 ዓ.ም ነው:: አናባቢው የሚያመለክተው የአነጋገር ዘዬን፣ የህዳግ ማስታወሻዎችን ሥርዓተ- ነጥብ እና አስረጅ ነጥቦች ከስድስተኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም መካተት ተጀምሮ በዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም የተጠናቀቀው ነው:: የተከናወነውም የአይሁድ ሊቃውንት ክፍል ከሆኑት ማሶሪተስ በሚባሉት ነው:: የተጠቀሙበትም የጽሑፍ ዓይነት፣ በሚሽናህ፣ ታልሙድ፣ ታርጉምስ፣ ፔሺታ፣ እና ቫልጌት አንድ ዓይነት ነው::
2. ሴፕቱዋጊንት (ሰባ) - ከባህል አኳያ ሴፕቱዋጊንት የተጻፈው በሰባ የአይሁድ ሊቃውንት ሲሆን በ70 ቀናት ለአሌክሳንደሪያ ቤተ-መጻሕፍት ሆኖ በንጉሥ ፕቶለሚ 2ኛ (285-246 ቅ.ል.ክ) ነው:: ትርጉሙ የተዘጋጀው ምናልባት በአሌክሳንደሪያ በሚኖሩ የአይሁድ መሪዎች ጥያቄ ሊሆን ይችላል:: ይህ ልምድ የመጣው፣ "ከአሪስታስ መልእክት" ነው:: ሰባ የተመሠረተው በተደጋጋሚ ከዕብራይስጥ ጽሑፋዊ ባህል ከራቢ አቂባ (ማጽ) በተለየ መልኩ ነው::
3. የሙት ባሕር ጥቅሎች (ሙባጥ) - የሙት ባሕር ጥቅሎች የተጻፉት በሮማ ቅ.ል.ክ ባለው ጊዜ (200 ቅ.ል.ክ እስከ 70 ዓ.ም) ሲሆን በአይሁድ የተለዩ ክፍሎች በሆኑ "ኤሰንስ" በተባሉ ተለይዎች ነው:: የዕብራይስጥ የብራና ጽሑፎች የተገኙት፣ በሙት ባሕር አካባቢ በበርካታ ቦታዎች ሲሆን፣ ከሁለቱም ማለት ከማጽ እና ከሰባ በተለየ መልኩ የዕብራይስጥ ጽሑፋዊ ቤተሰብ ናቸው::
4. የእነዚህ ጽሑፎች ንጽጽር፣ ተርጓሚዎች ብሉይ ኪዳንን እንዲረዱት እንዴት እንደሚረዳ ጥቂት የተወሰኑ ምሳሌዎችን ስንመለከት
   ሀ. ሰባው ተርጓሚዎችንና ሊቃውንትን ማጽ (ማሲኒክ ጽሑፍ) ይገነዘቡ ዘንድ ረድተዋቸዋል
      (1) ሰባ በኢሳ. 52፡14፣ "ብዙዎች <u>በእሱ</u> ይደነቁበታል::"
      (2) ማጽ በኢሳ. 52፡14፣ "ብዙዎች <u>በአንተ</u> ይገረሙ ነበር"
      (3) በኢሳ.52፡15 ተውላጠ ስሙ ልዩነቱ በሰባ ላይ ያለው ተረጋግጧል
         (ሀ) ሰባ፣ "ስለሆነም ብዙ ሕዝቦች በእሱ ይደነቁበታል"
         (ለ) ማጽ፣ "እሱ ብዙ ሕዝቦችን ይረጫል"
   ለ. ሙባጥ (ሙት ባሕር ጥቅሎች) ተርጓሚዎችንና ሊቃውንትን ማጽ (ማሲኒክ ጽሑፍ) ይገነዘቡ ዘንድ ረድተዋቸዋል
      (1) ሙባጥ በኢሳ. 21፡8፣ "እናም ነቢዩ ጮኸ፣ በቆምኩበት መጠመቂያው ማማ…"
      (2) ማጽ በኢሳ. 21፡8፣ "እናም ጨኸኩ አንበሳው! ጌታዬ፣ ሁልጊዜ በመጠበቂያው ማማ ላይ ቆሜያለሁ ቀኑን…"
   ሐ. ሁለቱም ሰባ እና ሙባጥ ኢሳ. 53፡11ን ለማብራራት ረድተዋል
      (1) ሰባ እና ሙባጥ፣ "ከነፍሱ መከራ በኋላ ብርሃንን ያያል፣ ይደሰታል"
      (2) ማጽ፣ "ያያል… ከነፍሱ መከራ በኋላ፣ ይደሰታል"

ለ. አዲስ ኪዳን

1. ከ5,300 በላይ የእጅ ጽሑፎች ከግሪክ አዲስ ኪዳን በሙሉ ወይም በከፊል ጠፍተዋል:: 85 የሚሆኑት በፓፒረስ የተጻፉ ሲሆኑ 268 ደግሞ በቁም ጽሕፈት የተጻፉ የብራና ጽሑፎች ናቸው:: ቆይቶም፣ ወደ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም ቅጥልጣይ ጽሑፍ እየተስፋፋ መጣ:: የግሪክ ጽሑፎች የተጻፉት በቁጥር 2700 ይሆናሉ:: በተጨማሪም 2100 የሚሆኑ ቅጂዎች የቅዱሳት መጻሕፍት ጽሑፎች ዝርዝር ለአምልኮ የሚሆኑ ሌክሽናሪስ ብለን የምንጠራቸው አሉ::
2. 85 የሚሆኑት የግሪክ የእጅ ጽሑፎች የአዲስ ኪዳንን የተወሰኑ ክፍሎች የያዙትና በፓፒረስ ላይ የተጻፉት ሙዝየሞች ውስጥ ተቀምጠዋል:: አንዳንዶቹ በሁለተኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም ያስቆጥራሉ፣ ነገር ግን አብዛኞቹ የሦስተኛውና የአራተኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም ናቸው:: ከእነዚህ ጽሑፎች አንዳቸውም የተሟላ አዲስ ኪዳንን አልያዙም:: እነዚህ ጥንታዊ የአዲስ ኪዳን ቅጂዎች ናቸው ማለት ግን በራሱ ጥቂት ልዩነት አላቸው ማለት አይደለም:: አብዛኞቹ የእነዚህ ቅጂዎች ለአካባቢው ጥቅም ይውሉ ዘንድ በችኮላ የተጻፉ ናቸው:: በሂደቱ ላይ ጥንቃቄ አልነበረም:: በመሆኑም ብዙ ልዩነቶች አሏቸው::
3. ኮዴክስ ሲናይቲከስ፣ በዕብራይስጥ ፊደል ( ) (አሌፍ) ወይም (01) በመባል የሚታወቀው፣ በቅዱስ ካተሪኒ ገዳም በሲና ተራራ በቲስቼንዶርፍ ተገኝቷል:: ዓመቱም ከ4ኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም ሲሆን በውስጡም የብኪን ሰባ እና የግሪክን አኪ ይዟል:: እሱም "የአሌክሳንደሪያ ጽሑፍ" ዓይነት ነው::
4. ኮዴክስ አሌክሳንድሪነስ፣ "ሀ" ወይም (02) በመባል የሚታወቀው፣ የ5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የግሪክ የእጅ ጽሑፍ በአሌክሳንደሪያ ግብፅ የተገኘው፣

5. ኮዴክስ ቫቲካነስ፣ "ለ" ወይም (03) በመባል የሚታወቀው፣ በሮም በቫቲካን ቤተ መጻሕፍት የተገኘ ሲሆን፣ ዓመቱም ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዓ. ም እኩሌታ ነው፡፡ በውስጡም የብሉይ ኪዳን ሰባ እና የግሪክን አዲስ ኪዳን ይዟል፡፡ እሱም "የአሌክሳንደሪያ ጽሑፍ" ዓይነት ነው፡፡
6. ኮዴክስ ኤፍራሚ፣ "ሐ" ወይም (04) በመባል የሚታወቀው፣ የአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የግሪክ የእጅ ጽሑፍ በከፊል የተበላሸው፣
7. ኮዴክስ ቤዜ፣ "መ" ወይም (05) በመባል የሚታወቀው፣ የአምስተኛ ወይም የስድስተኛ ክፍለ ዘመን የግሪክ የእጅ ጽሑፍ ነው፡፡ "የምዕራብ ጽሑፍ" ተብሎ ከሚጠራው ዋንኛው አስረጅ ነው፡፡ በውስጡም በርካታ ተጨማሪዎች የያዘ ሲሆን እንዲሁም ዋነኛው የግሪክ እማኝ ሆኖ በኪንግ ጀምስ ትርጉም ላይ አገልግሏል፡፡
8. የአኪ. MSS በሦስት ሊመደብ ይችላል፣ እንዲያውም በአራት፣ አንዳች ባሕርይ በሚጋሩ፡፡
   (ሀ) የአሌክሳንደሪያ ጽሑፍ ከግብፅ
      (1) ገ[75]፣ ገ[66] (200 ዓ.ም አካባቢ)፣ ወንጌላት የተጻፉበት
      (2) ገ[46] (225 ዓ.ም አካባቢ)፣ የጳውሎስ መልእክቶች የተጻፉበት
      (3) ገ[72] (ከ225-250)፣ የጴጥሮስና የይሁዳ መልእክቶች የተጻፉበት
      (4) ኮዴክስ ለ፣ ቫቲካነስ የሚባለው (325 ዓ.ም)፣ ሙሉውን ብኪ. እና አኪ. የያዘ
      (5) ከዚህ የጽሑፍ ዓይነት የተጠቀሱ ምንጮች
      (6) ሌሎች MSS የዚህን የጽሑፍ ዓይነት የሚያሳዩት ?፣ C፣ L፣ W፣ 33፣
   (ለ) ከሰሜን አፍሪካ ምዕራባዊ ጽሑፍ
      (1) ከሰሜን አፍሪካ የቤተክርስቲያን አባቶች የተጠቀሰ፣ ተርቱሊያዊ፣ ሲሪያዊ፣ እንዲሁም የጥንታዊ ላቲን ትርጉሞች
      (2) ከኤሪናዩስ የተጠቀሱ
      (3) ከቲታን እና ከጥንታዊ ሲሪያ ትርጉሞች የተጠቀሱ
      (4) ኮዴክስ መ "ቤዚ" የዚህን ጽሑፍ ጻይነት የሚከተል
   (ሐ) ከኮንስታንቲኖፐል የምዕራብ ባይዛንታይን ጽሑፍ
      (1) የዚህ ጽሑፍ ዓይነት ከ80% በላይ የሚሆነውን የ5300 MSS ያንጸባርቃሉ
      (2) በአንቲሆች በሶርያ የቤተክርስቲያን አባቶች የተጠቀሰ፣ ካፐዶቅያ፣ ክሪሶስቶም፣ እና ቴሮዶሬት
      (3) ኮዴክስ ሀ፣ በወንጌላት ብቻ
      (4) ኮዴክስ ሠ (ስምንተኛ ክፍለ ዘመን) ለሙሉ አኪ.
   (መ) አራተኛው ሊሆን የሚችል ዓይነት "ቂሳሪያዊ" ከፓልስታይን
      (1) በቅድሚያ የታየው በማርቆስ ብቻ ነው
      (2) ጥቂት አስረጅዎች ገ[45] እና W

II. "የመለስተኛ ትንታኔ" ወይም "የጽሑፋዊ ትንታኔ" ንድፈ ሐሳባዊ ችግሮች

ሀ. ልዩነቶች እንዴት ተፈጠሩ?

1. ሳይታወቅ ወይም በድንገት (አብዛኛው ሰፊ ክፍል የተፈጠረበት)
   ሀ. በዓይን የተፈጠረ ስህተት፣ ማለትም በእጅ በሚጻፍበት ጊዜ ሁለት ተመሳሳይ ፊደላት ላይና ታች መስመር ይዘው ሲመጡ ሁለተኛውን ጽፎ በመጀመሪያው መስመር ላይ ያሉትን ቃላት እንዳለ መግደፍ (ሆሞቲሉቶን)
      (1) የዓይን መሳሳት ጥንድ ቃላትን ወይም ሐረግ መግደፍ (ሀፕሎግራፊ)
      (2) የሐሳብ መሰረቅ ሐረግን ወይም መስመርን ሲደግሙ፣ የግሪክ ጽሑፍ (ዲቶግራፊ)
   ለ. የጆሮ ስህተት፣ በቃል ሲነገር በተጻፈ ወቅት የተሳሳተ ንባብ ሲቀርብ የሚፈጠር (ኢታሲዝም)፡፡ ብዙውን ጊዜ ይህ የተሳሳተ ንባብ ተመሳሳይ ድምፅ ባላቸው የግሪክ ቃላት ይፈጠራል፡፡
   ሐ. የቀድሞዎቹ የግሪክ ጽሑፎች ምዕራፍም ሆነ የስድ ንባብ ክፍሎች አልነበራቸውም፣ ጥቂት ወይም ምንም ሥርዓተ ነጥብ ነበራቸው፣ በፊደልና ፊደል መካከልም ክፍተት አልነበረም፡፡ እናም መልእክቶቹን በተለያየ ቦታ መክፈልም ሆነ ሌሎች ቃላትን መመሥረት ይቻል ነበር፡፡

2.ሆንተብሎ
   ሀ. የሚቀዳውን ጽሑፍ ሰዋስዋዊ ቅርፅ ለማሻሻል ሲባል ይደረጉ የነበሩ ለውጦች
   ለ. ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች ጋር አረጋጋጭ እንዲሆኑ ይደረጉ የነበሩ ለውጦች (የአቻዎች ኅብር)
   ሐ. ሁለት እና ከዛ በላይ የሆኑ የተለያዩ ምንባቦችን ወደ አንድ ወጥ ጽሑፍ ለመቀየር ሲባል የተደረጉ ለውጦች፣ (ድብለቃ)
   መ. በጽሑፉ ውስጥ ስህተት ያለ መስሎ ሲታሰብ ለማስተካከል የተደረጉ ለውጦች (1ኛ ቆሮ. 11፡27 እና 1ኛ ዮሐንስ 5፡7-8
   ሠ. ከተጨማሪ መረጃ፣ ከታሪካዊ አቀማመጥ ወይም ከተገቢ ትርጓሜ አንጻር በአንድ ጸሐፊ የሰፈረ በግርጌ ማስታወሻ በሌለኛው ጸሐፊ ደግሞ በጽሑፉ ውስጥ እንዲካተት ሲደረግ (ዮሐንስ 5፡4)

ለ. የጽሑፋዊ ትንታኔ መሠረታዊ መርሖዎች (በዋንኛው የጽሑፉ ንባብ ላይ ልዩነቶች ሲኖሩ ለመወሰን የሚሆን አመክኖአዊ መመሪያ)

1. በጣም አስቸጋሪው ወይም ሰዋሰዋዊ አገባቡ እንግዳ የሆነው ዋነኛው ጽሑፍ ሊሆን ይችላል
2. ቅልጥፍ ያለው ጽሑፍ ዋነኛው ሊሆን ይችላል
3. ከዋናው ጋር በታሪክ ይቀራረባል ስለሚሰጠው ብዙ ክብደት የሚሰጠው ለጥንታዊው ጽሑፍ ነው፣ ሌላው እኩል ሆኖ

4. MSS በመልክዓ ምድራዊ የሚለያዩት ብዙውን ጊዜ ዋነኛውን ምንባብ ይዘዋል
5. ደከም ያሉት የእምነት መግለጫዊ ጽሑፎች፣ በተለይም ከዋናዎቹ የሥነ-መለኮት ማብራሪያዎች ጋር የሚገናኙት የእጅ ጽሑፎቹ ጊዜ ሲለወጡ፣ እንደ ሥላሴ ያሉት ፣ በ1ኛ ዮሐንስ 5፡7-8 የተመለከቱት ይመረጣሉ።
6. የዋናውን ጽሑፍ በተሻለ መልኩ ሊገልጹ የሚችሉ ሌሎች ጽሑፎች
7. እነዚህን አስቸጋሪ ልዩነቶች ሚዛን ለመጠበቅ የሚረዱ ማሳያ ሁለት ጥቅሶች
   ሀ. የጄ. ሃሮልድ ግሪንሊስ መጽሐፍ፣ *የአዲስ ኪዳን ጽሑፋዊ ትንታኔ መግቢያ፣* "ማንኛውም የክርስቲያን መሠረተ እምነት በአከራካሪ ጽሑፍ መሆን የለበትም፤ የአኪ. ተማሪም ጽሑፉ፣ ተመስጧዊ ከሆነው ከዋናው ጽሑፍ የተሻለ ቀጥተኛና ከመሠረተ እምነት አኳያ የጠነከረ እንደሆነ ከመፈለግ መጠበቅ ይኖርበታል" (ገ. 68)
   ለ. ደብልዩ. ኤ. ክሪስዌል ለጌርግ ጋሪሰን *የበርሚንግሃም ኒውስ* ሲናገር እሱ (ክሪስዌል) የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ሁሉ ተመስጧዊ ናቸው ብሎ አያምንም፣ "ቢያንስ ቢያንስ ሁሉንም ቃላት ለዘመናዊው ሰው የቀረበው በምዕት ዓመታት ተርጓሚዎች" አለ ክሪስዌል፤ "በጽሑፋዊ ትንታኔ በጣም የማምን ነኝ። ይህ እንግዲህ፣ እንደማስበው፣ የማርቆስ 16ኛ ምዕራፍ የመጨረሻው አጋማሽ አጠራጣሪ ነው፤ ተመስጧዊ አይደለም፣ የተደባለቀ ፈጠራ ነው… እነዚያን የእጅ ጽሑፎች ወደ ኋላ መለስ ብላችሁ ብታነጻጽሩ እንደ ማርቆስ ወንጌል መደምደሚያ ያለ አታገኙም። አንዱ ጨምሮት ይሆናል።

የበቁ የSBC አባቶች እንደሚከራከሩት ከሆነ "ተጨማሪ" ነገሮች መኖራቸውን በዮሐንስ 5 ያለው በቤተሳይዳ መጠመቂያ የኢየሱስ ሁኔታ ማስረጃ ነው። ሁለቱንም የተለያዩ የይሁዳን የራሱን መግደል ሁኔታዎች የገለጸበት (ማቴ. 27 እና ሐዋ. 1)፡ "ይህ የተለየ ዓይነት ራስን የመግደል ሁኔታ ነው፣" ይላል ክሪስዌል። "በመጽሐፍ ቅዱስ ቢሆን ኖሮ፣ ለዚህ መግለጫ በኖረው ነበር። እናም ሁለቱ የይሁዳ ራሱን የመግደል ሁኔታዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ፣" ክሪስዌል ጨምሮም፣ " ጽሑፋዊ ትንታኔ በራሱ አስደናቂ ጥበብ ነው። ጊዜያዊ አይደለም። ተዳፋሪነትም አይደለም። በእንቅስቃሴ ላይ ያለና ማዕከላዊ ነው…"

III. የእጅ ጽሑፍ ችግሮች (ጽሑፋዊ ትንታኔ)

ሀ. ለተጨማሪ የንባብ ምንጮች ጥቆማ

1. *መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንታኔ፡ ታሪካዊ፣ ሥነጽሑፋዊ እና ጽሑፋዊ፣* በአር. ኤች. ሃሪሰን
2. *የአዲስ ኪዳን ጽሑፍ፡ አስተላለፉ፣ ጥፋቱ እና ዳግም መመለሱ* በብሩስ ኤም. ሜዝገር
3. *የአዲስ ኪዳን ጽሑፋዊ ትንታኔ መግቢያ፣* በጄ. ኤች ግሪንሊ

# ተጨማሪ መግለጫ ሶስት
# የቃላት ፍቺ

**ልጅነት መወከል**፦ ይህ ጥንት የነበረ አስተሳሰብ ሲሆን ኢየሱስ ከመለኮታዊነት ጋር የነበረውን ህግኙነት ያጣቅሳል። ፅንሰ ሃሰቡ መሰረት የሚያደርገው ኢየሱስ በማንኛውም መንገድ ሰው ሲሆን ልጅነትን ያገኘው በእግዚአብሔር በተለየ መልኩ ማለትም በጥምቀቱ /በማቴ 3፡17፤ ማርቆስ 1፡11/ ወይም /በሮሜ 1፡4/ በተመለከተው መሰረት ነው። ኢየሱስ ምሳሌያዊ በሆነ መልኩ በዚህ ዓይነት እንደኖረ እግዚአብሔርም በአንዳንድ ሁነቶች /በጥምቀትና በትንሳኤ/ እነደ ገዛ ልጁ እንደሆነው /ሮሜ 1፡4 ፊሊጵ 2፡9/ በተመለከተው መሰረት ያሳያል። ይህ የእምነት መግለጫ በ8ኛው ክፍለ ዘመን የነበረ የአናሴ ቤተ-ክርስቲያን ጥስታዊ አስተሳሰብ የነበረ ነው። አምለሰክ ሰው ሆነ /ስጋዊ/ ከማመልከት ይልቅ ገለባብጦ ሰው እንዴት አምላክ እንደሆነ ያመላክታል።
ኢየሱስ አምላክ የሆነው ወለድ ቀድሞ መለኮት ምሳሌያዊ ሕይወት በመኖሩ እግዚአብሔር አከበረው ብሎ በቃላት ለማስረዳት ይቸግራል። እሱ ከቀድሞ ጀምሮ አምላክ ከሆነ እንዴት ክብርን ይሸለማል? እሱስ ቀድሞ የነበረ መለኮታዊ ክብር እያለው እንዴት ተጨማሪ ክብር ይሰጠዋል? እርግጥ ይህን ልንደርስበት በርግጥ ይቸግረናል፤ ማለትም አብ ኢየሱስን በተለየ መልኩ የአባቱን ፍቃድ በመፈጸሙ መከበሩን ለማሳየት ይሆናል።

**የአሌክሳዳሪያ አስተምህሮት**፦ ይህ ዓይነቱ የመጽሐፍ ቅዱስ የትርጓሜ አግባብ በግብፅ አሌክሳንደሪያ በ2ኛው ክፍለ ዘመን የተጀመረ ነው። መነሻ ያደረገውን መሰረታዊውን ፊሎአዊ የፍቺ መርህ ተከታይ የሆነው ጀሎን ያመላክታል። ተምሳሌታዊ ዘዴ በመባል የታወቃል። እስከ ተሃድሶ ዘመን ድረስ በቤተ ክርስቲያን ሲሰራበት ኖሯል። የተርጓሚው ሊቃውንት ሲረገንና አውስጢኖስ ናቸው። /ለተጨማሪ መረጃ የMoises Silva "ቤተክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን አሳስታ ተርጉማው ይሆን?" የሚለውን አንብብ /1987 ዓ.ም/።

**አሌክሳዳሪያ**፦ ይህ በ5ኛው ክፍለ ዘመን በአሌክሳዳሪያ የተገኘ የግሪክ /ቅርፅ/ የብራና ፅሑፍ ሲሆን፣ በውስጡም ብሉይ ኪዳን፣ የራዕይና አብዛኛውን ሐዲስ ኪዳን ያካተተ ነው። ፅሁፉ የግሪኩን አዲስ ኪዳን ቅጂ በተመለከተ ዋናኛው ማጣቀሻ ነው። /ከማቴዎስ፣ ከዮሐንስ ወንጌል አንዳንድ ክፍሎች እና ከሁለተኛ ቆሮንቶስ በቀር/ይህ ጽሑፍ ማለትም ልዩ ስሙ "ሀ" የተባለውና የቫቲካሉ ጽሑፍ ልዩ ስሙ "ለ" የተባለው በንባብ ላይ ሲሰማ በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቆች አማካኝነት በብዙ አገባቦች እንደ ዋነኛ ተደርገው ይወሰዳሉ።

**ተምሳሌታዊ**፦ ይህ አይነቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ በመጀመሪያ የተስፋፋው በአሌክሳንደሪያ የአይሁድ እምነት ነው። እያገነነ የመጣው በአሌክሳንደሪያው ፊሎ ነው። የመሰረታዊ እምነቱም ፍላጎት ቅዱሳት መጻሕፍትን እንደየሰው ባህል፣ ፍልስፍናና ስርዓት በማጣጣም የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪካዊ መቼት /ቦታና ጊዜ/ ስነጽሁፋዊ ይዘት በመተው ነው። በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙትን የተሸሸጉትን እያንዳንዳቸውን ትርጓሜዎች በመመርመር ላይ ያተኩራል። ኢየሱስ በማቴስ 13 እንዲሁም ጳውሎስ በገላትያ 4 እውነትን ለመግለጽ የተጠቀሙበትን ተምሳሌት ያመላክታው። ዳሩ ግን ይህ ተምሳሌታዊ ሳይሆን ጽሑፋዊ መልክ የያዘ ነው።

**ስርወቃላዊ ትንታኔ**፦ ይህ አንደኛው የምርምር ዘዴ ሲሆን በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኙትን የግሪክ ስርወ ቃላት ለመለየት ይረዳል። በግሪክ የፊደል ተራ መሰረት ቅርጹና ዋናው መግለጫ /ትርጓሜ/ የያዘ ነው። ግሪክኛን ለሚያነሱ አማኞች ሰዩ ትርጓሜ አያይዞ በማስቀመጥ የግሪክን የሐዲስ ኪዳን ሰዋሰውና ስነጽሑፋዊ አገባብ ለመረዳት ያስችላል።

**የቅዱሳት መጻሕፍት ተመሳስሎ**፦ ይህ ሐረግ ለማስረዳት የሚሻው ሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነና እርስ በርሱ የሚቃረን ሳይሆን የሚደጋገፍ እንደሆነ ለማመላከት ነው።
ይህ አይነቱ በውል የተቀመረ አቀራረብ ቃሉን መሰረታዊ በሆነ መልኩ በንጽጽር በማስቀመጥ የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍሎች ይተረጉማል።

**አሻሚ ትርጓሜ**፦ ይህ የሚያመላክተው አሻሚ ትርጓሜ ያላቸውን የጽሑፍ ሰነዶችን ሲሆን ሁለትና ከዚያም በላይ ፍቺ ሲኖር፤ ወይም ሁለትና ከዛ በላይ የሆኑ ነገሮች በአንድ ጊዜ በማጣቀሻነት ሲቀርቡ የሚከሰት ነው። ዮሐንስ ሆን ብሎ በዚህ ዘዴ ተጠቅሟል /ማለትም በእጥፍ አገባብ/
**ሰዋዊ ምዕላድ**፤ ይህ አይነቱ ፍቺ ከሰው ልጆች ጋር የተያያዘውን ሲማመላክት ጥሬ ቃሉም ሃይማኖታዊ ቋንቋዎችን ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ቁርኝት ነው። ስርወ ቃሉ ከግሪክኛ የመጣ ሲሆን የሰው ልጅ ማለት ነው። ፍቺውም እኛ ስለ እግዚአብሔር የምንናገረው በሰውኛ ዘይቤ ማለት ነው። እግዚአብሔር በአካላዊ፣ በማህበረሰባዊ፣ በስለልቦናዊ ቃላት ከሰው ልጆች ጋር በተንዳኛ /ዘፍ 34፤ 1ኛ ነገስት 22፡19-23/ እንደተጻፈው ሲነገር ማለት ነው። እርግጥ ይሄ ተመሳስሎ ብቻ ነው። ያም ሆነ ይህ ከሰው ልጆች በቀር ልንጠቀምበት የምልኝልበት ምድብ ወይም ቃል የለም። ስለሆነም ስለ እግዚአብሔር ያለን እውቀት እውነትን ተንተርሶ ውስንነት እንዳለው ያመላክታል።

**የአንቲሆች አስተምህሮት**፦ ይህ አይነቱ የመጽሐፍ ቅዱስ የትርጓሜ ዘዴ በአንቲሆች ሶሪያ በ3ኛው ክፍለ ዘመን የተንሰራፋ ሲሆን የአሌክሳንደሪያ ግብጽን ተምሳሌታዊ ዘዴ የሚቃረን ነው። መሰረታዊ እምነቱን ለመጽሐፍ ቅዱስ ታሪካዊ ትርጓሜ ላይ ያተኩራል። መጽሐፍ ቅዱስን እንደማንኛውም የሰው ልጆች ስነጽሑፍ ይተረጉማል። ይህ አስተምህሮት ከክርስቶስ ክልዔ /ሁለት/ ባሕርይ አለው ከሚለው /ንስጥሮሳዊ/ አስተምህሮትና ወይም ደግሞ አንድ

ባሕርይ አለው /ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው/ ከሚለው አስተምህሮት መሐል በተነሳው ውዝግብ ውስጥ ገብቶ እንደነበር ይታወቃል። ኋላም በሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ተነቅፎ እንደመናፍቅ ስለተወሰደ ወደ ፋርስ ሊሄድና ድጋሚ ሊቋቋም ቢሞክርም ውል ያለው አቋም ሳይዝ ቀርቷል። መሰረታዊ የአተረጓም መርሆቹ ግን ለትርጓሜ አግባብ ይሆኑ ዘንድ ለሉተርፕ ለካልቪን የፕሮቴስታንት የተሀድሶ አራማጆች ጥቅም ላይ ሊውል ችሏል።

**አንቲሄትካል**፡- ከሶስቱ አንደኛው ዓይነት ገላጭ ጽሑፋዊ ዘዴ ሲሆን የእብራይስጥን የቅኔ ሐረጎች ተዛምዶ ያመላክታል። ፍቺያቸው የማይገጣጠሙትን የቅኔ ሐረጎች/ዘውጎች ተዛምዷቸውን ይመለከታል/ምሳሌ 10፡1፤15፡1/።

**ራዕያዊ ስነጽሑፍ**፡- ይህ በአብዛኛው፤ በተለየ መልኩ የአይሁድ የስነጽሑፍ ዘውግ ነው። ይህ ዓይነቱ ምስጢራዊ ጽሑፍ ከአዪዳውያን በውጭ ኃያላት ይወረሩና ሲገዙ የሚዘወተር ነው። በጽሑፉ ይዘትም እግዚአብሔር ዓለምን እንደፈጠረ፣ ሙላዋ የሱ እንደሆነችና መበዤት እንደሚችሉ አመላክቶ ለእስራኤልም የተለየ ዓላማ እንደሚጠነቀቅለት ያሳያል። ስነ ጽሑፉ የመጨረሻው ድል የሚገኘው በእግዚአብሔት ልዩ ክንድ እነደሆነ አጽንዖት ይሰጣል።
ጽሑፉ በጣም ተምሳሌታዊና ምስል ከሳች ምስጢራዊ ቃላት ይበዙበታል። ብዙውን ጊዜ እውነትን በቀለማት በቁጥሮች በምስል ከሳች ሁኔታ በሕልሞች በመላእክታዊ ክስታ በምስጢራዊ ቃላት የሚገለጽ ሆኖ ጊዜ በሰናይና በክፉ መሐል በመንታዊ ሰይፉ ከፍሎ ያልፋል።
የዚህ ዘውግ አነዳንድ ምሳሌዎች 1ኛ በብሉይ ኪዳን ሕዝቅኤል/36-48/ ዳንኤል /ምዕ 7-12/ ዘካሪያስ እና ዘርፍ ሲሆን ደግሞ ማቴ 2 ማር 13 2ኛ ተሰሎ 2 እና ራዕይ ናቸው።

**አፖሎጀስት**፡- ይህ የግሪክ ስርወ ቃል ሕጋዊ ተከላካይ የሚል ነው። ከስነ-መለኮት አንደኛው የትምህርት ንዑስ ዘርፍ ሲሆን ለክርስትና እምነት ተገቢ የመከራከሪያ ማስረጃና አመክኗዊ የክርክር አግባብን ይቀምራል።

**ቀዳማይ**፡- ይህ ቃል ቀደም ሲል ከተሄደበት አግባብ ጋር ጥብቅ መሰረታዊ ቁርኝት ያለው ነው። የሐሳብ አወራረዱም ቀደም ሲል ከወጡትና ከተቀበልናቸው ትርጓሜዎች መርሆች ወይም አቋሞች በመመስረት እንደ እውነት በመቀበል መቀጠል ነው። ያለ ምንም ተጨማሪ ምርምርና ትንታኔ የምንቀበላቸውን ማለት ነው።

**አርዮሳዊነት**፡- አርዮስ በአሌምሳንደሪያ ግብፅ ፕሬስቤታሪያን ቤተ-ክርስትያን በ3ኛ እና በ4ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ የነበረ ነው። አጽንዖት ሰጥቶ የሚከራከረው ምሳሌ 8፡22-31 ያለውን ቃል ሲሆን እየሱስ ቀድሞ እንደነበረ ቢቀበልም መለኮትነቱ ክዷል። /ከአብ ጋር መስተካከል የለበትም ባይ ነው።/ ከአሌክሳንደሪያው ጳጳስ ተቋውሞ የገጠመው ሲሆን ይህም ከ318 ዓ.ም አንስቶ ለብዙ ዓመታት የቆየ ክርክር ነው። አርዮሳዊነት በተለይ የምስራቅ ቤተክርስቲያን መሰረተ እምነት ተደርጎ ተወስዶ ነበር። በ325 ዓ.ም በኣቅያ የተሰበሰቡት ሊቃውንት አርዮስን አውግዘውና ነቅፈው ተወልድን የተካከለ መለኮትነት አጽንተዋል።

**አርስጣጣሊስ**፡- የጥንታዊቷ ግሪክ ፈላስፋ ሲሆን የፕላቶ ተማሪና የታለቁ እስክስድር /አሌክሳንደር መምህር ነው። የሱ ተጽዕኖ እስካሁን ድረስ በዘመናዊው ጥናትና አስተምህሮት ላይ የጸና ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት በማስተዋልና ምደባዊ ፈር በያዘ የማስተማር። ስልት አጽንዖት በመስጠቱ ነው። ይህም አንደኛው የሳይንሳዊ ምርምር ዘዴ እንደሆነ ይታወቃል።

**አውቶግራፐር**፡- ይህ ለጥናታዊውና ወጥ ለሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች የተሰጠ ስያሜ ነው። እነዚህ ጥንታዊ ወጥ የብራና ጽሑፎች ሙሉ በሙሉ ጠፍተዋል። የቅጂ ቅጂ ብቻ ነው ያለው ይህም የጽሑፋዊ ይዘት ልዩነቶችን በዕብራይስጥና በግሪክ የብራና ጥንታዊ ጽሑፎች መሐል ሲፈጥር ችሏል።

**ቤዛ**፡- ይህ የ6ኛው ክፍለ ዘመን የግሪክና የላቲን ጽሑፍ ነው። የሚል መለያ ሲኖረው ወንጎላትንና ግብረ-ሐዋርያትን እንዲሁም አንዳንድ መልዕክቶችን አካቷል። ከዚህም በላይ ሌሎት በርካታ ስንክሳሮችን /ጽሑፎችን/ ይዟል። በኪንግጀምስ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂ ወስጥ መካተት ስላለባቸው መሰተር ጥሏል። /እንደ መነሻ ሆኗል።

**አድልዖ**፡- ይህ ቃል የሚያመለክተው በአንድ ነገር ወይም አመለካከት ላይ ቀደም ተብሎ የተያዘ አድሏዊ ግትር አቋምን ነው። አእምሮ በአንድ ነገር ከተያዘ ማድላቱ የማይቀር መሆኑል ያሳያል። ቀደም ብሎ የተያዘ ፍርደ-ገምድላዊ አቋምን ያመላክታል።

**መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረዳት**፡- ይህ ቃል በተለተ መልኩ ጥቅም ላይ የሚውል ነው። ይህም ማለት የመጀመሪያው ፀሐፊ በዘመኑ ምን ለማለት እንደፈለገና አሁን በዘመናችን በምን መልኩ ተግባራዊ እንደምናደርገው ያለውን ያካትታል። መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረዳት ቃሉን ስልጣናዊ መመሪያ አድርጎ መውሰድ ነው። የሆነ ሆኖ የትርጓሜ መዛባት እንዳይከሰት የመጽሐፍ ቅዱስን ትርጓሜ በታሪካዊና በሰዋሰዋዊ ዘዴ ብቻ መወሰኑ ይበቃል።

**ደንብ**፡- ይህ ቃል በተለይ ተመስጧዊ በሆነ ሁኔታ በተመስጧዊ የሆኑትን ጽሑፎች ይመለከታል። ይህም ሁለቱንም የብሉይና የሐዲስ ቅዱሳት መጻሕፍትን ያካትታል።

**ማዕከለ ክርስቶስ**፡- ይህ ቃል የኢየሱስን ማዕከላዊነት ያመላክታል። ቃሉን ለመጠቀም የተፈለገው ኢየሱስ የመጽሐፍ ቅዱስ ጌትነቱን የሚያሳየውን ጽንሰ ሐሳብ ለማሳየት ነው። ብሉይ ኪዳን ወደ እሱ አመላካች ነው። እሱም የቃሉ ፍጻሜና ግብ ነው /ማቴ 5፡17-48/

**ሐተታ ትርጓሜ**፡- ይህ የተለየ ዓይነት የሐተታ መጽሐፍ ነው። ለመጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ ዳራ ያስነብባል። እያንዳንዱ የመጽሐፍ ክፍልን ትርጓሜ ለመስጠት ይሞክራል አንዳንዶች በተግባራዊ አያያዝ ላይ ሲያተኩሩ ሌሎች ደግሞ በጽሑፍ ቴክኒካዊ አግባብ ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ። እነዚህ የትርጓሜ መጻሕፍት በጣም ጥቅም ይሰጣሉ። ዳሩ ግን ከእነሱ በፊት አጥኚው ግለሰብ የራሱን ጥናት መካሄድ ይጠበቅበታል። እነዚህ የትርጓሜ መጻሕፍት ሐተታዎችን መቀበል የሚገባው በወል መርምሮ መሆን ይገባል። ለዚሁም የተለያዩ ትርጓሜዎችን ከተለያየ ስነ-መለኮታዊ ትምህርቶች አቋም አኳያ መመልከቱ ተመራጭ ነው። ቃላት ዝርዝር ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ምርምራዊ መጽሐፍ ነው። በብሉይም ሆነ በሐዲስ ያሉትን ቃላት ሁሉ በየአገባባቸው በዝርዝር የያዘ ነው። በብቁ መንገድ እገዛ ያደርጋል። 1/ እያንዳንዱን የእንግሊዝኛ ቃል ምን መሆን እንዳለበት ከዕብራይስትና ከጽርዕ/ግሪክ/ እንደሆነ ያመላክታል 2/አንቀጾችን በማነጻጸር የመሳሳይ የሆነ የግሪክ ወይም የዕብራይስጥ ቃል ጥቅም ላይ መዋሉን ለማወቅ ያስችላል። 3/ሁለት የተለያዩ የዕብራይስጥም ሆነ የግሪክ ቃላት በተመሳሳይ የእንግሊዝኛ ቃል ተርጉመው እንደሆነ ያመላክታል። 4/ቃላቶች በምን ያህል ድግግሞሽ በየትኞቹ መጻሕፍትና ጸሐፋት እነደተፈረገ ያሳያል። 5/ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ተጠቀሰው ቃል አመላካች የሆነ አንቀግ ያሳያል /ዋልተር ክላርክ የብሉይ ኪዳን ግሪክኛ እንዴት ጥቅም ላይ እነደዋለ የጥናት መረጃ መጽሐፍ ገጽ 54-55።

**የሙት ባሕር ጥቅሎች**፡- ይህ የሚያመለክተው የጥንታዊ ጽሑፍ ጥቅሎች የሆኑ በዕብራይስጥና በአረሚክ የተፃፉ ሙት ባሕር አጠገብ በ1947 የተገኙትን መጻሕፍትን ነው። እናዚህ ጥቅሎች ሃይማኖታዊ ቤተ-መጽሐፍት ሲሆኑ የይሁዳነት ክፍል የሆኑ በ1ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩትን ነው። የሮማ የግዛት መስፋፋትና በ60ዎቹ የተካሄዱት የቀናኢነት ውጊያዎች ገዳም በመሰሉና በዋሻዎች ውስጥ በሸክላ ታሽገው እንዲቀመጡ እንዳስገደደ ይገመታል። ጥቅሎች የ1ኛው ክፍለ ዘመን ፍልስጤምን ታሪካዊ መቼቶችን እንድንገነዘብና ማሰራዊ ጽሑፎች የሚባሉትን ትክክለኛነት እንድንረዳ /ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበረውን/ አስችለውናል። በአድሕሮት በመባል ይታወቃሉ /ሙ/ባ/ጥ/ የሙት ባሕር ጥቅሎች።

**ዲዳክተር**፡- ይህ አይነቱ ተአመክንዮ አገባብ ከአጠቃላይ መርሕ ተነስቶ ወደ ዝርዝር ሁኔታ ውስጥ የሚገባ ሎጂካዊ አስተሳሰብ ነው። ከአንደክቲቭ አስተሳሰብ ተቃራኒ ነው። ማለትም ሳይንሳዊ የሆነውን ከዝርዝር አስተውሎች በመነሳው ወደ አጠቃላይ ንድፈ ሃሳብ የሚያደርሰውን።

**ዲያሌክቲካዊ**፡- ይህ አይነቱ የአስተሳሰብ ዘዴ ተቃራኒ የሆኑትን ነገሮች ያስቀምጥና /አይዎ/ በሁለቱም በኩል ያለውን ተቃርኖና ተዛምዶ የሚመረምር ነው። ብዙ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮቶች ዲያሌክታካዊ ጥንዶች አሏቸው። ለአብነትም ቀድሞ የተወሰነና - ነጻ ፍቃድ ደሕንነት - ጥረት እምነት ስራ ውሳኔ ስርዓታዊት ክርስትያናዊ ነጻነት ክርስትያናዊ ሐላፊነት።

**ዲያስፖራ**፡- ይህ ቃል የግሪክ ሲሆን ከነዓናዊ አይሁዶች አገራቸው ውጭ ያሉትን ከመልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ከተስፋይቱ ምድ ዳርቻ ወጭ የሚኖሩትን አይሁዳውያን ለመጥራት የሚጠቀሙበት ነው።

**ፍጹማዊ አቻነት**፡- ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ የትርጓሜ ሐሳብ ሲሆን ትርጓሜዎቹም ቃል በቃል አቻ እና አንድ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ከዕብራይስጥም ሆነ ከግሪክ አቻውን አግኝተው መተርጎም የሚገባው ሲሆን ይህ ከልሆነም በሐረግ መልክ ሐሳብ በጥንቃቄ ከምንጩ ሳይዛባ እንዲተረጎም ይደረጋል። በእነዚህ ሁለት ንድፈ ሐሳቦች መሐል ፍጹማዊ አቻነት መነሻ ጽሑፉን አተኩሮ ይዚ በዘመናዊ ሰዋሰውና ፈሊጥ መተርጎም ይኖርበታል ይላል። የእነዚህ የትርጓሜ ንድፈ ሐሳቦች ትንታኔ መጽሐፍ ቅዱሳን እንዴት በመረዳት እናንብብ ገጽ 35 በሚለው ሰፊ እና ስታዋርት መጽሐፍ ላይ /ሮበርት ባራቸር/ መግቢያ በሰጡበት እናገኘዋለን።

**ኤሌክቲክ**፡- ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው የመጽሐፉን ቅኝት ለማከናወን ብቻ ነው። ጠቀሜታውም የተለያዩ ንባቦችን ከግሪክ ጽሑፎች ውስጥ በመምረጥና በመመርመር ዋነኛውን ወጥ ጽሑፍ ጋር ለመድረስ የሚያስችል ነው። ከግሪክ ጽሑፎች መሐከልም ዋነኛውን ተንተርሰው በግል አስተያየት መልክ የተሰጡትን አይቀበልም።

**ኤሲጀሲስ**፡- ይህ የኤክሰሳይስ ተቃራኒ ነው። ማለትም ኤክሲጂሰሲ ከዋነኛው ጸሓፊ ሐሳብ ያፈነገጠ /የወጣ/ ከሆነ ኤሲጀሲስ ደግሞ ባዕድ ሐሳብ ወይም አስተያየት ውስጥ ማጨቅን/በብዛት መግባትን ማስገባትን/ ይመለከታል።

**ስርወቃል**፡- ይህ የስርወ ቃላት የማጥኛ ዘዴ ሆኖ መነሻው ከምን እንደሆነ ይመረምራል። ከቃሉ ስር ፍቺ በመነሳትም ቃሉ እንዴት እቅም ላይ እነደዋለ ለማወቅ ያስችላል። በትርጓሜ ጊዜ ግን ኢቲሞለጂ ዋነኛ የትኩረት ነጥብ አይደለም። አወዳዊ ፍቺና የቃሉ አገባብ ነው የሚተኮርበት።

**ኤክሰጀሲስ**፡- የተወሰነ አንቀጽን ለመተርጎም የሚውል ቃል ነው። ይህም ማለት ከጽሑፉ ወጣ ባለ መልኩ በመርመር የዋነኛ ጸሐፊውን ሃሳብ ለመረዳት የሚያስችል ነው። ከታሪካዊ ዳራና መቼት /መቼ እና የት/ ስነ ጽሑፋዊ ፈርጅ ለዋሰውና ወቅታዊ የቃሉን ፍቺ ይቃኛል።

**ዣነ**፡- የፈረንሳይ ቃል ሲሆን የተለያዩ የስነጽሑፍ ዘውጎች ማለት ነው። ተመሳሳይነት ያላቸውን የስነጽሑፍ ዓይነቶች አንድ ላይ ይመድባቸዋል። ለምሳሌም ታሪካዊ ትረካ ቅኔ ምሳሌ ትንቢታዊ /ምስል ከሳች/ ሕጋዊ ይገኙበታል።

**ግኖስቲስዝም**፡- ስለዚህ ጉዳይ ያለን እውቀት የሚመነጨው በሁለተኛው ክፍለ ዘመን ከነበሩይ የግኖስጢክ ጽሑፎች ሲሆን አስተሳሰቡ ግን ከ1ኛው ክፍለ ዘመን ከነበሩት የግኖስጢክ ጽሑፎች ሲሆን አስተሳሰቡ ግን ከ1ኛው ክፍለ ዘመን ወይም ቀደም ሲል የነበረ ነው።
አንዳንዶች እንደሚሉት የቫለንታይን እና የቆረንታይን የ2ኛው ዘመን ግኖስጢስ 1/ቁስ አካልና መንፈስ ዘላለማዊ ሲሆኑ አንድነትም ምንታኤም /ሁለትነትም/ ይዘው። ቁስ አካል ክፉ ሲሆን መንፈስ ግን ሰናይ ነው። መንፈስ የሆነው እግዚአብሔር በቀጥታ ክፉ ነገርን በማበጀት ውስጥ አይገባም። 2/በእግዚአብሔርና በቁስ አካል መካከል የረጅም ጊዜ ወይም የመላዕክታዊ ደረጃ አለ። የመጨረሻው ወይም ዝቅተኛው ያህዌህ? /YHWH/ ሲሆን አለማትን የመሰረተ ነው። አንዳንዶች ከፍተኛ አድርገው በመመሰጥ ከእግዚአብሔር ያነሰ /በመለኮትነቱ ሳይሆን/ የሰው አካል ለብሶ መለኮት ሊሆን አይቻለውም። እሱ መንፈስ ነው 1ኛ ዮሐ. 1፡1-3 4፡1-6 /እና 4/ ደሕንነት ሊገኝ የሚችለው በኢየሱ በማመንና የተለያየ እውቀት በማግኘት ይህም ልዩ እውቀት በልዩ ሰዎች የሚታወቅ ነው። እውቀት /የማለፊያ ቃል/ ወደ መንግስተ ሰማያት ለመግባት ያስፈልጋል። የአይሁድ የሕግ እውቀትም ወደ እግዚአብሔር ለመድረስ ይህ እንደሚያስፈልግ ያመለክታሉ።
የግኖስቲክስ የሀሰት መምህራን ሁለት ዓይነት ስነ ምግባራዊ ተጻራሪ ስርዓቶች ያስቀምጣሉ። 1/ለአንዳንዶች የአኗኗር ስርዓት /ዘዬ/ ከደሕንነት ጋር ምንም ዓይነት ተዛምዶ የለውም። ለእነሱ ደሕንነትና መንፈሳዊነት ምስጢራዊ እውቀት /የማለፊያ ቃል/ በሚሰለው የተጎዳኘ በመላዕክት ክልል ነው ይላሉ። ወይም 2/ለሌሎች ደግሞ የአኗኗር ስርዓት በደሕንነት ላይ ትልቁ ነጥብ ነው። ለተሻለ የሕይወት ዘይቤም አጽንኦን በመስጠት ለእውነተኛ መንፈሳዊነት በማስረጃ ያቀርባሉ።

**ሄርሜኒዩኒክስ**፡- ቴክኒካዊ ቃል ሲሆን ለ ኤክሴጂሲስ እንደ መርሕ ያገለግላል። ሁለትዮሽ የሆነ የተወሰነ መመሪያና ተሰጧዊ ጥበብ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ወይም የተቀደሰ በሚል ሄርሜሊዮኒክስ በሁለት ምድብ ማለትም፡- አጠቃላይ መርህና ዝርዝር መርሆች በሚል። ይህም ከተለያዩ መከጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙ ስነ ጽሑፎች ጋር ይዛመዳል። እያንዳንዱ የተለየ የስነጽሑፍ ዘውግ የየራሱ የተለየ መመሪያ ያለው ሲሆን ከሌሎች ጋር ደግሞ ግምቶችንና የትርጓሜ አገባቦችን ይጋራል።

**ኃየር ክርቲዝም**፡- ይህ የመጽሐፍ ቅዱሳዊ የትርጓሜ አገባብ /ደንብ/ ሲሆን አተኩሮቱም በአንድ በመጽሐፍ ቅዱስ መጽሓፍ ላው በታሪካዊ መቼትና በስነጽሑፋዊ መዋቅር ላይ ነው።

**ፈሊጥ**፡- ይህ ሐረግ የተለያዩ ባህሎችን ተንተርሶ ከዋናው ቃል ትርጉም ጋር ያልተያዘ ትርጉም የሚሰጥ ነው። አንዳንድ ዘናዋ ምሳሌዎች፤ የመጥፎ ጥሩ ነው ገደልከኝ የሚሉ አሉ። መጽሐፍ ቅዱስም የዚይ ተመሳሳይ የሆኑ ሐረጎች አሉት።

**ማብራሪያ**፡- ይህ ስያሜ የተሰጠው እግዚአብሔር ለሰው ልጆች መናገሩን ለማመልከት ነው። ሙሉ ጽንሰ ሐሳቡ የሚገልጸው በሶስት መልክ ነው። 1/ራዕይ እግዚአብሔር በሰው ታሪክ ውስጥ መስራቱ 2/ ተመስጦ፡- ለድርጊቱ ተገቢ የሆነ ትርጓሜ እና ፍቺ ለተመረጡ ሰዎች በተመስጦ በማስታወቅ መዝግበው ለሰው ልጅ እንዲያስተላልፉ ማድረጉ 3/ማብራሪያ፡- መንፈሱን ለሰው ልጆች በሰጡት ስለ እሱ እንዲያውቁና እንዲያስተውሉ ማስቻሉ።

**ኢንዳክሪቭ**፡- የሎጂክ አንዱ ዘዴ ሲሆን ከዝርዝር ነገሮች ተነስቶ ወደ አጠቃላይ የሚተነትን ነው። ለዘመናዊው ሳይንስ በተግባር ዘዴ በመሆን በማገልገል ላይ ነው። ዘዴው በመሰረቱ የአርስቶትል ነው።

**ኢንተርላይነር**፡- ይህ የምርምር መሳሪያ ዘዴ ዓይነት ሲሆን የመጽሓፍ ቅዱስን ቋንቋ የሚያነቡትን እንዲተነትኑና ፍቺውንና መዋቅሩን እንዲረዱ ያስችላል። የእንግሊዝኛውን ትርጉም ቃል በቃል በማስቀመጥ ከዋናው የመጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋ ጋር አነጻጽሮ ያስቀምጣል። ይህ የምርምር አገባብ ትንተናዊ ስርወቃልን በመደባለቅ ለሰው ልጆች የተናገረው መሰረታዊ ለሆኑት የዕብራይስጥና ግሪክ ፍችዎች መልክ ይሰጣል።

**ተመስጦ**፡- ይህ ጽንሰ ሐሳብ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የተናገረው የመጽሐፍ ቅዱስን በጸሐፍት በትክክልና በግልጽ መገለጡን እንዲያፍሩ ነው። ሙሉ ጽንሰ ሐሳቡ በሶስት መልኩ ይገለጻል።
1/መገለጥ /ራዕይ/ እግዚአብሔር በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ መስራቱ 2/ ተመስጦ ለድርጊቱ ተገቢ ይርጓሜ እና ፍቺ ለተመረጡ ሰዎች በተመስጦ ለማስታወቅ መዝግበው ለሰው ልጅ እንዲያስተላልፉ 3/ ብርሃነ /ማብራሪያ/ መንፈሱን ለሰው ልጆች በመስጠት እሱ ሽሽግነት እንዲያውቁና እንዲያስተውሉ ማስቻል።

**የገለጻ ቋንቋ**፡- ይህ ብሉይ ኪዳን የተጻፈውንና ፈሊጦቹን ለማገናኘት ታስቦ ነው። እሱም የዓለማችንን የአበጋገር አግባብ በአምስቱ የስሜት ሕዋሳት በማስመርኮዝ ያቀርባል። ሳይንሳዊ ገለፃ ማለት ግን አይደለም።

**ሕጋዊነት**፡- ይህ አዝማሚያ የሚያመለክተው ለሕግጋትና ለክብረ በዓላዊ አምልኮተ ስነስርዓት አፅንኦት የመስጡትን ነው። የሰው ልጆች የሚያደርጉትን ደንቦችና ስርዓቶች እግዚአብሔር ይቀነለዋል ብሎ መወሰን ነው። ግንኙነትን ዝቅ የሚያደርግና ክዋኔዎችን ከር የሚያደርግ ሆኖ ሁለቱንም ኪዳናዊ ግንኙነቶች /በቅዱሱ በእግዚአብሔርና በኃጢያተኛው ሰውነት እንደሚካህወድ ያስምጣል።

**ጽሑፋዊ ፍቺ**:- ይህ የጽሑፋዊ ፍቺ ላይ የሚያተኩር እና ታሪካዊ የአተረጓጎም ዘዴ የሆነውን የአንቲሆችን ባህል ይከተላል። ይህም ማለት ትርጓሜ መያዝ ያለበት ተራ ወጌና ግልጽ የሆነውን ፍቺ በሰው ልጆች ቋንቋ እንዳለ ነው ይላል። ይህም ማለት ግን በተምሳሌታዊ ቋንቋ የተጻፉ ክፍሎች መኖራቸውን አይክድም።

**ጽሑፋዊ ዘውግ /ክፍል**:- ይህ የሰው ልጆች መግባቢያ የሆነ የጽሑፍ ክፍሎችን ማለትም ቅኔ ታሪካዊ ትረካ የመሳሰሉትን ያካትታል። እያንዳንዱ ዓይነት ስነ ጽሑፍ የየራሱ የትርጓሜ አገባብ ሲኖረው በተጨማሪም ለሁሉም የስነ ጽሑፍ መርሖችን ይከተላል።

**ጽሑፋዊ አሃድ**:- ይህ የሚያመለክተው ዋነኞቹን የመጽሐፍ ቅዱስ ያስተሳሰብ ክፍሎችን ነው። ይህም በጥቂት ምንባቦች አንቀጾች ወይም ምዕራፎች ሊዘጋጅ ይችላል። በየራሱ ሙሉ የሆነና ማዕከላዊ የጽሑፍ ዓይነት የያዘ ነው።

**ሎወር ክርቲዝም**:- /ቴክስቲወሐነ ክርትዝም/ ተመልከት የእጅ ጽሑፍ /የብራና ጽሑፍ/። ይህ ቃል የግሪኩን የሐዲስ ኪዳን ልዩ ልዩ ኮፒዎች ያመላክታል። ብዙውን ጊዜ በልዩ ልዩ ዓይነት ይመደባሉ። 1/ከተጻፈባቸው ቁሳቁስ /ፓፒረስ፣ ብራና/ ወይም 2/ የጽሑፍ የራሱ ቅርጽ /በካፒታል/ በቁም ጽሑፍ ወይም በቅጥልጣይ መሆኑ። በአጽሕሮተ ቃልም "MS" የብዙ ቁጥር ይባላሉ።

**ማአሶሬቲክ ቴክስት**:- የዘጠነኛውን ክፍለ ዘመን በብሉይ ኪዳን የዕብራይስጥ የእጅ ጽሑፎችን ያመለክታል። ይህም በአይሁዳዊ ጠበብት የተጻፈና አካባቢ ድምጾችን ተጓዳኝ እዝሎችን የግርጌ ማስታወሻዎችን ያካተተ ነው። ለእንግሊዝኛው ብሉይ ኪዳን የሚሆነው ጽሑፍ ከዚህ የተገኘ ነው። ጽሑፍ በታሪካዊ መልኩ በዕብራይስጥ እንደሆነ የተረጋጠ ሲሆን በተለይ ትንቢተ ኢሳያስ በሙት ባሕር ጥቅሶች ታውቋል። በአጽሕሮትም "MS" ይባላል።

**ሚኢቶናሚ**:- ከንግግር ክፍሎች ሆኖ የአንድ ነገር ስም ከሌላው ጋር በተጓዳኝ በመጥቀስ የሚገለጥበት ነው። ለምሳሌ ጀበናው እተፈላ ነው ሲል በጀበናው ውስጥ ያለው ውኃ እየፈላ ነው ለማለት ነው።

**ሙርአቶርያን ፍራግመንትስ**:- ይህ የደንብ /የሕግ/ መጻሕፍትን ዝርዝር ያካተተ ኪዳን ክፍል ነው። የተጻፈውም በሮሜ ከ200 ዓ.ም ቀደም ብሎ ነው። እነዛኑ 27 የሐዲስ መጽሐፍት በፕሮቴስታንት አዲስ ትርጉም ነው። ይህም በሮም ግዛት የሚገኙት የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ዋነኞቹ የቤተክርስቲያን ምክር ቤቶች /በ4ኛው ክፍለ ዘመን ከነበሩት/ በፊት እንደተበጀ ያመላክታል።

**ተፈጥሯዊ መገለጥ**:- ይህ እግዚአብሔር ራሱን ለሰዎች የሚገልጽበት አንደኛው ክፍል ነው። ተፈጥሯዊ ስርዓትን /ሮሜ 1፡19-20/ እና ሞራላዊ የሕሊና ሚዛንን /ሮሜ 2፡14-15/ ያካትታል። በመዝሙር 19፡1-6 እና ሮሜ 1-2 ተጽፏል። ከልዩ መገለጥ ይለያል፣ ማለትም የእግዚአብሔር የራሱ መገለጥ በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በናዝሬቱ ኢየሱስ ማለት ነው።
ይህ የስነ መለኮት ምድብ እንደገና አጽንዖት እየተሰጠው እንደ ሁግሮስ በመሳሰሉ ክርስቲያን ጸሐፍት በአሮጌው ዓለም ንቅናቄ ላይ ተመልክቷል። እነሱም ይህን ምድብ ሁሉም እውነት የእግዚአብሔር እውነት እንደሆነ ያጸኑበታል። ተፈጥሮ በእግዚአብሔር ለማወቅ የተከፈተ በር ነው ይህም ካልተመሰጥ /ከመጽሐፍ ቅዱስ/ ይለያል ዘመናዊው ሳይንስ የተፈጥሮ ስርዓትን እንዲያጠና ነጻነትን ይሰጠዋል። እንደኔ አስተያየት ለዘመናዊው ሳይንሳዊ የምዕራቡ ዓለም ለመመስከር አዲስ አስደናቂ ዕድል ነው እላለሁ።

**ንስጥሮሳዊነት**:- ንስጥሮስ በ5ኛው ክፍለ ዘመን የኮንስተንበኖፕል ፓትርያርክ የነበረ ነው። የተማረውም በንሪሆች ሶርያ ሲሆን የመከራከሪያ ነጥቡም ኢየሱስ ሁለት ባሕርያት ሲኖሩት አነደኛው ሙሉ ለሙሉ ሰው፣ ሌላኛው ሙሉ ለሙሉ መለኮት ነው ባይነው። ይህም ከአሌክሳንደሪያው የኦርቶዶክስ አንድ ባሕሪ /በተዋህዶ/ ከሚለው ያፈነገጠ ነው። የንስጥሮስ ዋነኛው አትኩሮቱ ለማርያም የተሰጠው የአምላክ እናት የሚለው ስያሜ ነው። ንስጥሮስ በሌክሳንደሪያው ሲሪል ነቀፋ ገጥሞታል። ይህም ዞሮ ዞሮ በተማረበት በአንቲሆች ማለት ነው። በወቅቱ አንቲሆች የታሪካዊ ሰዋሰዋዊ ጽሑፋዊ አገባብ ያለው የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትረጓሜ ማዕከል ስትሆን አሌክሳንደሪያ ደግሞ በአራትዮሹ /ተምሳሌታዊ/ ጉባዔያት የትምህርት ትርጓሜ ማዕከል ነበረች። ንስጥሮስ ከማዕረጉ ወርዶ በግዞት እንዲቀመጥ ተደርጓል።

**ዋነኛው ጸሐፊ**:- ይህ የሚያመለክተው ዋነኞቹን የቅዱሳን መጻሕፍት ጸሐፊዎችን ነው።

**ትይዩ አንቀጾች**:- እኒህ የጽንሰ ሐሳብ ክፍሎች፣ መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የተሰጠ እና ፍጹም የሆነው የሆነው ተርጓሚም እሱ እንደሆነ፣ አደናጋሪ የመሰሉንን እውነቶች እንኳ ሚዛናዊ በሆነ መልኩ የሚፈታ ነው። ይህም አንድ ሰው ግልጽ ያልሆነለትን አሻሚ አንቀጽ ሲተረጎም ሲሻ ሊረዳው ይችላል። አንቀጾቹ በተጨማሪም ግልጽ ተዛማጅ ክፍሎችን በርዕስ ጉዳዩ ዙሪያ ከቅዱሳት መጻሕፍት ያመላክታሉ።

**አጽሕሮት**:- ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ይረጓሜ ንድፈ ሐሳብ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ቃል በቃል የተረገና ተያያዥነት ቅርጽ የያዘ ሆኖ የእንግሊዝ ቃል ለዕብራይስጥም ሆነ ለግሪክ ቃል ፍቺነት ተፈልጎ፣ የክፍሉ /የአንቀጹ/ ፍሬ ሐሳ ዝቅ ባለ ግምት ከዋናው ጽሑፍ ጋር እየተያየ የሚተረጎምበት ነው። ከእነዚህ ሁለት ዓይነት ንድፈ ሐሳቦች ፍጹም አቻዎች የሚባለው ግን ዋናውን ጽሑፍ በዘመናዊ ሰዋሰው እና በዘይቤና በፈሊጥ ለመተርጎም

የሚሞክር ነው። ይህን በተመለከተ ደህና መብራሪያ /የትርጉም ንድፈ ሐሳቦች /በ Fee እና Stuart መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት በመረዳት እናንብ ገጽ 35 ተመልከት።

**አንቀጽ፡-** ይህ በስድ ንባብ የሚደረግ ዋነኛው የትርጓሜ ክፍል ነው። አንድ ዋነኛ ሃሳቡን ይዞ እያዳበረ ይሄዳል። አንዳንድ በአነቀጽ ላይ ብቻ አኩረን ትርጉሙን ስነሻ /አናሳ አንቀጽ ላይ/ የዋናውን ጸሐፊ ሃሳብ ላናገኘው እንችላለን።

**ፖራኮሊዝም፡-** ይህ የሚያሳየው በአድሏዊነት የተያዘን የአጥቢያ ስነመለኮታዊና ባህላዊ ጉድኝትን ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን ፍጹም ባህል /የባህሎች ሁሉ የበላይነት/ እና የአተገባበር እውነቱን ግምት ውስጥ እያስገባም /አይቀጠልም/።

**አያዎ፡-** ይህ የሚያመላክተው ተቃራኒነት ያላቸው የመሰሉ እውነቶችን ሲሆን /ይሆናሉ አይሆኑም/ የሚል መልክ ይዞ ነው። እውነትን የሚያቀርበው ተቃራኒ አቅጣጫዎችን ይዞ ነው። ብዙዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች የሚቀርቡት በዚህ /አያዎ/ ወይም በዲያሌክታካዊ ጥንዶች ተቃርኖ አገባብ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታዎች ተለያይተው እንደተቀመጡ ከዋክብት ሳይሆኑ ምድብ ምድብ በያዙ የክዋክብት ክምችት ይመስላሉ።

**ፕላቶ፡-** ከጥንታዊ ግሪክ ፈላስፎች አንደኛው ነው። የሱ ፍልስፍና የጥንታዊዋን ቤተክርስትያን በአሌክሳንደሪያ ግብፅ ሊቃውንት እንዲሁም በአውግስጦስ አማካኝነት ተጽዕኖ አሳድሯል። ፕላቶ በምድር ላይ ያለ ማንኛውም ነገር የመንፈሳዊ ዓለም ግለባጭ /ቅጅ/ ነው ብሎ ያምናል። የስነመለኮት ጠበብት በኋላ ይህን ተፕላቶን አስተሳሰብ ቅርፆች/ሐሳቦች በሚል ለመንፈሳዊ ተግባር ጥቅም ላይ አውለውታል።

**ቅድመ ግምት፡-** ይህ ስለ አንድ ነገር ቀድመን የምናስበው ወይም የምንገምተው ነው። ጽሑፉን ከመመርመራችን በፊት ብዙ ጊዜ አስተያየትና ፍርድን /አቋምን/ ስለ አንድ ነገር ማድረግ ይዘወተርብናል። ይህ ቅድመ ግምት፣ አድልዖ በመባልም ይታወቃል። ግምት ወይም ቅድመ እውቅና ይባላል።

**ፕሩፍ ቴክስቲንግ፡-** ይህ ተግባት ከለን በቁጥር ብቻ /ሙሉ ክፍልን ሳይሆን/ ወይም ዋናውን የክፍሉን አጠቃላይ ሃሳብ ሳይሆን የመተርጎም ስራ ነው። ይህም ቁጥሮቹን ከዋናው የጸሐፊው ሐሳብ ባፈነገጠ መልኩ የግል አስተያየትን በሚካተት የመጽሐፍ ቅዱስን ስልጣን ትቶ ማለት ነው።

**ይሁዳዊ መምህርነት፡-** ይህ ዓይነቱ የአይሁድ ሕዝቦች የኑሮ ስርዓት የተጀመረው ከ586-538 ቅ.ል.ክ ከባቢሎን ግዞት በኋላ ነው። የአይሁድ ቀሳውስትና ቤተመቅሰሱ ከቀሩ በኋላ የአጥቢያ ምኩራቦች የአይሁድ ብሔራዊ የዕምነት ማዕከላት ለመሆን ቻሉ። እነዚህ አጥቢያ ማዕከላት የአይሁድ ባህል፣ ሕብረት የአምልኮና የቅዱሳት መጻሕፍት ጥናት ማካሄጃ በመሆን የብሔራዊ ሃይማኖታዊ የትኩረት ማዕከላት ሆነዋል። በጂሲየስ ዘመን እነዚህ የጸሐፍት ሃይማኖት ተብለው የሚታወቁት ቀሳውስቱ ጋር በትይዩ መልኩ አገልግለዋል። በ70 ዓ.ም ከኢየሩሳሌም መውደቅ በኋላ ጸሐፍቱ አካል የፈሪሳውያን የበላይ ለመሆን ከመቻሉም በላይ የአይሁድን ሃይማኖታዊ ሕይወት መቆጣጠር ችሏል። ባሕርዩም ተግባራዊ ሕጋዊ ትርጓሜዎች ላይ የሚያተኩር ሆኖ ባህላዊ /ስነ ቃለዊ/ የሆነውን ዘዴ በመጠቀም ታልሙድን ማብራራት ነው።

**ራዕይ፡-** ይህ እግዚአብሔር ሰለው ልጆች የሚናገርበትን ጽንሰ ሐሳብ የሚገልጽ ስያሜ ሙሉ ሐሳቡ ብዙውን ጊዜ በሶስት መንገዶች ይገለፃል። 1/ራዕይ፡- ማለትም እግዜአብሔርን በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ የሚከናወነውን 2/ ተመስ፡- እሱ ትክክለኛውን ትርጓሜ ለድርጊቱ ሁሉ የሚሰጥበትን ይህም በተመረጡ ሰዎች አማከኝነት ሆኖ መዝግበው ለሰው ልጆች የሚያስተላልፍበት አገባብ። 3/በማብራሪያ ማለትም መንፈስን በመስጠት የሰው ልጆችን በማገዝ ስለ እሱ ይበልጥ እንዲረዱ ማድረግን ያጠቃልላል።

**የቃላት የዓረፍተነገር ትርጉም፡-** ይህ አጠቃላይ የቃላት ትርጉም ጋር የተያያዙ ደረጃዎችን ያመላክታል። በመሰረቱ የቃላት የተለያየ ትርጉም በየአግባቡ /በየጽሑፉ/ /በየወርዱ/ የሚታየበት ነው።

**ሴፕቱኤጀንት፡-** የዕብራይስጥ ብሉይ የግሪክ ትርጉም ነው። ከባህል አንፃር በሰባ የአይሁድ ሊቃውንት በሰባ ቀናት ተጽፎ ለአሌክሳንደሪያ ግብፅ የተፃፈ እንደሆነ ይነገራል። ባሕላዊ ጊዜውም 250 ቅ.ል.ክ እነደሆነ ሲገመት /በተግባር ግን ጽፎ ለመጨረስ ከመቶ ዓመት በላይ እነደወሰደ ይገመታል/ ይህ ትርጉም ጠቀሜታው የላቀ ሲሆን፣ ይህም 1/ጥንታዊ የሆነውን ጽሑፍ ከዕብራይስጥ ማስረቲካ ጋር እንዲነጻጸር 2/የአይሁድን የትርጉም አገባብ በ3ኛው ክፍለ ዘመን ከክርስቶስ ልደት በኋላ የነበረውን ያሳየናል። 3/የአይሁድን ሜስነክ መረዳት /አስተሳሰብ/ ማለትም ክርስቶስን ካለመቀበላቸው በፊት የነበረውን ያሳያል። አጽሕሮቱም "LXX" ነው።

**ሲናቲኮስ፡-** የ4ኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም የነበረ የግሪክ የብራና ጽሑፍ ነው። የተገኘውም ቲስከስዶርፍ በተባለ የጀርመን ሊቅ በቅድነት ናተሪኒ ገዳም፣ በጃቤሳ መሳ የተባለ ባሕላዊ ስም ባለው በሲናይ ተራራ ክልል ነው። ይህ የብራና ጽሑፍ /የእጅ ጽሑፍ/ በዕብራይስ የመጀመሪያ ፊደል በሆነው በአልፋ [x] ይታወቃል። እሱም ብሉይ ኪዳንና የተጠቃለለውን ሐዲስ ኪዳንን ይዟል። በጣም ጥንታዊ ከሆኑት የተለየ የእጅ ጽሑፎች አንደኛው ነው።

**የመንፈሳዊ፡-** ይህ ቃል ተምሳሌታወኮ ከማድረግ ጋር ተመሳሳሰይ ሲሆን ሃሳቡም ታሪካዊና ተራ የሆነውን የፅሁፉን ክፍል በማስቀረት በልቶ መስፈርት የመተርጎም አግባብ ነው።

**ተመሳሳይ፡-** ይህ የፅሁፉን ፍቺ ያመለክታል። 15/ምንም እንኳ ሁለት ቃላት ፍፁም ተመሳሳይ ትርጉም ባይኖራቸውም /በጣም የተቀራረቡ ከመሆናቸው የተነሳ በአረፍተ ነገር አወቃቀር ላይ የትርጉም ለውጥ ሳይኖር አንዱ አንዱን ሊተካው ይችላል። በተጨማሪም የእብራይስጥ ቅኔ ከሆኑት 3 የትይዩ ዘርፎች አንደኛውን ለመመስረት ያስችላል። በዚህ መሰረት ባለሁለት መስመር የሆኑትን ቅኔዎች /ግጥሞች/ ያመላክታል። /መዝ 1-3-3/

**ሰዋሰዋዊ፡-** ይህ የግሪክ ቃል ሲሆን የአረፍተ ነገርን አወቃቀረአ ያሳያል። ይህም የአረፍተ ነገር አደራደር ሙሉ አስተሳሰብን እንዲገልፅ ተደርጎ ሲዋቀር ያለውን ያሳያል።

ሳይንዚቲካል፡- ከእብራይስጥ ቅኔ /ግጥሞች ከሶስቱ አይነቶች አንደኛውን ያመለክታል። ይህም የቅኔ /የግጥም/ መስመሮች /ሀረጎች/ አንደኛው ከአንደኛው በመቀናጀት አጠቃላይ ስሜት ሊሰጡ በሚችሉ መልኩ ሲዋቀሩ ነው። አንዳንዴም ተለዋዋጭ ይባላል። /መዝ 19:7-9/

ስልታዊ የስነ መለኮት ትምህርት፡- ይህ ትርጉም ደረጃው አይነት የመፅሀፍ ቅዱስን እውነት ህብር እና ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ሲያቀርቡ ነው። ከታሪካዊነቱ ይልቅ ሎጂካዊነቱ /ምክንያታዊነቱ/ ያመዝናል። የክርስትና የስነመለኮት ትምህርት በየምድቡ በማድረግ /እግዚአብሄር፣ ሰው፣ ሀጢያት፣ ደህንነት ወዘተ/ እያለ ይቀርባል።

**ታልሙድ፡-** ይህ የአይሁድ የስነ ቃል /ባህል መለያ ነው። አይሁድ እግዚአብሄር በሲና ተራራ ላይ ለሙሴ በቃሉ እንደተናገረው ያምናሉ። በተግባር ሲታይ ግን ለዓመታት የተከማቸ። የአይሁድ መምህራን የጥበብ ክምችት ነው። ሁለት ዓይነት የተለያዩ የፅሁፍ ቅጂዎች /እትሞች/ አሉት ታልሙድ እነሱም የባቢሎኑና ያልተጠናቀቀው በአጭር የተፃፈው የፍልሰጥሙ /የከነአኑ/።

**የቃሉ ምርመራ፡-** ይህ የቅዱሳን መፃህፍትን ጡናት ማካሄድ በተመለከተ ነው። ይህ አይነቱ ጥናት አስፈላጊ የሚሆነው ዋነኞቹ ፅሁፎች ስለማይገኙ ቅጂዎቹ የተለያዩ በመሆኑ ነው። ልዩነቶችን ለማብራራትና በተቻለ መጠን ወደ ዋነኞቹ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ፅሁፎች መነሻ ለማድረስ ነው ብዙውን ጊዜ ዝቅተኛው ምርመራ ይባላል።

**የፅሁፍ አቀባበል፡-** ይህ ስያሜ የተሰፋፈው ወደ አኤልዚንር ትርጉም ከሆነው በ1633 የግሪክ አዲስ ኪዳን እትም ነው። በመሰረቱ ይህ የግሪክ የአዲስ ኪዳን የወጣው /የተገኘው/ ጥቂት ቀደም ሲል ተፅፈው ከነበሩ የግሪክ የእጅ ፅሁፎች እና የላቲን እትሞች ማለትም ከአራሳመስ /1510-1535/ እስጢፋኖስ /1546-1559/ እና ኤልዚንር /1624-1678 ከተፃፉት ነው የአዲስ ኪዳን ፅሁፋዊ ምርመራ /ገፅ 27 መግቢያው ላይ ኤቲ ሮበርትስን/ የባይዘንታይን /የግሪክ/ ፅሀፀፍ በተግባር ሲታይ ፅሁፎችን መቀበል ነው ብሏል። የባይዘንታይን ፅሁፍ የመጨረሻው ዝቅተኛው የሆነ በጣም ጠቃሚ ከሆነፀ ከሶስቱ ከቀደምት የብራና /የእጅ ፅሁፎች/ /በምዕራብ በሌክሳንደሪያና በባይዘንታን/ ካሉት የሚመደብ ነው። በውስጡም በእጅ ሲፃፍ ለዘመናት የተደረጉትን ግድፈቶች /ስህተቶች/ አከማችቶ ይዟል። ሆኖም ግን ኤ ቲ ሮበርትሰን ደግሞ እንዳለው፣ ፅሁፎቹ የተወልን ነገር በውስጡ ያለው ተገቢ ፅሀፀፍ ነው ብሏል /ገፅ 21 ላይ/ ይህ የግሪክ ፅሀፀፍ /በተለይም የአራስመስ 3ኛ እትም በ1522 /የንጉስ ጀምስ እትም ማለትም 1611 ዓ.ም የታተመውን መሰረት እንደሆነ ይታመናል።

**ቶራ፡-** ይህ የዕብራይስጥ ቃል ማስተማር ማለት ነው። እሁም ለሙሴ ፅሁፎች /ከዘፍጥረት እሰከ ዘዳግም/ ያለውን የሚያካትተ ርዕስ ነው። ይህ ለአይሁድ ታላቅ ስልጣን /ተቀባይነት/ ያለው ክፍል ነው።

**ታይፖሎጂካል፡-** ይህ ጥልቀት ያለው ሙያዊ ትራጓሜ ነው። ብዙውን ጊዜ የሀዲስ ኪዳን እውነት ከብሉይ ኪዳን ተምሌታዊ መልኩ የሚያስጠቅስና የሚያስማማ ነው። የትርጉም ምድብ ዋነኛው የአሌክሳደሪያን ዘዴ የተከተለ ነው። የዚህ አይነቱን ትርጉም በአግባቡ አለማከናወንን ለማስቀረት ትርጓሜው ሲካሄድ በተወሰኑ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች መሆን ይኖርበታል።

**ቫአቲካነስ፡-** ይህ የ4ኛ ክፍለ ዘመን የግሪክ የእጅ ፅሑፍ ነው። የተገኘውም በቫቲካን ቤተመጽሀፍት ሲሆን ዋናውን ብሉይ ኪዳን ተነባቢት /ራዕይ/ እና አዲሰ ኪዳንን ያካትተዋል። የተወሰኑ ክፍሎች ማለትም ከዘፍጥረት፣ ከዕብራውያን፣ ከሌዋውያን ሆኖም የተወሰኑ ክፍሎች ማለትም ከዘፍጥረት፣ ከዕብራውያን፣ ከሌዋውያን ፊሊሞና እና ከራዕያ ጎድለውብታል። ዋናውም የቃሉን የእጅ ጽሑፍ በመወሰን በኩል በጣም ጠቃሚ የሆነ ጽሑፍ ነው። መለያውም ፊደል "ቢ" ነው።

**ቫሰጌት፡-** ይህ የጀሮም የላቲን ትርጉም የሆነ መጽሀፍ ቅዱስ ነው። ይህ የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ዋነኛ ትረጉም ተደርጎ ተወስዷል። በ380 ዓ.ም ነው የተፃፈው።
ጥበባዊ *ሥነ-ጽሁፍ፡-* ይህ ቃል የሥነ-ጽሑፍን ዘውግ/ዓይነት/ የተለመደ ዓይነት ሆኖ በቅርብ ምስራቅ የጥንት አካባቢ /ዘመናዊው ዓለም/ የሆነውን ያመለክታል። ይህ በቅኔ/በግጥም/በምሳሌያዊ አነጋገር፣ በወገዊ ጽሁፍ አማካኝነት አዲሱን ትውልድ ለማስተማርና ስኬታማ ሕይወት እንዲኖር የሚያስችል ነው። መልእክቱም ለአጠቃላይ ለማህበረሰቡ ሳይሆን በግለሰቦት ላይ ያተኮረ ነው። የታሪክን ሁኔታ በማጣቀስ አይጠቀምም፣ ይልቁንም የሕይወትን ልምድና አስተውሎትን ይቃኛል። ከመጽሀፍ ቅዱስ ከእዮብ ከመሃልየ ማሃልየ የሚታሰበው የያህዌን መገኘትና ማምለክን ሲሆን ይኼውም መንፈሳዊ ዓለም አስተሳሰቡ በግልፅ በየሰው የሕይወት ልምድ በሁሉም ጊዜ እንደማይደረግ ያታወቃል።

እነደ ሥነ-ጽሁፍ ዘርፍ በአጠቃላይ እውነት ላይ ያተኩራል፡፡ ይህ የሥነ-ጽሑፍ ክፍል /ዕይነት/ግን በእያንዳንዱ ሁኔታ ጥቅም ላይ አይውልም፡፡ እነዚህ አጠቃላይ ሀሳቦች በእያንዳንዱ ሰው ባለበት ሁኔታ ላይ የማይከናወኑ ናቸው፡፡

አነዚህ እነዚህ ፅሑፎች የሕይወትን ጠንካራ /ዋነኛ/ ጥያቄ ያነሳሉ፡፡ ብዙውን ጊዜ ሀይማኖታዊ ሆነው ባህል የሚደባለቁ አመለካከቶችን /ኢዮብ/መክብብ/ ያነሳሉ /ይከራከራሉ/፡፡ ለሕይወት ጥያቄዎች ሚዛናዊ ምላሽ በመስጠት በተለይ አሰዛኝ/ሰቆቃዊ/ በሆኑት ላይ ያተኩራሉ፡፡

**ወርድ ፒክቸር እና ወርደ ቪው፡-** እነዚህ ተጓዳኝ ቃላት ናቸው፡፡ ሁሉም ፍልስፍናዊ ጽነሰ ሃሰቦች ሲሆኑ በአፈጣጠር ላይ ያተኩራሉ፡፡ የዓለም ምስል የሚሰጠው እንዴትን ሲያመለክት ስለአፈጣጠር ደግሞ የዓለም አመለካከት የሚለው ማን የሚለውን ያሳያል፡፡ እነዚህ ቃላት በተለይ ዘፍጥረት 1-2 ለመተርጎም በመጀመሪያ በመጀመሪያ ማን፣ የሚለውን ያነሳሉ "እንዴት" የሚለውን የአፈጣጠር ጥያቄ ትተው፡፡

**ያህዌ፡-** ይህ የእግዚአብሄር የቃል ኪዳን ስም በአዲስ ኪዳን ነው፡፡ ይህም ዘፀአትን 3.14 ያለውን ያነትናል፡፡ ይህ የዕበራይስጥ ምክነያታዊ ስም በመጥቀስ መሆን የሚሰውን ያሳያል፡፡ አይሁዶች ይህን ስም ለመጥራት ፍርሐት አለባቸው ምንም አንኳ ቢቀበሉትም፡፡ በመሆኑም ወደ ዕብራይስጥ ለውጠው አዶናይ/ጌታ/ ይሉታል፡፡ በዚህም ምክንያት ነው ይህ የቃል ኪዳን ስም ወደ እንግሊዝኛ የተተረጎመው፡፡

# ተጨማሪ መግለጫ አራት
# የእምነት መግለጫ

በግል በተለይ በእምነት መግለጫም ሆነ የዕምነት ማስታወቂያ ብዙ አያሳስበንም ይልቁንም መጽሐፍ ቅዱስን ማፅናቱ ይሻለኛል። ዳሩ ግን እኔ የዕምነት ሁኔታ ለመረዳትና ለመፈተሽ ለሚፈልጉ የዕምነት መግለጫው ይረዳቸው ይችላል። በርካታ ሥነ-መለኮታዊ ሕጸጾችና የተዛቡ አመለካከቶች ባሉበት ሁኔታ የእኔን ሥነ- መለኮታዊ ትምህርት አጭር ማጠቃለያ አቀርባለሁ።

1. መጽሀፍ ቅዱስ ብሉይም ሆነ አዲስ ኪዳን ሁለቱም ተመስጧዊ የሆነ የማይወድቅ /የማይሻር / ሙሉ ሥልጣን ያለው የእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ቃል ነው።

ቃሉ የራሱ የእግዚአብሔር መገለጥ ሲሆን በመንፈሳዊ ምሪት በሰዎች አማካኝነት የተመዘገበ /የተፃፈ/ ነው። ስለ እግዚአብሄር ንፁህ እውነት እና ስለ ተግባሩ የሚገልፅ ብቸኛ ምንጭ ነው። እሱም ለራሱ ቤተክርስቲያን የዕምነትና የተግባር ብቸኛ ምንጭ ነው።

2. አንድ ብቻውን የሆነ ዘለዓለማዊ ፈጣሪ የሚቤዥ እግዚአብሔር አለ። እሱም የሚታየውንም ሆነ የማይታየውንም የሁሉም ነገር ፈጣሪ ነው። ራሱን በአፍቃሪነቱና በጠባቂነቱ /በተንከባካቢነቱ/ የገለፀ ሲሆን ራሱም ፍፁምና /መልካም/ ትክክለኛ ነው። ራሱን በሦስት አካላት ገልጧል። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በእኩል አካል የተለያዩ ባህርያ ግን አንድ የሆነ።

3. እግዚአብሔር ከቃሉ ጋር ሁሌም ነው። እናም ዘለዓለማዊ እቅድ ለፍጥረቱ ያለ ሲሆን ይህም ማስተካከያ የማይደረግለት በእያንዳንዱ ሰው ነፃ ፍቅር ላይ ያተኮረ ነው። ያለ እግዚአብሔር እውቅናና ፍቃድ የመሆን ነገር የለም ይህም ቢሆን ግን ለሰዎችም ሆነ በመላእክት ነፃ ፍቀድን ፈቅዷል። እየሱስ አብ የመረጠው ሰው ነው። ሁሉም የሚመረጡት በሱ ነው። የእግዚአብሄር የሁኔታዎች ቀድመ እውቅና የሰው ልጆችን ቅድመ ፅሑፍ ቃሉን ከመቀበል ለመወሰን አያዳግታቸውም። እያንዳንዳችን ለምናስበውም ሆነ ለምንሰራው ሃላፊነትን እንወስዳለን።

4. የሰው ልጅ ምንም እንኳን በእግዚአብሄር አምሳል ቢፈጠርና ከሃጥያት ነፃ ቢሆንም በእግዚአብሄር ላይ ማመፅን መረጠ። አዳምና ሄዋን ምንም እንኳ ከተፈጥሮ በሆነ ወኪል ቢፈተኑም ፈቅደውና ወደው በግለኝነት በወሰዱት አቋም ሃላፊነት አለባቸው። የእነሱ አመፅ ነው የሰው ልጅንም ሆነ ፍጥረትን ለጉዳት የዳረገው። እኛ ሁላችንም ከእግዚአብሔር ምህረት ከአዳም ለወረስነውም ሆነ በሰውነታችን ለፈፀምነው አመፅ ያስፈልገናል።

5. እግዚአብሔር ይቅርታውንና ምህረቱን ለወደቀው ሰውነታችን ስጥቶናል። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ብቸኛ ልጅ ሰው የሆነ፣ ያለ ሃጥያት የተመላለሰ እኛን ውጦ በሞተልን፣ የሰው ልጆችን የአሃጢአት ቅጣት ተቀበለ። እሱ የደህንነት መንገድና ከእግዚአብሔር ጋር ለሚምረው ስውረት ብቸኛ መንገድ ነው። ስለደህንነት ሌላ ምንም መንገድ የለም ራሱ ሰርቶ በጨረሰው ሥራ ከማመን በስተቀር።

6. እያንዳንዳችን በግል የእግዚአብሔርን ይቅርታ ስጦታ በእየሱስ የሆነውን ደህንነት መቀበል ይኖርብናል። ይንንም ማግኘት የሚቻለው በእግዚአብሔር ተስፋ በማመን፣ በኢየሱስ በኩል ፍቃደኝነት ከሃጢአት መራቅ ነው።

7. ሁላችንም ሙሉ ምህረት እና መመለስ የምናገኘው ክርስቶስ እምነትና ሃጢአት በመመለስ ነው። የአዲስ ህይወቱ ማስረጃም በተለመደና እየተለወጠ ባለ ህይወቱ ይታወቃል። እግዚአብሄር ለሰው ሰጆች ያለው ዓላማ አንድ ቀን በመንግስተ ሰማያት የሚሆን ሳይሆን አሁን ክርስቶስ በመሰለ ሕይወት መመላለስ ነው። በትክክል መቤዠትን ያገኙ በስህተት ሃጢአት ቢሰሩም በዕምነታቸው ቀጥለውበት በንሥሐ ህይወት በሕይወት ዘመናቸው ሊመላለሱ ይገባል።

8. መንፈስ ቅዱስ ሌላው እየሱስ ነው። እሱም በዓለም ላይ አለ፣ የጠፉትን ወደ ክርስቶስ ለመምራትና በዳኑትም ክርስቶስ የመሰለ ሕይወት እንዲኖሩ በማስቻል። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ደህንነታችን ስንቀበል ይሰጡናል። እነርሱም የእየሱስ ሕይወትና አገልግሎቶች ሲሆኑ ለአካሉ ለቤተክርስቲያን የተሰጡ ፀጋዎቹ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍላጎቱንና ሐሳቦቹን ለማስፈፀም በመንፈስ ፍሬ የሚታዩ ናቸው። መንፈስ ቅዱስ ፊት እንደነነረ አሁንም ይጠራል።

9. አብ ከሙታን የተነሳውን ኢየሱስ ክርስቶስን የሁሉም ፈራጅ አድረጎታል። ወደ ዓለም ይመለሳል በሁሉም የሰው ልጆች ላይ ለመፍረድ በኢየሱስ ያመኑና ስማቸውም በበጎ ሕይወት መጽሀፍ ላይ የፃፈ ሰማያዊ የከበረ አካላቸውን በዳግም ምፅአቱ ያገኛሉ ከእሱም ጋር ለዘለዓለም ይሆናሉ። የእግዚአብሄርን እውነት ለመቀበል ያልፈለጉ ለዘለዓለም ከእግዚአብሄር ህብረትና ደስታ ይለያሉ። ከሰይጣንና ከመልአክቱ ጋር ይፈረድባቸዋል።

ይህ በእውነቱ የተጠናቀቀና የጠለቀ ባይሆንም የልቤን ሥነ-መለኮታዊ መዓዛ ይሰጣቸኋል ብዬ አምናለሁ። ጽሑፉን እወደዋለሁ።

"ከአስፈላጊዎች ሁሉ — ህብረት፣ ከምርጫዎች- ነፃነት ከሁሉም ነገር- ፍቅር"